አምስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፩
5me ANNÉE № 1

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፭ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 3 JANVIER 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ለገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የመንግሥት ማስታወቂያ ።

በኢትዮጵያ ቦታና መሬት ለውጭ አገር ሰው የሚያከራይ የኢትዮጵያ ሰው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ደንብ ጠብቆ እንዲዋዋል ደንብ ተደርጓል ።

መጀመሪያ ።

አከራዩው የሚያከራየው ቦታ ወይም መሬት በከተማ ውስጥ የሆነ እንደሆነ በሜትር ኪራ ይለካል። ከከተማ ውጭ የሆን እንደሆነ ግን በኪራይ የተሰጠው መሬት ባለርስቱና ተከራዩው ተስማምተው በሚያኖሩት በሚታይ ምልክት ይወሰናል።

ሁለተኛ ።

የቦታው ወይም የመሬቱ ኪራይ እንደ ቦታውና እንደ መሬቱ ለምንነትና ውድነት ሁለቱ ተዋዋዮች እንደ ተስማሙበት ይረጋል።

ሶስተኛ

ቦታ ወይም መሬት የሚከራይ የውጭ አገር ሰው በላዩ የተሠራውን ቤትና ማናቸውንም ነገር ሁሉ የውሉ ዘመን ሲፈጸም አለዋጋ ላከራዩ ለቆ የሚሔድ የሆነ እንደሆነ የፈቀደውን ያህል ቤት ሊሠራበት ይችላል፤ ግምት ተቀብሎ የሚለቅ የሆነ እንደሆነ ግን ዋጋው ይህን ያህል ብር የሚፈጅ ይህን ያህል ቤት እሠራለሁ ብሎ ከከራዩ ጋራ ሳይስማማ እርሱ እንደ ፈቀደ ቤት እንዳይሠራ ተከልክሏል ።

አራተኛ ።

ቦታውን ወይም መሬቱን ለውጭ አገር ሰው የሚያከራይ የኢትዮጵያ ሰው ከሠላሳ ዘመን የበለጠ ውል ተዋውሎ እንዳያከራይ ተከልክሏል።ከሠላሳ ዘመን በኋላ ግን ውሉን ለማደስ ቢፈልጉ ለኢትዮጵያ መንግሥት አስታውቀው መንግሥት በተለየ የፈቀደ እንደሆነ ለማደስ ይችላሉ ።

አምስተኛ ።

ቦታ ወይም መሬት የሚከራይ የውጭ አገር ሰው በተከራየው መሬት ላይ እህልም ቢዘራ፤ አትክልትም ቢተክል፤ እንደ አገር ደንብ አሥራትና ግብር ይከፍላል ። እህሉንና አትክልቱንም ከኢትዮጵያ መንግሥት አስቀድሞ ፍቃድ ሳይቀበል ወደ ውጭ አገር ለማውጣት አይችልም ። ወደ ውጭ አገርም ለማውጣት መንግሥት የፈቀደለት እንደሆነ እንደ ኢትዮጵያ ጉምሩክ ደንብ ቀረጥ ይከፍላል ።

ስድስተኛ ።

ማንም የውጭ አገር ሰው በተከራየው ቦታ ወይም መሬት ውስጥ ማዕድን ወይም አንቲካ ነገር ቢገኝ የመንግሥት ገንዘብ ነውና በተለይ ከመንግሥት ሳያስፈቅድና ሳይዋዋል ለማውጣት አይችልም ። መንግሥትም በዚያ ውስጥ የሚገኘውን ማዕድንና አንቲካ ለራሱ ለማውጣት ቢፈልግ ለተከራየው ሰው በሠራው ሥራ ኪሣራውን ሰጥቶ ለማውጣት ይችላል ።

ሰባተኛ ።

አንድ የውጭ አገር ሰው በተከራየው ቦታ ወይም መሬት ላይ ሌላው ሰው በቦዩ ወሃ ቢወስድ ለማሰናከል አይችልም ። ነገር ግን ወሃው በሚሔድበት ላይ የሚበላሽ አትክልት ወይም እህል እንዳለ ኪሣራውን ይቀበላል ።

ስምንተኛ

ለገበያም ለቤተ ክርስቲያን፡ለምሽግና ለምድር ባቡር፡ይህን፡ለመሰለ ለሕዝብ ጥቅም ለሚያስፈልግ ሥራ ሁሉ መንግሥት ቦታውን ወይም መሬቱን ለማስለቀቅ የሚያስፈልገው የሆነ እንደ ሆነ ተከራዩ ከሣራውን ተቀብሎ ይለቃል እንጂ ለማሰናከል - አይችልም ።

ዘጠነኛ

የውጭ አገር ሰው በተከራየው ቦታ ወይም መሬት ላይ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ሰዎች እርስ በራሳቸው የተጣሉ እንደሆነ በኢትዮጵያ መንግሥት ዳኛ ይዳኛሉ ።

አሥረኛ

ቦታና መሬት የሚከራይ ሰው ሁሉ የሚገባውን ክፍሎ ውሉን በውል ማኖሪያና መመርመሪያ ቤት መዝገብ ያስገባል ። ተከራዩም ገንዘብ በየዓመቱ በመቶው አንድ ብር ለኢትዮጵያ መንግሥት ይከፍላል ።

አሥራ አንደኛ

የውሉ ዘመን በተፈጸመ ጊዜ ሁለቱ ተዋዋዮች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ሽማግሎች መርጠው ባለ ርስቱ ፈቃድ የተሠሩትን ቤቶች ግምታቸውን ይወስናሉ አራቱ ሽማግሎች ያልተስማሙ እንደሆነ ግን አምስተ ሽማግሌ መርጠው በበዛው ወገን እንደተገመተው ይቀበላል ። ቦታ ወይም መሬት የተከራየ የውጭ አገር ሰው ከባለርስቱ ሳያስፈቅድ ቤት የሠራ እንደሆን ባለርስቱ በፈቃዱ ገዝቶ ካላስቀረው በቀር የውሉ ዘመን በተፈጸመ ጊዜ የተከራየውን ቦታ ወይም መሬት እንዳለ ትቶ በፈቃዱ የሠራቸውን ቤቶች አፍርሶ ይሔዳል።

NOTE OFFICIELLE.

La location des terrains par les propriétaires Ethiopiens à des Etrangers est soumise aux dispositions suivantes.

Art. 1. Les terrains donnés en location dans l'agglomération urbaine seront déterminés par leur surface en mètres carrés. En dehors de la ville les limites de la propriété louée seront déterminées par des signes conventionnels apparents sur le terrain.

Art. 2. Le prix de location devra être determiné d'un commun accord entre les parties selon l'étendue et la valeur de rapport du terrain.

Art. 3. Si, le contrat de la location prévoit qu'à son expiration les constructions faites par le locataire resteront au propriétaire et que le locataire remettra les lieux loués en état, ce dernier construira à son gré. A défaut d'une telle clause, le locataire ne pourra construire sur le terrain loué qu'après une entente formelle avec le propriétaire au sujet du nombre et de la valeur des constructions à édifier par le locataire.

Art. 4. Les baux de propriétés urbaines ou rurales ne peuvent être, entre propriétaires Ethiopiens et locataires Etrangers, d'une durée supérieure à trente ans. Pour prolonger un bail semblable au delà de trente ans, une autorisation spéciale du Gouvernement *E*thiopien est obligatoire.

Art. 5. Le locataire *E*tranger qui, sur le terrain loué exercera une industrie agricole ou maraichère sera tenu personnellement des impôts et de la dîme conformément aux lois locales. L'exportation des céréales et des légumes est soumise à une autorisation préalable du Gouvernement *E*thiopien Les produits exportés avec l'autorisation du Gouvernement sont soumis aux droits de douane en vigueur.

Art. 6 Les mines ou les objets archéologiques qui pourraient être découverts dans les terrains loués sont propriété de l'Etat Ethiopien et leur exploitation ne peut avoir lieu sans une autorisation spéciale et un contrat précis du Gouvernement. Si le Gouvenement veut entreprendre lui même l'exploitation da la mine découverte, ou continuer les fouilles archéologiques, le locataire cédera la jouissance du terrain loué. Mais il aura droit à une indemnité tenant compte de son prejudice de la part du Gouvernement

Art. 7. Le locataire Etranger ne peut s'opposer à l'établissement d'acqueducs ou d'autres conduites d'eau à travers le terrain loué. Si l'acqueduc ou la conduite d'eau passe à un endroit cultivé, celui qui exige le passage à cet endroit est tenu d'indemniser le locataire.

Art. 8. Au cas d'expropriation du propriétaire Ethiopien pour cause d'utilité publique (établissement d'un marché, église, fortification. voies de chemin de fer, etc.) le bail sera résilié de plein droit et le locataire ainsi évincé a droit à une indemnité de la part du Gouvernement.

Art. 9 Les procés entre Ethiopiens habitant sur un terrain loué par un Etranger sont soumis exclusivement à la juridiction Ethiopienne.

Art. 10. Le locataire est tenu de faire enregistrer son bail au Bureau du Contrôle et de payer ses droits afférents á cet enregistrement. Il est tenu en outre envers le Gouvernement d'un impôt de 1 % sur le montant diloyer.

Art. **11.** La valeur des constructions élevées avec l'autorisation du propriétaire, à l'expiration du contrat, sera détermnée par quatre arbitres nommés à rasion de deux pour chacune des parties .Si les quatre arbitres ne sont pas d'accord, ils désigneront un surarbitre pour les départager. Si le locataire construit sans l'autorisation du propriétaire, il devra à l'expiration du bail remettre les lieux loués en etat, et enlever ses constructions élevées à ses risques et périls, si une entente amiable n'intervient pas pour leur rachat par le propriétaire du terrain.

BRITISH MUSEUM
P 21 38 B M

ስለ ኢትዮጵያ ።

እናታችን ኢትዮጵያ መልካም ቈንጆ ናት ፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ ሁለት የከበሩ ጌቶች ከሩቅ አገር መጥተው አግብተው ሁለቱም ወለዱላት። የባሎቿም ስም ይሁዳ ሌዊ ነው ። ከይሁዳ የወለደቻቸው ልጆቿ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና እስከ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ድረስ ፈጣሪአቸውን ፈርተው ሃይማኖታቸውን አጽንተው ጋሻቸውን መክተው ዘውዳቸውን ደፍተው ይኖራሉ ። ከሌዊ የወለደቻቸው ልጆቿ ግን ያባቶቻቸውን የሌዋውያን ሥርዓት እምነትን ግዝረትን ከጡኑ በኋላ ከጥምቀት ጀምሮ እስከ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ድረስ ያለውን ሥርዓት ለመማር ከአባታቸው አገር ከነጋድያን ጋራ ሒደው ፹፩ መጣፍ ተምረው ሲመለሱ የተሾመት ሹመት አዋጅ ሲነገርላቸው ምንም ቢያምሩ ቢማሩ አይከበሩ አይሾሙ አይሸለሙ የሚባል አዋጅ አስነግረው እየተከዙ አገሪቱ ገቡ፡ይህን ያቈ የሰሙ ሁሉ ለዚህማ ባይማሩ ባያምሩ አባትስ ባይኖራቸውም ፍሬ አለው እያሉ ሲናገሩ ብሰማ ተናድጄ ይህን መወድስ ሰጠሁ ።

ኢትዮጵያ ዕቤር ቀዳሚተ ኵሉ
ደኃሪተ ኵሉ ትሰመይ ባረከዋ አበዊሃ።
ድኅረ ውሉዳ አልህቀት በሕግ አበው አሚሃ።
ወላእግረ ጻድቃን ነጋድያን
ድኅረ ሐፀበት በአሚን እዴሃ።
እስመ ባረክዋ አበዊሃ
ኢትዮጵያ ኢትልህቅ ከመ ከማሆን ለዘከማሃ ።
ንሕነሰ ናስተበቍዖ ለአበ ስብሐት ብዙኅ።
ውሉደ እምአበው ኢይፍልጥ በጊዜሃ።
እስመ ሐዋርያ አዘዘ አክብሮተ አበው ብውሑ።
ወአበው ኢያስተቍጥዑ ውሉዶሙ በንስሐ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

ስለ ቅዱስ ገብርኤል በዓል አከባበር ።

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ቅዱስ ገብርኤል አመቤትችንን ያበሠረበት ቀን መታሰቢያ በዓል ነበረና ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት በጥዋት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ወረዱ ። ግርማዊ ንጉሥም ከቤታቸው በግረ ዓጀብ ወርደው በአራት ሰዓት ያው ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ገቡ። ግርማዊ ንጉሥም ከገቡ በኋላ ትንሽ ቈይቶ ታቦቱ በጣና ዑደት ተደረገ ። ከዑደቱም በኋላ ሊቃውንቱና ካህናቱ ሲያሸበሽቡ አምረው ታዩ።

ከዚህ በኋላ ታቦቱ ገባና ስለ በዓሉ ክብር መድፍ ተተኰሰ። ግርማዊ ንጉሥም ወደ ቤተ መንግሥቱ ገቡ ።

ስለ ልደት በዓል መሰናዳት ።

ታኅሣሥ ፳፱ ቀን የእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ መታሰቢያ በዓል ስለሆነ በየቤቱ ሁሉ ለበዓሉ የሚያስፈልገውን ነገር ማሰናዳት ይዘዋል። በትልልቅ ቤትም ጌጥና መብራት እንዲደረግበት የልደት ዛፍ ይተከላል። ስለ ልደት በዓል አከባበርም በሚከተለው ቍጥር ጋዜጣችን እንድንጽፍላችሁ ተስፋ እናደርጋለን ።

ብርሃንና ሰላም ቡሩክ የደስታ በዓል ያድርግላችሁ እያለ ላንባቢዎች ሁሉ መልካም ምኞቱን ያቀርባል ።

መወድስ ።

እምኍልቈ ራብዕ ዘመን ፍና ዮርዳኖስ መንገለ ኃምሴ
ዓም ኢየሩሳሌም እመ ቀርበ ።
ብርሃንና ሰላም ቦአ ኢትዮጵያ ምዕራበ ።
ወሰደደ እለ ይሠይጡ ቃለ ጽድቅ ርግበ ።
ወየዓርግ ለለጸባሑ ተግሣፀ ጥበብ ወምክር እንተ ደብረ
ዘይት ዓቀበ ።
መፍትውሂ ከመ ንግበር በዓለ ልደት ዕፁብ ።
ብርሃንና ሰላም መድኃኒትነ አመ ከመ ዮም እስመ ተረክበ።
በሕቱ ኢይጥዓም ምንተ እምነ በዓሉ ነበበ ።
በቃለ መጻሕፍት ደመ በግዕ ልብሰ እንቲአሁ ዘኢሐፀበ።

ስለ ዘበኞች ትጋት ።

በታኅሣሥ ፲፫ ቀን ሌሊት አንድ ሌባ ከቤት በቅሎ ከነኮርቻው ሰርቆ ይዞ ሒዶ ሌሊቱኑን ጃልዳ ለሚባል ሌባ በ፳፭ ብር ሌጣዋን ሸጠለት ጃልዳም በቅሎዋን ገዝቶ የራሱ እንድትመስል ሊያታልል በአሮጌ ኮርቻ ጭኖ ከሸጠለት ሌባ ጋራ በማቋረጫ መንገድ እያቋረጡ ሲሔዱ ዘበኞች ከፍላቸውን ሲጠብቁ በቀራቢአቸው ያለውን ሲፈትሹና ሲጐበኙ ሌባውንና ገዥውን ከነበቅሎዋ ይዘዋቸው ቢመረምሯቸው መሰረቃቸውን አምነው ታሥረው ሰንብተው በቅሎዋም ለባለቤቱ ከተመለሰች በኋላ በ፲፯ ታኅሣሥ ደግሞ ሌቦቹን ኮርቻውን ያደረጉበትን ከሚሰርቁ ቢመረምራቸው ሻጩ ሌባ ኮርቻውን ከሰንሰል ውሥጥ ደብቄዋለሁ ብሎ ተናግሮ ከዘበኞች ጋር እንዲያመጣ ልከውት ኮርቻውም ከሰንሰሉ ውሥጥ ተገኝቶ ለባለቤቱ ተመልሶ እነኝህ አታላዮቹ ሌቦች በዘበኞች ትጋትና ብርታት ተይዘው ታሠሩ ። ፪ኛ ከሌሊቱ በ፯ ሰዓት ዘበኞች ሲፈትሹ አንድ ሌባ ድጅኖውን ይዞ የሰው ቤት እየቆፈረ ሲሰረስር ዘበኞች ደርሰውበት ይዘው ቢመረምሩት ጥንትም ሌባ ነኝ አሁንም ልሰርቅ ነበር ብሎ አምኖ ታሠረ። ፫ኛ ሶስት አታላዮች አንድ ከጉማ የመጣ ባላገር በቅሎ ለመግዛት ሲጠይቅ ሰምተውት አንደኛው አታላይ እኔ እሸጥልሃለሁ ብሎት ሁለተኛውም አሻጭ ሶስተኛው እማኝ ሆነው ተማክረው ያነን ባላገር ናና በቅሎዋን እናሳይህ ብለው አንዷን እመስክ የምትግጥ የማንንም በቅሎ አሳይተውት በ፳፯ ብር ሊሸጡለት ተስማምተው የበቅሎዋንም ዋጋ ፲፬ ብር ተቀብለውት ዳግሞ በ፩ ብር ፍንጥሩን ጠጅ ከጠጡ በኋላ ያንን ባላገር አታለውት ጠፉ ።

ያም ባላገር የዘበኞቹን ብርታትና ትጋት ተማምኖ አቤቱታውን ያደረጉትን አኳኋን ሁሉ ለዘበኞቹ አመልክቶ ሳለ ዘበኞቹም ይኸንን በሰሙ ግዜ በፍጥነት ሒደው እነኝህን አታላዮች ሲፈልጉና ሲመረምሩ አታላዮቹንም አግኝተው ይዘዋቸው እነሱም አምነው ታሠሩ ዘበኞቹም ሌሊት በውርጭ ቀን በፀሐይ መጠን በሌለው ትጋት ከተማዋን ስለሚጠብቁ ወደፊትም

ፊቱን ሲበና አታላይ ጠፍቶ ጸጥታና ሰላም ሰፍቶ እንዲኖር ሥርዓት የለውም ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

የጨረታ ማስታወቂያ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ አገር ጋራ ያለውን የመገናኛ መንገድ ለማስፋትና ለማሻሻል ሲል ከዓለም ሁሉ ጋራ የሚያገናኘው ያለሽቦ የቴሌግራፍ መሥሪያ ለማቆም ቁርጥ ሐሳብ አድርጓል ።

ስለዚህም ሥራ ነገር ከዚህ ቀደም ከብዙ ስፍራ የመሣሪያው ዓይነትና ዋጋውም ልዩ ልዩ ሁኖ ደርሶልናል ። ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግሥት የሚፈልገው መሣሪያ ዓይነቱና የመኪናው ጕልበት ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

፩ኛ፤ ሙሉ መሣሪያ ያለው ያለሽቦ ቴሌግራፍ መሥሪያ። አንድ የቴሌግራፍ ቃል ማሳለፊያ ከ፳ እስከ ፳፭ ኪሎዋት የሚሆን ። ደግሞ ከ፵ እስከ ፶ ሜትር አንድ ሁኖ ያለማቋረጥ ሁል ጊዜ ከፓሪስና ከሎንዶን ከሮማና ከቤርሊን ጋራ ከአውሮፓ ሁሉ ለመሥራት የሚችል ። አንድ የቴሌግራፍ ቃል መቀበያ ሙሉ መሣሪያ ያለው ከዚህ በላይ ለተጻፈው መሣሪያ መቀበያ የሚሆን ከአውሮፓ በተቀር ከአሜሪካንም ቃል ለመቀበል የሚችል ።

፪ተኛ፤ በአገር ውስጥ በየስፍራው የሚቆም እስከ ፰፻ ኪሎ ሜትር ድረስ የቴሌግራፍ ቃል ለማሳለፍና ለመቀበል የሚችል ፭ ሙሉ ፤ ያለሽቦ ቴሌግራፍ መሥሪያ ሙሉ መኪና።

ከዚህ በቀር ያለሽቦ ቴሌግራፍ መሥሪያ ለማቆም የሚያስፈልገውን መሣሪያ ሞተር ለአንቴን የሚሆን ምሰሶ ሽቦ የኤሌክትሪክ መስጫ መኪናና ይህንንም የመሰለውን ለዚህ ሥራ የሚያስፈልገውን መሣሪያ ሁሉ ጅቡቲ ድረስ መጥቶ የሚፈጀውን ዋጋ ።

ይህነኑ ሥራ በየስፍራው ለማቆም የሚችሉ መሐንዲሶችና ሌሎችም ሠራተኞች አዲስ አበባ ድረስ መጥተው ሥራውን በየስፍራው በሙሉ አቁመው መኪናው እንደ ደምቡ እንደሚያስፈልገው በትክክል ሁኖ የቴሌግራፍ ቃል መላክና መቀበል መቻሉን አስመርምረው የሚያስረክቡ ለነዚህ የሚፈጀው ዋጋ። ይህንን ከዚህ በላይ የተጻፈውን ሁሉ የጨረታውን ዋጋ ለማስታወቅ በሚላከው ወረቀት ውስጥ ዝርዝሩንና ዋጋውን ለይቶ ማስታወቅ ያስፈልጋል ። የጨረታውን ዋጋ ለማስታወቅ ከዛሬ ጀምሮ እስከ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት ድረስ ተወስኖ ተቆርጧል ። ከዚህ ከተወሰነው ቀን አሳልፎ የሚመጣው የጨረታ ወረቀት ሁሉ አይረጋም ።

ይህንን ሥራ ለማቆም የሚመጡት መሐንዲሶችም መሣሪያው አዲስ አበባ ከገባበት ቀን አንሥቶ እስከ ስድስት ወር ድረስ ሥራውን በየስፍራው በሙሉ አቁመው ጨርሰው እንዲያስረክቡ ጊዜያቱ በዚህ ተወስኖዋል ፤ ደግሞ ሥራውን ጨርሰው ካስረከቡበት ቀን አንሥቶ እስከ ፪ ዓመት ድረስ መሣሪያው የተሰናከለ እንደሆነ የሸጠው ሰው ወይም ኩባንያው አላፊ ሁኖ የተበላሸውን መሣሪያ ሁሉ በኪሳራው ሊያድስ ውል መግባት አለበት ።

የገንዘቡም አከፋፈል በሦስት ላይ ተከፍሎ ነው ፤

መጀመሪያ ፤ ውሉ ሲታተም አንዱ እጅ ይከፈላል።

ሁለተኛ ፤ መሣሪያው ጅቡቲ ሲገባ ሁለተኛው እጅ ይከፈላል ።

ሦስተኛ፤ በየስፍራው ሁሉ መሣሪያው በሙሉ ቁሞ ሲያልቅ ሦስተኛው እጅ ይከፍላል ።

ታኅሣሥ ፳ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ፤
የኢ. ፖ ቴ ቴ ምኒስቴር

AVIS D'ADJUDICATION.

Le Gouvernement éthiopien afin d'améliorer et de développer les relations extérieures a décidé de procéder à l'installation d'un poste international de T.S.F.

Ayant reçu a cet effet de nombreuses offres s'établissant sur une échelle de prix très variables et de fournitures également très différentes, le désir du Gouvernement serait d'avoir une installation suivant les détails ciaprès :

1° — Une installation complète de T.S.F. qui comprendra :

Un poste émetteur de 20 à 25 Kilowatts pour ondes de 40 à 50 mètres pouvant travailler en permanence avec l'Europe : Berlin, Londres, Paris et Rome.

Un poste récepteur complet permettant de recevoir les postes ci dessus et en outre l'Amérique.

2° — Installations et fournitures de cinq postes émetteurs et récepteurs, d'une portée de 800 kilomètres environ à monter dans l'intérieur du pays.

Le montant des offres devra comprendre :

a) le prix Cif Djibouti (matériel pour toute l'installation, moteurs, pylones, antennes, appareils d'éclairage etc.)

b) les voyages et les appointements des ingénieurs et des ouvriers spécialistes nécessaires pour le montage et pour assurer le fonctionnement du poste qui sera remis après essais concluants au Gouvernement éthiopien.

Délai d'option pour l'adjudication deux mois soit jusqu'au 28 février 1929. Passé ce délai les offres ne seront plus prises en considération

L'installation devra être terminée 6 mois après le jour de l'arrivée du matériel à Addis-Abeba.

L'adjudicataire devra s'engager à un bon fonctionnement du poste, pour deux années et prendra les réparations a sa charge pendant cette période à partir du jour de l'installation.

Réglement : 1/3 a la commande.

1/3 a l'arrivée du matériel Djibouti.

1/3 à la fin de l'installation et a la mise en marche du poste.

Addis-Abeba 31 Décembre 1928.

MINISTERE DES POSTES
DES TELEGRAPHES et
DES TELEPHONES.

ስለ ዓሰብና ደሴ ንግድ ጠቀሜታ ሐሳብ

ከቦሌቲና ኤኮኖሚኮ የኤሪትሬአ ጋዜጣ የተገኘ ባጭሩ፤ ከዓሰብ እንሥቶ እስከ ደሴ የሚጠረገው የአቶሞቢል መንገድ ርቀቱ ፭፻፹ኪሎ ሜትር ያህላል ። ያሁኑ የዓሰብና የደሴ ንግድ በበቅሎና በግመል ይመላለሳል። አሁን ከዓሰብ እንሥቶ እስከ ደሴ ድረስ የጭነት ክብት ኪራይ በኩንታል መቶ ሀያ ሊሬ ነው ። መንገዱ ተሰናድቶ በካሚዮን የተጫነ እንደሆነ ግን በመፍጠኑና ብዙ በመሸከሙ በመከናወኑም ሳይኪራዩ ከዓሰብ እንሥቶ እስከ ደሴ በኩንታል መቶ አምስት ሊሬ ይሆናል።

ማስታወቂያ

የኔ ሠርግ በጥር ፯ ቀን መሆኑ ቀርቶ በጥር ፲፫ቀን መሆኑን ለወዳጆቼ ሁሉ አስታውቃለሁ።

ባላምባራስ ክብረት በንት ይርጉ ።

ሹመት ።

ደጃዝማች ወንድ ይራድ ሊሙንና ትቤን ተሾሙ ።

ቀኛዝማች አሥራት ፊታውራሪ ተብለው የቀኝ ዘበኛነትን ተሾሙ።አጋፋሪ ወልደማርያም ፊታውራሪ ተብለው የግራ ዘበኛነትን ተሾሙ ።

ግራዝማች ፍቅረ ሥላሴ ቀኛዝማች ተብለው የእልፍኝ አስከልካይነትን ተሾሙ ።

ባላምባራስ ውብሸት አጋፋሪነት ተሾሙ ። ልጅ ተፈራ አበበ የባላምባራስ ውብሸት የነበረውን የሻምበልነት ተሾሙ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ላገኙ እንኳን ደስያላችሁ እያለ ሥራቸውም እንዲከናወንላቸው መልካም ምኞቱን ያቀርብላቸዋል ።

ስለ አየር መለወጥ ።

በታኅሣሥ ወር በአዲስ አበባ አየሩ በጣም ወርጭቶ ብርዱ ከፍቷል እርጥበት የሚያደርቅ የፀሐይ ሙቀት የማያስወግደው ከፉ ውርጭ ይወርዳል ። በሌሊት የወረደ ውርጭ በንዳንድቦታ ተጋግሮ ተጋግሮ ትልልቅ የበረዶ ጥፍጥፍያህል ይገኛል፡ከብርዱ የተነሣም ብዙ ሰው የብርድ ጉንፋን እየያዘው ይታመማል ብዙ ሕፃናትም ይሞታሉ።የዘንድሮ ብርድ ድሮ በመከር ከሚወርደው ብርድ በጣም የተለየ ነው ።

አንዳንድ ቀን የአየር መለኪያ ቴርሞ ሜትር ብንመለከት ብርድ በጣም በበረታበት ሌሊት ከዜሮ በታች ሁለት ግሬድ ያህል ወርዶ ይገኛል ።



ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።


COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠሩ ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሁ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ሳገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚሁ አቶሞቢል በተለይወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሉንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና ጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አሉው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚሁ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬስ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፺ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኚልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።


GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
1-28-7
GOODYEAR
ጉዲዪር

ከሁሉ የሚበልጥ አደስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት· ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድዪር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድዪር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።፡

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኮንን ፡ ኢትዮጵያ መንግሥት ፡ አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፪
5 me ANNÉE № 2

ሐሙስ ጥር ፪ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 10 JANVIER 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ያራተኛ ዓመት ቁጥር የ፲፻፹፮ ገጽ ተከታይ ።

ምዕራፍ ፪

ሀብት ።

(፯)ሀብትና የፍጥረት ክብት ። (ገንዘብ)

የፍጥረት ክብት ማለት አለ ሥራ በብዛ እጃቸው የተሰጡ እንደ ፀሐይና ዓየር ውኃ ናቸው ።

እንደ ሕዝብ አሳብ ሀብት ወርቅና ብር ይመስለዋልና ሀብታም ሰው ወርቅና ብር ያለው ነው ይላል። ይህ አሳብ ግንከ እውነት በጣም የራቀ ነው ፡ አንዱ ተከራካሪ ደግሞ እንግዲያ ሰፊ መሬት የያዘ ነው። ሀብታም ይል ይሆናል፤ ይህ አሳብም ልክ አይደለም፤ ስለምን ስፋቱ ከስፍራውና ፍርያምነቱ ሊመዛዘን ይገባዋልና ለምሳሌ አንድ ሰው በሐረር(ጨርጨር) አንድ ሁለት ዋና ቀላድ ያለው እንደሚገባው ቢያፈራ ሀብታም ሊባል በተቻለ፤ ሌላው በደንከል ወይም በሶማል አገር ብዙ ቀላድ ቢኖረው ግን ሀብታም ሊባል ባልተቻለም እንዲሁም የአፍሪቃና የአውስትራልያ የእስያና የአሜሪካ የጥንት ባላባቶች ኤውሮፖች ሳይዙት ሰፊ መሬት ነበራቸው፤ ግን ያው ድሆች ነበሩ። እንግዲያስ እውነት ነው መሬት ብቻዋን ሀብት ልትሆን አትችልም። ሁለተኛም አንባቢው እንዲህ ብሎ ሊከራከር በቻለ፤ ሀብት ለማቆም ፍርያማ መሬት ብትሆን ማለት ፈሳሾች ወንዞችና ኩሬዎች ጥሩ አየርና የሚበቃ ዝናም ያሉባት ብዙ ሚኔራል (መዓድን) ማለት የድንጊያ፤ ከሰል፤ ብረት፤ እስራዚ፤ ዚንጎ፤ እርሳስ፤ አልማዝ፤ ወርቅ፤ ብር፤ ነሐስ (መዳብ) የሞሉባት ሀብታም አገር ልትባል ትችላለች ።

የሀብት እውቀት ።

አሳቡ ደግ ነበር። ግን እኒህ ሁሉ የፍጥረት ሀብት መባል ይገባቸዋል እንጂ ብቻቸውን የሀብት እውቀት እንዳልሆኑ ቀጥለን እናስረዳለን። አንድ ሕዝብ በፍጥረት ሀብት በሞላበት መሬት ተቀምጦ ድሀ ድሀ ሊሆን ይችላል፤ ለምሳሌ የአሜሪካ ባላገሮች ህንዶች የሚባሉ የጥንት ባላባቶች አሁን ስታቲኡረቲ (የአንድነት መንግሥታት) በሚባሉ የገንት መንግሥታት በወጡበት አገር ነበሩ። ግን ችሎትና ፍላጋ ስላልነበራቸው ማለት የፍጥረት ሀብት እንዴት አድርጎ እንደሚሠራና ለሀብት እንዲቆም ስለላወቁ ያው በጣም ድሆች ነበሩ። ሆላንድን የመሰለ መንግሥት ግን በድሀና በጠባብ መሬት ከባሕር እየተታገለ(እየተዋጋ) ተቀምጦ በእውቀትና በማስተዋል በኢንዱስትሪና በንግድ እንዴት ሀብታም ሕዝብ እንደሆን ይሄው በግልጥ ያስረዳል ።

ላሳጥረው ኤኮኖሚስታ ጸሐፊው እውነተኛ አሳቡን ለመግለጥ የሚፈልገው ሀብት ከመሬት ደግነትና በአየር መልካምነት ከመፈለግ በሥራና በትጋት መፈለግ እንዲገባና እንዲበልጥ ለማስረዳት ነው እንዲህ ከሆነ እነኛ ድሆች ሕዝቦች ሁሉ ከነዚያ የሠለጠኑና ሀብታሞች መግሥታት እንደተካከሉ የግድ ነው ።

፪ ሀብት ምንድር ነች ።?

ከእንግሊዝ ኤኮኖሚስቲ ከትልልቆቹ አንደኛው ጕሊልሞ ናሳው ሲኒዮር የሚባል እንዲህ ሲል ይወስናል ። ቀጥ ብላ ይሁን ወይም በዙርያ ደስታ ወይም ኅዘን (ጉዳት) የምትሰጥ ነች። ይህች ቃል በጭሩዋ ጥቅም ብለን ልንቈርጣት (ልንተረጕማት) እንችላለን ።

ሀብት—ማለት
- ፩ኛ ብዛት የተወሰነ
- ፪ኛ መተላለፍ (መለዋወጥ)
- ፫ኛ ጥቅም ።

አሁን የነዚህ ሦስት ቃሎች ዓይነት ወይም ጠባይ ሀብት ማለት ምን እንደሆነ ትክክለኛ ትርጓሜዋ ማለት በሌላ ንግግር መወሰን መለዋወጥ ጥቅም ምን ማለት እንደሆነ ገልጠን ለማስረዳት እንጥራለን

(፫) ሀብት በብዛት በመስጠት የተወሰነች ነች ።

ማናቸውም ነገር ብዛቱ ያልተወሰነ ሀብት አይባልም። ማስረጃ ለምሳሌ (አየር ሀብት አይደለም ። አፋችን በከፈትን ቍጥር ልክ የሌለውን እንተነፍሳለን ። ስለዚህ የአየር ጥቅም የሚመዘዘነውና የሚተከከለው እንደሌለ ለማንም አይሠወርብትም ሕይወታችን ነውና። ግን ምንም ስንከፍልበት የሚያስፈልገን ያህል በየትም እናገኘዋለን ። በአንድ ጥልቅ መሬት ማለት ሚኔራል ለማውጣት የሚቈፈር ግን የተወሰነ ነውና ያን ጊዜ እንደ ሀብት ይቈጠራል ።

አልማዝ በጣም የተከበረ ነውና ብዙ ይፈለጋል፤ ዋጋው በጣም እጅግ ከፍ ማለቱ ጥቂት በመሆኑ ነው እንጂ ለትንሽ ሽልማት መሰይና ለመስተዋት መቍረጫ ለድንጊያ መንደፊያ ብተቀር ለሌላ ቁም ነገር ምንም አይረባም ። እንዲሁም ከወርቅ ይልቅ የብረት ጥቅም ትእልፈት አእላፋት ጊዜ ይበልጥ ነበር ግን ከማነሱ የተነሣ የወርቅ ዋጋ እጅግ ይከብራል ።

እንግዲያስ ዋጋው ከፍ የሚል ከጥቂትነቱ ብቻ የተነሣ ነውብንልም ትንሽ ስሕተት አይታጣበትም። ስለምን ቢሉ ብዙ ዓይነቶች ሚኔራሎች እስከ ዛሬ ድረስ በጥቂት ብቻ የሚገኙ አሉ። ግን ገና የሚሠሉበት ስላልተለመዱ (ስላልታወቁ) ዋጋቸው ብዙ ክቡር አይደለም ። ከነዚሁ ራዲዮም የሚባል በጥቂቱ የሚገኝ ሚኔራል ፤ የወርቅ ብርዕ ጫፍ ማሠሪያ ለማድረግ ስለተለመደ ግን በጣም ከፍ በለ ዋጋ ይሸጣል ። በዚሁ ፕሮብሌም አከኼድ በማነሱ በጥንካሬው በመለመዱ መሣርያ ማድረግ ዋጋው ከፍ የሚል ይመስላል ። ሚካኤል ተሰማ።

ከዚህ የቀረ በሚከለተው ይታተማል።

ስለ ልደት በዓል አከባበር ።

ታኅሣሥ ፳፰ ቀን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ በዓል ዋዜማ ስለሆነ ከጥዋቱ በስድስትና በሰባት ሰዓት በየቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ ደወል ተደወለና የዋዜማ ሥርዓት ተደረገ። በ፳፱ ቀን ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ማኅሌት ተቁሞ አደረና ቅዳሴ ከተቀደሰ በኋላ ጎህ ሲቀድ ስለ ልደት በዓል የምስራች መድፍ ተተኰሰ። ስለ በዓሉም ደኅንነት በቤተ መንግሥቱ ለመኳንንትና ለሠራዊት ትልቅ የደስታ ግብር ተደርጎ ዋለ ። በዚሁም ቀን በዘጠኝ ሰዓት የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ልጆች ልጅ እስፋ ወሰንና ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ ፡ ልጅ መኰንን ፡ ስለ ልደት በዓል ክብር ብዙ ሕፃናት ጠርተው ነበርና ሰዓቱ ሲደርስ የተጠሩት ሕፃናት በግርማዊ ንጉሥ ቤት ተሰበሰቡ። ወዲያውም አምሮ በተሰናዳው አዳራሽ ገብተው በደስታ ሻይ ተጋበዙ። ከዚህ በኋላ ሕፃናቱ ሁሉ የገና ዛፍ ከተተከለበት ክፍል ገቡና በልዕልት መነን ፊት ተሰብስበው የንጉሡን ልጆች ደስ የሚያሰኝ ጨዋታ ተጫውተው እንደ ሽማግሌ መልክ ሆኖ የተቀረጸ ሥዕል በፊቱ ያጠለቀ ሰው የልደትን ስጦታ በየዓይነቱ ለሕፃናቱ ሁሉ አደለ። ሕፃናቱም በተቀበሉት ስጦታና በፈንጠዚያውም ሁሉ እጅግ ደስ ብሏቸው ወደ ቤታቸው ሔዱ። የስጦታውም ብዛትና የልደቱ ዛፍ አኳኋን ፤ ያሰናዷዎቹም አቀለጣጠፍ፤ ያለቃቸውም የልጅ እስፋው መጠንቀቅ፡ እጅግ የሚመሰገን ነበር። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ በዓል እንደዚህ ሁኖ በደስታ ተፈጸመ። ብርሃንና ሰላም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ፤ለልዕልት መነንና፤ ለመላ ኢትዮጵያም ረጅም ዕድሜ እየተመኘ እንኳን የደስታ በዓል ያደረግላችሁ ይላል።

ስለ ፍቅርና አገልግሎት ማኅበር

ታኅሣሥ ፲፯ ቀን የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ማኅበራቸው የተመሠረተበትን ቀን ለማክበር በነፃ ልጆች ትምህርት ቤት ተሰብስበው ነበር ። በዚያን ጊዜ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር አቶ ያሬድ የትምህርት ቤቱን አኳኋን በየክፍሉ እየዞሩ አሳዩ። ተማሪዎችም ተሰልፈው እንደ ሰልፈኛ አካሔድ እየተራመዱ በማረ አቀባበል ተቀበልዋቸው ። ቀጥሎም የትምህርታቸው ክፍል አናጢ በአናጢ ስፍራ ፤ሸማኔው በሸማኔ ስፍራ ፤ ሰፊ በስፌት ስፍራ፤እየሆኑ ታዩ። የሥራውንም አኳኋን መጀመሪያ ጊዜ ሲሆን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበረ ።



ከዚህ በኋላ ማኅበሩ ለበዓል ወደተሰናዳው ስፍራ ገብተው የማኅበራቸውን ጉዳይ ጀመሩ። ልጆቹም በየረድፋቸው ቆመው ማለፊያ መዝሙር ይዘምሩ ነበር ። በዚያን ጊዜ የማኅበሩ ፕሬሲዳን ክቡር አዛዥ ወርቅነህ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

የተወደዳችሁ ወንድሞቼና ልጆቼ ።

እነዚህን ሦስቱን ዓመታት በደህና ስላለፍናቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን ። ወደፊትም ለመንግሥታችንና ለወገናችን በፍጹም ልብ አገልጋዮች ለመሆን እግዚአብሔር እንዲባርከን እንጸልያለን ።

በዚህ ባለፈው ዓመት ውስጥ የተማሪ ቤታችን ሥራ በመልካም ተኪያሂዶልናል ብዬ ልነግራችሁ በጣም ደስ ይለኛል ። ይልቁንም ተማሪዎቹን የሚጠብቅና የተማሪ ቤታችንም ጥቅም ፤ ያለው ሥራ የሚሠራ ወንድማችንን አቶ ያሬድን ስለማግኘቴ ዕድለኛ በመሆኔ ደስ ብሎኛልና ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርብለታለሁ ። ደግሞ ሴቶቹንና ልጃገረዶቹን የሚጠብቁትን የልጆችንም ምግብ እንደሚገባ ዘወትር የሚያሰ

ናዲትን እሜት ደሜን አመሰግናቸዋለሁ ። በዚህም ላይ ደግሞ ለዘሬው በዓላችን ይህን መልካም ምግብ ላዘጋጁልን ወይዘዝር ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

እንግዲህ ዲሬክቱሩ አቶ ያሬድ የተማሪ ቤቱን ወጪና ገቢ ፥ የልጆቹንም ሥራ በዝርዝር እንዲነግረን እለምንዋለሁ።

ነገር ግን ከዚህ አስቀድሞ ስለ ግርማዊት ንግሥታችንና ስለ ግርማዊ ንጉሣችን ጤና ጽዋችንን አንሥተን እንጠጣለን።

ከዚህም ቀጥሎ ዲሬክተሩ አቶ ያሬድ የሚከተለውን ተናገሩ ።

ክቡራን የፍቅርና የአገልግሎት ማኅበረተኞች ሆይ።

ግርማዊት ንግሥት በቸርነታቸው ይህን የተጋበዝንበትን ቤት ሰጡን፤ግርማዊ ንጉሥም በርኅራኄያቸው ብዛት አምስት ሺብር ሰጡን የተከከለውን ለትምህርት እርዳታ ለሰጡን ንጉሦቻችንን በአብርሃም ዕድሜ እግዚአብሔር ይጠብቅልን ዓሜን። በማኅበሩ ድካም የፍቅርና ያገልግሎት ተማሪዎች ወንድ እስከ ሴቶች ድረስ ንባብ ከጽሕፈት ድምርና የሒሳብ ትምህርት እስከ ማካፈል ደርሰዋል።የእጅ ጥበብ ሥራ የተማሩት ደግሞ ነፃ ድሆች ልጆች ሸማኔነትና ሐኪና መስፋት፥አናጢነት ድረስ፥አዙሎቹ ተምረዋል።ተከዚህም ጋር ተማሪዎቹ ቁጥራቸው ፶ ሁነዋል፥ አሁንም በቅርቡ ቀን የጠፍር ስፌት የብር አፍሳሽነት እንዲማሩ ከልብ የመንግሥታቸውን ድሆችና ደካሞች ሁሉ ለንባብ ትምህርት የሚሰበስቡ ክቡር አዛጋር ወርቅነህ፥ ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ፥ በነሱ መሪነት ማኅበራችን እስከዚህ ደርሰዋል ። ክቡር አዛገር ወርቅነህም በቅንነት ፍቅራቸው ሰውነታቸውን እያደከሙ ለአገራቸው ልጆች ንጹሕነትን አጽንተው የሚያጸኑ በጥበብ በፍቅር በውቀት ሥራቸውን ዘወትር በድካም ያሳያሉ። ስለዚህ ምንም አንደኛው ማኅበረተኛ እሳቸው ቢሆኑ የፍቅርና ያገልግሎት ማኅበር ሁሉ ሥራውን ትክክል በማስኬዳቸውና በመድከማቸው የልጆቹን አክሔድ ሁሉ ስለ ተመለከቱ ፍጻሜ ለሌለው ማስደሰቱን ለዚሁ በመልካም በዓላችን ተሰብስበን ምሳ አድርገን ፍቅራችንን በባታችን ፊት መግለጻችን ያስረዳዋል።ይልቁንም ደግሞ በሕመማቸው ምክንያት ወደ አውሮጳ ሒደው ሁለቱም ሐሳቢዮቻችንና የፍቅር ተጻማጆቻችን ከሰማነው ከክፉ ነገር አልፈው ወደዚህ መጥተው ከማኅበሩ ተቀላቅለው በበዓሉ ክብር አንድ መሆናቸው ለፍቅር አገልግሎት ታላቅ ዕድል ስለ ሆነለት ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል። ፍቅርና አገልግሎት ማለት በመስማማት መንፈሳዊ ሥራ ለማኖር አባት እናት የሌላቸውን ደካሞች ድሆችን ለመሰብሰብ የተወሰነች ማኅበር ናት።ይህቺ ማኅበር ከልብ በፍቅርና ሥራ የቆመች ስለ ሆነች ከራሷ ጥቅም ፈጽማ የራቀች መሆንዋን የሚመሰክርላት ዘመድ አቅም የሌላቸውን ደካሞች ወንድሞቹን ለትምህርት ተመሬት እያነሣች የምትደክምበት ፍሬዎቿ እነሆ እንደምታዩዋቸው ጀምረዋልና ይህን የጀመሩትን እንዲያስፈጽማቸው እግዚአብሔርን እለምናለሁ።ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ደኅንነት፥ ስለ ፍቅርና አገልግሎት ጽናት፥እመኛለሁ።ያሬድ ወልደ የሱስ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዘውድ ጭነው ከነገሡ ወዲህ ።

በየጊዜው ስለ ሥራ መሻሻል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በዘመናቸው ሕዝባቸውን በሥልጣኔ ከፍ ከፍ ለማድረግና አገራቸውን ለማሳደግ ፍጹም ምኞታቸው ስለሆነ የኢትዮጵያ ልጆች ተምረው ክፉና በጎን የሚለዩበትን ንጉሥንና እግዚአብሔርን የሚፈሩበትን የሚበቃ እውቀት ለማግኘት የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት በግድ እንዲማሩ አዋጅ ማስነገራቸውን ከሁን ቀደም በ፲፭ ጥቅምት በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ጽፈናል ።

የትምህርት ሚኒስቴርነቱን ሥራ እየሠሩ አዋጅ የሚጸናበትን ሕፃናቱ ተምረው እውቀት የሚያገኙበትን መንገድ ለመምራት የታዘዙ ያገር ግዛት ሚኒስትር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ነበሩና ፤ አሁን በውሥጣቸው ሁኖ የትምርህት ሚኒስቴርነቱን ሥራ የሚሠሩ ከዚህ ቀደም በእውቀቱና ባገልግሎቱ በመታመኑም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ጸሐፊ የነበረ ያገሩንና የውጭ አገርንም ቋንቋ አጥርቶ የሚያውቅ አቶ ማህሉ ፀዳሉ የጥበብ የትምህርት ዲረክተር ተብሎ ከተሾመ ወዲህ የትምህርት ሚኒስቴር ቤት ስለ ተከፈተ የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢትዮጵያን የሚወዱ ሰዎች ሁሉ ደስ ብሏቸዋል ።

ደግሞ ግርማዊ ተፈሪ አዋጁን ብቻ አስነግረው ዝም አላሉም ነገር ግን በኢትጵያ ምሥራቅና ምዕራብ፥ሰሜንና ደቡብ፥ በየሻለቃው አገር፥ በየትልልቁ ከተማ ሁሉ፥የሚያስተምሩ መምህራን እየተላኩ እንዲያስተምሩ የሚላኩትም መምህራን እውቀታቸው የሰፋ ምግባራቸው የቀና እንዲሆን እየመረመረና ለሥራቸውም የሚያስፈልጋቸውን ደምብ ከግርማዊ ንጉሥ እየተቀበለ ለመምህራኑ እንዲሰጣቸው ለትምህርት ለጥበብ ሚኒስቴር ዋና ዲረክተር ለአቶ ማህሌ ፀዳሉ ትእዛዝ አሳልፈዋል።

ይህ አሳብ ለኢትዮጵያ ዋና ሕይወቷና ጥቅሟ ስለሆነ የግርማዊ ንጉሥ ምኞታቸውን በመልካም መንገድ እንዲፈጸምላቸውና በዘመናቸውም ኢትዮጵያ በሥልጣኔና በእውቀት ስታድግ ለማየት እንዲያበቃን ተስፋ እያደረግን ለግርማዊ ንጉሣችን ረጅም ዕድሜ ስጥልን እያልን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

Application.

Pratique du Programme des Reformes de S M Le Negus Teferi.

Ensuite de son Couronnement

Dans notre numéro du 15 Tekkemt 1921, nous avons déjà relaté la ferme volonté de Sa Majesté le Negus Teferi d'élever au cours de Son règne le degré de civilisation et de développement intellectuel de Son Peuple. Sa Majesté vient de promulguer une loi institua l'instruction obligatoire pour la jeune génération qui recevra une éducation morale ayant á sa base la crainte de Dieu et le respect du Roi

Jusqu'ici, Son Excellence le Dedjazmatche Wolde Tsadik, Ministre de l'intérieur, était chargé seul de l'application de la loi sur l'instruction publique et des nombreuses questions d'ordre pratique qu'elle soulève.

Sa Majesté vient de créer un Département spécial pour l'instruction publique. Cette innovation rencontre l'approbation unanime du peuple Ethiopien et des amis de l'Ethiopie. Ce département de l'instruction Publique, adjoint au Ministère de l'intérieur, est placé sous la Direction Générale d'Ato Sahlé Sedalou, qui occupa autrefois le poste de secrétaire Générale aux Affaires Etrangères auquel il fut appelé à raison de ses connaissances étendues, de sa fidélité et de son dévouement.

Sa Majesté ne s'est pas bornée à promulguer la loi sur l'Instruction publique, mais Elle s'est préoccupée aussi de son application pratique. Dans ce but Elle a prescrit à Ato Sahlé Sedalou Directeur Général de l'Instruction Publique de choisir des professeurs qualifiés, tant par leur connaissance qui par leur moralité, de leur transmettre les programmes et les réglements élaborés par Sa Majesté Elle même et de les mettre en activité dans toutes les Provinces de l'Empire.

Ces décisions présentent un intérêt considérable et même vital pour l'Ethiopie. Nous prions Dieu d'aider à l'heureuse réalisation de ces volontés royales, de permettre que l'Ethopie grandisse sous le règne de Sa Majesté le Négus, que la Providence accorde longue vie à Sa Majesté et nous permette de voir le développement prochain de notre Patrie.

በውጭ አገር የሚታተሙ ጋዜጦች ስለ ኢትዮጵያ በሚጽፉት በአንድ አንድ ቃል ውሥጥ የሚያትሙትን ሐሰት ነገር ለማስቀረትና ስሕተቱንም ለማረም ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ይህንኑ ለማስረዳት ቀጥሎ የተጻፈውን ይገልጻል።

መጀመሪያ ።

የውጭ አገር ጋዜጦች ብዙ ጊዜ እውነትና ሐሰት መሆኑን በማናቸውም ረገድ ሳይመረምሩ በአገራችን ላይ ሐሰት የሆነና ምክንያቱ ያልታወቀ ቃልእያተሙ ያወጣሉ ብዙ ጊዜ እነዚህን ሐሰት ቃሎች የሚናገሩ ከመንግሥት ከንሰሲዮን እየተቀበሉ ያተርፉናል ብለው ያሰቡትን ትርፍ ለማግኘት ሳያውቁበት የቀሩ ሰዎች ናቸው። አንድ አንድ ጊዜም ይህን የመሰለ ነገር እያስመሰሉ ለባለጋዜጦች የሚነግሯቸው በታላቅ ነውር ምክንያት ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የተፈረደባቸው ሰዎች ናቸው ።

ሁለተኛ

የግርማዊት ንግሥታችን ስማቸው ዘውዲቱ ነው። አንድ አንድ የአውሮፓ ጋዜጦች ግን ዘውዲቱ የተባለውን ስማቸውን እየለወጡ በአይሁዳዊቱ ስም ዩዲት እያሉ ይጽፋሉ።

ደግሞ ዘውድ ከመጫናቸው አቀድሞ ልዕልት ወይዘሮ ዘውዲቱ ይባሉ ነበር።ዘውድ ጭነው ከነገሡ በኋላ ንግሥት ዘውዲቱ ይባላሉ እንጂ ወይዘሮ ዘውዲቱ አይባሉም።አንድ አንድ የአውሮፓ ባለጋዜጦች ግን ወይዘሮ ማለት ስም እየመሰላቸው ንግሥት ወይዘሮ ዘውዲቱ እያሉ በማተማቸው ስሕተት ያደርጋሉ።

ሶስተኛ

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በመስከረም ፳፯ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ዘውድ ጭነው ከነገሡ በኋላ ንጉሥ ተፈሪ ተብለዋል።አንድ አንድ የአውሮፓ ባለጋዜጦች ግን ይህን ሁሉ ካለማስተዋላቸው የተነሳ ራስ ማለት ስም እየመሰላቸው ንጉሥ ራስ ተፈሪ እያሉ በማተማቸው ስሕተት ያደርጋሉ·

A titre d'information, dans le but de contribuer à redresser certaines erreurs ainsi que le faire cesser si possible la publication dans la presse étrangère de recits mensongers au sujet de l'Ethiopie,

le journal „Lumière et Paix„ estime utile de déclarer

1.

Nous avons constaté à plusieurs reprises que la Presse Etrangère, sans contrôler en aucune manière la vérité de ses infomations, publie des articles profondément tendancieux et inexacts sur notre Pays.

La plupart du temps ces articles émanent de personnes qui, ayant obtenu du Gouvernement de concessions importantes, n'ont pas su en tirer tout le profit qu'elles en attendaient.

D'autres fois, ce sont des individus, expulsés du pays pour fautes graves, qui surprennent la bonne foi des journalistes.

2.

Sa Majesté l'Impératrice d'Ethiopie porte le nom de ZEODITOU; Cependant plusieurs journaux étrangers l'appellent du nom israélite; JUDITH.

Avant accession au trône Impérial, Sa Majesté avait le titre de Woïzero (Princesse) Zéoditou.

Son titre exact actuel est: Sa Majesté l'Impératrice Zeoditou.

Pensant à tort que "Woïzero" est un nom propre (et non pas un titre) plusieurs journaux étrangers nomment S. M. l'Impératrice d'une manière erronée, S. M. l'Impératrice "Woïzero "Zéoditou.

3.

Depuis Son Couronnement, le 27 Mask. 1921, Son Altesse Impériale Teferi Makonnen a Pris le titre de Négus (Roi) Teferi.

Plusieurs journaux Etrangers continuent à lui donner le titre de „ Ras „ dans l'idée fausse que „ Ras „ est un nom propre, et ils appellent à tort Sa Majesté le Roi Teferi S. M. le Roi Ras Teferi„.

ስለ ክቡር የቤልጅክ ሚኒስቴር ከአዲስ አበባ መሔድ ።

ሙሴ ዠራር የቤልጋዥክ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ወደ አገራቸው ለመመለስ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት በባቡር ተሳፍረው ሔዱ ኢትዮጵያ በነበሩበት በስድስት ዓመት ውሥጥ ከመንግሥቱም ከሹማምቱም ተስማምተው ሥራውን በፍቅር፡ ሲሠሩ እስከ ዛሬ ቈይተው ነበርና አሁን ወደ ሀገራቸው በጭራሽ መሔዳቸው በተሰማ ጊዜ ለወዳጆቻቸው ሐዘን ሆነ ።

ስለ ሙሴ ዠራርም ክብር ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የዲፕሎማቲክን ሰዎች ሁሉ ራት ጋብዘው ነበርና በሸኙ ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ ቀጥለው የተጻፉትን ቃሎች ተናገሩ ።

ክቡር የውጭ አገ. ሚኒስትሮች ተቀዳሚ ሆይ ።

ከመሔድዎ አስቀድሞ ዛሬ ከእርስዎ ጋራ እናመሽ ዘንድ ፈቃዳችን ሆነ ወደ አገርዎም እንዲመለሱ መጠራትዎን በመስማማታችን አዘንን የተግባርዎን መልካምነት በጎ አድራጊነትዎንና ተወዳጅነትዎን ለመንግሥታችንና ለእኛም ለእራሳችን በልዩ ልዩ ጊዜ ስለገለጹልን ስለ ታላቅ ዋጋ እንቈጥረዋለን።በአዲስ አበባም የኖሩበት ጊዜ ሁሉ መልካም መታሰቢያ ሁኖልን ይኖራል።መልካም ምኞታችንም ይከተልዎታል።

ወደ አገርዎም አሁን በሚሔዱበት ጊዜ ለንጉሥዎ ለቤተ ዘመዶችዎ ሁሉ ስለ ደስታቸውና ስለ ጤናቸው የምንመኘውን መልካም ምኞት እንዲያቀርቡልን እንለምንዎታለን ።

ሙሴ ዠራርም ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

ግርማዊ ንጉሥ ፈቃድዎ ሁኖ አሁን ስለኔ በተናገሩት መልካም ቃል ሰውነቴ በደስታ ስለተነካ ጥልቅ የሆነ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ ።

ስለኔም የተናገሯቸው ቃሎች ከባድ ቃሎች ናቸውና ይህን ያህል የሚገባኝ አይደለሁም ።

በኢትዮጵያም በተቀመጥሁበት ዘመን ሁሉ ሥራዬንም ለማቅለል ለእኔም ለራሴ ቢሆን የተደረገልኝ የግርማዊና የመኳንንቶቹ በጎ ሥራ እጅግ ብዙ ነው ምንም አሁን ወደ አገሬ ጨርሼ መሔዴ ቢሆን ልቤ በኢትዮጵያ መቅረቱን ለግርማዊነትዎ አደላድዬ አስታውቅ ዘንድ ይፍቀዱልኝ ብለው ጨረሱ።

አዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።

ማስታወቂያ ።

የኢትዮጵ መንግሥት ዜጋ የሆኑ አቶሞቢል የሚነዱ ሰዎች ሁሉ ለነጂነት እየተቀጠሩ ከሚያገኙት ደሞዝ ሁለቱን እጅ ለምግባቸውና ለልብሳቸው እየተቀበሉ አንዱን እጅ ወደ ማዘጋጃ ቤት ድረስ እያመጡ እንዲያስረክቡ ደምብ ሁኑዋልና የአቶሞቢሎች ጌታ የሆኑት ሰዎች ሁሉ ለነጂው ከሚሰጡት ደሞዝ ላይ ሁለቱን እጅ በቀጥታው ለነጂው ሰጥተው የአንዱን እጅ ወደ ማዘጋጃ ቤት ድረስ እያመጡ እንዲያስረክቡ መታዘዛቸውን እናስታውቃለን ።

ይኸውም የሆነው አቶሞቢላ ስለሚነዱት ሰዎች ጥቅም ከደሞዛቸው ላይ አንዱን እጅ ማዘጋጃ ቤት እየተቀበለ እባንክ እንዲያኖርላቸው ነውና የኢትዮጵያ ዜጋ የሆኑትን አቶሞቢል ነጂዎች የቀጠሩ የአቶሞቢል ጌቶች ሁሉ ከዚህ በላይ እንዳመለከትነው ከነጂዎች ደሞዝ ላይ አንዱን እጅ ወደ ማዘጋጃ ቤት እያመጡ በየወሩ ያላስረከቡ እንደሆነ ለገንዘቡ ኃላፊነት ያገኛቸዋል ።

ይህም ሥራ የሚጀመረው ከጥር ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ጀምሮ ነው ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም

የአዲስ አበባ ከተማ ከ፡ ቲባ ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ፣ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ፉርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማነዳሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ሻረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።


COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አራብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድሪስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አሉው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጅነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ኒለያ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የሩማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆን ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ።ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።፡


GOODYEAR
ALL WEATHER
GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
1-28-7
GOODYEAR
ጉድይር ጎዙ

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ፤ ቍጥር ፭
5 me ANNÉE № 5

ሐሙስ ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ።
JEUDI 17 JANVIER 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ያሥረኛ ገጽ ተከታይ ።

(፱)ሀብት የምትተላለፍ (የምትለዋወጥ) ነች ።

መለዋወጥ (መዘወር) የምንለው፡ አንድ ነገር ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሲያልፍ ነው ። ምሳሌ አንድ ሰው የቀላድ ወይም የፋብሪካ ጌታ ዋነኝነቱን ለሌላ ሲያስተላልፍ (ሲያወርስ)እንዲሁም አስተማሪዎች ወይም መጻሕፍት፡ ጥቅማቸውና ደስታቸው ወደ ሌላው ሲተላለፉ ፥ መዘዋወር እንለዋለን ።

እንደነዚሁም የሚፈለጉ ነገሮች ብዙዎች ነበሩ፡ ግን ካንዱ ሰው ወደ ሌላው ሊያልፉ አይችሉም ። ምሳሌ አንድ ጌታ አንድ ጠንካራ አሽከር ሊገዛ(ሊያሠራ) ይችላል ።ኃይሉን(ጕልምስናውን)ግን ሊያገኘው አይችልም።እንዲሁም ቢታመም ትልቅ ሐኪም ሊያሠራ ይችላል፡ጤናውን ግን ሊገዛው አይችልም። እንዲሁም። ቤተ ዘመዶች ፍቅር ሊገዛ ወይም ሊሸጥ ፥ የወዳጆች ክብረት፡እውነተኝነትና ጥሩ ሕሊና ደስታና መልካም ንግግሮች ሁሉ፡ በሀብት ሊገዙ አይችሉም ። እነዚህ ሁሉ በፍጥረታቸው የማይደረሱ (የማይተላለፉ) ናቸው ።

ስለዚህ ኤኮኖሚያ ፖሊቲክ የደስታ ነገሮች ሁሉ ለማወቅ ልትፈትን አትመኝም ። እስዋ የበጎነት ነገር ሞራሊቴ ግድ የላትም ። ስለምን ቢሉ ሊሸጡና ሊለወጡ አይችሉምና፡ ሀብት አይደሉም ። አንድ ድኻ ሰው፤ ጥሩ ጤና፡ የረጋ ሕሊና፡ መልካሞች ወዳጆች ያሉት ፥ ከሀብታም ይልቅ ባለ ደስታ ነው ቢባል፤ ሌላው ሀብታም ሰው ስለ ሆነ፡ ደስታውና የሕሊናውን ጥሩነት ገንዘቡ ያጠፋዋል ያሳጣዋል አልተባለም ።

ሀብት ጥቅም ብቻ አይደለችም፤ ደግም ነች። ስለምን ሸካራ ሥራ ታስወግዳለች፡ በድንገት የሚወድቅ ፍራት (ድንጋጤ) ታርቃለች፤ ብዙ ደስ የሚያሰኙ ነገሮችና የሚለዋወጡ ሥራዎች ለማግኘት (ለመግዛት) ትፈቅዳለች ።

(፲) ሀብትና ጥቅም አገልግሎት ።

ጥቅም ያ በቀጥታ ወይም በዙርያ ደስታ የሚሰጥ ፥ወይም ድካም (አዘን) የሚያመጣ ነው» ብሎ ሴኖር እንደ ወሰነ ባፊት አመልክተናል ።

አስረጅ ምሳሌ ምግብ ራብን ያስወግዳል፡(ይከለክላል) መድኃኒት ቃንዛን(ንዝናዜ)ያቀላል።ሙዚቃ መልካም ሁኖ ሲመታ ደስ ያሰኛል ። ግን ታላቅ ደስታ እንደሚሰጥ ወይም ታላቅ አዘን (ጉዳት)እንደሚያመጣ ለይቶ በትክክል ለመፍረድ ችግር ነው፡ ጥቅም በጣም ታላቅ የምትሆነው (ድካሚቱ) ጕዳቲቱ ስታንስ ወይም ደስታይቱ ስታድግ እንደሆነ ግን እናውቃለን።ቀጥለንም ጥቅም በቀጥታ ትሁን ወይም በዙርያ ደስታ እንደምትሰጠን መወሰን ያስፈልገናል ። ለምሳሌ በቀጥታ ደስታ የሚሰጡ እንደምንለብሰው ልብስ፡ወይም እንደምንመገበው እንጀራ በዙርያ ደስታ የሚሰጡንና የሚያገለግሉን የሚጠቅሙን እንደሚሠሩት ሽማኔዎች ወይም እንደ መጋገሪያው(ማብሰያው)ምጣድ ናቸው። ላሳጥረው ሀብት የሚባል፡ ሰው የሚፈልገው የሚጠቅም የሆነ ነገር ሁሉ የሚገዛና የሚሸጥ ነው ። አገልግሎት የሚባል መሣርያ ሁሉ ነው።

ሚካኤል ተሰማ ።

በሚከተለው ቍጥር ይታተማል ።

ስለ ዘበኞች ትጋት ።

አንድ አድለ ቢስ ልጅ ያባቱን ገንዘብ ሰርቆ ሌሊት በኦቶመቢል ሊሔድ ኦቶመቢል አስመጥቶ ኦቶመቢል ነጂውም በቀጠሮው ከማታው በአኩል ሰዓት ጀምሮ እስከ ሶስት ሰዓት ድረስ ነጂው ኦቶመቢሉን አባቱ ቤት አጠገብ አቁሞ ሲጠብቅ ትጉዎቹና ንቁዎቹ የከተማ ዘበኞች የዚህን የኦቶመቢል ሁናታ ለመረዳት ተሠውረው፡ደፍጠው፡ሲጠባበቁ ያም ያልታ–

ደለ ከንቱ ልጅ ሁለት ጊዜ ተመላልሶ ከነጅው ጋራ እየተመከረ አባቱ እስኪተኙለት እቤት ገብቶ ቆይቶ ይሄም ሌባ ያባቱን ሽያ ብር ሰርቆ ሊሳፈር ሲሄድ ዘበኞች ይዘው ቢመረምሩት በመሰል መክፈቻ ሰርቆ መውሰዱን አምኖ ታሥሮ ሳለ አባቱ በማግሥቱ መጥተው ከሁን ቀደምም በያይነቱ ቁልፍ እየከፈተ የወሰደብኝ ፳፱ ብር ያህል ሆኖአል። አሁንም ይኸን ያገኘሁት በዘበኛ ጥበቃና ትጋት ነው አሉ።ስለተያዘላቸውም መንግሥታቸውን እያመሰገኑ፤የዘበኞቹንም፤ጥንቃቄ እያደነቁ፤ገንዘባቸውን ይዘው ሄዱ።

፪ኛ፤ አንድ ነጋዴ ለንግድ ሞጆ ሄዶ ሳለ ከውጭ በቅሎቹን ሌሊት ሁለት ሌቦች ከታሠሩበት ፈተው ይዘውበት ሲሄዱ ነቅቶ ከብቶቹን ለማስጣል ከሌቦቹ ጋራ እየተሯሯጠ ሲታኮስ ሌቦቹ ባለገንዘቡን በጥይት መትተው፤ሁለቱን በቅሎቹን ይዘው ሌትና ቀን፤ወደ አዲስ አበባ ለመሸጥ መጥተው፤በቅሎቹንም ለዘጠና ብር ሸጠው፤ ሁለቱ ሌቦች ተከፍለው ኖሮ የከተማችን ዘበኞች በተሰጣቸው ሥልጣን መጥፎ ሐሳብና መጥፎ ሥራ የሚሰሩትን ወስላቶችና አታላዮች ሲመረምሩ፤ አንደኛውን ሌባ አግኝተው ይዘው ቢመረምሩት፤ ሰውየውን በጥይት መምታታቸውንና በቅሎቹንም ወስደው መሸጣቸውን አምኖ፤ አንዲቷንም በቅሎ ከሸጧት መስክ ስትግጥ ተገኝታ፤ እሲዘ ለባለቤቶቹ ተመለሰች። እነሱም የመቱት ሰው ስለሞተ እሱም ከሟቹ ዘመዶች ጋራ ስለ ደሙ ተያይዞ ሊፋረድ ቆይቷል ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ለወይዛዝሮች የሚሆን የማስታወሻ በረከት ።

ክቡራን የሀገሬ ወይዛዝሮች ለታላቁ ማዕርጋችሁና ለተመልካቹ አእምሮአችሁ የሚገባ ሰላምታዬን አቀርቤላችሁ ትንሽ ለምክር የሚሆንዋችሁ ቃሎች ጽፌላችኋለሁና ትምሕርትም የተማራችሁ ከልባችሁ እንድትመለከቱትና እንድታስቡት ፤ ትምሕርትም ያልተማራችሁ እተማሪ ቤት ሄዳችሁ እንድትማሩትና እንድታጠኑት፤ ከስንፍና ጕጆ ወጥታችሁ ወደ ትጋት አዳራሽ ገብታች እያጠናችሁ ትፈጽሙታላችሁ በማለት ብርታታችሁን እየተማመንኩ ልጽፍላችሁ ሐሳቤ ነው ።

የተማሩ ወይዛዝሮች ባሎቻቸውን እንደሚረዱና ለጉዳእቸው እንደሚጥሩ የሚያመለክቱ ቃሎች ከሁንቀደም ብዙዎች የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ጽፈውላችሁ ነበር ።

የተማሩት ለትዳራቸው ባልና ሚስቱም ተሳስበው ይኖራሉ። ይኸውም መተሳሰባቸው ከፋቸው ሳይሆን ከልባቸው፤ ባልየው ባንድ ፋብሪካ ቤት ሲሠራ ሚስቱም ባንድ ቦታ ተቀጥራ እየሠራች፤ ሁለቱም በወር በወሩ የሚያገኙት ደሞዛቸው ለትዳራቸው በቅቷቸው፤ሕይወታቸውን ጠብቀው በሥራቸውና በሚያገኙት ገንዘባቸው፤ በዚህ ዓለም እስከሉ ድረስ ደስ ብሏቸው ይኖራሉ ይባላል ።

፪ኛ፤ እናንተ ግን እንኳንስ ለትዳራችሁ የሚበቃ ገንዘብ ሠርታችሁ ለማግኘትና ላመት ልብሳችሁ የሚበቃ ገንዘብ ያለማግኘታችሁን ባንድ ዓመት ውሥጥ የምትሠሩትና በሥራችሁ የምታገኙት ያስረዳናል። ባንድ ዓመት ውሥጥ ከንዲት እረዳት እጅሥራ አግቢ ጋር ምናልባት በትጋት ብትሠሩ ፩ ኩታ ብታደርሱ ነው። ያውም ባመት የተጨረሰ አንዱ ኩታ ደህና ሸማኔ ሲሠራው ለጁ ፭ ብር ያህል ይጠይቃል ። ለሀሩም ፫ ብር ያህል ያወጣል፤ ጥጡም ፬ብር ያህል ይጨርሳል።ይኸውም ኩታ ከናንተ ድካም በተቀር በሥራው ፲፩ ብር ያህል ጨርሶ በሽያጭ ዋጋ ቢገመት ከአርባ ብር ያነሰ ነው እንጂ የበለጠ አያወጣም።እንግዲህ ከ፵ው ብር ውሥጥ ፲፩ ብር ሲነሳለት ፳፱ብር የናንተ እጅ ዋጋ መሆኑ ነው። ይኸው ፳፱ብር ግን እንኳን ለናንተ ልብስና ቀለብ ሊሆን ቀርቶ ለዚያች ለረዳት እጅሥራ አግቢ ገረዳችሁ ለልብሷ እንኳን አይበቃም። በዚህ ዓለም ላይ እንኳን ባልና ሚስት ቀርቶ እናትና ልጅም ቢሆን ተረዳድተው ካልሠሩና ካልተሳሰቡ፤መሰለቻቸታቸውና መጣላታቸው አይቀርምና፤ሥራችሁን በትጋት ብትሠሩና ብታስቡበት፤ይሻላችኋል።

፫ኛ ፤ በአንድ በኩል ስንመለከት ከእናንተ ሥራ ይልቅ የድሆች ሴቶች ሥራ ኤውሮፓችን ሴቶች ትጋት ተከታታይና በሥራቸው ብርታት ያስረዱናል። የሀገራችን የደሃ ወገኖች ሴቶች ለራሳቸውና ለባላቸው ከንድ ሁለት ሙሉ ልብስ ለራሳቸውና ለባሎቻቸው እየሠሩ በዚሁ ላይ የትዳራቸውንና የጓዳቸውን በትጋት በመሥራታቸው ጥንክርናቸውንና ትጋታቸውን ይኸ ሥራቸው ምስክራቸው ነው።

፬ኛ፤ መንገድ ወይም ሽርሽር ስትሄዱ በግራና በቀኝ ደጋፊ፤ በፊትና በኋላ አጀብ፤ታጅባችሁ ትሄዳላችሁ።ቀዋሎም እራታችሁ ደንገ ጡሮች በክብት አስከትላችሁ፤ ከነሱም ቀዋሎቿና ፯ ገረዶች በእግራቸው ሆነው ይከተሏችኋል። እናንተ ባመት የምትሠሩት ሥራችሁ ፳፱ብር ሆኖ እናንተ ሥራ አስፈትታችሁ የምታስከትሏቸው ገረዶች ፯ና ፰ሲሆኑ ጊዜ ይህ የነኝህ ቀለብና ደሞዝ ከየት አምጥታችሁ ልትሰጡአቸው ነው ። ባላችን ይከፍልልናል ብትሉ ባላችሁ የሚሠራው እንደ እራሱ ነው ለናንተና ላሽከሮቹ ፤ለደንገ ጡሮቻችሁና ለገረዶቻችሁ የሚከፈለውን ወጭ መመልከትና ማሰብ ነው።

እኔንስ የሚገርመኝ በቅሎዋ ፈጣሪዋ የሰጣት ዓይኖች እያሉአት፤ለዚሁም ተቀማጩ ወደ ፈቀደበት የሚመራበት ከዋቂዎች ዘንድ የተሠራ ልጓም ተደርጎበት ስትሄድ፤ ከዚህ በላይ እንደ መሪ ዓይነት እፊታችሁ የምትአስከትሏቸው ገረዶቻችሁ ያሳዝናሉ ።

፭ኛ፤ እመቤቶቼ ሆይ እረ አስተዳደራችሁን ጉብኙ።ሥራፈትነትንም ናቁ፤ ጥበብንም አስቡ፤ ለመታጀብም አትጣሩ፤እከሌ ቢወልድ እከሌ እያላችሁ ከመኩራት በሥራችሁ መኩራት ይበልጣልና።ዘር ከተቋጠሩ ዶሮ ለሚጨቷ አያት ናት እንደሚባለው ሁሉ ነው ዳግም በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እርዳታና ደግነት ለሀገራቸው መከበሪ፤ለወገናቸው መጠቀሚያ፤ለመማር ሲሉ ብዙዎቹ ልጆቻችሁና ወንድሞቻችሁ እውቀትና ሥልጣን ትጋትና መሥራት ከሉበት አገር ለትምሕርት መሄዳቸውን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ።እነዚህ ወንድሞቻችን ከዚያ ከሄዱበት አገር የታዘዙትን ሥራ ፈጽመው በተመለሱ ጊዜ እራሳችሁና ልጆቻች

ሁም ይሉንታን ንቀቻችሁ፥ በጥበብ ታጥቃችሁ፥ የሥራ መስታዋታችሁን ዘርግታችሁ፥ ስንፍናን አበጥሮ የሚአጠፋ ማዶአችሁን ሺጣችሁ ጥበብን ለሀገራችሁ ሸምተው የሚመጡበትን ወራቶችና ቀኖች እየናፈቃችሁ ብትጠብቋቸው እነኛም የሀገራችሁ ልጆች በችግርና በጉዳት በሥራቸው ብዛት የተጉሳቈሉ ሰውነቶቻቸው ሀገራቸው በገቡ ጊዜ በእናንተ አረማመድ ደስ እያላቸው ከልጆቻችሁም ውሃ አጣጭአቸውን ያገቡ ይቀመጣሉ ግን ልጆቻችሁን ባታስተምሩ፥ አስተዳደራችሁን ሳትጉበኙ ብትቀሩ መጭዎችም ወንድሞቻችን ከበዕድ እየተጋቡ እዚህም ያሉት ወጣቶች ከስንፍናችሁ እየራቁ፥ከበዕድ እየተጋቡ፥በተቀመጡ ጊዜ እንዳይነዳችሁ ስል አሳስባችኋለሁ አሁኑ በሥራና በትምሕርት ላይ እንድትጣጣሩ ።

በቀለ ዘለቀ።

ስለ ትምህርት ።

ብርሃንና ሰላም ስለ ተማሪ ቤት ማቆም አራት ዓመት ሙሉ ሲጮኽ እየተሰማ የኢትዮጵያ ዙፋን ደጋፊዎች (አገረ ገዦዎች) ጩኸቱን እየሰሙ ቸል በማለታቸው በሩቅ ሆኖ የሰማ ሳይታዘብ ይቀር ይመስላቸዋልን ። በገራችን ያሉ ዛሬ መኳንንቶች እንደ ቀድሞ ጊዜ ስንኳ ገንዘብ ችግር አያገኛቸውም በድሮ ዘመን ግን ወታደርነት የሚፈልግ ሰው በዳር አገር በተሾሙ ሻለቆች ቤት ይበዛ ነበር።ስለዚህ በዳር አገር የሚኖሩ ገዢዎች ቤተ ሰብእ እየበዛባቸው ተቀማጭ ገንዘብ አያገኙም ነበር ይባላል። ዛሬ ግን በዳር አገር ያሉ መኳንንቶች የቤት አሽከሮቻቸው ጥቂቶች ይሆናሉ ። ገቢ ገንዘባቸውም ለከተማ ቤት ማደሻ ወጭ ይሆን እንደሆን ነው እንጂ በጭፍራ በኩል በጣም አያሠጋቸውም። በመንግሥት ፈቃድ ለሻለቆች የየሚታዘዙ ሠራዊት ቢኖሩዋቸው የድካማቸውን ዋጋ መንግሥት ይሰጣቸዋል።ስማቸውም የቁጥር ጦር ይባላል አሁን ይኸን እንደ አርአስት መነሻ አድርጌ ስለጻፍኩት ዋናው ወደፊት ይህ ነው መንግሥት ስለ ሕዝብ ጥቅም ትምህርት እንዲሠፋ አዋጅ አደረገ ስለጥበብ ተማሪ ቤትም ዲረክተር ሾመ ። እንግዲህ ደንጊያን ካልወቀሩት እንጨትን ካልጠረቡት ከሥራ ሊገባ አይችልም የኢትዮጵያ ልጆችም የተማሪ ቤት ተሠርቶ መምህር ካላገኙ ሊማሩ አይችሉም ። ደግሞ ተማሪ ቤት አገረ ገዦዎች ሀብታሞች ካላቆሙት ድሆች ሊሠሩት አይከናወንላቸውም። ስለምን ማለት የገንዘብ ኃይል የነሣቸዋልና ። ለምሳሌ አንድ ባለማዕርግ ሰው ቤት ሥራ ቢጀምር ሕዝቡን በትሕትና ቃል ይለምናቸዋል።ይላልም ታላላቆቹ አባቶቹ ታናናሾች ወድሞቹ ቤት ሥራ ጀምሬያለሁና እርዳታ እንድታደርጉልኝ እምናችኋለሁ ። የተለመኑትም ሰዎች በገንዘብ፥በእንጨት፥በማር ይረዱትና የተጀመረው ቤት በቶሎ ይፈጸማል እንዴት ያገራችን መንግሥት ስለሕዝቡ እውቀት ሲጣጣር ድሆችም እንደ አቅማቸው ለመርዳት ሲፋጠኑ ባለብዙ ሚሊዮኖች አገረ ገዦዎች ወደ ኋላ በመዘግየታቸው ብርሃንና ሰላም አይወቅስም ። ሰማችሁ እንግዲህ መኳንንትና አገረ ገዦዎች በፈቃዳቸው ገንዘብ አውጥተው የተማሪ ቤት እስኪያቆሙ ድረስ ሳይዘገዩ አይቀርም ። ለወደፊቱ ግን ለተማሪ ቤት እርዳታ እንዲህ ቢሆን ይሻል ይመስለኛል። ማንም አገረ ገዥ የሆነ ሁሉ ከገቢ ገንዘቡ ከሥር አንድ እንዲያወጣ የመንግሥት ትእዛዝ ቢሆን ያስፈልጋል ። እነሆ አንድ ሻለቃ (አገረ ገዥ) በዓመት መቶ ሺ ብር የሚያገኝ አለ አምሳ ሺ ብር የሚያገኝ አለ ፥ አሥር ሺ ብር የሚያገኝ አለ የዚህም ከሥር አንድ ቢወጣ ፲፮ሺ ይሆናል ። ከሰስት ሻለቃ ይህን ያህል ገንዘብ ሲገኝ በመላ ኢትዮጵያ ያሉትን ብናስብ እንዴት ብዙ ብዙ እርዳታ ይገኝ ይሆን? ። ነገር ግን አንዳንዶቹ መኳንንቶች ገቢያቸው ማር ፥ ዱቄት ፥ ብረት ፥ ሸማ፥እንስሳ፥ነው።የዚህም ግምት እየተጻፈ ከሥርአንዱን በተገመተ የገንዘብ ሒሣብ ረገድ ለተማሪ ቤት ሊሰጥ ይቻላል።እንደዚህ የሆነ እንደሆነ የተማሪ ቤት ለእርዳታዋ በዓመት ፩ ሚሊዮን ብር አተጣም። አስተማሪና ተማሪ ያለ ችግር ሥራቸውን በፍጥነት ያስኬዳሉ።ጥበብ ትበዛለች፥ ስንፍና ትጠፋለች፥ አገራችን ትለማለች፥ ሕዝቡ እራሱን ረድቶ ለመንግሥቱ ቀንቶ የጤንነት ኑሮ ይኖራል።መንግሥትም ካገረ ገዦዎች ስለሀገር ጥቅም ከሥር አንድ ገንዘብ እያነወጣ በየአውራጃው የተማሪ ቤት በቶሎ ቢያቆምና ሕዝቡን ወደ ታላቁ ሥልጣኔ ደረጃ ቢያደርሰው በዓለም ሁሉ ላይ የታወቀ ይሆናል። የወርቅ ሐውልት ይቀረጽለታል።ሕዝቡም በሠለጠነ ጊዜ ምስጋናውንና አገልግሎቱን ለአሠልጣኙ እንዲያደርግ የታወቀ ነገር ነው ሁለተኛ ከኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በየዓመቱ የሚወጣው የገጸ በረከት ገንዘብ ከሁለት መቶ ሺ እንዳያንስ ምክንያቱን ለብርሃን ልጆች ለሰላም ወዳጆች በብርሃንና ሰላም ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፲፮ በዝርዝር ስለ ጻፍኩት መደጋገም አያስፈልግም አሁንም ይኸ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ለመንፈሳዊ ተማሪ ቤት ረገድ እንዲሆን ምኞቴን እገልፃለሁ ገንዘብ እያለ እንደሌለ መሆኑ የግዴታ ትእዛዝ በመሻት ነው፥አሁን ለጊዜው ሕዝቡ የትምሕርትን ጥቅም በፍጹም ልቡ እስኪረዳው ድረስ መንግሥት በትእዛዝ ኃይል እየጐተጐተ ገንዘብ ማስወጣትና የተማሪ ቤት በፍጥነት ማቆም ያሻዋል እንጂ ለእንደዚህ ያለ ጥቅም ነገር ሊታገሥ አይቻለውም።ሽማግሌም ሲተርት ይሉኝታና ጥቅም አንድነት አይገኝም ይላል። ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ምናልባት የተገደፈውን አቅንታችሁ የተሳሳተውን አርማችሁ ብታስረዱኝ ምኞቴ መሆኑን ለባሕረ ጥበበት ልቡናችሁ እገልፃለሁ

በቀለ አበዬ

ስለ ፈረስ እሽቅድድም

ጥር ፬ ቀን የፈረስ እሽቅድድም እንዲሆን ተወርቶ ነበርና በጥዋት ብዙ ሰው የፈረስ እሽቅድድም ወደሚደረግበት ወደ ጃን ሜዳ ሲጓዝ አረፈደ። ሶስት ሰዓትም ሲሆን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በክቡራን መኳንንቶቻቸውና ሠራዊቶቻቸው ታጅበው ወደ ጃን ሜዳ በሔዱ ጊዜ አምሮ በተሰናዳላቸው ስፍራ ተቀመጡ። ወዲያው የሽቅድድሙ ሰዓት ደረሰና እሽቅድድም ተጀመረ ።

አንደኛ እሽቅድድም ኖቢስ የተባለ ዋንጫ ።

የሚዳው ርዝመት ፰ መቶ ሜትር ነው ፥ በዚሁ እሽቅድድም አንደኛ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሁኖ

ዋንጫና አርባ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የሙሴ ረፈይ ፈረስ ሁኖ ሠላሳ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ እሽቅድድም የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዋንጫ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ፫ መቶ ሜትር ነው፤ በዚሁ እሽቅድድም አንደኛ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሁኖ ዋንጫና ፶ ብር ተቀበለ። ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሁኖ ሠላሳ ብር ተቀበለ ። ሦስተኛ ቀዳሚ የሙሴ ምቶርሎ ፈረስ ሁኖ አሥራ አምስት ብር ተቀበለ።

ሦስተኛ የኢትዮጵያ መኳንንት እሽቅድድም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ሁለት መቶ ሜትር ነው፡ በዚሁ እሽቅድድም የቢቾክ ጎርጎርዮስ ፈረስ ቀደመና ሠላሳ ብር ተቀበለ ።

አራተኛ እሽቅድድም የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ዋንጫ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ሁለት መቶ ሜትር ነው ። በዚሁ እሽቅድድም የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ቀዳሚ ሁኖ ዋንጫና ፶ ብር ተቀበለ ።

አምስተኛ እሽቅድድም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ሁለት መቶ ሜትር ነው ፡ በዚሁ እሽቅድድም የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ቀደመና አርባ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የማርኪስ ደሴይ ሞንቴበየርድ ፈረስ ሆነና ሠላሳ ብር ተቀበለ ። ሦስተኛ ቀዳሚ የሙሴ ረፈይ ፈረስ ሆነና ሀያ ብር ተቀበለ ።

ስድስተኛ የትልልቆች ሰዎች እሽቅድድም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ አምስት መቶ ሜትር ነው፡ በዚሁ እሽቅድድም አንደኛ ቀዳሚ የማዳም ሻምበርድ ፈረስ ሁኖ ሁለት ዋንጫና አርባ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የሙሴ ኮራ የኢጣሊያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ፈረስ ሁኖ ሠላሳ ብር ተቀበለ ።

ሰባተኛ እሽቅድድም የፈረንሳዊ ስጦታ ።

የሚዳው ርዝመት ሁለት ሺ አምስት መቶ ሜትር ነው ፡ በዚሁ እሽቅድድም አንደኛ ቀዳሚ የመዳም ረፈይ ፈረስ ሁኖ የጥብብ ሥራ እቃና አምሳ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሁኖ ሠላሳ ብር ተቀበለ

ስምንተኛ የዝላይ እሽቅድድም ።

የሚዳው ርዝመት ሦስት ሺ ሁለት መቶ ሜትር ነው ፡ በዚሁ እሽቅድድም አንደኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሁኖ ዋንጫና አምሳ ብር ተቀበለ፤ ሁለተኛ ቀዳሚ የሙሴ ኮራ የኢጣሊያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ፈረስ ሆነና አርባ ብር ተቀበለ ። ሦስተኛ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሁኖ ሠላሳ ብር ተቀበለ።

እሽቅድድሙም ከተፈጸመ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ከመኳንንቱ ጋራ ከእሽቅድድም ማኅበርቤት ገብተው ከእሽቅድድሙ ማኅበረተኞች ጋራ ሻምፓኝ ተጋብዘው ከግብዣውም በኋላ ባማረ ዓጀብ ሁነው ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ ።

ብርቱ የሆነ አደጋ ።

ከአዋሽና ከድሬዳዋ መካከል በምድር ባቡር መንገድ ላይ በኅዳር ፲፩ ቀን ብርቱ አደጋ መሆኑን ሰማን ። ከአዋሽ የሚወርደው የንግድ እቃ ባቡር የኮራን ጣብያ ካለፈ በኋላ ተገለበጠ ።

እንደሰማነው ይህ አደጋ የሆነው የኩባንያው ሠራተኞች የባቡሩን ፍጥነት ማገጃ መኪና ፈጽመው በጥንቃቄ ባለመጠበቃቸው ምክንያት ነው ። በዚህም አደጋ ምክንያት የጉምሩክ ተጠባባቂ ሠራተኛ ጌታሁን እዚያው ሞተ ሌሎችም ሁለት ሠራተኞች ቈሰሉ ። ከእነዚህም ከቈሰሉት ሠራተኞች አንደኛው ታችበሌ የሚባለው እግሩ ተቈርጦ ሆፒታል ተኝቷል ።

በመንገደኞች ላይ አደጋ እንዳይደርስባቸው የኩባንያው ሠራተኞች ከልባቸው አለመትጋታቸውን መስማት እጅግ ያሳዝናል ።

የኩምፓንያው ሹማምንቶች ለሠራተኞቻቸው ጽኑ ትእዛዝ እንዲሰጡ ፤ ለአደጋው አላፊ የሚሆኑትም ሰዎች በብርቱ እንዲቀጡ የሞቱም ዘመዶችና ሌሎቹም ቍስለኞች ፍጹም ካሣውን እንዲያገኙ ፤ በዚህ አደጋ ነገር መንግሥት ኩባንያውን አጥብቆ ይጠይቀው ዘንድ ተስፋ እናደርጋለን ።

Grave Accident

Nous apprenons que le 20 Novembre un accident grave a eu lieu sur la ligne de chemin de fer entre Aouache et Diré-Daoua ·

Le train facultatif partant d'aouache fut deraillé après la station de Khora .

Cet accident du d'après les renseignements qui nous sont parvenus au manque total de surveillance dés freins de la part du personnel de la Compagnie coûte la vie au controleur des Douanes Ato Guétahoun qui fut tué sur le cou ·

Deux autres employés furent blessés, dont l'un le nommé Tatchhbelie , a du perdre sa jambe et se trouve encore à l'hopital .

Il est regettable de constater que le service personne de la Compagnie s'occupe si inconsciencieusement de la sureté des voyageurs, et nous pensons que le Gouvernement, fera en la circonstance des vives et energiques démarches auprés de la Compagnie, afin que des ordres sévéres soient donnés par la Direction de la Compagnie à son personnel, que les responsable de l'accident seront sévèremnt punis. et que la famille du décédé ainsi que les autres blésés seront entièrement endommagés. -

ስለ ሥላሴ በዓል አከባበር

ጥር ፯ቀን የሥላሴ በዓል ስለሆነ ግርማዊት ንግሥት ንገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በመኳንንቶቻቸውና በሠራዊታቸው ታጅበው በዓሉን ለማክበር ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሔደው አከበሩ የዑደትም ሥርዓት በተፈጸመ ጊዜ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ምክር መክረው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱት ። ከዚህ በኋላ ታቦቱ ገባና ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በማረ ዓጀብ ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሱ ።

ከጀርመን ሊጋሲዮን የመጣ የጥር ፯ ቀን ራድዮ የዕለት ወሬ ።

ሞስኮው፡የጀርመን መላክተኛ ሊትቢኖፍና ትልልቅ የሩሲያ መኳንንት፡ደግሞ የጀርመንና የሩሲያ ሊቃውንት ተቀበሉት ።

ኒዮርክ፡ የአሜሪክ የአርሻ አስናጂዎች አለቃ ቶማስ ክምፕቤል የቶበለ አሥር ሚሊዮን አክር መሬት(አንድ አክር ፬ሺ ፵፯ ሜትር ከሬ ያህላል) የአሜሪክ፡ የሚታጨድ እህል ወዳለበት ወደሩሲያ ለመሔድ ተሳፈረ ።

ቤርሊን ፡ የአፍጋን ሌጋሲዮን እንደሚለው ንጉሥ አማኑላህ ከሕዝቡ ጋራ እንዲታረቅ ለትልቅ ወንድሙ ለኢናያቱላህ መንግሥቱን ሰጥተዋል፡ኢናያቱላህ በ፲፰፻፹፰ ዓ ም ተወለደ፡የንግሥት ቡሬያህንም እህት አግብቷል፡አማኑላህ በኤሬፕላን ወደ ከንዳሃር ሔዷል ። የቱርክ ሚሊቴር መላክተኞችም ወደካቡል እንደ ገቡ ይወራል።

ቤልግራድ ፡ የቤልግራድ ቡርጎማስተር ከማንዲ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተሾመዋል፡አግሬም አቡኪት ማትሩኒች የንግድና የጥበብ ሥራ ሚኒስትር ተሹሟል ።

ስቶክሆልም፡የኖይርዌጂያ አሌን ወራሽ የሽዌዴን ንጉሥ ወንድም የዲዮክ ዊስት ንትላንድን ልጅ ሊያገቡ ነው ።

ፓሪስ፡ ማሬሻል ፉሽ ስለ ታመሙ አያሌ ሐኪሞች ተጠርተው ነበር ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፲ መ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ፱ መ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፯ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፮ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ከረጻ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጻ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጸር	፩ ከረጻ	፻፯ ብር
ባለሰይጣን		፻፺፯ ብር ተኩል
፡ ፡ ባለ ድመት	።	፻፴ ብር
፡ ፡ ባለአህያ	።	፻፵፰ ብር
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፶ ብር
ባለ አንበሳ	፡ ፡	፻፶ ብር
ሱክር	፩ ጁኒያ	፷፭ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ፺፰ ሳን
ባንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፹፯ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ብር፴፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፯ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማንደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወኪያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።



COGNAC S.E.A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮና፡ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጆቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።



ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷኝነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የዶማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ዮንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ጉድይር ግዙ

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።፡


GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
1-28-7
GOODYEAR

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ፣ ቍጥር ፬
5me ANNÉE № 4

ሐሙስ ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 24 JANVIER 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen , profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ዓመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊደት ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፲፰ ገጽ ተከታይ ።

ምዕራፍ ፫ ።

፲፩ ጥቅምና የዓይነቱ ደረጃ ፤

ሰው አንድ ዓይነት ነገር ብቻ ከማግኘት ከሁሉ ዓይነት ትንሽ ትንሽ ማለት (ልዩ ልዩ)የሆኑ ነገሮች ሊኖሩት ይፈቅዳል (ይወዳል)። ምሳሌ አንድ ሰው ብዙ ምጣድ ካለው ወይም አንድ ዓይነት ሁኖ ትልቅ ነገር ከሚበላ ፤ ሌላው አንድ አንድም ቢሆኑ ጋን ማሰሮ ፤ ድስት፡ ብረት ምጣድ፡ዋንጫ፡ጠረጴዛ፡ ወንበር፡ማጥን፡ አልጋ፡ እነዚህንም የሚመስሉ ሁሉ የመኖሪያ እቃዎች ቢኖረው ከብዙ ዓይነቶች ምግብም ትንሽ ትንሽ ቢበላ ደስ እንዲለው ጥርጣሬ የለበትም ።

ሌላ ለማግኘት የማይቻለው ቢሆን ደግሞ የግድ የሚያስገድደው (የሚያስፈልገው)ነውና ከሁሉ በፊት እንጀራ ቢያገኝ ደስ ይለዋል ። እንጀራ ካገኘ ወዲያ ሥጋና መጠጥ ይፈልጋል ። እንዲሁ ሰው የሚበቃ ምግብ ካገኘ ፤ የሚበቃ ልብስ ካገኘ ፤ መልካም ቤት ካገኘ፡ ጥሩ ጥሩ የቤት ዕቃ ለማግኘት ያስባል ። ስለዚህ በዚህ ባህል ልንወስነው እንችላለን። ከሁሉ በፊት የሰውን ሕይወት የሚያዙ (የሚያስፈልጉ) ዋና ጥቅሞች የሚባሉ አየር፡ ምግብ፡ ልብስ፡ስፍራ(ቤት)እቃ፡ (መኖሪያ) መጀመሪያ የደረጃ ጥቅም ይባላሉ ። ቀጥለው ሁለተኛ የሥልጣኔ ፍሬ ፤ የመልካም አንዋወር ምኞት ይከተላል።

ምኞትና ፍለጋ ምን ልዩነት አለው የሚል ሰው አይጠፋም(ይሆናል፤ አስረጂ) ራበኝ፡ ጠማኝ፡ ማለት ፍለጋ ይባላል ። መልካም በበላሁ፣በተሸምኩ፣በጸደቅሁ፣ማለት ፤ ምኞት ይባላል።ስለዚህነው ከሁሉ በፊት ፍለጋ ይቀድማል ያልነው ሁለተኛ የምኞት ማዕርግ ይከተላል ያልነው ፤ ሁለተኛ (አስረጅ) ፍለጋ የተወሰነ ነው ። የአዳም ዝሚትህ ባህል እንዲህ ይወስናል ፤ የምግብ ፍለጋ እየነፍስ ወከፍ ሰው ሆዱ ሲሞላ (ሲጠግብ)ተወስንዋል ። ግን ክብረትና ማዕርግ፡ሽልማትና ልብስ፡ ቤትና አሽከር፡ወርቅና ብር፡ ሁሉ ወሰንና መጨረሻ የሌለበት ይመስላል፡ ማለት የሀብታም(ወይም የከበርቴ) ምኞት ወሰን(ወይም መጨረሻ) የለውምና። ለምሳሌ) አንድ መልካም ቀላድ ያለው ሰው ። ሁለተኛ ቀላድ ለማግኘት፡ሺ ብር ያለው ሁለት ሺ ብር ለማድረግ፡ ፈታውራሪው ደጃዝማች ለመሆን፡ደጃዝማቹ ራስ ለመሆን፡ ራሱ ለመንገሥ ፤ ንጉሡ ለዓለማዊ ሁኖ ዓለምን በመላ ለመግዛት ሲመኙ ያልፋሉ ። በጭሩ ይልቁን በሠለጠኑ አገሮች ከሆነ ምንም ሀብታም(ወይም ከበርቴ) ቢሆን፡ ካለበት ይልቅ (ይበልጥ) ሁለ ጊዜ ሊጨምር እንጂ ያለኝ (የተሰጠኝ) ይብቃኝ የሚል ሰው አንድ ስንኳ አይገኝም ።

ሀብት ተቀጣጥሎ እንጂ አንድ ዓይነት ብቻ ከሆነ ቢበዛም ለሰው ሕይወት ኑሮ ጥቅም እንደሌለበትና ፤ የዓይነቱን ደረጃ ልዩ የሚበቃ ምሳሌ (አስረጅ) ከሰጠን እንዲሁም በጅምላ ፤ ማለት በአንድ መንግሥት ፤ ልዩ ልዩ ሥራ ካልተሠራ ወደ እውቀትና ሀብት እንዳይደርስ ለማስረዳት እንጥራለን ። አስረጅ ተማሪዎች ሁሉ ቅኔ ብቻ ቢማሩ ፤ ገበሬዎች ሁሉ ጤፍ ብቻ ቢዘሩ፣አንጠረኞች ሁሉ ማረሻ ብቻ ቢሠሩ፣ ሸማኔዎች ሁሉ ኩታ ብቻ ቢሠሩ ፤ ፋብሪካዎች ሁሉ ጠመንጃ ብቻ ቢሠሩ፣ አናጦች ሁሉ አልጋ ብቻ ቢሠሩ፣ ጻፊዎች ሁሉ ገድል ብቻ ቢያሳትሙ ፤ ከሁሉ በፊት ሠራተኞቹ በጣም በተጎዱ ነበር።ማለት ሰው የሚፈልገው ብዙ ልዩ ልዩ የሆነ ዓይነት ነውና ፤ እቃው ሲበዛ ገዢው ሲያንስ እንዳፈሩት ልክ የሚገዛላቸው ሰው አያገኙምና ፤ እነሱም (ሠራተኞቹ) የሚገዛላቸውን ካላገኙ አይሠሩምና ፤ አገሩ በድኽዩ በምቾትም ባልኖረም ነበር ። ግን ተከፋፍለው ፤ ማለት ተማሪዎች አንዱ ዜማ፡አንዱ ጽፈት፡ አንዱ ቍጥር፡ እነሱንም የሚመስለውን

ሁሉ ቢማሩ ፤ ገበሬዎች አንዱ ሥንዴ፡ አንዱ፥ ዳጉሳ ፥ አንዱ በርበሬ ፥ የሚመስለውንም ሁሉ ቢዘሩ ፤ አንጠሮኞች አንዱ ማጭድ፥ አንዱ ቢላዋ፥አንዱ ዶማ፥ የሚመስለውንም ሁሉ ቢሠሩ ፤ ሸማኔዎች አንዱ ጋቢ፥አንዱ አቡጀዲድ ፥ አንዱ ማቅ፥ የሚመስለውንም ሁሉ ቢሠሩ፥ፋብሪካዎች አንዱ ጥይት፥ አንዱ ባሩድ፥ አንዱ መርከብ ፥ አንዱ አቶሞቢል ፥ አንዱ አኤሮፕላን፥የሚመስለውንም ሁሉ ቢሠሩ ፥ አናጦች አንዱ አልጋ፥ አንዱ ጠረቤዛና ወንበር፥ የሚመስለውንም ቢያንጡ፤ ጸፊዎች አንዱ ታሪክ፥አንዱ ጂዮግራፊ፥ (የመሬት ጽሬት) አንዱ ልብ ወለድ ታሪክ፥አንዱ ግጥም፥ የሚመስለውንም ቢጽፉ ፥ እውቀት ስለ ተከፋፈለ እያደገ (እየሠለጠነ) ይሔዳል።ሠራተኞችም ብዙ ገንዘ ያገኛሉና ብዙ ያፈራሉ፤ አገሩም ለኑሮው የሚያስፈልገውን ሁሉ ካገኘ ሀብታምና በምቾት የሥልጣኔ መልክም እንዋወር የሚኖር ሕዝብ ተብሎ ደሙ ሊከበር፥በሔደበት በክብሬታ ሊጠራ፥ ነፃነቱ ሊታፈር ይቻላል ።

ቀጥሎም አንድ ነገር የሚጠቀምበት ወይም የማይጠቀምበት (የማይወደድበት) መለየት (ማወቅ) የግድ ነው።የጥቅምን ክብረት መወደድ እንደ መፈለጉ እንደ ጊዜው እንደ ብዛቱ ነው ተብሎ ባህሉን ይወስናል ። ማለት እንደ መፈለጉ ያልነው ከሚፈለገው የእቃው ብዛት (ቍጥር) ይልቅ የገዢው (ፈላጊው) ቍጥር ሲበልጥ ፤ እንደ ጊዜው ያልነው (ለምሳሌ) ማቅ ከበጋ በክረምት ከመንዝ በአዲስ አበባ ይከብራል ፤ እንደ ብዛቱ ያልነው ፤ እንደ አየርና ዝናም ናቸው ። እንዲሁም ብዙ ነገሮች እንደ አየርና ዝናም አለልክ የሚገኙ የሆኑ ሁሉ ሀብት አይባሉም ፤ ስለምን አለድካም ከሚያስፈልገን በላይ እንዲያው እናገኘዋለንና ።

የወሀ ጥቅምነት በዓለም ያለ ሁሉ ነገር ሊተካከለው አይችልም ይባላል ። ማለት ለሰው ኑሮ ሕይወት ከሁሉ በፊት (ይልቅ) የሚያስፈልገው ጥማቱን ያስወግዳልና ። ግን ዝናሙ ወሀው በጣም የበዛ እንደ ሆነ ቤት ያፈርሳል ። ጐርፍ እርሻ ነቃቅሎ ይጥላል፥ ሰውና እንስሳንም ይወስዳል፥ሁለተኛ አስረጅ አንድ ሰው ለሚመጣው የምንጭ ጉድጓድ ውሀ ቈፍሮ ቢያገኝ ጥቅም ይባላል ። ግን አንድ ማኅበር የደንጊያ ከሰል ሲቈፍር በብዙ የፈለቀ እንደሆነ ሥራውን ያቆመዋልና ጉዳት ይሆናል፥ እንግዲያስ ብዙ ነገርም የምታጠፋ ከሆነች ወሀ ሁሉ ጊዜ ጥቅምናት ብለን ለመወሰን አንችልም፥ ግን ስትፈለግና በልክ ስትሆን ጊዜ ጥቅም ናት ለማለት እንችላለን ።

ከዚህ የቀረ በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል ።

ሚካኤል ተሰማ።

ስለ ጥምቀት በዓል አከባበር ።

ጥር ፲፩ ቀን የጥምቀት በዓል የሚከበርበት ቀን ስለሆነ በዓርብ ቀን በዋዜማው የየአድባራቱ ታቦታት ሁሉ በየአጥቢያቸው ወደ አለው ወንዝ ግሩም በሆነ ዓጀብ ወርደው አደሩ ። በዚሁም ቀን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የጥምቀቱን በዓል ለማክበር ብዙ ታቦታት በአንድነት ተሰብስበው ወደ አደሩበት የሚወርዱ ስለሆነ መኳንንቱ ሁሉ በብዙ ሽልማት ባጌጠ ሠራዊት እያታጀቡ ወደ ግርማዊ ንጉሥ ቤት በተሰበሰቡ ጊዜ ከሰውም ብዛት የተነሣ በታው አልበቃ ብሎት ምድረ ግቢው ይጨንቅ ነበር። ግርማዊ ንጉሥም ብቅ ባሉ ጊዜ ነጋሪቱ ሲጐሸም፥ በቀኝና በግራ የቆመውም ወታደር የሰላምታ ሙዚቃ ሲነፋ፥ ለሚሰማ ድንቅ፥ ለሚያይ ብርቅ ሁኖ ይታይ ነበረ ። እንዲሁም ሁኖ ዓጀቡ እየዳማረ ከወንዙ ደረሱ ። ከዚያውም አምሮ በተሰናዳላቸው ቦታ ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ በተቀመጡ ጊዜ ካህናቱና ሊቃውንቱ ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው ከባሕሩ ዳር ቁመው የጥምቀትን አደራረስ አደረሱ ። ብፁዕ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ውሀውን ባርከው በግርማዊ ንጉሥና በመኳንንቱ ላይ ረጩላቸው ። ከዚህ በኋላ በዚያው የነበረ ሠራዊቱ ሁሉ የተባረከውን ውሀ ይሻማ ነበር ። ሕዝቡም ሁሉ ግማሹ ከውሀው ውሥጥ እየገባ፥ ግማሹም ከውሀው ዳር እየቆመ እርስ በርሱ በውሀው ይራጭ ነበር። ሥርዓተ ጥምቀቱም ከተፈጸመ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ከወንዙ ዳር ተነሥተው ባጠገቡ ባለው ሜዳ ተቀመጡ። ክቡራን መኳንንቶቻቸውም እንደየመዐርጋቸው ተቀመጡ። በዚያ ጊዜ የውጭ አገር መኳንንትና ወይዛዝር መጥተው ከግርማዊ ንጉሥ ጋራ እየተገናኙ በየመዓርግ ቦታቸው ተቀመጡ። ካህናቱና ሊቃውንቱም በግርማዊ ንጉሥና በመኳንንቱ ፊት ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ የሚለውን አቡን ዘመው አመርገደው ሲጸፉ እጅግ ያምሩ ነበር ። ከዚህ በኋላ ጉዞ ሆነና ታቦቱ በፊት ሁኖ ግርማዊ ንጉሥ በኋላ ታቦቱን ዓጅበው፤ ሰልፉ ግራና ቀኝ ከቦ፥ነጋሪት እየጐሸመ፥ መለከትና እምቢልታ፥ ጥሩንባም እየተነፋ፥ጃን ሜዳ ደረሱ ።

የሰልፉም አኳኋን እንዲህ ነበር። ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የወርቅ እቃ ባስጨነቃት በቅሎ ላይ ሁነው፥ የወርቅ ጃን ጥላ ተይዞላቸው፥ በግራና በቀኝ ሰማያዊ ክት የለበሰ መትረየስ እንጋች የግርማዊ ንጉሥ የክብር ዘበኛ ዙርያውን ከቦ፥ ከነሱ ትንሽ እልፍ ብሎ ደግሞ ካኪ ክት የለበሰ የግርማዊ ንጉሥ እግረኛ ወታደር፥ ቀጥሎ የግርማዊ ንጉሥ ፈረሰኛ ወታደርና የማዘጋጃ ቤት እግረኛና ፈረሰኛ ዘበኛ በሶስተኛው ረድፍ ተሰልፎ ቁሞ ሜዳውን ገጥሞ በያዘው ጊዜ፥ የሰልፉ አሠራርና የሰልፈኛው ማማር ካለፉት ዓመታት የበለጠ ሆነ። የተሰበሰበውም ሰው ሜዳው አልበቃ ብሎት ጭንቅንቁ እንዲህ አልነበረም። በዚህም ጊዜ ወታደሩ በሙዚቃ ተመርቶ፥ ሰላምታ ሲሰጥ ሕዝቡ በያለበት ጸጥ ብሎ ረጋ፥ ታቦቱም ቆመ። ግርማዊ ንጉሥም በዙፋን ላይ ተቀመጡ።በስተቀኝም በኩል ልዑል ራስካሣና የኢትዮጵያ መኳንንት ተቀመጡ።በስተግራም በኩል ብፁዕ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና የውጭ አገር መኳንንትና ወይዛዝር ተቀመጡ ። በዚያም ሊቃውንቱና ካህናቱ አሳምረው አሸበሸቡ ። ይህ ሁሉ ሲሆንም ፎቶግራፍ አንሺዎች እየተጣደፉ ሥዕል ያነሡ ነበር። ካህናቱና ሊቃውንቱም ሥርዓታቸውን ከደረሱ በኋላ ብፁዕ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ባርከው አሳረጉ። የውጭ አገር መኳንንትና ወይዛዝርትም ግርማዊ ንጉሥን እየተሰናበቱ ወደ ቤታቸው ሔዱ። ግርማዊ ንጉሥም ተነሡና ከላይ እንደ ተነገረው ዓጀብ እንደ አማረ ሁኖ ጉዞ ተጀመረ ። ግርማዊ ንጉሥም

ታቦቱን ወደ እየቦታው ሸኝተው ከክቡራን መኳንንቶቻቸውና ሠራዊቶቻቸው ጋራ ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ ።

ስለ ቃና ዘገሊላ በዓል አከባበር ።

ጥር ፲፪ ቀን ጌታች ኢየሱስ ክርስቶስ ውሀውን ጠጅ ያደረገበት የመታሰቢያ በዓል ቀን ነው ፤ ወዲያውም የቅዱስ ሚካኤል የወር በዓል ነውና የቅዱስ ሚካኤል ታቦት ለጥምቀት ወደባሕር በጥር ፲ቀን ወደወንዝ ወርዶ፥ጥምቀትን ውሎ፥ አድሮ፥ በ፲፪ ቀን እንዲገባ ከጥንት የቈየ ልምድ ነው ። በዚሁም ቀን በጥዋት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በመኳንንቶቻቸውና በሠራዊቶቻቸው ታጅበው ሒደው ታቦቱን በትልቅ ክብር ወደ ቤተ ስርቲያን አግብተው በሚያስደንቅ ዓጀብ ተመልሰው ወደ ቤታቸው ገቡና ለመኳንንትና ለሠራዊት ሁሉ ትልቅ የደስታ ግብር ሁኖ ዋለ ።

አገርን ስለ ማልማት ።

ግርማዊ ንጉሥ ቀድሞ ውድማ ሁኖ ይኖር የነበረ በአሩሲ አውራጃ ጩካ የሚባል እርስት አላቸው።በክረምት ከሩቅ አገር ጋላው ከብቱን ይዞ ሣሩን እየገዛ ሁለት ወር አብልቶ ለቆት ይሔድ ነበር እንጂ በዚያ ላይ እያረሱ የሚቀመጡ ሰዎች ቍጥራቸው ከአሥር በታች ነበር ። አሁን ግን ግርማዊ ንጉሥ በተለመደው ቸራኄአቸው ይህን መሬት ገዝቶ ለሚኖር ሰው መጀመሯ ለማልሚያ ሁለት ዓመት ነፃነት ስለሰጡት፤ ከ፪ት ዓመትም በኋላ ለመሬቱ የሚከፈለው፥ግብር ስለ ወሰኑለት፥ የሲሶ እርሻና የመንደር ጣጣ፥ የሚባል ብዙ ግፍና የሥራ መሰናከል ስለማያገኛቸው፥ይህ ውድማ ሁኖ የሚኖር አገር በሁለት ዓመት ውሥጥ የሕዝቡን ብዛትና ብርታት ፤ ደልቁንም እንደሌላው ሁሉ ሳይሰቀቅ አንድ ልብ ሁኖ በመሥራቱ የመሬቱን ልማትና መወደድ ላየው ሰው ያስደንቃል ።

በላዩም ያለ ሕዝብ ሺ ስምንት መቶ ይሆናል።ይኸውም መታወቂ በዚያ የሚኖሩ ሕዝብና በየቀኑ የሚወለደው የሚሞተውም ፤ ከውጭም የሚገባውና ከዚያም የሚመጣው ስለ ተጻፈ ነው ።

እንባቢዎች ሆይ ይህ ምሳሌ የሆነ በረኃ አገር እንደዚህ የሆነ ለሙ የውሀ ችግር የሌለበት አገር ሁሉ ይህን የመሰለ የተወሰነ ግብር ቢያደርጉለትና ገበሮች ነፃነት ቢያገኙ የኢትዮጵያ ዕድል ብዛት ለልጆቿ ምን ያህል ደስ ባሰኛቸው ነበር ?። አሁንም ይኸን የመሰለ ዕድል በግርማዊት ንግሥታችንና በብልሁ አልጋ ወራሻችን በግርማዊ ንጉሥ ጊዜ ተፈጽሞ የደስታዋ ተካፊይ እንድንሆን ተስፋ እናደርጋለን ።

አንተና ሚስትህ ።

ሚስት አግብተህ እንደሆነ ሚስትህን እንደምትወዳት እምነት አለኝ ። ግን ሁለት ዓይነት መውደድ አለ ። መጀመሪያ መውደድ ስለቍንጅናዋ ስለአለባበሷና ስላጌጠች ወይንም ስለ ሞያዋና ስለቤት አስተዳደር ማወቋ ብቻ አይደለም።መውደድ ማለት ሐሳብህና ሐሳብዋ አመልህና አመልዋ እኩል ተሆነ የሚአስመሰግን መውደድ ነው።ሚስትህን ከንጀትህ ነውን ወይንስ ከንገት በላይ ነው የምትወዳት እውነት ሚስትህን ስለ ቍንጅናዋና ስለአለባበሷ፥ስለአስጌጥከት ጌጥና ስለሞያዋ፥ስለቤት አስተዳደር ማወቋ እንደሆነ የምትወዳት ይህ መውደድ እቃ እንደመውደድ ያህል ነው እንጂ ከንጀት እሷን እንዳትወዳት አውቃለሁ ። ምናልባት ሚስትህ በአውቀት የከበረች ብትሆን ፍቅርህን ትፈልጋለች እንጂ ከንተ ጌጥና ልብስ መግሪያ አትፈልግብህም፥ልብህን ወደሚስትህ አድርገህ ከንጀትህ ውደዳት። ነፍስህንና ነፍሷን በፍቅር ሰንሰለት እሥር ። በትልቅ አዳራሽ ውሥጥ ከንገት በላይ ከምትወዳት ሴት በዳስ ውሥጥ ሁነህ ከንጀት የምትወዳት ሚስት ብትሆንልህ ይሻላል፥ከንተ ፍቅር ሳይኖራት ቀርታ በቤት በመሏ ተፈቅራ የምትመሰገን ሴት ገትኖር ይህ ባሏን ማፍቀር አይባልም ነፍስህን እንደምትወድ ያህል ለሚስትህ ምግቧ ያንተ ፍቅር ነውና እሷን ደስ የሚያሰኝ ፍቅር እንደሆነ እወቅ።በፍህ ሚስትህን የምትወዳት እንደሆን ይህ ፍቅር አይባልም።ልጅ አትሁን በፍህ ሚስትህን የምትወዳት እንደሆንክ ከንተ ይልቅ ርግብ ከንፉን እየጋረደ አሽኮርምሞ ሚስቱን ይወዳልና ከንተ እንዲበልጥ እወቅ ከንጀት የምታገለግልህንና በመሏ ደስ አሰኝታ ደግ የምትመኝልህን ሚስት ውደድ ፍቅር ማለት ይህ ነው ። ሚስትህን አክብራት፥ነገርም በተናገረች ጊዜ አታሳፍራት፤ በቤትህም ውሥጥ እንደታዛዥና እንደተወራጅ አድርገህ አትግዛት፤ ሚስትህናት እንጂ በፊያህ አይደለችምና።ስለምን የዕድሜህ ሙሉ ባልንጀራህና አጣማጅህ ናት። ልብህን ለሚስትህ ግለጽላት ሕመምክንና የሥራህን ሁሉ አኳኋን አትደብቃት ። ስንት ያህል ሴቶች በትንሽ ምክራቸው ባላቸውን ከብዙ መከራ ያድኑታልና ሚስትህን አክብራት ከንጀትህ ወደህ አስተዳደሯንም ከንጀት ያፈቀርካት እንደሆን ፍቅር ማለት ይህ ነው ።

፪ኛ፥አንተና ባለጋራህ።ባለጋራ አይኑርህ ለማለት አልችልም ብትፈልግም ባትፈልግም ሐሳብህንና ሀብትህን ለማጥፋት አንተን የሚጠላ ሰው አይጠፋም።ወታደር፥ባላገር የሚኖር በጦርነት ብቻ አይደለም ምናልባት አንተ ደግ ሐሳበኛ፥ሐቀኛ፥እውነት የምትናገር፥ በውነት የምትሠራ ሰው ብትሆን፣ ለዚሁም ሁሉ ምንም ቢሆን አንተን የሚጠላና የሚመቀኝህ አታጣም እንዲሁ የበግ ሌጦ ለብሶ የልብ ወዳጅ እየመሰለ በሆዱ ውሥጥ ግን እንደ ዓይነጥላ ይመለከትሃል። በግልጽ ፊት ለፊትህ ጕራዴውን የሚመዝ ባለጋራንአትፍራ እነዚህ ግን አንተን ለማጥፋት አይችሉም ከየሃቸው ግን እራስህን ለመጠበቅ ትችላለህና ወዳጅ መስለው እቤትህ ገብተው በልተው ጠጥተው ውሥጥ ለውሥጥ አንተን ለማጥፋትና ቤትህን ለማፍረስ የሚፈልጉ ሰዎች የባሰ ባላገሩና ማለት ምናምንቴዎች እነሱ ናቸው። አንተን የሚቀርብህን ወዳጅህን ሁሉ ጠርጥረው አልልህም፥ስለምን ጥርጣሬ ለሰው ክፉ ሐሳብ ነው። ያንተን ጤንነትና የሰው መውደድህን ያሳጣሃልና ማናቸውንም ወዳጅ ማመን አይገባም ከመንከው ወደዚያ በደኅና መላስ እየሸነገለ ዙሮ ከፋት ያረግብሃል አእምሮ ይኑርህ የሰውን መውደድ አመል ያርግልህ። የባልንጀራህን እውቀት መዝን ከመዘንክ በኋላ ደግ ቢሆን አ

ቅርበው፡ክፉ ቢሆን አርቀው፤ ለሰው ባለጋራ አትሁን አልልህም፤ ስለምን ለጠማማ፡ለክፉ፤ ለሸፍጠኛ፤ ለምቀኛ፡እነዚህን ሁሉ ብትጣላቸው ነፍስህን ለመጠበቅ ነውና ። የባለጋራም ደግና ክፉ አለ አንተ ግን ደጎና ባለጋራ ሁን ሐሳብህን የሚጠላ ቢኖር በደግና በሐቅ የሚአወጣህን መልስ መልስለት እሱ ያንተን ሐሳብ እንደሚጠላና እንደሚአዋርድህ አይተህ እሱን እንዳትመስልና በሕግና በጋዜጣው መካከል በተቀመጥክ ጊዜ ጥቅም ያለው ነገር ብትናገር ያ ሐሳብህን የሚጠላ ሰው ቢአፈርስብህ ነገሩን ጠልቶ አይደለም አንተን ስለ መጥላቱ ነውና አትከራከረው አንተ ግን ልብህን ሰፊ አድርገው፤ የወዳጅህና ያንተ ሐሳብ ቢስማማ አታርቀው ስትከራከረውም በደግ መልስለት እንጂ እንዳታስቀይመውና እንዳታዋርደው ተጠንቀቅ ግን አንተ መልክም ሐሳብህን ከሆድህ አታጥፋ ።

ክሪኮር ዳራክጅያን ።

ሰርግ ።

ጥር ፲፱ ቀን ክቡር ባላምባራስ ክብረት የቀኛዝማች ማህሉ ይልማን ልጅ ወይዘሮ ከማዬን አገቡ ።

ክቡር ፊታውራሪ መንገሻ ይልማም ስለ ወንድማቸው ልጅ ያደረጉት ሰርግ ፡ የባላምባራስ ክብረትም ሰርግ ፡ ተከናውኖ ተፈጸመላቸው ።

ብርሃንና ሰላም የተጋቡትን ሙሽሮች ንብረታቸው የተባረከ እንዲሆን እየተመኘ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

የዘበኞች ትጋት

አንድ የሚያስገርም አታላይ ሌባ ለጌታ አድሮ ሲያገለግል ጌታውም ካንድ ወዳጁ መደብር ለቤቱ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሽከሩን በላክ ጊዜ እንዲልኩለት ነግሯቸው ይኸነ አታላይ አሽከሩን እሙን መስሎት ኑሮ ከባለሱቆቹ አገጣጥሞት ይኸውም አሽከሩ ጥቂት ወራቶች የሒሳብ ማምጫውን ደብተር ይዞ እየሔደ ጌታው ያዘዙትን ሲሠራ ሰንብቶ ከጥቂት ወራቶች በኋላ ከጌታው ተጣልቶ ተሰናብቶ ሲሔድ የሒሳብ ማምጫውን ደብተር ደብቆ ይዞበት ሔደ ከሱ ቤትም ከወጣ በኋላ ጌታዬ ላኩልኝ ብሏል ብሎ የ፳፱ብር ሒሳብ አረቂ ወስዶ ሔዶ ወደዚያውም ጌታው ድንገቱን እዚያ ሱቅ ቢሔድ ባለሱቆቹም ሂሳቡለትን አስታወቁት እሱም እኔ ከሰናበትሁት ቆይቷል ብሎ ነገሯቸው ባለገንዘቦቹም ይህ አታላይ ያደረጋቸውን ለዘበኞች አስታውቀው ከዘበኞች ጋር አጥብቀው ሲፈልጉ አግኝተው ይዘው ቢጠየቅ አልወሰድኩም ብሎ ክዶ በከሚሳርያው ዳኛ በተተከከለ ምርምርና በዘበኞቹ ትጋት ብዙት ፲ጠርሙስ አረቂና ፩ትንሽ ቆርቆሮ ዘይት ከደበቀበት አግኝተው ተይዞ ሌባው በቅጣት ታሥሯል ።

፪ኛጥር ፫ቀን አንድ ሌባ ጉለሌ የተዘጋ ቤት ቀን ቁልፉን ሰብሮ በቤቱ ውስጥ ያገኛቸውን ልብሶችና ብሮች በሱ አሮጌ ሸማ ጠቅሎ ተሸክሞ ሲሔድ ዘበኞች አግኝተው ይዘውት የራሱና የሰው መሆኑን ለማወቅና ለመመርመር ቢጠይቁትየሰው ቤት ሰብሮ መስረቁን አምኖታሥሯል ባለገንዘቦቹ ፍትሕና መንግሥት እያጥፉ ጠፍቶብን የነበረው ገንዘባችን በዘበኞች ጥበቃና ትጋት ተገኘልን ብለው ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን እያመሰገኑ በዘበኞቹም ብርታትና ትጋት እየተደነቁ ገንዘባቸውን ይዘው ሔዱ ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ማስታወቂያ ።

(ለኤሶና ለስታር ባር አንድ ሲርክል)

ለነጋዴዎችና ለሕዝብ ሁሉ ማስጠንቀቂያ ።

የእስታንዳር እዋል ኩንፓኒ ኦፍ ኔወዤርዚ (ኤታዙኒ) ይህ ኩባኒያ የቆመው ብዴላዋር መንግሥት ደንብ ነው ዋና ቤታቸው በዊልሚንቶን ሚባል ከተማ ነው ዴልዋር መንግሥት ውሥጥ ማለት (አሜሪካ አገር ውሥጥ)የኤሶና የእስታር ባር አንድሲርክል የፋብሪካው ማርካ ባየዓይነቱ ከዚህ በታች እንደተጻፈው ይሠራል ።

ESSO

የነዚህ የሁለቱ የፋብሪካው ማርክ ሥራቸው

የመኪና ዘይት ማውጣት ነው ፤ በያይነቱ የተጣራ ያልተጣራም፡ከጋዝም የወጣ፡ሌላ ነገር ሳይደባለቅ የአውሬ ጮማም ሳይገባበት፤ የቅጠልም ሳይገባበት፤ ይህ ዘይት ለመብራት ያገለግላል እሳትም ያነዳል፡ሞተርም ያስነሳል፤ መኪና ለመቀባትም ይሆናል ሌላም ነገር ሲያቀልጡትም ይኸንን መዳኒት ይጨምሩበታል፡ አልስፋትና የአልስፋት እጣብ ይበጅበታል፡ወርኒስም ይወጣዋል፡ ለጭት ማማመሪያ፤ ላጣብ ሚሆንም ዘይት ያወጣሉ ደግሞም ለኩርፓና ለጠፍር ሥራ ሚሆን ያበጃሉ ።

ለሕዝቡ ሁሉ እናመለክታለን ይህ ማስታወቂያ የተደረገው ይህ ሁለቱ ማርክ (የኤሶርና የእስታር ባር አንድ ሲርክል)እስ መስለው ሠርተው ሕዝቡን እንዳያሞኙ ይህ ደንብ የተበጀ የሮጳና የአሜሪካን አገር ደንብ ተከትለው ነው የእነኝህንየሁለቱ ማርክ ዘይት አስመስላለሁ ብሎ አበጅቶ የተያዘ ሰው በዳኛ ይከሰሳል ቅጣትም መንግሥት በፈረደበት ፍርድ ይቀጣል ።

ተጻፈ አዲስ አበባ ፬ጥር ፲፱፻፴፫ ዓመት በፈረንጅ ለእስታንዳር እዋል ኩንፓኒ ኦፍ ኔው ዤርዚ ።

ይህንን ለማሳተም የታዘዘ ሙሴ ፖል ሻኑዋ የሚባል ጠበቃ ነው ።

የከተማ ወሬ

ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር የወለጋ ገዥ ጥር ፲፫ ቀን ወደ አዲስ አበባ ገቡ ።

ብርሃንና ሰላም ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያምን እንኳን በደኅና ገቡ ይላል ።

ያ፩ኛ ዓመት የ፫፻፹ ገጽ ተከታይ።

ዝኒት የምትባለው የጻፈችው የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ምስጢር ያለው የሕይወት ታሪክ በከፒቴን ባቢኪያን ታርሞ ተጻፈ።

፪ ተኛው ክፍል

ታላቁም ደክ አባቷ በምሳ ጊዜ ከገበታ ስለታጣች ምን ሆነች ብሎ ጠየቀኝ፡እኔም ተነሥቼ ልዑል ሆይ ራስዋን ትንሽ ስላመማት ወደ መኝታ ቤቷ ነችና ለልዑል ንገርልኝ ብላኝ ነበር ብዬ መልስ ሰጠኋቸው። ታላቁም ዱክ በጥርጣሬ ዓይን እያዩኝ በየጊዜው ራሷን ያማታልን ይህ በሽታ መቸም ከፍጥረቷ ዓይደለም፡አሁን የንጉሥን ቤተ ዘመድ የሚያክመው ዶክቶር ኢህባልት መጥቶ ይመርምራት አሉኝ።በዚያ ጊዜ ልጁ አሊክስ ከአንድ የፋብሪካ ዲሬክተር ልጅ ጋራ በፍቅር መጻመድዋን ታላቁ ደክ አያውቁም ነበሩ፤ የሁለቱ ቀጠሮ ብዙ ጊዜ ይመላለስ ነበርና።

ባራተኛው ቀን ሌሊት አሊክስ ወደ እልፍኝዋ ጠራችኝ። እኔም ሂጄ ባያት ክፉኛ ትንፋን አሟት አገኘኋት ። እርስዋም ወደ ውጭ ውጪና ባ፲፫ተኛው ቁጥር መንገድ ላይ ሂደሽ አንድ ቢስኩት መሸጫ ቤት ታገኛለሽ ከዚያም ገብተሽ ፲፫ተኛው ቁጥር ጠረጴዛ ላይ ሪዶልፍን ታገኝዋለሽ። እራሴን ጥቂት አሞኛልና ከ፪ቀን በኋላ እመጣለሁ በዪው።እርሱም የኔ እህት መሆንሽን ይረዳው ፡ እኔም ትእዛዝዋን ተቀብዬ ባመለከተችኝ ስፍራ ሂጄ ሪዶልፍን አገኘሁት ፥ እንዳለችኝም ነገርሁት ። እርሱም ይህን በልኩት ጊዜ ክብርት ሆይ ስለምን አድራሻችሁንና የቤታችሁን ኑሜሮ አትነግሩኝም፡ አንችና እህትሽ ሁልጊዜ የአንድ ፋብሪካ ዲሬክተር ልጆች ነን ብቻ ትሉኛላችሁ ብሎ በልመና ቃል ጠየቀኝ ።

እኔም ወንድሜ አባክህ ይህን እንተወው፡የምንደብቅህ እናታችንን ፈርተን ነው፡ ካንተ ጋራ አንድነት እንዳለን ያወቀች እንደሆነ በብርቱ ትቆጣናለች አልኩት።

ከፒቴን ባቢኪያን

በሚከተለው ሳምንት ይቀጠላል

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፩ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፮ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፲፪ ብር
ባለሰይጣን		፻፲፪ ብር
፡ ፡ ባለ ድመት ።		፻፲ ብር
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፹ ብር
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፳ ብር
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፭ ብር
" " ጃፖን		፻፰ ብር
ቡኩር	፩ ጁኒያ	፳፭ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፶ ሳን
ባአንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፲፬ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ብር ፶ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፮ ብር

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማነደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሉንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጀቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የለ ለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ። የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጕርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ለ ቅፆ


GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
I-28 7
GOODYEAR
ጉድዬር ጎዝ

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንክራ ነው· በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።፡

አምስተኛ ዓመት ፥ቁጥር ፭
5 me ANNÉE № 5

ሐሙስ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 31 JANVIER 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊለን በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፳፮ ገጽ ተከታይ ።

፲፪ የጥቅም ድምርና የጥቅም ብልጫ ። (መበላለጥ)

ከሁሉ በፊት የምግብ ጥቅም ሕይወታችን የምትይዝ ናትና በጣም ትልቅ ናት። በየቀኑ የምንበላው ወደ አሥረኛው አፍዋ ብናሳንሳት (ብናጐድላት) መሥዋዕታችን በቀለለ ነበረ። ይሆንን? እስቲ ፩ ሰው በ፳፬ ሰዓት (ሌትና ቀን) የሚጨርሳትን ምግብ በትክክል በአሥር መቍነን (ክፍል) እንደተከፈለች እናስባት ። ምግቢቱ የኋለኛይቱ መቍነን ያነሰች (የጐደለች) እንደሆነች ሥቃዩ ትንሽ በሆነ ። ሁለተኛይቱ መቍነን የጠፋች እንደሆነ ጕድለትዋ በጣም የተሰማ በሆነ ። ሶስተኛዋ መቍነን ብትጐድል በርግጥ ችግር በሆነ። እንዲሁ በየመቍነኑ ጕድለት፣ አንድ ቀን በሞት እስኪገኝ ድረስ አመሙ (ችግሩ) እየከበደ በሄደ ።

ማለት ከአሥሩ መቍነን ለያንዳንዱ ክፍል የሚያድግ ብለን የምንጠራው ትርጓሜው እያንዳንዳቸው የሚያድጉ ምግቦች ከሚቀድመው (መቍነን) የሚከተሉት ጥቅም ያንሳል ማለት ነው ።

የጥቅምን መለዋወጥ ልክ የሆነ አሳብ ቀጥሎ ባለው አንደኛ ሥዕል እናመለክታለን። ምንጣፊቱ መስመር (ሀ) (ለ) የምግብን ብዛት ታመለክታለች በአሥር ክፍል በትክክል ክፍለናታል ከነዚያ አሥር ቋሞች ወይም የሚተከከሉ አደጎች ፤ እያንዳንዳቸው በመስመር የተዘጉ ስፋቶች፣ ያንዳንዱን ብልጫ ያመለክታሉ። እንደሚታየው የመጨረሻዋ አድገት ትንሽ ናት፤ ወደ (ሀ) እየቀረብን ስንሄድ እያደገች ትሄዳለች። እስከ በቍ ፩ና ፪ ስንደርስ ማለት መጨረሻ የሌላት እስክትሆን ድረስ እያደገች ትሄዳለች። ስለዚህ ለሕይወታችን የሚያስፈልጉ ናቸውና ታላቅ ጥቅም ትባላለች ።

እንዲሁ የምግብ ጥቅሙና ድምሩ በልክ ለማወቅ የዚያችን ክፍል ብልጫ በትክክል የከፈልናት ማለት የስፋቱን ድምር ማድረግ ይበቃል ። አስረጅ ፥ የኋለኞቹ የአምስቱ ስፋቶች ባንድነት ድምር ፤ ከ፪ኛው ወይም ከ፩ኛው ስፋት ያንሳሉ ።



፩ኛ ሥዕል።

የምግብ ግን በትክክል በአሥር ክፍል መክፈል ግራ ይመስላል ። ብዙ ክፍሎች መጀመሪያው ሳይለዋወጥ ፥ አምስ ፥ መቶ፥ የሚበልጡም ክፍሎች ለመውሰድ በቻ

ልን ። ማለት በየትንሺቱ ክፍል እየተጨመረች ብትሄድ ለምትቀድማት ኋለኛይቱ፡ ጠቀሜታዋ እያነሰ በሄደ ። ምንም እንኳን የእድገቱ (ብልጫው) ትንሽ ቢሆን ፡ ሥርዓት በበሀልዋ እውነትኛ መሆንዋን አትተውምና። ስለዚህ ጥቅምን ባንድ ጐባጣ መስመር ለማመልከት በ፪ኛ ሥዕል ትጨምራለች ።

መስመሮች (ረ) (ተ) (ቀ) (በ) የጥቅምን ብልጫ (መብላለጥ) የሚያድጉ (ረ) ና (ቀ) ፤ ካልናቸው መስመሮች በ(ሰ) (ነ) የተያዙ ስፋቶች ፡ የጥቅምን ድምር ያመለክታሉ ።

እንግዲያስ የጥቅም ድምርና መበላለጥ ፡ ሁለት ልዩ ልዩ ሐሳብ ይገልጣሉ ማለት ነው።? እውነት ነው ፊተኛይቱ በአንድ ስፋት፤ ሁለተኛይቱ በአንድ መስመር አሳይተው ያስረዳሉ (ይገልጣሉ)።



፪ኛ ሥዕል ።

ባጭሩ የጥቅምን ደረጃ ፡ (ብልጫ) በዚህ ልንወስነው ፤ እንደፍራለን ። ካሁሉ ይልቅ የሚያስፈልግ የሆነ ነገር ፥ በጣም የተከበረና የተፈለገ አይደለም ። አስረጅ ፤ አለ ውኃ አንድ ቀንም ልንውል ባልቻልንም።ግን በፊት እንዳመለከትነው እለልክ ብዙ ስለ ሆነ ምን ያህልም ቁም ነገር አንቈጥረውም። (አናከብረውም) አንድ ጊዜ ቢጐድልብን ግን ፡ ያነን ጊዜ የወኃን ደረጃ ከሁሉ ከፍ ያለና የሚበልጥ ጥቅም መሆኑን በጣም ከበሬታውን በወቅነው ። ከልክ ያለፈ እንደሆነም እንፈልገውም ማለት አንድ ሰው የሚበቃ ውኃ ምግብ ገንዘብ ካገኘ ፡ ኑሮውን ያልተወሰነ ብዛት ለማግኘት አያስገድደውምና ። አሁን አንድ ነገር ሀብት ናት የምትባለውን በብዛትዋ የተወሰነች መሆንዋ የሚበቃ ማስረጅያ የሰጠሁ ይመስለኛልና ወደ ዋና የምትባለው ቃል ያልተለየች ብርቱ ሐሳብ ለማውጣት ሳላልፍ ፤ ስለ የጥቅምን ብልጫ ስለ ንግግሩ ይሁን ስእሉ ያመለከትኩት፤ ትርጓሜው ወይም አሳቡ የማይገባው ሰው አይጠፉም ይመስለኛልና ፤ በጣም ቀላል የሆነች ምሳሌ ልጨምርበት (ልቀጥልበት) ፈቀድኩ ።

አስረጅ፤አንድ የራበው ሰው ወደ መብላት ሲቀርብ፡ መጀመሪያ የሚጐርሳትን ጥቅምዋ መጨረሻ የላትም።እንዲሁም፤ ሁለተኛ የሚጐርሰትም ጥቅምዋ ልክ የላትም።ሶስተኛ የሚጐርሳት ግን ጥቅምዋ ከፊተኛይቱ ጐርሻ አነስ ያለች ትሆናለች እንዲሁ ከዓራተኛዋ የሚጐርሳት፡አምስተኛዋ የሚጐርሳት፡ ከአምስተኛዋ የሚጐርሳት፡ ስድስተኛዋ የሚጐርሳት፡ከስድስተኛዋ የሚጐርሳት፡ ሰባተኛዋ ሚጐርሳት፡ከሰባተኛዋ የሚጐርሳት፡ ስምንተኛዋ የሚጐርሳት ፡ ከስምንተኛዋ የሚጐርሳት ዘጠነኛዋ የሚጐርሳት፡ከዘጠነኛዋ የሚጐርሳት፡ አስረኛዋ የሚጐርሳት፡ጥቅማቸው እያነሰ ይሄዳል።ማለት ባጭሩ፡ በጐረሳቸው ቍጥር ብዛት ጥቅማቸው እያነሰ ይሄዳል ማለት ነው። ከጠገበ ወዲያ ፈጽመው ጥቅም መሆናቸው ቀርተው፤ እንደገና መጐረሱን መብላቱን ቢጨምር ጕዳት እስከመሆንም ይደርሳሉ ።

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል ።

ሚካኤል ተሰማ ።

ስለ ትምሕርት ።

ኢዮአስ የይሁዳ ንጉሥ በኢየሩሳሌም በነገሠ ጊዜ ካህናት ስለ ደም ዋጋ የሚቀበሉትን ገንዘብ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መጠገኛ እንዲሆን ትእዛዝ አድርጎ ሥርአትም ሠርቶ ነበር ። የደም ዋጋ ማለትም እንደ ሀገራችን ባለደም በወጆ(በጉማ) ሲታረቅ እንደ ሚከፍለው ገንዘብ ነው ። ይኸም እስከ ዛሬ ድረስ የደም ዳኝነት እየተባለ ይጠራል ። በዚያ ዘመን ካህናቱ ያንን ገንዘብ እየተቀበሉ ሀያ ሦስት ዓመት ሙሉ ከማስቀመጥ በቀር ምንም ሥራ እንዳልሠሩበት ባየ ጊዜ ፥ ንጉሥ ኢዮአስ ገንዘቡ አናፆች ሠራተኞች የፈረሰውን ቤተ መቅደስ እየጠገኑ ስለዋጋቸው እንዲቀበሉ አዘዘ ። በካህናቱም በኩል ከቤተ መንግሥት ሠራተኛ ሹም ጸሐፊ ሾመ ። ስለዚህ ከቤተ መቅደስ ጉድለት ያለው ሥራና ለመጠገን የሚያስፈልገው ሁሉ ከህናቱን የሚያተጋ ሹም ከቤተ መንግሥት ስለተደረገ በቶሎ ተከናውኖ ተሠራ ። የዚህም ታሪክ ፬ ነገ ፡ ምዕ ፡ ፲፪፥ ቁ፡ ከ፮ደ እስከ ፲፯ ፡ ይገኛል።ሁለተኛ ዜና መዋዕል ምዕ፥ ፳፬ ፡ ቁ ፭፥ (ኢዮአስ) ካህናትና ሌዋውያንን ሰበሰበ አላቸውም ወደ ይሁዳ ከተሞች ውጡ ከእስራኤልም ሁሉ በየዓመቱ ያምላካችሁን ቤት ለማደስ ብር ሰብስቡ ያንንም ፈጥናችሁ አድርጉ።ሌዋውያን ግን ቸል አሉ። ንጉሥም ዮዳዳን አለቃውን ጸራ አለውም ስለምን ሌዋውያንን አላተጋኻቸውም ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ከእስራኤል ማኅበር ሁሉ ስለ ፲ቱ ቃላት ድንኳን ከሙሴ ከእግዚአብሔር ባርያ የታዘዘውን ግብር ያመጡ ዘንድ ይላል ። እንደዚህ እንዳይሆንና የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ወዴትም እንዳይቀር መንግሥት በመንፈሳዊም በሥጋዊም በኩል የሚያስፈልገውን ጥቅም ሊያደርገው ችሎት አለውና ከየቤተ መቅደሱ የሚወጣው የገጸ በረከት ገንዘብ ለመንፈሳዊ ረገድ ተማሪ ቤት በቶሎ ሥራ እንዲ(ዝ ደጋግሜ አስታውሳለሁ ። አሁንም ንጉሣችን ግርማዊ ተፈሪ መኰንን ከቀዳማዊ አባታቸው ከንጉሥ ኢዮአስ ቢበልጡ እንጂ አያንሱምና ቅንዓት መንፈሳዊ በልቡናቸው ስለ አደረ የቅዱሳት መጽሐፍ

ትን ንባባቸውንና ትርጓሜያቸውን በብዙ ሺ ወርቅ ማተሚያውን ገዝተው አስመጥተው ያሳትሙልናል ።

እንግዲህ መንግሥት ለሕዝቡ ጠቀሜታ ሲያደርግ ጊዜ እኛም ጥቅማችን እንዳያንስ ከጥንት ጀምሮ የታወቀች አገራችን ዛሬ ከሠለጠኑት በታች እንዳትቈጠር በሥልጣኔ ለማደርጀት፥ተማሪ ቤትን ለመርዳት፥ ከገንዘቡ ጣል ጣል ማድረግ ያስፈልጋል ።

ምሳሌ መንግሥት እንደ ራስ፥እንደ ዓይን ፥ እንደ ጆሮ፥ ነው ። ሕዝብም እንደ እጅ፥እንደ እግር፥ እንደ ሌሎች ሕዋሳት ነው ።እራስ ቢታመም እጅ እግር ይታመማል ፥ እጅ እግር ቢታመም እራስ ይታመማል ። ማቴ ምዕ፥ ፮፥ ቁ ፳፫፥ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን ሥጋህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል።በንተ ያለውም ብርሃን ጨለማ ከሆነ ጨለማውስ ስንት ይሆን፥ ይላልና መንግሥት እውቀት እንዲሠሩ ጥበብ እንዲበዛ ሲያነቃቃን ጊዜ እንዴት የሐሣቡን ፍለጋ በእግረ ሕሊና አንከተልም ። አንድ ሰው ልጆች ቢኖሩት ፫ሚሊዮን የሚሆን ብር ለልጆቹ ቢያወርስ፥ እነሱም ባይማሩና እውቀት ባይኖራቸው፥ ያ ገንዘብ በከንቱ ይጠፋል ። ወይም ሥራ ሳይዝ በከንቱ ይቀመጣል ።አሁን እንደተባለ አንድ ሰው በደፋት አገር የሚኖር ነበር፥ የምግቡ ዓይነት ቆሎ፥የልብሱ ዓይነት ደበደበ፥ ጭርንቁስ ነበር ። ነገር ግን አራሽ ነበርና በዓመት ውስጥ እህል እየሸመተ ፫፻ብር ያገኝ ነበር ብዙ ዘመን በጉዳት ገንዘቡን እያጠናቀረ፥ ሲኖር በጽኑ በሽታ ታመመና ዘመዶቹ መጥተው ያለ ገንዘብህን እንወቀው ተናዘዝ ቢሉት እኔ ጨርቅ፥ ለብሼ፥ ጥሬ በልቼ ያጠናቀርኩት ገንዘብ ለናንተ ሊሆን ብሎ ተመቅኝቶ ሳይናዘዝ ሞተ ዘመዶቹም የቤቱን ዙሪያ ሁሉ ፯ቀን ድረስ ቆፍረው ገንዘብ አጥተው እንዲያው ቀሩ ። አሁንም የኢትዮጵያ ሐብታሞች ለልጆቻችሁ ገንዘብ ከማቆየት የተማሪ ቤት አቋማችሁ ብታስተምርዋቸው በሐብት ላይ ሀብት ይጨምራሉ። ከክፉ ነገር ይከለከላሉ ትምሕርት ቤት ባትሠሩና ባታስተምሩዋቸው ገንዘብ ብቻ ብታቆዩዋቸው ገንዘቡን ሥራ ከልሠሩበት ተማሪ ቤት ገብተው የንግዱን የሂሳቡን የወጭና የገቢውን የቀሪውን አኳሆን ካላወቁ የማብዛትና የማጉደልን ማከፈልና የመደመርን አከሄድ ካልተማሩ ገንዘብ ቢኖራቸው ጥቅም (ትርፍ) አያገኙበትም የገንዘብን አሠራር የማያውቅ ሰው ብዙ ሚሊዮን ቢኖረው በእጁ አፈንጫ የወርቅ ቀለበት እንደ ማንጠልጠል ነው ። አሁንም መኳንንትና አገረ ገዥ ምስለኔና መልከኛ የሆነ ሁሉ መንግሥት ከሠጠው ከሚያገኘው ገቢ ውሥጥ ከሥር አንድ ለተማሪ ቤት እርዳታ ቢያወጣ ለኢትዮጵያ ታላቅ ሐውልት ማቆሙን እናሳስባለን፤ የሥጦታውም ሁኔታ ባለፈው ጋዜጣ በዚሁ ዓመት በቁጥ ፫ እንደተጻፈው ለተማሪ ቤት ከሥር አንድ እንዲያወጣ ነው ፤ ነገር ግን ገቢያቸው እንስሳ፥ እህል፥ ማር፥ ሸማ፥ ብረት ፥ የሆነ እንደሆን ይህ እየተገመተ ከሥር አንዱ ወጥቶ ገንዘብ እንዲከፈል እንመኛለን። አገረ ገዥዎች አገር ለማሠለጠን መንግሥት ከሠጣቸው ማግኘት ከሥር አንድ ለጥበብ ተማሪ ቤት ቢያወጡ አንዳች ጉዳት አይመጣባቸውም ። ግን ገንዘብ እሚያወጡ ከሆነ ለሀገር ጉዳት፥ ለሚመጣው ትውልድ ዕንቅፋት መሆኑን ለብርሃኔ ልጆች አሳስባለሁ ማለት ጥበብ ያንግሣል፥ድንቍርናን ያስፋል፥ ባላጋራ ይደረጃል አሁን አምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ነው ለአምሳ ሰው ግን ጌጥ ነው ይባላል ። የኢትዮጵያ አገረ ገዥዎችም ከሥር አንድ ቢሰጡ ወጭያቸው ቀላል ነው መንግሥት ግን በሙላ ኢትዮጵያ የጥበብ ተማሪ ቤት ለማቆም ብቻውን ሕዝብ ሳይረዳው ከግምጃ ቤቱ ወጭ ገንዘብ ቢያደርግ ቀለብተኞችንና ደሞዘኞችን ችግር ያገኛቸው ይመስለኛል ። ስለዚህ መንግሥትና መኳንንት እየተጋገዙ የተማሪ ቤት ለማቆም ሐሣባቸውን በአንድነት ቢጀመር መሠረቱ የጸና ይሆናል። ነገር ግን ከመኳንንቶችና ከሀብታሞች የተማሪቤት ሥራ መንግሥት ቢያደርገው ያቁም ባያደርገው ይቅር፥ ገንዘብ አናወጣም የሚሉ ቢኖሩ ንጉሥ ወደ ሰልፍ በገባ ጊዜ ሠራዊቱ ባይረዱት እርሳቸው እንደ ሚጎዱና እንደሚጠፉ እንደዚሁ መንግሥታችንን በገንዘብ ካልረዳነው በጥበብና በእውቀት በኩል ካልሠለጠንን የዓለም ጉዳት የሚሆን ድንቁርና ጥፋት ያመጣብናል ክቡሩ አንባቢዎች ያምራል ብሎ ከመናገር ይከፋል ብሎ መተው ይሻላል የሚሉት ተረት አለና ከዚህ በላይ የተጻፈውን የተቃና ሀሳብ መስሎኝ በድንቁርናዬ ስለጻፍኩት ስሕተት ቢኖርበት ይቅርታ እንድታደርጉልኝ ከእውቀታችሁ ደረጃ በታች ወድቄ ክቡርነታችሁ በትኅትና እለምናለሁ ።

በቀለ አበዬ።

ስለ ዘበኞች ትጋት ።

አንድ ሐሰተኛ አታላይ አዋቂ ጠንቋይ ነኝ እያለ የሚያታልል ሰውዬ የማታለያ መጽሐፎቹን ይዞ አንዳንዶችን ግብዞች ሲያታልል ሳለ የከፍላቸውን ጥበቃ በትጋት የሚጠብቁ ዘበኞች ይኸንኑ አታላይ በምርመራ ከነመጽሐፉ ይዘውት ከ፳ኛው ኮሚሳርያ ዳኞቹ ሥራውን ቢጠይቁት መጠንቆሉንና መጽሐፉም የሱ መሆኑን አምኖ ስለታሠረ የዚሁ ያታላይ አባቱ ለኮሚሳርያው ሹም ፯ብር ጉቦ ይዞ ቀርቦ ይኸንን መታያ ይቀበሉኝና ልጄን ይፍቱልኝ ብሎ ለመነ። የኮሚሳርያው ሹም እኔ መንግሥት የሰጠኝ የወር ቀለቤ ለትዳሬ አላነሰኝም ፥ እኔ መሾሚ ጥፋተኞችንና አታላዮችን ልጠብቅ ነው እንጂ በገንዘብ ልዋዋል አይደለም የተሾምኩት ብለው ተናገረውት ፯ቱንም ብር ለጉቦ ያመጣውን አሲዘውበት አታላዩ ጠንቋይ እንደታሰረ ቈየ ።

፪ኛ ደግሞ አንድ አታላይጠንቋይ አዋቂ ነኝ ብሎ ብዙህ ወሬዎች ያልተማሩና መጻሕፍቶችን ያልመረሩ ከንቱ ሐሳቦችን የሚከተሉትን ሰዎች እያጨበጨበና እየገዘፈ ሲያታልል ሳለ ፭ኛው ኮሚሳርያ ጠባቂዎች በጥንካሬ ጥበቃቸውና ምርመራቸውን ይኸንን አታላይ አግኝተውት ይዘው ፭ኛው ኮሚሳርያ ዳኞች ላይ አቅርበው ቢጠይቁት መግዘፉንና ማጨብጨቡን አምኖ ለቅጣቱ በእሥር ቆይቷል ።

፫ኛ አንድ ሌባ ከሥላሴ በተክስቲያን አጠገብ ካለው ሚዳ አንድ አህያ ሰርቆ እየነዳ ሲሄድ የ፫ስተኛው ክፍል ኮሚሳርያ

ዘበኞች የማን አህያ ትነዳለህ ብለው ቢጠይቁት የጐረቤት አህያ ነው ብሎ መለሰላቸው ይህ አህያ የጐረቤትህ አይደለምና ውነቱን ንገረን ብለው ቢመረምሩት የጐረቤቴ አህያ አይደለም ከሜዳ የሚግጠውን ሰርቄ መሄዴ ነበር ብሎ መስረቁን አምኖ ለቅጣቱ ታሥሮ በለገንዘቦቹም ተገኝተው አህያውን ወሰዱ።

፩ኛ ፪ ሌቦች አጐረቤታቸው ላይ አንዱ ሰራቂ ሁለተኛው ተቀባይ ሆነው አንድ ለበን ጠመንጃ ሰርቀው ለአንዱ ወዳጃቸው ሰጥተው ሳለ ባለ ገንዘቡም በረቱ ከቤቱ እንደ ተሰረቀ አኳኋን ለዘበኞች አለቃ አቤቱታውን አቀረበ የዘበኞቹም አለቆች ባቅራቢያው ያሉትን ሲመረምሩ ከቤት ውሥጥ የሰረቀውንና እውጭ የተቀበለውን አግኝተው ቢጠይቋቸው አምነው ደግሞ እነሱ የሰጡት አስቀማጩ ባላደራ ክዶ እዘበኛ ሹም ላይ ቀርበው። የዘበኛው ሹምም በጽኑ ምርምር ያንን የከደውን ባላደራ ቢመረምሩት ጠመንጃውን መቀበሉንና ለአንቱ አገር ቤት እንዲሰድለት ጠመንጃውን መስጠቱን አምኖ አቀባዩ ተነተቀብዩ ባላደራውም በቅጣት ቆይተዋል ።

እነሆ የተዋበች ከተማችንም በመንግሥቶችዋ እርዳታና ኃይል በዘበኞችዋ ጥበቃና ትጋት፡ አታላዮችና ቀጣፊዎች እየጠፉ፡ ሰላምንም እያሰፉ ዘበኞቹም ትጋታቸውንና ጥበቃቸውን እያሻሻሉ በመሄዳቸው፡ ለተመልካቾቻቸውና ለተወላጆቻቸውም በጣም ታላቅ የደስታ ደስታ እየሆነ ይታያል ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ስለ አስተርእዮ ማርያም በዓል አከባበር ።

ከበዓለ ጥምቀት እንሥቶ እስከ በአተ ጾም ያለው ወራት አስተርእዮ ይባላል ። ይህም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆን በዚህ ዓለም ተገልጦ ቅዱስ ወንጌልን ያስተማረበትና ተአምራት የሠራበት ስለሆነ ነው።አስተርእዮም ማለት መገለጥ ማለት ነው። የእመቤታችንም የእግዝትእን ማርያም የዕረፍትዋ ቀን በዚሁ ወር ውሥጥ ስለሆነ አስተርእዮ ማርያም ይባላል። ስለዚህ ጥር በ፳፩ቀን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በዓሉን ለማክበር ባማረ ዓጀብ ሁነው በጥዋት ወደ እንጦጦ ቤተ ክርስቲያን ወጥተው በዓሉን አክብረው ባማረ ዓጀብ ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሱ ።

ዝኒት የምትባለው የጻፈችው የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ምሥጢር ያለው የሕይወት ታሪክ በከፍቴን በቢክያን ታርሞ ተጻፈ ።

፱ኛ፡ ክፍል ።

የተወደድሽ ሆይ በትልቅ አደጋ ውስጥ ልታገቡኝ ይመስለኛል እንዴት ያለ ትልቅ ሕመም ይመልሻል አንድ ሰው እንዲት ሴት በወደደ ጊዜያት ቤቷንና አድራሻዋን ባያውቅ እስቲ መልኬንና ፊቴን ተመልከች እህትሽን ፈጽሜ እንድወዳትና እንዳመልካትም የሚያስረዳ ጽሬት ታነቢያለሽ በኔ ዘንድ በዓለም ካለው ነገር ሁሉ የበለጠች ናት እንደዚህ ባልሆን ወደዚህ አገር አልመጣም ነበር ይህንንም ካለኝ በኋላ መልሼ አልኩት ወንድሜ ሆይ በርግጥ አውቃለሁ እህቴን እንድታምናት አሁንም በዚህ ፍቅር ይዤሃለሁ ይህን ነገር እንድነግርህ እታስጨንቀኝ ዝም በለኝ

ሪዶልፍም ይህን ባልኩት ጊዜ ዝም ማለት አልተቻለውም እጄን ወደዝኒት ዘርግቶ በውኑ እህትሽ ከኔ ጋራ ያላት ፍቅር አለመጠን ያነሰ ነውን ? ይህንንም ባለኝ ጊዜ በልቤ ልንገረው ወይስ ልደብቀው ኢያልኩ አመነታሁ። ከዚያ በኋላ ወንድሜ ሆይ በውነት እህቴም አንተ እንደምትወዳት ትወድኃለች አልኩት

ሪዶልፍም መልሶ አለኝ እየ የተወደድሽ ሆይ እኔ ከህትሽ ጋር ከመጋባት በቀር ሌላ ሐሳብ የለኝም።ከዚህም ንግግራችን በኋላ የሪዶልፍና የአሊክስ ፍቅር ከወሰን ያለፈና ልክ የሌለው መሆኑን መዘንከት ወዲያው እርሱን ትቼ በሥውር መንገድ ወደ ግቢያችን ገባሁ።ከአሊክስም ዘንድ በደረስሁ ጊዜ እርሷ ያለ ትዕግሥት ተጠብቀኝ ነበር እኔም የተነጋገርነውን ሁሉ ነገርኳት አሊክስም የነገርኳትን ሁሉ ከሰማች በኋላ ትንፋሽዋን ከፍ አድርጋ ተነፈሰችና እየ ሪዶልፍ በውነት የትልቁ ሰው ልጅ ነው፡ደግሞም የተወደደ ነው፡ ፍቅራችንም ብዙ ጊዜ ከልክ ያለፈ ሆነ አለች፡ እኔም መልሼ አልኳት እየ እህቴ ሆይ ይህ ነገር ትልቅ አደጋ ያመጣብሻል፡ መቼም ከሪዶልፍ ጋራ እንድትጋቢ ታውቂያለሽ፡ አንች የንጉሥ ልጅ ነሽ ስለምን ዘርሽንና ወገንሽን አታስረጅውም ገልጸሽ የነገርሽው እንደሆነ ፍቅራችሁ መጨረሻው አለመጋባታችሁን ከታወቀ በኋላ አደገኛ ሳይሆን አይቀርም።

አሊክስም ከዳነች በኋላ ሶስት አራት ጊዜ በሥውር ሁና ወደ ሪዶልፍ ሄደች ከዚያም በኋላ አንድ ቀን ከንጉሥ ቤት ዘመድ ብትሆን ከታላቋ ከማዳም ሄርት ፌሊት ጋር ለመናፈስ ፈቅደን ተነሳን፡ ወዲያውም ለመውጣት ወደ በሩ ሳንቀርብ ሪዶልፍ ከደጃፉ ቆሞ ይጠብቀን ነበር ሰውነቱም ግሎ ፊቱ እሳት መስሎ ይታይ ነበር።

ከዚያም በታየነው ጊዜ አወይ ጉድ እነሆ ማን እንደሆናችሁ አወቅሁ፡አንቺ ማን እታለሽኝ ነበር፡አንቺም አልጋ ወራሺቱ አሊክስ አይደለሽምን በዚያን ጊዜ አልጋ ወራሺቱ አሊክስ ደነገጠች አንዳችም ነገር ለመናገር አልተቻላትም ከድንጋጤም የተነሳ እንደ ፡ ረዶ ተዘቀዘች ሪዶልፍም እንቅጥቅጥ እንደያዘው ሁኖ ተንተበትቦ የማክበር ሰላምታ ከሰጠ በኋላ ተሰናብቶ ሄደ በዚያን ጊዜ ማዳም ሄርት ፌልት ባትኖር ግን አሊክስ ይቅርታ አድርግልኝ ብላ በኋላ በኋላው ለመሮጥ ፈቃድ ነበራት።

ማዳም ሄርት ፌልት በመደነቅና በቁጣ ቃል ይህ ሰውማነው ብላ ጠየቀች እኔም ይህ ያለ ጥርጥር አራሱ የዞረ ነው ብዬ መለስኩ ወዲያው በልቤ የፈራሁት ደረሰ አልኩ ።

እንዴሁም ሪዶልፍ ያፈቀራት ሴት ምን እንደሆነች ከወዴትስ ወገን እንደሆነች አወቀ ከዚህም በኋላ ይህች ሴት አልጋ ወራሽ ስለሆነች ለመጋባት የማይመቸውና እንዲያው ለርሷ በለመዋልና ፍቅር ለመሆን የሚቻለው መሆኑን ተረዳው

ሽርሽር ብለን ከተመለስንም በኋላ አሊክስ አቤቷ ገብታ ፫ ቀን ሙሉ አለቀሰች።

ከአንድ ሳምንት በኋላ አሊክስ አንድ ከሎንድር የመጣ ወረቀት ተቀበለች ይህም ወረቀት ስለምን እንደተጻፈ አልነ-

ገረችኝም። እኔም በሥውር ብመለከት አሊክስ አኔት ለምትበለዋ ጓደኛችን ለዚህ ወረቀት መልስ በቴሌግራም እንዲሄድ ወደ ፖስታ ቤት ላከችው። በዚያ ቀን ንጉሥ ነገሥቱ ቢልሄል ታላቅ የወታደር ሰልፍ አደረገ። አሊክስም በንጉሡ ፊት መቅረብ የግድ ሁኖባት ነበረ ። ደግሞ በዚሁ ቀን ሁለተኛው ቴሌግራም ከሎይድ መጣላት። ይህንንም ቴሌግራም ተመልክታ ታላቅ ድንጋጤ ወደቀባት፤ ወደ ሰልፍም ወጥታ ከንጉሡ ነገሥቱ ፊት ለመቅረ አልቻለችም ።

ካፒቴን ባቢክየን።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል።

Avis.

Le délai pour les offres d'adjudication pour la fourniture et l'installation des postes de T. S. F. prévu par l'avis du 31 décembre dernier qui devait avoir lieu le 28 février 1929 a été retardé jusqu'au 20 mars 1929.

Ministre des Postes et Télégraphes

ማስታቂያ ።

ያንደኛ	ዓመት	ብርሃንና ሰላም	ተጠርዞ ዋጋው	፳፫	ብር
የሁለተኛ	”	”	”	፳	”
የሶስተኛ	”	”	”	፲፫	”
ያራተኛ	”	”	”	፲	”

የውጭ አገር ወሬ

ከጀርመን ሌጋሲዮን የመጣ የጥር ፳፩ ቀን የለት ወሬ ። ፔሻዋር፤ የአማኑላህ አንድ ክፍል ወታደር ወደ ቀቡል በፍጥነት እንደ ቀረበ፤ ሐቢቡላህም ገንዘብ ያገሮቹን ይዞ ወደ ተራሮች በአየሮፕላን ለመብረር እንደ ተሰናዳ ይወራል።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የ ሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፪ ብር
ነበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፬ ብር
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኮረጃ	፻፹፫ ብር
ባለሰይጣን		፻፹ ብር
፡ ፡ ባለ ድመት ።		፻፸፪ ብር
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፸ ብር
፡ ፡ ባለሰበ ግመል ።		፻፶፫ ብር
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፬ ብር
“ “ ጃፖን		፻፶፬ ብር
ሉክር	፩ ጁኒያ	፳፫ ብር
ቃዬ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፶ ሳን
ባአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፮ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞ ቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባትሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋ ውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሽ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ገረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።



COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈ/ስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሬስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELÆKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ አሸቴ ሙዚቃ ሸከላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጕርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሸቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደላም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድቀም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

ቆማርማሮ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፮
5 me ANNÉE № 6

ሐሙስ ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 7 FEVRIER 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፴፬ ገጽ ተከታይ ።

ምዕራፍ ፬፡

(፲፫) ዋጋ ማለት ምንድር ነው?።

በኤኮኖሚያ ከሁሉ ይልቅ ዋጋ ማለት ለይቶ ማወቅ የሚያስፈልግ ነው ። ይልቁንም ለኛ ኢትዮጵያውያን በቋንቋችን (አማርኛ) ሦስት ልዩ ልዩ የሆኑ ነገሮች በአንድ ቃል ዋጋ ብለን የምንጠራቸው ስለ ሆነ በጥንቃቄ ለይተን ማወቅ ያስገድደናል ። (Costo, Prezzo, Valore,)

ዋጋ ማለት አንድ የሚያዝ ጉልህ ነገር (ኰንክሬቶ) አይደለም ፤ ሁለት ወይም የሚበልጡ ነገሮች መለዋወጫ ሚዛን ነው እንጂ። ምሳሌ) አንድ ጠመንጃ ፶ብር ቢሸጥ የጠመንጃው ዋጋ አምሳው ብር አይደለም፤በጠመንጃውና በብሩ ስምምነት ነው እንጂ ። እንዲሁም እንደ ጉድጓድ ውኃ ጥልቀቱ ፴ ሜትር ቢሆን በሁለቱ ትልቅነት ስምምነት ነው እንጂ ጥልቀቱ ሜትር ነው ሊባል አይቻልም ። በሁሉ እንዲህ ይወሰናል ዋጋ ጉልህ (ኰንክሬቶ) የሚያዝ የሚታይ አይደለም፤ ረቂቅ (አስትራቶ) የማይያዝ የማይታይ ነው እንጂ ።

ይህንን ገንዘብነት ወይም ብዛት ብለን የምንጠራውን ዋጋ ከሁለት ወይም የሚበልጡ ነገሮች ሲበላለጡ ነው እንጂ አንድ ነገር ብቻ በሆነች ዋጋ አላት ፤ወይም ዋጋ የላትም ለማለት ባልቻልንም።ስለምን እንደ ትልቅነታቸው ወይም እንደጠንክርነታቸው፤ወይም እንደ ክብደታቸው፥ አንድ ወይም ሁለት ፤ወይም የሚበልጡ የሚያስማምዋቸው (የሚያስተካክልዋቸው) በመካከላቸው ሊኖሩ ያስፈልጋቸዋልና ዋጋን የምርጫ፥ የክብረት፥ የማዓርግ አሳብ ሊሆን ይችላል ። (ምሳሌ) ከአንዲት አህያ አንዲት በቅሎ ትበልጣለች ብል ጠቀሜታየን አስተካክላለሁ ።ማለት ከአህያቱ ከማገኘው ጥቅም ይልቅ ከአንዲት በቅሉ የማገኘው የምታገለግለኝ ፥ ወይም ብሸጣት የምታተርፈኝን (የምታረብኝም) አስባለሁ ። እንዲያው በቅሎ ብዙ ታወጣለች ብል ግን በአእምሮዬ በጅምላ ከሌሎች ነገሮች ወይም ብር ይልቅ ከፍ ያለች መሆንዋን ማሰቤ ነው።በመጨረሻ አዳም ዝሚት እንዳመለከተው ዋጋ የምትባለውን ቃል ሁለት የተለያዩ ትርጓሜዎች አሏት።አንድ አንድ በልይ ያንድ ነገር (ስቃ) ጥቅም ታስረዳለች፤አንድ አንዱም ሌላ እቃ ለመግዛት የዚህ ገንዘብነት የሚያስማማ ማለት አንዱ የመሥሪያ ዋጋ ሌላው የመለዋወጫ ዋጋ ሊባል ይቻላል ።

(፲፬) የመሥሪያ ዋጋ ።

የመሥሪያ ዋጋ ማለት ለአንድ ሰው ያለው፤ወይም ሊያገኘው የሚፈልግ የተሰጠው(የፍጥረት) ሀብት ጥቅም ነው ።ይህን ዋጋ ያልነው እንደሰው፥ እንደ ጊዜው፥ እንደ ስፍራው፥ተለዋዋጭ ነው።ምሳሌ ላልታመመ ሰው መድኃኒት አያስፈልገውም ፥ ወይም ማንበብ ለማያውቅ ሰው መጽሐፍ (ዋጋ) ጥቅም የለውም ። በረዶ በሙቀት ጊዜ እንጂ በብርድ ጊዜ ማንም አይፈልገውም ።

ወሀ እንደዚያ ያህል ጥቅም ሳለው ምንም ዋጋ የለውም ስለምን ከሚያስፈልገን በላይ አልፎ ተርፎ እንዲያው አንድ ነገር ሳንሠራበት ይቀራልና ፤ ስለዚህ የዋጋ መዓርግ ምንም የለውም ይባላል። አንድ ቀን ወሀ በማይገኝበት በረሃ ብንገኝ ግን አንድ ማሰሮ ወሀ በጣም ከከበረ አንድ ደበጃን አረቂ በተወደደች።

(፲፭) የለውጥ ዋጋ ።

የለውጥ ዋጋ ለሌላ መለዋወጥ ከምትችለው ነገር የተሰጠች ነች ።እስረጅ አንድ ዓይነት ነገር (እቃ)ለያንዳንዳችን ልዩ ልዩ ጥቅም ይሰጠናልና ፥ ስለዚህ አንድ ነገር እንዲያው ከአንድ ሰው ወደ ሌላው ሰው ስላለፈች ዋጋዋን ታንሳለች ወይም ት

ክብራሎች (ታድጋሎች) ይሂው ሁለት ወይም የሚበልጡ ሰዎች በገበያ ሲገናኙ ለየጥቅማቸው በሥራ፡ወይም በንግድ ዋጋቸውን ሊለዋወጡ ይችላሉ ። ገብረ ማርያም ሁለት የኪስ ሰዓት ቢኖረው ሁለተኛው የኪሱ ሰዓት ትርፍ ነውና የሚያደርግለት ከሌለው በራሱ ዘንድ ሁለተኛ የኪሱ ሰዓት ርካሽ። ነው ስለምን ጥቅሙ ትንሽ ነችና የኪስ ሰዓት ለሌለው ለገብረ እግዚአብሔር ግን የሚያስፈልገው ነውና ዋጋው በጣም ከፍ ያለ ይሆንለታል። ስለዚህ ገብረማርያም ሁለተኛውን የኪስ ሰዓት ለመተው ቈርጥዋልና መለወጫው ሌላ ነገር (ለምሳሌ) ባርኔጣ ወይም ጫማ ከገብረ እግዚአብሔር ይፈልጋል፣ በዚሁ ስምምነት የተለዋወጡበትን ነገሮች የልውውጥ ዋጋ ይባላል ።

ስለለውጥ ዋጋ ስንነጋገር ሳለን ብዙ ሌሎች ነገሮች እንደምትይዝ (እንደምታወጣ) እናውቃለን። የወርቅ ሰዓት ወይም አልማዝ ያለበት ቀለበት የለውጥ ዋጋቸው በጣም ከፍ ያለ ነው ስለምን ከሌሎች ብዙዎች ሀብቶች የሚለዋወጡ በመሆናቸው ነው እንጂ፡ የመሣርያ ዋጋቸውን፡ የጥቅሞ ዋጋቸውን ጥቂት ነበር።ሥጋ ግን የለውጥ ዋጋ ምን ያህልም የላትም፡ ስለምን በትንሽ መለወጫ ልትገኝ ትችላለችና ። የመሣርያ ወይም የጥቅም ዋጋዋ ግን የትና የት ከሁሉ ከከበሩ ዕንቆች በጣምከፍ ያለች ነች።እንዲሁም በፍጥረት ካብቶች መኻከል በመለዋወጫ ዋጋቸው ልዩነት አለ።ምሳሌ በአንድ ተሙን ከሥጋ ይልቅ ብዙ እንጀራ፡ከጠጅ ይልቅ ብዙ ጠላ፡ከአረቂ ይልቅ ብዙ ወተት ሊገዛ ይቻላል።የጥቅም ዋጋቸው ግን ከሥጋ እንጀራ፡ከጠጅ ጠላ፡ከአረቂ ወተት እንደሚበልጥ ማንም አይስተውም ይሆናል።እንደሁም እንጀራ ለራበው አንድ ሰውና ላልራበው ሰው የለውጥ ዋጋው አንድ ልክ ነው።የጥቅም ዋጋው ግን ስንት ልዩነት አለው። በጭሩ ዋጋ የምትባለውን ቃል በአንድ ነገር ሌላው ነገር እንደሚለዋወጥ ብቻ ያመለክታል። የትክክልነታቸውና የብዛታቸው መለኪያ ግን የነገሮችም ሁሉ የሚለክ የጥሬ ምዋጋ ነው። ማለት የማቀረብና የጥያቄ (ዶማንዲ ኦፌርታ)ብዛት በብር ዋጋ ንግድን ያስማማል ።

አስረጅ መቶ ኪሎ ብረት በመቶ ኪሎ ሥንዴ ሊለዋወጥ ብትቻለ መለኪያቸው አንድ በአንድ መሆኑ ነው ። መቶ ኪሎ ነሐስ ግን ሠላሳ ጊዜ የሚበልጥ(ማለት ፫ሺ. ኪሎ)የሥንዴ መለኪያ ባወጣ ። እዚሁ ልክነታቸው ከአንድ እስከ ሠላሳ ብሆን። ፩ ኪሎ ብረት ስለ ምንድርነው ፫ ጊዜ የሚበልጥ ማለት ፫፻ ኪሎ ሥንዴ የማታወጣ? ትርጓሜው በፊት በመለከት ነው የጥቅምን መጨረሻ (ፊናለ)መፈለግ ነው ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ሳምንት ይታተማል ።

ሚካኤል ተሰማ ።

ስለ ኢትዮጵያ አቡን ።

ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ የወጣው ሞክታም የሚባለው ጋዜታ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ጽፏል ።

ረቡዕ ጥር ፱ ቀን እቤታቸው እንዲሰበሰቡ ሊቀ ጳጳሱ በልዩ አድርገው ከጠሯቸው ሰዎች የኢየሩሳሌምና የቃና ግሪካውያን፡ሐፊዝ አፊፊ ቤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ነሞቲኢ. ፓሻ፡ ሱሌማን ፓሻ፡ ዶስ ፓሻ፡ ፈ. ሞቲኢ. ፓሻ፡ እስሜክ ፓሻ፡ከሊኒ ፓሻ፡ አዋድ ቤ፡ አንቱን ቤ፡ ሰደላ ቤ፡ ሞክራፌ ኤፌንዲና አዲስ አበባ ለመቀመጥ የተመረጡት የምስር አገር ቆንሲል ፋራጣ ሙሳ ተሰብስበው ነበር ።

እንዳንዶቹ አማካሪዎች ባልንጀሮቻችን አልተጠሩምና ለመምጣት አይቻለንም ብለው አስታወቁ።

የሊቀ ጳጳሱ ቤት ዲሬክተር ሙሴ ሲዳሮስ ቤ ቢሽሬ የዴር ሡልጣንን ነገር የሚከራከሩበት መስሏቸው ላማከሪዎቹ አቀረቡላቸው ።

ሱሌማን ፓሻ የኢትዮጵያንና የምስርን መንግሥት የሚያገናኛቸው መንገድ እንዲሰፋ ሲሉ ከንጉሥ ተፈሪ ጋራ የተነጋገሩትን ነገር እስከ እኩል ሰዓት ድረስ አስረዱ ፡ ስለዚህም ድካማቸው ሳርዋት ፓሻ አመሰገኑአቸው ። ከዚህ በኋላ ከንጉሡ ጋራ የተጻጻፉትን ወረቀት ለጉባኤው አነበቡ።ምሥጢሩም የተማሩና ደኅና አድርገው ማስተማር የሚችሉ አንድ ሊቀ ጳጳስ ከግብጽ በሥራቸው የሚረዷቸው የሚያስፈልገውን ያህል የኢትዮጵያ መምህራኖች ኤጲስ ቆጰስነት እንዲሾሙ የሚጠይቅ ነው፡ ከዚህም ሌላ ንጉሥ ተፈረ ሱሌማን ፓሻን ስለ ክፍታው አዲስ አበባ መሆኑ ቀርቶ ድሬዳዋ በደስታ እቀበላቸዋለሁ ይላል። የዴር ሡልጣንን ነገር የሆነ እንደሆነ ግን በኢትዮጵያውያንና በግብጻውያን መካከል ሳይቆረጥ የቆየና መቆረጥ የሚገባው ነገር ቢሆን እንኳን ቅሉ በወረቀቱ ውሥጥ በግልጽ አልተነገምና ስለዚህ ጉባኤው ሳይከራከርበት ቀረ።የተከራከሩት ባቡን ነገር ብቻ ነው።በዚህም ነገር ሐፊዝ አፊፊ ቤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአቡኑ ነገር ለመንግሥታችን የቤተ ክርስቲያንና የሃይማኖት መንገድ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ላገሩም የሚጠቅም ነገር መስሎ ስለታየው እንደ ኢትጵዮያውያን ጥያቄ ሁኖ አቡኑ በቶሎ ቢሾሙ ፈቃዱ መሆኑን ለሊቀ ጳጳሱና ለተሰበሰበው ጉባኤ እንዳስታውቅ ታዝዣለሁ ብለው ተናገሩ ።

መንግሥትም ምስርና ኢትዮጵያ የሚገናኙበትን መንገድ ለማፅናት ነውና ፍላጎቱ በዚህ ነገር ኢትዮጵያውያንና የግብጽ ቤተ ክርስቲያን እንዲስማሙ የምትጠይቁትን በችሎታው ያለውን ነገር ለማድረግ የተዘጋጀ ነው አሉ።ሲጨርሱም እንደ ክርክራችሁና እንደ ወረቀቱ ቃል የሆነ እንደሆነ የኢትዮጵያውያን ጥያቄና የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው ነገር እጅግም አልተራራቁ ብለው ተናገሩ። ስለዚህም ንግግራቸው ጉባኤው አመሰገንዋቸው።በ፲፩ ሰዓት ከሩብ ወጥተው ሔዱ።

ጉባኤው እስከ ፲፪ ሰዓት ከሩብ ድረስ ቆይቶ ተከራክሮ አንድ ላይ ተስማምቶ ከዚህ በታች የሚከተለው ቴሌግራም በፈረንሳዊ ቋንቋ ለንጉሥ ተፈሪ እንዲያልፍላቸው ፈርሞ ሰጠ።

ለልጃችን ለሱሌማን ፓሻ ግርማዊ የላኩላቸውን ወረቀት አነበብነው ። የግብጽና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያኖች የሚገናኙበት መንገድ እንዲፀና መፈለግዎን ስለተረዳነው እጅግ አድርጎ ደስ አለን ። የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንና ልጆቻችንን ኢትዮጵያውያንን እንደምናፈቅራቸው በኔም በግብጻውያንም ስም ሁኜ ለግርማዊነትዎ አስታውቃለሁ ። የሚጠይቁትንም ነገር ሁሉ የሚያውቅ አንድ አቡን ለኢትዮጵያ ለመሾም የተ-

ዝጋጀን መሆናችንንም እስታውቅዎታለሁ ። የቤተ ክርስቲያንም ሕግ ቢፈቅድልን ኖሮ ሌሎች አቡኖች ለመቀባት እንዲችሉ ሥልጣን እንሰጣቸው ነበር። ነገር ግን ይህ የማይቻል ስለሆነ ከዚህ ቀደም ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ሳይሞቱ ሱሌማን ፓሻ እጨጌን ይላኩልንና አቡን አድርገን እንቀባቸዋለን ብለው ለግርማዊነትዎ የጻፉትን ቃል ደግመን እናረጋግጥልዎታለን ። አቡኑንም በሥራቸውና በኢትዮጵያ ግዛት ውሥጥ የሚረዷቸው የሚበቃ የሚመስልዎትን ያህል የግብጽ አቡኖች ለመሾም የተዘጋጀን ነን ።

በኢትዮጵያውያንና በግብጻውያን መካከል ያለው ሳይቆረጥ ቆየው ነገር ሁሉ ለሁለቱም ወገኖች እንደሚስማማቸውና ግርማዊንም ደስ እንደሚያሰኝም ሁኖ እንዲቆረጥ በሙሉ ልባችን መፈለጋችንን እናረጋግጥልዎታለን ።

ዋና እርዳታዎን የሚገልጽልንና የኢትዮጵያም አቡን በቶሎ እንዲሾም የሚረዳነን መልስዎ እየጠበቅን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ለልዑላን ቤተ ዘመዶቻችሁ ለራሰቹና ለሕዝቡም ቡራኬአችንን ልከንላችኋል ።

አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ።

ይህ ቴሌግራም ሐሙስ ጥር ፲ ቀን አለፈ ።

የዴር ሡልጣንን ነገር ኢትዮጵያ እንደገና አነሣች ።

ደግሞ ሞከታም የሚባለው ጋዜታ ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ (ጥር ፱ ፲፱፻፳፱) የወጣው እንደዚህ ይላል ።

ንጉሡ የዴር ሡልጣንን ነገር እንድንጨርስ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ እለምንዎታለሁ ብለው ለሱሌማን ፓሻ ወረቀት ጽፈውላቸዋል ያዲስ አበባም አየር ለጤናዎ የማይስማማዎ እንደሆነ ከሌላ ከተማ እቀበልዎታለሁ ብለዋቸዋል ። ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ዮሐንስም ይኽን ወረቀት ካነበቡ በኋላ የኤስንና የኢየሩሳሌምን የቃናን አቡኖች ደግሞም የዴር ሡልጣንን ነገር የሚያውቁትን ትልልቆች ሰዎች እንደነ ሱሌማን ፓሻ፡ማርቆስ ሐና ፓሻ፥ እስሜል ፓሻ፥ዶስ ፓሻ፥ከሊኒ ፓሻ፥ፌህሚ ፓሻ፥ሞቲኢኒ ፓሻ ፡ያሉትና የቀሩትንም ማክሰኞ ጥር ፱ ቀን ተሰብስበው በዚህ ነገር እንዲከራከሩና ሱሌማን ፓሻ ለንጉሥ ተፈሪ የሚሰጡትን መልስ እንዲቆርጡ የግድ የሚያስፈልግ መስሎ ስለታያቸው ጠርተዋቸው ነበር ። ደግሞም የምስር መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋራ የሚያገናኘውን መንገድ ሁሉ አጥብቆ ስለሚከተል የሚገናኙበት መንገድ እንዲጠነክር ሁኖ የዴር ሡልጣን ነገር ቢጨርስ የመንግሥቱ ጥቅም መሆኑን ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ዮሐንስተረድተውት ሐፌዝ አፊፊ ቤን የውጭጉዳይ ሚኒስቴር ከጉባኤው እንዲመጡ ጠርተዋቸዋል ። ስለ ጉባኤውም መሰብሰብ ምክንያት ይኸው ጋዜታ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ጽፏል ።

ከስልሳ ዓመትና ይበልጥ ጀምረው ኢትዮጵያውያን ይኸን ነገር በልዩ ልዩ መንገድ ማንሣታቸውን አልተዉም ሲያነሡትም በቱርክ ግዛት ጊዜ ትልልቆቹን መንግሥታት መስኮብ፣ እንግሊዝና ኢጣልያን፣እንዲረዷቸው እየለመኑ ነው ።እንደዚህም አድርገው ቢጠይቁ ገዳሙ ውሥጥ ለራሳቸው አንድ በር እንዲከፍቱ ቱርኮች ፈቀዱላቸው ።

የኋለኛ ጥያቄአቸውን ያቀረቡት በ፲፱፻፳፬ ዓ ራስ ተፈሪ ወደ ሮፓ ለመሔድ በምስር በኩል ሲያልፉ ነው፤ራስ ተፈሪም በጉባኤው ከሚሰበሰቡት ሰዎችና ከቀሩትም ጥቂቶች ትልልቆች ሰዎች ጋራ ቢነጋገሩ ጉባኤው በሙላው ሲሰበሰብ ነገሩን እናቀርባለንስላሉ ለሐሳባቸው መጨረሻ ነገር ሳይደርግላት ቀረ።

ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ግን ነገሩን ለመቁረጥ ሲሉ ለመቀመጫ ብቻ የሆነ እንደሆነ እንዳይከለክሉ ብለው የገዳሙን ግማሽ ሰጥዋቸው ደግሞም በዚሁ መንገድ አንድ የስምምነት ውል ሐሳብ አሰናድተው በሚያዚያ ወር ፲፱፻፳፯ ዓ ላቡነ ማቴዎስ ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዲያቀርቡለት ልከውላቸው ሳለ ሊቀጳጳሱ ለሐሳባቸው መልስ ባለማግኘታቸው ከአቡነ ማቴዎስ ሞት በኋላ ቢደርስ ይመስላል ።

ይኸነን ሐሳብ የወደዱና የገዳሙን ግማሽ ለመቀመጫ ብቻ ስጡን እኛ በዚህ ምትክ አዲስ አበባ ለግብጻውያን አንድ ቦታ እንሰጣቸዋለን ብለው የጠየቁ ወደ ምድረ ግብጽ በመጡ ጊዜ ንጉሥ ተፈሪ ራሳቸው ናቸው ይባላል ። ዛሬ ግን ይኸነኑ ሐሳብ ይቀበሉ እንደሆነ ወይም ደግሞ ትርፍ ነገር ይጠይቁ እንደሆነ አልታወቀም ።ሁሉም ይሁንና ይኸን ነገር አቡኑ ሳይሾሙ አስቀድሞ ለመጨረስ ፈቃዳቸው መሆኑ ተረግጧል ።

ዛሬ ኢትዮጵያውያን ገዳሙን በሙሉ በጃቸው አድርገዋል የቀራቸው እውሥጡ ካሉት ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች አንደኛውን በጃቸው ማግባት በመንገዱ ለማለፍ ሥልጣን እንዲኖራቸውና የጥንቱን ያረጀውን ቤት አፍርሰው ለመነኰሴዎቻቸው አዳዲስ ቤት ለመሥራት እንዲቻላቸው ርስትነቱ የራሳቸው መሆንዋን ማስረገጥ ነው ። እስካሁን ድረስ ከግብጻውያን ጋራ ስላልተስማሙ አልሆነላቸውም ግብጻውያንም ዛሬ በገዳሙ ምንም አያገኙበት ።

ግብጻውያን የወንድሞቻቸውን የኢትዮጵያውያንን ፍቅር እንዳያጠብቁ ስንፍና ገብቷቸዋል ።

ሚስር የሚባለው ጋዜታ ዲሬክተር ታድሮስ ማንከበዲ ጥር ፱ቀን በወጣው ጋዜታ ሲጽፍ ግብጻውያን ከጥንት ጀምሮ ከኢትዮጵያውያን ጋራ የሚያገናኛቸው መንገድ እያለ ፍቅራቸውን ለማስፋት እየሰነፉ የቀሩት መንግሥታት ብዙ ሰዎቻቸውን እየላኩ ዛሬ በኢትዮጵያ በጣም የተደላደሉ የውጪ አገር ገዳሞች በመገኘታቸው አዝናለሁ ይላል ።

ወደ አጼ ምኒልክም ተልከ መጥቶ የሳቸው ጸሐፊ ሁኖ ትኒሽ ቀን የተቀመጠውንም ግብጻዊ ስም ያነሣል። ለግብጻውያን ሽልማት ለመስጠትና አስተማሪዎችም ለመጠየቅ አጼ ምኒልክ ወደ ምድረ ግብጽ መልክተኞች እንደላኩና የሐና ቤሳሊብንም መልክት ይናገራል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ይኸን ሁሉ ሲያደርግ ግብጻውያን ችላ እያሉ በኢትዮጵያ ያሉት የቀሩት የውጪ አገር ሰዎች የነሱን ቦታ እንዲይዙና ተንከል እንዲሠሩባቸው ተቻላቸው ይላል ።

ዝኒት የምትባለው የጻፈችው የቀድሞ የመስኩብ ንግሥት ምስጢር ያለው የሕይወት ታሪክ በክፒቴን ባቢክያን ታርሞተጻፈ።

፪ተኛው ክፍል ።

እኔም ወደ እልፍኝዋ በገባሁ ጊዜ አዬ እቴ ሆይ ወዳጄ ረዶልፍ ራሱን ገደለ አልኋት። ወዲያው አንድ ቴሌግራም ና አንድ ደብዳቤ አሳየችኝ፡ ይህ ደብዳቤ ግን ረዶልፍ ተብሎ በመፈረም ፋንታ ቻርልስ ተብሎ ተፈርሞበታል፤ ይህም ወረቀት ሳይሞት ከ፲፭ ደቂቃ በፊት የተጻፈው ነበር ፤ በዚያም አገር ማለት (በሞተበት በእንግሊዝ አገር) የንግሊዝ መንግሥት ረዶልፍ የሞተበትን ምክንያት ለሕዝብ ለመግለጽ አልፈቀደም ። የጀርመን መንግሥት ቤተ ንጉሡን አክብሮ በዲፕሎማቲክ ደብዳቤ ለአሌክስ አባት ለታላቁ ዱክ ላከለት ።ታላቁም ዱክ ይህን ወረቀት ከተቀበለ በኋላ ሰውነቱ ደንግጦ ይህ ወረቀት ያንቺ ነው መሰለኝ ያውልሽ ብሎ ሰጣት

አስቀድሜ በመጀመሪያው ጊዜ እንዳመለከትኩት የሎንዶን ጋዜጦች ይህን ነገር ለመግለጽ ፈቅደው ነበር ።ነገር ግን ምስጢሩን አላገኙትም ፡ እነሆ እኔ ዘንድ ገለጥሁት እንጂ ።

ይህም ሕይወት በጥፋትና ደም በማፍሰስ የተደረገው አሌክስ የምትባለው የመስኩብ ንግሥት መጀመሪያ ምስጢር ያለው የሕይወት ታሪክ ነው ።

ሁለተኛ ክፍል አለቀ ፡ ፫ተኛው ክፍል በሚከተለው ሳምንት ይቀጥላል።

ካፒቴን ባቢኪያን ።

ሹመት

ጥር ፳፫ ቀን ክቡር ልጅ ኃይለ ማርያም ገሠሠ ግራዝማች ተብለው የቀኛዝማች ፍቅረሥላሴ የነበረውን የምድር ባቡር ተቈጣጣሪነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ ያለዎ እያለ ለክቡር ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ መልካም ምኞቱን ያቀርብላቸዋል።

በባቡር የገቡ

ጥር ፳፯ ቀን በባቡር የገቡ ሙሴ ክርስቲአን ታምስ ቀድሞ የኖርቤጂያ ሚኒስትር የነበሩ ።

ድማሞ ሙሴ ፒሊ ፡
ሙሴ ማራንቲዮስ ታምስ ።
ኮንት ዣን ታርኖስኪ ።
ሙሴ ጋርማን እስታድሄም ።
ሙሴ አርቱል ፔልሴን ናቸው ።

እነዚህም የእርሻና የማዕድን መሐንዲሶች ናቸው ይባላል ።

የአንበጣ አመጣጥ ።

ጥር ፳፯ ቀን ብዙ አንበጣ ባዲስ አበባ አልፎ ወደ መንዝ አቅንቶ ሔዷል፡ ሽምብራና እንዲሁም የመሰለውን እህል ሳይ ጎዳ አይቀርም ።

ስለ ምድር መናወጥ ።

ጥር ፲፭ ቀን በጅቡቲ ማታ ጀምሮ እስኪነጋ ድረስ ምድር ሲናወጥ አደረና አንዳንድ የግንብ ቤት ተናደ፡ ላሌም ብዙ ቤት ተሰነጣጠቀ ፡ ብዙ ሰውም ቈሰሏል ።

ጥር ፲፰ ቀን ፱ሰዓት ተኩል በአዲስ አበባ ቀላል ምድር መናወጥ ሆነ ።

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የመጣ ራዲዮ
የጥር ፳፬ ቀን የለት ወሬ

ብሪያንድ በፓሪስና ቡዌኖስ አይሬስ መካከል የቆመውን የራዲዮ ቴሌግራፍ ሥራ መረቀ ፤ ከአርጀንቲን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋራም ተነጋገረ ።

ሎንዶን ፤ የፓርላሜንት ኮሚሲዮን በማንሽ በእንግሊዝና በፈረንሳዊ መካከል ያለ አጭር ባሕር ቱኔል(እንደ በርሜል ሁኖ የተሠራ መገናኛ) ለመሥራት ምክር አድርጓል ፤ የሚያስፈልገውም ሁለት ቱኔል ርዝመቱ እያንዳንዱ ሰላሳ ሁለት ኪሎ ሜትር ነው ፤ ዋጋውም ሰላሳ ሚሊዮን እስተርሊን ይሆናል፤ ግማሹ ፈረንሳዊ ግማሹም እንግሊዝ እንዲከፍል ታስቧል ።

የጥር ፳፯ ቀን የለት ወሬ

የሩማኒያ መንግሥት የስዊድንን የክብሪት ሞኖፖል ለማግኘት ሰላሳ ሚሊዮን ዶላር(የብር ገንዘብ)ሊከፍል አስረግጥዋል።

የጥር ፳፰ ቀን የዕለት ወሬ ።

ፍራንስ ፤ ማሬሻል ፎሽ ሕመማቸው ተሽሎዋቸዋል ።

የሬፑብሊክ ፕሬዚዳ የዳኒማርክን ንጉሥ ተቀብለዋል ፤ ባላንስ ፤ በስጳንያ በባላንስ ሽፍትነት እንደተነሣ ይወራል ። ጄኔራል ካባኔላስ የባላንስ ገጋር በጦር አማካሪዎች ሸንጎ ፊት ሊቀርብ ነው ።

ከጀርመን ሌጋሲዮን የመጣ ራዲዮ
የጥር ፳፯ ቀን የለት ወሬ ።

ሎንዶን ፡ ንጉሥ በጣም ስለተሻላቸው ሰኞ ከልጋ መነሳት ጀመሩ ።

ቤርሊን ፤ የአማኑላህ ትልቁ ልጅ ከፓሪስ ተነስቶ አባቱ ከካንዳሀር ሳይወጣ አያሌ ቀን አስቀድሞ ደረሰ ።

ሎንዶን ፤ ሻምበርሌን ስለ ቃቡል በጣም ምርመራ እንዲያደርግ ፡ ምክር ቤት አስታውቋል ።ጋዜጣ እንደሚያወራው ኮሎኔል ላውሬንስ በሶስተኛ ክፍል መርከብ ሆኖ ከህንድ ተነስቷል ።የህንድ መንግሥት ስለ አፍጋኒስታን የተወራውን ነገር ሊመረመር ነው

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።
ሐኪም አምብር ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ትመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታቂያ ።

ያንደኛ	ዓመት	ብርሃንና ሰላም	ተጠርዞ ዋጋው	፳፫	ብር
የሁለተኛ	”	”	”	፳	”
የሶስተኛ	”	”	”	፲፫	”
ያራተኛ	”	”	”	፮	”

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።
በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት በየዓይነቱ የደብዳቤ ወረቀትና እንቬሎፕ ፋክቱራና የንግድ ወረቀት ሁሉ ይታተማል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፵፱ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፮ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፬ ብር
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኮረጃ	፻፯ ብር
ባለሰይጣን		፻፯ ብር
: : ባለ ድመት ።		፻፳፭ ብር
: : ባለአህያ ።		፻፴ ብር
: : ባለሳቢ ግመል ።		፻፵፭ ብር
: : ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፳፭ ብር
“ “ ጃፓን		፻፵፱ ብር
ሱኳር	፩ ጁኒያ	፳፭ ብር
ሻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፹፬
ባአንድ ብር	፳ ሊሬ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም ያኦቶሞቢል ዘይትና የሚረክስ ቤንዚን ይሸጣል ።



COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ ሕገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኲላሊት ። የጆማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

ድ ራ ሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጀል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።


GOODYEAR
BALLOON
ALL WEATHER
2-28-15

ጉድዬር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፯
5me ANNEE № 7

ሐሙስ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 14 FEVRIER 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደረሴ ባገሪቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumiére et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumiére et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Dirèction et Rèdaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም ማፈልጎት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣቱ ለፊስን በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፵፪ ገጽ ተከታይ ።

፲፯፡ዋጋ የሥራ መለወጫ ነውን?

አሁን ዋጋ ከሥራ እንደሆነች፣ ወይም በሌላ ነገር የምትከብረው እንመለከት (እናስተውል) ። ብዙ ኤኮኖሚስቶች በንግድ ውሥጥ፣ (ለምሳሌ) ወርቅ ብዙ ክቡር መሆኑና ብዙ ሲያወጣ ቢመለከቱ ለማግኘቱ ብዙ ሥራ ያስፈልጋልና የክብረቱ ተአምራት (ምክንያት) ለማግኘቱ በተደከመ ብዙ ድካም ልክ ነው ይላሉ ።

ግን ሌሎች ኤኮኖሚስቲ የዚችን ባህል ተቃዋሚዎች የሆኑ ደግሞ ይህነን ባህል እውነት ቢሆን ብዙ ሥራ የሚያስፈልግ የሆነ ነገር ሁሉ ዋጋው በጣም ከፍ ያለ በሆነ ነበር ፤ ግን እውነት እንዳልሆነ ሁሉ ያውቃል ሲሉ ባህላቸውን ያቆማሉ። (አስረጅ) አንድ መጽሐፍ መጻፍ ማተሙ መጠረዙ ብዙ ሥራ ይፈጃል ፤ብዙ ሰው የማይፈልገው እንደሆነ ግን እንደ አንድ ማንም ወረቀት መቁጠሩ (መሆኑ) ጥርጥር የለበትም ፤ አንድ ነገር ዋጋ ልታወጣ ለማድረግ እንዲያውመሥራት ብቻ አይበቃም እንድትጠቅምና ለሰው ደስ እንደምታሰኘው ማለት መልካም አድርጎ መሥራት ያስፈልጋል እንጂ ።

እንዲሁ ሌሎች ብዙ ሥራ ያልፈጁ ነገሮች ብዙ ዋጋ ያወጣሉ ። (ምሳሌ) አንድ ባለ ዕድል አረኛ ጥቅል ወርቅ በበረሓ ቢያገኝ አንድ ሥራ አልፈጀበትም፣ ግን የዚያው ያገኘው የወርቁ ዋጋ እንደ ጥራቱ ፤ታይቶ እንደ ሚዛኑ ተለክቶ ያው በውድ እንደ ሁሉ ብዙ ሥራ የፈጀ ወርቅ ይሸጣል ። እንዲሁም በልዩ ልዩ ስፍራ ወርቅ የሚወጣባቸው ብዙ የጉድጓዶች ወርቅ አሉ፣ ግን በአንድ አንድ ጉድጓድ ብዙ ወርቅ

ይገኝባቸዋል። የሚፈጁት ሥራ የሁሉ ጉድጓዶች ያው ትክክል ሁኖ ሳለ ግን ፤ ወርቁ (በፊት እንዳመለከትነው) እንደ መጥራቱ እየታዩ እንደ ክብደቱ እየተመዘነ ፤ የመጣበት ስፍራ ወይም የፈጀበትን ሥራ ሳይጠየቅ ሁሉ፡ትክክል በአንድ ዋጋ ይሸጣል ።ማለት ዋጋ የሥራ መለወጫ ነው የሚለውን ባህል ልክ ቢሆን እነዚያ ከሁሉ ወርቅ የሚያወጡ ሰዎች ሥራቸው ትክክል ሳለ ፤ ጥቂት ወርቅ ብቻ ያገኙ ሰዎች ፤ ከነዚያ በብዙ ያገኙ ሰዎች ይልቅ በውድ ሊሸጡት ይገባቸው ነበር ። ስለዚህ ዋጋ የሥራ መለዋወጫ ፡ ወይም መስማሚያ እንዳልሆነ በግልጥ ያስረዳል ። ወርቅ ብዙ ዋጋ ያለው መሆኑግን ብዙ ሰዎች ወርቅ የሌላቸው በብዙ ሊያገኙት ወርቅ ያላቸው የሚበልጥ ሊጨምሩበት በጣም የሚፈልጉት ስለ ሆነና የመጨረሻ ዋጋውም በጣም ከፍ ያለ ስለ ሆነ ነው ።

ስለ ወርቅ ዋጋ ሌላ ምሳሌም ልንጨምር እንችላለን ። በትንሽ ሥራ ድካም እንደ ወርቅ ዋጋ ከፍ ያለ ለማግኘት የሚቻል ቢሆን ፤ ብዙ ሰዎች የወርቅ ቈፋሪዎች (ሚናቶሬ) በሆኑና ብዙ ወርቅም ባፈሩ ። እሱም ከፊተኛው (ያለ) ይልቅ በብዙ የተፈለገ ቢሆን ዋጋው እንደ ፊተኛው በቆመ (በሆነ)። ግን አንድ ሰው ያልተወሰነ ወሰን ወይም ኍልቍ የሌለው) ብዛት አይፈልግምና ፤ በፊት እንዳየነው ሀብት የተወሰነች ስትሆን ነች ። ስለዚህ ወርቅ ብዛቱ እንደ ብረት ያህል ቢሆን በአሁኑ ያለው ዋጋ ሊቆም ባልቻለም ። ስለምን የጌጥ ዕቃ ፤ ሰዓት፣ ዋንጫ፣ (እንዲሁ) በሚመሰሰሉ ምን ያህል ቁም ነገር በሌላቸው ነገሮች በቀር ለሌላ ጥቅም አይሆንምና ነው ።

ይኸው በተተካከለ አሳብ የዋጋን ባህል ልናቆመው እንችላለን አንዲት ነገር በትንሽ ሥራ (ድካም) በብዙ ስትገኝ በለሁ ነገር ደስ ቢልህ የሚበልጥ አትመኝም ፤ወይም ምኞትህ ትንሽ

ታገኝ የምትፈልገውን ብዙ፣ ስጥወታውና መሻቱ ካልተለዋወጠ፣ የመማርያን ዋጋ ማለት ለንግድ የለውጥ ዋጋ ቅምን ያህልም ከፍና ዝቅ አያደርገውም። ሚካኤል ተሰማ።

ከዚህ የቀረ በሚመጣው ሳምንት ይታተማል።

ማህሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ ።

ባምስተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም በቍጥር ፳ መጀመሪያ ግብጻውያን የሚጠይቁዋቸውን ነገር ሁሉ የሚያውቁ አንድ አቡን እንዲሾሙልንና በኢትዮጵያ ግዛት ውሥጥ የሚያስፈልገውን ያህል የግብጽን አቡኖች እንዲሾሙ ያመለክታል ። ሁለተኛ እጨጌን ይላኩልንና አቡን አድርገን እንሾማቸዋለን ብለው ማሰባቸውን ያስታውቃል።የግብጽ ቤተ ክህነት በቤተ ክርስቲያንና በሃይማኖት ላይ ያገር ጥቅምና የፍቅር አንድነት እንዲጸና ማሰቡን ያስረዳል።በዚህም ቃል ግብጻውያን የኢትዮጵያን ልጅነት በሃይማኖትና በፍቅር የፈለጉ ይመስላል። እኛ ኢትዮጵያውያን የግብጻውያንን አበትነታቸውን መፈለጋችንን የሚያስረዳ ነገር ማርቆስ አባታችን እስክንድርያ እናታችን ስንል እንኖራለን።የዴር ሡልጣን ነገር በኢትዮጵያውያንና በግብጻውያን መካከል ሳይቈረጥ የቈየና መቆረጥ የሚገባው ነገር ቢሆን እንኳ በወረቀቱ ውሥጥ በግልጽ አልተነገምና ስለዚህ ጉባኤው ላይ ክርክርበት ቀረ ይላል። በሰስተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ቍጥር ፲፪ ከ፺፱ እስከ ፺፫ ገጽ ስለዴር ሡልጣን ገዳማችን ነገር ብ፲፱፻፲፬ ዓመት ለታላቁ አባታችን አቡነ ቄርሎስ ያመለከትነውን ቃል ጽፈ ነበር። የኛ መነኰሳትና የግብጽ መነኰሳት ከሚጣሉበት ደረጃ ላይ ግብጻውያን ምንም ለመሥራት አይችሉም፡ የኛን ሰዎች ሥራ እንዳይሠሩ ከመከልከል በቀር፡ በቤተ ክርስቲያኑ ውሥጥ ከዴር ሡልጣን ወደ ጎልጎታ የሚያስኬድ በር አለ የበሩን ቍልፍ የያዙ ግብጾች ናቸው፡ በዚያ በር የኛና የግብጽ መነኰሳቶች አንተ ግባ፡እኔም አልገባ እየተባባሉ ሲጣሉ ይውላሉ።

መጀመሪያ የኢትዮጵያንና የግብጽን ፍቅር ያደከመው የኢየሩሳሌም ርስት ነገር ነውና የሃይማኖት አባቶቻችን ርስታችንን በፍቅር እንዲለቁልን እናሳስባቸዋለን ።

ሁለተኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የጠየቁት ቃል፡ምሥጢር የተማሩና ደግና አድርገው ማስተማር የሚችሉ አንድ ሊቀ ጳጳስ ከግብጽ እንዲልኩላቸውና በሥራቸው የሚረዱዋቸው የኢትዮጵያ መምህራኖችን የሚያስፈልገውን ያህል ኤጲስ ቆጶስነት እንዲሾሙ ነው ፡ ሐፌዝ ሐፊፊ ቤን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዳስታወቁት ቃል ። ዮሐንስ ም ፮ ቍ ፴፯ ኵሉ ዘወሀበኒ አቡየ ይመጽእ ኀቤየ ፤ ወለዘሂ መጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወጽኦ አፍአ ያለውን ይዘው ግብጻውያን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሾሙት ጳጳስ የኛን የልጆቻቸውን ፈቃድ ተከትለው በኢትዮጵያ አውራጃ እንደ ሚያስፈልግ የኢትዮጵያን መምህራኖች ኤጲስ ቆጶስ አያሉ እንዲሾሙ ሙሉ ፈቃድ ይሰጡልናል ብለን እንመኛለን ። ሰስተኛ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ዮሐንስ ለልጆቻቸው ለኢትዮጵያ መምህራን ባንድነት ቤተ ክርስቲያን የክህነት ማዕርግ በደስታ እንዲፈቅዱልን እንለምናቸዋለን ። ይህንም በፍቅር የተሳበ ቸርነታቸውን ሳይርቅ በቅርቡ ይፈጽሙልናል ብለን ተስፋዎን እንጠብቃለን ። ተስፋውም የሚፈጸመው በሰላማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ረድኤትና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እውቀትና ቸርነት ነው። ጸጋ ሥላሴ ጌታሁን ።

ንጉሥ ሚካኤል።

ስለ ንጉሥ ሚካኤል ዓፅም ።

ንጉሥ ሚካኤል በጳጕሜን ፫ ቀን በ፲፱፲፩ ዓ ም ታመው አረፉ። በሕይወተ ሥጋቸው ሳሉ ተንታ ሚካኤልን አሠርተው ነበር፡ነገር ግን ሰው ምንም እስከ ቀኑ ገገር ሁኖ ቢቆይ ፍጻሜው ሞት ስለሆነ በረፍሁ ጊዜ ከሠራሁት ቤተ ክርስቲያን ቅበሩኝ ብለው ነበርና ተንታ ላይ በተለየ ወዳሠሩት መቃብር ቤት ዓፅማቸው እንዲሔድ ስለተቈረጠ ልዕልት መነን ዓፅሙ አርፎ ከቆየበት ከሆለታ ቤተ ክርስቲያን አስነሥተውና ሸኝተው ለመስደድ በየካቲት ፬ ቀን ከጧቱ በ፪ ሰዓት ከዲስ አበባ ተነሥተው በ፩ሰዓት ገነት ገቡ ። ከገቡም በኋላ በኦቶሞቢል አጅበ ለሔደውና እየቀደመም ለቆረው መኳንንትና ወይዛዝር፡ ሲፈቱም ላደሩት ካህናት ግብር አድርገው አመሹ ። በማግሥቱ ማክሰኞ ከጧቱ በ፲፪ ሰዓት ዓፅሙ ወዳለበት ድንኳን ገብተው የሰዓት እኩሌታ ያህል ከተለቀሰ በኋላ ዓፅሙን ተከትለው ሸኝተው ተመለሱ። ደግሞ ከንጉሥ ሚካኤልም ጋራ በደስታቸውም፡ በመከራቸውም ያልተለዩዋቸው እኅታቸው ወይዘሮ የተመኝ መርድ በሰኔ ፲፪ ቀን በ፲፱፻፲፫ዓ ም አርፈው ዓፅማቸው ከዚያው ከንጉሥ ሚካኤል ዓፅም ጋራ ቆይቶ ነበርና ልዕልት መነን የወይዘሮ የተመኝ ዓፅም ከወንድማቸው ዓፅም ጋራ አብሮ እንዲሔድ ስለፈቀዱ አብረው ሰደዱዋቸው። እኒህም ሴት በወንድማቸው ቤት የተከበሩ በእውቀታቸውና በደግነታቸው የተመሰገኑ ነበሩ።የዓፅሙም መያዣና(ሣጥን)ጉዘው የአከሔዱም ሁኔታ እጅግ የከበረና ያማረ ነበር ።

ይኸውም አኳኋን የኑኃሚን ምሳሌ ይከተላል ።

ኑኃሚ ሠናይ ለብእሲ ለእመ ኮነ መቃብርቱ ውስተ እርስቱ እንዳለች፡እሷ በሕይወቷ ሳለች እንዲሁ ብላ ብትሔድ የ-

ተበረከ ልጅ መውለድ ደግ ነውና ዓፅማቸው በሕይወታቸው ሳሉ ላሠሩት ቤት ክርስቲያንና መቃብር ቤት መብቃቱ ለሞቶች፥ ለቆሙትም መልካም ዕድል ነው ።

ልዕልት መነንንም ተከትለው የሔዱ መኳንንትና ወይዛዝር ቁጥር ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

ክቡር ራስ ገብረ ሕይወት ።
ክቡር ራስ ይመር ።
ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ
ክቡር አፈንጉሥ አረጋይ ።
ክቡር ደጃዝማች መታፈሪያ
ክቡር ደጃዝማች አመዴ ዓሊ
ክቡር ደጃዝማች ገድሌ ፤
ክቡር ፊ ዓምደ ሚካኤል ፤
ክቡር ደጃዝማች ዋቄ፡
ክቡር ነጋድራስ መኰንን ።
ክቡር ደጃዝማች መልኬ ።
ክቡር ፊታ ገብረ ማርያም።
ክቡር ነጋድራስ ጠና ጋሻው
ክቡር ፊ አበበ አየለ ወርቅ
ክቡር ፊታ ባንቲደሩ ፤
ክቡር ፊታ መንገሻ ይልማ።

ክብርት ወይዘሮ አፀነሽ ።
ክብርት ወ ጌጤነሽ፡
ክብርት ወ ወለተ እ፣ ራኤል ሥዩም ።
ክብርት ወ ወለተ ኢየሱስ።
ክብርት ወ ትሰሜ አድገህ።
ክብርት ወ ልክም የለሽ ኃማ
ክብርት ወ ዘውዲቱ መንገሻ
ክብርት ወ ጽጌ ማርያም ገብረ ሩፋኤል ።
ክብርት ወ ዘርፈሽዋል ዋልቴ
ክብርት ወ ባፈና ወልደ ሚካኤል ።

ሌሎችም ብዙ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች ነበሩ ።

ዓፅሙንም ተከትለው የሚሔዱ ።

ክቡር ራስ ይመር ፤
ክቡር ደጃዝማች አመዴ ዓሊ ።
ክቡር ፊታውራሪ አበበ አየለ ወረቅ ።
ክቡር ፊታውራሪ ባንቲይደሩ ፤
ክቡር ቀኛዝማች ከልክሉ ናቸው ።

ስለ መሬት ማደላደል ።

ከከተማ ውጭ ያሉ ባላባቶች ከሥር እስከ መቶ ጋሻ መሬት ድረስ የያዙ አይታጡም፥ ይኸውም እኛ በጭር ስናስበው ነው ከዚህም መሬት ውስጥ ከለሙ ጠፍ ይበዛል፡ ይኸውም ጠፍ መሬት የአውሬና የወንበዴ መከማቻ ሁኖ ይቀራል፡ ይኸም መሬት ሥራ ከሚፈታ ለመንግሥት እያገለገሉ ጥቅም የሌላቸው ሰዎች ሞልተዋልና እንደሚገባው ደንብ እያሸሹ ቢአደላድሉት ለመንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም ይሆን ይመስለናል ።

ስለ ለማኞች ።

በዚህ ከተማ ውስጥ በየስፍራው እየዞሩ የሚለምኑ ሰዎች በጣም ይበዛሉ፥ ከዚሁም መካከል አካሉ ከተበላሸው ደኅነኛው ለማኝ ይበዛል፡ እነዚህም ለማኞች ባልተዘከሩአቸው ጊዜ፥ ከባለቤቱ ወይም ከማንም ሰው ጋር አባንር ያነሣሉ በየደረሱበትም ስፍራ ጭቅጭቃቸውን እየፈሩ ማንም ሰው ገንዘብ ይሰጣቸዋል፥ ይኸንንም ገንዘብ አከማችተው፡ ሳይለብሱትም፥ ሳይበሉትም፥ ወይም ለዘመዶቻቸው ሳያወርሱ በጸከር ልብቸው ይቀብሩና ገንዘቡን መሬት ውስጥ በከቱ ጠፍቶ ይቀራል፡ በዚሁ ከተማ መካከል ያለው ለማኝ ማነሱና መብዛቱ አልተመረመረም፥ ከከተማ ውጭ ያለ ሕዝብ ግን ተዝካርና ማኅበር፥ ዝክርና ምጽዋት ባደረገ ጊዜ ድሀ አጥቶ ለማን ልመጽውት እያለ ያዝናል፡ ይልቁንም አካሉ የጐደለበት ሰው ምክንያት አለው። የበሽ ነፃ ደንብ ከቆመ ወዲህ ቁጥሩ ያልታወቀ ስንት የሚአህል ባሽ በየመቃብር ቤትና በየደጀሰላሙና በየኪራይ ቤት እየተቀመጠ፡ ቀን ልብሱን እየለወጠ፥ ሌት ወደ ሌብነት ይሰማር ይመስለናል፡ ስለዚህ ነገር ደኅነኛውንና በሽተኛውን ለማኝ በየስፍራው ሁሉ ተጽፎ ቁጥሩ ሲታወቅ ከከተማ ውጭ ለሚኖሩ አገረ ገዢዎች እንደ ማዕርጋቸው መጠን ከመከከላቸው አንዳንድ አለቃ እያደረጉ ማደል ነው ፤ እነዚህም አገረ ገዢዎች የድሀ ድርጎ ደንብ አድርገው መቀለብ ያሳስባቸዋል ። ይኸነን ማሰባችን ስለ ውስልትናቸው ብቻ አይደለም የከተማውን ሰው በየመንገዱና በየሱቁ ሲያስመርሩ ስለ አገናናቸው ነውና በሽውንና አካለ ጐደሎውን፥ ደኅናውን፥ በየክፍሉ ሁሉ ልኩ እንዲታወቅ መመርመር ያስፈልጋል ። በላይነህ ።

አንተና ባለዕዳህ ።

ተሰው ገንዘብ አትበደር አልልህም፡ ስለምን ሰው በተቸገረ ጊዜ ገንዘብ መበደሩ አይቀርም፥ ግን በብዙ ዕዳ አለመኖርን ልምድ አድርግ፥ ሽማግሎቻችን እንደዚህ ይሉ ነበር፥ ሁለት ነገርን ፍሩ ፩ኛ ከኃጢአት፡ ፪ኛ ከዕዳ ነፃ መሆን ነው ፤ ገንዘብ ሳይኖርህ ተሰው ተበድረህ ቤት ብትሠራና ቦታ ብትገዛ፡ አዲስ ሥራም ብታቆም ይህ ሁሉ በሰው ገንዘብ ስለሆነ ምንም ቢሆን የሚቆይ አይምሰልህ፡ አንተ ግን ከወዳጅህ የተበደርከውን ገንዘብ እመልሳለሁ እያልክ አለጥርጣሬ ባልታሰበ ዕለት ድንገት አደጋ ወድቆብህ ቤትህ ቢወረስ፡ ቦታህ ቢያዝ፥ ያቆምከው ሥራ ቢበላሽ የተጐዳው ያበደረህ ወዳጅህ ነው እንጂ አንተ አይደለህም።ስንትና ስንት ሰው ባልንጀራው ደክሞ ለፍቶ በብዙ ጭንቅ ያገኘውን ገንዘብ ይበደርና ሳይመልስለት ይቀራል ። ይህ ሁሉ ከማጣት የተነሣ ነው እንጂ የተበደረውን በምስጋና ቢመልስ ጠልቶ አይደለም ፤ አለ እውቀትና በስሕተት የራስህ ገንዘብ ቢጠፋ ይህ ክፉ አይምሰልህ፡ ስለምን ክፉና ደግ አስረድቶሃልና ለዳግመኛው ትጠነቀቃለህ፡ ማለት አንተ አጥፍተህ ባልንጀራህን ከሳራ ታመጣበታለህ ። ባተሌ ሰው ሁነህ ከሰው ገንዘብ ተበድረህ ብታጠፋ ይህ ደግ ሥራ አይደለም። አያሌ ሰዎች በብዙ ልመና አስጨንቀው ምለው ተገዝተው የታቦት ዋስ እየጠሩ ገንዘብ ይበደሩና መክፈያቸው ሲደርስ፥ ወይንም ታገር ይጠፋሉ፥ ወይንም እሺ ነገ ማለት እያሉ በውስልትና የሰውን ገንዘብ ያስቀራሉ ። ደግ እውቀት ያለው ሰው የተበደረውን ገንዘብ ከፍሎ ዕዳውን ቢያወጣ የተገባ ነው ። ነጋዴ እንደሆንክ በዕዳህ ላይ ዕዳ አትጨምር፤ የቀደመውን ዕዳህን ከፍለህ እንደገናም ብትበደር ትችላለህ፡ ዕዳውን የማይከፍል ነጋዴ ከበሬታ የለውም፥ አለ ከበሬታም ደግሞ ንግድ አይሆንም ዕዳን ክፈል ከበሬታን እንድትገኝ። በችግረኛነትህ የተበደርከውን ገንዘብ ባልፈለገህ ጊዜ አስታውሰህ ዕዳህን ክፈል፥ ስለምን ለስምህ ከበሬታ ይሆንሃል ። በሥራ ፈትነትህ ጊዜ እከፍ

ላለሁ፡ ብለህ ምለህ የተበደርከውን ሥራ በገኘህ ጊዜ ሰውሁንና ዕዳህን ክፈል፡ጭራሽ ለሰው ገንዘብ አታበድር አልልህም፡ ግን ከማበደርም ተጠንቀቅ፤ ይልቁንም ምንም ጥቅም የሚያመጣልህ ቢሆን ለማታውቀው ሰው ገንዘብ አታበድር ። ለወዳጅህና ለምታውቀው ሰው ምንም የታመኑ ቢሆኑ ገንዘብ ስታበድራቸው ውልህን ደምብ ለሚያውቅ ሰው አማክረው።ወደፊት ብዙ ገንዘብ አገኛለሁ ብለህ በእጅህ ያለውን ሀብት እንዳታበድር ተጠንቀቅ፡ በሽንገላ መላስ አታሎ ብድር ከሚፈልግልህም ሰው ተጠንቀቅ፡ውልህንም አጥብቅባቸው ። ብዙ ሰዎች ገንዘብ ሳላቸው በገንዘባችን ላይ ትርፍ እንጨምራለን በማለት ከሰው ሌላ ገንዘብ ይበደሩና ሥራው ሳይሆንላቸው ቀርቶ የራሳቸው ከሳራ እንሰ ሰውን አክስረው ይቀራሉና፡ዕዳውን ሳይከፍል ሞተ ከመባል ተጠንቀቅ። ክሪከር ዳራክይያን።

ዝኒት የምትባለዋ ባለምዋል የጻፈችው የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ምሥጢር ያለው የሕይወት ታሪክ።

በከርቴን ባቢከየን ታርሞ ተጻፈ ።

፫ተኛ ክፍል

የዚች የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ሕይወት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እጅግ በመስኮብ መንግሥት ላይ የክፋና የሚ ስደንቅ ድርጊት ይልቁንም በጊዜው እጅግ የከፋ ነገር ይታይበት ነበር ።

የማይረሳው የሪዶልፍ ሞት አንድ ዓመት ከሆነው ጀምራ አልጋ ወራሺቱ አሊክስ ማናቸውም ነገር ደስ አያሰኛትም፡በየጊዜውም በንጉሡ ግቢ ውሥጥ ማታማታ ፈንጠዝያ በተደረገ ጊዜ እርሷ በልቧ ብርቱ ኀዘን ስላለባት ደስም አይላት።

በመጋቢት ወር ውሥጥ አባቷ ታላቁ ዱክ ሞተ፡ከዚያም በኋላ ያባቷ ቤት ዋና እርሷ ስለሆነች ያስተዳደሩን ሥራ ደህና አድርጋ ፈጸመች ከጥቂት ጊዜም በኋላ ወንድሙዋ የታላቁን ዱክ ከበርከን ልጅ አገባ ነገር ግን አሊክስ ከወንድሙዋ ሚስት ከምራቷዋ ጋራ ተስማምታ መቀመጥ አልቻለችምና በቤታቸው ውስጥ አምበጓሮና ሁልጊዜ ጭቅጭቅ ሆነ

የጀርመን አገር ንጉሠ ነገሥት ከይዘር ጉልዬም ላልጋ ወራሺቱ አሊክስ ክብር ሲል አንድ ቀን ታላቅ ግብዣና ልዩ ልዩ ጨዋታ የሚታይበት በዓል አድርጎ ነበር ነገር ግን ብእንግሊዝ አገር ሮምተው የሪዶልፍ ነገር ከልብዋ ላይ አልተወገደምና በዚያ ቀን እንኳን በፊትዋ የደስታ ምልክት አልታየም የንጉሠ ነገሥቱ ከይዘር ጉልዬም ዓይኖች አተኵረው ይመለከትዋት ስለነበረ ኀዘንዋን ከንጉሡ ለመሠወር አልተቻላትም በዚያ ቀን የንጉሡ ግቢ ገነት መስሎ ይታይ ነበረ። በዚያው ጊዜ ድንገት አልጋ ወራሺቱ ተሠወረች እኔም በየክፍሉ በየእልፍኙ ብፈልጋት አጣሁዋት በመጨረሻው ንጉሡ ከይዘር ጉልዬም በሚጽፍበት እልፍኝ አጠገብ አለፍሁ ንጉሡም ያለበት ቤት ላየው የሚያስፈራ ነበረ በበሩፉ አጠገብ ፪ወታደሮች የጦር መሣሪያ ባዮኔት ያለበት ጠመንጃ ይዘው ያደፈጡ አንበሶች መስለው ይታዩ ነበር በዚያም ጽሕፈት ቤት ውሥጥ ንጉሡ በጠረጴዛው ላይ ተመርኩዞ አልጋ ወራሺቱን አሊክስን አቁሞ ይጠዩቀት ነበር እስከዚያ ቀን ድረስ ንጉሡ ከይዘር ጉልዬሞ አሊክስን በማናቸውም ነገር ሊነጋገሯት አልፈቀደውም እኔም በዚያን ጊዜ አሊክስን አጥብቆ በመጠየቁ አንዳች የሚያስፈራ ነገር እንዳሰበባት ተረዳሁት ግቢውም ሁሉ ነገሩ የማያስፈራ ስለሆነ መንቀጥቀጥና ፍርሀት መላበት የሆነው ሁዋ ዓመት በዓሉን በደህና አለፍነው ከዚያ ቀን ወዲህ ንጉሠ ነገሥቱ ከይዘር ጉልዬምና አልጋ ወራሽቱ አሊክስ ግብዣ ይጠራሩ ጀመር ከጥቂት ቀን በኋላ አልጋ ወራሺቱ አሊክስ መስኮብ አገር ያለውን ታላቁን ዱክ ሴርክ አሊክሳንድርቤችን ያገባችው እኅቷ የጻፈችላትን ደብዳቤ ተቀበለች ይህም ወረቀት አሊክስ ወደ መስኮብ አገር ሒዳ የክረምቱን ወራት እንድትቀመጥ የተጻፈ ልመና ነበር ወረቀቱንም እንደተቀበለች ንጉሡ ከይዘር ጉልዬም ግብዣ ጠራት በዚያ ቀን ነው እኔን ትታኝ መሔድ የጀመረችው እኔም ምክንያቱን ከብዙ ጊዜ በኋላ አገኘሁት ከንጉሡ ግብዣ ከተመለሰች ወዲህ ወደ መስኮብ አገር ፔትሮግራድ ከተማ ለመሔድ ተነሣን የምንሔድበትም ነገር ምሥጢር ያለውና የማይረሳ መሆኑን አወቅሁ ። ክርቴን ባቢክያን ።

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል

ማስታወቂያ ።

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ መልክም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ ሰዎች ዳውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም ከአዲስ ዓለምም ወደ አዲስ አበባ እንጨት ወይም ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ፡ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም

ከጀርመን ሌጋሲዮን የመጣ የጥር ፬ ቀን ራዲዮ የዕለት ወሬ

በርሊን ፤ በስተምሥራቅ በኩል ያለ መካከለኛ ኤውሮጳ ላይ መዓት የሆነ ብርድ እንደወረደ ይወራል ።

ከስታንቲኖፕል ፤ ሠላሳ ስድስት አድመኞች ተከሰው ቀርበው አምስቱ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው ። አሥራ ስድስቱ ደግሞ አሥራት ተፈረደባቸው ።

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የመጣ ራዲዮ የጥር ፬ ቀን ። የዕለት ወሬ ።

ሮማ፤ ሙሶሊኒና ካርዲናል ጋስፓሪ ስለሮማውያን መስማማት ይፈርማሉ ።

ሬባል ፤ የብርያንድና ኬሎግ ውል ፓርላሜንት ፈርሞበታል።

ቦምበይ ፤ በፋናቲኮችና በሃይማኖታውያን የተነሣው ሁከት እየቀጠለ ይሔዳል ።

በርሊን ፤ ብርቱ አዲስ የግሪፕ በሽታ ተነሥቶ ብዙ ሰዎች እየታመሙ ሙተዋል ።

የጥር ፳ ቀን የዕለት ወሬ ።

ሮማ፡በኩሪናልና (ቤተመንግሥት) በባቲካን ቤተክህነት)። የተደረገውን መስማማት ተፈርሟል ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።
ሐኪም አምባር ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታቂያ ።

ያንደኛ ዓመት	ብርሃንና ሰላም	ተጠርዞ	ዋጋው	፳፫ ብር
የሁለተኛ	,,	,,	,,	፳ ,,
የሶስተኛ	,,	,,	,,	፲፫ ,,
ያራተኛ	,,	,,	,,	፯ ,,

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።
በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት በየዓይነቱ የደብዳቤ ወረቀት
ና እንቬሎፕ ፋክቱራና የንግድ ወረቀት ሁሉ ይታተማል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፩ ብር
ጎበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፯ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ከረጂ	፻፺፱ ብር
ባለሰይጣን		፻፺፫ ብር
: : ባለ ድመት ።		፻፹ ብር
: : ባለእህያ ።		፻፹፫ ብር
: : ባለሳቢ ግመል ።		፻፺ ብር
: : ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፶፫ ብር
" " ጃፓን		፻፸፫ ብር
ሱክር	፩ ጁኒያ	፳፫ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፹
ባአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ከ፹ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ማሬብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከበሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል።



ዝኒት የእጅ ሰዓት።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቅዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አሉ።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቀደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጀማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሂዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠክራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፰
5me ANNEÉ , № 8

ሐሙስ የካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDı 21 FEVRIER 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumiére et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Dirèction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጠውንም ማረልጉት ወይ ጸሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጠው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መዓዘት ሰፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ማስታወቂያ ።

ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ መታተሙ ከተጀመረ አራት ዓመት አልፎ አምስተኛው ዓመት ተጀምሯል።ግን ጋዜጣውን እየተቀበሉ ዋጋውን ያልከፈሉ ብዙ ሰዎች አሉና፡ያልከፈሉትን የጋዜጣውን ዋጋ እንዲከፍሉን በማክበር እናመለክታቸዋለን።

የ፶ ገጽ ተከታይ ።

፲፯፡ ስለ ምንድር ነው ሉል ዋጋ ያለው?።

የነዚያን ነገሮች በጣም ለመግለጥ የዚችን ኃይለኛ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እንጥራለን ። ዋጋቸው በጣም ክፍ ያለ ስለ ሆነ ብዙ ሰዎች ሉልን ለመፈለግ በባሕር ውሥጥ ይጠልቃሉ ። ብዙ ሰዎች ለመጥለቅ የሚገደዱ ሉል በውድ የሚሸጥ ስለ ሆነ ነውን ።

ሉልን መፈለግ፡ ብዙ ድካምና ጉዳት ያለበት ሥራ ነው። ዓሣ አጥማጅ እዚያ ውሥጥ እንዲያጠልቀው ትልቅ የከበደ ነገር ተሸክሞ (ተጭኖ) ወደ ባሕር ውሥጥ ይገባል። በውሥጥ ዛጐሉን (ዓሣ ነባሪ) ሲለቅም ሳለ ብዙ ሳይተነፍስ ረዢም ጊዜ ያቈያል ። ለማግኘታቸው በሚደክመው ሥራ ልክ የማለፊያ ምችን ሉል ብዛት ጥቂት ነው የሥራውም ደመወዝ (ልውጫ) ልክ እንዲሆንለት በደከመው ልክ የነዚያን ያገኛቸውን ሉሎች ዋጋ ከሥራው መለዋወጫ የተስማሙ (ፕሮፖርሲዮኔ) ሊሆኑ ይገባቸው ነበር ።

ግን ይህ ብቻ የሉልን ዋጋ ማደግ እውነቱን ሊያጠግምበክር ሊሆን አይበቃም ፤ ስለምን እኒያ በውሥጣቸው ሉል የሚገኝባቸው ዛጐሎችም የሉል ዋጋ ልክ ሊኖራቸው ይገባ ነበር፡ ግን ሰዴሮቹ በትንሽ ዋጋ ይሸጣሉ ። እንዲሁም በውሀ ውሥጥ በገባ ቁጥር መጀመርያ የሚያገኛትን ደንጊያ ትሁን ዛጐል ክፍ ያለ ዋጋ ልታወጣለት፡ በፈለገ እውነቱ ግን እንደዚህ ነው ሉል ዋጋው ክፍ ያለ መሆኑ እነዚያ ያላገኙት ብዙ ወይዛዝሮች በብዙ ሊያገኙት፡ እነዚያ ያላቸውም ከፊተኛው ይልቅ የሚበዛና እጅግ ጥሩ የሆነ የሚያምር ሊጨምሩበት በጣም የሚመኙ ስለ ሆነ ነው ። ማለት ባጭሩ ሉል ዋጋው ክፍ ያለ መሆኑ ብዙ ወይዛዝሮች ሊሸለሙት እጅግ ይጐመጃሉና እስከ ዛሬ ድረስ ለመሻታቸው የሚበቃ ብዛት ስለ አልተገኘ ለወደ ፊቱም ከባሕር ጥልቀትና ጨለማነት፡ ችግርም የተነሣ የሚለቅመው የማይበቃ ስለ ሆነ፡ በብዙም ሊያገኙት የማይችሉ ስለ ሆነ ነው ።

ስለዚህ እንዲህ ስንል የዋጋና ሥራ ባህል እናቆማለን። የሚጠቅም ሥራ ብዙ ትርፍ የሚያፈራ ብዙ የሚፈለግ ሲሆን ነው ። ብዙ ይሁን ጥቂት ልታገኘው የምትመኘውን ስጦታ ያፈራል፡ የዚችን ብዛት የፍለጋን ዋጋ ትወስናለች ።

ምናልባት ለአንድ አንዱ አንባቢ ጠንክር ባለ በአንድ አንድ ስፍራ አሳቡ ሠወር እንደሚለው አሳቡ ይጠረጥራልና ከሁን በፊት ረዘም አድርጌ ያመለከትኩትን ሁሉ ማለት የመጀመርያ ክፍል ሁሉ ባጭሩ ፲፯ ባህል በተወሰነ አሳብ ለአንባቢው በጣም እንዲበራለትና በትክክል እንዲገለጥለት ቀጥሎ ዋና ማሠርያውን እደግምለታለሁ። ሚካኤል ተሰማ ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ስለ ተወለዱበት አገርና ስለ ነጻነት

ያገር ክብሬቱ በፍቅር አይደለም ከሁሉ የበለጠ ዋና ምግባር ነው ። ላገር ሲሉ ሚስትን፡ልጅን፡ ክብትን፡ትቶ እየተዋጉ መሞት በጣም የማረ ነው ። ላገሩ ሲል የሞተ ሰው እ

መ ከላገለገለ ይበልጣል፡ በማናቸው ምክንያት ቢሆን ሰው በገሩ ላይ መነሣት አይገባውም፡ ማንም ሰው ንጽሕናንና ትሕትናን ካልጠበቀ አገሬ አገሬ እያለ ቢጮህ አትመኑት እርሱ ክፉ መናፍቅ ነው ። እውነተኛ ሰው በቀር በርግጥ አገርን ወዳድ የለም ከማለት ምግባሩን ወደና ተሰምቶት የሚፈጽም ነው፤ የደግነት መጀመሪያ አገርን መውደድና ማክበር ነው፤ ያለ ሃይማኖትና ያለ መንፈሳዊ ሥራ በቀር ሁሉም ነገር ላገር የሚሠዋ ነው ። መልካም አድርጎት የሚሠራው ሰው የሚጠቅም ምክር ለልጆቹ አውርሶ እነርሱም ተቀብለውት በማናቸውም ሁሉ ቋም ነገር ሲሠሩበት ነው። በእውነት ይህች ዓለም የኛ አይደለችም፡ ከዚህች በደግነትና በንጽሕና ለመቀመጥ አይቻልም ፤ከሌላ ከላይኛዋ ግን ጭንቅ ማቅለያ እርፈት ነው የቅጥፈትም መዳኛ ነው ። በብዙ ሰዎች ነጻነትና ያገር ስም ብከንፈራቸው ነው፤ግን በእውነት ዘንድ በልባቸው ነው፤አገርን ለማገልገል ከብዙ መከራ መጣድ ያስፈልጋል ። በተለይ የራስን ጥቅም ለሕዝብ ለቆ እንደ ላንጻ መዋረድ እንደ ወንድማማች መፋቀርና መተጋገዝ ነው፤አገርን መውደድ ከፖሊቲክ መጨመር (መግባት) በተሾሙበት ስፍራ ማንፈራጠጥ፡ መንግሥትን ማናወጥ፡ ሕዝብን ማስጨነቅ ፤ጠላትን ማስደሰት አይደለም፡ በውነቱ ያገርን ልማትና የሕዝቡን ጥቅም መፈለግ ነው ። አገርን ለራስ ብቻ መውደድ አያስፈልግም፡ የሁሉ እርስትና ገንዘብ መሆንዋን ማወቅ ነው ። ደግሞ እርሷን መውደድ እውቀትን ሲሠሩበትና ለሚጠቅማት ነገር ገንዘብን ሲያወጡ፡ ወደ አዲሱ ሥልጣኔ በሥራና በኃይል ሲገፉ ነው። ምቀኝነት በመንግሥት ላይ የመነሣት ምልክት ነው፡ መለያየት ብሁሉ ዘመንና በሁሉም አገር ለውጭ ሰው ጥቅም ነው፤ የነጻ ስም የማናቸውንም ሰው ኃይል አያሳንስ፡ የማንም ጊዜ አያጠፋ፡ የሰውንም ስም አይከብድ፡ ሹሞች ብልሆች ከሆኑ ሕዝብ ነጻነትን ያገኛል፡ ነጻነት ከሁሉ ነገር ይበልጥ ይረባል፡ ያለ ክፉ ነገር በጎ ነገር የሚሠሩ እንደሚገባ ነጻ ናቸው፡ ነጻ ነኝ ማለት በትክክል የሥልጣኔን ደንብ መፈጸም ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤የኢትዮጵያ ስም ከሁሉ ይበልጥ የሚጣፍጥ፤ከሁሉ ይበልጥ የተመረቀ፡ ከሁሉ ይበልጥ የተቀደሰ ነው፤ ስለምን አገራችን ኢትዮጵያ የተወደደች እናታችን ነች፤በየትም ስፍራ ብንኖር በትልቅ ፍቅር መውደድ ይገባናል፤ደስታችንን፡ ኀዘናችንን፤ ተስፋችንን የምትችል እርሷ ናት ። ይህችን ከእግዚአብሔር የተመረቀች አገር እንውደዳት፡ ታሪኳን እንማር ደንቧን እናክብር፡ኃይሏንና ችሎቷን እናሳድግው፡ በማናቸውም ዓይነት እንጥቀማት፤ ሁላችንም አንድጋር ሁነን በውቀትና በሥራ ለትልቅነቷ እንርዳ።

አበበ በላቸው ።

ወዴት እንሔዳለን

በጥቂት አዲሶችን ትውልድ ለማዳን እንጥራለን ።

የክቡር ቄስ ስብከት ።

~~ክቡር ቄስን ካየኋቸው ብዙ ጊዜ ስለሆኑ እጅግ አድርጌ~~ ናፍቄአቸው ነበርኩ፤አንድ ቀን በድንገት ሳያስታውቁኝ ከምሥ [illegible]

እንደገቡ ዝም ብለው ቆሙ፤ ፊታቸውንም አኰማትረው በጸጥታ ይመለከቱኝ ነበር፤በሆዳቸው ያሰቡትን የቁጣ ቃል እንጋገ ፡ ስላልፈቀዱ ምንም ፊታቸው ቢኰማተር እንደ ቀድሞዋቸው ደግና ደስ ያለው ሰው ለመምሰል ይፈቅዱ ነበሩ፤የቤቱ ጌታ ስለሆንኩ መቀመጫ ስፍራ እስክፈልግላቸው ድረስ አላስችል ብሏቸው በትእዛዝ ቃል ስማ ልንገርህ አሉኝ፤ ወዲያው ደነገጥሁና ቀና ብዬ አየኋቸው፡ ቀጥሎም የሚናገሩትን ለመስማት ዓይኖቼን ኢትኵሬ፡ ጆሮዎቼን አቅንቼ፤እሰማቸው ጀመርሁ፤ የሚናገሩትም ነገር ለፍጥረት ሁሉ ይልቁንም ለኛ እጅግ የሚጠቅም ነው ከአልማዝና ከሉል የበለጠ ነውና ።

ክቡር ቄስም ንግግራቸውን ቀጥለው ጀመሩ የተወደድህ ወዳጄ ክፒቴን ሆይ ታላቁ የጀርመን አገር ሰው ቢዝማርክ የተናገረውን ልብ ታደርገዋለህን።

ባለጠኖችና ሰውነታቸው ብርቱ የሆነ ሕዝብ ያሉት መንግሥት እርሱ ብርቱ ነውና የማይሸነፍ ጦር ማሰናዳት ይችላል፤ እንዲሁም እርሻና መሬት የሚሰጠው ለእንደዚህ ያለ ሕዝብ ነው፤ደግሞም መጻሕፍትና ብዕር እውቀትና ደግና አንጐል ያለው፡ ራስ ያላቸው ይህ ባለጤና ሕዝብ ነው እንዴት የታደለ መንግሥት ነው ለሕዝቡ ጤንነት የሚጥር ።

እኔም አዎን ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ አንብቤዋለሁ ብዬ ልነግራቸው ስጀምር በቁጣ አስተያየት ዝም አሰኙኝ፤የመጣበት ነገር ምን ይሆን እያልኩ በድንጋጤ አመነታ ጀመርኩ፤ እርሳቸውም ንግግራቸውን እያከታተሉ ይነግሩኝ ጀመር፤ ወዳጄ ሆይ እኔ በርግጥ ዛሬ መንግሥታችን ላዲሱ ትውልድ አዲስ የሥልጣኔ አካሔድ ለማድረግ እንደተነሣ አውቃለሁ፤ የሕዝብ ትምህርት ሚኒስትር መሾሙን ፤ በየአገሩ ተማሪ ቤት እንዲቆም የተነገረ አዋጅ ይህንን የመሰለ ነገር ሁሉ እንደተደረገ ሰማሁ፤ግን ለዛሬና ለወደፊት መልካም የሆኑ አዲስ ትውልድ የሚሰጡን ባለጤኖች አሉን ይመስልሃልን? ይሁን እንጂ ጥቂቶች አይታጡም ቁጥራቸውን በጃችን ጣት ልናስበውና ልናውቀው እንችላለን፤ ነገር ግን ከሁሉ በፊት ባለጤኖች ቤተ ዘመዶች ማሰናዳት አይገባንምን። እነሆ ኢትዮጵያ ከነዚህ ባለጤኖች ቤተ ዘመዶች ንጹሕና የጠራ ትውልድ ለማግኘት ትችላለች።

ከሚጋባ በሽታና ዘርን ከሚያበላሽ በሽታ ለመከላከል አይገባንምን። መልካሙንና እውነተኛውን ትውልዳችንን፤ ሕዝባችንንም እንደ ማጭድ ሁኖ ያጭደዋል ።

እንግዲህ ማናቸውንም በውጭና በውሥጥ የምንሠራውን ሥራችንን ሁሉ ተወት አድርገን የጤንነትን ሥራ በትክክል ለማቆምና ለማሰናዳት በሙሉ ሐሳባቸው መጣር አያስፈልገንም ።

የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ካላቆምን ጥቂት በጥቂት እያለ የኢትጵያን ሕዝብ ዘር ፈጽሞ እንዲያጠፋው ከተረዳነው ከቶ ምን እንጠብቃለን፤በመላው ዓለም ከዚህ የበለጠ የሚያስፈራ አደጋ ይገኝ ይሆን። ከባላገር ወደ ከተማ ሴቶች እንደ ግንብ ይርጣሉ፤ በከተማም ያሉ ገረዶች ሀያ ብር ያህል ካገኙ በኋላ የመሸታ ንግድ ይጀምራሉ፤ በመሸታ ቤታቸውም ውሥጥ የብዙ ሚክሮብ (ትል) ጎጆ ይሠራሉ፤ ከዚህም በተቀር የብልግናን ምንጭ የፈልቃሉ፤ አስቀድመው አእምሮዋቸውንና ሕይወታቸውን

ይገድላሉ፡ቀጥለውም የዋሁን ሕዝብ ይደመስሳሉ ።

በከተማው ውስጥ በጨዋው መንደር የሴትኛ አዳሪና የመሸታ ቤት ቁጥር በቀን በቀኑ መጨመሩን አናስበውምን ። በነዚህ መሸታ ቤቶች ውስጥ ለሠራተኞቻችንና ለወታደሮቻችን ይልቁንም ለሕዝባችን እውነተኛውን መርዝ በሰውነቱ ያቀብላሉ፤ እነዚህም ሠራተኞች ሕዝብና ወታደሮች የተቀበሉትን መርዝኛ ትል ይዘው ሒደው አንዱ ላንዱ እያቀበለ ባገር ውስጥ የሚተላለፈው በሽታ የፀና ይሆናል።ባል ለሚስቱ ሚስቱ ደግሞ ለሌሎች ስታቀብል እነሆ አንድ ሕዝብ በ፲፱፻፳፩ ደኛው ዘመን ውስጥ ፈጽሞ ወደኋላ ሲመለስ ዓይኖቻችን ይመለከታሉ፡ይኸውም የሚሆነው የጤንነት ሥራ ባለመኖሩ ነው። መቸ ይሆን? እንደ አውሮፓ ደምብ የሴትኛ አዳሪዎችን ሰፈር የምንለይ የበረታውን የዘበኝነት መቈጣጠርና የጤንነትን ሥራ የምናደርግላቸውስ ምን ጊዜ ይሆን በከተማ ውስጥ ቁጥራቸው የበዛውን ቆማጦች ከከተማ ውጭ የሚመገቡበትና የሚኖሩበት ስፍራ ምን ጊዜ እናበጅላቸው ይሆን?እነዚህ የዋሆች የቍምጥና በሽታ የያዛቸው ድውያን በብዙ ችግር ሕይወታቸውን በመንገድ ላይ ተኝተው ለንጹሖቹና ለባለጤኖቹ ሕዝቦች በሽታቸውን በዝንብ፤በዓየር፤በየመንገዱም ላይ ከቆሰለው ገላቸው ደም እያፈሰሱ ሕርፈት እየጣሉ፡ እንዲሁም በልዩ ልዩ ነገር ከቅጫም ያነሰውን ትላቸውን(ሚክሮብ)ያወርሳሉ(ያጋባሉ) መቸ ይሆን እንዲህ ያለ ደምብ የሚያረገውን ጋብቻ የምናስጥል?። ይገባልን የዋሁ ሕዝባችን እንደ ልብስ ሚስቶች ሲለዋውጥ ዝም ብለን እንመለከት ዘንድ እንዲህ ከሆነ ከቶ እንዴት ይታወቃል የሕዝቡ ጤንነት ባልና ሚስት እንዴት ተማምነው በፍቅር መኖርና ልጆች መውለድ ይችላሉ?ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የቆየን የቤተ ክርስቲያናችን ትእዛዝ በብርቱ እንዲከለከል እናውቃለን ስለምን እንመለከተውም ደግሞስ እኛ ቀሳውስቱ ለመንግሥታችንእርዳታ አይገባምን መንግሥትን መርዳት ከሁሉ የበለጠ አይደለን የሕክምና ቤተ ዘመዶች ሁሉ ጠንቅቆ ስለጠበቃቸው ባለጤኖች ብርቱ ብርቱ ልጆች ይወለዱ ጀመር ። ይህ መልክም ዘር የሚወለደው በድንገት ከተገኘች ሴት አይደለም ።

ክቡር ቄስም ከዚህ በላይ በቁጣ ቃል ሲናገሩ ቆይተው ጥቂት ቁጣቸው በረድ ሲል የርሳቸውን ንግግር መሠረት አድርጌ ቀጥሎ የተጻፈውን መለስኩላቸው ። የተወደዱ ቄስ ሆይ በዚህ አገር ተግሣፅ አልተለመደም ባለመታደል ምክንያት ተግሣፅን የሚያደርግ ሰው ከቁም ነገር አይቆጠርም ፡ ነገር ግን በአውሮፓ የሆነ እንደሆነ የጋዜጣ ጸሐፊ ተግሣፅ ታምር ነው እንዲሁም የሥልጣኔን በር የሚከፍት ተግሣፅ ነው ይሁንና እርስዎ ከዚህ በላይ በተናገሩት ንግግርዎ ውስጥ ሶስት ዋና ዋና ነገር አገኘሁበት ።

መጀመሪያ፤ የሕዝብ ጤንነት ሚኒስትር ሥራ ማሠልጠን።

ሁለተኛ፤ የዘገየውን የዘበኝነት ሥራ ሥልጣኔ ።

ሶስተኛ፤ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በብርቱ የማሠልጠን ሥራ ክቡር ቄስ ሆይ የዲስኩርዎ ፍች ይህ አይደለምን ። ቄሱም መልሰው አሉኝ፤ ተባረክ ጕበዙ ክፒቴን መልካም አድርገህ ፈታኸው።እነዚህን ሶስቱን ነገሮች ደምቡን ጻፈውና በሚመጣው ሳምንት መጥቼ እየዋለሁ ይህን ባሉኝ ጊዜ ከድንጋጤ የተነሣ ከተቀመጥሁበት ድንገት ዘለልሁና እንዳበደ ሰው አዩ ክቡር ቄስ ሆይ እኔ በየጊዜ ለዚህ ነገር ሐሳቡንና ደምቡን በመጻፍ ታክቶኛል እንግዲህ ወደፊት እያደረ ተስፋዬን ሳልቆርጥ አልቀርም ኢያልኩ ጮህኩ።ይህነንም ሰምተው የተወደዱ ቄስ በቁጣ ቃል ሁለተኛ እንደዚህ ያለ ንግግር ከአፍህ አይውጣ፤ለሰው መጥቀም ከፈቀድህ እኔን ብቻ ተከተለኝ ሌላም አያስፈልገኝም ።

ክፒቴን ባቢኪያን ።

ስለ ጋምቤላ መንገድ ።

ከጐሬ ወደ ጋምቤላ የንግድ ዕቃ ለማመላለስ በከብት ጭነትና በሰው ሸክም ስለሆነ ከጐሬ እስከ ጋምቤላ መንገዱ ሁሉ ጠንካራ ወባና ሌላም የሰውና የከብት በሽታ ስላለበት በየዓመቱ ከአምስት መቶ እስከ ሺህ የሚሆን ሰውና ከአምስት ሺህ እስከ ሰባት ሺህ የጭነት ከብት ይሞት ነበር ።

ይኸን በየዓመቱ የሰውንና የከብቱን ማለቅ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ስለሰሙ ከጋምቤላ ወደ ጐሬ የካሚዎንና የአቶሞቢል መንገድ በፍጥነት ለመሥራት ለኩፓንያ በውል ተሰጠ ። በውሉም ውስጥ ኩምፓንያው አክሲዮኑን መጀመሪያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይሸጣል ተብሎ ስለተጻፈ አሁን ኩምፓንያውን አክሲዮኑን እንደ ውሉ ቃል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሊሸጥ ነውና ለመግዛት የምትፈልጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየካቲት ፲፫ቀን ፲፱፻፳፩ዓ ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ፲፫ቀን ሁለት ወር ድረስ በነጋድራስ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል በኩል ለመጠየቅና ለመግዛት ትችላላችሁ ።

ኩምፓንያው እስከ አንድ ወር ጠብቆ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ወገን በሙሉ የተወሰነውን አክሲዮን የሚገዛ ያለገኘ እንደሆነ በውሉ ውስጥ የተረፈውን ወይም በሙሉ እርሱ ለፈቀደው ይሸጣል ተብሏል ። ይህም አክሲዮን የተወሰነው በአስር በአስር ብር ነው።ነገር ግን ለአንድ ሰው ከአስር አክሲዮን በታች እንዲገዛ አይፈቀድም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መጀመሪያ በዚህ መንገድ የሚያልቀውን ሰውና ከብት አስበው መንገዱ እንዲሠራ ማድረጋቸው ዋና እርዳታ ነው ።

ሁለተኛውም በዚሁ በመንገድ ሥራ የሚገኘውን ጥቅም ወደ ሌላ እንዳይሄድ አክሲዮኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲገዛ ማድረጋቸው ትልቅ ጥቅም ነውና አሁን በተወሰነው ጊዜ ይህን አክሲዮን ሳትገዙ ቀርታችሁ ጊዜው ቢያልፍ ጸጸቱና ጕዳቱ የራሳችሁ መሆኑን እናሳስባችኋለን። የካቲት ፲፫ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም

ሹመት።

የካቲት ፲ ቀን ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ሆሎን ተሾሙ። ክቡር ፊታውራሪ በላይነህ ጃንጀሮን ተሾሙ።ክቡር ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ የፊታውራሪ በላይነህ የነበረውን ባልደራስነትን ተሾሙ። ክቡር ባላምባራስ ኀይሉ በረደድ የሥራ ሚንስቴር ዲሬክተርነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ላገኙ መኳንንቶች እንኳን ደስ ያላችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ያቀርባል ።

ሠርግ ።

የከቲት። ፯ ቀን የግርማዊ ንጉሥ የወታደር ሐኪም ክቡር ዶክተር ሐራልድ ኒስትሮም ወይዘሮ ማርታን በተክሊል አገቡ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር ዶክተር ሐራልድና ለባለቤታቸው ለወይዘሮ ማርታ ትዳራቸውን እግዚአብሔር እንዲባርክላቸው ይመኝላቸዋል ።

የከቲት ፲፪ ቀን ክቡር አቶ መድኅኔ የፈረንሳዊ ሌጋስዮን ትርጁማን ክብርት ወይዘሮ አፀደ ማርያምን አገቡ ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር አቶ መድኅኔና ለክብርት ወይዘሮ አፀደ ማርያም እግዚአብሔር ትዳራቸውን እንዲባርክላቸው ይመኝላቸዋል ።

ማስታወቂያ ።

ክቡር ዶክቶር ሐነር ጨርሰው ወደ አገራቸው የሚሔዱ ስለሆነ እቃቸውን ሁሉ ይሸጣሉ።ፈረሶች፡ኰርቻ፡ የቤት እቃ፡ የሰኒ እቃ፡የወጥ ቤት እቃ፡ እንዲሁም የመሰለ ብዙ እቃ ይሸጣሉ ።

እቃውን አይቶ ለመስማማት የፈለገ ሰው ከዘጠኝ ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ድረስ እየመጣ ማየትና ዋጋውን መስማማት ይችላል ።

በባቡር መሳፈር

ክቡር ከንቲባ ነሲቡ አያሌ ቀን ታመው በቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ዘተፈሪ መኰንን ታክመው በኋ ሁነዋል።ግን በጣም እንዲሻላቸው አየር መለወጥ የሚያስፈልጋቸው ስለሆነ የከቲት ፲ ቀን ከባለቤታቸው ጋራ ወደ ጂቡቲ ለመሔድ በባቡር ተሳፈሩ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር ከንቲባ ነሲቡ ድነው ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ይመኝላቸዋል ።

በባቡር የገቡ

ከስዊስ አገር ፡ ዶክቶሬስ ሒድቢግ ።
ዶክቶሬስ ማሪ ሞስ ።
ዶክቶሬስ ዜና ።
ዶክቶር ሚኢንቤርጅ።
የከቲት ፱ ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

ከአሚሪክ፡ ሚስተር ዋልተር ።
ሚስተር ራልፍ ።
የከቲት ፲፩ ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የመጣ ራዲዮ ።

የጥር ፯ ቀን የዕለት ወሬ ።

ፓሪስ ፤ ሞንሲኘር ሬች በፓሪስ በካርዲናል ዱቢ ፕሬስ

ንግግር አደረገ)። የጽላጣ ማኅበር የፈረንሳዊና የደቡብ አሜሪክ የአሬዎፕላን ጽላጣ ማኅበር እስከ ፓራጓይ ድረስ እንደሚቀጥል ያስታውቃል። የብርድ ማዕበል በፓሪስ እየባሰ ይሔዳል። በፓሪስ የብርድ መለኪያ ፲፬ ግሬድ ወደታች ወርደዋል ።

ከጀርመን ሌጋሲዮን የመጣ ራዲዮ ።

የየከቲት ፯ ቀን የዕለት ወሬ ።

አንጎራ ፤ የመንግሥቱ ጉባኤ ከውጭ አገር ሴቶች ስለ ሚያገቡ መኳንንት ደንብ አወጣ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤የጦር ሚኒስቴር፡ የመርከብ ጦር ሹም (አሚራል) የሆኑ፤ መኳንንት ከውጭ አገር ሴት አግብተው ቢገኙ ከሹመታቸው ይሻራሉ።

ካይሮ ፤ ምስር የእንግሊዝና የቤልጂክ ውል አልቀበልም ብሏል ።

በርሊን፤በጀርመን አገር ብርድ ከፍቷል።በአንዳንድ አገር እስከ አሥራምስት ግሬድ ወደታች ወርደዋል ።

አለሀባድ ፤ በያሌ የሀንድ አውራጃ ላይ በሽታ ተነሥቶ ባለፈው ሳምንት ፳፻ ሰው ገደለ ።

አልባላቅ ከተባለ ጋዜጣ የተገለበጠ ።

በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል ያለ ነገር ።

አልባላቅ የተባለ የካይሮ ጋዜጣ በጥር ፳፯ በጻፈው ቍጥር ፓትሪያርኩ ለላኩት መልክት ንጉሥ የመለሱትን ምላሽ በጥር ፳፩ ቀን ደረሰ ብሎ አትሟል ። ይህንኑ መልክት ለመቀበል ጥር ፳፰ ቀን ጉባኤ አደረጉ። በሉሎቹ መካከል ስለግብጽ መንግሥት ሆኖ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ሐቢብ ቤይ መጥቶ ነበር ። ይህም እንደ መጨረሻ ጉባኤ ነበር ።

የንጉሡ ምላሽ ስለ አቡን ነገር ብቻ ነበር እንጂ ስለ ዴር እልሡልጣን አንዳች አይናገርም ተብሏል ። ንጉሥ ስለ ዴር እልሡልጣን ዝም ማለታቸው ለግብጻውያን በካይሮ ባለፉ ጊዜ በ፲፱፻፳፬ የተባለውን ሐሳብ እንደ ተቀበሉት ሆኖ ተሰማቸው ። ከዚያ ነገር ወዲህ ኢትዮጵያውያን ከገዳሙ እኩሌታውን (፭ ክፍል ቤት)ከሁለቱ ቤተ ክርስቲያንም አንዱን አግኝተዋል፡ መተላለፊያውም ለሁለቱ ሆነዋል ግን ርስተኛቹ ግብጻውያን [illegible] ።

ንጉሥ በመልክታቸው የዴር እልሡልጣንን ነገር ጭራሽ አለማንሣታቸው ይኸንን ነገር እንዳተቀበሉት ያስረዳል ።

ጥር ፳፯ ቀን ከታተመው ከምስር ጋዜጣ የተገለበጠ ።

በአዲስ አበባ ስለሚቆመው ያለሽቦ ቴሌግራፍ ።

ንጉሥ በአዲስ አበባ ያለሽቦ ቴሌግራፍ እንዲቆም ማሰባቸውን የፖስጣው ሚኒስቴር አስታወቀ ። ራዲዮው ሩቅ ካሉት አገሮች ወሬ እንዲያቀብልና እሩቅ ስለሆኑት አውራጃዎች ለማዘዝ መንግሥትን የሚረዳ በመሆኑ ብዙ የሚያስፈልግ ነገር ነው ።

ይህን ሥራ ለማቆም እንግሊዝ እንዲያገኘው ተስፋ አድርጓል ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።
ሐኪም አምባር ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ሰፈሩ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታቂያ ።

ያንደኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ተጠርዞ ዋጋው	፳፫ ብር
የሁለተኛ " " "	፳ "
የሶስተኛ " " "	፲፫ "
ያራተኛ " " "	፯ "

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።
በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ማ
ተሚያ ቤት በየዓይነቱ የደብዳቤ ወረቀት
ና እንቬሎፕ ፋክቱራና የንግድ ወረቀት ሁ
ሉ ይታተማል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
ጎበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኮረጃ	፻፺፱ ብር
ባለሰይጣን		፻፺፫ ብር
: : ባለ ድመት ።		፻፳ ብር
: : ባለአህያ ።		፻፳፫ ብር
: : ባለሳቢ ግመል ።		፻፺ ብር
: : ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፶፰ ብር
" " ጃፖን		፻፸፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፫ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፹
ባንድ ብር	፰ ሊሬ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ከ፹ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቬርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ ጫቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ፀለባተሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋ ውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማኅደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅግ ላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት የእጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና (ጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የለለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጆማት የጨጉጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ሳይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዳይ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ፊሑድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠከራ ነው በኋላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፱
5me ANNEÉ № 9

ሐሙስ የካቲት ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 28 FEVRIER 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumiére et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፶፯ ገጽ ተከታይ ።
(፲፰)ውሳኔ (ድንጋጌ)

፩ኛ፡ የሀብት አውቀት ማለት ሊማርዋት የሚገባ የማኅበር ሥርዓት ነች ። ኤኮኖሚያ ፖሊቲክ በአራት ይከፈላል ፡ ፍሬ፡መዘዋወር፡መከፋፈል፡የሀብት መጨረሽ ።

፪ኛ፡ ወደእውነተኛ መንገድ ለመድረስ በሜቶዶ ኤንዲቲብና በሜቶዶ ዴዲቲብ ይከፈላል ። እንዲቲብ ማለት ስለሚደረግና ሊደረግ ላለው ነገር ማሰብ ማለት በመጀመርያው የሚያመጣውንና ለወደ ፊቱ የሚያመጣውን ነገር መመልከት ነው።

ዴዲቲብ ማለት ከተደረገ ነገር ከሚከተል ፍጻሜ ማሰብ የፊተኛውን ነገር ሁሉ አስቀምጦ ሌሎችን የረቂቆች ዓይነቶች መጀመርያ ለማግኘት መጨመር ማለት ነው ። ምሳሌ)ነፍሰ ገዳዮች የፍጥረታቸው ሥራና አመላቸው ምሳሌ)የጀሜትሪያ ባህል የመጀመሪያውን ለሚከተለው ፊተኛው ተቀጣጥሎ እውነቱን እንዴት ብሎ እንደሚያወጣው ።

፫ኛ፡ሀብት የሚጠቅም ነገር ማለት ለሰው የሚያስፈልገውና ደስ የሚያሰኘው ማለት ነው ።ጥቅሞች በሁለት ይከፈላሉ፥የፍጥረት፥ ጥቅም፥ የተፈጥሮ ሀብት የሚባሉ እንደ ውሀ፥ አየር፥ፀሐይ፥ የመሰሉ፥ አለ ሥራና ድካም በገዛ እጃቸው ከፍጥረት የተሰጡ ጸጋ ናቸው ። ሀብት ሰው በሥራና ድካም ሊያገኛቸው የሚችል እንደ እንጀራ፥ልብስ፥ ወርቅ ማለት በጭሩ ብዛታቸው የተወሰኑ ነገሮች ናቸው ።

፬ኛ፡ ሀብት በቤኒ ማቴሪያሊና ሥራ ይከፍላል ። ምሳሌ) ቤኒ ማቴሪያሊ ማለት ሥጋ፥ ጫማ፥ መኪና፥ ብር፥የመሰሉ ናቸው ። ሥራ ወይም አገልግሎት)ማለት ክራይ መጫኛ፥ማከም፥

፭ኛ ቢዞኚ አስፈላጊዎች ነገር የሰው ፍላጋ መጨረሻ ጉልቁና ወሰን የለውም፤ምኞቱም ብዙ የተለዋወጠ ልዩ ልዩ ነው። ሰው፥ገንዘብ፡ክብረት፡ቤት፡ንብረት፥ ጨዋታም፥እንዲሁ የመሳሰለ ሁሉ ይፈልጋል። ፍላጋና ምኞት የተለያዩ ናቸው ፍላጋ የፊሎሶጂክ እንደ መተኛት መንቃት ፍጥረት ነው። ምሳሌ) እኔ ርቦኛል ማለት ምግብ ያስፈልገኛል ምኞት የፒስኮሎጂካ (አእምሮ ፍጥረት ነው ማለት ቁጣ፥መጣላት፥ልበና፥ እንዲሁ የመሰሉ ሁሉ ናቸው ምሳሌ)እኔ ሥጋን መብላት እፈልጋለሁ ።

(፮ኛ) የሰይ የሚባል ኤኮኖሚስታ ሕግ እንዲህ ይላል ። አንድ ንግድ በብዙ ተገኝታ በቀላል ልትሸጥ ትችላለች ። አስረጅ) ሁሉ አገር የወይን ጠጅ ብቻ ቢያፈራ እንደ ብዛቱ ልክ የሚገዛው አይገኝም ። ግን በየተሰጣቸው አንድ አገር ብዙ ሥንዴ አንድ አገር ብዙ የከብት ሥጋ፥ አንድ አገርብዙ ልብስ፥ አንድ አገር ብዙ ማዕድን፥ አንድ አገር ብዙ መኪና፥የመሰሉ ሁሉ ቢገኝባቸው ግን ማለት በየተሰጠው ሥራና ሀብት ብዙ ነገር እያፈሩ ወደ አልተሰጠው አገር እየላኩ ቢለዋወጡ ለሁሉ ዓለም ብዙ ጥቅም ይሆናል ።

(፯ኛ) ጥቅም ማለት የሰውን ፍላጋ (ምኞት) የሚጐዳው ወይም የሚጠቅመው ቢሆን የሚያበርድ ነው ምሳሌ እንጀራ፥ ውኃ፥ አየር፥በረት፥ መርዝ፥የመሰሉ ሁሉ ናቸው። ማለት አንድ ሰው ሊሞት ፈልጎ መርዝ ቢጠጣ ፍለጋውን ፈጸመለት ማለት ነው ።

(፰ኛ) የጥቅም ድምር ወይም ሬላቲብ ማለት ድምር ወይም የማስተካከል ብልጫ ልትሆን ትችላለች ። የጥቅምና ድምር ክፍል የሰውን ፍላጋ ደስ ሊያሰኝ ተሰጥተዋል ። ምሳሌ) የውኃን ጥቅም በመላ ዓለም ባለ ውኃ (ማለት በአየር፥ በባሕር፥በወንዝ፥ በቆሬ ያለ) የተሰጠ ነው ። የጠቅላይ ድምር ማለ

(ጥቅም) ሀብት	ከፍጥረታቸው ተሰናድተው የተገኙ ሀብቶች።	አየር ውሀ ፀሐይ እሱን የሚመስሉ ማለት የሚጠቅሙ ነገሮች ሁሉ ፍጥረትን እንዲያው ለሰው የምትሰጣቸው ናቸው ።
	ሪኬላ (ሀብት)	መሣሯ የሚባሉ እንደ ወቅር ፡ እንጀራ ፡ ልብስ ፣ (ብረት ጥይት) ማለት የሚጠቅሙ የሆኑ ሁሉ ነገሮች ሰው በኃይሉ ሊያገቸው የሚችል ናቸው ።
		ሥራ የሚባሉ፣ እንደሐኪም ጥየቃ፣ የሕግ አዋቂ ጥብቅነት፣ አስተማሪ ፣ ትያትር ክራይ የመሰሉ ሁሉ ናቸው ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ሚከኤል ተሰማ።

የመንግሥት ፤ማስታወቂያ ።

◆

ብቱጃርና በነጋዴዎች መሐከል ለሚገበያዩት ነገርና ደግሞ ስለደላሎች መዝገብ መጻፍ የተደረገ አዋጅ ።

በከተማ ያሉት ደላሎች በመዝገብ እንዲጻፉ ሲሉና በነጋዴዎችና በቱጃር መሐከል ለሚገበያዩት ነገር በደንብ እንዲሆን ሲሉ የንግድ ሚኒስቴር ቀጥሎ የተጻፈውን አውጀዋል።

(ሀ) A ስለ ቱጃርና ስለ ነጋዴ ።

ይህ ማስታወቂያ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ወር ድረስ ነጋዴ፣ ቱጃር፣ ደላላ የሆነ ሰው ሁሉ ቀጥሎ የተጻፈውን አዋጅ በጉምሩክ በተለየ አክብሮ ጠብቆ መኖር ግዴታ አለበት።

በቆዳ፣ በሰም፣ በቡና የሚነግዱ ወደ ውጭ አገር የሚጭኑትም የማይጭኑትንም ነጋዴዎች ሁሉ የገዙትን ዕቃ ዋጋ ለነጋዴው እስከ አምስት ቀን ድረስ ጨርሰው እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል ቀኑም የሚቆረጠው ገዥ ዕቃውን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ነው ። ገገርዎቹም የሆኑትን ነጋዴዎች እስከ አምስት ቀን ድረስ የገዙትን ዕቃ ዋጋ ሳይሰጡ የቆዩ እንደሆነ ከዚህ ከተቆረጠው ቀን በኋላ ሻጩ፣ ነጋዴ ገንዘቡን ባለመቀበሉ የቆየውን ያህል ቀን ገዥ ነጋዴ የቤቱን የምግቡንና የከብቱን ከሳራ ሁሉ እንደሚገባው መስጠት አለበት ።ለዚህም ለከሳራ በሚከፈለው ገንዘብ ሁለቱም ያልተስማሙ እንደሆነ አንዳንድ ሽማግሌ መርጠው እነዚያ ሁለት ሽማግሌዎች በቆረጡት ያለይግባኝ ነገሩ **ይቆረጣል** ።

ከአገር ውሥጥም የሚመጡ ነጋዴዎች ሁሉ ጭነው የማስመጡት ሌላ የማታለያ ነገር ያልገባበት እንዲሆን ያስፈልጋል።ገዥውም የገዛው ዕቃ ዓይነትና ሚዛኑ የተካከለ እንዲሆንለት ዕቃውን እንደገዛ በዚያኑ ጊዜ ፈትሾና መርምሮ የተበላሸ ነገር ቢኖር ወዲያው ያስታውቃል። ዕቃውንም በመምረጥ ገዥና ሺያጩ ሳይስማሙ የቀሩ እንደሆነ ሁለቱም ተስማምተው አንድ አዋቂ ይመርጣሉ ። ይህንንም ደንብ ተላልፎ የተገኘ ነጋዴ ሁሉ ገዥውን አሳስቶ የወሰደበትን ትርፍ ታስቦ በዋጋው ግምት አታሎ የወሰደበትን ያህል በዕጥፍ ለገዥው ይከፍላል ።

በዚህም ደንብ ላይ ሳይጻፍ በቀረ ነገር ገዥና ሺአጩ የተጣሉ እንደሆነ ሁለቱም በየወገናቸው ላልተስማሙበት ነገር አንዳንድ ሽማግሌ ይመርጣሉ ። እነዚህም ያልተስማሙ ሰዎች ሽማግሌ ወይም አዋቂ በመምረጥ ያልተስማሙ እንደሆነ ወይም የተመረጡት ሽማግሌዎች ሳይስማሙ ቢቀሩ ያስፈለገ እንደሆነ የጉምሩክ ሹም ተቆንሲሎቹ ጋራ ተስማምቶ ይግባኝ የሌለበትና ቃሉ የማይሻር አንድ የበላይ ሽማግሌ ይመርጣል።ነጋዴዎች ሁሉ ትምሕርት የሌላቸው ስለሆኑ ማናቸውም ዓይነት ውልና የደረሰኝ ወረቀት ሁሉ ከጉምሩክ ነጋዴዎች ከሚጻጻፉበት ቦታ ላይ ካልተዋዋሉና ካልተፈራረሙ በቀር ከሌላ ቦታ ላይ የተጻፈ ውልና የደረሰኝ ወረቀት አይረጋም ።

(ለ) B ደላላ።

(1)ደላላ የተባለ ሁሉ ለቱጃሮች የተሠራውን በትክክል መጠበቅ አለበት ደግሞም ከጉምሩክ በተለየ በተሰናዳው ደብተር ስሙን ማጻፍ የግድ አለበት ።

(2)እነዚህ በመጀመሪያው ክፍል ስማቸውን ከዚህ በላይ በተባለው ደብተር ላይ ለማጻፍ ግዴታ አለባቸው የተባሉትነጋዴዎች ለመጻፍ እንዲችሉ በከተማ ውስጥ በጣም የታወቁ የሁለት ነጋዴዎች ወይም ዜጋው ለሆኑት የቆንሲሉ ፊርማ ያለበት በትክክል የሚሠሩና መልካም ስም ያላቸው ነጋዴዎች መሆናቸውን የሚመሰክርወረቀት ለጉምሩክ ሹማምንት ማቅረብ አለባቸው ።

(3)ይህንንም የፈቃድ ወረቀት ለመስጠት ጉምሩክ ላንድ ጊዜ ብቻ አሥር ብር ይቀበላል።ይህንንም የፈቃድ ወረቀት የተቀበሉ ነጋዴዎች ሁሉ ንግዳቸውን ያለ እውከት እንዲነግዱ ተፈቅዶላቸዋል ።

(4)ከመዝገብ አስቀድሞ ሳይጻፍ በቆዳ፣ በሰም፣ በቡና፣ የሚነግድ ሁሉ ሀያ አምስት ብር አደብ ይከፍላል።ይኸውም አደብ የከፈለው ሰውዬ የፈቃድን ወረቀት ሳይቀበል ደግሞ ሲነግድ የተገኘ እንደሆነ መቶ ብር አደብ ይከፍላል።በሰስተኛው ግን አደቡ ሁለት መቶ ብር ይሆንበታል ።

ደግሞ ወደፊት ስለ ሚዛን የሚያስፈልገውን አዋጅ እናወጣለን ።

የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፩። የኢ. መ የንግድ ሚኒስቴር።

የዘበኞች ትጋት ።

ወልደ አማኑኤል የሚባል ሰው ተክለ አብ የሚባለውን የባልንጀራውን ዝናር ከነጥይቱ ልብሱንና በርኖሱን ለመውሰድ ሲል ወደ ሴት ቤት አብረኸኝ እንሒድ ብሎ አስከትሎት ሒዶ በመሸታ ቤት በመጠጥ አስክሮ ፍልወሀ ሜዳ ሲደርሱ እንረፍ ብሎ በደንጊያ ላይ አርፈው እዚያው እረፉበት እንደተደገፈ በሰንጢ መጀመሪያ ትከሻውንና ሆዱን ወግቶ በመጨረሻው አንገቱን አርዶ ገደለው። ይኸንኑም ያደረገው፡በጥር ፲ ቀን እሁድ ማታ ለሰኞ አጥቢያ ነበርና ሰኞ ጧት ዘበኞች እሬሳውን አግኝተው አቶ በላይነህ ለሚባል የመቶ አለቃ ነግረውት እሱም በፍጥነት ለባሻ ደነቀ ከስታወቀ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ይኸነን ነገር ሰምተው በዚህ አሟሟት እጅግ ስላዘኑ የማዘጋጃ ቤቱን ዲሬክተር ነጋድራስ አስታጥቄን በፍጥነት አስጠርተው በብርቱ እንዲመረመርና እንዲፈለግ አዘዙ።

ይህ ክፉ አድራጊ ወልደ አማኑኤል ከሟቹ ከተክለ አብ ጋራ ሲተናነቅ ሰንጢው ፊቱን ሚጭሮት እጁንም ቆርጦት ኑሮ የእጁ ደም በየመንገዱ እየተንጠበጠበ ምልክት ስለ ሰጠ ዘበኞች ይኸንኑ ደም እየተከተሉና ምልክት እያደረጉ ሲፈልጉ እስከ ታጠበበት ወንዝ ድረስ አደረሳቸው፡ ወዲያው የሟቹ ዘመዶች ተገኝተው ለዚህ ለወንድማችሁ አለቃውስ ማነው ባልንጀራውስ ማነው ይባላል ብሎ ባሻ ደነቀ ቢጠይቃቸው ባልንጀራውማ ወልደ አማኑኤል የሚባል ነው ስላሉ ወደ የ፳፫ አለቃው አበበ ገብሬ ወደ ሚባለው ልከው ወልደ አማኑኤል እንዲያዝ አድርገው እሑድ ሌሊት ለሰኞ አጥቢያ ገድሎ ማክሰኞ ከተያዘ በኋላ ያደረበትንና የዋለበትን ሁሉ ጠይቀው ከሟቹም ጋራ ሲተናነቅ ሰንጢ የሚጨረውን ፊቱን፡የቈረጠውን እጁን ደም ነክቶት ያጠበውን ልብሱን በብዙ ምርምር በባሻ ደነቀ ላይ አምኖ የሟቹንም ዝናሩን ከነጥይቱ በርኖሱንና ልብሱንም በየሰዉ ቤት አደራ ያስቀመጠበትን አሳየ። በነጋድራስ አስታጥቄም ላይ በዚሁ ቃል አምኖ በየካቲት ፲፫ ቀን በግርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርቦ መግደሉን በቃሉ አመነ፤ ስለዚህም የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ተሰቀለ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በብዙ ርኅራኄና ለሕዝባቸው በመጨነቅ ብዛት ዘበኞቹን አትግተው ገዳዩ ወልደ አማኑኤል በገደለ በማግስቱ መያዙና በተያዘ በሦስተኛው ቀን ተሰቅሎ የሟቹ ደም መከፈሉ በደባባይ የዋለው ሰው ሁሉ የግርማዊ ንጉሥን ዕድሜ ያርዝመው፡መንግሥታቸውን፤ ያስፋው እያለ እየመረቀ ሔደ ።

ዘበኞችም ምንም እንኳ በየጊዜው ብዙ የሚያስመሰግን ሥራ ቢሠሩ የዛሬው ሥራቸው የበለጠና ደስ የሚያሰኝ ስለሆነ ይኸነን ነገር ከሥር እስከ ጫፉ መርምሮ ያወጣው ባሻ ደነቀ ፫ኛ ማዕረግ ኒሻን ተሸለመ ።ደግሞ የክፍል ሥራው እንኳ ሳይሆን በቅንነትና መንግሥቱን ደስ ለማሰኘት ሲል እሬሳውን አይቶ የደሙን ምልክት እየተከተለ በድንጋይ ላይ የነጠበ ደም ሳይቀር እያቀረበ በመመርመር ለደከመው ላቶ በላ

ለማ ለደከመና ለተጋ ለልጅ ዘለቀ አበየ፤ ይኸንኑ ምርምር በሚገባ አስተካክሎ ለጻፈ ላቶ ከተማና መጀመሪያ እሬሳውን አይተው ላቶ በላይነህ ላስታወቁ አበነህና አያኔ ለሚባሉ ዘበኞች፤ ስለ ትጋታቸው እንደ ሽልማት የሆነ ገንዘብ እንዲቀበሉ ታዘዘላቸው ።

ሥራ ሠሪውን፡እሾህ አጣሪውን እንደሚባል አቶ አማከለ የሚባል የፍርድ ጸሐፊ በጥር ፲፬ ቀን ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት ወደ ቤቱ ሦስት ሌቦች መጥተውበት ፪ቱ አምልጠው ሦስተኛው ዘሰንሰል ቅጠል ውሥጥ ተደብቆ ኖሮ አቶ አማከለ ዓይቶ በጠመንጃ ገደለው ወዲያው ጐረቤትና ዘበኛ ደርሶ በዚያው በደጁ መግደሉንና የገደለውም ከሌሊቱ በ፯ ሰዓት መሆኑ ተመሰከረለት ። የሞተውም ሥራና አለቃ ወይም ጌታ ያለው መሆኑ ወይም አርሶና ነግዶ ነዋሪ መሆኑን የሚያውቅለት አልተገኘም። አኅቱ ነኝ የምትል አንዲት ሴትም ተጠርታ ትፋረጃለሽ ወይ ቢሏት ይህ ሰው ከኔ ዘንድ ከሔደ ፲፫ ቀን ይሆነዋል አልፋረድም ስለ ማለቷ በማናቸውም ዓይነት ለሟቹ መልክም ወሬ ስላልተወራለትና ስላልተመሰከረለት ገዳዩ አቶ አማከለ እንደታሠረ ከግርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርቦ በሁለት ዋስ ተለቀቀ ።

ስለ ትምህርት ፍቅር ።

ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር የወለጋው ገዥ በየካቲት ፲፰ ቀን በ፱ ሰዓት የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ተማሪ ቤት ለማየት መጥተው ነበር ። የተማሪ ቤቱም ዋና ሹም አዛዥ ወርቅነህና ዲሬክተሩ ሙሴ ቶማዚኒ በየክፍሉ እያገቡ ደጃዝማችም የፈረንሳዊ ቋንቋ ይናገራሉና ተማሮቹን የፈረንሳዊ ትምህርት እየጠየቁ ያሳዩአቸው ነበር።ከዚህ በኋላ ወደ መጻሕፍት ቤት አግብተው መጻሕፍቱንም በየዓይነቱ ዓይተው እጅግ ደስ አላቸው ። ከዚህም በኋላ ሹራብ ወደሚሠራበት ቤት ወስደው አሳዩአቸው ። ከዚህ በኋላ የሸማ ሥራ እሚማሩትን አሳዩአቸው ። ከዚህም በኋላ እንጨት ሥራ ወደሚማሩበት ወሰዱአቸው። ከዚህም በኋላ ለሻይ ግብዣ ወደ ተሰናዳው አዳራሽ ወሰዱአቸውና በደጃዝማች በስተቀኝ ዋናው ሹም አዛዥ ወርቅነህ በግራ ዲሬክተሩ ሙሴ ቶማዚኒ በግምባር ተቀመጡ።ከዚህም በኋላ የነነዌ ጾም በሆነበት ቀን በመምጣታቸው እያዘን ወተት ያልተደባለቀበት ሻይ አቀረብንላቸው ። ከሻዩም በኋላ ሻምፓኝ በቀረበ ጊዜ አቶ ኤፍሬም የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ። ክቡር ሆይ በተማሪ ቤቱ ዋና ሹም ፈንታ ሆኜ የምናገረውን ቃል ክቡርነትዎ እንዲፈቅዱልኝ እለምናለሁ ። ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የደጉን የዳግማዊ ምኒልክን ፈቃድ ተከትለው ይህን ተማሪ ቤት አቆሙ ። ክቡርነትዎም በለጋስነትና በደግነት በየመቱ የሚያደርገውን ቸርነት እንኳንእኛ ስምዎን ተጽፎ ያየው ሁሉ ያመሰግናል። ባገርዎም የትምህርትን ነገር ለመዘርጋት መጣጣርዎን እየሰማን ኢትዮጵያውያን የሆነ ሁሉ እጅግ እናመሰግናለን ። ክቡር ሆይ ዛሬም ስለተማሪ ቤቱ ክብር መጥተው ስላዩልን በስተማሪዎቹና በተማሪዎቹ ስም ምስጋና

ሜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ። ለኢትዮጵያም ሰላምና ደኅንነት ይስጥልን ብለው ከጨረሱ በኋላ ቆይተው ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር ተነሡ ። እኛም ወረቀት በጃቸው አላየንምና መሐዳቸው መስሎን ነበር አእምሯቸው ከጽሕፈት አብልጦ የተዘጋጀ ኑሮ በቃላቸው የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

ክቡራን የተማሪቤቱ ዋና ሹምና ዲሬክተር ከዚህ ቀጥዬ እምናገረውን ቃል እንዲፈቅዱልኝ በትሕትና እለምናለሁ አዲስ አበባ የተባለች ቀድሞ ነበር ግን የቀድሞው ትንቢት ነበር እንጂ አዲስ አበባ ማለትስ የዛሬ ስሟ ነው እግዚአብሔር በቸርነቱ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን አስነሥቶ በዕውቀት እንደነሠለጥን ይጣጣሩልናል እኔም በገሬ ሳለሁ ወሬአቸውን እየሰማሁ ደስ ይለኝ ነበር በኋላም አባቴ ሙተው የወግ ዕቃ ይገፈ መጥቼ በወሬ ከሰማሁት ይልቅ ባይኔ ያየሁት በልጦልኝ ደስ ብሎኝ ወደ አገሬ ተመለስሁ፡ ዛሬም ለግብር ያመጣሁትን ገንዘብ የተማሪ ቤት በገርሀ ላይ ሥሩበት ብለው ስለፈቀዱልኝ ከልቤ የማይጠፋ ደስታ ስላደረጉልኝ እጅግ አመሰግናለሁ ። ሰው ሐውልት ማሠራቱ ለስሙ መጠሪ ነው ግን ሐውልቱ የማይነቃነቅ ነውና የሚመሰገነው በገሩ ብቻ ነው የትምህርት መታሰቢያ ግን በሁሉ ስፍራ ነውና የግርማዊ ንጉሥ መታሰቢያም ለዘላለም በዓለም ላይ የበለጠ እንዲሆን ተስፋ አደርጋለሁ የሀገሬም የወለጋ ልጆች በየሚሰዮኑ የሚበቃ ትምሕርት ባያገኙ በባቡር መሔጃ ገንዘብ ስለሌላቸው በግራቸው ወደ ከርቱም ሲሔዱ እኩሎቹም በጎዳድ ያልቃሉ፤ እኩሎቹም የሚማሩበት ገንዘብ ስላልኖረቸው የፈለጉትንም አጥተው በሰው አገር ይንከራተታሉ ። ተንግዲህ ወዲህ ግን ልብሳችንን ስንኳ ቢሆን ሽጠን ለተማሪዎች እርዳታ እንድንሰጥ ቁርጥ አሳባችን ነው ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት፤ ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ኢትዮጵያን ለዘላለም ያኑርልን ብለው በጨረሱ ጊዜ ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ ያጠናሁት ብቻ ትንሽ ጻፍሁ እንጂ ለጆሮ የሚጣፍጥ፤ ለልብ ደስ እሚአሰኝ ብዙ ተናገረው ነበር፤ ሙዚቃውና መዝሙሩም እጅግ ደስ እሚአሰኝ ነበር ፤ ከዚህ በኋላ ደስ እሚሰኝ ሲኒማ ተደረገና በሙዚቃ ተሰናብተው ሔዱ ።

ትናንት የነበረው ሁሉ የነገሩ ማማር ደስ እያለኝ ጽሕፈት ስላበዛሁ ከአንባቢዎች ይቅርታ እለምናለሁ ።

ትንሽ ወንድማችሁ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።

ለጨረታ ማስታወቂያ።

ድሬ ዳዋ ላይ ስለ ሚሠራው አዲስ የፖስታ ቤት ዋጋውን ለመጫረት የሚፈልግ ተቋራጭ ሁሉ የሚሠራበትን የዋጋውን ልክ ለፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ምኒስትር ከዛሬ ዠምሮ እንዲያስታውቅ እናመለክታለን ።

የሥራውንም ዓይነት አይቶና መርምሮ የዋጋውን ልክ ለመቍረጥ የሚአስፈልገውን ወረቀቶች ሁሉ (የቤቱ ሥዕልና የሥራው ዝርዝር ያለባቸው) ድሬ ዳዋና አዲስ አበባ ፖስታ ቤት ይገኛሉ ።

የጨረታውም ወረቀት እስከ የካቲት መጨረሻ ቀን ድረስ ይረጋል ከዚህ ቀን አልፎ የሚመጣ የጨረታ ወረቀት ሁሉ አይረጋም

ADMINISTRATION DES POSTES
ET DES TELEGRAPHIES ETHIOPIEN
ADJUDICATION

M. M. les Entrepreneurs sont invites des maintenant a faire connaitre a M. Le Ministre des P. T. T. leurs prix relatifs a la construction d'un nouveau bureau de Postes a Diré-Daoua.

Ils peurrent prendre connaissance des decusents (devis et plan) pour la détermination de ces prix, dans les bureaux de Postes de Diré Daoua et Addis-Abeba qui se tiendrent a leur disposition.

Delai d'optien jusqu'ua 31 mars 1929

Le Ministre des P. T. T.

ስለ መንገድ መሻሻል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አገራቸው በእውቀትም በሥራም በኩል እንድትሠለጥንና እንድትሰፋ የሚፈልጉ ስለሆነ ደልቁንም ደግሞ ሥራ የሚለማው መንገድ ሲበዛ እንደሆነ ተረድተውት ከጎሬ እስከ ጋምቤላ ድረስ ያለው መንገድ እንዲሠራ ፈቅደው ውሉን ለሙሴ ዜርበስና ለሙሴ ዳናሊስ ሰጧቸው።

ሙሴ ዳናሊስ ለዚህ ለመንገድ ማኅበር ለማቆም ወደእንግሊዝ አገር ተሻግረው ነበርና በብልሀነታቸው ይኸን ያሰቡትን ማኅበር አቁመው ተመልሰው መጡ ማለትን ሰማን ። ይህ መንገድ መሠራቱ ላገራችን ለኢትዮጵያ ዋና ጥቅሟ ነው ከዚህ ቀደም በጎሬና በጋምቤላ መካከል ዕቃ የሚያመላልሱ ብዙ ከብቶች በየመቱ ያልቁ ነበር ከከብቱ ይልቅ ደግሞ የሚያሳዝነው ተሸካሚው ሰው እንደዚሁ ብዙ ያልቅ ነበረ ። አሁን ግን ይህ መንገድ ከተሠራ ፱ያመቱ ያልቅ የነበረው ሰውና ከብት ይድንልናል ሰውም ወደእርሻው ተመልሶ ጠቀሜታውን ያገኛል ከብቱም ሌላ ሥራ ይሠራል ። መንገዱም ጎሬ ከደረሰ በኋላ ሸቀጥ ለማመላለስ አያስቸግርምና በጎሬ አውራጃ ያሉ ቡን ተከዮች ቡናቸውን ወደውጪ አገር ለመስደድ ሁውከት ስለ ማያገኙቸው አትክልታቸውን እያሰፉ አገራቸውን ያለማሉ ። ላገራችን ጥቅሟ ይህ ነው የኢትዮጵያ ቡን በኢትዮጵያ ብቻ ነው እንጂ በሌላ አገር አይገኝምና ።

ስለ ምስር ቆንስል መግባት ።

ሙሴ ፋራግ ቤይ ሙሳ የምስር ቆንስልነት ተሹመው ባለፈው ሳምንት ወደ አዲስ አበባ ገቡ።

ብርሃንና ሰላም የምስር ቆንስል ሙሴ ፋራግ ቤይን እንኳን ደኅና ገቡ ይላል ።

ስለ ክቡር ራስ ጉግሣ መግባት

የካቲት ፲፱ ቀን ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ ከክብርት ባለቤታቸው ከወይዘሮ ሻሽወርቅ ጋራ በባቡር አዲስ አበባ ገቡ። ክቡር ራስ ጉግሣንና ክብርት ወይዘሮ ሻሽ ወርቅን ለመቀበል ብዙ መኳንንትና ሠራዊት እስከ ባቡር መረፊያ ድረስ ወርደው

በትልቅ ክብርና በሰልፍ ተቀበልዋቸው ።

ብርሃንና ሰላም ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያንና ክብርት ወይዘሮ ሻሽ ወርቅን እንኳን ደኅና ገቡ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የመጣ ራድዮ የየካቲት ፲፰ቀን የዕለት ወሬ።

ዋሽንግቶን ፤ ፕሬሲዳን የመረጣቸው ሰዎች የሚከተሉት ናቸው የመንግሥት ጸሐፊ ሰክሬተር ስትሩመን ፤ ግምጃ ቤት ትሬዘሪዩ ሚሎን ፤ ያገር ውሥጥ ራሲማን ፤ የባሕር አዳም ፥ ትስጣና ተሌግራፍ ብሮውን ።

ማመልከቻ ።

ጨርጨር ለሥራ ታዘው ወርደው የነበሩ ሙሴ ሐንሪፔቲ አሁን ሲመለሱ በግርማዊ ንጉሥ ፈቃድ ወደ ጥንት ሥራቸው፥ እውጭ ጕዳይ ሚኒስትር ተመለሱ ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርበስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

ሐኪም አምባር ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሌት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
ያበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኸረጃ	፲፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኸረጃ	፲፯ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኸረጃ	፻፹ ብር
ባለሰይጣን		፻፹፪ ብር
፡ ፡ ባለ ድመት ።		፻፳ ብር
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፳ ብር
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፵ ብር
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፶ ብር
“ “ ጃፖን		፻፷፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፷፯ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፹
ባአንድ ብር	፳ ሊሬ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ክ፲ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋ ውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ማረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
ΚΟΝΙΑΚ - ΜΕΤΑΞΑ



ዝኒት የእጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆኑ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ሳገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያ ዎችና በያይነቱ ሳስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቀበት ዘወትር ይገኛል

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናበለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ኒኮላ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ኩሚ ባንያ የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር በተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪከን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋውን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው።

ጉድዬር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲
5me ANNEÉ № 10

ሐሙስ የካቲት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 7 FEVRIER 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህነን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

◆

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Dirèction et Rèdaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ ባ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፷፮ ገጽ ተከታይ ።

፱ኛ፡ዓሬላቲብ ጥቅም ያች የልዩ ልዩ የጥቅም ክፍል ነች ምሳሌ) የሚያስፈልገኝን የሚበላ ሥጋ በብዙ ክፍሎች ልከፋፍለው እችላለሁ ። ከነዚያ መጀመርያይቱ ከሁለተኛይቱ ከሦስተኛይቱ፤ ከአራተኛይቱ፤ጥቅማቸው እያነሰ ይሔዳል።

፲ኛ፤የመጨረሻይቱ ጥቅም ማለት ሊከፋፈሉ የሚችሉ ጥቅሞች ማለት ናቸው ። እስረጅ) የመጨረሻይቱ የወኃ ጥቅም ምንም የላትም፤ስለምን መጨረሻው ሊኖረኝ የሚችል አንድ ብርጭቆ ወኃ ምንም አያወጣም ። ከልክ ያለፈ ወኃ አለኝና ለሚያስፈልገኝ ነገር አይጠቀመኝም ። ወኃ በማይገኝበት በአንድ በረሃ ግን የመጨረሻይቱ ብርጭቆ ወኃ ጥቅምዋ በጣም ከፍ ያለ ታላቅ ነው፤ ስለምን ያች ብትፈስብኝ በጥማት ወደ ሞት ለመድረስ እችላለሁና ሕይወቴን የምትይዝ ናት ።

፲፩ኛ፤ ሶጂቲብ የመሣርያ ዋጋና አጂቲብ የለውጥ ዋጋ በሁለት ነገሮች ይለያያል ። ሶጂቲብ ሬለቲብ ለያንዳንዱ ሰው ምሳሌ መውደድ ፤ መጣፈጥ ፤ አጂቲብ ለሁሉ ትክክል ምሳሌ) የጆሜትርያ ዓይነት ክብደት ቁመት ።

፲፪ኛ፤ የሶጂቲብ መሠረቱ የመሣርያ ዋጋ ለአንድ ሰው ያለው ወይም ሊያገኘው የሚፈልግ ስጦታ የሀብት ጥቅም ነው። ምሳሌ) በጣም ለማያይ ሰው መነጽር ለአንካሳ ሰው ምርኩዝ እንበል ስለምን ቢል ፤ በጣም ለማያይ ሰው መነጽር ጥቅም በጣም ትልቅ ነውና በቀላል ዋጋ የሚያገኘው ቢሆንም በብዙ ሺ ብር በገዛው በደኅና የሚያይ ሰው ግን ምንም ጥቅም የለውም (ሊነግድበት ካልሆነ) በአንድ ቤሳም መግዛት ይቅርና ወድቆ ቢያገኘውም ባላስነሣውም ።

(ባሎሬ አጂቲብ)የለውጥ ዋጋ ለሌላ መለዋወጥ ከምትችለው

ንዘብ ብቻ ይመለከታል።ለሚማርበት ተማሪ ግን ብዙ ጥቅም አለበትና የበለጠ ውድ ቢሆንም በብዙ ሺ ብርም በገዛቸው። ልብስ ነጋዴ የዋጋውን ገንዘብ ይመለከታል። ለሚለብሰው ሰው ግን ጥቅሙ ብዙ ነውና በብዙ ገንዘብ በገዛው እንደዚሁም ሥንዴ (እህል) ነጋዴ ዋጋውን ብቻ ይመለከታል።ለሚበላው ሰው ግን ጥቅሙ እጅግ ታላቅ ነውና ማለት እንጀራ በቀላል ዋጋ የማያገኘው ቢሆን ያለውን ገንዘብ ሁሉ ጨርሶ ለመግዛት ባንድ ጊዜም ቢሆን የግድ በሆነበት ።

፲፫ኛ፤ሌላ ምሳሌ) አልማዝ (የኢሳ) የመሣርያ ዋጋው በጣም ዝቅተኛ ነው ። የለውጥ ዋጋው ግን በጣም ከፍ ያለ ነው።ስለምን የሚፈልጉት ሰዎች ጥቂቶች ናቸውና፤ እንጀራ ግን (የኢሳ) ማለት የመሣርያ ዋጋው በጣም ከፍ ያለ ነው ፤ ስለምን ሰው ሁሉ እንጀራ ይጨርሳልና፤ የለውጥ ዋጋ ግን በጣም ዝቅ ያለ ነው ስለምን ለሁሉ የሚበቃ ይገኛልና ።

፲፬፤ የዋጋ ምክንያት እንደ ብዙዎች ሰዎች ባህሎች ዋጋ የፍጥረት ሀብት ወይም ጥቅም ከማነስ የተነሣ ነው ይላሉ። ለምሳሌ አልማዞች እጅግ ጥቂቶት ናቸውና ብዙ ዋጋ ያወጣሉ።ግን ይህች ባህል እውነቱን ሁሉ አትናገርም።ስለምን በጣም ጥቂቶች የሆኑ ብዙ ነገሮች ምንም የማያወጡ አሉና።እስረጅ፤የሬድዮ ደንጊያ የሚባሉ (ከሁሉ ያነሱ ደቃቆች ፍጥረቶች በደንጊያ ውሥጥ የሚገኙ ከሁሉ የተሻለና የበለጠ መድኃኒት የሚሆኑ ነገሮች(በበዬሚያ የሚባል አገር ብቻ የሚገኙ ከጥቂቶች ዓመቶች በፊት አንድ ቤሳም አያወጡም ነበር። ስለምን የራዲዮን ደንጊያ ጥቅም አልተለደም ነበርና አሁን ግን በጣም የተፈለጉ የተከበሩ ናቸውና ሌላ (ምሳሌ) ገብረ ማርያም በመላ ሕይወቱ አንድ ደብዳቤ ብቻ ጽፎ (ት

፲፯ኛ ፤ እንደሌሎች ሰዎች ባህል ደግሞ ዋጋን ከጥቅም (ከመፈለግ፡ ወይም እንደፈላጊው ምኞት) የተነሣ ነው ይላሉ። ለምሳሌ ጥሩ ልብስ ብዙ ዋጋ ያወጣል። ብዙ ሰው ይፈልገዋልና፡ ግን ይህች ባህልም ልክ አይደለችም፤ውኃ ብዙ ትጠቅማለችና ብዙ ሰው ይፈልጋታል ግን ምንም ዋጋ አታወጣም።

፲፰ኛ፡ በመጨረሻ ሦስተኛይቱ ባህል ዋጋ ከሥራ ነው ስትል ታቆማለች ። ይህች ባህልም ልክ አይደለችም እውነትኑሮው ቢሆን በአንድ የጥቅም ነገር የድካም ሥራ የሚያስፈልገን ሰጥፍ ዋጋ ሁኖ ባገኘነው ነበር ። ግርምቢጥ ግን አንድ መልክም ትልቅ ዘማሪ ፡ በአንድ ማታ ማለት በአንድ ሰዓት ከሺ፰፻ እስከ ፫ሺ ብር የሚበልጥም ሊያወጣ ይችላል። በመሬት ውሥጥ ደንጊያ የሚሰብር አንድ (ሚናቶሬ) ወይም አንድ የሰኀራ ጥራጊ ሰው ግን፡ በአንድ ሰዓት ሥራው የሚያወጣውን ብር ወይም በ፭ ተሙን ይገመታል ። አንድ ተከራካሪ አንባቢ ብዙ አዋቂ የሆነ ዘማሪ ከአንድ ደንቆሮ ሰው ሊመዘን ልክ አይደለም ሊል በቻለ ። ግን ሰዚሁ አሳብ አፍራሽ መልሱ ቀላል ነው ፤ አንድ ፕሮፌሰር (አስተማሪ የአንድ ሰዓት ሥራው የሚያወጣው አላይ፡ አንድ ብር ፡ ቢበዛ እስከ ሁለት ብር ምናልባት የኡኒቤርሲታ እስከ ሦስት ብር ይገመታል ።

፲፱ኛ፡ እንግዲያስ ዋጋ፡በፊት ከመለስንኩዋቸው በአንድነት ከሦስት ነገሮች ነው ። ማለት ለማግኘቱ ማር (ጥቂትነቱና ሥራው) ከመፈለጉ ነው ።

ሚካኤል ተሰማ

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል ።

ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል አከባበር ።

የካቲት ፳፫ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል ወይንም የዓድዋ ጦርነት መታሰቢያ በዓል ስለሆነ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በክቡራን መኳንንቶቻቸውና በሠራዊታቸው ታጅበው ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ገቡ። በዓሉን ለማክበር የተሰበሰበው ሰውም እጅግ ብዙ ነበረ ። ክቡር መልአከ ገነት ወልደ ሐናም ሊቃውንቶቹንና ካህናቱን ሥርዓታቸውን በጥንቃቄ እንዲፈጽሙ ስላደረጉዋቸው የሊቃውቱና የካህናቱ አኳኋን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበረ ።

በዚያን ጊዜም ክቡር ሊቀ ጠበብት ረዳ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኙ ።

ክቡር ይእቲ ።

ርቱ ገጻተ እንተ ነጸረ ወልደ ነጐድጓድ ባሕቲቱ ።
ይሁዳ ቅሩፍ እመ ረከበ በታሕቱ ።
ዓለመ ይንግእ በዘአኪን ድልወቱ ።
ዋሕደ ገጸ እምኢያትረረ እምነ ገጸት ርቱ ።

ዕጣነ ሞገር ።

በትረ ብርዕ ቀጥቂጥ እንተ አስመከ ገሃደ።
ሥርዎ ገሞራ በእደ አስተዋደደ ።
ምኒልክ በጸሎቱ ወበሃይማኖቱ ዘንእደ ።
እምጣነ አግዚነ ወአውረደ ።
መልአከ ሰማይ እሳተ ነዳዲ ወጊዮርጊስሃ በረደ ።
ንገሥት እስከ ተቀጥቀጡ ወከነ ሐመደ ።
ኃይለ ሥላሴ ወንጌለ ከመ ይስብክ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘዖደ ።
አንባለ ፃማ ወሐፍ እምአስከለ ድንግል ተወልደ ።
አድኅኖተ ዓለም እስመ ፈቀደ ።
ወለፍቅረ ሰብእ ዘከነ ልደቶ ዘክሕደ ።
በሕይወቱ ይከውን ምክያደ ።

ከቅዳሴ በኋላም ውዳሴ ተደረገና ከውዳሴ በኋላ ካህናቱና ሊቃውንቱ በግርማዊ ንጉሥና በመኳንንቱ ፊት ሲያሸበሽቡ አምረው ቆዩ። ከዚህ በኋላ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ባርከው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱት ።

ይህም ቀን የኢትዮጵያ ጀግኖች ስለ ሀገራቸው ደማቸውን አፍሰው ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡበትን ቀን መታሰቢያ በዓል ነው ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ ዘንድሮ ፴፫ ዓ አለፈ።

ግን ዛሬ ብዙ ጥል ብዙ ፍቅርን ያመጣል እንደሚሉት ሁሉ በኢትዮጵያና በኢጣልያ በሁለቱ መንግሥታት መካከል የፍቅር መሠረት ስለተጀመረ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ብዙ የፍቅርና የስምምነት መገናኛ ተደርጓል ። ይህ የሁለቱ፡ ፍቅርና መስማማትም በሁለቱ መንግሥታት የፀና እንደሚሆን አይጠረጠርም ።

ስለ ፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ።

የካቲት ፳፫ ቀን ግርማዊ ንጉሥ ነፃ የወጡ ልጆች የሚማሩበትን ትምህርት ቤት ለማየት መምጣታቸው በታወቀ ጊዜ ክቡር አዛጋ ወርቅነህ የፍቅርና አገልግሎት ማኅበርተኞችንና የነፃ ተማሪዎችን ሰብስበው የግርማዊ ንጉሥ መምጣት ይጠባበቁ ነበር ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅም ማኅበርተኞችና የተጠሩ መኳንንቶች ሻይ የሚጋበዙበት ቤት በሥርዓት እንዲሰናዳ አደረጉ ።

ዓሥር ሰዓትም በደረሰ ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ ባማረ አቶሞቢል ተቀምጠው ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ ደረሱ፤ ማኅበርተኞችና ተማሪዎቹም በሰልፍ ተቀበሉዋቸው።ግርማዊ ንጉሥ በገቡ ጊዜም ተማሪዎቹ የእጅ ሥራ የሚማሩበትን በየክፍሉ አይተው ለሻይ ግብዣ በተሰናዳው ቤት ገቡ።

በዚያን ጊዜም የትምህርት ቤቱ ዲሬክቴር አቶ ያሬድ ከማኅበርተኞችም ከተማሮችም ብዙ ንግግር ተደረገ ይልቁንም ተማሪዎቹ ስለኢትዮጵያ ያደረጉትን ከሚደ ግርማዊ ንጉሥንና መኳንንቱን በዚያም የነበረውን ሰው ሁሉ እጅግ ደስ አሰኘ ።

ግርማዊ ንጉሥም የሥራው አጀማመር ደስ ስላሰኛቸው ላገራቸው እርዳታ በመትጋታቸው ለክቡር አዛጋ ወርቅህና ለማኅበርተኞቹ በጣም አመስግነው የሚያደርጉላቸውን እርዳታ ለወደፊቱ እንዲያስታውቋቸው ደስ የሚያሰኝ ተስፋ ሰጥዋቸው።

አርአያ ሥላሴ የተባለ ተማሪ ባነጋገሩ ሁሉ ግርማዊ ንጉሥንና መኳንንቱንም ደስ ስላሰኘ ግርማዊ ንጉሥ የወርቅ ሰዓት ሸለሙት

አቶ ያሬድ ስለ ትምህርት ቤቱ ሒሳብ የተናገረው ንግግር ።

እጅግ ቸር ቻይ የሆኑ ግርማዊ ንጉሥ

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት በቸርነታቸው ብዛት ለድሆቻቸው መማሪ ይህንን ቤት ሰጡን ነፃ የወጡትንና አባት እናት የሌላቸውን የሆኑ ልጆች ለ[illegible] እጅ ሥራ መማሪ

ግርማዊ ንጉሥ በሰጡን እርዳታ ገንዘብ ዓይናቸውን መክፈት ስለ ጀመሩትና እንደዚሁ የኢትዮጵያን ልጆች በጥበብ ለማስፋት በየስፍራው ሁሉ የትምህርት ቤቶች ስለ ከፈቱልን በግርማዊትና በግርማዊ ስም እስከ ዘለዓለም ሲታሰብ ይኖራል። እነዚህ ሕፃናቶች ያፈሩትን ፍሬ በግርማዊ ንጉሥና በመኳንንቶችም ፊት ቀርበው በየዓይነቱ የእጅ ሥራቸውንና መማሩቸውን ስለ አሳዩ ፍጻሜ የሌለው ደስታ ለፍቅርና አገልግሎት የማይረሳ መታሰቢያ በልባችን እንደ ታተመ ሆነ ።

ክቡር አዛዥ ወርቅነህ የነፃ ተማሪ ቤትን ሥራውን ለማስኬድና ለማስተማር ከሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት ከሰጡኝ ጀምሮ ገቢና ወጭውን ከዚህ በታች ጽፌ አስረክባለሁ።
ተማሪ ቤቱ ከተመሠረተ ከ፲፱፻፲፰ ዓ ግንቦት ፳፬ ቀን ጀምሮ እስከ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ድረስ ቀሪው ብር ፲ሺ፰፻፶፱ ብር ከ፸፩ ሳንቲም ይገኛ።

	ገቢ.	ወጭ
የሰኔ ወር ገቢ.	፲ሺ፫፻፳፰ ብ ፳፫ ሳ	ሺ፩፻፴ ብር ፶ ሳን
የሐምሌ ወር ገቢ.	፻፴. ፶፯	፫፻፲፰. ፶፰
ነሐሴ ወር ገቢ.	፩፻፫. ፶	ሺ.፶፱, ፲፱
መስከረም ”	፻፳፫. –	፩፻፴፫. ፲፰
ጥቅምት ” ”	፵፱, ፳፫	፫፻፯. ፲
ኅዳር ” ”	፪፻፳፫ –	፫፻፳፫, ፳፯
ታኅሣሥ ” ”	፷፩ –	ሺ.፫፻፵፫, ፶፬
ጥር ” ”	፯፻፯	፳፻፳፫. ፸፯
የካቲት ” ”	፺፱, ፶	፩፻፴፫, ፳
	ድ ፯ሺ፳፻፹፱, ፳	ድ ፯ሺ፯፻፶፫. ፶፬

በየካቲቱ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ቀሪ ገንዘቡን ሁለት መቶ ሐያ ስምንት ከስልሳ ስድስት ሳንቲም (228,66)

የወጭው ምክንያት

ያውቶ ሞቢል መንገድ የተሠራበት፡ የነፃ ተማሪ ቤት የታደሰበት፡ ለተማሪዎች ቀለብ፡ ለልብሳቸው፥ በየቁጥራቸው ልክ ሳልጋ ለፍራሽ፡ለምንጣፍ፥ ለብርድ ልብስ፥ለእጅ ሥራ አስተማሪዎች ደመወዝ ፡ በየሰምንቱ ለሚያክማቸው ሐኪም ደሞዝ፥ ስለ መድኃኒት ዋጋ ፡በሽተኞች ወደ ሆስፒታል መውሰጃ፥ አቶሞቢል ኪራይ፡ የነዚሁም ነፃ ተማሪዎች፡ የእጅ ሥራ ሸማኔነት፡መኪና ሰፊነት፡ አናጺነት ፡ ጥቅጥቅ ስፌት ፡ ብር አፍሣሽነት ከዚህ የተረፈ ያማርኛ ንባብ-፳፬ የሴቶች ሥራ ድውር አደዋሪ፥ ያክርሚ ሥፌት፡ የነዚሁም ነፃ ተማሪዎችና አባትና እናት የሌላቸው ድሆች ሁሉም በንድነት እስከ አምሳ ሆነዋል። የኢትዮጵያን መንግሥት ኢየሱስ ክርስቶስ በቃል ኪዳኑ እየጠበቀ ለንጉሉና ለጥበብ ለዘላለም ኢትዮጵያ ትመሥረት ።ያሬድ ወልደ ኢየሱስ

ነጋድራስ ደስታ የተናገሩት ንግግር ።

አንደኛ ምኞታችን ።

ኢትዮጵያን የሚወዱ ሰዎችና የኔም ምኞት ከዚህ በታች የሚነገር ነው ።

ላገር ጥቅም የሀብትና የሥልጣኔ ምንጮች መጀመሪያው የተማሪ ቤት በየአውራጃው አቋሞ ሕፃናትን ማስተማር ነው።

ሁለተኛም፥ ከጐረቤት የሚአቃርብ መንገድ ከከተማችን እስከ ወሰናችን የሚደርስ በየሀገራችንም ክፍሎች ሁሉ የራቀውን የሚአቀርብ መንገድ መሥራት ነው ።

ሦስተኛ፥ የመሬታችንን ጥቅም በእርሻና በታክልት ከብትም በማርባት እንድናገኝ ነው ።

አራተኛ፥ የመሬት ግብር በገንዘብ መወሰን ለሕዝቡና ለመንግሥቱ ታላቅ ጥቅም ይሰጣል ።

አምስተኛ፡ ሕዝቡ ለመንግሥት የታመነ ታዛዥና ባንድነትም የበና መለያየት የሌለበት እንዲሆን የሚአስፈልግ መሆኑ የኢትዮጵያን ሕይወት መጠበቅ ይመስላል ።

ስድስተኛ፡ መንግሥቱም በሀገሩ የሰጠው ሕግ የታመኑዋስ ሁኖ ሕዝቡን እንዲያስተዳድር ነው።በታመነ ሰው አደራ ይቀመጥበታል፡ እኛም የኢትዮጵያ ልጆች የታመንን ስንሆን የጐረቤታችን ሕዝብ ለገንዘቡና ለሕይወቱ አደራውን ቢአስጠጋብን ጥቅማችንና ክብራችን እንዲበዛ ይሆናል።የኢትዮጵያ ፈላሾች ምንም ሥራ ሳይሠሩ የኢትዮጵያን ወሰን አልፈው ወደ ውጭ አገር ይፈሳሉ ። በኢትዮጵያ ውሥጥ የበቀሉ ዛፎችና ማሮች ምንም ሥራ ሳይሠሩ እሳት ይበላቸዋል። በዚህም ነገር እንኳ እኛ መንገድ አላፊዎችም ያዝናሉ ።

ሰባተኛ፡ የኢትዮጵያ መሬት ላትክልትና ለእህል እጅግ የተመቸ ነው። የኢትዮጵያ ሰው እህል በመሸጥ ፈንታ እህል ከውጭ አገር መግዛቱ ያስደንቃል ። አሁን በ፲፱፻፳ ዓመት ግርማዊ ንጉሥ ከቸርነታቸው ብዛት የተነሣ የሕዝቡን ረኃብ አይተው ከውጭ አገር እህል አስመጥተው በርካሽ ዋጋ ለሕዝቡ ዓደሉት ። አንድ ጆንያ እህል እስከ ፳ብር ዋጋ ሁኖ ነበረ ። በዚያው ጊዜ አንድ ጆንያ ማሽላ በ፯ ብር ገዛን ። ይህንም ግርማዊ ንጉሥ ያደረጉልነን ወረታ የበላው ሆዳችን አይረሳውም፡ነገር ግን ከውጭ አገር መጥፎ እኛ የገዛነውን እህል ያህል ከኢትዮጵያ ወደውጭ ቢሸጥ የበለጠ ጥቅም ነበረን።

ስምንተኛ ፡ ግርማዊ ንጉሥ አገራቸውን ኢትዮጵያንም ድሩ ፥ ፍሬአማ፡ሕዝቡን ሠላማና፥ ለማድረግ አሳባቸው በታላቅ ኃይል የተነሣ ነውና እኛም ስለኢትዮጵያ ቀቅም በሚሆነው ጉዳይ ሁሉ እንድናገለግላቸው የመልከሙ ሐሳባቸው ምስክር እንድንሆን ተስፋችን የታመነ ነው ።

ዘጠነኛ ፡ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ለኢትዮጵያ ጥቅም የሠሩላት ለዘላለም የማይረሳ ሥራታ ከዚህ ቀጥሎ የሚነገረው ነው።

መጀመሪ፤ ኢትዮጵያ በፍሪካ ውሥጥ ነፃነት ያላት የተከበረች መንግሥት እንድትሆን ወደ መንግሥታቱ ማኅበር ማግባታቸው ነው ።

ሁለተኛ ፤ የተማሪ ቤት አዋጅ ማውጣትና የተማሪቤትም በገንዘባቸውና በስማቸው አቁመው ሁለት መቶ የሚሆኑ ሕፃናት የትምህርት ወተት እየተጋቱ ያድጉባታል ።

ሦስተኛ፥ ወደውጭ አገርም ለትምህርት ብዙ ሕፃናት ልከዋል ።

አራተኛ ፤ ለሕዝቡ ጤና ሆፒታል በገንዘባቸው ሠርተዋል

አምስተኛ ፤ የቀድሞውን አስተዳደር ከባዱን ሸክም ለማቅለል የሕዝቡን አተዳደርና የዳኝነትንም አኳኋን አሻሽለዋል

ስድስተኛ ፤ በኢትዮጵያ ከንዱ አገር ወደሁለተኛው አገር የሚሔድ መንገድ ለመሥራት አስተዋይዎች ዓይኖቻቸው ይመለከታሉ ።

ሰባተኛ፤ሌሎችንም ከዚህ የሚበልጡትን የኢትዮጵያን ጥቅሞች እንዲሠሩልን ዕድሜና ጤና እናለምንላቸዋለን ።

እኛም የፍቅርና ያገልግሎት ማኅበረተኞች ለጥቅም አስኘጂው ለግርማዊ ንጉሣችን አገራችንን ለማገልገል አሳባችን ተነሣሥቶ ጥቂት ልጆች ለማነጽና ሰው ለማድረግ የነፃነትን ምልክት አሳይተናል። ሰው ማለት አእምሮው ከእንስሳ የተሻለ፤ ባልንጀራውን ወደደኅንነት የሚመራ፤ ለተሻለ ኑሮ የሚጥር ሲሆን፤ አገሩን መሥራት፤ ባልንጀራውን የሚአንጽ የሚችል ሲሆን ነው የሰው ኑሮ እንደዚህ ካልሆነ ከእንስሳ ብልጫ የለውም። ዝንጀሮ በገር ውሥጥ እንደ ባላገር ሀኖ ይኖራል። ነገር ግን እየጫረ ላፉ እንደመብላቱ ይዘራ በሆን ከበርቱ ባላገር ይባል ነበረ ሰነፍ ልጅ እናቱን ራበኝ ራበኝ የሚላት ቢሆን የእናትነትዋን ያላትን ቃጉርሰዋኝ ኢትዮጵያም ለኛ ሳንሠራ እስከዛሬ ትመግበናለች። ኢትዮጵያ የጌትነት አገራችን ሳንሠራ የምንበላበት አገር ለዘላለም ትኑር ልንእኛም በጌትነታችን ሳንመክ ለሥራ የምንጥር እንድሆን አምላክችን ይርዳን ።

ለግርማዊት ንግሥታችን ዕድሜና ጤና ሰጥቶ ዘመናቸውን ሁሉ የሰላም ዘመን ያድርግላቸው።

ለግርማዊ ንጉሥ የኢትዮጵያን ጥቅም በማሰናዳት ከዚህ ቀድሞ ከነበሩት ነገሥታት ዕድል አግኝተው ኢትዮጵያን ለመሥራት ጥቅሞችን ሁሉ መመሥረትና መሥራቱም ዕድሉ ለግርማዊ ንጉሥ ይሁን።

ከሽዩ በኋላ የማኅበሩ አለቃ ክቡር አዛዥ ወርቅነህ
የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

በዛሬ ቀን ተማሪ ቤታችንን ለመጐብኘት በቸርነትዎ ስለ መጡልን ወሰን የሌለው ደስታዬን እየገለጽሁ በራሴና በማኅበሩ ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ይህም የዛሬው አመጣጥዎ ጥሪያችንን ከማክበር ይልቅ ወደፊት በሥራችን እንድንጠነክርና እንድንተጋ አገራችንን ኢትዮጵያንም በበርታትና በፍቅር እንድናገለግል በጣም ይረዳናል።

የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር በርትቶ ይህንን ሥራ መሥራቱ ላገር ጥቅም ከመሆኑ በላይ ለውጪ አገር ሰዎችም ደስ እንዲያሰኛቸውና ይህንንም አድራጎት ከመልክም ፍሬ እንደሚቆጥሩት ስለ ተረዳው ነው ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ይህን ቤትና ቦታ ስለ ሰጡን በጣም እናመሰግናለን ። ግርማዊ ንጉሥም በየጊዜው ስለሚረዱን እርዳታ ወሰን የሌለው ምስጋና እናመሰግናለን ። እነሆ እነዚህ ልጆቻችን ከሁን በፊት ያደረጉት አገልግሎታቸውና ሥራቸው ምንም እንኳ ብዙ ጥቅም ባይኖረው ለወደፊት ብዙ ፍሬ ይገኝባቸዋል ስንል ትልቅ ተስፋ አለን ።

ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ይስጥልን ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ።

ይህንን ተናግረው ከጨረሱ በኋላ ተጨበጨበ።ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ወደቤታቸው ተመለሱ ።

የከተማ ወሬ

ሁለት ባለ ስድስት መንኰራኩር አቶሞቢል በሙሴ ለብላንክ የሬኖ ፋብሪካ ዋና መሐንዲስ ተመርተው ከካይሮ ተነሥተው የካቲት ፳፫ ቀን ከማታው በአንድ ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ ገቡ። እነዚህ አቶሞቢሎች ከካይሮ ተነሥተው የመጡበት በሮሴር ፤ በኢሻንጉል አገር በነጆና በአምቦ በኩል ተራራና ወንዙን፤አለትና ዱሩን፤ እየጣሱ በአዲስ አበባ በስተምዕራብ በኩል ዘለቁ ። ከካይሮ ተነሥቶ ወደ አዲስ አበባ ባልተጠረገ መንገድ አቶሞቢል መዝለቁም ያልተደረገ ነገር ነበርና በዚህ መንገድ መጀመሪያ መዝለቃቸው ነው ።

የሬኖ አቶሞቢል ወኪል ሙሴ ሀርዲ ደግሞ ባለ ስድስት እግር አቶሞቢል ይዘው ወደ ቢሎ (ከነቀምቴ ወዲህ) ፹ ኪሎሜትር ተቀብለዋቸው ሶስቱ አቶሞቢሎች ከቢሎ ተነሥተው በአዲስ ዓለም አድርገው ወደ አዲስ አበባ ገቡ። በዚህ በመጨረሻ መንገዳቸውም በአንድ ሰዓት ፴፭ ኪሎሜትር ያህል ሔዱ።

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የመጣ ሬድዮ የየካቲት ፳፭ ቀን የዕለት ወሬ

ፍራንስ፤ ሙሴ ብሯንድ ነገ ማታ ወደ ጄኔብ ለመሔድ ይነሣሉ።

ከጀርመን ሌጋሲዮን የመጣ ሬዲዮ የየካቲት ፳፯ ቀን የዕለት ወሬ

ለንደን፤ጋንዲ የተባለ ሰው ሂንዱዎችና ሲዮናሊስቶች ሙሉ ተከታዮቹን ከውጭ አገር የጨርቅ ረገድ እንዳይገባ እንዲቃወሙ በማድረጉና ተከታዮቹ ለፖሊስ ባለመታዘዛቸው በካልኩታ ታሠረ

በባቡር የገቡ የውጭ አገር ሰዎች ።

ካፒቴን ጉዬማንና ምኒስቴር ቃምቦ ጅቡቲ ወርደው ተመለሱ።
ሙሴ ደማሊንግሮ ከባለቤታቸው ጋራ እናሲ ወርደው ተመለሱ።
ከቡዳፔስት፤ ሐሚል ቤላ ።
ከካይሮ፤ ሙሴ ኒኮላ ሙስከሪስ ።
ከማርሴይ፤ ሙሴ ሮክስ ።
ከፓሪ፤ ሙሴ ካንደ ራይም ከባለቤታቸው ጋራ ።
ከግሪክ፤ ሙሴ ስፀስታሊኖ ።

ስለ መንገድ መሻሻል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አገራቸው በእውቀትም በሥራም በኩል እንድትሠለጥንና እንድትሰፋ የሚፈልጉ ስለሆነ ይልቁንም ደግሞ ሥራ የሚለማው መንገድ ሲበጅ እንደሆነ ተረድተውት ከጐሬ እስከ ገምቤላ ድረስ ያለው መንገድ እንዲሠራ ፈቅደው ውሉን ለሙሴ ዜርቦስና ለሙሴ ዳናሊስ ሰጧቸው።

ሙሴ ዳናሊስ ለዚህ ለመንገድ ማኅበር ለማቆም ወደእንግሊዝ አገር ተሻግረው ነበርና በብልሀነታቸው ይኸን ያሰቡ

ትን ማኅበር አቁመው ተመልሰው መጡ ማለትን ሰማን ። ይህ መንገድ መሠራቱ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ዋና ጥቅሚ ነው ከዚህ ቀደም በጐሬናበጋምቤላ መካከል ዕቃ የሚያመላልሱ ብዙ ከብቶች በየመቱ ያልቁ ነበር ከከብቱ ይልቅ ደግሞ የሚያሳዝነው ተሸካሚው ሰው እንደዚሁ ብዙ ያልቅ ነበረ ። አሁን ግን ይህ መንገድ ከተሠራ በየመቱ ያልቅ የነበረው ሰውና ከብት ይድንልናል ሰውም ወደእርሻው ተመልሶ ጠቀሜታውን ያገኛል ከብቱም ሌላ ሥራ ይሠራል ። መንገዱም ጐሬ ከደረሰ በኋላ ሸቀጥ ለማመላለስ አያስቸግርምና በጐሬ አውራጃ ያሉ ቡን ተክዮች ቡናቸውን ወደውጪ አገር ለመስደድ ሁውከት ስለ ማያገኙቸው አትክልታቸውን እያሰፉ አገራቸውን ያለማሉ።ላገራችን ጥቅሚ ይህ ነው የኢትዮጵያ ቡን በኢትዮጵያ ብቻ ነው እንጂ በሌላ አገር አይገኝምና ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

ሐኪም አምባር ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

የዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ከረጅ	፲፫ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጅ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጸር	፩ ከረጅ	፻ ፺፬ ብር
ባለሰይጣን		፻፳፱ ብር
፡ ፡ ባለ ድመት ።		፻፵፩ ብር
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፳ ብር
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፺ ብር
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፵፯ ብር
" " ጃፖን		፻፳፱ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፫ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፹
ባአንድ ብር	፳ ሊሬ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ከ፵ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል መዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማኅደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል "ሣረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ነው።



COGNAC S. & E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬዱባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዎርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያስናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ነከላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የዶማት የጨጉሩ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጎርስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ ጎብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤትነው።

ጉድይር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
5me ANNEÉ №11

ሐሙስ መጋቢት ፭ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 14 MARS 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ሐሙስ በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊተኑ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፸፬ ገጽ ተከታይ ።

ሁለተኛ ክፍል ።

ምዕራፍ ፩፡

፲፱፡ የሀብት አፈራር ።

የኤኮኖሚያ (ቁጥር) ፖለቲክ አፈራር በትንሽ ነገር ወይም በቀላል መንገድ ጥቅምዋን ማግኘትና መከተል ነው።ማለት ለሰው የሚያስፈልገው ታላቅ ደስታና ጥቅም በትንሽ ድካም ለማግኘት አሁን የተሻለች መንገድ የትኛይቱ እንደሆነች እንመርምር።ከሁሉ በፊት የሚጠቅሙ የትኞች እንደሆኑ የማይጠቅሙ የትኛ ነገሮች እንደሆኑ እንወስናለን።የሰውን ፍላጎት በሙሉና በተስማማ ልክነት ደስ ለማሰኘት ነው ብለናል።ስለዚህ የማይጠቅሙና በሥራ የማይውሉ ነገሮች ከሰው ፍለጋ በላይ ማፍራት አያስፈልግም።ምሳሌ አናጢ ብዙ ጠረጴዞች ጥቂቶች ወንበሮች ከማድረግ ይልቅ ብዙ ወንበሮች ጥቂቶች ጠረጴዞች ቢሠራ ይሻላል ። ከዚህ በላይ ንግድ ሁሉ ለምትፈለግበት ቀን የተዘጋጀች ልትሆን ይገባታል ብዛትዋም የሚበልጥ ሁኖ ሊገኝ አያስፈልግም ።

ስለዚህ የማፍራትን ዋና መሠረቱ ሥራ ፣ ማተሪያ (የፍጥነት ክበት ወይም መሬት) አለ ማበላሸትና አለ ማጥፋት ነው ሥራ የማያሰቅቅ (ፔኖስ) ነውና እስከሚቻለን ድረስ ማሳነሱ ይበልጣል።በዚሁ አሳብ ሄሬን የሚባል እንዲህ ይወስናል የኤኮኖሚያ ፖለቲክ የሰውን ፍለጋ ደስ ለማሰኘት የጣር እውቀት ነች» ከዚሁ በግልጥ ለማስረዳት ተስፋ እምናደርገው ለሥራችን በትንሽ ድካምና ባጭር ጊዜ ብዙ ትርፍ ለማግኘት ነው።

እንደተለመደው የሰው ንግግር ሀብት ይፈጠራል ይባላል። እኛ ግን ለዚሁ አሳብ ጥቅም የሚፈጠር ማለት ነው ብለን እ

ም ወይም ምናምን ሁኖ ጠፍቶ ሊቀር አይችልም ተብለዋል። ባፍጥረት ቢሆንም አንድ ነገር ሊፈጠር፤ ወይም አንድ ነገር ሊጠፋ አይችልም ተብሎ ሕጉና ባህሉ ቁመዋል። ፍራንቼስኮ ባኮኔ እንዳለው « ሰው ምንም ሌላ ሊያደርግ አይችልም ለፍጥረት አካላቶች እየደበለቀና እየገጣጠመ፤ ወይም እየለያየና እየበታተነ፤ ማንቀሳቀሳቸው በቀቀር ፍጥረቲቱን በነሱ በላይ እየሠራች የቀረውን ትፈጽመዋለች ። እኛም ሰው ሌላ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል እናያለን፤ ማለት ማሰብ፤ መግፋት፤ ማንሣት፤ መጨቈን፤ማምጣት፤መውሰድ፤ ማመላለስ፤ የመኪና ሥራዎችም መጠንቀቅና መለዋወጥ እነዚህን የሚመስሉ ሁሉ በተቀር።አንዱ ተከራከሬ እንበል ግን እንዴት ትናንት በቅርቡ ማርኮኒ የሚባል ኢጣልያዊ አለ ስልክ ቴሌፎን ሲፈጥር፤ ልብስ ሲያረጅ ተበጣጥሶ ሲጣል፤ እንጨት በእሳት ሲቃጠል አመድ ሲሆን፤ ሰው ሲሞት አካላቱ አፈር ሲሆን፤ወኃ በደረቅ መሬት በፈሰሰው መሬት ጠጥቶት በክፍት ማሰሮ ብተወው ፀሐይ ጠጥቶት ሲያልቅና ሲጨረስ በዓይኔ እያየሁት ፣ የሚፈጠርና የሚያልቅ የለም ይላል በሚል አሳብ ምናልባት የሚታለል ሰው ቢኖር ከዚሁ ለማስረዳቱ መጀመሪያ ሰፈሩ አይደለም።ሁለተኛ ጊዜና ቦታ አይሰጠንምና በፍጥረት ዑቀት በፊሎሶፍያ ለኛ ያለቀ የሚመስለን ፍጥረት ሁሉ እንዴት ብሎ እየተለዋወጠ እንደሚመላለስ ተመልክቶና መርምሮ እንዲረዳው እናስበዋለን።

ስለዚህ ማፍራት ማለት ሀብትን መፍጠር አይደለም።ግን ጥቅምን መፍጠር ነው እንጂ።ምሳሌ መርከብ ነጂ የሚጭነው የከራይ እቃም ፍሬ ነው።ስለምን በተፈጠረበት አገር ሊረባ የማይችል የነበረውን ሀብት ለጥቅም ለውጦታልና።(አስረጅ) በፔሩ የሚባል አገር ጉዋኖ የሚባል ብዙ ድልብ የወፎች ኩስ ባለም ከሉ ሁሉ ፍግ የበለጠ ከዚያ ምንም አይሠሩበትምና አይ

ብዙ ጥቅም ይሆናል፤ እንዲሁም ብዙ እህል ያለበት አገር (ማለት ለአገሩ ሕዝብ በቅቶ የሚተርፍ) ወደውጭ አገር ልከው ካልሸጡት ምንም ጥቅም ሳይሆን ይቀራል ።

እንግዲያስ ማፍራት ማለት የፍጥረቶች ሀብትን ገንዘብህ ማድረግና ለሰው ፍለጋ ደስ የሚያሰኝ ለመሆን የተሰጠ ማድረግ ነው (ምሳሌ) ወርቅ ፤ እንዴት አድርጎ ከመሬት እንዲወጣ፤ ኋላ እንዴት አድርጎ ገንዘብ እንደሚሠራና እንደሚቆም ነው። ስለዚህ ለሁሉ በየነፍስ ወከፍ ሥራዎች እኒህን ሦስት ነገሮች ተገጣጥመውና ተደባልቀው እናገኛቸዋለን። ፍጥረት ሥራ ካፒታል (ገንዘብ) ለምሳሌ በእርሻ ሥራ የገበሬን ሥራ ለሱ መሬት የምትሰጠውን የፍጥረት ሥራ እናገኛለን ማለት መሬት ፤ ውኃ ፤ ሙቀት ፤ እሱንም የመሰሉ ሁሉ የሰውን ሥራ፤ መዝራት፤ መጠበቅ፤ ማጨድ፤ መውቃት እሱንም የሚመስሉ ሥራዎች ሁሉ በመጨረሻ የካፒታልን (ገንዘብ) የሚውለውን ማለት ዘር፤ ፍግ ፤ እንስሳ ፤ ማረሻ ፤ መቆፈሪያ ዶማ ፤ እሱንም የመሰሉ ሁሉ።

ሚካኤል ተሰማ ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ስለ ዓቢይ ጾም መግባት ።

ይህ በዚህ ሰሙን የተጀመረው ጾም ዓቢይ ጾም ይባላል። ይህም ጾም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ለማዳን ሰው በሆነ ጊዜ በተወለደ በሠላሳ ዓመቱ ከአንድ በረኃ ገብቶ የጾመው ጾም መታሰቢያ ነው። ስሙም ዓቢይ ጾም፤ጾመ አርብዓ፤ ሁዳዴ ተብሎ በሦስት ስም ይጠራል። ዓቢይ ጾም መባሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ስለሆነ ነው።ጾመ አርብዓም መባሉ ጌታችን የጾመው አርብዓ ቀን ስለሆነ ነው። ሁዳዴም መባሉ በንጉሥ አገር የሚኖር ሰው የንጉሥን ሁዳድ መሆደድ እንዲገባው እንዲሁ በክርስቶስ ያመነ ክርስቲያን እንዲጾመው የተገባ ስለ ሆነ ነው ።ይህንንም ከጥንት ሲያያዝ እንደ መጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓመት በዓመቱ ሳያስታጕል እየጾመ በፋሲካ (በትንሣኤ) ይገድፋል ።

ጾሙን አስፈጽሞ ለብርሃነ ትንሣኤው እንዲያደርሰን ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ያቀርባል ።

ከካይሮ እስከ አዲስ አበባ በአቶሞቢል ስለ መጡት ስለ ሬኖ የአቶሞቢል ፋብሪካ መልክተኞች ።

ከካይሮ ተነሥተው አዲስ አበባ ድረስ በአቶሞቢል ስለ መጡ ሰዎች ባ፲ኛ ቍጥር ጋዜጣችን አመልክተን ነበር። አሁንም ያመጣጣቸውን ነገር በሰፊው እናመለክታለን ።

ሙሴ ሊብላን ማዳም ሊብላንና ካፒቴን ብሩኖ ከካይሮ ተነሥተው የሱዳንን ግዛት ጨርሰው በቤኒሻንጉልና በወለጋ አድርገው በአቶሞቢል አዲስ አበባ ለመድረስ እጅግ አድርጎ መጨከናቸውና መበርታታቸው ያስደንቃል ። የመንገዱ ርዝመት፤ የወንዙ ብዛት፤ የዳገቱ፤ የቁልቁለቱ ማስፈራት ጕድጓዳውን መሬቱን ሁሉ እየደለደሉ፤ ታላላቅ ደንጊያ እየፈነቀሉ ባንዳንድ ወገን አቶሞቢሉን የሚያሰምጥ ማጥ በገጠማቸው ጊዜ ማጡን በድንጋይ እየደለደሉ በዚያ ላይ መሔድ፤ የአቶሞቢሉን መንኰራኵር ጭቃ በዋጠው ጊዜ ወይም እጅግ ቀጥ ያለ ዳገት በሆነ ጊዜ መቶ ክንድ የሚሆን የተገመደ ሽቦ ከአቶሞቢሉ ግምባር ላይ ተርትረው በዛፍ ላይ ሽቦውን አሥረው ሲጠመጥሙት በገዛ ኃይሉ ጭቃውንና ዳገቱን መውጣት ይህ የሚያስደንቅ ነው ።

ሙሴ ሊብላንና ካፒቴን ብሩኖ ስማቸው የታወቀ ታላላቅ ሰዎች ናቸው ። ራሳቸውን ስለ መጠበቅና አሳባቸውን ለመፈጸም አቶሞቢላቸውን በትጋትና በጥንቃቄ ይጠብቁ ነበር ። ሱሪያቸውን አሳጥረው እጀ ጠባባቸውንም እንደዚሁ አሳጥረው ሰውነታቸው በአቧራና በሐሩር ተጕሳቍሎ መልካቸው ተለውጦ ነበረ ። ስለ ሆነም የመንገዱ ያለማስሔድ ችግር ባገኛቸው ጊዜ ችግሩን እናልፋለን የማለት ደስታ እያበረታቸው መሰልቸትና መበሳጨት የለባቸውም ነበር ።

የፈረንሳዊ ሚንስትር ሙሴ ደሬፌም እነዚህ ሰዎች በኢትዮጵያ ግዛት ላይ አልፈው መምጣታቸውን አስቀድመው ለግርማዊ ንጉሥ አስታውቀው ነበርና ። ግርማዊ ንጉሥ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ለብላቴን ጌታ ኅሩይ ትእዛዝ ሰጥተው ሙሴ ሊብላንና ጓደኞቻቸው በሚያልፉበትና በሚደርሱበት ስፍራ ሁሉ አለችግር እንዲያልፉ ለየአገር ገዢው ትእዛዝ አልፎ ነበርና በየደረሱበት ሕዝቡ እየረዳቸው በደኅና አለፉ ።

የሚቀበሏቸውም ሰዎች ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አቶ ሙማና በአዲስ አበባ የሬኖ ወኪል የሆኑት ሙሴ ሐርዲ ስንቅና ቤንዚን ይዘውላቸው ሔዱ ።

ከካይሮ በተነሡ በ፴፭ ቀን የካቲት ፲፱ ቀን ከማታው በሁለት ሰዓት አዲስ አበባ ገቡ ።

አዲስ ዓለምም ድረስ ሊቀበሏቸው የወረዱ የፈረንሳዊ ሚኒስትርና ብዙኅ የፈረንሳዊ ተወላጆችና ጥገኞች ነበሩ ። ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቤትም እንኳን ደኅና መጣችሁ ብሎ የደስታ ሰላምታ ለማቅረብ አቶ ተስፋዬ ተገኝ ከንጉሥ ታዞ ወርዶ ነበረ።

ሐሙስ የካቲት ፳፫ ቀን ከግርማዊ ንጉሥ ለመገናኘት ቀጠሮ ተደርጎላቸው ነበረና በሌላው አገር ሁሉ እንደሚደረግላቸው ክብር ይደረግላቸው ዘንድ የግርማዊ ንጉሥ ፈቃድ ስለሆነ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን ይዘዋቸው ወደ ንጉሥ ግቢ ሲያመጧቸው አሥር ሰዓት ከሩብ ሲሆን ሔዱ የዓጀቡም አካሔድ እንደዚህ ነበረ ።

መጀመሪያ የማዘጋጃ ቤት ፈረሰኞች ፤ ቀጥሎ የፈረንሳዊ ሌጋሲዮን በፈረስ የተቀመጡ ዘበኞች፤ ከዚያ ቀጥሎ ብላቴን ጌታ ኅሩይና ሙሴ ደሬፌ የፈረንሳዊ ሚኒስትር በመንግሥት አቶሞቢል ፤ ከዚያ ቀጥለው ሙሴ ሊብላን፤ ባለቤታቸውና ካፒቴን ብሩኖ ከካይሮ በመጡት በሁለት አቶሞቢል ተቀምጠው ከዚያም የማዘጋጃ ቤት የፈረስ ዘበኞች ሆነው አጀቡ ደምቆ አምሮ ነበር ።

ከግርማዊ ንጉሥ ግቢም በደረሱ ጊዜ የግርማዊ የክብር ዘበኞች አምረውና ተሰልፈው ቆዩ። ግርማዊ ንጉሥም በዙፋናቸው ከመኳንንቶቻቸውና ከሚኒስትሮቻቸው ጋራ ሆነው ተቀበሏቸው

ጥቂትም ተነጋግረው አቶሞቢሎቹን ለማየት ወጥተው ካዩ በኋላ ተመልሰው ገብተው ሽምፓኝ ተከፈተና ግርማዊ ንጉሥ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

ከወዳጃችን ከፈረንሳዊ መንግሥት ሕዝብ ውሥጥ አንዱ በዓለም ስመ ጥሩ የሆነው የሬኖ ማኅበር አቶሞቢል ጥራቱንና ኃይሉን ለማስመስከር በተራራማዋ አገራችን ላይ ለአቶሞቢል የሚያስቸግሩን ወንዞችና በረኃዎች ሁሉ አልፎ ዛሬ በዋናው ከተማችን ላይ መልክተኞቹንና እነዚህን ኃይለኞች የሆኑትን አቶሞቢሎች በማየታችንና በመቀበላችን ደስ ብሎናል።

ይኸንኑም ደስታችንን ለትጉሁ ሬኖና ለማኅበሩ፣ ለሠራተኞቹም እንድታስታውቁልን እንለምናችኋለን ብለው በጨረሱ ጊዜ የሬኖ ፋብሪክ መልክተኛ ሙሴ ለብላን ቀጥለው የተጻፉትን ቃሎች ተናገሩ። ግርማዊ ንጉሥ ፈቃድዎ ሁኖ አሁን ለተናገሯቸው መልካም ቃሎችና በተደረገልን አቀባበል ሰውነታችን በደስታ ተነክቷልና ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ብዙዎች ለማለፍ አተችሉም ያሉንን አገር አሁን አልፈን እዚህ መድረሳችንና የተደረገልንን መልካም አቀባበል ሙሴ ሬኖ በሰሙ ጊዜ አጥብቆ ደስ የሚአሰኛቸው ይሆናል። ግርማዊ ንጉሥም እንዳደርስላቸው ያዘዙኝን ቃል በደስታ አደርሳለሁ። ጽዋዬንም ስለ ኢትዮጵያ ልማትና ስፋት እየተመኘሁ አነሣለሁ ብለው ጨረሱ ።

ቅዳሚት የካቲት ፴ ቀን ባ፲ሰዓት ባዲስ አበባ ያሉት የሬኖ አቶሞቢል ፋብሪክ እንደራሴ ሙሴ ሐርዲ ስለ ሙሴ ለብላን ክብር የኢትዮጵያን መኳንንቶችና የውጭ አገርን ሰዎች ለሻይ ጋብዘው ነበርና ከሻይ በኋላየሬኖ መልእክተኞች ሙሴ ለብላን የአቶሞቢሉን ዳገት አወጣጥ መጀመሻ በአቶሞቢሉ ግምባር ያለውን ሽቦ ተርትረው ከታላቅ ዛፍ ላይ አብተው አቶሞቢሉ በገዛ ኃይሉ ሽቦውን ሲጠቀልለው ወደላይ እንደምን እንደሚያወጣው አሳዩ።

ሁለተኛ ደግሞ ዛፍ በሌለበት አገር ዓቀበት ለመውጣት እንደምን እንዲደረግ ለማሳየት የአቶሞቢሉን አንዱን ትርፍ መንኰራኵር ከመሬት ቀብረው ከዚያ ላይ ሽቦውን አብተው አቶሞቢሉ በኃይሉ እየጠቀለለ ዓቀበቱን ሲወጣ አሳዩ። ከዚያም የነበረ ሰው ሁሉ የብልሐቱን መልካምነት አደነቀ። ከግብዣውም የነበሩ ታላላቅ ሰዎች ቀጥለው የተጻፉት ናቸው።

ልዑል ራስ ካሣ፡ልጅ አስፋ ወሰን፡ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ፣ በጅሮንድ ዘለቀ፡ነጋድራስ መኰንን፡ብላቴን ጌታ ኅሩይ፣ ደጃዝማች ኃብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር፣ ደጃዝማች ከሣ ስብሐት፣ ሌሎችም ሰዎች ነበሩ ።

በዚህ ቀን ማታ በሁለት ሰዓት ስለ ሬኖ አቶሞቢል በደኅና መድረስ ግርማዊ ንጉሥ የፈረንሳዊን ሚኒስትርና እነዚህ የሬኖ አቶሞቢል መልክተኞች ሌሎችንም ትልልቅ ፈረንሳዎችና የኢትዮጵያም መኳንንቶች ለራት ጋብዘው ነበርና ሁሉም በደስታ ተጋብዘው ግርማዊ ንጉሥን እያመሰገኑ ወደቤታቸው ተመለሱ ።

ተጠንቅቆ ስለመኖር ።

የዓለም መንግሥታት ሰላም በዓለም እንዲነግሥ መንግሥታትም እርስ በራሳቸው በስምምነት እንዲኖሩ ያስባሉ ። ለዚሁም ብዙ ሥራ ይሠራሉ።ግን ይህ ሁሉ ሲሆን መሥራትና ተሰናድቶ (ተደራጅቶ) መኖር እንደሚያስፈልጋቸው አውቀው በመሣሪ ሆነ በገንዘብ በሠራዊትም እንዲበረቱ ዕለት ዕለት ትጋታቸውን አልተዉም።ይህነንም የዓለም ሰላም ጸር እንዳልሆነ መጠርጠራቸውን ያስረዳናል ። የዓለም መንግሥታት ሰላምን መፈለጋቸው ብዙ መልካም ነው።በዝንጋታ አለመኖራቸውም የበለጠ ነው ። የሚፈልጉት የሰላም ኑሮ እግዚአብሔር ቢፈቅደው ይፈጸማል። ባይሆንም ተሰናድቶና ተደራጅቶ የሚመጣውን መጠበቅ የተገባ ነው ። በሁሉም ነገር የሚጐዳ ዝንጉ ሁኖ በቸልታ መኖር ነው ። በመጽሐፍትም ብንመለከት ተሰናድተው የሚመጣውን ነገር ነቅተው ያልጠበቁ ትጉሃን ያልሆኑ ሰዎች የሚደርስባቸው አደጋ ጽኑ መሆኑን እንረዳዋለን ። ስለዚህ ተሰናድቶና ተደራጅቶ መኖር ያስፈልገናል። ስንዱና ትጉ መሆን በሰላም ጊዜም ቢሆን ባደጋ ጊዜ ምስጋና አያሳጣም ።

ዝሆንና ዓይነ ሥውሮች ።

ስድስት ዓይነ ሥውሮች ሰዎች የዝሆንን አኳኋን ለመመርመር ይናፍቁ ነበርና ዝሆን ወደ አለበት ሒደው እያንዳንዱ እንደ ሐሳባቸው መረመሩ ።

አንደኛው መጥቶ ጭኑን ዳበሰና እግዚኦ ዝሆን ልክ ግምብን ይመስላል ብሎ አደነቀ ።

ሁለተኛውም መጣና የዝሆኑን ጥርስ ዳብሶ ይህ ድቡልቡልና የሾለ ነገር ምን ዓይነት ነው ለእኔ እንደሚመስለኝ ግን ዝሆን ልክ ጦር ይመስላል አለ ።

ሶስተኛውም ወደ ዝሆኑ ቀርቦ ኩምቢያውን ዳሰበና እየተገረመ ዝሆኑ ልክ ዘንዶ ይመስላል አለ።

አራተኛውም በእጁ የዝሆኑን እግር ዳበሰና ዝሆን ዛፍ ይመስላል አለ ።

አምስተኛውም ደግሞ የዝሆኑን ጆሮ ዳበሰና ዝሆን ሰፌድ እንደሚመስል ዕውር ሳይቀር ሊያውቅ ይችላል አለ ።

ስድስተኛውም ቀስ ብሎ የዝሆንን ጅራት ዳበሰና ዝሆን ልክ ገመድ እንደሚመስል ታዘብኩ አለ ።

ከዚህ በኋላ ዓይነ ሥውሮቹ በየሐሳባቸው እንደ መሰላቸው እንዲህ ነው አይደለም እየተባባሉ እርስ በርሳቸው ተከራከሩ እያንዳንዳቸውም የየራሳቸው እውነት መስሎ ታያቸው። ስለ ሆነ ግን ሁሉም ተሳስተው ነበር ይባላል ።

እኛም ሁላችን አገራችን የምንጠቀምበትን መንገድ በሕሊናችን እየዳበስን የሚመስለንን እየጻፍን በየጊዜው እንገልጻለን ። ነገር ግን እንደሚመስለን ተናገርን እንጂ ገና ልኩን አላገኘነውምና እንደ ዓይነ ሥውሮቹ ሳንሆን ልኩን እስከናገኘው ድረስ እንደገና እንዳብስ ።

ስለ ውሀ ቦንባ ።

ከእንጦጦ በቦንባ የሚመጣው ውሀ ቦንባው ውሀ መስጠቱን ሲያሳንስ የታወከበትን ምክንያት ለመፈለግ በየጊዜው ሲቆፈርና ሲታደስ ብዙም ሰው ሲደክምበት እናያለን ፤ በየጊዜው የሚቆፈርበትም ምክንያቱ ከመሬት ውሥጥ እየተቀበረ አፈር እየበላው ይመስለኛል። ይልቁንም አልፎ አልፎ እመንገድ ላይ ያለውን ከብት እየረገጠ ያበላሸዋል ።

በየጊዜው ብዙ ሰው ከማልፋቱና ቦንባውም አለ ጊዜው እየተበላሸ ከሚታደስ ፩ጊዜ ቦምባው እስከሚቆምበት ስፍራ ድረስ ቦምባው የሚቀመጥበት ቦይ ባሻዋና በኖራ ግራና ቀኝ ተገምብቶ በላዩ እንደ ድልድይ ሥራ ጠፍጣፋና ለሥራ የማያጎድል ድንጋይ ቢረበረብበት ደግ ይመስለኛል። ምናልባት ቦምባው ውሀ መስጠቱን ቢያሳንስ ተረብርቦ የነበረው ድንጋይ በፍጥነት ያለ ድካም እየተነሣ ምክንያቱ ሊፈለግ ይቻላል ።

ይኸውም በቦምባ ጉድጓድ ላይ የተነጠፈው ድንጋይ ከቦታው እንዳይንቀሳቀስ ለባለሰፈሩ የፀና ማስታወቂያ የተደረገ እንደሆነ ይጠነቀቅበታል ። ይህ የሆነ እንደሆነ ቦምባውን አፈር አይበላውምና ብዙ ዓመት ይኖርና ብዙውን ሰው ከድካም ያሳርፍ ይምስለኛል ። ጌታቸው ቀንድቤ ።

ስለ መንገድ መሻሻል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አገራቸው በእውቀትም በሥራም በኩል እንድትሠለጥንና እንድትሰፋ የሚፈልጉ ስለሆነ ይልቁንም ደግሞ ሥራ የሚለማው መንገድ ሲበዛ እንደሆነ ተረድተውት ከጐሬ እስከ ገምቤላ ድረስ ያለው መንገድ እንዲሠራ ፈቅደው ውሉን ለሙሴ ዜርቦስና ለሙሴ ዳናሊስ ሰጧቸው።

ሙሴ ዳናሊስ ለዚህ ለመንገድ ማኅበር ለማቆም ወደ እንግሊዝ አገር ተሻግረው ነበርና በብልሀነታቸው ይኸን ያሰቡትን ማኅበር አቁመው ተመልሰው መጡ ማለትን ሰማን ። ይህ መንገድ መሠራቱ ላገራችን ለኢትዮጵያ ዋና ጥቅሚ ነው ከዚህ ቀደም በጐሬናበጋምቤላ መከከል እቃ የሚያመላልሱ ብዙ ከብቶች በየመቱ ያልቁ ነበር ከከብቱ ይልቅ ደግሞ የሚያሳዝነው ተሸካሚው ሰው እንደዚሁ ብዙ ያልቅ ነበረ ። አሁን ግን ይህ መንገድ ከተሠራ በየመቱ ያልቅ የነበረው ሰውና ከብት ይድንልናል ሰውም ወደአርሻው ተመልሶ ጠቀሜታውን ያገኛል ከብቱም ሌላ ሥራ ይሠራል ። መንገዱም ጐሬ ከደረሰ በኋላ ሸቀጥ ለማመላለስ አያስቸግርምና በጐሬ አውራጃ ያሉ ቡን ተካዮች ቡናቸውን ወደውጪ አገር ለመስደድ ሀውከት ስለማያገኛቸው አትክልታቸውን እያሰፉ አገራቸውን ያለማሉ። ላገራችን ጥቅሚ ይህ ነው የኢትዮጵያ ቡን በኢትዮጵያ ብቻ ነው እንጂ በሌላ አገር አይገኝምና ።

ማመልከቻ ።

ልጅ የወለዱ፣ሠርግ ያደረጉ፣ ሰው የሞተባቸው በጊዜው

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ መልከም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ ሰዎች ዳውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፣ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፣ እንጨት፣ወይም ማናቸውንም ዓይነት እቃ፣ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል ።

ሽልማት ።

የካቲት ፳፫ ቀን ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም የአገራቸውን ሕዝብ ደኅና አድርገው በማስተዳደራቸው መንግሥትን ደስ ስላሰኙ መንግሥት የሚገባቸውን ሽልማት ሸለማቸው ።

ብርሃንና ሰላም ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያምን እንኳን ደስ አለዎ ይላል ።

ሠርግ ።

የካቲት ፴ቀን ክቡር አቶ አብርሃ መንገሻ ክብርት ወይዘሮ ለድያን በተክሊል አገቡ ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር አቶ አብርሃ መንገሻና ለክብርት ወይዘሮ ልድያ እግዚአብሔር ትዳራቸውን እንዲባርክላቸው ይመኝላቸዋል ።

በባቡር የገቡ ሰዎች ።

ከሎንዶን ልጅ ጆርጅ ዓሩይ ።
ከግሪክ አገር ማሪ ሚላ ።
" " " ኤብሪዲክ ሚላ .
ከከርቱም ሙሴ ኢሽሚት የጀርመን ሰው ።

ከፈረንሳዊ ሊጋሲዮን የመጣ ራዲዮ ።

የመጋቢት ፣ ፩ ቀን የዕለት ወሬ ።

ሮማ፡ የዲፕሎማቲክ ሰዎች ወደ ቅዱስ ወንበር በቀረቡ ጊዜ ጳጳሱ ዕፁብ የሆነ ንግግር ተናገሩ ።

የመጋቢት ፫ ቀን የዕለት ወሬ ።

ፍራንስ፡ ሙሴ ቢሪያንድ ከጀኔብ ተመልሰው ገቡ ። ሲትሮኤን የተባለ ትልቅ የኦቶሞቢል ሥራ ቤት አርት ኤሚቴ በተባለ ሰፍሬ ጉባኤ አድርጎ ነበርና በጉባኤው ንግግር የሠራተኛ ደመወዝ ከፍ ማለቱ የሥራው ማሻሻል ምልክት ነውና የሚሸጥ እቃ ዋጋው ከፍ ሳይል ያሉት ሠራተኞች ዕጥፍ ደመወዝ ተቀብለው ሥራው ቢሻሻል ዕጥፍ ገቢ ይገኛል ብለው ተናገሩ ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበር።

የማህበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማህበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማህበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቀበኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

ሐኪም አምባር ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ሕሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፵ ብር
ያበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኩረጃ	፲፫ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኩረጃ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኩረጃ	፻፺፱ ብር
ባለሰይጣን		፻፳፱ ብር
: : ባለ ድመት ።		፻፵፩ ብር
: : ባለአህያ ።		፻፳ ብር
: : ባለሳቢ ግመል ።		፻፶ ብር
: : ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፵፯ ብር
" " ጃፓን		፻፳፱ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፫ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፹
ባንድ ብር	፳ ሊሬ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ከ፵ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቀርቀሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል መዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምበት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማጎደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆን በነዚሀ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጽ ሰየስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው። ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ, ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቀባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ ሕገር የባርባሬስ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ኒለፀ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሽክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳንባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨጎጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምልክት ። ባለወርቅ ብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላሰቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንክራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላሰቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋውግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤትነው።

ጉድይርን

GOODYEAR

2-28-14

አምስተኛ ዓመት ቍጥር ፲፪
5me ANNÉE , № 12

ሐሙስ መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 24 MARS 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ዘመናዊ ፅሕፈት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም ፡ የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፫ኛ ገጽ ተከታይ ።

፳) መሬት ወይም የፍጥረት ሀብት (ማተሪዬ) ምንድር።

ማፍረት ማለት በላቲን ቋንቋ ወደ ውጭ ማውጣት ማለት ነው።ይህች ትርጓሜ እርግጥ መሆንዋ ጥርጥር የለበትም። ማለት ሀብትን ለማግኘት የፈለግን እንደሆን ወደ መሬት፡ወይም ወደ ወንዝ፡ወይም ወደ ባሕር ሔደን ሀብትን የሚለውጡ ነገሮችን እናገኛለን ።

ከመሬት ስፋት፡ወይም ከመሬት ውስጥ፡ወይም ከወንዝ፡ ወይም ከኵሬ፡ ወይም ከባሕር የማይወጣ ፍሬ የለም ። የሚበልጠው ምግባችን ከመሬት እንደ እህልና የአትክልት ፍሬ፡ጐመንንም የመሰለ ሁሉ፡እንስሳና ወፎች፡ልብሳችን ጥጥ፡የተልባእግር፡ ጠጕር። ሚኔራል ሚታሊ ማለት የብረት ዘር ሁሉ (መዓድን) ከመሬት ይገኛሉ።የሚጠጡ ውኆችና ባሕሮችም መጀመርያ የጥቅም ምግባቻችን ናቸው።ከመጠጣችን በላይም ለምግባችን ልዩ ልዩ ዓሦችና ዘይት እሱንም የመሰሉ ብዙ ሌሎች ጥቅሞች ይሰጡናል። ከነዚሁ በተቀር ፤ ማለት የፍጥረት ሀብት ከሌላ ምንም ሀብት ሊፈጠር አይችልም ። ከፍጥረቶች ሀብት በላይም የመኪና ኃይል ለጉልበታችን ድካም አጋዥዎች ያስፈልጉናል። ማለት ማቴሪዬ የሚባለው ውኃና የሚዘለው ኃይል ተብሎ የሚጠራ ነው።

ባለፉ ዘመኖች ሰው አጋዥዎቹ እሱንም የሚመስሉ ወንድሞቹ ባሮች አድርጎ ማፍረት በተቀር ሌላ የተሻለ ነገር ለማግኘት አልበቃም ነበረ ። የዛሬ ሰው ግን ፍጥረቶችን አጋዦችና ተገዦዎች ለማድረግ ቻለ ። ማለት ፍጥረትን(መሬት) በዙርያዋ ያሉ ሁሉ ስጦታዎች ለማፍራት ታግዘናለች ። ለሀብት ተለውጠው ያልቆሙ እንደ የሞቶር ኃይል ነፋስ እየዘለለ ጠል ሙቀት ነምቡስቲቢል የሚባል የኤሌትሪክ ኃይል የመሰሉ ሁሉ።አስረጅ ነፋስ መርከብን ሲያስኬድ፡ ዘላይ ውኃ ወፍጮን ሲያዘዋውር፡ ከብቶች መሬትን ሲያርሱ፡ወይም አንድ ነገር ሠረገላን የመሰለ ሁሉ ሲጐትቱ፡ ጋዝ አውቶሞቢል (በግሪክ ቋንቋ በገዛ እጁ የሚነቃነቅ) ሲያስኬድ፡ኤሌትሪክ ማኪናን ሁሉ ሲያንቀሳቅስ፡ ጨለማን ሲያበራ፡ ብርድን ሲያሞቅ፡ ለሰው አጋዦችና ተጋጋዦች ይባላሉ።

ግን ኃይሎች ሁሉ ትክክል አይደሉም። የፀሐይ ሙቀትና ነፋስ እንዳያው በነፃ ይገኛሉ ። ማለት ይልቁን ከመለከትናቸው ጥቅሞች በለይ የፀሐይ ሙቀትና የባሕር ኃይል የጥቅም ሀብትን ለማድረግ የሠለጠኑ ብልሆች ሰዎች ተስፋቸውንና አሳባቸውን አስረግጠው ቈርጠዋል ። የከሰል ሙቀት ላቦት ወይም ጢስ ብዙ ጥቅም አለበት ። እንዲሁም ነጭ ከሰል ማለት የዘላይ ውኃ ኃይል ኤሌትሪክ ጥቅሙ ወሰንና ስፍር የሌለበት ሁኗል ። ማለት አንድ ጊዜ ሠርተው ከቆሙኋ ለብዙ ዘመን የሚቀመጥ ስለ ሆነ ነው።ኃይሉ ለብርሃንና ለመኪናዎች ሥራ ይሁን ለባቡርና ትራም ማስኬድ ሥራውን ሁሉ ፈጽሞ ቀጥ አድርጎ ይዘዋል።ወዮው ጉድ ሥልጣኔ ማለት ስንት ድንቅና ዕድል ነው።ብልሆቹ ውኃን ከየመንደሩ አግደው እየጠራቀሙ ስንት ሲጠቀሙበት ምስኪኗ ኢትዮጵያ ለራሷ በቅቶ ለሌላ አገር እንኳ አልፎ የሚተርፍ ሳትጥር የተፈጥሮ ጸጋ ባሕር ጣናን የሚያህል ዘላይ ውኃ ሳለላት በድህነትና ችግር፡ አለምኞት መኖርዋን እጅግ ደም ያስለቅሳል ። ይህ ያቈይልንና የጀመርነውን አሳብ ለመከተል እንመለስ።

ሚካኤል ተሰማ ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ስለ አዲስ አበባ ከተማ ቦታ ።

ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የአዲስ አበባን ቦታ ሲያደላድሉ በመኳንንቱና በመሳፍንቱ ስም እያከፈሉ ለብዙ ሠራዊት መኖሯ እንዲሆን ርስት አድርገው ሰጥተዋል ይባላል ። የቦታውንም ክፍል ከብዙ በጥቂቱ በአራቱ ሰፈርተኛ ስም ጽፌ ነገሬን አሳጥራለሁ ። ለምሳሌ የሠራተኛ ሰፈር ፤ የሥራቤት ሰፈር ፥ የአናጢ ሰፈር ፥ የዘበኛ ሰፈር ፥ ይባላል ፤ ይኸን የመሰለ ሁሉ እንደዚሁ በታውና ሰፈሩ በሥራው ክፍል ዓይነት ሲጠራ ይኖራል ። ደግሞ ጃንሆይ አፄ ምኒልክ በዘመናቸው ለነበሩ ሹማምንቶች በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ ለቦታ(ለመሳፈሯ) ፳ ጋሻ መሬት የሚያህል የመሩት አለ ፤ ፬ ጋሻ የሚሆንም የያዘ አለ ፥ ፫ ጋሻ የሚያህልም ተመርቶ የቈየ አለ ፤ ዳግማዊ ምኒልክም ይኸን ያህል ሰፊ ቦታ ለአንዳንድ ሻለቃ መስጠታቸው የተከታዮቹን ደጅ ጥናት የሠራዊቱን ብዛት ስላዩ ለብዙ ሕዝብና ለወታደር መኖሯ እንዲሆን አስፍተው አብዝተው ሰጡ ይባላል ። እውነትም ለአንድ መስፍን (መኰንን) ለአጥር ግቢ ብቻ ከሚበቃ በግምት ኩርማን ጋሻ ከሚሆን ቦታ በቀር በከተማ ውሥጥ አስፍቶ ለመያዝ አያስፈልግምና ከዚህ በላይ እንደተጻፈው የቦታው ስፋት ለብዙ ሕዝብ እንዲበቃና እንዲተርፍ መስጠታቸውን ያስረዳል። ግን ማናቸውም ሰፈር ቢሆን በየመኳንንቱ ስም ይጠራል እንጂ በተራው ሕዝብ ስም ሊጠራ አይቻልም። ይኸነን በምሳሌ አስረዳለሁ። እንዲህ ይባላልና የአቡነ ማቴዎስ ሰፈር ፥ የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ሰፈር ፥ የእራስ ዳርጌ ሰፈር ፥ የእራስ መኰንን ሰፈር ፥ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሰፈር ፥ እንደነዚህም ያሉ መሳፍንትና መኳንንት አሉ። ሁሉንም ስማቸውን በዝርዝር ለመጻፍ ብዙ ስፍራ እንዳይዝና ወረቀት እንዳይፈጅ ላንባቢም እንዳይሰለች ለምሳሌ ለማስረጃ ያህል እነዚህን ከላይ የተጻፉትን አምስቱን የሕዝብ አሳዳሪዎች ጽፌን የቀሩትን ትተናቸዋል ።

አሁን ዋናው ነገር ይህን ለመጻፍ ያሰሰበኝ ምክንያቱ ወደፊት ቀጥሎ የተጻፈው ነው። በአሁኑ ጊዜ ማዘጋጃ ቤት ለመንግሥቱ ጥቅም፤ ለሕዝቡ ሰላም እንዲሆን አስቦ በአዲስ አበባ ቦታ ያለው ሰው ሁሉ የሰፈሩን ሻለቃ ማኅተም እያመጣ በታውን ካርታ እንዲያስነሣ በመዝገብ እንዲያስገባ ትእዛዝ አደረገ። ነገር ግን ካርታ ሳያስነሣ ግብር ሳይገብር ርስቱ ነው ብሎ ለመሸጥ ለመለወጥ፤ መያዣም አድርጎ ገንዘብ ለመበደር እንዳይችል በአእምሮ ጋዜጣ በዓመተ ምሕረት ፲፱፻፲፰ ፥ በቍጥር ፻፳ ፫ኛ ዓመት ገልጾ አስታወቀ ። ስለዚህ ሕዝቡ ብዙ ዘመን የኖረበት ቦታውን ካርታ ለማስነሣት ቢፈቅድ አንዳንድ ሻለቆች ርስትነቱ የኛ ነው ተሳፋሪውም ሕዝብ ጢሰኞችን ነውና ካርታ ለማስነሣት የምስክርነት ወረቀት አንሰጠውም ብለው በዚህ ምክንያት ከየሰፈሩ ሻለቃ እየተካሰሰ በየሸንጎው ሥራ ፈቶ የሚጉላላው ሰው ልክ የሌለው ነው። የሕዝቡም ሥራ መፍታትና ክርክር ማንሣት በጣም ለመንግሥት ጉዳት ነው። ምናልባት ማዘጋጃ ቤት ለመኳንንቱ የሚገባቸውን ያህል ሰጥቶ ተከቦ ውጭ የተረፈውን ለሕዝቡ ርስት ቢያደርግለት የተሻለ ይሆን። ? አሁን ሻለቆች እንደዚሁ እንደተባለው በክበባቸው የሚወሰኑ ቢሆን ለልጆቻቸው ጉዳት የሚመጣ ይመስላቸው ይሆናል። እኔ እንደሚመስለኝ ግን ከብዙ ሐሳብ ዕረፍት ያገኛሉ ። ማለት ለአንድ ሰው የማይችለውን ከባድ ኪሎ ቢያሸክሙት ይደክማል ወይም ይወድቃል ። ሻለቆቹም በጊዜአቸው ለብዙ ሠራዊት መስፈሯ የተሰጠውን(የሚሆነውን) ቦታቸውን ለመያዝ ቢያስቡ ከመሬቱ ርኅቀት፤ከቦታው ስፋት፤ የተነሣ ሁሉን ለማከናወንና ሥራ ለማስያዝ የማይቻልነውና ምድረበዳ ይሆናል፤ሁኑዋልም ማለቱም ሕዝቡን በየጊዜው ከቦታው ለማስነሣት እያሳጉት አታክልት ለመትከል፤ውሐ ለማውጣት፤ ማለፊያ ቤት ለመሥራት አይጣጣርምና አታክልትና ውሐ ካሌለው እንደ ዱር መሆኑን ለማሳሰብ ነው ደግሞ በአዲስ አበባ ሰፊ ቦታ ያላቸው ሻለቆች በግምት ከ፷ አይበዙም ይመስለኛል ፤ ይበዛሉ የሚልም ቢኖር አያከራክርም መልካም ነው ፤ ነገር ግን ይህን ያህል ሰፊ ቦታ (መሬት) ይዘው በውሥጣቸው ለሚኖረው ሕዝብ ቦታ አንሰጠውም ለኛ ብቻ ይገባናል የሚሉ ከሆነ ፤ ድፍን የአዲስ አበባ ቦታ ለ፷ ሰዎች ብቻ መሆኑን ያሰስበናል ። እንደዚህም ከሆነ መንግሥት እንደ ገና ሌላ ከተማ ሠርቶ ለተራው ሕዝብ የከተማ ቦታ እንዲሰጥ ሊያስፈልገው ነው ። ካሁን ቀድሞ ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ እንደዚሁ ካርታ እንዳያስነሡ የሰፈራቸውን ሰዎች ከልክለዋቸው ይኖሩ ነበር ። በኋላ የሕዝብ ጉዳት የመንግሥት ጉዳት እንደሆነ ስለተረዱት ከጥር ግቢዬ በቀር በውጭ ያለው ሰፈርተኛ ርስትነቱ እንዲረጋ በታውን ካርታ ያስነሣ፤የዓመት ግብር ይገብር ብለው የምስክርነታቸውን ማኅተም ሰጥተዋቸው ካርታ አስነሡ ይባላል።

ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስም በውነት የሕዝብ አሳዳሪ፤ የመንግሥት እንባ ጠባቂ መሆናቸውን ይህ ያስረዳናል ። አሁንም የከተማ ቦታ መኳንንትና ሠራዊት፤ ባለጸጋና ድሀ አያሰኝም ሁለተኛ ዋና ከተማችን በአዲስ አበባ ስንኳን ኢትዮጵያዊ የሆነና እያሌ የውጭ አገር ሰዎች ቦታ ገዝተው፤ ርስት አድርገው፤ ካርታ አስነሥተው ይኖሩበታል ። ክቡራን የሆናችሁ መኳንንትና አለቆች የሕዝብ አስተዳዳሪዎች ናችሁና ከዚህ በላይ የተጻፈውን በልቡናችሁ መዝናችሁ ከወንድሞቻችሁ ጋራ ያለክርክር ያለጸብ በፍቅር አንድነት በኑሮ ስምምነት እንድትኖሩ ለምስሉ ምኞቴን በትሕትና አስታውቃለሁ። ልዑል እግዚአብሔር በብርሃን ለሚመሩን፤ በሰላም ለሚያኖሩን ለግርማዊት ዘውዲቱ ምኒልክና ለግርማዊ ተፈሪ መኰንን ረጅም ዕድሜ ይስጥልን።

በቀለ አበዬ

ስለ ሬኖ አቶሞቢል አክሒድ ።

መጋቢት ፲ ቀን በአሥር ሰዓት ተኩል በጉለሌ በራስ ኃይሉ ሆቴል ባለ ስድስት እግር ሬኖ አቶሞቢል አክሒዱን ለማሳየት ከዚያ እንደሚሞከር ማስታወቂያ ወጥቶ ነበርና በዚሁ ሰዓት ብዙ ሰው በአቶሞቢል እየሆነ ከራስ ኃይሉ ሆቴል ድረስ ተጓዘና ብዙ ሰው ተሰበሰበ። ግን ዝናብ ስለዘነበ ዝናቡ እስኪያበራ ድረስ መታየቱ ቈየ ዝናብ ካበራ በኋላ ከሜ

ጸው ከለ ዛፍ በነዱ ላይ አቶሞቢሉን አስጠግተው አንዱ ላይ ደግሞ በአቶሞቢሉ ላይ በተጐነጐነው የብረት ገመድ ከጫፉ ላይ አሠሩና አቶሞቢሉ ሲስበው ጊዜ ከ ሩ ተገነደሰ። ተመንግሎ ሲወድቅም ቢማየት ሰው ሁሉ እጅግ አድርጎ ኦደነቀ ። ከዚህ በኋላ አቶሞቢሉ ጐድጓዳ ወንዝ እንዴት እንደሚሻገር፥ ቍልቍለት እንዴት እደሚወርድ፥ ዳገትም እንዴት እንደሚወጣ ለማሳየት ወደ ወንዙ አወረዱትና አከሔዱን ለማየት ሕዝቡ ተከትሎት ሲሔድ ወንዙን ተሻግሮ ቍልቍለቱን ወርዶ ገደሉን ሲወጣ ብርቱውን ገደል ሲወጣ አካሔዱ እንዴት እንደሆነ ለማሳየት ከአቶሞቢሉ በስተፊት የተጐነጐነውን የብረት ገመድ ዘርግተው ጫፉ አንድ ዛፍ ሥር አሠሩትና ሞቶሩ ተነሥቶ ገመዱን ወደ ራሱ እየጠመጠመ በገዛ ራሱ ተጐትቶ ገደሉን ሲወጣው ጊዜ ከዚያ የነበረ ሰው ሁሉ እጅግ አደነቀና አጨበጨበለት። በዚሁ ትንሽ ማሳየታቸው እንኳ የሰዎቹ ብርታትና ልፋት ብዙ ነበረ። ግን የማበዕን አገር ጨርሰው በሱዳን ዘልቀው በስተ ኢትዮጵያ ምዕራብ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ሲገቡ የሠሩት ሥራ ቢገመት ሠራተኞቹ ብርታታቸውና ጉብዝናቸው የሚገርም ነው።

ይህ አቶሞቢል ሥራው ሲሠራ ሙሴ ላብላና ክቢቴን ብሩኔቶ አቶሞቢሉን እንደሚገባ ለማስኬድ ሲታገሉ ብዙ አቶሞቢል ነጂዎች ተሰብስበው ይመለከቱ ነበር። ይህን በማየታቸውም በከተማ ውሥጥ በለዘበ መንገድ በሚብለጨለጭ አቶሞቢል መኳንንትና ወይዛዝርትን ከንዱ ቤት ወዳንዱ ቤት ማድረስና ማመላለስ ሳይሆን እንዲህ በመሰለ ብርቱ አቶሞቢል ለመንግሥት ሥራ በሜዳም በገደልም ቢሆን በብርታት ሥራችንን እየፈጸምን ብንመሰገን በንት መልካም ነው። መንግሥትም እንዲህ የመሰሰሉ ወይም የበለጡ አቶሞቢሎች አስመጥቶ ሥራ ይሰጠናል እኛም አቶሞቢሉን ካገኘን እንዲህ አድርጎ ማስኬድ አያቅተንም ብለው አስበው ይሆናል ።

መከራንና ችግርን ያለመደ ጌትነትን አይለምድም።

ይኸውም መከራን ያለመደ ጌትነትን አይለምድም ያልኩት ነገር ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ። በኤውሮፓ አገር እውቀትና ሥራት፥ትጋትና መሥራት ሠልጥነው፥አምረውና ተከናውነው የሚኖሩትን ሀገሮችና ሕዝቦች በሀልና የአኗኗር ሁናቴያቸውን ታሪክና ዝና ስንሰማ በጣም ያስደንቃል። ይኸውም ቀጥሎ እንደሚነገረው ነው፥ በኤውሮፓ የመኳንንቶችና የመሳፍንቶች፥የደሃ ወገኖችና የነጋዴዎች፥የሐብታሞችና የባለጠጎች ልጆች ሁሉ በሕፃንነታቸው ጀምረው እስከ ፳ ዓመት ድረስ በትምህርት ቤት በትምህርትና በሐሳብ፥ በችግርና በጉዳት እየተጐሳቈሉ በጽሕፈትና በሥራ ትምሕርታቸውንና ሐሳባቸውን ታክናወኑ በኋላ የምስክር ሰርቲፊካቸውን ተቀብለው ግማሾቹም የወታደርነት፥ ግማሾቹም የእጅ ሥራ፥ ግማሾቹም የግብርናንና የአትክልት፥ ግማሾቹም የንግድ፥ ግማሾቹም መሃንዲስነት፥ግማሾቹም ሐኪምነት፥እንዲሁ ሁሉም የሚያስፈልግ የሚያስፈጋቸውን ሥራ እየተማሩ ከከናወኑና ማወቃቸውም ከተመሰከረላቸው በኋላ በእውቀታቸውና በሥራቸው እየተመረጡ በሥራቸውም ላይ በትጋታቸው ምስክር እየሆናቸው በዚህ አለም እስከሉ ድረስ በሕፃንነታቸው ተጐድተው በተማሩት ትምህርታቸው ተወደውና ተከብረው ለትዳራቸውና ለጥቅማቸው እየሠሩ ገዥዎቻቸውንና መንግሥታቸውን ሀገራቸውን አክብረውና ፈርተው ሲኖሩና ለውድ ሀገራቸውና ለመንግሥታቸውም ሲያገለግሉ ይኖራሉ ይላሉ ።

በኢትዮጵያ ሀገራችን ውሥጥ ባለፉት ዘመኖች ሁናቴ ስንሰማ አንዳንድ የታደሉ የደሃ ልጆች በብዙን ድካም ይሾማሉ እንጂ የመሳፍንት ልጆችና የባለጸጋ ልጆች ካልሆኑ ሹመትን አያገኙም። ግን በሁን ጊዜ ከጥቂት ዘመናት ወዲህ በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ብርታትና ማስተዋል ብዙ የደሀ ልጆች በእውቀታቸውና በምግባራቸው ደግሞም ሀገርና መንግሥታቸውን አክባሪና አፍቃሪ በመሆናቸው በሀገራቸውና በመንግሥቶቻቸው ዘንድ ሲመረጡና በየሥራው ላይ ቁመው የውቀታቸውን ፍሬ እየሠሩ ሲአሳዩ ስላየሁና ካለፉት ዘመኖች ጋራ ሳመዛዝነው ብዙን ልዩነት አገኘሁበት ። ይህም የሥልጣኔና የገር ፍቅር ምልክት ነው ።

በቀለ ዘለቀ ።

ንግድ በኢትዮጵያ።

በኢትዮጵያ ንግድ እየሰፋና እየሠለጠነ ይሔዳል። ንግድ ቢሰፋና ቢሠለጥንም የመንግሥት ክብር፥ የሕዝብም ብልጽግና ነው። ይህንም በማወቃቸው የንግድ ሚኒስቴሩ ክቡር ነጋድራስ መኰንንና የጉምሩክ ዲሬክተር ክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔር እየተማከሩ ከገር ውሥጥ እየመጡ ለሚነግዱ ነጋዴዎችና በከተማ ለሚኖሩ ነጋዴዎች የተሻለ ደንብ አውጥተውላቸው ያገራችን ሕዝብ በንግድ እንዲሠለጥን ችግሩን እንዲያቃልሉት ይጣጣራሉ ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በየመንገዱና በየከተማው የሚያገኘውን ችግር ካቀለሉለት የንግድን ጣም ያውቅና እየነገደ ይተርፋል ። ለራሱ ይጠቅማል ከትርፉ ለመንግሥት ቢያከፈልም አይጐዳም ። ነጋዴ እንደ ልቡ እንዲነግድ የሚጠብቀውና የሚመለከተውም ባስፈለገው ጊዜ በቶሎ እንዲደርስለት በየማእዘኑ ደኅና መንገድ መዘርጋት ያስፈልጋል። ይህንም መንግሥታችን አውቆ ጀምሮታልና በቶሎ እንዲከናወን ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓል አከባበር ።

ገብረ መንፈስ ቅዱስ ማለት የመንፈስ ቅዱስ አገልጋይ ማለት ነው፥ ብዙ ሰውም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በማለት ፈንታ አቦ ብሎ ይጠሩዋቸዋል። እኒህ ጻድቅ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በአዲስ አበባ በደቡብ ምሥራቅ በኩል በሰፊ ሜዳ ላይ ጉብ ባለው ዝቋላ በሚባል ትልቅ ተራራ ላይ ብዙ ጊዜ በሕታዊ ሁነው ሲኖሩ በመጋቢት አምስት ቀን አረፉ ። በዓላቸውንም ለማክበር ከሩቅ ድረስ እየመጣ በዝቋላ የሚሰበሰበው ሕዝብ ቍጥሩ መሳፍርት የለውም። ይህም የዝቋላ ተራራ ከእግሩ አንሥቶ እስከ ጫፍ በእግር የሶስት ሰዓት መንገድ ይሆናል። ከአናቱም ላይ ከቤተ ክርስቲያኑ ሥር ትልቅ የኩሬ ውሀ አለበት፥ ይህም ውሀ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የጸለዩበት ነው ይባላልና ሕዝብ ሁሉ ይጠመቅበታል ። ተራራው ግን ከ

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በፊት በረሱ የነበረ ይመስላል።ይህም ይታወቅ ዘንድ አቡነ ገብረ መ ፈስ ቅዱስን በገድላቸው ከአንበሳና ከነብር፥ከሌላም ብዙ አውሬ ጋራ ኖሩ ይላቸዋል ። ይህነንም በዓል ለማክበር መጋቢት ፭ቀን ግርማዊት ንግሥተነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በአዲስ አበባ ወደአለው ያቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ሒደው በዓሉን አክብረው ተመለሱ።

ስለ ዝናም

ዘንድሮ በአገራችን በጣም ድርቅ ሆኖ ነበረ።ግን በእግዚአብሔር ቸርነት መጋቢት ፯ቀን ፲ ሰዓት ሲሆን መጠነኛ ዝናም ዘነበ።በየመንገዱ ያስቸግር የነበረ አቧራውን ጸጥ አደረገው። አየሩም ከደርቅ ወደ እርጥበት ተለውጦ ደስ የሚያሰኝ ሁኗል።

በኢትዮጵያ በስልክ ቤት በኩል የመጣ የገር ውስጥ ወሬ ።

እንኮበር፥ መጋቢት ፯ቀን አንኮበርና፡ ደብረ ብርሃን ፣ ሰላ ድንጋይ ፣ ደህና አድርጎ ዘንቧል ።

በወሎ፥ ሳዘት ለገሎሬና ለገሂዳ፥ ለገምቦ፡ ደሴም ከወረይሉም፥ ግዛት ውጭውን እስከ ነደድ ድረስ ዘንቧል ፣ ከረም አጥግቦ ዘንቧል ፣ መርጦ ከፊያ ነው ።

በጐጃምና፥ በወለጋ፥ መጋቢት ፯ቀን ቶኬና፥ጨልያ፥ትቤ፥ አርጆ ፣ ቢሎና ለቀምት፥ ገተማ፥ደህና አድርጎ አጥግቦ ዘንቧል ።

ከአባይ፥ ወዲህ ግን ደበረት፥ ከፊያ ነው። ጐጃም፥ በሙሉ አጥግቦ ዘንቧል ።

በጌምድር፡መጋቢት ፯ቀን ደብረ ዘይት፡ደብረ ታቦር መስን ብቻውንም ዘንቧል፡ጎንደርና ጭልጋ ስሜን ዛሬ አጥግቦ ዘንቧል

ሰላሌ ፣ መጋቢት ፯ ቀን ደብረ ሊባኖስና ፣ ፍቼ በከተማውም ዙሪያ ሁሉ ዘንቧል ።

በወለጋና በከፋ፥መጋቢት ፯ቀን አዴጆበ፡ሮጌ ዘንቧል፤ሊሙ ጃን ጆሮ፡ጅማ ጉማ አላጠገበም እንጂ ዘንቧል። ከፋ አጥግቦ ዘንቧል።

አንኮበር መጋቢት ፰ና ፱ ቀን ደሴ በከተማው ዳርዳር ማይጨውና መቀሌ ዘንቧል ።

ወለጋና ከፋ መጋቢት ፱ ቀን ጅማ ጉማ ከፋ ሁርማ አይጆቦ አጥግቦ ዘንቧል ። ሊሙ ፣ የሞቦ፥ ጐሬ፥ ቡሬ፥ሰዮ ፥ኖኖ፥ ጭቱ ፣ አዲስ ዓለም ከፊያ ነው ።

አሩሲና ባሌ፥ መጋቢት ፱ ቀን አድዓ ወረዳ እስከ አዋሽ ድረስ አላጠገበም እንጂ ዘንቧል ፣ አሩሲ አውራጃ ፣ በሙሉ አጥግቦ ዘንቧል ፣ አሁንም አለቀቀም ይዘንባል ። በባሌ አውራጃም ፣ አጥግቧል ፣ አሁንም አላቀቀ ይዘንባል ።

ወላሞ ፣ መጋቢት ፱ ፲ ቀን ማረቆ ፣ ስልጢ ፣ ከምባታ ኩሎ ፣ ወላሞ ሲዳሞ ፣ አጥግቦ ዘንቧል ።

በወለጋና በጐጃም ፣ መጋቢት ፲ ፣ ቀን መታልያ ፣ ጀልዱ አጥግቦ ዘንቧል።ግንደ በረት አላጠገበም እንጂ አልፎ አልፎ ዘንቧል ። ጐጃም አምቦና ቶኬ ፣ ጨልያና ትቤ፥ ጌምቦ፥ አጥግቦ ዘንቧል። ቤሎና አርምጆ፥ አልፎ አልፎ አጥግቦ ዘንቧል ። ለቀምት በሙሉ አጥግቦ ዘንቧል

ደግሞ በወላሞ፥ መጋቢት ፲ቀን ሥልጢ፥ ከምባታ፥ ወላሞ፥ ሲዳሞ፥ ገሙ፥ ዘንቧል ።

ደግሞ በበጌምድር፥ መጋቢት ፲ቀን ከደብረ ዘይት እስከ ጭልጋ፥ አጥግቦ ዘንቧል ።

ደግሞ በአንኮበር፥ መጋቢት ፲፩ቀን ግድምና፥ ይፍራታ፥ ደሴ፥ መርጦ፥ ከረም፥ ማይጨው፥ ደህና አድርጎ ዘንቧል ።

የውጭ አገር ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ መሬት ሲገቡ የይለፍ ወረቀትና ፓስፖርታቸው አጠረፍ ካለው ከኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስል ሳያስፈርሙ አከተማ ገብተው እንዳይቀመጡ አዋጅ ስለተደረገ ያለፈቃድ እንዳዋጁ ቃል ሳያስፈርሙ ቀርተው በባቡር መጥተው የተያዙ።

አሊ ኑር የሚባል ሱማሌ ፣ ሰይድ አሊ የሚባል አረብ፥ አህመድ በደኒ የሚባል አረብ ፣ ሞሀመድ የሚባል አረብ ። አሱማን የሚባል አረብ ።

እነዚህ አምስት ሰዎች አላይ የተጻፉት የይለፍ ወረቀትና ፓስፖርታቸውን እንደደምቡ ከኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስል ሳያስፈርሙ በባቡር ተደብቀው ስለመጡ እንደ እሥር ሆነው በዘበኛ የባቡሩን መሳፈሪያ ማዘጋጃ ቤት ከፍሎ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ድረስ በመጋቢት ፲፩ ቀን በባቡር ተሳፍረው ሄዱ።

ከውጭ አገር በባቡር የገቡ ሰዎች ።

ከኦትሪሽ ሙሴ አይግዝነር ከነባለቤታቸው ።

ከኤሊሳክንድሬ ሙሴ ጆክ፡ሙሴ ኮነታ ባሲሊ፥ ሙሴ ሳል ባቶ፡ደግሞ ሙሴ ኮትሮ ።

ከአስትራሊ ሙሴ በርቶን ።

ከሀምቡርግ ሙሴ ጉስታብ ከነባለቤታቸው ።

ከአቴን ሙሴ ክሪስቶ ክርዳሉ ኝስና ሙሴ አሪስቲድ ።

ከጀርመን ሊጋሲዮን የመጣ ሬድዮ የመጋቢት ፯ቀን የዕለት ወሬ

ለንደን ፣ የዮርክ ዱክ ሳጭር ጊዜ በርሊን በመጐብኘቱ ጋዜጦች ይ ፈመራሉ ።

ሰፊያ፥ ማሪትስ የተባለ ወንዝ ጉርፉ ክልክ ስላለፈ ፊልፐፔል የተባለ አገር ውኃ ሞላና አሥራ አምስት ቤቶች ፈረሱ። ያገሩ ሰዎችም በቅርብ ያቸው ወዳለ ከፍተኛ ቦታ ሸሽተዋል ።

ስለ መንገድ መሻሻል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አገራቸው በእውቀትም በሥራም በኩል እንድትሠለጥንና እንድትሰፋ የሚፈልጉ ስለሆነ ይልቁንም ደግሞ ሥራ የሚለማው መንገድ ሲበዛ እንደሆነ ተረድተውት ከጐሬ እስከ ጋምቤላ ድረስ ያለው መንገድ እንዲሠራ ፈቅደው ውሉን ለሙሴ ዜርቦና ለሙሴ ዳናሊስ ሰጧቸው ።

ሙሴ ዳናሊስ ለዚህ ለመንገድ ማኅበር ለማቆም ወደእንግሊዝ አገር ተሸግረው ነበርና በብልሀነታቸው ይኸን ያሰቡትን ማኅበር አቁመው ተመልሰው መጡ ማለትን ሰማን ። ይህ መንገድ መሠራቱ ላገራችን ለኢትዮጵያ ዋና ጥቅሚ ነው ከዚህ ቀደም በጐሬና በጋምቤላ መከከል እቃ የሚያመላልሱ ብዙ ከብቶች በየመቱ ያልቁ ነበር ከከብቱ ይልቅ ደግሞ የሚያሳዝነው ተሸካሚው ሰው እንደዚሁ ብዙ ያልቅ ነበረ ። አሁን ግን ይህ መንገድ ከተሠራ ብየመቱ ያልቅ የነበረው ሰውና ከብት ይድንልናል ሰውም ወደእርሻው ተመልሶ ጠቀሜታውን ያገኛል ከብቱም ሌላ ሥራ ይሠራል ። መንገዱም ጐሬ ከደረሰ በኋላ

ሸቀጥ ለማመላለስ እያስቸገርምና በጐሬ አውራጃ ያሉ ቡን ተካዮች ቡናቸውን ወደውጪ አገር ለመስደድ ህውከት ስለ ማያገኛቸው አትክልታቸውን እያሰሩ አገራቸውን ያለማሉ።ላገራችን ጥቅሟ ይህ ነው የኢትዮጵያ ቡን በኢትዮጵያ ብቻ ነው እንጂ በሌላ አገር አይገኝምና ።

ማስታወቂያ ።

የአዲስ አበባ ከተማ መዘጋጃ ቤት ።

የመኪና ግብር ከሁን ቀደም በወር አራት መሐለቅ የነበረው ከመጋቢት ወር ጀምሮ ባንድ መኪና በየወሩ ስድስት ፮ መሐለቅ እንዲከፈልበት ደምብ ሆኖአልና ስለዚህ ይህነን የተቆረጠውን ግብር ሠራተኞች በጠየቋችሁ ጊዜ አንከፍልም በማለት ሠራተኛ ያጕላላ ሰው አሥር አሥር ብር አደብ ይከፍላል ። ይህም ደምብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ይጸናል ።

መጋቢት ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓመተ ምሕረት ።

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ መልከም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ ሰዎች ዳውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፡ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፡ እንጨት፡ወይም ማናቸውንም ዓይነት እቃ፡ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል ።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበር።

የማህበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማህበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማህበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፡ የርሻ፡ የፋብሪካ፡የደን፡ የማዕድን ሥራ፡ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅበኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እና ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ሟረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው። ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊያ በቦስቶን በማድራስ በአደንና ጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አሉው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚሁ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል

ባርባሬሶ

ኮኛክ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪክ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪክ ነው።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷንት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በኮፓሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በኮፓሱሉ ላይ የለለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ኒለፀ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪክ ይገኛሉ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራጋ ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል። የልብ። የደረት። የጉበት። የኩላሊት። የዐይማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት። ባለወረቀት ባለምኒልክ። ባለወርቅ ቨርሴ ሎሲዮን።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድዬር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም በፍሬ አያድጠውም በድንጋዩም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከሬ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድዬር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉድዬር ግዙ

GOODYEAR

Z-ZB-14

አምስተኛ ዓመት ቍጥር ፲፭
5me ANNÉE, № 15

ሐሙስ መጋቢት [illegible] ዓ·ም።
JEUDI 28 MARS 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውን የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numéro 2 piastres

የ፹፱ ገጽ ተከታይ ።

፳፱ ሥራ ።

አንድ የማይሠራ ሰው በዙሪያው ሁሉ ፍርያም መሬት ከበት ሳላም በራብ በሞተ ። በገዛ እጃቸው የሚበስሉ የበረኽ ፍሬዎችና የዱር እንስሶች ቢፈልግም መልቀምና ማደን ያስገድደዋል ። ጥሩ ምግብና መልክም ልብስ የተመቸ ስፍራና የጠዳ ቤት የፈለገ እንደሆነ ብዙ ሥራ ያወጣል ። የአንድ ሕዝብ በሀብት አድገት ከሥራዋ ትጋትና ችሎትዋ ነው እንጂ የሚገዛ ከፍጥረት ሀብት እንዳይደለ የአሜሪካን ሀንዶች የሚባሉ የጥንት ባላባቶች ምሳሌን በፊት ሰጥተናል ።

ስለዚህ ሰውን ከእንደዚህ ያለ ሥልጣኔ ያደረሰው ሥራ ነው እንጂ ሌላ አይደለም ። ሰውን በቀኝ እጁ ዓለምን ለውጦታል እንደተባለ ። እውነተኛ የሰው ኃይል እውቀት ናት፤ የታናናሾች ፍጥረቶች ማለት የጕንዳኖች እንኳ ከሰው የተሻለ ቢሆን ሰውን ጭራሹን ለማጥፋት፣ ወይም ባርያቸውን ለማድረግ በቻሉ ነበር ። እንዲሁ ባይሆን ከሰው ይልቅ በሬን ባከበርን ነበር ፤ ማለት የአንዱ በሬ ኃይል ከሰው ኃይል ዓሥር ጊዜ ይበልጣልና ።

ሀብትን ለማፍራት ሥራ የግድ የሚያስፈልግ ነው ። አሁን እኛ የሰውን ሥራ ብቻ ነው የምንናገረው ያለን ። እሱ (ማለት ሥራ) ጥቅሙን ለማፍራት ሰው የሚፈጽመው ትግል ነው። ስለዚህ የኤኮኖሚያ ሥራ ሁሉ ጊዜ የሚያደክም ይሆናል ። ምሳሌ አንድ ጀልባ ቀዛፊ ከአንድ ወንዝ ወደ ሌላ ወንዝ ሰዎችን የሚያሻግር የኤኮኖሚያ ሥራ ይፈጽማልና ፤ የድካም ሥራ ይሆንበታል ። አንድ ማለፊያ ጕረምሳ ግን ለጨዋታው ወይም ጂናስቲክ (መንቀሳቀስና አካላት መቅጣት) ጀልባ የሚቀዝፍ ግን የድካም ሥራ አይገኘውም ሥራ የሱ- ሥራ የሚባል ፤ መሀንድስ፣ [illegible] ንገሥት አዋቂ፣ አስተማሪ፣ ሐኪም፣ እሱንም የሚመስሉ ሁሉ፤ ፪ኛ ሥራ የሚባል [illegible] ጠራጊ፣ አናጢ፣ ገምቢ፣ እሱንም የሚመስሉ ሁሉ ናቸው። ደግሞ ሥራ በሚያሠራና በሚሠራ ይከፈላል። የሚያሠራ ማለት እንደ ዋ[illegible] ወይም ዲሬክቴር የሚሠራ ማለት ሠራተኛው፤ ማለት ሥራውን የሚፈጽም ነው። በመጨረሻ ሥራ ሠሪ ወይም ተሠሪ ሊሆን ይችላል። ምሳሌ ኤዲሶን የሚባል አሜሪካዊ ኤሌትሪክ ፎኖግራ[illegible] (ዘማሪ) ሲኒማ ቶግራፍ በግሪክ ቋንቋ የሚንቀሳቀስ ጽሬት ያወ[illegible]

፴፫ ካፒታል (ዋና ገንዘብ)።

ካፒታል ማለት ለሚሰጣ ፍሬ ማገዣ ልትሆን ከ[illegible] ሀብት ተጠራቅማ (ማለት ትቈጥብ) የቀረች ሀብት [illegible] ረጅ እርሻ ሌላ ነገር አይደለም ከሊጡ የቀረ ለኋለኛ[illegible] ብኩያ ሊሆን የተቀዋጣ ነው እንጂ። ስለዚህ ካፒታሉ በ[illegible] ነው የተወለደ የሚባል ንግግር እርግጥ ነው። ግን እ[illegible] ፊት የተፈራ ሀብት መሆኑን አንርሳው ፤ እኛ ብዙ [illegible] ዓይነት ካፒታል አሉን ፤ ፩ኛ የቆመ ካፒታል [illegible] የ[illegible] ራት ሥራን የሚፈጽም ምሳሌ እየመላለሱ ብዙ [illegible] የሚያ[illegible] ፈሩ ማኪናዎች ። ፪ኛ የሚዛወር ካፒታል ግን ማፍራቱ በአንድ ጊዜ የሚያልቅ ። ምሳሌ የፍጥረት ሀብት እንደ ከሰል፣ የኤሌትሪክ ኃይል፣ ዘይት፣ የመኪና ቅባት ፤ ቀለም እሱንም የመሰሉ ሁሉ ። ፫ኛ የደመወዝ ዋና ገንዘብ ምሳሌ ዋንኛው ፤ ወይም አለቃው ለሚያፈራ ሠራተኞች አስቀድሞ የሚሰጣቸው ብር ። ፬ኛ የቆመ የመሣሪያ ዋና ገንዘብ ምሳሌ መቈፈሪያ፣ መዶሻ፣ ማረሻ፣ እሱንም የመሰሉ ሁሉ ። ፭ኛ ሌሎች ካፒታሎች ደግሞ ለጌታቸው ጥቅምን የሚሰጡ ስለሆኑ እንዲሁ ዋና ገንዘብ ተብለው ይጠራሉ ። ምሳሌ ቤት፣ ቀለድ፣ የ[illegible] ውድስ፣ ወይም የጌጠኛ ገንዘብ፣ እነዚህ ሁሉ ለጌታቸው ጥቅ-

ስለዚህ ብዙ ሀብትን ለማፍራት መሬትና ሥራ ብቻ አይበቃም ። ሦስተኛ ገንዘብ ያስፈልጋል እንጂ ከሁሉ በፊት መሣሪያና ሠራተኛ ለማቆም ዋና ገንዘብ ያስፈልጋል፤ ማለት መሬት ታርሶ ተዘርቶ፤ እህሉ በቅሎ፤በስሎ፤ ታጭዶ፤ተወቅቶ፤ እስከገበ ያልተሠራ የፍጥረት ሀብት በኢንዱስሪ ገብቶ ተሠርቶ። ማለት አውቶመቢል በገዛ እጁ የሚንቀሳቀስ ወይም ልብስ ወይም የቤት ዕቃ ዓይነት ሁሉ እንደኔ ስሀን ሁኖ ሲበቃ ተሸጦ ብር እስኪገኝ ድረስ ፤ ለሠራተኞች ለሕይወታቸው ማቆሚያ ምግብና ልብስ ቤትም ያስፈልጋቸዋልና ። በማናቸውም ነገር ሀብትን ለማቆም አለ ዋና ገንዘብ አይሆንም ፤ ማለት ለመሥራትና ገቢ እስኪገኝ ድረስ ለመቈየት (ገንዘብ) የግድ የሚያስፈልግ ነው ። የትኞቹ መሣሪያዎች ዋና ገንዘቦች በፊት ከተገኘው ሀብት ለኋላ ማስገኛ ሊሆኑ ተቈጥበው የቈዩ ናቸው አለዚያ አለ ገንዘብ ሰውን በራብና ችግር ባለቀ ምሳሌ እንዳየነ እህል ዘር የመሰለ ሁሉ ።

ግን የፊተኛው ገንዘብ ከየት እንደተሰበሰበ ማለት እንዴት ብሎ እንደተጠራቀመ፤ ወይም በየትኛው መንገድ እንደመጣ ለመናገሩ ቀላል ነገር አይደለም ማለት በመጀመርያ የጥንት ሰዎችን በሰልባጅ ኑሮ ሲኖሩ እህልና ፍሬን አመጣጥ ተርጕሞ ለማስረዳቱ እጅግ ጭንቅና ረቂቅ ነው ። የፊተኛው በላቲን ቋንቋ መጣ ተብሎ የተጠራ (ገንዘብ) እንደ መቈፈርያና ማደኛ የመሰሉ በጣም ቀላሎች የሆኑ መሣርያዎች ነበሩ እንዲሁ ቀስ ቀስ እያሉ ብዙ ገንዘብ በብዙ ሺ ዘመናት ተሰብስበው ገናም እየበረቱና እያደጉ ይሔዳሉ ። የአሁኑ ዘመናችን የሥጣኔ ጊዜ ብዙ ዋና ገንዘብ በይኖር ፤ በምችት ለመቀጥ ማለት ለምግባችንና ለልብሳችን ፤ ለሰፈራችንና ለቤት ዕቃዎቻችን በትንሽ ጣርና መሥዋዕት ለማግኘት ባልቻልንም ነበር ።

ሚከኤል ተሰማ ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

የክቡር ቄስ ትእዛዝ ።

አንተና ያንተ ሥራ ሐሳብህን ለምታደርገው ነገር ብቻ ወስነው ። ደግሞም በተቻለህ መጠን ከፍ ወዳለው ማዕረግ ለመድረስ ጣር እንጂ ከቶ ሐሳብህን ከመሐከል አታስቀረው ። ሥራህ [illegible] ክበረና እውነተኛ እንዲሆን ተጠንቀቅ ። በሥራህ ው[illegible]መንፈስህ የተፀመደ ይሁን፤ መንፈስህ የሌለበት ሥራ የ[illegible] ነውና በሕይወትህ ሁሉ ይከፋሃል ነገር ግን ምንም ቢከፋህ ከፋኝ ብለህ ሥራህን አትተው ። ከፍተኛው ሥራህ ይዋረጻልና ። የሥራህን ዋጋ የምታሳይበት ጊዜ ሲደርስ በጠከረው ስፍራህ ላይ ትቆማለህ፤ ሰውነትህንም ደምብ መፈጸምን አስለምድ ። በዚሁ በሥራህም ቢሆን በወገኖችህም በመላው ዓለምም ቢሆን ክብር ታገኝበታለህና ። የታዘዝከውንም ሥራ ያለማዛነፍ ፈጽም ። ሌላም ከፍ ያለ ሥራ መቻልህን ግለጽ ።

ዋና የሥልጣኔ መቀዳደም ሐሳብ እንደ አንድ ያትክልት ቦታ ይመስላል ። አትክልት መሬቱ ጥሩ የሆነ እንደሆነ መልክም ይሆናል የሥራህን ጊዜ ከፈጸምህ በኋላ የዕረፍትህን ጊዜ በከንቱ አታሳልፈው፤ ደግ ነገርና ለወገኖችህ ነጻነት። ለሥልጣኔ ማስቢያ አድርገው እንጂ ። እውቀትን ለማግኘት በተቻለህ መጠን ጣር ።ነገር ግን እንጀራህን ለማግኘት የምትፈልገውን እውቀት በመላው ለማግኘት በተቻለህ መጠን ጣር ሁሉ ጊዜ የዓለምን ታሪክ በማንበብ ተፀመድ ።

የጊዜ ዋጋ ጊዜውን ሥራ ከሚሠራበት በከንቱ የማያሳልፈው ብዙ ዋጋ ይከሰራል ጊዜን ሁሉ በሥራ ማሳለፍ ይገባል ሕይወት ነውና ።

ስለ ሕይወት። ራስህን መቻል በጀመርክ ጊዜ የምትመራበትን የምርኩዝን በትር ሌላ ሰው አይያዘው አንተው ተመራበት እንጂ ።

ባህሬና ዕድል እነዚህ ፪ ቃላት እንደ ሐሳባችሁ ተርጕመው በሕይወታችን ውሥጥ ብዙ ፍቺ አለችና እንዴት ይሠሩ ይሆን እኔ እንኳን አላውቅም ነገር ግን ከዚህ በላይ የጻፍኩልህን ምክር ብትፈጽም ዕድልህንና ባህሬህን ከእንቅልፍ እንደተነሣ ያነቃዋል በልንጀራ በመምረጥ ተጠንቀቅ ።

የደፈረ የገኛል ተስፋ የምትቆርጥበት ጊዜ የመጣል በዚያ ጊዜ ተስፋህን አትቁረጥ ተስፋ መቁረጥ የሞት ያህል ነውና እንደ ዓውሎ ነፋስ የሚያልፈውን የልጅነት ወራት ከጨረስከው በኋላ ጸጥ ያለ ኑሮ ታገኛለህ ሥራ ሁሉ ደግና ክፉ አለው ደፋር የሆነ ምንም የጠነከረ ሥራ ቢኖረው ጥቅም ያገኝበታል አስቸጋሪን ነገር ሁሉ ለማቸነፍ አትፍራ በኋላ ቀላል ሁኖ ታገኘዋለህና ደግ አድራጊ ሁን እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ መልክም ጠባይ ይኑርህ እነዚህን ሦስቱን ነገሮች አጥብቀህ ያዛቸው ወደ ከፍተኛው ማዕረግና ክብር ያደርሱሃልና ይህም ላንተ ሽልማትህ ነው ።

ይህ የክቡርቄስ ትእዛዝ የተቀበሉት እንደሆነ ላዲሶች ትውልድና ለሕዝብ ሁሉ የሚጠቅም ስለሆነ ብዙ ጥቅም አለው ።

ክርቴን ባቢኪያን

ስለ ስስት ።

አንድ ገበሬ አንድ የእርሻ ቦታ ነበረችው ያችንም ቦታ እጥር አዞሮባት ነበረ በዚያም ውሥጥ አሳሞችና ደሮች ነበሩ ግን ቁልፍ የለውም ነበረና ልጆቹ ጊዜያቸውን አሳማ ለመጠበቅ ያሳልፉ ነበር አንድ ቀን ሚስቱ ለዚያ በር ቁልፍ ግዛለትና ልጆቹ ወደ ተማሪ ቤት ሔደው ይማሩ አለችው ዋጋው ስድስት ቤሳ ነውና ይቆይ አላት ግን የቁልፉ ዋጋ ከሁለት ከሦስት አያልፍም ነበረ ።

አንድ ቀን ገበሬው በፈረስ ቤት ፈረስ ሲያሥር ሳለ ከውጭ የልጆቹን ጫጫታ በሰማ ጊዜ በድጋሚ ሔዶ ቢጠይቃቸው አሣማችን አምልጣን ወደ ጫካ ገባች በሉት ጊዜ እየሮጠ ሔዶ ከጫካ ውስጥ ገባ የሚስቱም ወንድም ያየውንና ተከተለው በዚያም ጊዜ ከጉድጓድ ዳር ወደ አንዱ ዳር እዘላለሁ ሲል ወድቆ ተሰበረ የገበሬውም ሚስት በወጥ ቤት ልብስ ስትተኩስ ነበረችና ልብሱንም ከእሳቱ ዘንድ ሳታነሣው ባልዋን ተከትላ ሔደች ልጅትዋም ይህን ስታይ መብሉን በእሳት ላይ ትታ እናትዋን ተከ-

ትላ መጣች በዝያ ሜካ ውሥጥ ቤተ ሰብ ተገናኙና ያንን የተሰበረውን ሰውዬ ይዘውት በገቡ ጊዜ ልብስ መብሉ ሁሉ ተቃጥሎ አገኙት ። ገበሬውም ሚስቱንና ልጁን ሰድቦ ወደ ፈረስ ቤት በገባ ጊዜ (፮) ሰያስረው የሔደው ፈረስ እንደኛውን ፈረስ ረግጦ ጥሎ ሰብሮት አገኘው በዚህ ነገር እያዘነ ወደ ቤቱ ተመልሶ በቤት ያለውን ከበሉ በኋላ ሚስቲቱ ለብቻው ጠርታ አለችው። ወዳጄ ሆይ የአሳማይቱ መጥፋት የፈረሱ መሰበር የወንድሜ መሰበር የልብሱና የምግቡ መቃጠል ለአንድ ምክንያት የመጣ ነው ። ያኔ ለበሩ ቁልፍ ግዛ ያልኩህ ጊዜ ለስድስቱ ቤሳ ባትሰስት ይህ ሁሉ ባልደረሰብንም ነበር።አሁንም እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ ስስት ክፉ እንደሆነ ሲመክረን ነውና አትዘን አለችው።

አሁንም ጌቶቼ ሆይ መሰሰት በእግዚአብሔርና በተማሪ ሰው ፊት በጣም ጸያፍ መሆኑን አስረዳኋለሁ በለዚህ ያዕቆብ ምዕራፍ ፭ ከቁጥር ፩ኛ እስከ ፮ እጽፋለሁ ።

አሁንም ሑዱ እላንተ ባለጸጎች አልቅሱም ባለ ጸግነታችሁ ጠፍትዋልና ልብሳችሁንም ብል በልቶታልና ወርቃችሁም ብራችሁም ዛገ ዝግነቱም ምስክር ይሆንባችኋል በጌታ ፊት። ነገር ግን ባለን ገንዘብ ይህን ብንመጸውት ለነፍሳችን፣ ተማሪ ብናስተምርበት ለአገራችን ነውና ስለዚህ ያዕቆብ ከገሠፀን ተግሣፅ የበለጠ ከሰው አናገኝምና ስስትን ጣል አድርገን ፍቅርን አቅፈን ለደጉ ንጉሣችንና ለለምለሚቱ እናታችን የኢትዮጵያ እንድንረዳ ኃይሉን ይስጠን አሜን ተማሪ ነኝና የተሳሳተ ቃል እንድታርሙልኝ በማክበር እለምናችኋለሁ ።

የንጉሥ ትምህርት ቤት ተማሪ ጸጋ አብ ገ ።

ስለ ግርማዊ ንጉሥ ጅምጅም መድረስ ።

መጋቢት ፲፰ ቀን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ በአቶመቢል እየሆኑ በጥዋት ገሥግሠው ወደ መናገሻ ደረሱና ከዚያ እንጨት የሚያነግሠውን ወታደር አይተው ግብር ከተበላ በኋላ ወደ ገነት ከተማ ሔደው አደሩ። **መጋቢት ፲፱ ቀን** ከገነት ተነሥተው በአዲስ ዓለም በኩል አልፈው በ፫ ሰዓት ወደ ጅምጅም ገቡ። ጅምጅም (ጥግ)ጥጉ ርዝመቱና ውፍረቱ ከልክ ያለፈ ግሩም የሆነ የጥድ ዛፍ ያለበት ሜዳ ሜዳውም ውኃ የሞላው ደስ የሚያሰኝ መስክ ያለበት ቦታ ነው። ግርማዊ ንጉሥና መኳንንቱም ይህን አይተው ደስ ካላቸው በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ተመልሰው ወደ ገነት ገብና ከዚያው ግብር ተበላ ከግብርም በኋላ በዓሥር ሰዓት ተኩል ተነሥተው በአስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ወደማታ አዲስአበባ ገቡ ።

ግርማዊ ንጉሥ የተቀመጡበትን አቶሞቢል ተከትለው ይሔዱ የነበሩ ክቡራን መኳንንቶች የተቀመጡባቸው አቶሞቢሎች እጅግ ብዙ ነበሩ ። አካሔዳቸውም በልክ በልክ ተራርቀው ሥርዓታቸውን ጠብቀው አሳምረው ይጓዙ ነበር ። ዙሪያ ዙሪያ በሆነ መንገድ ሲጥመለመል የአቶሞቢሉ ዓጀብ ከማማሩ የተነሣ ላይታው ያስደንቅ ነበር።ያዲስ ዓለም መንገድ በአቶሞቢል ለመሔድ እንደሚገባ ሁኖ የተሰናዳና የተመቸ ነው ።

ግርማዊ ንጉሥም ወደ አዲስ አበባ በቀረቡ ጊዜ ክቡር ባሻ ደንቄ ዘበኞችን አሰልፈው ከገፈርሳ ተቀበሉ በማረፊያ በማረፊያውም ዘበና እየተሰለፈ ሕዝብም ከመንገዱ ዳር እየቆየ የደስታ ሰላምታውን ይሰጥ ነበር ። ከግርማዊ ንጉሥ ጋራም ክቡር ልጅ አስፋ ወሰንና ልጅ መኰንን ተፈሪ ሒደው ነበር ። ግርማዊ ንጉሥን ተከትለው የሔዱ መኳንንቶችም ከዚህ በታች የተጻፉ ናቸው ።

ልዑል ራስ ካሣ፡ክቡር ራስ ጉግሣ፡ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ፡ ክቡር ደጃዝማች ሙሉጌታ፡ክቡር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል፡ክቡር ደጃዝማች ካሣ፡ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ፡ ክርቡ ደጃዝማች ገድሌ፡ ክቡር ደጃዝማች እደፍርሰው፡ክቡር ደጃዝማች ከበደ፡ክቡር ፊታውራሪ ዓምዬ፡ ክቡር ፊታውራሪ ወልደ አማኑኤል፡ ክቡር ሊጋባ ወዳጆ፡ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻ፡ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው፡ ክቡር ፊታውራሪ መንገሻ፡ክቡር አቶ ፋሲክ፡ ክቡር ቀኛዝማች እምባቸው፡ ክቡር ቀኛዝማች ታደሰ፡ክቡር ቀኛዝማች ተፈራ፡ክቡር ቀኛዝማች አጥናፍ ሰገድ፡ክቡር ቀኛዝማች ለጥ ይበሉ፡ክቡር ግራዝማች ኃይለ ማርያም።ሌሎችም ብዙ ነበሩ። ብርሃንና ሰላም ለግርማዊ ንጉሥና ለክቡራን መኳንንቶች እንኳን በደኅና ተመለሳችሁ ይላል።

ሽቦ ስለሌለው ቴሌግራፍ።

ያለ ሽቦ ቴሌግራፍ መሥሪያ የሚሆን መሣሪያ ለመግዛት የፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር በታሕሣሥ ፲፱፻፳፩ ዓመት በወጣው የአዋጅ ቃል ይህንን መሣሪያ ለማስመጣት ጨረታ የገቡ ሰዎች ሁሉ በመጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት በፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ምኒስቴር ተሰብስበው የጨረታ ወረቀታቸውን አቀረቡ የጨረታውንም ወረቀቶች አከፋፈትና የዋጋውንም ልክ የሚመረምሩ ሰዎች ታዘው ነበርና የጨረታውም ወረቀት ሁሉ በሰዎቹ ፊት ተከፈተ መርማሪዎቹም የጨረታውን ወረቀት ከመረመሩ በኋላ በስድስተኛው ቁጥር የቀረበው የጨረታ ወረቀት ዋጋው ና የገንዘቡም አከፋፈል ውልእጅግ መልካም ስለሆነ ጨረታውን ሙሴ ቤርቶሶኒ ወሰዱ ደግሞም የሚአመጡት መሣሪያ ዓይነቱ እጅግ መልካም የሆነና መሣሪያውም በመሀንድስ ተመርምሮና ተፈትኖ መልካምነቱን ሳይመሰክሩ ከመንግሥት ዋጋ አልቀበልም ብለው እንደዚህ ያለ ውል ገብተዋል ማለትን ሰማን እንደዚህ ያለ ታላቅ ሥራ ለማቆም መታሰቡና ቁርጥ ማድረግ ለሕዝብ ንግድ ስፋትና ልማት ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ አዲስ አበባ ገበያ ።

አዲስ አበባ ከተማ የሚሸጥ ዕቃ የተወሰነ ዋጋ የለውም በዚህ ምክንያት መከራከር የሚያውቅ ሰው በምስት የሚገዛው መከራከር የማያውቅና ገር ሰው በዓሥር ብር ገዝቶ ለመሔድ ይችላል ። ስለዚህ ብዙ ነጋዴዎች ለሚያውቅ ይሸጣሉ ከማያውቅ ሰው ይቀማሉ ለማለት ይቻላል ።

ግን ከውጭ አገር የሚገባውና ከአገር ውሥጥ የሚገኘው የንግድ ዕቃ ዋጋው የታወቀ ሁኖ ነጋዴ ከየዓይነቱ ዕቃ ሊያተርፈው የሚገባ ተወስኖ በተወሰነ ዋጋ ቢሸጥ መልካም ነበረ ከተወሰነው ትርፍ በላይ አሞኝቶ ሸጦ የተገኘ ነጋዴም ቀጣት

ቢደረግለት ትንሽ ቢተሻለ፡ ብዙ የውሃንም ባልከሰሩም ። ከያሉ ቡቅ ዓንድ አይነት ዕቃ ቢጠየቁ ዕቃው አንድ ዓይነትሁኖ ይገኛል

በሌላ አገር የሚሸጥ ዕቃ እንደውድነቱ ልክና እንደ ጌዜው እየታየ የነጋዴ ትርፍ ይወሰናል ። ባልሆነ ዋጋ የሚሸጥ ነጋዴም ፈታሾች መርምረው ከወቁት በኋላ ይቀጣል በሱቅ ጉብቶ ወጣ ውረድ በማለት ጊዜ ማጥፋትም የሚያሳፍር ነው። ላንዱ በርከሽ ላንዱም በውድ ትሸጣላችሁን ብለን አያሌ ነጋዴዎችን ብንጠይቃችው በገዛ ገንዘባችን እንደፈቀድን እንሸጣለን ምን ቸገራችሁ ይላሉ እንጂ አይሰጉበትም ።

ዋጋው ትክክል እንዲሆንና ገር ባላገር ሁሉ እንዳይጐዳ የከተማ ሹማምንት ነቅተው እንዲጠብቁና የገበያውን ነገር እንዲያደላድሉ እናሳስባቸዋለ ።

ስለ ክቡር ልጅ ያቦነህ ስረዓት

ልጅ ያቦነህ ቀድሞ በከንቲባ ወስኔ ጊዜ የመዘጋጃ ቤት የዘበኛ ምርመራ ጸሐፊ ሁኖ ይሠራ ነበር በጣም ጠንካራ ሰው መሆኑን አውቀው የሶስተኛው ክፍል ከሚግርያ ጸሐፊ ሁኖ በሥራውም ተመስግኖ ነበር

ሽ ፰፻፺፩ ዓመት ጥር ፯ ቀን ተወለደ ነገር ግን ሰው ኑሮ ኑሮ ከሞት አይቀርምና በተወለደ በ፴ ዓመቱ መጋቢት ፲፫ ቀን ከሌሊቱ በ፱ ሰዓት ከሩብ ዓረፈና በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ። በዚውም የነበሩ መኳንንቶች። ክቡር ደጅዝማች ወልደ ጻድቅ ። ክብር ደጅዝማች ገብረ ሥላሴ ። ክቡር አፈንጉሥ አረጋይ ። ክቡር ሊጋባ ወዳጆ ። የግቢ ወነበሮች ሁሉም መጥተው ነበር ። ብርሃንና ሰላም ለክቡር አባቱ ለባላምባራስ ኃይሌና ለክብርት እናቱ ለወይዘሮ በሽዋም የል ለወንድሞቹ ላቶ ማሩና ላቶ ኪዳነ ማርያም፣ ላቶ ብርቅነህ፣ ለእኅቱ ለመየት ንጋቷ፣ ለባለቤቱ ለመየት በለጤ ለባልንጀሮቹና ለወዳጆቹ ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ።

ባላጋራና ባላጋራ ዳኛው በፈጣጠመው ቀን ሳይቀርብ ቀርቶ ባላጋራው ሰማንያ ያስከነዳው እንደሆነ ሰማንያውን ክዶ ፡ ወይም አምኖ የተረታ እንደሆነ ባላጋራውን ሰዶ እርሱ ቀርቶበ ጉሳላበት የተጉሳላው ሰው ከሰማንያው ከምስት አንድ ይብላ እፎት ክዶ ሰማንያ የከነዳ ግን እንደተለመደው የሰማንያው ገንዘብ ወደ ዳኛው ይግባ መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት

ስለ ክቡር ደጃዝማች ብሩ።

ከወለጋ ተሺረው ወደ ሲዳሞ ስለሄዱብን በየሃገሩ ላለን ነጋዴዎችና ሕዝቦች ትልቅ ጉዳት ሆነብን ። ክቡር ደጃዝማች ብሩ በወለጋ ሳሉ ይሠሩት የነበረ ሥራቸው ሁሉ እንኳን አብሮአቸው ለተቀመጠ ሰውና በውጭ ሁኖ ዝናቸውን ለሰማሁሉ የሚያስደንቅ ነው። ይልቁንም የውጭ አገር ነጋዴና ፈረንጆችን ማክበራቸውና መውደዳቸው ከልክ ያለፈ ነበር ። ከሥራቸው ትክክለኛነትና ከመውደዳቸው የተነሣ የውጭ አገር ፈረንጅ ብዙ ነበር። እኔም ስለ ንግድ ሥራ ፲ዓመት ወለጋ ተቀምጬ ስኖር እንደ ወንድሜ በክቡር ራስ ናደው አገር የሚኖር አለና ከወለጋ ወደጐሬ እየተመላለስን እንነግድ ነበር ። ክቡር ራስ ናደው በግዛታቸው በጐሬ እጅግ ለመንግሥታቸው ጥቅምና እርዳታ ያለው ነገር ይሠራሉ። በጐሬ ያለ ሕዝብ እንኳን ፈረንጅ የኢትዮጵያ ሰው ስልጣኔውና ንጹሕ ልክ እንደ አዲስ አበባ ነው። አሁን በቅርቡ ተጐሬ ተነስቼ በመስከረም አዲስ አበባ ገባሁ ። የክቡር ደጃዝማች ብሩ በሲዳሞ አገር ደግሞ ባንድ ዓመት የሠሩትን ሥራ ሰምቼ ደስታዬ ከልክ ያለፈ ሆነ ቀድሞ በሲዳሞ አገር የውጭ አገር ፈረንጅ ነጋዴ እንደሌለና ሕዝቡ እንዳልሰጠለነ ንግድም እንዳልተዘረጋ እሰማ ነበር።ይህም ደግሞ ተወደ አገረ ገዦዎች ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ነው ይመስለኛል ። አሁን ግን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ከተሾሙ ወዲህ ብዙ የፈረንጅ ነጋዴ በሃገሩ እንዲገባ ንግድም እንዲስፋ ወንበዴና ቀማኛም እንዲጠፋ የድልድዩም ሥራና የመንገዱም ጥርጊያ እንዳማረ ሰምቼ ብዙ አድርጌ አመሰገንኩ ። እንደዚሁ አገረ ገዦ ሁሉ የተሾመበትን አገር እንዲለማና እንዲሰፋ ደሃውን ቢረዳው ንግድም እንዲሰፋ ቢጥር የኢትዮጵያ ሕዝብ በጥቂት ቀን ከሥልጣኔ ደረጃ እንዲደርስና ልክ እንደ ኤሮፓ መንግሥት ሊሆን ይችል ነበር። በሲዳሞ አገር ከዚህ ቀደም በዋናው ከተማ በሀገረ ሰላም አንድ ቆርቆሮ ቤት እንኳ አልነበረትም አሁን ግን ካንድ ዓመት ወዲህ ዓሥር የሚሆን የቆርቆሮ ቤት እንደተሠራና ደግሞ አሁን በኅዳር ወር ፬ ፈረንጅ ታጁር ነጋዴዎች እንደ ገቡና ክቡር ደጃዝማች ብሩ አክብረው እንደተቀበሏቸው ሰማሁ ። ይልቁንም በሲዳሞ አገር ሐኪምና አስተማሪ ስለሌለ አሁን ክቡር ደጃዝማች ብሩ በገንዘቤ ተማሪ ቤትና ሆፒታል እሠራለሁ ብለው ስለ አሰቡ ለሀገራቸው ማሰባቸውና መቆርቆራቸው ይህ ብቻ ያስረዳል።ይህም አሳብ የሚደረገው በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን መሪነት እንደሆነ ማንም አይስተውም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱንና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ዕድሜ ሰጥቶ አቆይቶልን የሲዳሞን አገር ፍጻሜውን ለማየት እንዲያበቃን እግዚአብሔርን እለምናለሁ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።

ሚካኤል ዲስ

በባቡር የሄዱ ሰዎች

ክቡር አቶ ብርሃን ማርቆስ የፖስታ ቤት ዲሬክተር ከክብርት ባለቤታቸው ጋራ ወደ ፓሪስ በመጋቢት ፲፰ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕ'ት በባቡር ተሳፍረው ሄዱ ።

ከጀርመን ሌጋሲዮን የመጣ ራድዮ የመጋቢት ፲፯ና፲፰ ቀን የዕለትወሬ

ጀኔብ፡ በባሪያ መነገድን ለመከልከል በ፲፱፻፳፯ ዓ ም የዓለም መንግሥታት ያደረጉትን ውል የአሜሪካ መንግሥት ወዶ መቀበሉን የሚያስታውቁ ወረቀቶች በቤርን ያለው የአሜሪካን

ሚኒስቴር በዮናይትድ ዕስታትስ መንግሥት ስም ለመንግሥታት ማሕበር ዋና ጽሕፈት ቤት አቀረበ ።

ሐምቡርግ ፤ በሎሞ ቦሳ፡ከሚባል ሥፍራ ላይ ይሠራ የነበረውና ሥራው ፈጽሞ ሊአልቅ ጥቂት ቀርቶት የነበረው ኤሮፓ የተባለው ባለ ፵፬ሺ ቶን መርከብ በጭራሽ ተቃጠለ ። የሐምቡርግ ከተማ እሳት አጥፊ ወታደሮች በባሕርም በጠረፍም የሚቻላቸውን ሁሉ አድርገው ነበር እሳቱ ግን እስከሁን ድረስ እንደተንበለበለ ነው ዘበኞቹ እሳቱ ሲያያዝ ያዩት ማክሰኞ ለት ነበር ። የእሳቱ ሃያያዝ እጅግ የለፈጠነ መርከቡ በጭራሽ ሳይቃጠል አይቀርም ይባላል ።

የመርከቡ ክሣራ እስከ ፶ ሚሊዮን ማርክ ተገምቷል

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የመጣ ራድዮ የመጋቢት ፲፬ቀን የዕለትወሬ

ፍራንስ ፡ ማሬሻል ፎሽ ከሞቱ በኋላ በአርክ ዲትርዮንፍ ዓርፈው ሬሳቸው ፍትሐት ወደሚደረግበት ወደ ኖትር ዳም ይሔዳል ። የቤልጅግ ንጉሥ አልቤርትም ለቀብር መጡ ። ከየመንግሥታቱም የነዘን ቴሌግራም ለፈረንሳዊ መንግሥት ደረሰለት ። በየመንግሥታቸውም ስም ሁነው የየመንግሥታቱ መኳንንት ለቀብር መጡ ።

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ መልክም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጪት ለሚፈልጉ ሰዎች ዱቄላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፡ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፡ እንጨት፡ወይም ማናቸውንም ዓይነት እቃ፡ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበር።

የማህበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማህበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማህበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፡ የርሻ፡ የፋብሪክ፡የደን፡ የማዕድን ሥራ፡ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርበስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፡ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።ፈርማበጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጡን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቁርቁሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ማሪዋያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወደያውም ለአቶሞቢል ዘይትና የማረኪን ቤንዚን ይሸጣል ።



COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK- METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ኬዎርከፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊሪስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎ ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በለንደን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጀቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መጫሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተቃላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከናቡሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከናቡሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ኒለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm. Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ አሸቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የዶማት የጨጓራ የቂጥኝና የጨቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጉዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ሳይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ በለእንጨት ። በለወረቀት በለምልክ ። በለወርቅ የብርሌ ሶብየን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ በዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማቈድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ያበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።


GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
1-26-7
GOODYEAR
ጉደይር ዘ

አምስተኛ ዓመት ቍጥር ፲፬
5me ANNÉE № 14

ሐሙስ መጋቢት ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 4 AVRIL 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መሻሻት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፺፰ ገጽ ተከታይ ።

(፳፬) ፍሬ ።

የሚበልጥ አድርጎ ለማፍራት እንዴት ያለ አሠራር ይሻላል? ከሁሉ በፊት የማፍራትና ያለማፍራትን ሥራ መለየት ያስፈልጋል። አንድ ሥራ የማፍራት የሚባል ከፊት የነበሩ ጥቅሞች የማያሰይግ እንደሆነ ነው ። እንዲሁ የመሀንድስ ፥ የማኪኒስታ ፥ የሐኪም፥የነጋዴ፥የገበሬ፥የወታደር፥እሱንም የመሳሰሉ ሥራዎች ሁሉ፥የፍሬ ሥራዎች ናቸው።ግን ለሠሪው ጥቅምና ትርፍ የሚሰጡ ቢሆኑ እንኳ፥ ለሕዝቡ፥ ማለት ለአንድነት ኅብረት ጉዳት ስለሆኑ ፥ ፍሬ የሌላቸው የጉዳት ሥራዎች አሉ ። ምሳሌ እንደነ ሌብነት፥ ቅጥፈት፥ አታላይነት፥ ቁማር፥ ነፍስ ገዳይነት፥ እነዚህንም የመሳሰሉ ሁሉ ።

የሚበልጥ ለማፍራት እንዴት ያለ አሠራር ይሻላል ብለን ጥያቄ ሰጥተናል ። መልስ፥ ፩ኛ በተሻለ ጊዜ፥ ፪ኛ በተሻለ ስፍራ ፫ኛ በተሻለ መንገድ፥ ማለት ባጭሩ በተመቸ ጊዜ መሥራት ያስፈልጋል። አስረጅ (ሀ) (ሀ) (ለ) መ) ማለት ቍጥሮቹ ሁለተኛ እንዳይደገሙ ፩ኛ፥ ፪ኛ፥ ፫ኛ፥ ስፍራ ምትክ ናቸው፥ የጊዜ ምርጫ ማለት ለምሳሌ፥ ገበሬ በበጋ መሬቱን ያሰምራል፥ ዱሩን ይመነጥራል፥ ፍግ ይነሰንስበታል፥ በዘር ጊዜ እህልን ይዘራል፥ ስለዚሁ ነው በተሰጠው መልክም ጊዜ መሥራት ያስፈልጋል የሚባል ። ረጋም ጊዜ መሥራት ማለት በቀን ከስምንት ሰዓት የበለጠ መሥራትም አያስፈልግም። ለሠራተኛው ደግ አይደለምና እንደ አንድንጊዜም ማረፍ ያስፈልጋል ማለት እሑድ ለየስፍራ ምርጫ ማለት ሥራን በተሰጠው መሬትና ስፍራ ሊሠራ ይገባል። ምሳሌ፥ በኢጣልያ አገር እንደ ወይን እርሻ በጀርመን ወይም

እህል በደጊያ የሚዘራ ቢገኝ ዕብድ በተባለ። የድካም ሥራው እንዲያው ባክኖ ይቀርበታልና። በሌላ መንገድም የደረጃ መዓርግ አለበት ። ማለት በአንድ ስፍራ ብዙ፥ በሌላ ስፍራ ጥቂት ፍሬ ሊሆን ይችላልና ። እንዲሁ በእንግሊዝ አገርም ጥቂት ጥቂት ወይን ይበቅል ነበር፥ ግን ሥራውን ያንን ያህል ጨርሶ፥ በፈረንሳይ፥ በኢጣልያ፥ በስፓኛ አገሮች ወይኖች እጅግ በጣም የሚለመልሙ ስለ ሆኑ፥ እንዲሁ እንግሊዞች በአገራቸው የሚለመልም ሣር እየዘሩ ከብቶች እያረቡ ወተት፥ ቅቤ፥ አይብ፥ አፍርተው የሥራቸው ልክ የሚሆን ወይን በለውጥ ያገኛሉ ።

እንደዚሁ የዓለም ሀብትን ለማፍራትና ለማብዛት በያገሩ በተሰጠው አፍርቶ በዓለም መንግሥታት ገበያ ለ ለዋወጥ ያስፈልጋል (ይገባል) ። (አስረጅ) በእስያ ማለት በቻና ብዙ ሻይ፥ ሐር ፥ ህንድ ብዙ ጥጥ፥ ሩዝ፥ ሡካር፥ ልዩ ልዩ ቅመማት በአውስትራልያ ጠጕር፥ ቈዳ፥ ሥጋ፥ ሱካር፥ ወርቅ፥ አልማዝ፥ መዳብ፥ በአሜሪካ ሰሜን ስታቴ ኡኒቲ ብዙ ጥጥ፥ ፍሬ፥ እህል፥ ወርቅ፥ ብር፥ መዳብ፥ ነሐስ፥ ብረት፥ ጋዝ፥ በአሜሪካ ደቡብ ብዙ እንስሶች (ማለት የሥጋ ከብት፥ ጠጕር፥ ቈዳ፥ ቀንድ፥ ውድ የሆነ ዓጥንት እሱንም የመሰለ ሁሉ ያፈራሉ ።

እያንዳንዱ አገር (ማለት በየስፍራው በተሻለ ለማፍራት የሚቻለው ሸቀጥ (ዕቃ) አለው። ስለዚህ የዓለም ሰዎች ሁሉ (ማለት መንግሥታት በጣም የሰፋ የንግድ ነጻነት ማሳለፍ ሊሰጡ በተገባቸው ነበር ።

(መ)የመንገድ ምርጫ፥ አንደኛ በዕውቀት ሁለተኛ ሥራ በመካፈል ፥ ሦስተኛ በተሰጡ መሣርያዎች ፥ ባጭሩ ሥራ በተሻለ መንገድ ሊፈጸም ይገባል ብለናል ። የታይሎር የሚባል ትልቅ ብልህ አሜሪካዊ እንደወሰነው ሠራተኛው በሀል በማይደርስ

ተሰናድተውና ተዘጋጅተው በአጠገቡ ማስገኘት ማለት ሲያበጅና ሲያሥር፡ሲፈታ እንዳይበዝን ያስፈልጋል። ይህ ታይሎር የሚባል ታላቅ ኤኮኖሚስታና አችያዮ ያወጣ ነው። (አችያዮ ማለት ብረትና ከሰል ተደባልቆ ይሰራና ብረቱን ብረት ሊቆርጥ የሚችል ስዋና ዋና ስራ የሚሆን።ለምሳሌ፡ለአሬዮፕላን የሚሆን ክብረት ዘር ሁሉ ዓይነት እጅግ የጠነከረ ነው።)የዓለምን ሠራተኞች ሁሉ በማይረባ ነገር በአንድ ቀን ስንት ሰዓት እንደሚያባክኑ አስበ ገምቶ የዓለምን ኤኮኖሚያ የአንድ ዓመት ጉዳትዋ ብቻ ብዙ ሚልያርድ ብር እንደሚደርስ አሳይቶ ይገልጣል ።

ሚካኤል ተሰማ ።

ከዚህ የተረፈ በሚከተለው ይታተማል ።

ስለ ሕዝብ ጤናነት ።

መንግሥታችን ሕዝቡ ከበሽታው እንዲፈወስና ጤናነቱ እንዲጠበቅ የሚያክሙና ልዩ ልዩ በሽታን በመድኃኒት የሚቃወሙ ብዙ ሐኪሞች አስመጥቶ በየክፍሉ ሥራቸውን ይሰራሉ።ይህም ለሕዝባችን ትልቅ እርዳታ ነው ። መንግሥታችንም ለሕዝቡ አባት ለልጆቹ እንዲያስብላቸው ማሰቡን ያስረዳል ።

ነገር ግን በሀገራችን ሐኪሞች ሊቃወሙትና ሊያጠፉት የማይቻል እንደ ብርቱ ጕርፍ ሁኖ በሀገራችን ውሥጥ የገባ ክፉ በሽታ አለ።እርሱም ማንም የማይስተው የአልኮል(አረቂ)አመል ነው። የአረቂ መጠጥ ለሕዝባችን ዋና ጕዳትና በሽታ እንደሆነ ሐኪሞች ሁሉ ይመሰክራሉ ። ያገራችንም ሕዝብ አረቂን ያለ ልክ ይጠጣል ። ከነጋዴዎችም አረቂን የሚሸጥ ነጋዴ በቶሎ የሚነግለት ስለ ሆነ በቶሎ ይከብራል። በከተማ ይቅርና ባገር ቤት ስንኳ እህሉን ለአረቂ እየሸጠ ይጠጣል። ባላገሩም ያረቂን መርዝምነት አያውቅምና ባገኘው ጊዜ ያለ ልክ ይጠጣዋል ። አንድ አንድ ጊዜም ምን ምን የመሰሉ ጆግኖች አረቂ በመጠጣት ተሸንፈው ከመንገድ ላይ ወድቀው ሲንደበለሉ ይገኛሉ ። ይህንንም ማየት በጣም የሚያሳዝን ነው ።አረቂንም የሚጠጣ ሰው ድንገት ባንድ ነገር የቆሰለም እንደ ሆነ ደሙ ስላለቀ መርዙ እያቸነፈ ቍስሉ በቶሎ አይሽርለትም።

የዘመኑንም ሥልጣኔ ጥቅም ያገራችን ሕዝብ እንዲረዳውና እንዲሰለጥን መሪ እንደሚያስፈልገው እንደዚሁም ሁሉ የዚህ ዘመን መጠጥ መርዝምነቱን አያውቅምና ከእሳት ውሥጥ ግብቶ እንዳያልቅ አረቂ ፈጽሞ ከገር እንዳይገባ ወይም ማንም እንደማያገኘው በሕግ ወስኖ እንዳገኙ እንዳይሸጥ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ራሳቸውን በሚጠብቁ በሠለጠኑ ሕዝብ ስንኳ ያረቂን መርዝምነት ስለአወቁ ሕዝቡ ባረቂ አመል እንዳይያዝና ጤናነቱን እንዳያበላሽ ባንዳንዱ አገር ጭራሽ አረቂ እንዳይገባ ክልክል ነው ። በአንድ አንዱም አገር አረቂ ለማንም ሰው እንዳይሸጥ በሕግ ተወስኖዋል።በዩናይትድ ስቴት የንግድ እቃ የሚያመጡ መርከቦች ድንገት በውሥጣቸው አረቂ እንዳይገኝ ብቻውና ወደ አገራቸው አረቂ እንዳይገባ በጥንቃቄ ይፈትሻሉ።

ይልቁንም ሕዝባችን አረቂ የሚጐዳ መሆኑን እጅግ አያውቀውምና እውቀት ያላቸው መኳንንትና ሹማምንት ከረቂ ሊጠብቁትና መርዝ እዳይጠጣ ሊከለክሉት አረቂንም ሊያስወግዱለት ይገባል።የገዛ ሕዝባችንም ገንዘቡንና ሕይወቱን ሲያጣ ዝም ብሎ ማየት አይገባንም።መንግሥታችንም ሐኪምና መድኃኒት እያስመጣ የሕዝቡ ሕይወት እንዲጠበቅ ማድረጉ መልካም አድርጓል።ደግሞ ይህ ሐኪሞችን የሚቃወም መርዛሙ መጠጥ ከሕዝቡ እንዲርቅ ቢያደርግ የበለጠ ያደርጋል ። አረቂም ለሚሸጠው ሰው ብዙ ትርፍ ይሰጠዋል፤ ለሚጠጣው ግን ጕዳት እንጂ ጥቅም አይሰጠውም ።

ስለ መረዳዳት ።

ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ባንባቢ ፊት ይቅርታና ሞገስ እንዲያገኝ እለምናለሁ። ገበሬ ያለበሬ በሬ ያለ መሣርያ መስራት የማይመች ስለሆነ ገበሬው ሁሉንም አስማምቶ እሾሁን እየመነገለ፡ድንጋዩን እየፈነቀለ ፤ አባጣ ጐባጣውን፡ዳገት ቁልቁለቱን ፤ አስተካክሎ ካረሰና መሬቱ ከለሰለሰ በኋላ በዘር ወራት ተስፋውን በእግዚአብሔር አድርጎ ለመሬቱ የሚስማማውን እህል በያይነቱ ይዘራል ። እህሉም በቅሎ ለመታረም በደረሰ ጊዜ ወራቱ ሳይታላለፍ እንዳይቀጭጭና እንክርዳድ የበዛበት እንዳይሆን ዘመድ ወዳጁን ሰብስቦ አንድነት ሁነው አረሙን ያርማሉ። እህሉም መሰናክል የሚሆንበትን አራሞች ስላረሙለት መልካም ፍሬን ያፈራል። የፍሬን መንገድ ይዞ ሸቶ ባየነው ጊዜ ልንቀምስለት እንወዳለን።በመከርም ጊዜ በዓውድማ ላይ ከገለባው ፍሬው አመዝኖ ይገኛል ። ገለባው (ጭዱ) ለቤት ሥራና ለእንስሶች ምግብ ይሆናል።

ገበሬ፡በሬንና ማረሻን አስማምቶ በእግዚአብሔር ተስፋነት የዘራው ለመብቀል፡ፍሬውን ለማሳነስ፡በማሀሉ የበቀለው አረም የሚባለው መሰናክል ታርሞ መልካም ፍሬ አፍርቶ ከሰው እስከ እንስሳ ምግብ እንደሆነ፤ እኛም በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ጸሎት፤ በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ትጋት፡ወደ ከፍተኛው ደረጃ ለመድረስ ተቃርበናል ።

ትምህርትን በሬ እርዳታን ገበሬ አንድነትን(መተባበር)ማረሻ አድርገን፤ ድንቁርና የሚባለውን ድንጋይ ፤ አለመተባበር የሚባለውን እሾህ፡ ቂም የበለውን አባጣ ፤ ንፍገት የሚባለውን ጐባጣ፡ዳገት የሚባለው ኩራት፤ ንቀት የሚባለውን ቍልቍለት አረም የሚባለውን ስንፍና ፤እነዚህ ወዳጅ መስለው ለማጥቃት የተጠጉን ጠላቶች ለመቃወም እንዲቻለን ፤ ምግብና መጠጥ በየጊዜው እንደምንሻና እንደምንወድ፡ፍቅርን እንደ ምግብ ብንሸት፤ እንደ ልብስ ብንለብሳት፤ ሞገስ መሆንዋን ማንም አይስተውም።ፍቅርን፡ጋሬ አይጋርደውም እንደሚባል እንዴ አገሩን ወዳጅ ትንሹ ተማሪ መ ሥ መ በ፱ኛው ዓመት ቁ ፴፱ ብርሃንና ሰላም አይቻለኝም እንጂ የሚቻለኝስ ቢሆን ለሀገሬ ስለሕዝቡ ጥቅም ራሴን ወደ አንድ ቦታ፡እግሬን ወደ አንደኛው፡እጄን ወደ ሌላው ልከፍላቸው እወድ ነበር ። ባሉኝ ገንዘቤ (መጻሕፍት) የ፲፪ መጽሐፍ አንድ አንድ መሐለቅ ሒሳብ ፯ብር ከ፩ድ መሐለቅ ለሠረቀ ብርሃን ተማሪ ቤት ፰ብር እርዳታውን አድርጌ ስለ ሀገሬ ጥቅም አስከታትሎ ጽፏል ።

የአንድ ተማሪ ያህል መረዳዳት እንደምን ያቅተን?፡ ሲሆን የራሱን ያህል፡ያለዚያ እኩሌታውን እንኳ መረዳዳት እንዴት ይቸግረን፧ትንሽ ተማሪ ይህን ያሳሰበው በተማሪ ቤት ነውና ያለው ዋና መሠረት ፍቅርና ትምሕርት እንደ ሆነ ተረድቶት ነው ። አንዱን ከላየ አንዱ አይነቃምና መረዳዳት የሚያስፈልገን ስለሆነ የግርማዊ ንጉሥ ተማሪ ቤት ገንዘብ ተቀባይ እርዳታዬን እንዲቀበሉኝ እለምናለሁ ።

እንኳንስ አልፎ አልፎ የተማሪ ቤትና ብዙ የሥራ ቤት (ፋብሪክ)ለማቆም ባልተሣነንም ነበር።አለመተባበር የሚባለው ነውና ያስቸገረን ፍቅር ፣ ዋና ቀዋሚ መሠረት ከደረገን ከላይ ከተጠሩት ክሰዉቱ ጠላቶች ለመዳን ይቻለናል።ገበሬዎች(መምሕራን)የዘሩት መልክም ፍሬ እንዲሆን በጣም እናስብ፡ እውቀትንም ለመፈለግ በየክፍሉ ያሉ ወንድሞቻችን እግዚአብሕር ጠብቋቸው ትምሕርታቸው ፍሬያማ እንዲሆን መንግሥታቸውንና እናታቸውን ኢትዮጵያን ደስ እንዲያሰኝዋት፡እንዲያገለግሏትም የቃመን ተስፋ ስለ አለን ልጅ በሕፃንነቱ ወራት ትምህርትን እንደሚጠላና አባት እናቱ በከባድ ቀንበር ይዘው እንደሚያስተምሩት እንሁን ያለዚያ የተማሪ ቤት ማቆሚያ ሕዝባችን የሚያወጣውን የጥበብና የትምህርት ሚኒስቴር ዲሬክተር መ ስ ወ ድሐ እንዳይጠቃ ሀብታም እንዳይቆጣ እንዳለው ድሐና ሀብታሙ ያወጣውን ደንብ አልፈው አርሶ ከሚያድረው የርሻ ሚኒስቴር፡ንግድ ከሚያድረው የንግድ ሚኒስቴርና ማዘጋጃ ቤት፡ከመንግሥት በወር ቀለብ ከሚያድረው የጦር ሚኒስቴርና የገንዘብ ሚኒስቴር እየተቀበሉት ይህንም ገንዘብ ከመቶ ይህን ያህል ለዚህ ተማሪቤት እያሉ ከፋፍለው ቢጀመርበት መልክም ይመስለኛል አቃንተን የትምህርትን መንገድ እንያዝ እንጂ ችላ አንበል ። ጌታቸው ቀንድቤ ።

የ፺፪ ገጽ ተከታይ ።

ዝኒት የምትባልዋ ባለምዋል የጻፈችው የቀድሞ
የመስኮብ ንግሥት ምስጢር ያለው የሕይወት
ታሪክ በክርቴን ባቢኪያን ታርሞ ተጸፈ

እመስኮብ አገር ሔደን በቤተ መንግሥት ግቢ ስንደርስ ያልጋ ወራሺቱ የአሊክስ እናት በታላቅ ክብር ተቀብለውን በመጀመሪያ ንግግራቸው እንደዚህ አሉ ።

በውነት የምወድሽ አሊክስ ሆይ በጀርመን አገር ሰለሽ አርምሽታት በሚባለው ቤተ ንጉሥ እንደዚህ በታላቅ ጭንቀት መቀመጥሽን አላውቅም ነበር። አሁን በቅርቡ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ዊልሄም ስላንቺ ሁናቴ ጻፈልኝ። እኔም ነገሩን ከሰማሁት በኋላ እንድትመጪ ቴሌግራም አሳለፍሁ አሁንም በእጄ ከገባችሁ ወደ ሌላ እንድትሄዱ አልሰጣችሁም፤ እነዚህን ወራት ከኔ ጋር ሆናችሁ እንድታሳልፉ እፈቅዳለሁ ።

እኛም ይህን ቃላቸውን በሰማን ጊዜ በብዙ ደስታ ተቀብለን አያሉ ወራት በተድላ ተቀመጥን ከዚያም በደረስን በሰስተኛው ቀን በክረምት ወራት ለመቀመጫ በተሠራው ቤተ መንግሥት ታላቅ ግብዣ ተደርጎ አሊክስ ተጠርታ እኔም ከርስዋ ጋር ሔድሁ። ያም የተጠራንበት ቤት ኒኮላ በሚባለው ንጉሥ ስም የተሠራ ነው።አሁን የቤቱን አሠራርና ማማር በመጻፍ ጊዜ አላሳልፍም።ነገር ግን ታላቅነቱ እጅግ የሚገርም ነው።ለጨዋታ ብቻ የተሠራው አዳራሽ ለሶስት ሺ ሰው ጨዋታ ይበቃል።በዚያ ቀን የነበሩት ታላላቅ ሰዎችና ወይዛዝርት የለበሱት ልብስና ጌጥ ለቤቱ ማማር ሁለት እጅ ውበት ጨመረለት ። እንዲሁም አልጋ ወራሺቱ አሊክስ ከመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ልጅ ከአልጋ ወራሹ ኒኮላ ጋር ተገናኘች፡ከዚያም ንግሥቲቱ የኒኮላ እናት አሊክስንና ልጅዋን ኒኮላን አስተዋወቀቻቸው።አልጋ ወራሹ ኒኮላ ግን አይናፋር ነበርና ከነሱ ጋር ተቀምጦ ሊያነጋግራቸው አልደፈረምና።ትቶዋቸውም ወደ ውጭ ወጣና ከንግሥቲቱ ከአሊክስ ጋር እጅግ የከበሬታ ጭውውት ሲጫወቱ ቈዩ ። ከጥቂት ቀን በኋላ አልጋ ወራሺቱን አሊክስን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አቅርበዋት ለሴላ ቀን ምሳ ግብዣ ተጠራች።በግብዣውም ቀን ሔደን በብዙ ማዕረግና ክብር ተቀብለውን በደስታ ግብዣችንን ጨረስን።ደግሞ በተራቸው ንግሥቲቱ ለብቻቸው በከበሬታ ለግብዣ ጠሩን ፤ ንግሥቲቱ ስማቸው ፊአደሮውና ይባላሉ፤ ከዳንማርክ ንጉሥ ከደግማር ተወለዱ፤ ቁንጅናቸውም በዓለም ካሉ ሴቶች ይበልጥ ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱ ዘወትር የመስኮብ ጠባቂ መልአክ ይላቸው ነበር፡ ብዙ ክፋት ያላቸውም ሰዎች ያምዋቸው ነበር፤ ነገር ግን ምንም ቢያምዋቸው ብዙ ትዕግሥት ስላላቸው ይልቁንም ባህሪያቸው መልክም ስለሆነ የመስኮብ ሕዝብ ሁሉ ይወዳቸው ነበር፤ ይህም ግብዣ እጅግ ደስ ስላሰኘን አሊክስ በየጊዜው ቻርስኮየ ሴሎና ፔትርሆፍ ከሚባለው ስፍራ ግብዣ ትጠራ ጀመር። እኔም ከምትሔድበት ስፍራ ሁሉ ቀርቼ አላውቅም። ብዙ ጊዜ በተጋበዝንበት ስፍራ ሁሉ አልጋ ወራሹን እናገኘው ነበር፤እርሱ ግን በቀላል ከበሬታ ነበር የሚያነጋግረን፤ አሊክሲም ከርሱ ጋር መገናኘት ደስ አይላትም ነበር፡ ለኔም አንድ ቀን ይህ ሰው ደስ አይለኝም ብላ ነገረችኝ ።

አንድ ቀን ፔትርሆፍ በሚባል ስፍራ ባትክልት ውስጥ ከአልጋ ወራሹ ኒኮላ ጋር ተገናኝ ንግግሩም ጣም የሌለውና የማይረባን እንደሆነ አየሁ። አሊክስም በምን እንደ ጠላችው በዚያን ጊዜ ተረዳሁት።እርሱም ማዳሚዜል ሊያን ጋርሎቲ ከምትባለዋ የከፈ ኮንሴሬ ሆቴል ዘፋኝ ወዳጅ መሆኑ በሕዝብ ሁሉ የታወቀ ነበር ። በሚከተለው ይታተማል።

ክርቴን ባቢኪያን

የእውቀት ጉዳና ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ሰው በየአቅሙና በየእውቀቱ እንዲረዳዳና እንዲያስታውስ እንደ ተፈጠረ አትስቱትም።እኔም በዚች ትንሽ እውቀቴ የማስታውሳችሁን የጐደለ ሞልታችሁ የጠፋውን አቃንታችሁ እንድታነቡልኝ ተስፋዬና ምኞቴ ነው ። ብዕር ያለቀለም አይጽፍም፤ ቀለምም አለመያዣ (ብልቃጥ) አይያዝም፡ብዕርን አለቀለም ስትጽፍበት ብትውል የምታደርገው ቁም ነገር የለህም፡ይልቅስ ወረቀትህን እየበጫጨርህ ታጠፋለህ እንጂ ቀለምም አላንድ እቃ አይዘለሁ ብትል ይፈስብሃል እንጂ በጅ ብሎ አይያዝልህም ። አሁንም እስቲ ብዕርና ቀለም ብልቃጥም እንዴት እንደሚረዳዱ ንእ

መልክት ምንው እኛስ እርስበርሳችን እንረዳዳ። ልንረዳዳና አገራችንን ልናበለጥግ ብንፈልግ ጉበት ልጆቹን በተማሪ ቤት ሊያገባቸው ግድ አለበት ልጆቹም በርትተው እንዲማሩና ተምረው ሲያበቁ ያልተማሩትን ያገራቸውን ልጆች አስተምረው ከጨለማ ወደ ዕውቀት ጎዳና ሊያሻግሯቸው ያስፈልጋቸዋል ፡፡ ነገር ግን በዚህ አገር ባሉት የተማሪ ቤቶች ተምረን ላገራችን እንረዳለን እናስተምራለን ለማለት አይችሉም ስለምን ከዚህ አገር ያሉ የተማሪ ቤቶች ፤ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ስላልበቁ ነው ፡፡ አሳንሼ ብገምተው በኤውሮጳ አገር ምናልባት ባንድ ኮሌጅ ተማሪ ቤት ፪ሺ ፣የሚያህሉ ተማሪዎች አይታጡም ባንድ ዩኒቨርሲቲ ደሞ ፩ሺ፭፻ የሚያህሉ አይጠፉበትም ፡፡ እስቲ እናስበው አገራችን ኢትዮጵያ ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ እስኪታቆም ድረስ ብዙ ጊዜ ያልፍበት የለምን ፡፡ ሌላስ ይቅርና ቤቱ እስኪሠራ ድረስ እንኳ ጊዜ ያልፍበታል ፡፡ ደግሞ ለኮሌጅና ለዩኒቨርሲቲ የሚበቁ ፪ሺና ፩ሺ፭፻ የሚያህሉ ተማሪዎች እስኪተሰበሰብ ድረስ ብዙ ጊዜ ይወስዳል ፡፡ ጊዜ ገንዘብ እንደሆነም አትስቱትም፡ ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ግን ቢሆን መቶ የሚያህሉ ልጆች ባንድ ጊዜ ወደ ኤውሮጳ አገር በተላኩ አለበለዚያ ግን በትምህርት ተመርጠው የተገኙትን ልጆች እንኳ እየላኩኝ እንድታስተምር ያስገድዳት ነበር ፡፡ ለሚሔዱት ልጆች በዚህ አገር ሳሉ ምን ዓይነት ሥራ ለመማር እንዲፈልጉ መጠየቅ ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ግን የጌጥ ትምህርት ቋንቋ ተምረው ቢመለሱ ኢትዮጵያን ምንም አይጠቅምዋትም። ለኮሌጅና ለዩኒቨርሲቲ የሚበቁ ቤቶች እስኪሠሩና ልጆችም እስኪሰበሰቡ ድረስ ኤውሮጳ አገር የሔዱት ልጆች ተምረው እንዲያበቁና ተመልሰው ባገራችን በቆሙት የተማሪ ቤቶች እንዲያስተምሩና አገራችንን እንዲረዱ የታወቀ ነው ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ሁለት ሦስት ልጆች ቢላኩ ላገራችን ምን ይጠቅሙዋታል?በኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች ሊሆኑ ነውን ወይስ ሌላ ሥራ ሠርተው አገራችንን ሊጠቅሙዋት ነውን። እስቲ እንመልከት መንግሥታችን በሦስት ባራት ዓይነት ሥራ አንድ አንዳንድ ሰው መሾሙ የተማሩ ሰዎች ስላነሱ ነው ፡፡ ስለምን አንድ ሰው ብዙ ሥራ የያዘ እንደሆነ አንዱን ትቶ አንዱን ሲያስብ ሌላው በከኖ ይቀራል እንጂ አይሳካለትምና ፡፡ ይልቁንም አእምሮው ይበላሽበታል። አንድ ሥራ ቢይዝ ግን ባንድ ሐሳብ ቀጥሎ ሥራውን ያስኬዳል።ለመንግሥቱም እርዳታ ይሆናል።ስሙም በምስጋና ሲጠራለት ይኖራል ፡፡ ይህ ቃልሆነ ግን አገራችን ብልጥግናዋ ይጠፋል። የባዕድ አገር ሰውም የረገጣት እንደሆነ ከማእዱ ልንከፈልበት አንችልም ፡፡ ሌላስ ይቅርና ዱሮ አያቶቻችን የሚያገኙት የእህሉ ሽመታ በጣም እርካሽ ነበር።አሁን ግን እየተወደደና ሕዝቡም እደኸየ ሔዷል ፡፡ ይህ ሁሉም ምንም አይረባንም ግን ቀድሞ እንደተባለ እንደ ብዕርና ቀለም ቢልቃጥም ብንረዳዳ ያገራችን ማእድኛ አለልክ ተርፎ ለውጭ አገርም ይተርፍ ነበር ፡፡

የብርሃን ወዳጆች ሆይ ይህን መጻፌ እናንተን አመክራለሁ ብዬ አይደለም።ነገር ግን ያገራችን ወደኋላ መቅረት ቢያሳዝነኝ ነው አጥፍቼም እንደሆነ በጉልበታችሁ ላይ ወድቄ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ፡፡ ትንሹ ልጃችሁ ዮሐንስ ረዳ።

በባቡር ስለ ተሳፈሩ ሰዎች

መጋቢት ፳፩ ቀን የቤተ ሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ሆስፒታል ሐኪም ክቡሩ ዶክቶር ሐነር ከባለቤታቸውና ከልጃቸው ከረዳቶቻቸውም ከሲስተር ቢናና ከሲስተር ቤሪ ጋራ ስለ ዕረፍት ወደ አገራቸው ወደ ሺዊድን ስድስት ወር ድረስ ቈይተው እንዲመለሱ በባቡር ተሳፍረው ሔዱ ፡፡

ክቡር ዶክቶር ሐነር በቤተ ሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ሆስፒታል ሦስት ዓመት ሙሉ ሆስፒታሉን እንደሚገባ በጥንቃቄ ይዘው ብዙ በሽተኞች በትጋት እያከሙና እየተከባከቡ አድነዋል ይልቁንም በኦፔራሲዮን ሥራ ብልህና አዋቂ ስለ ሆኑ ለሕዝባችን ሊቈጠር የማይቻል ብዙ ጥቅም ሠርተውለታል። ይህንንም የመሰለ ብልህና ብዙ ጥቅም ያለውን ሐኪም አስመጥተው ለሆስፒታሉም ሥራና መማርያ ጉልቍ የሌለው ገንዘባቸውን መሥዋዕት አድርገው እንዲህ ያለ ሥራ ላቆሙልን ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ያየና የሰማ ሰው ሁሉ ልክ የሌለው ምስጋናውን ያቀርባል።ይልቁንም ብዙ ዓመታት ሲጨነቁ ኑረው ለጥቂት ጊዜ ሕይወት ያገኙ ብዙ ሰዎች ምርቃታቸው ከልክ ያለፈ ሆነ።

እውነትም ዶክቶር ሐነር እንዲህ ያለ የሚያስመሰግን ሥራ መሥራታቸው ብልህና አዋቂ ብቻ ስለ ሆኑ አይደለም ዕድላምም ጭምር ናቸው እንጂ። በሕክምና ሥራ በሽተኞችን ለማዳንና በኦፔራሲዮንም ወጌሳነት በሀገራችን እንደ ዶክቶር ሐነር አድርጎ የተመሰገነ ሐኪም አልተገኘም ነበር ከዚህ ቀደም የሆስፒታሉ ሥርዓት እንዳይበላሽና ቤቱም እቃውም በንጹሕ ሁኖ እንዲጠበቅ በብዙ ጥንቃቄና ብርታት ያለሹራት ይሠሩ ነበር፥እንዲሁም ለዕረፍት የተቀበሉትን ጊዜ በደስታ ፈጽመው ለሕዝብ ጥቅም ወደ ሆነው ሥራቸው በደህና እንዲመለሱ እንመኝላቸዋለን ፡፡

በዚሁም ቀን የሴቶች ልጆች አስተማሪ ክብርት ወይዘሮ አናሊና ለዕረፍት ወዳገራቸው ወደ ሰዊድን በባቡር ተሳፍረው ወረዱ። ብርሃንና ሰላም በደህና እንዲመለሱ ይመኝላቸዋል ፡፡

ያገር ውሥጥ ወሬ ፡፡ የሰዮ የእሳት አደጋ ፡፡

በመጋቢት ፳ቀን፡ ከሌሊቱ በ፰፡ ሰዓት በሰዮ ከተማ ብርቱ የእሳት አደጋ ተነሥቶ ከምሳ በላይ የሚሆን ቤቶችና ብዙ ዕቃ ተቃጠለ ፡፡ ከተማዋ እንደ መጠኑዋ የንግድ ቦታ ስለሆነች በየቱጃሩ ያለ መደበር የቤቱና የዕቃው ግምት ከሚልዮን ብር በላይ ይሆን ነበር ፡፡ ምንም የተቃጠለው ቤት ማሳዘኑ ባይቀር የቱጃሮች ነጋዴዎች ቤትና የመንግሥት ጉምሩክ ስላልተቃጠለ ኪሳራው ብዙ አይደለም ፡፡

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ መልከም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ ሰዎች ዳውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፥ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፥ እንጨት፥ወይም ማናቸውንም ዓይነት እቃ፥ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበር።

የማህበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማህበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማህበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፡ የርሻ፡ የፋብሪካ፡የደን፡ የማዕድን ሥራ፡ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርበስ ቤት ፊት ለፊት ነው። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፈ.ማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተ ፲፫ መ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
ያበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ክረጃ	፻፸፩ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፪ ብር
: : ባለ ድመት ።		፻፵፫ ብር
: : ባለአህያ ።		፻፷ ብር
: : ባለሳቢ ግመል ።		፻፶፫ ብር
: : ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፯ ብር
" " ጃፖን		፻፸፩ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፵፯
ባአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፶፬ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ክ፸፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቶርቶሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማጎደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም [illegible] ዘይትና [illegible] ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳየ ስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሉንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያስናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከኘሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከኘሱሉ ላይ የለለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ኣለሀ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሽከላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የዶማት የጨጐጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያጥልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉየስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበዮቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምልክ። ባለወርቅ ጉብርሌ ሎሲዮን።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ። ፧


BALLOON
GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
1-28-7
GOODYEAR
ጉድይር ቱቦ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
5me ANNÉE, № 15

ሐሙስ ሚያዝያ ፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ·ም።
JEUDI 11 AVRIL 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regnér dans son pays la lumière et la paix, a voulu quĕ ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Dîréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም ማፈልገት ወደ ዲረክተሩ ይስታወቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በዓመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር በዓመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፩ኛ ገጽ ተከታይ ።

፮ኛ) የሥራ አከፋፈል።

ሕዝብ እየሰለጠነ ሲሔድ ልዩ ልዩ ዓይነት ሥራውን ይከፋፈላል፤እንዲሁ በየክፍሉና በየወገኑ ሥራውን ዋና ዋናውን ዓይነት ሊለይ ይችላል ። ማለት ለየክፍሉ በታላቅ ሊጠቀም እየንዳንዱ ለዚያ ለመፈጸም ለተሰጠው ሥራ ይሠራል። በዚሁ ሥራ ወደ ታላቅ ልክነት ሊደርስ ይችላል ። አስረጅ ፡ ለሰው እንደ መሐንዲስነትና ሐኪምነት፡ ሕግ አዋቂነትና አስተማሪነት ብቻ መለየየት አልበቃውም። ግን ከመሐንዲስነት የኤሌትሪክ የድልድይ፡ ከሐኪምነት፡ የዓይን፡ የጥርስ፡ የመቀመጫ፡ [illegible] ከሕግ አዋቂነት የንግድ፡ የሕዝብ፡ የወታደር ። [illegible] የቍጥር፡የታሪክ የሽንስ፡ (እውቀት) የቋንቋ፡ [illegible] በትንሽ በትንሽ በልዩ ልዩ ሕዝቦችም ሥራ [illegible] ጿል።ማለት እ[illegible] ሕዝብ [illegible] በሚችለው፤ በአየር ይሁን በመሬት ይሠለጥንበታልና ምሳሌ፡ እንግሊዞች በጠጕር ልብስና በጦር፡መርከብ በመሥራት፤ ፈረንሳዎች የጌጥ የሆነ ነገር ሁሉ በመሥራት፡ጀርመኖች በመኪናዎች በኢንዱስትሪ ኬሚክና መክኒክ በመሥራት፡ኢጣሊያኖች በአርሽና ኤሌትሪክ በመሥራት ፤ መስኮቦች የከብትን ፍጥረት በማጥራት፡ማለትእህል፡ጋዝ፡ሚኔራልና መዓድን፡ሠልጥነውበታል።

እንደዚሁ ወደ ጥንት ተረትና ታሪክ ብንመለከትም ሁሉ ሲቀር እንኳ የወንድና የሴት ሥራ የተከፋፈለ እንደነበር በጥንት ቤተ ሰዎች የሥራን ክፍፍል አናገኛለን።አባት ዱር ሲመነጥር፡ መሬት ሲያርስ፤ እናት ምግብን ስታበስል፡ ቤት ስታዘጋጅ፡ስትፈትል፤ ወንድ ልጅ ከብት ሲጠብቅ፡ ወይም ሲያድን፡ሴት ልጅ ወኃ ስትቀዳ፡ እንጨት ስትለቅም፤ እናያለን፤ እንደዚሁ በዘመ ገለጥ አድርገን ወደ ጉዞዎቻቸው ብንመለከት የተስማማና የተስተካከለ የሥራን ክፍፍል እናይባቸዋለን። አስረጅ፡ በማረፊያቸው ጊዜ፡ አንዱ እቃ ሲጠብቅ፡ አንዱ ወኃ ሲቀዳ፡ አንዱ ዕንጨት ሲለቅም፡ አንዱ እሳት ሲያነድ ፤ አንዱ ቂጣ ሲጋግር ፡ አንዱ ከብቶችን ሲያግድ፡ አንዱ ለሌሊት የሚሆን የከብት ምግብ ሣር ሲያጭድ፡ ሥራውን ይከፋፈላሉ። አለዚያ አብረው በአንድነት ወኃ ለመቅዳት ፡ ወይም ከብት ለመጠበቅ ቢሔዱ ፤ ሥራው ሊከናወንላቸው ይቅርና በአሰቡት ስፍራ ሊደርሱ ባልቻሉም ። ግን ሥልጣኔ እየሰፋና እየደገ ሲሔድ ብዙ ልዩ ልዩ ሥራዎች እየተከፋፈሉ ሔዱ ፤ ሥራዎችና ጥበቦች ተወለዱ። በየመንደሩ [illegible] እናጢ ፤ እንጀራ ጋጋሪ፡ ሥጋ አራጅ ፤ ፋቂ፡ ሸክላ [illegible] ሸማኔ ፤ እሱንም የሚመስሉ ሥራዎች ሁሉ [illegible] የሥራ አከፋፈል የምትባለው ማለት እየንዳንዱ [illegible] በለጠ የሚሠለጥንበት ከኢኮኖሚያ ሀብት እየሰፋ [illegible] እየደጉ ይሄዳሉ። የሥራን አከፋፈል ዓይነት በአንድ አንድ ለይተን በየመንግሥታቱ ሁሉ ለመቍጠርስ ይቄይና በልዩ ልዩ ስፍራና አገርም፡የሥራውን አከፋፈል ለይቶ ልኩን ለማመልከት ብዙ ነው። ማለት በአንዲት መንግሥት ብቻ በየከተማው በየመንደሩ ፤ በየአውራጃው ፤ የተላያዩ ዓይነቶች፤ የንግድ ሥራና ኢንዱስትሪ ፤ እህልና አትክልት አሉባቸው ፤ ይህች የመሬት ሥራ አከፋፈል ትባላለች። ይህም ብቻ አይበቃም ፤ በአንድ ዓይነት ኢንዱስትሪ ብዙ ሠራተኞች ሲገቡ ። ሁሉን አንድ ዓይነት ሥራ አይሠሩም። ግን አንዱ አለቃ አንዱ ተቈጣጣሪ፡ አንዱ ግምጃ ቤት፡አንዱ ጸሐፊ፡አንዱ ማኪኒስታና ጠራጊ፤ አንዱ እሳት ቈስቋሽ ፤አንዱ ተሸካሚ፡አንዱ መሐንዲስ፤ እንደዚህም የመሰለ እየሆኑ ሥራውን ይከፋፈሉና በጣም ይሠለጥኑበታል ። እንዲሁም ሌላ ምሳሌ ብንጨምር በአንዲት


GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
GOODYEAR
ጉድይር
1-28-7

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም ብጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ወጥቤት፥ እሳት ቈስቋሽ፥ ከሰል አመላላሽ፥ እሱን የመሰሉ ሁሉ ብንት አሉ። የዓይነታቸውን ልክ ወደ ብዙ ቍጥር ይደርሳል። ስለዚ ለያንዳንዱ ሠራተኛ አንድ ሥራ ሊፈጸም አደራ ይሰጣል፥ እንደ አደም ዝሚትህ ምሳሌ፥ አንዲት ድፍን መርፌ ለመሥራት አንድ ሰው ራስዋን፥ሁለተኛው ሰው ስለትዋን፥ ሶስተኛው ሰው ሚፍዋን ተከፋፍለው ሲሠሩዋት የተከናወነች ሥራ ትፈጸማለች፥ማለት በጣም ይሠለጥኑበታልና። እንደዚሁ የክፍፍል ምሳሌ የሚሰጠው አሳብ፥የሙዚቃ (ፒያኖ ፎርቴ)፴፮ ዓይነቶች ሥራ፥የሸማኔ (የጥጥ)፪ ዓይነቶች ሥራ፥ ማለት የነዚሁ ቀላሎች ብቻ እንደዚሁ የሚያህል ብዙ የክፍፍል የሥራ ቍጥር አለው። ይህች የሥራን ክፍፍል ቴክኒክ ትባላለች። ስለዚህ በዓለም ሁሉ ማለት ጭርሱን ያልሠለጠኑ ስልባጅ ወይም በርባሬ (አረማውያን) ብለው ኤውሮጳች የሚሉዋቸው ሕዝቦች በቀር ፤ በሕዝብ ሁሉ የሥራን አከፋፈል በጣም እየሰፋና እየሠለጠነ ይሔዳል ። ሚካኤል ተሰማ ።

በሚመጣው ሳምንት ይታማል ።

ሥራን ስለ መውደድ ።

በታሪክ እንደምናውቀው ሕዝብ የሚነግና የሚከብር ፤ አገር የሚለማና የሚበለጥግ ሥራ እንደመውደዱና እንደ መትጋቱ ልክ ነው። ሥራ የሚጠላና የስንፍና ኑሮ የሚወድ ሕዝብም እየሰነፈና እየደኸየ ይሔዳል።ብዙ ታላላቅ የሕዝብ መሪዎች የሆኑ ሰዎችም የሥራን ጥቅም የስንፍና ኑሮን፥ ጕዳት ስላወቁ ሕዝባቸው ለሥራ እንዲነቃና እንዲበረታ ያነቃቁታል በሚቻላቸው ሁሉ ይረዱታል።ይህ በማየትም ደኅና ደኅና ዕውቀት ያላቸው ሠራተኞች የሰውን ድካም የሚያቀል ለሥራ እርዳታ የሚሆን የጥበብ መሣሪያ አወጡና ተከናወነላቸው።ዱሮ በብዙ ሰውና በብዙ ድካም ይሠራ የነበረው አሁን በመኪና በጥቂቶች ሰዎች ያለብዙ ድካም ይሠራል ። በሠለጠኑ ሕዝብ ሥራ እንደዚህ ቀላልና ምቹ መሆኑ ክትጋታቸው የተገኘ ፍሬ ነው። « ብዙ ለሥራ የማይተጉ ሕዝብ ግን ሌላ ሠራተኛ ሕዝብ እየመጣ ወረሳቸው ። »

ግርማዊ ንጉሣችን የሥራን ጥቅም ስላወቁ ሕዝባችን ሥራው እንዲሻሻልና እንደ ዘመኑ ሥልጣኔ በብልሃት ሊሠራ እንደሚያስፈልገውና በብልሃት ሥራ ወደ ብርታትና ወደ ብልጽግና እንዲደርስ ተረድተውት፥ሥራ የሚያውቅና ሥራ የሚያስኬድ ሰው ቢገኝ የሚያስፈልገውን እርዳታ እየሰጡ ያተጉታል አሁን በአገራችን ብዙ ሠራተኞች የሥራ መውደዳቸውና ትጋታቸው እየታየ ንጉሣችን ያከበርዋቸው ብዙ ናቸው ። ዱሮ ግን በእጁ የሚሠራ ሠራተኛ ይህን ያህል ክብር አያገኝም ነበር ።ይህ ብቻ አይደለም ግርማዊ ንጉሣችን የጥበብን ሥራ እንማራለን ለሚሉም የጥበብ ሥራ ትምህርት አቁመው እንዲማሩ ይረዱዋቸዋል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የሆነም ቢሆን ሥራ አውቃለሁ ብሎ የሚችለውን ሥራ ላመለከተ የሚያስፈልገውን እየሰጡ ሥራውን እንዲሠራ ይፈቅዱለታል ።

የሥራና የሠራተኛ ወዳጅ ንጉሥ አግኝተን የሥራ ጥቅም ከታወቀ፥እኛም በትጋት ተንሥተን ለሥራ ከታጠቅን፥ አገራችን ከፍ ትላለች፥ሕዝባችንም ይበለጽጋል፥ የድካማችን በሥራትም ወደስቱ እንመገባለን ።

አገራችን ገና ሠራተኞች የሚጠብቅ ድንግል መሬት ነውና እንሥራ ፤ እንሥራ ፤ እንሥራ . . . .

ስለትምህርትና ስለ አገር ጥቅም ።

ፍጥረት ሁሉ ከትንሽነት ወደ ትልቅነት፥ከጭርነት ወደርዝመት፥ከቅጥነት ወደ ውፍረት እንደሚደርስ። እንዲሁም ዕውቀትና ትምህርት እያደጉና እየሰፉ እየተሻሻሉ በአገር ላይ ሲሔዱ ደስ ያሰኛሉ። ስለዚህ ትምህርትና ዕውቀት የአገር የሕዝብ ለመንግሥት የሚጠቅሙ ስለሆኑ ናቸውና የግድ ተጠንቅቀን እስበንልንደዛቸው ይገባናል፥ሙጀመሪያ ትምህርት አገርን መውደድና እርስ በርሳችን መፋቀር ነው።ፍቅር ከሌለ ምንም ሥራ ለመሥራት የሚቻል አይመስለኝም ትምህርት በፍቅርና አገርን በመውደድ ላይ የተገኘች እንደሆነ አንዲት አድርጎ እንዲጠቅም እንኳንስ ለእናንተ አእምሯቹሁ በትምህርት ለታደሰውና ለኔ እንኳን ለቲኒሹ ታውቆኝ ይህን ለመጻፍ አሳሰበኝ። አሁንም በኢትዮጵያ አንድ አንድ የትምህርት ቤት ተከፍቶልን የኢትዮጵያ ልጆች ያለዝንጋታ ትምህርታችንን እንማራለን የኢትዮጵያ ልጆች ይህንን ያለዝንጋታ ትምህርታችንን መማራችንን አይተው ባለጸጋዎችም እንደ ተቻላቸው በየአገር ግዛታቸው የትምህርት ቤት አቁመው የአገራቸውን ልጆች ከድንቁርና ወደ ዕውቀት፥ከጭለማ ወደ ብርሃን ቢያደርሱት ለነርሱም ምስጋናቸው ለዘለዓለም የማይቋረጥ ለአገራቸውም ጥቅም ይሆን ነበር ። ደግሞ ድኆም እንደድኅነቱ ከወርደሞዙ የተቻለውን ያህል አዋጥቶ የማኅበር ገንዘብ አድርጎ አንድ አንድ የተማሪ ቤት ማቆም ይገባዋል ። እንደዚህ አድርጋችሁ አገራችሁን ኢትዮጵያን ከቲኒሽነት ወደ ትልቅነት ማድረስ ያስፈልጋችኋል ።እነዚያም በትምህርት ቤት ተምረው አድገው ሥራ ይዘው ገንዘብ በገኙ ጊዜ ከዚህ በለጥ ያለ የትምህርትና የእጅ ሥራ ተማሪ ቤት አቁመው አገራቸውንና ያገራቸውን ሕዝብ በትምህርትና በሥራ ጠብቀው ያኖሩታል ። ይህን በታደርጉ ግን ኢትዮጵያ እናታችሁ ሳትወቅሳችሁ አትቀርም የሚመስለኛል ።እጆቿን ዘርግታ አቅፋን የነበረ በሰበሰበችው ጊዜ [illegible] እንጠፋለንም። አገር ነጻ ካልሆነ አገር መግዛት፥ መሾም፥ መሸለም፥ ባለገንዘብ መሆን፥በደኅና ቤት በተድላ በደስታ መኖርም አይገኝም ከገዥነትም ወደተገዥነት መውረድ ይመጣል ከዚህ ሁሉ [illegible] ፍቅርን፥ትምህርትን፥ ሥራን፥ከዚህም ሁሉ አገር መውደድን እነዚህን አራቱን ነገሮች መጠበቅና በየጊዜው ሳናቋርጥ ማሰብ ያስፈልገናልና እንድታስታውሱት በማክበር አቃውቃችኋለሁ ። ትኒሹ ልጃችሁ ኃ ተማ ።

ኤረር ።

በኤረር የሰነበትኩባቸው ጥቂቶች ቀኖች ሳስታውሳቸው እጅግ ደስ ይሉኛል። ኤረር ከድሬደዋ ወዲህ ሁለተኛ ጣቢያ ነው። በቡር ከዚያ ሲቆም ከመውረጃው ላይ እንዳለፉቱ ጣቢያዎች ብዙ መልከም ነገር ይታያል ።

የወሀ ከተማ ሆቴልም ወኪሎች ፈጥነው በደስታ ይቀበላሉ ። ያን ጊዜም ሰውነት ደስ ወደ ሚያሰኝ አየር እንደ ደረሰ ይሰማዋል።በቅሎችም ከጣቢያው እጅግ ስፋርቁ

ቁመው ይጠብቃቸዋል። ከኤረርም ማቢያ እልፍ ሲሉ በስተ ግራብኩል በኤረር ያሉ ቤቶች በበረኻ መሀከል እንዳለ ጨፌ ውልል ብለው ይታያሉ ቤቶቹም በከረብቶች ዙርያ እንደ አውሮፓ አሠራር ሁነው አምረው ይታያሉ ።

ከጣብያውም አንሥቶ እስከ ሆቴሉ ድረስ ኦቶሞቢል የሚያስኬድ የተጠረገ መንገድ አለው ።የመንገዱም ርዝመት ሰባት ኪሎ ሜትር ተኩል ነው ። በመንገዱም ወደዚያው የሚሔዱ ሰዎች የሚቀመጡበት አንድ ኦቶሞቢል አለ ።

የበቅሎችም መንገድ በሌላ በኩል አለ ። እርሱም አቋራጭ ሁኖ በዱር ውሥጥ ነው። ከረብቶቹን አልፎ የኤረር ውሀ ከተማ ሆቴል ይታያል ። ከሁሉ በፊትም መጀመርያ ከሰፊው ሜዳ ላይ ብዙ ሠራተኞች ይታያሉ ። ሁሉም በትጋት ለሥራ ይሽቀዳደማሉ። በኤረር ያለው የዛሬ ሆቴል ትንሽ ነው ። ነገር ግን ትልቅም ባይሆን የተከናወነና አቀማመጡም ያማረ ነው ። ኤረር የውሀ ከተማ ከትልቁ ተራራ ዝቅ ያለ ከጣቢያው ሺ ሜትር ያህል ከፍ ያለ ነው። በሆቴሉ በረንዳ ላይም ቁጭ ብሎ ዙርያውን ሲመለከቱ ብዙ ዛፍና ብዙ ከረብቶች ባጠገቡ ስላሉ፣ ስፍራውም ከፍተኛ ስለ ሆነ ሲያዩት ደስ ያሰኛል ። በረንዳውም በሆቴሉ መግቢያ በኩል አምሮ የተሰናዳ ስለ ሆነ ቀን ሙሉ ቢውሉበት ጥላው ሐሩር የማያስነካና የማይሰለች ነው ። በሆቴሉም አንድ አዳራሽና ስድስት ክፍል ቤት የእንግዶች ማረፍያ አለበት ። ነገር ግን ቤቶቹ የጠዱና የተዘጋጁ ናቸው እንጂ እጅግ ጌጥ የለባቸውም ። ሰፋፊም ሁነው መልክካም አልጋ ያለባቸው ናቸው ። አሁን ላጊዜው ስድስት ክፍል ብቻ አለ፡ውሎ አድሮ ግን ሳይሰፋ አይቀርም እንደ ሚያስፈልግም የተዘጋጀ ምግብና አገልጋዮች የሠለጠኑ አሉበት።

ከሆቴሉም በላይ ባንድ ከረብታ ላይ የተሠራ የግርማዊ ንጉሥ ቤት ይታያል።ነገር ግን በጣም ያማረ ነው እንጂ ሕንፃው እጅግ ትልቅ አይደለም ። በቤቱም ዙርያ እንደ ቀስተ ደመና ሁኖ የተሠራ በረንዳ አለበት ከሆቴሉም ይልቅ የንጉሡ ቤት ያምራል።ቦታውና አቀማመጡ እጅግ ከሁሉ የተመረጠ ነው ።

ከሆቴሉም ወደታች ወረድ ብሎ መልካሙ የኤረር ከተማ ወሀ ምንጭ ይገኛል። ውሀውም የሚፈላ ነው ።ምንጩም ክፍት ሁኖ ውሀው ሳያቋርጥ ይፈልቃል ።

ባጠገቡም አንድ ትልቅ መስኮት ያለው በድንጋይ ግምብ የተሠራ መ ታጠቢያ አለ።እሱም ሁለተኛ ምንጭ ነው፡ውሀው እንደዚያው አንድ ዓይነት ሁኖ በብዙ ይፈልቃል፡ባንድ ደቂቃ ውሥጥ የሚፈልቀው ሁለት ሺ ሊትር ይሆናል፡ግማቱም እንዳይወጣ ተዘግቶዋል ውሀው ከምንጩ በቦምባ እየመጣ ወደ መታጠቢያው ይፈሳል ። ይህም መታጠቢያ ትንሽ ሆኖ እጅግ ንጹሕ ነው በሆቴሉ ዙርያ ንጽሕና እጅግ የበዛ ነው። ሦስት ክፍል የመታጠቢያ ቤት አለ በዚሁም በያንዳንዱ ሁለት ሁለት የብረት ገንዳ መታጠቢያ አለበት።ሲታጠቡበት እንዴት ደስ ያሰኝ ይመስላችኋል?በሦስቱ መታጠቢያ ብዙ ውሀ ስላለበት እንደልብ ለመታጠብ ይቻላል። ከታጠቡም በኋላ ገላ ይለሰልስና ለሰውነት ይቀላል።የውሀው ሙቀት ገና ከምንጩ ሳለ አርባ አምስት ግራድ ያህል ይሆናል ። ከመታጠቢያው በደረሰ ጊዜ ግን ከሠላሳ ሁለት እስከ ሠላሳ ሦስት ግራድ ይሆናል።አሁን ውሀው በፍጥነት እንዲወርድና ሙቀቱ የተሻለ እንዲሆን የውሀው መምጫ በምበ መለወጥ ያስፈልጋል የቦታውም አየር ቀላልና ልዝብ ስለ ሆነ ለሰውነት የተስማማ ነው ከታጠቡም በኋላ ሰውነት ምግብ ያምረውና ደስ ብሎት ተመግቦ ከብስጭት ይድናል።

ከሆቴሉም ወጣ ብሎ ለሽርሽርና ለዓይን የተመቸ ቦታ አለ።ከዚያውም ስስና ሚዳቋ መልቷል ። ከሆቴሉም ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ የግርማዊ ንጉሥ ያታክልት ቦታ ይገኛል ። አታክልቱም ዛሬ የማስፋፋቱና የመሰናዳቱ ጊዜ ነው። አሁን የተጀመረው ከየይነቱ አትክልት፣ ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ በየይነቱ፣ ከእህልም ዓይነት ጥራጥሬ፣በየይነቱ አበባም ተዘርተዋልና ሲያዩት እጅግ ደስ ያሰኛል።በሰፊውም ሜዳ ላይ በየይነቱ ተክል ለምልሞ ይታያል። ተክሉም ከውቼና ጥጥንም የመሰለ በየይነቱ፣ ብርቱካንና ሎሚ፣ ሌላም ልክ የሌለው ያታክልት ዓይነት ብዙ ጸድቀዋል።አንዳንዱም ትልቅነቱ እጅግ የሚያስደንቅ ነው። በዚህ ዓመት እንደ ሎሚና እንደ ብርቱካን ያለ ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ ሁለት መቶ ሺ ያህል፣ ቡናም አምስት መቶ ሺ ያህል፣መቶ ሺ ወይንና ሌላም በየይነቱ ተተክለዋል። ሁሉም ያተከከሉና ያደራረጉ ሥርዓት የሚያስገመጅ ነው።በዚያ ግድም አንድ ሥራ የፈታ መሬት የለም ።

አትክልቱ የሚጠጣውም ውሀ የሚመጣው በቦይ ነው የቦዩ ውሀ የሚነሣበት ወንዝም በድንጋይ ተገንብቶ የተሠራ ነው። (ቁመቱ ዓሥራ ሁለት፣ ርዝመቱ አርባ ሜትር ይሆናል)። ከዚያውም አንሥቶ እስከ አታክልቱ ውሀው የሚሔድበት ቦይ ሁለት ኪሎ ሜትር ከአራት መቶ ሜትር ይሆናል ።

ኤረር የውሀ ከተማ ውሀ የመላበትና ላታክልት የተመቸ ቦታ ስለ ሆነ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ከድሬ ዳዋም ከጅቡቲም ከዓደንም ለመጣ ሰው እንደ ገነት ሁኖ የተመቸ ማረፍያ ይሆናል።ግርማዊ ንጉሥም ይህነን የመሰለ ቦታ እንዲህ አድርገው መቈርቈራቸው ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ ነውና ብዙ ምስጋና ልናቀርብላቸው ይገባል በኤረር ሰንብቴ ጣዕሙን ስላወቅሁት፣ነፋስ መለወጥም ለሚፈልጉ ሰዎች መልካምነቱን ለማስታወቅ ይህነን ጻፍሁ ።

የመስኮብ ሐኪም አልጋ ስኒያቢን



ስለ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ለማ ዕረፍት ።

ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ማርያም በፊት ጎፋን ተሹመው ይገዙ ነበር ።ኋላ ደግሞ ሸዋ ግሚራን ተሹመው ይገዙ ነበር ። በጦርነትም ጊዜ በብዙ ቦታ ላይ በአያሌ ጦርነት ደኅና አድርገው በመዋጋታቸው በጀግንነት የተመሰገኑ ናቸው ።

ዕድሜያቸው ፫ርቢ አንድ ዓመት ሲሆን በ፲፱፻፳፩ ዓ ም መጋቢት ፳፫ ቀን ዓረፉ ።

ብርሃንና ሰላም ለዘመዶቻቸውና ለወዳጆቻቸው ለቤት ሰዎቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ ይላል ።

ስለ ዘበኞች ትጋት

አንድ ሌባ ከሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ ካንድ መኰንን ቤት ሌሊት ለመስረቅ ሒዶ በሩን ሲነቀንቅ ባለቤቶቹ ሌባ መሆኑን ስላተረዱ ጥይት ተኰሰበት የተኰሱትም ጥይት ቀኝ እጁን መትቶት ኑሮ እጁን እንደተመታ አምልጦ አፈንጉሥ እስጢፋኖስ ቤት በታች ካለው መስክ ከወንዙ ውስጥ ተኝቶ ሳለ የ፪ተኛው ኮሚሳርያ ዘበኞች ክፍላቸውን በትጋት ሲጠብቁና ሲፈትሹ በጥይት የተመታውን ሌባ ተኝቶ ስላገኙት በጥይት የተመታበትን ነገር ለማወቅ ሲሉ ይዘውት ወደ ኮሚሳርያ ወስደው ቢመረምሩት ሌሊት ሊሰርቅ የሰው መዝጊያ ሲነቀንቅ በጥይት መመታቱን አምኖ የተመታበትንም በታ አሳይቶ ለቅጣቱ በእሥር ቆይቷል ።

፪ተኛ፡ ነጋዴዎች ከሰፈራቸው የገዙትን ሸቀጥ ወደ ሀገራቸው ለመሔድ ከብቶቻቸውን ሲጭኑ አንዱ ሌባ በድንገት አንዱን በቅሎ ሰርቆባቸው ስለሄደ ባለገንዘቦቹ ከብቶቻችንን እሁን ስንጭን አንዱን በቅሎ ሰረቁብን ብለው ለ፫ተኛው ኮሚሳርያ ዘበኞች ቢያመለክቱ የ፫ኛው ኮሚሳርያ ዘበኞችም በትጋት አጥብቀው ሲፈልጉ ከፊታውራሪ ዓምዴ ቤት አጠገብ በቅሎዋ ፭ ጭልጌ፡፩ ስልቻ፡ ፩ ሸራ እንደተጫነች ከነሌባው ዘበኞች ይዘዉት ከባሻ ወልደ ጊዮርጊስ ላይ ሌባው ቀርቦ ቢጠየቅ መሰረቁን አምኖ ታሥረ።ባለገንዘቦቹም በዘበኞቹ ትጋትና ብርታት በቅሎውን አግኝተው ሔዱ።የአዲስ አበባ ከተማ ዘበኞች በትጋትና በብርታት በየክፍላቸውና በየቦታቸው ስለሚጠብቁ ሌቦች በከተማው ውስጥ ሰርቆ ለማምለጥ አልቻሉም ዘበኞቹም እንደሁኑ ትጋታቸው ዓይነት ወደፊት ጨርሰው ሌባ የተባለውን ሁሉ ሳያጠፉልን፡ ውነትንም ሳያሰፉልን አይቀሩም በማለት የማያቋርጥ ተስፋ አለን ።የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

የትምህርትና የደግነት ብልጫ ።

የደጉ የኢትዮጵያ ወዳጅ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ዲሬክተር ክቡር ሙሴ ቶማዚኒ ቀድሞ ለማስተማር ተመርጠው መጀመሪያ ከፈረንሳዊ፡፪ተኛ በቱኒዚ፡ ፫ተኛ በአልባኒ፡ ፬ተኛ በቱርክ አገር፡ ሲያስተምሩ ይኖሩ ነበር ።

ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ቍጥር በ፲፱፻፲፱ ዓ ም በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈቃድ ላስተማሪነት ተጠርተው ለማስተማር ወደ ኢትዮጵያ መጡ በአስተማሪነትም ደስ አሰኝተው ሲያገለግሉ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ዲሬክተር ተብለው በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ተሾሙ።ከዚያም ወዲህ በዲሬክተርነታቸው ሹም ነኝ ብለው ሳይኰሩ አምስተኛውን የፈረንሳዊ ክፍል በትጋት ያስተምራሉ ።

ግርማዊ ንጉሥም የጠባያቸውን ማማርና ሕገባችንን ማክበራቸውን ለሥራም መትጋታቸውን ስለ አወቁ ምስጋና ያለበት የምስክር ወረቀት ሰጥተዋቸው ነበርና ታላቁ የተከበረው የፈረንሳዊ መንግሥት የግርማዊ ንጉሥንና የቀድሞውንም በየሔዱበት ሁሉ አገር የተቀበሉትን ደስ የሚያሰኝ ሴርቲፊካ (የምስክር ወረቀት) ባየ ጊዜ አፊሲዬ ዳካዴሚ ተብለው ሲጋልም ደፊስ ዳካዴሚ የሚባለውን የማዕርግ ሊሻን ላከላቸውና መጋቢት ፳፭ ቀን ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን ተቀበሉ።ይልቁንም ክቡር ሙሴ ቶማዚኒ የኢትዮጵያ ወዳጅነታቸውን የሚያስረዳ በኤውሮፓውያን ቍጥር የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፰ ፊላቴሊስት በሚባል፡ በአንድ ጋዜጣ አገራችንንና ንጉሦቻችንን የሕዝባችንንም ደግነት የሚገልጽ ጽፈዋል።የደጉ የሙሴ ቶማዚኒን ሽልማት ላዕድሜና ለጤና ያድርግላቸው እያልን እንመርቃለን ።

ሚያዝያ ፪ ቀን በባቡር ተሰፍረው የሔዱ ሰዎች

ፓስፖርታቸውን እንደ ደምቡ ከኢትዮጵያ መንግሥት ቆንሲል ሳያስፈርሙ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው (ተሸሽገው)በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እያታለሉና የድኃውን(በይተዋር)ገንዘብ እየነጠቁ የሚኖሩ ዓረቦችና ሱማሌዎች ስላሉ ከነዚሁ ከአታላዮችና ፓስፖርታቸውን ከጠረፍ ካለ ቆንሲል ሳያስፈርሙ እየተደበቁ መጥተው ተይዘው በእሥር ሰም እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ተመልሰው የሄዱ፡ስማቸው ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው።

አሕመድ ዓብደላ የሚባል ዓረብ፡ዓሊ ዓብደላ የሚባል ዓረብ፡ ኅጂ ቃይድ የሚባል አረብ፡ጀማ የሚባል ሱማሌ፡እነዚህ አራቱ ሚያዚያ ፪ ቀን ማዘጋጃ ቤት በባቡር አሳፍሮ ሰደዳቸው ።

ማስታወቂያ ።

በየካቲት ወር ውስጥ አንዲት ጥቁር ድንክ ውሻ ደረቷና እግሮችዋ ነጭ የሆነች ጠፍታለችና አግኝቶ ላመጣ ሰው እንሚገባ እሰጠዋለሁ ቤቴም ነጋድራስ መኰንን ግቢ ነው ።

ወይዘሮ ጌጤነሽ ።

ከጀርመን ሌጋሲዮን የመጣራድዮ የመጋቢት ፳፯ቀን የዕለት ወሬ

አንጎራ፡ ዕድሜኣቸው በሀያ አምስትና በአርባምስት ዓመት መካከል ያለ ሰዎች ሚስት ሳያገቡ የተገኙ እንደሆን ብዙ ግብር እንዲከፍሉ መንግሥት አዞዋል ።

ሻንጋይ፡ በጄኔራል ቻንግኬይቼክ የሚታዘዝ የናሲዮናሊስት ጦር የሀንኮው ብርቱ ጦር ድል አድርጎ አምስት ሺ ሰው አራት ሺ ጠበንጃ፡ አሥራ ሁለት መድፍ ማረከ ።

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውስጥ መልካም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት የሚፈልጉ ሰዎች ዳውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላችኋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፡ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፡ እንጨት፡ወይም ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ፡ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ሊነጋገር ይችላል።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበር።

የማህበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግር ማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠበቂነት ቆሟል።የማህበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማህበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ፣ የርሻ፣ የኣብ ሬት የደን፣ የማዕድን ሥራ፣ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርበስ ቤት ፊት ለፊት ነው።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡት የሚበላ ዘይት ስለ ፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው።ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለዱም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው።

ሐኪም አምበር።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተ ፲፫ መ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
ሰበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጸር	፩ ከረጂ	፻፸፩ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፪ ብር
፡ ፡ ባለ ድመት ።		፻፵፫ ብር
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፳ ብር
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፶፰ ብር
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፯ ብር
" " ጃፖን		፻፳፩ ብር
ስኳር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፵፯
ባአንድ ብር	፹ ሊሬ ከ ፶፬ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ከ፸፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፰ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈረሰ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቶርቶሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሰደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ አና ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።





COGNAC SbE&A METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መበለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድሬስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተቃላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ሳሎም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔሬቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሸቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ። የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የዶማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ቢሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምልክት ። ባለወርቅ የብርሌ ሱሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆን ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።


GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
GOODYEAR

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድ ዬር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ እያደጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንክሬ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድ ዬር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ፡፡

ጉድዬር

አምስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፮
5me ANNÉE . Nº 46

ሐሙስ ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 18 AVRIL 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፻፲፩ ገጽ ተከታይ ።

፳፪) የመሬት ስጦታ ።

ሁለተኛ አከፋፈል ልዩ ልዩ ዓይነቶች ለሆኑት የሥራ ክፍሎች ጥቅም ለኢንዱስትሪ መትከያ የሚሆን የተከናወነና የተመቸ ስፍራ መምረጥ ነው ። በፊት እንዳመለከትነው እያንዳንዱ ሥራ በብዙ እንዲአፈራ የተሻለና የተስማማ ቦታ ያስፈልገዋል። ማለት በተሰጠው አየርና የፍጥረት ሀብት፡ ወይም መሬት በመላበት ለሰው ኦጋር የማኪና ጉልላት ለማንቀሳቀስ የሚቻለው እንደ ጻና ባሕር ያለ ዘላይ ውኃ ያለበት አገር በሚገኝበትና ጭነት ጭኖ ለማመላለስ የተመቸ ስፍራ በሆነ ነው ።

አንድ አንዱ እቃዎች ከአንዱ ስፍራ በሌላው ስፍራ የተሻሉ ሁነው ይሠራሉ። ይህ ልክና እውነት ነው ፤ እያንዳንዱ ሰው በጣም ይሠለጥንበታልና በአንዳንድ ሥራ ላይ እንደስጦታው ብዙ ሥራ ለመሥራት ይችላል ።

ግን ሁለ ጊዜ አይቻልም ። ሁል ጊዜም እንደዚሁ ይሆናልና ይፈጽማል ። ኢንዱስትሪዎች በጣም አርነት ሲያገኙ የሥራ ክፍፍል ከከተማና ከተማ ፤ ከአውራጃና አውራጃ ብቻ አይደለም ። ከተራራቁ መንግሥታትና መንግሥታትም ነው እንጂ። እንዲሁም ንግድ በመንግሥታት መካከል ለሀብታቸው ማሳደግና ለሥራቸውና ድካማቸው ማሳነስ፡ ወይም መቈጠብ ፤ የተሻለ መንገድ ከመሆኑ በላይ ለወዳጅነታቸው ኀይል ይሰጣልና ያበረታታቸዋል ። እንዲሁም ሕዝቦች ሁሉ ሊደርሱበት በሚገባቸው የሥልጣኔን ደረጃ በአንድነት በጫፍዋ ቢደርሱ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በስምምነት የየፍሬያቸውን ሀብት በንግድና በሥራ እየተለዋወጡ እንደ አንዲት መንግሥት ሁነው

፳፫) የሰው ስጦታ ።

ሶስተኛ የተሻለ ዋና ጥቅም የሥራን ክፍፍል ለሰው በተሰጠው በጣም በሚችለው ሥራ ማስያዝ ነው ፤ ማለት በፊት በመለከትናቸው ኢንዱስትርዮች ሰው በጣም ሊሠራ የሚችላትንና የለመዳትን ሥራ ሊሠራ ይገባል ። እንደዚሁም እንደፍጥረቱ፡ ማለት ጉልበተኛ ሰው ፤ ብረት ፤ ቀጥቃጭ ፤ ደካማ ሰው ፤ ሸማኔ ፤ ወይም ሰፌ ፤ ብልህና አዋቂ ፤ ማኪኒስታ ፤ ኤሌትርቺስታ። ደንቆሮ፤ ደንግያ ሰባሪ ፤ ቍሻሻ ጠራጊ እየሆኑ በየተሰጣቸው ሥራውን ይከፋፈላሉ። በአንዲት ፋብሪካ ውስጥ ብቻ ልዩ ልዩ የመዓርግ ችሎትና ትጋቶች ፤ አውቀቶችና የጥንካሬ ጉልበቶች አሉ ። ለአንድ ሠራተኛ ሰው ከተሰጠው ኃይል ያነሰ ለማሠራትና ጊዜውን ለማበላሸት፡ ወይም ከኃይሉና ከእውቀቱ በላይ ከፍ ያለና የበለጠ ሥራ ለማሠራት አይገደድም። ሴቶችና ልጆችም ብዙ የማያደክሙን ሥራዎች ሊፈጽሙና ቀላሎች ሥራዎችን ልይዙ ይችላሉ። የፋብሪካውም ዋና ኢምፕሬንዲቶሬ ማለት (መሬት ወይም የፍጥረት ሀብት ካፒታል ገንዘብ ሠራተኞችን ሰብስቦ የሚያጋጥም) የእውቀት ሰው ነውና ፤ ሥራውን በሁሉ መንገዶች ያከናውናል። የተተከከሉም ውሎችና የተሻሻሉ ሥራዎችን ይፈጽማል ። እንዲሁ ግምጃ ቤቶች ወጭውንና ገቢውን በትክክል እያሰቡ መዝገባቸውን በጥንቃቄ ይይዛሉ ። የቴክኒክ አለቆች ሥራውን በመከፋፈልና በማዘጋጀት ፤ ሠራተኞችን በማዘዝና በብዙ ጥንቃቄ በመጠበቅ ሥራውን ቀጥ አድርገው ያስኬዳሉ ። ሠራተኞችም በየተመሰከረላቸው ሥራ ለመፈጸም ይከተላሉ ። እንደዚሁም በያለበት ሥራውን በብዙ ሊያፈራው በሚችልና ሌሎችንም የሚጠቅም ለሁሉም የተመቸ የሆነ ሥራን ለፈመጸም ይዘዋል። እንዲሁም ሥራን ለመቈጠብ ብዙ ነገሮች አንድ ጊዜ ሲደረጉ፤ ብዙ ሰዎችን ይጠቅማሉ ። አስረጅ) መኪናዎች በቀላል ድካም ለ

ለምሳሌ)አንድ መጽሐፍ ለማሳተም፤ለጸሐፊው፡ለሰቃሚው፡ ለወረቀትና ቀለም ብዙ ገንዘብና ጊዜ ይፈጃል። ግን አንድ ጊዜ ከተሰናዳ ወዲያ ማተሚያይቱ ብዙ አእላፋት መጽሐፍ እያተመች ከወረቀቱና መጠረዣያው ዋጋ ትንሽ ከፍ የሚል አድርጋ ትሸጠዋለች። ሞኔታም (ማለት እንደ ብርና አላድ፡ ተሙን፡ ቤሳና ልሻን፡ የመሰለ) አንድ ጊዜ ቀርጦ የሚፈስበት ሞዴሉ) የመልክ ዓይነት ዕቃ) ከተሰናዳ ፡ ለመሥሪቱ ቀላልና የሥራ ዋጋው ጥቂት ይሆናል። እንደዚሁ ስሃን ፡ ብርጭቆ፡ ጠርሙዝ፡ ብርሴ፡ ዋንጫ ፡ ወረቀት ፡ ልብስ ፡ ጠመንጃ) መድፍ፡ ጥይት፡ አውቶምቢል ፡ ቢላዋ ፡ እሱንም የመሰሉ ሁሉ አንድ ጊዜ ሞዴሌው ብረቱ ይሁን ሸሀላው የሚፈስበት የዕቃው መልክ ከተሰናዳ ወዲያ ፡ በቀላል ሥራና በትንሽ ድካም፡ በጥቂት ዋጋ ትእልፊት አእላፋት እየተመላለሰ በጭር ጊዜ ሊሠራ ይችላል ። በጥንት ዘመን ከአንድ አውራጃ አገር ወደ ሌላ አውራጃ አገር አንድ ደብዳቤ ለመላክ ስንት ሥራና ድካም፡ ስንት ጊዜና ዋጋ ይፈጅ ነበር። ዛሬ ግን የዓለም ማኅበር ፖስቶች ከቆሙ ወዲህ ከአንዱ አውራጃ ወደ ሌላው አውራጃ ይቄይና ከሞላው ዓለም ጋራ ለመላላክ ስንት ቀላልና የተመቸ ሁኗል ።

እንደ አዳም ዝሚትህ ባህል የሥራን ክፍፍል ማለት ኢንዱስትሪ ይሁን ማናቸውም ሥራ በቀላል ሥራዎች ቢከፋፈሉ ይበልጣል ይሻላልም ። አሁን ይህች የሥራ ክፍፍል ጥቅምና የማይጠቅም ነገር አለባት ።

የኢንዱስትሪ ሥራ ክፍፍል ጥቅም እንደሚከተሉ ናቸው። ፩ኛ በሥራ መሠልጠን (መልመድ) አስረጅ በፊት እንዳመለከት ነው ሠራተኛ ስፒሎ (ራሳም መርፌ) ራስዋን ብቻ የሚሠራ የሚያስደንቅ ብልሀነትንና ሥልጣኔን ያገኝበታል (ማለት ሠራተኞቹ በአንዲት ፋብሪካ ራሳም መርፌ ሲሠሩ ከሠራተኞቹ አንዱ ክፍል ራስዋን፡አንዱ ክፍል ጕድጓዋን፡ አንዱ ክፍል አፏዋን፡ አንዱ ክፍል ስለትዋን፡ቢሠሩ ሥራውን በጣም ይለምዱታልና የተሻለና በፍጥነት በትንሽ ጊዜ ይሠራታል ማለት ነው። እዚሁ አዳም ዝሚትን ገልጦ የሚያሳየው አስረጅ አንድ የብረት ቀጥቃጭ ሰው ፡ ገና ሳይለምደው ራሳም መርፌ ለመሥራት ሲጀምር ፡ በአንድ ቀን ከ፪፻ እስከ ፫፻ የበለጠ መርፌ ሊሠራ አይችልም። ከለመደው ወዲያ ግን ከ፰፻ እስከ ሺ መርፌ ወይም ምስማር በቀን አንድ ሊሠራ ይችላል።በልጅነታቸውና በጕበዝነታቸው ጀምረው ራሳም መርፌ ወይ ምትሠሪ ማኪና የገቡ ግን እስከ ፪ሺ፫፻ መርፌ በአንድ ቀን ለመሥራት ይችላሉ ።

ሚካኤል ተሰማ ።

በሚከተለው ይታተማል ።

ስለ ትምህርት ቤት መቈርቈር·

መጀመሪያ አገርን መውደድና ለርሷም ማሰብ ጠቀሜታዋን ሲፈልጉላት ነው ። የምትጠቀመውም ልጆቿ በሥልጣኔና በውቀት ሲጕለምሱላት ነው ። እንግዲህ በሥልጣኔና በውቀት መጕልመሻው በየአገሩ የተማሪቤት አሠርቶ፡ የተመረጡ መምህሮች፡ቀጥሮ፡ዕውቀትንና ደግ አስተዳደግን፡የእጅ ብልኃትን፡ ለልጆች ሲያስተምሩበት ነው ። ከዚህ ቀደም ብዙን ሰዎች ላገራቸው የተቈረቈሩ ለዚሁ ነገር በብርሃንና ሰላም ጽፈው አስታውቀው ነበር። ነገር ግን ሐሳባቸው ገና አልመላላቸውም ከነዚህም ውሥጥ የጻፉት ሰዎች አንዳቸውም ሥልጣን ያለውና በማዕረግ ላይ የነበረ አይመስለኝም ያገር ፍቅር ስላላቸው ደከሙ እንጂ ። ለእኔ የሚመስለኝ ግ ከድሆች ይልቁንም ሥልጣን ያላቸው መኳንንቶች ይበልጥ በንደዚህ ያለ ነገር ማሰብ ይገባቸዋል ። ማለት በገንዘብ ክብሮ ከሞት መኳንንትና በለጠጋ ይልቁንም ላገሩ ሲል የማይረሳ ነገር በገንዘቡ አሠርቶ የሞተ ይሻላል በሚመጣውም ትውልድ ስሙ ከመቃብር በላይ ሲጠራ ይኖራል፡ማዕረጉንም በየተሾመበት ላገሩና ለሕዝቡ ጥቅም እንዲሠራበት ይገባዋል እንጂ ለራሱ ጥቅም ብቻ አይደለም ። ዛሬ በሌሎቹ አገር ሥልጣኔና እውቀት፡ጥበብ፡ ከልክ አልፏዋል።ሰዎቹ ይኸ ብቻ አልበቃቸው ብሎ ዘወትር አንዱ አንድ አዲስ ነገር አወጣ ሲባል የሰማ እንደሆን መዝገቡን ተመልክቶ (ይዞ ከዚያ ይበልጥ ግሩም ድንቅ አድርጎ ይሠራል። ይኸ ሁሉ ለምን ይመስላችኋል ? አገርን በመውደድና ከሰውነታቸው ስሟ እንዳይጠፋበት ነው።እውቀት ለሰው መብራትና ላገር ጥቅም ነው ። ግን ሳያውቁና ሳያሰውቁ ገንዘብን ያላንድ ምክንያት በመሬት ደብቆ፡ ወይንም በሳጥን ቈልፎ እንዲያው በፍ አገራችንን እንወዳታለን መልካም ነች ቢሉ ከንቱ ነገር ነው እንደጠላት መቈጠር ነው ። ዘወትር የንጉሥን ገንዘብ ምንም ቢብቀው (ቢይዘው)በመጨረሻው ሥራ ሳይሠራበት በታኝ ያገኝበታል ። ግርማዊ ንጉሥ መጀመሪያ አጥብቀው ላገራቸው አሳቢ ስለሆኑ ታላቅ የሆነና ያማረ ተማሪ ቤት በራሳቸው ገንዘብ አሠርተው፡ መምህራኖች ከውጭ አገር አስመጥተው ቀጥረው፡ ብዙኝ ልጆች ያስተምሩበታል። የዚህም ፍሬ ያፈራ ጊዜ ያለጥርጥር ለኢትዮጵያ ጥቅም ነው ። ብርሃንና ሰላም ከተመሠረተበት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አንዳንዱ አንኳን ቢፈጸም የተጻፈው ሁሉ መናው ይሻሻል ነበር።መኳንንቱና በለጠጋው ላገራቸው ያላሰቡ እንግዲህ ማን ያስብ ? ከኛ በኋላ የወጡ (የቃወቁ)አገሮች በሥልጣኔና በእውቀት ከኛ የቀደሙት ይህን ያህል ነው ለማለት አይቻልም ስለዚህ ተከብረውና ተፈርተው በሰላም ይኖራሉ። (ሁለ ጊዜ በመንፈስና በውቀት የተመላው ሰው በሌላቸው ላይ ይከበራሉ)በገሩ ውሥጥ ሥልጣኔ ያልገባበትና እውቀት የሌለው ሕዝብ ራሱን ለመቻል አይበቃም ። ይኸነንም ለማወቅ ታላቁ ንጉሥ ሰሎሞን ያለውን መገንዘብ ነው ። ባለፈው ጋዜጣዬ ሚስትን፡ልጅን፡ ከብትን፡ ትቶ ላገር መሞት በጣም ያማረ ነው ብዬ ነበር። ስለዚህ ነገሩን ብመለከተው ላገሩ የሚጥርና የሚያስብ ያላጋዘ አላንድ ሰው የለም ። ይሁን እንጂ ይኸነኑ ሰው ብቻ ሳይረዱ ቢመለከቱት እርሱ ብረት አይደለም ስለ ሰውነቱ ይደክማል ። በሌሎች አገር ምንም እውቀት ቢገባቸው አንዱ ራሱ ብቻ የሁሉን ሥራ ይዞ ለመሥራት አይችልም። ሁሉም ማለት ሹማምንቱ)በየተሾመበት ክፍል ለሕዝቡና ላገሩ የሚጠቅመውን አስቦ እያወጣ በወረቀት ሲያቀርብለት ይሆናል አይሆንም ብሎ ይመልሳል እንጂ ። አሁንም የተባለውን ምክር ሁሉ ባንድ ጆሮ ሰምቶ ባንድ ጆሮ አለማዳመጥ፡ ለነገ ማቈየት

አገርን የሚጎዳ ነውና ችሎታ ያለው ሰው በፍጥነት በገንዘቡ የተማረ ቤት መክፈትና ደግ ሥራ መሥራት፤ሕዝቡን ማሠልጠን ይገባል"።

አበበ በላቸው ።

የሚገባ ፍርድ ።

መሸሻ የሚባል ሰው ጨርጨር አውራጃ ጉባ ቆርቻ ከሚባል አገር በየነ የሚባለው ባልንጀራው ወደ አማቶቹ ቤት ሲሔድ እኔም አብሬህ እሔዳለሁ ብሎ ተከትሎት ሔዶ ፥ ከሜከ በታ በደረሱ ጊዜ በጠመንጃ ገደለው። ከዚያም አምልጦ ወደተወለደበት አገር ወደምንጃር መጥቶ ኑሮ በዚህ መካከል የጨርጨር አበጋዞች ሰው ገድሎ ወደምንጃር መምጣቱን አስተውቀው ነበርና ግርማዊ ንጉሥ ላገሩ ሹም የበረታ ትእዛዝ አሳፈልው ተያዘ።አገዳደሉንም ከዚያው ከአገሩ ዳኛ ላይ እምና በሚያዚያ ፫ ቀን ከግርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርቦ፤መዝገቡ ተነቦ፤ ሁለተኛ አምሮ ሞት ተፈረደበትና ከዚያ ክፉ ሥራ ከሠራበት አገር ሔዶ እንዲቀጣ ታዘዘ ። የዚህም ሰው አሽከር አብሮ ታሥሮ መጥቶ ነበረና ምንም በይገድል ጌታው ሰው ለመግደል ማሰቡንና መዛቱን አውቆ በምክሩ ተቀላቅሎ ተከትሎ በመሔዱ ታሥሮ እንዲቀጣ ተፈረደበት ።

ደግሞ ዋናው መልከም አድራጎት የሚቼ ወገኖች ምንም በዘመዳቸው ሞት ጉዳት ቢያገኛቸው ደመኛቸውን በመፈለግ ሳይወጡ ሳይወርዱ ፤ ከተያዘም በኋላ ሳይጮላሉ በሚገባ ምርመራና ፍርድ ደማቸው ስለተከፈለላቸው አጅግ ደስ የሚያሰኝ ነውና የሕዝባቸውን ሕይወት ለሚጠብቁና ደሙንም ለሚያከፋፍሉ ንጉሣችን ረዢም ዕድሜ ይስጣቸው።

የባለ ሥራ ትጋት

ሙሉጌታ የሚባል አታላይ ፥ በመጨረሻውም የክፋት መንገድ በመከተሉ ራሱን ያታለለ አሁን በቅርቡ ወራት ያዩ ተሰማ ዓሊን ማኅተም ለሌላ ጉዳይ የታተመውን ከፈረንጅ ቤት ወስዶ በምሳሌው አሠርቶ፤ፈርማውን አስመስሎ ፈርሞ ፩ ጊዜ ፳ ብርና ጐራዴ ከነ አውራረሱ ከወሰደ በኋላ ፤ ደግሞ ወር ሳይሞላው ስሙን አዛውሮ አጐናፍር የሚባል የደጃች ዋቄ ባልደረባ አባቱ ደጅ ሲጠና ሞተ ተበድሮ የበላው መቶ ብር ዕዳ አለብኝና ይክፈሉልኝ ብሎ ለግርማዊ ንጉሥ ቢያመለክት ፴ ብር እርዳታ ይቀበል ብለዋል የሚል ቃል ያዩ ተሰማ አሊን ማኅተምና ፊርማ አስመስሎ አትሞና ፈርሞ ለድርጎኛው ክፍል ጸሐፊ ሰጥቶት ኑሮ ጸሐፊውም እንደ ደንቡ አሰናድቶ ለማስፈረም ወደ ክቡር ባላበራስ ተክለ ማርቆስ ባቀረበ ጊዜ ዕዳው መቶ ብር ከሆነ ሰውዬውም አገልጋይ ከሆነ የግርማዊ ንጉሥ ችሮታ የታወቀ ነው ወይም በሙሉ ይከፈልለት ይሉ ነበር እንጂ የነፍስ ዋጋ ይመስል እንደምን ፴ ብር ይታዘዝለታል፤ከሆነም ለዚህ ሰው ይኸንን ያህል ገንዘብ የሚገባው መሆኑንና አገልግሎቱንም አጠይቀ ዋለሁ፤ ዕዳም እንዳለበት የሚያስረዳ ምስክር ማግኘት የሚያስፈልግ ነውና ሰውዬውም ለነገ ቀርቦ ልጠይቀው ብለው ማዘዣውን ሳይፈርሙ ለጸሐፊው መለሱለት ፤ ይኸውም አታላይ ይኸንን በሰማ ጊዜ ሊያሲዙኝ ነው ብሎ ተደብቆ ወደሐረር ተሳፍሮ ኑሮ ክቡር ባላበራስ ተክለ ማርቆስ ይኸንን ሰምተው ለድሬዳዋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር ላቶ አስቃ ጥቄ ቴሌግራም አሳልፈው ባቡር ሲገባ ተይዞ በፍጥነት ወደ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ ማኅተም በምሳሌ ማሠራቱንና አስመስሎ ፈርሞ ገንዘብ መቀበሉን አምኖ በመጨረሻውም ከግርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርቦ ጥፋተኛ ነኝ አቀጣለሁ ብሎ በገዛ ራሱ ፈርዶ ተገረፈና በእሥራት ሊቀጣ ሐረር ይውረድ ተባለ ።

ጓደኛውም ከዚህ ሸሽቶ ሔዶ ሐዋሽን ተሻግሮ ቦርደዴ ሲደርስ የት ትሔዳለህ ስልክ ተልፏልና ትያዛለህ ቢሉት ሸሽቶ አዲስ አበባ መጥቶ ከከተማ ተይዞ በዘበኛ እጅ ቈይቷል ።

አንባቢ ሆይ እንኳን በአርአያ ሥላሴ ለተፈጠረ ለባለ አእምሮ ሰውና አእምሮ ለሌላቸው እንስሳት ሁሉ ምግባቸውን ፈጣሪያቸው እንዳይነሣቸው እርግጥ ነው። እንግዲህ ሰው ሁሉ በጉልበቱ ሠርቶ የሚበላው የማያስከፋንና የማያበቀጣ የድካም እንጀራ እያለለት በምድርም በሰማይም ጉዳት በሚሆን መንገድ መድከም ምን ነበር ።

የሆነ ሆኖ የግርማዊ ንጉሥ የጽሕፈት ዲሬክተር ክቡር ባላምባራስ ተክለ ማርቆስ በጌታቸው ሥራ ላይ እንዲህ በመትጋታቸው፤ወስላታውንም በብዙ አፈላለግና ምርመራ እንዲቀጣ በማድረጋቸው ብዙ ምስጋና ይገባቸዋል። ለወደፊቱም በረቂቅ ተንኰል ጥቅም ለማግኘት የሚጥሩትን ሰዎች ከዚህ እውቀት እንዲሠውራቸው እግዚአብሔን እንለምናለን ።

ለፎሽ ተሰጥቶት የነበረውን እውቀት ሙሴ ፑዋንካሬ በፈረንሳይ አገር ስም ሆኖ አከበረ ።

እነሆ ኤንባሊድ ላይ ሙሴ ፑዋንካሬ የተናገረው(ዲስኩር) ቃል በእነኝህ በረጃጅም ሳምንቶች ውሥጥ በግዙፍነትም በረቂቅነትም ፎሽ ከሞት ጋር ሲታገል እስከ መጨረሻው ድረስ ፈረንሳይ መሸነፉን አላምንም እያለች፤ ይህ ታላቅ ሰው ጠፍቶ በዓለም ላይ የሚቀረውን ኀዘን አላሰበችውም ነበር ። እነሆ አሁን ያለነው በእውነተኛው ኀዘን ላይ ነው ። አሁንም የጠፋው መብራት ከመሬት ላይ ብርሃኑ መቼም መቼ ቀልነበረ የበለጠ ገናናውና የበለጠ ጎሩው ነው ።

እንደሌሎች መንግሥታቶች የእኛም መንግሥት በታሪኩ ውሥጥ ብዙ ታላላቆች ካፒቴኖች ይቆጥራል።ከእነኝሁም መካከል ብዙዎቹን በታላቁ ቤተ ክርስቲያን አሁን የመጨረሻ እንቅልፉን በያዘበት ፎሽ ያገኛቸዋል ዋና ዋናዎቹን ምግባሮች ሁሉ ይዘዋቸው እንደነበረ እርግጥ ነው ።

የኤንባሊድን ቤተ ክርስቲያን ማንሳርድ በጨረሰ ጊዜ ስለ አንድ ጀግና መልክ ባህሬ) በሱኤ እንዲህ ብሎ ዘርዝሮ ተናግሮ ነበር ጀግንነት ፤ ከፍተኝነት ፤ ደግነት ፥ እውነተኝነት ። ንቃት፤ ዘሊቅነት ፤ የእውቀት እድገትና ፍጹምነት።እርሱ ግን ከዚህ ሁሉ በላይ የካቶሊክ ሰበኪ ለሰው ሁሉ ይበልጣል የሚለው ገና ሊገመት የማይቻለውን ርኅራኄን ይዞ ነበር ።

በታላቅ ሥራ ውሥጥም በመልክም መሥራትና ከእውነተኛ ሥራም በኋላ ክብር እንዲመጣ ማሰብ የሚያስፈልግ መሆኑን ከሰው ሁሉ ይልቅ ያውቅ ነበር ።

ከዚህም ሁሉ ግማሾቹን በራሱ ሐሳብ ከገኛቸውና ግማሾቹን በአሁኑ ጊዜ ባህል በሚደርሰው ነገር ከገኛቸው ሚያዎች ጋራ ደግሞ ሌሎችም ሚያዎች ነበሩት።እነኝሁም ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሰዎች ጋራ ሲያስተያዩት የማይጠፉ በላይነትን ሰጡት ።

ከወዳጅ አገር ለመርዳት ለመጡት ሚሊዮን ለሚሆኑ ወታደሮች እርሱ ሳይፈልግ አለቃ ለመሆን ክብር አገኘ። ሕዝቡን በመላው ወደ ጦርነት መራው፤ ይኸኑም የሚያደርገው በሐሳብ ግዴታ ነው እንጂ በትዕቢት አልነበረም።የውጭ አገርንም መሬት ድል አድርጎ ለመውሰድ አልነበረም ፤ የተያዙትን አገሮች ነጻ ለማድረግ ነበር እንጂ። ከማገልገልም በቀር ሌላ መመኪያ የለበትም ነበር ። የሚገባውን ሥራ ለመፈጸም ነበር እንጂ ሌላ የድካሙን ዋጋ አይፈልግም ነበር። እነሆ ዛሬ የገባንበት ኀዘን ያወቁት ሰዎችና የወደዱት ሰዎች ፤ ሥራውንም ሲሠራ ያዩት ሰዎችና በእርሱ ትእዛዝ እያደሩ ይሠሩ የነበሩ ሰዎች ኀዘን ብቻም አለመሆኑ ስለዚህ ነው። ይህም ኀዘን የፈረንሳይና የሚበልጡት ወገን የሠለጠኑት ሕዝቦች ኀዘን ነው። መሞቱን ሰምተው ከሬሳው ዘንድ ለመድረስ በመጀመርያ ረድፍ የመጡት ሰዎች ታላቁን የመንግሥት ሰው በፈረንሳይ አገር የድል መንሣት መንግሥት አለቃ የነበረውንና የሚያስደንቀውን ክፍ ያለውን ሰው ጦርነቱ ሲጀመር የዘለዓለሙን ሥራት በዓለም ላይ ቁርጥ አድርጎ ያቆመውን ለማግኘት እንደሆነ ተለይቶ ይታወቃል።

አንድ የማይረሳ ምሳሌ ።

ጌቶቹ ሆይ በእነኚህ ቀኖች ለክቡር የሬፑብሊክ ፕሬዚዳንትና ለመንግሥትም ከዚህ ዓለም መሬት ሁሉ ከያለበት የተላከውን ኀዘን ብታዩት ይህ ሁሉ በአንድነት ሁኖ ወረታ ያለው መሆኑንና ማክበሩን ጸጸትና ደግነት አንድጋ ያለበትንም ኀዘኑን ትረዱት ነበር ። እንደዚህ ያለውም ሰው ምንም መጥፋቱ የተጠላ ቢሆን የማይረሳ ምሳሌ ትቶት ነው እንጂ የሔደው ጨርሶ አልጠፋም ትሉ ነበር ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ጥሩነሽ ዕረፍት ።

የክቡር አዛዥ ዘአማኑኤል ባለቤት ወይዘሮ ጥሩነሽ ባላቸው ከሞቱ እስከሁን ድረስ መንኵሰው ሲኖሩ አሁን በ፲፱፻፳፩ ዓ ም ጥቂት ቀን ታመው ሚያዝያ ፬ቀን ዐርፈው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ።

ብርሃንና ሰላም ለልጆቻቸውና ለዘመዶቻቸው፤ ለቤተ ሰዎቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ ይላል።

በባቡር የገቡ ሰዎች ።

(ከአቴና)ሙሴ ኒኮላና ሙሴ ክሎቡሎስ(ከጅቡቲ)ሙሴ አጉስትና አቦከ ዳኒ ከባለቤታቸው ጋራ አዲስ አበባ ለመቀመጥ ሚያዝያ ፯ ቀን ሰኞ ለት ገቡ ።

በባቡር የተሳፈሩ ሰዎች ።

በሚዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት ክቡር በጅሮንድ ዘለቀ የገንዘብ ምኒስትር በባቡር ወርደው ለመመለስ ወደ ጅቡቲ ሔዱ ።

ክቡር ፊታውራሪ መንገሻ ይልማ ወደድሬደዋ ወደ ግዛታቸው ወረዱ ።

ክቡር የኢጣልያ መንግሥት ቆንሲል ሲኞር ፖርታ ከክቡራን ቤተሰቦቻቸው ጋራ ወደ ሀገራቸው ወደ ኢጣሊያ በሚዝያ ፱ ቀን በባቡር ተሳፍረው ሔዱ ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።

ሁለተኛ ማስታወቂያ ።

በአዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ በየመንገዱና በማናቸውም ስፍራ ስለሚገኙት እከካሞችና በሽተኞች ውሾች ለሰው ጉዳት የሚሆን ስለ ሚገኙባቸው አሁን ከሚዝያ ፲ ቀን ጀምሮ ወደ አደጋ ይወድቃሉና ጤና ያላቸውን ውሾቻችሁን እንድታሥሩ ስንል እናስታውቃለን ።

ሁለተኛ ።

ግመል፡በቅሎ፡ፈረስ፡አህያ፡ማናቸውም እንስሳ ሁሉ የሚሞትበት ሰው በፍጥነት ወደ ከተማ ጥዳት ቢሮ ማመልከትነው፤ ሠራተኞች ወዲያው ለማንሣት የተዘጋጁ ናቸው፤ነገር ግን በማናቸውም ስፍራ ጉትቶ ጥሎ የተገኘ ሰው መቀጮውን አሥር ብር መክፈሉን እናስታውቃለን ።

ሚያዝያ ፲ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ።

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ መልከም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ ሰዎች ዱውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፤ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፤ እንጨት፡ወይም ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ፤ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል።

የእርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበር።
የማህበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማህበሩ ዋና ቤት አዲስ አበባ ። የማህበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፡ የርሻ፡ የፋብሪካ፡የደን፡ የማዕድን ሥራ፡ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተነሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፡ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊ.ማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተ፲፫ መ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፶ ብር
ገበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፸፩ ብር
ባለሰይጣን		፻፹፱ ብር
፡ ፡ ባለ ድመት ።		፻፵፫ ብር
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፳ ብር
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፵፰ ብር
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፯ ብር
" " ጃፓን		፻፸፩ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፵፯
በአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፶፩ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ከ፸፩ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ማሪብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC SᴅE&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊሪስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንዲ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና ፲ ጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔሬቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፻ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንፎር ቤት በዲ.ቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበሰል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የሩማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለአንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሚዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።


GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
1-28-7
GOODYEAR
ጉድዬር

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድዬር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድዬር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፯ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 25 AVRIL 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

[illegible] ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው [illegible] ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

[illegible]

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፩ኛ ገጽ ተከታይ ።

፪ኛ የጊዜ መቈጠብ ወይም መጠራቀም። አስረጅ) ጊዜ መቈጠብ ማለት ሌላ ነገር ሳይከተሉ በፊት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አስቀድሞ ማዘጋጀት ነው። ቀጥሎ አንድ ሠራተኛ ፣ [illegible] አንድ ጊዜ ከሥራት መሳሪያ ሲሠራት በብዙ ፍጥነት [illegible] ለመሥራት ይቻላል ግን ልዩ የሆነች ሌላ ዓይነት [illegible] ለመሥራት [illegible] መፍጠንና ጊዜ መቈጠብ [illegible] ብዙ ጊዜ ማጥፋት ፤ ከብዙ [illegible] ይሆንበታል ።

፫ኛ የፍጥረት ሀብት (ማቲሪዬ ፕሪሜ መሬት) መቈጠብ ፤ ሠራተኛው ሲሠለጥን ፥ የማይሳሳት ይሆናል ፤ የፍጥረት ሀብትንና መሬትንም አያጠፋምና አያበላሽም። አስረጅ) አንድ ሸህላ ሳሕን፣ ወይ ደግሞ ብርሌን የሚሠራ ካለመደው ጐበጣ፣ ወይ ጠማማ የሆነበት እንደሆነ ያንን ሲሰብር ፥ ያንን ሲጥል የፍጥረት ሀብትን ይፈጃልና ያበላሻል ። ግን በትክክል ከሠለጠነበት አንዲት ቅንጣት ማቲሪዬ ፕሪሚን አያበላሽም ።

፬ኛ የማኪናዎችን መፍጠር ፥ ሥራን የሚአቀሉና የሚያፋጥኑ [illegible] ለጥቃቅኑም ወሰንና የቍጥር ልክ የለውም ግን ማኪናዎች [illegible] ሥራ ለመሥራት እንጂ ያልተከፋፈሉ ሥራዎችን ለመሥራት ምንም አይችሉም። አስረጅ፤ [illegible] ወይ በበር፤ [illegible] ወይ ወረቀት ፣ እነዚህም [illegible] ስትጋግር ፤ ወይም በጭሩ ስትገረድፍ ፤ ስታልም ፤ አንዲቱ ለአቶሞቢል ሞቶሬ ስትሠራ፥ አንዲቱ ምስማር አንዲቱ ለእግሩ ፥ ጐማ ስትሠራ ባጭሩ ቍጥሩ ለበዛ ትንንሽ ክፍሎች ተከፋፍለው ማኪናዎቹ ሥራቸውን ለመፈጸም ማለት ቤት ይሁን አውቶሞቢል ፤ ባቡር ይሁን መርከብ ፣ አውሮፕላን ይሁን መድፍና ጠመንጃ ፤ ልብስ ይሁን ወረቀት፤ እነዚህም የመሰለ ሁሉ ሊሠሩ ይችላሉ ። ስለዚህ ዋናው የመኪናዎች መፍጠር ጥቅም የብዙዎቹን ሥራ አንድ ሰው በመኪና አገጋይነት በመቻሉ ነው ።

፳፫) የሥራ ክፍፍል ጒዳት።

በዚሁ አሳብ በጸሐፊዎች መካከል ብዙ ክርክር ገብቷል። የአንዱ ወገን ባህል በትክክል እውነት ያልሆነ የሥራ ክፍፍል ጥቅም አልባ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው። ፩ኛ፣ ሠራተኛው ሰው መልኩ መጥፎ ይሆናል ። ስለዚህ ያንን አንድ ዓይነት ሥራ ብቻ እየመላለሰ ዕለት ዕለት ሲሠራ እውቀቱና ብልሀነቱም ጭምር እያደረች፥ ቀስ ቀስ እያለች፥እያነሰች ተሔዳለች። አፍራሽ) ዛሬ ግን እውነት አይደለም ፤ ከ፲፱፻፳፩ ዓ ም (በኤውሮፓ ቍ) የዓለም ኮንፌሬንስ ንግግር ወዲህ፤ ዱሮ በፊት በለፉ ዘመናት ያለ ዕረፍት ረጋ፣ም ጊዜ አለማቋረጥ ይሠራ ነበረ።በአሁኑ ዘመን ግን የሚሠራባቸው ሰዓቶች ብልክ የተቈጠሩ ናቸው። ፪ኛ፤ ሠራተኛ የኤኮኖሚያ ተገዢ ስለሆነ ሌላ ሥራን መሥራት የማይችል ሠራተኛ ቢከፋውም ሊለወጥ አይችልምና የአሠሪው ባሪያ ይሆናል። ግን ይህም ልክ ስላልሆነ አፍራሹ ምላሽ አግኝተዋል። ማለት መኪናዎቹ ተገኝተው ዐሥራ ሁለቱና ከዋሉ ወዲያ፤ ከሚበልጡ ሥራዎች ሁሉ የሚመሳሰሉ አድርገዋቸዋልና አንድ ሠራተኛ ከአንዲት መኪና ወደሌላይቱ አለችግር አልፎ ሊዘዋወር ይችላል።

የዚህ ወደረኞች ሌሎች ወገኖች ደግሞ በበህላቸው እንዲህ

እንዲቱን ነገር ሁሉ ጊዜ መላልሶ እየሠራ በመኖሩ ሠራተኛው ክሌላ ዕውቀት ሳይደርስ ይቀራል። የሌሞንቴይ የሚባል ሰው የተናገራት ስመ ጥሩ የሆነች ቃል እንዲህ ትላለች። በሞላ ሕይወቱ የስፒሉን (የመርፌ) አሥራ ስምንተኛ እጅ መሥራት ብቻ ሌላ የማይችል ሠራተኛ ወደሌላ አገር ተሰዶ ቢሔድ ያችን የለመዳትን ሥራ ካላገኘ በራብና በብዙ ጭንቅ በተቸገረ። ሁለተኛ ደግሞ የፋብሪክ ሠራተኛ ጌታው የከሠረ እንደ ሆነ መኪናውን አቁሞ ቤቱን ይዘጋዋልና አዲስ ሥራን ለመያዝ ሥራውን (ጥበቡን) እስኪለምደው ድረስ የከበደ ጭንቅ ይሆንበታል። ስለዚህ ማኪኒስታ ይሁን ሸማኔ፥ አናጢ ይሁን ሰፊ፥ እሱንም የመሰሉ ሠራተኞች ሁሉ ፥ ከሚያውቁት በላይ መጠባበቂያ ሊሆናቸው፥ ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ዓይነት ሥራ ቢለምዱ ደግ ነው ይላሉ ።

ሚካኤል ተሰማ ።

በሚከተለው ይቃተማል ።

ሳለ መርፌ ።

ባዲስ አበባ ከተማችን ውሥጥ ሳለ መርፌ የሚባል ባህልና ወሬ በጣም ሠልጥኖ በወጣቶች ዘንድ ይታያል። ይኸውም ሳለ መርፌ እየተባለ የሚወራው ቀጥሎ እንደሚጻፈው ነው። ብዙዎች ወጣቶችና ጐልማሶች ሕግ ተላላፊነትን እያፈቀሩ በዘማዊነት ሁናቴ ወደዘላኖችና ሴተኛ አዳሪዎች ዘንድ እየሔዱ ስለሚማግጡና ሴተኛ አዳሪዎችም በየጊዜው በሐኪም ስለማይመረመሩ መጥፎ የሚተላለፍና የሰውን ሕይወት የሚያበላሽ በሽታ እርስ በርሳቸው እያመጡ ይኸውም በሽታ በሰውነታቸው ላይ በታየ ጊዜ ከሆዳቸው ውሥጥ ጨርሶ የሚያወጣና የሚያድን መድኃኒት እንደመፈለግና እንደመጠጣት ሁሉ ሰው በሽታቸውን እንዳያውቅባቸው ለመሠወር ሲሉ ይኸኑ በካላቸው ውሥጥ የወጣውን ሕመም ለጊዜው ለማጥፋትና ደኅና ለመምሰል ወደ ሐኪም ዘንድ ሔደው በሽታቸውን የሚሠውር መርፌ እየገዙ ይጠቀማሉ (ማለት ይወጋሉ)።በዚሁም በመርፌ በተወጉ ጊዜ ሕመማቸው ለጊዜው ይሻላቸዋል።እርሮጌ ጨርቀ በመርፌ በሰፋትና በጠቀቀሙት ጊዜ ለጊዜው ደኅና መስሎ እንደሚታይ ሁሉ ። በኋላ ግን ሴቶቹ በፀነሱና ባረገዙ ወራት ልጆች ሲወለዱ ያበመርፌ ተጠቀቅሞ የተደበቀው በሽታ ለሕፃናቱ ምንም ጤና አይሰጣቸውም ሕይወታቸውን ከማጥፋት በተቀር።ሕፃናቱም በተወለዱ በዓርባ ቀናቸው ያበመርፌ የጠፋፍናቶቻቸው ገንዘብ በእነኝህ ሕፃኖች ላይ ያለ ሥራቸውና ያለ ጥፋታቸው ይጠጣባቸውና ገና በጣም ሕፃን ስለሆኑ ሕይወታቸውን ወደሞት ያደርሰዋል።አንዳንዶቹ ጥቂት የታደሉ ሕፃኖች በብዙኅ ድካምትና በመድኃኒት ብዛት ይድናሉ።ለጊዜው እንኳን ቢድኑ ይህ በሽታ መርዙን ይተክልባቸውና ጥቂት በጥቂት ሲል ይቀሥፋቸዋል።ደግሞ ብዙኅ ሰዎች በዚሁ በሽታ ሁለተኛ ምላሽ ሲወጣባቸው ሰውነታቸውን ሽባና ድውይ ሲያደርጋቸውና መልካቸውን ያበላሻቸውን፥ አፍንጫቸውን የሰበራቸውን እናያለን።ይኸንኑም በሽታ በምን ምክንያት መሆኑን ስንጠይቅ በዚሁ በሽታ ነው ይሉናል።

እንደዚሁ ለመበሰወ [illegible] ሕመም ሁሉ [illegible] ንቅቶና ሰውነቱን ጠብቆ መኖር አለበት [illegible] ይሻላል እንጂ [illegible] ኃይልና [illegible] ማጥፋት አይገባም፤ ለዚህም [illegible] አዳሪዎችንና ሥራቸው እራሳቸውን ማስማማትና [illegible] የተቀመጡትን ሴቶች ሁሉ በየጊዜው በሐኪም ደኅና ጌታ ሳይመረም ማስመርመር ይሻላል እንጂ ዝም ለማለት አይቻልም።ስለምን የሕዝብ ጤንነት ካልተገኘ ኃይልና ጉልበት ብርታትና ድፍረት አይገኝምና።ይኸውም በሽታ በሴቶች [illegible] ሕመሙን እስኪድን ሐኪም እስኪመሰክርለት ድረስ በተለየ ቦታ አስቀምጦ ማስታመም ይሻላል እንጂ ዝም ሊባልና ለመታገስ አይቻልም ስል ለባለሥልጣኖች አሳስባለሁ።

በቀለ ዘለቀ።

ስለ አንድ አታላይ ለማኝ ።

ከግርማዊ ንጉሥ ግቢ በስተኋላ ወደ አራዳ በሚወስደው በራስ መኰንን ድልድይ በላይ ባለው ደፋታ መንገድ አንድ ጠብደል የጉዴላ ጉረምሳ ሁለቱን እግሩን ደም በተነከረ ጨርቅ አሥሮ፡ ሰውነቱንም ሁሉ ደም በሰከረ ቡትቶ ሸፍኖ፡ እግሩን ወደ ላይ፡ ራሱን ወደ ታች፡ ተዘቅዝቆ ተጋድሞ ፥ ፃዕረ ሞት እንደ ተያዘ ሲያቃስት ሠርቶ አልበላ፡ በአካላቴ አልኰራ፡ ስለ ሠርቶ አፍራሹ፡ እንደኔ ከመሆን ያድናችሁ ከትግሬ የመጣሁ በሽተኛ ነኝ የራቴን መግዣ ገንዘብ አያለ በሚያሰዝን አነጋገር ሲለምን መፀወቻውን ያለው ይሰጠዋል፡ የሌለው ግን እያዘነ ቆሞ ሳያስተውለው አይሔድም ነበር ። ከጥቂት ቀንም በኋላ ሚያዝያ ፬ ቀን ቀዳሚ በዚያው መንገድ ብዙ ሰው ወደ ግቢያ ሲያልፍ ከጉደኛው ስፍራ ላይ የሞተ ውሻ ወድቆ ነበርና እርሱም በሽታ የፀናበት እንዲመስል ከውሻው ሬሳ ጋራ አብሮ ተኝቶ ሲለምን በፈረሳቸው በዚያው ጥግ ያለፉ አንድ ትልቅ ሰው የውሻውን ሬሳ ከመንገዱ ለማስወገድ ዘበኛ ይዘው ከዚያ ቢደርሱ ያስተዋሉት ሰው በምን እንደ አወቀው አናውቅም ሲያልፍ ይህ ወመኔ ከዚህ በፊት አራዳ ላይ ሠርቆ ታሥሮ አልነበረምን ደግሞ ከትግሬ የመጣሁ በሽተኛ እያለ ሰውን ያታልል ገባ ወየው ጉድ ሲል ሰምተው ጠረጠሩና ርግጡን ለማወቅ ውሻውን ካስነሡ በኋላ ቀረት ብለው ተኪሳቸው ብር መዘዙና ጣል አደረጉለት። ብሩንም ለማንሣት እጁን ብቅ ሲያደርግ ቢያዩት፡ እሱስ ደኅና ኑሯል።ወዲያውም እግሩን ገልጠው ቢያዩ ምንም የሌለበት ወደላ ነው። ከዚህ በኋላ በከዘራ ቢያቀልጡት እንደ ጮሌ ፈረስ ዘልሎ አመልጣለሁ ሲል ከዚያው ጉረቤትና በየመንገዱም የነበሩ መንገደኞና ዘበኛ ከበው ይዘው ቢጠይቁት ሰርቆ ከመብላት ይሻላል ብዬ ነው አለ። ጀርባውንም ሁሉ ገልጠው ቢያዩ ብዙ ጠባሳና የግርፋት ምልክት ተገኘበት ። ከዚህ በፊት ተገርፈሃልን ብለው ቢጠይቁት አሁን [illegible] ነው እንጂ እንኳን እገሩና ምንም አልለከኝም አለ። ከዚህ በኋላ [illegible] ወደ [illegible]

[illegible] በማለቱ፡ ስርቆት [illegible] የተቀለ[illegible] ነው ።ነገር ግን [illegible] በዚህ ከተማ በ[illegible] የዝተት አ[illegible] የወደቀውን አ[illegible] አሮጌ [illegible] ከራስቸው[illegible] አየለበሱ ይሆን አ[illegible] እጅግ ብዙ ናቸው ። [illegible] የከተማ ጠበቆችቹ (የከ[illegible] እንዲያስቀሩት [illegible] እናደርጋለን።

የብርሃንና ሰላምን ጥቅም መረዳት ።

ብርሃንና ሰላም በየሳምንቱ የሚመጣለት አንድ ወዳጅ ነበረኝ። ከዕለታት አንድ ቀን ተመልከተው ብሎ ቢልክልኝ የጋዜጣን ጥቅም ስላላወቅሁ እንደዘበት አይቼ ነቅፌ መለስኩለት። እሱ ግን በድንቁርናዬ አዝኖ ኑሮ ከየት ዐት ቀን እየመላለሰ ስለላከልኝ አቤቱ ኋላ ወንድሜ ሆይ ይህን የምትልክልኝን ብርሃንና ሰላም ጥቅም አላገኘሁበትምና [illegible] ወደኔ እንዳይመጣ [illegible] ንግግር ስለማናገርሁት [illegible] ብዙን ትጋጽቶ ቆየና መልስ የሰውን ሐሳብ በጣም [illegible] መንቀፍ አ[illegible] ሁኖ ከልተ[illegible] ጥቅም የለበት [illegible] እንደሌለበት ሆኖ ይታያል። [illegible] ቀዘና [illegible] ለብቻህ ትሸከማለህ፤ [illegible] ብትሆን ለራስህ [illegible] ትሆናለህ፡(ምስ ም ፲ ቀ፡ ፲፮) ያለውን ባትመለከተው ይሆናል አለና ፡ ያንኑ በ፲፱፻፳፩ገጽ [illegible] የሚባል የጻፈውን ቢአሳየኝ አጥብቄብ [illegible] የሚጠቅም ነገር ያንኑ ድንቁርና የሚባል በሽ[illegible] ፡ እኔም ከጭለማ ብርሃን ከድንቁርና [illegible] አሰብሁና (መክ ም ፪ ቍ ፲፫) ወ[illegible] ወንድሜን ነገሩን ነቅፌ ስላስቀየምሁት ቶሎ ብዬ [illegible] ወድቄ ይቅርታውን ከደረገልኝ በኋላ መልሼ ይህን ሁሉ የሚአሠራኝ ድንቁርና የሚባል ደዌ ከልጅነቴ ጀምሮ እያመመኝ ቆይቷል ።

አሁን ግን፡ ሥሩን ሰዶ ጨርሶ ሊአጠፋኝ ነው ። ከሰብሁ-ልኝ አይቀር የሚአድነኝን ነገር ፈልግልኝ ብዬ ችግሬን በሚወ-ቀው [illegible] እጅግ አዘነልኝና መልሶ በሽታውን የደበቀ መድኃኒት [illegible] የተባለው ይህ ነው። እነሆ ሁኝ በመ-[illegible] ለኪነገሬን ያልተቀበልከኝ ለተንኰል [illegible] ኑሯል ብሎ መድኃ-[illegible] ድንቁርና ለሚባለው በሽታህ [illegible] ። ዋጋውም ፭ ብር [illegible] እንጂ እንደ [illegible] መድኃኒት በሰ-[illegible] ጊዜ

እንዲአስጨንቀኝ አውቃለሁና እዚሁ አጠገቤ በቀላል ዋጋ ይፈቁንም በቀመሱት ጊዜ ጣፍጠየሚገባ መድኃኒት በመገኘቱ ብዙ ደስ ስላለኝ ለመታከም አሰብሁ ።

የጋዜጣው ማኅበርተኛ እንድሆንም አምስት ብር ከፈልሁ። የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ግን ከዚህ በላይ ያለውን ቃል የሊቅነትና የፍልስፍና ንግግር አለበት ብዬ አልጻፍኩትም ብርሃንና ሰላምን ያለምክንያት አልፈለግሁትም ለማለት ነው። ቢሆንም በሽታዬ ድንቁርና ሆኖ መድኃኒት ፈላጊ መሆኔን እስረድቼ ስለጻፍሁ በነጋገሬ አታፌዙብኝም በማለት ተስፋ አደርጋለሁ ።

ደምሴ ወልደየስ ።

ስለ ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ ወደ ሀገራቸው መመለስ ።

ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ ግርማዊ ንጉሥ ስለነገሡ ደስታን ለመካፈል ከመቀሌ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሰንብተው ነበር ለግዛታቸው የሚያስፈልጋቸውንም ጉዳይ ከቤተመንግሥቱ ከ-ፈጸሙ በኋላ ለመዓርጋቸው የሚገባ ሽልማት ከመንግሥት ተሸልመው ደስ ብሉዋቸው ተሰናብተው ሚያዝያ ፲፬ ቀን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ በባቡር ተሳፍረው ሔዱ አብረዋቸው የመጡ ክቡር ደጃዝማች በላይና ብዙ መኳንንቶችም ከመንግሥት እንደ እየመዓርጋቸው ተሸልመው በደስታ አብረው ሔዱ ። ክብርት ባለቤታቸው ወይዘሮ ሻሸወርቅም ሸኝተው ለመመለስ በባቡር ተሳፍረው ወረዱ ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ ሲሳፈሩም ብዙ ትልልቅ መኳንንትና ሠራዊት እስከ ባቡር ማረፊያ ድረስ ሸኛቸው ። ብርሃንና ሰላም ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ መንገዳቸውን እግዚአብሔር እንዲያቀናላቸውና በደኅና አገራቸው እንዲገቡ መልካም ምኞቱን ያቀርብላቸዋል ።

የኤረር ሆቴል ።

ከድሬ ዳዋ ወደ አዲ አበባ በተዘረጋው የብረት መንገድ አምሳ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር አጠገብ በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ስም የተጀመረው የፍል ውሀ ቤትና ሆቴል ተሠርቶ አልቋል ወደዚሁ ለመምጣት የምትፈልጉ ሰዎች አስቀድማችሁ የመኝታ ቤት (ሻምብር) መገኘቱን እየጠየቃችሁ ለመምጣት ትችላላችሁ ።ሆቴሉ ከተከፈተ የመጡ በፍል ውሀውና በሆቴሉም መሰናዳት ደስ እያላቸው የሔዱ ክቡር አፈ ንጉሥ ከተማ፡ክቡር ቀኛዝማች ፍቅረ ሥላሴ ከተማ፡ ክቡር ከንቲባ ኑሲቡ ከነባለቤታቸው ናቸው።ደግሞ ከፈረንጆችም ሙሴ ኩሙዶሮስ ዋዚኪስ ከጂቡቲ ደግሞ ከአዲስ አበባ ዶክቶሬስ ሲኒአቢን ናቸው።መቸም አዲስ ሥራ አንድ ጊዜ አይዘጋጅምና ሁሉም ነገር እንደሚያስፈልግ ተሰናድቶ በለቀጊዜ የሆቴሉ ስም ይሰየማል ።

አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል ።

የከተማ መንገድ መሻሻል ።

ከአራዳ ወደ ልዑል ራስ መኰንን ድልድይ የሚወስደው ትልቁ መንገድ ዘንድሮ መሃከሉ ለአቶሞቢል መሄጃ ተለቆ ለእግረኛው ግራና ቀኙ በድንጋይና በሸዋ ተሠርቶ እግረኛውም መንገድ ስለተለየለት ያላንድ መሰናክል የአቶሞቢልም አደጋ

ሳያገኘው የተለየ መንገድም ስለተበጀላቸው፣ መንግሥታቸውንና ሥራውንም አስታውሰው ያሠሩትንና አስታውሰው ያመለከቱትን፣ መንገደኞችም፣እያመሰገኑ ሲጓዙ ብዙን ጊዜ ሳይቆዩ ነበር።በመጋቢት ወር መጨረሻ አንድ የጥርስ ሐኪም የሆነ ፈረንጂ በግቢው ውሥጥ ቤት ለመሥራት አስጀምሮ ኑሮ ግቢው ለድንጋይ ማስቀመጫ ስለጠበበው ለእግረኞች መሄጃ በተበጀው መንገድ ላይ ድንጋዩን ሲከምር ሳለ ያዲስ አበባ ከተማ የርስት ብታና የመንገድ ሹም የሚሠሩትን መንገዶች ጐብኝተው ሲመለሱ በእግረኞች መሄጃ መንገድ ላይ ድንጋይ ተከምሮ ስላገኙ ያንን ያስከመረውን ፈረንጅ አስጠርተው ይህነን ድንጋይ በመንገድ ላይ ለምን ከመርክ ቢሉት ቤት እሠራ ነበርና ግቢዬ ስለጠበበኝ ነው የከመርኩት አለ እሳቸውም ሲሆን ከኛ መጥተህ ፈቃድ ሳትጠይቅ በመንገድ ላይ ለማስቀመጥ አይገባህም ነበር።አሁንም እስከ ፫ ሰዓት ድረስ ይኸነን ድንጋይ ከመንገዱ ላይ እንድታነሣ ብለው ጥብቅ ትእዛዛቸውን ስለነገሩት፣ያም ፈረንጅ የርስትና የመንገድ ሹሙ በተሰጣቸው ሥልጣናቸው ማዘዛቸውን ትእዛዙን ተቀብሎ፣እሱም በስሕተት ማድረጉን አውቆ፤ያንን ድንጋይ በብዙና ጉራጌዎች አግዞ አሥነሣ።ይኸውም በፍጥነት ትእዛዝ ፈጽሞ በተሰጠውም ሰዓት ማስነሣቱ ላዛዦችና ለታዛዦች ሁሉ በጣም ደስ ያሰኛል።እንዲሁም በመንግሥት ሥራ ላይ ያላችሁ ሁሉ ያለቃችሁን ፈቃድና ትእዛዝ፣መጠበቅና መፈጸም ነው።ካለቃውና ከበላዩም የሚጠላና የሚያንጐራጉር ከውርደትና ከግዞት በቀር ምንም ትርፍ እንዳያስገኝ ይኸው በየጊዜው የምናየው ያስረዳናልና ከገዢውና ከበላዩ ተስማምቶና ፈቃድ ፈጽሞ መኖርም ክብሩንና ማዕረጉን እየሥጨመረ ከመሄድ በቀር የሚያጐድለው ስለሌለ ከበላያችሁ ያሉትን ሹሞች ያለመናቅና ትእዛዛቸውንም አይሆንም ያለማለት ፈቃድ መፈጸም ነው።ንጉሥና እግዚአብሔር መርጦ ከበላያችሁ ሾሞላችኋልና ። በቀለ ዘለቀ ።

ማስታወቂያ ።

በሚያዝያ ፲፯ ቀን ሐሙስ በ፫ ሰዓት በእንጦጦ መውጫ መንገድ አጠገብ ያለው የስዊዲሽ ኤቫንጌሊካል ሚሽን ተማሪ ቤት ይከፈታልና ተማሪ ቤት ለመግባት የሚፈልጉ ልጆች በዚያ ቀን እንዲመጡ እናስታውቃቸዋለን ። ፔ. ሹርኔ ።

ሞካተም ከተባለ የግብጽ ጋዜጣ የተገለበጠ ።

በመጋቢት ፴፩ቀን የታተመው ሞካተም የሚባለው ጋዜጣ በግብጽ አገር በምስራቃዊ ቋንቋ ትምህርት ቤት ቀድሞ የኢትዮጵያውያን ቋንቋ ያስተማሩበት እንደ ነበረ ሲናገር፣ በቅርብ ቀን ኢትዮጵያውያንም ለትምህርት መጣጣራቸውን ያመለክታል።

ጋዜጣውም እንዲህ ይላል፡ በኢትዮጵያ ትምህ ት እየሰፋ ይሔዳል። ኢትዮጵያኖችም ልጆቻቸውንም ወደ አውሮፓ ይልካሉ ። እነሆ ለምሳሌ ፤ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የብላቴን ጌታ ልጅ ሲራክ ኅሩይ እጅግ ብልህና፣ በቪክቶርያ ኮሌጅ ከሚማሩት ተማሪዎች ሁ ከከል መጀመሪ ነው፡

Le Journal MOKATTAM [illegible] Mars parlant pour l'enseignement de la langue Ethiopienne autrefois en Egypte dans l'école des langues orientales fait allusion aux efforts déployés par les Ethiopiens ces derniers jours pour l'instruction.

L'enseignement en Ethiopie va, dit-il, en progrès car les Ethiopiens envoient leurs enfants **en** Europe. Voilà par exemple Sirak Heronye, fils de Belatin Gueta Ministre des affaires Etrangères d'Ethiopie est très intelligents et le premier parmi les étudiants de Victoria College; il compte aller à Oxford pour faire ses études.

ከጀርመን ሌጋሲዎን የመጣ ራዲዮ የሚያዝያ ፱ ቀን ወሬ ።

በርሊን ፤ የአማኑላህ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንደ ማንም ሆኖ ጐብኝቶ ከሞስኮው መጣ

ፔሻዋር፤ አማኑላህ ድል እያደረገ እንደሔደና የሐቢቡላህ ተከታዮች ሁሉ ወባት እንደገቡ ይወራል ።

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የመጣ ራዲዮ የሚያዝያ ፲፩ [illegible] ቀን ወሬ።

በርሊን፤ [illegible] እንደሞተ ይወራል ።

ከሌስ ፤ በእንግሊዝ አገር የፈንጣጣ በሽታ ገብቷል። አሁን በፈረንሳዊ በር ለማለፍ የሐኪም የምስክር ወረቀት ያስፈልጋል።

ማስታወቂያ ።

በግርማዊ ንጉሥ ማተሚያ ቤት የታተመ የዮግራፊ ከርታው በልዩ ልዩ ዓይነት ቀለም ተሠርቶ ቃላቱ ሁሉ በማርኛ ተጽፎ በመጽሐፉ ውሥጥ እየገባ ከመጽሐፉ ጋራ በሰባት ብር ይሸጣል።

ይልቁንም የተከበሩ መኳንንቶች አገሬቸውንና በጉረቤታቸው ያሉ የድምበረተኞቻቸውን አገር ማወቅ ያስፈልጋቸዋልና እየገዙ የጅዮግራፊን መጽሐፍ እንዲያነቡ እናሳስባቸዋለን ።

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ [illegible] አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ [illegible] ስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን [illegible] ወደ አዲስ ዓለም፣ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ [illegible] ይም ማናቸውንም [illegible] በቀላል ዋጋ [illegible] በስተቀር [illegible]

[illegible] የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበር።

የማህበሩ ዋና ገንዘብ [illegible] ሚሊዮን ብር ። በግር [illegible] ንግሥት [illegible] በግርማዊ ንጉሥ [illegible] መኰንን ጠባቂነት [illegible] የማህበሩ ዋና ቢሮ አዲስ አበባ ። የማህበሩ ሥራ [illegible] የንግድ፡ የርሻ፡ [illegible] የማዕድን ሥራ [illegible] የሕዝብ ጥቅም [illegible] ሥራ [illegible] ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቀባኑግ (ዘይት) መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡት የሚበላ ዘይት ስለ ፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙ ም በጣም የተስማማ ነው፤ ለሰውነትም ጤና የማይከፋ መሆኑ የተፈተነ ነው፡፡ ፊ ማበዶሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

[illegible] አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም በፍሬ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ አሊ ሱቆች እንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፪ ብር
ያበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፺ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፺ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጂ	፻፸፪ ብር
ባለሰይጣን		፻፸ ብር
: : ባለ ድመት ።		፻፶፩ ብር
: : ባለአህያ ።		፻፷ ብር
: : ባለሳቢ ግመል ።		፻፺ ብር
: : ባለ አንበሳ አሜሪክ		፻፭ ብር
“ “ ጃፓን		፻፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፷ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፭
ባአንድ ብር	፷ ሊሬ ከ ፺፩ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ከ፲፩
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፷ ብር

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይፈርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል [illegible] ባለማገገሚያና ባለባቱሬ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል [illegible] እግሩ ላይ መጠበቂያ [illegible] ለለው [illegible] በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚሁ [illegible] በተለየ ወኪል [illegible]



[illegible] የአቶሞቢል ዘይትና የሚሪከን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከግሪክ አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከግሩም [illegible] የተመሰከረለት ዝናው [illegible] ማቲክ ኬምርኮፍ ቤት ይገኛል።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሁ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል—ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ጊዮምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፈረንሳይ [illegible] በማድራስ በአደንና [illegible] ችና፣በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በየይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በየይነቱ ቀባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬስ

[illegible]

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬስ ፋብሪካ ነው።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷነት ፈቃድ የተቀበለ።

ΣΥΜΒΟΛΟΝ ΤΟΥ ΕΡΓΟΣΤΑΣΙΟΥ

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ሩለሠ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፓር ቤት በዲቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የድማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት። ባለወረቀት ባለምኒልክ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድ ይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልቡ ያስኬዳል በድጥም ሰፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድ ይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።


GOODYEAR
ALL WEATHER
GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
GOODYEAR
ጉድ ይር

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
5me ANNÉE № 18

ሐሙስ ሚያዝያ ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 2 MAI 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም ለሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፻፺ ገጽ ተከታይ ።ምዕራፍ ፳ ።

፳፱) መኪናዎች የሥራ መሣርያ ።

በሥራ አኳኋንና አከፋፈል ዕውቀት በላይ እነዚህፍሬን የሚያሳድጉ መሣሪያዎች በሰውና በእንስሳ ኃይል ፈንታ ማወቅ ያስፈልጋሌ ። ለምሳሌ) ብረትን ለማቅለጥ ወናፍ ፤ ዕንጨትን ለመቍረጥ ምሳር ፤ እህልን ለመዝራት ማረሻ ፤ ለመሰብሰብ ማጭድ ፤ እሱንም የመሰሉ ሁሉለሰው ኑሮ ያስፈልጋሉ ። መሣሪዎችም የተስተካከሉ ሲሆኑ የሥራ አሠለጣጠን በጣም ያድጋል።

መሣሪያዎች ተከታትለው የተፈጠሩ ፍሬ ናቸው።ቀስ ቀስ እያሉ በብዙ መቶ ዓመታት እየተስተከከሉና እያደጉ መጡ። ሽህሞሌር የሚባል ሰው የደንጊያ መዶሻ ከተፈጠረ ፻ሽ ዓመት አልፈዋል እንዳለ።ግን የጥንት ታሪክ በጣም ጨለማ ነው።በእውነት የመሣርያ መጀመርያዎች ግን የእርሻ መሣርያዎች እንደሆኑ በግልጥ አለጥርጥር የታወቀ ነው።እርሻ የሥልጣኔ ጋሻ እንደተባለ።

ከመካከለኛ ዘመን ጀምሮ በውኃ የሚነቃነቁ መኪናዎችን መፍጠር ተቻለ። ግን ከማናቸውም ሊስተካከል የማይቻል የኤኮኖሚያ ጥቅም አሁን በዘመናችን የወጡ የባፖርና (ጢስ) የኤሌክትሪክ ሥራ ናቸው።እነዚያ በእጃችን ፋንታ የሚሠሩትን እነመዶሻን የእጃችን አጋዥና ጥቅም ብለን ልንጠራቸው እንችላለን ። እነዚያ ማቅናትና መጠበበቅ፥ ማስኬድና ማቆም ብቻ የሚያስፈልጋቸው ግን መኪናዎች ብለን እንጠራቸዋለን። መኪና የሥራ ሁሉ መሣርያ ነው ። በእውነት በትልቅ ልክነት ማናቸውም አእምሮና ዕውቀት(እንደ አውቶሞቢል መኪና) የፍጥረትን ኃይል የሚያበረክት ነው።(አስረጅ) ኤሌክትሪክ የጋዝ ሙቀት እሱንም የሚመስል ሁሉ ።

መኪናዎች ለሰዎች ትልቅ ጥቅም አመጡ፥ የማይቻሉ የስዌጽና ፓናማ ። የሰውን ሀብት እጅግ በብዙ አሳደጉት ። በቀድሞ ዘመን ባሮች ምትክ ሆኑ ። (ከሁሉ በፊት ብራሲሌ አሜሪካ በሽ ፰፻፹፰ ዓ ም በኤው ቀኍ ባሮችን አርነት አስወጣ)።

ግን በፊት ዘመን የእጅ ሠራተኞች ደመወዛችን ያሳንሱብናል ሲሉ በማኪናዎች መፈጠር የተነሣ ቀንተው ብዙ ተናደደው ነበር ። እውነት ነው።በመጀመርያ ጊዜ መኪና እነዚያን የእጅ ሠራተኞችዋን ትጐዳቸዋለች ። (አስረጅ) በእሳት ላቦት የሚሔድ በቱሊ (ወይም ሞቶስክፎ የሚባል ጀልባ ቀዛፊ)ኋላ ግን የእጅ ሠራተኞች ሁሉ ሥራ ሊይዙ ይችላሉ ። ከሁሉ በፊት ማኪናዎችን በመፍጠር የሸቀጥ ዋጋ ዝቅ ይላልና ብዙ እቃዎች ለማፍራት ይፈልጋሉ፥ ስለዚህ ብዙ የእጅ ሠራተኞች ሊጨመሩ ይችላሉ ። ሁለተኛ ደግሞ ኢምፕሬን ዲቶሬን ብዙ ያተረፈ እንደሆነ ገጋሮች ወይም ጨራሾች ብዙ ቍጥብ ትርፍ ያገኛሉ ። እነዚያ የመቈጠብን ካፒታል ወይም ገንዘብ በሌላ ሥራ ሊይዙ ይችላሉና እንደ ገና ሌሎች ሠራተኞችን ይጨምራሉ ። ባጭሩ መሬት ማቴሪየ ወይም የፍጥረት ሀብት ካፒታሌ (ገንዘብ)ሠራተኛን የሚያጋጥም ኢምፕሬንዲቶሬ የሚባል ዋነኛ ሰው ወይም ማኅበር በመጀመርያ ማኪናዎችን ተክሎ ሲያቆም የእጅ ሠራተኞችን እያስወጣ ያሳንሳቸዋል።ኋላ ሥራው እየበዛ ሲሔድ ግን ያወጣቸውን ሠራተኞች ይጠራቸዋል ፤ እንደ ገናም ሌሎች ሠራተኞችን ይጨምራል ። ለምሳሌ ሚሊዮን አፍርቶ ፶ሺ ያተረፈ እንደ ሆነ ፵ሺውን ለራሱ ያደርገዋል።፲ሩን ሺ ወደ ባንክ ያገባዋልና እንደ ገና ሌላካፒታል ሁኖ ይሠራል።(አስረጅ) የፊት ዘመን መጻሕፍት ጻፊዎችና የአሁን ዘመን መጻሕፍት አታሚዎች ሥራ በመጨረሻ ማኪናውን ለመሥራት ብዙ የእጅ ሥራ ያስፈልጋልና ብዙ ሠራተኞችን ልትይዝ ትችላለች ።

ሚካኤል ተሰማ።

በሚከተለው ይቀጥላል ።

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሕማማቱ በዓል ክብር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው በመጋቢት ፳፯ ቀን ነው፤ የተነሣውም በ፳፱ ቀን ነው።ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጥንት በተሰቀለበት በአይሁድ ፋሲካ እንዲሆን ብለው የተወሰነ ሥርዓት አድርገዋል ። ስለዚሁ እንደ ባሕረ ሐሳቡ ቍጥር እየተዘዋወረ አንድ ጊዜ በመጋቢት አንድ ጊዜ በሚያዝያ ይውላል ። የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማት መታሰቢያ ሰባት ቀን በዓል ታደርጋለች ። በዚሁም በሕማማት ውሥጥ በገዳም፤በደብር፤በገጠር፤ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ካህናቱና ሊቃውንቱ ሁሉ እየተሰበሰቡ ከመጻሕፍተ ብሉያትና ከመጻሕፍተ ሐዲሳት ፤ ከመጻሕፍተ አዋልድም ተጠጣጥቶ የተጻፈውን ግብረ ሕማማት የሚባለውን መጽሐፍ በየሰዓቱ እያነበቡና እየተረጐሙ በዓሉን ያከብራሉ።ይልቁንም ከነዚሁ እጅግ የሚከበሩት ቀጥሎ የተጻፉት ናቸው። ከትንሣኤ በፊት ያለው እሑድ ሆሣዕና ይባላል።ይህም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ የከተማው ሕዝብ የወይራና የዘንባባ ቅጠል ይዘው በየመንገዱ ልብሳቸውን እያነጠፉ፤በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ሆሣዕና በአርያም፤ እያሉ የተቀበሉት መታሰቢያ ነው። ጸሎተ ሐሙስ፤ ጌታችን በማግሥቱ ሊሰቀል ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ እንደ አይሁድ ልማድ የፋሲካ በዓል ያደረገበት መታሰቢያ ነው ። በዚሁም ቀን ለራት ከቀረበው ኅብስትና ጽዋ አንሥቶ ኅብስቱን ሥጋዬ ነው ፤ ጽዋውን ደሜ ነው፤ ይህነንም ለዘለዓለም መታሰብያዬ አድርጉት፤ ብሎ ሐዲስ ሥርዓት ሠርቶላቸዋል።ዛሬም በየቤተ ክርስቲያኑ የምንቀበለው የጌታችን ሥጋና ደም (ቅዱስ ቍርባን) ከዚያ ቀን ጀምሮ ሲያያዝ የመጣው ነው ።



ዓርብ ዕለት የጌታችን የስቅለቱ መታሰቢያ ነውና ሕዝቡ ሁሉ ተሰብስቦ፤ቤተ ክርስቲያኑ በልዩ ልዩ በሚያምር ጌጥ ተሸልሞ የጌታችን የስቅለቱ ምስሌ ተደርጎ፤ሕዝቡ ሁሉ ኪርያላይሶን እያለ ሲሰግድ ይውላል ። ይኸውም ስግደት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሙስ ማታ የደም ወዝ እስኪወዛ ድረስ የሰገደው መታሰቢያ ነው ።በአሥራ አንድ ሰዓት ቄሱ ሕዝቡን በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ፵፩ ፵፩ እንዲሰግዱ ያዞዋል ። ይኸውም የጌታችን የመገረፉ መታሰቢያ ነው ። በኢ

ሥራ ሁለት ሰዓት ንሴብሖ እየተባለ፡ክብሮ እየተመታ፡ደስታ ይደረጋል።ይኸውም ክርስቲያን ሁሉ ጌታችን ጠላትን ድል ነሥቶ፥መርገምን አጥፍቶ፤ ከዲያብሎስ ባርነት፥ ከገሃነም እሳት ወህኒ ቤት ፤ እንዳወጣው ተሰምቶት ደስ ስለ አለው ነው ። ቀዳሚ ገብረ ሰላመ በመስቀሉ፡ ትንሣኤሁ አግሀደ፤ እየተባለ ለየሰዉ ሁሉ ቄጠማ ይታደላል። ይኸውም ኖኅ የላካት ርግብ የማየ አይኅን ማቋረጥ ስትነግረው የለመለመ ቅጠል ይዛለት እንደ መጣችና የማየ አይኅን ማቋረጥ እንደ ተረዳ፤እኛም በጌታችን ደም ፡ ኃጢአት እንደ ጠፋልን ስለ ተረዳን ነው ። እሑድ ሌሊት ሰው ሁሉ በነፍስ መብራት ይዞ ትንሣኤከ ለእለ አመነ፡ ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ፡ እያለ ቤተ ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ ይዞራል ። ይኸውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከጨለማ ወደ ብርሃን ፡ ከድንቁርና ወደ ዕውቀት ስለ ወጣን የደስታ ምልክት ነው ።

ኢየሱስ እውነተኛ መድኃኒት ነው።

ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በፊት እስራኤልን ለማዳን ብዙ መሳፍንትና ነቢያት በየጊዜው ተነሥተው ነበር፥ እውነትም እነዚያ ከብዙ ሥጋዊ መከራ እስራኤልን ያድኑ ነበር ። ስለሆነ ግን እነዚያ ብዙ ረዳት እየፈለጉና ፤ ብዙ ደም እያፈሰሱ ነው ። ይህ እውነተኛው መድኃኒት ኢየሱስ ግን ከመላእክት አለቆች አንዱን አስመጥቶ በአንድ ደቂቃ ጠላቶቹን ማጥፋት ሲቻለው ራሱን ለሞት አሳልፎ፥ ደሙን አፍስሶ ከጠላቶቹ ያንዱን ሰው ደም ሳያፈስ ሊያድነን ፈቃዱ ስለ ሆነ የመጣበትን መከራ ሁሉ በትዕግሥት ተቀበለ ። ከሽከሮቹም ወገን ሰይፍ መዞው ሰውን እንግደል ቢሉ ተቈጣቸው ። ይልቁንም እውነተኛ መድኃኒት የሚያሰኘው የአይሁድ ወገኖች ያን ያህል ሲመቀኙትና ሊገድሉት በየጊዜው ሲዶልቱበት እርሱ ሙታናቸውን ከማንሣትና ሕሙማናቸውን ከመፈወስ ፤ ለምጻሞቻቸውንም ከማንጻት፥ ለነርሳቸውም የወንጌልን የምስራች ከመስበክ፥ አይቦዝንም ነበር ። በየሔደበትም ቦታ በብዙ ልዩ ልዩ መከራ ሲሣቀዩ ያገኛቸውን ይህ እስራኤላዊ ነው፥ ይህ አረማዊ ነው ሳይል፥ ሁሉን ያድናቸው ነበረ። ይህም እውነተኛው መድኃኒት እንዲያሰኘው በብዙ ሰዎች ሕሊና የተረዳ ሁንዋል ።

አንድ ምሳሌ ፤ የዚህ ዓለም ጌታ ይወደው የነበረ አሽከሩ ቢበድለው በግዞት ቤት ያገባዋል ፤ ምሕረት ባደረገለት ጊዜ ግን ከእሥራት ፈትታችሁ አምጡት ብሎ አሽከሮቹን ልኮ ያስመጣዋል እንጂ እርሱ ራሱ ወደ ወህኒ ቤት ሔዶ ፤ ሰንሰለቱን ፈልቅቆ፥ አይፈታውም። ደግሞም ወደ ጦርነት ቢሔድ ጊዜ አሽከሮቹ አይዞህ ጌታችን እኛ እንሞትልሃለን፡ከጠላትም እናድንኃለን ሲሉት ደስ ይለዋል እንጂ፥ አይዝዋችሁ አሽከሮቼ፤ ሰውነቴን ስለናንተ አሳልፋለሁ፤ አይላቸውም ። ነገር ግን ምንም እንኳ ቢወዳቸው ለጊዜው ደስ የሚያሰኝ ሽልማት ይሸልማቸዋል ። እውነተኛው መድኃኒት ኢየሱስ ግን፥ ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ ፤ ቸር ጠባቂም ስለ በጎቹ ቤዛ ነፍሱን ያሳልፋል፤ እያለ በእውነተኛው ቃሉ እንደ ተናገረ ፥ ሰውነቱን ስለኛ ቤዛ አሳልፎ ሰጥቶ ፤ በትንሣኤው አዳነን ። አሁንም ወገኖቼ ሆይ ይህን እውነተኛውን መድኃኒት ለማግኘት፣ በእውነተኛው መንገድ ተመርተን ለመሔድ ደግ አእምሮ ሰጥቶ ላመቱ ያድርሰን ።

የልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከአዲስ አበባ ወደ መቃዲሾ መንገድ መሔድ።

በጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም የልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ካዲስ አበባ ወደ ኦጋዴን በሐረሩና በሲዳሞ፥በባሌ፥ አድርገው ሔዱ።አኳኋናቸውና የሰውነታቸውም መልካምነት ከዚህ ቀደም በጋዜጣ ተጽፎ ነበር። ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ መልካም ሰው መልካም ጌታ ናቸው ። በኢትዮጵያ ግዛት በመንገድ ሲጓዙ ከልጅም ሆነ ከመኳንንት በተገናኙ ጊዜ፥ ተበቅሎ ወርደው ፥ ባርኔጣ አንሥተው ፥ በጃቸው ሰላምታ ሰጥተው፥ መንገዳቸውን ይጓዛሉ ። በጌትነትም ምክንያት ሥራን መኰብኘት አይተውም ። ነገር ግን በየሥራው ዓይነት ሁሉን ይጐበኛሉ ። ደግሞ እንኳን ተከታዮቻቸውንና ማንም ሰውም ቢሆን በትሕትና እንጂ በሚያስቀይም ነገር ማየት የለባቸውም፤ ደግነታቸውም የበዛ ነው። በሐረሩ አውራጃ አሰላ በልጅ አበራ ገብረየስ ቤት በጥቅምት ፳፱ ቀን እንደ ተቻለው አሰናድቶ ቢጠራቸው ከድንኳናቸው ሔደው ከቤቱ ምሳ ተጋበዙለት። እሱም በፈረንጆች ልማድና በማለፊያ ጠረቤዛ አሰናድቶ ነበረ። ሺፓኝ ከተጠጣ በኋላ በመልካም መርቀውት ሔዱ። ሰፈርም የተደረገው በሱ ደጅ ነበረና የዘበኛ አለቆች የሆኑትን ሁሉ በመልካም ጋበዘ።በሐረሩ፤ ገደብ ከሚባለው አገር በጥቅምት ፳፰ ቀን በመንገድ ስንጓዝ የቁብሳ ቅዱስ ገብርኤል ነን ብለው ሁለት ቄሶች መስቀል ይዘው ቢቀበሏቸው ተበቅሎ ወርደው መስቀሉን ተሳልመው አመስግነው መንገዳቸውን ጀመሩ።

በባሌ አውራጃ ፤ ሂመኖ ከሚባለው ስፍራ በኅዳር ፯ ቀን ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጢት ገብተው መስቀል ተሳልመው መንገድ ገሠሩ ። ይህም ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ መንፈሳዊ ሰው መሆናቸውን ያስረዳል ። ከሰፈርም ማለዳ ሲነሡ እኩል ሰዓትና ፩ ሰዓት ድረስ ለተቀመጡበት ኩበት አገነው በእግራቸው ይሔዳሉ ። ማንም ሰው ቢሆን በቃላቅ ነገር ቢጮህና ብዙም ሰው ነገር ቢነጋገር ወደዚያው ተመልክተው ደስ ይላቸዋል እንጂ ይከብደኛል ብለው አይቀየሙም። በኅዳር ፲፪ቀን በባሌ አውራጃ ሐቆ በሚባለው ስፍራ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም ቀኛዝማች ወልደ መድኅን አዲስ ያሠሩት ቤተ ክርስቲያን በትንሽ መቃኞ ነበረ ። ሰፈር የተደረገው በዚያ ስለሆነ በኅዳር ፲፪ ቀን ሔደው መስቀል ተሳልመው ወደ ሰፈር ተመለሱ ።በኅዳር ፳፩ ቀን ሰፈሩ ጋሰራ ነበረ፡ በማለዳ ሲነሡ የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ከዚያ ነበረና ገብተው መስቀሉን ተሳልመው መንገድ ገሠሩ። በሩሱና በባሌ አውራጃ ሥራ ለሚረዱ መኳንንቶችና ለሚሼኙ ሁሉ በተሰናበቷቸው ጊዜ ደስ እያሰኙና መታሰቢያ እየሰጡ ይመልሷቸው ነበረ።በኅዳር ፳፯ቀን ሰፈሩ ሼክ ኑር ሑሴን ነበረ። የሼክ ሑሴን የመሥጊዱ ዋና ሹም ፫፻የሚያህሉ ሰዎች አሰልፈው ተቀበሏቸው። ልዑል ዱክም ተበቅሎ ወርደው ተገናኙ። ሰፈርም ሆነ። ከማታው በ፲ሰዓት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የሰጧቸው የተጌጠ ድንኳን ነበረና ሹሙን ይማማውን ከነ መኳንቶቹ በዚያ በድንኳን አስቀምጠው ጉዳዩ-

ቸውን አነጋገሯቸው። ለይማማው መልክም የሆነ የወርቅ ካባ መታሰቢያ አለበሷቸው። ለዝቅተኞቹም የሚታጠቁት ሰይፍ መታሰቢያ ሰጧቸው። ሌሊቱን ሁሉ በየእስላሞቹ ቤትና በይማማው ቤት ታላቅ ደስታና ፈንጠዝያ ሁኖ አደረ፤በማግሥቱም ልዑል ዱክ ከይማማው ጋራ መስጊዱን ጐበኙ ። ሰፈር በሆነ ጊዜና የሰፈር ውሎ በሆነ ቀን በገዛ መድኃኒታቸው እስከ ፲፭ና ፳ሰው ድረስ ይታከም ነበረ።የበሽተኛው ብዛት በሼኽ ሑሴን በቀን እስከ ፵ሰው ይታከም ነበረ።መርፌውንም አለ ዋጋ ነበረ የሚያክሙት ተጐሬ በታች ቤተ ክርስቲያን በምኞትም አልተገኘ፤ቤተ ክርስቲያን በተተከለበት አገር ሁሉ እያከበሩ ይሔዱ ነበረ፤በውጋዴ ግለሚስ በሚባለው ክፍል እስከ ፵ሰው ለመታከም ይመጡ ነበረ።ባላባቶቹንና ውጋዞቹን በውጋዴ አውራጃ መታሰቢያ እየሰጡ በመልክም እያሰናበቱ ይመልሷቸው ነበረ።

በጥር ፳፬ ቀን ሐውያ በሚባለው ጕስ፤ ስፍራዋም በልዩ ዋቢ ሸበሌ በምትባለው በታ፤ሡልጣን ኑሎል የኢትዮጵያ ዜጋ ሠራዊቱን አሰልፎ እሱም በተቻለው ተሰናድቶ ተቀበላቸው። ሰፈሩ ከሱ ቤት ነበረና ጧት መነሣት በሆነ ጊዜ መልክም የሆነ መታሰቢያ ሰጥተው አሰናበቱት ። በጥር ፳፮ ቀን በኢትዮጵያና በኢጣሊያን ድምበር መድረስ ሆነ።ልዑል ዱክን የኢጣሊያን መንግሥት ሕዝብ ሁሉ መውደዱ እጅግ ያስደንቃል። ክቡር ሲኞር ኰንዳቶረ አርነስቶ ኰይሎሮ ያነን የሚያስቸግር ብረኃ መንገዱን እያስጠረጉ ፤ አውቶመቢሉን ሁሉ በያይነቱ አደረሱላቸው።ባለ አውሮፕላኖችን ደምበኞች አዘው ያስፈልጉ ነበር።ግማሾቹም በራዴዮ ይፈልጉ ነበረ ። ልዑል ዱክም ከየመኳንንቶቹ መገናኘት ጀመሩ ። ልዑል ዱክም እንደሚቀበሏቸው የተዘጋጀውን እየጐበኙ ይሔዱ ነበረ።በየስፍራውም የከተማው ጥዳት የወታደሮችና የመሣሪያዎች መሰናዳት ፤ መድፉ ፤ ታንኩ ፤ መትረየሱ ፤ አውሮፕላኑ ፤ ሁሉ በያይነቱ ያምር ነበረ ። በከተማው ያለው ኤሌክትሪክ እንደ ቀን በሐይ ያሳይ ነበረ ።

በጥር ፴ ቀን በልዑል ዱክ ጅዋሐር በሚባለው ከተማቸው እብሮዋቸው ለሔደው ሰው ሁሉ አታክልታቸውንና ሁዳዳቸውን እንዲያዩ ለሰው ሁሉ ፈቅደው ነበር ። ግን የልዑል ዱክን አታክልት በግር ዞሮ አያለሁ ማለት ከንቱ ነው።ሁሉም ሰው ሁኖ በአውቶመቢል ሲመለከት ማየቱ ብቻ ፫ ሰዓት ፳ ደቂቃ የሚያህል አልተፈጸመም ።የታየውም የ፺ መቶ ጋሻ መሬትና ሁዳድ አዝመራ ነው።፲፭ የሚያህሉ የርሻ መኪናዎች ያርሳሉ የዋቢ ወንዝ ፈሳሽ ውሀ ለ፺ቱ መቶ ጋሻ መሬት የሚበቃውን ያህል ውሀ ከፍለውለታል።የ፺፱ ጋሻ መሬት ሠራተኛ ፺ሺ ሰዎች አሉበት ። የዋቤን ፈሳሽ ውሀ ሸረው የጥንት መንገዱን በሌላጋ ቀደው እንደከፈሉት ያስደንቃል።በመሐንዲስ እየተሠራ የቀላዱ ክፍልና የውሀው በዩ የአውቶመቢሉ መንገድና ሐዲድ የተዘረጋበት በርሻው መካከል ያስደንቃል የሠሪዎቹ ሹማምቶች ቤት ክፍል እጅግ ያምራል።አዝመራው የጥጡ፤የሸንኮር አገዳው ፤ የበቈሎ የተምር፤የኰኰዋ፤ የሙዝ፤የሱፍ፤ የገመድ አታክልት፤ በያይነቱ ይታያል መኪናው በያይነቱ ጥጥንና ጥጥፍሬን የሚለየው መኪና ጥጡን የቦንዳ ሸክም የሚያሥረው መኪና ጥጥፍሬውን ዘይት የሚያወጣው መኪና፤የንጨት መኪና፤የባቡርና፤ የብረት መሥርያ ወርሽ፤የሡካር መኪና፤ያልኮል መኪና፤ በያይነቱ አለ፤የሠራተኞቹ ቤታቸው የ፺ሺ ሰው ቤት በተለየ ነው።ከ፺፱ በላይ ወደ ፺፱ ጋሻ ሁዳድ ለመጨመር እንደገና ይጨፈለቃል ።ልዑል ዱክ ግን ፩ዱ ጋሻ መሬት ባጠፈታ የ፫ ጋሻ መሬት ሰብል እንዲመርተው ያስባሉ፤ ፍሬ የሚሰጠውም በመድኃኒት ነው ተብሏል።በሥራው ላይ የሱማሌ ሕዝብ ሠልጥኖበታል፤ በማናቸውም መኪና በጥር ፴ቀን ከማታው ሰዓት የሠራተኛው ስኒማ ሁሉ በጉባኤ ይታይ ነበረ።በየካቲት ፫ቀን ልዑል ዱክም ወደ መቃድሾ ከተማ ባ፰ ሰዓት ለመጕኘት ሔዱ።በፊትና በኋላ ፈረሰኞች ነበሩ ። ሠራዊትም ተሰልፎ ይቀበል ነበረ። ከተማውም በባንዴራና በልዩ ጌጥ ተጊጦ ነበረ መድፈኞችም የመድፉን ተኵስ ያሰሙት ነበረ ፤ ሲኞር ኰመንዳቶረ አርነስቶ ኰይሎሮ የልዑል ዱክን መበርታትና መሪ መሆን ለመኳንንቱ አስረዱ፤ ልዑል ዱክም በኢጣሊያን መንግሥትና በኢትዮጵያ መንግሥት በ፪ቱ መካከል ያለው ወዳጅነትና የመንግሥታቸውን አኳኋን፤የግርማዊንጉሥ ተፈሪን ምስጋና፤ተናግረው በጨረሱ ጊዜ ጭብጨባው በጣም ደመቀ። በየካቲት ፯ ቀን ስለ ልዑል ዱክ በመቃዲሾ ከተማ የተደረገው ጭዋታ ከማታው ባ፬ ሰዓት መኳንንቱ ሁሉ በሲኞር ኰመንዳቶረ አርነስቶ ኰይሎሮ ቤት ልዑል ዱክ ከዚያ ነበሩና በጣም ያማረ ጭዋታ ተደረገ።ባንዴራውና መብራቱም እንደ ቀን ሁኖ ይታይ ነበረ። ማናቸውም ሰው በየልማዱ በያገሩ ይጫወት ነበረ የመንግሥት ወታደሮችም ወደላይ ጠመንጃ እየተኰሱና ችቦ እያበሩ ያሳምሩት ነበረ።ነገር ግን ወታደሮች በማይገድል ጥይት ይተኵሱ ነበርና በመካከላቸው አንድም ስሕተት አልተደረገም። ይህም መሆኑ ከመንግሥት ወታደሮች በተቀር በሌላ ሰው እጅ ጠመንጃና ጥይት ባለመኖሩ ነው ።

ገብረ ዮሐንስ ።

ክቡራን ወዳጆቼና ታማኝ ወገኖቼ ሆይ ።

ለጊዜው በተሰጠኝ ሐሳቤ ውሥጥ የሀገሬን ሁኔታ ስለአዲሱ ሹመት ብመረምረው በሰዎች ሐሳብ የስሕተት ነገር ያለ ይመስለኛል፤ግን አሁን የምሔድበትን ሥራ ገልጬ እነግራችኋለሁ፤

ለኔ የኢትዮጵያ መንግሥት ይኸንን የከበረውን ታላቅ ሹመት ባለሙሉ ሥልጣን ምኒስቴር ብሎ ለታላቂቱ ለኢጣልያን መንግሥት መስጠቱ ሰላመነኝና ለሀገሬ አገልግሎቴን ስለወደደው ነው እንጂ እኔን ቅር ለማሰኘትና ያለ ጥቅሙ በከንቱ ለመሥራት እንዳይመስላችሁ አፅንቼ አሳስባችሁ አለሁ ። እኔ ልጃችሁም ከሰው አገር መሔዴ እናንተን ወገኖቼን ለመጥላትና አገሬንም ላለመውደድ መስሎ ይታሰባችሁ ይሆናል ። እውነትም አላችሁ አለሁ ።

ኃያሉም አምላክ በሚያውቅብኝና በሚረዳኝ የሁለቱ ታላላቅ መግሥቶች ካሁን ቀደም የመሠረቱትን ፍቅር አፅንቼ በሙሉ ልቤ ወደ እውነተኛው ሥራ ለወደፊት እየገፋሁ የምጥረው የፍቅር ደረጃቸውን እየቀጸሉበት እንዲሔዱና የሁለቱም መ-

ንግሥት መልክሞች ሕዝብ ደስ እያላቸው ሕይወታቸውንና ኑሮአቸውን ያላንዲት እንዲያሰልፉት ብዬ ነው ። አሁንም ለሀገራችሁ አሳቢ ክቡራን ወዳጆቼ ሆይ ለመሔዴ ቅር ሳይላችሁ እግዚአብሔር አገርህን ለመርዳትና መንግሥትህን ለማገልገል ጌቶችህም እንደአመኑህ ደስ ለማሰኘት ያብቃህና በዓለምም ይመልስህ ብላችሁ ስሕተቴን ሳታስተውሉ በይቅርታችሁ እንድትመርቁኝ እየለመንሁ እሰናበታችኋለሁ።

አክባሪ ልጃችሁና ወዳጃችሁ ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ።

ማመልከቻ

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ስም እየታተመ የሚሠራበት ክርኔና የማዘዣ ወረቀት ያለ ሹም ፈቃድና ያለ ማዘዣ ወረቀት እንዳይታተም ከግርማዊ ንጉሥ የጽሕፈት ዲሬክተር ማዘዣ ተቀብለናል ። እንደዚሁም ሁሉ በየክፍሉ ያሉ የሥራ ሹሞች ለሚያሳትሙት ክርኔና የማዘዣ ወረቀት የሹሙን ማዘዣና ፊርማ እየያዙ መጥተው እንዲያሳትሙ እናመለክታቸዋለን ። የዚህም ምክንያት ብዙ አታላዮች ክርኔ እያሳተሙ የቅጥፈትን ሥራ የሚሠሩ ስለ ሆን ነው ።

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ መልክም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ ሰዎች ዳውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፥ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፥ እንጨት፥ ወይም ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ፥ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ ብስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል።

የርሻና የንግድ ማስፋያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርበስ ቤት ፊት ለፊት ነው። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና ርጀቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔሬቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ አሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨጓጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።


GOODYEAR
GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
1-28-7
GOODYEAR
ጉድይር

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
5me ANNÉE № 19

ሐሙስ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም።
JEUDI 9 MAI 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፲፴፫ ገጽ ተከታይ ።

፴) ኢምፕሬዛ ።

ኢምፕሬዛ ማለት ሦስት ነገሮች ሥራ፣ ካፒታል፣ ፍጥረት (መሬት) ነው ። የጥቅምን ፍሬ ሊያፈሩ ፍጥረት፥ሥራ፥ ካፒታል በአንድነት ተገጣጥመው ሊደበለቁ ያስፈልጋል ። አንዳንዱን ለያይተው ቢወስዱት፥ወይም ብይዙት፥ምንም አይጠቅምም።ፍሬዋ ብዙ የመቈጠብ ኤኮኖምያና ደኅ የምትሆነው እነሱ በተሻለ አገጣጠም ሲቀላቀሉ ነው።ማለት እነዚህን ሦስት ነገሮች ፋቶሬ የሚባሉ የፍጥረትና የሥራ ካፒታል መበላሸት ሳይኖርባቸው፡ሦስቱ የተመዛዘኑ ፕሮፖርሲዮን በልክ ሊሆኑ ያስፈልጋል ።

አሁን በሥልጣኔ ዘመን እኒህ ሦስት ነገሮች ፋቶሬ የሚባሉ ተገጣጥመው በአንድ ሰው እጅ ጥቂት በጥቂት አልፎ አልፎ ካልሆኑ፥በብዙ ሊገኙ አይቻልም ። ፍጥረት (መሬት) ፎንዲያሪዎች በሚባሉ ባለ መሬቶች ፤ ብር ካፒታሊስቲ የሚባሉ ባንከኞች፥ ወይም ባለ ገንዘቦች፤ ሥራ በባለ ደመወዞች ሰዎች ይገኛል።ይህነን ሥራ በተሻለ መንገድ በአንድነት አገጣጥሞ ሦስቱ ፋቶሬ የሚባሉ ነገሮች ትርፍ ፍሬዋን ለማግኘት የሚያቆም የኢንዱስትርያ ካፒታሉ ኢምፕሬንዲቶሬ ይባላል። አንድ አንድ ጊዜም ኢምፕሬንዲቶሬ ዋነኛ ካፒታሊስታና ሠራተኛ ሊሆን ይችላል ። አንድ ትንሽ ነጋዴና ትንሽ ገበሬም ኢምፕሬንዲቶሬ ሊባል ይቻላል ። ኢምፕሬዛ ማለትም የኢምፕሬንዲቶሬ አዜንዳ ነች፥ ማለት እኒህ ፋቶሬ የሚባሉ ሦስት ነገሮች የሚፈለገውን ፍሬ ለማግኘት የተስተካከሉና የቀኑ ናቸው በኢምፕሬዛ የተጋጣሙ ሊሆኑ ይቻላል ። የዘመኑ ኢንዱስትሪ መሠረትና ዋና ነገር ነችና በዘመናችን በሥልጣኑ ፍል የፎንዲያሪ ዋነኞች የሚባሉ ባለመሬቶች ሰዎች ካፒታል፥ የአንድ ወገን ክፍል ካፒታሊስቲ የተባሉ ቈጣቢዎች፥ በወለድ የሚያበድሩ ባለ ገንዘቦች ሰዎች ሥራ ፥ በጣም ብዙ ወገን የሆኑ ክፍል የደመወዘኞች ሰዎች ገንዘብ ናት ።

እንግዲያስ የሀብት ማፍራት ከአንድ ሰው ፍለጋና ትጋት ሥራና ጥንካሬ ብቻ አይደለችም፤ከመሬትና ከካፒታል ከብዙም ልዩ ልዩ የወገን ክፍል ሠራተኞች ሰዎች ተገጣጥማ ነው። እንጂ እኒህን ሦስቱን ነገሮች የሚያገጣጥማቸው ኢምፕሬንዲቶሬ የሚባል ዋነኛው አዛጋር ሰው ደግሞ ከፎንዲያሪ ዋነኞች መሬት፥ ከካፒታሊስቲ ማቴሪዮ፥ ፕሬሚ (የፍጥረት ሀብት) የሞተር ኃይል፤ብር፥ ለደመወዘኞችና ለመኪና መግዢያ የሚሆነውን ጠይቆ አገጣጥሞ የሚያቆም ለሁሉ ትርፍ ሊሰጥ ግድ ነው ። ማለት ለፎንዲያሪ ዋነኞች ክራይ፥ ለካፒታሊስቲ ወለድ፥ ለሹሞኞችና ሠራተኞች ደመወዝ መስጠት፤በቀሪውን ለራሱ መውሰድ፥ አለበት ።

በኢምፕሬንዲቶሬ ሥራ የሦስቱ ፋቶሬ የሚባሉ ነገሮች መጋጠም ለኢምፕሬዛ ሕይወትን ይሰጣል። ኢምፕሬዛ በፊት እንደአመለከትነው አዜንዳ የሚባለውን ስም ወስዳ ገንዘቡ በአቲቦና በፓሲቦ (ገቢርና ተገብሮ) ተብሎ ይከፈላል። ስለዚህ ማፍራት እንዲህ ብላ ትሠራለች።

ኢምፕሬንዲቶሬ ።

መሬት፥ካፒታል፥ ሥራ ።

የኢምፕሬዛ ሰዎች በብዙ ዓይነቶች የተለያዩ ናቸው ብለናል። ለምሳሌ) እንዲሁ የቤት ሰዎች ፤ የኢምፕሬዛ ፍሬዋ ከአባት በታች ናት ። ባለፈው (ሚዲዮ ኤቦ) የሚባል መኻከለኛ ዘመን ኢምፕሬዛ በባለ ጕልቶች ነበረች ። አስረጅ ፆ

ያከፋፍላሉ ። አየቄየ ግን አርቲጃያኖ የሚባሉ ሠራተኞች እየሰፉና እየበዙ እየተዘጋጁ ሄዱ። ማለት ሠራተኛው ካፒታሊስታ (ባለገንዘብ) ለመሆን በበቃ ጊዜ የእጅ ጥበብ ሥራን አስተምራችኋለሁ በማለት ብዙ ወጣቶች ጕበዞችን እያሠራ ፍሬ እንዲያፈሩ ያደርጋቸው ነበር። ኢምፕሬንዲቶሬም ለሠራተኞቹ ሥራውን እያከፋፈለ ወደሚያርፋበት ወደየቤታቸው እየላከ የሚያሠራቸው ሥራው ኢምፕሬዛ ተብሎ ይጠራል። ለምሳሌ እንደ ብልሀ፣ መልከም ጥልፍ ጠባፊ፣ወይም ሰፊ፣የኢምፕሬንዲቶሬን ሠራተኞች ቢቀጥር ብዙ ደመወዝ መስጠት ያስገድደዋልና ገንዘቡንም ለመቈጠብ ያህል በየቤታቸው ቁጭ ብለው በየተመቻቸው ሰዓት እየሠሩ ሥራውን የሚፈጽሙለትን ሰዎች እየዘረ ፈልጎ ሥራውን ይዘረዝራል ። ስለዚህ ብዙ ሠራተኞች፣ ይልቁንም ያገቡ ሴቶች በአንድ ወገን የቤት ሥራቸውን እየፈጸሙ በዕረፍታቸው ጊዜ ትንሽ ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት፣ በታላቅ ደስታ ተቀብለው ሥራውን የሚፈጽሙ ሰዎች ብዙ ናቸው ። በጣም በሠለጠኑ መንግሥታት ግን መቸም የመንግሥት ዋና ሥራ የሕዝቡን ጤና ለመጠበቅ ፤ በአገር ውሥጥ ሕዝቡን በስምምነትና በሥልጣኔ ለማስቀመጥ ፤ ከውጭ አገር ጠላትም ለማዳን ነውና መጀመርያ ዋነኛው ሥራው ፤ ዋናሁኖ ለሚያሠራ ኢምፕሬንዲቶሬና ለአገር ኤኮኖምያ እንኳ ብዙ ጥቅም ቢሆን፣ ይልቁንም እነዚያ ያመለከትናቸው አገርን የሚያገለግሉና ከጠላት የሚያድኑ ጕበዛዝትንና አርበኞችን የሚወልዱ ሴቶች ከቤታቸው ሥራ በላይ ያነን ፈተኛ በቶሎ ጨርሰው ሌላ ደግሞ ለመያዝ በጣም ከልክ ባለፈ ቀንና ሌሊት ብዙ ሥራ በመሥራት ጤናቸውን የሚጎዱ ስለ ሆኑ ፤ በአገሩ ይህንን የመሰለ ሥራ እንዳይሠራና እንዳይሠለጥን መንግሥት በጣም አጥብቆ ከልክሎ ይጠብቃል። ዛሬ ግን በጣም የሰፉ ሥራዎች የፋብሪክ ኢንዱስትሪያ፣ የሥራ ቤት፣ (የጽሕፈት ቤት) ስልክ፣ እንደ ፖስታና ባንክ ሁሉ ፤ መርከብ የሚሠራበት አንቲዬሬ የሚባሉ፣ እነሱንም የመሰሉ ሁሉ ናቸው ።

ሚከኤል ተሰማ ።

በሚከተለው ይታተማል።

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በዓል አከባበር ።

ሚያዝያ ፳፮ ቀን ማታ የከተማው ሰው ሁሉ በየክፍሉ ወዳለው ቤተ ክርስቲያን እየሔደ የትንሣኤን የምስራች ቃል ሲሰማ አመሸ። ካህናቱና ሊቃውንቱም የትንሣኤን አደራረስ ደስ በሚያሰኝ አገባብ አሳምረው ፈጸሙት ። ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ስለ ትንሣኤ በዓል ክብር መድፍ ተተኰሰና ድምጹ ያስተጋባ ጀመር ። በዚያን ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ የደስታውና የዕልልታው ነገር የሚያሰደንቅ ሆኖ ነበር ። ከዚያ በኋላ ሰው ሁሉ እርስ በርሱ እንኳን ብርሃነ ትንሣኤውን ያሰያችሁ እየተባባለ ወደየቦታው ሔዶ የፋሲካውን ማዕድ ተመግቦ የትንሣኤውን በዓል በደስታ አከብሮ ዋለ ።

ብርሃንና ሰላም ለክርስቲያኖች ሁሉ እንኳን ብርሃነ ትንሣኤውን ያሳያችሁ ይላል ።

በግሪኮች ቤተ ክርስቲያን የትንሣኤ በዓል አከባበር ።

ሚያዝያ ፳፮ ቀን ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት ግሪኮች ሁሉ የትንሣኤን በዓል ለማክበር በቤተ ክርስቲያናቸው ተሰበሰቡና ክዑደቱ በፊት ክቡር ጳጳስ ሞን ሴኘር ኒኮላ ጥዋፍ አብርተው ከመቅደሱ ወጡ ሰውም ሁሉ ጥዋፍ ጥዋፉን እየያዘ መጥቶ ጳጳሱ ከያዙት ጥዋፍ እየመጣ ለኰሰ።ከዚህ በኋላበቤተ ክርስቲያኑ ዙርያ ዑደት ተደረገና በመስኩ መከከል ከፍ ያለ ድልድል ተደርጎ አምሮ ተነጥፎ በላዩ እንደ አትሮንስ ተደርጎበት ነበረና ጳጳሱ በዚያ ላይ ወጥተው ስለ ጌታችን ትንሣኤ የተጻፈውን ወንጌል በግሪክና ባማርኛ ቋንቋ አነበቡ ። በዚያን ጊዜ በየዓይነቱ እንደ ጥይት ድምጽ የሚንጣጣ መብራት እየተኰሱ ደስታቸውን ገለጹ። ይህ ከተደረገ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመለሱና ጳጳሱ የጌታችንን የትንሣኤውን ሥዕል ይዘው ቈሙ። ሰዉ ሁለም በተራ በተራ መጥቶ ሥዕሉን እየሳመ በየቦታው ቆመ ። ከዚህ በኋላ ቅዳሴ ገቡና ከተፈጸመ በኋላ በደስታ እየቤታቸው ሔዱ።

ስለ ፓስፖር ነገር ።

ከዚህ ቀደም በገራችን አረብና ሱማሌ ከየጠረፉ ሲወጡ ፓስፖር ሳይዙ፣ወይንም የያዙትን እርግጥ የራሳቸው መሆኑን ከጠረፍ ላሉት ለቆንስሎቻችን አሳይተው ሳያስፈርሙ፣እንደዚሁ በከተማ ውሥጥ እየገቡ ሥራቸውም እንዳይጠየቅ በየመደብሩና በየሱቁ አጠገብ እንዲት ዛኒጋባ ይሠሩና ዋጋ የሌለውን ሸቀጥ እየደረደሩ ሊገዛቸው የመጣውን ሰው ያላንድ ምክንያት ይደበድቡ ነበር።የተደበደበውም ሰው በከሰሳቸው ጊዜ እኛ ዜግነታችን ሌላ ነው ወደ ቆንሲላችን ሒዱ እያሉ ያላግጡ ነበር።ዛሬ ግን ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ባበቡር መቆምያ አንድ ቤት ለፓስፖር መመርመሪ አቁመዋል።በዚህም ቤት እነዚህ እላይ የተባሉት እንደተለመደ ፓስፖር ሳይዙ እርግጥም የራሳቸው መሆኑን ለቆንሲሎቻችን ሳያስፈርሙ የሚመጡትን ሁሉ ይመረምርበታል።የዚህም ሥራ አስኪያጁ አቶ ካሣ ገብሬ የሚባለው ላገሩ አገልጋይ ስለሆነ ጥንት ፓስፖር የሌላቸውን አረብና ሱማሌ በከተማ እያታለሉ የሚኖሩትን ያለ ድካም እየፈለገ አሥር የሚሆኑትን አግኝቶ፣በቅርብ ቀን ለማዘጋጃ ቤት እጃቸውን ሰጥቶ፣እኛ ጠረፍ ድረስ በዘበኛ አሲዞ ወደ አገራቸው አስሰደዳቸው። አንድ ቀን እንደዚሁ በመንገድ ሳልፍ ባንድ ስፍራ ብዙ ሰው ሲንጫጫ ሰማሁ። ምክንያቱ ምን እንደሆነ አንዱን ሰው ብጠይቅ በከተማ ውሥጥ ፓስፖር የሌላቸው ሰዎች የኛ ዜጋ ያልሆኑ እንዲሁ ሲኖሩ አሁን አቶ ካሣ ገብሬ የሚባል እንዲመረምር ተሾሞባቸው ይፈትሻቸዋል አለኝ።እኔም ጠጋ ብዬ ብመለከት አንድ መንጋ ዓረብና ሱማሌ አንድ ልጅ እግር ሰው በመሐከላቸው አድርገው እጁን እግሩን እየባሙ ይለምኑት ነበር ። እርሱ ግን በምር ቃል ወረቀታችሁን አሳዩኝ ያለዚያ መያዛችሁን እወቁት ይላቸው ነበር። እኔም በልጁ አኳኋን በጣም ተገረምኩና የምሔድበት ጉዳይ ጊዜ ስለ አልጨመረልኝ ነገሩ ሳይፈጸም ከዚያ ተነሥቼ ሔድኩ። ከአገራችን እንደነዚህ የመሳሰሉት አታላዮች ሲጠፉና በየ

ሥራውም ላይ ሰው ሁሉ እንደዚሁ እንደ ልጅ ላገሩ ሲያስብ በጣም የተሻለ ነው ።

ወልደ ማርያም ጸጋዬ ።

ነፋስና ፀሐይ ።

ነፋስና ፀሐይ በኃይልና በብርታት እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ተባብለው እርስ በርሳቸው ተጣሉና ከሁለታችን በጕልበትና በኃይል የሚበልጥ እንዲታወቅ ባንድ መንገደኛ ሰው ጕልበታችንን እናሳይ ተባብለው ተስማሙ። (ማለት የመንገደኛውን ሰው በኃይል ኮቱን የገፈፈ እርሱ የበለጠ ኃይለኛ ይባል ተባብለው ተወዳደሩ)።

በዚያን ጊዜ ነፋስ ቀዳሚ ሆነና አውሎ ነፋስ ሁኖ በብርቱ ተነሥቶ ነፈሰ። ወጨፎ ያለበትንም ዝናብ አምጥቶ በሰውዬው ላይ ቀዝቀዝ ለቀቀበት ግን መንገደኛው ይህ ሁሉ ሲሆን ኮቱን አጥብቆ ቈልፎ ያዘና ይህን ያህል ብርታትና ኃይል ይዞ መጥቶ የመንገደኛውን ኮት መግፈፍ ተሳነው (አቃተው) ።

ከዚህ በኋላ ፀሐይ ከደመና ውሥጥ በግ ብሎ ወጣና የነበረውን ቅዝቃዜና ጕም ደግሞ አስወገደና የሚተኵስ የጮራን ሙቀት በዝናብ በራሰና በበረደው መንገደኛ ላይ ሰደደ ጥቂት ቈይቶም መንገደኛው ከፀሐይ ትኩሳት የተነሣ ይፈዝና ይደክም ጀመር ። የፀሐዩንም ትኩሳት መቀበል በተሳነው ጊዜ ኮቱን አውልቆ የሚያርፍበትና የሚጠጋበት ጥላ ያለበት ዛፍ ፈለገና ሊጠጋ (ሊያርፍ) ቸኰለ ። ባገኘ ጊዜም ኮቱን አስቀምጦ እዛፍ ጥላ ሥር ተጋድሞ ዓረፈ ።

በኃይልና በጕልበት በሽከረም መላስ ሊያሸንፉት የማይችሉትን ባለጋራ በለሰለሰ መላስና በለዘበ ቃል፤ወይም በበጎ ሥራ፤ ሊያሸንፉት ይቻላል የሚለውን ቃል አለመዘንጋት ያስፈልጋል ።

እምቢልታ ነፋንላችሁ አልዘፈናችሁም ።
የልቅሶ ዜማ ቀነቀንላችሁ አላለቀሳችሁም ።

ይህ ከዚህ በላይ የተነገረው ቃል እግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ቃል ነው ። እግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ቃል እንዲናገር ያነሣው በጊዜው አመለቢስ የሆነ ሕዝብ ስላየ ነው ። ከጌታችን በፊት መጥምቁ ዮሐንስ ተነሥቶ የንስሐን ስብከት እየሰበከ ያጠምቅ ነበር። ብዙ ሰዎችም ትምህርቱን እየተቀበሉ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር ። ግን ብዙ እውቀት አለን የሚሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥበብ ንቀው፤ ዮሐንስን ከሰው ተለይቶ በበረኻ የሚኖር አይበላ ፤ አይጠጣ ፤ ጋኔን አለበት፤ እያሉ አመል ያወጡበት ነበር ። መንቀፍ እንጂ በጎ ነገር አይተው ሰምተውም እንዳይቀበሉና ወደ ደኅንነት እንዳይመለሱ የሕሊናቸው ዓይን ተሰውሮ ነበርና ጌታችን በጎ ሥራውን ሲጀምር ይህ ደግሞ የኃጢአተኞች ወዳጅ ይበላል፤ ወይንም ይጠጣል፤ እያሉ ይነቃቀፉት ጀመር ። ባሕታዊ መስሎ ያስተማረውን አመል አወጡበት ፤ ከሰዎች ጋራ እየተቀላቀለ በጎ ሥራን የሚሠራ በጎ ትምህርትን የሚያስተምርበትን መንገድ የሚመራውንም አመል አወጡበት ስለዚህ በሚጫወቱና በልንጀሮቻቸው ዘመርነ ለክሙ ወኢ ዘፈንክሙ ፤ አስቆቀውነ ለክሙ ወኢ በከይክሙ በሚልዋቸው አመለቢስ በሆኑ ልጆች ይመስላቸዋል ።

በጎ አሳብ የሚያስቡልን ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸው መሪዎቻችን የሚጠቅመንን እውነተኛውን መንገድ ሲያሳዩን፤የሚያስተምሩንን ትምህርት መቀበል ፤ በሚያሳዩን ቀና መንገድ መመላለስ ፤ ላገራችንና ለሕዝባችን ጥቅም የሆነ ነገር ሲያስቡልን ሐሳባቸውን እየተከተልን መታዘዝ ፤ ይገባናል እንጂ ልባችንን እያደነደንን በጎውን ሐሳብ ወደ ክፉ እየተረጐምን ነገርን አናጣምም ፤ እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት ማለትን እንልመድ እንጂ ራሳችንን በመውደድ የመላ ሕዝብን ጥቅም አናጥፋ ። አመለ ቢሶች አንሁን ። አመለቢሶች የሆኑ ባልንጀሮች በምቾትም ሆነ በመከራ ጊዜ ደስ አያሰኙም ። የጠቢባን ወገን ግን ጥበብን ይቀበላሉ ፤ ጥበብንም ያከብራሉ። ትርጓሜያቸውም ጥበብ ነውና እውነትን ወደ ብርሃን ያወጣታል ። ጥበብ በውርደት ብትታይም ያውቋታል ። በክብርም ብትታይ ይከተሏታል ። ስለዚህ ጠቢባን እንሁን እውነተኛ ብርሃንንም እንከተል እንጂ ፤ አመለቢስ በመሆናችን አምላክንና ሰውን እናሳዝን ።

ምን ?

የተወደዳችሁ መኳንንትና ወይዛዝራት ሆይ ፤ ከዚህ በታች የምጽፋቸውን ቃሎች የልጅ ነገር ብላችሁ እንደ ዋዛ እንዳታዩብኝ በማክበር እለምናችኋለሁ፤ነገሬንም በዚች በሽማግሌዎች በተጠቀሰች ጥቅስ ላይ መሥርቼ እጀምራለሁ። እሷውም ጥቅስ ይህች ናት ሲያውቅ የተኛ ቢጠሩት አይሰማም ።

ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝራት ሆይ ፤ ወደ ኋላችሁ ተመልሳችሁ ብትመለከቱና ብታስቡ በ፲፱፻ ዓመት ስንት ነገር እንደ ተለዋወጠ ሳታገኙት አትቀሩም፤ ማለት ከፍ ያለው መንግሥት ዝቅ ሲል ዝቅ ያለው ከፍ ሲል ፤ ደግሞ የሰው አሳቡና እውቀቱ እንዴት እንደሰፋ ሥልጣን በዓለም ላይ እንዴት እንደ ተዘረጋች ። አሁን እንኳን በዚህ ባንዱ መቶ ዓመት ጃፓን እንዴት አድርጎ በዓለም ኃይለኛና እውቀተኛ ከሚባሉት መንግሥቶች ጋር ለመቆጠር እንደ በቃ ሳታውቁት አትቀሩምና ምንም ያህል በጃፓን ላይ መናገር አያስፈልገኝም። ግን እንደዚሁ በቶሎ ሥልጣኔን ለመውረስ የበቃበትን ምንም ብታውቁት እንደ ገና ብትሰሙት ምንም ያህል ጊዜ አይወስድባችሁምና ባጭሩ ልናገረው ዘንድ በማክበር እለምናችኋለሁ። ጃፓን ሥልጣኔን በቶሎ ለመውረስ የበቃው ሌላ ምንም ያህል አልሠራም ፤ ሕዝቡ በአንድነት ተባብሮ አሳቡን ወደ ሥልጣኔ መንገድ መለሰ ስለ ሥልጣኔ ነገር ለገንዘቡ አልሳሳም፤ ወንዱንና ሴትዋን ልጁን ወደ ተማሪ ቤት አገባ መንግሥቱን ከበርቴ ጃፖኖች እረዱት፤ ማለት እንደ ችሎታቸው ልጆች እንዲማሩ ወደ ውጭ አገር ሰደዱ፤ገሚሶችም ተማሪ ቤት እንደ ማኅበር እየሆኑ አቆሙ ስለዚህ በትምህርት ላይ አሳባቸውን ስለ ጣሉ በቶሎ ሠለጠኑ ።

አሁንም እኛ ኢትዮጵያውያን እንደነሱ አሳባችን ለእውቀት ቢሆን ምንም ያህል ጊዜ ለመሠልጠን ባልወሰደብን ነበር። ደግሞ ለእውቀት ከቶ ጥቂት አለማሰባችንን የሚገልጽ ትልቅ ምክ

ክር እሰጣለሁ።የኢትዮጵያ ሰው ለገንዘብ ሳስቶ አይደለም ልጁን ያለማስተማሩ፤ግን ትምህርት አልታየውም።ስለምን ታላቁ ንጉሥ አጼ ምኒልክ ያገራቸው ልጆች ያለ ችግር እንዲማሩ ብለው መምህር ቀጥረው ቤት ሠርተው፤የፀዳ ተማሪ ቤት አቁመው ነበር፤ ግን በተማሪ ቤቱ ያሉ ተማሪዎች ቁጥራቸው ዋጋ ሳይከፍሉ ደሞዝ እየከፈሉዋቸው የሚማሩበት ተማሪ ቤት ይቅርና በዓመት ሺህ ፲፬ ብር እየከፈሉ እደሚማሩበት ተማሪቤት ያህል ልጆች አይገኙበትም ። ይህ እንግዲህ ሕዝቡ ለትምህርት አለመጓጓቱን ይመሰክራል ።

ኢትዮጵያውያውን ሆይ ተዉ በርትተን እንነሳ፤ዛሬ እግዚአብሔር ይመስገን አገር አማን ነው፤ወንድ ልጅ ያላችሁ በቶሎ ወደ ተማሪ ቤት አግቡት እ ጁ፤ ደጅ ይጥና ፤ ለጌታ ይደርና ኮቴው እስኪ ነቃ ድረስ ጌታውን ተከትሎ እንጀራው ይውጣለት ብላችሁ አበባ ጊዜውን በከንቱ አታሳልፉበት ። ዛሬ ዘመን አቶ ሠቢል እያለ ጌታን መከተል አያስፈልግም ዛሬ ግን የሚያስፈልገው ተምሮ አገርን መርዳት ነው ደግሞ ሴቷንም ልጃችሁን መፍተል መስፋት መጥመቅ መጋገርና መቀመም ትማር ብላችሁ በከንቱ ጊዜዋን አታሳልፉባት ዛሬ እድሜ ለብልሆች ፤ የሚፈትል መኪና እያለ ለኩታም ለቀሚስም ቢሆን ምንም ያህል ችግር የለብንምና ብታስተምሯት እራሷንም አገርዋንም ትጠቅማለችና አስተምሯት። በቀሩት አገሮች ሴቶችና ወንዶች ባንድነት ሆነው ያገራቸውን ጥቅም እንደሚፈልጉ ፤ እናንተም ባንድነት ሁናችሁ የአገራችሁን ጥቅም ትፈልጉ ዘንድ ፍጹም አሳባችሁ ይሁን።እናታችሁስ ኢትዮጵያ የጓደኞቿ ልጆች ሠራተኞች ሆነው ፤ የሷ ልጆች ሰነፎች ስትሆኑባት ጊዜ ታዝንባችሁ የለምን ።

ጌቶቼ እመቤቶቼ ሆይ ዛሬ ላገራችን የሚያስፈልጋት የተማረና ያወቀ ሰው ነውና ስለዚህ በርትታችሁ ትምርትን አስፉ ። እኛ ፊት የተሰጠን በቅጡ ሳንማርና ሳናሰፋ የቀረነው ባንተጋ ነው እንጂ የተጉበትማ አሁን በመስከረም ተነሥተው በኅዳር ለማንበብና ለመጻፍ ቻሉ። እረ ይህ የተሠራው በየት አገር ነው ይህ የተሠረው በቱርክ አገር ነው። ሙስጠፋ ከሚል የዱሮ ያረቦች ፊደል ምንም ቢከናወንና ቢያምር በጣም የሚያስቸግር ነበር፤ ይህ የማይረባ ነው ብሎ ሌላ አዲስ ፊደል (ላቱርኮች አዲስ ነው) አውጥቶ ሕዝቡም ይህን እንዲማርና እንዲቀበል ጋዜጣም ባዚሁ ፊደል እንዲታተም አዋጅ አሳልፎ ይኸው ዛሬ በቱርክ በመስከረም ምን እንደሆነ የማያውቅ ገበሬ በኅዳር ለማንበብ ቻለ። ይህ እንግዲህ ለሥልጣኔ የጓጉና አገራቸውን በጣም የሚወዱ መሆናቸውን ይመሰክራል። ለዝናውም ፊደልን መለወጥ እንዴት ይቀፍ ነበርና ግን የማይረባ ስለሆነ ብለው ለወጡት ።

ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝራት ሆይ እኛም እንደ ወንድሞቻችን ጥቅማችንን ብንፈልግ ሳንጠቀም አንቀርምና ስለ ትምህርት ነገር በጣም መበርታትና ማሰብ ያስፈልገናልና እንድታስቡበት ስል በማክበር ታላቁን ጥቅማችሁን አሳስባችኋለሁ ።

ዓ ወ ዘ ።

ማስታወቂያ ።

ከዛሬ ጀምሮ ወደ ፊት ካዲስ አበባ ደወሌ ድረስ በምድር ባቡር መንገድ ግራና ቀኝ ማንኛቸውንም አውሬ ያለፈቃድ ማንም ሰው እንዳያድን ተከልክሎዋል።ያለፈቃድ አድኖ የተገኘ ሰው መቀጮውን አምሳ ብር ይከፍላል። ጠመንጃውም ወደ መንግሥት ይገባል ፤ ፈቃድ የሚጠይቅ ሰው ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ምድር ባቡር ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ሊጠይቅ ይችላል ።

ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፳፩ ።

AVIS AU PUBLIC

Il est interdit dès aujourd'hui de faire la chasse, pour toute sorte d'animaux, se trouvant sur les deux cotés de la ligne du chemin de fer partout d'addis-Abeba jusqu'à Dawollé.

Les personnes qui chasseront sans avoir optenu l'autorisation de la part du Gouvernement, ils seront indemnisé d'une somme de 50 th. et on leur prendra les fusils de chasse.

Ceux qui désire avoir l'autorisation pour la chasse doivent s'adresser chez le représentant du Gouvernement Ethiopien. se trouvent au bureau du chemin de fer Franco-Ethiopien, à Addis-Abeba.

ማመልከቻ

ሚያዝያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት በ ፲፯ ቁጥር በብርሃንና ሰላም የብርሃንና ሰላም ጥቅም መረዳት የጻፈ አቶ ደምሴ ወልደየስ የሚባል በራሱና ባባቱ ስም በስመ ሞክሼ ስማችን ስለገጠመ ነው እንጂ እኔ አለመሆኔን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አስታውቃለሁ ።

ደምሴ ወልደየስ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ተማሪ ቤት ጸሐፊ ።

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውሥጥ መልክም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ ሰዎች ዳውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፥ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፥ እንጨት፥ወይም ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ፥ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል።

የአዲስ አበባ የእህልና የሥጋ ከብት ገበያ ።

በዚህ ወር የእህል ሽመታ ከለፉት ወራት ተሽሎ ነበር ። ግን በበዓሉ ምክንያት አሁን በፋሲካ ተወደል እህል እንደ መወደዱም የሥጋ ከብት ተወደል ። የእህልና የሥጋ ከብት ዋጋ ከፍ ማለቱ ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ ያስረዳናል ።

የእህል ገበያ ፤

ጤፍ ፩ ጆንያ	፲፭ ብር
ስንዴ ” ”	፲ ብር
ገብስ ” ”	፰ ብር
ሽምብራ ” ”	፯ ብር
ማሽላ ” ”	፯ ብር
ማር ፩ ጉንዶ	፲፪ ብር

የሥጋ ከብት ገበያ

በሬ ማለፊያ ሰንጋ	ከ ፸-፹ ብር
” መናኛ	ከ ፵-፵፭ ብር
” ወይፈን	ከ ፴-፴፭ ብር
ላም መሲና	ከ ፵-፵፭ ብር
በግ ሙክት	ከ ፲፭-፲፯ ብር
” መሲና	ከ ፱-፲ ብር
” መናኛ	ከ ፯-፰ ብር
” ጠቦት	ከ ፬-፭ ብር
ፍየል ሙክት	ከ ፲-፲፭ ብር
” መሲና	ከ ፰-፱ ብር
” ጠቦት	ከ ፫-፬ ብር
ዶሮ ፪ቱ	፩ ብር
እንቁላል (፶ውን)	፩ ብር
ቅቤ አንድ ቁርቁሮ	፳ ብር

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅበኑግ (ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ው ። የንጠጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪም በየዓይነቱ እና ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሁ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና (ጂቡቲ በነዚሁ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷንት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የለለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንክራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።


GOODYEAR
BALLOON
ALL WEATHER
GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
1-28-7
GOODYEAR
ጉድየር

አምስተኛ ዓመት ቍጥር ፳
5me ANNEE № 20

ሐሙስ ግንቦት ፰ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 16 MAI 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ የሚታተም ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ሥልጣኔ ትምህርት ነገር ።

፲፱ ቁጥር ብርሃንና ሰላም ዓ ወ ዘ የጻፈው ነገር መልካም ነገርና ደስ የሚያሰኝ ነው። ይኸውም ጋዜጣ የታላቁን ንጉሥ የዳግማዊ ምኒልክን ትምህርት ቤት ለአገሩ ሕፃናት መማሪያ እንዲሆን ስላቆሙና ሕዝቡ ጠንክሮ ስላለመማሩ ይናገራል። ደጉ ንጉሥ ለአገራቸው ሥልጣኔ አስበው መጀመራቸው እውነት ነው። አጀማመራቸውም የትምህርቱ ቤት በአዲስ አበባ ብቻ እንዲሆን አይደለም። በ፩ ጊዜ በመቀሌ፣ በአንኮበር፣ በሐረር፣ በአዲስ አበባ፣ የሥልጣኔን ትምህርት ለማስተማር አስጀምረዋል። ለሌሎቹም የኢትዮጵያ አውራጆች እንደዚሁ ማሰባቸው አይጠረጠርም ። ነገር ግን አንድ ሰው አትክልት ሲተክል ያ አትክልት በትንሽነቱ ቡቃያ ሁኖ እንዲቀር አስቦ አይተክልም። ሐሳቡ እንዲያብብና እንዲያፈራ ነው። የደጉ ንጉሥ ሐሳብም ለሥልጣኔ አትክልታቸው ያሰቡት አሳብ እንደዚሁ ነበረ ። ግን ይኸን እንደ ጀመሩ ሰየቋቋሙት ታመሙ። ከዚያ በኋላ የሥራ ጊዜ ሳላገኙም። የትምህርት ቤቱም አዲስ አበባና ሐረር ያለው እስከሁን በቡቃያነቱ ቈይቷል። ሌሎቹ የትምህርት ቤቶች ግን ያንጊዜውን ቀሩ ። አሁን ም ሁለቱን ቡቃያዎች ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ለአበባና ለፍሬ እንዲያደርሱት ሙሉ ተስፋ አለን። አበባና ፍሬ ማለትም የትምህርት ቤቶቹ ለሐይስኩልና ለኮሌጅነት ሲደርሱ ነው። ለዚህም የሚያደርሷቸው ገንዘብና የትምህርት ቤቱ ድርክቴር ብርታት ናቸው ። ዐ ቸም ድርክቴሩ አቶ ሣህሌ ጸዳሉ ብርቱ ሰው ተሹመውበታል። እሳቸውም ወደ ፊት የሚመሰገኑና የሚታመኑ በገንዘቡ አኳኋን ነው። ዳግመኛም በሥራው አካሔድ ነው። መቼም ለሥራው የሚበቃ ገንዘብ ካላገኙ አንድም የሚቻል ነገር የለም። ይኸ ገንዘብ ከጕምሩክ ለትምህርት ቤት ተብሎ ከነጋዶች የሚወጣው ገንዘብ ብቻ ነው። ይኸም ገንዘብ እንደግምቱ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ትምህርት በጣም ትንሽ ነው። ትንሽ አለ ተብሎ ለመጠራት እንኳ ይከብዳል ። መቼም ዛሬ ዋና የኢትዮጵያ እርዳታ የሥልጣኔ ትምህርት ቤት መሆኑን እራሱ ብቻ ላግኝ ለቀረው ግድ የለኝም የማይሉ ሰዎች ሁሉም ያውቁታል።

ብር ካለ በሰማይ መንገድ አለ ብለው የሚተርቱ ሰዎች ግን የኢትዮጵያ እርዳታ ዛሬ የሥልጣኔ ትምህርት መሆኑን ይክዳሉ። ስለዚህ እርዳታ ከሆነ ነጋዶች ብቻ አረድተው አይጠቀሙንምና ይኸ እርዳታ ባአራሾችም በመኳንንትና በወታደርም ትንሽ እንዲከፈል ቢታሰብ መልካም ነው። ይኸም አከፋፈል በባለመሬቶች ላይ በጋሻ ሁለት ብር፣ የጢሰኛ በጢስ ሩብ፣ ቢሆን ቀላል ነው። ይኸም በየአውራጃው ሁሉ የሥልጣኔ ትምህርት ቤት እንዲቆምበት ነው። ደግሞ ነጋዶችም ረድተዋል። ማለት የአዲስ አበባ፣ የድሬደዋና የሐረር፣ የጎሬ፣ የጋምቤላ ጕምሩኮች ብቻ ናቸው። የረዱትም የዚህ ነገር ይገርማል መቼም የኢትዮጵያን ገበያና በር መንግሥታችን ለመስፋፋትና መኳንንት መስጠቱን እናውቃለን ይኸ የትምህርቱ ቤት ገንዘብ ሌላ ነገር ነውና ወደ ትምህርቱ ገንዘብ መግባት ይገባዋል። በርና ገበያም ያላቸው ሰዎች ያገቡት ይሆናል። ደግሞም መንግሥታችን ከራሱ ገቢ ፩ድ ክፍል የሆነ ገንዘብ ለትምህርቱ ቤት ይሰጥልናል ስንል ሙሉ ተስፋ አለን። ሁለተኛ ዓ ወ ዘ ሕዝቡ ለገንዘብ ሰስቶ አይደለም የሥልጣኔ ትምህርት አልታየውም ስላለው ቃል ትንሽ እከራከራለሁ፤ ሕዝቡ የትምህርትን ጥቅም አውቆታል ነገር ግን ከላይ እንደ ጻፍሁት የትምህርቱ ቤት እስካሁን ቡቃያ ስለ ሆነ አበባና ፍሬ ያለመስጠቱን አይቶ ተቸገረ ማለት ከትምህርቱ ቤት የሚገቡት ሕፃናት ፯ት ዓመትና ፲ ዓመትም ቢማሩ ሥራ አልያዙበትምና የ

ህርት ቤት እንደ ኤሮፓ ደንብ ሎወር እስኩል ይባላል። ሎወር እስኩል ማለትም ትንሽ ዝቅተኛ የትምህርት ቤት ማለት ነው። ለዚያም አልበቃም፤ ለምሳሌ በአገራችን የመንፈሳዊ ትምህርት የፊደልና የንባብ ትምህርት ቤት አለ ። ደግሞ የዜማ ትምህርት ቤት፤ የቅኔ ትምህርት ቤት፤ አለ። የትርጓሜ የሐዲስና ብሉይ ትምህርት ቤት አለ።እንግዲህ በፊደልና በንባብ ትምህርት ቤት ብቻ የተማረውን ልጅ ና ቅኔ ምሩ፤ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ተርጉም ከትምህርት ቤት ነበርህና ቢሉት የማይቻል መሆኑን ሁሉም ያውቀዋል ። አሁንም እንደዚህ ሁሉ እንደ ኤውሮፓ ትምህርት ቤት ደንብ የሥልጣኔውን ትምህርት ቤት ለሐይስኩልነትና ለኮሌጅነት ካልበቃ፤ለዚህ የሚበቃ ገንዘብም ካላገኘ፤ የሚማሩትም ልጆች በቀን ፮ ፯ ጊዜ በዓመት ሙሉ ዘጠኝ ወር እንደ ዓለም ደንብ ካልተማሩ ጊዜያቸው በከንቱ ያልፋልና ምኞታችን ሁሉ ከንቱ ነው ። ጥቂቶቹም የኢትዮጵያ ልጆች ሐሳባችንን በየጊዜው በጋዜጣ መጻፋችን እንደ ሌላው ዓለም፤ ሕዝቡ ጋዜጣ አንብቦ ጉዳቱንና ጥቅሙን ይረደዋል ብማለት አይደለም። የጋዜጣውም ነገር ከ፳፻ሰው እየተቀባበለ አንባቢውም ከ፪ ፲ሺህ ሰው እንዳይበልጥ እናውቃለን። ያገሩም ታላላቆች እስከ ጋዜጣውም ለማንበብ ጊዜ ማግኘታቸውን እንጠረጥራለን ብቻ መንግሥታችን ይኸን ሐሳባችንንና ጩኸታችንን እንዳያስቀርብን ሙሉ ተስፋ አለን ስለዚህ ነው።

ፊ ዴሬሳ ።

የ፻፵፯ ገጽ ተከታይ ።

፴፩) ልዩ ልዩ ዓይነት (የአንድና የብዙ ኢምፕሬዜ ።

ኢምፕሬዜ በኢንዲቢዱዋሌና ከሌቲቦ (በአንድ ሰው ብቻና በብዙ ሰዎች ይለያያሉ) ። ኢንዲቢዱዋሊ ማለት የአንድ ሰው ሥራና ገንዘብ ብቻ ነው ፤ ከሌቲቦ ብዙ ሰዎች ማኅበርተኞች የሆኑ ናቸው፤ በዚሁ መንገድ ሦስት ዓይነት ማኅበርተኞች እናገኛለን ።

፩ኛ ከሌቲቦ የሚባሉ ማኅበርተኞች ገንዘብ አበዳሪዎችና የሚመልሱ ናቸው ። ማለት ቢከስሩ ወደ ማኅበር የገባው ገንዘባቸው ዕዳቸውን ለመክፈል የማይበቃ ሲሆን ፤ ያንን የማኅበር ገንዘባቸውን ብቻ ለመክፈል አይደላም የሚገደዱ ፤ ከልዩ ገንዘባቸውም ለባለ ዕዳቸው የሚከፍሉ ናቸው እንጂ ።

ይህም አይበቃም ፤ ማኅበርተኞቹ በአንድነት ያገቡት ገንዘብ ወይም ከግል ገንዘባቸው ፤ እንደየድርሻቸው ለመክፈል የማይበቃቸው ቢሆን፤ ከነሱ (ከማኅበረተኛው) ውሥጥ ፤ ለመክፈል የሚችል አንድ ሀብታም ቢኖር ፤ ሀብታሙ ብቻ ከግል ገንዘቡ የማኅበርተኞቹን ሁሉ ይከፍላል። ኋላ ግን ቀስ ቀስ እያለ በየጊዜው ከማኅበርተኞቹ ገንዘቡን ሊቀበል ይችላል ።

፪ኛ የአኮሜዲታ ማኅበር የምትባል፤ ከነዚያ ማኅበርተኞች ይልቅ የነዚህ ብድር ደስ የሚያሰኝ ነው።መጀመሪያ ከማኅበርተኞቹ ካፒታል፤ይህ የማይበቃ ከሆነ ደግሞ ከአንድ እንዱ ከማንዳታሬ ከሚባሉ ማኅበርተኞች ገንዘብ ይከፈላል ። ግን እነዚያ ኮማንዳንቲ የሚባሉ ማኅበርተኞች ሊነኩ አይችሉም ። ማለት ሁለተኞች ማኅበርተኞች ፤ ማኅበሩ ቢከስርም፤ ያ በፊት ያገቡት ገንዘብ ብቻ ይጠፋል እንጂ ማኅበሩ ቢከስር እንኳ ሊከስሩና ሊከፍሉ አይችሉም ። (አይገደዱም) ። እነዚያ አለቆች ባለ ካፒታሎችና ሥራውን የሚያቆሙና የሚፈጽሙ ዋነኞች ማኅበር የከሰረ እንደ ሆነ ግን ከሌላው የግል ገንዘባቸው ሊከፍሉ ይገደዳሉ ።

፫ኛ ሶቺታ አኖኒሜ የሚባል እያንዳንዱ ማኅበርተኛ ወደ ማኅበሩ ባገባው ገንዘቡ ልክ ብቻ ይመልሳል እንጂ በሌላ ነገር ሊታወክና ሊገደድ አይችልም ። የዚህም ማኅበር ካፒታል በትክክል ይከፈላል ። ስሙም አሊዮኒ ይባላል። እያንዳንዱም አሊዮኒ ለእያንዳንዱ የጥቅም ክፍል ሊሰጥ ሥራት ይሰጣል ። ስሙም ተካፋይ ይባላል።ይህንን ሶቺታ ማኅበር ከሁሉ የታወቀና የሚበልጥ፤ከሁሉ የሚጠቅምና የሚረባ ነው ። ሚካኤል ተሰማ።

በሚከተለው ይታተማል ።

ኢትዮጵያ? ኢትዮጵያስ ደግ ነበረች። ነበረች ብቻም አይደል ማለፊአ በሆነች ።

ላገር ልማት ለመንግሥት ክብረት መሠረቱ እርሻና እህል ነው ። የቀረው ግን ተከታይ ነው። ከደጊቱ ከለምለሚቱ ኢትዮጵያ ቀጠና ሥር መስደዱ ብዙ ያሳዝናል ያስተክዛል። ጣልቂአ ጣልቂአ ተገባው ተትንንሹ በረሃ በተቀር የኢትዮጵያ አገር ለከብት ማርባት፤ለእህል ማምረት፤ የተመቸ ነው። ነፋሱ መድኃኒት፤ ነፋሻው ሕይወት፤ ድደኑ ያልጨከነ፤ ጉሙ ያልጨለመ፤ ፀሐዩ ያልጠመረረ፤ ዝናሙ የለገሰ፤ ወንዙ የፈሰሰ፤ ማሩ የለሰለሰ፤ ዛፉ የለመለመ፤ ተራራው የኰራ፤ ሜዳው ላይን ያቃለለ፤ መሬቱ የሰባ፤ ሰው ያልማሰነበት ዱር ልምላሜው ከገነት የተፈካከረ፤ የወራጁ ወሀ የገደሉ ምንጭ አንጀት ያረሰረሰ፤ ለልብ የፈወሰ አገር አለን ። ይሕን ሁሉ የግዜር ስጦታ አስቸንፎ ተላልፎ በደጊቱ በለምለሚቱ አገራችን በየጊዜው ራብና ቀጠና ሥር ሰዶ እግሩን ዘርግቶ ይኖርባታል። አዩ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያስ ደግ ነበረች ።

ይሔ ሁሉ መሆኑ እርሻና ቁፋሮ በማነሱ ነው። እርሻና ቁፋሮ አለመብዛቱም ባላገሩን ገበሬውን አይዘህ የሚል በመታጣቱ ነው። አይዘህ ማለት የሚገባቸውም አገረ ገዦዎችና መሳፍንቱ ነበሩ። መንግሥት ለድሀው የሚሆን ደግ አሳብ በጀመረ ጊዜ እነዚሁ መኳንንትና መሳፍንት ዕንቅፋት እየሆኑ መልጐምጐም ይጀምራሉ። የሰማይ ስባሪ የሚያክል መሬት ይዘው ለርሻ ሳይጓጉ ጌጣቸውንና ኩራታቸውን በጀብ ወስነውት ይኖራሉ። አጀቡም በቀን ሲያምርበት በሌሊት ችጋር ሲዘፍንበት ያድራል። ባገራችን እርሻ ባለመብዛቱ የተነሣ ዛሬስ ጉዱ በዛና በሀል ረገድ ኢትዮጵያ ለሌላ አገር መትረፏ ቀርቶ በቀድሞ ዘመን ባገራችን የጦጣና የዝንጀሮ መቋደሻ ሲሆን የነበረውን ማሽላና ዘንጋዳ ከህንድ አገር በብር ሚዛን እያስመጣን ለጊዜ መሸገሪአ አደረግነው። እንዲህ ያለው ነገር ለሰሚውም ግራ ለተናጋሪውም እፍረት ነው። የውጭ አገር ሰዎች ባዲስ አበባ የሚኖረውን ውርጋጥና የመንደር አፈሌ ስላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥራ ባለመውደዱ ነው ችጋር መብዛቱ ይላሉ። ይሔ ውሸት ነው። በሔትም አገር ቢሆን ተከተማ

ብዙ አውደልዳይና መንደረኛ ይኖራል። ነገር ግን በያገር ቤት ያለውን ሕዝብ ቢአዩት እንደ ኢትዮጵያ ባላገር ያለ ሥራ የሚወድና የሚተጋ የለም። ቀን ሲአርስ፥ ሲኰለኵል፥ ሲዘራ ውሎ በሌሊት ቀራቱን ሠርቶ፥እንቅልፉን አጥቶ ፥ ወንጭፉን ዘርግቶ፥ ጠጠሩን ለቅሞ፥ ሲወነጭፍና ጃርት አሳማውን ሀይ ሀይ ሲል ያድራል ሲነጋም እንቅልፉን ባይኑ እንዳጠለጠለ ወደ ሥራው ይመለሳል ።

ነገር ግን ዱግና ጭቃሹም ፥ ምስለኔና ቱኪ ፥ እንደ ዋስ አጋች እጁን ይዞ ሲጎተተው ያ ያልታደለ ባላገር እንዴት አድርጎ የገዛ መሬቱን የገዛ፥ ጉልማውን ጨርሶ ለማረስ ይቻለዋል ። ስለዚህ በገዛ መሬቱ አሚከላና ጉድይ፥ እንቧጮና እንቧይ፥ ሰፍኖበት ይቀራል ። እንጦጦ የተቆረቆረ ጊዜ አዲስ አበባ ላይ፥ በቀረውም በየጋላው አገር ሁሉ ባንድ ብር ስምንት ስምንት ዳውላ ጥቁር ጤፍ ይሸመት ነበረ ። እንዲህ እህል መትረፉ እኛ መጥተን ግልብጥብጡን እስክናወጣውና እስክናጠፋው ድረስ በዓለ [illegible] መጠመድ፥እህል መፍጨት፥ ዶቄት መጫን፥አጥር ማጠር፥እንጨት መፍለጥ፥አልነበረበትም። ሁሉም ለራሱ አጋፋሪ ሳይጠራው፥ጭቃሹም ሳይቆጣው፥ ምስለኔ ሳያንገራግረው፥የሽለቃ ሳያስረው፥ዝም ብሎ ሳይታወክ፥የጀመረውን ሥራ ሳያቋርጥ፥ ሁሉም ራሱን እራሱ እያዘዘው፥ የገዛ መሬቱን እያረሰ፥ እየቆፈረ፥ አህሉን እያፈሰ፥ለራሱ ጠግቦ ለሌላ ተርፎ፥ ያራትና ያምስት ዓመት ድልብ ያደልብ ነበረ ። ከብዛት የተነሣ እህሉ የሚበላው አያጣ ናሽቶ ነቅዞ ይቀር ነበረ። አዬ ኢትዮጵያ ። ኢትዮጵያስ ደግ ነበረች ። ዛሬ ግን የሚነቀዘውና የሚናሸው እህሉ አይደለም ። ያልታደለው ደኻና ገፈኛው አውደልዳይ ነው ።

መንግሥት ከወደደ ቀጠና ከሥራ ይነቀላል ።

የድኻ ዕንባ ቀስት ነው ይወጋል ።የመኳንንት ማንጕራጕርና መጕተምተም የቅሉት ልማድ ነው ። ስለዚህ መንግሥት ጨክኖ በዚህ ካሰበበት ከለምለሚቱ ኢትዮጵያ ውሥጥ ችጋርና ቀጠና እንዳይኖር ለማድረግ ይቻለዋል ። ስለምን እርሻና ቁፋሮ ከበዛበት አገር ራብና ቀጠና ስፍራ አግኝቶ ለመኖር አይችልም። ለዘላለሙ ይነቀላል ። አዲስ አበባ ዛሬ ከዶቄት ሱክር ይረክሳል ። ዶቄት ከዚሁ ተፈጭቶ ዕጥፍ ዋጋ ማውጣት ፥ ሱካር ከሩቅ አገር በመርከብ መጥቶ፥በባቡር ተጭኖ፥ቀረጥ ከፍሎ፥ ከዶቄት አንሶ መሸጡ፥በጣም ያስደንቃል ። ቀጠና መበርታቱ በዚህ ይታወቃል ። ዘንድሮ [illegible] እያለቀ በየገሩ [illegible] ሲገትነው ይታያል ። በፈረንጅ አገር አንድ ሰው ብቻ በራብ ሞተ ሲባል አገሩ ሁሉ የሽብር ቃሉን ለመንግሥት ያሰልፋል ። መንግሥትም በቶሎ እህል እንዲበዛ፥ ከብት እንዲረባ፥ፍሬና አታክልት እንዲለማ ያደርጋል ።

እንዲህ በለው ጊዜ ዋና ቀንቃኙ፥ አስተማሪው፥ አስጠንቃቂው፥ ጩሒው፥ለደኻ ጠባቂው፥ ጋዜታ ነው።የከንቱ ምስጋናውን ወይም ሰው ማዋረዱን ብቻ ከተወ እውነተኛ ለደኻ ጠባቂና፥ለመንግሥት መሪ፥ ለህዝብ አስተማሪ ዋና አስተዋሽ ጋዜታ ነው።መንግሥትም የጋዜታውን ቃል ተከትሎ የሚጠቅመውን ምክር ተቀብሎ የጋዜታ ምክር ሳይንቅ ሳገሩ ያስባል። እንዲህም ለማድረግ መንግሥት በየሥራው ዓይነት አዋቂዎች ምንስትሮች ይሾማል።የመንግሥት ደጉ አሳቡ እንዳይሰናከልበት መኳንንቱ፥አገረገዦው፥ መሳፍንት ምስለኔው፥ ማንላቸውም ደኄ ሳይቀር፥ ለመንግሥት ማገዝ ይገባዋል። እርሻ እንዲሰፋ፥ እህል እንዲበዛ፥ ከብት እንዲረባ፥ አታክልት ፍሬ እንዲለማ፥የሚያደርግና ባገር ራብና ቀጠና እንዳይገባ ለማድረግ የሚገባው የርሻ ምንስትር ነው ። እህልና ከብት እንዲበዛ ለማድረግ ብቻም አይደለ፥ የርሻ ምንስትር የከብት ዘር እንዲአምር፥የእህል ዘር እንዲሻሻል፥ፍሬው እንዲጣፍጥ፥ ወተቅ ቅቤው እንዲበዛ፥ላሞቹ ዘራቸው እንዲታደስ፥ ወይፈኑ፥ ጥጃቱ፥ ቁመቱ ዘለል፤ወርዱ ሰፋ ያለው እየተመረጠ በጉ ጠጕሩ መልካሙ ሥጋው ጥፍጡ እየተመረጠ እንዲራባ በየአውራጃው በየደጋው፥ በየቆላው፥ለየባላገሩ ለየምስለኔው ይናኛል። ፈረስ በቅሎውም እንደዚሁ።ዶሮ ሳይቀር ቁመትና ወርዱ የላቀው፥እንቁላሉ የከበደው፥ እየተመረጠ እንዲረባ እንዲራባ ይሆናል። ዶሮ አክሉ ቢአንስ ከብዛት የተነሣ በምግብ ነገር ብዙ ስፍራ ይይዛል፥ጥቅሙ ብዙ ነው።

እንዲሁ እየተደረገ፥እርሻው እየሰፋ፥ ከብቱ እየረባ ሲሳይ እየበረከተ ራብና ቀጠና ይጠፋል።ባገራችን አሥር ላሞች ከማስቀመጥ አንዲት የፈረንጅ ላም ማስቀመጥ ይሻላል። ስለምን ያገራችን አሥሩ ላሞች በቀን የሚታለቡት ቢበዛ ሀያ ወይም ሀያ አምስት ጠርሙስ ወተት ነው።የፈረንጅ አገር አንዲቱ ላም ብቻ እስከ ፳፰ ጠርሙስ ወተት በቀን ትታለባለች። እሔ መሆኑ ዘራቸው እየተመረጠ ስለ ረባ ነው። ወተት የማይለግሡትን ላሞችና ቁመትና ወርድ የሌላቸውን ወይፈኖች ዘር እንዳያበላሹ ወደመቃረጃቸው ይሰዷቸዋል ።

ዳኔማርክ የሚባለው ያንድ መንግሥት አገር አሁን እስከ ቅርብ ዘመን እንዳገራችን ችጋረኛ ጠፍ አገር ነበረ። አሁን በቅርብ ዘመን ጀምሮ መንግሥቱ ያለፈውን ጥፋት አይቶ ባላገሩን አይዞህ እያለ፥ጠፉን መሬት እያሰባ፥ ዢቅጋሮቹን እያደረቀ፥ እርሻውን እያሰፋ፥ከብቱን ዘሩን እየመረጠ እያረባ ሳሩን ለከብት የሚጠቅመውን ወተት የሚያበዛውን እያለማ፤ ዛሬ አገሩን ወተትና ቅቤ ብቻ አደረገው። መንግሥቱ ከበረ፤ ለድሀው አለፈለት፤ አገሩ ባለጸጋ ሆነ፤ ለሌላ አገር ተረፈ።

ይሔው ዳኔማርክ የሚባለው አገር ሰፋቱ ፵ሺ ኪሎመትር ካሬ ነው። ማለት ከኢትዮጵያ ፳፮ ጊዜ ያንሳል ። አሁን ባገሩ የረባው ላም አንድ ሞልዮን ታምስት መቶ ሺህ ሆነ።ባንድዓመት አራት ሚሊአርድ ከሰባት መቶ ሺ ጠርሙስ ወተት ይታለባል ።

እርሻና ፋብሪክ ቢበዛ ከብቱ ቢረባ ወተትና ቅቤው ቢበዛ፥ ይሔ ሁሉ ጥረትና ምስንት ሕዝቡ እንዳይራብ፥እንዳይቸገር፤ከራብ ቀጠና ነፃ እንዲወጣ ነው ። የዚህ ሁሉ አሳብ በሔትም አገር ቢሆን በመንግሥት ላይ ነው ።

ትልቁ ሙሶሊኒ

በኢጣልያ አገር እርሻ በማነሱ የሚበቅለው እህል ለህዝቡ ላመት ቀለብ የማይበቃ ስለሆነ በየመቱ ከውጭ አገር ወርቅ እየደፋ ይሸምቱ ነበረ።ትልቁ ሙሶሊኒ በዚህ አዝኖ ተክዞ ታገራችን የሚታረስ መሬት ሞልቶ ስልምን ለህል እየተባለ ያገራችን ወርቅ ወደባዕድ አገር እየወጣ ያልቃል ብሎ ተጠምቶ በዋጁም፥በምክርም፥ እያደረገ እርሻ ለሚአሰፋና እህል አሳምሮ

ለሚአበቅል ሽልማት እየሸለመ ገንዘብ ላጣ ማገገር ገንዘብ ብድርም ይሁን ለገበሬ እየሰጠ፤አራሹን ሁሉ አይዘዝ አለ ። ስለዚህ አራሹና ቆፋሪ ለጥቅሙ ብቻም አይደለ እየተቃና ለመሸለም፤ለመመስገን፤ ለመደነቅ እያለ እርሻውን በሐትም በሐት እንጋለለው ። እንዲህ ስላሆን በኢጣልያ አገር በሙሶሊኒ ትጋትና ምኞት በንድ ዓመት ብቻ ሰባት መሊዮን ዳውላ እህል ወትሮ ከሚገባው በልጠ ገባ።ሰባት መሊዮን ዳውላ እህል ለኢጣዮጵያ ሕዝብ ለብዙ ጊዜ ቀለብ በበቃ ነበረ ። መሬቱ ግን እህል በመድፈሩና ድንግል በመሆኑ የኢትዮጵያን የመሰለ አገር የለም ። በስፋት ደግሞ ኢትዮጵያ አንድ መልዮን ከመቶ ሺ ኪሎሜትር ካሬ ናት ። ኢጣልያ ግን ሦስት መቶ ከሥር ሺህ ኪሎሜትር ካሬ ብቻ ናት ኢትዮጵያ በስፋት ወደ አራት እጥፍ መሆኗ ነው ።

እንኳንስ የርሻ መብዛትና የከብት መርባት የፍሬ መልማት ይቅርና የዶሮ መርባት ሳይቀር ለሕዝብ ብዙ ጥቅም ነው። ብፍሪክ ውስጥ ማሮክ የሚባለው አገር አሁን በቅርቡ ዶሮ ማርባት ጀምሮ በንድ ዓመት እንቁላል ብቻ ታገሩ ውስጥ የሚበላው ተበልቶ የቀረውን እንቁላል ወደውጭ አገር በሰማንያ መልዮን ፍራንክ ሸጠ ። በኢጣልያ አገር ዛሬ ያ ት ሚሊአርድ ሊር ዶሮና እንቁላል አለ ። ሚሊአርድ ሲባል በቃል ሲናገሩት አጭር ነው ቁም ነገር አይመስልም ። በግብጠ አንድ ሁለት እያሉ የሚቆጠር ቢሆን ግን ሳያቋርጡ ሌት ተቀን ለመቍጠር በማንያ አራት ዓመት ያቆያል ብለው ሊቆቹ ተናግረውታል ። እንዲህ እየሆነ የዶሮ እንኳ ጥቅሙ ልክ የለውም። ብገራችን ግን በመናቅ የተነሣ ዶሮውም እንቁላሉም ለሰት ምግብ አይበቃም ሁሉም ነገር ዛሬ የፊቱ ኋላ የኋላው ፊት ሆነና ሁሉም በአቶ ሞቢል ይንሸረሸራል በአቶሞቢሉ ዋጋ አስንት እርሻ በሰፋበት አስንት ጥገት በተጠጋበት ነበረ።ከዚህ በኋላ ግን ብትርፉ ብንሸረሸር ለሁላችን ባማረብን። ነጋድራስ አፈ ወርቅ።

ወዮለት እምነት ላጣ ለሚጠራጠር ልብ ።

እምነት የሚሠራው ሥራና ለሰውነትም የሚሰጠው ቅረፍት እጅግ ብዙ ነውና በዚህ ጽሑፌ የምዘልቀው አይደለም ይሁን እንጂ በጥቂቱ መጻፌን አልተውም። ሰው ጌታም ቢሆን ደሀ፡ ትልቅም ቢሆን ትንሽ፤ ያለእምነት ለመኖር የማይቻለው መሆኑን ምንም አንባቢዎች የምታውቁት ቢሆን ለሐሳቤ መክፈያ አንዲት ምሳሌ እጽፋለሁ። አንድ ሰው በቤቱ ሚስትና ልጆች፡ አሽከርና ገረዶች፤ ይኖሩታል። እንግዲህ ባለቤቱ የቤቱን ሥራ ለቤተ ሰዎቹ ትቶ (ጥሎ) ወደ ሥራው ሊሒድ ግድ ይሆንበታል፡ ከሥራው ሲመለስ ሚስቱና ቤተ ሰዎቹ ምግቡን በያይነቱ አሰናድተው ያቀርቡለታል ። እንጀራውን ቆርሶ፤ ወጡን አጥቅሶ፤ የሚበላው ምን እንዳለበት አውቆ ነው? አምኖ ነው። ጠላውና ጠጁን ደስ እስኪለው ድረስ የሚጠጣው ምን እንዳለበት አውቆ ነው? አምኖ ነው እግሩን ሲታጠብና በቅቤ ሲታሽ ምን እንዳለበት አውቆ ነው አምኖ ነው። እሺ እንግዲህ የልቤን ሐሳብ እስክዘረዝረው ድረስ ጊዜያቱ ይዘገያል። ደልቁንም አንባቢዎች ይሰለቹኝ ይሆናልና ይህን ተወት አድርጌ ወደ ቀድሞ ሐሳቤ ልመለስ። የአውሮፓ ሊቃውንቶች የራሳቸውን ጥ]ም ሳያስቡ ለኋላ ልጅ እንዲሆን ብለው ለፍተው ደክመው የሠሩት ሥራ ስንት (ምን) ለፍር ቁጥር አለው። የሠሩትንም ሥራ ለማስረጃያና ለማስገንዘቢያ ብለው በመጽሐፍ ይጽፉታል። መጽሐፉንም እያነበቡ ብልሆች ይከተሉታል፤ ሰነፎች ይንቁታል። አሁን ይህን የጻፍሁበት ምክንያት እኛ የኢትዮጵያ ሰዎች በሃይማኖትና በቁም ነገራምነት ይልቁንም በእርበኝነት ስመ ጥሩዎች ነን፤ በጥበብ ግን እጅግም አይደለን። ይህም የሆነበት ምክንያቱ አጭር ነው ። አውሮፖች የጻፉትን የጥበብ መጽሐፍ በቶሎ ለመቀበል በመጠራጠርና በመጠንቀቅ በቸልተኝነትም ስለዘገየን ነው ። ይሁንና ለኔ መልከም መስሎ እንደታየኝ የልቤን ሐሳብ እጽፋለሁ።የአውሮፓ ሊቃውንቶች ከጻፉት መጽሐፍ አንዱ ዋነኛው ጅዎግራፊ ነው። ዋነኛነቱም የሰማይንና የምድርን፤ የፀሐይንና የጨረቃን፤ የከዋክብትንም፤ በዚህም ውስጥ ያሉትን ፍጥረቶች የሚያስረዳ ስለሆነ ነው። አንዱም ጉድ የሆነ ነገሩ ዓለም ትዞራለች ማለቱ ነው። ወይ ግሩም ከቶም ዘወርዋራ ናት አንድ ጊዜ ጭለማ፤ አንድ ጊዜ ብርሃን፤ ትሆናለች። እንግዲህ ዓለም ዘዋሪ ናት ለማለት ምን ይቸግረናል። ምንስ እንጠቀማለን እንዲያው መተው ይሻላል፡ ነገር ግን ይህንም ለመናገር መድረሴ ጥቂት ጥቂት የጅዎግራፊን መጽሐፍ በማንበቤ ነውና መጻሕፍትን እገሌ ጽፎታል ብሎ ከመንቀፍ አምኖ ተቀብሎ መጽሐፉን መርምሮ ሲከዳ ቢገኝ መተው ይሻላል። ቅዱስ ጳውሎስም ሁሉንም መርምሩ የተሻለውን ያዙ ብሏል። ለታደሉት መቅደም ነበር እንዴት መከተል ይቅር የተማሩት ሊቃውንቶች የጻፉትን ከነቀፍን እኛ እልከኞችና አንገተ ደንዳኖች እንባላለን እንጂ እነሱማ ጥበባቸውን እንደያዙ ይቀራሉ። መቼም እኔ የጻፍሁበት ምክንያት ሥራ ነገሩ እመኑ ስል ነውና ሁሉን ለማመን እንዴት ይቻላል የሚለኝ ሰው ቢገኝ መጠንቀቅን ጨምርበት ስል ነገሬን አሳጥራለሁ። ክቡራን አንባቢዎች ሆይ እንደ ተማረ ሁኜ በናንተ ባዋቂዎች መካከል ይህቺን ያልተከከለች ቃል እንድታነቡልኝ በመጻፌ ጊዜያችሁን ስላባከንኩ ይቅርታ እለምናለሁ ። ተሰፋዬ ከማ ።

ማስታወቂያ

በሥራ ሚኒስቴር ክፍል ከባቡር ቤት ውስጥ መልከም ወፍጮ አቁመናልና እህል ለማስፈጨት ለሚፈልጉ ሰዎች ዳውላውን በስድስት መሐለቅ እናስፈጭላቸዋለን ደግሞ ከአዲስ አበባ ወደ አዲስ ዓለም፤ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ፤ እንጨት፤ወይም ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ፤ በባቡር ለማስጫን የፈለገ ሰው በቀላል ዋጋ እናስጭንለታለን። ይህንንም ለመጠየቅ ከእሑድ በስተቀር ዘወትር ከሥራ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የመጣ ሰው ያለ ችግር ለመነጋገር ይችላል።

ፔር ዳኜይ ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ድሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ።)

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበበ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፣ የርሻ፣ የፋብሪካ፣የደን፣ የማዕድን ሥራ፣ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት)መዓዘው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዚርቢስ ቤት ፊት ለፊት ነው። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊ.ር ማህጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር እክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተ ፲፬ ሡ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፭ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፶፪ ብር
ጎበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
የበግ ቆዳ	፩ ከረጺ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጺ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጸር	፩ ከረጺ	፻፸ ብር
በለሰይጣን		፻፳፰ ብር
፡ ፡ ባለ ድመት ።		፻፵፫ ብር
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፳ ብር
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፶፩ ብር
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፫ ብር
" " ጃፓን		፻፸፩ ብር
ሱክር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፳፯
በአንድ ብር	፳ ሊሬ ከ ፶፬ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፸፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፰ ብር

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰበኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሬም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ማረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርከፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርከፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና ቦምቤ፡ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ክኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ አሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክት ሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ በለእንጨት ። ባለወረቀት በለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።


GOOD COVERS
DESERVE GOOD TUBES
GOODYEAR TUBES
I-28-7
GOODYEAR
ጉድይር ግዙ

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
5me ANNEE № 21

ሐሙስ ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 23 MAI 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፺፬ ገጽ ተከታይ ።

እንደገና ደግሞ ብዙ ልዩ ልዩ የሆኑ ሶቼታ ተሰብስበው አንድ ማኅበር ይሆናሉ ። ፩ኛ ክርቴል የሚባሉ የገበያ ዋጋ ዝቅ እንዳይልና እንዳይረክስ የሚከለክሉ ፤ ፪ኛ ፖል (ውል) የሚባሉ ሸቀጥንና ክራይን የሚከፋፈሉት፥ ምሳሌ፤ ከጦርነት በፊት (ማለት ከ፲፭ ዓመት በፊት የነበረ ጦርነት) በጀርመን አገር ኖርዴን ቴስኬር ሎይድ እና አማሪይ አሜሪካ ሊሚ የሚባሉ ሶቼታ ፥ በመካከላቸው ያለውን ጠብ ለማብረድና ለመተው በአንድ ውል የበሕር መሜን ክራይና የመሬት ገበያ ሸቀጥን ተከፋፈሉት ። አንደኛይቱ ሶቼታ ማኅበር ወደ አሜሪካ ልትጭን ሁለተኛይቱ ሶቼታ ወደ ምሥራቅ አገር ልትጭን ምሥራቅ ማለት ግብፅ ፥ ቺና፥ህንድ ፥ ጃፖን ፥ በአጠገባቸውም ያሉት ትንንሾች አገሮችም ናቸው) ተስማሙ ። እንዲሁም አሁን በጊዜያችን የአሜሪካ ስታቲ ኡኒቲና የኢጣልያ ሶቼታ ፖል (ውል) አለ። ማለት ዲን በሁለቱ አገሮች ብቻ ነውና ብጣም የሚገኝ፥ኮንኮሬንሳ የሚሉት ፉክክር እንዳያደርጉ አሜሪካኖች በአሜሪካ በሞላ ሊሸጡ ፥ የኢጣልያ ሶቼታ በሞላ ኤውሮፓ ሊሸጡ ተስማምተው ተዋውለዋል ።

፫ኛ ትሬስት (እምነት) የሚባል ሶቼታ ከሁሉ በጣም የበለጠ ነው ። በዚሁ ኢምፕሬዜ (ሥራ) በታላቂቱ ኢምፕሬዜ የታጡና የጠፉ ይመስላሉ ሊባል ይደፈራል።ትሬስት(እምነት) ለያንዳንዳቸው ኢምፕሬዜ ሥራ የኢንዱስትሬ ማፍራቱን ሊያበዙት ወይም ሊያሳንሱት ፥ ሊያዝዋቸው ፤ ከነዚሁ አንድ አንድ ኢምፕሬዛም ሊያስዘጉዋቸው ይችላሉ ።

ስለዚህ በዚህ ሥርዓት የፍሬውን ብዛት የመሸጫውና የንግድ ዋጋው ሥርዓት ይቆማል ። ትልቁ ኢምፕሬዛ ታናሹን ብቅጡ አታፈሩምና ኮንኮሬንስ አታድርግብኝ ብሎ ሥራውን አቁሞ ያስዘጋዋል ስላልን ግን ያ ታላቁ ኢምፕሬዛ የሚያገኘውን የኢንዱስትሬ ፍሬ ፥ ትርፉን እንደ ገንዘባቸው ብዛት ፕሮፓርሲዮን ልክነት ወይም ሚዛን እየታየ ፥ ከታናሹ እንዳያፈሩ ከተዘጋው ኢምፕሬዛ ጋራ ትርፉን አብረው ነው የሚከፈሉት ። ስለዚህ እነዚያ ፋብሪካቸው የተዘጋባቸው ሶቼታ ፥ ቊጭ ብለው ትርፋቸውን ከገኙ ባይሠሩም ግድ የላቸውም ። እነዚያ ታላቅ ኢምፕሬዛም ፤ እነዚያ የማይረቡ የኢንዱስትሬ ፍሬ ገበያቸው ከልክሰረባቸው፥ የሚበልጥ ያገኛሉና ፥ ለነዚያ ለሚሠሩት ከፍለው ይበልጥ ይረባሉ እንጂ ፥ ምንም አይጐዱም።

በነዚሁም ፕሪባቶ የሚባሉ ሶቼታ አጠገብ ደግሞ ፥ የሕዝብ ኢምፕሬዛም (ሥራም)አሉ ። ማለት እነዚያ ኢምፕሬዜ መንግሥት አገር ፥ አውራጃ ፥ መንደር ፥ ቀሸት ፥ የሚሠሩትን ሁሉ ። አስረጅ)የደግነት ምጽዋት ሥራ ፥ የመድኃኒት ቤት (ሆፒታል)የመቄጠብ ቤት፥ የአደራ ቤት፤በቡር ፥ ትራም፥ አውቶቡስ (አውቶሞቢል)የሥጋ ከብት ማረጃ ፤ የሕዝብ መጠጫና መታጠቢያ ጥሩ ውኃ ፥ በከተማ የሌሊት ብርሃን ለኤሌትሪክ ፥ የጨውና የትምባሆ ፥ የብርና የገንዘብ ወረቀት ሞኖፖል ፥ እሱንም የመሳሰሉ ሁሉ። ኢምፕሬዛ ትልቅ ስትሆን፥ የአንድ ሰው ኃይል አይበቃትም ብቻው የሚኖር ሰው ፥ ብዙ ጊዜ የሚቄይ ኢምፕሬዛ ሊይዝ አይችልም ። ስለምን በሽታና ሽምግልና ፥ ድህነትና ሞት ያቋርጡታልና። ስለዚህ የሠለጠኑ ሰዎች ሶቼታ ማኅበር ሁነው ኢምፕሬዛን ሊያቆሙ ይሮጣሉ፤አንድነት ኃይል ይሰጣል እንደተባለ ። ግን በፊት እንደአመለከትነው የሶቼታ ዓይነት ብዙ ነው ። ከሁሉ የበለጠ ሶቼታ ኢንአኮምዲቲ አኖኒሜ (አሲዮን) የሚባሉ ናቸው ብለናል ፥ ማለት ብዙ ገንዘብ የሚሰበስቡ ፥ ረዢም ዘመን የሚቄዩ ፤ የክሬዲቶ አደራ ገንዘብ ሶቼታ ፥ የመርከብ ባሕር ሶቼታ ፤ የአሲኩራሲዮን የመጠበቅያና ማስረገጫ ማኅበር ፤ ትልልቆች የሕዝብ

የደግነት ሥራ ፡ የከናል ሰዊስና ፓናማን የመሰሉ ሥራ ሁሉ፤ አኖኒሜ የሚባሉ ሶቺታ ማኅበር ናቸው የፈጸሙት ፡ የሚፈጽሙትም ።

ግን በሶቺታ አኖኒሜም ትንሽ ጕድለት (ወይም ጕዳት ብንለው ይሻላል) አይታጣበትም ። ማለት ከማኅበርተኛውና ከአሥረው ዲሬክተር ዋና አላፊ በስልጣት ። አሁን ግን ሶቺታ አኖኒሜ ክርቴልና ትሬስት በሚባል ከማኅበርተኞቹ በመሥራታቸው በጣም ተሻሽለዋል ።

ክርቴሉ ንግድን ለማዳን (ማለት ዋጋ እንዳይረክስ)በጀርመን አገር ነው መጀመርያ የወጣ ብለናል ። እሱ አንድ ዓይነት የሆነ እቃ ፡ በአንድ ዋጋ ሊሸጥ ፤ ወይም የሸቀጡ ብዛት የተወሰነ ሊሆን ፤ ወይም በየወገናቸው ገበያን ለመከፋፈል፤ ወይም በአንድነት ሁነው ሸያጩን አንድ አንድ በነፍስ እንደሚገባቸው ሊከፋፈሉት ከአፍሪዎቹ (ከነጋዴዎቹና ኢንዱስትሪዎቹ)ሁሉ የስምምነት ኩንትራት ውል ነው።ትሬስት በአሜሪክ ነው የተጀመረ ብለናል ። ማለት ዋናዎቹ ዓይነቱ ኢንዱስትሪዎች ባለ ጋሮቻቸውን (ሌሎች ኢንዱስትሪዎች)ለማክሰር ሲሉ ከዋጋው በታች ይሸጡ ስለ ነበሩ ።

መንግሥትና ሕዝብም የኢምፕሬዛ ሥራ ሊከናወኑ ሊያዙ ይችላሉ ብለናል። በሕዝብ ዋናዎቹ ኢምፕሬዛዎች የተለዩ ቢሆን መልካም ነበር ። ግን አይደለም ፡ ሊሆንም አይችልም። ልምድና ወግ ከመንግሥታትና መንግሥታት ይቀርና ፡ ከአውራጃና አውራጃ ስንኳ በጣም የተለዩ ናቸው ። ማለት ለአንድ አገር ደግ የሆነው ለሌላው ክፉ ወይም ጕዳት ይሆናል ። ለምሳሌ ፡ በጀርመን አገር ባቡርን በመንግሥት ፡ በስትቲክ ኢንዱስትሪ በሶቺታ ናቸው ። በኢጣልያ መንግሥት ለሕይወት ማስፈጊያ አሲኩራሲዮን፡ ኪኒና ትምህርትና ጨው በፈረንሳዊ መንግሥትም በነቤሲንስ የልብስ መሥሪያ ፡በሲቢርስ የሰፀን ሥራ አሉዋቸው።

ሚካኤል ተሰማ።

በሚከተለው ይታተማል።

የአቡን ተክለሃይማኖት በዓል አከባበር ።

ግንቦት ፲፪ቀን የአቡን ተክለሃይማኖት የፍልሰት ዓመታዊው በዓል ስለ ነበረ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በክቡራን መኳንንትና በሠራዊት ታጅበው ወደ አቡን ተክለ ና ቤተ ክርስቲያን ሔዱ። ቅዳሴውም ከተፈጸመ በኋላ ታቦት ወጥቶ ዑደት ተደረገና ከዑደቱ በኋላ ቡራኬ ተደርጎ ሕዝቡ ወደየቤቱ ሔደ።ከዚህም በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በማረ ዓጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ።የአቡን ተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን ለመሳለምና በዓሉን ለማክበር የተሰበሰበውም ሕዝብ የብዛቱ ነገር ያስደንቃል።

በዚሁም በዓል የደብሩ ሹም ክቡር አለቃ ወልደ ትንሣኤ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኙ ።

ክብር ይእቲ ።

ርስተ እስራኤል አበው ኢከፈለ እንበለ ፀሐይ ኢያሱ ።
እምጣነ በፀሐይ ምድረ ሕዝበ እስራኤል ወረሱ ።
ወልድሰ ኢኮነ ኅባሴ ምክንያት ለርእሱ ።
አእጋረ አዳም ፀሐይ እምድኅረ ጸልመ ።
ሕሰመ ውስተ ርስቶሙ ጊሁ ።

ዕጣን ሞገር ።

ዓማ ተክለ አሚን ግዕደወ ድኅረ ተዘርአ በምድር ።
ወበውስተ ዓለም በጽሐ ለማእረር ።
እስመ ገበሁ አንዘ ሐዊን ከመ ዮሐንስ ዘንሥር።
አስተርአየ ላዕለ ደብር ።
መንክረ ትዒ ፆርዎ በመልዕልተ ዕፀ ግቡር ።
ለዘሞተ በፈቃደ ርእሱ ለዴቀያስ እግር ።

አሠረ ንጉሥ ።

ለእመ በዐምር ጌዴዎን ተወከፎ ለጠለ ለማይ ቆሪር ።
ኢተለክዎተ ምንተ ኃይለ ሥልጣኑ ሐመር ።
ኃይለ ሥላሴ ማእምር ።
ኢነሦሙ ጠለ ምስለ ዐምረ ክብር።
ከመ እሙ እስመ ጠለ ወፀምር ።

ስለ ልጅ አስተዳደግና ትምህርት ።

ሐለይኩ መዋዕለ ትክት፡ተዘከርኩ ዓመተ ዓለም ወአንበብኩ፡ሌሊተ ተዛዋዕኩ ምስለ ልብየ ወአንቃሕኩዋ ለነፍስየ።መዝሙር ፸፯ ሙሉ ሰው የሚያደርጉ ፫ ነገሮች አሉ።እነዚሁም ፩ኛ፡ የወላጅ አስተዳደግ፡፪ኛ፡የመምህራን አስተዳደግ፫ኛ፡የአገር አስተዳደግ ናቸው እያለ ብላቴናው ዳዊትን ያጫወተ መንፈስ በሚገባ ሲያጫውቶኝ አደረ።ልጅ በቤቱ ሳለ ከወላጆቹ በመልከም ሥርዓት ማደግ ይገባዋል፡ወላጆቹም ልጆቻቸውን በመልካም ማሳደግ ሊያሳድጓቸው ይገባቸዋል።ለምን ይህ ዛሬ ልጅ ዕውቅ ያለ ሕግን በቤቱ በሥራ ያደገ እንደሆነ ኋላ ምሉ ሰው ሲሆን ለሀገሩና ለመንግሥቱ በጎ ነገር ለመሥራት ዘወትር የታጠቀ ይሆናልና።ይህም ልጅ አእምሮው ትንሽ በትንሽ የሚሰፋና የሚያድግ የአእምሮውም ሐሳብ ጥቂት በጥቂት የሚሠለጥንና የሚጐለምስ የሚያጠራቅምም ነውና ከሁሉ በፊት በቤቱ ሳለ መልከምሥራትን ከእናት ከአባቱ ሊቀበል ግድ ይገባዋል፡ ልጅንም በሥራት የሚያሳድጉ ሦስት ሰዎች ናቸው።እነርሱም እሊሀ ናቸው እናት በማፍቀርዋ፤ አባት በሥልጣኑ፡ካህን በመንፈሳዊ ትምህርቱ። እናት ፤ ምክርዋ፤ አባት በአብነቱ፡ካህን በስብከቱ፤ ይህች በልጅነት የምትገኝ አስተዳደግ ከሁሉ በፊት ስለሚቀበላት በልቡ ጽላት የማትደመሰስ መታሰቢያ ሁና ተቀርጻና ብዙ ብርታት ያላት ዓይነተኛ መሠረት ይህች አስተዳደግ ናት ።ነገር ግን የቤት አስተዳደግ ብቻ አይበቃምና ልጅ ሊማረው የሚገባው ሌላ ብዙ ነገር ደግሞ አለ። እርሱም ንባብና ጽሕፈት ለይቶ ከአወቀ በኋላ ለሀገሩና ለመንግሥቱ የሚጠቅም ትምህርት በሕሪ ጥልቀቱን ገብቶ ሊዋኝበት ይገባዋል ሲል ብላቴናው ዳዊትን ያጫወተ መንፈስ ሲያጫውቶኝ አደረ።

ሰው የሀገሩን ቋንቋ መሠረት አድርጎ ወደ ባዕድ ቋንቋ ሲያልፍ ግርማው ነውና እንደ አሁኑ ልጆቻችን የሀገራቸውን ሥራት ሳይከተሉ ፋሙንም ሳይገሙ፤ ሰዋስውንም ሳይዘልቁ፤ ቅኔውን ሳይቈጥሩ፤ አቡሻሕርንም ሳይመረምሩ፤ በሕረ ሐሳቡንም በአንጎላቸው ሳያገቡ ፤ ብሉይና ሐዲሱንም በባሕረ ምሥጢሩ ገብተው አጥለቅልቀው ሳይዋኙበት ፤ ወይም ደግሞ እንደ ኢ—

ውሮጳውያን (ተክኒክ) የሚባል ለንግድ የሚሆን ትምህርት (ኖርማሊ) የሚባል የልጆች አስተማሪ የመሆን የሚፈልጉ የሚማሩበት ትምህርት (ጂንናዚዮ) የሚባል የመጻሕፍት ንግግርና ጥሩ የሰዋስው አነጋገርን የሚያሥለጥን ትምህርት (ሊቸዮ) የሚባል የፍላስፍነትና የሌላ ዕውቀት ነገርም የሚያሥለጥን ትምህርት (ኡኒቨርሲታ) በሚባል ከፍ ከፍ ያለና የረቀቀን በየዓይነቱ ዕውቀትም ሁሉ የሚነገርበት ትልቅ ትምህርት ቤት ገብተው ባሕሩ ጥልቀቱን ሳይዋኙበት ከዚሁም ከዚያም ላይ ሆነው መቅረታቸውን ሲያጫውቱኝ አደረ። መቸም ግርማዊት ንግሥታችንና ብልሁ ግርማዊ ንጉሣችን ስለዚህ ብለው ትምህርት ቤት ማቆማቸውና መምህራንንም መቅጠራቸው አልቀረም። ልጆቻችን ግን የሀገራቸውን ቋንቋ መጀመሪያ ማወቅ ክብራቸውና ማዕርጋቸው መሆኑን ሳያውቁ ያበሻ ቋንቋ ብማር ምን ያደርግልኛል እንጀራ የሚወጣለትና አዋቂ የሚባል ትንሽ የፈረንጅ ቋንቋ የተማረ ነው እያሉ ሲናገሩ እንሰማለን ።

የአሁኑ ልጆቻችን የሀገራቸውን ቋንቋ ወደ ግራ ጥለው የባዕድ ቋንቋ ለመማር ብቻ ስለሚጣጣሩ ከፈረንጁም ከሀገራቸውም መሠረት ያለውን ትምህርት ስላልተማሩ ሳያብቡ ሳያፈሩም ዘለዓለም ቡቃያ ሆነው ይኖራሉ በመጀመርያ በሀገራቸው ቋንቋ ግሥ ገሥው ሰዋስው ዘልቀው ወደ ባዕድ ቋንቋ አልፈው ቢሆን ግን ንባቡን ብቻ ለመማር ያስፈልጋቸው ነበር እንጂ የሰዋስውን አካሔድና አምደ ምሥጢሩን ለማወቅ አያስቸግራቸውም ነበር ። አሁንም መሠረት የሌለው ዕውቀት ይጐዳል እንጂ አይጠቅምምና ፅኑ ሕግ ተደርጎላቸው ፩ኛ ንባብና ጽሕፈት ተምረው፤ ፪ኛ ግሥን ገሥው ፫ኛ ሰዋስውን ዘልቀው ራሳቸውን ችለው ወደ ባዕድ ቋንቋ ትምህርት ቤት ሲያልፉ ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው በጎ ነገር ለመሥራት ዘወትር የታጠቁ ይሆናሉ ስል ብላቴናው ዳዊትን ያጫወተ መንፈስ ሲያጫውተኝ ያደረ እጫውታችሁ አለሁ ።

አባ ተስፋ ሚካኤል ከ ሡ ።

ፈረሶች ።

ፈረስ ከጥንት ጀምሮ ደግና የተሻለ የሰው ወዳጅ እንስሳ ነው ። አንድ ሕዝብ ብዙና ጥሩ ጥሩ ዓይነት ፈረሶች ቢያገኝ ሀብታም ይሆናል ። መንግሥትም ቢሆን የተሰናዱ ጥሩ ጥሩ ዓይነት ፈረሶች ያሉት እንደሆነ ሥልጣኔውና ብርታቱ በፈረሶቹ ይገለጣል ።

ክክርስቶስ ልደት በፊት ብዙ ሺ ዓመታት የነበሩ የጥንት ሕዝብ በጦርም ሆነ በሰላም ጊዜ ፈረሶችን ቀልበው አሰናድተው ያስቀምጣሉ። ዜንዳባስታ የተባለ የህንድ መጽሐፍ አምስት ሺሕ ዓመት ክክርስቶስ ልደት በፊት ህንዳውያን ለወታደሮች እቃን የሚያመላልሱ የፈረስ ሠረገሎች እንደ ነበርዋቸው ይናገራል ። ደግሞ ከማየ አይኅ በፊት የቻና ሕዝብ ፈረሶች ነበርዋቸው ። ግብፃውያንም ክክርስቶስ ልደት በፊት ሁለት ሺሕ አራት መቶ ዓመት ያህል ፈረሶች ነበርዋቸው ።

የጥንት ሰዎች ፈረሶች እንደ ነበርዋቸውና በሥርዓት እንዲያስቀምጥዋቸው ብቻ ተናግሬ ዝም አልልም ለምሳሌ የሚሆን ደግሞ የባቢሎን ንጉሥ ስምንት መቶ ድንጉላ ፈረስ (አለሌ) ሺ ስድስት መቶ ባዝራ (ወላድ ፈረስ) ነበሩት ። ሴሶርስ የተባለ የግብፅ ፈርዖን (አጤ) ወታደሮቹ የሚቀመጡዋቸው ሰሳ ሺሕ የሚሆኑ ጥሩ ጥሩ ጠንካራ ፈረሶችና አሥራ ሁለት ሺሕ የጦር ሠረገሎች ነበሩት። ደግሞም የንጉሥ ሰሎሞን የፈረስ ማርባቱን ነገር አነሣለሁ ። ንጉሥ ሰሎሞን በጊዜው ፈረሶችን ለማርባት ከግብጽ አገር ድንጉሎችን ወሰደ ። ንጉሥ ሰሎሞንም ፈረሶችን አርብቶ ብቻ ዝም አላለም ። ነገር ግን ወደ ግብፅ አገር ፈረሶች ሰዶ እያስነገደ ብዙ ጥቅም ያገኝ ነበር። ንጉሥ ሰሎሞን አሥራ ሁለት ሺ የኰርቻ ፈረሶች አራት ሺ ለሥራ የሚሆኑ ፈረሶች ሺ አራት መቶ የጦር ሠረገላም ነበሩት ። በታሪክም የዓረብ ፈረሶችና የኢትዮጵያ ፈረሶች ዘራቸው ከሰሎሞን ፈረሶች ዘር እንደ ሆነ እንረዳለን። ለኰርቻና ለጋልቢያ የሚሆኑ ፈረሶች የሚበልጡት ከምሥራቅ አገርና ከምዕራብም ከመንጉሊ አገር ናቸው ። ያሁን ዘመን ሰዎች በማማርም ሆነ በብርታት ፤ በመፍጠንም፤ በቁመት ፤ የበለጠውን የፈረስ ዓይነት እንዲያገኙ ዘሩን እየመረጡ ያዳቅላሉ ።

ኤውሮጳውያን ከዓረቦች ፈረሶች ዘር በብዙ ወስደው አራብተዋል ዘሩም በጥንካሬ ሆነ በፈጣንነት የበለጠ ነው ። የዚሁም ዓይነት እንግሊዝ ዘር ይባላል ።

በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አምስት ዓመት በኒውማርክ (ህንድ) የእንግሊዝ ዘር ያምቢክ በተባለውና ዓሊ በተባለው ጥሩ የዓረብ ዘር መካከል እሽቅድድም ተደረገ ። የሜዳውም ርዝመት ሰስት ማይል ነበረ ። በዚሁም እሽቅድድም ያምቢክ ከዓሊ የበለጠ አሥራ ስድስት ተኩል ኪሎ ተሸክሞ ነበር። ነገር ግን በፍጥነት ዓሊን ቀደመው ። ባሁኑ ዘመን ሕዝብ ፈረሶችን ማርባትና አሰናድቶ ማስቀመጥ ዋና ነገር ሆንዋል ። አሁን በያገሩ ያለውን የፈረስ ማርባት ሥራ አኳኋን በዝርዝር ለይቼ ለመጻፍ ቦታ ይፈጅብኛል ። ከትልቁ ጦርነት በፊት በመላ ዓለም የነበሩ ፈረሶች ቍጥራቸው ሰሳ ሚሊዮን ከአምስት መቶ ሺሕ ያህል ነበር ። ዓይነታቸውም አርባ ዘጠኝ ክፍል ይሆናል ።

እንግዲህ ስለ ኢትዮጵያ ፈረሶች እንናገራለን፤ በፊት እንዳልነው እነዚህ ፈረሶች ከሰሎሞን ፈረሶች ዘር የመጡ ናቸው። በኢትዮጵያ ባያሌ አገር የምሥራቅ ዘር ዓይነት ፈረሶች አሉ። ግን የኢትዮጵያ ፈረሶች በጣም ትልልቆች አይደሉም። ትልቅነታቸውም መቶ ሠላሳ ሁለት እስከ መቶ አርባ ስድስት ሳንቲም ይሆናሉ። አከላታቸውም ወፍራም አይደለም አጥንታቸው ም ቀጭን ነው። እንዲሁም ሰውነታቸው አጭር ሁኖ አንገታቸው የከረረ ነው፤ ራሳቸውም ትንሽ ሁኖ ለትንሽ ሜዳ ሩጫ ፈጣኖች ናቸው ። ከመቶም ፈረሶች የሚበልጡት የአግራቸው አቋቋም ያለሥርዓት ነው።ሌላም ጕድለት አለባቸው። ከሽኾናቸው በላይ ያለው አጥንት ጠንካራ ነው ። ጥፍራቸውም የፀና ነው ።

የኢትዮጵያ ፈረስ ፍጥነቱ ሁለቱን ሺሕ ሜትር ከሁለት ደቂቃና ከአሥራ ሁለት ሴኮንድ እስከ ሁለት ደቂቃ ከአርባ አምስት ሴኮንድ ይጨርሰዋል ። የኢትዮጵያ ፈረስ ዋናው መልኩ አምባላይ፤ ጥረኝ፤ ዳማ፤ መጋል፤ ቦራ፤ ቡላ፤ ዳለቻ ነው ። ያሁኑ ዘመን የኢትዮጵያ ፈረስ ለብርቱ ሥራ የሚሆን ዓቅም የላቸውም ። ባሁን ዘመን የምዕራብና የምሥራቅ ሕዝቦች

ፈረሶችን ለማርባትና በሥርዓት ለማድረግ ብዙ ጥረትና ጥንቃቄ እያደረጉ የፈረስን ዘር ያጠራሉ ። በኢትዮጵያ ግን ፈረስ ማርባትና በሥርዓት ማሳደግ በትክክል አልተደረገም። ፈረሶቹም የተሻሉ አይሆኑም።እያደርም ዘራቸው እየተበላሸና ቁመታቸው እያነሰ ይሔዳል ። ደግሞም የዚህን ምክንያት በሚከተለው እንገልጻለን ።

፩ኛ፡ በኢትዮጵያ ፈረሶችን ማርባት፤ በሥርዓት ማሳደግ፤ ጉድለታቸውንም መርምሮ ማወቅ፡ዘራቸውንም፡ከየይነቱ መምረጥ ፤ እንደ ሚገባ ገርቶ ማሳደግና መቀለብ በጠቅላላውም ፈረሶችን መከባከብ ባለመኖሩ ነው።

፪ኛ፤ አገሩ ከሌሎች አገሮች ጋራ ተራርቆ ይኖር ስለ ነበረ ነው ።

፫ኛ፤ በኢትዮጵያ ፈረስ አርብቶና አሳድጎ የሚገኘውን ጥቅምና ብልጥግና ለመንግሥትና ለሕዝቡ ዋና ነገር ሁኖ ባይታየው ነው። አሁን ግን መንገድ ስለ ተከፈተ ከሌሎች አገሮች መገናኘት ሁንዋልና የርሻና የከብት ማርባት ይሻሻል ይሆናል። ደግሞ ኢትዮጵያውያን የከብትን አስተዳደግ እውቀት እንደ ሚገባ ሳያገኙ ደኅና በቀሎ ለማግኘት አይችሉም። ምንም እንኳ የአህያ አለሌ ቢገኝ ይህ ብቻ አይበቃም። ነገር ግን ባዝራዎቹ የተመረጡ እንዲሆኑ ያስፈልጋል። ማን ያውቃል የተመረጡና ብርቱዎች ፈረሶች የሚፈለጉበት ቀን ይመጣል፤የኢትዮጵያ ሕዝብም የፈረስ ማርባትና በሥርዓት አስተዳደግ በገር ውሥጥ ባህመኖሩ ይጸጸት ይሆናል። ከሥር እስከ አሥራ አምስት ዓመት ፈረስና በቅሎ ለቀላል ሥራ እንኳ ቢሆን እንዳይታጡ ያስፈራል

አሁን ኢትዮጵያ ወደ ሥልጣኔ መንገድ እንደ ተራመደች ደኅና መንገድ መበጀቱ ፤ ደኅና ደኅና ቤት መሠራቱ፤የጲስጣና የስልክ ሥራ ደኅና ሁኖ መተከሉ ፤ ተማሪ ቤትና ሆስፒታል መከፈቱ፤አታክልት በሥርዓት መተከሉ ፤ እንዲሁም የመሰለ ብዙ ሥራ መከናወኑ ይመሰክራል ። እንደዚሁም ሁሉ የከብት ማርባትና በሥርዓት አስተዳደግ በቶሎ ተጀምሮ የከብት ዘር የተሻለ ሁኖ ኢትዮጵያ ከብት በማባርት በሚገኘው ትርፍ እንድትበለጥግ ተስፋ እናደርጋለን ።

ደ ሰኒያቢን ።

ካፒቴን ደ ካባሌሪ ኢምፔሪያል መስኩብ ።

ያማረ ጨወታ በግርማዊ ንጉሥ ቤት ።

ግንቦት ፲፭ ቀን ማታ ብዙ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና መኳንንቶች፡የኢትዮጵያ ሚኒስትሮችና መኳንንቶችም በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ቤት ራት ተጋብዘው ነበር ። ከራት በኋላም በሚያንፀባርቀው አዳራሽ ዳንስና ኰሜዲ እንዲደረግ ተሰናድቶ ነበርና ጨዋታውን ለማየት የተጠሩ ሰዎች ሁሉ በማረው አዳራሽ ተሰበሰቡ።ግርማዊ ንጉሥና ልዕልት መነንም ከመኳንንትና ከወይዛዝሩ ጋራ መጥተው አምሮ በተሰናዳላቸው ዙፋን በተቀመጡ ጊዜ ጨዋታው ተጀመረና ድንቅ ሁኖ ታየ። ኰሜዲውም እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበረ።በጨወታውም መካከል ጭብጨባው ይቀልጥ ነበር።

ከውጭ አገር በባቡር የገቡ ።

ክቡር አቶ በላቸው የአለካል ሞኖፖል ዋና ዲሬክተር ስለ ሞኖፖል ሥራ ተልከው ወደ ፈንረሳዊ አገር ሔደው የሔዱበት ጉዳይ ተከናውኖ ተፈጽሞላቸው ሚያዝያ ፴ ቀን ገቡ።

ክቡር አቶ ወልደ ማርያም ውል መርማሪ ።

ከባለቤታቸው ጋራ ከፈረንሳዊ አገር ግንቦት ፯ ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

ወደ ውጭ አገር በባቡር የተሳፈሩ ።

ግንቦት ፱ ቀን ክቡር ነጋድራስ መኰንን እንዳልካቸው የንግድ ሚኒስትር የኢትዮጵያ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር በሎንዶን ተብለው ወደ እንግሊዝ አገር ለመሔድ ከክብርት ባለቤታቸው ጋራ ተጓዙ።ክቡር ነጋድራስ መኰንን ለመሸኘት ወደ ባቡር ማረፊያ የወረዱ መኳንንቶችና ወይዛዝሮችም ብዙ ነበሩ።

እንስሳን በማረድ ስለሚሆን ጉዳት ።

በኢትዮጵያ አገር ከዛሬው እየባሰ ሥጋ ሳይወደድ፤ አይቀርም እንስት የሆኑ በጎችና ፍየሎች እየታረዱ ተተበሉ ባዳልና በሱማሌ አገር እንኳን ላርደው ሊበልዋቸው አገባያም አውጥተው አይሸጧቸው በትንሱ ብነገምተው በኢትዮጵያ አገር በ፭ ዓመት ውስጥ ፲ ሚሊዮን የሚያህሉ እንስት እንሰሶች ሲታረዱ ጉዳቱና ከሣራው ብዙ ነው። ያ፭ ዓመት ችግር ለብዙ ዓመት ጥጋብ ይሆናልና ይህንን የሚያሰዝን ትልቅ ከሣራ በቶሎ ብንተወው ይሻላል ።

ለመንገድ ስለሚያስፈልግ ድንጋይ ።

በአዲስ አበባ ከተማ፪ ዓይነት በሀ ድንጋይ አለ ነጭና ጥቁር። ከዚሁ የብርጭቆ አሸዋ ያለበት የሌለበት ዓይነት አለ፤ የብጭርቆ አሸዋ ባለው በሀ ድንጋይ የተሠራው መንገድ ቶሎ ይበላሻል። የብርጭቆ አሸዋ በሌለበት በሀ ድንጋይ የተሠራው መንገድ ደህና ሆኖ ለብቻው ተለይቶ ይታያል ።

የብርጭቆ አሸዋ ያለው በሀ መቼም ቢሆን ደረቅ ነውና እርስ በርሱ እየተፋጨ እየተሸሸ ያልቃል።መኪናም ይጨርሳል። ለመንገድ የሚሆነውን በሀ ድንጋይ መምረጥና መመርመር ያስፈልጋል ። አለሙ አብተ ሚካኤል ።

ትልቅ ግብር ።

ግንቦት ፲፫ ቀን ክቡር ሊጋባ ወዳጄ ለመኳንንትና ለሠራዊት ሙሉ ግብር አሰናድተው ጠርተው ነበርና በዚሁ ቀን ከ፰ ሰዓት ጀምሮ መኳንንቱ ሁሉ ጭፍራውን እያስከተለ ወደ ክቡር ሊጋባ ወዳጄ ቤት ይጓዝ ጀመር የተሰበሰበውም ሰው እጅግ ብዙ ሁኖ ከሊጋባ ወዳጄ ግቢ ፊት ባለው ሜዳ ቁሞ በተራ በተራው ይገባ ነበር። በግቢውም መካከል እጅግ ሰፊ የሆነ አዳራሽ ድንኳን ተተክሎ በዚያ ውሥጥ በየክፍሉና በየመዓርጉ ሁኖ ለመኳንንቱና ለሠራዊቱ የሚበቃ በየዓይነቱ ምግብና መጠጥ ቀረበ ነበር።ልክ ስድስት ሰዓትም ሲሆን ግብሩ ተጀመረና እስከ ማታ ድረስ ሠራዊቱ በደስታ ሲመገብ ውሎ ስለ ሲሳዩ ብዛትና ስለ ሥራዓቱ ማማር ክቡር ሊጋባ ወዳጄን እያመሰገነ መንግሥታችንን ያኑርልን እያለ ወደየቤቱ ሔደ ።

የሚሸጥ የእንጨት መሰንጠቂያ መኪናና ካሚዮን።

በእንግሊዝ ሌጋሲዮን ቆንስላ ትእዛዝ አስበ ተፈሪ ያለው የሚስትሪ ፕራምጅ ጋንጋሬም የእንጨት መሰንጠቂያ መኪናና አንድ ካሚዮን ቅዳሚት ግንቦት ፲፪ ቀን በ፱ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ ሚስርስ መሐመዳሊና ኩባንያው በሐራጅ መሸጣቸውን እናስታውቃለን ግንቦት ፰ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ምሕረ ።

የእንግሊዝ ሌጋስዮን ቆንስላ ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ብዙ የውጭ አገር ሰዎች በጋበዙበት በግንቦት ፲፩ ቀን ማታ በእባብ ምሳሌ የተሠራ የብር ቀበቶ በግርማዊ ንጉሥ አዳራሽ ተገኝቷልና ይህ ዕቃ የጠፋበት ሰው ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይጠይቅ።

Avis.

Il a été trouvé une ceinture en argent dans la salle de soirée offerte par S. M. le Négus Teferi, dans la journée du 19 courant. Le propriétaire du dit objet est prié de s'adresser au bureau du Ministère des affaires étrangères.

ፔር ዳኔይ ።
አበካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ፡ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዶ.ር አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፣ የርሻ፣ የፋብሪክ፣የደን፣ የማዕድን ሥራ፣ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ሉምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተኑሁት እጅግማስፈያ የሆነጣዕሙም በጣም የተስማማነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ማረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ΕΓΓΥΗΣΙΣ ΕΛΛΗΝΙΚΗΣ ΚΥΒΕΡΝΗΣΕΩΣ
KONIAK

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ስያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሪስ በአደንና በጀቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያስናኛነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በኮፖሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በኮፖሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ኒሳዐ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒሳ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔሬቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪየር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ። የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨሁጥ የቁጥኝና የቋቁቻ ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም ሽሽታ ሁሉ ያሽማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ .

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሉሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ክፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
5me ANNÉE № 22

ሐሙስ ግንቦት ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 30 MAI 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በዓመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር በዓመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በኢትዮጵያ ውስጥ የቦልሼቪክን ነገር ለማስተማር ስለ አሰበ ስለ ዶክተር ገብሬሎፍ ከገር መውጣት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ተራው ሰው ለውጭ አገር ሰዎች መልካም ሥራ መሥራት ልማዳቸው መሆኑ የታወቀ ነው ። ነገር ግን በማናቸውም አገር ቢሆን አንድ አንድ ክፉ ሰው አይታጣምና ከነዚሁ ከውጭ አገር ሰዎች አንድ አንዱ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በመልካም ኑሮ ኑረው፥ ገንዘብ አግኝተው፣ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ አገሩንም ሕዝቡንም እየነቀፉ ጋዜጣ ይጽፋሉ ። የአውሮፓም ሕዝብ ምንም የተማሩትና ትልልቆች ሰዎች ነገሩን እውነት ነው ብለው ባይቀበሉ እንኳ ባላገሮችና ሴቶች በጋዜጣ የተጻፈው ሁሉ እውነት ሳይመስላቸው አይቀርም። ይህንም ያደረጉ ቍጥራቸው ብዙ ነው ። ከነዚሁም አንዳንዱ የማይገባ ሥራ እየሠሩ ከገር እንዲወጡ የተፈረደባቸው ናቸው ።

አሁን ባለፈው ዓመት እንኳ ዶክተር ጋራቢዲያን የሚባል የአርመን አገር ሰው ኮኬይንና ሞርፊን እየሸጠ ሕዝቡን በመጉዳቱ ከገር ስለ ወጣ ወደ ዠኔብ ሔዶ የጻፈውን የሐሰት ጋዜጣ ብዙ ሰዎች አንብበውታል ። ነገር ግን በከንቱ ደከመ እንጂ እውነት ነው ብሎ የተቀበለው አንድም ሰው አልተገኘ።

ደግሞ ያናሽ የሚባል የጀርመን አገር ሰው የማይገባ ክፉ ሥራ ስለ ሠራ ተፈርዶበት ከገር ስለ ወጣ በኢትዮጵያ ላይ የሐሰት ወሬ እየጻፈ አሳትሟል ። አሁን ደግሞ አስቀድሞ የማዘጋጃ ቤት ሐኪም የነበረ ዶክተር ገብሬሎፍ የማይገባ ክፉ ሥራ ሲሠራ ተገኝቶ ከገር ስለ ወጣ በኢትዮጵያ ላይ ክፉ ነገር የጻፈ እንደ ሆነ ነገሩን የሚሰሙ ሁሉ እውነት እንዳይመስላቸው የሠራ-

በመስኮብ መንግሥት የሕዝቡ ብዛት፤ የገሩ ልማት፤ በዓለም ሁሉ የታወቀ ነበር ።

ነገር ግን በ፲፱፻፲ ዓመተ ምሕረት አንዳንድ ክፉ ሰዎች ወስላታውንና ማንዘራሹን፤ ሌባውንና ሥራ ፈቱን ፥ ባንድነት ሰብስበውና አድማ አስነሥተው የነገሥታቱን ዘር በሙሉ አጠፉ። ቀጥለውም መሳፍንቱንና መኳንንቱን፤ ጳጳሳቱንና ቀሳውስቱን፥ ባላባቶችንና የጨዋ ልጆችን፤ አጠፉ። ቤተ መንግሥቱንና ቤተ ክርስቲያኑንም እየዘረፉ አጠፉ። አስቀድሞ በመዓርግና በክብር የሚኖሩትን ሀብታሞችና ባለጠጎችን ሁሉ ድንጋይ እያስፈጩ፥ እንጨት እያስፈለጡ፥ ሸክም እያሸከሙ፥ አስቀድሞ እነርሱ የሚሠሩትን የውርደት ሥራ ሁሉ እያሠሩ፥ አዋረዷቸው፤ በዚህ ላይ ደግሞ አንድ ቤት ለአንድ ሰው ብቻ፥ አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ብቻ፥ መሆን አይገባም እያሉ፥ የመሳፍንቱንና የመኳንንቱን ሚስቶች እየነጠቁ እየወሰዱ፥ ማላገጫ አደረጓቸው። በዚህ ሁሉ ምክንያት በመስኮብ አገር የሰው ደም እንደ ውሃ ፈሰሰ። በየአደባባዩና በየደጁ የሚታረደው የሰው ሬሳ ብቻ ሆነ። አገሩም ጠፋ፤ በዚህም ምክንያት መሬት የሚያርስና ንግድ የሚነግድም ስለ ታጣ በገሩ ውስጥ ረኃብ ሆኖ ከሰይፍና ከጠመንጃ የተረፈው ሕዝብ በችጋር አለቀ። ይህንንም ሁሉ ሁከትና መከራ ያመጡ ሰዎች ቦልሼቪኮች ተባሉ ።

ነገር ግን ከሕዝቡ መካከል መንግሥታቸውንና ንጉሣቸውን የሚወዱና የቦልሼቪክን ኑሮ የሚጠሉ አንድ አንድ ሰዎች እየተሰደዱ በአውሮፓና በሌላውም አገር ተበተኑ። ለእነዚህም እየተሰደዱ ከአገራቸው ለሚወጡ መስኮቦች የአውሮፓና የሌሎችም መንግሥቶች ልብስም ምግብም ማረፊያም እየሰጡ በብዙ ረዱቸው ። ይህም ወሬ በተሰማ ጊዜ ከቦል-

ሹለ ጸናባቸው፡ ወዲያውም ሁከት ለማስነሣት ሲሉ፡ በደቀኞች እየመሰሉ ወደ አውሮፓና ወደ ሌላውም አገር እየገቡ፡ ውሥጥ ለውሥጥ ሁከት ሲያስነሡ እየተገኙ እየተያዙ ፡ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ።

ከነዚህም ከደቀኞቹ መስከቦች አንድ አንዱ ወደ ኢትዮጵያ ስለ መጡ የኢትዮጵያም መንግሥት ሥራ ለሚያውቁት ሥራና ደመወዝ እየሰጠ፡ ሥራም ለማያውቁት በቸርነቱ ገንዘብ እየሰጠ በብዙ ሲረዳቸው ኖረ ። የኢትዮጵያም ሊቃውንትና ካህናቱም በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ቦልሼቢኮች በግፍ ስለ ገደሉት ስለ መስከብ ንጉሥ የፍታት ጸሎት አድርገው ወዳጅነታቸውን ገለጡ ።

ነገር ግን በስንዴ መካከል እንክርዳድ አይጠፋምና ከዚሁ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው ከመጡት መስከቦች መካከል ዶክተር ገብሬሎፍ የሚባለው በማዘጋጃ ቤት የሐኪምነት ሥራ አግኝቶ ሲኖር በሚሠራው ሥራና በሚናገረው ነገር ሁሉ የቦልሼቢክ ወገን መሆኑ እየተገለጠ ይሔድ ጀመር ።

መጀመሪያ ያንዱን ያንዱን ሰው የባልንጀራውን ሚስት ነጥቆ በግልጥ ወሰዳት፡ ዶክተር ገብሬሎፍን ለመቃወምና ለመክሰስ የማይቻለው ስለ ሆነ ከመዋረድ ራሱን ባጠፋ ይሻለኛል ብሎ በገዛ እጁ ጠመንጃ ተኩሶ የገዛ አካሉን አጠፋ ።

ቀጥሎም ከልዩ ልዩ አገሮች እየመጡ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ሐኪሞች ሕዝቡን እያከሙ ሲረዱ አይቶ የእኔ ሃይማኖት የመስከብ ኦርቶዶክስ ነውና በሃይማኖት የምመስላችሁ ሐኪም እኔ ሳለሁ ወደ ሌሎች ሐኪሞች አትሒዱ እያለ እየመከረ ሕዝቡ በበሽታ እንዲጎዳ አደረገ ።

ሶስተኛም የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ዲሬክተር የነበረውን ሙሴ ሐና ቢይ ታሞ ነበርና ዶክተር ገብሬሎፍ በድፍረትና በችኮላ ሲያክመው ያንጊዜውን ሞተ ።

ይህም ሁሉ የክፋት ሥራው እየተገለጠ ስለ ሔደ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ከሐኪምነት ሥራው አስወጣው።

አንዳንድ ሰዎች ለመታከም ወደ እርሱ ቤት ሲሔዱ አገር የሚያጠፋ፡ሕዝቡን የሚጎዳ፡ክፉ ምክር ይመክር ጀመር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እግዚአብሔርን የሚፈሩ ንጉሣቸውን የሚያከብሩ ክርስቲያኖች ስለሆኑ ምክሩን መቀበላቸው ይቅርና እንዲያውም ወደ ዘበኞች አለቃ እየሔዱ የነገሩትን ምስጢር ሁሉ ያስታውቁበት ጀመር ።

የዘበኞች አለቃም ይህን ነገር ለመረዳት ሲል የታመኑ ሰዎች ፈልጎ ሰላዮች አደረገበት። እነዚህም ሰላዮች የእርሱ ወገኖች ቦልሼቢኮች መስለው ስለ ታዩት ምስጢሩን ሁሉ ያጫውታቸው ጀመር። በመጨረሻውም ንግሥትና ንጉሥ፥ መሳፍንቱና መኳንንቱ ፡ ሊቃውንቱና ካህናቱ ፡ ወታደሩና ሕዝቡ ሁሉ፡ በአንድነት በተሰበሰቡበት ስፍራ የሚፈነዳ ቦምብ ወርውሮ፡ባንድ ጊዜ ለመፍጀትና ኢትዮጵያን ለማጥፋት አስቦ ከቡልጋሪ ከተማ ከሶፊያ እንዲመጣለት ወደ አንድ ወዳጁ የጻፈውን ደብዳቤ ላንዱ ሰላይ ስለ አሳየው ፡ ሰላዩ መጥቶ ለዘበኞች አለቃ በምስጢር ነገረበት ።

ከሶስት ወር በኋላ ግን ዶክተር ገብሬሎፍ ለጻፈው ደብዳቤ ምላሽ የሚፈነዳውን ቦምብና ሌላም መሣሪያ ልከንልሃል የሚል ደብዳቤ መጣለት። ዶክተር ገብሬሎፍም ቦልሼቢክነቱ እንደ ተገለጸበትና እንደ ተወራበት ልቡ ጠርጥሯልና የታመነ መስሎት ፡ ይህን የመጣለትን ደብዳቤ ለአንድ ሰው ሲያሳይ ይህ ደብዳቤ በድንገት ወደ ዘበኞች አለቃ እጅ ገባ ።

የዘበኞች አለቃም ከሶስት ወር በፊት ነገሩን በሰላዮች አግኝቶት ቈይቶ ነበርና አሁን ይህን ደብዳቤ ስላገኘ ነገሩ ሁሉ ከሥሩ እስከጫፉ የተያያዘና እርግጠኛ መሆኑን ተረዳው። ከዚህ በኋላ ዶክተር ገብሬሎፍ የኢትዮጵያን መንግሥት የሚያጠፋና ሕዝቡን የሚጎዳ ይህን ክፉ አሳብ ለደጉና ለክርስቲያኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስተማር በማሰቡ ፡ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ስለ ታዘዘ በዘበኞች ተይዞ በግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት ከአዲስ አበባ በባቡር ተሳፍሮ ሔደ ።

የዶክተር ገብሬሎፍን የቦልሼቢክነት ሥራ ከሥርእስከ ጫፉ የሚያስረዳና ሚገልጽ የደብዳቤው ቃልበቃል በሁለተኛው ጋዜጣ ይታተማል ።

የአክሱም ጳጳስ ስለ ሚባሉ የግሪክ ሜትሮፖሊስ ሞንሲኘር ኒኮላ ወደ እስክንድርያ መመለስ።

ግንቦት ፲፰ ቀን ብፁዕ ሞንሲኘር ኒኮላ ወደእስክንድርያ ለመመለስ የሚነሡበት ቀን ስለሆነ የግሪክ ቈንስል ክቡር ዶክቶር ዜርቦስና ግሪክውያን ሁሉ ወደ ባቡር ማርፌያ ወርደው ለመሸኘት ተሰበሰቡ። ብዙ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና መኳንንቶች፥ ብዙ ትልልቅ ነጋዴዎችም እስከ ባቡር ማርፌያ ወርደው ሸኝዋቸው ።

ብፁዕ ሞንሲኘር ኒኮላም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ጥልቅ ምስጋናቸውን አቅርበዋል ። ደግሞ የኢትዮጵያ መኳንንትና ሊቃውንትን ሁሉ እጅግ አመስግነዋል። በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱም የእግዚአብሔር በረከት እንዲያርፍበት መልካም ምኞታቸውን እያቀረቡ በአዲስ አበባ በቈዩበት ጊዜ ሁሉ ባዩትና በሰሙት በተመለከቱትም ነገር በጣም ደስ እንዳላቸው ተናግረዋል።ከመውደዳቸውም የተነሣ እንደገና ተመልሰው ኢትዮጵያን ለማየት ተስፋ እያደረጉ ሔዱ ።

በመንገዳቸው ሁሉ እግዚአብሔር እንዲረዳቸውና ወደ ከበረው ስፍራቸው በደኅና እንዲደርሱ ብርሃንና ሰላም ይመኝላቸዋል ።

ማስታወቂያ ።

የሚሸጥ ማተሚያ መኪና ።

በእግር የሚዞር መኪና የቅጹ ስፋት ፳፱ ሳንቲም በ፴፭ ሳንቲም ነው ። አንድ በሽቦ መስፊያ መኪና ። አንድ መጠቀጠቂያ መኪና ። አንድ ማፈፍያ መኪና። የኢትዮጵያና የፈረንሳዊ የአርመንም ፊደላት ጭምር ይሸጣል ። ሁሉም አዲስ እቃ ነው ።

ሊገዛ የሚፈልግ ሰው ሙሴ ሐራንት ባግዳሳርያንን ይጠይቅ። ስፍራውም በራስ መኰንን መንገድ ነው ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ዋና ዲሬክተር ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ስለ ትምህርታቸው ከጀርመን አገር የመጣላቸውን የምስክር ወረቀት በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ፊት እንደ ተቀበሉ ።

በትጋትና በቅንነት ሥራውን የሚሠራና መንግሥቱን የሚያገለግል ሰው በሕይወቱም በሞቱም ለስሙ መጠሪያ የሚሆን ዋጋ አያጣም ።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የመንግሥት ሥራ ይዘው መንግሥታቸውን ሲያገለግሉ ፳፩ ዓመታቸው ነው።በዚህም ሁሉ ዘመን ሥራቸውን ሁሉ በትጋትና በቅንነት ስለ ሠሩ ከማዕርግ ወደ ማዕርግ እየወጡ አሁን የውጭ ጉዳይሚኒስተር ዋና ዲሬክተር እስከ መሆን ደርሰዋል።ይህም አሁን የደረሱበት ማዕርግ ከትልልቆቹ ከውጭ አገር መንግሥቶች እንደራሴዎች ጋር የሚያገናኝ ስለ ሆነ እጅግ ከፍ ያለ ማዕርግ መሆኑ የታወቀ ነው።

ደግሞ የመንግሥታቸውን ሥራ በትጋት በመሥራት ላይ በዕረፍት ሰዓታቸው ጊዜ እያሰቡ የመጻሕፍትን ድርሰት እየደረሱ ፳፩ መጻሕፍት ጽፈዋል ስለዚህም በምሉ ኢትዮጵያና በአውሮፓም በሌሎችም በውጭ አገሮች ሁሉ ስማቸው የታወቀ ሆነ ።

በአውሮፓም በየመንግሥቱ የሚኖሩ ብዙ ትምህርትና እውቀት ያላቸው ሊቃውንት ሰዎች የማኅበር ቤት እያቆሙ እውቀት የሚያሰፉበትን፡ ሕዝብ የሚሠለጥንበትንና የሚበለጥግበት፡ መንግሥትም የሚጸናበትን፡በንድነት እየተሰበሰቡና እየተማከሩ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ይጽፋሉ ።

እነዚህም የእውቀትና የጥበብ ሊቃውንቶች ክቡር ብላቴን ጌታ ከጻፏቸው መጻሕፍቶች አንዳንዱን በየቋንቋቸው እያስተረጐሙ ስለ እነሱ በየመጻሕፍታቸው ውሥጥ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ስም በምስጋና እያገቡ ጽፈውላቸዋል ።

በጀርመን አገር ያሉት የእውቀትና የጥበብ ሊቃውንት ማኅበር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ምንም አገራቸው ኢትዮጵያ ሩቅ ስለ ሆነ በየጊዜው እየመጡ ባንድነት ለመምከር የማይቻላቸው ቢሆን እንኳ ስማቸው በማኅበራችን መዝገብ ውሥጥ ገብቶ እንዲጻፍ ይገባቸዋል ብለው የክብር ማኅበርተኛ አደረጓቸው።ይህንም የማዕርግ ስም ለማግኘትና ማኅበርተኛ ለመሆን እንዲገባቸው ለማስረዳት የተጻፈውን የምስክር ወረቀት አዲስ አበባ ያሉት የጀርመን ሚኒስትር ክቡር ዶክተር ፕሩፈር ለብላቴን ጌታ እንዲያስረክቡላቸው ለመኑ ።

የጀርመን ሚኒስትር ክቡር ዶክተር ፕሩፈርም በኢትዮጵያ እንደዚህ ትምህርትና እውቀት ያለው ሰው መገኘቱ ክብሩ ለአገሩም ጭምር ነው እንጂ ለብላቴን ጌታ ኅሩይ ብቻ አይደለም ብለው ይህንኑ የምስክሩን ወረቀት በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ፊት ለማስረከብ ቀጠሮ ጠይቀው ነበርና በግንቦት ፳ ቀን ወደ ማታ በ፲ ሰዓት እንዲገናኙ ፈቃድ ተቀብለው መጡ ።

ግርማዊ ንጉሥም በንጉሥነታቸው ወንበር ተቀምጠው ተቀበሏቸው ።

በዚያም ጊዜ በግርማዊ ንጉሥ አጠገብ የነበሩ መኳንንቶች የገንዘብ ሚኒስትር ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅና የባሌው ገዢ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ፡ የፈረስ ዘበኞች አለቃ ክቡር ፊታውራሪ እምሩ ነበሩ ።

ክቡር ብላቴን ጌታም የምስክር ወረቀቱን ለመቀበል በመካከል ቆመው ነበር ።

ክቡር ዶክተር ፕሩፈርም ስለ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ትምህርትና እውቀት በቃላቸው ብዙ ከተናገሩ በኋላ ባማርኛ ቋንቋ የተተረጐመው ተነበበ፡ ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ

የመንግሥትዎን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክቶር ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው በእውቀታቸው በጣም ረድተው ልዩ ልዩ የሆኑ ብዙ መጻሕፍትን ጽፈው ስለ አሳተሙ ይህ የእውቀታቸው ዜና ወደ ጀርመን አገር ስለ ተሰማ ምስጋናቸውን ለማሳየት ሲሉ ዶቼ ሞርጌንሌንዲሼ ጌዜልሻፍት የሚባለው በዓለም ሁሉ እጅግ የታወቀ ማኅበር የክብር ማኅበረተኛ ማድረጋቸውን የሚያስረዳ የላኩልኝ የምስክር ወረቀት (ዲፕሎም) ግርማዊ ንጉሥ ለብላቴን ጌታ እንዲሰጡ እለምንዎታለሁ ።

ለዚሁ ማኅበር የክብር ማኅበረተኛ የሆኑት ሊቃውንቶች ሰዎች ጥቂቶች ናቸው።ስማቸውና ማዕርጋቸው ከዚህ በታች እንደ ተጻፈው ነው ።

፩ኛ ፕሮፌሶር ኖልዴኬ ቀድሞ የእስትራስቡርግ ዩኒቬርሲቴ ፕሮፌሶርና የኦሪየንታሊስት ማኅበር ዋና ሊቅ ማኅበረተኛ ።

፪ኛ ኮማንዳቶር ኢግናዚዮ ጉይዲ ። የአማርኛ ፡ የግዕዝ ፡ የዓረብ ፡ ቋንቋ ሊቅ ፡ የሮማ ዩኒቬርሲቴ ፕሮፌሶርና የሮማን ሴና ማኅበረተኛ ።

፫ኛ እስኑክ ሁርግሮንጄ ። የሌይደን ዩኒቬርሲቴ ፕሮፌሶር የሆላንድ መንግሥት በቅኝ አገር ነገር አማካሪ የእስላሞች እውቀት ነገር መጀመሪያ መርማሪ ።

፬ ጆኮቢ ። የሳንስክሪት ቋንቋና የህንድ ቋንቋ ፕሮፌሶር በቦን ከተማ ።

፭ኛ ሰር ጆርጅ አብረሃም ግሪኤርሰን የህንድ ቋንቋና የእንግሊዝ ሊቅ ።

፮ኛ ሰር ኦሬል እሽታኝ የቡዲዝምና የህንድ እውቀት መርማሪ ።

፯ኛ ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ያማርኛና የግዕዝ ቋንቋ ሊቅ ።

ከዚህ በኋላ ክቡር ዶክተር ፕሩፈር የምስክሩን ወረቀት ለብላቴን ጌታ አስረከቡ ።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ለሚኒስትሩ ተናገሩ ።

አሁን በተናገሩት ቃል ስለሁለት ነገር በጣም ደስ ብሎኛል ። አንደኛው ነገር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ይህን ማዕርግና ስም ለመቀበል የሚገባው ስለ መሆኑ ነው ።

ሁለተኛው ነገር ወደ ፊት የሚነሡት የኢትዮጵያ ልጆች ለዚህ ማዕርግ ለመድረስ ሲሉ ለትምህርትና ለእውቀት እንዲተጉ የሚያነቃቃቸው ስለ መሆኑ ነው ።

እነዚህም የእውቀትና የጥበብ ሊቃውንት ማኅበር አስበው ለብላቴን ጌታ ኅሩይ ይህን ስለ ማድረጋቸው ምስጋናችንን እንዲያቀርቡልን ክቡርነትዎን እንለምናለን አሏቸው ።

ከዚህም በኋላ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ስለ ደስታቸው በግርማዊ ንጉሥ ፊት ቀርበው እጅ ነሥተው ወዲያው ለጀርመን ሚኒስትር ምስጋና አቀረቡ ። ሚኒስትሩና በዚያ ያሉት መኳንንትም እንኳን ደስ አለዎ የሚል ቃል እየተናገሩ ደስታቸውን ገለጡላቸው ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ይህን ትልቅ ማዕርግ ስለ አገኙ ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አለዎ እያለ መልካም ምኞቱን ያቀርባል

Remise officielle en présence de S. M· le NEGUS TAFARI

à Son Excellence le Belaten Gueta HÉRROUY, Directeur Général du Ministère des Affaires Etrangères d'un diplome envoyé d'Allemagne et qui lui a été conféré en témoignage de sa culture et de son savoir.

Toute personne qui par son travail sert son Gouvernement avec droiture et devouement ne manque pas de mériter de son vivant ou après sa mort une renommée immortelle.

Il y a 21 ans écoulés que S· E. Belaten Gueta HERROUY sert son Gouvernement. Pendant cette longue période il a fait preuve dans ses fonctions d'une droiture et d'une activité toutes particulières. De cette façon il n'a cessé de s'élever et a obtenu aujourd'hui le poste de Directeur Général du Ministère des Affaires Etrangères. Ces Hautes fonctions qu'il occupe actuellement et qui le mettent en contact permanent avec les plus Représentants les plus éminents des Puissances Etrangères, sont d'une importance toute particuliere.

De plus, il emploie tout le temps qu'il ne consacre pas au service de son Gouvernement et qui devraient être ses heures de loisir á la rédaction et á la publication d'ouvrages littéraires. Il en a déjà publié 21.

Pour cette raison, sa reputation s'est étendue aussi bien dans sa propre partie. l'Ethiopie qu'en Europe et dans d'autres pays Etrangèrs.

Dans chaque pays d'Europe les savants les plus éclairés forment des Assemblées où se font des conférences sur les sciences sociales, politiques et écnomiques et où s'élaborent des ouvrages divers.

Ces savants ayant traduit et étudié certaines œuvres publiées par S. E. le Belaten Gueta ont publié dans leurs propres livres des appréciations élogieuses sur lui.

La Socilété Allemande des Sciences Orientales bien que S. E. le Belaten Gueta ne puisse coopérer directement à l'activité de cette Société à cause de l'éloignement de sa patrie l'Ethiopie, l'a l'admis parmi ses Membres en lui conférant la titre de Membre Honoraire. Pour affirmer qu'il est digne de cet honnerur, la Société a demandé à S.E. le **Dr. PRUFFER.** Ministre d'Allemagne en Ethiopie de bien vouloir lui remettre son Diplome,

Son Excellence le Dr PRUFFER considèrant que l'existence en Ethiopie d'un homme au savoir et á la culture si vastes comme le Belaten Gueta HERROUY était un honneur non seulement pour lui-même mais aussi pour sa patrie, demanda une audience de S. M. le NEGUS TAFARI afin de lui remettre son Diplome en Sa présnce. L'audiénece fût fixée pour le 28 Mai 1929 à 4 Heures de l'après midi.

SA MAJESTE le NEGUS reçut S.E. Monsieur PRUFFER dans la salle du Trône.

A côté de S.M. le NEGUS se tenaient les grands Digntaires suivants:

S.E. le Dedjazmatch WOLDE TSADIK Ministre de l'Intèrieur.

S.E. le Dedjazmatch HAILE SELLASSIE Gouverneur du Balè.

S.E. le Fitaourari AMDE Gènéral de la Cavalerie.

S.E. Belaten Gueta HERROUY était parmi eux pour recevoir son Diplòme

Son Excellence le Dr. PRUFFER aprés avoir fait l'èloge du savoir et de la culture de S.E. Belaten Gueta HERROUY le discours suivant en amharique fut lu.

Majesté,

La Société allemande des Sciences Orientales, bien connue dans le monde entier, désireuse de témoigner son admiration, à Son Excellence Bellaten Guéta Herouy Wolde-Sellassé Directeur Général des Affaires Etrangères de Son Gouvernement, qui, depuis de longues années jusqu'à ce jour a bien servi son Gouvernement et sa Patrie par son savoir, en écrivant et en publiant un grand nombre de livres et dont la renommée est parvenue jusqu' en Allemagne, m'a envoyé un Diplòme lui conférent le titre de Membre Honoraire. Je prie respectueusement Votre Majesté de bien vouloir le lui remettre.

Le nombre des Membres Honoraires de cette Assemblée est restreint.

Voici la liste par ordre de ces savants célèbres:

Nöldeke ancien professeur à Strasburg, maitre juré des orientalistes.

Commendatore Ignazio Guidi le Savant le érudit dans es langues Ethiopienne, amarigna et arabe professeur àl'université de Rome, membre du Sénat Romain

Snouk Hurgronje professeur à l'université de Leyden, conseiller du Gouvernement Hollandais dans toutes les questions coloniales, le savant le plus versé dans les sciences islamiques

Jacobi professeur de la langue Sanskrite et de d'indologie à Bonn (Université)

Sir George Abraham Grierson indologue anglais.

Sir Aurel Stein explorâteur du Buddhisme et de l'Inde

Son Excellence Bellatén Guéta Herouy Directeur Général du Ministère des Affaires Etrangères d'Ethiopie. Savant en langue Amharique et Gueez.

Ensuite S. E. Monsieur le Dr Pruffer fit la remise du Diplòme à Son Excellence Belaten Gueta Herouy.

Sa Majeste Le Négus Tafari répondit en ses termes au Ministre:

Les paroles que vous venez de prononcer Nous font un double plaisir, en premier lieu parce que le Belaten Gueta Herouy mérite cet honneur et ce titre; en second lieu parce que cette distinction constituera un précieux encouragement pour la jeune génération Ethiopienne qui ne manquera pas de faire tous ses efforts en vue d'acquérir une plus grande culture.

Nous prions Votre Excellence de bien vouloir transmettre nos remerciement à la Société Allemande des sciences orientales d'avoir bien voulu conférer au Belaten Gueta cette flatteuse distinction.

Ensuite le Belaten Gueta Herouy ému de l'honneur dont il avait été l'objet s'approcha de Sa Majeste Le Negus et s'inclina Il remercia également son Excellece le Ministre d'Allemagne qui se joignit aux hauts Dignitaires présents pour lui adresser ses plus vives félicitations

Le BRHAN et SELAM saisit cette occasion de transmettre ses chaleureuses felicitations à son Excellence le Belaten Gueta Herouy pour la flatteuse distinction dont il a été l'objet

ፔር ዳኔይ ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

COGNAC S. & E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK- METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሁ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድሬስ በአደንና ርጀቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷት ፈቃድ የተቀበለ።

ΣΥΜΒΟΛΟΝ ΤΟΥ ΕΡΓΟΣΤΑΣΙΟΥ

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

1

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔሬቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜኪኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፫ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የዶማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
5me ANNÉE № 25

ሐሙስ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 6 JUIN 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣት ለፊስግ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ መታመንና በትምህርትና በዕውቀት ወደ ትልቅ መዓርግ ስለ መድረስ ።

በጥቂት ነገር የታመነ ሰው ከብዙ መዓርግ ይደርሳል ። በሹመት ላይም ሹመት ይጨመርለታል ። በጥቂት ነገር ያልታመነ ሰው ግን ያው ያለው ጥቂቱ ሹመት፣ ወይም ገንዘብ ከርሱ ይወሰድና ለዚያ ብዙ ላለው ሰው ይሰጥበታል። ማቴ ፳፭ ፳፫-፴።

እንደዚሁም በኢትዮጵያ ካሉት ከታመኑት ሰዎች መካከል አንደኛው ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከትጋታቸው የተነሣ በትርፍ ጊዜያታቸው ለሀገራቸው መንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም የሚሆኑ ብዙ የመጻሕፍት ድርሰት እያደረሱ ስለ አሳተሙ መጻሕፍቶቻቸው ወደ አውሮጳ ተሻግረው የክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይን ትምህርትና ዕውቀት መሰከሩላቸው ። በጀርመንም አገር ያሉ በዓለሙ ሁሉ የታወቁ የዕውቀትና የጥበብ ማኅበር ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይን ሰባተኛ የክብር ማኅበርተኛ ስለአደረጓቸው መጻሕፍቶቻቸው በፍሬያቸው የታወቁ ሆኑ ።

ለወደ ፊቱም ግርማዊ ንጉሥ እንደ ተናገሩት የኢትዮጵያ ልጆች ከዚህ መዓርግ እንድርሳለን በማለት ተግተው ተምረው ለኢትዮጵያ መንግሥት የታመኑ አገልጋዮች እንዲሆኑ እመኝላቸዋለሁ ።

ለክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይም እንኳን ደስ አለዎ ብዬ የሚከተሉትን ቅኔዎች አቀርብላቸዋለሁ ።

መወድስ

ኅሩይ ኅሩይ እንተ ኅረየከ
ኃይለ ሥላሴ ሰሎሞን ንጉሠ ጽዮን ኢትዮጵያ ።
እምንግሥተ ምድር ኵሎሙ እስመ ውእቱ ኬንያ ።
አንተ ሞገሳ ወኅሩይ ንዋያ ።
ወበጽድቅ ዕንቈ ባሕርያ፤
ዘኢትደሉ ትትወደይ ፤ ቅድመ ገጸ ባዕድ ሐራውያ።
ለጽዮንሂ ጥበብከ ኃይለ ሥላሴ ኅረያ ።
ማኅደረ ከመ ትኩኖ ጽርሐ መቅደሱ እስከ ረሰያ ።
እምነ ጠባባት አድባር እስመ ይሜኒ ላህያ ።
ወበስነ መልክዕ ኪነ ጥበብ አልቦ ዘይትሜረያ።

ሥላሴ ቅኔ

ኅሩይ ዘኅረየከ፤ አእምሮ ሊቃውንት ኃይለ ሥላሴ፤
ብርሃነ ሰላም ፈጠረ አቅዲሙ ከመ ኢያዕቅፎ ጽልመት።
አመ በስድስቱ ዕለታት ጠበብት።
ለኵሉ ዓለም ፈጠሮ ወለቀዳሚት ሰንበት።
ዕለተ ኅርየትከ ሳብዒት።
ቀደሳ ወአከበራ እምዕለታት ።
ወዓልዓላ እምኵሉ ፍጥረት ።

አለቃ ዳንኤል አ ደስታ

መወድስ

ደግሞ የትምህርትና የእውቀት ፍቅር ያደረባቸው አለቃ መርሻ ይህንን ለብላቴን ጌታ ኅሩይ የተደረገውን ታላቅ ክብር በሰሙ ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቅኔ አበርክተው አቀረቡ ።

ይቀድም ነቅዐ እምነ ውኂዝ፤
ወኊልቈ አሐዱ ይቀድም እምነ ደኅራይ ሳብእ።
እስመ ሳብዓይ ንባቡ ለጥበበ ጀርመን ምሉእ።
እምጣነሰ ሐዋርያሁ አነ በኢድልወትየ ለኅሩይ እግዚእ።
እቤ እምቅድመ ሰብዕ ።
ነቅዐ ጥበባት ኅሩይ ሀ ዘውኂዛት ምስትጉቡእ ።

ቅማጽሐፍ ኢዮብሞያ ወዘልበ ኅሩይ አቀንስ።
እምነ ቀዳማይ ልደት እስከ ደኃራይ ርስዕ።
እስመ በ እዝነ ኢአምሮ ወበ ዓይነ ሰሚዕ።

የ፻፷፱ ገጽ ተከታይ ።

በየአገሩ ክፍል መዘጋጃ ቤትም (ኮሙኒ) ሞኖፖል ይሁን እንዲያው ኤሌክትሪክ፥ ትራም፥ የሚጠጣ ጥሩ ውኃ፥የመድኃኒት ቤት ፥ እሱንም የሚመስሉ ሁሉ በእጃቸው ናቸው ብለናል። ግን እኒህ የፖሊቲክ ሰዎች መንግሥትና ሕዝብ የሚባሉ ፥ የሚጠቅምና የማይጠቅም (ትርፍና ጉዳት) አለበት ። የሚጠቅም መንግሥት የታመነ የማይከስርና የሥርዓት መጀመርያ ጠባቂ ዋና ዋስ ነውና ፥ የሚከስር ሰው የለም ። ሕዝብም አይታለልምና ዝቅ ባለ ዋጋ ይገዛል ። ከዚህ በላይም መንግሥትና ሕዝብ ንግድ አግኝተው ያተረፉ እንደሆነ ወደ መንግሥት (ቴዞሮ) ግምጃቤትና ወደ ሕዝብ መዘጋጃ ቤት ነውና የሚገባ...ገቢው በዝቶ መንግሥትና መዘጋጃ ቤት ሀብታሞች ሲሆኑ ለሕዝብ ግብር ይቀልለታል ።

የማይጠቅም ያልነው ደግሞ በኤኮኖሚያ ፖሊቲክ ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ስለ በለጠና ስለ በዛ ነው። ማለት የፖሊቲክ ሰዎች (መንግሥትና መዘጋጃ ቤት) የኤኮኖሚያ ነገር ሊሠሩ ቢፈልጉ ምንም ችሎት የላቸውምና እንደ አንድ ሰው ፕሬብቶና ሶቺታ አይከናወንላቸውም ። ስለምን በማናቸውም አገር ቢሆን ከመንግሥት ሠራተኛ ይልቅ ፕሬባቶ የሚባል በራሱና ለራሱ የሚሠራ ሰው ነውና የሚበልጥ የሚያፈራ ። የመንግሥት ሠራተኛ ግን ለደመወዙና ለክብረቱ ሲል ትንሽ ትንሽ ተለግሞ መሥራት በተቀር አይተጋም።ለራሱ የሚሠራ ሰው ግን ያልፍልኛል ሲል ፥ ያለፈለት ደግሞ ጌታ እሆናለሁ ሲል፡ሌትና ቀን በብዙ ትጋት ይሠራልና ብዙ ያፈራል።ከዚህ ሁሉ የበለጠ ጉዳት ደግሞ የኢምፕሬንዲቶሬ ማጣት ነው ። ስለምን እየደጋገምን በፊት እንደመለከትነው የመንግሥት ሹም ምን ያህል ጠንክሮ አይሠራም ። ለሠራተኞቹም እንደሚገባቸው መጠን አይጠበበቅም ። ኢምፕሬንዲቶሬ ግን (ዋነኛ ገንዘብ መሬት ሠራተኛ የሚያገጣጥም ሰው) ሌት ሲያስብ ቀን ሲሠራና ሲጠባበቅ በጥንክሬ ሲያሠራ የኢንዱስትሪ ፍሬውን መልክምና የተከናወነ እንዲሆንለት ሲጥር ሲግር ፥ ዕድሜውን ያሳልፋል። ስለዚህ የማናቸውም አገር ታሪክ ብንመለከትና በአሁኑ ዘመናችንም ብንመረምር በመንግሥት እጅ የሆነ ኢንዱስትሪ ይሁን ንግድ የሠለጠነ የለም።በዚሁ ምክንያት የተነሣ የአሁኑ መንግሥት አዲስ ሥራ መያዙ ይቅርና የቀደመውን እየለቀቀ (ማለት ፖስታና ቴሌግራፍ ብርና ተሙን በተቀር) ለሶቺታ ማኅበር ሰጥቶዋቸዋል፤ ይሰጣቸዋልም። ስለነዚሁ ያመለከትናቸው ሶስት ነገሮችና ስለ ነፍጥና መሣርያም ሁሉ ምሽግም ጭምር በመንግሥት እጅ የሚሻሉት ስለምን እንደሆኑ በቦታቸውና በጊዜያቸው እንናገራቸዋለን ።

፫)ታናሽና ታላቅ ኢምፕሬዝ ።

ኢምፕሬዝ ከትንሽ የሸቀጥ ቤት ጀምሮ በጣም ትልቅ እስከ ሆነ ትሬስት እስከሚባል (የመንግሥታት ንግድ)ይደርሳሉ። ምሳሌ የአሜሪካ ስታንደር ኦይልና ሮያል ዱች የሚባሉ የጋዝ ኢንዱስትሪ ፥ የዓለምን ሁሉ ሞኖፖል የያዙ ፥ ከዓለም ከ ጋዝ ሁሉ ሶስት ሩብ የሚያፈሩ ማኅበር ናቸው ።

ስለዚህ ኢምፕሬዝ በታናሽና ታላቅ ሲከፋፈሉና ፥ እርስ በእርሳቸው ሲቀጋገሉ ይኖራሉ ። ታልቂቱ ኢምፕሬዝ ከታናሺቱ ይልቅ የምትጠቅምበት ነገር አላት። ፩ኛ፡ ብዙ የምታፈራ ስለ ሆነች፡ ለጉዳይ የምታጠፋውን ገንዘብ፡ላፈራችው ሁሉ የምታካፍለው ስለ ሆነች፡የፍሬዋን ዋጋ ዝቅ ታደርገዋለች ። ማለት ዋጋው ርካሽ ከሆነ ገርው ወደ እስዋ ይሄዳል ማለት ነው። ፪ኛ፡የተከፋፈለው ሥራ በተሻለ ሊከፋፈል ይችላል።፫ኛ፡በደግ የርካሽ ገበያ የፍጥረት ሀብትና (መሬት ወይም ፍጥረት) ካፒታሌ (ገንዘብ)ሊገኙ ይችላሉ። ስለምን በብዙ ይወስዳልና እምነትም ይገኛል።ይታመናልም።፬ኛ፡ የበለጡና የተሻሉ ታላላቆች ማኪናዎች አሉትና የተከናወነ ደግ ፍሬ ይሠራል።፭ኛ፡ለማፍራት የሚያጠፋውን ገንዘብ ያህል(ስፔዜ)በጣም ሊያተርፍ ይችላል።ማለት ለሠራተኞቹና ለአለቃው፡ለመጋርያውና መኪናው ባጠፋው ገንዘብ ልክ ፕሮፓርሲዮኔ ሁነው አያድጉም።በተሰጠው መኪናና መሬት ትንሽ ቢያፈራ ያጠፋው ገንዘብ ያው ብዙ ነውና ጉዳት ይሆነዋል ። ለምሳሌ በአንድ ቀን ፴ሺ ኪሎ ሐር የሚያፈራ ኢንዱስትሪ፡ ፲ሺ ሠራተኞች ቢኖሩት፡ሌላው በቀን ፷ሺ ኪሎ ሐር የሚያፈራ ኢንዱስትሪ ፥ ቤት ይሁን ሠራተኞች ዕጥፍ ማለት ፳ሺ ሠራተኞች አያስፈልጉትም። ቢበልጥ ቢበልጥ ከ፲ሺ በላይ ከሶስት እስከ አምስት ሺ ሠራተኞችን ይጨምር እንደሆነ ነው እንጂ ። እንዲሁም በሁሉ ነገር ብዛት ሲገዛ እንደዚሁ ነው ። እንዲህ ስላልን ግን ፥ ለታናሺቱ ኢምፕሬዝ ታላቂቱ ታንቃታለች። ማለት የሚታመን ነገር አይደለም ። እስዋም ብዙ ጥቅም አላትና ታናናሾቹ ኢምፕሬዞች ፥ ከዋነኛው (ኢምፕሬንዲቶሬ)የፍቅር ጥበቃቸውን ያገኛሉ ። የአንድነት ኑሮዋቸውንና ሥራቸውን ከጌትዩውና ከሠራተኞቹ ጋራ ስምምነትን ያስነሳሉ ። በፊት ታላላቆቹን ኢንደስትሪዎችን ሊያሸንፉ ፥ የሚበልጡ ሰዎች ፍላጋቸው ነበር ።ካርሎ ማርክስ የሚባል ፥ የታናናሾቹን ጥቅማቸውን ገልጦ ከስረዳ ወዲህ ግን በአሁኑ ጊዜ ምን ያህልም ልዩነት የሚያደርግላቸው ሰው የለም። በአንድ አገርና በአንድ ዘመን ታላላቆች መኪናዎችና ፥መኻከለኞች ፥ ታናናሾችም፥ እንደ ዓይነቱና እንደ ሥራው ያስፈልጋሉ ።

ሚካኤል ተሰማ ።

በሚከተለው ይታተማል ።

ስለ አቡን ነገር በኢትዮጵያ ።

ካያሌ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ስለ አቡን ነገር በኢትዮጵያ ሲያዝኑበትና ሲያስቡበት ይኖሩ ነበር።ግን ለሁሉ ጊዜ አለውና ገና አቡነማቴዎስ በሕይወት ሳሉ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ነገሩ ተቀሰቀሰ።በ ፯ ቁጥር ብርሃንና ሰላም በሁለተኛው ዓመት ጋዜጣ ለዲቁናና ለቅስና ወደ አዲስ አበባ ለመጡ ሕፃናት የደረሰባቸውን አደጋ ቢያመለከት ፥ ቀጥሎም ክቡር ነጋድራስ ደስታ በ፲፱ ቁጥር በዚሁ ዓመት ጋዜጣ በግልጽም መንገድ ለዲቁናና ለቅስና ወደ አዲስ አበባ ለሚመጡ ሕፃ-

ናት የደረሰባቸውን አደጋ አምርረው ቢጽፉት፣ ክቡር አቶ አ ቻትቁም የ፲፯ና የ፲፱ቍጥር ጋዜጣ አገናኝተው ጠቅሰው ነገሩ ቸውን በ፳፬ኛ ቍጥር ጋዜጣ ቢገልጹ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የሆነ ይተክዝ ይቈረቍር ጀመር ። ክቡር ባላምባራስ ክብረት ባንትይርጕም ይህንን ከዚህ በላይ የተነገረውን ጠቅሰው ሐሳባቸውን በምር አመለከቱ፥ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ደለለኝም በ፳፫ ቍጥር ጋዜጣ ይህ ከዚህ በላይ የተነገረውን ሁሉ መሠረት አድርገው ስለ እውነተኛ ጠባቂና ስለ ብንደኛ የሚለውን ለኢትዮጵያ ሊቃውንት ልብ የሚነካ ቃል ጻፉ።ይልቁንም የኢትዮጵያ ተማሪ ተብሎ ስሙ የተጠራ ኢትዮጵያዊ በ፳፯ቍጥር ጋዜጣ ከፍትሐ ነገሥት እየጠቀሰ በኢትዮጵያ ግብፃዊ እንጂ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ አይሾም የሚለውን የሥርዋጽ ቃል እየነቀፈ ኢትዮጵያዊ ጳጳስነት ሊሾም እንደሚገባው የሚያስረዳ ቃል ጠቅሶ ማስረጃ እየሰጠ፤ በኢትዮጵያ አውራጃ ኢትዮጵያውያን ኤጲስቆጶሳት እንዲሾሙ እንደሚያስፈልግ ለአቡኑ አመለከቱ።ከዚህ በኋላ የብርሃንና ሰላም ተማሪ የተባለ በ፴ቍጥር ጋዜጣ ብርቱ ብርቱ ቃል ጻፈና ነገሩ እየበረከተ ሔደ።በዚሁ መካከል ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ በብርቱ ታመው በኅዳር ፲፯ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ዓረፉ ።

አቡነ ማቴዎስ ከሞቱ በኋላ ግን በወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል እንደሚሉ ፤ አዳማጭ የነበረ ሁሉ አለሁ አለሁ ይል ጀመር።ብዙ ሊቃውንትም ሐሳባቸውን በብርሃንና ሰላም እየጻፉ ለሕዝባቸው ጉዳቱን አስታውቀው ጥቅሙን አመለከቱት ። የሚበቃ ያህል በብርሃንና ሰላም ከተነገረ በኋላ ፤ ነገሩ በቤተ መንግሥትና በቤተ ክህነት ምክር እስከሁን ድረስ ቈየ ።

አሁን እንደሚወራው ስለ ቤተ ክህነት ሹመት መዓርግ እንዲቀበሉ ብዙ ሊቃውንት ወደ ግብፅ አገር ተልከዋል። ብርሃንና ሰላምም እንደፈለገውና እንዳመለከተው እንዲሆንለትና ፍጻሜውን አይቶ ለወዳጆቹ ደስ የሚያሰኝ እርግጥና ወሬ እንዲያሰማቸው በሙሉ ተስፋ ይጠብቃል ።

የሆነም ቢሆን ስለ አቡን ነገር በኢትዮጵያ ሥርዓቱ እንዲታይስ ነገሩን የጀመረና ብዙ ሥራ የሠራ ብርሃንና ሰላም መሆኑ በአንባቢዎች ዘንድ የታወቀ ነው።የሚያስተውል አእምሮም አያጣውም።ይህንን ማለታችንም እውነቱን ለመግለጽ ነው።በዚህም ነገር የምንፈልገው ያገራችንን ጥቅም ነው እንጂ የራሳችንን ጥቅምና ውዳሴን የምንፈልግ አይደለንም ።

ከብቶቻችሁን እንዳይገድል በሽታን ግደሉ ።

ሻርቦ ባክቴሪዲያን የሚባለው የማሬያ በሽታ ከከብት ወደ ሰው እንዳይጋባ ለማድረግ የሚያስፈልግ ጥንቃቄ ።

ከወላሞ፥ ከጅማና ከሲዳሞ በሚመጣው ጓዝ ምክንያት ይህ በሽታ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ገብቷል። ይልቁንም ይኸው በሽታ ከሀያ ሁለት ቀን ጀምሮ በከተማ ውስጥ በሉ በቅሎና ፈረሶች ላይ የጸና ሁኗል ። በቅሎችን በያዛቸው ጊዜ ሙብል ይተዋሉ፥ ሙቀታቸውም ከ፵፩ እስከ ፵፪ ተኩል ይደርሳል ። በሽታው በውጭ ሲሆን እምቢያቸውን ወደውጭ ያሳብጠዋል።ከባቢ የሆነ እንደሆነ ግን በወደውስጥ ነው የሚያሳብጠው ። ደግሞ እንደዚህ ጉሮሮዋቸውን ያሳበጠ የደም ተቅማጥ ያስቀምጣቸዋል። ይኸው በሽታ ሲጠነክርባቸው በቅሎች ከ፳፬ ሰዓት የበለጠ ለመቀመጥ አይችሉም። ፈረሶች ግን ከሁለት እስከ አራት ቀን ድረስ ይችላሉ ። በሽታው በውስጥ በኩል ሲሆን እብጠቱ ለመታየት አይችልምና ምልክቱ ሁሉ አይገኝባቸውም።ለቀንድ ከብቶችም ቢሆን እንደዚሁ ነ ነውና ብርንዶ ሥጋ ከመብላት የተነሣ ወደ ሰው እንዳይተላለፍ ይህ በሽታ የጸና ነውና በቀንድ ከብቶች ሁሉ መኖሩን አስቀድሜ እያስረዳሁ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ አመለክታለሁ

መጀመሪ፡ከገበያና ከከተማውም ዙሪያ ቢሆን በቁመና ጤንነታቸው የሚያጠራጥረውን ከብቶች በጭራሽ አለመግዛት ነው።

ሁለተኛ፣ ከከተማ ዙሪያ ከብት አስመጥቶ ለማረድ የሚፈልግ ሰው በቁመና ጤንነቱ የሚያጠራጥር የሆነ እንደሆነ ለከብት ሐኪም ሳያስመረምር አለማረድ ያስፈልገዋል ።

ሶስተኛ ፤ ከታረደም በኋላ ቢሆን ጤንነቱ የሚያጠራጥር የሆነ እንደሆነ የታረደውን ከብት በቀጥታ ለከብት ሐኪም አሳይቶ ማስመርመር የሚያስፈልግ ነው ።

አራተኛ፣ የከብት ሐኪም የጤንነት ምርመራ ማኅተም ያልታተመበትን ሥጋ ከሉካንዳ በጭራሽ አትግዙ ። ይህንንም ማለቴ ብዙ ሰዎች ዘወትር ከብቶቻቸው ሲታመሙ አርደው ለሉካንደኞች በትንሽ ዋጋ ይሸጡላቸዋል ። ይልቁንም ዛሬ ከብት ውድ በመሆኑና ዋጋው በመብዛቱ የተነሣ ሉካንደኞቹ እንደዚህ ያለውን ከብት ለመግዛት አይመለሱም።ስለዚህ የሕመምተኛውን ከብት ሥጋ በመብላት የተነሣ በሽታው ወደ ሰው ይጋባል ። ወደ ሰው በተዛወረ ጊዜ በፍጹም የማይድን በሽታ ነውና በሕዝቡ መካከል ከመቶው ዘጠናው የሞት አደጋ የሚደርስባቸው ይሆናሉ ።

በቅሎና ፈረሶቻችሁ ግን በጸና እንኳን ቢታመሙ ሊያድናቸው የሚችል የክትባት መድኃኒት አለ።ስለዚህ እንደምታውቁት ሁሉ የበቅሎና የፈረስ ዋጋ በጣም የበዛ ነውና አደጋ ሳያገኛቸው ከአንድ ቀን በፊት ለከብት ሐኪም እያስታወቃችሁ ከብቶቻችሁን ብታሳክሙ ከከብቶቻችሁ ጉዳት የሚያድናችሁ ይሆናል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የርሻ ሚኒስቴር የከብት ሐኪም

ሚህራን ከይማኪያን

እሽቅድድም።

ግንቦት ፳፪ ቀን እሽቅድድም እንዲደረግ ታውቆ ሰንብቶ ነበርና በዚሁ ቀን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንቶቻቸውና በብዙ ሠራዊት ታጅበው ከጥዋቱ በሶስት ሰዓት ወደ ጃንሜዳ ደረሱ ። በዚሁም ጊዜ አምሮ በተሰናዳው ቦታ ተቀመጡና እሽቅድድሙ ተጀመረ ።

አንደኛ እሽቅድድም ኖቢስ ዋንጫ ።

የሚጻው ርዝመት ፰፻ ሜትር በዚሁ እሽቅድድም መጀመሪያ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆኖ ዋንጫና ፹ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ፤የኢጣሊያን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የሙሴ ክራ ፈረስ ሁኖ ፴ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ፤የሙሴ ዶ ሬፌይ ፈረስ ሆኖ ፲ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ እሽቅድድም የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዋንጫ

የሜዳው ርዝመት ሺ ፭፻ ሜትር በዚሁ እሽቅድድም መጀመሪያ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆኖ ዋንጫና ፶ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ፥የሙሴ ቴዎድሮስ ማርቲን ፈረስ ሁኖ ፴ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ፤የሙሴ ዶ ሬፌይ ፈረስ ሁኖ ፳ ብር ተቀበለ ።

ሶስተኛ እሽቅድድም የኢጣልያን ዋንጫና የአሜሪካን ምኒስትር የሙሴ ሳውቃር የሰጡት ትንሽ ዋንጫ ።

የሜዳው ርዝመት ሺ ፭፻ ሜትር፥ በዚሁ እሽቅድድም መጀመሪያ ቀዳሚ የማዳም ሻምብር ፈረስ ሁኖ ሁለት ዋንጫና ፵ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ፥ የሙሴ ክሮሊዩ ፈረስ ሁኖ ፴ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ የኢጣልያን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የሙሴ ክራ ፈረስ ሁኖ ፲ ብር ተቀበለ ።

አራተኛ እሽቅድድም የሙሴ ሐሪንግቶን ዋንጫ ።

የሜዳው ርዝመት፤ሺ ሁለት መቶ ሜትር በዚሁ እሽቅድድም የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሁኖ ዋንጫና ፵ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሁኖ ፳፭ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ የሙሴ ሬፌይ ፈረስ ሁኖ ፲፭ ብር ተቀበለ ።

አምስተኛ እሽቅድድም የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን፤ዋንጫ

የሜዳው ርዝመት ፪ሺ ሜትር፤ በዚሁ እሽቅድድም መጀመሪያ ቀዳሚ፥የማርኪስ ዶ ሴይ ሞምበያር ፈረስ ሁኖ ዋንጫና ፻ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የማዳም ዶ ሬፌይ ፈረስ ሁኖ ፶ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሁኖ ፴ ብር ተቀበለ ።

ስድስተኛ እሽቅድድም የልዑል ዱክ ዴዝ አብሩክ ዋንጫ።

የሜዳው ርዝመት ሺ ፰፻ሜትር፤በዚሁ እሽቅድድም መጀመሪያ ቀዳሚ የኢጣሊያን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የሙሴ ክራ ፈረስ ሁኖ ዋንጫና ፻ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሁኖ ፶ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሁኖ ፴ ብር ተቀበለ ።

ከዚህ በኋላ እሽቅድድሙ ተፈጽሞ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ባማረ አጀብ ሁነው ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ ።

Tentatives Bolcheviques par le Docteur Gabrilow Son Expulsion. (suite)

Traduction.

Camarade (Tovarysez) Gabrilow.

Nous avons reçu vos lettres ainsi que de l'argent dans deux enveloppes en somme totale de Lstg. 50.-,-

Nous avons fait tout. Nous vous informons que Nous avons mitrail. . . . système Allemand - On peut démonter . . . Nous nous obligeons de les transporter et livrer à port-said. les adresses et photographies de vos gens ~~nous~~ avons reçu alors nous leurs remettrons tout.-

En ce qui concerne de bombes à mains ainsi que celles-ci avec l'horloge (peut être machine infernale) ,d'après ce que vous avez écrit on peut les employer à n'importe quel moment . . . . il y a la possibilité de les transporter et livrer à port-said.-Il y aura nécessaire de dépenser Lstg. 500,-,-pour 50 pièces.-

L'organisation vous prie de remettre de l'argent sur les adresses que vous connaissez très bien (3 adresses).-

vous demandez de vous envoyer de gens; dans la prochaine session cette question sera résolue et le résultat nous vous remettrons par port-Said.-

Notre salutation de camarade

P.M.C B.O.

ባለፈው ቁጥር ስለ ዶክቶር ገብሪሎፍ ይተተማል የተባለው የደብዳቤ ግልባጭ ።

ትርጓሜ ።

ባልንጀር (ቶባሪስክዝ) ገብሪሎፍ ።

ደብዳቤዎችዎ ከገንዘቡ ጋራ በድምሩ አምሳ ጊኒ በሁለት እንቦልብ ውሥጥ፤ደረሰን ሁሉንም አዘጋጅተናል።የጀርመን ዓይነት መትረየስ እንዳለን እናስታውቅዎታለን ይህንም መትረየስ ለመፈታታት ይቻላል አሳጭነን ፖርት ሣይድ ላይ ለማስረከብ ግዴታ እንገባለን የሰዎችዎም ፎቶግራፍና አድራሻቸው ደርሶልናል ሁሉንም ለነርሱ እናስረክባቸዋለን እርስዎ እንደ ጻፉልን ደብዳቤ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን እንዲፈነዳ ለማድረግ የሚቻለውን በሰዓት ተሞልቶ በእጅ የሚወረወረውን ቦምብ እስከ ፖርት ሳይድ ድረስ ለማድረስና እዚያው ለማስረከብ ይቻላል ። ላምሳው ቦምብ ሶስት መቶ ጊኒ መክፈል ያስፈልጋል ። በሥርዓት ለሚያውቋቸው ለሶስቱ አድራሻዎች ገንዘብ እንዲሰጡ ማኅበራችን ይለምንዎታል ።

ሰው ላኩልኝ ብለው ስለ ጠየቁ ወደ ፊት በሚደረገው ጉባዔ ነገሩ ይቆረጣል ። ፍጻሜውንም በፖርት ሳይድ በኩል እናስታውቅዎታለን ።

የባልንጀራ ሰላምታችንን እናቀርባለን ።

ፐ መ ስ በ አ ።

ፔር ዳኔይ ።

አቮካት ።

የፍትሕ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማመልከቻ ።

ደክቶር ኤ ሚዬንቤርገር በዜሪች (ሱዊስ) መታከሚያ መድኃኒት ቤትና ኡኒበርሲቴ ወጌሻ ሐኪም የነበሩት በኢትዮጵያ መንግሥት በአዋላጅ ሕክምና ቤትና መድኃኒት ቤት ሹም የሆኑት፥ አሁንም የአዋላጅ ሕክምና ቤት እስኪከፈት ድረስ ለጊዜው በቤተሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ሆስፒታል ሹም ሆነው የተቀመጡት፥በቅዱስ ጊዮርጊስ መድኃኒት ቤት(በሙሴ ዛህን መድኃኒት ቤት) የምክር ጉባኤ ያደርጋሉ ። ጉባኤውም ከእሑድ በቀር ሁሉ ቀን ከ፰ ሰዓት እስከ አሥር ሰዓት እንደሚደረግ ያስታውቃሉ ።

-Avis-

Le docteur E. Meyenberger. ancien chef de clinique à la clinique chirugicale de la faculté de medecine de l'université de zürich (Suisse), engagé par e gouvernement éthiopien enqualité de chirurgien chef de la Clinique chirurgicale et de la Maternité actuellement médecin remplecent en chef à l'hopital Bethe - Saida en attendant l'ouverture de la Maternité a l'honneur de porter à la connaissance du public, qu'il donnera des consultations privées, à partir du 1 juin. Les consultations auront lieu tous les jours sauf le dimanche de 2 à 4 heures, dans l'immeuble contigu à la pharmacie St. Georges (pharmacie Mr. Zahn.)

የርሻና የንግድ ማስፋያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊረስ ሰዓት ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው ኦቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያከረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ ኦቶሞቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና (ጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መጣሪያዎችና በየይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በየይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷነት ፈቃድ የተቀበለ።

ΣΥΜΒΟΛΟΝ ΤΟΥ ΕΡΓΟΣΤΑΣΙΟΥ

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የለለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፭ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል። የልብ።የደረት። የጉበት። የኩላሊት። የዶማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት። የድራሌ ሽቱ በለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት። ባለወረቀት ባለምኒልክ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን።

ጥሩ ሱቅ ከሆን ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሂዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን፤አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድዬር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
5me ANNEE № 24

ሐሙስ ሰኔ ፮ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 13 JUIN 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊዎቹ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መውጫ ለፊደል በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በኢትዮጵያ አንድ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳሳትና አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ስለ መሾማቸው ።

የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ማቴዎስ ካረፉ ጀምሮ እስከ ዛሬ ጳጳስ ሳይመጣ የቈየበትን ምክንያት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ምንም እንኳ ለመኳንንቱና ለሊቃውንቱ ቢያስታውቁ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በአዋጅ ገልጠው ካለማስታወቃቸው የተነሣ ምክንያቱን ያላወቁ አንዳንድ ሰዎች እስከሁን ጳጳስ ባለመምጣቱ በነገሩ ይደነቁ ይሆናል ።

ደግሞ ከመኳንንቱና ከሊቃውንቱም ወገን ቢሆን ምክንያቱን ከሚያውቁት የማያውቁት ይበልጣሉና እስከሁን ጳጳስ ሳይመጣ የቆየበትንና አሁን እንዲመጣ ነገሩ የተቈረጠበትን ለመኳንንቱና ለሊቃውንቱ፥ ለሕዝቡና ለካህናቱም ገልጠን እናስረዳለን።

ኢትዮጵያ በክርስቶስ ብርሃን ሰላም ተሰብካ ክርስትናን ከተቀበለች አንድ ሺ፮፻ ዓመት ያህል ይሆናል ። በዚሁም ሁሉ ዘመን ከእስክንድርያ ጳጳስ እየተሾመ ሲመጣ ይኖራል እንጂ የኢትዮጵያ ሰው ጳጳስነት እንዳይሾም ይከለከል ነበር። ምክንያቱም አንድ ግብፃዊ የራሱን አሳብ በሠለስቱ ምእት ስም አድርጎ ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሚሙ ሊቀ ጳጳሳት እማእምራኒሆሙ ብሎ በፍትሐ ነገሥት አግብቶ ስለጻፈው ነበር።

ነገር ግን ሰሎሞን መክብብ በሚባለው መጽሐፉ ለሁሉ ጊዜ አለው ብሎ እንደተናገረ የኢትዮጵያ ልጆች በትምህርትና በእውቀት እያደጉ ስለሔዱ በዓለም የሚኖር ሰው መንፈሳዊ ትምህርት፥ ተምሮ ሃይማኖቱ የፀና ምግባሩ የቀና ከሆነ ጳጳስ ለመሆን አይከለከልም ፤ የኢትዮጵያ ሰው ብቻ ጳጳስ እንዳይሆን መከልከሉ በሰው ነው እያሉ ከመጻሕፍት እየጠቀሱ ማስረጃ እየጻፉ በብርሃንና ሰላም በአእምሮም ጋዜጣ አሳባቸውን ይገልጡ ጀመር ። የውጭ አገር ጋዜጦችም ይህንንም እየተከተሉ ይጽፉ ጀመር ።

ይኸውም አሳብ የተነሣውና በጋዜጣ መውጣት የጀመረው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት አቡነ ማቴዎስ ገና በሕይወት ሳሉ ከ፲፱፻፲፰ ዓመት ጀምሮ ነበር ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ልጆች አሳብ የሚፈጸምበት ጊዜው ደርስዋልና አቡነ ማቴዎስ ምንም ለመቃወም አልሆነላቸውም። ለመቃወምም አስበው በነበረ የኢትዮጵያ ልጆች ትልቅ ሁከት ሳያነሡባቸው አይቀሩም ነበር ።

ዳሩ ግን ከኢትዮጵያ መምህራን ጳጳስ እንዲሾምልን ይገባል ብለው ከሚከራከሩት ከነዚሁ ከኢትዮጵያ ልጆች ወገን አንድ ልጅ ብቻ ፍሬ ነገሩን ትቶ የማይገባ የስድብ ቃል ስለ ተናገረ አቡነ ማቴዎስ ለግርማዊ ንጉሥ አቤቱታቸውን አቅርበው ታሥሮ ነበር። ከንድ ወር በኋላ ግን ምሕረት አድርገውለት ተፈታ ።

ስለ ዚሁም ነገር የተጻፈውን ጋዜጣ የሚያነቡ የኢትዮጵያ መኳንንቱና ሠራዊቱ፥ ሊቃውንቱና ካህናቱ የኢትዮጵያ ሰው ጳጳስ ለመሆን የሚገባው መሆኑን ስለ ተረዱት ከሀገራችን ከኢትዮጵያ መምህራን እየተመረጡ አንድ ሊቀ ጳጳሳትና ለያውራጃው የሚሆኑ ብዙ ጳጳሳት ይሾሙልን የሚሉት እየበዙ ሔዱ ።

ይህም የመኳንንቱና የሕዝቡ አሳብ በቃልም በጋዜጣም ስለተወራ ነገሩ ወደ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ደረሰ፤ ግርማዊ ንጉሥም የኢትዮጵያን ስፋት የሕዝቡን ብዛት ተመልክተው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመምህራንዋ መካከል ጳጳሳትን ብታገኝ ለኢትዮጵያ ትልቅ ክብር መሆኑን ያውቃሉና ይህንን ነገር አስቀድመው ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፥ ቀጥሎም ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ፥ ለሊቃውንቱም አስረድተው ነበር ። በዚህም ነገር የግርማዊት ንግሥት አሳብ ከግርማዊ ንጉሥ አሳብ ጋራ አንድ

ንቱም አንድልብ ሆነው በምክሩ ስለተስማሙ የምክሩ ቃል ወደ እስክንድርያ ፓትሪያርክ ወደ አቡነ ቄርሎስ ተልኮ ነበር። አቡነ ቄርሎስ ግን ይህ ነገር ትልቅ ስለ ሆነ የግብጽ ማኅበር ሁሉ ተሰብስበው የሚጨርሱት ነው እንጂ እኔ ብቻ የምጨርሰው ነገር አይደለም የሚል ምላሽ ሰጥተው ሳሉ ነገሩ ሳይጨረስ እርሳቸው ዓረፉ ።

ከዚያም በኋላ በእስክንድርያ በመንበረ ማርቆስ የሚቀመጠው ሊቀ ጳጳሳት እስቲመረጥ አንድ ዓመት ከምስት ወር ስለ ቈየ የኢትዮጵያም ጳጳስ ነገር እንዲቈይ የግድ ሆነ ።

ከዚህም በኋላ በእስክንድርያ የፓትርያርኩ ወኪል ሆነው የሚኖሩት ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ ለፓትሪያርክነት ስለ ተመረጡ ብታሕሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ተሾመው በመንበረ ማርቆስ መቀመጣቸው በቴሌግራም ተሰምቶ ነበርና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ከዚህ ቀድሞ ያሰቡትን ከግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ከመሳፍንቱ ከመኳንንቱና ከሊቃውንቱ ጋራ የተስማሙበትን ከኢትዮጵያ መምህራን መከከል ተመርጠው ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳት ሆነው እንዲሾሙ ለማድረግና ነገሩን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ወደ ፓትርያርክ ዮሐንስ በቴሌግራም መላላክ ጀመሩ ።

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አሳብ ከግብጽ አንድ ሊቀ ጳጳስ ተሹሞ መጥቶ አዲስ አበባ ሲደርስ ከኢትዮጵያ መምህራን እየመረጠ ጳጳሳት እያደረገ እንዲሾም ነበር ። የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ ግን ለጊዜው ይህን አሳብ አልተቀበሉም ነበርና ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቴሌግራም አላኩ ።

ግርማዊነትዎ የላከውን መልክት ሰማን ።

በግብጽ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መከከል ያለውን መልካም ወዳጅነት አጠንክሮ ለማኖር ስለገጡልን ልባችን በደስታ ተነካ። ለግርማዊነትዎና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለሕዝብዋም ተድላ እንዲሆን ስለ ራሳችን ስለ ግብጽም ሕዝብ ሁነን የምንመኘውን መልካም ምኞታችንን በደስታ እናቀርባለን ።

ለግርማዊነትዎ በማንኛውም ነገር የሚስማማ መልካም ብሕሪ ያለው አንድ ጳጳስ ለመሾም ከዚህ ቀድሞ መፍቀዳችንን እንደገና እናረጋግጣለን። የቤተ ክርስቲያኑ ሕግ የሚፈቅድልን ቢሆን ኖሮ ይህነኑ ሊቀ ጳጳስ ጳጳሳትን ለመሾም እንዲችል አድርገን ብንሾመው ደስ ይለን ነበር ። ይህ በተለይ የቤተ ክርስቲያን ሕግ የሚያውክ ስለሆነ ብፁዕ ፓትሪያርክ ሱሬል በዮሴፍ ፓሻ ሾሊማን በኩል ያስታወቁትን አሳብ እናረጋግጣለን ። ጳጳስ ብለን እንድንሾማቸው ብፁዕ እጨጌን ግርማዊነትዎ ይላክልን ። ከሊቀ ጳጳሱም ጋራ አንድነት ሁነው በኢትዮጵያ በየክፍሉ ላለው ሥራ የሚረዱ ሁለት የግብጽ ጳጳሶች እንሾማለን።በኢትዮጵያ ልጆችና በናታቸው በግብጽ ቤተ ክርስቲያን መካከል እስካሁን ሳያልቅ የቈየውን ነገር ሁሉ ለሁለቱም ወገን ጥቅም የሚሆንና ለግርማዊነትዎም ደስ በሚያሰኝ መንገድ ለመጨረስ ቁርጥ የሆነ አሳባችን መሆኑን እናረጋግጣለን። ሁለቱን አገሮች የሚያስተሳስረው የፍቅር ማሠሪያ እየጠበቀ እንድሔድ እንደ ግርማዊነትዎ እየተመኘን ምላሹን እንጠብቃለን ሐዋርያዊ ቡራኬያችንን ለግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊነትዎ ለቤተ ዘመዶቻችሁም ለቤተ ክርስቲያን ልጆቻችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንሰጣለን ።

ዮሐንስ ፓትሪያርክ ።

ግርማዊ ንጉሥም የፓትርያርኩን የአቡነ ዮሐንስን ቴሌግራም ከተመለከቱ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ምላሽ በቴሌግራም አላኩ ።

ለብፁዕ ወለቅዱስ ፓትርያርክ ዮሐንስ ቴሌግራምዎ ደረሰን ። መልካም ባሕሪ ያለው አንድ ሊቀ ጳጳስ ለመሾም እርሱንም የሚረዱት ሁለት የግብጽ ጳጳሳትና ከእኛም ለአንዱ ለእጨጌ ጳጳስነት ለመስጠት መፍቀድዎን የሚያስታውቅ ቃል በቴሌግራምዎ ላይ አየን ። ይህ አሳብ ግን እኛ እንዳሰብነው የትምህርት ችግራችንን የሚያቃልልን አልሆነም። የሚጨመሩትንም ሁለቱ ግብጾች መቸም ቋንቋችንን አያውቁትምና ፈቃድዎ ሆኖልን ዛሬ ለጊዜው በቋንቋችን ከሚያስተሩ ሊቃውንት መርጠን የሚያስፈልገንን ያህል ከመልክተኞቻችን ጋራ ሰደንልዎ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ሥርዓት የሚከለክል ሕግ ከተገኘ እኛም ያስፈልገናል ያልንበትን ምክንያት አስታውቀው እርስዎም የቤተ ክርስቲያኑ ሕግ የሚከለክልበትን ሥርዓት አስረድተዋቸው የሚመጣው ሊቀ ጳጳስ ከዚህ ለመሾም የማይቻል ነው ከተባለ እነዚህ መርጠን የምንሰድልዎ ሰዎች ከዚያው ተሹመው ከሊቀ ጳጳሱ ጋራ አብረው ይምጡልን ።

ይህንንም ፈቃድዎን አለመጋፋታችን እስከ አሁን ጸንቶ የኖረው ያባትና የልጅነት መተማመን እንዳይጐድል ብለን ነው እንጂ የእኛም የሕዝባችን ፈቃድ ግን ያው ቀድሞ እንደላክንብዎ ቃል መሆኑን እንዲአውቁልን እንለምንዎታለን ።

ንጉሥ ተፈሪ ።

ይህም ነገር በቴሌግራም መላላክ የማይፈጸም ስለሆነ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ነገሩ በቶሎ እንዲፈጸም አስበው የትምህርት ሚኒስቴር ዲሬክተር አቶ ማህሉ ፀዳሉ ወደ ምድረ ግብጽ ወርዶ ከፓትርያርኩ ከአቡነ ዮሐንስ ጋራ በወዳጅነት ተነጋግሮ ምላሹን እንዲያስታውቅ ትእዛዝ አደረጉ ።

አቶ ማህሉ ፀዳሉም ወደ ምድረ ግብጽ በደረሰ ጊዜ ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የተላከውን ሁሉ ለፓትርያርኩ ለአቡነ ዮሐንስ ካስታወቀ በኋላ አቡነ ዮሐንስ የግብጽን አርቶዶክስ ማኅበር ሁሉ ሰብስበውና መክረው የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን አሳብ ወደውና መልካም ነው ብለው ከተቀበሉ በኋላ ከዚህ ቀጥሎያለውን ቃል ቴሌግራም አላኩ ።

ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ።

ሐዋርያዊ ቡራኬያችን ለግርማዊነትዎ ይሁን ።

ከኢትዮጵያ መምህራን አምስት ሰዎች ተመርጠው ጳጳሳት ሆነው አምስት የኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጳሳት ሹመት እንዲሾሙ ፈቅደናልና አምስት መነኩሳት እንዲልኩልን እንለምናለን ።

ፓትርያርክ ዮሐንስ ።

ግርማዊ ንጉሥም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በቴሌግራም መለሱ ።

በማህሌ ፀዳሉ በኩል ላስታወቅንዎ ጉዳይ ከቡራኬዎ ጋራ በላኩልን ምላሽ ደስ ብሎናል መነከሳቱንም እንደሚያስፈልጋ አድርገን እንልካለን እግዚአብሔር ቅዱስነትዎን ይጠብቅ ።

ንጉሥ ተፈሪ።

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪና በፓትርያርኩ በአቡነ ዮሐንስ መከከል በተደረገው መላላክ ከኢትዮጵያ ሊቃውንት አምስት መምህራን ተመርጠው ጳጳስነት እንዲሾሙ ነገሩ ከተቈረጠ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪየነገሩን ጨቈረጥ ለመስፍንቱና ለመኳንንቱ ለሊቃውንቱና ለካህናቱ አስታውቀው ጳጳሳት ለመሆን የሚገባቸው ትምህርትና ምግባር መዐርግም ያላቸው መምህራን እንዲመረጡ ትእዛዝ አደረጉ ።

ከዚህም በኋላ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፤ መልአከ ገነት ወልደ ሐና ፤ መምህር ደስታ ፤ አለቃ ወልደ ተክሌ ፤ መምህር ኃይለ ሚካኤል ፤ አለቃ ወልደ ትንሣኤ ፤ ሁነው እንደ ትእዛዙ ቃል ጳጳስነት የሚገባቸን መምህራን ስም ስማቸውን አስታወቁ ።

ነገር ግን ጳጳስነት የሚሾሙት አምስት ብቻ መሆናቸውን አላወቁም ነበርና ዓሥር አድርገው ስለ መረጡ ከነዚሁ መከከል አምስት ብቻ እንዲመረጡ ታዘዘ ። አመራረጡ ግን በዕጣ እንዲሆን ምክሩ ተቈርጦ ነበርና በዕጣው ላይ ሰባት ቀን ሙሉ በቤተ ክርስቲያን ጸሎት እየተጸለየበትና ቅዳሴ እየተቀደሰበት ቈይቶ ላምስቱ መምህራን ዕጣ ወጣላቸው ። ስማቸውም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

መምህር ደስታ ፤
መምህር ኃይለ ማርያም ፤
መምህር ወልደ ኪዳን ፤
መምህር ኃይለ ሚካኤል፤ ናቸው። አምስተኛው ግን ወደ ግብጽ አልወረዱምና ስማቸውን ወደ ፊት እናስታውቃለን።

ከዚህም በኋላ ከመምህራኑ ጋራ ወደ ምድረ ግብጽ ወርደው ሊቀ ጳጳሳቱንና ጳጳሳቱን አሹመው በክብር ይዘው ወደ አዲስ አበባ የሚመለሱ የገንዘብ ምኒስትር ክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ታዘው የግርማዊት ንግሥትና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ደብዳቤ ይዘው በግንቦት ፱ ቀን ከአዲስ አበባ በባቡር ተሳፍረው ወደ ጂቡቲ ወረዱ ።

ከጅቡቲም በግንቦት ፲ ቀን በመርከብ ተሳፍረው ወደ ካይሮ ሔዱ ። በካይሮም ፲፫ ቀን ያህል ከቈዩ በኋላ በግንቦት ፳፭ ቀን እሑድ ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ለመሆን የተመረጡት አንደ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳሳት ተሾመው ፤ ከኢትዮጵያም የተመረጡት አራቱ መምህራን ጳጳሳት ተብለው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ተሾሙ ፤ ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቴሌግራም አሳለፉ ።

ዛሬ በግንቦት ፳፭ ቀን አባ ቄርሎስን ሊቀ ጳጳሳት አድርገን አራቱን የኢትዮጵያ መምህራን ጳጳሳት አድርገን ስማቸውንም ጴጥሮስ፡ አብርሃም፡ይስሐቅ፡ሚካኤል፤ብለን ቀብተን ሾመናቸዋል

ፓትሪአርክ ዮሐንስ ።

አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ወኖብያ ወኢትዮጵያ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በቴሌግራም አሳለፉ ።

ለብፁዕ ወለቅዱስ ፓትሪያርክ ዮሐንስ የሊቀ ጳጳሱንና የጳጳሳቱን መሾም ስላስታወቁን እናመሰግንዎታለን። ይኸውም ነገር በቅዱስነትዎ ዘመን መፈጸሙ የኢትጵያና የግብጽ ቤተ ክርስቲያን አንድነት እያፀና የሚሔድ መሆኑን ያስረዳናል ።

እግዚአብሔር ፓትሪያርክነትዎን ይባርክ ።

ከዚህም በላይ እንዳስረዳነው ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ከእስክንድርያ ፓትሪያርክ ከአቡነ ዮሐንስ ጋራ ተላልከው በኢትዮጵያና በግብጽ ቤተ ክርስቲያን መከከል ፀንቶ የቈየው አንድነት በወዳጅነት እንዲጨረስና የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን ክብር እንድታገኝ በማድረጋቸው አገሩን ኢትዮጵያን የሚወድ ሰው ሁሉ ሊያመሰግናቸው ይገባቸዋል ።

ደግሞ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን ክቡር ማግኘቷ የሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ደስታ ነው እንጂ

የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ብቻ አለመሆኑን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሁሉ እናስታውቃለን ።

የእስክንድርያም ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ የግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱንና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን አሳብ ወደውና ተቀብለው በዘመናቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን ክብር እንድታገኝ ስለፈቀዱ የሃይማኖት ልጆቻቸው የሆኑ የኢትዮጵያ ሰዎች ሁሉ ሊያመሰግንዋቸው ይገባል ።

ለዶክቶር ገብሬሉፍ የመጣለት ደብዳቤ ።



Тов. Габриель

Получили мы ваши письма и деньги
в двух конвертах всего 50 фунт.
Узнали все. Сообщаем вам что мы
[illegible] мест. [illegible]
Можно разобрать на [illegible]. [illegible]
[illegible] и [illegible] их в Порт Саид.
Через ваших людей и фотографичес-
ких мы получили, так что мы все [illegible]
здоровы. Относительно русских [illegible]
[illegible] и [illegible] вы писали.. [illegible]
[illegible] воспитывать.. можно
доставить их в Порт Саид и дальше. Из
50 [illegible] [illegible] [illegible] [illegible]
Организацию [illegible] все [illegible]
деньги на Те 1 адреса, которые вы
знаете (3 адреса). Вы просите чтоб
приехали люди, будущие организа-
ционным образом решить этот
вопрос и сообщим вам через Порт-
Саидских.

Шлем вам товар. привет
Г. Ц. С. Б. О.

የከብት ሕክምና ሥራ ማመልከቻ ።

በአዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ ስለሚበላው ሥጋ የመቈጣጠር ደምብ እንዲደረግለት ካስታወቅሁ ሰባት ስምንት ወር ይሆናል ። አሁንም ወደ ፊት በቅርብ ጊዜ ሥጋ መታጣቱ አይቀርምና እስከ ዛሬ ድረስ የተክከለ ደምብ ባለመቆሙ በነዚህ ባለፉት ጊዜያቱ ብዙ ነገር አገኘን ።

የከብትን ገበያ አኳኋን ብንመለከት ሥጋ ከመታጣቱ የተነሣና ውድ በመሆኑ ጥገት ላሞች ያሏቸው ሰዎች ሁሉ ለሉካንዳ መብል እንዲታረዱ ለመሸጥ የሚያደፋፍራቸው ሆኑአልና ምን ያለ ጉዳት ነው ? ለከብት ማርባትስ ምን ያለ አደጋ ይሆን? ።

የርሻ ሚኒስቴር የከብት ሕክምና ሥራ ደምቡ የጠነከረ ስለሆነና ሁል ጊዜ የምከለክል ስለሆነ ጥገት ላሞች መጥተው ለሉካንዳ መብል በቄራ ውሥጥ ሲታረዱ ለማግኘት አልተቻለኝም ። ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ ሉካንዶቹ ለምግብ የሚያርዱትን ከብት ሁሉ ከቄራ ውሥጥ እያገቡ እንዲያርዱ የሚያስገድድ ሕግ ስላልወጣ በንግድ ምክንያት ትርፍ ለማግኘት ሲሉ እነዚህን ጥገቶች የሆኑትን ላሞች እየደበቁ በየስፍራቸው ሳያርዱ ይቀሩ አይመስለኝም ።

ስለዚህ ቤት ሲቃጠል በመጀመሪያ ካላጠፉት ጣራውን ሁሉ ከያዘው አይጠፋምና ምንም ደምብ ቢያደርጉለት የማይሆን ነው

ለቅዱስ ሚካኤል በዓል የታረዱት ከብቶች በጣም የበዙ ስለሆኑ የማይወሰኑ ናቸው ። እንደ ዛሬው የከብት ገበያ አኳኋንና ለሉካንዳ ምግብ የሚታረዱ ከብቶች ውድ ሁነው የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ የሚበዛው ባሥጋ ማጣት ተቸግሮአል ። ደግሞ ለግብር እየተባለ በትልልቅ ሰዎች ቤት የሚታረዱ ከብቶች ብዙ ገንዘብ ይፈጃሉ ።

ከብት ከመወደዱ የተነሣ ከቄራ ብዙ ሰዎች ባዶ እጃቸውን እንደተመለሱ ያየሁ እኔ ብቻ አይደለሁም ።

ብርንዶ ሥጋ በሚባለው በኢትዮጵያ ሕዝብና የጅ ሥራ በሚሠሩት ሕዝቦች መሐከል ትክክል ሁኖ ሥጋ ለማግኘት ፍለጋ የሚያስፈልግ ሊሆን ነው ። ከዛሬ ጀምሮ ለሥጋ መብል የተክከለ ደምብ ካልወጣለት እንደዚሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ፊት ከውጭ አገር ሥጋ ለማስመጣት የሚያስገድደው ይሆናል።

እስከዚህ ድረስ ስለ ሥጋ መብል አኳኋን ተናገርሁ፤ ደግሞ ለርሻና ለከብት ስለሚሆነው ዋና ነገር ከዚህ አስከትዬ እናገራለሁ ።

ከጥቂት ወር ጀምሮ የኢትዮጵያ ሰማይና መስክ ሁሉ በንብጣ ተሸፍንዋል።ይኸውም የባላገሩን ሰብልና ሣር ከበላ በኋላ በኢትዮጵያ ውሥጥ በሚስማማው ስፍራ እንቁላሉን ይፈለፍላል።ስለዚህ እንቁላሉን ከፈለፈለ በኋላ እንደዚህ ያጠፋ እንደሆነ ከዛሬው ይበልጥ አገሩ ምን ይሆናል ?።

ሕዝቡና ከብቱስ ምን ይመገባል?።ከዚህ ቀደም ልዩ ደምብና ሕጉም አለ ። ይህነኑም ሥራ የሚሠሩ የርሻ መሐንዲሶች ብቻ አይደሉም።ደግሞ ያገር ግዛት ሠራተኞችም ሁነው ከርሻ ሚኒስቴር ጋራ እንደዚህ ያለው አደጋ እንዳይሆን ይሠራሉ ።ከዚህም በኢትዮጵያ ለዚሁ ነገር እንዲያስቡበት ተስፋ እናደርጋለን ።

ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀልና ክቡር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ስለ ሀገሩ እርሻ አኳኋን በታላቅ ብርታት ሲሠሩ ከዚህ በላይ ለተነገሩት ቃሎች የተከናወነ እንዲሆንላቸው አጥብቀን ተስፋችንን እናደርጋለን ። በሥራቸውም መልካም ጥቅም እንዲያደርጉና የተሻለውንም እንዲሠሩ እንመኝላቸዋለን ።

የከብት ሐኪም ።

ሚሀራን ከይማኪያን ።

ከድሬደዋ ወደሐረር ይሠራል የሚባለው መንገድ ለአውቶመቢል ።

መሥራት የሚያስፈልገው አሁን በቅርብ ቀን ነበር።ስለምን ከወጋዴን ጀምሮ እስከ ቡርቃ፥ ከኢሣ እስከ ድሬዳዋ ያለው ሕዝብ ያለመጠን ስለ ተራበ ሥራው ቢሠራ ጥቅሙ ሁለት ይሆ

ኛል ድኃዋም እየሠራ ገንዘብ ያገኛል መንግሥትም የአሰበውን ይፈጽማል። የጨው ጥቅሙ ሁለት ነው ወዲህም አያበሰብስም ወዲህም ይጣፍጣል ድኃም መንግሥትም የሚጠቀምበት ከሆነ ሥራው በቶሎ ቢጀመር በዚሁ ምክንያት እየሠሩ የሚመገቡት ችግረኞች መንግሥትን አመስግነው እንደስጦታ ይቈጥሩታል

ዘለቀ ታችበሌ።

የከተማወሬ
ሹመት

ክቡር ዋግ ሹም ከበደ ለማዕርጋቸው የተገባ ሽልማት ተሸለሙ ። ክቡር ግራዝማች ተሰማ ደጃዝማች ተብለው ጐላን ተሾሙ ክቡር ቀኛዝማች አያብቸው ገሠሠ ሊቀ መኳስ ተብለው የሊቀመኳስ መንገሻ የነበረውን(ቀኝ)ተሾሙ።ክቡር ልጅ መንገሻ ወሰኔ ሊቀ መኳስ ተባሉ ። ቀኛዝማች አጽናፍ ሰገድ ፊታውራሪ ተብለው የደጃዝማች ከበደ ጓንጕል የነበረውን ተሾሙ። ክቡር ደጃዝማች ከበደ ጓንጕል ወፍላን ተሾሙ ። ደጃዝማች ቦጋለ ከዋግ ውሥጥ አገር ተሾሙ ። ክቡር ደጃዝማች ካሣ ስብሐት ሰዶን ተሾሙ ። ክቡር ግራዝማች ካሣ አባ ውቃው ወለጋ የደጃዝማች ክንፉ የነበረውን አገር ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ለተሾሙት መኳንንት እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

ፔር ዳኔይ ።
አበካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዶሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቤት አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪክ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ማዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርበስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያ የሆነጣዕሙም በጣም የተስማማነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚሁ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና የሚሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶሞቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።



ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ እገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጇነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የባለጡ የኤሌክትሪክ ሞቶርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንፎር ቤት በዳቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ከሙሴ ጉርጉ ዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶሞቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶሞቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶሞቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጽ ሳያ በረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አፊቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሉንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ፡ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶሞቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያለናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ኩሜባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

እድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ፯ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
5me ANNÉE № 25

ሐሙስ ሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 20 JUIN 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ፡ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Etranger
Un an 5 Thalers — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በጥበብ የቀሠራ የብር እቃ እንዳበረከተ ።

ሰኔ ፪ ቀን በማስታወቂያው እንደ ተጻፈ ከማታው በዓሥራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ የማዘጋጃ ቤት ዘበኛ ከራስ መኰንን ድልድይ እስከ ማዘጋጃ ቤት ድረስ በመንገዱ ግራና ቀኝ አምሮ እንዲሰለፍ ታዘዘ ። የግርማዊ ንጉሥም መምጣት በደረሰ ጊዜ እግረኛና ፈረሰኛ የግርማዊ የክብር ዘበኛ መጣና ክቡር ግራዝማች ግርማ ማሞ በራስ መኰንን ድልድይ ላይ በሥርዓት አሰለፉት ። የማዘጋጃ ቤት ዘበኛም ከግርማዊ ንጉሥ የክብር ዘበኛ ቀጥሎ በፊት ፈረሰኛ ወታደር ፤ ቀጥሎ እግረኛ ወታደር በየሻምበሉ በሥርዓት ሰልፉን አሳምሮ ተጠንቅቆ ቆመ። አቶ አየለ ገብሬም ሰልፉ በሥርዓት እንዲሆን ጐብኝተው አስጠነቀቁት ።

ግርማዊ ንጉሥም ልክ አንድ ሰዓት ከሀያ አምስት ደቂቃ ሲሆን ከራስ መኰንን ድልድይ ደረሱ ። ክቡር ልጅ አስፋወሰን ተፈሪም አብረው ነበሩ ። ግርማዊ ንጉሥም በደረሱ ጊዜ በቀኝ የተሰለፈው ወታደር በሙዚቃ ሰላምታ ሰጠ ። ግርማዊ ንጉሥ በማረ አውቶምቢል ተቀምጠው ፤ በግራ በቀኝ በክብር ዘበኞች ታጅበው ሲጓዙ፥ በግራ በቀኝ የቆመውም የማዘጋጅ ቤት ዘበኛ ብረቱን ባሰላምታ እያያዘ ይዞ ቀጥ ብሎ ቁሞ ሲታይ፥ እጅግ ያስጐመጅ ነበር ። መንገዱም በኤሌክትሪክ ብርሃን ተበርቶ ነበርና የማማሩ ነገር የሚያስደንቅ እንግዳ ነገር መስሎ ታየ ። በማዘጋጃ ቤቱም ውሥጥ ግርማዊ ንጉሥ ከቤታቸው ከሚነሡበት ጊዜ ጀምሮ ማዘጋጃ ቤት እስኪገቡ ድረስ ፈ ዳርቴፌስ የተባለ የጨዋታ ተኵስ ይተኰስ ነበር። ግርማዊ ንጉሥም በገቡ ጊዜ ማርሽ ተፈሪ ተነፋና ዜማው እስኪጨርስ ድረስ ግርማዊ ንጉሥና ምኒስትሮቹ ቁመው አደመጡ።ከዚህ በኋላ ግርማዊ ከሚኒስትሮቹ ጋራ ለማርፍያ ወደ ተሰናዳው ስፍራ ወጥተው ትንሽ ቈዩና ወዲያው ለራት ግብዣ በተሰናዳው ቤት ገብተው ዕፁብ ሆኖ የተሰናዳውን ራት ተጋበዙ።

ከራትም በኋላ ግርማዊ ንጉሥና የውጭ አገር ሚኒስትሮች፥ የኢትዮጵያም ሚኒስትሮችና ትልልቅ መኳንንት ለጨዋታ በተሰናዳው አዳራሽ ገቡ።ጨዋታውንም ለማየት ተጠርተው የመጡ መኳንንትና ወይዛዝሮች ተሰበሰቡ።በዚያ ጊዜ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል በማዘጋጃ ቤትና በከተማው ሰው ስም ሁነው ከዚህ በታች የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፤ የአዲስ አበባን ከተማ ለመመሥረት ያሰቡበትን፥አሁንም ግርማዊነትዎ በየጊዜው የተሻሻለ ደንብ እየሰጡና አዋጅ እየነገሩ ማዘጋጃ ቤትን በመርዳትዎ አዲስ አበባ ከዚህ ከትልቅ ደረጃ መድረሷን ፥ በግርማዊነትዎ ፊት ቀርቤ በራሴና በማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ፥ በከተማውም ሕዝብ ስም ሁኜ ለመናገር በመቻሌ እጅግ የታደልኩ ነኝ።

ትልቁ ንጉሥ ኀይለ ሥላሴ አያትዎ ዋና ከተማቸውን በአንኮበር አድርገው በሸዋ አውራጃ ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ የአረመኔውን አገር ሲያቀኑ ከዚህ ስፍራ በደረሱ ጊዜ በዚህ ስፍራ ወደ ፊት ዋና ከተማ ይሠራበታል ብለው እንደ ትንቢት ተናግረው ለምልክት አንድ ቤት አሠርተውበት ነበር። በዚያ ጊዜም ስሙ ፊንፊኔ ይባል ነበር ። ይኸውም በዳግማዊ ምኒልክ ታሪክ ውሥጥ ተጽፎ ይገኛል።

ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክም ዋና ከተማቸውን በእንጦጦ ተራራ ላይ አድርገው በዚያው ቅብአ መንግሥት ተቀብለው፥ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ሲኖሩ ፤ አያታቸው ንጉሥ ኀይለ ሥላሴ በዚህ ቦታ ዋና ከተማ እንዲሠራ እንደ ትንቢት መናገራቸው ቃል ለቃል ሲነገር መጥቶላቸው ነበርና። ከእንጦጦ ተራራ ወርደው በዚህ ፊንፊኔ ሲባል በኖረው ቦታ ላይ ከተማ ሠርተው ስሙን አዲስ አበባ ብለው ሠየሙት ።

ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክም ያያታቸውን ንግር ሰምተው የአዲስ አበባን ከተማ ስለ መሠረቱ ዕረፍታቸውና መቃብራቸውም በዚሁ ከተማ ስለ ሆነ የስማቸው መታሰቢያ ሁኖ ይኖራል።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ፤ የጃንሆይ የዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ካለፈ በኋላ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት በሆኑ ጊዜ፥ ግርማዊነትዎም የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ለመንግሥቱ ሥራ እንደራሴ ከሆኑ ዓሥራ ሦስተኛ ዓመት ሊሆን ነው ።

በዚህ በዓሥራ ሦስት ዓመት ውሥጥ በግርማዊነትዎ እርዳታና ትጋት የአዲስ አበባን ከተማ ስፋት በጥርብ ደንጊያ የተሠሩትን የመኖሪያና የንግድ፥ የልዩ ልዩ ቤቶችን ማማር፥ የንግዱን ስፋት፥ የሕዝቡን ብዛት፥ በየሰፈሩም የታነፁትን ቤተ ክርስቲያኖች ይህን የመሰለውን አዲስ ሥራ ሁሉ ለሚመለከተው ሰው እጅግ ያስደንቃል ።

ከ ፲፱፻፲፱ ዓመት አስቀድሞ የከተማ ዘበኞች ቁጥር ፩፻፶ ሀል ነበረ። ወዲያው ግርማዊነትዎ የመንግሥት ሥራ በጀመሩበት በ፲፱፻፲፱ ዓመት ፩፻ ዘበኞች ተጨምረው ቁጥራቸው ፪፻፶ ሆነ።ከዚያም ወዲህ ከከተማው ስፋት ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ በከተማ አንዳንድ ወስላቶች ማታ ማታ ተኵስ እየተኰሱ የከተማውን ጸጥታ የሚያውኩ ቢሆኑ ግርማዊነትዎ ይህን ነገር መርምረው፥ ለከተማው ጥበቃ የሚያስፈልገውን ደንብ ሰጥተው፥ አዋጅ ነግረው በቀድሞዎቹ በ፪፻ ዘበኞች ላይ ሁለት ሺህ ዘበኞች እንዲጨመሩ አድርገው ሌባ፥ነፍሰ ገዳይ ለሚይዙ ዘበኞች ሽልማትና ገንዘብ እየሰጡ በሥልጣንዎና በትጋትዎ ኀይል ስለ ረዱቸው የዘበኝነት ሥራቸውን በጥንቃቄ እየሠሩ የከተማው ሕዝብ ያለ ስጋት በጸጥታ በመኖሩ ደስ ስላለው ምስጋናውን ያቀርብልዎታል ። ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ከ፲፱፻፲፱ ዓመት አስቀድሞ የማዘጋጃ ቤት ገቢ ገንዘብ ፶፰ሺ፩፻፲፰ ብር ያህል ነበር።ገቢውም ገንዘብ ከማነሱ የተነሣ በከተማው ውሥጥ መንገድም ድልድዩም ለመሥራት አልተቻለም ነበረ።ከ፲፱፻፲፱ ዓመት ወዲህ ግን ግርማዊነትዎ ለማዘጋጃ ቤት የተካከለ ደንብ በመስጠትዎና አዋጅ በመንገርዎ ብዙ ሥራ እየተቃና ስለ ሔደ ገቢው ገንዘብ እየበዛ የማዘጋጃ ቤት በከተማ ውሥጥ ብዙ መንገዶችና ድልድዮች ለመሥራት ተቻላትና የከተማው ሕዝብ ከንዱ ሰፈር ወደ ሌላው ሰፈር ያለ ችግር በፍጥነት እንዲተላለፍ የተመቸ ሆነ ።

በ፲፱፻፱ ዓመት የማዘጋጃ ቤት ገቢ ገንዘብ	፺፱ሺ.፫፻፲ ብር ነበር
በ፲፱፻፲ ዓመት	፫፻፴፩ሺ.፯፻፹፰ ብር ሆነ
በ፲፱፻፲፩ ዓመት	፻፺፰ሺ. ፴ ብር
በ፲፱፻፲፪ ዓመት	፻፴፯ሺ.፯፻ ፫ ብር
በ፲፱፻፲፫ ዓመት	፻፳፫ሺ.፪፻፺፰ ብር
በ፲፱፻፲፬ ዓመት	፻፵፪ሺ.፯፻፴ ብር
በ፲፱፻፲፭ ዓመት	፻፹፩ሺ. ፺፩ ብር
በ፲፱፻፲፮ ዓመት	፪፻፹ሺ. ፫፻፯ ብር
በ፲፱፻፲፯ ዓመት	፻፵፩ሺ. ፹፪ ብር
በ፲፱፻፲፰ ዓመት	፬፻፲፯ሺ.፯፻፹፪ ብር
በ፲፱፻፲፱ ዓመት	፭፻፺ሺ. ፬፻ ፫ ብር
በ፲፱፻፳ ዓመት	፭፻፸፫ሺ.፩፻፹፩ ብር ሆነ

ስለዚሁም በከተማው ውሥጥ ብዙ መንገዶች ተሠርተዋል። ወደ ፊትም ለመሥራት የማዘጋጃ ቤት መሐንድሶች ክሮኪ የሚባለውን የመንገዱን ሥዕል አስቀድመው ሥለው ስለጨረሱ መንገዱን እንደ ሥዕሉ እያደረጉ መግለጥ ጀምረዋል ። ይኸውም የተገለጠው መንገድ ሁሉ ፥ በግርማዊነትዎ እርዳታ በቶሎ እንዲሠራ ሙሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

ይህንንም የከተማውን መንገድና ድልድይ ነገር ከነማሁ ዘንድ፥ ግርማዊነትዎ የረዳውን ትልቅ እርዳታ ልዘነጋው አይገባኝም ። የቀድሞው ማዘጋጃ ቤት ከጠባብ ስፍራ ላይ ሁኖ ቤቱም የማይበቃ ስለሆነ ስለጉዳዩ ለሚመጣው ሕዝብ ለመውጣት ለመግባት እየጠበበው እጅግ ይቸገር ነበር። አሁን ግን ለማዘጋጃ ቤቱ ለሥራ፥ሕዝቡም ጉዳይ መፈጸሚያ ከተመቸ ቦታ ላይ የቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ቤት የነበረውን በ፻፲፩ሺ.ብር በግርማዊነትዎ ኃሳብ ጥረው አስገዝተው ማዘጋጃ ቤቱን ከዚህ ስፍራ ላይ በማቆምዎ ትልቅ መታሰቢያ ነው ።

ከብዙ ዘመን አስቀድሞ ፥ በትልቁ ንጉሥ በዳግማዊ ምኒልክ ትጋት ወደ አዲስ ዓለም የሚወስደው መንገድ በተሠራ ጊዜ፥ አባትዎ ልዑል ራስ መኰንን በአዲስ አበባ ከተማ መካከል አንድ ድልድይ ስለ ሠሩ በስማቸው ሲጠራ ይኖራል። ይኸውም ድልድይ ምንም በሥራው ጥንካሬ የማያሰጋ ቢሆን ከመጥበቡ የተነሣ ለአውቶምቢልና ለእግረኞች መተላለፍ የሚያሰጋ መሆኑን ግርማዊነትዎ በሰሙ ጊዜ ድልድዩ በቀኝና በግራ እንዲጨመርበትና እንዲሰፋ ፥ፕላኑንና የሚፈጀውን ገንዘብ አስታውቁኝ ብለው አዘዙ ። መሐንድሶችም ገምተው ፱ሺ.፰፻ብር ይፈጃል ብለው ቢያስታውቁ ፥ የዚህን ግማሹን ፬ሺ.፱፻፶ብር ከራስዎ ግምጃ ቤት ሰጥተው ፥ ሥራው ተጨርሶ በዚያ ለሚያልፈው ሰው ሁሉ ፥ እጅግ ደስ የሚያሰኝና የሕዝቡን ሕይወት ከአደጋ የሚጠብቅ ስለ መሆኑ ፥ የማዘጋጃ ቤት በራስዎና በከተማው ሕዝብ ስም ሁና ከፍ ያለ ምስጋና ታቀርባለች። ከ፲፱፻፱ዓመት በፊት መንገዱና ድልድዩ ተከክሎ ባለመሠራቱ ምክንያት ፥ የከተማው ሕዝብ ፥ ወደ ሥራውም፥ ወደ ጉዳዩም ሲመላለስ በበቅሎ ብቻ ይሔድ ስለ ነበረ በዚያን ጊዜ እጅግ ቢበዛ ባንድ ቀን አንድ ጉዳይ ብቻ ጨርሶ ይውል ነበር እንጂ የቀን ሥራውን ሁሉ እንዳሰበው ተመላልሶ በፍጥነት ለመጨረስ አይቻለውም ነበር ። አሁን ግን በግርማዊነትዎ ትጋት መንገዱና ድልድልዩ አምሮ ስለ ተሠራ ከአራት መቶ የሚበልጡ አቶሞቢሎችና ሞቶሲክሌቶች በከተማው ውሥጥ ለመመላለስ ቻሉ - ስለዚህ ቀድሞ ላንድ ጉዳይና ሥራ መፈጸሚያ አንድ ቀን ሙሉ ይወስድ የነበረውን በዛሬው ሥልጣኔ አኳኋን ባለ ጉዳዮችና ሠራተኞች በአቶሞቢል ፍጥነት እንደ ልብ ተመላልሰው ባንድ ቀን ብዙ ሥራና ጉዳይ ጨርሰው የሚውሉ ስለ ሆነ ፥ ትልቅ ጥቅም መሆኑ ታውቋልና፥ ስለዚህ የከተማው ሕዝብ በመላው ታላቅ ምስጋናውን ያቀርብልዎታል ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ፤

ከ፲፱፻፱ ዓመት አስቀድሞ ፥ በአዲስ አበባ ከተማ ታላቁ ንጉሥ ዳግማዊ ምኒልክ ያቆሙት አንድ ሆፒታል ብቻ ነበር ። ከ፲፱፻፱ ዓመት ወዲህ ግን በግርማዊነትዎ ትጋት ብዙ ሆፒታሎችና ብዙ ፋርማሲዎች ተሠርተው፥ብዙ ሐኪሞች መጥተው፥ የከተማው ሕዝብ ጤናው እንዲጠበቅ በማድረግዎ በታላቅ ምስጋና እናመሰግናለን። ይኸውም መልካም ሥራዎ ጧትና ማታ ለሚያዩት ለአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በቀሩትም በኢትዮጵያ አውራጆች በሐረርና በደሴ፥በወለጋ በራስዎ ገንዘብ ሆፒታል እያቆሙ የሕዝቡን ጤና መጠበቅዎና መርዳትዎ ከሕይወትዎም በኋላ መልካም መታሰቢያ ሁኖ መኖሩ የታወቀ ነው ።

ደግሞ ከ፲፱፻፱ ዓመት አስቀድሞ በአዲስ አበባ ከተማ ያሉት ሆቴል ኢምፔሪያልና ሆቴል ደ ፍራንስ የሚባሉት ሁለት ሆቴሎች ብቻ ነበሩ ። አሁን ግን ብዙ ሆቴሎችና ብዙ ሬስቶራዎች፥ ብዙ የቡና ቤቶችም ስለ ተሠሩ የከተማውም ሕዝብና ከውጭ አገር የሚመጡ እንግዶች ሁሉ የሚፈልጉትን ምግብና ማደሪያ ያለ ችግር እንዲያገኙ ሁነዋል ።

ግርማዊ ሆይ ፤

ከ፲፱፻፱ ዓመት አስቀድሞ ታላቁ ንጉሥ ዳግማዊ ምኒልክ ያቆሙት አንድ ተማሪ ቤት ብቻ ነበረ ። አሁን ግን ግርማዊነትዎ ኢትዮጵያ ወደ ታላቅ ደረጃ እንድትደርስ ትልቅ ሐሳብዎ ስለ ሆነ ፥ በገንዘብዎ የትምህርት ቤት አቁመው የኢትዮጵያ ልጆች እንዲማሩ በማድረግዎ ብዙ ልጆች ወደ ትልቅ እውቀት መድረሳቸውን በየመቱ የሚደረገው የትምህርት ቤቱ ራፖር አስረድቶናል።ከዚህም በተቀር ደግሞ ከመቶ የሚበልጡ ልጆች ወደ ውጭ አገር እሔዱ እንዲማሩ በማድረግዎ ኢትዮጵያ ስታመሰግንዎ ትኖራለች ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ፤ በአዲስ አበባ ከተማ የማዘጋጃ ቤት ማቆም ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ተረድተው እንደ ገና ትእዛዝዎንና እርዳታዎን እየሰጡ በሐረር ፥ በድሬ ዳዋ፥ በጂጂጋ፥ በአስበ ተፈሪ ፥ በደሴ ፥ በጐሬ ፥ የማዘጋጃ ቤት እንዲቆም በማድረግዎ አገርዎን ኢትዮጵያን ለማሠልጠንና ወደ ትልቅ ደረጃ ለማድረስ ፥ ሕዝብዎንም ለመርዳትና ለመጥቀም እውነተኛና የተካከለ አሳብ እንዳለዎ ያስረዳናል ።

ወደ ፊትም በየታላላቁ አውራጆች ከተሞች ሁሉ የማዘጋጃ ቤት እየቆመ፥ ሆፒታልና የትምህርት ቤት እየተሠራ፥ በየአውራጃው ያለው ሕዝብ ጤናውን እንዲጠብቅና ትምህርት እንዲያገኝ ለማድረግ ይኸው መልካሙ አሳብዎ ወደ ፊት እየገፋ መሔዱን አንጠራጠርም ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ፤ በቀድሞ ዘመን ወንጀለኛ የሆነ ሰው እጁ በተያዘ ጊዜ በከተማ ያለው ቦታውና ቤቱ ፤ በባላገርም ያለው ርስቱ ይወረስ ነበርና ሚስቱና ልጆቹ ቤተ ሰዎቹም የሚገቡበት ቤትና የሚኖሩበት ቦታ እየቸገራቸው ሲጨነቁ ይኖሩ ነበር ። አሁን ግን ፤ ወንጀለኛ የሆነ ሰው በእሥራትና በገንዘብ ይቀጣ እንጂ በከተማ ያለው ቦታና ቤቱ በባላገርም ያለው ርስቱ አይነቀል ፤ አይወረስ የሚል አዋጅ ባለፈው ኅዳር ወር ስለ ተነገረ የከተማው ሕዝብና ባላገሩ ያገኘውን ደስታ ጨርሰን ለመናገር አንችልም ። በቀድሞ ዘመን ጊዜ ነፍስ ገድሎ ይሙት በቃ ተብሎ የተፈረደበት ሰው ለባለ ደሙ ተሰጥቶ ባለ ደሙ ግልጥ በሆነ ስፍራ ላይ በጦር እየወጋ፥ በጐራዴ እየጨፈጨፈ ፃዕሩን አብዝቶ ይገድለው ነበር። የከተማውም ሕዝብ ይህነኑ በብዙ ፃዕር የሚሞተውን ሰው ለማየት እየተሰበሰበ የፃዕሩን ብዛት የሟቹንም ጭንቀት እያዩ በመሳቀቅ እያለቀሱና እያዘኑ ይመለሱ ነበር ።

አሁን ግን ግርማዊነትዎ ርኅራኄዎን ለመግለጽ ሲሉ ሟቹ ፃዕር ሳይበዛበት በፍጥነት እንዲሞት፤ የከተማውም ሕዝብ የሟቹን ፃዕሩን በማየት እንዳይሰቀቅ በተለየ የሞት ፍርድ ማስፈጸሚያ ቤት በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በማሠራትዎና ፍርድ በሚገባ እንዲፈጸም በማድረግዎ ኢትዮጵያ አንድ ትልቅ ዋና ደረጃ መውጣቷን በግልጽ ያስረዳናል ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ፣ አሁንም ወደ ፊት ለኢትዮጵያና ለከተማዎ ለሚሠሩላት ፤ ላለፈው ለደከሙላት ምንም የሥራዎ ዋጋ ግምት ፤ ባይሆን ፤ የንጉሥነት ዘውድ ክብርዎና የሥራ ሙሉ ሥልጣንዎ ሰይፍ ሲመዘዝ ፤ የዚህ ደስታ ተካፋይነቷን ለመግለጽ የአዲስ አበባ ከተማ በኔ በከንቲባው እጅ ይኸነን በጥበብ የተሠራ የብር ዕቃ ታቀርብልዎታለች ።

ይኸነንም ማስታወሻ ስታቀርብ ምኞቷ ከአውሮጳ ከተሞች እንዳንዱ ሁና ሕዝቡን ደስ ለማሰኘት፥ ለሥራው መታሰቢያ ለመሆን ነውና በኔም፥በዲሬክተሩም፥ በከተማው ዘበኞችና በማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ስም ሁኜ ሥልጣንዎንና እውነተኛ ፍርድዎን እየተማመንን እሙንነታችንን ሳናቋርጥ አገልግሎታችንን ለመግፋት የቆረጥን መሆናችንን እናስረግጣለን ።

እንኳን ደስ አለዎ ለማለት የታደልን ስለ ሆንንም ለደስታችን መጠን የለውም ።

እግዚአብሔር ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ይጠብቅ ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ያኑርልን ።

ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ተናግረው በጨረሱ ጊዜ ጭብጨባው ቀለጠ ። ከዚህ በኋላ ለግርማዊ ንጉሥ የሚሰጠው በጥበብ የተሠራ እቃ በግርማዊ ንጉሥ ፊት ቀረበና ዳር እስከ ዳር ደግሞ እንደ ገና ጭብጨባው ቀለጠ ።



የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ያበረከተው የብር ዕቃ።

ግርማዊ ንጉሥም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ልብ የሚነካ ንግግር ተናገሩ ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ለዘውዳችን በዓል መታሰቢያ አድርጎ በማዘጋጃ ቤት በኩል በከንቲባው እጅ ያቀረበልንን በጥበብ የተሠራ ዕቃ ስንቀበል ፣ ምስጋናችን ለከተማው ሕዝብ ይሁን እያልን የኢትዮጵያን ልማት እንመኛለን ።

አሁን ስለ አስረዳችሁት ስለ ከተማው መሻሻል ፤ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሥራ መሪዎችና ሠራተኞች የሆናችሁ ሁሉ የሚገባችሁን ምስጋና ታገኙ ዘንድ እንፈቅዳለን ።

ገርምሩ ተቋርጦ የቀረበትን ትጉህ የነበረው አገልጋያችንን ከንቲባ ወሰኔንም ሥራውን እያሰብን ስሙን እዚህ ላይ ሳናስታውሰው ለማለፍ አንፈቅድም ። ጀንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የአዲስ አበባን ከተማ ከቆረቆሩ ጀምሮ እስከ ዕረፍታቸው ዘመን ድረስ ፤ የጀመሩት ታላቅ ሥራ ሁሉ ወደ መልካም ፍጻሜ እንዲደርስ፤ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና የእኛም የራሳችን አሳብና ፈቃድ መሆኑን ይህነኑ ምክናያት አድርገን እንገልጥላችኋለን ። በየጊዜውም ከተማውን ለማሳመር የሚደክሙ መሐንዲሶች ሥራ ፤ የሕዝቡንም መልካም አስተዳደር የሚጠብቁ ዘበኞች ትጋት ፤ ለከተማው ሕዝብ ሁሉ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ስለ ሆነ ፤ ለከንቲባውና ለሠራተኞቹ የሚያስመካች ሁና የሚያትጋችሁ ነው።

የሕዝብ በፍጹም የተሻለ አካሔድና ሥራ ሁሉ ፤ ከልማቱ ጋራ በመቀራረብ ካልተሠራ ፤ ልማቱ እውነተኛ ነው ለማለት አይቻልም ። ስለ ሀገር ልማት የታሰበው አሳብ ፍጻሜ እንዲያገኝ የተፈለገ እንደሆን ፤ ለዘወትር ሕዝብን በመልካም ሥራ የሚመሩና የሚያበረታቱ ፤ በመንግሥት ሥራ ላይ አዛዥ ለመሆን ክብር ያገኙ ሹማምንቶች ፤ በበታቻቸው ላሉት ሠራተኞች የመልካም ምስሌ እንዲሆኑ ያስፈልጋል ።

የሕዝባችንም እውነተኛ አሳቡና የክርስቲያንነት ሃይማኖቱ እጅግ የጠነከረ ነው ።

ክመው ደከም ሁሉ ከንቱ ሁኖ ይቀር ነበርና ፤ አሁን የሥራውን ፍሬ ሕዝብ መልክም አከሔድ ሲገልጽ በመመልከታችን ደስ ብሎናል ።

ወደ ፊትም ሥራችሁን ለማስፋትና ለማልማት ፤ የሕዝቡንም ሕይወትና ጤና ለመጠበቅ በምትሠሩት ሥራ ሁሉ እ፫ዳርታችነን እናጉድልባችሁምና በትጋትእንደትሠሩ ይሁን ።

Il nous plait, en acceptant des mains du Kantiba, l'objet d'art que nous offre la ville d'Addis-Abeba, en souvenir de notre couronnements, de présenter nos remerciments à la population en formant des voeux pour la prospérité de l'Ethiopie.

Nous éprouvons un plaisir particulier à rendre un juste hammage à tous les membres de la Municipalité, les chefs aussi bien que leurs subordonnés, qui ont cooperé à l'heureux développement de la ville que vous venez d'exposer.

Nous ne voulons pas laisser passer cette occasion sans évoquer le nom de notre zélé serviteur, le Kantiba Wassanié, en rappelant l'œuvre qu'il avait entreprise et que le destin inexorable l'obligea à laisser inachevée.

Nous tenons à vous faire connaitre, en cette circonstance que S. M. l'impératrice Zaouditou et nous-même, sommes animés du dessein constant et de la ferme volonté de faire heureusement aboutir l'œuvre grandiose entreprise dès l'époque de la fondation de la ville d'Addis-Abeba par S. M l'Empereur Menelick et qu'il a poursuivie jusqu'à son dernier souffle.

Les efforts des ingénieurs en vue d'embellir la ville, la vigilance de la Police à assurer la tranquillité de la population, sont autant de motifs de satisfaction pour tous et pour le kantiba et ses collaborateurs, une cause de fierté légitime et un encouragements à perséverer.

Un progrés ne peut-être vraiement harmonieux que si le perfectionnement moral est étroitement associé aux améliorations matérielles. Pour qu'une œuvre entreprise dans l'interêt du pays soit féconde, il est du devoir de ceux qui ont l'honneur de diriger et de commander, de donner à ceux qui sont placés au-dessous d'eux, de tels exemples dans l'exercice de leurs fonctions publiques, qu'ils soient continuellement un sujet d'édification et d'encouragement pour tous.

Nous avons la joie de constater, dans le profond attachement à la foi chrétienne et aux principes religieux dont fait preuve notre Peuple, l'heureux épanouissement de ces qualités morales sans lesquelles tout progrés matériel reste vain et toute œuvre stérile.

nous continuerons, à l'avenir comme dans le passé, à vous apporter les encouragements que vos efforts méritent, car ils ont pour but le développement de votre œuvre et le bien-être de la population. Persévérez donc avec Zèle dans vótre tâche.

ግርማዊ ንጉሦ ተናግረው ከጨረሱ በኋላ ሰዉ ከደስታው የተነሣ ረጅም ጭብጨባውን ከባቢ እስከ ውጭ አንጉደው። ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያ ማርሽ ተመታ።ደጓሞም ፕያኖ እየተመታ ማዳም ተፈራ በለው፤ ማዳም ዋዜል መ አትማጂያንና ማዳም ባይክቢትች ጣሩም የሆነ ዘፈን በማሰየታቸው ሰውን በጣም ደስ አሰኙት ። ወዲያውም ፕያኖ እየተመታ ዘፈን ተጀመረ ። በዘፈኑም መካከል ሰው ሁሉ በያይነቱ መጠጥና ምግብ በተሰናዳበት ቤት ገብቶ እንዲጋበዝ ተፈቀደለትና ሁሉም በልቶ ጠጥቶ የሥርዓቱን ማማርና የሲሳዩን መብዛትና መሰናዳት ደስ አሰኝቶት ክቡር ከንቲባ ነሲቡንና የማዘጋጃ ቤትን ሹማምቶችና አገልጋዮችንም ሁሉ እጅግ አመሰገነ። ከዚህም በኋላ ፕያኖ እየተመታ ዘፈኑ እየደመቀ ሔደ ። ከዚህ መካከል ግርማዊ ፊ ዳርቴሬስ የሚባለውን የጨዋታ ተኵስ ለማየት ወጡ ። የተተኰሰው እሳት ወደ ሰማይ ተወርውሮ ሲወጣና በአየር ላይ ወጥቶ ፈንድቶ በያይነቱ የብርሃን አበባ መስሎ እየተፈነጠረ ሲጠፋ ላይታው ያስገርም ነበር ።

ይህ ከተደረገ በኋላ የውጭ አገር ሚኒስትሮች ከግርማዊ እየተሰነባበቱ ሔዱ።ግርማዊ ንጉሦም ወደ ቤታቸው ለመሔድ ተነሡና ግጀቡ እንደ ፊተኛው አመጣጥ ሁኖ እንደ አማረ በስምንት ሰዓት ከቤታቸው ገቡ ።

የሥርዓቱ ሁሉ መከናወን ፤ የፈንጠዝያው ማማር፤ የቤቱ መሰናዳት፤ እጅግ ግሩም ነው ተነግሮም አይዘለቅ። ክቡር ከንቲባ፤ የማዘጋጃ ቤቱም ሹሞችና ሠራተኞች ሁሉ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ እንደ ሕልም ሁኖ ይታያቸው ነበረ ። እውነትም ለሁሉ ሰው እንግዳ ነገር ሁኖ ታየው ግሩም ነው ።

(ከፓሪስ ተላላኪያችን የመጣ) ።

የፈረንሣዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ክቡር ሙሴ ዱሜርግ በፓሪስ የኢትዮጵያ ልዩ መላክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሁነው ለተሾሙት ለክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ስለ አደረጉት የክብር አቀባበል ።

ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ በፓሪስ የኢትዮጵያ ልዩ መላክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሁነው ስለ ተሾሙ የሹመት ወረቀት ለፈረንሣዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ለክቡር ሙሴ ዱሜርግ ለማስረከብ እንደ ደንቡ ከፕሮቶኮል ሹም ከክቡር ሙሴ ፉኬር ጋራ ተገናኝተው ነገሩን አስታወቋቸው።ክቡር ሙሴ ፉኬርም በመልክም አቀባበል ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተን ተቀብለው አስቀድሞ ከፈረንሣዊ መ

ንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከክቡር ሙሴ ብሪያን ጋራ መገናኘት ያስፈልጋል ብለው ቀጠሮ ሰየቁላቸው ። በቀጠሮውም ቀን ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሔዱ ጊዜ በዚያም የክብር አቀባበል ተደረገላቸው ። ከፕሬዚዳንትም ጋራ የሚገናኙበትን ቀንና ሰዓት አስታወቋቸው ።

ከጥቂት ቀንም በኋላ በሚያዝያ ፳፩ ቀን (እንደ አውሮፓ ቁጥር በግንቦት ፫ ቀን) የሹመታቸውን ደብዳቤ ለክቡር ሙሴ ዱሚርግ ለማስረከብ ነገሩ ተቆርጦ ነበርና በዚሁ ቀን በተቆረጠው ሰዓት ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመውሰድ የታዘዙት ክቡር ሙሴ ፋኬር የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ባማረ በመንግሥት አቶሞቢል ሁነው ሌላም ሁለት አቶሞቢሎች አስከትለው ወደ ክቡር ቤትወደድ ጌታቸው መጡ ክቡር ቤትወደድ ጌታቸውም ክቡር ሙሴ ፋኪርን ተቀብለው ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመሔድ ተነሡ በመጀመሪያው አቶሞቢል ክቡራን ቢትወደድ ጌታቸውና ሙሴ ፋኬር ፣ በሁለተኛው አቶሞቢል በፓሪስ የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ጸሐፊ አቶ እንዳርጋቸው መሰይና የኢትዮጵያ ቆንስል አቶ ኤፍሬም ተቀምጠው ወደ ቤተ መንግሥቱ መንገዝ ጀመሩ። በሦስተኛው አቶሞቢል ግን ሁለት የፈረንሣዊ መኳንንቶች ተቀምጠው በፊት በፊት ይሔዱ ነበር ። እንደዚህም ባማረ አካሔድ እየተጓዙ ጋርድ ሬፑብሊክ የሚባሉ መቶ የሚሆኑ ወታደሮች ወደ ተሰለፉበት ኤሊዜ ወደሚባለው ቤተ መንግሥቱ ደጅ ደረሱ ።

የተሰለፉትም ወታደሮች የወታደር ሙዚቃ እየመቱ የክብር ሰላምታ ለክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ አቀረቡ ። እርሳቸውም ሰላምታ እየሰጡ ወደ ቤተ መንግሥቱ ደረጃ በደረሱ ጊዜ ከአቶሞቢሉ ሲወርዱ የሰልፍ ልብስ የለበሱ አራት ታላላቅ መኳንንቶች ተቀብለው ወደ እንግዳ ማረፊያው ክፍል ወሰዱዋቸው በዚያም ውሥጥ የማዕርግ ልብሳቸውን የለበሱ ብዙ መኳንንቶች ቁመው ነበርና ከቆሙበት ሥፍራ ሳይዛወሩ ሰላምታ ሰጡዋቸው ። ወደዚያውም የፈረንሣዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ክቡር ሙሴ ዱሚርግ በእንግዳ መቀበያው የቤት ክፍል ሜዞ ሲቢልና ሜዞ ሚሊቴር የሚባሉትን ከርሳቸው ጋራ እንግዳ የሚቀበሉት ብዙ መኳንንቶች በቀኝና በግራ አድርገው ይጠብቁ ነበርና ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ወደዚያው በተጠሩ ጊዜ እርሳቸውን ተከትለው የነበሩ ክቡር ሙሴ ደፋኬር ከፍ ባለ ድምጽ እነሆ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ብለው ተናገሩ ።

በክቡር ሙሴ ዱሚርግ ዙሪያ የነበሩትም መኳንንቶች ከኢትዮጵያ መንግሥት የተሸለሙትን ኒሻን አድርገው ነበር።ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተም ወደ ክቡር ሙሴ ዱሚርግ ቀርበው ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡር የሬፑብሊክ ፕሬዚደንት ሆይ ።

የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መንግሥት ዛሬ በመጀመሪያ ጊዜ ከታላቁ ከፈረንሣዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ዘንድ የሚወክል ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሩን ሾመ ። ይህም ዘወትር በሁለቱ መንግሥቶች መከከል

መገናኛ ዋና ምክር ነው ። የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና የግርማዊ ንጉሥ ሐሳብ ለክቡርነትዎ ታማኝ አስተላላፊ ለመሆን ክብር በማግኘቴ ለኔ እጅግ ደስታዬ ነው ።

በሁለቱ አገሮቻችን መካከል ከጥንት ጀምሮ የሚኖረው ወዳጅነት በሁለቱ ሕዝቦችመካከል በየቀኑ እየጠበቀ የሚሔደውን የመፋቀርን ማስተሣሰሪ ስለ አቆመ ከዚህም የበለጠ ይጠብቅ ዘንድ ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ ወደ ታላቁ ፈረንሣዊ ሬፑብሊክ ዘንድ ልከውኛልና ይህን የተላክሁበትን መልእክት በፍጹም ልብና አሳብ ለመፈጸም እጥራለሁ ። ክብር የመላበት ታሪኩ የኢትዮጵያውያንን ልብ በደስታ በሚቀሰቅሰው በፈረንሣዊ ሕዝብ ዘንድ የኢትዮጵያ መንግሥት በማክበር የሾመው መጀመሪያው እንደራሴ በመሆኔ ደስታዬ ምን ያህል እንደሆነ እናገር ዘንድ ክቡርነትዎ ይፍቀዱኝ ።

ይህ የማይዘነጋ ቀን የኔን የራሴን ምኞቶች መፈጸም ያረጋግጣልና ሳይዘነጋኝ ዘለዓለም በአሳቤ ተቀርጾ ይኖራል።

ስለዚህ በፈረንሣዊ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳን ዘንድ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚንስትር አድርጎ የሚሾመኝን የግርማዊት ንግሥትና የግርማዊ ንጉሥ ማኅተም ያለበትን ደብዳቤ ለክቡርነትዎ በክብር አቅርቤ አስረክባለሁ ።

Monsieur le Président de la République.

Pour la première fois, le Gouvernement impérial de Sa Majesté Zeouditou. Reine des Rois, et de Sa Majesté Teferi Makonnen, délègue pour le représenter auprès de la grande République Française un Ministre Plénipotentiaire, consécration solennelle des sentiments de l'aimable amitié qui préside depuis toujouss aux heureuses relations des deux Gouvernements.

Et c'est à mois qu'échoit l'indicible joie d'avoir l'honneur d'être auprès de votre Excellence l'interprète dévoué de la pensée de leurs Majestés.

La traditionnelle amitié des nos deux nations a créé entre leurs peuples des lieus d'affection que je voie se resserrer chaque jour et c'est pour les rendre encore plus étroits que leurs Majestés n'ont envoyé auprès du Gouvernement de la noble République Française, mission que je m'efforcera de remplir avec toutes les ressources de coeur et de l'esprit.

Laissez-moi dire à votre Excellence combien je suis touché d'être le premier représentant que l'empire d'Ethiopie a l'honneur d'aceréditer auprès de la nation Française, dont toute la glorieuse Histoire fait vibrer d'émotion le coeur des Ethiopiens.

Cette date mémorable consacre la réalisation de tous mes voeux personnels et restera toujours vivante en ma mémoire.

En conséquence, j'aì l'honneur de présenter et de remettre à votre Excellence, la lettre revêtue des sceaux de leurs Majestés qui m'accrédite comme Ministre Plénipotentiaire de l'Empire d'Ethiopie auprès du Président de la République Farnçaise.

ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው ተናግረው ከጨረሱ በኋላ ። ክቡር ሙሴ ዱሚርግ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ ።

የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መንግሥት ክብርነትዎን የኢትዮጵያ ልዩ መልክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርገው ከፈረንሣዊ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት ዘንድ የሾሙበትን ደብዳቤ ስቀበል አጥብቆ ደስ ይለኛል ። ሁለቱን ሕዝቦቻችንን አንድ የሚያደርገውን ወዳጅነት አረጋግጦ ለማጠንከር ከዚህ የተሻለ አድራጎት አይገኝም ። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ፈረንሣዊ በትጋት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ባለመቋረጥ ያስብላታል ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ከፈረንሣዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ጋራ የቋጠሩዋቸው የመተማመን መገናኛዎች ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ወዳጅነት ከማረጋገጥም በቀር ኢትዮጵያ እየለማች ትሔድ ዘንድ ፈረንሣዮች እንዲተጉ ልዩ ታላቅ ምክንያት ያገኙ ዘንድ እነዚህ መገናኛዎች ፈቀዱላቸው ። ፈረንሣዊ ለኢትዮጵያ ወዳጅነቷ እየጸና መኖሩን የሚገልጽ ምስክር ብዙህ ጊዜ ሰጥታለችና ይኸውም በታላቁ ተግምቶላታል ይህንኑ አሳብ ተከትላ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሚጥርበት ልማቱ እርዳታዋን ባለማቋረጥ ትሰጣለች ከዚህ ቀድም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን መልከም ፈቃዳቸው ሆኖ በጐበኙን

በሁለቱ አገሮቻችን መካከል ያሉት የወዳጅነት ማስተሳሰሮች እንደጸኑ እንዲኖሩና እየጸኑ እንዲሔዱም በሬፑብሊኩ ፕሬዚዳንት ዘንድ ፍጽሞ ፈቃድ እንዲያገኙ መረጋገጥ ይችላሉ ።

Monsieur le Ministre,

Il m'est bien agréable de reçevoir les lettres par lesquelès le Gouvernement Impérial de Sa Majesté Zaouditou, reine des rois, et de Sa Majesté Teferi Makonnen, régent plénipotentiaire, accrédite votre Excellence en qualité d'Envoyé Extraordinaire et de Ministre plénipotentiaire de l'Empire d'Ethiopie auprès du président de la République Française.

Nulle décision ne pouvait mieux sceller l'amitié qui unit nos deux nations. Depuis longtemps, la France n'a cessé de s'interesser activement à l'Ethiopie et à son peuple.

Les relations si confiantes que l'Empéreur Minilik II avait su nouer avec le Gouvernement de la République n'ont pas seulement confirmé une tradiction qui remonte loin dans le passé, mais elles ont donné en même temps à l'activité Française une occasion particulièrement brillante de s'employer au développement de l'Abyssinie.

La France reste animée envers l'Ethiopie des sentiments de sympathie dont elle lui a si souvent donné des gages hautement appréciés. C'est dans cet esprit qu'elle continuera à contribuer à l'oeuvre de progrès à laquelle le Gouvernement impérial consacre le meilleur de son effort. Naguère encore Sa Majesté Teferi Makonnen, au cours de la visite qu'il a bien voulu nous faire, a pu se convaincre de l'affection et de l'intérêt que rencontre en France tout ce qui concerne l'Abyssinie. Vous pouvez être assuré de trouver auprès du président de la République la volonté la plus ferme de collaborer au maintien et au resserrement des liens d'amitié entre nos deux pays.

ንግግሩም ሲጨረስ ። ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ወደ ክቡር ሙሴ ዱሜርግ ቀርበው በእጆቻቸው ሰላምታ ሰጥተው የሹመት ወረቀታቸውን አስረከቡ ። ከዚያ በኋላ ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ተከታዮቻቸውን በየስማቸውና በየማዕርጋቸው እያቀረቡ አስተዋወቁ ። እንደዚሁም ክቡር ሙሴ ዱቀሚርግ መኳንንቶቻቸውን በየስማቸውና በየማዕርጋቸው እያቀረቡ አስተዋወቁ ። ቀጥሎም በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ተቀመጡ በዚያን ጊዜ መልካም የወዳጅነት ንግግር ከተነጋገሩ በኋላ ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው ተሰናብተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

የቤልጅክ ምኒስትር ወደ አዲስ አበባ እንደገቡ ።

በአዲስ አበባ የቤልጋርክ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የነበሩት ሙሴ ማክሲም ዤራር ወደ ሌላ አገር ስለተሾሙ ። የቤልጊክ ንጉሥ ግርማዊ አልቤር የተለየ መልክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርገው ክቡር ሙሴ ፍራንሲስ ዠንስንስን ሾመው ወደ አዲስ አበባ ስለ ላኩ ፤ ክቡር ሙሴ ፍራንሲስ ዠንስንስ የሹመት ወረቀታቸውን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በሰኔ ፯ ቀን ከጧቱ በ፬ ሰዓት ተኩል እንዲያስረክቡ ተቆርጦ ነበር ። በዚሁ ቀን ከጧቱ በ፬ ሰዓት ያገር ግዛት ሚኒስትር ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅና ፤ የውጭ ጉዳይ

ማዘጋጃ ቤት ፈረሰኞች አስከትለው ክቡር ሙሴ ፍራንሲስ ዣንሳን ለጊዜው ወደ ተቀመጡበት ደ ሆቴል ኢምፔሪያል ሔዱ ፤ ወደ ሆቴሉም በደረሱ ጊዜ ከክቡር ሙሴ ፍራንሲስ ዣንሳን ተገናኝተው ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ በአቶሞ ቢል ሆነው በፊትና በኋላ የክቡር ፈረሰኞች ተሰልፈው ወደ ቤተ መንግሥቱ መጡ ፤ ከቤተ መንግሥትም ከመጀመሪያው ከታላቁ በር ጀምሮ እስከ ታላቁ ቤተ መንግሥት ደረጃ ድረስ በመንገዱ ዳር ዳር በቀኝና በግራ የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ መኳንንቶችና ወታደሮች ተሰልፈው ነበር ። በቤተ መንግሥቱም ደረጃ አቅራቢያ በቀኝና በግራ የመንግሥት ዘበኞች ቆመው ነበሩና ሚኒስትሩ በዚያ በደረሱ ጊዜ የክብር ሰላምታ አቀረቡ ወደዚያውም ክቡር ሊጋባ ወዳጆ ሚኒስትሩን ተቀብለው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ፤ ግርማዊ ንጉሠ ወደሚጠብቁበት ወደ ታላቁ እልፍኝ አስገቡዋቸው ፤ በዚያውም ሥፍራ ታላላቁ መኳንንቶች የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ቆመው ነበር ። ክቡር የቤልጂክ ሚኒስትር ሙሴ ፍራንሲስ ዣንሳንም ሰላምታ እየሰጡ ወደ መንበረ መንግሥቱ ወደ ሚያወጣው ደረጃ በቀረቡ በደረሱ ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ ።

ግርማዊ ንጉሠ ሆይ ።

ክፍ ያሉ ንጉሬ ንጉሡ የተለየ መላክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርገው የሾሙበትን ደብዳቤና ከእኔ አስቀድሞ የነበሩት የታወቁ ሚኒስትር መቀረታቸውን የሚገልጹ ደብዳቤዎች ለግርማዊነታችሁ በማክበር አቀርባለሁ ።

ይህንንም ምክንያት አድርጌ የንጉሡን የጠበቀ ወዳጅነት የሚያረጋግጡትን ቃሎችና ፤ ደግሞ ለግርማዊነታችሁ ደስታ ለመንግሥታችሁም ልማት የሚመኙትን ከልብ የሆነ ምኞት ለማድረስ ፈቃድ ላገኝ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሠ ሆይ፡ እነዚህን አሳቦች ስገልጽ ትልቅ የሆነ አክብሮቴን ጨምሬ እናገር ዘንድ ፍቀዱልኝ ።

የምጀምረውንም የተላክሁበትንም ሥራ በምሠራበት ጊዜ የግርማዊነታችሁን በበጎ የተመላ እምነት በሚገባ ለማግኘት የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ ይህንም እምነት ባገኝና፤ድካሜም ከዚህ ቀድሞ በኢትዮጵያና በቤልጂክ መካከል የሚኖሩትን የወዳጅነትናየጥቅም ማስተሳሰሪዎች ለማጠንከር ቢረዳ፤ሰውነቴን የታደለ አድርጌ እቆጥረዋለሁ ።

ይህንም ቃል ተናግረው እንደጨረሱ የሹመት ወረቀታቸውን ለግርማዊ ንጉሠ አስረከቡ ። ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል መለሱ ።

ክቡር ሆይ ።

ግርማዊ የቤልጂክ ንጉሠ እርስዎን የተለየ መላክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርገው የሾሙበትንና ፤ ደግሞ ከእርስዎ በፊት የነበሩት የታወቁት ሚኒስትር መቀረታቸውን የሚገልጹትን ደብዳቤዎች ስንቀበል ፤ ለዚህ ሹመት በመመረጥዎ ደስ ብሎናል ።

ከእርስዎ በፊት የነበሩት ክቡር ሙሴ ዢራርም በኢትዮጵያ የግርማዊ የቤልጂክ ንጉሠ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆነው በተቀመጡበት ዘመን ፤ የሁለቱን መንግሥቶች ወዳጅነት ለማጽናትና የሁለቱንም አገሮች ጥቅም ለማስፋት ሲደክሙ እንደነበሩ ፤ እርስዎም ደግሞ በዚሁ አሳብ ተመርተው ሥራዎን ለማከናወን እንዲጥሩ አንጠራጠርም ።

ግርማዊ የቤልጂክ ንጉሠ ፈቃዳቸው ሆኖ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለእኔም ለራሴ መልካም ምኞታቸውንና የጠበቀ ወዳጅነታቸውን የሚገልጹትን ቃሎች እንደ ያደርሱ ስለ አዘዙዎ ፤ ግርማዊነታቸውን እያመሰገንን፤እኛም በወገናችን ለግርማዊነታቸው የምናቀርበውን ግልጥ የሆነ የወዳጅነት ምኞት እንዲያደርሱልን ፈቃድዎ ይሁን ዘንድ እንለምንዎታለን።

እርስዎም በኢትዮጵያ የግርማዊ ቤልጂክ ንጉሠ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆነው በሚቀመጡበት ጊዜ ሁሉ ከዚህ ቀድሞ በቤልጂክ መንግሥትና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ያለውን ወዳጅነትና የጥቅም ማስተሳሰሪዎች እያፀኑ ይሔዳሉ ብለን እናምናለን ።

ክቡር ሆይ ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በራሴም፤ በኢትዮጵያም ሕዝብ ስም ሆኜ ፤ ወደ አገራችን እንኳን ደህና ገቡ እያልሁ የወዳጅነት ምኞቴን አቀርብልዎታለሁ ።

ግርማዊ ንጉሠም ንግግራቸውን ሲጨርሱ መድፍ መተኮስ ጀመረ ወደ ዚያውም ክቡር የቤልጂክ ሚኒስትር ወደ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ወደ ግርማዊ ንጉሠ ቀርበው ሰላምታ ከቀረቡ በኋላ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ በዚያ የነበሩትን የኢትዮጵያ መኳንንቶች በየስማቸውና በየማዕርጋቸው አስተዋወቋቸው ። ክቡር ሙሴ ፍራንሲስ ዣንሳንም በተዘጋጀላቸው ወንበር ጥቂት ጊዜ ከተቀመጡ በኋላ ተሰናብተው እንደ ፊተኛው ታጅበው ወደ ሆቴል ኢምፔሪያል ተመለሱ ።

ማስታወቂያ ።

የግሪክ መንግሥት ቆንስል ጄኔራል ቤት ከጉለሌ ያለውን የሟቹ የፓናዮቲስ ኩምቢስን ሁለት ቦታዎች የርስት ወረቀት ያላቸው ያንድኛው የካርታ ቁጥር ፪ሺ፭፻፷፪ የሁለተኛው ፩ሺ፱፻፲፯ ቁጥር ያለው ። የመጀመሪያው የሥፋቱ ልክ ፳፬ሺ፱፻፵፭ አራት ማዕዘን የሁለተኛው ሥፋት ፴ሺ፭፻፹ አራት ማዕዘን ብዙ የባሕር ዛፍ የሞላባቸው በምንም ዕዳ ነገር የማይታሙ ነጻ የሆኑ በሐራጅ ይሸጣሉና እነዚሁን ቦታዎች ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ከ፲፱ ሰኔ አንስቶ እስከ ሐምሌ ፲፱ ድረስ ከቆንስላ ቤት መጥተው የሚገዙበትን ዋጋ እንዲያቀርቡ ያስታውቃል ።

የርስት ወረቀታቸውም ከግሪክ ቆንስላ ቤት ተቀምጧል ።

የግሪክ መንግሥት ቆንስላ ጀኔራል ቤት ።



ለስ ክቡር ንቡረ እድ አድማሱ እረፍት ።

ንቡረ እድ አድማሱ እውቀት ያላቸው ብልህ ሰው ነበሩ።ስለዚህም የኢዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ በመጀመሪያ ያቡነ ማቴዎስ ባልደረባ አደረጓቸው ቀጥሎም በካህን ላይ ቢትወደድ አድርገው ሾምዋቸው ።ኋላም ያዲስ አበባ ጊዮርጊስ ሹም ሁነው መልአከ ገነት ተብለው ነበር።ደግሞም ከ፲፱፻፯ ዓመተ ምሕረት ጀምረው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ባዲስ ዓለም ማርያም ንቡረ እድ ተብለው በክብረትና በመዐርግ ሲኖሩ አስቀድመው ባለቤታቸው ዓረፉና እርሳቸውም ከባለቤታቸው በኋላ አንድ ወር ያህል ቈይተው ሰኔ ፰ ቀን ከሌሊቱ በሶስት ሰዓት ዓርፈው ባዲስ ዓለም ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ። ብርሃንና ሰላም ለልጆቻቸውና ለዘመዶቻቸው ለቤተ ሰዎቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ፔር ዳኔይ ።

አበካት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርበስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



COGNAC SA.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገሩ ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሉንዶን ከተማ ነው ።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በየይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በየይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጊርጊሮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
5me ANNÉE № 26

ሐሙስ ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 27 JUIN 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አዋጅ ።

የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ከብዙ ቀን ጀምሮ እንደተመለከተውና እንደ መረመረው ከውጭ አገር እቃ የሚያስመጡ ብዙኅ ነጋዴዎች ይልቁንም የድርና የማግ የቱባው አከፋፈል በአንዳንዱ ቱባ ውሥጥ ሊገኝ ይገባ የነበረው ቍጥር ክር ስለ አነሰና ደግም የሚወጣው ጣቃ ጨርቅ ልኩ በዋር ወይም በሜትር ይኸነን ያህል ዋር ይኸነን ያህል ሜትር ተብሎ ይመጣ የነበረው ሁሉ ዕጥፋቱ የሐሰት ዕጥፋት፥ የሰው ማታለያ የሆነ ያርድና ሜትሩ ያልተጻፈበት ስለሚመጣ በዚህ ምክንያት የተነሣ ለጉምሩክ ሥራም ምርመራና ተመን ብዙኅ ሁውከት ሆነ።የዚህንም የማታለያ መንገድ መርምሮ ለማያውቀው ሕዝብ በግዢ ላይ ዋና ጉዳት ስለሆነበትና የማታለልን ሥራ የሚሠሩ ነጋዴዎችም እያታለሉ በመኖራቸው የሚያበረታቸው ነገር ስለሆነ በኢትዮጵያ ላሉ ነጋዴዎች ሁሉ ቀጥሎ የተጻፈውን እናስታውቃለን ።

መጀመሪ ስለ ድርና ማግ

በአንዱ ቱባ ውሥጥ መገኘት የሚገባው የቍጥር ክር የሌለበት የክሩ ቍጥር እያነሰ የተከፋፈለ ቱባ ድርና ማግ ወደ

ዓሥር ነጥር የሚመዝን የፈትል ጥቅል ንምሬ ፳ ፳ ቱባ እንዲገኝበት ያስፈልጋል
" " " " " " ፴-፴ " " "
" " " " " " ፴፪-፴፪ " "
" " " " " " ፹-፹ " "
፫ት " " " " ፴-፷ " "
፹-፴

ላሥር ንምሬ ፈትል ብቻ እንደተለመደው ፓኬው ዓሥር ነጥር ሁኖ ሀያ ቱባ እንዲገኝበት ተፈቅድዋል። ፓኬው እንደ ደንቡ ክምስት ወይም ካሥር ነጥር በታች የሆነ እንደሆነ እንደ ሚዛኑ ማነስ የቱባውም ቍጥር በሒሳቡ ያነሰ ይሆናል (ማለት) ፴ ንምሬ ፓኬው ዘጠኝ ነጥር የመዘነ እንደሆነ የቱባው ቍጥር ፲፰ ይሆናል እንጂ አይበልጥም፤ ሚዛኑ ስምንት ነጥር የሆነም እንደሆነ ባንዱ ጥቅል ውሥጥ የቱባው ቍጥር ፲፮ ብቻ መሆን ይገባዋል ።

እንደዚሁ ሚዛኑ ሲአንስ በመጠኑ እንደሒሳቡ ቱባው ማነስ ግዴታ አለበት፤ ክምስት ነጥር በላይ እስከ ዓሥር ነጥር ለሚመዝነው ፓኬት ሁሉ የጉምሩኩን ቀረጥ በዓሥር ነጥር ፓኬት ሒሳብ ይከፍላል።

ሁለተኛ ስለማናቸውም የጨርቅ ዓይነትና የሐር ጨርቅም።

ነጭ ሁኖ እየተጠቀለለ ከሚመጣው ጣቃ በተቀር የቀረው ጣቃ ሁሉ በያርድ፥ ወይም በሜትር ልክ መታጠፍ ይገባዋል። እየጣቃውም ላይ ሁሉ የርዝመቱ ልክ በደኅና እንደሚታይ ተደርጎ ያርዱ ወይም ሜትሩ ይጻፍበታል ። ይህም የርዝመት ልክ በክብ ተጠቅልሎ ለሚመጣው ጣቃ ሁሉ ላይ ሜትሩ ወይም ያርዱ ይጻፍበታል ።ማናቸውም ዓይነት ጨርቅ ሁሉ የርዝመቱ ልክ የማይታወቅ ላፕስ፥ወይም ፋልድ (Laps ou Falde)

ይህም ደምብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ዓሥር ቀን ድረስ ለነጋዴዎች ጊዜ ተሰጥቷል ።

ይህም ዓሥር ቀን ጊዜ የተሰጠበት ምክንያት ከዚህ ቀደም በዚህ አዋጅ የተከለከለውን እቃ ዓይነት ለማስመጣት የተዋዋሉና የተስማሙ ነጋዴዎች እንዳሉ ከዚህ ቀን በፊት መዋዋላቸውንና መስማማታቸውን የሚያስረዳ የቃውን ቊጥርና ዓይነት በዝርዝር የተጻፈ ወረቀታቸውን ሁሉ ለጉምሩክ ማቅረብ ግዴታ አለባቸው።እነኝህንም የቃው ቊጥር በዝርዝር የተጻፈባቸውን ወረቀቶች ጉምሩክ የሚቀበለው እቃውን ለማስመጣት የተስማሙበትን ከንትራትና የተጻጻፉትን እውነተኛ የሆነ ወረቀት አብሮ እንዲገኝ ያስፈልጋል።በዚህ በተሰጠው ቀን ውሥጥ ለማስመጣት የፈለገ ሰው ወይም በዚህ ዐሥር ቀን ውሥጥ የሚያስፈልገውን የምስክር ወረቀት ለጉምሩክ አሳይቶ ያላጻፈ ነጋዴ ሁሉ ከሳራውን ለመጠየቅ የማይችል ነው።ተጻፈ አዲስ አበባ ሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።

ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ገብረ እግዚአብሔር።

የከብት ሐኪም ማስታወሻ

በአዲስ አበባ ውሥጥና በሙሉ ኢትዮጵያ

የውሻ በሽታና ዋና የጤንነት ጉዳይ።

የውሻ በሽታ በኢትዮጵያ ውሥጥ፤ ይልቁንም በአዲስ አበባ ከተማ አደገኛ የሆነ በሽታ ሁኖዋል ።በየወሩም በሕዝቡ መሐከል በዚሁ በውሻ አደጋ የተነካ ብዙዎቹ ወደ ሐኪም ይሔዳሉ። ይልቁንም ከሕዝቡ መሐከል ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ብዙ ሰዎች አደጋ ያገኛቸዋል ።

መጀመሪያ፤ ይኸውም በሽታ ውሻ ከነከሳቸው ጋር አለመገናኘት ነው፤ ቢገናኙም መድኃኒት ወደሚያደርግላቸው ሐኪም መሔድ ነው፤ደግሞ ከቤታቸው ያሉት ውሾች ቢታመሙ አለመጠጋት ነው።

ሁለተኛ፤ በሚሻል ዓይነት መድኃኒት መከላከል ነው፤ይኸውም አሁን የሚደረገው መድኃኒት በዛሬው ዘመን የሕክምና ሥራ ያልተመረመረና ያልታወቀ ነው፤ ይኸውም መድኃኒት በሽተኛ የሆነው ውሻ ለነከሳቸው ሰዎች የሚያደርጉት ነው።ስለዚህ ጤነኛ ወይም በሽተኛ የሆነ ውሻ ሲነክሳቸው ይህነን መድኃኒት ያደርጋሉና ሕዝቡ በለማወቅ የሚያድን መድኃኒት እየመሰላቸው ብዙ ሰዎች በዚሁ በሽታ አደጋ ያገኛቸዋል ።

ሦስተኛ፤ እግዚአብሔር ሰዎች ራሳቸውን ከሚያገኛቸው አደጋ የሚከላከሉበትን ያልሰጠ ይመስል እግዚአብሔር ያውቃል እያሉ በመተዋቸው ነው ።

አንደኛ፤ ሰው መናከስ የጀመረውን ውሻ፤ ወይም ከቤታቸው ያለውንም ውሻ ቢሆን የሕመም ዓይነት ባዩበት ጊዜ አለመንካትና አለመጠጋት ነው ።

ለዚሁም ሁለት ዓይነት የውሻ በሽታ አለ።አንደኛው፤በሽታ፤ ውሻው የዕብደት ምልክት ሳይኖርበት (ሳይናከስ ሳያለቅስ)በዝምታ ባለቤቱ እንኳን ውሻው መታመሙን ሳይረዳው የሚያስተላልፍ ነው።ይህነንም አንዳንድ ሰዎች አስቀድመው ለከብት ሐኪም ሳያሳዩ የጉሎ ዘይት ያጠጡዋቸዋል፤ ወይም ሌላ ዓይነት መድኃኒት ያደርጉላቸዋል።ውሻውም ከሕመሙ ፅናት የተነሣ ጉሮሮው ተዘግቶ የሚሰጡትን መድኃኒት ለመዋጥ አይሆንለትም።ስለዚህ ባለቤቱ በግድ ለማጠጣት ሲይዘው ውሻው ይነክሰዋል፤ወይም ይተፋበታል፤ በዚሁ የተነካ በሽታው መዘዋወሩን ይጀምራል፤ ውሻውም የዕብደት ምልክት ሳያሳይ በጸጥታ ይሞታል፤ ሕዝቡም ቢሆን የዝምታ በሽታ መኖሩን ባለማወቃቸው በዚህ በሽታ የተነካ እውነተኛ አደጋ ያገኛቸዋል። ይኸውም አደጋ ሁልጊዜ ውሾች ባሉዋቸው ሰዎች ላይ ይደረጋል ።

ሁለተኛው ዓይነት ግን የሚያስፈራና ከፊተኛው ሦስት ጊዜ ልዩነት ያለው ነው።ይኸውም ሲጀምረው ድካምና ዝምታ ያሳድርበታል፤ ከዚያ በኋላ ግን የአውሬነትና የዕብደት ምልክት ይታይበታል ። (ማልቀስ ፥ እሰው ላይ መውደቅ ፥ መናከስ ነው)

የሚበዙትም ሰዎች ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የሚደርስባቸው ይገኛሉ ። እስከዚህ ድረስ ስለ እውነተኛው የውሻ በሽታ ተናገርኩ። ደግሞ በመርዝና በመድኃኒት የተነካ አንጎላቸው እየጠፋ እንደተሰበ በሽታ ሁኖ እንደዚያው ያሳብዳቸዋል ።

እነዚሁም በድንገት ሰው የነከሱ እንደሆነ ሰዎች እያበረሩ በዱላ፤ ወይም በድንጋይ ይገድሏቸዋል።እነዚህም ውሾች በከብት ሐኪም አልተመረመሩምና የተነከሱት ሰዎች ሐሳባቸውን ዕብድ ውሻ እንደነከሳቸው ሁሉ አድርገው ብዙ ገንዘብ የሚፈጀውን ሕክምና ይታከማሉ ።

፪ኛ፤ ማናቸውንም ያልታወቀ መድኃኒት ማድረግ፤ ይልቁንም በኢትዮጵያ በሽተኛ ውሻ የነከሳቸውን ሰዎች በሥር በአበበ በቅጠልና በሌላም መድኃኒት፤ወይም በበሽተኛው ውሻ ሐሞት የሚያክሙ አሉ ። ነገር ግን ከዚህ በላይ የተነገሩት መድኃኒቶች በውነተኛው የውሻ በሽታ አደጋ ምንም ጥቅም አላደረጉልንም፤ስለዚህ ከማናቸውም ሰዎች ዕውቀት የሕክምና ቤት ያደረገው የሚሻል ይሆናል።የሕክምና ቤት የውሻን፤ ወይም የሌላውን ከብት በሽታ ከመረመረ በኋላ ብዙ መድኃኒት ሞክሮዋል፤የሀገሩ ሰዎች መድኃኒት ግን የሚያድን አይደለም።

ከዚህም በቀር አሁን በቅርቡ አንድ ሰው በዚሁ በሽታ ታሞ ያንዱን ሰው መድኃኒት ጠጥቶ የማያድነው ሁኖ ስለሞተ ያገሩ ሰዎች መድኃኒት በዋናው አደጋ ጊዜ ምንም የማይጠቅም መሆኑን ተረድተነዋል ።

፫ኛ፤ ማናቸውንም ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ያውቃል መተው፤

እዚህ በእግዚአብሔር መተውን ዋና ነገር አይደለም ለማለት አልፈቅድም።ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ከእንስሳ ለይቶ ሐሳብንና ዕውቀትን ሰጥቶ፤ክፉን፥ ደጉን ለመለየት እንዲያውቅ አድርጎ ነውና የፈጠረው ስለዚህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይዘን እኛው ራሳችን ለራሳችን ማሰብ የሚገባን ነው ።

ስለዚህ በጭሩ አድርጌ ቀጥሎ እንደተጻፈው አስታውቃለሁ ። ለውሻ በሽታና ላደጋውም ሁሉ የሚያድነውና የሚሻለው ነገር ምንድር ነው? በከተማው ውሥጥ የውሻ በሽታና እሱንም የሚመስለው ነገር ሁሉ እየበዛ ስለሔደ፤ የቤት ውሾች

የሚያጠራጥሩ ሲሆን ወደ ከብት ሐኪም አምጥቶ ማስመርመር የሚሻል ነው ። በየመንገዱ ሰው የሚነክሱትን ውሾች ግን ስለጤንነታው ለመረዳት ከነነፍሱ ለመያዝ የሚቻል የሆነ እንደሆነ ከነነፍሱ ይዞ ለመያዝ የሚቻል እንደሆነ ግን ራሳውን ለከብት ኃኪም አስመርምሩችሁ አኳኋኑን ከነገራችሁ በኋላ የሚያስፈልገውን ለማድረግ ትችላላችሁ። ነገሩን ከተረዳችሁት ኋላ ስለጤንነታችሁ አሁን በሙሴ ፕሮባንሳል እጅ የሚገኘውን የክትባት መድኃኒት ለማድረግ ጊዜ አይወስድባችሁም። ይኸውም ዶክተር ፕሮባንሳል አዲስ አበባ ላይ ለዚሁ በሽታ ማከሚያ ቤት በማቆሙ ለኢትዮጵያ ትልቅ ውለታ ሠርቶአል። ደግሞ ለዚሁ ነገር በየመንገዱ የሚዞሩትን ውሾች ለማጥፋት የዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ጀምሮአልና እንደዚሁ ያደጋ መሠረት የሚሆኑትን ውሾች ጨርሶ እንዲያጠፉ ተስፋ አደርጋለሁ።

የርሻ ሚኒስቴር የከብት ሐኪም ።

ሚሀሬን ከይማኪያን ።

ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር ሰው አንዳች ነገር ሊያደርግ አይችልም

የዶክቶር ገብሬሎፍን ነገር ባለፈው ሳምንት በብርሃንና ሰላም ስላነበብሁት በመጽሐፈ አስቴር ከተጻፉት ቃላት ሁለት ነገሮች ትዝ አሉኝ ። አንደኛው ንጉሡን አሕሻዊሮስን ለማጥፋት መክረው የነበሩትን ሰዎች የተንኰል ምሥጢራቸውን አውቆ፥በፈቃደ እግዚአብሔር መርዶክዮስ ንጉሡን አሕሻዊሮስን ከክፉ ነገር ማዳኑ ነው ። አስቴር ምዕ ፪ ቍ ፳፩ ከምዕ ፮ ምዕ ፲።

ሁለተኛው ሐማ ሊያጠፋቸው ቈርጥ አድርጎ የመከረባቸውን መርዶክዮስንና ወገኖቹን ሁሉ አስቴር ለንጉሡ ነግራ በፈቃደ እግዚአብሔር የማዳንዋ ነገር ነው ። እንደዚሁም ሕዝበ ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ከጸላቶቻችን የሚያድነንን ፈጣሪያችንን እያመሰገን ሁል ጊዜ እጃችንን ወደ እግዚአብሔር ለጸሎት መዘርጋት ነው።አሁንም ይህ ነገር ስላነሣሣኝ ይህን የጻፍኩትን መወድስ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ባለመሰልቸት እንድትመለከቱት በማክበር እለምናችኋለሁ ። ማለት ዶክቶር ገብሬሎፍ የሠራብን ሥራ ሕዝበ ኢትዮጵያን ሁሉ የሚያሳዝን ነገር ነውና ።

መወድስ ።

ሕገ ፈጣሬ ተሥዕረ በሕገ ፍጡር፡ በጽሉ ፈጣሬ ንጉሥ
ዘተጽሕፈ ትእዛዘ ቃል
እምከመ ይቤዞ ሰብአ ፍዳ ዘይቤ ኢትቅትል ለ
በቀይሐ ባሕርይ ቀለመ ወርቅ
አምጣነ ተጽሕፈ ሕገ ሰብአ ዘይብል
ቅትል ወእኅጉል
ባሕቱ በብእሲ ፍጡር ተሥዕሮተ ሕግ ኢይትከሀል
እምትኅልፍ ኢትዮጵያ አሪተ ዘውዲቱ አክሊል
ዘተጽሕፈቶ በአዕባዕቱ ለኃይለ ሥላሴ አበ ጠቅልል
ኅልፈተ ሰማይ ወምድር ከመ ይቀልል
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያ አምጣነ ዜነወነ በወንጌል
አለቃ [illegible]

በ፪፻፵፱ ቁጥር በ፫ኛ ዓመት አእምሮ ጋዜጣ ለብርሃንና ሰላም ስለ ተጻፈው ወቀሳ መልስ።

ብርሃንና ሰላም ፩ኛ ዓመት ፱ ቁጥር በጋዜጣ ሊታተም ሐሳባቸውን ጽፈው ለሚልኩ ሰዎች ሁሉ ማስታወቂያ አውጥቷል ። ይኸም ብርሃንና ሰላምን የወቀሰ ሰው ብዙ ጊዜ እየጻፈ ልኮ ሳይታተምለት አልቀረም ። ነገር ግን ከዚያ ከላከው ውሥጥ ብዙው አማሬኛው ለሰው የማይገባና ላንባቢ የሚያስቸግር የተሳከረ ስለሆነ፥ወይም በሌላ ምክንያት ሳይታተም ቀርቶ ይሆናል ። ብርሃንና ሰላምም ተጽፎ የመጣለትን ቃል እየመረመረ የሚያስፈልገውንና የተሻለውን ያትማል ጥሩ ቃል እንኳ ቢሆን ለጊዜው የማይስማማ መስሎ የታየውን እስከጊዜው ድረስ ማቈየቱ አይቀርም ።

አንዳንድ ሰዎችም የማይረባውን ነገር ተባትበው አምጥተው ካድ ካልታተመልን ብለው ያስቸግራሉ ፤ መቼም እንዳይታተም ላንባቢው ግራ የሚያገባ ለሰሚውም ደስ የማያሰኝ ነውና በግድ ይቀራል ። የማይሆን መሆኑንም ቢያስታውቋቸው ጉድለታቸውን እያውቁትም ና የባሰ አምባጓሮ ይፈልጋሉ ።ስለዚህ በስፈለገ ጊዜ ይታተማል የሚል ምላሽ ያገኙ ይሆናል ።

ይኸም ሰውዬ እንደዚህ ካሉት ሰዎች አንዱ ይሆናል እንጂ በደግነው እንዲህ አልጻፈም ።

እውነተኞች ጸሐፊዎች ግን ሳይታተም የቀረባቸው እንደሆነ ለጊዜው የማያስፈልግ መስሎ ቢታየው ነው ያስቀረው ብለው ሌላ መልክም ቃል ይጽፋሉ እንጂ እንዳላዋቂዎች ሁሉ ለምን ቀረብን እያሉ ፀብ አይፈልጉም። አላዋቂዎች ግን ከነሱ ሌላ አዋቂ ያለ አይመስላቸውምና የሆነም ቢሆን የኛ ሐሳብ ለምን ሳይታተም ይቀራል እያሉ ያስቸግራሉ ጠብም ይፈልጋሉ። ይህ ግን ደግአይደለም ። ይኸ ሰው ሐሚቱን ነውና የገለጠው በመጽሐፈ ምሳሌ ም ፲ ቍ ፲፰ ። ያለውን ቃል ይመልከት ።

ብርሃንና ሰላም ያልሆነውንና ለጊዜው የማያስፈልገውን ለይቶ እያስቀረ ፤ ደኅናውንና የሚያስፈልገውን እየመረጠ ማተሙ እርግጥ ነው ይኸም ያስመሰግነዋል እንጂ አያስነቅፈውም ። ለምን ቀረብን የሚሉም ብርሃንና ሰላምን ከማማት ይልቅ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ማስታወቂያውን ማስተዋል ይበልጣል ።

አሁንም አእምሮ ጋዜጣ ይኸን ተቀብሎ ማተሙ ብርሃንና ሰላምን እቃወማለሁ ብሎ አይደለም ። አእምሮና ብርሃንና ሰላም አብረው በስምምነት የሚሠሩ ናቸው እንጂ ተቃራኒዎች አይደሉምና ግን ይህ ሰው ያሰበው ሁለቱን ለማቀያየም ነውና ይኸ ምንም ቢሆን አይሆንለትም ። አእምሮ እርሱ ያሰበውንና የጻፈውን ተቀብሎ ማተሙ ስለ ነፃነቱ ነው እንጂ ለብርሃንና ሰላም መቃወም መሆኑ አስበበት ቢሆንስ እንዳያትመው እናምናለን ።

ቀጥሎ ስለ ምንዛሬ በተጻው ላይ ያለ ስሕተት ።

ስለ ምንዛሬ ነገርም ጽፏል ። ባገር ውሥጥ ያለውን ገንዘብ አውቆ በኋላ የምንዛሬውን ነገር ቢጽፉ አይከፋም ።

የተቀረፀውን ብር አለማወቅ እጅግ ያስደንቃል ። በዳግማዊ ምኒልክ መልክ ተቀርፆ የተሠራው ብር መኖሩን ያላወቀ ሰው ከብርሃንና ሰላም ጋራ መዋቀስ አያስፈልገውም ነበር ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ስለ ከፋ አውራጃ አገዛዝ ።

የከፋ አውራጃ ገገር በከፋ ውሥጥ ያሉ ከተሞች እንደ ረቻና ሸረዳ የሚባሉ ከተሞች አሉ፤ለከፋ አውራጃ ገጋር የታዘዙትን ግብር ወደከተማው የሚአገቡ ባላገሮች የ፪ቀንም የ፫ቀንም መንገድ ራቅ ያሉ አሉ።ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ተሐዱ ጀምሮ በየመንገዱ ሌባ እየበረታባቸው ባላገሮቹ አለ ዘበኛ ግብራቸውን ወደከተማ ለማምጣት አይሆንላቸውም ነበር።አሁን ግን ክቡር ደጃዝማች ደስታ ተገቡ አገሩ ሰላም ሁኖ ገባሮቹም አለ ዘበኞች ግብራቸውን ይዘው ከከተማው ድረስ ገቡ። ሴቲም ባሏን ምስለኔው ቢአሥረው የሦስት ቀን መንገድ ብቻዋን ወጥታ ጮሀ አስፈታችው ። ጥንት ሌባው ከቤት እየሰበረ ከብት ይወስድ የነበረው ከብቱ ከበረት እየጠፋ ከሜዳ እያደረ ይገኛል አሉ። ፪ኛ በግብር ጥናት በሌባ ምክንያት የተሰደድህ በየባትህ ርስት ግባ የመልከኛህን ግብር እኔ እከፍላለሁ ብለው አዋጅ ነግረው ገባሩም ተሞተና ሩቅ አገር ከሔደ በተቀር በየባቱ እርስት ገባ የመልከኛውን ግብር ክቡር ደጃዝማች ደስታ ይከፍላሉ። እሳቸው ዕድሜአቸው ቆይቶ በከፋ ሀገር ከሰነበቱልን አገሩ ለምቶ በዕንጨት እንጣላ እንደሆን ነው እንጂ ገባሩን መልከኛው ማጉላላት ፤ ሌባ ከብታችንን መውሰድ አለብን ብለን አንጠረጥርም። ፫ኛ ድሀው እንዳይበደል ዳኝነት አላድ የስማ በለው ሁለት መሐለቅ አርገውልናል ። አዲስ ለገባ ገበር የላምና የበሬ መግዣ ሰጥተውታል ብለው በገሩ ላይ ያሉ መኳንንቶችና ነጋዴዎች ባላገሮች ቢነግሩኝ የዳኝነታቸውን ዕናት፤ የሰውነታቸውን ደግነት እንድታውቁት ብዬ ጽፌአለሁ ። ይቸገር የነበር በሌባ ጤት ማታ ዓለሙን አየ አሉ ከፋ በደስታ ። ከፋን ጣዛ ብለው ንጉሥ ቢሰዱት ። የገባሮች ገበር ሁኖ አገኙሁት ። ደጃዝማች ደስታ ጌታ ነው እያሉ ። የሰው አሳላፊ አዳይ ሆኑአል አሉ ። የከፋ መኳንንት ጠጅም አያምራችሁ ። ደስታ አሳላፊው እሱ ታለላችሁ ። የከፋ ገባሮች እንዴት ተመቻችሁ ። እናንተ ከርታታችሁ ንጋሮ አሥገበራችሁ ። ከፋ በሕር ገቡዩ ሲጨንቅ ሲጠበብ ። ተፈሬ አባ ጠቅል አዳነው በመርከብ ።

መሐሬ ረታ ።

ቃለ በረከት ዘአበው ኤጲስ ቆጶሳት ።

ዘወትር ቅጆችዋን ዘርዓታ ወደ እግዚአብሔር የምትለምን ብፅዕት ማራ ይስሐቅን ወልዳለችና ።

ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ ።
አክሊለ መስቀል ምክሕነ እስመ ለዓለም አብርሃ ።
ኃይለ ሥላሴ ንጉሥነ በጽሐ ።
ዮም ለኢትዮጵያ ንዜኑ ፍስሐ ።
ኢሳይያስ አክሊለ መንግሥት እመ በእንቲአኪ ፀርሐ ።
እንዘ ይብል አብርሂ አብርሂ ተፈሥሒ ኢትዮጵያ ሀገረ ብዙኅ ንስሐ ።
እስመ ፈርዖን ቃለ ግዝትኪ ውስተ ባሕር ተነፅኅ ።
ዮም ለኢትዮጵያ ንዜ ፍሥሐ ።
ለዘመነ መንግሥትከ ጴጥሮስ፥ወአብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ወሚካኤል ከንዋ አርአያነ
ንጊሥ ኅቤነ ወኢንርኅቅ እምኔነ ።
እስመ ኃይለ ሥላሴ ላዕሌነ ።
ዮም ለኢትዮጵ ንዜኑ ፍሥሐ ።
እስመ ኮነ ብርሃነ ወጸብሐ ።
ስብሐት ለአብ ኪያከ ዘፈጠረ ለነ ።
ስብሐት ለወልድ አክሊለ መንግሥትከ ዘአርአየነ ።
ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ልብሰ መንግሥትከ ኃይልነ ወፀወንነ ።

አባ ተስፋ ሚካኤል ከ ሠ ።

የከተማ ወሬ ።

በዚህ ሰሙን አዲስ የተሾሙት ጳጳሳት ይገባሉ ተብሎ ስለ ተወራ የከተማው ሰው የጳጳሳቱን አቀባበል ለማየት በደስታና በናፍቆት ይጠባበቃል ።

ይልቁንም በቤተ ክህነቶቹ በጳጳሳት አቀባበል የሚወረብ ግሥ ያሳናዳሉ።አዲስ አበባም ጳጳሳቱ በደኅና እንዲገቡ እየተመኘች ያማረ የጳጳሳት አቀባበል እንድታይ ትጓጓለች ።

መንግሥት ሊያዝንላቸው የሚገባ ።

መጀመሪያ፤ በቀን ከአንድ ሩብ የበለጠ ሊያገኙ የማይችሉ ዶንጊያ ሲፈልጡና መሬት ሲቆፍሩ፥አፈር ሲግፉ፥ በየቤቱም እየገቡ አዘብ ሲዝቁ የሚውሉት ሠራተኞች።ሁለተኛ ፤ ለጨኸት፥ወይም ለሌላ ጉዳይ፥ወይም ደግሞ ግብርን ለመስጠት ከአገር ቤት ወደ ከተማ የሚመጡ ሰዎች ሽጠው ስንቅ ለማድረግ አንዳንድ መአዘን፥ወይም እንጨት፥ በጭንቅላታቸው እየተሸከሙ የሚመጡት፥ሦስተኛ ምንም ምን የሌላት ሴትኛ አዳሪ ባልቴት ዶቄት በሩብ፥ ወይም በአላድ ሸምታ ምናልባት አንድ፥ወይም ሁለት መሐለቅ ቢተርፋት ያነኑ ጋግራ ጉበያ ወስዳ የምትሸጥ፥ እነዚህንም የሚመስሉትን ኣንዳንድ ሠርቶ በላ ድኃዎች ቀረጥ አምጡ እየተባሉ በየመንገዱ በፈታሽ እጅ ሲጉተቱ እናያለን።

ስለዚህም እነዚህ ከላይ የተጻፉት ሰዎች በዚሁ ሥራቸው የጊዜውን ችግርና የሽመታውን መወደድ ብንመለከተው ከዕለት ምግባቸው አልፎ ሌላ ትርፍ እንዳያገኙ እርግጥ ነውና አዛኙና ርኅሩኁ መንግሥታችን በቸርነቱ ቢጐበኛቸው መልካም ሳይሆን አይቀርም ።

ከኢጣልያን ሌጋሲዮን የመጣ ራድዮ የሰኔ ፲፬ቀን የዕለት ወሬ

እለ እስክንድርያ(ግብፅ)። ዓሥራስድስት የሚያህሉ የኢጣልያ መርከቦች ደረሱናለሕዝቡ የሚያስደንቅ ማየት ሆነለት።ሕዝቡና የመንግሥት ሰዎችም ለመርከቡ መኳንንቶችና ለመርከቡ ሠራዊት ደስ በሚያሰኝ አቀባበል ተቀበልዋቸው ።

በርሊን ስትሬስማንና ብርያንድ ጥዋንካሬም በፓሪስ ስለ ተገናኙ የጀርመን ጋዜጦች የጀርመንን አዲስ ፖሊቲክ ነው እያሉ ፈልስመው ይራቀቁበታል ።

ፔር ዳኔይ ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ጸሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

የግሪክ መንግሥት ቆንስል ጀኔራል ቤት ከጉለሌ ያለውን የሚቺው የፓናዮቲስ ኩምቢስን ሁለት ቦታዎች የርስት ወረቀት ያላቸው ያንድኛው የካርታ ቁጥር ፪ሺ፫፻፹፪ የሁለተኛው ፩ሺ፱፻፲፯ ቁጥር ያለው ። የመጀመሪያው የሥፋቱ ልክ ፳፬ሺ፱፻፺፫ አራት ማዕዘን የሁለተኛው ሥፋት ፬ሺ፫፻፹ አራት ማዕዘን ብዙ የባሕር ዛፍ የሞላባቸው በምንም ዕዳ ነገር የማይታሙ ነጻ የሆኑ በሐራጅ ይሸጣሉና እነዚሁን ቦታዎች ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ከ፲፪ ሰኔ አንስቶ እስከ ሐምሌ ፲፪ ድረስ ከቆንስላ ቤት መጥተው የሚገዙበትን ዋጋ እንዲያቀርቡ ያስታውቃል ።

የርስት ወረቀታቸውም ከግሪክ ቆንስላ ቤት ተቀምጧል ።

የግሪክ መንግሥት ቆንስላ ጀኔራል ቤት ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም እምበር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና የሚረክስ ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል “አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻ ነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንደን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።



ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፓሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፓሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔሬቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ አዲቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጆማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሴ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሴ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሆኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሴን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሴ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሴ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሴ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሔዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
5me ANNÉE № 27

ሐሙስ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 4 JUILLET 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ በለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሊቀ ጳጳሳቱና የጳጳሳቱ አቀባበል ።

ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ ከምድረ ግብፅ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ እነርሱን አሹመው ለመመለስ ተልከው የሔዱት የገንዘብ ምንስትር ክቡር በጅሮንድ ዘለቀና የትምሀርት ሚኒስቴር ዲሬክተር ክቡር አቶ ማህሉ ፀዳሉ አልተለዩዋቸውም ነበር ።

ከአዲስ አበባም የካህናቱ ባልደረባ ክቡር መልአከ ገነት ወልደ ሐና ፤ አለቃ ወልደ ተክሌ፡ አለቃ ወልደ ትንሣኤ፡ ጳጳሳቱን ለመቀበል ታዘው እስከ ድሬ ዳዋ ወርደው ነበር ።

በድሬ ደዋም የሐረርና የውራጃዋ ሁሉ እንደራሴ ክቡር ደጃዝማች እምሩ በታላቅ ክብር ተቀበልዋቸው ።

ደግሞ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ማኒስቴር ዋና ዲሬክተር ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ እስከ ሞጆ ወርደው እንዲቀበሉ ታዘው ነበርና ከሞጆ ጀምሮ በየባቡሩ መቆሚያው የክብር አቀባበል እየተደረገላቸው ወደ ማታ በ፲ ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ ደረሱ።

በፕሮግራሙ እንደ ተመለከተው በሰኔ ፳፩ ቀን በባቡር ማረፊያ ለሊቀ ጳጳሳቱና ለጳጳሳቱ መቀበያ የሚሆን ግምጃ ድንኳን ተተክሎ በውስጡ ያማረያማረ ምንጣፍ እየተነጠፈበት ጌጠኛ ጌጠኛ ወምበርም ተደርድሮበት ነበር ። በድንኳኑና በብረት መንገዱም መካከል ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ ከባቡሩ ወርደው ወደ ድንኳኑ የሚገቡበት መተላለፊያ ሳንቃ ተዘርግቶ ግምጃ ተነጥፎበት ነበር ። ጣራውና ግድግዳውም በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተጊጦ ነበረ ። በሰገነቱ ግራና ቀኝም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተተክሎ ይውለበለብ ነበረ ። ዘጠኝ ሰዓትም ሲሆን ሠራዊቱ ሁሉ ወደ ባቡር ማረፊያ እንደ ጎርፍ ይወርድ ርደ ድምፃቸው እንማያቋርጥ ነጐድጓድ ሆነ ። ሠራዊቱም በባቡሩ ማረፊያ ተሰበሰበና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ወደ ባቡሩ ማረፊያ ለመምጣት መነሣታቸው በተሰማ ጊዜ ክቡር ሊጋባ ወዳጆና ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያም ከቀኛዝማች ክልክሉም ከተከታዮቻቸው ጋራ ሠራዊቱን በመንገዱ ግራና ቀኝ በሥርዓት አሰለፉት ። ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ በክብር ዘበኛ ታጅበው ወደ ባቡር ማረፊያ ወርደው በድንኳኑ ውስጥ አምሮ በተሰናዳው ዙፋናቸው ላይ ተቀመጡ ።

በዓሥራ አንድ ሰዓትም ተኩል ባቡሩ ገባና ግርማዊ ንጉሥ ሊቀ ጳጳሳቱንና ጳጳሳቱን ለመቀበል ቀረቡ ። ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱም ከባቡር እየወረዱ ከግርማዊ ንጉሥ ጋራ ተገናኝተው የቡራኬ ሰላምታቸውን ሰጡ። ከዚህም በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ። በወንበር በተቀመጡ ጊዜ ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱም እንደየመዓርጋቸው በግርማዊ ንጉሥ በስተቀኝ ተቀመጡ ። በስተግራም በኩል ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስና የኢትዮጵያ መኳንንት ተቀመጡ ። ወዲያውም ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተነሥተው ወደ ሊቀ ጳጳሳቱና ወደ ጳጳሳቱ ቀርበው የደኅና መምጣታቸውን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ንግግር ተናገሩ ። ሊቀ ጳጳሳቱም የምስጋና ቃል ተናግረው ባርከው አሰረጉ።

ከንግግሩም በኋላ መኳንንቱና ሊቃውንቱ እንደየመዓርጋቸው እየቀረቡ ከሊቀ ጳጳሳቱና ከጳጳሳቱ ቡራኬ ተቀበሉ። ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ በአቶሞቢል እየሆኑ ለማረፊያ ወደ ተሰናዳላቸው ቤት ሔዱ። ግርማዊ ንጉሥም ወደ ቤታቸው ተመለሱ ። የዓጀቡ ብዛትና የሰልፉም ማማር እጅግ ያስደንቅ ነበር ።

ሰኔም ፳፪ ቀን በሦስት ሰዓት ተኩል ከየአድባራቱ የመጡ አክሊል የደፉ ካህናትና መስቀል የያዙ ዲያቆናት የሚያንጸባርቅ

ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ ባሉበት ቤት ደጃፍ ከመንገዱ ዳር ዳር ተሰልፈው ቆሙ ። የመንግሥት መለከትና እምቢልታ ነፊዎች ነጋሪት መችዎችም ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ እስኪወጡ ከውጭ ሁነው ይጠባበቁ ነበር።ለሊቀ ጳጳሳቱና ለጳጳሳቱም በላይ በኩል ግልጥ የሆኑ አቶሞቢሎች ተሰናድተው ቀረቡ ።

፱ ሰዓት ሲሆንም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ለሊቀ ጳጳሳቱና ለጳጳሳቱመበቀያ በተሰናዳውስፍራ ሒደው በዙፋናቸው ተቀመጡ። በዓሉንም ለማየት የተጠሩ የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎችና ሌሎችም ትልልቆች ሰዎች ወደቤተ መንግሥት መጥተው በተዘጋጀላቸው ወንበር ተቀመጡ

በ፲ ሰዓት ተሩብ ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ በተሰናዳላቸው አቶሞቢል ተቀምጠው ጕዞ በተጀመረ ጊዜ መለከቱ ያቅራራ፥ እምቢልታው ይነፋ፥ ነጋሪቱ ይጐሰም ጀመር ። ከሊቀ ጳጳሳቱ ባር እስከ ቤተ መንግሥቱ ድረስም ኍልቍ ስፍር የሌለው ሠራዊት በመንገዱ ግራና ቀኝ ሰልፉን አሳምሮ ጸጥ ብሎ ቆሞ ነበር። በዚሁ መካከል ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ ሲጓዙ በፊት በፊታቸው ያንበሳ ጐፈር በራሳቸው ያሠሩ፥ ያንበሳ ለምድ የደረቡ፥ ሰባሪ አንበሳ የመሰሉ ጀግኖች ወታደሮችና ሰይፍ ጃግሬዎች ነበሩ ፡በኋላ በኋላቸውም ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚኒስትርና ክቡር በጅሮንድ ዘለቀ የገንዘብ ሚኒስትር፥ ክቡር መልአክ ገነት ወልደ ሐና፥ ክቡር አቶ ማህሌ ፀዳሉ፥ ነበሩ። በግራና ቀኝ ካህናቱና ዲያቆናቱ እክሊል እንደ ደፉ መስቀል እንደ ያዙ ይጓዙ ነበር ። ከካህናቱና ከዲያቆናቱ ሁለተኛ ረድፍ የግርማዊ ንጉሥ ዘበኛ ክቡር ፊታውራሪ ወልደ አማኑኤል አሰልፈውት እንዳጥር ሆኖ ይሔድ ነበር ። ፊት መርቶ የሚሔደውን ሰልፉን እንዲያሳምርና በሥርዓት እንዲሔድ ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ክቡር ቀኛዝማች ከልክሉ ይጠባበቁ ነበር ። እንደዚሁ ሁኖ ዓጀቡ ከመንገዱ መካከል በደረሰ ጊዜ የሚያስደንቅ የሚያስገርም ሆኖ እየታየ ዓጀቡ እንዳማረ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ወደ አሉበት ቦታ ደረሰ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ባሉበት ግምጃ ድንኳን ውሥጥ በቀኝ በኩል የውጭ አገር ሚኒስትሮችና ታላላቆች ሰዎች ተቀምጠው ነበር ። በስተግራም፥ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቀጥሎ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ፥ ክቡር አፈ ንጉሥ ከተማ ፥ ክቡር ራስ ገብረ ሕይወት ፥ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ፥ ክቡር ደጃዝማች መርድ ፥ ክቡር ደጃዝማች ይገዙ ፥ ክቡር አፈ ንጉሥ አረጋይ ፥ ክቡር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል ፥ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ፥ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ፥ ጸሐፊ ትእዛዝ አፈወርቅ ፥ ደጃዝማች መኵሪያ፥ ፊታውራሪ እምዴ ፥ ብዙ ሌሎችም መኳንንቶች ተቀምጠው ነበር ከደረጃው በታች ከትልቁ ድንኳን ዝቅ ብሎም የየአድባራቱ ካህናትና ሊቃውንት የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ የሚቆሙበት ድንኳን ተተክሎ ነበርና በዚያ ቆመው ተሰናድተው ይጠባበቁ ነበር ። ካህናቱና ሊቃውንቱ ከቆሙበት በኋላ የከተማ ዘበኛና የግርማዊ ንጉሥ ሰልፈኛ ወታደር ክብ ዙሪያ እየሆነ ሜዳውን ግጥም ብሎ ሞልቶት ነበር የግርማዊ ንጉሥ የክብር ዘበኛም እግረኛና ፈረሰኛ ወታደርም ነጭ ሱሪ ታጥቆ ሰማያዊ ከት ደርቦ መትረየስ መትረየሱን እንዳነገተ በሠራዊቱ መካከል ብርቅ ሆኖ ይታይ ነበር ። በመካከልም ባንድ ቦታ ሙዚቃ ነፊዎች ተሰናድተው ቁመው ነበር ።

ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱም በመልካም ዓጀብ ሁነው ከዚያ ቦታ ሲቀርቡ ክቡር ሊጋባ ወዳጆና የእልፍኝ አስከልካዩ ክቡር ቀኛዝማች ፍቅረ ሥላሴ ክቡር ባላምባራስ ደስታም፥ በመንገድ የነበረውን ሰው ሁሉ ስፍራ ስፍራውን አስይዘው፤ ሊቀ ጳጳሳቱንና ጳጳሳቱን በመልካም ሰልፍ ተቀበልዋቸው ። ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳሳቱም በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ፥ በግርማዊ ንጉሥ ፊት በቀረቡ ጊዜ የሰላምታ ሙዚቃ ተነፋና ሠራዊቱ ሁሉ የሚገባ ሰላምታውን ሰጠ ። ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳጳሳቱም ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ፥ ከግርማዊ ንጉሥ ዙፋን እየቀረቡ የቡራኬ ሰላምታቸው ሰጡ። በዚያን ጊዜ ፳፩ የመድፍ ተኵስ ነጐደ ። ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ ከግርማዊ ንጉሥ በስተቀኝ በተዘረጋላቸው ወንበር ተቀመጡ ። ወዲያውም ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ዋና ዲሬክተር የውጭ አገር የዲፕሎማቲክን ሰዎች እያቀረቡ ከሊቀ ጳጳሳቱና ከጳጳሳቱ ጋራ አገናኟቸው። ከመኳንንቱና ከሊቃውንቱም ታላላቆቹ እየቀረቡ ቡራኬ ተቀበሉ።

ከዚህ ቀጥለን የካህናቱን አቀባበል እንጽፋለን።

በእግዚአብሔር ቸርነት በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በግርማዊ ንጉሥ ትጋት አንድ ሊቀ ጳጳሳትና አራት ጳጳሳት ከእስክንድርያ ፓትሪያርክ ተሹመው መምጣታቸው ስለ ተሰማ ትልቅ የክብር አቀባበል እንዲደረግላቸው ስለ ታሰበ በየአድባራቱ ያሉት ካህናት ለዚሁ ለጳጳሳቱ አቀባበል የሚሆን ወረብ እንዲያሰናዱ የካህናቱ ባልደረባ ክቡር መልአክ ገነት ወልደ ሐና አስታውቀዋቸው ነበር ።

ደግሞ አንድ ሰው ስሙን ሳይጽፍ ወረቡን ብቻ ጽፎ ሰጥቶ ነበርና ሁሉም ባንድነት ተቀላቅሎ ትልልቆች ሊቃውንቶች ምስጢሩ ያማረውን ወረብ እንዲመርጡ ታዘዙ ።

እነዚያም ሊቃውንቶች የቀረበላቸውን ወረብ ሁሉ መርምረው ሁሉም እጅግ መልካም ነው ፤ ነገር ግን ምስጢሩ አሁን ለጊዜው የሚስማማው ስም ሳይጸፍበት ያገኘነው ወረብ ነው ብለው አስታወቁ ።

ከዚህ በኋላ ይህ የተመረጠው ወረብ አምሮ ተለዝቦ ነበርና ሊቀ ጳጳስቱና ጳጳሳቱ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ቡራኬ አድርገው በየወንበራቸው በተቀመጡ ጊዜ ካህናቱ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ እያሉ ቀርበው ወዲያው አራት ድምፀ መልካም ደብተሮች ተመርጠው ወረቡን ይቆሙ ጀመር ።

ወረቡም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

እእምሩ እእምሩ ከመ በጽሐ ጊዜሁ ለነቂህ እምንዋም ። አልጸቀት ሕይወትነ ሲመተ ጳጳሳት ፤ እንተ ይእቲ ተስፋነ በእስካለ ማርያም ። ሐለፈ ሌሊት ወመጽአ መዓልት ኃይለ ሥላሴ ንግድፍ እምላዕሌነ ምግባረ ጽልመት ንዑ ናንሶሱ በብርሃኑ ለቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ።

ለዚሁ ለጳጳሱ አቀባበል እንደ ወረብ ብቻ ተለዝቦ እንዲብቃ ምንም ነገሩ የተወሰነ ቢሆን ከያድባራቱም እየተሰናዳ የመጣው ወረብ ሁሉ ምሥጢሩ እጅግ ያማረ መሆኑን ስለ ተረዳነው ሁሉንም ከዚሁ ቀጥለን አትመነዋል ።

ይቤሎ ዮሐንስ ለቄርሎስ ዕቀብ ማኅፀንተከ ኢትዮጵያ ዘተወከፍከ እምነገሥት እስከለ ማርያም ወኃይለ ሥላሴ ከመ ትዕብክ ቃሎ ቀዊመከ ምስለ ሢመተ እዴሆሙ ለካህናት ወኵሎሙ ጳጳሳት ከመ ትስብክ ቃሎ ቀዊመከ ።

የእንጦጦ ማርያም መንበረ ፀሐይ ።

ይቤላ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ለቅድስት ኢትዮጵያ አንሰ ብቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ቀደስኩኪ ከመ ይሰባሕ ስምየ በላዕሌኪ ማኅበረ ጳጳሳት ረሰይኩኪ ወከዕበ ትብል ንግሥትነ እስከለ ማርያም ወልድ እኁየ ኃይለ ሥላሴ ቃልከ አዳም ጥቀ ሥሙር እምወይን ።

ዘደብረ ኃይል ራጉኤል ።

ጸለዩ እንዘ ይብሉ ንግሥትነ እስከለ ማርያም ወንጉሥነ ኃይለሥላሴ ዲበ አትራኖስ ንበር ሊቀ ጳጳሳት ለካህናት ዐቀቦሙ ወለሕዝብ በቃል ጥዑም ተናገሮሙ ወአስተርአዮሙ ከመ ማኅቶት ለሕዝብ ።

የዑራኤል ደብረ ጽጌ ።

አንትሙሰ ከመ እብነ ሕይወት ተሐነፁ ቤቶ ለመንፈስ ቅዱሳ ወለክህነቱ ቅዱስ ከመ ትባርኩ መንግሥቶ ለኃይለ ሥላሴ ወትንግሩ ሠናይታ ለእስከለ ማርያም አባ ባርከኒ ቄርሎስ አባ ከመ ባረከ አብርሃም ለይስሐቅ ወልዱ ።

ዘመከነ ሥላሴ ።

ውእቱ እሚረ ይትወሀበሙ ክልኤ ልብ ትሠርዕ ሃይማኖት ወይትመዋዕ ሞት ትመጽዕ ጽድቅ ወይትጋባእ ትዕግሥት ውእቱ አሚረ ደነቅሐ ዓለም ዘአልቦ አመ ነቅሐ ።

ዘንኑተ ጽጌ ጊዮርጊስ ።

ለስሚዕ ዕፁብ ግብር ጥበቡ ለእግዚአብሔር አጽናፈ ዓለም እለ ተዘርዉ ለስብከተ ወንጌል አስተጋብኦሙ በምዕር ወተፈሥሑ እስከለ ማርያም ወኃይለ ሥላሴ ሶበ ተጋብኡ ኅቡረ ገብሩ በከመ አዘዞሙ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ወከመ ቀዳሚ ተመይጡ ኵሎሙ ።

የግቢ ገብርኤል ።

ብፁዓን እሙንቱ ጳጳሳት እለ ወሰኑ ወሠርዑ ሃይማኖተ ከመ ይዕቀቡ ሕገ ወይኅሡ ሥርዓቶ ለክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ገብሩ ሰላመ ለአሕዛብ ለነገሥት ወለበሐውርት ወኮኑ ብርሃና ለኢትዮጵያ ።

ዘሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ።

ይቤ እግዚአብሔር በነቢይ ኃይለ ሥላሴ በጽድቅ ወበተፋቅሮ እስመ ረከብኩ እምውስተ ደቂቅኪ ሀገረ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት አምኂ አምኂ ኢትዮጵያ ደቂቀ ንግሥትኪ ኅሪት እስከለ ማርያም ሀየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ ጳጳሳት ተወልዱ ለኪ ።

ዘደብረ ሰላም መድኃኒ ዓለም ።

ደምረነ ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳኒከ ምስለ አብርሃም ይስሐቅ ወጴጥሮስ አበዊነ እለ አምዓለም ምስለ እለ ተኅርዩ እምከርሠ እሞሙ እስከለ ማርያም ወረከቡ ዘአሰፈዎሙ ኃይለ ሥላሴ ኃይልነ ወፀወንነ ወምስካይነ አምላኩ ለቄርሎስ ።

ዘእስጢፋኖስ ደብረ ሰላም ።

ብፁዕ አንተ ቄርሎስ ዘኅረየከ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ዓለም ወትብለከ ኢትዮጵያ እስኩመ ንግረኒ አንተ እለ ሤሙከ ጳጳሰ ወይቤልዋ ኢጲስቆጶሳት ለእስከለ ማርያም ንግሥተ ነገሥታት ንሕነ አዕበይነ ክህነተ ወተሠየምነ ንበብኪ አዳም አዕይንትኪ ዘርግብ ለኪ ነዓርጓ ስብሐተ ።

ዘደብረ ማህል ሚካኤል ።

አፀሐይ አቡነ ቄርሎስ እስመ አብራህከ በስብከትከ ወርኀ ወከዋክብተ ጳጳሳት ይሰግዱ ለከ በወንጌል እስከለ ማርያም ወበጳውሎስ ኃይለ ሥላሴ ተሰብከ ዜናከ ።

ዘጴጥሮስ ወጳውሎስ ።

ሤሞሙ አብ ዮሐንስ ጳጳሳተ አስተጋብኦሙ እምበሐውርት እምጽባሕ ወእምዓረብ ወመስዕ ወባሕር ነገሮሙ ነገረ ሰላም ለንግሥትነ እስከለ ማርያም ወኃይለ ሥላሴ በኅብረተ ቃል ተጋብኡ ማኅበር በእስክድርያ ሀገር ገብሩ መንበረ መሀሩ ወሰበኩ ወሃይማኖተ አርትዑ ።

ማርቆስ ወንጌላዊ ቦአ እለ እስክንድርያ በጊ ወፈጸመ መንግሥቶሙ ወለንግሥትነ እስከለ ማርያም ወንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ።

ወሤመ ሎሙ ጳጳሳተ ኢጲስ ቆጶሳተ ዘኅረዩ እምውስቴቶሙ በሃይማኖተ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

ዘአለቃ መርሻ ።

ከስድስት ሰዓትም በኋላ ያቀባበሉ በዓል ስለ ተፈጸመ ሊቀ ጳጳሳቱና ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ባንድ ኦቶሞቢል ሁነው ጳጳሳቱም በየመጡበት አቶሞቢል ሁነው ግድቡም እንደአመጣጡ ሁኖ ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ ቤት ተመለሱ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም በክቡራን መኳንንቶቻቸውና ሠራዊቶቻቸው ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ ።

ለሊቀ ጳጳሳቱና ለጳጳሳቱ የተደረገላቸው አቀባበል ዕፁብ ድንቅ ነው ። ብርሃንና ሰላም እንዳቀባበላቸው ማማር የሥራቸውን ፍሬ አይቶ ደስ እንዲለው እየተመኘ ለትልቁ የእግዚአብሔር እርሻ የኃላፊነት ሥራ ዋና እንዲሆኑ ለተመረጡ

ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስና ለኢትዮጵያውያን ጳጳሳት አቡነ ጴጥሮስ፥አቡነ አብርሃም፥አቡነ ሚካኤልና አቡነ ይስሐቅ እንኳን ደህና ገባችሁ ይላል ።

አንድ ኢትዮጵያዊ ስለጳጳሳቱ ያበረከተው ቅኔ

ሥላሴ

ኢትትሀከይ ለተሠርግዎ ኵለሄ ሐዳስ ኢትዮጵያ ፤
ኅብረ ኅልቀተ ወርቅ ጽሩይ ሥርጋዌ አምጣነ ምሉዕ ውእቱ።
በአፃብዒሂ ጳጳሳት ኃምስቱ
ወአመ ኢፈቀደ ምንተ ይእዜ ፣ ከመ ይበልዎ ሉቱ ።
እጓለ ንጉሥ ኃይለ ሠለስቱ ።
ሙሴ ሕግነ ዘቅድመ ዝንቱ ።
ተመነየ ይሰደድ እምቤቱ ።

ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ በሰላም ስለገቡልን እግዚአብሔርን ከወንድሞቼ ከኢትዮጵያ ልጆች ጋራ ሁኜ እያመሰገንሁ ለክቡራን አባቶቼ ይህን መወድስ አበረክታለሁ።

በረከተ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ላዕሌክሙ ይኅድር ።
ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ።
ወላዕለ ተፈሪ ንጉሥ ከመ ይትሐደስ መንግሥቱ ።
ወቤተ ዮሐንስ ቄርሎስ ኢይወድቅ ለእመ ገፍዖም ነፋሳት
አሠርቱ ።
አምጣነ ተሐንፀ መሠረቱ ። በመልዕልተ ጴጥሮስ ኰኵሕ ።
ወበአዕማድ አርባዕቱ ።
እምኀበጽሂ ሰበ ተመይጡ ፤ ደቂቀ እስራኤል እሙንቱ።
ኢተሴለዮሙ ሚካኤል ኖላዌ እስራኤል በበፍኖቱ ።
ወባሕረ ሚመት ምሉዕ ዘኢይየሐፅፅ ምልዓቱ ።
በእደ ሙሴ ኃይለ ሥላሴ ተከፍለ ለክልኤቱ ።
አለቃ ዳንኤል እንግዳ ደስታ ።

ስለ እንግሊዝ ሚኒስትር መምጣት ።

ሰኔ ፲፰ ቀን ክቡር ሰር ሲድኒይ ባርቶን የእንግሊዝ መንግሥት በሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የሹመታቸውን ወረቀት ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ አቀረቡና በዚያን ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ንግግር ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

ታላቁ ንጉሤ ግርማዊ ፭ኛ ጆርጅ በእግዚአብሔር ጸጋ የታላቂቱ ብሪታንያና የአይርላንድ ከባሕርም ማዶ ያሉት የእንግሊዝ ግዛቶች ንጉሥ የሃይማኖት ጠባቂ የህንድ ንጉሠ ነገሥት ፤ በአዲስ አበባ ቤተ መንግሥታችሁ እኔን የእንግሊዝ መንግሥት ልዩ መላክተኛ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርገው የሾሙባቸውን በንጉሡ እጅ የተፈረሙትን ደብዳቤዎች በንጉሡ ትእዛዝ ለግርማዊነታችሁ አቀርባለሁ ።

የተላክሁበትም ምክንያት በኢትዮጵያ መንግሥትና በአገሬ መካከል እስከሁን ድረስ በደስታ ጸንቶ የኖረውን የጠበቀ ወዳጅነትና መልካም ስምምነት የበለጠ ለማጽናትና ለማሻሻል እኔም ይህነኑ የታላቁ ንጉሤን አሳብ ለመፈጸም የሚቻለኝን ያህል ከሙሉ ልቤ ለመጣር ብርቱ ምኞቴ ነው። እንዲሁም ግርማዊነታችሁ የግርማዊነታችሁም መንግሥት ይህነኑ የአንድነት በጎ ፈቃድ ከፍ ከፍ ለማድረግ በደስታ እ ዲረዳኝ ተስፋዬን በማክበር አገልጻለሁ ።

ደግሞ ታላቁ ንጉሤ ለግርማዊነታችሁ ያላቸውን አክብሮትና አሳብ ለግርማዊነታችሁ ጤንነትና ደህንነት ፤ ለሕዝባችሁና ለአገራችሁም ልማት የሚመኙትን የልብ ምኞት እንድረጋግጥ ታዝዣለሁ ።

እንደዚህ የመሰለ ከፍ ያለ ታላቅ መልክት ለማድረስ በመታዘዜ ጥልቅ የሆነ ደስታ ይሰማኛል ። አሁንም ከኔ በፊት የነበሩት ሚኒስትር መቅረታቸውን የሚያስታውቅ የንጉሡን ደብዳቤ ሳቀርብ ለግርማነታችሁ ጤንነትና ደህንነት በኢትዮጵያም ሕዝብ ልማት የኔን የራሴን ምኞት እያቀረብሁ እንድጨርስ ፈቃድ እለምናለሁ ።

ሚኒስትሩም ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ ።

የታላቂቱ ብሪታንያ የአይርላንድና ከባሕርም ማዶ ያሉት የእንግሊዝ ግዛቶች ንጉሥ ፤ የህንድ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ጆርጅ አምስተኛ በእኛ ዘንድ እርስዎን የእንግሊዝ መንግሥት ልዩ መላክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርገው መሾማቸውን የሚያስታውቁ ደብዳቤዎች ስንቀበል ደስ ይለናል።

ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መከከል በደስታ እስከ ዛሬ ጸንቶ የኖረው የወዳጅነት መገናኛ እየጠበቀ እንዲሔድ እኛም ፍጹም ምኞታችን ነውና እርስዎም እንደ ገለጹት የተላኩበት ምክንያት ከእኛ አሳብ ጋራ የተባበረ ስለ ሆነ ደስታችን የበለጠ ነው ።

ይህንንም የተላኩበትን ሥራ በሙሉ ልብዎ እየጣሩ ለመፈጸም ብርቱ ምኞት እንዳለዎ ስለ አስታወቁን እኛም በበኩላችን ይህ በወዳጅነት አሳብ የሚመራ ሥራዎ እንዲከናወንልዎ የሚገባ እርዳታችንን እናጎድልብዎትም ።

የታላቂቱ ብሪታንያ ንጉሥም ግርማዊ ጆርጅ አምስተኛ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ለእኛ ለራሳችንና ለሕዝባችን ደህንነት፤ ለሀገራችን ልማት የሚመኙትን መልካም ምኞት ያረጋገጡልን ዘንድ ስለ አዘዙዎ ግርማዊነታቸውን እያመሰገንን እኛም በወገናችን ፤ ለግርማዊነታቸው ፍጹም ጤና ፤ ለንጉሣዊ ቤተ ዘመዶቻቸውም ደህንነት የምንመኘውን የወዳጅነት ምኞታችንን እያቀረብን የምንገልጸውን የአክብሮት አሳብ እንዲያደርሱልን እንለምንዎታለን ።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ ፤ ለእኛ ለራሳችንና ለሀገራችን በራስዎ ስም ስላቀረቡልን መልካም ምኞት እያመሰገንሁ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በራሴም ፤ በኢትዮጵያም ሕዝብ ስም ሆኜ፤ ወደ ሀገራችን እንኳን በደህና ገቡ እያልሁ የወዳጅነት ምኞቴን አቀርብልዎታለሁ ።

ሰኔ ፲፱ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት አዲስ አበባ ።

በሰኔ፳ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ለወጣው የአ አ ጉምሩክ አዋጅ ጭማሪ

በ፲ ንምራ ድር ወይም ማግ ውስጥ ቱባው ፲ መሆን ይገባዋል የተባለ ቱባው ፲ ሊሆን አይችልም፡ ፭ ቱባ ነው እንጅ። ስለዚህ ነጋዴ የሆነ ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት የሚችለው ድርና መጻቀጥሉ እንደተጻፈው ነው። በንድ ማሠሪያ ውስጥ ድር ወይም ማግ እርዝመቱ፡ ፳፻፴ ያርድ መሆን የባድ አሊበት ።

(ማግ ባለ ፲ ነጥር)

ንምራ	ቱባ	ማሠሪያ	ትት
2	20	1	7
4	20	2	7
6	20	3	7
8	20	4	7
10	20	5	7
12	12	10	7
14	14	10	7
16	16	10	7
18	18	10	7
20	20	10	7
22	22	10	7
24	24	10	7
26	26	10	7
28	28	10	7
30	30	10	7
32	32	10	7
34	34	10	7
36	36	10	7
38	38	10	7
40	40	10	7
80	40	20	7

(ድር ባለ፲ ነጥር)

ንምራ	ቱባ	ማሠሪያ	ትት
4,2	20	1	7
6,2	15	2	7
8,2	20	2	7
10,2	25	2	7
12,2	12	5	7
14,2	14	5	7
16,2	16	5	7
18,2	18	5	7
20,2	20	5	7
22,2	22	5	7
24,2	24	5	7
26,2	26	5	7
28,2	28	5	7
30,2	30	5	7
32,2	32	5	7
34,2	34	5	7
36,2	36	5	7
38,2	38	5	7
40,2	40	5	7
60,2	40	5	7
80,2	40	10	7
84,2	42	10	7

ቀጋው ከሐምሌ አንድ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ጀምሮ ከሥር ንምራ እምስቲ ብር ከአሥራ አንድ ንምራ እስከ ፳ ስድስት ተኩል ከ፳፩ እስከ ፴ ፱ ከ፴፩ እስከ አርባ ፲፩ ከአርባ አንድ እስከ ፶ ፲፫ ከሃምሳ አንድ እስከ ፷ ፲፬ ከስሳ አንድ እስከ ፸ ፲፭ ተኩል ከ፸ አንድ እስከ ፹ ፲፯ ከዚህ በላይ ፲፱ ብር ይህ ለቀይ ማግ ነው ። ለነጭ ማግ ፲ ንምራ ፩ ከ፲፩ ፳ ንምራ ፯ ብር ከ፩ መሐለቅ ፴ ንምራ ፲፪ ብር ፹ ንምራ ፲፱ ብር ከዚህ በላይ ያለ ንምራ ፳ አንድ ብር ድር ከ፴ አንድ እስከ ፵ ንምራ ፲፫ ከ፵ አንድ እስከ ፶ ንምራ ፲፬ ከ፶ አንድ እስከ ፳ ፲፯ ብር ፸ አንድ እስከ ፸ ፲፰ ብር ከ፹ አንድ እስከ ፹ ፰ ብር ከዚህ

የሀንድ አገር ባለ አሥር ነጥር ፓኬት ቱባው ባለ ፳፻፴ ያርድ

ማ ግ

ንምራ	ቱባ	ማሠሪያ	ትት
4	10	5	7
$6\,1/2$	13	5	7
8	16	5	7
$8\,1/2$	17	5	7
10	20	5	7
$10\,1/2$	21	5	7
$11\,1/2$	23	5	7
$12\,1/2$	25	5	7
$14\,1/2$	29	5	7
$16\,1/2$	33	5	7
20	20	10	7
$20\,1/2$	21	10	7
21	21	10	7
24	24	10	7
25	25	10	7
30	30	10	7
35	35	10	7
40	40	10	7
50	40	10	7
60	40	10	7

ከሀንድ አገር የሚመጣ ማግ ብቻ ነው።

ከጃፖን ለሚመጣ

ባለ፲ ነጥር ፓኬት ቱባው ባለ ፳፻፴ያርድ

ድ ር

42,2	42	5	7

ማግ

40,1	40	10	7
42,1	42	10	7
44,1	44	10	7

ከኢጣሊያን አገር ለሚመጣ ድርና ማግ

ማ ግ

ንምራ	ቱባ	ማሠሪያ	ትት
6	12	5	7
$6\,1/2$	13	5	7
8	16	5	7
$8\,1/2$	17	5	7
10	20	5	7
$12\,1/2$	25	5	7
18	18	10	7
20	20	10	7
21	21	10	7
24	24	10	7
32	32	10	7
40,5	40	10	7

ጥለት በያይነቱ ባለ ፳አምስት ነጥር ፓኬት ቱባው ባለ ፳፻፴ ያርድ የአክሩፈሉ ደንብ

ቀይ ጥለት

ንምራ	ቱባ	ማሠሪያ	ትት
40	20	10	7
30	30	10	7
28	28	10	7
25	25	10	7
20	20	10	7
60	30	10	7
32	16	10	7

ብጫና አረንጓዴ

20	20	5	7
40	20	10	7

ጥቁር

15	15	10	7
20	20	10	7
21	21	10	7
24	24	10	7
26	26	10	7
28	28	10	7

ሰማያዊ ።

15	15	10	7
20	20	10	7
21	21	10	7
24	24	10	7
26	26	10	7
28	28	10	7
32	16	10	7
40	20	10	7

ባለ አሥር ነጥር ፓኬት ቱባው ባለ ፳፻፴ ያርድ

ድር

ንምራ	ቱባ	ማሠሪያ	ትት
40,2	40	5	7
42,2	42	5	7
44,2	44	5	7

ደማሞ

40,2	40	7	7
42,2	42	7	7
44,2	44	7	7

ማስታወቂያ ።

ከሐምሌ አንድ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት ጀምሮ የበሬ ቆዳ ቡሽሬ ግምት በፈረሲላ ፲፪ ብር መሆኑ ቀርቶ በአሥር ብር ተገምቶ ቀረጡን ይከፍላል ። ቆዳ በአሥር ብር ይገመት የነበረው ቀርቶ በስምንት ብር ተገምቶ ቀረጡን ይከፍላል ። ቡን ግምቱ በፈረሲላ ሰባት ብር የነበረው ቀርቶ ፈረሲላው በዘጠኝ ብር ተገምቶ ቀረጡን ይከፍላል ። የፍየል ሌጦ ከረጀው በአሥራ አንድ ብር መገመቱ ቀርቶ በአሥራ ሁለት ብር ተገምቶ ቀረጡን ይከፍላል ። የበግ ሌጦ ኰረጀው በ፰ ብር ተገምቶ ቀረጡን ይከፍላል ። ሻሽ ከረጀው በሠላሳ አራት ብር መገመቱ ቀርቶ በሐያ አምስት ብር ተገምቶ ቀረጡን ይከፍላል ። የእንግሊዝ ወረቅ ሸረፋው በአሥር ብር መታሰቡ ቀርቶ በአሥራ አንድ ብር ይታሰባል ።

ለጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ገብረ እግዚአብሔር ።

አንደኛ የሕዝብ ጉዳት አረቂ መጠጣት ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አረቂ እየጠጣ ከለቀ በዚች በለምለሚ ሀገሩ ላይ ማነው የሚቀመጠው ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር ምላሹን እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፤ አረቂ የሚሸጥ ወይም አረቂ የማይጠጣ ይሆናል ። ይህንንም አረቂ የረቀቀ ዘመቻ ኃይለኛ መንግሥታትን ተዋግቶ ከልመለሰው አንድ አንድ ሰው አረቂ አትጠጡ ብሎ በጋዜጣ እየጻፈ ቢለምን የሚሰማው የለም መንግሥት ካላስገደደ።

ሁለተኛ የሕዝብ ጉዳት ።

በኢትዮጵያ አውራጆች ያሉ ቆማጦች ናቸው እነኚህንም የሚጋባ በሽታ ያለባቸውን ወንድሞቻችንን መንግሥታችን አንድ ስፍራ እንዲከማቹ ቤት ሠርቶ ግቡ ቢላቸው አንገባም ብለው እስከሁን ቆይተዋል ስለምን እነርሱ እሳባቸው ለምንን ያመጣነው በሽታ አይደለም በተለየ ስፍራ መቀመጣችን ምን ብጠፋን ነው እያሉ ይናገራሉ ።

ያሥሩ ሺ ቆማጣ በሽታ የ፴ ሚሊዮኑን ሕዝብ ጤና ያበላሸው ማለታቸው ነውና መንግሥታችን ማስገደድ ይቻለዋል ።

ማስታወቂያ ።

ስለ ጳጳሳቱ አቀባበል በተደረገበት በሰኔ ፳፪ ቀን አንድ የዝናብ ልብስ በግቢ ተገኝቷልና ይህ የዝናብ ልብስ የጠፋበት ሰው ወደ ውጭ_ጉዳይ ሚኒስቴር ይጠይቅ ።

AVIS.

Le samedi 29 Juin à la cérémonie de la reception des Evêques, il a été trouvé au Palais Impérial un impermiable. Le propriétaire du dit impermiable est prié de s'adresser au Bureaux du Ministère des Affaires Etrangères.

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕራንት ባግዳሣሪያን ።

ከ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋውን ግን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የተገኘ ወሬ

ሰኔ ፳፰ ቀን የጦር መርከብ ሰዎች አሥር መኳንንቶች ፤ አሥር ምክትል መኳንንቶች፥ ሀያ የባሕር ወታደር፥ ሀያ ሙዚቃ መችዎች ወደ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ወደ ግርማዊ ንጉሥ ቀርበው እጅ ለመንሣት ይመጣሉ ።

ከጥዋቱ በሁለት ሰዓት አዲስ አበባ ይገባሉ ።

ከእኩለቀን በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥተ ነገሥታትና ከግርማዊ ንጉሥ ይቀርባሉ ። ማታ ግርማዊ ንጉሥ እራት ይጋብዙችዋል ።

ቅዳሜ በአራት ሰዓት ሰዎቹ ወደ ክቡር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ሔደው ይገናኛሉ ። በሰባት ሰዓት የፈረንሣዊ ሌጋሲዮን እራት ይጋብዛቸዋል ። ከዚያ በኋላ ቄይቶ የፈረንሣዊ ሌጋሲዮን ሻይ ይጋብዛቸዋል ። ወደ ማታ ከሶሲዬቴ አሚካል ፍራንሴ ትልቅ ፈንጠዚያ ይደረጋል ።

እሁድ ከጥዋቱ በሦስት ሰዓት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውሥጥ በግልጥ የሙዚቃ ጨዋታ ይደረጋል። ከእኩለቀን በኋላ ወደ ፈረንሣዊ ሌጋሲዮን ለተጠሩ ሰዎች ዘፈን ይደረጋል ።

ማስታወቂያ ።

አንድ ያማረ የፈረንጅ ዓይነት ዕድሜው አንድ ዓመት የሚሆን ቁመቱ ረጅም መልኩ ቀይ ዳለቻ ጎፈሯም ጆሮ ትልቅ የሆነ ውሻ ጠፍቶብናልና አግኝቶ ይዞት የመጣ ወይም ያለበትን ስፍራ ያመለከተ ሰው እንደሚገባው ጉርሻ ያገኛል ።

ለዌዲሽ ሚሲዮን ሴቶች ተማሪ ቤት ጉለሌ

ማታስወቂያ

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ትምህርት ቤት ስለ ክረምቱ ከሐምሌ አንድ ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት ወር ይዘጋል ።

ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።

ፔር ዳኔይ ።

አ ፀ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደጃች አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

የግሪክ መንግሥት ቆንስል ጀኔራል ቤት ከጉለሌ ያለውን የሚቺው የፓናዮቲስ ኩምቢስን ሁለት ቦታዎች የርስት ወረቀት ያላቸው ያንደኛው የካርታ ቁጥር ፩ሺ፰፻፹፱ የሁለተኛው ፩ሺ፱፻፲፯ ቁጥር ያለው ። የመጀመሪያው የሥፋቱ ልክ ፳፬ሺ፱፻፶፫ አራት ማዕዘን የሁለተኛው ሥፋት ፬ሺ፰፻፳ አራት ማዕዘን ብዙ የባሕር ዛፍ የሞላባቸው በምንም ዕዳ ነገር የማይታመሙ ነጻ የሆኑ በሐራጅ ይሸጣሉና እነዚሁን ቦታዎች ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ከ፲፱ ሰኔ አንስቶ እስከ ሐምሌ ፲፱ ድረስ ከቆንስላ ቤት መጥተው የሚገዙበትን ዋጋ እንዲያቀርቡ ያስታውቃል ።

የርስት ወረቀታቸውም ከግሪክ ቆንስላ ቤት ተቀምጧል ።

የግሪክ መንግሥት ቆንስላ ጀኔራል ቤት ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው፤ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው።ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ቤት በማጥለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶሞቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶሞቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቅዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶሞቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ገምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚሁ አቶሞቢል በተለይ ወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤት በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዴልፊያ በቦስቶን በማድራስ በሕንድና በጅቡቲ፡ በነዚሁ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚሁ አቶሞቢል የሚያስፈልጉት የመለዋጫ መሣሪያ ዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

KONIAK
EN ΠΕΙΡΑΙΕΙ

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታለችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸከላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጕርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበድቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ካለን ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይጀበሁን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶
5me ANNÉE № 50

ሐሙስ ሐምሌ ፲፰ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 25 JUILLET 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaíre paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የማፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መዲወ ኤቦ ።

በኢጣልያ ቋንቋ መዲወ ኤቦ በፈረንሳዊ ሞዩን አጋር ማለት መካከለኛው ዘመን ማለት ነው ። መካከለኛ ዘመን የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ፫፻፺፭ ዓመት ጀምሮ እስከ ፲፬፻፶፫ ዓመተ ምሕረት የነበረው ዘመን ነው ። ወይም በዓለሙ ላይ ሰፍኖ የነበረው የሮማ ትልቅ መንግሥት ወደቀና እስጥንቡል በእስላሙ በሁለተኛው ሙሐመድ እጅ የሆነ ጊዜ ጀምሮ እስከ ፲፬፻፶፫ ዓመት የነበረው ዘመን ነው ።

በዚሁ ዘመን የኤውሮፓ አገር ተከፋፍሎ በያውራጃው በየተራራ፥ በየጉጡ በየወንዝ፥በየደሴቱ ባላባትና ባለጉልቶች ማርኬዜ፥ ባሮኔ፥ኮንቴ ቢስኮንቴ፥ እየተባሉ፥ ሲገዙ ነበረ ። እነዚሁ አገረ ገዦዎች ሕዝቡን እንደፈቀዳቸው ሲአዝዙ፥ሲዳኙ፥ሲቃኙ፥ ይኖሩ ነበረ ። ባህላቸው ሁሉ እንደዛሬ አልነበረም፤ እየብቻው ነው ። ባህሬአቸው ሁሉ የዝራትና የመዝረፍት ብቻ ስለነበረ በትልቅ አጀብ ተከበው፥ በሽልማ ታጥረው፥ በፊት በኋላቸው እምቢልታ እያታለላቸው ሙዚካና ነጋሪት ቀንዳመለከት እያነቃቃቸው፥መሬት በተጠየፈች ሰጋር፥በፈነደቀ ጮሌ ተጀንነው፥ ድኃው እንደፈጣሪ እየሰገደላቸው እንደአምላክ እያመለከባቸው እነሱ ሲነቁት፥ ሲአጠቁት፥ ሲአስጨንቁት፥ይኖሩ ነበረ ። ገባርና ዜጋውን እነሱ በገዛዳቸው እንደነጩት ጠራርበው፥እንደግንድ ጀራርገው፥እንደጭቃ ጠፍጥፈው፥ እንደሊጥ ለውሰው፥አሞልሙለው፥ዓይን ጆሮውን፥ አንገት ከንፈሩን ቀርጸው አፍ ብለው ነፍስ የዘሩበትና ያቆሙት ያስመስሉት ነበር እንጂ እውነት እንደነሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈጠረና እንደነሱ ተወልዶ፥ አድጎ አርጅቶ፥ የሚሞት አይመስላቸውም ነበረ። በዚሁ ድኃ ላይ የሚሠሩት ግፍ ሁሉ የተገባ ሥራ ይመስላቸው ነበረ ። በላያቸው የሚቆጣ ንጉሥ ስላጡ በድኃው ላይ እነሱ ባዘዙት እነሱ በፈረዱት ያልቅ ይደቅ ነበረ ። በነሱ ጊዜ ጸሐፊው ብርቅ፥ፍርዱ፥ ጭንቅ ሁሉ በቃል፥ ሁሉ በቀላጤ፥ሙግቱና ፍርዱ መንገድ ለመንገድ ነበረ ። አንድ ጊዜ የተፈረደው ሦላሳ ጊዜ ይለወጥ ይደረጥ ነበረ ። በዚሁ ዘመን በኤውሮፓ የነበረው ባህል በጣም የሚያስደንቅ አጀቡና ጌጡ የሚአብረቀርቅ ነበረ። አንዳንድ ጊዜ በሥዕል እንደምናየው ፈረሱ በወርቅ መሳሪያ ተሸልሞ የሠራካላቱ በጥሩር ተለብጦ፥ ከጆሮው እስከ ሰኮናው ህብሩ በማይታወቅ መሳሪያ ተጀቡኖ፥ ፈረሰኛውም እንዲሁ ተጣር እስከራሱ በደመቀና በለሰለሰ ከፈይ ተጐናጽፎ፥ በሸከረና በከበደ ጥሩር ሰውነቱ ጠልቆ፥ በቡቅዳዴና በከፈተ አረንጓዴ ራሱን ጨንብሎ ይሒው ጭንብል በስተ ጀርባው ወርዶ እጣርበቱን አላብሶ ፈረሱን ዘሎ መሬት እየዳሰሰ ጡታም የብረት መንዶ በጉኑ አንጠልጥሎ ጣምራ ጦሩን በጫንቃው የዘሆን አንገት እንደጉበት የሚቆርጥ አፉውን በወገቡ ጣል አድርጎ የወርቅ ኩፍታውን ባራሱ ቁብ አድርጎ ያ ፈረሰኛ መኳንንት ሰቀላ በሚያህል ፈረስ ብቅ ባለ ጊዜ አንድ መላክ ከሰማይ ደመናውን ገላልጦ በከዋክብት ታጀቦ በቀስተ ደመና ተከቦ በፀሐይ ጮራ ተጋርዶ ዱብ ያለ ይመስል ነበረ ። ያንን መኳንንት በዚህ ግርማው ላየው ሰው ሞትም የሚደፍረው፥ እርጅናም የሚአጸወልገው፥ መቃብርም የሚነካው፥ አፈርም የሚአሳድፈው አይመስልም ነበረ ። ከተ የእግዚአብሔር ቀርቶ በሰው ዳኝነት የሚፈረድ ሁኖ ቢሆን እንዲህ ያማረው መኳንንት፥ እንዲህ ያለው ችምችም ጉበዝ፥ እንዲህ ያለው ወቃቢአማ ጀግና፥ ሞትም በጠገቡ እንዳይደርስ፥ እርጅናም ላሒውን እንዳያፈርስ የሚፈረድለት በመሰለ ነበረ ።

በእግዚአብሔርፍርድ ግና ምንም ቢአምሩ፥ምንም ቢአጌጡ ቢኳሉ፥ቢወለወሉ፥ምንም ቢኮሩ፥ቢወዘሩ፥ ምንም ቢገዙ ቢነዱ፥ ምንም ቢነግሡ ቢሰፍኑ፥ ከዚያች ከሞት መንቆር አንገቱን የ-

ማያገባና የሚአመልጥ የለም የእግዚአብሐር ፍርድ ይሕ ነው። አይላጥ አይለወጥ፡ይግባኝ ቀጠሮኝ የለበትም፡ሥጋ ለብሶ የትል መራገጫ የምሽጥ መራወጫ፡ መሆን አይቀርም የሰው ኩራት፡ የሰው ምቀኝነት፡ የሰው ትንኮል፡የሰው ማማር፡የሰው ውበት፡ እስከዚህ ድረስ ነው ደንበሩ ወሰኑ ። የዚያን ዘመን በፈረንጅ አገር የነበረው የሰውም የፈረሱም ጌጥና ሽልማት ባፍ ተነግሮ በጆሮ ተደምጦ አያልቅም ነበረ ። ለፈረስ ለበቅሎ ሲቀጠቀጥ የነበረው ወርቅና ብር ጉብጉብ ሳይጠይቁት የሚቀበጥረው፡ ሽሁሩና ድምፁ ሥሉሴ ተጋሽ ላይ በሥፍራ የሚባለው የወርቅ ጣፋ ከሰይፍና ትፈንዜው የተዘጋጀው ሙጣና ጫማ ከሾተሉ ጫፍ የሚብለጨለጨው ሎሚታ ከፋቅ ይጠቅሰል በቅርቡ ላይን ይገረምማል ። ለጥፉፍ የሚሸረበው የወርቅ ዝምዝም የካባ የላንቃው የወርቅ ክፈፍ የዙሪአው አጫዋች ከነፋስ ጋራ አምባጓሮ በገጠመ ጊዜ ተንቅልፍ ያበንነ ደንቆሮ ያሥደነግጥ ነበረ ። የቀለሙም አደማመቅ እንኳን ለደሀና ለውሽ ያጸድል ነበረ ። እንዲህ ላለው የከንቱ ጌጥ መደሻ ሲማስንበት የነበረው ወርቅና ብር በመሸጉ ተዝቆ፡ በቅርጫት ተሰፍሮ አይገፈትም ነበር ። ይሕ ሁሉ ጌጥ ለባለጸጋና ላገረ ገዥ ብቻ ነበረ። ድኻ ባላገር ግን እንኳን ጌጥ እርቃናውን የሚተግንበት ጨርቅ ባፉ የሚጉርሰው፡ጊጣ የሚልሰው ሙቅ፡ የሚአፈላው አጥሚት፡ አልነበረውም ። የዚህ ሁሉ ድኻነት ምክንያቱ ወታደሩም ሲአጅብ እየዋለ ሥራ በመፍታቱ ባላገሩ ገበሬም እርሶ በገበው ዘርቶ በፈራው፡ባሳደገው ፈረስ፡በወፈረው ከብት፡ በሚአልብት ጥገት፡ባለማዘዙና አገረ ገዢው ወታደር አውደልዳዩ ስለቀማው ስለወረሰው ነው ። ኋላ ግን በጥቂት በጥቂት ሲል በድፍን ኤውሮፖ ሥልጣኔና እውቀት እየሰፋ ሔደና በየተራራ በየወንዙ የነበሩት አገረ ገዢዎች ሥልጣናቸው ኃይላቸው እያነሰ እየተቀነሰ ሔደና አገር እየተጠቀለለ በንጉሦች እጅ ሆነ ። በየመንግሥቱ አንዳንድ ንጉሥ ከሆነ ዘንድ ለሕዝብ የተሻለ ሕግ ይወጣ ጀመረ። የግፍ መንገድ እየተዘጋ የእግዚአብሔር መንገድ እየተከፈተ ሔደ፡የገዢዎችም የተገዢዎችም ዓይን እየተገለጠ ሔደ። አጀብና ላይን የሚገለማ ጌጥ ተናቀ፡ቀረ፡ወደቀ። ደኅው የሚለብሰው አጥቶ ብርድ ሲአንገደግደው እርኩሱ ፈረስና በቅሎ ማጌጡን ሳያውቀው በወርቅና በብር መቃፈኑ የግፍ ግፍ መሆኑ ታወቀ ። ለመኳንንቱ በሚአንጸባርቀው ጌጣቸው ስፍራ ላይን የሚያሰለች የረቀቀ የጠዳ ልብስ ተተከበት ለፈረሰ ለበቅሎ በሚጠፈጠፈው ወርቅና ብር ግምጃና ከፈይ ስፍራ የቆርበት ኮርቻ የጠፍር እርካብ ተተካበት ። እንዲህ ስለሆነ ፈረሱም አልተቀረመ ፈረሰኛ መኳንንትም ከመዓርጉ አልተዋረደ ። ስለምን ብዙ ጌጥ የዝሙት መስተሀት የቀሬነት መሠረት በመሆኑ ተመስክሮለታል ። በመካከለኛው ዘመን አገረ ገዢዎች ባጀብ ሲሔዱ ነበረ የኋላ ንጉሥዎችና መኳንንቱ እስከሬንና የባላገር ሰርገኛ ይመስል ለምን ነው አጀብ ብለውናቁት፡ አጠየፉት፡ቀረ ። ወዲሁንም አጀብ ማብዛት ሥራ ማስፈታት አገር ማደኅየት ለታጃቢውም እንቅልፍ ማጣት አሳብ ማብዛት መሆኑ ታወቀ ። አለአጀብ መሔድ ግን ነውር መናቅ ትሕትና ማላቅ ነው እንጂ መኳንንቱን ከመዓርጋቸው ከመከብራቸው አይቀንስባቸውም ።

ስለዚህ ዛሬ በድፍን ኤውሮፓ ንጉሡ መኳንንቱ ባለጸጋው መሳፍንቱ እንኳን አጀብ አንድ አሽከር ማስከተል ብርቱ ጸያፋቸው ነው ። አጀብ እንዲህ ስለቀረ እርሻው ሰፋ፡ ንግዱ ለማ፡አገር ከበረ፡ችጋርና ድኻነት ጠፋ፡ ገበያው ጠገበ፡ለደኀው አለፈለት፡ፍትሕ አገኘ ፡ ንጉሦችም ከሕዝባቸው ፍቅር ክብር፡ እምነት፡ምስጋና፡ባንድ ላይ አገኙ ። ከዚህም ቀጥሎ ጥቂት በጥቂት ሲወርድ ሲዋረድ ሕዝቡ ራሱን የሚችልበት አገሩን ንጉሡን የሚደግፍበት እውቀትና ሥልጣኔ ከደረበት በኋላ በ፲፪፻፳ ዓመተ ምሕረት መጀመሪአ በንግሊዝ አገር ሕዝቡ ፈጽሞ ነጻነት አገኘ፡ቀጥሎ በፈረንሳዊ አገር በ፲፯፻፺፪ ዓመተ ምሕረት፡በኢጣልያ አገር በ፲፰፻፵፯ ዓመተ ምሕረት ለህዝቡ ነጻነት ተሰጠ ። ከዓለሙ ሁሉ በፊት የእንግሊዝ መንግሥት አስቀድሞ ለሕዝቡ ነጻነት ስለሰጠ ከዓለሙ ሁሉ በፊት መንግሥቱ ገነነ ሀብቱ በጣም ሰፋ ። ስለምን ነጻነት ያለው ሕዝብ ንግዱን ሥራውን እርሻውን አለአሳብ ጠንክሮ ለመያዝ ይመቸዋልና ነው ። ከዚያን ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሀብት የክብረት ላገር ለመንግሥት የሚጠቅም የኑሮና የደስታ መሠረት እርሻ ብቻ መሆኑ ታወቀ ከርሻ በላይ አንድም ነገር እንዳይገኝ የታወቀ የተረገጠ ነው ።

ታላቁ ገርማሜ

የደግ አድራጊ ስሙ የሚነግ፡ክብሩ የሚነግሥ፡ሐውልት የሚሠራለት ከሞተ በኋላ ነው በቁሙ ሳለ ግን ቁጥሩ እንዳንድ ሰው ነው ። ደጃች ገርማሜ የተማሩበትን ጊዜ የተማሩበትንም ስፍራ ሔት እንደሆነ ለማወቅ አልቻልም ። ብቻ ያሳባቸው ትክክልነት የርሻን መጥቀም ያጀብን አጥፊነት ዛሬ በኤውሮፓ እንደሚታወቀው ያህል ያውቁ ነበረ ። በትምህርት አይደለም በተፈጥሮ ነው ። በኤውሮፓ ያሁኖች ነገሥታት አጀብ መጥላታቸውን፡ለሥራ መትጋታቸውን ሳያውቁና ሳይሰሙ በፊት ታላቁ ገርማሜ በጦርነት ጊዜ ከሁሉ ቀድመው ሲገኙ በቀር በፊት በኋላቸው አጀብ ቢቀርባቸው አይወዱም ነበረ የሳቸው ጌጥና ኩራት ባሕር የመሰለ ቅብቅብ ያረረጌን ሰፈር ድንኳን የመሰለ ክምር ማየት ነበረ ። በደጋ በቆላ የነበረው እርሻ በያገሩ የነበረው ጉድጓድና ጕተራ እንኳን ለሌላ ለራሳቸውና ለምስለኔዎቻቸው ቁጥሩና ልኩ አይታወቅም ነበረ። በ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምህረት ከብት አለቀና ትልቅ ራብ ገብቶ ሰውን ይጨርሰው ጀመረ ። በዚህ ጊዜ እንኳን የሌላው ቤት የትልቁ ንጉሥ የዳግማዊ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ሳይቀር ተቸገረና ያዳራሽ ግብር ተደፈነ ጕተራው ተሟጠጠ የልፍኝ ግብር ጠበበ በቀን አንድ ጊዜ ሆነ ።

ይሔን ወሬ ታላቁ ገርማሜ በሰማ ጊዜ መጣና ለጃንሆይ እኔ ሳለሁ ግብር ለምን ይዘጋል ቤትዎስ ለምን ይቀዘቅዛል ፥ ቀለብተኛና ባለድርጎስ ለምን ይራባል ፥ እርስዎ ጉልበት እኔ እህል እሆናለሁ ያስጭኑ የቆላው ቢአልቅ የወይና ደጋው የወይና ደጋው ቢአልቅ የደጋው እህል አለኝ ሁሉም የርስዎ ነው ቀጥሎም የዘራሁት ይደርሳል አይስጉ አሉ። ጃንሆይም ደስ አላቸው። ሠራዊቱ ሁሉ እየታዘዘ በያገሩ እየሔደ የደለበውን እህል

ይጭን ጀመረ። ቤተ መንግሥቱ እንደ ገና ሞቀ ደመቀ። ትልቁ ለጋሹ ገርማሜ ለቤተ መንግሥት ብቻም አይደል ለየሻለቃው፣ ለሠራዊቱ፣ለደኀ ለሀብታሙ፣ ባይድ ዘመድ፣ታናሽ ታላቅ ሳይሉ፣ ጕተራቸውን ከፈቱለት ጠገቡ፣ አለፈለት፣ከመልካሙ ዘመን ደረሰ ዕድሜ ለገርማሜ አለ መረቀ ።

ጌጥ ማለት እርሻ ነው፣እጀብ አይደለም ጌጥ ማለት ደግነት ነው፣ኩራት አይደለም፣ ጌጥ ማለት መስጠት ነው ማግኘት ብቻ አይደለም ። ጽድቅ ማለት ለድኀ ማብላት ነው ቤተ ክርስቲያን ማዘውተር ብቻ አይደለም ፡ ይሔን ሁሉ ደግነት ሰብስቦ ይዞ የነበረ ታላቁ ገርማሜ ብቻ ነበረ ። በፈረንጅ አገር ሁኖ ቢሆን እንደገርማሜ ላለው ሰው ሰማይ የሚነካ ሐውልት በተሠራለት ነበረ ።

ነጋድራስ አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ።

በእግዚአብሔር ቸርነት በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ኃይልና በዘበኞቻቸው ትጋት የሆነ ቅጣት ።

በሰኔ ፲ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ለማክሰኞ አጥቢያ አንድ ሰውዬ መታፈሪያ የሚባል ከሲዳሞ የመጣ ነጋዴ እቃቂ ላይ ሞቶ ተገኘ የከተማ ዘበኞችም ሰምተው ሬሳውን አስቀብረው ግራዝማች አማረ የሞተበትን ምክንያትና የገደሉትን ሰዎች መመራመር ጀምረው በምርምር ብዛት ገዳዮቹ ተገኙ ስማቸውም አንደኛው መሻሻ አንደኛ ደግሞ ኩምሳ ይባላሉ እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ከሲዳሞ ከሟቹ ጋራ ለንግድ ብለው ባንድነት የመጡ ናቸው እነዚህም ሰዎች ከተመረመሩ በኋላ መሻሻ የሚባለው ከንደኛዬ ከኩምሳ ጋራ ሆነን በደንጊያ ቀጥቅጠን ገድለነዋል ብሎ አመነ ኩምሳም አስቀድሞ መሻሻ በደንጊያ ሲመታው አይቻለሁ ብሎ ካመነ በኋላ መልሶ ደግሞ አልገደልኩም አላየሁም ብሎ ካደ ከዚህም በኋላ ያንለት ባንድነት ነበራችሁ ስትለያዩ ምን ጊዜ ነው ተብሎ ኩምሳ ቢጠየቅ በጊዜ ነው ብሎ ስለተናገረ ለዚሁ በጊዜ ወደ ቤትህ መግባትህን የሚያውቅልህ አለ ወይ ተብሎ ቢጠየቅ አዎን ሶስት ሰዎች አሉኝ ብሎ ስላለ እነዚህ ሶስት ሰዎች በጊዜ አልገባም ብለው ቢመሰክሩብህ በደሙ ታልፋለህ ተብሎ ተጠይቆ ተፈሬደሙት አልፋለሁ ብሎ ከተፈጠመ በኋላ ሶስቱም ሰዎች በጊዜ አለመግባቱን በዚያ ቀንም በመጠጥ መሻሻን ከዚህም በቀር ምነው ዛሬ ከነከነኝ ያንን ወንድሜን ብር ይዟልና ሳይገድሉት አይቀሩም ብሎ መናገሩን ጭምር ስለመሰከሩበት በሐምሌ ፩ ቀን ከግርማዊ ችሎት ሁለቱም ቀርበው ከዚህ በላይ የተጻፈውን ሁለቱም ቃላችን ነው ብለው ካመኑ በኋላ የሟቹ ወገኖች ያስሞታችኋል ብለው ተፋርደው አደባባዩ በሙሉ፣ ፍትሐ ነገሥትም ትሞታላችሁ ብሎ ፈርዶባቸው ሁለቱም ወደ ወህኒ ወረደ። ዘበኞችም እንደዚህ ያለውን ደም ተመራምረው ባመጡበት ምስጋና ተቀብለው ኄደ. ቅዳሚት በ፲፫ ሐምሌ ደግሞ እነዚህ የተፈረደባቸው ገዳዮች ከገደሉበት ቦታ ላይ እንዲሰቀሉ ተብሎ ለዘበኛ ተሰጡ ።

ሁለተኛ በባሻ አባይረድ ክፍል ድጉማ ከሚባል ሰው ጋራ ሌቦች ባንድነት ሰርቀው ሲሔዱ ወልደ አማኔል የሚባል ዘበኛ ደርሰባቸው ሊይዛቸው ሲል በጩቤ ቢወጉት ድንጋጤ ሳይገባው ንጉሡንና መንግሥቱን ስለ ወደደ ይዟቸው ጓደኞቹ ዘበኞች ደርሰውለት ተይዘው ይህንኑም ተመርምረው አምነው እግርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርበው ሞት ተፈረደባቸው።

ሶስተኛ አብቶ ወልደ አሸባሬ ለሚባል ፈረስ ዘበኛ ንጉሥን አምና የከተማውን ዘበኞች ጠባቂነት ሳይጠራጠር ከቤቱ ተኝቶ ሌቦቹ ሔደው ክፈትልን ቢሉት አልከፍትም ምንድናችሁ ቢል ፈታሽ ዘበኞች ነን ቢሉት ሌሊት አትገቡብኝም ቢል እምቢ ብለው ስለከበቡት ዘበኞች ከሆናችሁ ምን አረጋለሁ ብሎ ቢከፍት ገብተው ቤቱን በርብረው ጠበንጃውን ወስደው ሌቦች መሆናቸውን አውቆ ቢከታተላቸው ተኩሰውበት የሚያደርገው አጥቶ ተጨንቆ ሲመለስ አቶ ኢዮብን አግኝቶ ለአቶ ኢዮብ ስለነገረው አቶ ኢዮብም ጭፍሮቹን አዘ በሱ ትጋት በዘበኞቹ ብርታት ተይዘው ይህንኑም ቃል አምነው እግርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርበው ሞት ተፈረደባቸው ።

አራተኛ ካንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ከሁለት ጊዜ ሦስት ጊዜ የሠረቁ ሌቦች በምስጢር በላይና በዘበኞቹ ብርታት ተመርተው ተገኝተው፣ ፵ አርባ ተገርፈው በቁም እስር ሆነው ሥራ እንዲሠሩ ተፈረደባቸው ። የነዚህም ፍርድ በለቶ ጊዜ ለሕዝቡና ለሹበኞቹ ለዘበኞቹም የሚያተጋቸውና የሚያበረታ የምስጋና ቃል ። ለሕዝቡም ቅጣቱን በገዛ እጁ ሕዝቡ እየለመነ አሳባችንን ሊያስጨክነው ነው ብለው ግርማዊ ንጉሥ ስለ አስረዱት የዘበኞቹም ትጋት ያጥፊውም ባሚገባ መቀጣት ጥበቃችን እየጸናልን ሔደ በማለት ደስ አለው ።

ለዚህም ሥራ ለረዱት ሹማምትና ወታደሮች የሚገባ ሽልማትና ጉርሻ ሰጥተው ግርማዊ ንጉሥ ደስ እንዳሰኙዋቸው ሰምተናል ። ከነዚህም ነፍስ አጥፊዎቹ ስለተሰቀሉ የከተማው ሕዝብ ደስታ እጅግ የሚያስደንቅ ነው።

ብርሃንና ሰላምም ለውነተኛ ፍርድና ለከተማ ዘበኞች ምስጋናውን ያቀርባል ።

ስለ ሻይ አታክልት ።

በምዕራብ ኢትዮጵያ የሻይ አታክልት እጅግ ውብ ሆኖ መብቀሉ ፥ሻይን አበቅቀል በሚያቁ በሚስተር ሆላንድ ተመርምሮ ታወቀ ።

ስለዚህ አሁን ክቡር ራስ ናደው ወትሮ በየለቱ ወደ ፊት በሥልጣኔ እየገፉ በሚሄደው ሥራቸውና ላገር ልማት ለይሉባቦር ሕዝባቸው በሚጠቀመው ነገር ለመርዳት ሁሉ ግዜ ናፍቆት ስላላቸው ወደ ህንድ (ኢንዲያ) አገር የሻይ ዘር ለማስመጣት ብዙ ብር ልከዋል ስለዚህ ይሉባቦር ከመላው ኢትዮጵያ በመጀመሪያ ብዙ የሻይ አትክልት የመላባት አገር ትሆናለች ።

የእንግሊዝ መንግሥት እንደሚያደርገው ሁሉ እንዲሁ በኢትዮጵያ ስለዚህ ስለ ሻይ ተክል አጥብቀው ቢያስቡበት እጅግ የተለየ ጥቅም ይሆናል ።

በእንግሊዝ ቅኝ አገር በከይሎን እህንድ አጠገብ ቀድሞ በብዙ አድርጎ ቡና ይበቅል ነበር ከዚያ በኋላ ግን ባገሩ ው

ሥጥ ሻይ መዝራት ተጀመረና ሻዩ ወደ ውጭ አገር ሂዶ እየተሸጠ ለሻዩ ዋጋ የገንዘብ ምላት አለመጠን ወደ አገሩ ውሥጥ ይገባ ጀመረ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሳይሎን የሻይ ዋጋ ባመት ባመት ሁለት መቶ ሚልዮን ብር ያገባ ጀመረ ። አሁን ግን የሳይሎን ሻይ ወደ ውጭ አገር ሂዶ እየተሸጠ ባመት ባመት ወደ ሳይሎን የሚገባው ብር ስድስት መቶ ሚልዮን ብር ነው ።

እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት የዚህን የሻይ ዘር ተክል በርትቶ እንደሚቀናና እንደሚከናወን አድርጎ ቢሠራው ለሀገሩ ለኢትዮጵያ ብዙ ሚልዮን ብር ባገባለት ነበር ።

ኃይሉ ለውጤ ጐሬ ።

ማስታወቂያ ።

እኔ ሚካኤል ማክራስ ቀበና እንግሊዞች ድልድይ አጠገብ ያለኝን ቦታዬን እሸጣለሁ፤ከቦታውም ላይ አንድ ትልቅ የማር ክዳን ሶስት ክፍል ቤት፤ አንድ የፋርኖ መጋገሪያ ቆርቆሮ ክዳን ቤት፤ አንድ ቆርቆሮ ክዳን የከብት ቤት፤፫፻፶የባሕር ዛፍ፤ የቦታውም ስፋት ፫ሺ ፮፻ አራት ማእዘን ሜትር ነው።ይኸንን ቦታ ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ እፊታውራሪ ግዛው በየነ ቤት በታች ያለው ቤቴ ድረስ ብትፈልጉኝ እገኛለሁ ።

ሚካኤል ማክራስ ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ከጀርመን ሌጋሲዮን የመጣ ራዲዮ ሐምሌ፲፬ ቀን የፅለት ወሬ

እንጎራ፤ አሮጌውን ከተማ በእሳት እንደተቃጠለና ከሰባት ሺ የሚበልጡ ቤቶች ወና እንደሆኑ ይወራል ።

ሎንዶን፤ ከቦኔስ አይሬስ ጋራ የሚገናኝ ቴሌፎን በሰኞ ይከፈታል ።

ከፈረንሳዊ ሌጋሲዮን የመጣየሐምሌ ፲፬ቀን የዕለት ወሬ

እንግሊዝ፤ ጆርጅ አምስተኛ የእንግሊዝ ንጉሥ ፈጽመው እንዲድኑ ቀርበዋል ።

የግብጽ ንጉሥ ትላንት ወደ ሎንድራ ገቡ ።

ከኢጣልያ ሌጋሲዮን የመጣ የሐምሌ ፲፬ ቀን የፅለት ወሬ ።

ትሬንቶ ፤ ብርቱ የእሳት አደጋ ተነሥቶ በጣም ስለበረታ እምሳ ቤት አቃጠለ ። አምስት መቶ የሚያሀሉ ሰዎች ቤት አጥተዋል ።

ዋሽንግቶን ፤ የፈረንሳዊ መላክተኛ በብሪያንድ ስም ሆኖ ለአሜሪካ መንግሥት ጦርነትን ለማገድ በመስኮብና በቺና መካከል ገላጋይነት እንደገቡ የልመና ማስታወሻ አቀረበ ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕራንት ባግዳሣሪያን ።

ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላቲን) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋውም ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

ማስታወቂያ ።

ስለ ትልቅ ሳልና ስለ ነቀርሳ የምክር ቃል በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታትሞ ይሸጣል ስለ ጤንነት ዋና ጥቅም ያለው መጽሐፍ ነውና እያንዳንዱ ሰው ሊይዘው የተገባ መጽሐፍ ነው ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

ጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተ ፫ ሙ
ሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር
ዘባድ	፩ ወቄት	፫ ብር
ነም	ፈረሲላ	፳፪ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	ፈረሲላ	፲፩ ብርተ፫ ሩብ
የወላሞ	ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፱ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፳፪ ብር
ባለሰይጣን		፻፳፪ ብር
፡ ፡ ባለ ድመ ።		፻፵፫
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፵
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፶
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪክ		፻፲፫
" " ጃፖን		፻፳፪ብር
ሱክር	ጁኒያ	፳፯ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ፵
ባአንድ ብር	፳ ሊሬ ከ ፺፩ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፷፪ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫

ማስታዋቂያ ።

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ። (ቤታቸውም ብአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፌያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው።

ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ደገኛል ቤቱም ክግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆን በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጸ ሰያ ስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድሬስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ፥ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናኝነት ፈቃድ የተቀበለ።

ΣΥΜΒΟΛΟΝ ΤΟΥ ΕΡΓΟΣΤΑΣΙΟΥ

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የለለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

ALEM

የወርቅ ሰዓት



ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ማስታወቂያ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och **Karlstad**

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል። የልብ።የደረት። የጉበት ። የኩላሊት። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

በማርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
5me ANNÉE № 31

ሐሙስ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 1 AOUT 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ላያተርፍ አይነግድ፡ላይተች አይፍረድ መባሉ ሰው ፍሬ በሌለው ነገር እንዳይደክም ማስረጃ ነው ።

ክቡር ነጋድራስ አፈወርቅ ከዛሬው ጊዜ ጋራ የሚመሳሰል መስሏቸው መካከለኛ ዘመን ብለው በሐምሌ ፲፰ ቀን በ፫ኛ ዓመት በቁጥር ፴ በወጣው ብርሃንና ሰላም ያሳተሙት ቃል ከጥቅሙ ጕዳቱ የሚበዛ መሆኑን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሳናስረዳ ብንቀር ሕሊናችን ይወቅሰናል ።

ክቡር ነጋድራስ አፈወርቅ ይህን ጋዜጣ ያሳተሙት በማርኛ ቋንቋ ብቻ ነውና መካከለኛ ዘመን ማለት ብቻ ይበቃቸው ነበር እንጂ መዲወ ኤቦ ወይም ሞየን አገ ማለት አያስፈልጋቸውም ነበር።ነገር ግን የኢጣልያና የፈረንሳዊ ቋንቋ ማወቃቸውን ለማስረዳት ይሆናልና ይኸን ብንዘለውም አያጕዳንም ።

እንግዲህ ክቡር ነጋድራስ አፈወርቅ በአውሮጳ አስመስለው ለተናገሩት ነገር ሁሉ በክፍል በክፍል እያደረግን እንመልስላቸዋለን ።

፩ኛ ክፍል ፤ መካከለኛ ዘመን የሚባለው ከ፬፻፸፮ ዓ ም ጀምሮ እስከ ፲፬፻፶፫ ዓ ም የነበረው ዘመን ነው።በዚህም ሁሉ ዘመን የአውሮጳ አገር ተከፋፍሎ በባላባትና በባለ ጕልት ፤ ማርኬዝ፡ኮንት፡ እየተባሉ ይገዙት ነበር።በኋላ ዘመን እውቀት እየሰፋ፡ሥልጣኔ እየበዛ፡ የባላባትና የባለጕልት ኃይላቸው እያነሰ፤ አገር እየተጠቀለለ በንጉሦች እጅ ሆነ ብለው ጽፈዋል ።

ምላሽ፤ይህነገር ነጋድራስ አፈወርቅ እንደሚሉት አይደለም፤ በመካከለኛው ዘመን አውሮጳን እጅግ ኃይላቸው የበረታ ነገሥታት ይገዙት እንደነበረ ከነጋድራስ አፈወርቅ በቀር የማያውቅ ሰው የለም።ነገር ግን እነዚህ ባላባቶችና ባለ ጕልቶች ከነገሥታቱ በታች እየሆኑ በየግዛታቸው ታፍረውና ተከብረው ይኖሩ ነበር ብለው ጽፈው በነበረ ነገራቸውን እውነት ብለን እንቀበላቸው ነበር ።

፪ኛ፤እነዚሁ ባላባቶችና ባለ ጕልቶች ባህርያቸው ሁሉ የኵራትና የመኵራራት ብቻ ስለነበረ በትልቅ ዓጀብ ተከበው፥ በሽልማ ታጥረው፥ በፊትና በኋላቸው እምቢልታ እያታለላቸው፥ ሙዚቃና ነጋሪት እያነቃቃቸው ፥ መሬት በተጠየፉች በሰጋር በቅሎ ተጀንነው፥ ደኃው እየሰገደላቸው እንደ አምላክ እያመለካቸው፤ይኖሩ ነበር፥ ብለው ጽፈዋል ።

ምላሽ፤ነጋድራስ አፈ ወርቅ ወደ አውሮፓ ሔደው ነበር እየተባለ ሲወራ እንሰማ ነበር በዚሁ አጻጻፋቸው ግን አውሮጳ ይቅርና ጂቡቲም የደረሱ አይመስሉም ። በአውሮጳም ንጉሡ ወይም የጦር አለቆች በሰልፍ በሚወጡበት ጊዜ እምቢልታው፥ መለከቱ፤በልዩ ልዩ ድምፅ እየተነፋ ፥ ነጋሪቱ በልዩ ልዩ ምት እየተመታ፥ በያውራው መንገድ ሲተላለፉ እጅግ ደስ ያሰኛል ሲሉ ሰምተናል፥ አይተናልም፥ ነገር ግን የእምቢልታውና የመለከቱ የሙዚቃውም የድምፅ ስልት ከዱሮው የበለጠ ሁንዋል ብለው ቢጽፉ እንኳ እውነት ነው ይባልላቸው ነበር እንጂ ዛሬ ይህ ሁሉ ቀርቷል ቢሉ የሚሰማቸው የለም።

መሬት በተጠየፉች በሰጋር ባቅሎ ተጀንነው ማለታቸውም በጭራሽ የእውነት ቃል አይደለም ። በዚያ ዘመን የተጻፈውን ታሪክ ስንሰማ በአውሮጳ የነበሩ ባላባቶችና ባለጕልቶች በፈረስ ወይም በሠረገላ ይቀመጡ ነበር ሲሉ አልሰማንም።

ነጋድራስ አፈወርቅ ግን በቀድሞዎቹ በአውሮጳ ባላባቶች ላይ የተነገረ መስሏቸው ሳያስቡት በድንገት በሰጋር በቅሎ የሚቀመጡትን የኢትዮጵያን ባላባቶች ተናግረው ይሆናል ። ስለሆነም በለውቀት ያደረጉት ነውና በዚህ ነገር ቂም የሚይዝባቸው የለም ።

ከሁሉም ይልቅ ደሀው ለባላባቶቹና ለባለ ጕልቶቹ እንደ ፈጣሪ እየሰገደላቸው እንደ አምላክ እያመለካቸው ደኖሩ ነበር ብለው የጻፉትን ቃል የማንም ልቡና እውነት ነው ብሎ

ሊቀበለው አይችልም ። ስለዚህም የአውሮጳን ነገሥታት ታሪክ አንብበናልና፣ ፈጣሪ ነኝና ስገዱልኝ፣ አምላክ ነኝና አምልኩብኝ ብሎ የተናገረ ንጉሥ ፣ ወይም ባላባት ስሙ ተጽፎ አላገኘንም ። ከሕዝቡም ወገን አገሌ ንጉሡን እንደ አምላክ አመለከ ተብሎ አልተጻፈም ።

ዳግም ነጋድራስ አፈወርቅ በኢጣልያ አገር ያማርኛ ቋንቋ ፕሮፌሶር ተብለዋል ሲባል እንሰማ ነበር እሳቸው ግን በዚህ አሁን በሳተሙት ጋዜጣ የአውሮጳ ባላባቶችና ባለ ጉልቶች ባህርያቸው የኩራትና የመኩራራት ነው ብለው ጽፈዋል። ባህርይ ማለት ለፍጡር ሲሆን በተፈጥሮ የሚያገኘው፣ የማይለየው ነገር ማለት ነው።

እንግዲህ እነዚያ የአውሮፓ ባላባቶችና ባለጉልቶች ኩራትንና መኩራራትን በባህርያቸው ካገኙት ነጋድራስ አፈወርቅ እንደነውር አድርገው ለምን ጻፉባቸው ። ማንም ሰው ቢሆን በተፈጥሮ የተሰጠውን ነገር ለመለወጥ አይችልም። ስለዚህ ነጋድራስ አፈወርቅ ባህርያቸው በማለት ፈንታ ሥራቸው፣ ልማዳቸው ብለው በጻፉ ይሻል ነበር ።

ደግሞ ገባሩንና ዜጋውን እነርሱ እንደ ዕንጨት ጠርበው፣ እንደ ጭቃ ጠፍጥፈው ፣ እንደሊጥ አሞልሙለው የፈጠሩት ይመስላቸው ነበር እንጂ ፣ እንደነርሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈጠረ አይመስላቸውም ነበር ያሉት ነገር፣ በጭራሽ የሐሰት ቃል ነው ። ማንም ንጉሥ፣ ማንም ባላባት ቢሆን ሰውን ልፍጠር ብሎ ያሰበና ያደረገ በዓለም ላይ አይገኝምና በዚህ ነገር በጣም እንደተሳሳቱ ጥርጥር የለበትም ።

ሦስተኛ ክፍል ፤ በነዚሁ በባላባቶችና በባለጉልቶች ዘመን ጸሐፊው ብርቅ፣ ፍርዱ ጭንቅ ስለነበረ ሁሉም ነገር በቃል፣ ሁሉም ነገር በቀላጤ ነበ፤ ፍርዱም መንገድ ለመንገድ ነበር፣ አንድ ጊዜ የተፈረደው ፴ጊዜ ይለወጥ ነበር ብለው ጽፈዋል ።

ምላሽ ፤ ክቡር ነጋድራስ አፈ ወርቅ ነገር ለማድነቅና ለማጋነን እንዲመቻቸው ነው እንጂ እኛ እንኳ እንደ ሰማነው ከ፭፻፳፰ ዓ ም ጀምሮ የፍርድ መጽሐፍ ተጽፎ ትልቁ ቄስጠንጢኖስ በፍትሐ ነገሥት ይፈርድ እንደነበረ ፤ ያውም እስከ ዘመናችን እንደደረሰ የታወቀ ነው ።

ፍርዱም ፴ጊዜ ይቅርና ሦስት ጊዜ እንኳ የተለወጠበት ጊዜ የለምና ነጋድራስ አፈወርቅ እገሌ ባላባት፣ እገሌ ንጉሥ የፈረደው ፍርድ ፴ጊዜ ተለወጠ ያሉትን ነገር ለማስረዳት እንዳይችሉ እርግጥ ነው ። የፍርዱ መጽሐፍ እየተሻሻለ ሔደ ቢሉ እንኳ ውነት ይመስል ነበር። ፍርዱም መንገድ ለመንገድ ነበር ስለማለታቸውም ምንም ማስረጃ አያገኙም ። ቢሆንስ እንኳ የተበደለ ደሀ ንጉሡን በመንገድ አግኝቶ ችግሩንና በደሉን ሲያመለክት ንጉሡ በመንገድ ላይ ለምን ደፈረኝ ያዙት እሠሩት ሳይል ባላጋራው እንዲቀርብለት፤የታሠረው እንዲፈታለት ቀላጤ ቢሰጥ ፣ ለሕዝቡ የሚራራ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ ንጉሥ ነው ተብሎ ያስመሰግነዋል እንጂ፣ በመንገድ ላይ የድኆች ጩኸት ሰምቶ ፈረደ ተብሎ አያስነቅፈውም ።

፬ኛ ክፍል፤ በአውሮጳ በዚያ ዘመን የነበረው የሰውም፣ የፈረሱም ጌጥና ሽልማት ባፍ ተነግሮ ፣ በጆሮ ተደምጦ አያልቅም ብለው ነቅፈው ከተናገሩ በኋላ እንደገና ደግሞ በጉራዴና በጋሻ በጦርም ጌጥ ማድረግን ፣ ቢብርና በወርቅ እቃ በተጫኘ በቅሎ መቀመጥን ነቅፈው ጽፈዋል ።

ምላሽ፣ ምናልባት ነጋድራስ አፈወርቅ በጣም የሚያውቁት የንግድ ሥራ ስለሆነ ይሆናል እንጂ የቤተ መንግሥትን ሥራ የተማሩና ያወቁ ቢሆኑ የጌጥን ነገር አይነቅፉም ነበር፤በአውሮጳም የጌጥ ነገር ቀርቷል ብለው የሐሰት ወሬ አያወሩም ነበር።

በአውሮጳ ነገሥታቱና መሳፍንቱ፣መኳንንቱና ሚኒስትሮቹ በቆባቸውና በልብሳቸው፣ በጉራዴያቸውም ላይ፣ የሚያጌጡትን የወርቅ ጌጥ ምናልባት ወደ አውሮጳ በሔዱ ጊዜ አላዩም ይሆናል ። የእንግሊዝ ንጉሥ ብቻ በዘውዳቸው ላይ እስከ ፩ ሚሊዮን ብ የሚያወጣ አልማዝ አለበት ይባላል ።

ደግሞ የየመሳፍንቱና የየመኳንንቱ፣ የየባላባቱ፣ሚስቶች እያንዳንዱ በየራሳቸ ና፣ በያንገታቸው፣በየጆሮአቸውና በየእጃቸውም የሚያጌጡት የአልማዝ ጌጥ ዋጋው አንድ አንድ ሚሊዮን ብር ይሆናል ሲሉ ሰምተናል ። በዚህም ላይ ደግሞ ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ካፒታኑ ድረስ በብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት ከወርቅና ከብር የተሠራ ኒሻን እንዲያጌጡ ከነጋድራስ አፈወርቅ በቀር የማያውቅ የለም።ደግሞ በአውሮጳ ይህ ሁሉ ጌጥ ቀርቶ የፈረስና የበቅሎ እቃ የጠፍር ሆነ ብለው ጽፈዋል። መቸም ነጋድራስ አፈወርቅ ተጨንቀው መጻፋቸው ገንዘብ በከንቱ እንዳይበላሽ አስበው ይሆናል ። ነገር ግን የብሩና የወርቁን መጣምር ከጠፍር እቃ ጋራ ዋጋውን ብናመዛዝነው የብር መጣምር ዋጋው እጅግ ቢበዛ እስከ ፶ ብር ነው፣ ወርቅ ቅብ መጣምርም እስከ ፻ ብር ነው።አሁን ከአውሮጳ የሚመጣው እጅግ ያማረው የጠፍር እቃ ግን ከ፪፻ ብር በታች አይገኝም።ስለዚህ የነጋድራስ አፈወርቅ ግምት ከንቱ መሆኑ ነው ።

፭ኛ ክፍል፤ ክቡር ነጋድራስ አፈወርቅ ጌጥ የዝሙት መስተዋት፣የቅሬኔት መሠረት ነው ብለው ጽፈዋል ።

ምላሽ፤በአውሮጳም፣በሌላውም ዓለም ቢሆን በቤተ መንግሥት ከንጉሡ ጀምሮ እስከ አምሳ አለቃ ድረስ፣ በቤተ ክህነትም ከጳጳሱ ጀምሮ እስከ ዲያቆኑ ድረስ ጌጥ ያለበት የማዕርግ ልብስ የማይለብስ የለም ። ስለዚህ ጌጥ የዝሙት መስተዋት፣ የቅሬኔት መሠረት ነው ከተባለ ፣ ጌጥ ከማያጌጡ ከነጋድራስ አፈወርቅ በቀር በዓለም ላይ ንጹሕ ሰው ይገኛል ለማለት የማይቻል ነገር ሊሆን ነው ።

፮ኛ ክፍል፤ ቀድሞ በአውሮጳ ባላባቶች ሁሉ ባጀብ ሲሔዱ ነበር አሁን ግን እስክሬንና የባላገር ሠርግ ይመስል ዓጀብ ለምንድነው ብለው አስቀርተውታል ብለው ጽፈዋል ።

ምላሽ፤ በበዓል ቀን፣ በሰልፍ ካልሆነ አይታጀቡም ብለው ቢሆን እንኳ እውነት ይመስል ነበረ እንጂ በጭራሽ ዓጀብ ቀረ ለማለትማ ማን እውነት ነው ብሎ ይቀበላቸዋል ። እነሆ በሲኒማ እንኳ ንጉሡም መኳንንቱም በጀብ እናያለን ። ደግሞስ እንደ ነጋድራስ አፈወርቅ ያለ ሰው ከሆነ በቀር ነገሥታትና መሳፍንት ብቻቸውን ይሔዱ ብሎ ለመፍረድ የሚችል ማነው፣ ብቻም በመሔድ ጥቅሙ ምንድነው።

፯ኛ ክፍል፤ ክቡር ነጋድራስ አፈወርቅ በመጨረሻ ቃላቸው ደጃች ገርማሚን እያመሰገኑ ጽፈዋል በዚያ ዘመን ም-

ንም የደጃች ገርማሜን ያህል ባይሆን እንኳ እንደባለጸግነታቸው ያገኙትን ያህል እየሰጡ ሕዝቡን መርዳታቸው አልቀረም ነበር።ግን የነዚያ ሰዎች ስማቸው ሳይነሣ የቀረበትን ምክንያት ጊዜው ሲደርስ ወደፊት እናስታውቃለን፡ ለሰው ሁሉ፥ ይልቁንም አውቃለሁ ለሚል ከሁሉ አስቀድሞ ያገሩን ታሪክ እንደምን እንደሆነ መመርመር ይገባዋል ።

ቀጥሎም የተወለደበትንና ያደገበትን የከበረበትንም አገሩን የክፉ ጊዜ ሥራ ምሳሌ ማድረግ አገርን መጉዳት እንደሆነ ማወቅ ይገባዋል ።

የኢትዮጵያ ነገሥታትና መሳፍንት፥ ባላባቶችና መኳንንቶች፥በዘመናቸው ለነበረው ችግር አገር ለማቅናት፥ ስለ ሃይማኖታቸው ከአረማውያንና ከእስላም ጋራ ለመዋጋት፥በአርበኞቻቸው እየታጀቡ፥ግብር እያበሉ፥ የማዕርግና የጌጥ መሣሪያ እየሸለሙ፥ ነጻነታቸውን ጠብቀው እስከ ዛሬ መኖራቸው ያስመሰግናቸዋል እንጂ እያስነቀፋቸውም።እንዲያውም ያልተማረ ሕዝብና የሕፃን አእምሮ እኩል ነውና ሥራ እንዲሠራ ቢያስተምሩት ነው እንጂ ሳይማር ይኸን የመሳሰለ የድፍረትና የማይገባ ቃል እየጻፉ ቢሰጡት መልካም አሳቡን ማበላሸት ፥ጌታና ሎሌውንም ማለያየት ነው እንጂ ሌላ ትርፍና ጥቅም አይገኝበትም ። ማወቅም አገርን በምክርና በትምህርት ለመርዳት ነበር እንጂ ለመንቀፍ አልነበረም ።

ክቡር ነጋድራስ አፈወርቅ ደጃች ገርማሜን እያመሰገኑ የደግ አድራጊም ሰው ስሙ የሚነሣና ሐውልት የሚቀረጽለት ከሞተ በኋላ ነው እያሉ ጽፈዋል ።እንግዲያው ምነው ስማቸው እንዲነሣ፥ከሞቱም በኋላ ሐውልት እንዲቀረጽላቸው፥በየባንኩ ካስቀመጡት ገንዘብ ለትምህርት ቤት ወይም ለሆፒታል እያሉ ጥቂት ጥቂት የማይሰጡለት ስለምንድር ነው ።

ደግሞም በአስመራ ብዙ እርሻና ብዙ እህል እንዳላቸው ሰምተናል ። እንግዲያው አምና አዝመራውን ለበላበት ለትግሬ ሕዝብ እንደ ደጃች ገርማሜ ፪፻ ዳውላ እህል እንኳ የማይሰጡለት ስለምንድር ነው ።

ነጋድራስ አፈ ወርቅ ከኢጣልያ አገር ወደ ሀገራቸው ወደኢትዮጵያ ከተመለሱ ወዲህ ለሀገናቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የረዱት በማስተማር ነውን፥ወይስ በተሾሙበት በነጋድራስነት ሥራ ነውን፤ ወይስ ለተቸገሩ ድኆች ገንዘብ በመስጠት ነውን።ካዚህ ሁሉ እንዳቸውን የሚያውቅ ሰው እንዳለ ቢያስረዳን ደስ ይለናል ።

ይኸንንም ሁሉ መጻፋችን የሰው አገር ታሪክ በመልመከትፋንታ ያገሩን አኳኋንና የሕዝቡን ችግር መመልከት አገር የሚለማበትን፥ ሕዝብ የሚበለጥግበትን፥ ጀግናው የሚረታበትን፥ የዘመኑ ልጆች ትምህርት የሚአገኙበትን ምክር መስጠት ነበረ እንጂ ጥቅም የማይሆን ምሳሌ ጽፎ ለሕዝብ መስጠት ይህን ተናገረ ይበሉኝ ከማለት በቀር በውሥጡ ሌላ አሳብ እንደሌለበት ለመረዳት ብለን ነው ።

እኛ ግን ለወንድሞቻችን ለኢትዮጵያ ሰዎች የምናመለክታቸው ገንዘብ ያላቸው ባለጠጎች ከገንዘባቸው እያዋጡ የትምህርት ቤት እንዲከፍቱ ፤ በትምህርት ቤትም የሚገቡ ልጆች ያለፉትን አባቶቻቸውን ሳይነቅፉ ወደፊት ተምረው የኢትዮጵያን ነጻነት የሚጠብቁበትን፥ንጉሣቸውን ለመውደድና ለማገልገል የሚበቁበትን እንዲማሩ ነው።ያለፉትን አባቶቻቸው ሳይነቅፉ ማለት ኖረው ቢሆን ባጀብ ለመሔድ ሽልማት ጌጥ ላርበኞቻቸው እንዲሰጡ ያስፈልጋቸው እንደነበረ ሊያስረድዋቸው ይችሉ ነበርና አሁን ባልተረዱትና ባላወቁት ነገር ሊነቅፍዋቸው አይገባቸው ማለት ነው ። ባላ ተክለ ማርቆስ ።

ከውሻ መታመም ስለሚመጣው ጉዳት ።

ከዚህ አስቀድሞ ብርሃንና ሰላም አምስተኛ ዓመት ፳፮ኛ ቁጥር ፪፻፰ ገጽ የእርሻ ሚኒስቴር የክብት ሐኪም ሙሴ ሚሀራን ከይማኪያን የታመሙ ውሾች ሰውንና እንስሳን የሚጐዱ ስለ ሆነ ከዚሁ ጉዳት ለማዳን የሚያስፈልገውን ነገር በሚያስረዳ ጽፈው አስታውቀው ነበር ። ዛሬ ግን በከተማ ውሥጥ ብዙ ውሾች እያበዱ ሰውንና ከብቱን ከምንከሣቸው የተነሣ ከትልቅ እስከ ትንሽ ድረስ ሰው ሁሉ መጨነቅና መጠበቡን እናይም እንሰማም አለን ።

የዚህም ነገር እጅግ የሚያስገርምና የሚያሳዝን ነው። ማለት እጅግ ሀብታሞችና በልተው የሚያተርፉ፥ ራሳቸውን የቻሉ ሰዎችም ይሁን ውሻ ያሳድጉ። እነዚያውም ቅሉ ከተረፈን ብለው ቢያሳድጉ ቀጥተው አሥረው ሊያኖሩ ቢታመም ለሀኪም ሊያሳዩ ይገባል እንጂ ስድ መሥደድ አይገባቸውም ። እረ በልቶ የማያተርፍ ሰው እንዴት ውሻ ያሳድጋል። ትለብሰው የሌላት ትከናነበው አማራት እንዲሉ ከሀብታሞቹ ይልቅ ድኖቹ ብዙ ውሾችን ያሳድጋሉ። ይህም ሁሉ ጊዜ በራሥ ላይ ፍርድን መሸከም ነው። ባገር ቤት ያለ ሰውስ ድኃ እንኳ ቢሆን ውሻ ማሳደጉ ጠጣ ዝንጀሮ ይጠብቅልኛል ብሎ ነው ። የከተማ ደኃ በሬ አይደል እያርሰው፥ላም አይደለ እያልበው፥ ሲያገኝ ሰርቆ ይብላ ሳያገኝ እከክ ወርሶት እየተቈረመደ አገር ያበላሽ፥ እያለ ብዙ ብዙ ውሻ መንዳቱ ስለምን ይሆን ? በዚሁም ላይ ዋና የሌላቸው ከየባላገሩ የሚሰበሰቡ ውሾች እጅግ ብዙ ናቸው።

ስለዚህም በሥራቸው ሁሉ የተመሰገኑ የከተማ ጠባቆቻችን በዚህ ነገር አጥብቀው እንዲተጉበት እናሳስባቸዋለን።ነገር ግን የነዚህ ውሾች ነገር በሥርዓት ካልሆነ የከተማው ሰው ጉዳቱ እንዲበዛ ጥርጥር የለበትም ።

ስለ አዲስ ዓለም መንገድ ማስታወሻ ።

ትልቁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ የሠሩት ታላላቅ ቀዋሚ ሥራ ሁሉ እጅግ ብዙ ስለሆነ አሁን እኔ ጽፌ የምዘልቀው አይደለም ።

ዳሩ ግን ከንደኛው ሥራቸው ውሥጥ በጊዜ ብዛት ያረጀው የአዲስ ዓለም መንገድ እንደታደስ ስል ማስታወሻዬን ከዚህ ቀጥዬ አመለክታለሁ ።

የአዲስ ዓለም መንገድ ከዳግማዊ ምኒልክ አንሥቶ እስካሁን ድረስ በበርና ጋሪ፥ አቶመቢልና ካሚዮን ሲመላለስበት የሚኖር ትልቅ መንገድ መሆኑን ሁሉም የሚያውቀው ነው ። አሁን ከሁለት ዓመት በፊት ልዑል ዱክ ዴዛብሩዝ አገራችንን ለመጐብኘት በመጡ ጊዜ በግርማዊ ንጉሥ ትእዛዝ የሥራ ሚኒስቴር መንገዱንና ሶስቱን ድልድዮች ስለ አሳደሰና ምናም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታቱና ግርማዊ ንጉሥ ሠራዊታቸውን ይዘው

የገፈርሳን ድልድይ ስለሠሩት ለባቡርና ለጋሪ፥ለካሚዮንና ለአቶመቢል የተመቸ ሁንዋል ። በዱሮው ጊዜ ከበርቴ በበቅሎ፥ ደኃ በእግሩ፥መሔዱ ግድ ነውና አዲስ ዓለም ደርሶ ለመመለስ የሁለት ቀን ድካም ያስፈልገው ነበር ። አሁን ግን በግርማዊ ንጉሣችን ትጋት ፥ ባገራችን እውቀት መስፋት ስለጀመረና በከተማው አቶመቢልና ካሚዮን እየበዛ ስለሔደ፡ ከበርቴው በአቶመቢል፥ ደኃው በካሚዮን እየሆነ አዲስ ዓለም ደርሶ ለመመለስ እጅግ ቢበዛ ከ፯ሰዓት አይበልጥም ። ስለዚህ በከንቱ ይባክንብን የነበረው ክቡር ጊዜያችንና ድካማችን ስለቀረልን ለኛ ለሕዝቡ ታላቅ ጥቅም ነውና ። አስቀድመን ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክን፥ ሁለተኛ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትንና ግርማዊ ንጉሣችንን ብጣም ልናመሰግናቸውና ልንመርቃቸው ይገባናል ።

ከሁን ፊት የታደሰው መንገድና ድልድይ የበሰ የባሰው ታይቶ ለጊዜው ያስፈለገውን ነው እንጂ ወደፊት (ለዘለቃው) እንዲቈይ ሁኖ እንደሚገባ በመላው ስላልታደሰ ብዙ የላሉ (የተሰነጠቁ)ድልድዮችና የተበላሹ መንገዶች ሞልተዋል ። ይልቁንም ከትልቁ ወንዝ ከገፈርሳ ወዲህ ማዶ ወደ አፋፍ ብቅ መበያ (መዝለቂያ)ላይ ያለው ፈፋ ወሀው የመንገዱን ግራና ቀኙን አፈሩን እየሸረሸረ ስለወሰደው በጣም ተበላሽቷል ። አሁን የቀረውም መንገድ ስፋቱ ከሁለት ሜትር ተኩል አይበልጥም ። እንዲያውም አሁን ዘንድሮ በፍጥነት ካልተሠራ ጊዜው ክረምት ስለሆነ የመንገዱን ግራና ቀኝ ወሀው በልቶ ይጨርሰውና በጭራሽ ሳይናድ አይቀርም ይመስለኛል ። ስለዚህ ባቡርና ጋሪ፥ ካሚዮንና አቶመቢል ሊያልፍበት አይችልምና ከላይ የተናገርነው የሕዝቡ ጥቅም ይጎድልበታል ።

መቼውንም መንግሥታችን ዋናው ፍላጎቱ አገሩ እንዲለማ፥ ሕዝቡም እንዲጠቀም መሆኑ አይጠረጠርም ። ለአገር ልማትና ለሕዝብ ጥቅም የሚሆን አንዱ ዋናው ነገር መንገድ መሆኑ የታወቀ ነውና ይህቺን ማስታወሻ ተከትሎ የአዲስ ዓለምን መንገድ የተበላሸውን ሁሉ በመሐንድስ አስመርምሮ ካሁኑ የበለጠ አድርጎ ለዘለቃው እንዲሆን በመላው መንግሥታችን እንዲአሳድሰው ተስፋ እናደርጋለን ። ካሁኑ ፊትም ይኸው መንገድ እንዲታደስ ግርማዊ ንጉሥ አስበው ሕዝቡ ገንዘብ እንዲያዋጣና በመላው እንዲታደስ ትእዛዝ አድርገው ገንዘቡም እየወጣ ሥራውም መሠራት ተዠምሮ ነበር ። ነገር ግን እስከሁን አልተፈጸመምና፥በዚሁ ሐሳብ ሥራው በቶሎ ቢፈጸም የተሻለ ይሆናል ስል በሕዝቡ ስም ሁኜ አስታውሳለሁ ።

ለዚሁም ለጻፍኩት ማስታወሻ እንደኔ ያለ አንድያ ሰው ሁሉ ጥቅም የመሰለውን ነገር ሁሉ ጽፎ ለማስታወቅ እንዲችል ብርሃንና ሰላም ለሰጡን ጌታችን የማቱሳላን ዕድሜ እግአብሔር ይስጥልን ብዬ ነገሬን እወስናለሁ ።

ተስፋዬ ካሣ ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ከጀርመን ሊጋሲዮን በመጣ ራድዮ በሐምሌ ፲፰ ቀን የሮማ ጳጳስ የቅዱስ ያዕቆብ ሐዋርያን በዓል ለማክበር ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው በደረሰ ጊዜ የከተማው ሰው ሁሉ ወደዚያው ተሰበሰበ ፡ የቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ ደወል ተደወለ፥ሀያ ሺ የሚያህሉ ከየወገኑ ወታደር ተሰልፈው ለጳጳሱ የተገባ ሰላምታ ሰጡ። በዓሉን ለማክበር መቶሺ ሰው ተሰብስቦ ነበር ። ግሩም የሆነ ዝማሬና ቅዳሴ ፀሎትም ተደረገ የሚል ወሬ ሰማን ።

ማስታወቂያ ።

እኔ ሚካኤል ማክራስ ቀበና እንግሊዞች ድልድይ አጠገብ ያለኝን ቦታዬን እሸጣለሁ፥ከቦታውም ላይ አንድ ትልቅ የሣር ክዳን ሦስት ክፍል ቤት፥ አንድ የፍርኖ መጋገሪያ ቆርቆሮ ክዳን ቤት፥ አንድ ቆርቆሮ ክዳን የከብት ቤት፥፫፻፶ የባሕር ዛፍ፥ የቦታውም ስፋት ፫ሺ ፮፻ አራት ማእዘን ሜትር ነው ። ይኸንን ቦታ ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ እፌታውራሪ ግዛው በየነ ቤት በታች ያለው ቤቴ ድረስ ብትፈልጉኝ አገኛለሁ ።

ሚካኤል ማክራስ ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ያዲስ አበባ የግሪክ መንግሥት ቆንስል ጄኔራል ቤት የሙሴ አስታሰቢያ ሱኒዬስን አበዳሪዎች ለሆኑት ከዛሬ ጀምሮ እስከ ፫ ወር ድረስ ሰነዳቸውንና ሌላውንም የማስረጃ ወረቀቶቻቸውን ሁሉ ይዘው እንዲቀርቡ ያስታውቃል ።

ከዚህ ከተቆረጠው ቀን ያለፈ የቆንስላ ጄኔራል ቤት አቤቱታቸውን ሊቀበል አይችልም ።

፲፱፻፳፭ ዓመት ሐምሌ ፳፪ ቀን ተጻፈ ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕራንት ባግዳሣሪያን ።

ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋውማን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቀዳሚ ቀዳሚ ነው ።

ማስታወቂያ ።

ስለ ትልቅ ሳልና ስለ ነቀርሳ የምክር ቃል በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታትሞ ይሸጣል ስለ ጤንነት ዋና ጥቅም ያለው መጽሐፍ ነውና እያንዳንዱ ሰው ሊይዘው የተገባ መጽሐፍ ነው ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሜበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፈርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።

አቡካት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ብአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጩት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ፡

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባትሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።



COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሪስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ ሕገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

ALEM

የወርቅ ሰዓት



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዲቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፈኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል። የልብ። የደረት። የጉበት። የኩላሊት። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንጂ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤትነው።

ጉድይር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
5me ANNÉE № 52

ሐሙስ ነሐሴ ፪ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 8 AOUT 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous lés Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣቱት አፈለገ ፱፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numèro 2 piastres

የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሽልማት ።

ሐምሌ ፳፯ቀን የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትምህርት የበለጡት የሚሸለሙበት ቀን ስለ ሆነ ተማሪ ቤቱ ከውጭው እስከ ግቢው ልዩ ልዩ መልክ ባለው ጌጥና አበባ ተጌጦ ነበር ። ትማሪዎቹም ሲሸለሙ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ወደ ተማሪ ቤቱ እንዲመጡ ታውቆ ነበር ። የውጭ አገርም ሚኒስትሮችና ወይዛዝሮች፥ መኳንንትም፤ የኢትዮጵያም፥ ሚኒስትሮችና መኳንንት የተማሪዎችን ሽልማትና ደስታ ለማየት ተጠርተው በስምንት ሰዓት ተኩል መጡ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም በክቡራን መኳንንቶቻቸውና ሠራዊታቸው ታጅበው ወደ ተማሪ ቤቱ በደረሱ ጊዜ ተማሪዎቹ በሰልፍ ተቀበልዋቸው ። ያገር መዝሙር ተዘመረ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም በቤቱ ገቡና አምሮ በተሰናዳላቸው ዙፋን ተቀመጡ። የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳት ፥ ሚኒስትሮችና መኳንንትም፥ እንደየመዓርጋቸው ተቀመጡ። ከዚህ በኋላ ያገር ግዛትና የትምህርት ቤቱ ሚኒስትር ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ቀጥሎ ያለውን ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት
ግርማዊ ንጉሥ ሆይ

ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዓን ጳጳሳት ክቡራን ሚኒስትሮች ወይዛዝሮችና መኳንንቶች ።

፩ኛ፤ ይህ በታላቁ ንጉሠ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ስም የቆመ የትምህርት ቤት በሥራው እንደዚህ በመሻሻሉና የኢትዮጵያም ልጆች በትምህርት እየተጉ፥ በቁጥር እየበዙ መሔዳቸውን እያየን ደስ ብሎናል ።

፪ኛ፤ በዚሁም ላይ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የአባታቸውን የታላቁን ንጉሠ ነገሥት የዳግማዊ አፄ ምኒልክን ትክክል ሐሳብ ተከትለው ይህን ተማሪ ቤት እንዲሻሻል በማድረጋቸው ብዙዎችን ደስ የሚያሰኙ ሆነዋል ።

፫ኛ፤ ይልቁንም ለሀገር ልማትን፥ ለሕዝብ ጥቅምን የሚአተርፍ ትምህርት እንደሆነ ግርማዊ ንጉሥ ተረድተዉት፥ አገረ ገዦዎች ታላላቆች ተማሪ ቤቶችን በየግዛታቸው እንዲአቆሙ ፥ ልጆች ያሉአቸውም ልጆቻቸውን ለትምህርት እንዲአስገቡና እንዲአስተምሩ ደጋግ ሐሳብዎን ሁሉ እየገለጹ በየጊዜው የሰጡንን ምክርዎን ከቶ አንዘነጋውም።

፬ኛ፤ ይኸውም እርግጠኛው ተበቶ ያለው ጥሩ ምክርዎ ሕሊናችንን እያንቀሳቀሰው አገራችን ኢትዮጵያ ልማትን እንድታገኝ፥ የተባረከ ሕዝቧ ሐሳቡን ለትምህርት ባንቀሳቀሰበት በሁኑ ጊዜ የግርማዊ ንጉሥን ቀና የሆነ መልካም ሐሳብዎን ሁሉ እየተከተልን በያለንበት የትምህርትን ሥራ ለማስፋት ብንጣጣር ከሁሉ የበለጠ ጥቅማችን መሆኑን መርምረን በግልጥ ተረድተነዋል ።

፭ኛ፤ ሰው ለጥቅሙ መሆኑን ተረድቶት ሊሠራውና ሊአከናውነው የሚያስፈልግ የተገባ ሥራ መሆኑን ተገለጸለት ይኸውም በሚገባ ሊሠራው ያለ ሥራ ለጥቅሙ መሆኑን ከተረዳው ዘንድ ሊሠራበት የተሰጠውን ጊዜውን ሳይሠራበት በከንቱ ቢአሳልፈው እየቆየ ጸጸት ሳይሆንበት አይቀርም ።

፮ኛ፤ ስለዚህ እኛም ይህነን ልንሠራበት የተሰጠንን ጊዜ የምንሠራ መስሎን በከንቱ ብናሳልፈው ወደፊት የሚወለዱት ልጆቻችን የግርማዊ ምክርዎንና ሐሳብዎን እያስታወሱ ሳይወቅሱን አይቀሩም ።

፯ኛ፤ማንም ቢሆን ልጁን ካለመማር ወደ መማር አልፎ፥ ካለማወቅ ወደ ማወቅ እንዲደርስለት የማይመኝ ሰው ይገኝ አይመስለኝም ። እንግዲህ ይህነን ደገኛውን ነገር ከተመኘው እህል የሚዘራ ገበሬ አርሶ፥ ቀብቅቦ፥ መሬቱን አለስልሶ፥ የዘና-

ምን ወራት ተጠባብቆ፥ በጊዜው እንዲዘራና በቃያውን ጠብቆ እሸቱን አይቶ ሲያፈራለት ያዝመራውን ማማር እየተመለከተ መከር ሲደርስ አጭዶ፥ወቅቶ ሲያመርት ፡ ምርቱን አይቶ ደስ እንደሚለው ሁሉ፥ ልጅ ያለውም ሰው በሕፃንነቱ ወራት ጊዜውን ተጠባብቆ ከተማሪ ቤት ቢያስገባውና እንዲማር ቢያደርገው ተምሮ አውቀትን ቢያገኝለት እጅግ ደስ እንዲለው ያለጥርጥር ይታወቃል ።

፰ኛ፡ የተማረ የድኃ ልጅ በትምህርቱ እንዲከበር፡ ያልተማረ የጌታ ልጅ ባለመማሩ እንዳይከበር መሆኑን የሚስተው የለም ። የሚአከብረውን ትምህርት እንዲማሩላችሁ ብዙዎች ወንዶች ልጆቻችሁን ወደ ተማሪ ቤት በማስገባታችሁ ምስጋና ይገባችኋል ።

፱ኛ፡ ስለሆነ ወንዶች ልጆቻችሁን እንድታስተምሩ፥ ሴቶች ልጆቻችሁንም በጊዜአቸው ትምህርት እንዲማሩ ብታደርጉላቸው የተገባ ነውና ምስጋናችሁ ሰፍፍ እንዲሆን የተረገጠ ነው ።

፲ኛ፡ የተማረ ወንድ የተማረች ሴት መሰሉን ካላገኘ ከልተማረችው ጋራ ኑሮውን በሙሉ በመጻጻት በከንቱ ያሳልፈዋል። ተስፋ እንደሚያደርገውም በእውነተኛው በክርስቲያን ጋብቻ በትክሊል ሊጋባ የሚመኘው ምኞት ሳይፈጸምለት ተሰናክሎበት ይቀራል ።

፲፩ኛ፡ ስለዚህ ከዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት፥ ከተፈሪ መኰንንም ተማሪቤት የሚማሩትን ሕፃናት የሚያሳዩትን ፍሬ እየተመለከታችሁ ወንዶችም ሴቶችም ልጆች ያሏችሁ ሁሉ ሐሳባችሁን ባንድነት አስተባብራችሁ ወደ ተማሪ ቤት እያስገባችሁ እንድታስተምሩና ተማሪቤቶችንም በየአውራጃችሁ እርዳታ እያደረጋችሁላቸው በያለንበት ሁላችንም ብንጣጣር የተሻለ ነው ።

፲፪ኛ፡ አሁን በቅርብ ጊዜ ስለዚህ ስለ ትምህርት ምክንያት በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በግርማዊ ንጉሥ ሐሳብ ተማሪ ቤቶችን በሚአስፈልጋቸው ሁሉ የሚደግፍና የሚረዳቸው፥ ሥራቸውንም እያለማ የሚያስተዳድራቸው፥ ሕፃናትም በያሉበት ለትምህርት እንዲገቡ የሚያነቃቃና የሚያስገድድ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ስለቆመ ሥራውን በትክክል ለማስኬድ የሚያስፈልገውን ደምብና ሕግ እያደራጀ ሊያወጣ ጀምሯል። አሁንም ይህ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ሥራውን እንዳሰበውና እንደ ወጠነው ሐሳብ እየፈጸመው ከሔደ ለወደፊቱ ተማሪቤቶች በቁጥር እያደጉና በያሉበት የኢትዮጵያ ልጆቹ ተምረው ለሀገራቸው እራሳቸውን የቻሉ ብዙ አገልጋዮች እንዲገኙላት ተስፋ አለን ።

፲፫ኛ፡ በዚህም ባለፈው ዓመት ውስጥ የአስተማሪዎቹ ትጋትና የተማሪዎች በትምህርት መራመድ ካለፉት ጊዜያት በጣም የተራራቀ ሆኖ ስለአየሁት የተማሪቤቱን ዲሬክተርና መምህራኑንም በተለየ አመሰግናቸዋለሁ ።

፲፬ኛ፡ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ። ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት፥ ብፁዓን ጳጳሳት፥ክቡራን ሚኒስትሮችና ወይዛዝሮች ፥ መኳንንቶች ዛሬ የትምህርት ቤታችንን በዓል ለማክበር ስለመጣችሁልን እጅግ ደስ ብሎን ከልባችን ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እናቀርብላችኋለን ።

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሀብትና ልማት፥ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ረጅም ዕድሜ ሰጥቶልን ምኞታችንን ሁሉ እንዲያስፈጽመን ስል ሙሉ ተስፋ አደርጋለሁ። ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ደሀንንም ተናግረው ሲጨርሱ በጣም ተጨበጨበላቸው።

ቀጥሎም የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ሙሴ ዋዲዘኪ መልክም ንግግር ተናገሩ ።

ከዚህ በኋላ በእንግሊዝ ትምህርት የበለጡት ልጆች እንደ የማዕርጋቸው የሚገባቸውን ሽልማት ተቀበሉ ። በዚህም ጊዜ ተማሪዎቹ በፈረንሣዊ ቋንቋ መልክም ጨዋታ አሳዩ። ቀጥሎም የኢጣሊያ ቋንቋ የተማሩ ልጆች እንደ ማዕርጋቸው ተሸለሙ።ደግሞም አንድ ልጅ በእንግሊዝ ቋንቋ መልክም የሆነ ንግግር ተናገረ ። ይህም ከሆነ በኋላ የሻይ ግብዣ ተደረገና ተማሪዎቹ በአማርኛና በፈረንሣዊ ቋንቋ እየዘመሩ ሰውን ሁሉ ደስ አሰኙት ። ቀጥሎም ተማሪዎቹ በሙዚቃ እየተመሩ ጅምናስቲክ አሳዩ ። የኢጣሊያ ቋንቋ ተማሪዎችም በኢጣሊያ ቋንቋ መልክም የሆነ ጨዋታ አሳዩ ። ከዚህ በኋላ በፈረንሣዊ ቋንቋ በትምህርት የበለጡት እንደየ ማዕርጋቸው የሚገባቸውን ሽልማት ተቀበሉ።የተሸለሙ ተማሪዎችም ሁሉ የትምህርት ቤቱን ሽልማት ከተሸለሙ በኋላ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ከግርማዊ ንጉሥ፥ ከሊቀ ጳጳሱም ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ልዩ ስጦታ ተቀበሉ ።

ከዚህ በኋላ በፈረንሣዊና በማርኛ ትያትር ተደረገ ። በጉባኤውም መሐከል አንድ ልጅ ተነሣና ስለ ፍቅር በማርኛ ቋንቋ መልክም የሆነ ስብከት ተናግሮ ሰውን ደስ ባሰኘ ጊዜ ረጅም ጭብጨባ ተጨበጨበለት ። ከዚህ በኋላ ሥርዓቱ ሁሉ ተፈጽሞ ሚኒስትሮቹና መኳንንቱ፥ወይዛዝሮቹም ሁሉ እየተሰነባበቱ ሔዱ።ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም ባማረ ዓጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥና በዙሪያውም ስለገባው ፒሮፕላስሞዝ የሚባል የፈረስ የበቅሎና ያህያ በሽታ ።

ፒሮፕላስሞዝ የሚባለው የፈረስ በሽታ በደቡብ አፍሪካና በምዕራብ አፍሪካ ልዩ ዓይነት ሆኖ የሚዘዋወር በሽታ ነው ። በአውሮፓ ውስጥ ግን ምንም ያህል አይገኝም ይኸውም በሽታ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ገብቶ ከዚህ በላይ በተጠሩት ከብቶች ላይ ብርቱ አደጋ መጣል ከጀመረ ጥቂት ቀን ሆኖታል ።

በየቀኑም ከዚሁ በሽታ የተነሣ የታመሙ ከብቶች(በቅሎና ፈረስ)ሳላገኝ ይልቁንም በዚሁ በሽታ የሞቱ ከብቶች ጥምብ በገበያ በየመንገዱና በየፈረፋሩም ውስጥ ሳላይ ቀርቼ አላውቅም ።

የዚህም በሽታ መሠረቱ ጥሮፕላስማ ኤኪ. የተባለ በቀዩ ደም ሥር ውስጥ ገብቶ የሚዘጋው ነው ። በዝናም ወራት ይልቁንም ክረምት ሲገባና ሲወጣም ቢሆን ይኸው በሽታ ይነሣል ። አንዳንድ ጊዜም የፀና ሆኖ የሚያስፈራ አደጋ ይጥላል ።

ይኸውም በሽታ የሚተላለፍበት ዋናው ምክንያት በመጋገር በዝምብና በትንኝ ነው ደግሞ በከብቶቹ ካንዱ ወዳንዱ አገር መዛወር ፤ በጨፌ ውሥጥ በመጋጥ ፤ በድካም ፤ ጾዳት በማጣት ፤ የሚበቃ ምግብ ካለማግኘት የተነሣ ነው ። ይልቁንም የክረምት ወራት ለዚሁ በሽታ ዋና በር ከፋች መሆኑን መገንዘብ የሚያስፈልግ ነው ።

የበሽታው ምልክት ፤ በሽታው በጀመረ ጊዜ እያንቀጠቀጠ ያተኩሳል ፤ ሕመምተኛው ይደክማል ፤ ትንፋሹ ይቃትታል። የልቡም አመታት የበረታ (የከፋ) ይሆናል ፤ በፍጥነት የሚዘዋወርና የሚገለጥ የሆነ እንደሆነ እዳሪውን ያደርቀዋል ፤ በዝግታ የሚተላለፍና የሚገለጥ ሲሆን ግን ያስቀምጠዋል ፤ ከብቱም ያንጊዜውን ይከሳል ከሰስትና ከራት ቀን በኋላ ግን ሞት ይመጣበታል ፤ በሽታው በዝግታ የሚሔድና የሚተላለፍ በሆነ ጊዜ እንደበሽታው ኃይል ይሆናል ፤ የታመመው ከብት የዳነ እንደሆነ ለማገገሚያ ብዙ ጊዜ ያስፈልገዋል ።

የሚያስፈልገው ነገር የሚቻል ቢሆን ከብቶችን ካንዱ ወዳንዱ አገር ከማዘዋወር መጠንቀቅ ነው ። ይልቁንም ከከፍተኛ አገር ወደዝቅታ ውሥጥ አለመውሰድ ነው ። በሽታው በገባበት አገር የጽዳትንና የምግብን መጠን እንደተቻለ ያህል ማብዛት ነው ፤ ጨፌ ከማጋጥ መጠንቀቅና ማራቅ ነው ፤ የሚጠጣውም ውሀ የጠራ መሆኑን መጠበቅ ነው ፤ መጋገርን ዝንብና ትንኝን እንደተቻለ መጠን ለማጥፋት መበርታትና መጣጣር ነው ። ከብቶቹ በታመሙ ጊዜ ከጋጣ አለማስጣት ነው ። ጋጣውንም ንጹሀ ማድረግ ነው ፤ በየጊዜውም ከመቶ ሐያ የሚሆን ክሬዚል የተባለ መድኃኒት ማድረግ ነው ።

ከዚሁ በሽታ ጽናት የተነሣ የሞቱትን ከብቶች ጥምብ መቅበር ነው እንጂ በየስፍራው ወይም በየፈረፈሩና በየጉድባው ውሥጥ አለመጣል ነው ።

ለማዳን የሚሆን በሽታው በጀመረው ጊዜ የከብት ሐኪሙ በሚጠጣ ወይም በደም ሥሩ ውሥጥ ተጠግቶ በሚገባ መድኃኒትም ቢሆን ለማዳን ይቻለዋል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የርሻ ሚኒስቴር
የከብት ሐኪም ሚሀራን ከይማኪያን ።

ስለ እህል ጠላት ።

ነቀዝን ለማጥፋት ትንሽ ምክር ላመልክታችሁ ለወንድሞቼ በጣም ላስቸገራቸሁ ።

እህል ከጐተራ ውሥጥ የነቀዘ እንደሆነ በመጀመርያ ጐተራውን መልካም አድርጎ መጥረግ ነው ከተጠረገ በኋላ የጐተራውን ዳርቻ ኖራ ቀብቶ ጥቂት ቀን እህል ሳይገባበት አንድም ቀዳዳ ሳይቀር መርጎ መተው ነው ከዚያ በኋላ እህሉ ሲገባበት ፈጽሞ እንዳይነቀዝ ከእህሉ ጋራ ደረቅ ሽንኩርት በየከት አድርጎ አብሮ ጐተራው ውሥጥ መጨመር ነው ። የሽንኩርት ሽታ እህሉን አያጠፋውም ነቀዝን ግን በጣሙን ያርቀዋል ።

ደግሞ ስለመጻሕፍት መጠበቅ ምክር ። መጻሕፍት በአያሌው ብዙ ትንንሽ ትሎች የሚያበላሹት አለ ስለዚህ እነዚህን ትሎች ለማራቅ። በመጻሐፍ ማኖርያ ውሥጥ ባንዲት ብልቃጥ የተሬቤንቲን ቅባት በሻሽ ሸፍነው ማስቀመጥ ነው ትሎች ፈጽመው ከመጻሕፍቶች ይርቃሉ ።

አልቤር መሱላም ።

ስለ ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ ዕረፍት ።

ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ በማዘጋጃ ቤት ዲረክተርነት ብዙ ዓመት መንግሥታቸውን አገልግለዋል ። አሁን ከጥቂት ቀን በፊት ስለ ታመሙ ነፋስ ለመለወጥ ወደ ጂቡቲ ወርደው ሰንብተው ደኅና ሁነው ነበር። ከዚያም ተመልሰው ጥቂት ቀን ታመሙና በሐምሌ ፴ ቀን ዓርፈው በነሐሴ ፩ ቀን ብዙ ሚንስትሮችና መኳንንቶች ተሰብሥበው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ።

ብርሃንና ሰላም ለዘመዶቻቸውና ለባለቤታቸው ለቤተ ሰዎቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ስለ ክቡር ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም ልጅ ዕረፍት ።

ያገር ግዛት ሚኒስቴር ዲረክተር የክቡር ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም ልጅ ነሐሴ ፩ ቀን ዓርፎ በጴጥሮስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ።

ብርሃንና ሰላም ለወላጆቹና ለቤተ ዘመዶቻቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ከኢጣልያ ሌጋሲዮን የመጣ ራድዮ ።

በርሊን ፤ እንደ ጋዜጦቹ ወሬ የመስኮብና የቺና ነገር በድንገት የበረታ ይመስላል ። የቺና መንግሥት ስለ ማንቹሪያ የብረት መንገድ መስኮቦች የፈለጉትን ነገር እምቢ ብሏል። የተቀማውን የብረት መንገድና የታሠሩትን የመስኮብ ሰዎች ለማስለቀቅ የሚያስገድድ ነውና መስኮብለናንኪን መንግሥት የሚከተለውን ሐላፊነት በራሱ ላይ እንደሆነ አመልክቷል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታቹሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። ብጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።



በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲ ስና ልጆቹ ። የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

ማስታወቂያ ።

እኔ ሚካኤል ማክራስ ቀበና እንግሊዞች ድልድይ አጠገብ ያለኝን ቦታዬን እሸጣለሁ፤ከቦታውም ላይ አንድ ትልቅ ዩማሮ ክዳን ሦስት ክፍል ቤት፥ አንድ የፍሮኖ መጋገሪያ ቆርቆሮ ክዳን ቤት፥ አንድ ቆርቆሮ ክዳን የከብት ቤት፥፫፻፺ የባሕር ዛፍ፥ የቦታውም ስፋት ፫ሺ ፯፻ አራት ማእዘን ሜትር ነው።ይኸንን ቦታ ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ እፋታውራሪ ግዛው በየነ ቤት በታች ያለው ቤቴ ድረስ ብትፈልጉኝ አገኛለሁ ።

ሚካኤል ማክራስ ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።
ሔራንት ባግዳሣሪያን ።

ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።

መንገድ ላይ ።

ከላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋው ግን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

ማስታወቂያ ።

ያዲስ አበባ የግሪክ መንግሥት ቆንስል ጄኔራል ቤት የሙሴ አስቷስቢ,ያ ሱኒዬስን አበዳሪዎች ለሆኑት ከዛሬ ጀምሮ እስከ ፫ ወር ድረስ ሰነዳቸውንና ሌላውንም የማስረጃ ወረቀቶቻቸውን ሁሉ ይዘው እንዲቀርቡ ያስታውቃል ።

ከዚህ ከተቀረጠው ቀን ያለፈ የቆንስላ ጄኔራል ቤት አቤቱታቸውን ሊቀበል አይችልም ።

፲፱፻፳፩ ዓመት ሐምሌ ፳፱ ቀን ተጻፈ ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኖስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፪ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ከረጢ	፮ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጢ	፳፱ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ከረጢ	፻፶ ብር
ባለሰይጣን		፻፹ ብር
፡ ፡ ባለ ድመ ።		፻፵፫
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፵
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፳
፡ ፡ ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፲፫
" " ጃፖን		፻፴፯ ብር
ሱካር	ጆኒያ	፵፫ ብር
ሻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፶ ሳቲንም
በአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፺፩ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፸ ሳንቲም
እንድ ወቄት ወርቅ	፵፰

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኜ ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ጴጥ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ፥ ባለወረቀት ባላምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆን ባዲስ አበበና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ደገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ኬርቢስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት ቢቶሎፍ አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው ኢሬት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓኒ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠሬው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጂቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪክ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪክ ነው።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያበናጁንት ፈቃድ የተቀበለ።

ΣΥΜΒΟΛΟΝ ΤΟΥ ΕΡΓΟΣΤΑΣΙΟΥ

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በክንቡሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በክንቡሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

ALEM

የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፌኒክስ (PHENIX) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኑላ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪክ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሂዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤትነው።

ጉዲዪር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፫
5me ANNÉE № 53

ሐሙስ ነሐሴ ፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 15 AOUT 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የርሻ ሥራ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን አዳ ቢሾፍቱ አባቡር መቋሚያ አጠገብ የርሻ ሚኒስቴር በቅርብ ጊዜ አዲስ የጀመረውን የርሻ ሥራ(ፌርም) ስለመጎብኘታቸው ።

ሐምሌ ፳፮ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ባማረ በተለዬ ባቡር ከመኳንንቶቻቸው ጋር ሆነው ቢሾፍቱ አባቡር መቋሚያ ደረሱ ።

በዚያም ጊዜ ከዚያው ያለው የመንደሩና የባላገሩ ሰው መምጣታቸውን ሰምቶ ተሰብስቦ ይጠባበቅ ስለነበረ ገና ባቡሩ ሲደርስ ባንድነት የደስታ እልልታውን ቢያሰማ በፍሬው በደስታ ተመላ። ከዚህ በኋላ ጊዜው እኩለ ቀን ነበረና የፀሐዩ ኃይል ስለበረታ ፀሐዩ እስኪበርድ ከዚያው ከጣቢያው አጠገብ ክቡር የግቢ ሚኒስቴር ቤትወደድ ወልደ ገብርኤል ባሰናዱት ቤት እንዲቆዩ ስለተቆረጠ ከባቡሩ ወርደው ከተሰናዳው ቤት ገብተው ግብር ሆነ ።ከቀኑ ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን ከግብር ተመልሰው ከዚያው ከጣቢያው አጠገብ ያለውን ትንሽ ባሕር አይተው እርሻው ወዳለበት ቦታ ለመጓዝ ተነሡ።

ባዚያም ጊዜ ሶስት አቶመቢል ቀርቦ ባንደኛው ግርማዊት ንግሥት በሁለተኛው ግርማዊ ንጉሥ በሶስተኛው በትልቁ አቶመቢል ክቡራን መኳንንቶች ሆነው ወደርሻው ሰፍራ ጉዟቸውን አመሩ ።የርሻውም ሰፍራ ርቀቱ ከጣቢያው ሶስት ኪሎ ሚትር ያህል ስለሆነ በሩብ ሰዓት እርሻው ወዳለበት ቦታ ብቅ አሉ ።

ከዚህ በኋላ እየተከታተለ ያዩት እርሻና ቡቃያ ከዚህ አስከትለን እንዳመለከትነው ነው ።

፩ ኛ ከርሻው ወሰን እንደ ደረሱ በርሻው ዳር ዳር እየሄዱ በስተቀኝ በኩል ለላሞች ምግብ እንዲሆን ተብሎ የተከለከለውን ሣርና የሚዳውን መስክ በግራ በኩል እጅግ የሚያምር ያተር ቡቃያ ።
፪ኛ የስንዴ ቡቃያ ።
፫ኛ የኑግ ቡቃያ ።
፬ኛ በግራ በኩል የገብስ ቡቃያ ።
፭ኛ ለሽምብራ መዝሪ ተብሎ ታርሶ የተሰናዳውን እርሻ ።
፮ኛ በስተግራ በኩል በሰፊ ታርሶ ጤፍ የተዘራ እርሻ፤ በስተቀኝ በኩል ደግሞ ለሽምብራ የተሰናዳ እርሻ ።
፯ኛ እንዲሁ ደግሞ በሰፊው ታርሶ የተዘራውን ጤፍ ።
፰ኛ በስተቀኝ በኩል የዘረዘረ ባሕርማሽላ(በቆሎ) በግራ በኩል ደግሞ የገብስ ቡቃያ ።
፱ኛ ብዙ የተተከለ በርበሬ ።
፲ኛ፤ በስተቀኝ በትረተሩ ላይ የተዘራውን የምስር ቡቃያ ።
፲፩ኛ በባሕሩ ዳር ዳር የተዘራውን የተልባ ቡቃያ ።
፲፪ኛ ላገርዘር ማልሚያና ማሻሻያ እንዲሆን ከአውሮፓ መጥቶ በርሻው መሐንድስ በዶክተር ሆሰን አዘጋጅነት በጥቂት በጥቂት ሆኖየተዘራውን እህልና አትክልት ዓይነቱና ዝርዝሩም ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

አራት ዓይነት ድንች።
ሁለት ” ቤቴራብ ” ” ለከብት ምግብ የሚሆን።
ሁለት ” ሹ ራብ ለከብት ምግብ የሚሆን ።
አንድ ” ናቤ ለከብት ምግብ የሚሆን።
አንድ ” ጥቁር ስንዴ(ሳራሶን)ለሰውና ለከብት ምግብ የሚሆን
ሁለት ” ሹ ፉራጋር ለከብት ምግብ የሚሆን።
ሦስት ” ፈጥን ለከብት ምግብና ለከብት ማሰቢያ ።
አንድ ” ሲራዲል ለከብት ምግብና ለከብት ማሰቢያ።

ሦስት	ዓይነት	ሊዘርን ለከብት ምግብ የሚሆን።
ሁለት	"	ኢፓርሲት ለከብት ምግብ የሚሆን
አንድ	"	ኖቪት ለከብት ምግብና ለዘይት የሚሆን
አንድ	"	ኮልዛ ለዘይት የሚሆን
አንድ	"	ሰናፍጭ ለዘይት የሚሆን
አንድ	"	ሷያ ለከብት ምግብና ለዘይት ለከብት ማወፈሪያ
አንድ	"	አተር ለከብት ምግብና ለሰው የሚሆን
አንድ	"	ባቄላ
አንድ	"	አደንጓሬ የሰው ምግብና የከብት ማስቢያ
አንድ	"	ሞሐር ለከብት ምግብ የሚሆን
አንድ	"	ምስር ለከብትና ለሰው ምግብ የሚሆን
አንድ	"	ቢስ ለከብት ምግብና ማስቢያ
አንድ	"	ተልባ ለከብት ምግብና ለዘይት
አንድ	"	ሸምብር ለዘይትና ለፈትል
አንድ	"	ቀይ ማገጥ ለከብት ምግብና ማስቢያ
አንድ	"	ሲናር ለከብትና ለሰው ምግብ የሚሆን
አንድ	"	ማሽላ " " "

ሰባት ዓይነት የዛፍ አትክልት

ይህንን ሁሉ በያይነቱ ዘረው ካዩ በኋላ ከአውቶሞቢል ወርደው ቀጥሎ የተጻፈውን ማየት ጀመሩ

፲፫ኛ የርሻውን መኪና ቤትና በያይነቱ ተዘጋጅቶ የተቀመጠውን የርሻ መኪና ትራክተርና በያይነቱ በበሬ የሚጐተት ያውሮፓ ማረሻ።

፲፬ የወፍጮውን ቤትና ሊሠራም የቀረበውን የወፍጮ መኪና

፲፭ኛ ጀልባ የሚወድቅበትን ባሕርና ሊሠራ የተጀመረውን ጀልባ።

፲፮ኛ የላሞቹን ቤትና የቅቤውን መኪና ቤት። ይኸውም ለላሞች ቤት ተብሎ የተሠራው ቤት ፹ላም የሚይዝነው

፲፯ኛ ለርሻ ተማሪ ቤት መሥሪ የተሰናዳውን ቦታ።

፲፰ አተራራው ላይ ለመናፈሻ እንዲሆን ታስቦ ቤት ሊሠራበት የታቀደውን ቦታ።

፲፱ ከዚያው ከተራራው ላይ ለጊዜው የቆመውን ሆቴል ጐበኙተው ወደዚያው ሻይ ትጋበዙ የባለሆቴሉም ልጅ እጅግ ያማረ አበባ አዘጋጅታ አቀረበች።

ይኸውም ሁሉ ሲሆን ሠራተኞቹ በየሥራቸው ላይ ሆነው ለሰላምታ ያቀርቡ ነበር።

ይህም ከዚህ በላይ ያመለከትነው የርሻ ሥራ ሁሉ ከዚህ ቦታ ላይ ከተጀመረ አራት ወሩ ነው።

ከዚህም ሁሉ በኋላ የርሻና የመሥሪ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ክቡር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ስለ መጐብኘታቸው የሚከተለውን የምስጋና ቃል አቀረቡ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በዚች ቀን የርሻ ሥራችንን ለመጐብኘት በመምጣታችሁ በመላ ኢትዮጵያ የርሻ ሥራ እንዲሰፋና ፤ ደግሞ በመኳንንቱና በሠራዊቱ በባላገሩም ልብ የርሻ ሥራ ሐሳብ እንዲነሳሣና እኛም ሠራተኞቻችሁ እንድንተጋ እርግጠኛ ምኞትና ሐሳባችሁ መሆኑን ያስረዳናል።

የርሻና የመሥሪ ሚኒስቴርም የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እርዳታ መሠረት በማድረግ አሁን እንደታየው ይህን ሥራ የወጠነበትን ሐሳብ በሚከተለው ቃል ማስረዳቱን እንድናመለክት ባጭሩ እንለምናለን።

፩ኛ ከአውሮፓ የርሻ መሣሪያ አምጥተን ያገሩን የርሻ መሥሪያ ለማሻሻል።

፪ኛ ከገር ውስጥ መልካም መልካሙን የእህልና ያትክልት ዘር እያማረጥን ላራሾች ለመስጠት።

፫ኛም ያውሮፓን ያትክልትና የእህል ዘር ባገር ውስጥ ለማርባት።

፬ ከአውሮፓ በያይነቱ የከብት ዘር እያስመጣን ለማርባት።

፭ የቅቤ መኪና አቁመን ቅቤ ለመሥራት።

፮ የርሻውን ሥራ ለማየት ለመናፈስም ለሚመጡ እንግዶች መናፈሻ እንዲሆን በዚህ በሚታየው ባሕር ላይ ጀልባ ለማድረግ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ይህንንም ምክንያት በማድረግ ክቡር የግቢ ሚኒስቴር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል በርሻ ሥራችን ላይ መርዳታቸውን ሳንገልጸው ለማለፍ አንፈቅድም እንዲሁም በርሻና በመሥሪ ሚኒስቴርና በምኒስቲሩ በክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ስም ሆኜ ዛሬ ስለውድ መጐብኘታችሁ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እግዚአብሔር ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እረጅም እድሜና ጤና ይስጥልን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር። ብለው ሲጨርሱ ዳር እስከዳር ተጨበጨበ።

ከዚህ በኋላ ጊዜው መሽቶ ስለ ነበረ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ከሆቴሉ ተነሥተው ወደባቡር መሳፈሪ ቦታ ደርሰው ወደ አዲስ አበባ ከተማ የመመለስ ጉዟቸውን አቃኑ።

ይህን የርሻ ሥራ ሰውን ሁሉ ያስደነቀው በጥቂት ጊዜ ይህ ሁሉ እርሻ በየዓይነቱ ሆኖ በመከናወኑ ነው።

ሕዝብ ከችግር የሚድንበት መንግሥት የሚበለጽግበት በርሻ ሥራ መሆኑ የታወቀ ስለሆነ ይህን መሠረት አድርገው መኳንንቱና ሕዝቡ በርሻ ሥራ ላይ ይተጋሉ ብለን ሙሉ ተስፋ አለን።

በበታቻቸው ላሉ ሠራተኞች መርህና ረዳት ሆነው ለሚሠሩት ሚኒስቴር ለክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀልና ትጉህ ለሆኑት አሳቢና አጋዥቸው ለዋናው ዲሬክተር ላቶ መኰንን ሀብተ ወልድ የነሱም አጋጋሪች ሆነው ለሚሠሩት ሠራተኞቻቸው ምስጋናቸውን በማቅረብ ሐሳባቸውን ማስፈጸሚያ ረጅም እድሜና ጤና ይስጣቸው ብሎ ጥልቅ የሆነ ምኞቱን ብርሃንና ሰላም ይገልጻል።

ልዑል ዱክ ዴገ አብሩሲ በኢጣልያን አገር ተመልሰው በሮማ ቤተ መንግሥት በኢጣልያ መንግሥት እልጋ ወራሽ በልዑል ዑምበርቶ ፊት ስለ ኢጣልያና ስለ ኢትዮጵያ ወዳጅነት የተናገሩት ቃል ከዚህ የሚቀጠለው ነው።

ልዑል ሆይ።

እኔና መኳንንቶቼ ወደ ዋቢ ወንዝ ለመሄድ አስቀድሞ አዲስ አበባ ላይ በደረስን ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት በመ

ልክም ወዳጅነት እንደተቀበለኝ ለኢጣልያ ሕዝብ ሁሉ የተገለጸ ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ስለ መንገዳችን አኳኋን የሚያስፈልገውን ትእዛዝና ፈቃድ ሁሉ ለአሩሲና ለባሌ አገረ ገዢ አሳለፉልን። ስለዚህ ከአዲስ አበባ ከተነሣንበት ቀን ጀምሮ በተጓዝንበት ጊዜ ሁሉ ወደ አገራችን እስከ ደረስንበት ቀን ድረስ በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ወዳጅነትና ደግነት አለችግር መንገዴን አከናወንሁ።

በሱማሌ አገር ወሰን በአጌሬ በደረስሁ ጊዜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ለግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ምስጋና ለማቅረብ የጻፍኋቸውን የደብዳቤዎች ቃል እኔው እራሴ የኢጣልያ ሕዝብ ሁሉ እንዲያውቀው እዚህ ለማንበብ ደስታዬ ነው ።

የላክኋቸውም የደብዳቤዎች ቃል ከዚህ ቀጥሎ እንዳለው ነው ። ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ።

ግርማዊት ሆይ ።

መንገዴን አለችግር በደህና እንድፈጽም ግርማዊነትዎ ስላሳለፈው ትእዛዝ ሁሉ መንገዴን ጨርሼ ከወሰናችን በደረስሁ ጊዜ በራድዮ ለግርማዊነትዎ ያሳለፍኩትን ቃል ዛሬ በዚህች ደብዳቤ እያደስሁ የልብ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። ግርማዊነትዎ ስለመንገዴ መከናወን የገለጹልኝ መልካም ምኞት በእግዚአብሔር ፈቃድ በደህና ተፈጸመ። ወንዙን ሁሉ ከምንጩ እስከ ድምበራችን ድረስ አለድካምና አለችግር ጐበኘሁ ።

ይህነን የምስጋና ቃልና የልብ ወዳጅነቴን የገለጽኩበትን ደብዳቤ በክቡር ሚኒስትር ኮራ በኩል ለግርማዊነትዎ እንዲያደርስ ሙሴ ቸሩሊን አዝዤዋለሁ ። ግርማዊነትዎ ያደረገልኝን ሁሉ ላጐቴ ልጅ ለግርማዊ ንጉሠ ቢክቶር አማኑኤል አስታውቃለሁ ። ይኸውም በሁለቱ አገራችን መካከል ያለውን ወዳጅነት ለማጽናትና ለማስፋት እንዲጠቅም አይጠረጠርም ።

ሉይጂ ዲ ሳቦያ ።

ደግሞ ለግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ያሳለፍኩት ቃል ይኸነው
ለግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን።

ግርማዊ ሆይ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አገር ውሥጥ ሰስት ወር ከተጓዝሁ በኋላ ወደ ወሰናችን በደረስሁ ጊዜ በራዲዮ ያሳለፍኩትን ቃል በዚህ ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ አድሳለሁ ። ጉዞዬ አለችግር እንዲከናወን ግርማዊነትዎ ስለ አሳለፈው ትእዛዝና ለኔና ለመኳንቶቼ ስለ አደረገው እርዳታ ሁሉ ከልብ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ከሲዳሞ አገር ጀምሬ እስከ ኢትዮጵያና ኢጣልያ ወሰን ድረስ ወንዙን ከምንጩ እስከ ጫፉ ጐበኘሁ።በማናቸውም ቦታ ትንሽም ችግር አላገኘኝም። በሼክ ሑሴንና በሳዊን አገር ውሥጥ ለመኳንንቶቼና ለወታደሮቼ የሚያስፈልጉትን ግመሎች ለማዘጋጀት ትንሽ ቀን ከቆየሁ በኋላ ግራዝማች ገብረ ዮሐንስና ወታደሮቹ በመልካም እየረዱኝ በእነዚሁ ደስ በሚያሰኙት በግርማዊነትዎ ዘበኞች ትጋት እንደ አሳቤ በፍጥነት ሔድሁ ።

ይህነን ደብዳቤ በሙሴ ኮራ በኩል ለግርማዊነትዎ እንዲያደርስ ሙሴ ቸሩሊን አዝዤዋለሁ ። በዚህ ዓመት ግርማዊነትዎ ያደረገልኝነገር ሁሉ የማይረሳ የወዳጅነት ምልክት ነውና ላጐቴ ልጅ ለግርማዊ ንጉሠ ቢክቶር አማኑኤልና በሞላውም ለመንግሥቱ ደስታዬን አስታውቃለሁ ። ሉይጂ ዲ ሳቦያ።

እንደዚሁም በኢትዮጵያ መንግሥት እርዳታ መንገዴን ሁሉ በቶሎ አለ ችግር ፈጸምሁ ።

የጋዜጣን ጥቅምነት በምሳሌ ለማስረዳት ።

ጋዜጣ ለሰው ኑሮ በሚጠቅመው ደገኛ ነገር ሁሉ ይመሰላል። ስለዚህም አስቀድመን በመልካም ምክርና በኮሶ እንመስለዋለን አባት ልጁን፥ ሽማግሌም አላዋቆችን ሲመክሩ የዚህን ምክር ጥቅምነት የሚታወቀው ክፉንና መልካምን ፤ ጠላትንና ወዳጅን ፣ ማጣትንና ማግኘት ፤ ታማሚመሆንና በጤና መኖርን ካወቁ በኋላ ነው ። ማለት ልጅና አላዋቂ ሲመከሩት ስለ ራሱ ጥቅም መሆኑን እስኪ ያውቅ ድረስ ከመካሩ ጋራ ይጣላል፥ ነገሩንም ይንቃል ። ጥቅሙን ካወቀው በኋላ ግን ፈጽሞ ደስ ብሎት ይልቁንም በፊተኛው ምክርን ስለ መቃወሙ እጅግ እየተጸጸተና እያዘነ ባለ ዘመኑ ሁሉ ከብልህ ሰውና ከሽማግሌ እየጠየቀ፥የምክር መጻሕፍትንም እያነበበ ለዕውቀት ሲጣጣር ይኖራል ። በተፈጥሮውም ዕውቀት የተሰጠው ከሆነ ትንሽ ጕድለት ሲገኝበት እንኳንስና ምክር ቢመቱትና ቢሰድቡት ቅሉ ብትሩን ከሹመት ፣ ስድቡን ከሽልማት ቈጥሮት በውቀት ላይ ትምህርትን ይጨምራል።መካሩንም እንደ ወንድሙ ይወደዋል፥ እንደናትና አባቱ ያፍረዋል፥ እንደ ንጉሥ ያከብረዋል ፥ እንደ እግዚአብሔር ይፈረዋል ። ጋዜጣም የሰውን ጕድለት፥ የአገርን ጥፋት አከናውኖ ሲጽፍ ያለበት ለጊዜው ይጠላዋል ። ኋላ ግን ነገሩን እያማታና እያንጓለለ እንደጤፍ አበጥሮ፥የጐደለን መልቶ፥ የጠመመውን አቅንቶ፥የከበደውን አቅሎ፥ የተበላሸውን አሻሽሎ፥ ሥርዓት በማደሱ ለሕዝብ ጥቅም፥ ለአገር ሰላም ይሆናል ። ኮሶም ሲጠጡት ለጊዜው ይገርማል ፤ ይመራል፤ ይጐፈንናል፥ ያቅለሸልሻል፥ ከሆድ ያለውን ትልና ሸቀን አውጥቶ ሰውነትን ካጠራ በኋላ ግን ያ የጠጣው ሰው ሰውነቱ ጤናማ በመሆኑና ደስ በመሰኘቱ፥የበላውና የጠጣው በመስማማቱ ጥቅሙን ስላገኘ በፊት ያስቀቀውን የምሬቱን አኳኋን ረስቶት ለወደፊት ተሎ ተሎ ለመጠጣት ሐሳብ ያድርበታል ።

ጋዜጣም ታናሽ ታላቅ፤ ድኻ ባለ ጸጋ፤ ጌታ ሎሌ፤ ገረድ እመቤት ፤ ቄስ መነኵሴ ፤ ነጋዴ ገበሬ ፣ ባላገር ወታደር ፤ ሳይለይ ለሁሉም እያንዳንዱ ጕድለት ጕድለቱን ሲናገርበት ያ ጕድለቱ የተነገረበት ሰው በፊት ተመስግኖ ኋላ ከመታማት አስቀድሞ ተከብሮ ፥ ኋላ ከመዋረድ ይልቅ በፊት ተምሮና ተመክሮ፥ተነቅፎና ታምቶ፥ በኋላ መመስገን፥ በክብር ላይ ክብር መጨመር መሆኑን ሳያውቅ እጅግ ያፍራል፥ያዝናል፥ ይበሳጫል ፥ ለምን ተደፈርሁ ይላል። በኋላ ግን ነገሩን በማስተዋል ከጥፋት ወደ ልማት ፤ ከድንቁርና ወደ ዕውቀት ፤ ከስንፍና ወደ ብርታት፤ ከክፋት ወደ በጎነት በተመለሰ ጊዜ ባለፈው ነገር እየተቈረቈረ በትጋት ጋዜጣን ለማንበብና ሰውነቱን

እየመረመረ አእምሮውን ለማከናወን ፤ ሥራውንም ለማሻሻል አጥብቆ ይጣጣራልና ። አንድም ጋዜጣ በመስተዋት ይመስላል ፤ በመስተዋት የሰውነት መክሳትና መወፈር ፤ መቅላትና መጥቆር እንዲያዩበትና በገጹ ያለውን ጕድፍ እንዲያወጡበት በጋዜጣም ያገርን ጥፋትና ልማት ያውቁበታል፡ካገርም ቀጣፊንና አታላይን ያወጡበታልና ።

አንድም ጋዜጣ የውነተኛ ንጉሥ ምሳሌ ነው፤ ውነተኛ ንጉሥ እግዚአብሔርን ፈርቶ፤ ፍርዱን በመጠንቀቅ ማማለጃ መቀበልንና በለወገንነት ምክንያት የሰው ፊት መፍራትን ታግሥ ደኃ ተበደለ ፤ ፍርድ ጐደለ ፤ እያለ ጥፋት የተገኘበትን እንደየኃጢአቱ መጠን ዓይኑን በፍላት፥ልጅ እግርን በስለት ሲቀጣ ፤ ያልተማረ ሕዝብ ለጊዜው ይጠላዋል ፤ ኋላ ግን ሌባና ወንበዴን ፤ ቀጣፊና አታላይን ፤ አጥፍቶ ድኃውን ጠብቆና ረድቶ ፤ ተማሪ ቤቶችን አሠርቶ ፤ አገርን አቅንቶ ፤ ሕዝብን አብዝቶ ፤ ከተማን አስፍቶ ፤ ሃይማኖትን አፅንቶ ፤ ሁሉንም በየሥራው ባደራጀው ጊዜ ሁሉም ለፍቅሩ ይሳሳል ወደእግዚአብሔርም ይለምንለታል ። በየተቻለውም ይረዳዋል እያንዳንዱም የሱን ፍለጋ ተከትሎ ላገሩ አሳቢና ተቆርቋሪ ይሆናል ። ጋዜጣም ያገርን ጉዳትና ጉስቁልና ፤ የሰውንም ክፋትና ስንፍና፤ በድፍረት ሲጽፍ ያልተማረ ሕዝብ ለጊዜው ይጠላዋል። በጻፈውም ላይ አምባጓሮ ለማንሣት ይፈልጋል፡ነገሩን ተረድቶ ጥቅምነቱን ካወቀ በኋላ ግን በትጋት እያነበበ ምሥጢሩን ይመረምርና የኑሮውን አካሔድ ያሻሽላል ።

አንድም ጋዜጣ በአጣቢ ፤ በሳሙና ፤ ይመስላል እነዚህ ማናቸውንም ነገር እድፉን አስወግደው ለዓይን የሚደምቅ ለገላ የሚሞቅ እንዲያደርጉ፥ ጋዜጣም ስንፍናንና ክፉ ልማድን በማስወገድ መንግሥትን ያከብራል ፤ ከተማን ያደምቃል፥ ሕዝብን ያነቃቃልና ።

አንድም ጋዜጣ በአንጥረኛ በነፋስ ፤ በመሸን፥በወንፊት፥ በማንዘርዘሪያ፥በወንጠፍት ይመስላል እነዚህ እህልንና ገለባን፥ ጥሩንና አተላን ፤ እንዲለዩ፥ ጋዜጣም በሥጋዊና በመንፈሳዊ ነገር ሁሉ ክፉንና መልካምን ለይቶ በማስረዳት ብዙ ጥቅምን ያስገኛልና ።

አንድም ጋዜጣ በሹመት ፤ በቀረርቶ ፤ በነጋሪት ፤ በሸለላ ፤ በቀንዳ መለኸት ፤ ይመሰላል ። እነዚህ በጦር አፊና ጊዜ በየስልታቸው ልዩ ልዩ ድምፅን አሰምተው የጀግናውን ሁሉ ልብ በማነቃቃት ድፍረት መጠጥን ያሰክሩና ፍራት ልብሱን አስጥለው ከሽሽት ወደ መዋጋት ፤ ከመጨፈን ወደማየት ፤ ጥይት ያለቀበትን ጕራዴ ወደመምዘዝ፥ ጕራዴ የላሸበትን ዱላ ወደመንጠቅ ፤ ዱላ ያለቀበትን ጉረሮ ወደማነቅ እያስማሩ ኃይልንና ብርታትን ሰጥተው ድል ከመሆን ድል ወደማድረግ ከመሰደድ ወደ ማሳደድ ፤ ከመጠቃት ወደማጥቃት፥ ከባርነት ወደነፃነት ፤ በማድረሳቸው ላገር ጤንነት ለሕዝብ ፍቅርና አንድነት ለመንግሥት ፅናት ይገኛል ። ታቦት ከመንበሩ ፤ ካህን ከደብሩ፥ ላም ከበረቱ፥ ባላገር ከርስቱ፥ ንጉሥ ከመንግሥቱ፥ጳጳስ በክህነቱ ፀንተው በመንፈሳዊና በሥጋዊም ነገር ሁሉ የሕዝብን አናዋወር ያሻሽላሉ ።

ጋዜጣም የሩቁን ወደ ቅርብ ፤ የቅርቡንም ወደ ሩቅ ፤ በአንድ አገር የሆነውንም በያገሩ ሁሉ በማዳረሱና ክፉ ክፉውን ልማድ ጠፍቶ መልካም ደምብ እንዲቆም በማነቃቃቱ ፤ በየነገሩም ስልት ብልሀንና ብልሀን በጥያቄና በምላሽ በማጋጨቱ ትምርትን አስፍቶ ነፃነትን ያበረታልና ። ማለት ብልሀ ከብልሀ ደቀ መዝሙር ከመምህሩ የተከራከሩ እንደሆነ በትምህርት ላይ ትምርት በጥበብ ላይ ጥበብ መጨመሩን መናገር ነው። እስመ እምትክሕዶ ይትወለድ ስነ ባቁዕ እንዳለ ቄርሎስ(ተስእሎ)ክፍል ፲ ኤ ነሆም ሁለ ጊዜ በአእምሮና ብርሃንና ሰላም አንዱ ለጻፈው አንዱ ምላሽ ሲሰጥ ላላስተዋለ ሰው ለጊዜው የመነቃቀፍ ነገር ይመስልዋል ። ኋላ ግን ተሠውሮ የነበረው ምስጢር ይገለጥና ለታላቅ ለታናሹ በእምር የተረዳ ይሆናል ። ደግሞም ጋዜጣ የመምህር ምሳሌ ስለ ሆነ በውነት ነገር ማንንም አይፈራም፤ መምህር ወመገሥፅ ዘኢያደሉ ለገጽ እንዲል።ጢሞ ፫ ፩ በዚያውም ላይ የተናገርሁትን ካልተሰማልኝ ያዘዝሁት ካልተደረገልኝ በማለት ሥራውን አይፈታም። በበረኻ የሚፈስ ውሀ የሚቀዳኝ የሚጠጣኝ የለም በማለት ሥራውን እንዳይተው። ደግሞም ንግር ወኢታርምም ናሁ ረሰይኩክ ብርሃኖሙ ለአሕዛብ የተባለ ምንም ለጊዜው ቅዱስ ጳውሎስ ቢሆን ዛሬ በእነርሱ ፋንታ ገብቶ ሥጋዊንና መንፈሳዊን ነገር በማስተማር ለዓለም ብርሃን የሆነው ይኸው ጋዜጣ ነውና ። ግብ፡፲፫ ፵፯። ፲፰፡፲። ኢሳ ፵፱፡፮። ጋዜጣንም እንዲህ እያደረግን በመልካሙ ነገር ሁሉ ልንመስለው እንችላለን።ነገር ግን ብዙ ስፍራና ጊዜ የሚወስድብን ስለ ሆነ ይህ ይበቃናል ። ይህነንም የጻፍሁበትን ምክንያት ካላዩና ካልሰሙ መጠየቅ፥ካልጠየቁ ማወቅ፥ ካላወቁ መሥራትና መጠንቀቅ አይገኝም ስል ነውና ሁሉንለማየትና ለመጠየቅ ለመረዳትና ለማወቅ ለመሥራትና ለመጠንቀቅ ያብቃን ስል ምኞቴን እገልጻለሁ ።

መኰንን ኢ.ደቄም ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በየይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የድ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪክ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንዖር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒካላ።



Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ አዩ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ ።

የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማስታወቂያ ።

እኔ ሚካኤል ማክሬስ ቀበና እንግሊዞች ድልድይ አጠገብ ያለኝን ቦታዬን እሸጣለሁ፤ከቦታውም ላይ አንድ ትልቅ የሣር ክዳን ሦስት ክፍል ቤት፣ አንድ የፍርና መጋገሪያ ቆርቆሮ ክዳን ቤት፣ አንድ ቆርቆሮ ክዳን የከብት ቤት፤፫፻፶ የባሕር ዛፍ፣ የቦታውም ስፋት ሮሺ ፯፻ አራት ማእዘን ሜትር ነው።ይኸንን ቦታ ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ አፈታውራሪ ግዛው በየነ ቤት በታች ያለው ቤቴ ድረስ ብትፈልጉኝ አገኛለሁ ።

ሚካኤል ማክሬስ ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕሩንት ባግዳሣሪያን ።

ከማሪክ ቤት ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋው ግን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሜበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ ባጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።

አበክት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው ።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለአንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው ። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ። ሐኪም አምባር ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከበሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያ ዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጥም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤትነው።

ጉድ ደር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

አምስተኛ ዓመት ቍጥር ፶፩
5me ANNEE № 51

ሐሙስ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 22 AOUT 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በኢትዮጵያ መጀመሪያ የአየር ባቡር ስለ መምጣትና አዲስ አበባ ስለ መግባት ።

የአየር ባቡር ማለት በአየር ላይ የሚበር የብረት መኪና ማለት ነው። በአውሮጳም ቢሆን በቀድሞ ዘመን በነፋስ ኃይል ወደ አየር የሚወጣ ባሎን የሚባል ነበር እንጂ የአየር ባቡር አልነበረም ። ባሎን ምንም በነፋስ ኃይል ወደ አየር ቢወጣ፡ ለዋና ችግርና ጉዳይ ለሥራም እጅግ አይጠቅምም ነበር ።

ካ፲፭ ዓመት ወዲህ ግን የአየር ባቡር ብልሃት ስለተገኘ በፍጥነት ለመሥራት ለሚያስፈልገው ለማናቸውም ጉዳይ ሁሉ እጅግ የሚረባና የሚጠቅም ስለ ሆነ በሠለጠነው አገር ሁሉ ማስፈለጉ የግድ ሆነ ።

ይልቁንም በአየር ባቡር ፖስታ ማመለስ ከተጀመረ ወዲህ የንግድና የሌላውም የመንግሥትና የሕዝብ ጉዳይ በቶሎ እየተፈጸመ ጥቅሙ በጣም የታወቀ ሆነ ።

አስቀድሞ የአየር ባቡር እንደተጀመረ ጊዜ ፩ የአየር ባቡርከ፩ እስከ ፫ ሰዎች እንጂ ከነዚህ የበለጠ አይችልም ነበር። አሁን ግን ሥራው እየተለመደ የሠራተኞቹ እውቀት እየሰፋ ስለሁደ ከ፲ እስከ ፶ ሰዎች የሚይዝ የአየር ባቡር ይሠራ ጀመር። ከ፲፱፻፲፩ ዓመት አስቀድሞ በኢትዮጵያ የአየር ባቡር ወሬ አይሰማም ነበር ። በ፲፱፻፲፩ ዓ ም ግን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ጅቡቲ ደርሰው የእንግሊዝ መንግሥት መርከቦች ማቆሚያ ወደ ሚሆነው ወደ ዓደን ከተማ በተሻገሩ ጊዜ በእግንሊዝ የአየር ባቡር ላይ ወጥተው የዓደንን ከተማ ባየር ላይ ዞረው ነበርና ይህ ወሬ አዲስ አበባ በተሰማ ጊዜ እውነት መሆኑ ታወቀና የሰማው ሕዝብ ሁሉ አደነቀ ።

ደግሞ በ፲፱፻፲፮ ዓ ም አውሮጳን ለመጐብኘት ብዙ መኳንንቶችን አስከትለው በሔዱ ጊዜ ገና በማርሴይ ባሕር ጠረፍ ሲደርሱ ብዙ የፈረንሳዊ መንግሥት የአየር ባቡሮች በደስታና በክብር ተቀብለዋቸው ነበር።ወደ ፓሪስም ከደረሱ በኋላ ዋናውን የፈረንሳዊን መንግሥት የአየር ባቡሮች መቆሚያና ማረፊያ ለማየት ከፓሪስ ከተማ ውጭ ሔደው ነበርና ብዙ የሰማይ ባቡሮች በአየር ላይ ተሰልፈው ሰላምታ ሰጥተው ነበር ።

እንደዚሁ ሁሉ በሮማም፡በሎንዶንም፥ በቡርክሴልም፥ በአቴናም፥በሌሎችም ግርማዊነታቸው በደረሰባቸው ከተሞች ሁሉ የአየር ባቡሮች በአየር ላይ ሲበሩና የመንግሥቱንና የሕዝቡን ችግር ሲረዱ እያዩ በሀገራቸው በኢትዮጵያም እንደዚሁ የኢትዮጵያ መንግሥት የአየር ባቡሮች ካየር ሲበሩ ለማየት ምኞታቸው መሆኑን ለተከተሏቸው መኳንንቶች ሲነግሩ ነበር ።

እግዚአብሔርም በቅን ልቡና በእውነተኛ ሕሊና ለሚለምኑት ሁሉ ልመናቸውን ይሰማልና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ከ፲፱፻፲፮ ዓ ም ጀምሮ ስለ የአየርባቡር ወደ ኢትዮጵያ መግባት የተመኙትን ምኞታቸውን ሁሉ ስለፈጸመላቸው እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባቸዋል ።

የኢትዮጵያ መንግሥትም ለራሱ የአየር ባቡር እንዲያገኝ ምኞታቸው ምንም ከ፲፱፻፲፮ ዓ ም ጀምሮ ቢሆን አሁን ምኞታቸው እንዲፈጸም ለማድረግ ያነሣሳቸው ሁለት ነገር ነው ።

፩ኛው በኢትዮጵያ በያውራጃው ሁሉ የምድር ባቡር ወይም የአውቶሞቢል መንገድ ስለሌለ ፖስታ ማመላለሻ ችግር በመሆኑ የኢትዮጵያ መኳንንቶችና ሕዝቡ በየአውራጃው የሚሆነውን ይቅርና በዋናው ከተማ ባዲስ አበባ የሚሆነውን ነገር እንኳ ለመስማት ብዙ ችግር መሆኑን ስለ ተረዱት ለፖስታ ማመላለሻ እንዲሆን ብለው ነው ።

፪ተኛው አሁን ባለፈው ዓመት አንበጣ መጥቶ በያውራጃው ብዙ እህል አጥፍቶ ከሔደ በኋላ አሁን ደግሞ በየአውራጃው እየተመለሰ ስለታየ በኢየሩሳሌም አውራጃና በሌ-

ላውም በአፍሪካ አገር የተነሣውን አንበጣ በአየር ባቡር አጠፉት የሚሉ ወሬ ስለሰሙ ምናልባት ይህ ባለፈው ወራት መጥቶ የነበረው አንበጣ ከመስከረም በኋላ ተመልሶ የመጣ እንደሆነ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን በዚሁ በየአር ባቡር አንበጣውን ለማስፈጀትና የኢትዮጵያን ሕዝብ ከእህል ችግር ለማዳን ብለው ነው።

ይህም ሁሉ ችግር ስለተሰማቸው የመንግሥቱንና የሕዝቡን ችግር ለማቃለል ሲሉ ይህን አሳባቸውን አዲስ አበባ ለሚኖሩት ለትልልቁ መንግሥቶች ለፈረንሳዊና ለእንግሊዝ ለኢጣሊያም እንደራሴዎች አስታወቁዋቸው ።እነዚሁም የሦስቱ መንግሥቶች እንደራሴዎች ባንድ ወገን ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ያላቸውን ወዳጅነት ለማፅናትና ግርማዊ ንጉሥን ደስ ለማሰኘት ሲሉ፤ በሁለተኛውም ወገን ኢትዮጵያ ከዓለም መንግሥታት ጋራ ማኅበርተኛ ስለሆነች የሚገባትን ለማግኘት የሚገባት መሆኑን ስለተረዱት የአየር ባቡር ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ተነጋግረው በመጣባቱ ተስማምተው ነገሩ ተጨረሰ ።

ከዚህም በኋላ በኢትዮጵያ መንግሥት ስም መጥተው ጅቡቲ የገቡት የአየር ባቡሮች ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ግርማዊ ንጉሥ ጅቡቲ ላለው ለኢትዮጵያ ቆንሲላ ቤት ትእዛዝ አሳለፉ ። ነገር ግን ባለፈው በሐምሌ ወር ውሥጥ በጎታና በየረር መካከል ያለውን የባቡር መንገድ ከነድልድዩ የዝናብ ጐርፍ ስላበላሸው፤የምድር ባቡር ኩምፓንያም ከ፪ ወር አስቀድሞ ሥራውን ለመጨረስና ባቡር እንዲሔድ ለማድረግ አለመቻሉን ስላስታወቀ፤ጅቡቲ ገብተው የተቀመጡት የአየር ባቡሮች በጥቂት ምክንያት የተበላሹ እንደሆነ ለመንግሥታችን ትልቅ ኪሳራ ይሆናል እያሉ ያስቡ ጀመር። የአየር ባቡሩንም ለመንዳት ከፈረንሳዊ አገር የመጣው ሙሴ ማዬ አዲስ አበባ ነበርና ግርማዊ ንጉሥ በዚሁ ነገር ትልቅ አሳብ እንደገባቸው አይቶ እኔ ወደ ጅቡቲ ወርጄ ከሣጥኑ አውጥቼ እዚያው አገጣጥሜ በአየር ላይ እያበረርሁ አመጣዋለሁና በምድር ባቡር መበላሸት ትልቅ አሳብ አይግባዎ የሚል ቃል ስለነገራቸው እጅግ ደስ አላቸው ።

ሙሴ ማዬ ወደ ጅቡቲ ወርዶ የአየር ባቡሩን መኪና አገጣጥሞ ከጨረሰ በኋላ በነሐሴ ፱ ቀን አሙስ ከጠዋቱ በ፫ ሰዓት አዲስ አበባ እገባለሁ የሚል ቴሌግራም አሳለፈላቸው፤ የአየር ባቡሩንም ማረፊያ ገና ወደ ጅቡቲ ሳይወርድ መርጦ አሳይቶ ነበርና ግርማዊ ንጉሥ ቴሌግራሙ እንደ ደረሰላቸው ስፍራው እንዲዘጋጅ አዘዙ ።

የአየሩ ባቡርም ከጅቡቲ ማለዳ ፲፪ ሰዓት ሲሆን ተነሥቶ በሦስት ሰዓት አዲስ አበባ መግባቱን ግርማዊ ንጉሥ በቴሌግራም ሰምተው ነበርና በነሐሴ ፲፪ ቀን ከጧቱ በአንድ ሰዓት ድሬ ዳዋ መድረሱን ፣ድሬ ደዋ ስልከኛ አስታወቀ ። ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ መኳንንቱን ሁሉ አስከትለው ለአየር ባቡር ማረፊያ ወደ ተሰናዳው ስፍራ ሔዱ ።

ከከተማውም ሕዝብ ብዙ ትልልቅ ሰዎች ሴቶችና ከፍ ከፍ ያሉ ልጆችም ሁሉ የአየር ባቡሩን ለማየት እየቸኰሉ ሔደው ነበር ።

በአዲስ አበባም ያሉት የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሹሞችና ሌሎችም በልዩ ልዩ ስፍራ የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች ወይዛዝሮችም ሔደው ነበር ።

ደግሞ ይህ ቀን ኢትዮጵያ አንድ ትልቅ የሥልጣኔ ደረጃ የወጣችበት ትልቅ ቀን በመሆኑ የደስታ ቀን ነበርና ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስና ሌሎችም የኢትዮጵያ ጳጳሳት የአየሩን ባቡር ለማየት ሔደው ነበር ።

ከጧቱም ሁለት ሰዓት ተኩል በሆነ ጊዜ ሞጆን ማለፉ ተሰማ፤ ነገር ግን ሞጆን ካለፈ በኋላ በቢሾፍቱ ባቡር መቆሚያ አጠገብ ሲደርስ ወደ መሬት ወርዶ አረፈ ብሎ የቢሾፍቱ ስልከኛ አስታወቀ ። ነገር ግን የሰማዩ ባቡር ወርዶ ያረፈበት ስፍራ ከቢሾፍቱ የሁለት ሰዓት ያህል መንገድ ስለሆነ ያረፈበትን ምክንያት በቶሎ ለማወቅ አልተቻለም ነበርና ምናልባት በአደጋ ምክንያት ወድቆ ነጂውን ሙሴ ማዬን የሞት አደጋ አግኝቶት ይሆናል ብለው ግርማዊ ንጉሥና በዚያውም የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ እጅግ አዘኑ ። ይልቁንም ሚስቱ ማዳም ማዬ የአየሩ ባቡር ወደ መሬት ማረፉን በሰማች ጊዜ ያንጊዜውን ፊቷ በኀዘን ስለ ተለወጠ ያያት ሰው ሁሉ እጅግ አዘነ ።

ያረፈበትንም ምክንያት ለማወቅ አንድ ሰዓት ያህል ጠብቀው ምላሹን በቶሎ ለማግኘት የማይቻል መሆኑን አውቀው ወደ ባቡር ማቆሚያ ለመውረድና ከዚያም በባቡር ተሳፍረው ወደ ቢሾፍቱ ለመውረድና የሙሴ ማዬን አኳኋን ለማየት አሳብ አደረጉ ። ነገር ግን ማዳም ማዬ በብዙ እንዳትደነግጥ ብለው ለማፅናናት ሲሉ ያረበፈት ምክንያቱ ቀላል ነው አሉ፤ ቢሆንም ለስልኩ እንዲመቸን ወደ ባቡር መቆሚያ እንውረድ ብለው ከመኳንንቱ ጋራ በራሳቸው አቶሞቢል አስቀምጠውዋት ወደባቡር መቆሚያ ወረዱ ።

በባቡር መቆሚያም ሆነው በስልክ እየተላላኩ ሲጠብቁ ሙሴ ማዬ የአየር ባቡሩን ያሳረፈበት ምክንያት ከዚህ ቀጥሎ እንዳለው ሁኖ ተገኘ ።

ሙሴ ማዬ ሞጆን አልፎ በቢሾፍቱ አኳያ ሲደርስ ጊዜው ደመናና ዝናም ሁኖ ነበርና ደመናው ከየሩ ባቡር በታች ስለሆነበት መሬቱን በትክክል ለማየት ካለመቻሉ የተነሣ ደመናው ካለፈና ዝናሙ ከቆመ በኋላ ለመነሣት አስቦ ወደመሬት አርፎ ነበር።በዚያውም ባረፈበት መሬት አጠገብ የበጅሮንድ ውብሸት ቤት ኑሮ በጅሮንድ ውብሸት ያየሩ ባቡር ወደ መሬት መውረዱን አይተው በፍጥነት ሔደው የወረደበትን ምክንያት ቢጠይቁት በዝናሙና በደመናው ምክንያት ነው እንጂ ሌላ ምንም አደጋ አላገኘኝም፤ አሁንም ደመናው ገለጥ ሲል እነሣለሁ ብሎ ስለ ነገራቸው ይህንኑ ቃል በፍጥነት ለግርማዊ ንጉሥ በስልክ አስታወቁ ።

ይህም የሙሴ ማዬ የደኅንነት ወሬ በተሰማ ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ እጅግ ደስ አላቸው ። ወዲያውም ለመኳንንቱና ለማዳም ማዬ አስታውቁ ብለው አዘዙ ።

ደመናውም ሲገለጥ ሙሴ ማዬ መነሣቱ እርግጥነቱ በታወቀ ጊዜ እንደገና ተመልሰው ወደ ማረፊያው ስፍራ ቀድመው ለመቆየት በፍጥነት ሔዱ ።

ሙሴ ማዬም በሰባት ሰዓት አዲስ አበባ ደርሶ በቤተ መንግሥቱና በሌሎቹም በትልልቆች ቤቶች ላይ የአየር ባቡሩን እያንዣበበ ሲያልፍ ለማየቱ ቸኵለው በየደጁና በየመንገዱ ዳር፣ በየደርቡም ላይ እየቆሙ ሲጠብቁ የነበሩ ያከተማው ሰዎች በደስታ እያጨበጨቡና ዕልል እያሉ አሳለፉት ።

በሰባት ሰዓት ከሦስት ደቂቃ ለማረፊያው ወደ ተዘጋጀለት ስፍራ ደርሶ ዓረፈ ።

ግርማዊ ንጉሥም በታላቅና በሰፊ ድንኳን ውሥጥ ከመኳንንቱና ከውጭ አገር ሰዎች ጋራ ሁነው የአየር ባቡርን መምጣት ሲጠብቁ ነበርና በድንኳኑ ላይ ሲያንዣብብ ሰምተው ከድንኳኑ ውጭ ወጥተው ይመለከቱ ነበርና ወዲያው ከመሬት ላይ እንደ ዓረፈ መኳንንቱን አስከትለው ወደዓረፈበት ስፍራ ሔዱ ። ሙሴ ማዬም በደስታ ሰላምታ አቀረበ በዚያ ጊዜ በዚያው የነበሩ ሰዎች ሙሴ ማዬን በትከሻቸው ተሸክመው ወደ ድንኳኑ ድረስ ወሰዱት ። ከዚህም በኋላ ግርማዊ ንጉሥ የኢትዮጵያን የክብር ኮከብ ንሻን ለሙሴ ማዬ በአንገቱ አሠሩለት፤ ለመኪናው አጋጣሚ ለሙሴ ፒካፔርም የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ንሻን ባለ አምበሉን በደረቱ አደረጉለት ።

ከዚህ በኋላ የፈረንሳዊ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሙሴ ደረፊ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ግርማዊ ሆይ ።

መጀመሪ ጊዜ የኢትዮጵያን አየር አቋርጦ በመሬቱ ላይ በራሪ መኪና ያረፈበት ይህ የዛሬው ቀን ለኢትዮጵያ የከበረ ቀን ነው ። በግርማዊነትዎ አገርና በውጭ አገሮች መካከል ያለው የፍጥነት የአየር መገናኛ በዚሁ በዛሬው ቀን ተመሠረተ። ይህም የሥልጣኔ ታላቅና አዲስ እርምጃ ነው ።

ግርማዊ ሆይ ወደ ኢትዮጵያ በመጀመሪ የመጣውን የአየር ባቡር ዛሬ በመቀበላችን የሚሰማን ደስታ በእርስዎ አሳብና በጥበብም እጅግ የቀደሙትን አገሮች መንገድ ለመከተል የጋለ ምኞት በመመኘትዎ ምክንያት የተገኘ ደስታ ነው ።

በፍጥነት የሚገናኙ መንገዶች የሚያመጡትን ጥቅም ሁሉ ተረዱት ። ወደፊትም በዚህ በአሁኑ ዘመን በሚሠራው በራሪ መኪና እጅግ ከራቁት ከመንግሥትዎ አገሮች ጋራ በጥቂት ሰዓት ለመገናኘት ይችላሉ ።

ግርማዊ ሆይ፤ በጅቡቲና በዋና ከተማዎ መካከል ያለውን አየር በመጀመሪ አቋርጦ የመጣ ከአገሬ ሰዎች አንደኛው በመሆኑ ለእኔ ታላቅ መመኪያ እንደሆነ እንገልጽልዎ ዘንድ ፈቃድ ላማኝ ።

ከአየር ባቡር ነጂዎችዎ ለአንደኛው እጅግ ደፋርና ቀልጣፋ ለሆነው ለሙሴ ማዬ ሰላምታ እያቀረብሁ ዛሬ በአጠገብዎ ሁኜ ልቀበላቸው በመቻሌ ምክንያት ፤ ስለሚሰማኝ ደስታ እርሱንና ደግሞ መኪና ሠራተኛውን ቀልጣፋ የሆነውን ሙሴ ፒካፔርን አመሰግናለሁ ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ፤ ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ፤ ጀግኖች የሆኑ የአየር ባቡር ነጂዎችም ይኑሩ እያልን ሁላችንም ድምፃችንን ከፍ ለማድረግ እንችላለን ።

Allocution prononcée Par Monsieur de Reffye Ministre de France en Ethiopie à l'occasion de l'arrvée à Addis-Abeba de l'Avion NE:SRE TAFARI.

Sire.

C'est aujourd'hui un grand jour pour l'Ethiopie que celui où le premier oiseau mécanique est venu traverser son ciel e se poser sur son sol. De ce jour date la liaison rapide par voie des airs entre le pays de votre Majesé et les pays Etrangers; c'est un nouveau pas, et un pas considérable, franchis vers le progès.

c'est à votre initiative, sire, à votre ardent désir de marcher sur les traces des pays les plus avancés dans la science que nous devons la joie d'avoir à accueillir aujourd'hui le premier avion arrivé en Ethiopie. Vous avez compris tout l'intérêt des communications rapides grâce à cet instrument moderne vous pouvez en quelques heures avoir dèsormais des communications avec les provinces les plus reculées de votre Empire.

Il me sera bien permis, sire, de vous dire que je suis très fier que ce soit un de nos compatriotes qui ait pu le premier réaliser la liaison aérienne entre Djibouti et votre Capitale. Je salue en Monsieur Maillet un de vos pilotes les plus hardis et les plus adroits; je le remercie, ainsi que son habile mécanicien, Monsieur Picaper, de me donner aujourd'hui la joie de pouvoir les accueillir à vos côtés.

Nous pouvons crier ensemble; Vive l'Ethiopie, vivent Leurs Majestés l'Impératrice et le Negous. vivent nos vaillants aviateurs.

የሙሴ ደረፌ ዲስኩር ሲጨረስ ሙሴ ማዬ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገረ ።

ከፈረንሣዊ ሱማሌ ጠረፍና ከኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከዲስ አበባ መካከል፤ መጀመሪውን ያየር መገናኛ ፈጻሚ እሆን ዘንድ ምክንያት ለሰጡኝ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

በዚህ ባደረግሁት ሥራ የሚሰማኝን ደስታና የልቤን አሳብ ለመግለጽ የደስታዬ ብዛት ሊያናግረኝ አልፈቀደልኝም ።

የፈረንሳዊ ሚንስትር አረጋግጠው የተናገሩት ቃል ሳይፈጸም በመቅረቱ ምሕረት እለምናለሁ። ምንም ፖስታ ሳልይዝ መምጣቴ አስቀድመው ተስፋ ሰጥተውኝ በኋላ ስለ ከለከሉኝ ነው።

ስለሆነም አሳቤ ከንቱ እንዳልሆነ እቆጥረዋለሁና ይኸው አሳቤ ወደፊት በሚፈጸምበት መንገድ ሊታደስ ይችላል ።

ለሁለቱ አገሮቻችን መቀራረብ ያደረግሁት ነገር ቢኖር ከእኔ ይበልጥ ደስ የሚለው ሰው የለም ግርማዊ ንጉሥ ሆይ የፍጹም ታማኝነት አገልግሎቴን እንዲረዱት እለምናለሁ ።

Discours de Monsieur Maillet.

Je remercie Sa Majesté l'impératice Zeouditou, ainsi que Sa Majesté le Roi Tafari Makonnen de m'avoir procurer l'occasion de réaliser entre la Cote Française des Somalies et la capitale de l'Ethiopie addis-abeba la première liaison aérienne.

Je suis trop ému pour pouvoir exprimer mes sentiments et la joie que cette réalisation me causent

Je m'excuse d'être obligé de démentir l'affirmation de monsieur le Ministre de France, si je n'apporte aucun courrier malgré la promesse qui m'avait été faite, c'est que ce courrier m'a été refusé.

Je reste malgré tout persuadé que mon initiative n'a pas été inutile et que mon geste pourra être renouvelé plus efficacement.

Si j'ai pu faire quelque chose pour le rapprochement de nos deux pays, je suis le plus heureux der hommes, et soyez persuadé, Majesté, de mon dévouément sincère.

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ኢትዮጵያ ወደ አንድ የሥልጣኔ ደረጃ መውጣቷን የሚያመለክት የአየር ባቡር በዘመናቸው ወደ አዲስ አበባ በመግባቱ ደስ ስለ አላቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የምረቃ ቃል ተናገሩ ።

ማናቸውም አገር ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለመራመድ ሕይወቱ ኃይል የሚያገኝበት የመገናኛ መንገድ በሚቻለው ዓይነት ሁሉ መሥራት ዋና መሠረት መሆኑ የታወቀና የተመሠከረ ስለሆነ ፤ የሕዝብም ሥልጣኔ የሚስፋበት መንገድ ከምድር ባቡርና ፤ አሁንም በዘመናችን በየር መንገድ የሚሔደው የማይለያይ የተሣሠረ መሆኑን የማያውቅ ሰው አይገኝም ። ዳግማዊ ምኒልክም በአውቀታቸውና በትጋታቸው በፍጥነት የሚሔድ መገናኛ ሁሉ እጅግ ታላቅ ጥቅም መሆኑንና አገራቸውም እንዲጠቀም ልማትም እንዲከተለው በልማቱም ሕዝበ እንዲበለጽግ ስለ ተረዱት፡ በዘመናቸው ከሁሉ የተሻለው መገናኛ የምድር ባቡር እንዲሠራ በማድረጋቸው ምስጋናቸውን ለሁለ ጊዜ አንረሳም ።

እንደዚሁም የምድር ባቡር በሶስት ቀን የሚሔደውን አሁን የአየሩ ባቡር በ፫ ሰዓት ቀርጦ በመሔዱ ፍጥነቱ ከምድር ባቡር የሚበልጥ ስለሆነ ፤ በዛሬውም ዘመን በሞላው ዓለም ለፍጥነት ሥራም ጥቅም ፤ በሥራውም የሚያስደንቅ፡በሠለጠኑትም መንግሥቶች ዘንድ በየለቱ ብርቅ የሆነውን፡አገራችንን ከፍ ወደ አለው ደረጃ እንዲራመድ ያደርገዋል ብለን ስለ አሰብን፤ ካዲስ አበባ እስከ ጠረፍ በጓዝ መንገድ እየተሔደ እስቲደረስ የሚያጐድለው ጥቅሙ እንዳይቀር ጉዳያችንን በፍጥነት ለመፈጸም እንዲረዳንና መንግሥታችን ከመኳንንቶቹና ከከተሞቹ ጋራ በፍጥነት የሚገናኝበት ጥቅሙ እንዲሰፋለት ስንል ይህን የአዌር ባቡር ለማስመጣት አሰብን ።

ለኢትዮጵያም ትልቅነትና በሥልጥንናም መንገድ ከክርስቶስ ልደት አስቀድሞ ከኢየሩሳሌምና ፤ ከዓረብም፥ ከህንድም መንግሥቶች ጋራ፤ በንግድም፥ በፖለቲካም ጉዳይ ይገናኝ እንደ ነበረ፥ ከክርስቶስም ልደት በኋላ ከፖርቱጋልና ከእስፓንያ፥ ከቀሩትም መንግሥቶች ሁሉ ከያንዳንዱ ጋራ በፖለቲካ ይገናኝ እንደነበረ ማንም አይስተውም ። ከ፲፰፻፹፱ ዓመት ወዲህ ግን ባጼ ምኒልክ ትጋት የኢትዮጵያ መንግሥት ስም ጥንት ወደ ነበረችበት ማዕርጓና ኃይሏ መመለስ ትጣጣር ጀመር። አሁን ሳለንም የሚከተሉንም ለዚህ ትጋት እንዲበረቱ በዘመናችን ያሉት መኳንንትና ጀግኖች፥ ጉበዛዝት፥ ትጋታቸው ተስፋችንን ዘወትር እንዳሞቀና እንዳጋለው ነው ።

ይህም የአየሩ ባቡር አዲስ አበባ ስለ መግባቱ ደስታ ለማድረግና ደስታችንንም ለማካፈል ለመጡት ሁሉ ምስጋናችንን እንሰጣለን ። የአየር ባቡሩንም አዲስ አበባ ድረስ መርቶ ለማምጣት በመጀመሪያ ጊዜ ማበቸገሩን ሳይፈራ በድፍረትና በዕውቀት ከጂቡቲ አዲስ አበባ ድረስ እየበረረ የመጣውን ሙሴ ማዬን ከጥልቅ ልባችን እናመሰግናለን። እንደዚሁም ብልህ ለሆነ መኪና ሠራተኛውን ሙሴ ፒካፎር ደግሞ እናመሰግናለን።ለኛም ደስታ፥ ለአገራችንም ክብር የሰጠውን የአየር ባቡር ለመግዛት ትእዛዛችንን በትጋት የፈጸመውን አገልጋያችንን ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያምንም እንደዚሁ ከልባችን እናመሰግነዋለን ።

እግዚአብሔር ለግርማዊት ንግሥት ረዢም ዕድሜ ይስጥልን ፤ ኢትዮጵያንም ለዘለዓለም እድገቷንና ልምላሜዋን ከሚመኙላት ልጆቿ ጋራ እንዲጠብቃት እንመኛለን ።

Discours de S. M. Tafari Makonnen

Il est incontestable qu'un pays, quel qu'il soit, pour arriver à un degré supérieur de la civilisation, doit avant tout développer ses moyens de communications qui constituent le principal facteur de sa vie et de sa puissance. Nul n'ignore que les moyens de progrès des peuples sont intimement liés aux voies des communications, telles que, voies ferrées, et de nos jours, voies aériennes. Nous sommes à jamais reconnaissants à Sa Majesté l'Empereur Menelik II dont l'intelligente activité ayant saisi l'importance des grands avantages que procurerait la rapidité des communications, utile à son pays, et à la prospérité qui s'en suivrait et qu'elle donnerait à son peuple le bien être, a autorisé la construction du chemin de fer qui était de son temps le moyen le plus perfectionné des communications

La comparaison dans la rapidité est tout à l'avantage de l'avion qui accomplit le trajet en 3 heures alors due le chemin de fer met 3 jours. Aujourd'hui, c'est l'avion, ce merveilleux instrument que le cerveau humain a créé, qui est employé pour les affaires urgentes; Le vif et constant intérêt que le monde civilisé porte à notre pays Nous a donné à penser que l'avion nous permettra d'atteindre un degré supérieur de civilisation; il pourra aussi contribuer à récuperer, par sa rapidité, les avantages qui nous échappaient à cause de la longueur de la route caravanière d'addis-abeba jusqu'à la cote; Notre gouvernement pourra jouir d'un autre avantage, non moins appréciable, c'est celui de pouvoir communiquer avec ses Chefs et ses différentes villes.

Personne n'ignore que bien avant la naissance de JesusChrist l'Ethiopie jouissait d'une haute considération grâce à sa puissance et à sa civilisation; elle entretenait des relations politiques et commerciales avec la Palestine, l'Arabie et les Indes; après la naissance de notre Saint Sauveur et à commencer du quinzième siécle, elle a cultivé les mêmes relations avec le Portugal, l'Espagne et avec d'autrés pays.

Apartir de 1884, grâce à l'esprit clairvoyant de Sa Majesté l'Empereur MENELIK II, l'Ethiopie s'est efforcée de reprendre son ancien rang et sa puissance d'autrefois Nous ainsi que ceux qui nous suivront, devons continuer dans cette voie.

Il est juste de reconnaitre que nos Chefs, nos guerriers et notre jeunesse ont tenu à cœur d'encourager et de raviver nos espoires par leur activité.

NOUS exprimons Notre gratitude à tous ceux qui ont bien voulu partager Notre joie à l'occasion de l'arrivée à Addis-Abeba du premier avion. NOUS félicitons de tout Notre cœur Monsieur Maillet qui en bravent les difficultés a piloté l'avion de Djibouti à Addis-Abeba avec un remarquable sang froid et avec une grande habilité. nous rendons égalements hommage à l'habilité professionnelle de Mr Picaper NOUS félicitons également Notre fidèle serviteur le Belattin Guiéta Wolde Mariam qui a mis tout son zèle à exécuter NOS ordres pour l'acquisition de cet avion qui fait aujourd'hui l'objet de notre joie et l'honneur de notre pays.

Que Dieu accorde longue vie à Sa Majesté l'Impératrice et protège éternellement l'Ethiopie ainsi que ses fils, soucieux de sa grandeur et de sa prospérité.

የግርማዊ ንጉሥ ምርቃን በአማርኛና በፈረንሳዊ ተነበ ሲጨረስ ማርሽ ተፈሪና ማርሺዝዬ ተነፋና ተጨበጨበ ።

ከዚህ ቀጥሎ በአንድ ወገኑ የግርማዊ ንጉሥ መልክ ያለበት፣ ደግሞ በአንድ ወገኑ የአየሩ ባቡር ሥዕልና ንሥረ ተፈሪ የሚለው ስሙ የተጻፈበት የወርቅ ሜዳይ ለአየሩ ባቡር መምጣት መታሰቢያ እንዲሆን ተብሎ ለኢትዮጵያ መኳንንቶችና ለውጭ አገር ሰዎች በግርማዊ ንጉሥ እጅ ታደለ።

ደግሞ ይህ የአየር ባቡር በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በግርማዊ ንጉሥ ዘመን ወደ አዲስ አበባ ስለ መግባቱ መታሰቢያ ሁኖ የሚኖር በላዩ የኢትዮጵያ አንበሳና የአየሩ ባቡር የተሣለበት ንሥረ ተፈሪ የሚል ቃል የተጻፈት የወርቅ መዝገብ የተባለው በክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል እጅ ቀርቦ ግርማዊ ንጉሥና የኢትዮጵያ መኳንንቶችና ሚኒስትሮች ከውጭ አገር ሰዎችም በዚያው የተገኙ ትልልቆቹ ሁሉ ፈረሙበት ።

ከዚህ በኋላ ሸፓኝ ማደል ተጀመረ ፤ ይህም ሁሉ አደራረግ ሲፈጸም የአየሩ ባቡር ስሙ ንሥረ ተፈሪ ተብሎ ተሠየመ። ስሙም ሲሠየም ሰው ክርስትና ተነሥቶ የክርስትና ስም ሲሠየም የክርስትና አባት እንዲደረግለት የአየር ባቡርና ሌላም ይህን የመሰለ ትልልቅ መሣሪያ ስም ሲሰየም በውሮፓ አባት ይደረግለታልና ይህም የኢትዮጵያ የአየር ባቡር ንስረ ተፈሪ ተብሎ ሲሠየም የግርማዊ ንጉሥ ሁለተኛው ወንዱ ልጃቸው ልዑል መኰንን ተፈሪ አባት ሁኖ በአየሩ ባቡር ላይ ሸፓኝ አፈሰሰና ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ከመኳንንቱ ጋራ በብዙ አቶሞቢሎች ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሱ ።

የአየር ባቡሩ አቀባበል በተደረገ በማግሥቱ በነሐሴ ፲፫ ቀን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ለፈረንሳዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ለሙሴ ዱሜርግ ደስታቸውን ለማካፈል ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በቴሌግራም አሳለፉ ።

ይድረስ ለክቡር ሙሴ ዱሜርግ ።

የፈረንሳዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ። የኢትዮጵያ መንግሥት ከፈረንሳዊ አገር ከፖቴዝ ቤት ያስመጣው የአየር ባቡር የፈረንሳዊ ተወላጅ በሆነ በሙሴ ማዩ ነጂነት ከጅቡቲ ተነሥቶ አዲስ አበባ በሦስት ሰዓት ስለ መድረሱና ፤ ደግሞ በክቡርነትዎና በእኛም ጊዜ የአየር ባቡር መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ስለ መግባቱ ደስታችንን እናካፍልዎታለን ።

ንጉሥ ተፈሪ።

TELEGRAMME

Son Excellence Monsieur Doumergue.

Président de la Republique Française Paris

Nous tenons à faire à part à votre Excellence de la joie que nous avons ressentie à l'occasion de l'arrive en 3 heures à addis-abeba de l'aéroplane qne le Gouvernement Ethiopien à fait venir de la maison potez plote de Djibouti par un français Monsieur Maillet ainsi que pour la réalisation de cet évenement ayant eu lieu pour la premier fois sous la haute presidence de votre Excellence et sous notre Règne.

NEGOUS TEFERI.

ቀጥሎም ንስረ ተፈሪ የተባለው የአየር ባቡር ለተሠራበት ለፖቴዝ ቤት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቴሌግራም አሳለፈዋል ።

ይድረስ ከሙሴ አንሪ ፖቴዝ ።

ከእናንተ ቤት የመጣው የአየር ባቡር በመኪናው ጠንካራነትና በነጂው ብርታት ከጅቡቲ ተነሥቶ አዲስ አበባ በሦስት ሰዓት ስለ ገባ ደስታችንን እናካፍላችኋለን ።

ንጉሥ ተፈሪ

Je suis trop ému pour pouvoir exprimer mes sentiments et la joie que cette réalisation me causent

Je m'éxcuse d'être obligé de démentir l'affirmation de monsieur le Ministre de France, si je n'apporte aucun courrier malgré la promesse qui m'avait été faite, c'est que ce courrier m'a été refusé

Je reste malgré tout persuadé que mon initiative n'a pas été inutile et que mon geste pourra être renouvelé plus efficacement.

Si j'ai pu faire quelque chose pour le rapprochement de nos deux pays, je suis le plus heureux der hommes, et soyez persuadé, Majesté, de mon dévouément sincère.

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ኢትዮጵያ ወደ አንድ የሥልጣኔ ደረጃ መውጣቷን የሚያመለክት የአየር ባቡር በዘመናቸው ወደ አዲስ አበባ በመግባቱ ደስ ስለ አላቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የምረቃ ቃል ተናገሩ ።

ማናቸውም አገር ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለመራመድ ሕይወቱ ኃይል የሚያገኝበት የመገናኛ መንገድ በሚቻለው ዓይነት ሁሉ መሥራት ዋና መሠረት መሆኑ የታወቀና የተመሠከረ ስለሆነ ፤ የሕዝብም ሥልጣኔ የሚስፋበት መንገድ ከምድር ባቡርና ፤ አሁንም በዘመናችን ባየር መንገድ የሚሔደው የማይለያይ የተማሠረ መሆኑን የማያውቅ ሰው አይገኝም ። ዳግማዊ ምኒልክም በእውቀታቸውና በትጋታቸው በፍጥነት የሚሔድ መገናኛ ሁሉ እጅግ ታላቅ ጥቅም መሆኑንና አገራቸውም እንዲጠቀም ልማትም እንዲከተለው በልማቱም ሕዝብ እንዲበለጽግ ቅሉ ተረዱት፡ በዘመናቸው ከሁሉ የተሻለው መገናኛ የምድር ባቡር እንዲሠራ በማድረጋቸው ምስጋናቸውን ለሁሉ ጊዜ አንረሳም ።

እንደዚሁም የምድር ባቡር በሶስት ቀን የሚሔደውን አሁን የአየሩ ባቡር በ፫ ሰዓት ቆርጦ በመሔዱ ፍጥነቱ ከምድር ባቡር የሚበልጥ ስለሆነ ፤ በዛሬውም ዘመን በሞላው ዓለም ለፍጥነት ሥራም ጥቅም ፤ በሥራውም የሚያስደንቅ፡በሠለጠኑትም መንግሥቶች ዘንድ በየለቱ ብርቅ የሆነውን፡አገራችንን ከፍ ወዳ አለው ደረጃ እንዲራመድ ያደርገዋል ብለን ስለ አሰብን፡ ከዲስ አበባ እስከ ጠረፍ በጓዝ መንገድ እየተሔደ እስቲደረስ የሚያጐድለው ጥቅሙ እንዳይቀር ጕዳያችንን በፍጥነት ለመፈጸም እንዲረዳንና መንግሥታችን ከመኳንንቶቹና ከከተሞቹ ጋራ በፍጥነት የሚገናኝበት ጥቅሙ እንዲሰፋለት ስንል ይህን የአየር ባቡር ለማስመጣት አሰብን ።

ለኢትዮጵያም ትልቅነትና በሥልጥንናም መንገድ ከክርስቶስ ልደት አስቀድሞ ከኢየሩሳሌምና ፤ ከዓረብም፡ ከህንድም መንግሥቶች ጋራ፤ በንግድም፡ በፖለቲካም ጉዳይ ይገናኝ እንደ ነበረ፡ ከክርስቶስም ልደት በኋላ ከፖርቱጋልና ከእስፓንያ፡ ከቀሩትም መንግሥቶች ሁሉ ከያንዳንዱ ጋራ በፖለቲካ ይገናኝ እንደነበረ ማንም አይስተውም ። ከ፲፰፻፹፬ ዓመት ወዲህ ግን በዳ ምኒልክ ትጋት የኢትዮጵያ መንግሥት ስም ጥንት ወደ ነበረችበት ማዕርግና ኃይሏ መመለስ ትጣጣር ጀመር። አሁን ሳለንም የሚከተሉንም ለዚህ ትጋት እንዲበረቱ በዘመናችን ያሉት መኳንንትና ጀግኖች፡ ጉበዛዝት፡ ትጋታቸው ተስፋችንን ዘወትር እንዳሞቀና እንዳጋለው ነው ።

ይህም የአየሩ ባቡር አዲስ አበባ ስለ መግባቱ ደስታ ለማድረግና ደስታችንንም ለማካፈል ለመጡት ሁሉ ምስጋናችንን እንሰጣለን ። የአየር ባቡሩንም አዲስ አበባ ድረስ መርቶ ለማምጣት በመጀመሪያ ጊዜ ማስቸገሩን ሳይፈራ በድፍረትና በዕውቀት ከጅቡቲ አዲስ አበባ ድረስ እየበረረ የመጣውን ሙሴ ማዬን ከጥልቅ ልባችን እናመሰግናለን። እንደዚሁም ብልህ ለሆነ መኪና ሠራተኛውን ሙሴ ፒካፔር ደግሞ እናመሰግናለን።ለኛም ደስታ፡ ለአገራችንም ክብር የሰጠውን የአየር ባቡር ለመግዛት ትእዛዛችንን በትጋት የፈጸመውን አገልጋያችንን ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያምንም እንደዚሁ ከልባችን እናመሰግነዋለን ።

እግዚአብሔር ለግርማዊት ንግሥት ረዥም ዕድሜ ይስጥልን ፤ ኢትዮጵያንም ለዘለዓለም እድገቷንና ልምላሜዋን ከሚመኙላት ልጆቿ ጋራ እንዲጠብቃት እንመኛለን ።

Discours de S. M. Tafari Makonnen

Il est incontestable qu'un pays, quel qu'il soit, pour arriver à un degré supérieur de la civilisation, doit avant tout développer ses moyens de communications qui constituent le principal facteur de sa vie et de sa puissance. Nul n'ignore que les moyens de progrès des peuples sont intimement liés aux voies des communications, telles que, voies ferrées, et de nos jours, voies aériennes. Nous sommes à jamais reconnaissants à Sa Majesté l'Empereur Menelik II dont l'intelligente activité ayant saisi l'importance des grands avantages que procurerait la rapidité des communications, utile à son pays, et à la prospérité qui s'en suivrait et qu'elle donnerait à son peuple le bien être, a autorisé la construction du chemin de fer qui était de son temps le moyen le plus perfectionné des communications

La comparaison dans la rapidité est tout à l'avantage de l'avion qui accomplit le trajet en 3 heures alors due le chemin de fer met 3 jours. Aujourd'hui, c'est l'avion, ce merveilleux instrument que le cerveau humain a créé, qui est employé pour les affaires urgentes; Le vif et constant intérêt que le monde civilisé porte à notre pays Nous a donné à penser que l'avion nous permettra d'atteindre un degré supérieur de civilisation; il pourra aussi contribuer à récuperer, par sa rapidité, les avantages qui nous échappaient à cause de la longueur de la route caravanière d'addis-abeba jusqu'à la cote; Notre gouvernement pourra jouir d'un autre avantage, non moins appréciable, c'est celui de pouvoir communiquer avec ses Chefs et ses différentes villes.

Personne n'ignore que bien avant la naissance de JesusChrist l'Ethiopie jouissait d'une haute considération grâce à sa puissance et à sa civilisation; elle entretenait des relations politiques et commérciales avec la Palestine, l'Arabie et les Indes; après la naissance de notre Saint Sauveur et à commencer du quinzième siécle, elle a cultivé les mèmes relations avec le Portugal, l'Espagne et avec d'autres pays.

Apartir de 1884, grâce à l'esprit clairvoyant de Sa Majesté l'Empereur MENELIK II, l'Ethiopie s'est efforcée de reprendre son ancien rang et sa puissance d'autrefois Nous ainsi que ceux qui nous suivront, devons continuer dans cette voie.

Il est juste de reconnaitre que nos Chefs, nos guerriers et notre jeunesse ont tenu à cœur d'encourager et de raviver nos espoires par leur activité.

NOUS exprimons Notre gratitude à tous ceux qui ont bien voulu partager Notre joie à l'occasion de l'arrivée à Addis-Abeba du premier avion. NOUS félicitons de tout Notre cœur Monsieur Maillet qui en bravent les difficultés a piloté l'avion de Djibouti à Addis-Abeba avec un remarquable sang froid et avec une grande habilité. nous rendons également hommage à l'habilité professionnelle de Mr Picaper NOUS félicitons également Notre fidèle serviteur le Belattin Guiéta Wolde' Mariam qui a mis tout son zèle à exécuter NOS ordres pour l'acquisition de cet avion qui fait aujourd'hui l'objet de notre joie et l'honneur de notre pays.

Que Dieu accorde longue vie à Sa Majesté l'Impératrice et protège éternellement l'Ethiopie ainsi que ses fils, soucieux de sa grandeur et de sa prospérité.

የግርማዊ ንጉሥ ምርቃን በአማርኛና በፈረንሳዊ ተነበ ሲጨረስ ማርሽ ተፈሪና ማርሽዝዬ ተነፋና ተጨበጨበ ።

ከዚህ ቀጥሎ በአንድ ወገኑ የግርማዊ ንጉሥ መልክ ያለበት፥ ደግሞ በአንድ ወገኑ የአየሩ ባቡር ሥዕልና ንሥረ ተፈሪ የሚለው ስሙ የተጻፈበት የወርቅ ሜዳይ ለአየሩ ባቡር መምጣት መታሰቢያ እንዲሆን ተብሎ ለኢትዮጵያ መኳንንቶችና ለውጭ አገር ሰዎች በግርማዊ ንጉሥ እጅ ታደለ።

ደግሞ ይህ የአየር ባቡር በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በግርማዊ ንጉሥ ዘመን ወደ አዲስ አበባ ስለ መግባቱ መታሰቢያ ሁኖ የሚኖር በላዩ የኢትዮጵያ አንበሳና የአየሩ ባቡር የተሣለበት ንሥረ ተፈሪ የሚል ቃል የተጻፈት የወርቅ መዝገብ የተባለው በክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል እጅ ቀርቦ ግርማዊ ንጉሥና የኢትዮጵያ መኳንንቶችና ሚንስትሮች ከውጭ አገር ሰዎችም በዚያው የተገኙ ትልልቆቹ ሁሉ ፈረሙበት ።

ከዚህ በኋላ ሽፓኝ ማደል ተጀመረ ፤ ይህም ሁሉ አደራረጓ ሲፈጸም የአየሩ ባቡር ስሙ ንሥረ ተፈሪ ተብሎ ተሠየመ። ስሙም ሲሠየም ሰው ክርስትና ተነሥቶ የክርስትና ስም ሲሠየም የክርስትና አባት እንዲደረግለት የአየር ባቡርና ሌላም ይህን የመሰለ ትልልቅ መሣሪያ ስም ሲሰየም ባውሮፓ አባት ይደረግለታልና ይህም የኢትዮጵያ የአየር ባቡር ንስረ ተፈሪ ተብሎ ሲሠየም የግርማዊ ንጉሥ ሁለተኛው ወንዱ ልጃቸው ልዑል መኰንን ተፈሪ አባት ሁኖ በአየሩ ባቡር ላይ ሽፓኝ አፈሰሰና ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ከመኳንንቱ ጋራ በብዙ አቶሞቢሎች ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሱ ።

የአየር ባቡሩ አቀባበል በተደረገ በማግሥቱ በነሐሴ ፲፫ ቀን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ለፈረንሳዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ለሙሴ ዱሜርግ ደስታቸውን ለማካፈል ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በቴሌግራም አሳለፉ ።

ይድረስ ለክቡር ሙሴ ዱሜርግ ።

የፈረንሳዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ። የኢትዮጵያ መንግሥት ከፈረንሳዊ አገር ከፖቴዝ ቤት ያስመጣው የአየር ባቡር የፈረንሳዊ ተወላጅ በሆነ በሙሴ ማዬ ነጂነት ከጂቡቲ ተነሥቶ አዲስ አበባ በሦስት ሰዓት ስለ መድረሱና ፤ ደግሞ በክቡርነትዎና በእኛም ጊዜ የአየር ባቡር መጀመሪ ወደ ኢትዮጵያ ስለ መግባቱ ደስታችንን እናካፍልዎታለን ።

ንጉሥ ተፈሪ።

TELEGRAMME

Son Excellence Monsieur Doumergue.

Présideni de la Republique Française Paris

Nous tenons à faire à part à votre Excellence de la joie que nous avons ressentie à l'occasion de l'arrive en 3 heures à addis-abeba de l'aéroplane qne le Gouvernement Ethiopien à fait venir de la maison potez plote de Djibouti par un français Monsieur Maillet ainsi que pour la réalisation de cet évenement ayant eu lieu pour la premier fois sous la haute presidence de votre Excellence et sous notre Règne.

NEGOUS TEFERI.

ቀጥሎም ንስረ ተፈሪ የተባለው የአየር ባቡር ለተሠራበት ለፖቴዝ ቤት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቴሌግራም አሳልፈዋል ።

ይድረስ ከሙሴ አንሪ ፖቴዝ ።

ከእናንተ ቤት የመጣው የአየርባቡር በመኪናው ጠንካራነትና በነጂው ብርታት ከጅቡቴ ተነሥቶ አዲስ አበባ በሦስት ሰዓት ስለ ገባ ደስታችነን እናካፍላችኋለን ።

ንጉሥ ተፈሪ

TELEGRAMME.

Addis-Abeba le 19 Août 1929.

Monsieur Henry Potez
Ingénieur Constructeur
Rue Clément 14
Levallois
Seine.

Appareil acheté chez vous a fait parcours Djibouti Addis-Abeba en trois heures prouvant sa résistance et capacité pilote Stop Nous vous faisons part de Notre satisfaction

NEGOUS TEFERI.

መሥራት መታደል ።

ለመንግሥታቸውና ለሕዝባቸው ሥራ ለመሥራት የሚያስቡ፤ አስበውም የሠሩ ብዙ ነገሥታት ነበሩ ። ነገር ግን መሥራትንና መታደልን ባንድነት ያገኙ እጅግ ጥቂቶች ናቸው ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ቀድሞም አልጋ ወራሽና እንደራሴ ሲባሉ ፤ አሁንም ንጉሥና አልጋ ወራሽ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከሆኑ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፡ለኢትዮጵያ መንግሥትና ለሕዝቡ የሚያስቡትን አሳብና የሚሠሩትን ሥራ የኢትዮጵያ ጠላት ከሆነ በቀር የማያውቀውና የማያመሰግን የለም ።

እህል ዘርቶ እሸቱን ፤ ወይን ተክሎ ፍሬውን መብላት እጅግ መታደል ነውና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ለኢትዮጵያና ለሕዝብዋ የሚያስቡት አሳብ ሁሉ እየተከናወነና እየተፈጸመ መሔዱ በሠሪነታቸው ላይ የታደሉ መሆናቸውን ያስረዳል ። እኛም ዛሬ ያለነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመናችን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን የመሰለ አሳቢና ሠሪ ንጉሥ ማግኘታችንና ማየታችን እጅግ መታደላችንን ይመሰክርልናል ።

ወደ ፊትም እግዚአብሔር ለግርማዊት ንግሥታችንና ለግርማዊ ንጉሣችን ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ ሰጥቶ ኢትዮጵያ ከዚህ ወደሚበልጠው የእውቀት ደረጃ የምትደርስበትን ሥራ እንዲሠሩልን ያድርግልን እያለ ብርሃንና ሰላም እውነተኛና ከልብ የሆነ ምኞቱን ይገልጣል ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ከጀርመን ሌጋሲዮን ከመጣ ራዲዮ የተገኘ የዕለት ወሬ።

ግራፍ ዜፔሊን የተባለ ትልቅ የጀርመን የአየር ባቡር ዓለምን እንዲዞር ከበርሊን ተነሥቶ በሲቤሪያ አውራጃዎች እየበረረ አልፎ በነሐሴ ፲፫ ቀን ወደ ቶክዮ ከተማ ገብቶ ከከተማው ላይ እየተንዠበበ ዞረ።የከተማው ሰዎችም ከልክ ባለፈ አቀባበል ተቀበሉት ።

ከኢጣልያን ሌጋሲዮን የመጣ ራድዮ የዕለት ወሬ ።

እያ ፤ የኢጣልያንና የፈረንሳዊ፥ የቤልጂክና የጃፓን መልክተኞች የእንግሊዝን ሐሳብ እንደገና ተመልክተው የዮንግ ሐሳብ አከሔድም መለወጡ የማይቻል መሆኑን አውቀው ፤ ጥቃቅኖች የሆኑ ትንንሽ ክፍሎችን ለመለወጥ እንዲሞክሩ እንዲሚሻል ቈርጠዋል ።

የአውሮጳ ጋዜጦች የጉባኤው መሰብሰብ ፍሬ እንደሚገኝበት አያምኑም ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤትበርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባሌሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፪ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ክረጃ	፻፸፰ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፰ ብር
: : ባለ ድመ ።		፻፵፭
: : ባለአህያ ።		፻፵
: : ባለሳቢ ግመል ።		፻፰
: : ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፲፪
" " ጃፖን		፻፸፰ብር
ሱካር	ጁኒያ	፵፫ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፺ሳቲንም
ባአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፺፬ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፹ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፱

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንቸር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒክላ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኬያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ። የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቁርጥማትና [illegible]፣ የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊኖ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።

ANTICA CASA FONDATA NEL 1857
Borsalino

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሶማሌ ወኪል ሴ ፈ ፊርናንዴ ሰፍ ልጆቹ ። የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሱቅ ።

ማስታወቂያ ።

እኔ ሚካኤል ማኩሩስ ቀበና እንግሊዞች ድልድይ አጠገብ ያለኝን ቦታዬን እሸጣለሁ፤ከቦታውም ላይ አንድ ትልቅ የሣር ክዳን ሦስት ክፍል ቤት፤ አንድ የፍርኖ መጋገሪያ ቆርቆሮ ዘገኝ ቤት፤ አንድ ቆርቆሮ ክዳን የከብት ቤት፤ ፲፻፺ የባሕር ዛፍ፤ የቦታውም ስፋት ፫ሺ ፺፫ አራት ማእዘን ሜትር ነው።ይኸንን ቦታ ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ አፊታውራሪ ማሙ በየነ ቤት በታች ያለው ቤቴ ድረስ ብትፈልጉኝ አገኛለሁ ።

ሚካኤል ማኩሩስ ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።
ሕራንት ባግዳሣሪያን ።

[illegible] ቤት [illegible] ፊት ለፊት [illegible] መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋው ግን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፈርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።

አ በ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ጄሮ አቶ ብርሃነ ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየዓይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በ፳ መታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው።

ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቀባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

የሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

ሲዲል ዓይነት [illegible] ቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንዳቱ እጅግ የፈጠነነው ፡ የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የታመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድኖም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያቤትነው።

ጉድይር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
5me ANNÉE № 55

ሐሙስ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 29 AOUT 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በአገራቸው
ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በኢትዮጵያ የችጋር አደጋና ከዚሁም ለመዳን የሚያስፈልግ ብልሃት ከምግብ ማነስ የተነሣ የከብት ማለቅ ። በአንበጣ ምክንያት ሰዎችንና ከብቶችን ስለሚያም በሽታ ።

የኢትዮጵያን ሰማይ ብዙ ጊዜ በለበሰው አንበጣ የተነሣ ስለከብት ነገር ስናገር፥ በቅርብ ጊዜ አደጋ መምጣቱን በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ውሥጥ ካስታወቅኩ ብዙ ጊዜ አይሆንም። በዚሁም ነገር የመንግሥትን ትጋት አሳስቤ ነበር ። አሁን ግን ይኸውና ከዚሁ አደጋ አላመለጥንም ። ካሁን ቀድሞ የተነሣው አንበጣ ብርቱ ጉዳት ማድረጉን ስለጀመረ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች የሚያደርጉትን ነገር ሰላጡ ተስፋ ቈርጠው እርዳታ ይለምናሉ ።

ይልቁንም ካሁን በፊት በቅርቡ እቱርክ አገር እንዳየሁት ሁሉ፥እንደሲኒማ ሥዕል ሁኖ ይታየኛል። አደጋው አሁን በመጀመሩ ካልጠፋ የሚያስቸግር ነውና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ነቅቶ አንበጣን ለማጥፋት እንደተቻለ መጠን ፈጥነው ቢጀምሩ የሚገባ ነው ። ይኸውም ሥራ በርሻ ሚኒስቴር ላይ ብቻ ሊሆን አይገባም። ነገር ግን እዚህም እንደሌላው አገር ሁሉ ያገሬ ግዛት ሚኒስቴርና የጦር ሚኒስቴር ከርሻ ሚኒስትር ጋር ሁነው እንደተቻላቸው መጠን ይህነኑን አንበጣ ለማጥፋት የሚያስፈልገውን ነገር ቢያደርጉ የሚገባ ነው ። ይኸውም ሥራ ለዛሬው ብቻ አይደለም ነገር ግን በማናቸውም ይህ አንበጣ በሚወለድበት ጊዜ ሁሉ ሊደረግ ይገባል ። በእንደዚህ ያለው ሥራ እነዚህ ሦስቱ ሚኒስትሮች፥የየከተማው ሹሞችና ምስለኔዎች ሁሉ፥ በሌላው አገር ለገበሬዎች ምክር እየሰጡ፥ ወይም በገንዘብ ያበረቱዋቸዋል ። እንደዚህም ሲሆን ሰብሉን፥ከብቶቹንና ቤተ ሰቦቹን ሁሉ ለማዳን መበረታት ይጀምራል ። አደጋው ለእህል ብቻ አይደለም ነገር ግን ለሣርና ለማናቸውም የከብት ምግብ ሁሉ ነው ከእህል ጥፋት እንደዚሁ የሣር ጥፋ ፡ ሲሆን የከብት ማለቅ ይሆናል።ይልቁንም በገጠር አገር የሙቀት አገር በሽታ ባለበት በሽታ ያለበት ሣር አለ ። በ፲፱፻፲፫ ዓመተ በቱርክ አገር አንበጣ ባደረበት አገር ሁሉ ገጠሩን ተላላፊ የከብት በሽታ እንደያዘው እኔው ራሴ እመሰክራለሁ ። ስለዚህ ከዚህ በላይ የተጠሩት ሦስቱ ሚኒስትሮች እንደሚቻላቸው መጠን ይህነኑ አንበጣ ገና ክንፍ ሳያወጣ እንደሚያስፈልግ እንዲያጠፉት ትጋታቸውን እንዲያደርጉ አሳስባቸዋለሁ ። ደግሞ የርሻ ሚኒስትር አንበጣ ባጠፋበት አገር ላሉ ገበሬዎች አንበጣ የማይበላው ስለእህልና ስለሣር የሚተከ ነገር እንዲተክሉ ከዛሬ ጀምሮ ማስታወቂያ እያደረገ እንዲያመለክታቸውና እንዲያስታውቃቸው ማሳሰቤን አልተውም።

በዚህም ረገድ አገሩን ከችጋር፥ከብቶቹ ከምግብ ማጣት የተነሣ ከሚያገኛቸው በሽታና በችጋር ከማለቅ የሚያድናቸው ይሆናል ።

ሚህራን ክይማኪያን ።

ንጉሥ ተፈሪ በኢትዮጵያ ።

በብርሃንና ሰላም ቍ ፶፬ እንደተጻፈው ነሐሴ ፲፪ ቀን የአየር ባቡር አዲስ አበባ በገባ ጊዜ ወድያው በያገሩ አውራጃ ላሉ አገረ ገዦዎች ወሬ ደረሰላቸውና ሁሉም ደስታቸው ከልክ ያለፈ ሆነ ።

ይኸውም ንጉሡ ተፈሪ በነሐሴ ፳፪ ቀን በዓሥር ሰዓትና ፳፫ ቀን በ፱ ሰዓት በአዲስ አበባ ተንዣቦ የከተማው ሰው ሁሉ በአየር ላይ ከፍ ብሎ ሲገለባበጥና ሲዞር በሚያስገርም አስተያየት መብረሩን አሳይቶ ወደ ስፍራው ተመለሰ ።

የኢትዮጵያ አገረ ገዦዎች የአየር ባቡር በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ብርታት ወደ አገራችን መግባቱ ደስ ያላቸው

የአየሩ ባቡር በአገራቸው ላይ እየተንዣበበ መጥቶ በሉበት ቦታ በቅጽበት ደብዳቤና የሚያስቸኵለውን መልእክት ሲያደርስላቸው የሥራው መክናወንና ፍጥነቱ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ስለ ሆነ ነው ። ሥራውን ሲሠራ ለማየትም በጣም ይጓጓሉ ።

እያሌ ያልተማሩ ሰዎች የአየር ባቡር ለጕዳት ብቻ የተሠራ ይመስላቸው ይሆናል ። ግን የአየር ባቡር በፍጥነት በሮ የሚደርስ በመሆኑና የሚሔድበት መንገድ በአየር ላይ ስለ ሆነ መንገድ መጥረግ፥ ድልድይ መሥራት የማያስፈልገው የድካም አቅላይና የመንግሥት ረዳት ነው ። የብረት መንገድ በተዘረጋበት የምድር ባቡር አለ፤የሠረገላ መንገድ በተዘረጋበትም አቶሞቢል አለ ። እነዚህ ሁለቱ እስኪሰናዱና እነሱ በችኵል የሚያስፈልገውን በፍጥነት ሊያደርሱት በማይችሉበት ቦታ ደግሞ የአየር ባቡር ንሥረ ተፈሪ ማስፈለጉ ጥርጥር የለበትም።

ስለ ንሥረ ተፈሪ አለቃ ዳንኤል የተቀኙት ቅኔ ።

ሥላሴ

ይባእ ገነተ ፥ ድላ ፈረሰ እስክድር ንሥረ ጥበብ
ሰማያተ ዓርገ በሥጋ ፥ እስመ ከመ ልቡ ፈቀደ ።
ውእቱ መባልዕተ ሥጋ እምንእሱ ለመደ ።
ወለእመ ነሐትተ ንሕነ ተፈሪ ፥ እንተ ንሥርከ ነገደ ።
እምንሥረ እስክድር ዘተወልደ።
አመጣነ ሎቱ ሠራዕከ ፥ በጊዜ ወረደ ።
መርኅበከ ዘሥጋ ማዕደ።

መወድስ

ለንስረ ተፈሪ ንጉሥ በመዋዕሊሁ፥
ለእመ በምድር ትሄሉ ፥ ንግሥተ ሳባ እግዓዚት ።
በውስተ ሀገሩ እምወድቀ ዘሰኰና እግረ ቅርፍት ።
ጳበለ ደዌ ከመ ይንግፍ ፥
በአክናፍ አምጣነ አውረዶ እምኤዶም ገነት ።
ንስረ ተፈሪ ነደ እሳት ።
ለዘፈረየ እስከለ ፥ መንግሥተ ምኒልክ ዕፀ ሕይወት ።
ተክሉሂ ሃይመተ ክብር በመርኅበ ሥጋ ስፍሕት ።
እንስርተ እለጸውዑ ንጉሠ ዓለም ወንግሥት ።
ጊዜ ንፍሐተ ቀርን ዓቢይ ፥ እፍራሰ ተፈሪ እንስርት ።
ገደላ ኅበ ህለወ አምጣነ ይትጋብኡ በቅጽበት ።

ስለ ጳጳሳት ሹመት በደብረ ብርሃን የተደረገ ደስታ።

ከሀገራችን ሊቃውንት ጳጳስነት ስለ ተሾሙ የደብረ ብርሃን ካህናቶች በቴሌግራም አድራሻውን አይተው ስለደስታቸው የደረሱትን ድርሰትና የተቀኙትን ቅኔ በሙሉ ለመጻፍ ቋማያደርስ ስለሆነ ከብዙ በጥቂቱ እነዚህን ቅኔዎች እንጽፋለን።

መወድስ ።

በገጸ አዕናቍ ንጉሥ ወንግሥተ ኃይል ።
ተከብቶ ኢትክል ሀገረ ማርቆስ ሃይማኖት ።
መልዕልተ ዕንዓን አድባር እስመ ተሐንፀት ።
ወለእሥራኤል አበዊነ መርሆሙ በዓምደ ደመና ሚካኤል ማኅቶት ።
በረከተ ቄርሎስ ቀዳማዊ እስመ ከመ ትካት
ይመልእ ዓውደ ምኒልክ መንግሥት ።
እመ ሦዓሂ ኃይለ ሥላሴ መሥዋዕተ ስብሐት።
አብርሃም ለአዕርጎ ወይሐስቅ ለመሥዋዕት ።
ላዕለ ደብረ መንግሥት ዓርጉ መርሆ ሰማያት ።
እስመ ነሥኡ እምእዴሁ ለጴጥሮስ መሠረት ።
ዘመ ምሬ ተክለ ማርያም ።

መወድስ ።

እምትእዛዘ ጴጥሮስ ሊቀ አደ ኅመልማል ።
ሃይማኖት ወይን ዘተተክለት በኒቅያ ።
ፍሬ አእምሮታ አጽገበ ለኢትዮጵያ ።
መትልወ ቄርሎስ ደኃራዊ አብርሃም ክልኡ አኮኑ ሰቀያ፥
ትርጓሜ ወንጌል ማየ ሕይወት ።
ዘልበ ሕሙማ ያሐዩ ወይነብር ለአርአያ ።
ለተንሣርሂ ኢይትከሃል ለብሑርን ዕበያ ።
ትኩኖ ማኅደረ ኃይለ ሥላሴ እስመ ሐረያ ።
ወክፍሉ ጸእቲ እስከለ ማርያም እስያ ።
ሊፍቁረ እግዚእ ኃይለ ሥላሴ ዮሐንስ ሐዋርያ ።
ዘደብተራ ኃይለ መስቀል ።

በሲዳሞ ሀገረ ሰላም ከተማ የጳጳሳትን የምስራች በዓልስለ ማክበር ።

፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ሰኔ ፳፱ቀን ስለ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስና ስለ አራቱ ጳጳሳት የምስራች ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ወደ ክቡር ደጃዝማች ብሩ የተላከው ቃል ሰኔ ፳፯ ቀን ክቡር ደጃዝማች ብሩና መኳንንቱ ሠራዊቱ ከየአድባራቱ ካህናትና ከተሰበሰቡበት ከሕዝቡ ፊት ተነቦ በተሰማ ጊዜ በሲዳሞ አውራጃ በሃገረ ሰላም ከተማ የተደረገው የደስታና የማኅሌት ቃል ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ።

መጀመሪያ ካህናቱ ከየአድባራቱ ተጠርተው ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው ንዋየ ቅድሳቱን እየያዙ በየመዓርጋቸው በሦስት ሰዓት መጡ። መኳንንቱና ሠራዊቱም በየሻለቃቸው ተሰብስበው ባዳራሹ ምንጣፉ አምሮ ተነጥፎ፥ ክቡር ደጃዝማች ብሩ በዚያ ተቀምጠው ዘበኞቻቸውን ግራና ቀኝ አሰልፈው ከዚህ በኋላ የየአድባራቱ ካህናት እንደ ማዕርጋቸው ተቀመጡ። የምስራቹም ወረቀት በቀረበ ጊዜ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ታጥቀው ቆመው ወረቀቱን አስነብበው ካህናቱና መኳንንቱ ሕዝቡም ሰምተው ይበጅ ያድርግ ብለው እጅ ነሥተው ደጃዝማች ከተቀመጡ በኋላ ሕዝቡ ዳር እስከ ዳር አጨበጨበ።ግራና ቀኝ ተሰልፈው የነበሩት ዘበኞችም ስለ ደስታቸው ብዛት ታዘው በጣም አድርገው ብዙ ጥይት ተኰሱ ። ሕዝቡም በጣም ደስ ተሰኝቶ ለእግዚአብሔር ምስጋና ሰጥቶ ለመንግሥታችን ብዙ ምርቃት አደረገ።ንግሥታችንና ንጉሣችን ሺህ ዓመት ያንግሡልን ጠላታቸውን ያልጥፉልን አለ።የመጡትም ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳ-

ኖም ሃይማኖታቸው ቀንቶላቸው እኛንም በሥጋ በነፍስ የሚያድኑን የኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጆች ይሁኑ አለ ።

ከዚህ የሚከተለው ምስማክ ወየዓብይዎ በማኅበረ አሕዛብ ተሰብኮ ወንጌል ከዮሐንስ ወንጌል አንቀጸ አባግዕ ተነቦ ምልጣንም ከኩብ ብሩህ ዘሠረቀ እምእስክንድርያ ተመለጠነ፡እስመ ለዓለም ሰባኬ ወንጌል አርጋኖነ ትንቢት ተባለ፡ቀጥሎም የሀገረሰላም አለቃ የነበሩት አለቃ ገብረ መድኅን ከዚህ የሚከተለውን ወረብወረቡ።

ወዕቀባ አባ ቄርሎስ ለቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያ እንተ ማረራ ማቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት፤ ወባርክ ላዕለ አባግዐ መርዔትከ እስከለ ማርያም ወኃይለ ሥላሴ ፀሐየ ዓለም ።
ከዚህም በኋላ ካህናቱ እንደየማዕርጋቸው ቅኔ ይሰጡ ጀመር ።

መጀመሪያ መወድስ

ቄርሎስ ሐውጽ ጽርሐ መቅደስከ ።
ዘኃይለ ሥላሴ ጠፈረ ወመሠረታ ንግሥተ ማህል ።
ወገጸ ድክምን ታብር በቅብዐ ዲዮስ ቆሮስ ኃይል ።
እምደመና ስብሐት ቃለ ዚአከ ።
ለይረድ ዕንዐ ተዋሕዶ ዘቄርሎስ ጠል ።
ገራህተ ሰላም ሀገሪትነ በነጠብጣብከ ፍቅር ዘርአ ሃይማኖት ከመ ታብቍል ።
ኢትፍራህሰ እምትግርምቶሙ ለቀተልተ ሥጋ አሕባል።
ከመ ታስተፃንዕ መሠረታ ለቤተ ምእመናን ቃለ ወንጌል።
እስመ ተፈኖከ ትሰድድ ቈናጽለ ክደት ወኃጕል።
ኀበ አባግዐ እለ ተገድፉ እምቤተ ማቴዎስ እስራኤል ።

አለቃ ገብረ መድኅን

ሁለተኛ መወድስ

እስከለ ማርያም ምሥራቅ ሙፃአ ፀሐይ
ቄርሎስሃ ፀሐየ ለኵልነ አሥረቀት ።
እስመ በጊዜሁ ኃለፈ ቃለ ማቴዎስ ክረምት።
ወካዕበ እመ ቆመ ለቄርሎስ ቃለ በረከቱ ዘአልቦ ሕፀፀት።
ለቄርሎስ ላዕሌሁ ናሁ ጸገዩ ጽጊያተ ወንጌል ካህናት።
ፈተወኒ ልበ ዚአነ እስከለ ማርያም ቅድስት።
አምጣነ ሠናይ ሥርወ ዚአሃ ኃይለ ሥላሴ ሥርወ መንግሥት
ኀበ ሙሐዘ ማይ ንግሥ እመ በቈለት ።
ሠናይ ዘትፈሪ እስከለ ማርያም ዕፀ ሕይወት ።

ደብተራ አሬጋ

ሦስተኛ መወድስ።

ኢትዮጵያ ትቴፌሣሕ በኃይለ ሥላሴ
እምጣነ ቄርሎስ መጽአ ወሠረፀ ብዝኀ ጽድቅ።
ወኮከብ ዘወጽአ በእስክንድርያ ምሥራቅ ።
ያበርህ ለኵሉ ወይከውን ዕርቅ ።
ወሰብአ ዜና ምጽአቱ እምዕንቈ ሰንፔር ይትበደር ወእምነ
ክቡር ወርቅ
ለዘመጽአኒ አበዊልነ ሆማዕና ዓለም ጥዩቅ ።
በስብሐት ተቀበልዎ አዕሩግ ወደቂቅ።
እንዘ ይብሉ ሐቀ ምስለ ወልደ ዮሐንስ ሊቅ ።
ቡሩክ ዘይመጽእ ምስለ እለ አብርሃም ወይስሐቅ።

አለቃ ጀንበሬ ።

ከሥላሴ ደብር አለቃ ተክለ ሃይማኖት የሚያስተምሯቸው ፰ ያህል ሕፃናት ነበሩና በረጃጅም ዕንጨት ላይ አበባ እያበጁ በየራሳቸው ይዘው መጥተው ያለፍርሃት ከክቡር ደጃዝማች ብሩ ፊት ቀርበው እንዲህ እያሉ ያሸበሽቡ ጀመር ። መንግሥቱ ዘለዓለም ወምኵናኑኒ ለትውልደ ትውልድ፤እምአፉነ እሳት ዘይነድድ አንግፈነ ብርሃናተ ዘይትዐፀፍ ተንሥአ ለነ ። እያሉ በወረብ አጣብተው ሲያሸበሽቡ ክቡር ደጃዝማች ፊሩም በጣም ደስ ብሏቸው አጋፋሪዎች ቢከለክሏቸው ተዉ አትከልክሏቸው (ኢትክልእዎ ለሕፃናት ይምጽኡ ኀቤየ) እንዳለ ጌታ በወንጌል እኒህንም አትከልክሏቸው ብለው ብዙ ጊዜ በክበሮ ሲያሸበሽቡ ቆዩ ። ሕዝቡም እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ በተባለው ቃል አውቆ እጅግ በሕፃናቱ ምስጋና ደስ ተሰኙ ። እኔም ከዚያው ነበርኩና ይህንን አይቶ ጻፍኩ።

ንዋይ ኀሩይ

የከተማ ወሬ ።

ባለፈው ሰሞን አንድ የወለጋ ሰው እሰንጋ ገባያ ከብት ሸጦ ወደ ሰፈሩ ሲመለስ፡ ከጥይት ቤት በታች ሀደረሰ ጊዜ የቋጠረውን ብር ሲንኳኳ ሰምተው፤ ፬ የሚሆሉ ሰዎች ተከታትለውት ሒደው ፤ መጠጥ እንጋብዝህ ብለው አታለው ከአንድ መሸታ ሸያጭ ሴት ቤት አግብተው እዚያች ሴት ቤት በሰንጢ አርደው ገደሉት ። ገንዘቡንም ተካፈሉት ። ለምርምር እንዲያስቸግር ብለውም እግሩንና እጁን ሳይቀር አካሉን ሁሉ ቈራርጠው ወደ ወንዝ ወስደው ጥለውት አሬሳው አሞራ ሲበላው ተገኝቶ በብርቱ ምርምር ብዛት የገደሉት ሰዎች ተያዙ። ከዚህም በኋላ ከጓርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርበው መግደላቸውን አምነው ፤ ይልቁንም በቤትዋ ያሳረደችና ከገንዘቡም ደርሷታል የተባለችውን መሸታ ሸያጭ አስተካክላ መስከራ ሦስቱ ሞት ተፈረደባቸው ።

ይህችም ሴት ምንም ሲገድሉት ለመከልከል ባትችል ዕለቱን ጮኻ፡ ወይም በማግስቱ ለጐረቤትና ለዳኛ ነግራ ሳታስይዝ በመቀረቷ ላፈርሳታውም ምርምር አጋጆ ካገኘች በኋላ እንደ ምሥጢር በመያዝዋ ፤ ከገንዘቡም ተካፋይ በመሆንዋ እስከ ዕድሜ ልኳ ትታሠር ተባለ ። ከ፬ቱ ሁለቱ ሰዎች ግን ለጊዜው የሚበቃ ምስክር ስላልመሰከረባቸው ለምርምር ታሥረው ቈይተዋል ፡

ለዚህም ለሞተው ሰው በምርምሩም ሰሞን፡ በፍርዱም ጊዜ ዘመድ አልተገኘለትም ነበርና የሚፋረድለት እንኳ አጥቶ ዘበኛ ተፋረደለት ። መንግሥት በእንደዚህ ያለው ደግ አድራጎቱ በየጊዜው ዘመድ ላለውም ለሌለውም ሁሉ ዘመድ ሁኖ ደሙን ስለተበቀለለት ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኘው ።

የከተማ ዘበኞችም እንደዚህ ያለውን ክፉ አድራጊ ነፍስ ገዳይና ቀማኛ፡ ሌባውንም ሁሉ የሰረቀውን ዕቃ እንኳ ለማጥፋትና ለመሠወር ሳይችል እጅ በእጅ እየያዙ መንግሥታቸውን ደስ በማሰኘታቸው፤ በምርምሩና ባጠያየቁም ሁሉ የመዝገባቸውን አካሔድ በመልካም የተጣራ በመሆኑ የበለጠ ምስጋና ይገባቸዋል ።

ሹመት ።

ነሐሴ ፲፱ ቀን ክቡር ግራዝማች አማረ የግራዝማች ማሀሉ የነበረውን የዘበኛ ጠቅላይ አለቃነትን ተቀብለው ኒሻንና ሴላም ለመዓርጋቸው የተገባ ሙሉ ሽልማት ተሸለሙ ።

ክቡር ግራዝማች አማረ በዘበኝነት ሥራቸው በጣም ትጉህና ጠንቃቃ ናቸውና የሚገባቸውን መዓርግ ስላገኙ የከተማው ሰው በጣም ደስ ብሎታል ። ይልቁንም ከፊት የበለጠ ሥልጣን ካገኙ የከተማውን ጥበቃ የተሻለ እንዲያደርጉ ሙሉ ተስፋ አለን ።

ብርሃንና ሰላም ክቡር ግራዝማች አማረን እንኳን ደስ አለዎ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልጻል ።

ኑዦልና ፍሊት ስለሚባሉት የሥራ ። ምልክት ማስታወቂያ ።

በ፲፱ቀን ኅዳር ፲፱፻፲፰ ዓመት በአእምሮ ጋዜጣ በወጣው ማስታወቂያ ጭማሪ ከዚህ በታች ያለውን ለነጋዴዎችና ለሕዝብ ያስታውቃል ።

ኑዦልና ፍሊት የሚባሉት የሥራ ምልክት ማስታወቂያ ከነዚሁ ጋር የተያያዘውን ደምብ ሁሉ ጨምሮ በኤታ ኡኒ በኒው ወርክ ከተማ ፳፮ ብሮድወዩ የቆመው የስታንዳር ኡኢል ኩፓኒያ በአውሮፓ ቁጥር በ፴ቀን መስከረም ፲፱፻፳፯ ዓመት በደላዌር አገር (ኤታኡኒ) በዊልሚግቶን ከተማ ለቆመው ለስታንዳር ኡኢል ኦፍ ኒው ዤርሲ ኩፓኒያ ለሚባለው አሳልፏል ።

እነዚሁኑ ኑዦልና ፍሊት የሚባሉትን የሥራ ምልክት ማስታወቂያ ከነሱም ጋር የተያያዘውን ደምብ ሁሉ ጨምሮ በደላዌር አገር (ኤታኡኒ) በዊልሚንግቶን ከተማ የቆመው ስታንዳር ዋል ኩንፓኒ ኦፍ ኒው ጀርሲ የሚባለው በደላዌር አገር (ኤታኡኒ) በዊልሚንግቶን ከተማ ለቆመው ለስታንኮ ኢንኮርፖሬቱድ ለሚባለው አሳልፏል ።

ይኸው የሥራ ማስታወቂያ ኑዦልና ፍሊት የተባለው ከታኅሣሥ ፴፩ቀን ፲፱፻፳፯ ዓመት ጀምሮ በደላዌር አገር(ኤታኡኒ) በዊልሚንግቶን ከተማ ላለው ለስታንኮ ኢንኮርፖሬቱድ ሁኑዋል ።የምልክቱም ዓይነት ከዚህ በታች ያለው ነው ።

Nujol **FLIT**

ኑዦል የሚባለው ምልክት የሚደረገው ከመሬት ከእንስሳትና ከአትክልት ለሚገኘው ተጣርቶ ለወጣለት ዘይት ለፖሮዱኢ ሺሚክ ለሕክምናና ለመድኃኒት መቀመሚያ ለሚሆነው ነገር ነው ፍሊት የሚባለው ምልክት ደግሞ የሚደረገው ለፖሮዱኢ ሺሚክ ለሕክምናና ለመድኃኒት መቀመሚያ የጋዝ ብህሬ ላለበት ነገር ትላትል ለሚገድል ለሚአጸዳ ሽታ ለሚለውጥ መድኃኒት ለማጽዳያና ለመወልወያ ለሚሆን ነገር ሁሉ ነው በኢትዮጵያ ለሥራ ምልክት ነገር ልዩ ደምብ ስለሌለ ይህ ማስታወቂያ ኑዦልና ፍሊት የሚባሉትን ሁለቱን ምልክቶች የሚጠብቅ መሆኑን ደግሞም በሮፓና በአሜሪካን እንዳለው ደምብ እነዚሁ ሁለቱ ምልክቶች ታውቀው በመንግሥት እጅ እንደተቀመጡ ያሀል ማስረዳቱን ሁለተኛም እነዚህን ኑዦልና ፍሊት የሚባሉ ሁለቱን ምልክቶች ለውጦ ወይም አስመስሎ የሠራ ሰው ሁሉ ይከሰሳል ስንል ለሕዝቡ እናስታውቃለን ።

፳፱ቀን ግንቦት ፲፱፻፳፭ ዓመት ስለ ስታንዳር ዋል ኩፓንያ ኦፍ ኒው ጀርሲ ዊልሚንግቶን ደለዌር አገር(ኤታ ኡኒ)ና ለስታንኮ ኢንኮርፖሬትድ ዊልሚንግቶን ደላዌር አገር(ኤታ ኡኒ)በዋኪልነት ።

ፊርማ ፖል ሻኑዋ ጠበቃ አዲስ አበባ ነዋሪ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፲፱ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፭ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፸፰ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፫ ብር
፡ ፡ ባለ ድመ ።		፻፹፭
፡ ፡ ባለአህያ ።		፻፵
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል ።		፻፷
፡ ፡ ባለ አንበሳ	አሜሪካ	፪፻፲
" "	ጃፖን	፻፸፰ ብር
ሱካር	ጅኒያ	፵፫ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፵፩ሳንቲምም
በአንድ ብር	፰ ሊራ ከ ፺፩ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፹ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየዓይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፡ የልብ ፡ የደረት ፡ የጉበት ፡ የኩላሊት ፡ የድማት የጨብጥ የቂጥኝና [illegible] [illegible] በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጌርጌሮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው





አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቶላችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ ።

የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS.

ማስታወቂያ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ፤ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በየዓይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

የላዕቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።
ሕራንት ባግዳሣሪያን ።

ከንግሥ ቤት ከርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ሙንገድ ላይ ።

በላዕቲክ (ላስቲክ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋው ግን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ ተረፈተን ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።
አ በ ከ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ጴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድ ራ ሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሥላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበበ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው።

ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ (ዘይት) መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና ያለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S.E.&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያቤትነው።

ጉድይር ግዙ

GOOD YEAR

2-28-14

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
5me ANNÉE № 36

ሐሙስ ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 5 SEPTEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen; profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፫ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ነሐሴ ፳፱ቀን የአየሩ ባቡር ከድሬዳዋ ሳይነሣ አስቀድሞ ከግርማዊንጉሥ ተፈሪ ወደ ድሬ ደዋ ማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር ወደ አቶ አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል ቃል አልፎ ነበር። ቃሉም ይህ ነው።

ንጉሥ ተፈሪ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ
ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ።
ይድረስ ከቶ አስታጥቄ ድሬ ዳዋ ።
ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል በጥንቃቄ ፈጽም ።

በ፴ ነሐሴ ባ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ከድሬ ዳዋ የኢትዮጵያን መንግሥት ፖስታ ይዞ ፤ ከጀርመን አገር ከዴሞክር ፋብሪካ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ያስመጡት አይሮፕላን በሐረርና በጨርጨር አልፎ አዲስ አበባ ባ፬ ሰዓት ይገባል። ያለፈበትን ቦታ ለማስታወቅ ይህ ደብዳቤ ሲወድቅላቸው የደረሰበትን ሰዓትና ደቂቃ እየጻፉ በፖስታ ወዲዲስ አበባ እንዲላኩ የሰዓቱ ልክ ተገልብጦ ለመታሰቢያ እንደገና ፖስታውን ላገኙት ሰዎች ይላክላቸዋል ።

የሚል ቃል በወፍራም ክርታ ላይ አሳትመህ መቶ ቁጥር ያህል ይያዝና አልፎ አልፎ እየጣለ ይምጣ ።

ሁለተኛ ጊዜ የአየር ባቡር ወደ አዲስ አበባ መግባት።

ነሐሴ ፳፱ ቀን የአየር ባቡር ወደ አዲስአበባ እንደሚገባ ታውቆ ነበርና ለመቀበያው የሚሆን ነገር ሁሉ በጃን ሜዳ ሲሰናዳ ዋለ ። ነሐሴ፴ቀን ከጥዋት ጀምሮ የከተማው ሰው ሁሉ አዲስ አበባ የሚገባውን የአየር ባቡር አገባቡን ለማየት ወደ ጃን ሜዳ አስቀድሞ ስፍራ እንዲይዝ ሲሽቀዳደም አረፈደ ። ሰባት ሰዓት ሲሆን ሜዳው እስቲጠበው ድረስ ልክ የሌለው ሰው ተሰበሰበ።ግርማዊ ንጉሥም ባማረ አጀብ ታጅበው ለአየር ባቡር መቀበያ ወደ ተሰናዳው ቦታ መጡና አምሮ በተሰናዳላቸው ስፍራ ተቀመጡ ። የከተማውም ዘበኛ ሰልፉን አሳምሮ ቁሞ ነበርና ግርማዊንጉሥ ሲመጡ እንደሚገባ ሰላምታውን ሰጠ። የኢትዮጵያና የውጭ አገርም ሚኒስትሮችና መኳንንቶች በግራና በቀኝ ተቀመጡ ። ፎቶግራፍ አንሺዎችም ሥዕል ለማንሣት ይሽቀዳደሙ ነበር ። ከከተማውም ሰውን የሚያመላልሱ አቶሞቢሎች መንገዱ እስቲጠባቸው ድረስ እጅግ ብዙ ነበሩ ። በዚህ ጊዜ ሰው ሁሉ የአየር ባቡርን መምጣት ቁሞ ሲጠባበቅ ብርቱ የሆነ ዝናብ ዘነበ ። ዝናቡም ካባራ በኋላ የአየር ባቡር በኤረር ተራራ ካረፈ ደመና ከፍብሎ ሲበር ታየና ሰው ሁሉ የደስታ ጭብጨባ አጨበጨበለት። አዲስ አበባም በገባ ጊዜ ከተማውን ሁሉ ዞሮ ጐብኝቶ ጃን ሜዳ ከተሰናዳለት ቦታ ላይ ሲአርፍ ፮ ሰዓት ካሥር ደቂቃ ነበር።ግርማዊ ንጉሥም ወደ አሉበት ቀርቦ ሰላምታ ለመስጠት በሰፊው ሜዳ ላይ እየተሽከረከረ ሲመጣ ላዩታው እጅግ ያስደንቅ ነበር ።

ግርማዊ ንጉሥም ከተቀመጡበት ተነሥተው የአየር ባቡሩ ወደ አለበት በቀረቡ ጊዜ ሰዎቹ ሙሴ ባሮኢንጌልን ተሸክመው አቀረቡትና ግርማዊ ንጉሥ እንኳን ደስ አለህ ብለው ሰላምታ ሰጡት።የአየር ባቡሩንም ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ሁነው ዞረው አዩት።ባየሩ ባቡሩ ውሥጥም የመጡ ሁለት መኪናውን የሚያስኬዱ ሰዎችና የድሬ ዳዋ ሐኪም ደክቶር ብሩምስ እና ጋጋሪውም አቶ አስፋው አንዳርጌ ናቸው ። ባየር ባቡሩም በጅንያ ሁኖ ብዙ ጳስጣ መጣ ። ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ከሚንስትሮችና ከመኳንንቱ ጋራ የሻምፓኝ ግብዣ ወደ ተሰናዳበት ወደ እሽቅድድም ማኅበር ቤት ገቡና በሻምፓኝ ጊዜ የጀርመን መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሙሴ ፕሩፈር የሚከተለውን ተናገሩ።

ግርማዊ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ለኢትዮጵያ ካስመጧቸው አውሮፕላኖች ሁለተኛው አሁን በመሬት ላይ ሲያርፍ ተመልክተን ጀግና የሆነው ነጂውና መኪና ሠራተኛው ጀርመኖች ስለሆኑ መጀመሪያ ግርማዊነትዎን እንኳን ደስ ያለው እላለሁ ። ደግሞ ከዚህ ቀጥዬ ይህ መኪና ስለ ኢትዮጵያ ሰላምና ሥልጣኔ የሚጠቅም ዋና መሣሪያ እንዲሆን የምመኘውን ምኞት እገልጽ ዘንድ ፈቃድ ላገኝ ።

Allocution prononcée par Monsieur de Prufer Ministre d'Allemand en Ethiopie à l'occasion de l'arrivée à d'Addis-Abeba du second Avion.

Discours de Monsieur Prufer.

Sire,

Nous venons d'assister à l'atterrisage du second des aéroplanes que votre Majesté a acquis pour l'Ethiopie. Son vaillant piiote et son mécanicien sont des Allemands. Et c'est pour celà que je tiens à féliciter votre Majesté le premier. Qu'il me soit permis d'ajouter à mes félicitations un vœux: que cet appareil soit un instrument puissant dans l'intérêt de la paix, dans l'intérrêt du progrès de l'Ethiopie !

ቀጥሎም ግርማዊ ንጉሥ የሚከተለውን ተናገሩ ።

ስመ ጥሩ ከሆነው ከጀንከርስ ቤት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ የመረጥነው አውሮፕላን ያለ ሥጋት በደህና ደርሶ በመቀበላችን እጅግ ደስ ብሎናል በብዙ ወገን አገልግሎቱን እንዲፈጽም የተመኘነው ተስፋችን ረጅም ነው ።

ይልቁንም በመጀመሪያ ጊዜ በዚሁ አውሮፕላን ጾስጣ ስለ መጣ የመጀመሪያውን እንዱን አገልግሎቱን መግለጹን ያስረዳል ። በብልሐትና በእውቀት የተመሰገነውን የአየር ባቡር ነጂ ባሮ ኤንጌል መኪና ሠራተኛውን ሙሴ ስሚትስን እናመሰግናለን ።

ከዚሁም ጋራ በዚህ ሥራ የረዱንን ማዦር እስቴፋንን እንዘነጋም ። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በድሬ ዳዋ የሕዝባችንን ጤና ሲጠብቅ የኖረ ዶክተር ብሩንስ አብሮ ስለ መምጣቱ ደስታችን ሁንዋል ብለው በጨረሱ ጊዜ ተጨበጨበ ።

Discours de S. M. le roi Tafari Makonnen.

Nous sommes très heureux de recevoir l'aéroplane que nous avons choisi à la fabrique Junkers de reputation mondiale. Nous sommes tous particulièrement heureux qu' il est arrivé sans difficulté.

Nous avons l'intime espoire qu'il nous servira utilement. Il a déja commencé son premier service en transportant par la voie aérienne des sacs postaux

Nous Exprimons notre haute satisfaction au vaillant pilote Baron Engel et au très habile mécanicien Monsieur Sehmit.

Nous n'oublions pas dans nos remerciments Mr Major Steffen qui nons a rendu d' un signalé service en cette occurence.

Nous sommes aussi heureux de voir descendre de l'aéroplane le Dr Brunus doit la seule préocupation a toujours été de veiller à la santé de notre population de Diré- Daoua.

ከዚህ በኋላ ለሙሴ ባሮኤንጌል የኢትዮጵያን የክብር ኮከብ ኒሻን በአንገቱ አሠሩለት ። ቀጥሎም ለሙሴ ሲምትስ በላምበሉን የኢትጵዮያ የክብር ኮከብ ኒሻን በደረቱ አደረጉለት። ቀጥሎም ለድሬ ዳዋ ሐኪም ለዶክቶር ብሩንስ የኢትዮጵያን የክብር ኮከብ ኒሻን ሸለሙት ። አቶ አስፋው እንዳርጌም እንዲሁ የክብር ኒሻን ተሸለመ ።

ባየር ባቡርም የመጣው ጾስጣ ጃን ሜዳ ላየሩ ባቡር ማረፊያ በተሰናዳው ቦታ ላይ መታደሉን የጾስጣ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስትር ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አፈ ወርቅ አስታወቀው ነበርና ብዙ ሰው እየመጣ ጾስጣውን ከዚያ ወሰደ። በዚያም ጊዜ ሙሴ ፓፓዚያን የሠሩት ለመታሰቢያ የሚሆን በኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ተጊጦ በመካከሉ የአየር ባቡር ሥዕል ያለበት ደብዳቤና ቴምብርም የተሣለበት በግርማዊ ንጉሥ ፊት ቀረበና ግርማዊ ንጉሥ ፈረሙበት ። በዚያውም የነበሩ የኢትዮጵያና የውጭ አገርም ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ፈረሙበት ።

የአየር ባቡር እየደጋገመ ወደ አዲስ አበባ በመግባቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም ደስ ብሎታል ። የአየር ባቡር ሲበር ያየ ሁሉ ማጨብጨቡና በደስታ መዝለሉ የሚያስገርም ነው። ይህ የአየር ባቡር በገባ ጊዜ ከጭብጨባውና ከደስታው ከውካታውም ብዛት የተነጋ ተናግሮ ለመሰማማት የተናገሩትንም ለመደማማጥ በጣም ይቸግር ነበር ። ግሩም ነው፤ እንዲህ ያለ ፈገጠዝያና ደስታም የለም ።

ሕዝቡ ሁሉ አምላክ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዕድሜ ይስጥልን እንጂ ኢትዮጵያ እንደ አረማመድዎ ፍጥነት ተስፋ የምናደርገውን የሥልጣኔ መዓርግ አግኝታ እናያለን ብሎ መርቋል ።

የኢትዮጵያ ልጆች የአየር ባቡርን መንዳት እንደሚገባ ተምረው ብዙ የአየር ባቡር የኢትዮጵያ ልጆች እየነዱዋቸው ሥራቸውን ሲፈጽሙ በማየት ሕዝቡ የበለጠ ደስ ይለዋል ። ግርማዊ ንጉሥም ይህ ዋና ኃሳባቸው ነውና በቶሎ እንዲደረግ እርግጥ ነው።ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታታችንና ግርማዊ ንጉሣችንን አምላክ ይጠብቅልን ። ከዚህ ቀጥሎም ሊቃውንት የተቀኙትን ቅኔ እናበረክታለን ።

ሥላሴ ።

ግሩም ኃይለ ሥላሴ ።
ኅብረ ገጻቲሆሙ ለለርእሱ ።
ለፀወርተ መንበር ዘለከ እሙንቱ ብዙኅ ጥበባተ አህጉር።
ወእምኔሆሙ አሐዱ ዘንበር ።
አየርነሰ አዳም ቀዲሙ ፡ ዘባሕቲትከ ንቡር ።

ሶበ ሰማያተ ንኤጽር ።
ይእዜ ምስሌከ እንዘ ትትናገር ።
ርኢናሃ ለሔዋን ባበ᎐ር ።

መወድስ

አልበ ንጉሥ እምቅድመ ተፈሪ።
እምድኅሬሁ ዳግመ በኢትዮጵያ ሐዳስ ።
እስመ ግዕዘ ሰማይ አእመረ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ።
ቅድመ ለሥጋ ወድኅረ ለነፍስ ።
ወህላዌ መልአከ ይትኃሠሥ ።
ሰማየ ሰማያት ዐርገ በሰረገላ መንፈስ ቅዱስ ።
ለሰማይሂ ተከፈልዎ እንበለ ሠራዊት አልባስ ።
ኤልያስ በሠረገላ ወንጉሠ ዕርዕ በፈረስ ።
ወኃይለ ሥላሴ መነነ ኃይለ ኤልያስ ።
አምጣነ በእልፋ ይትመየጥ ወበእልፍ ይገይሥ ።
ወልደ ኪዳን ዘሐረር መድኃኔ ዓለም ።

አሠረ ንጉሥ

ሕያወ ባሕርይ ንስርከ ኃይለ ሥላሴ።
እንተ በሳሌም ተወልደ ።
ዘበታሕቱ ሀለወት ኢትዮጵያ አርዓደ ።
አመ ምስለ ነፋስ ተጋየደ ።
ዘበላዕሉ ጠፈረ እስመ አንጐድጐደ ።
ወበእግሩ ደመናተ ኬደ ።

አለቃ ወልደ ኢየሱስ።

ስለ መጀመሪያው የአየር ባቡር ግርማዊ ንጉሥ ለላኩት ቴሌግራም የተላከ ምላሽ።

ከፓሪስ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ አዲስ አበባ
የገባበት ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓም
ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን አዲስ አበባ።

በፈረንሣዊ ፋብሪካ የተሠራና በአንድ ፈረንሣዊ የተመራ አንድ አኤሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ስለ መግባቱ በመልካም ፈቃድዎ ለላኩልኝ የወዳጅነት ቴሌግራም ለግርማዊነትዎ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። በኢትዮጵያ መንግሥት ዋና ከተማና በፈረንሣዊ መሬት መካከል መጀመሪያ ጊዜ የተደረገው ይህ የአየር መገናኛ ለልማትና ለጸጥታ ተግተው አሳቢዎች የሆኑትን የሁለቱ አገሮቻችንን አስተሳሳሪ ወዳጅነት ከጥንት የቆየ መሆኑንና የመተማመን ወዳጅነት መሆኑን ይመሰክራል ።

ጋስቶን ዱሜርክ

ከፓሪስ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓም አዲስ
አበባ የገባበት ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ
ንጉሥ ተፈሪ አዲስ አበባ

ግርማዊነትዎ ለላከልን ተወዳጅ ቴሌግራም ምሥጋናችንን እናቀርባለን ። መጀመሪያ ለኢትዮጵያ የአየር መንገድ መልካም ምኞታችንን ስናቀርብ የግርማዊነትዎ አክባሪና ታማኝ አገልጋዮች መሆናችንን እናረጋግጣለን ።

ፖቴዝ።

ስለ ክቡር ራስ ሀብተ ማርያም ዕረፍት

ክቡር ራስ ሀብተ ማርያም የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የናት ወንድም ናቸው ። ጃንሆይ አፄ ምኒልክ ታመው በቤት ከዋሉ ጀምሮ ለንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እንደ አባት ሁነው ስላገለገሉ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሲነግሡ ደጃዝማች ተብለው የገንዘብ ምኒስትርነት ተሾሙ ። ቀጥሎም የየጁ አገረ ገዥነት ተሾሙ ። ኋላም በ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ራስ ተብለው ወለጋ የራስ ደምሰው የነበረውን አገር ተሹመው ሲኖሩ በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ነሐሴ ፳፪ ቀን በዚያው በተሾሙበት አገር ዐርፈው ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዘመዶቻቸውም ሁሉ ነሐሴ ፳፭ ቀን ተረድተው በአዲስ አበባ ትልቅ ልቅሶ ተደረገላቸው። ብርሃንናሰላም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ለዘመዶቻቸውና ላሽከሮቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ ይላል።

በሲዳሞ ሀገር ስለ ነጋዴ ተስፋ ።

በክቡር ደጃዝማች ብሩ ግዛት ሲዳሞ አውራጃ በንግድ ውሥጥ ያለን ሰዎች አዳራችን ንግድ ሁኖ በዚሁም ብዙኅ ትርፍና ብዙኅ ስለሰፉልን ከዛሬ ቀደምም ብዙ የወለጋ ፈረንጆችና ነጋዴዎች ያለ ሐሳብና ያለ ችግር መኖራቸውን አውቀው ሙሴ ሚካኤልዲስ ያሳተሙትን ብርሃንና ሰላም አይተን እጅግ ደስ ብላለን እኛም የሲዳሞ አውራጃ ነጋዴዎች የቀደመውን ያለመሠልጠን ጨለማችንን የዛሬውን ብርሃናችንን የንግድ ማስፋፋትና ማሻሻል ለክቡራን ብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እናስታውቃለን ። መጀመሪያ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ሲዳሞ ሀገር እንደገቡ የቀድሞውን ቀረጥ ባንድ ጭነት ቆዳ ሦስት ብር ባንድ ጭነት አረቄ ሦስት ብር ባንድ ጭነት ፍየል ቄለጭ አምስት ብር እየከፈልን እንደ ተጐዳን ባዩን ጊዜ ቀረጡን በልክ ይሁንላችሁ አሉን። አገሩም ዳር አገር ሆኖ ሸቀጡም ቡናውም ስለአልተነሣልን እንደልብ አይተው ቀድመው ቀረጡን አሳነሡልን ። ወደንግድ ሀገርም ስንመላለስ አገሩም ቀላድ ሆኖ መሣፈሪያ ቦታ አጥተን ተቸግረን ነበር። አሁን በየመናኸሪያው መሣፈሪያ ሠርጊ ቦታ ሰጡን ። በመሣፈሪያችንም

ላይ ሌባ ከብቶቻችንን ቢወስድብን ከጠፋበት ቦታ አገር ይክፈላችሁ ብለው ደንብ አደረጉልን ።

በየገበያውና በየኬላውም ዘበኛ አቁመውልን እንደልባችን እንሔዳለን።በጣምም የሚብስብን እቃችን እየተቋረጠ የሚቀርበት ከሴ የሚባል በረኅ ነበር በዚህ መጕዳታችንን አይተው ለመንግሥት አስፈቅደው ፤ ከክቡር ደጃዝማች መሸሻ ጋር ተገናኝተው በሲዳሞ፣ በከምባታ፣ በአሩሲ ያለውን ባላባት አስጠርተው አገርና አገር እንዲስማማ እንዳይጣላ አማማሉዋቸው። ከመሐላም ወዲያ ጠብ ቢኖር ለመንግሥት የሚገባ መቀጫ ለሻለቃም የሚገባ መቀጫ ቆረጡልን። የተቀማውንም ገንዘብ እንዲከፈል ሰውም ሙቶ ባለደሙ የጠፋ እንደሆነ ባላባቱ እርስቱን ሲነቀል ደንብ አደረጉልን። ይህን ስላደረጉልን ያለሐሳብና ያለችግር መንገዳችንን እንሔዳለን ። አንድም ስለዚህ ደስታችን ለሽርሽርና ላደን ከሚሪካን ሀገር የመጡ ፈረንጆች ከወላሞ ወደ በረና ሀገር ሲሔዱ በክቡር ደጃዝማች ብሩ አገር ግዛት ሲዳሞ አውራጃን ብናይ መንገዱና ድልድዩ እንደአማረና እንደ ተሰናዳ፤ነጋዴውም እንደልቡ እየተመላለሰ፤የውጭ አገር ሰውም ቢመጣ አክብረው በማዕርግ ስላተቀበሉ በሌላው አገር ብናይ እንደዚህ ያለ ማዕርግ አላየንምና ስለዚህ ያለሐሳብ መኖራችሁን አይተን እኛም በጣሙ በልባችን ብዙኅ ተስፋ ለመኖርና ንግድ ለማስፋት አሰብን ብለው ፈጽመው የልባቸውን ሐሳብ አጫወቱን። እኛም እንዲህ ያለውን የሻለቃ ገዢ በንግሥተ ነገሥታት ግርማዊት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ስለአገኘን እነሱንም አሰንብቶልን የሲዳሞንም ልማቱን እንዲያሳየን ስንል እግዚአብሔርን ፈጣሪያችንን እንለምነዋለን። አሜን ።

የሲዳሞ አውራጃ ነጋዴዎች።

የውጭ አገር ወሬ ።

በምድረ ከነአን በአይሁድና በእስላም መካከል ብርቱ ሁከት ተነሣ። በሶርያ አገርም እንደዚሁ መናወጽ ሆነ ።አሁን በመጨረሻ ከኢጣልያን ሌጋሲዮን በሚመጣ የዕለት ወሬ በእምባጓሮው ውሥጥ ከአይሁድ መቶ ዘጠኝ ሙተዋል። ከእስላሞችም ሰማንያ ሦስት ሞቱ። አራት ክርስቲያኖችም ሙተዋል። ከሁለቱም ወገን የቈሰሉት ሦስት መቶ ሀያ ያህላሉ ይላል ። ጠቡም አሁን ወደ መብረድ ብሏል ።

ግራፍ ዜፔሊን ።

ከዚህ ቀደም በብርሃንና ሰላም ፴፬ ቍጥር እንዳመለከትነው ግራፍ ዜፔሊን የተባለ የጀርመን የአየር ባቡር ዓለምን ለመዞር ከበርሊን ተነሥቶ፣በጃፓን አገር አድርጎ ትልቁ ውቅያኖስን አቋርጦ፣በአሜሪካ በኒዩ ዮርክ ግሩም የሆነ አቀባበል ተደርጎለት፣ ከዚያ ተነሥቶ የአትላንቲክ ውቅያኖስን አቋርጦ እየበረረ ወደ ኤውሮጳ ገብቶ፣ በነሐሴ ፴ ቀን ወደ ጀርመን ዋና ከተማ ወደ በርሊን ገባ። ግራፍ ዜፔሊን ስለ ገባ በጀርመን አገር ልክ የሌለው የደስታ ፈንጠዝያ ተደረገ።በበርሊን ከተማ ሁነው ግራፍ ዜፔሊንን ለመቀበል የተሰበሰቡ ሰዎች መቶ ሺ ያህላሉ ። የአቀባበሉም ነገር የሚያስደንቅ እንደሆነ ከኢጣልያን ሌጋሲዮን በመጣ ሬዲዮ አገኘን ።

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ።

የትምህርት ዓመት ፲፱፻፳፪ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በመስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ይከፈታል።

በዚሁ ትምህርት ቤት እያደሩ የሚማሩ ተማሪዎችና ከቤታቸው እየተመላለሱ ምሳቸውን በተማሪ ቤቱ እየተመገቡ የሚማሩ ተማሪዎች፣ ደግሞ በቤታቸው እየተመገቡ ተመላልሰው የሚማሩ ተማሪዎችን ይቀበላል።

በዚሁ ተማሪ ቤት ልጆች የሚያደርጉበት የተጠነቀቀ ስነ ሥርዓትና የፀና ዋና ትምህርት፣ ደግሞ ለሰውነት ጤናና ጥንከሬ የሚበጅ የጉልበት ሥራና ጨዋታ ትምህርት ይገኛል። እጅግ ያማረና የተመቸ ትምህርት ቤት ነው ።

በዚሁ ትምህርት ቤት ለመማር ወደትምህርት ቤቱ የተላከው የልመና መልእክት እንዲመረመር ለትምህርት ቤቱ ዋና ሹም ወደ ክቡር አዛዥ ወርቅነህ ያልፋል ።

Lycée Tafari Makonnen .

Année scolaire 1929-1930.

La rentrée des classes du Lycée Tafari Makonnen aura lieu le 12 septembre prochain (2 Maskaram)

L'établissement accepte des internes, des demi-pensionnaires et des externes. Education soignée, études, sérieuses, sports. Très belle installation modernes

Les demandes d'inscription déposées au Lycée seront transmises pour examen à Mr l'administrateur Azaj Workneh.

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።
አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እቬቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒካላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ፥ የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ከሙሴ ጉርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።



በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፉ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕሩንት ባግዳሣሪያን ።

ከግሪክ ቤት ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋው ግን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቀባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቴም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።



COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች ብብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው ኦቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቸርቷል ቀብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ ኦቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድሬስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጋት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ለስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንዳር ኩምፓኒያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፌርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።
አበካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ፀአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን።

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባቶሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድዮር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድዮር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉድዮር ግዙ

GOODYEAR

2-ZB-14

በዳግማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቍጥር ፴፯
5me ANNÉE № 37

ሐሙስ መስከረም ፪ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 12 SEPTEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዣ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ርእሰ ዓውደ ዓመት ።

የኢትዮጵያውያንና የግብጻውያን፡ የግሪካውያንም፡ የዓመት መጀመሪያችን መስከረም ፩ ቀን ነው ። የዚህም ክብረ በዓል ስሙ በኢትዮጵያ ርእሰ ዓውደ ዓመት ይባላል ። ርእሰ ዓውደ ዓመት መባሉ በዓመቱ ውሥጥ ያሉት በዓላት ዓውደ ዓመት ይባላሉና መጀመሪያቸውና ማስገኛቸው ስለሆነ ነው። ዓውድ ማለትም አደባባይ (ሸንጎ) ማለት ነው ። ንጉሥ አንድ ጊዜ ወደ አደባባይ ብቅ ባለ ጊዜ ለመኳንንቱና ለሠራዊቱ፥ ለሕዝቡም ሁሉ በግልጽ እንዲታይ ፤ በዚሁም ቀን በዓመቱ ውሥጥ ያሉት በዓላት የሚውሉበትና አጽዋማት የሚጀምሩበት ቀን ይገለጻል ። ይህ ርእሰ ዓውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስም ይባላል ። ቅዱስ ዮሐንስ የተባለበት ምክንያት የመጥምቁ ዮሐንስ ዕረፍት በዚሁ ወር በ፪ ቀን ነው ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሊቃውንት የሐዲስ ሕግ መጀመርያና መንገድ ጠራጊ (ሰባኪ) እንደ ሆነ ፤ የሐዲስ ኪዳንም መጻሕፍት ታሪካቸውን የሚጀምሩት በርሱ ታሪክ ነውና፥ ለዓመቱም መጀመርያ ይሁን ብለው፥ የቅዱስ ዮሐንስ በዓል በመስከረም ፩ ቀን እንዲሆን ሥርዓት አደረጉ። በዚሁም ቀን የኢትዮጵያ ሊቃውንትና ካህናት በየቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ ተሰብስበው በዓመቱ ውሥጥ ያሉት በዓላት የሚውሉበትንና አጽዋማት የሚጀመሩበትን ቀን ለሕዝብ ያስረዳሉ ። ሕዝቡም ሁሉ ከያይነቱ አበባ አንዱ ካንዱ እየተቀባበለ ዕንቍጣጣሽ እየተባባለ የደስታና የምስራች ምልክት ያደርጋል ።

አሁንም ከምና ፲፱፻፳፩ ዛሬ ወደ ጀመርነው ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ላደረሰን አምላክ ምልቅ ምስጋናችንን እያቀረብን፥ ወደፊታችን ላለው ለሁለተኛው ዓመት እንዲያደርሰን ተስፋችን ሁኖ ፤ ዘወትር ባለማቋረጥ ልመናችንን ወደርሱ እናቅርብ። ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔርን ለማመስገን ተፈጥረዋል። እንስሳትና አራዊት ፥ አዕዋፍና አንስርት፥ ተሐዋስያንም ሁሉ፥ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ፥ በመጻሕፍት ተጽፎ እናገኛለን። ይልቁንም በምሳሌው የተፈጠረ ሰው ጥዋት ከጨለማ ወደ ብርሃን መውጣቱን ፥ ማታ ከድካም ወደ ዕረፍቱ መድረሱን አስቦ፥ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ሥርዓት ተደርጎለታል። እንዲህም ከሆነ ካንደኛው ወደ ሁለተኛው ዓመት ስንደርስ፥ በዓመቱ ውሥጥ ያሉትን ድካሞችንና ጨለማዎችን አልፈን ወደ ሐዲሱ ዓመት በተሻገርን ጊዜ፥ እጅግ የላቀ ምስጋናችንን ለልዑል እግዚአብሔር ልናቀርብ ይገባናል ።

በዚህ አሁን ባለፈው ዓመት ውሥጥ እኛ የምናውቃቸውና የማናውቃቸው ብዙዎች ወድሞቻችን ወደ ዘለዓለማዊ ዕረፍታቸው የሔዱ ብዙ ናቸው ። እኛ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት እስካሁን ድረስ ስለ ቄዬን አይተነው የማናውቀውን፥ በበር ሰው ተሸክሞ በአየር ላይ ሲበር ለማየት በቃን ።

ወደ ፊትም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱንና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ከቈየልን፥ እኛንም ከሰነበተን ፤ ብዙ መልካም ነገር እንድናይና አገራችን ኢትዮጵያም ወደ ትልቁ መዐርግ እንድትደርስ እየተመኘን፥ እግዚአብሔርን እንለምነው ። ብርሃንና ሰላም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ፥ ለኢትዮጵያ መኳንንትና ሊቃውንት፥ ለሠራዊትና ለሕዝቡም ሁሉ፥ እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ አሸጋገራችሁ ፤ ደግሞም ለሚመጣው ዘመን በደህና በሰላም ያድርሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ያቀርባል ።

ማስታወቂያ ።

በግርማዊ ንጉሥ ማተሚያ ቤትና መጻሕፍት ቤት አምሮ የተሠራ በልዩ ልዩ ዓይነት ጌጥና ቀለም ጥሩ ሁኖ የታተመ የነገሥታቱ መታሰቢያ የተጻፈበት ። በገበታው ላይ የዓመታት

ክፍሎች፣የበዓላትና የአጽዋማት ማውጫ ያለበት የኢትዮጵያና የአውሮጳ ጉልቄ ዕለታት(የቀን መቍጠሪ)በርካሽ ዋጋ በ፩ድ አላድ ይሸጣል ። የቀኑን ቍጥር ብቻ አይደለም ለቤታችሁም ጌጥ ነውና መጥታችሁ ግዙ ።

የአየር ባቡር በጃን ሜዳ ።

ጳጉሜ ፪ቀን ከጀርመን አገር መጥቶ በነሐሴ ፴ቀን አዲስ አበባ የገባውን የአየር ባቡር ለማየት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንና ልዑል ራስ ካሣ ወደ ጃን ሜዳ ሔዱ።ብዙ መኳንንትና ብዙ ሠራዊትም አብሮ ዋቸው ሔዱ ። ግርማዊ ንጉሥና ልዑል ራስ ካሳ የመኪናውን አኳኋን ካዩ በኋላ በአየር ባቡሩ ውሥጥ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ፣ክብር ፊታውራሪ ዓምዴ፣ክቡር ቀኛዝማች ተፈራ በለው፣ ክቡር ባላምባራስ ተክለ ማርቆስና ክቡር አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ገቡና የአየር ባቡሩ ነጂ መኪናውን አሥነስቶ ለመብረር እንዲነሣ በሜዳው ላይ አሽከረከረው። የአየር ባቡሩም ግሩም በሆነ አስተያየት ወደ አየር ወጣና በአዲስ አበባ ዙሪ እየዞረ ከፍና ዝቅ እያለ ለከተማው ሰው ሁሉ ታየ።

ቀኑም የገባያ ቀን ስለነበረ በከተማው ውሥጥ ብዙ ሰው ተሰብስቦ ነበርና የአየሩ ባቡር በከተማው ውሥጥ በጃንሜዳ ስላፈረ ሰውም ሁሉ ያለ ችግር እስኪበቃው ድረስ ማየት ስለቻለ ደስ ብሎታል።

ከዚህ ቀደም በጃን ሜዳ ብዙ ፈረሶች የፍጥነታቸውና የአግራቸው አነሣስ ተደንቆላቸው ነበር።ግን ዛሬ የአየር ባቡር ትልቁ አሞራ እየተሽከረከረና ሰማይ ለሰማይ እየበረረ ፍጥነቱን አሳየበት ።

ከዚህ በታችም ብላታ መኰሪያ ስለ ቅዱስ ዮሐንስና ስለ ንስረ ተፈሪ አስተባብረው የተቀኙትን ቅኔ እንጽፋለን ።

ሥላሴ ።

ዮሐንስ በምትረቱ፣ወበጥበቡ ኃይለ ሥላሴ ።
ኅበ መርዓተ ንስር ክንፍ አሐቲ፣እመ ሐዊረ አፍጠኑ ።
ክንፈ ንስር ዘማ ትከውን ለመኑ ።
እስመ በምትረቱ ዮሐንስ ወኃይለ ሥላሴ በኪኑ ።
ገቢረ መንክራት አመ ወጠኑ ።
በልብሰ ራጉኤል ክንፍ ወበስኑ ።
ሰማያተ ኅቡረ ከደኑ ።

ዕንቈጣጣሽ ።

ትንቢት ይቀድሞ ለነገር ትንቢት ነገርን ይቀድማዋል ይባላል።

ለዚህም ማስረጃ ገንዘብ ሳለ በሰማይ መንገድ አለ እየተባለ (ሲነበብ) ሲነገር ይኖርነበር። ዛሬ ግን በጆሮአችን ስንሰማ የኖረውን በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ትጋትና ብርታት ከነፋስ የሚቀድመውን ንስረ ተፈሪን በዓይናችን አይተናልና የሰማይ አባታችንን እናመሰግነዋለን ። ይህም ቀን የግርማዊ ንጉሥ መታሰቢያ ኢትዮጵያ ከታችኛው የሥልጣኔ ደረጃ ወደ ከፍተኛው ማዕርግ የወጣችበት ቀን መሆኑን ይገልጻል ። ይኸውም የመልካም አረማመድ ጐዳናው ወደፊት በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ኃይልና ሀብት እየሰፋ መሔዱ አይጠረጠርም። በዚህም በሰፊው ጐዳና እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ያለ ምርኩዝ ሳንሰነካከል ለመሔድ እንችላለን ። ንስረ ተፈሪም ሐዲስ የተማሬን ይመስላል ወንጌል ኢትበሉ ለጌሠም ያለውን ቃል ይዞ ላጡት የሚበቃውን ጐዳና በ፫ ሰዓት ወይም በአንድ ቀን ጨርሷልና ። ደግሞም ርግበ ኖህን ይመስላል። ርግበ ኖኅ ሐፀ ማየ አይኅ፣ ነትገ ማየ አይኅ እያለች ባፍዋ የወይራ ጫፍ የለመለመ ቅጠል ይዛ እንደተገኘች ቃለ አዋዲ ንስረ ተፈሪም እንደዚሁ የለምለሟን የኢትዮጵያ ባንዲራን ባፉ ይዞ፣ እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገራችሁ እያለ ለመላ ኢትዮጵያ አዲስ አበባን ያሳይ ነበረ።ከዚህም ቀጥሎ አከለከሙ መዋዕል ዘሐለፈ ያለፈው ዘመን ይበቃችኋል ዛሬ በተፈሪ ጊዜ ድንቁርና ተናቀ።ስንፍና ወደቀ፣እውቀት ጐለመሰ፣ጥበብም ታደሰ፣ መንገዱን ጽረጉ፣ አመኑ፣ንስሐ ግቡ፣ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና እያለ እየዞረ በሚያስፈራ ድምጡ ሲሰብክ በተሰማ ጊዜ ምድርም ፈርታ ዝም አለች።ባሕርም አይታ ሸሸች። ዮርዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ።መላ ኢትዮጵያም አደነቀ። ኋላም እንዲህ አለ፣ ከሁሉ ጥበብ ትበልጣለች፣ጥበብንም ግዛ፣ በክብትህም ሁሉ ማስተዋልን አትርፍ፣ከፍ ከፍ አድርጋት።እርሷም እንደኔ ከፍ ከፍ ታደርግሃለችና ብሎ ተናገረ።የዚህንም የአየር ባቡር ነገር ባይን ካልታየ በቃል ይናገሩት ዘንድ አይቻልም ። መክብብ ዓይን ከማየት አትጸግብም።ጆሮም ከመስማት አትሞላም፣ያ የሆነው ነገር ሁሉ እርሱ ተመልሶ ይሆናል፣ ማንም ይህንን ነገር አዲስ ነገር ነው ይል ዘንድ አይችልም።ሁሉም ከኛ በፊት በነበረው ዘመን ተደርጓልና ብሎ የተናገረውን ቃል በተሰጠኝ እውቀትና በዩሁብት በዓይኔ ልቡናዬ የመክቢብን ቃል ለውጬ እናገራለሁ። የዚያን ጊዜ ያልተደረገው ዛሬ በተፈሪ ጊዜ ተደርጎ አይቻለሁና። ይኸውም ለግርማዊ ንጉሥ መልካም ዕድል መሆኑን ያስረዳል። ማንም አይዘነጋውም።በኛም ልቡና እንደ ሐውልት ተቀርጾ በየልባችን ለዘላለም ይኖራል ። ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር፣ረጅም ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ይስጥልን ፤ ሀሳባቸውንም የኢትዮጵያ አምላክ ያስፈጽምልን፣ እያልኩ ልዑል እግዚአብሔርን እለምናለሁ ።

እሸቴ ክንፌ።

ማመልከቻ ።

በኢትዮጵያ ለተማሪቤቶች ሁሉ ዋና የተካከለ ደምብ አሻሽሎ አቁሞ የትምህርቱን አካሔድ ፕሮግራሙን ባንድ ዓይነት መንገድ ለማቆም አስቦ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ይህንን ሥራ እንዲያዘጋጁ የዳግማዊ ምኒልክንና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ዲሬክተሮችና መምህራኖቹን ለአማካሪነት መርጦ ለዚሁ ያሠራውን አካሔድ የፕሮግራሙን ሐሳብ እንዲያዘጋጁ አስታወቃቸው ።

በሺ ፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት ባውሮፓ ቁጥር በመስከረም ፫ ቀን ተደርጎ በነበረው በመጀመሪያው የምክር ጉባኤ በተሰበሰቡበት ላይ ክቡር የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ዋና ዲ-

ረክተር የመንግሥቱን አሳብ አማካሪዎቹ የሚያዘጋጁትን በሰፊው አድርገው አስታወቁ ።

ሁለተኛም አማካሪዎቹ የሆኑት መምህራኖቹ ፕሮግራሙንና የትምህርቱን አካሄድ አሳብ አዘጋጅተው መንግሥት እንዲያየው ሊያቀርቡ ተመርጠዋል ።

እነዚህም አማካሪዎች እንደሚከተሉት ናቸው ።

ክቡር አቶ ሣህሌ ፀዳሉ የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲሬክተር ።

ሙሴ ጋርኰኤክስ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ዲሬክተር፤

ሙሴ ዋዲ ዛኪ የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ዲሬክተር፤

ሙሴ ዓብደል ሰይድ የንግሊዝ አስተማሪ ።

ሙሴ ኦር የንግሊዝ አስተማሪ ።

ሙሴ ፖል ፍሮሜዥ የፈረንሳዊ አስተማሪ ሙሴ ብሎች፤ የፈረንሳዊ አስተማሪ ናቸው። እነዚህ አማካሪዎች በሺ ፱፻፳፱ ዓ ም በመስከረም ፮ ቀን ዓርብ ለት ባውሮፓ ቁጥር መጀመሪያ ጊዜ የተሰበሰቡት እንደዚሁ ሥራውን ተከትለው ለመፈጸም በትምህርትና በጥበብ ሚኒስትር ጽፈት ቤት በየሳምንቱ ቅዳሚት ቅዳሚት ለምክር ይሰበሰባሉ ። የተማሪቤቱ ፕሮግራምና የትምህርቱ አካሔድ ተተክክሎ ሲደላደል የትምህርት ሚኒስቴር ለሕዝቡ ገልጾ ያስታውቃል ።

COMMUNIQUÉ.

En vue de doter ses écoles d'un programme général et officiel, le Ministère de l'Instruction Publique et des Beaux-Arts vient de confier le travail d'élaboration de ce programme à une commission composée de M.M. les Directeurs des Lycées Menelik II et Tafari Makonnen ainsi que de M.M. les professeurs de ces deux Lycées.

Une première réunion a été tenue par cette Commission aux Bureaux du Ministère le Mardi 3 Septempre 1929, au cours de laquelle, en un exposé succinct, S.E. le directeur Général du Ministère a développé les idées du Gouvernement concernant la tâche que la commission aurait à entreprendre.

Une Sous-Commission a été choisie pour la préparation du programme et du plan d'études qui seront, par la suite, soumis à la sanction du Gouvernement. Cette Sous-Commission est formée comme suit:

S.E. Ato Sahlé Sèdalou, Directeur Général du Ministère - Président

M.M. Garicoix Directeur du Lycée Tafari Makonnen
W. Zaki - Directeur du Lycée Ménélik II
M. Abdel Sayed - professeur d'anglais
Oar - professeur d'anglais
P. Fromaigeat - professeur de français
Bloch - professeur de français
} Membres

La dite Sous-Commission s'est réunis pour la première fois le Vendredi 6 Septembre 1929, et elle continuera de siéger aux Bureaux du Ministère tous les Samedi à l'effet de poursuivre et de terminer ses travauux.

Une fois le programme et le plan d'études établis et sanctionnés, le Ministère les mettra à la portée du publique.

ክብቶቻችሁን እንዳይገድል በሽታን ግደሉ ።

በከተማው ዙሪያና በቅራቢያውም ሁሉ ተላላፊ ስለሆነ የከብት ሳምባ በሽታ፤በኢትዮጵያ ውስጥ አራት ወር የሚቆይ የዝናም ወራት ስለኖረ በየመስኩ ላይ ብዙ ኩሬ ያደርጋል በዚሁም በኩሬ ውስጥ መልካም ሳር ስለሚበቅል ከብቶች ይበሉታል ይህነንም ሣር ከመብላታቸው የተነሣ በያመቱ አደገኛ የሆነ በጋልኛ ዶዶ የሚባል የጉበት ትል በሽታ እየያዘ ከብቶቻችን እንዲፈጅ መሠረት ሆኖታል ።

ይኸው በሽታ ከሁን ቀደም በገር ውስጥ በመግባቱ ደግሞ ከዚሁ በሽታ የሚያድን የጤንነት መጠባበቂያ መድኃኒት ባለመደረጉ ምክንያት በአዲስ አበባ ዙሪያና በኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ሰፍራ ብዙ ከብት እየሞተ ያልቃል ።

ዶዶ ስለተባለው የጉበት ትል በሽታ የሚያስፈልገውን መከላከያና አኳኋን ወደፊት በብርሃንና ሰላም ታትሞ እናየዋለን አሁን ግን ከዚህ በላይ በጥቂቱ እንደአመለከትኩት በኢትዮጵያ ላለው በሽታ ሁሉ ዋና መሠረት ሆኖ ተላላፊ ስለሆነ ነውና በከተማው ዙሪያና በቅራቢያውም ሁሉ ብዙ አደጋ ወደሚያደርገው ወደ ከብት ሳምባ በሽታ ያለውንና የሚያስፈልገውን ነገር እናገራለሁ ።

ተላላፊ የሆነ የከብት ሳምባ በሽታ

ይህ የከብት ሳምባ በሽታ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ በጣም የታወቀ ነው ። ነገር ግን ባለከብቶቹ ለዚሁ በሽታ መከላከያ ባለማድረጋቸው በሀገሩ ከብቶች ላይ አደገኛ

ሁኑዋል። በያመቱ ይልቁንም በክረምት መጀመሪያና መጨረሻ በያለበት ብዙ ከብት ይጨርሳል ። እኔ በኢትዮጵያ ከመጣሁ ሦስት ዓመቴ ነው ።ይህኑም በሽታ እስከ አሁን ድረስ በከተማውና ቆቃ በሚባለው አገር ብቻ እስከ ዓሥር ጊዜ ያህል አግኝቻለሁ። አሁን ግን በዚሁ በሽታ የተማቀዩና የሚማቀዩ ብዙ አገሮች መኖራቸውን ተረዳሁት ።

ከሦስት ቀን በፊት ፍል ውሀ አጠገብ ባለው የወተት ቤት ውሥጥ በብርቱ ተሥንቶ ላሞቹን ያመማቸውን በሽታ ለመመርመር ተጠርቸ ሒጀ ነበር።ይኸውም በሽታ ልክ በክረምት መጨረሻ እንደገና መነሣቱ መሆኑን አየሁ።የነዚህም ላሞች ባለቤቶች ከዚህ በሽታ የሚያድንላቸው የክትባት መድኃኒት መኖሩን ሳያውቁ ተስፋ ቆርጠው ከብቶቻቸው ሲያልቁ ዝም ብለው ይመለከትዋቸዋል ።

እንዲህ ለከበረች ይልቁንም በከብት በኩል ክብረቷ የሚያስደንቅ በሆነች አገር ለክብረቷ አለማሰብ ብርቱ የሆነ ጥፋት ነው። እስከ ዛሬም ድረስ ከብቶቻችሁን ከዚሁ በሽታ የምታድኑበት ጉዳና ነበራችሁ። ለዚሁም ብታስቡበት ትልቅ ሥራችሁ ነው።

የበሽታው አካሔድ ይህ በሽታ የሚተላለፍበት ዋናው ነገር በመብልና በመጠጥ ነው። ይልቁንም ይኸው በሽታ የያዛቸው ከብቶች ልጋጋቸውን በመሰኩ ላይ ይጥሉታል።በዚህ ምክንያት ይህ በሽታ የሚተላለፍባቸው ከብቶች ከመቶው ሰባ አምስት ይሆናሉ ።

በመጀመሪያም ጊዜ እነዚሁ የታመሙ ከብቶች ገሚስ ሳምባችውን ያደማዋል። ይኸውም ላንዳንድ ሰዎች የማይታይና የማይታወቅ ነው። ወዲያውም በሽተኛው ከብት በየቀኑ እየመነመነ መብላት ይማነዋል።ይኸውም ገና ሲጀመር ነው ። ከዚህ በኋላ በሁለተኛው ጊዜ ሳል ይጀምራል፤ ይልቁንም ሌሊት ይጠነክርበታል።ወዲያውም የማይለቅ ተቅማጥ ይይዘዋል። በሦስተኛ ጊዜ በሽተኛው ከብት ከመብላትና ውሀ ከመጠጣት በመጭረሽ ይተዋል።በዚያን ጊዜ ብርቱ የሆነ መርዘኛ ሕማም ይታመማል፤ ከዚያ በኋላ ይኸው የታመመ ከብት ይሞታል፤ሲሞትም በሁለቱ አፍንጫው የደም አረፋ ይታያል።ሆዱንና ደረቱን ሲቀዱት በሆዱ ውሥጥ ምንም ነገር አይታይም፤ በደረቱ ውሥጥ ግን ከሁለቱ ክፍል ሳምባው አንደኛው ወገን ደም ሁኖ፤ ወይም ገሚሱ ሳምባ ተነፍቶ ይገኛል።የሚያስፈልገው አኳኋን ይኸው በሽታ በገባበት አገር ገና ከብቶቹንም ሳይጀምራቸው ቢሆን ማስከተብ ነው።በሽታው በከብቶቹ መሐልከል ከገባ በኋላ ግን ደኅናውንና በሽተኛውን ለመለየት የሚያስቸግር ነው። ይልቁንም ገና ሲጀምር አይታወቅም።ነገር ግን ለማስከተብ በማይቻልበት አገር ደኅነኞቹን ከብቶች ከበሽተኞቹ በቶሎ መለየትና እነዚህኑ ደኅና የሆኑትን ከብቶች ደኅና ግጦሽ ወዳለበት፤ ይልቁንም ይህ በሽታ ወደ አልገባበት ደረቅ አገር መውሰድ ነው ።

ዳግም ለሚመጣው ሳምንት ስለ በጎች፤ይልቁንም ስለ ጠቦቶች የሳምባና የጉበት ትል በሽታ እናወጣለን።ይኸውም በሽታ ከክረምት በኋላ ተነሥቶ ብዙ አደጋ የሚያደርግ ነው ።

የከብት ሐኪም ሚህራን ክይማኪያን ።

ነሐሴ ፴ ቀን የገባው የአየር ባቡር ነጂ ሙሴ ባሮን ኤንጌል ጃን ሜዳ ሲደርስ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በአየር ላይ ሁኖ የጣለው ደብዳቤ ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

ግርማዊ ሆይ ።

በኢትዮጵያ አየር ውሥጥ በመጀመሪያ ከሚበረው ከዠርመን አኤሮፕላን ላይ ለግርማዊነትዎ ሰላምታ ለመስጠት ስለበቃሁ ለኔ ትልቅ ክብር ነው። በዛሬውም መብረር አዲስ ያየር ንግድ ዘመን ስለ ግርማዊነትዎ ሥራ መጀመሩን ተስፋ አደርጋለሁ ። የዛሬው አዲስ አበባ መግባታችን ወደፊት እንደዚሁ አካሔድ ለመሥራት መልካም ፈቃዳችን መሆኑን እንዲአስረዳ ከሁሉ የበለጠ ምኞታችን ነው ።

ብዙ ዘመን የቆየው የግርማዊነትዎ ግዛት አውራጃ ጠቅላይ ከተማ በነበረችው ሐረር ላይ ስንበር አየር ውሥጥ ወደላይ የታላቅ ደስታ ሰላምታዋን እንድናቀርብልዎ ስለላከችን በጥልቅ አክብሮት ለግርማዊነትዎ እናቀርባለን ።

ግርማዊ ሆይ ፤ የጥልቅ አክብሮት ገጸ በረከታችንን እንዲቀበሉን እንለምንዎታን ።

ባሮን ኤንጌል ።

የውጭ አገር ወሬ

ከኢጣልያን ሌጋሲዎን የመጣ ራድዮ እንደሚያመለክተው ። በመስከብና ቺና መከከል በሆነው ጦርነት አዲስ የብርቱ ደም ማፍሰስ ጦርነት በአየር ባቡርም ሳይቀር ሆነና የቺና ሰዎች በብርቱ ተጐዱ የሚል ወሬ ከማንቹሪያ ተሰምቷል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪክ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ አሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒካላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል። የልብ።የደረት። የጉበት። የኩላሊት። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጕርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ።
የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ማስታወቂያ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት።

ሕሩንት ባግዳሣሪያን።

ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን።
መንገድ ላይ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋውግን ርካሽ ይሆናል።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በድሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምብር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቀባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባትሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያማረ ቤንዚን ይሸጣል ።



COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ቱብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ ኒውዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መጣሪያ ዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ እለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ እያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋውግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ግሬብያን ትሬዲንግ ኩባንያቤትነው።

ጉድዩር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

[illegible] የኢትዮጵያ መንግሥት [illegible] ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
5me ANNEE № 38

ሐሙስ መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 19 SEPTEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hebdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክቱሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በቱጃርና በነጋዴዎች መሐል ለሚገበያዩት ነገርና ደግሞ ስለ ደላሎች መዝገብ መጻፍ የተደረገ ማስታወቂያ ።

በከተማ ያሉት ደላሎች በመዝገብ እንዲጻፉ ሲሉና በነጋዴዎችና በቱጃር መካከል ለሚገበያዩት ነገር በደንብ እንዲሆን ሲሉ የንግድ ሚኒስትር እንደራሴ ቀጥሎ የተጻፈውን አስታውቀናል ።

(፩) ስለ ቱጃርና ስለ ነጋዴ ።

ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ወር ድረስ ነጋዴ፣ ቱጃር፣ ደላላ፣የሆነ ሰው ሁሉ ቀጥሎ የተጻፈውን በተለየ አክብሮ ጠብቆ መኖር ግዴታ አለበት ።

፩ኛ ።

በቆዳ፥በሰም፥ በቡና የሚነግዱ ወደ ውጭ አገር የሚጭኑትም፥ የማይጭኑትም ነጋዴዎች ሁሉ የገዙትን እቃ ዋጋ ለነጋዴው እስከ አምስት ቀን ድረስ ጨርሰው እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።ቀኑም የሚቈረጠው ገዡ እቃውን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ነው ። ገዢዎችም የሆኑት ነጋዴዎች እስከ አምስት ቀን ድረስ የገዙትን እቃ ዋጋውን ሳይሰጡ የቆዩ እንደሆነ ከዚህ ከተቆረጠው ቀን በኋላ ሻጩ ነጋዴ ገንዘቡን ባለ መቀበሉ የተነሣ የቆየውን ቀን ታስቦ በቆየው ቀን ልክ ገዡ ነጋዴ የቤቱን ኪራይና የምግቡንና የከብቱን ኪሣራ ሁሉ እንደ ሚገባው መስጠት አለበት ። ለዚህም ለኪሳራ በሚከፈለው ገንዘብ ሁለቱም ያልተስማሙ እንደሆነ አንዳንድ ሽማግሌ መርጠው እነዚያ ሁለቱ ሽማግሌዎች በቈረጡት ያለ ይግባኝ ነገሩ ይቈረጣል ።

፪ኛ

ከአገር ውስጥም የሚመጡ ነጋዴዎች ሁሉ ጭነው የሚአመጡት እቃ ሌላ የማታለያ ነገር ያልገባበት እንዲሆን ያስፈልጋል ። ገዢውም የገዛው እቃ ዓይነትና ሚዛኑ የተካከለ እንዲሆንለትና ዕቃውን እንደገዛ በዚያኑ ጊዜ ፈትሾና መርምሮ የተበላሸ ነገር ቢኖር ወዲያው ያስታውቀዋል ፡ ዕቃውንም በመምረጥ ገዢና ሻጭ ሳይስማሙ የቀሩ እንደሆነ ሁለቱም ተስማምተው አንድ አዋቂ ይመርጣሉ ። ይህንንም ደንብ ተላልፎ ገዢውን አሳስቶ የተገኘ ነጋዴ ሁሉ አታሎ የወሰደበትን ትርፍ ታስቦ በዚህ አታሎ በወሰደው ገንዘብ ልክ ሁለት አጠፌታ አታላዩ ይከፍላል ።

፫ኛ ።

በዚህም ደንብ ላይ ሳይጻፍ በቀረ ነገር ገዢና ሻጩ የተጣሉ እንደሆነ ሁለቱም በየወገናቸው ላልተስማሙበት ነገር አንዳንድ ሽማግሌ ይመርጣሉ ። እነዚህም ያልተስማሙ ሰዎች ሽማግሌ ወይም አዋቂ በመምረጥ ያልተስማሙ እንደሆነ ወይም የተመረጡት ሽማግሌዎች ሳይስማሙ ቢቀሩ የጉምሩክ ሹም ተቀንሲሎቹ ጋራ ተስማምቶ ይግባኝ የሌለበትና ቃሉ የማይሻር አንድ የበላይ ሽማግሌ ይመርጣል ።

፬ኛ ፤

ነጋዴዎች ሁሉ ጽሕፈትና ንባብ የማያውቁ ስለ ሆኑ ማናቸውም ዓይነት ውልና የደረሰኝ ወረቀት ሁሉ ከጉምሩክ

ሠራተኞች ፊት የደረሰኝ ወረቀትና ውል ከሚጻፍበት ቦታ ላይ ካልተዋዋሉና ካልተፈራረሙ በቀር ከሌላ ቦታ ላይ የተጻፈ ውልና የደረሰኝ ወረቀት አይረጋም ።

በአዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ ነጋዴዎች እቃ በሚሸሻጡበት ቦታ ንግዱ የበዛበት ሰፈር እየታየ እንደ ሚያስፈልግ የደረሰኝ ወረቀትና ውል ለመፈራረሚያ አንዳንድ የጽሕፈት ቤት እንዲቆም ተደርጓል ። ነጋዴዎችም የደረሰኝ ወረቀትና ውል ለዚሁ ሥራ በቆመው ቤት ሲፈራረሙ ምንም የሚከፍሉት ገንዘብ የለባቸውም ።

(፩) ደላላ የተባለ ሁሉ ለቱጃሮች የተሠራውን ደንብ በትክክል መጠበቅ አለበት። ደግሞም ከጉምሩክ በተለየ በተሰናዳው ደብተር ስሙን ማጻፍ የግድ አለበት ።

(፪) እነዚህ በመጀመሪያው ክፍል ስማቸውን ከዚህ ባላይ በተባለው ደብተር ላይ ለማጻፍ ግዴታ አለባቸው የተባሉት ነጋዴዎች ለመጻፍ እንዲችሉ በከተማ ውሥጥ በጣም የታወቁ የሁለት ነጋዴዎች፣ ወይም ዜጋው ለሆኑት የቆንሲሉ ፊርማ ያለበት በትክክል የሚሠሩና መልካም ስም ያላቸው ነጋዴዎች መሆናቸውን የሚመሰክር ወረቀት ለጉምሩክ ሹማምንቶች ማቅረብ አለባቸው ።

(፫) ይኸነንም የፈቃድ ወረቀት ለመስጠት ጉምሩክ ላንድ ጊዜ ብቻ ዓሥር ብር ይቀበላል ። ይህንንም የፈቃድ ወረቀት የተቀበሉ ነጋዴዎች ሁሉ ንግዳቸውን ያለ ችግር እንዲነግዱ ተፈቅዶላቸዋል ።

(፬) ከመዝገብ አስቀድሞ ሳይጻፍ በቆዳ፣ በሰም፣ በቡና፣ የሚነግድ ሁሉ ሐያ አምስት ብር መቀጮ ይከፍላል ይኸውም መቀጮ የከፈለ ሰውዬ የፈቃድን ወረቀት ሳይቀበል ደግሞ ሁለተኛ ሲነግድ የተገኘ እንደሆነ መቶ ብር መቀጫ ይከፍላል። በሶስተኛው ግን መቀጮው ሁለት መቶ ብር ይሆናል።

(፭)ደላላ የሆነ ሁሉ የራሱ ጥቅም ባለበት ነገር የደላላን ሥራ እንዳይሠራ ተከልክሏል ። የራሱ ጥቅም ባለበት ነገር የደላልነትን ሥራ ሠርቶ ቢገኝ በመጀመሪያ ከዓሥር ብር እስከ መቶ ብር መቀጫ ይከፍላል ። በሁለተኛው ከመቶብር እስከ አምስት መቶብር መቀጫውን ከፍሎ የደላላን ሥራ እንዳይሠራ በጭራሽ ይከለከላል ። ስሙም ከደላሎች መዝገብ ሁለተኛ እንዳይጻፍ ሁኖ ይሠረዛል ። ይኸም የተባለው መቀጮ ሁሉ በደላላው ምክንያት የተጎዳው ነጋዴ ከሚጠይቀው ካሳ በቀር ነው ።

(፮)ደላሎች ሁሉ በሕግ ከተፈቀደላቸው መዝገቦች በቀር ደግሞ የሚአሻሽጡትን ዕቃ ሁሉ በአንድ መዝገብ ውሥጥ ማጻፍ ግዴታ አለባቸው። ይህም መዝገብ አስቀድሞ በደላሎች ስም መጻሪያ ቤት ቀርቦ የተፈረመበት እዲሆን የግድ ያስፈልጋል ። በዚህም መዝገብ የሚሠራው ሥራ ፍቀት የሌለበት ይሆናል

C ሴ የሚባለው ክፍል ።

ይህ ደንብ በመላው ሲቆም የሥራውን አካሒድ የሚመራ ማስታወቂያ አንድ የውጭ አገር ዜጋ ከደንብ ተላልፎ የተገኘ እንደሆን ከሕግ የተላለፈውን የውጭን አገር ዜጋ (የንግድ ሥራ ክፍል ከሚባለው)በልዩ በቆመው የፍርድ ቤት ቀርቦ ሥርዓቱን እንዲነጋገር የአገሩ ዳኞች የሚአስፈልገውን ያደርጋሉ ።

ይህም የንግድ ሥራ ክፍል የፍርድ ቤት ለተባለው (ፕሬዚዳንት) የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ነው ጥፋተኛው የውጭ አገር ዜጋ በሆነ ጊዜ ነገሩን ዜጋው ከሆነው ቆንሲልና ለዚሁ ሥራ ያውቃሉ ተብሎ በተለየ ከሚመረጡት ነጋዴዎች ጋር ሁኖ ። (ፕሬዚዳንት)ነገሩን ያያል ።

ደግሞ ይኸነን ዳኝነት ላይ የቀረበውን ነገር ለመመርመር ነጋዴ ያልሆኑ ሌላ (ስፔሲአሊስቶች) ያስፈለጉ እንደሆነ የንግድን ሥራ ከማይሠሩ ሰዎች ውሥጥ ለመምረጥ ይቻላል እነዚህም የቀረበውን ክስ ለመመርመር ተመርጠው ከዳኛው ጋር የሚቀመጡ ሰዎች አሳባቸውን ለዳኛ ለማካፈል ብቻ ነው እንጂ ዳኝነት የላቸውም ።

ነገሩ ካለቀ በኋላ የሚከፈለው የመቀጮ ገንዘብ ሁሉ የንግድ ሥራ ክፍል በልዩ የቆመ የፍርድ ቤት ከሚባለው መሥሪያቤት ነው። አገባቡም ከዚህ ቀድሞ በልዩ ለቆመው የፍርድ ቤት በሚከፈለው መንገድ አካሔድ እንዲከፈል ይሆናል ።

ለወደፊቱ የንግድ ሚኒስቴር ስለ ሚዛንና ስለ ሚዛን ድንጋይ የሚአስፈልገውን ማስታወቂያ ያደርጋል ።

AVIS.

Afin de mettre en vigueur l'enregistrement des courtiers et la règlementation des commerçants et des nagadis le Ministre du Commerce p. i. décrète:

Que dans le délai de deux mois à partir de la publication du présent avis tous les courtiers, commerçants et nagadis doivent se conformer aux dispositions suivantes:

A. COMMERÇANT ET NAGADIS

Art. I

Qu'un délai de cinq jours pour payer au nagadis la marchandise de livrée est accordé à tous les commerçants. Le délai commence du jour ou les commerçants entrent en possession des marchandises. Si les commerçants n'effectuent pas leur payement aux nagadis dans le délai de cinq jours ils seront tenus de payer aux nagadis tous leurs frais usuels de nourriture logement et entretien de caravane qui seront en cas de contestation fixés sans appel par deux arbitres les deux parties en choisissant un chaucune.

Art. II

Que les nagadis venant de l'Interieur sont tenus de livrer et de vendre des marchandises de bonne qualité marchande et exempte de corps étrangers ou dans des emballages d'usage de manière a garan-

tir a l'acheteur leur poids et leur qualité. Les marchandises achetées doivent être verifiées soigneusement au moment de la livraison par l'acheteur qui devra présenter ses observations immédiatement. En cas de contestation sur la sélection les deux parties nommeront un expert d'un commun accord . Tout nagadi contrevenant aux dispositions du présent article sera puni d'une amende égale au double de la valeur frauduleusement soustraite à l'acheteur.

Art.III

Que pour toute autre contestation non prévue dans les articles précèdents les parties en nommeront chacune un arbitre. En cas de désaccord entre les parties pour la nommination des arbitres le chef de la Douaue d'accord au besoin avec le Cousul ou les Consuls interessés choisira un surarbitre avec décision sans appel et irrévocable.

Art.IV

Que vue l'ignorance des nagadis les contrats et les reçus devront être passés sans frais par devant un préposé au Service de la Douane.

Que dans chaque quartier et suivant les besoins du marché on installera un bureau destiné a la passation des contrats et reçus.

Qu'en cas de litige entre les commerçants et les nagadis aucun contrat et reçu ne fera foi si les dispositions preuvues par cette article ne sont accomplies.

B.COURTIERS

Art.I

Que tous les courtiers sont tenus de se conformer aux règlementations concernant les commerçants et en outre ils doivent obligatoirement se faire inscrire dans un registre établi à cet effet au Bureau de l'Enregistrement.

Art.II

Que pour obtenir l'inscription dans le sus-dit registre tous les courtiers présenteront aux autorités de l'enregistrement une déclaration signée par deux commerçants connus en ville et si nécessaire authentifiée par le Consul de leur nationalité faisant foi de leur honorabilité et de leur bonne réputation commerciale.

Art.III

Que les autorités de l'enregistrement percevront une taxe de dix thalers une fois pour toute pour delivrer la patente. Tous les courtiers munis de cette patente seront libre de faire leurs transactions.

Art.IV

Que tout courtier faisant des transactions en peaux cires cafés etc. sans être préalablement enregistré sera passible d'une amende de thalers 25. Si la même personne continu a faire des transactions sans patente après la première amende elle sera punie d'une amende de thalers 100. Pour la troisième fois l'amende sera portée à la somme de thalers 200.

Art.V

Qu'il est defendu aux courtiers de se charger d'une opérations de courtage où il y a interét personnel, et la violation de cette prohibition entrainera à l'égard des contrevenants une amende de th. 10 à 100 en cas de première infraction et en cas de récidive non seulement une amende de th. 100 à 500 mais la radiation de la liste des courtiers inscrits avec interdiction d'y figurer de nouveau. Ces sanctions seront prises sans préjudice des dommages-interéts qui pourront être dus à la partie lésée.

Art. VI

Que les courtiers a part les registres réglementaires obligatoires de part la loi pour les commerçants ils eront tenus d'avoir un registre sur lequel ils tiendront note de leurs opérations. Ce registre sera tenu sans rature et devra être parafé par le Bureau de l'enregistrement des courtiers.

C. DISPOSITIONS GENERALES.

Que dans le cas d'infraction concernant un étranger cette infraction sera constatée par l'autorité locale et celle-ci prendra les dispositions nécessaires pour provoquer le Jugement du délinquant par devant le Tribunal Spécial.

SECTION COMMERCIALE

La section commerciale sera présidée par le Directeur Général des Douanes assisté par le Consul dont dépend le délinquant et par deux experts qui seront entendus a titre simplement consultatif choisis parmi des notables commerçant ou au besoin par des spécialistes même non commerçants.

Que le paiement des amendes sera effectué auprès du Tribunal Spécial (SECTION COMMERCIALE) à la fin du litige et par voie d'execution normale.

Que le Ministre du commerce p. i. se réserve le droit de faire paraitre ultérieurement un decret pour la règlementation des poids, balances etc..

Addis-Abeba le 19

Le Ministre du commerce p. i.

ማስታወቂያ ።

የንግድ ሥራ ለሚሠሩ ሰዎች በንግድ ሚኒስቴር ባለው መዝገብ ስማቸው እንዲጻፍና ይህም ሥራ ፀንቶ እንዲቆም ሲል የንግድ ሚኒስቴር ቀጥሎ የተጻፉትን ቃሎች አስታውቋል።

(፩ኛ)

ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንሥቶ እስከ ሁለት ወር ድረስ ማኅበር አቁመው የሚነግዱ ሰዎች ባለ ፋብሪካዎች፥ደግሞ ማኅበረተኞችም ሳይሆኑ ለየብቻቸው እንጻንድ ራሳቸውን የሚነግዱና የንግድን ሥራ የሚሠሩ፥ የሚለውጡ፥ የሚሸቅጡ ማናቸውም ሰዎች ሁሉ ከንግድ ሚኒስቴር ለዚሁ ሥራ በተለየ ከቆመው ሥራ ቤት ቀርበው እንደ ደንቡ ስማቸውንና ሥራቸውን ማጻፍ አለባቸው ።

(፪ተኛ)

በዚህም መዝገብ ለመጻፍ አስቀድሞ ነጋዴዎቹ ስማቸው ከመዝገብ ሳይገባ ከመዝገብ እንዲጻፍ ለማድረግ ጥያቄ የሚአቀርቡበትን ማስታወቂያ ወረቀት ከንግድ ሚኒስቴር ይቀበላሉ። በዚህ ስሙ እንዲጻፍ ጥያቄ በአቀረበበት በማስታወቂያ ወረቀት ላይ እንዲፈርም የሚገባው ነጋዴ ብቻ ነው ።

(፫ተኛ)

በዚህም መዝገብ ላይ ለመጻፍ ለአንድ ጊዜ ብቻ ዓሥር ብር ይከፈላል ።

(፬ተኛ)

ማኅበር አቁመው ሲሠሩ የኖሩ የንግድ ቤቶች ሁሉ ማኅበራቸው የተለዋወጠ እንደሆነ አስቀድሞ በስማቸው ተጽፎ የነበረው ነገር እንዲለወጥ ለንግድ ሚኒስቴር ማስታወቅ አለባቸው።

(፭ተኛ)

የንግድን ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ሁሉ የነጋዴዎች ሥምና ሥራቸው በሚጻፍበት መዝገብ መጻፍ ግዴታ አለባቸው። ይኸንንም ሕግ የተላለፈ ሰው ሁሉ በመጀመሪያ ፳ ብር በሁለተኛው ፶ ብር መቀጮ ይከፍላል ። ደግሞ በሦስተኛው ይኸውም ነጋዴ ከዚሁ ከተባለው መዝገብ ሳይጻፍ ቢቀር በጭራሽ የንግድ ሥራ ሁለተኛ እንዳይሠራ ይከለከላል ።

(፮ተኛ)

በኢትዮጵያ ለመኖር አዲስ የሚመጡ ነጋዴዎች ሁሉ በዚህ ለነጋዴዎች ስምና ሥራ መጻፊያ በቆመው መዝገብ ለመጻፍ ሁለት ወር ጊዜ ተሰጥቷቸዋል ።

(፯ተኛ)

ይኸንንም ማስታወቂያ ለውጭ አገር ዜጎች በትክክል ለማፅናትና ለማስፈጸም ለቱጃርና ለነጋዴዎችና ለደላሎች በወጣው ደንብ ማስታወቂያ ሴ በሚባለው ክፍል ላይ በተወሰነው ነገር ሥራው ይሠራል ።

A V I S.

Afin de mettre en vigueur le Registre du commerce fondé au Bureau du Ministère du Commerce, le Ministre du commerce p. i.

DECRETE

Art. I

Que dans le délai de deux mois après la publication du présent décret toutes les sociétés commerciales ou industrielles les négociants et toutes personnes faisant des échanges commerciaux devront se faire inscrire au Registre du commerce ouvert à cet effet au Ministère.

Art. II

Que la demande d'immatriculation sera établie suivant la forme prescrite et d'après la formule qui sera delivrée au Ministère. Cette demande sera signée par la ou les personnes competentes.

Art. III

Que l'immatriculation est fixée à dix thalers taxe unique.

Art. IV

Que toute modification de la Raison sociale d'une société devra être communiqué au Ministère afin de rectifier l'immatriculation primitive.

Art. V

Que l'immatriculation sera obligatoire th. 20 sera exigée. Cette amende sera portée à th. 50 pour une deuxième infraction. Si en troisième lieu le commerçant refuse de s'inscrire il sera considéré comme ne faisant plus partie du commerce et pourra être légalement empeché de pratiquer son negoce.

Art. VI

Que les nouveaux commerçants qui s'établieraient en Ethiopie auraient deux mois de délai pour se faire inscrire.

Art. VII

Que l'application du présent decret est reglée en ce qui concerne les étrangers par les dispositions générales (C) du décret de mise en vigueur des courtiers et règlementation des commerçants et nagadis.

Addis Abeba le 19

Le Ministre du commerce

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀደም ከተማ ውጭ የሚወጣው እቃ አብዛኙ በግመል ይጫን ስለነበረ የከቴውን በግመል ጭነት ይከፍል ነበር። በኋላ ግን በግመል ፈንታ ከከተማ ውጭ የሚወጣው እቃ ብዙ ጊዜ በካሚእን ስለሚጫን በግመል ይከፍል የነበረው የከቴ ቀረጥ ታስቦ ከአራት አንድ ማለት በካሚአን ሰባት ብር ሲከፍል ቆየ። አሁን ግን የካሚአን ሥራ እየሰፋ ስለሔደ ንግዱን ለማስፋፋት ስንል ከመስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፳፱፣ ዓመት ጀምሮ አራት ቶን፤ የሚጭን ካሚአን ስምንት ስምንት ብር ሁለት ቶን የሚጭን ካሚአን አራት አራት ብር እንዲከፍል አድርገናል ።

ማስታወቂያ ።

የአገራችን ሕዝብ በየጊዜው እውቀቱ እየሰፋ መሔዱን ስለ ተረዳን፥ ስለዚህ በውጭ አገር ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ተፈቅዷል ። ይህም ስለተባለ የሕዝብን አሳብ ወደ ክፉ መንገድ የሚመልሱ ማለት ። የሕዝብን አሳብ የሚአደፋርሱ፥ አገሩ እንዲሸበር ክፉ ሥራ እንዲሠራ የሕዝብን ጥቅም የሚአጠፋ ነገር የተጻፈባቸው መጻሕፍት ሁሉ፥ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ክልክል ናቸው ። እነዚህም የተከለከሉት መጻሕፍት መጥተው የተገኙ እንደሆነ ጉምሩክ ወርሶ ያቃጥላቸዋል ።

ሁለተኛ በውጭ አገር በኢትዮጵያ ቋንቋ ታትመው ወደ ኢትዮጵያ አገር የሚገቡ መጻሕፍት ሁሉ ቀረጡን እንደ ጉምሩክ ደንብ ይከፍላሉ ።

የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ገብረ እግዚአብሔር ።

በሐረር ከተማ የአየር ባቡር መጀመሯ መምጣትና አቀባበል ።

የአየር ባቡር ነሐሴ ፴ ቀን በ፱ ሰዓት ወደ ሐረር ይመጣል ማለትን ነሐሴ ፳፯ ቀን ሰምተን ነበርና ይኸውም ፫ ቀን ሶስት ዓመት መስሎ ታየን። በዚሁም ይመጣል በተባለበት ነሐሴ ፴ ቀን፥ በሐረር ከተማ ያለ ሕዝብ ሁሉ፥ ነጋ አልነጋ ሲል ፩ሰዓት ሳይሆን ፈረስ መጋላ ተሰበሰበ። ፩ሰዓት ተኩልም በሆነ ጊዜ ክቡር ደጃዝማች እምሩ መጥተው በተሰናዳላቸው ስፍራ ተቀመጡ ። በቀኝ በኩል የኢጣልያ መንግሥት ቆንስል ወኪልና የኢትዮጵያ መኳንንቶች፥ በግራ በኩል የከተማው ቃዲዎችና ከቢራዎች ተቀምጠው ነበር ። በፈረስ መጋላም ዙሯውን የከተማው ሕዝብ ቆሞ፥ መካከሉ ባዶ ሁኖ፤ ለአየሩ ባቡር ምልክት የሚሆን ነጭ ጨርቅ ዳር እስከ ዳር የሚደርስ እንደ መስቀልኛ ተዘርግቶለት ነበር ። በሰልፉም አልፎ አልፎ የኢትዮጵያ ባንዲራ አበባ መስሎ ይታይ ነበር ። ለምልክትም ከተደረገው ከነጭ ጨርቅ አጠገብ በአየር ባቡር የሚመጣውን ፖስታ የሚቀበሉ ሶስት የሚሆኑ የፖስታ ቤት ሠራተኞች መለዮ ለብሰው ቆመው ነበር ። ፊት ለፊት የከተማው ዘበኞች ተሰልፈው አምረው ይታዩ ነበር ። ከድሬ ዳዋም ተነሣ በተባለ ጊዜ አቶ ሰሙ ንጉሤ የከተማ ዘበኞች ሹም ዘበኞቹን ማስጠንቀቅና ማትጋት ጀመረ። ወዲያው ተነሣ በተባለ በ፲፩ኛው ደቂቃ በከንቦልሽ በኩል ወፍ መስሎ ከደመናው ውሥጥ ብቅ አለ። እኛም እሱ ነው አይደለም ስንል ወደኛው ቀረበና እሱ መሆኑ ታወቀ። ወዲያው ከተማዋን አንድ ጊዜ ዞረና ሕዝቡ የተሰበሰበበትን ካስረገጠ በኋላ ወደክቡር ደጃዝማች እምሩ የጻፈውን (ፔርሶኔል) ወረቀት በትንሽ በርሳ አድርጎ አሳዩም የኢትዮጵያ ባንዲራ አሥሮ በሕዝቡ መካከል በጣለው ጊዜ ያ እንደ ጭራ ሁኖ የሚውለበለበው የባንዲራው ቀለም ሲታይ ደመናውን አቋርጦ ከሰማይ የወረደ ጅራታም ኮከብ መስሎ ይታይ ነበር ያን ጊዜውኑ አቶ ሰሙ ንጉሤ ፈንጠር ብሎ ቆሞ የከተማው ዘበኞችን ባነጋገር እየመራቸው የሰላምታ ጥሩንባ እየነፉ ሰላምታ ሲሰጡ ለተመልካች ደስ ያሰኙ ነበር ። ወዲያው ፖስተኞች ያን የጣለውን ወረቀት አንሥተው ለክቡር ደጃዝማች እምሩ ሰጡ።ሁለቴም ያህል ከተማዋን እንደዞረ ወደ ምድር ቀረብ ብሎ አንድ በጆንያ የታሠረ (አፊሲዬል) ፖስታ ሲጥል ይኸንኑ የሚጠብቁ ፖስተኞች በፍጥነት አንሥተው ወደ ፖስታ ቤት ወሰዱት ። የአየሩም ባቡር አንድ ጊዜ ዞሮ ወደመጣበት ከተመለሰ በኋላ ያን በፊት የጣለውን ወረቀት ክቡር አለቃ ደስታ ለሕዝቡ ሁሉ አነበቡ ቃሉም ከዚህ በታች እንዳለው ነው ።

ክቡር ደጃዝማች እምሩ ።

የሐረርና የአውራጃዋ ሁሉ እንደራሴ ሐረር ።

ክቡር ሆይ በሚበረው በመጀመሯ አኤሮፕላን ላይ ሁኜ ለክቡርነትዎ ሰላምታ ስለ ማቅረቤ ለኔ ትልቅ ማዕረግ ነው ። ለኢትዮጵያ መንግሥት ሥራ ታዞ የሚበረው አኤሮፕላን በመጀመሯ ብሐረር ግዛት ስለ አለፈ በጣም ደስ ብሎኛል።ብዙ ዘመን ለኖረችው ለግርማዊ ከተማ የልብ የሆኑ ሰላምታዎቼን አቀርባለሁ።ያማረች ከተማዎንም በምድር መንገድ መጥቼ ጐብኝቼ ፤ ከክቡርነትዎም ተገናኝቼ ቃል ለቃል ለመጨዋወት ተስፋ አለኝ ።

ክቡር ሆይ እውነተኛ የማክበር ሰላምታዬን እንዲቀበሉኝ እለምንዎታለሁ ።

ሀ ወ ባሮን ኤንገሮል ።
የጀርመን አኤሮፕላን ነጂ።

ከዚህ በኋላ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ዳር እስከ ዳር እያስተጋባ ፫ጊዜ አጨበጨበ ። ክቡር ደጃዝማች እምሩም በስተቀኝ የተቀመጡትን መኳንንቶች ታዲያስ ደስ አላችሁ ወይ ብለው ጠየቋቸው፥ በጣም ደስ ብሎናል፥ ይኸን ላሳዩን ጌታችን ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ብለው መለሱ።እንደዚሁ ደግሞ በስተግራ የተቀመጡትን ቃዲዎችና ከቢራዎች ጠየቋቸውና እኛ ከደስታችን የተነሣ ምንም ልንናገር አንችል ዕድሜ ለንጉሣችን አሉ ።

ከዚህ በኋላ ክቡር ደጃዝማች እምሩ መኳንንቶቹን ይዘው ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ።በሸምፓኝም ጊዜ ክቡር ደጃዝማች እምሩ ተነሥተው እኛ ዛሬ ይኸን የአየር ባቡር በማየታችን የታደልን ነን።ደግሞ በጌታችን ትጋት ወደ ፊት ያገራችን ልጆች ሲነዱት ሲሠሩት እንድናይ ተስፋ አለን።አሁንም ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ይኸንን ላሳዩን ጌታችን ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ስለ ኢትዮጵያ ስፋትና ልማት ጽዋዬን አጠጣለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ፥ ዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ። በዚሁ ቀን በሐረር ከተማ አንድም ደስ ያላለው ሰው አልነበረም ለግርማዊ ንጉሥ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እንጂ በእግዚአብሔር ፈቃድና በጌታችን መሪነት አገራቸውንና ጌታቸውን የሚወዱ ያገራችን ልጆች ተምረው ሲሠሩትና በአየር ሲያበሩት እንድናይ የማይቈረጥ ተስፋ አለን።ለሰው ልጆች ይኸን ያህል እውቀት የሰጠ አምላክ ይመስገን፤አሜን ።

አስፋው አበጀ ።

ስለ ጋብቻ አኳኋን ።

የመላውን የዓለም ሕዝብ አንዋንዋር ስንሰማና ስንመለከትም ከኢትዮጵያ ሀገራችን ልዩ ሁነው ይታያሉ ። ልዩነታቸውም ቀጥሎ እንደሚነገረው ነው።በኤውሮፓና በአፍሪካ የሚኖሩ የክርስቲያን ሕዝቦች ሁሉ፤የሲጋቡ ሳሉ ያለተክሊል ለመጋባት አይችሉም።በተክሊልም ከተጋቡ በኋላ ለመለያየት ሳያስቡና ሳይጣሉ በዚህ ዓለም እስከሉ ድረስ ባልዮውም ለሚስቱ፤ ሚስቱም ለባሏ፤ እየተሳሰቡ፤አንቺ ትብሽ፤ አንተ ትብስ እየተባበሉ እንደ ሁለት የሚፋቀሩ ጓደኞች ሁነውና ተፋቅረው በምድር ለሥጋቸው ፤ በሰማይ ለነፍሳቸው የሚሆነውን እያሰቡና እየተሳሰቡ ይኖራሉ ይባላል። እኛም በዕድሚያችን እርግጥ መሆኑን ለይተን አይተናል ።

አንዳንድ ጊዜ እንኳን ባልሆነ ነገር በተቀያየሙና በተጣሉ ጊዜ ሁለቱም ወደ መምህሮቻቸው ሒደው፤ ጠባቸውን አመልክተው በኋላ መምህሮቻቸውም ይኸነን የነሱን ጠብ በመንፈሳዊ ዳኝነት ፈርደው፤ ጥፋተኛውንም መክረውና አስማምተው ይለዷቸዋል ። ባልና ሚስቶችም ያነን የመምህሮቻቸውን መንፈሳዊ ምክር ተቀብለው ፤ ያነን የተቀያየሙበትን ነገር ትተው በተድላና በደስታ ተስማምተው ይኖራሉ ይባላል። በሀገራችን ግን ከቀሳውስቶች በተቀር ሌላው ሕዝብ ምንም ያህል በሕግ እየተጋባ ተስማምቶ የኖረ እጅግም አይገኝ ይመስለኛል ። እኔም ይኸነን ስመለከተው ይህ ሁሉ ነገር መጻሕፍትን ያለመመርመርና ታሪክን ያለመመልከት ነው እያልኩ አዘንኩኝ ።

ይህን ለመሰለው ነገር መምህሮቻችንና መንግሥታችንም የጠነከረ ደንብና አዋጅ ቢያደርጉልን ይህ የተወደደና የተከበረ መንግሥታችን በጣም የተወደደና ኃያል በሆነ ነበር ።

፩ኛም ይኸ በሕግ በግድ ተጋቡ ተብሎ ሕዝብን መያዝና ማስገደድ ለጊዜው የማይቻል ቢሆን አንድ አጭር ነገር ባልና ሚስትን እንዳይለያዩ ማስማሚያ የሚሆን ነገር መደንገግና መደንባት በመንግሥት በኩል ያስፈልጋል ።

፪ኛ ባልናሚስት ለመጋባት ባተዋደዱ ጊዜ ወደ መንግሥት ዳኛ ሒደው ውላቸውንና ኮንትራታቸውን አቅርበው ከተፈራረሙ በኋላ በዚሁ ሥራትና ሕግ መታገድ ይችላሉ።ሕግም ቢያፈርሱ ሁለትና ሦስት ጊዜ ተመርምረው ከወንዱም ሆነ ከሴቷ ጥፋት ቢገኝ የሚገባቸውን ቅጣት እንዲቀበሉ ማድረግ ነበር ።

፫ኛ በሀገራችን ኢትዮጵያ ውሥጥ ባልና ሚስት ሲጋቡ በሰማኒያ ተፈጣጥመው ነው የሚጋቡት።ይኸውም ጋብቻ እንደ ኮንትራት ዓይነት ነው ። ሲፋቱም ሰማኒያ ማውረድ ስለ ሆነ በዚህ ነገር ምንም ስምምና ጥቅም ያለበት ነገር አይደለም ።

፬ኛ ይኸነን ባልና ሚስት ተስማምተውና ተዋደው፤ ተፈጣጥመው የተጋቡትን በኋላ ወንዱ ልፍታሽ ወይንም ሴትዋ ፍታኝ ባለች ጊዜ አልፈልጋም ያለውን አንደኛቸውን በነገራቸው ላይ ዳኛ መርምሮ ከወቀ በኋላ ያነን እንቢ ያለውን ሰማኒያ ብር እስከፍሎ ቢያለያዩዋቸው ደግ ነበር።ማለት በፊት ተዋደው ከተጋቡ ሁለተኛ ለመለያየት አይገባቸውምና ይህን የማይገባ ነገር ስላደረጉ የመንግሥት ሰማኒያ በከንቱ አይቀርምና ጥፋተኛውን መርምሮ ኮንትራቱን ያፈረሰውን ሰው ሰማኒያውን አስነሥቶ ማስከፈል ይሻላል።

አሁን ሁለት ባላጋሮች ተጣልተው እዳኛ ላይ ደርሰው ነገራቸውን ዳኛው ለሌላ ጊዜ ቢያቃጥራቸው በዚያው እዳኛው ላይ እንዲመጡ በተፈጣጠሙበት ቀን አንደኛው መጥቶ አንደኛው ቢቀር ከሰማኒያውና ከቀጠሮው ስለቀረ ጥፋተኛ በመሆኑና የመንግሥትን ሰማኒያ በማጓደሉ ሰማኒያውን ከንድቶ ለመንግሥት እንደሚያገባ ሁሉ ጥፋተኛውን እያዩ ሰማኒያውን ከወንዱም ሆነ፤ ከሴቷ ማስከፈል ይሻላል እንጂ በየቀኑ እየተጋቡ በየቀኑ እየተፋቱ የመንግሥትን ሰማኒያ ማራከስ አይገባቸውምና ስለዚህ ስለጋብቻ ነገር ደንብ ለማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶ ለተፈቀደላቸው መኳንንቶች ይህቺን ትንሽዋን ሐሳቤን ላሳስባቸው እወዳለሁ ። በቀለ ዘለቀ።

ማስታወቂያ ።

ከርሻና ከንግድ ማስፈያ ቤት በነጋድራስ በሀብቴና ባቶ ምትኬ፤ባቶ ይታጠቁ ሹመት ጊዜ ገንዘብ የተበደራችሁ ሰዎች ሁሉ ባሁኑ ወር መስከረም ፳ ቀን ጀምሮ እገንዘብ ሚንስቴር ጽሕፈት ቤት ድረስ ዋናውን ከነወለዱ እያመጣችሁ እንድትከፍሉ እናስታውቃችኋለን ። የገንዘብ ሚኒስቴር ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂክኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።



በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕሩንት ባግዳሣሪያን ።

ከግሪክ ቤት ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋውማን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።


BALLOON
GOODYEAR
ALL WEATHER
GOODYEAR
2-28-14

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ።እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ።ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው።

ጉዱዬር ግዙ

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
5me ANNÉE № 39

ሐሙስ መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 26 SEPTEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት እልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሓፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አዋጅ

ይኸን የመጣውን ያንበጣውን መቅሠፍት እግዚአብሔር በቸርነቱ እንዲመልስልን፡ሩጣሬያችን ከለመኑት ጨከኝ አይዶ-ለምና ቤት ክርስቲያን የሚቀርብህ በያጥቢያህ፡ቤተ ክርስቲያን የራቀህም፡በየደጅህ እግዚአታውን(ምህላውን) አታስታጉል ።

ባደባባይም ለነገር የተቀመጥህ ሰው በየቤትህ ገብተህ እስከ ታኅሣሥ ልደታ አዝመራህን ሰብስብ ። ደግሞ ምሕረት ለሚለምን ምሕረት ማድረግ የሚገባ ስለ ሆነ፡ዳኝነትና ውርርድ ሰማንያ እስከ መስከረም ሚካኤል ያለውን የኛንም ምረናልና አገር ገዢም ማርልን ።

የዘንድሮውንም የ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ድኃው መከሩን እንዲሰበስብና ከንበጣ የተጐዳውም አገርበ ጭራሽ እንዳይጠፋ፡ ላንድ ዓመት የዳኝነትና የውርርድ ዕዳ ግማሹን እንዲከፍል አድርገናል ።

የማር ግብርም የሚከፍል ሰው፡ማር ያገኘ እንደሆነ እንደቀድሞው ማሩን ይገብር ። ማር የማያገኝ ድኃ ግን፡በያንዳንዱ ዋንጫ ማር ሒሳብ አንዳንድ ብር ይክፈል ። መኸትም የሚገብር፡ ያለው ሙክቱን ፡ የሌለው ግን ባንድ ሙክት ፩ ብር ይስጥ ። የወፍጮ ግብር ያለበትም፡ጥንት እየፈጨ ከሚጭነው እኵሌታው ወፍጮ ቀርቶለት፡ እኵሌታውን ጥሬና እኩሌታውን ዱቄት ይጫን ። ቈላ አገር ግን በድርቅና በውርጭ፡ ባንበጣም፡ በችግር ምክንያት ሰብል ስቶብህ፡ከ፲፰፻፺፱ ዓ ም፡ ከሶስት ዓመት ወዲህ፡ቤትህን ዘግተህ፡ በጭራሽ ተሰደህ፡ ቦታህን ለቀህ፡የሔድክ ሰው፡ ከተሰደድህበት አገር ተመልሰህ ገብተህ እረስ፡ያለፈውን የግብር ዕዳ ምረንሃል፡ወደ ፊትም የጠፋብህን እርሻና ቤትህን የምታቀናበትን ሁለት ዓመት ቀን ሰጥተንሃል ።

መስከረም ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ።

የቂም ፍላጎት ።

አንዳንዶች ፈረንጆች አንድ ትሙን በኪሳቸው ሳይዙ ይመጡና የማይቻላቸውን ኮንቼሲዮኔ (ኮንሴስዮን) ከመንግሥት ይለምናሉ ። ወይም ታቅማቸው ዘለው በትልቅ ደመወዝ የመንግሥት ስፍራ ይለምናሉ፡፡መንግሥትም ደግሞ በሚአስፈልገው ነገር የፈላጊውን አመልና እውቀት ወሬውን አጥቶ ጠይቆ ሥራ ይሰጠዋል፡በሚያስፈልገውም ነገር መቸም ለመጣው ሁሉ ደስ ለማሰኘት አይቻልምና ስፍራ የለም ይላል ። በዚህ የተነሣ ስፍራ ያላገኙት ፈረንጆች ወደ አገራቸው ሲመለሱ፡የቂማቸውን ፍላጎት ለማስጣት አገራችንን፡መንግሥታችንን በማይገባ ስድብ እያዋረዱ በትንንሽ ጋዜታ ላይ ይጽፋሉ ፡፡በትንንሽ ጋዜታ ላይ መጻፋቸው ዋኖ ዋና ስመ ጥሩዎች ባለጋዜታዎች እውነትና ሐሰቱን እንደ ወንፊት ነፍተው፡እንደ ወንጠፍት አጥርተው ያውቃሉና የሐሰት ወሬአቸውን እንዳይቀበሏቸው ስላወቁ ነው ። እነዚህ ፈረንጆች እንኳንስ እኛን ከዚህ ታገራችን የሚኖሩትን ደኅችን ፈረንጆች ሳይቀር በጋዜታ ይሰድቧቸዋል፤የሌለባቸውን አመል ይሰጡቸዋል

ስለምን ፥ የውሸት ወሬ በጋዜታ በመጻፋቸው እንዲኘቋቸው ያውቃሉና አስቀድመው በር የያዝን እየመሰላቸው ነው። በሩ ግን የገለበ ውታፍ ነው። ለሁሉም ነገር እነዚሁ ወሸት አውሪ ፈረንጆች ተደፋፍረው ውሸት ማውራታቸው መቸም በኢትዮጵያ፥ በአውሮፓ፥ ሕዝብ በሚአውቀውና ሁሉ በሚአነበው ቋንቋ የሚታተም ጋዜታ የለምና ውሸትም ብናወራ በቶሎ የሚያሳፍረን፥ ውሸታችንን የሚገልጥብን የለም ብለው ነው ። እኛ ግን ጋዜታ በማጣት አይዶለም ዝምታችን ። ብቻ የውሸት ወሬ በጋዜታ ተጻፈ ብለን ፖለሚክ ማድረግና መከታተል ጠባንጃ ለጉሞ ትንኛና ዝንብ እንደመከታተል ይሆናል ስንል ነው ። በቀረውም ዝምታ ወርቅ ይላል ተረቱ ።

ደግሞ አንዳንዶች ፈረንጆች፥የተመኙትን ደመወዝና የመንግሥት ሥራ ስላላገኙ ወደ አገራቸው ሲመለሱ በኢትዮጵያ አገር ሌባና ወንበዴ እጅግ ይበዛል ። ከዲስ አበባ ውጪ አንድ ሰዓት መንገድ ሳይርቁ መንገደኛ በጤናው አያልፍም፥ገንዘቡን ይዘረፋል፤ እቃውን ይበዘበዛል፤ሌባውም አይያዝ፤ ቢያዝም አይቀጣ እያለ በትንንሽ ጋዜታ ላይ ይጽፋል ። ይሔም በቂም የሐሞቱን አረፋ መደፈቁ ነው ። እኛም ዝም እንላለን።እሱም በደፈቁ ያጊጥበት ። እኛ ግን ሌባና ቀማኛ ጭራሹን የለም ማለት አንችልም ።

ስለምን፥ በዚህ ዓለም አድማስ እስከ አድማስ ቢዞሩ ሌባና ቀማኛ የሌለበት አገር ይገኛል ማለት ትልቅ ውሸት ነው።ነገር ግን በኢትዮጵያ ያለው ሌባና ቀማኛ በጣት ይቆጠራል። ከሌላ አገር በሚገኘው ዓይነት ብናመዛዝነው ካለ አይቈጠርም። ጥቂት ነው። እኛን በሚሰድቡትና በሚነቅፉት አገር፥ይልቁንም በጣም በሠለጠኑት፥ ብዙ ዕውቀትና ሥልጣኔ በሰፋበት አገር በድፍን ኤውሮጳና በመሪካ አገር ያለው ወምበዴና ቀማኛ፥ ሌባ ስፍር ቍጥር የለውም።

ባገራችንስ ሌባና ወንበዴ ቢኖር እንኳ፥ አዩኝ አላዩኝ እያለ ቀን በደመና፥ ሌት ጨለማ ለብሶ፥ ከበረሃና ከዱር ተሸሽጎ፤ የዛለና የሰነፈ ሰው ሲአገኝ ነው የሚቀማ፥የሚሰርቅ ። የተማረና የሠለጠነ ፖሊስመን (ዘበኛ) በሞላበት አገር በኤውሮፖና በመሪካ አገር ግን፥በየጊዜው በጋዜታ እንደምናየው፥ ወንበዴና ቀማኛው ቀናለቀን ሽጉጡን መዞ ቶሎ ተከተማው መሀል ከየባንኩ እየገባ፥ የባንክ ሹማምንትና ሠራተኞች ሁለት እጃቸውን እንዳሞራ ክንፍ ወደሰማይ እንዲዘርጉ እያንገራገረ፥ ያለውን ሁሉ ገንዘብ ዘርፎና አሟጦ ይሔዳል። በያደባባዩም የሕዝቡን ልብስ በምላጭ እየሸረከተ፥ከብብት የተሸሸገውን ገንዘብ (ባንክኖት) ይወስዳል ። ሌትም ግንብ አፍርሶ፥ ሳንቃና መስኮት አወላልቆ፥ የብረት ሣጥኑን (ኩፍር ፎር) እንደ ጉበት ዘብትሮ፥ሰርቆ ይሔዳል። ከምንም ከምን የተሸሸገው ገንዘብ አያመልጠውም ። በዚህ ዓይነት በሌባ ነገር ላሁኑ እንደ ኢትዮጵያ ያለ የጤና የንቅልፍ አገር አይገኝም፤ ገነት ናት ። ከዚህ የሚኖሩት ፈረንጆች በጣም ያውቃሉ ። አሔን ስላልሁ ግን ያገራችን ሌባ እንደሌላው አገር አይበዛም ስለማለት ነው እንጂ ያገራችን ሌባ ነባይ ነው ስለማለት አይደለም፤ የሌባ ነባይ የለውም ። ትልቅም ቢሰርቅ፥ ትንሹም ቢሰርቅ የሌባ አሳብ መቸም ያው ስርቆት ነው ። ብቻ ለሁለቱም ክንፍ አላቸው ተብሎ ዝንብና አሞራ ትክክል ናቸው ማለት አይቻልም ።

ላገራችን አገረ ገዦዎች ።

ለሁሉም ነገር አስቀድመን ላገራችን አገረ ገዦዎች የምንሰጠው ምክር ባገራችን ያለውን ሌባና ቀማኛ እንደ ወርከሥር ሳይሰድ በሬቱ እንዲነቅሉት ነው።አለዚያ ግን እደሌሎች አገር በኛም አገር ሌባና ቀማፊ እየበዛ ይሔዳል ።

አሁን በፍጥነት ካላጠፋነው አገራችንም ይበላሻል፤ ለባለ ጋዜታም እንመቻለን።ሌባ፥ ቀማኛ፥ ወንበዴ፥ ሽፍታ ለማጥፋት የሚገባቸው አገረ ገዢዎች ናቸው ። መንግሥት ለመኳንንት ሰፊ አገር መስጠቱ፥ መሾምና መሸለሙ፥ ሁሉም በየተሾመበት አገር ተቀምጦ አገር ሊጠብቅ፥ ሌባ፥ ሽፍታ፥ ወንበዴ ሊአጠፋና አገር አማን እንዲሆን፥ መንገደኛ እንደልቡ እንዲተላለፍ ነው። በዚህ ሁሉ ነገር ሌባና ወንበዴ እየበዛ ቢሔድ ጥፋቱ ያገረ ገዦዎች ነው እንጂ በመንግሥት ጥፋት የለበትም።ለከብቶቹ ጠባቂ ያስቀመጠ ባለቤት እሱ ራሱ ዱር ሒዶ ከብት መጠበቅ አይገባውም።

ንጉሥ በከንቱም ይታማል ፤ በውነትም ይታማል ።

በውነት መታማቱ፥ እግዚአብሔር በላቀው፥ ሕዝብ በመረቀው ስፍራ ተቀምጦ፥ ሕዝቡ ተባብሮ በቅንነት ሲአግዘው፥ የሕዝቡ እግዣ እግዚአብሔር ከሰጠው ኃይል ጋራ ተዋሕዶ የማይሰበር፥ የማያስጠቃ መሣሪአ ይሆንለታል ። በዚያ መሣሪያ ያፈነገጠውን እያሸራሸረ፥ያጐነደውን እያስጨነቀ፥ የተዛነፈውን እየከረከመ፥ የላላውን እያጠበቀ፥ የጐበጠና የጠመመውን እንደሞፈር እያረቀ ፥ ሁሉንም በስፍራ በስፍራው ካላደረገው፥ ባያውቅበት ወይም ቢሰንፍ ወይም ቢለግም ወይም ማን አለብኝ ብሎ ቢኰራ ነው ተብሎ ቢታማ ይገባዋል። ስለዚህ ላገር ጠንቅ፥ ለሕዝብ መሰናከል በሚሆነው ሁሉ ነገር ንጉሥ ከመታማትና ከመነቀፍ እንዳይደርስ ቢጨክን ጨክን ነው መባል አይገባውም።

ሕዝብ ማለት፥እንደ አንድ ሰው አካል ነው።የሰው አካል ሁለግዜ ጤናማ፥ሁለግዜ ትክክል አይሆንም።ወይ እግሩ ወይ እጁ ወይ ጆሮው ወይ አጣቱ ወይ ክንዱ ወይም ከሥራ ሁለት አካላቱ አንዱ ይታመማል ፤ የማይድን ቍስል ይወጣበታል ። ይሔን ቍስል የሚድን ቢሆን አክሞ፥ አስታሞ ካላዳኑት፥ የማይድንም ከሆነ ቆርጦ፥ፍቆ ካልጣሉት፥የቀረውን ደኅናውን ወገን አግምቶ፥ የትል መጫወቻ አድርጎ፥ ሰውየውን ይገለዋል። ስለዚህ ላገር ጠንቅ በሚሆነው ነገር ሁሉ ንጉሥ ቢጨክን ይመሰገናል እንጂ ክፉ ጨካኝ አያሰኘውም።በፈረንጅ አገር ሲተርቱ አዛኝ ሐኪም ቍስል ያበረታል ይላሉ ። ጨካኝ፥ ቍስሉን ጠርጎ፥ ፍቆ፥ ቆርጦ ቢጥለው ግን በሽተኛው ይድናል ።

ጥንት ፓፓ ሲስቶ በሚባለው ሊቀ ጳጳሳት ጊዜ ሮማ ላይ ሌባና ቀማኛ፥ ወንበዴ፥እየቀማ፥እየሰረቀ ሕዝቡን መከራ ሥቃዩን ሲአሳይ ይኖር ነበረ ። የጳጳሱ ወታደሮችም እንዳይዙት ያ ሌባና ወንበዴው በሮማ ከተማ ዙሪያ ትልቅ ዱር ነበረና እየቀማ፥ እየሰረቀ፥ ከዱሩ ጥልቅ እያለ እየገባ፥ለመያዝ አስቸገረ። ሊቀ ጳጳሱ በዚህ ተናደደና ዱሩን ሁሉ አቃጥሉት ብሎ አዘ

ዘ ። ሹሞቹ ከዱሩ መካከል ቤተክርስቲያን አለበትና ለማቃጠል አይቻልም አሉ። ፓፓ ሲስቶ ተቆጡና ያክርስቶስ ቤት የሌባ መቃጠሪያና መሸሸጊያ አይሆንምና ጨምራችሁ አቃጥሉት አሉ። ዱሩም ቤተክርስቲያኑም ተቃጠለ። ሌባና ወንበዴውም የሚሸሸግበት ስፍራ ሳጣ በግዱ ነብይነት ተምሮ ከተማ ኑዋሪ ሆነ ። በተቃጠለው ቤተክርስቲያንም ፈንታ ትልቅ ያማረ ቤተክርስቲያን ተተከበት ። የፓፓ ሲስቶ ጭከና ለሕዝቡ ምሕረትና ጤና ሆነ፤ቤተክርስቲያኑም በልጦ ተሠራ። ንጉሥም በሚአስፈልገው ጊዜ ቢጨክን ጨካኝ አያሰኘውም፤ሕዝቡን፤አገሩን መንግሥቱን ለማዳን ነው ።

ንጉሥ የእግዚአብሔር ምስለኔ ነው ።

ምስለኔ ማለት እንደኔ፡ እንደራሴ ማለት ነው ። በእግዚአብሔር ዘንድ ንጉሥን ምስለኔ ማለት እንደኔ እንደራሴ ሁነህ እኔ ለፈጠርሁት ሕዝብ ጠባቂ አድርጌሃለሁና እስብለት፤ጠብቀው፤ በትክክል አሳድረው፤በሚጠቅመው መንገድ ምራው ማለት ነው። ንጉሥና እግዚአብሔር በአንድ ነገር ብቻ ይለያያሉ።እግዚአብሔር አምላክ ነውና በሚሠራው ነገር ሁሉ አጋዥ አያስፈልገውም ። ንጉሥ ግን ፍጡር ነውና አጋዥ ከሌለው ብቻውን ሁኖ ምንም ሊአደርግ አይቻለውም ። ቢቻለውም አንድ ሰው ከሚሠራው ሥራ የበለጠ ነገር መሥራት አይችልም ። አጋዥ ያስፈልገዋል ፤ አጋዥ ማለት ሕዝብ ነው ። ሕዝቡ በቅንነትና በኅብረት፣ በትጋት ፤ አለልግም ያገዘው እንደሆነ የሕዝቡ እርዳታ የማያስጠቃ መሣርያ ይሆንለታል ። በዚያ መሣርያ ንጉሡ የሚገባ ሥራ ለመሥራትና ሕዝቡን በሚገባ በተደላደለ መንገድ ሊመራው ይችላል ። ሕዝቡ ግን በቅንነትና በትጋት ካላገዘው ሥልጣኑና መብቱ የሰነፈ ይሆናልና የገዛ ዜጋውን በትክክል መንገድ ሊመራው አይችልም፤ ያቅተዋል ።

እንዲህም ከሆነ ንጉሡ በስንፍና ስም ሊጠራና ፌታማ ዘንድ አይገባውም ። ሕዝቡ ግን ለንጉሡ ማገዙ ለገዛ ራሱ ማገዙ ነው እንጂ ለንጉሡ ማገዙ አይደለም ። በቅንነት ለንጉሡ ካላገዘ በገዛ ራሱ መለገሙ ነው ። በገዛ ራሱ የለገመ ሰው ንጉሡን ማማት አይገባውም ። የሕዝብ እገዛ ዓይነቱ ብዙ ነው ። እኩሉ በጉልበቱ፤እኩሉ በምክር፤ እኩሉ በሥራ፤ እኩሉ በብልሐቱ፤እኩሉ በንግዱ፤ በርሻው፤ ያገለግላል። ሁሉም በአንድ ላይ ሲሆን ለንጉሡም ኃይል ጉልበት ይሆናል። ላገርም ጸጋና ሀብት፤ ደስታ ይሆናል ። ካንዱ እገዛ ያንዱ ይሻላል ማለት በከንቱ ነው ። እርሻ አለንግድ፤ ንግድ አለ እርሻ፤ ወታደር አለባላገር፤ ባላገር አለወታደር መኖር ይችላል ማለት ተረት ነው ። ይኸ ሁሉ እገዛ ተሰብስቦ በንጉሡ እጅ ከሆነ ወድያ ንጉሡ ባለማወቅም ይሁን፤በስንፍናም ይሁን፤ በኩራትና በልግምም ይሁን፤ በምንግዴና በጨዋታ፤ በዘፈን መሙደድና በስካር ፤ በዝሙት ማብዛት የተነሣ ወይም የማይረባ ምክር እየሰማ የተሳሳተ እንደሆነ መታማት ብቻ አይደለ፤ ከመፈገምም ይደርሳል።የገዛ መንግሥቱን፤የገዛ ሕዝቡን የገዛ አገሩን እየገፋ ወደ ገደል ጫፍ ማድረሱ ነው ። ሳርዳናፓሎ እንደዚሁ ሁኖ ቀረ ።

አፈ ወርቅ ዘብሔረ ዘጌ ።

የበግና የፍየል ጠቦቶች የሳምባና በትል ተላላፊ የሆነ በሽታ ።

መጀመሪያ ፤ ተላላፊ የሆነ የበግ ጠቦት የሰምብ በሽታ

እንደሌላው የበግና የጠቦቶች ተዘዋዋሪ በሽታ ሁሉ ይህም በሽታ በበጎቻችን ላይ ትልቅ አደጋ ያደርጋል።ይልቁንም ይኸው በሽታ በኢትዮጵያ ውሥጥ በክረምት ወራት የሚነሣ ስለሆነ በየመቱ ከዚሁ በሽታ የተነሣ የሚያዝኑ ባለበጎች ሳላገኝ አልቀረሁም።ባለፈው ዓመት ይኸው በሽታ በእንጦጦ ተነሥቶ ብዙ አደጋ አድርጎ ነበር።ነገር ግን በዚያን ጊዜ ባለበጎች ከሆኑት ሰዎች መካከል አቶ በቀለ ኪሮስ ብቻ ወደ ከብት ሐኪም መጥቶ በመድኃኒት እርዳታውን እንዲያደርግለት አስታወቀ እንጂ የቀሩት ባለበጎች ግን በጎቻቸው ሲያልቁ ዝም ብለው ነበር።አሁንም በዚህ ዓመት ይኸው በሽታ እንደገና ተነሥቶ በበጎቹ ላይ አደጋ መጣሉን ጀምሯል። ስለሆነ ከዚህ በሽታ መከላከያ የሚሆን የክትባት መድኃኒት መኖሩን ሰው ሁሉ ስላላወቀ ባለበጎች ለሆኑ ሰዎች ይህንኑ እያስታወቅሁ ደግሞ በዚሁ በጋዜጣ ከዚሁ በሽታ መጠባበቂያ የሚሆነውን ነገር አመስክታቸው ዘንድ ትልቅ ሥራዬ አድርጌ እቆጥረዋለሁ ።

የበሽታው አካሔድ የበጎች የሳምባ በሽታ አነሣሥና አጀማመር በጭራሽ የማይታወቅና የማይለይ ምልክት የሌለው ነው። ሁልጊዜም የዚሁ በሽታ አጀማመር ዝግ እያለና እየበረታ የሚሔድ ነው።በሽተኛውም በግ እስከመጨረሻ ድረስ ይበላል ። ነገር ግን ከሦር ወይም ከሥራ አምስት ቀን በኋላ ይከሳል በሽታውም ጠንክሮበት ይወድቃል፤ይኸው በሽታ ሲጀምረው ይፈዛል።ብርታትም ያጣል ማብላትም ካልቻሉ ጥቂት ጥቂት ያስለዋል በዚህም ጊዜ ሕመምተኛው በግ ይተኛል፤ ትኩሳትም ይሰማዋል፤ መተንፈስም ያቅተዋል፤ ሳሉም እየበረታ አስቸጋሪ ይሆናል፤በዚያም ጊዜ ብጫ የሚመስል ልጋግ ይጥላል፤መቆምም ይሣነውና እንደ ሽባ ከብት ሁልጊዜ እየተጥመዘመዘ ይወድቃል፤ ከዚያም በኋላ ሞት ይመጣበታል ።

ለዚሁ በሽታ መጠባበቂያ ፤ ፩ኛ በሽታው የሚተላለፍበት ዋናው ነገር የሚበረታበትና የሚጸናበት በሚክሮብ ስለሆነ መጀመሪያ በልጋግ ከመስክም ላይ በሣር የተነሣ ይሆናል። ደረቅም በሆነ የበግ ቤት ካበረው የተነሣ ደኅናዎቹን ይይዛቸዋል። ስለዚህ ደህናዎቹን በጎች ፤ ለይቶ ለብቻቸው ማድረግ የሚገባ ነው ። ፪ኛ እንደሚገባ አድርጎ የበጎቹን ቤት መጥረግና በኖራ ዱቄት ወይም በተበጠበጠ ኖራ መለቅለቅ ነው ። ፫ኛ የከብት ሐኪም የሚያስታውቀውን መድኃኒት ማድረግ በሚጠጡትም ውሃ መጠንቀቅና በሽተኞቹ ደኅናውን ውኃ ጠጥተው የሚያጋባ እንዳያደርጉት መጠባበቅ ። ፬ኛ ደኅናዎቹን በጎችና ግልገሎቹን ሁሉ በቶሎ ማስከተብ ። ፭ኛ በሽታው በገባበት አገር በሽታው በጎቹን እስኪያማቸው ድረስ ቆይተው እንዲያስከትቡ አይደለም። ነገር ግን ከዚህ በላይ እንደጻፍኩት በሽታው እስኪታወቅ ድረስ የሚዘገይ በመሆኑ ብዙ በጎች አስቀድመው ይያዛሉና አስቀድሞ ማስከተብ ነው ።

ሁለተኛ ከዚህ በላይ ከተነገረው በሽታ ጋር አንድነት ሁኖ በትል ስለሚነሣው ተላላፊ ለሆነው የበግ በሽታ ግን ከዚህ

በላይ ለተነገረው የሳምባ በሽታ ካስከተቡ በኋላ ለታመሙት ከብቶች የከብት ሐኪም የሚያመለክተውን የሚያድን መድኃኒት ማድረግ ነው ። የከብት ሐኪም ሚሀራን ካይማኪያን ።

እንቍጣጣሽ ።

እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ ያሸጋገራችሁ ስል የሚከተሉትን ቅኔዎች ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ፥ ለልዕልት ወይዘሮ መነን፥ ለብርሃንና ሰላም፥ለሊቀ ጳጳሱና ለጳጳሳቱ አቀርባለሁ ። ደግሞ ወደ ዘመነ ሉቃስ በደኅና እንዲያደርሳቸው እየተመኘሁ ይህቺን ቅኔ አበረክታለሁ ።

ሥላሴ

መስቀለ ዕዳ ሮምያ፥ አንተ ወድቀ ዲበ ምድር፥
በቀራንዮ ኢይፀርር ባሕቲቶ ፥
መትከፈ ብእሲ ክርስቶስ
መስቀለ ዕዳ ቀራንዮ አውፅአት በጢስ
እሌኒ ንግሥት ባሕቲ፥ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ
አውፅአ በኃይል ወበነፋስ
ለክንፈ አይሮፕላን ክቡድ ዕዳ ንስር ዕኑስ
እንተከነ በሰማይ ሐዳስ

ሥላሴ

ይርዓዩ መንክራቲሁ፥ ተለውዎ ሕዝብ ብዙኃን፥
ለብርሃነ ሰላም ክርስቶስ ማሕየዊ፥
እምገጸ ዕውራን ዓትምት
ውእቱ አምጣነ ሰደዶ ለእኩይ ጽልመት
ወአመ በገዳም ተሰእነ ፈጺሞ ወሀቤ መና ክህነት
ለዘመጽኡ ሕዝብ እምበሐውርት
አጽገበሙ በክልኤ ዓሣ ነገሥት
ወበኃምስቱ ጳጳሳት ኅብስት

መወድስ

መቃብረ ጥበብ ወልድ ከመ ይሕውጺ፥
አመ ነሀ ጽባሕ ከነ ኤሮፕላውያን አርዳኢሁ
ዘያስተዓፅብ ረዊጸ እንዘ ይትባደሩ በጽሒ
መንገለ ተቀብረ ምኒልክ ሥጋሁ
ለኃይለ ሥላሴ አእዳዊሁ
መቃብረጥበብ ኅትምተ፥በመንፈቀ ሌሊት እምድኅረ፥ፈትሐ
መሪረ፥ አንብዐ ደም፥ ከመ ይብክያ ላዕሌሁ
እስከለማርያም አንተ ዕፍረት ወመግደላዊት መርዓት ጽርሐ
መቃብረ ጥበብ ጌሣ እንዘ ፍና ጽልመት ዓዲሁ
ወለሐዋርያት ሰባክያን ሰበከ ትንሣኤሁ

አለቃ ዳንኤል እ ደስታ።

ያዔ መስቀል በዓል አከባበር ።

መስከረም ፲ ቀን ያዔ መስቀል በዓል ነበርና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በማረ ዓጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ወርደው፥ አምሮ በተሰናዳው ድንኳን ገብተው በዙፋን ላይ ተቀመጡ ። አራት ሰዓትም ሲሆን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት መጡና በዙፋናቸው ተቀመጡ ። ከዚህ በኋላ የውጭ አገር ምኒስትሮችና ቆንስሎች፥ መኳንንቶችና ወይዛዝሮችም መጡና በውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ዋና ዲሬክተር በክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ አቅራቢነት ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ከግርማዊ ንጉሥ ተገናኝተው እንደየመዓርጋቸው በተሰናዳላቸው ስፍራ ተቀመጡ ።

ከዚህ በኋላ የየአድባራቱ ካህናት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ከተቀመጡበት ድንኳን ፊት ለፊት ቀርበው፥ ያዔ መስቀልን በዓል አደራረስ የሚፈጽሙበት ድንኳን ተተክሎላቸው ነበርና ሊቃውንቱና ካህናቱ በድንኳኑ ውሥጥ ሁነው ሥርዓታቸውን በዜማና በንባብ በፈጸሙ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ከያይነቱ አምሮ የተጐነጐነውን አበባ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ሰጡ ። በትልቅ ጠረጴዛ ላይ የተደረደረውም አበባ ከዚያ ለነበረ ሕዝብ ሁሉ ታደለ ። ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ባርከው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱት ።

የመስቀል በዓል አከበባር ።

መስከረም ፲፯ ቀን የመስቀል በዓል ዋዜማ ስለሆነ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በር ፊት ለፊት ባለው ሜዳ የደመራው ዕንጨት ቆመና በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ጥግ የመስቀልን በዓል ፈንጠዚያ ለማየት የመጡ የውጭ አገር መኳንንትና ወይዛዝር፥የኢትዮጵያ ሊቃውንትና መኳንንት የሚቀመጡበት፥ ሶስት ሰፋፊ ያማረ ትልልቅ ግምጃ ድንኳን ተተከለ ። በመካከሉም ግርማዊ ንጉሥ የሚቀመጡበት ከፍ ያለ በሚያንጸባርቅ በወርቅ የተጌጠ ዙፋን ተሰናዳ ። ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ፥ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና መኳንቶች የሚቀመጡበት ወንበርም ከግርማዊ ንጉሥ ዙፋን በስተ ቀኝ በኩል ተሰናዳ ። በስተ ግራ በኩልም እጨጌና የኢትዮጵያ ሚኒስትሮች መኳንንቶችም የሚቀመጡበት ወንበር በሥርዓት ተደረደረ። ሰልፍ የሚጀመርበት ጊዜ ዘጠኝ ሰዓት መሆኑ ታውቆ ነበርና ሰዓቱ ሲደርስ አስቀድመው ሊቀ ጳጳሳቱ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ጳጳሳቱ መጡ ። ወድያውም የውጭ አገር ሚኒስትሮች መጡና በየስፍራቸው ተቀመጡ ። ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ በማረ አውቶሞቢል ሆነው ደረሱና አምሮ በተሰናዳው ዙፋናቸው ተቀመጡ ።

ከዚህ በኋላ የየአድባራቱ ካህናትና ሊቃውንት መጥተው በደመራው ዙሪያ ቆመው የሚገባውን ሥርዓት አድርሰው ወንጌል ተነበበ ። ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ጳጳሳቱ ወደ ደመራው ቀረቡና ፵፩ እግዚኦታ አድርሰው ደመራውን ፻ ጊዜ ዙረው ገለል ሲሉ ግርማዊ ንጉሥ

ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ ሰስት ጊዜ ደመራውን ዞረው ተመለሱ ።

ከዚህ በኋላ የጦር ሚኒስቴር ሠራዊት በክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ በጦር ሚኒስትሩ እግር ሆ እያለ፥ አበባውን በደመራው ላይ እየጣለ፥ ሰልፉን እያሳየ አለፈ ። ቀጥሎም የጃንሆይ ግቢ ሠራዊት ባግቢ ሚኒስትሩ በቢት ወደድ ወልደ ገብርኤል እግር ሰልፉን እያሳየ አለፈ።ቀጥሎም የገንዘብ ሚኒስቴር ሠራዊት በገንዘብ ሚኒስትሩ በበጅሮንድ ዘለቀ አግደው እግር ሰልፉን አሳይቶ አለፈ። ቀጥሎም የሥራ ሚኒስቴርሠራዊት በአቶ ፋሲል እግር ሰልፉን አሳይቶ አለፈ።ቀጥሎም የጽሕፈት ሚኒስቴርሠራዊት በጸሐፌትእዛዝ አፈወርቅ በጽሕፈትሚኒስቴሩ እግር ሰልፉን እያሳየ አለፈ።ከዚሁ ጋራም የጽፈት ሚኒስትር ሠራዊት አብሮ አለፈ።

ቀጥሎም የንግድ ሚኒስቴር ሠራዊት የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔር አሰልፈውት ሠራዊቱ በፊትና በኋላ ተከፍሎ እርሳቸው በመካከል ሆነው የየክፍሉ ሥራ አለቆችም ኋላ ኋላቸውን እየተከተሉ በጥዳታቸውና በአካሔዳቸው ማማር ሰውን ደስ አሰኝተው አለፉ ። ከዚህ ቀጥሎ የከተማ ዘበኛ ክቡር ግራዝማች አማረ መርተውት ሙዚቃ ነፊዎች ልጆች ሙዚቃ እየነፉለት ባለቃ ባለቃው ያካሔዱን ማማር እያሳየ አለፈ ። በመጨረሻም የማዘገጃ ቤት ጸሐፊዎች ነጭ ኮት ለብሰው፥ ዲሬክተሩ አቶ አየለም ነጭ ኮት ለመዓርጋቸው የተገባ ለብሰው፥በነጭ ፈረስ ተቀምጠው፥ ያማረ ሰልፋቸውን አሳዩ ። ይህ ሲሆንም ሙዚቃ ነፊዎች በመካከል ቁመው ሙዚቃ ይመቱ ነበር ።

የከተማው ዘበኛ ሰልፉን አሳይቶ ካለፈ በኋላም የግርማዊ ንጉሥ ሠራዊት መምጣት ጀመረ።ከዚሁ ሠራዊትም አስቀድሞ ድሮ በፊታውራሪ ሀብቶ ጊዮርጊስ ውሥጥ የነበረው የጨበጦርና ነጭ ለባሽ ፥ ሠራዊት በክቡር ፊታውራሪ ገብረማርያም እግር ሰልፉን እያሳየ አለፈ ። ከዚህ በኋላ በሰልፍ ትምህርት የሠለጠነ ወታደር ሰልፉን እያሳየ አምሮ አለፈ ። ቀጥሎም ሰማያዊ ኮት የደረበ መትረየስ አንጋች ሠራዊት ሰልፉን እያሳየ አለፈ።ቀጥሎም ሰማያዊ ኮት የደረበ ፈረሰኛ ወታደር በሁለት በሁለት ተሰልፎ በሁለቱ መካከልም መትረየስ የተጫነ በቅሎ እየያዘ ግሩም የሆነ ሰልፉን አሳየ ።

ቀጥሎም ካኪ ኮት የለበሰ ወታደር እንደዚሁ ባለቃ ባለቃው ሰልፉን እያሳየ መድፍ የተጫኑ በቅሎችም በመካከል በመካከል ሆነው አምረው እየታዩ አለፉ ። ሰስት ታንክም በሰልፉ መካከል እየንጐደጐደ የሥራውን ሁኔታ አሳየና ሰውን ሁሉ አስደነቀ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሶስት የአየር ባቡር ከጃን ሜዳ ተነሥተው በአየር ላይ እየተንጃበቡ መጥተው ሰልፉን ለማየት በተሰበሰበው ሕዝብ ላይ አበባና በሰንደቅ ዓላማችን በሶስት ቀለማት [illegible] የተከበበ፥በቀይና በሰማያዊ ቀለም የታተመ ግጥም ይጥሉና ሰው ይሻማው ነበር።የአየር ባቡሮች በአየሩ ላይ እየተገለባበጡ ግሩም የሚያስደንቅ ጨዋታና ሽርሽር አደረጉ።የአየር ባቡር የጣለው የእንቍጣጣሽ ግጥም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

የመስቀል ዕንቍጣጣሽ ።

ለኢትዮጵያ አርበኞችና ጀግኖች ።

የመስቀል በዓል ክብር ምንኛ ገነነ ።
ከምናም ዘንድሮ የበለጠ ሆነ ።

ንግሥትና ንጉሥ በዙፋን ላይ ሁነው ።
ጀግናው ተሰልፎ መኳንንቱ ከበው ።

በግራ ና በቀኝ በግርጌ በራስጌ ።
አምስት ጳጳሳት ስድስተኛ እጨጌ ።

ደግምሞም ተንገርበበ በስተላይ በየር ።
ከጓደኞቹ ጋር የተፈሪ ንስር ።
አበባን ሊነዛ በዓሉን ሊያከብር ።

ይህ ንስረ ተፈሪ ባለ መልካም ዕድል ፡፡
ፈርዖን ድንቁርና አይቶ እኛን ሲበድል ።

በሰማይ ላይ ሁኖ ተመልክቶ እኛን።
ሰበከልን ዑቀት በሙሴ ባሮን ።

በዘንድሮው መስቀል በዛሬው ብንል ።
እጅግ ደስ ይበለን ዕልል እንዘል ።
ኤርትራን አልፏል ጥበብ እስራኤል ።

እንግዲህስ ዑቀት መናን እንመገብ ።
ከላይ መጥቶልናል በሰማይ ሲንገርበብ ።

ብርሃንን እንልበስ ሰላምን እንውደድ ።
ጊዜው ተፈሪ ነው ጨለማ እንሒድ።

በአየር ላይ ሁኖ አበባን ሲዘራ ።
ከተከታዮቹ መልክተኞች ጋራ።
ዕንቍጣጣሽ ይላል የተፈሪ አሞራ ።

ሰልፉ ታይቶ ከተጨረሰ በኋላ የውጭ አገር ሚኒስትሮች በክቡር ብላቴንጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር አቅራቢነት ከግርማዊ ንጉሥ እየተሰናበቱ ሔዱና ግርማዊ ንጉሥ በማረችና በወርቅ ዕቃ በተንቈጠቈጠች በቅሎ ተቀምጠው፥ ሰማያዊ ኮት የደረበ የክብር ዘበኛ በግራና በቀኝ፥በፊትና በኋላ ከቦ፥ በመኳንንትና በሠራዊት ታጅበው በሚያስደንቅ አጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ገቡ እንደዚሁ የመስቀል በዓል ግርማ አኳኋን ተፈጸመ ።

ብርሃንና ሰላም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ፥ለኢትዮጵያ ሚኒስትሮችና መኳንንቶች፥ለሠራዊቱና ለሕዝቡ ሁሉ፥ እንኳን ብርሃን መስቀሉን ያሰያችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ፤ (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ሲሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንስት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚልዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠበቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቤቱ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው።

ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርባስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞ ቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

ማንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጣጣን ዳገት በቶሎና አይደክም ለማውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቁርቁር መቶ ሰበኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ሞቱሩም ባለማግኔቶና ባለፀተሩ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዊንጣውም ናኪል ነው አራቱ እግሩ ላይ ማጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኮምፓኒ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል።



COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
ΚΟΝΙΑΚ - ΜΕΤΑΞΑ

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፤ ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፸፰ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፰ ብር
ባለ ድመ	።	፻፵፫
ባለአህያ	።	፻፵
ባለሳቢ ግመል	።	፻፳
ባለ አንበሳ	አሜሪካ	፻፲፱
“ “	ጃፖን	፻፸፰ ብር
ሱካር	ጁኒያ	፹፫ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፵ ሳንቲም
በአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፶፩ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፮ ከ፷ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፱

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት



ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፈኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒካላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ። የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የድማት የጨብጥ የቂጥኝና ቋቁቻ፥ የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል [illegible] ከሙሴ ጌሪጅ [illegible] ፊት ለፊት ክዲሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።





Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቶችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ ።

የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ማስታወቂያ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በየይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕራንት በግዳሚሪያን ።

ከማሪክ ቤት ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋውን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው።

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኮንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵
5me ANNÉE № 40

ሐሙስ መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 3 OCTOBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ሐሙስ በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በዓመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መውጫ አንዱን በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የብዙኃን ማርያም በዓል አከባበር ።

መስከረም ፳፩ ቀን የብዙኃን ማርያም በዓል ስለ ነበረ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በክቡራን መኳንንቶቻቸውና ሠራዊቶቻቸው ታጅበው ወደ እንጦጦ ማርያም ወጡ ። ከዚያም በገቡ ጊዜ ቅዳሴ ተጀመረ ። ከቅዳሴም በኋላ ታቦት ወጥቶ ሊቃውንቱና ካህናቱም ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ምሥራቅ ባለው መስክ በግርማዊ ንጉሥ ፊት «ዘዲበ ኢዮር መንበሩ፥ኢይሠዓር መንግሥቱ፥ደመና መንኰራኵሩ ለኃይለ ሥላሴ እኮ እንጋ ልደቱ እምአስከለማርያም ወእስተርአዮቱ ለቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት» ብለው ሲወርቡ ማኅሌቱ በጣም ደምቆላቸው ነበርና በግርማዊና በመኳንንቱ ፊት አምረው ታዩ።ከዚህ በኋላ ዑደት ተደረገና በቤተ ክርስቲያኑ ምዕራብ ባለው መስክ ታቦቱ ቆመ።ግርማዊ ንጉሥም በዚያው አምሮ በተሰናዳላቸው ቦታ ተቀመጡ። በግራ በኩልም ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ጳጳሳቱ ተቀመጡ።በቀኝ በኩልም ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተቀመጡ። ክቡራን መኳንንቶችም እንደ የማዕርጋቸው ተቀመጡ ። በዚያን ጊዜ ካህናቱ በሁለተኛው ቅጥር ባለው መስክ ሁነው «ወእንቲኢ ታቦት እምኀበኢ መጻእኪ ወኀበኪ ተሐውሪ መድኃኒተ ኩኒ ለምኒልክ ንጉሠ ነገሥት» ብለው ወርበው ሲፈጽሙ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ታሪክ ተናግረው፥ሕዝቡም በንጽሕና እንዲኖርና በሃይማኖቱም እንዲፀና መክረው፥ ስለ መንግሥቱና ስለ ሕዝቡም ጸሎት አድርገው ፥ ባርከው አሳርገው አሰናበቱት ።

ከዚህ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በማረ ዓጀብ ሁነው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ የሥልጤ ትምህርት የተማረ ወታደር በየመንገዱ ተሰልፎ እየቈየ ሳምታ ሲሰጥ ዓምሮ ይታይ ነበረ ። እንደዚህ ሆኖ አጀቡ እንደ አማረ አምስት ሰዓት ተኩል ሲሆን አዲስ አበባ ገቡ። በግርማዊ ንጉሥ ቤትም ትልቅ ግብር ተሰናድቶ ነበርና ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ገብተው መኳንንቱና ሠራዊቱ መልካም የሆነ የደስታ ግብር ሲጋበዝ ዋለ ።

የቦልሸቢኮች የክፉ አውሬነት ጠባይ ።

ሁለተኛ አንድ አቡን ከቀሩት አቡኖች ከመካከላቸው ዕድሜው ከፍ ያለውን የእግዚአብሔር መንፈስ አደረበትና አብረው ለታሠሩት ሰዎች እንደዚህ ሲል ተናገረ ። እነዚህ የሰይጣን ጭፍሮች ወደ ገሃነም ለመውሰድ ይነዱናል። ትላንት ማታ የሰጡኝ ጥቁር ደረቅ ዳቦ አለና ይኸነን ችየ ለመብላት አልቻልም፤ጥርሶቼ አልቀዋል፥በእርጅናም አንጀቴ ተጣብቋል ብሎ በትንንሹ እየፈረፈረ፥ ቍርስ አድርገልብሎ፥ እሱ አስቀድሞ፥ ቀምሶ ለያንዳንዱ በየ አፋቸው አደረገላቸው፤ እንደ ቍርባን ምሳሌ ። አጠገቡ ላለው ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ አለው፥እኔ አሁን እጅግ አርጅቼ ደክሞኛል፤ ይኸ የርጅና ጕልበቴ ስለ ሙታን መቃብር ለመፍታት አልተቻለውምና አንተ ፍታ አለው ። የዚያን ጊዜ ኤጲስ ቆጶሱ እየሔደ ከመንገድ ላይ የሙታን ፍታት መፍታት ጀመረ፤ አብረው ታስረው ይሔዱ የነበሩት ሠሚናሮች ጳጳሳቱ የሙታንን ፍታት መፍታታቸውን አላወቁም ነበር ። ከዚያው መካከል ፩ ፩ ሠሚናሮች የእግዚአብሔር ተአምር እንደ ያድናቸው ተስፋ እያደረጉ ይጠብቁ ነበር ። ከነዚሁም ፩ ሠሚናር ሲጃራውን አንስቶ ከጠገቡ ላለው የቦልሸቢክ ወታደር ሰጠው ። እንዲህ ሲል፥እስኪ ቅመሰው፥በጣም የጣፈጠ ጣም ያለው ሲጃራ ነው ። ወታደሩም ሲጃራውን ዝም ብሎ ተቀበለና ለመጠጣት ፈቃዱ ሆኖ አለቃውን ባይኑ እየተመለከተ እንዲህ ብሎ ተቈጣ፥ አሁን በጨለማ በትሔዱ ንግግር ተከልክሏል፥ የአቡኖች ሰልፍ ቶሎ ታለፈ በኋላ ከመጨረሻው ላይ ያለው ፈጽሞ እንደ አቡን

ልብስ የለበሰ ነበር። ጢሙም ከንገቱም ላይ ያለው መስቀል የአቡኖችን የመሰለ ነው ። ዓይኖቹ ግን የጉጉት ዓይን ይመስሉ ነበር ። አኳኋኑ ሁሉ እንደ ሳጥናኤል የሆነ ነበር ። በአቡኖቹ ላይ ሲፈረድባቸው ግን አልነበረም ። አስቀድመውም ሲመረመሩ እሱ ከዚያ ውሥጥ በማናቸውም ምክንያት አልነበረም ። ይኸ እሱ የተያዘበት ነገሩ በፖሊቲካ ሥራ ምክንያት ኑሯል ።

ይኸ ሰው ጥንት የመጣው ከጀርመን አገር የጀርመን ንጉሥ ነገሥት ዊሊየም ኑርዋል የላከው።እንደሱ ያለም ፲፪ ሰዎች ከጀርመን አገር ወደ መስከብ አገር ባሳቻ ልብሳቸውን እንደ ካህናቶች ልብስ አለባበስ እያደረጉ በድብቅ የተላኩ ሰዎች ናቸው፤ ነገር ሊያጠፉ ። የነዚህም ዋና ሹማቸው ከነሱው መኻከል ሰሙ አባ ራስ ፑቴን ይባል ነበር ። አስቀድሞ የቦልሼቪክ መንግሥት ሳይቆም የመስከብ አገር ሕዝብ እንደ እነዚህ ያሉትን ሰዎች ባገኙዋቸው ጊዜ ሁሉ እያነቁ ገድለው ይጥልዋቸው ነበር ። ሰላይ ነታቸውን እያወቁ ይኸም አቡን መስሎ ይከተል የነበረውም ከነዚሁ ሰላይ ከተባሉት አንዱ ነው። ከአቡኖች ጋር በሰልፍ ተራ ሲሔድ ከደረቱ ላይ ያለውን የአቡን መስቀል በቀኝ እጁ ይዞ እየነቀነቀ እንደ ጨዋታ እያደረገ ይሔድ ነበር። በሀሳቡም ከጥንት ጀምሮ የሠራውን ሥራ ሁሉ እያሰላሰለ ምንና ምን አድርጌ ኑርዋል እያለ ባሳቡ እየፈለገ ይሄዳል።አንድ ትንሽ ነጥብ የምትሆን የብርሃን የደግነት ሥራ ቅንጣትም አላገኘም።ዕድሜውን ሁሉ የጨረሰው በአታላይነትና በተንኰል ሥራ አካሄድ ነው እንጂ ዕድሜውም የ፵ ዓመት ሰው ነበረ።አብሶም ከ፲፰ ዓመት ወዲህ የካህናትን አሳቻ ልብስ ከለበሰ በኋላ ሥራው ሁሉ እንዱን ከአንዱ ጋር እንዳፋጀና እንደ አጋጨ በውስልትና ይኖር ነበር።ከመጀመርያ አኑዋኑዋሩ እንሥቶ እስከሁን ድረስ ያደረገውን ሁሉ ከወጣቶች ሴቶች ልጆች ጋር አብረው እንደ ማኅበር ሁሉ አድርገው ስማቸውን የማኅበረተኞቹን የእግዚአብሔር ወዳጆች በሉን ብለው እንዲሁም እየተባሉ እሱም ከነሱ ጋር ሳይለይ ይኖራል ። የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ሚስት በልጅነቷ ሳለች እንሥተው እስከ ትልልቆች መኳንንቶችና መሳፍንቶች ሚስትና ሴት ልጆቻቸውን ሐጋቸውን እየገሰሱ የቀሩትንም ማዕረግ ያላቸውን ሰዎች ሚስቶች ድረስ እያማገጡ በያለበት ቀንጆ የተባለች ሴት ሳትቀራቸው እያስረገዙ ይኖሩ የነበረው አኑዋኑዋር ሁሉ በሐሳቡ እያወጣ እያወረደ ያሰላስል ነበር። ይኸን ሁሉ ሥራ እሱና አብረውት የነበሩ እንደሱ ያሉት ሁሉ ሰዎች ሥራ ከመስኮብ አገር የሚደረገውን ሚሥጥር ሁሉ ገልጸው ለማወቅ ነበር።ከየመስኮቦቹ ዋናች ሚስቶችና ሴት ልጆች ሚስጥርን ለመቅዳት ያደረጉት ነው።ባሎቻችን እንዲህ ያስባሉ፥እንዲህ ያደርጋሉ። ልጆቹም አባቶቻችን እንዲህ ያስባሉ፥ እንዲህ ሊያደርጉ ነው እያሉ ሲነግርዋቸው እነሱ ይኸን ሁሉ እየቀዱ ወደጀርመን አገር ወደ ንጉሡ በድብቅ አድርገው ይላላኩ ነበር። ይኸም የአውሬነታቸው ጠባይ አከፋፋቸው ብዛት ከገዳም ያሉትን ደናግል መነከሳት ሴቶች ስንኳን አልቀርዋቸውም፥ ሲያረክሷቸው።

ይኸ ሁሉ ሲደረግ ፩ቀን ከተፈጠረ ፈሪሃ እግዚአብሔርን አያውቀውም ነበር። አምላክን፥ቅዱሳንን መንፈሳዊን ሥራ ሁሉ ይሰድብ፥ያላግጥና ያንቅ ነበር ። አንድ ጊዜ ከክፉ ከመጥፎ ሥራ ሳይወጣ የሚያስበው ገንዘብ ማግኘትንና ተንኰልን ብቻ ነበር። ይኸን እየሰላሰለ ሲሔድ ፩ጊዜ ወዲያው አእምሮው በጣም ተለዋወጠና ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ፥ንስሐ ለመግባት ባደረገው ሁሉ አምላክን ይቅርታ ለመለመን አስቦ፥ወደ አምላኩ ልቡን ሰጥቶ ወደ ሰማይ ሲመለከት ቀና ብሎ ከነዚሁ ታሥረው አብረው በሚሄዱበት ሰዎች ሁሉ በየ፩፩ አኳያ ላይ ፩፩ መልአክ በክንፍ እያንዣበበ ሲከተላቸው አየ። ወደ ራሱ አኳያ ቀና ብሎ ደግሞ ሲመለከት ጊዜ በሱ ራስ አኳያ ፩ድ ሰይጣን ክንፉን ዘርግቶ አየ።ሲከተለውም ተመለከተ ሊቀ መልአኩ ሚካኤል ግን ሰይፉን መዞ ከመላእክቶች ሁሉ ፊት ፊት ቀዳሚ ሆኖ በክንፍ ሲሄድ አየ ከየ፩፩ዱ አቡን ላይ ያሉት መላእክት ግን ከትከሻቸው እንሥቶ በደረታቸው አድርጎ እስከ ወገባቸው ድረስ ቀስተ ደመና የሚመስል መታጠቂያ መለዮ ምልክት ነበራቸው ። በዚያን ጊዜ እነዚያን አቡኖች ላየ ሰው በስተ አርጅና የደከሙትን ኃይል ሰጥቶ እንዲበረቱ የሚያስኬዳቸው መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ነው ሳይል አይቀርም ነበር። ይኸው ሰውየ እስከሁን እንቅልፍ የወሰደው መስሎ የነበረው በአኳኋኑ ሁሉ ይኸንን ባየ ጊዜ ግን አለ፤ ኢየሱስ ናዝራዊ ሆይ ገና አሁን ረታኸኝ በቶሎም ብሎ ተናገረ ። ይኸ ሁሉ ሲሆን አቡኖቹ የሙታን ፍታት እንዳደረጉ ነበር። በዚህ በጨለማ ካህናቱ እንደ ካህናት አረማመድ እየሔዱ ወዳልታወቀው ወደ ሞት መንገድ ይሔዱ ነበር ።

ከፒቴን ባቢክያን ።

መልካም አስተዳደግ ።

ከሁሉ በፊት የፈጠረህን አመስግን፥ በንጹሕ ልብህ ትእዛዙን ፈጽም፥ ያባትህን ስም ዘወትር አክብር፥አገርህን ውደዳት ጠብቃት፥(ተከላከላት) ወርቅን አትጥላ። ግን ከወርቅ በላይ ደግን ሥራና የውነተኛውን ክብር ውደድ።እንደዚህ ሁነህ ከደግህ እንደ አንድ ዛፍ በወንዝ ዳር ያደገ ቅጠሉ የማይበጠስና ፍሬው ለሰው የሚያስደንቅ ዓይነት ሁነህ ትቀራለህ፤ በሕይወትህ ሳለህ እንድትመስገንና እንድትወደድ ሥራ፥ በሞትክም ጊዜ እንድትጸድቅ ብልሃት ወጥነህ በትዕግሥት ፈጽመው፥ ታናሹን ነገር አትርሳ፤ ድር ሲያብር ዝሆን ያሥራል። ከመዋሸት ዝምታ ይሻላል ። በስርቆት ከመክበር መደህየት ይሻላል ። ከሞኞች ጋር ባልንጀርነት (ማኅበር) ከመሆን ብቻ መኖር ይሻላል። ሰው በተጣላህ ጊዜ ለመጣላት አትቸኩል።ግን በግድ ከመጣብህ እውነተኛነትክን እስክታገኝ ማናቸውንም ያነሰ ነገር ሳትዘነጋ እንድታሸንፍ ጠንክረህ ፈልግ።ላንተ ከሚመስልህ ይበልጥ ይኑርህ ከምታውቀው ያነሰ ተናገር ። ከምትታመነው ይበልጥ ተማር ። እንደዚህ ከኖርህ ከሀያው ሰስት ዓሥር ታገኛለህ ። ሐሳቦችህን ለከንፈሮችህ አደራ አትስጣቸው ። በሥራዎችህ ውሥጥ ክፉ (መጥፎ) አሳብ አትጨምር ። ገንዘብህን ለማበደርና ለሰው ማዋስም አትፍቀድ፥ስለምን የሚያበድርና የሚዋስ ሁሉ ጊዜ ገንዘቡንና ወዳጁን ያጣል ። ሥራዎች ምንም እንኳን ቢያንሱ በመልካም ሐሳብ መመራት ይገባቸዋል። ሁሉም ነገር ብኑን ነው፤በቶሎ ተረት ይሆናል፥በፍጥነትም ይረሳል፤ታላላቆችና

የታወቁት ሁሉ ባለፉ ጊዜ ይረሳሉ፤ እኛ ግን እናስታውሳቸዋለን፡ይገባናልና፤ ሁሉም ነገር ከንቱ ነው ። እንግዲህ ምን ማድረግ ያስፈልገናል፥ የቀና ሐሳብ መያዝ፡እርስ በራሳችን ደግ ሥራ መማራት፥ ዘወትር ከብለት መራቅ፥ የሚመጣውን አዲስ ነገር እንደሚያስፈልግና እንደተለመደ ሁሉ መያዝ፡ ሰው አለማማት፥ በማናቸውም ነገር አለማዘን (አለመጸጸት)ማን፡ንም ኃጢአተኛ አለማድረግ፡ በየትኛውም ነገር እራስን ከፍ አድርጎ (አልቆ) አለመናገር ነው ። የሥጋዊን ነገር ሁሉ መብልን፡መጠጥን፡ልብስን፡መኝታን፥ አሽከርን፥ በውነት ከሚያስፈልጉህ (ከሚያገለግሉህ) በቀር አታስቀምጥ ። ደግሞ ቀን የሠራኸውን ሦስት ጊዜ በሐሳብህ ሳትመረምር በዐይኖችህ እንቅልፍ አይዙር ። እራስህን እንደዚህ ብለህ ጠይቀው ወዴት ውዬ ነበር፥ምን አድርጌ ነበር፥ ምን ማድረግ ይገባኝ ነበር፥ እደስታ ለማድረስ ሥራና ትዕግሥት ያስፈልጋል።ዳግም ለማስቀመጥ (ለመጠበቅ) በልክ መሆንና መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። እመሰላል ጫፍ ለመውጣት በጣም በዝግታ ከደረጃ ደረጃ መተላለፍ ያስፈልጋል። ግን እመሬት ለመውደቅ አንድ መጥፎ እርምጃ ይበቃል ። ብዙን ነገር አደርጋለሁ የሚልን አትመን፤ስለምን እርሱ ቀላል ፥ ቀጣፊና አጥፊ ነው ። በንግግር ላይ ማንንም የበላይህ ይምስል አክብረው ፥ የምታፍርበትን አትሥራ ወደ ላይ እይ እንጂ ወደታች አትይ፡በመንገድ ውሸትን ስታገኝ ተለወጥበት፡እውቀትን ስታገኝ ምሥጢርዋን ንጠቃት፡ደግነትን ስታገኝ ጠብቃት፥ መከራን ስታገኝ አስተዛዝናት ፥ በንግግርህ በሥራህ ጨዋ ሁን፤ሰውን አታጥቃ ዘወትር ሰው ከማሠራት እራስህ ሥራ ምጽዋት አድርግ። በምክርና በሥራ ድሆችን እግዝ ፥ ወጭ ገንዘብህ ከምታገኘው አይብለጥ ። ሦስት ፈረሶች የተራቡና የከሱ ከማያዝ ሁለት የጠገቡና የወፈሩ መያዝ ይሻላል። አንተና ነገሮችህ ሁሉ በውጭና በግቢ ከሰው ጋር የተስማሙና አንድ ዓይነት ይሁኑ ፥ አትጥላ አትፎክክር፥ አትኩራ በሥራህ ፥ በንግግር፥ በሐሳቦችህ በምታደርገው ነገር ሁሉ ትክክል እውነተኛና ሥራ ወዳድ ሁን።ከመጣላት ከለመተበበር ከበደብ እራቅ ፥ በሥራት ቢጫኑህ በትዕግሥት አሳልፈው ።

አበበ በላቸው።

ፈደላትን ስለ ማሻሻል ።

ከዚህ በፊት ብርሃንና ሰላም በሁለተኛ ዓመት ፴ቍጥር የኢትዮጵያውያን ፊደሎቻችን በሥርዓት ስለ አልሆኑ የኢትዮጵያ ሊቃውንትና መምህራን በመልክ ተለያይተው በድምፅ አንድ የሆኑትን ፈደላት አገባባቸውንና ሥርዓታቸውን፡ኅርመታቸውንም በጽሕፈት እንዲያመለክቱንና ወደ ፊትም እንዲያቃኑልን በተስፋ እንጠብቃለን ብሎ ተስፋውን በጽሕፈት ገልጾ አስታውቆ ነበር ። ስለዚህም ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች እንደ ታያቸው መጠን እየጻፉ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ገልጸዋል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሽማግሌችና ሊቃውንት እድግ ስላልነቁበት በጅምር ቈየ ።

አሁንም ይህንኑ ሐሳብ መሠረት አድርገን ስለ ፊደላትነገር እናስታውሳለን፤የኢትዮጵያ ፊደላት በየዘመኑና በየጊዜው ያተለዋወጡ (የተሻሻሉ)ይመስላል።ይህም ማለት፤የድሮ ዘመን አባቶቻችን በእውቀታቸውና በብልሐታቸው የጐደለውን መልተው፥ ያልተተከከለውን አቃንተው ፥ ትርፉን አውጥተው የሚያሻሽሉት ስለ ነበሩ ነው እንጂ የጥንቱ ፊደላት ጠፍተው እንደገና አዲስ ፊደል አወጡ (ሠሩ)ማለት አይደለም። በየጊዜውም እንደ ተሻሻሉ የሚገልጽ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ በዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ የአክሱም ቤተ ክርስቲያን ለማደስና የቀዳማዊ ምኒልክን ዓፅም ለመፈለግ መሬት ሲያስቈፍሩ በወጣው ድንጋይ ላይ ተጽፎ የተገኘው የነገሥታቱ ስምና የጊዜው ታሪክ በግዕዝ ፊደል ብቻ ነበር ይባላል ። (ከሌብ ሲል ከለበ ፥ ገብረ መስቀል ሲል ገበረ መሰቀለ) ኋላ ግን አንዱ ፊደል ከሰባት ላይ ተከፍሎ፥ በመልክና በቅርጽ ተለይቶ ፥ ግዕዝ ፥ ካዕብ ፥ ሣልስ ፥ ራብዕ ፥ ኃምስ ሳድስ ፥ ሳዕብ ፥ተብሎ ተሰይሞ ባይሆን ፥ ጥቂት በርከት (በዛ) ይላል እንጂ ለነገር የተመቸ ሆነ ። ቀጥሎም በቅርቡ ዘመን አማርኛ ቋንቋ እየሰፋና እየሠለጠነ ቢሔድ ፥ መጻሕፍትም የሚተረጐሙት ባማርኛ ቋንቋ ቢሆን ፥ በጥንቱ (በግዕዝ ያልነበሩት ሽ ፥ ቸ ፥ ኘ ፥ ኸ ፥ ጀ ፥ ጨ ፥ እንደዚህም የመሳሰሉ ብዙ ፊደሎች ተጨምረዋል ። ጥንት አለመኖራቸውም የሚታወቀው ይኸው ዛሬ የዓረቢ ፊደል ብለን እንጠራቸዋለን ። ይህንንም ፊደል የጨመሩ ሰዎች ጊዜ ስለ አልረዳቸው ባያስታውሱትና ወይም ኃጢአት ቢመስላቸው ይሆናል እንጂ እስታውሰውት ጉርስ ቢሆን ከተደራረቡት ፊደላት አንዳንዱን ነጥለው ወስደው ስም ቢሰጥዋቸው ድካማቸው ይቀል ነበር ። ወይም እንደ አውሮጳ ፊደላት ሁለት ሁለቱን፥ ሦስት ሦስቱን አንድ ላይ እያይዘው ባንድ ፊደል ስም ቢጠርዋቸው ይሆን ነበር ። ምሳሌ በኢጣሊያ ኘ ሲል Gne፥ከ ሲል Che፥ገ ሲል Ghe። በአውሮጳ ሁሉ እንደዚሁ ነው። ነገር ግን እንዲህ አለማድረጋቸው ከነዚህ የተደራረቡ ካልናቸው ፊደላት ባማርኛ ቋንቋ ድምፃቸው አንድ ቢሆን በትግርኛ የተለየ ድምፅ አላቸው ለማውጣት ባይመቻቸው ይሆናል ሊነቀፉ አይቻልምና።እነዚሁም ሐመሩ ሐ ፥ ዓይኑ ዐ፥ ኸ ፥ ቐ፥ ናቸው። እውነትም እነዚህ ለአውሮጳ በተቀር በኢትዮጵያ ላማርኛና ለመላ አፍሪቃ ለሚበዛውም ለእስያ ክፍል ሕዝብ የሚያስፈልጉ ናቸውና ሊጣሉ አይገባም ።

አለዝያም የኢትዮጵያ ቋንቋ ባማርኛ ብቻ እንዲሆን ተወስኖ ጉድለትም ቢገኝበት ከግዕዝና ከትግርኛ ከጋልኛም ቢሆን ተምልቶ እነዚህን ፊደላትና ከሁለቱ ሀ፡ከሁለቱ ሰ፡ከሁለቱ ጸ አንዳንዱን ፥ እንደዚሁም ከተደራረቡት ፊደላት ነጥሎ ወስዶ በዲሶቹ ፊደላት በታ አግብቶ፥ መደበኛ ቢያደርጉት አይከፋም ነበረ። ጸና ፐም በመልክና በቅርጽ የተለያዩ ቢሆኑ በንግግር የተጠጋጉ እጅግ ያልተራራቁ ናቸውና አንዳቸው ይበቁ ነበር። ይልቁንም በፐ የሚነገር ቃል በኢትዮጵያ ቋንቋ ምንም ያህል አይገኝም፤ ሳድሱም ከጥና ከኘ ጋራ አሳሳች ሁኖ ላንባቢ ያስቸግራል፤ ራብዑና ሳብዑም እጅግ ያልተለያዩ ናቸውና መሻሻል የሚያስፈልገው ነው።ለኛ ለኢትዮጵያውያን ቅሉ ከጥንቱ ፊደላት የሌለ በንግግራችን ሁሉ ያለ አንድ ፊደል ያስፈልገናልና ባንዳቸው በታ ብናገባው ይሻል ነበር ። እሱም በአውሮጳ

ፊደል እንደ V ያለው ነው ። የሚፈለግበትም ቦታ አበበ፡ ከበበ፡ ጠበበ ፡ እንደዚህም የመሰለ ብዙ ንባብ ስናነብ በመድረሻ ያለው ያንደኛው በ ድምፁ ሌላ ሊሆን ያስፈልጋል።

ደግሞም በመጨረሻ ያሉት አንዳንድ ፊዳላት (ጐ ቈ ኰ ጐ)ከላይኛው እንደ ተነገረው ሳዕዝ፡ሣልስ፡ራብዕ፡ኃምስ፡ሳድስ፡ የሚያደርግ ከመደበኞቹ ፊደላት አንዳንድ ፊደል እየተጨመረባቸው ቢነበቡ የተመቹ ናቸውና የወረቀት መፍጃ ናቸው እንጂ ቢቀሩም አያስጐዱም።ሁወ ቁወ ኩወ ጉወ እየሆኑ ሊነበቡ ይቻላል። ግዕዛቸውና ሳድሳቸውም በቃል መድረሻ ሲሆኑ ጥቂት ያስቸግራል እንጂ ግዕዙ ሳብዕ፡ሳድሱ ከዕብ፡ለመሆን ይችልነበር ። ምሳሌ ሆለቈ ለማለት ሆለቆ፡ሁልቍ ለማለት ሁልቁ፡ እንደዚህም በመሰለ ሁሉ ላይ አይመቹም፡ ይህነንም ቢያሻሽሉት አጭር ነገር ነው።

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሆይ አሁን እኛ ይህ ይበጃል ፤ ይህ ይከፋል ማለታችን እንደ ታየን መጠን ነው እንጂ እኛ ባልነው ይሁን፡ እኛ በጻፍነው ይወሰን ማለት አይደለም ። ነገር ግን ከዚህ ቀደም አሳታውሰናችሁ የሚበቃ መልስ ስለ አላገኘን እንደ ገና ማስታወሳችን ነው ። ስለዚህም ችላ ባለማለት ያዲሱን ዘመን ሥልጣኔ ከተማሩ ሰዎች ጋራ እየተመካከራችሁ። ለዛሬው ጊዜ ለሥራ እንደሚመች አድርጋችሁ፡ ከበዛው ቀንሳችሁ፡ለሌለው ዐድላችሁ፡ የማያስፈልገውን ጠልታችሁ፡ ደኅናደኅናውን መርጣችሁ፡ እንደ አባቶቻችሁ አሻሽላችሁ ፡ አደላድላችሁ፡ አሳምራችሁ፡ ብትሰጡን እኛም በጊዜያችን ደስብሎን ስንሠራበት የቈየን እንደ ሆነ በየጊዜው ምስጋናችሁን እናጓድልም። ኋላም ስማችሁ፡ለልጅ ልጅ መታሰቢያ ሁኖ ይኖራል።

ማሻሻልም ከጥንት ሲያያዝ የመጣ መልካም ሥርዓት ነው እንጂ የሚነቀፍ አይደለም።ይኸውና ጥንት አዳም ሲፈጠር ከነበረው ጀምረን እስከ ዛሬው፡ ዘመናችን ሥራን ሁሉ ብንመለከተው በየጊዜውና በየዘመኑ እንደ ተሻሻለ በመጻሕፍት እናነባለን ። ይልቁንም ባገራችን ብኢትዮጵያ በየጊዜው መሻሻል እንዳለ እናውቃለን ። ከብዙውም አንዱ ጥንት የነበረው የኢትዮጵያ የድጓና የጾመ ድጓ ዜማ ተንቆ፡ በጐንደር አውራጃ ቤተ ልሔም በሚባል አገር አዲስ ዜማ ወጥቶ ሰው ሁሉ ወደዚያው እየሔደ አዲሱን ዜማ የሚማር ሁንዋል። ከዚሁም አገር ሔዶ ድጓና ጾመ ድጓ ካልተማረ ዜማ ያውቃል አይባልም።ስለዚህም የኢትዮጵያ ሊቃውንትና መምህራን ሆይ ሕግ የሠሩ አባቶቻችሁ ከኛ የቀረውን እናንተው አይታችሁ እንደጊዜው አሻሽሉ ብለው ፈቅደውላችኋልና እንኳን ይኸን ቀላሉን ሌላም የቸገረ ነገር ሲገኝ እንዲሁ በብርሃንና ሰላም እያስታወስናችሁ ችግራችንን ታሻሽሉልናላችሁ ስንል በጅምር የቈየውን ሐሳባችንን እንደገና ደግመን እያስታወስን ተስፋችሁን እንጠብቃለን ። አ ተ መ።

የ፱፻፴፮ ገጽ ተከታይ። የኢኮኖሚያ ፖለቲክ።

፫ኛ፡ ኮኦፔራቲቭ፡ የኮንሰሞ የሚባሉ የጨራሾቹ የአንድነት ማኅበር ከሚያፈሩት ከኢንዱስተሪ (ፋብሪካ) ነጋዴን ለማብረር በገዛ ራሳቸው በቀጥታ የሚገዙ ናቸው ። እኒህ የጨራሾቹን (የተመጋቢዎችና ለባሺዎች) ማኅበረተኝነት፡ ይልቁንም በወታደሮችና በባቡር ነጂ ፡ በመንግሥት ሠራተኞችም በጣም የገነነ ነው ። ማለት እነሱ ባቆሙት ሱቄታ በቀጥታ በርካሽ ዋጋ ከኢንዱስትሪ በብዙ (በጅምላ) የሚገዙ ስለ ሆኑ፡ ነጋዴው ሊያተርፍባቸው የነበረ መክፈሉ ይቀርላቸዋልና ለቤታቸው ዕቃና ምግብ ፡ ለሰውነታቸው ልብስና ፡ለቤታቸው መሣርያና ጌጥ፡ በሆቴላቸው ጨዋታና መጠጥ፡ ቢፈልጉም ዋጋው በጣም ርካሽ ይሆንላቸዋል ። ስለዚህ ከሁሉ በፊት እንደዚሁ የመሰሉ ማኅበሮች እንኳ በኢትዮጵያ ቢቆም ለኢትዮጵያ ሠራተኞች እጅግ ጥቅም ነበር።ከአሁን በፊት እንኳ በድሬ ዳዋና በአዋሽ በአዲስ አበባም ትንሽ የሚመሳስል፡ለስሙ ሆቴል መሳይ ቁሞ ፡ ከአምስት ዓመት በፊት አይቸው ነበር ። ግን እንደሚገባው ስላልተከናወነና በሙላ ኢትዮጵያም በጣም እየተዘረጋና እያደገ፡እየገፋና እየሠለጠነ፡እየበለጠገና እየገነነ፡ ስላልሄደ በጣም ያሳዝናል ። ከሁሉ በጣም የሚገርምና የሚያስለቅስ ደግሞ ገንዘባቸውን አዋጥተው ያቆሙት ማኅበረተኞቹ ሳይቀሩ ትተውት በሌላ የባዕድ ሆቴል፡ ሲበሉና ሲጠጡ፡ ሲጫወቱም ሲያይዋቸው ነው ። ይህ ጭራሽ ትንሽ አንጐል በማጣት ነው ለማለት ይደፈራል ። ግን የአገር ፍቅር የሚባል በሽታ ገፋ ስላደረገን ነው እንጂ የሺንዳን ነገር ስንነጋገር ቦታው ከዚህ ስላይደለ እንደመተው አድርገን ወደ አሳባችን መቀጠል እንመለስ።

(፴፩) የኢምፕሬዝ ተከታታይዎች ።

የኢምፕሬዝ ቍጥር ፣ ልዩ ልዩ የሆኑ የኢንዱስትሪ ዓይነቶች እንደሚከተለው ናቸው ። ፩ኛ፡ ኢንዱስትሪዬ ኤስትራቲቦ የሚባሉ ፡ ማደን ዓሣ ማጥመድ ፡ ሚኒራል ማውጣት ፡ ዱር መመንጠር እነሱንም የመሰሉ ሁሉ ናቸው።ስለ ሆነ ግን በዛሬ ዘመን ሳይተኩበት አንዲት ዛፍ ብትሆን እንኳ እንዳይቈርጡ በሠለጠኑ አገሮች በሕግ በጥብቅ ክልክል ነው ። አንባቢ ስለ ምን ቢል የዛፍን ጥቅም ጉልቍና ወሰን የሌለው ስለሆነ ነው። ዛፍ ውኃን ስቦ ያዘንማል፡ መሬት እንዳይሰነጠቅ አጥብቆ ይይዛል፡ቍጥርና ስፍር የሌላቸው ትሎች የእህልን ዘርና አትክልትን የሚያጠፉ የሆኑ ጠላቶቻችን የሚባሉ የብዙ ወፎች ማሳረፍያና መኖርያ፡ለቤትም ዕቃና መሣርያ፡ ለምግባችን ማብሰያ ይሆናል።ቀን ቀንም ለጤናችን የማይስማማ መጥፎውን አየር ይዞ የሚስማማንን ኦሲጂኖ የሚባለውን መልካም አየር ያመጣልናል።

፪ኛ፡ ኢንዱስትሪ ሩራሊ የሚባል የገጠር እርሻ፡የከብትና ዓሣ ማሳደግ ፡ የሐር ትልና ንብ አበዛዝ ፡ የቅቤና የአይብ ፋብሪካ ፡ የዘይትና የወይን ጠጅን አጠራር የመሰለ ሁሉ ነው።

፫ኛ፡ኢንዱስትርዬ ማኒፋትሪቼ የሚባሉ፡እነዚያ ያልተሠራ ማተሪዬ ፕሬማ እንደነ ጥጥና ጠጉር ሁሉ ፣ ለሰው የሚያስፈልጓ የሆነውን ነገር የሚለውጡ ናቸው ። (አስረጅ) መፍተልና ሸማኔነት፡ የብረት ሥራና የኪሚኬ ኢንዱስትሪ፣ እሱንም የሚመስል ሁሉ ነው ።

ሚከኤል ተሰማ ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል።

የውጭ አገር ወሬ፤ በኢየሩሳሌምና በውራጅዋ የሆነ አደጋ

ባለፈው ሰሙን እስላሞችና አይሁዶች ተጣልተው ተጋድለው ነሐሴ ፯ ቀን ጀምሮ ከተማው ኢየሩሳሌም አገሩም ሁሉ ታውኮ ሰነበተ ።

እስላሞች አድማ ሲመክሩ ሰንብተው ባ፲፯ ነሐሴ ዓርብ ቀን እንደ ልማዳቸው ለመስገድ የመጡ መስለው፥ ከየመንደሩ ከየገጠሩ ሁሉ ወደከተማ ተሰብስበው፥ ከቤተ መቅደሱ ውሥጥ ገብተው፥ የሰግደታቸው ሰዓት ሳይደርስ፥ በ፯ሰዓት ተሩብ ከውሥጠኛው ከተማ ወጥተው፥ በውጭው ከተማ በመንገድ ያገኙትን አይሁድ በጩቤ እየወጉ፥ በዱላም እየመቱ፥ እስከ ፲፪ሰዓት ድረስ ሲጋደሉ አመሹ ።

ቀኑም ዓርብ ባይሆን ብዙ ሰው ይፈጅ ነበር ። የከተማው ዘበኛ ቁጥሩ ስላነሰ፥ የሚበልጠውም እስላም ስለሆነ፥ ከዘበኛውም በቀር ባገሩ ወታደር ባለመኖሩ ሹማምንቶቹ ጠቡን ሊያበርዱት አልቻሉም ።

ሰው ቢቸግራቸው የመንግሥት ሠራተኛ የሆነ ሰው አገር ለማየት የመጡ እንግሊዞች ብረት እየሰጡ የከተማውን ጥበቃ አግዙን ብለው ተሳልፈው አደሩ ይባላል።

በማግሥቱ በየገጠሩና በየመንደሩ፥ በቀሩት ከተሞችም በኬብሮን ፥ በያፋ ፥ በሐይፋ ፥ በተባሉ ከተሞች ሲጋደሉ ዋሉ። መሰንበቻቸውን እስከ ፯ቀን አላቋረጡም ።

ባ፰ኛ ቀኑ ወታደር ከምስር፥ መርከብም ከማልጣም አስመጥተው አረጉት ። ከዚያ በኋላ እየተሻለ ሔደ።የሞተውና የቈሰለው ግን፥ የሁለቱም ወገን እኩል ሳይሆን አይቀርም ይባላል።

የሞቱት አይሁድ ፻፳፫፥ የቆሰሉት ፻፹፫ ተብለዋል።ከእስላሞች የሞቱት ፹፫ የቆሰሉት ፻፳፪ ተብለዋል። ይኸውም በከተማ ብቻ አይደለም የባላገሩንም ጭምር ነው ። እምቢ ያለውን በሉት ስለተባለ እምቢ ያለውም እስላም ስለሆነ ዘበኛና አኤሮፕላን የገደለው ጉዳቱ የስላም ይበዛል ።

ከብትና የተቃጠለው፥ የተዘረፈው ቤት የአይሁድ ይበልጣል ይባላል፥በዚሁ ጠብ ውሥጥ ፲፰ የሚሆኑ ክርስቲያኖቹ ሞቱ ይባል።

ጠቡም የተነሣበት ምክንያት አይሁድ ከቤተ መቅደስ በውጭ በስተምዕራቡ ሁለ ጊዜ ከዝያ እየሔዱ የሚጸልዩበትና የሚያለቅሱበት በተለየ ቦታ አላቸው። ስሙም የመላቀሻ ቦታ ወይም ዓምብ ይባላል ። በየዓመቱ በነሐሴ ወር በ፯ቀን ጀምሮ እስከ ፲ኛው ቀን በጾም፥በጸሎት፥ በልቅሶ፥ይዘክሩታል። የዚህም ምክንያት በዘመነ ብሉይ ፊተኛው ቤተ መቅደስ በናቡከደነጸር የባቢሎን ንጉሥ ከተማዋን ያፈረሰበት ቤተ መቅደስን ያቀጠለበት በዚሁ ወርና ቀን ነበር ። ፪ነገሥት ፳፭ ፤ ፰ በዘመነ ሐዲስም ጥጦስ የሮም ንጉሥ ሁለተኛውን ቤተ መቅደስ ያፈረሰበት ያቃጠለበት ወሩና ቀኑ አንድ ነውና ስለዚህ አምልኳችን የቀረበት ክብራችን የተቃጠለበት መንግሥታችን ሕዝባችን የጠፋበት ወርና ቀን ብለው ይዘክሩታል ። በዚሁ ሰበብ ዘንድሮ ከቀድሞ በረከት ብለው ቢመጡ በዝተው የመጡ ቦታችንን ሊቀሙን ነው ብለው አበረሩዋቸው። እቃቸውንም ጠረጴዛ መቅረዝ የመሰለ ሰባበሩባቸው።መጻሕፍቶቻቸውንም አቃጠሉባቸው ።

በዚሁ ሰበብ ፰ቀን ሙሉ ዶልተው ሰንብተው ከልፈጀናቸው አናርፍም ሲሉ ከመጋደል ደረሱ ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፮ ብር
ኈሐ ጽባሕ	፮ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፰ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፰ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፰ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፰ መሐ
የማልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፰ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፰ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፰ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ማጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የበገና ግጥም	፪ መሐ

KONIAK
COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጠ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፪ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተሶስት ሩብ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጇ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጇ	፳፪ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጇ	፻፸፪ ብር
ባለሰይጣን		፻፷፪ ብር
ባለ ድመ ።		፻፵፫
ባለእህያ ።		፻፵
ባለሳቢ ግመል ።		፻፳
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፳፬
" " ጃፖን		፻፸፫ ብር
ሱካር	ጁኒያ	፳፬ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፳ሳቲንም
ባአንድ ብር	፳ ሊሬ ከ ፶፬ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፺ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ ፵	

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የቸረተኝ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።

አ በ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበሳል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው።

ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅበኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባቱሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እጅግ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቀደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ባል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የድማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።



በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕራንት ባግዳሣሪያን ።

ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋው ግን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
5me ANNÉE №41

ሐሙስ መስከረም ፴ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 10 OCTOBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres



ልዕልት መነን ።



ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ።

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ዘውድ መታሰቢያ በዓል።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት መስከረም ፳፯ ቀን የኢትዮጵያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደ ራሴ ንጉሥ ተብለው ዘውድ ከጫኑ አንድ ዓመቱ ሞላ ። ይህም ቀን ከኢትዮጵያ የሥልጣኔ ደረጆች አንዱ ነው ። ይህም ሊታወቅ ከላይ በተነገረው ዓመተ ምሕረትና ቀን የኢትዮጵያ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደ ራሴ ንጉሥ ከተባሉ ወዲህ የሠሩዋቸው ሥራዎች ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

አንደኛ፥ በነገሡ በሁለተኛው ወር ጥቅምት ፲፫ ቀን ስለ ፖስትና ስለ ትምህርት የወጣውን አዋጅ በብርሃንና ሰላም አራተኛ ዓመት፥ ፵፫ኛ ቁጥር መመልከት ነው ።

ሁለተኛ፥ በሦስተኛው ወር ኅዳር ፳ ቀን ስለ ሕዝብ አኗንዋር ጥቅም የተሠራውን ደምብና የወጣውን አዋጅ በዚሁ ዓመት ብርሃንና ሰላም ፵፰ኛ ቁጥር መመልከት ነው ።

ሦስተኛ፥ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ተደርጎ የማያውቀውን ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጳጳሳት ተሾሙልን ።

አራተኛ፥ በውጭ አገር የሚኖሩት ዜጎቻችን ጉዳት እንዳያገኛቸው በየመንግሥታቱ አገር የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ቁሞ ዜጎቻችንን የሚጠብቁ ሚኒስትሮችና ቄንስሎች ተሾሙ ። የሰማይ ባቡሮችም በአየራችን ተንዣበቡ ። ይህም በአዋጅ የሆነውን፥ ሕዝብ ያወቀውን መጻፋችን ነው እንጂ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በየተማሪ ቤቱና በየሆስፒታሉ፥ በየሥራውም ሁሉ ለመጐብኘት በገቡ ጊዜ ሕዝባቸው በትምህርትም፥ በሥራም እንዲሠለጥንና አገራቸው ኢትዮጵያም እንድትለማ እንደ ሰበከት እያደረጉ የሚናገሯቸው የእውቀት ቃሎች ብዙዎችና እጅግ መልካሞች ናቸው ። ወደ ፊትም ሙሉ ሐሳባቸውና ፈቃዳቸው ኢትዮጵያ እንድትሰፋና እንድትለማ ፥ ሕዝብዋም እንዲበለጥግና በእውቀት እንዲሠለጥን ነው ። ይህም፥ በሚናገሯቸው ቃሎችና ባስጀመሯቸው ሥራዎች ይታወቃል ። ስለዚህ ለዚህ ሁሉ እውቀትና ሥልጣኔ መጀመሪያ የሆነውን የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ዘውድ ሁሉ ጊዜ ልናስበው እንጂ ልንረሳው አይገባም። ይልቁንም እንደ ተወለድንበት ቀን አድርገን በመት በመቱ እንድናከብረውና እንድናስበው ይገባል ። ሰው፥ ከሁሉ አብልጦ የተወለደበትን ቀን ማክበሩ ከጨለማ ወደ ብርሃን የወጣበት ቀን ስለ ሆነ ነው ። ይህም ዘውድ የብርሃን መሪያችን መሆኑን ተረድተን ሁሉጊዜ ልናስበው ግድ የሚያስፈልገንነው ።

ደግሞም ቅዱስ ጳውሎስ ለሁሉ የሚገባውን አድርጉለት እንዳለ አክብሮትና ምስጋና የሚገባቸውን የልዕልት መነን ምስጋና ችላ ማለት አይገባንም ። ሮሜ ፲፫ ፯። አንዳንዱ ሰው ባልንጀራው መልካም ሐሳብ አስቦ እንዲረዳው ያመከረው እንደ ሆነ ባልሆነ መልስ ያሰንፈዋል ፥ ዕንቅፋት ይሆንዋል ። ልዕልት መነን ግን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መልካም ሐሳብ ባሰቡ ጊዜ መልካሙ ሐሳባቸውን የሚያበረታ ምክር በማቅረብ ደስ ያሰኟቸዋል። ይህም ይገለጽ ዘንድ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ልጃቸውን ልዕልት ፀሐይ ተፈሪን ወደ አውሮጳ ለመስደድ ባሰቡ ጊዜ ልዕልት መነን ስለ ልጃቸው ወደ ውጭ አገር መሔድ እንደ ሌሎች ሴቶች አላዘኑም አልተከዙም ። ነገር ግን ልጃቸውን ልዕልት ፀሐይ ተፈሪን በደስታ በመሸኘታቸው እውቀትን ለሚፈልጉ ሁሉ መልካም አርአያ ሆኑ ። ሁለተኛ ፥ ከማርቆስ ቤተክርስቲያን አጠገብ ወደ መድኃኔ ዓለም መሔጃ ባለው ቦታቸው ላይ የሴቶች ልጆች ተማሪ ቤት አሠርተዋል። ስለዚህም የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ደግነትና መልካም ሥራ ስንጽፍ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሥራ ሁሉ እረዳትና አጋዥ የሆንዋቸውን የልዕልት መነንን መልካም ሥራ ማስታወስ ግድ ይሆንብናል ።

ይህች ለኢትዮጵያ ተስፋ የሆነው ዘውድ በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ራስ ላይ ቁብ ብሎ ያደረበት ቀን የተባረከችና የተቀደሰች ትሁን። ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ፥ ለልዕልት መነንና ለልጆቻቸውም ፥ ለኢትጵያም ሕዝብ ሰላምና ጤና ይሁን ፥ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ፥ አሜን ።

የመንግሥት ማስታወቂያ ።

የውጭ አገር ሰዎች ለንግድ ወይም ለሌላ ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ ስለ መግባታቸው ነገር ፥ በታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት በወጣው የመንግሥት ማስታወቂያ ላይ የሚጨመር ደንብ ።

መጀመሪ ።

ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስላ ከቆመበት አገር የሚነሡት ፥ የይለፍ ወረቀታቸውን በቆንስላው ቤት እያስፈረሙ እንዲመጡና የኢትዮጵያ ቆንስላ ከሌለበት አገር የሚነሡት የውጭ አገር ሰዎች ግን የኢትዮጵያ ቆንስላ ካለበት በኢትዮጵያ ወሰንተኛ አገር በደረሱ ጊዜ የይለፍ ወረቀታቸውን በዚያ ለሚገኘው ቆንስላ ወይም የኢትዮጵያ ቆንስላ የሌለበት አገር የሆነ እንደሆነ ሥልጣን ላላቸው ለኢትዮጵያ ወሰን ጠባቂዎች አቅርበው ቢዛ እያስደረጉ እንዲመጡ በታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት በወጣው በመንግሥት ማስታወቂያ ላይ የተጻፈው ቃል መሠረት ተደርጓል ።

ሁለተኛ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስላ ወይም በወሰን ያሉ የኢትዮጵያ ወሰን ጠባቂዎች ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት የሚፈልጉትን የውጭ አገር ሰዎች አኳኋናቸውን መርምረው ለመመለሻ ከሣራ ለአንድ ሰው አንድ መቶ ብር እንዲያሲዙ ለመጠየቅ ይችላሉ ። ነገር ግን ይህ የመመለሻውን ከሣራ ያስያዘ የውጭ አገር ሰው አዲስ አበባ ከደረሰ በኋላ ነገሩ ተመርምሮ በኢትዮጵያ ለመኖር የሚፈቀድለት የሆነ እንደሆነ ያስያዘው ገንዘብ ይመለስለታል ።

ሦስተኛ ።

ለንግድ ወይም ለሌላ ጉዳይ በየጊዜው በአዲስ አበባና በጅቡቲ መካከል በምድር ባቡር ለመመላለስ የሚያስፈልጋቸው የውጭ አገር ሰዎች አዲስ አበባ ካለው ቆንስላቸው የሚያመላልስ ጉዳይ እንዳላቸው የሚመሰክር ወረቀት ወደ

ኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እየመጡ አንድ አንድ ብር እየከፈሉ ለአንድ አንድ ዓመት የሚረጋ የተለየ ወረቀት ይቀበላሉ ።

ይህም የተለየ ወረቀት የሚረጋበት ጊዜ ሲፈጸም ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እየመጡ ማሳደስ አለባቸው ።

ይህ ተጨማሪ ደንብ ከጥቅምት ፩ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

AVIS OFFICIEL

DISPOSITIONS COMPLEMENTAIRES A L'AVIS OFFICIEL PUBLIE EN DATE DU 1ER TAHSAS 1921.

CONCERNANT L'ENTRÉE SU TERRITOIRE ETHIOPIEN DES PERSONNES ETRANGÈRES DANS UN BUT COMMERCIAL OU AUTRE.

Art. I.

En conformité de l'Avis Officiel publié en date du 1er Tahsas 1921, toute personne étrangère désireuse de pénétrer en territoire Ethiopien est tenue de s'adresser préalablement au Consulat d'Ethiopie établi dans le pays de départ pour y faire viser son passeport. Dans le cas où il n'existerait pas de Consulat Ethiopien dans le sus-dit pays elle devra s'adresser pour obtenir le visa au Consulat Ethiopien se trouvant en pays limitrophe ou bien dans le cas où il n'existerait pas de Consulat Ethiopien aux Autorités du Poste frontière Ethiopien.

Art. 2.

Le Consulat ou les autorités du Poste frontière Ethiopien peuvent, s'ils le jugent nécessaire exiger après enquête, un dépôt individuel de cent thalers des personnes Etrangères désireuses de pénétrer en territoire Ethiopien. Ce dépôt étant destiné en cas de besoin aux frais de rapatriement des dites personnes. Toutefois, dépôt qu'elles auraient ainsi effectué pourra leur être remboursé à leur arrivée à Addis-Abeba s'il était décidé après enquête de leur accorder un permis de résidence et de séjour en Ethiopie.

Art. 3.

Toute personne étrangère dans l'obligation, pour affaires commerciales ou autres, de se déplacer fréquemment par Chemin de fer entre Addis-Abeba et Djibouti, devra présenter au Ministère des affaires Etrangères une pièce justificative émanant de son Conculat. Il lui sera accordé un certificat spécial valable pour une année, contre paiement d'un thalers et renouvelable à l'expiration de ce délai.

Les dispositions du présent Avis entreront en vigueur à partir du 1er Tekkemt 1922. (11 octobre 1929.)

Fait à Addis-Abeba le 25 Meskerem 1922 5 Octobre 1929)

ስለ አረቄ ንግድ ።

በዚህ ዓለም ላይ ያለ ሕዝብ ሁሉ የሀገሩ መንግሥት የሚከበርበትን፥ ወገኑና ተወላጁ የሚጠቀምበትን እያሰበና እየተመለከተ ይሠራል እንጂ መንግሥቱ የሚጐዳበትን፥ሕዝብ የሚደኸይበትን ነገር ያገሩ ተወላጅ አይቶና ተመልክቶ ዝም ሊል፥ ሊታገስ አይችልምና እኔም አንዳንዶች ሰዎች መንግሥት ያቆመውን ሕግና ደንብ በሥውር እያፈረሱ ሲሠሩና ሲገበያዩ እያየሁ የመንግሥትን ገቢ ለማስቀረትና የራሳቸውን ጥቅም ለማበርከት መሆኑን አይቼ ስለ ተመለከትሁ ያለኀፍረት በድፍረት ያለሐሰት በውነት ነገሩን እገልጸዋለሁ ።

ከዚህ ቀደም ያረቄ ነጋዴዎች ሁሉ የበቃ ቀረጥ ሳይከፍሉና መጠጡም ሳይመረመር እንደልባቸው ይገበያዩ ነበር ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪም ይኸንን ያረቄ ነጋዴዎች የሚነግዱበትን አልኮል ያለበት መጠጥ ሁሉ ለሕዝብ ጤና የሚሆነውን እየተመረመረ፥ በዚያውም ላይ የመንግሥት ምልክት ባንደላት የሚባል እየተለጠፈ እንዲሸጥና ገዢውም እንዲገዛ በለው የተተካከለ ደንብ አውጥተውልን ገዢዎቹና ሻጮቹም ብዙን ጊዜ የዚሁን የቆመውን ደንብና ሕግ ሲፈጽሙና ሲሠሩ ይታዩ ነበር ።

አሁን ከጥቂት ጊዜ ወዲህ እንዲህ አንዳንዶቹ ነጋዴዎች እቤታቸው እየተከፈተ ከሚጠጣው ጠርሙስ ላይ ቀስ እያሉ እየላጡ ባንደሌቱን አደኀናው ጠርሙስ ላይ ሲለጥፉ እናያለን ። ደግሞ አንዳንዶች ሰዎችም ሊጠጡ ገዝተው የወሰዱትን ጠርሙስ ጠርሙሱ ሲከፈት ቀስ እያሉ እየላጡ ላረቄ ሻጮዎች፥ እየወሰዱላቸው ፩፩ዱን ባንደሌት ከመኖፖል በሚገዛበት በገሚስ ዋጋ እየገዙ፥ ደግሞ እየለጠፉ ሲሸጡ እናያለን መንግሥት ግን ይኸን ባንደሌት ፩ዱን ላንድ ጠርሙስ ላንድ ጊዜ ብቻ ያቆመውን እነሱ ሁለት ጊዜ ስለ ሚያደርጉት ይኸንን እንደዚህ ያለውን ሥራ በጥንካሬ እንዲያስጠብቁ ሥልጣን ለተሰጣቸው ሹሞች አሳስባለሁ ፤ ይኸንኑም እኳን ደፍሬ ለማመልከት ያሳሰበኝ ምንም ቢሆን ጥቅምና ጉዳቱ የመንግሥታችን ስለሆነ ዝም ብዬ ለመመልከት ስላልቻልሁ ነው እንጂ ሥራዬ ሆኖ አይደለም ።

በቀለ ዘለቀ

የ፫፻፳፰ ገጽ ተከታይ የኢኮኖሚያ ቦለቲን ።

፩ኛ ፥ ኢምፕሬዚ ኮሜርቼያሊ የሚባሉ የውጭ ንግድ ሥራ ፥ እንደነ ኤስፖርታቶሬና ኢምፖርታቶሬ የሚባሉ ወደ ውጭ አገር የሚልኩ ወይም ከውጭ አገር የሚያስመጡ ስፔኩላቶሬ የሚባሉ ናቸው ። በፊት ገንዘብን ሳይከፍሉ በብዙው-

ወዲያው ገዝተው ወዲያው የሚሸጡ፡ ሌሎች ደግሞ ግሮሲስቲ የሚባሉ በብዙ የሚሸጡ ኮሚሲዮናሪ (ሚባሉ በሌላ ሰው ሒሳብ የሚገዙና የሚሸጡ ናቸው ። ማዳያቶሬ የሚባሉ ገጋርና ሸያጩን የሚያሰማሙ (ደላሎች) ናቸው ። ሜርቻዮሊ የሚባሉ ትንሽ ሸቀጥ የሚለዋውጡና የሚሸጡ ፤ እንዲሁ የመሰለ ሌላ ትንሽ ሥራም የሚሠሩ እየሆኑ ይለያያሉ ።

፭ኛ- ኢምፕሬዛ ዲ ትራስፖርቶ የሚባሉ ፤ በባቡር ይሁን በመርከብ ፤ በኤውሮፕላን ይሁን ፤ በካሚኦን፡በጋሪ ይሁን በከብት ክራይ የሚያመላልሱ ከሙኒካሲዮን መልእክት የሚያስተላልፉ እንደነ ቴሌግራፍና ቴሌፎን የመሰሉ ሁሉ ናቸው ።

፮ኛ፡ ኢምፕሬዛ ዴል ክሬዲቶ የሚባሉ ፤ እንደነ አሲኩራዚዮኔ የሕይወት ማረገጥያ ቤት ፤ እንደነ ካሴ ዲሬ ፓርጢዮ የመቈጠብ ቤት ፤ እንደነ ባንክ የአደራ ቤት የመሰሉ ሁሉ ናቸው ።

ባጭሩ የኢምፕሬዛና አዚንዳ ደረጃ ተራ እንዲህ ነው። (ሀ)እንያ የደያንጊያ ከሰል፡ የብረት ዘር ሁሉ፡ እብነ በረድ፡ የከበሩ ደንጊያዎች ከመሬት ውሥጥ እየቈፈሩ የሚያወጡ፤እኒህ ኢምፕሬዛዎች ፍጥረትን እንዲያው እንደጸጋ የምትሰጥ ገንዘብ ለማድረግ የሚጥሩ ናቸው ።

(ለ) ደረጃ፡ኢምፕሬዛዎች እኒያ አራሾችና አረኞች ናቸው።

(መ) ኢምፕሬዛዎች ፤ በጣም የተከናወኑች ከማቴሪዮ ፕሪሜ የፍጥረት ሀብትን ለሰው ደስ የሚያሰኘውን የምትሠራ ኢንዱስትሪ ነች።

በመጨረሻ ልዩ ልዩ የሆኑ የንግድ ኢምፕሬዛ ሸያጮችና ገዢዎች፡ አሰማሚዎች፡ መልእክተኞች፡አበዳሪዎችና ክራይ አብጫኝዎች በድንገት እንዳይከስሩ፡ወይም በመንገድም እቃቸው እንዳይጠፉ ዋሶችና አላፊዎች እየሆኑ ይለያያሉ ።

ዋናው የነጋዴ ሥራው ያነን የጨራሾቹን የሕዝቡን ፍላጎት አውቆ በሚፈለግበት በጊዜውና በቅርብ ስፍራ አምጥቶ ለሕዝብ ፍላጋውን ደስ ማሰኘት ነውና ከነዚሁ ኢምፕሬዛ ከፋብሪካው በብዙ እየገዙ ለታናናሾቹ አዚንዳዎች የሚሸጡ ታናናሾች አዚንዳዎች ደግሞ ለጨራሾች የሚሸጡ እየሆኑ ይለያሉ ።

አሁን የገለጥነው አሳብ የኢምጥሬዛ ክፍል ብቻ ነው ። ግን የሚሆነውና የሚሠራው በጣም ልዩና የተከናወነ ነው ። ከሁሉ በፊት ከኢምጥሬዛና ኢምጥሬዛ ብዙ ነፃነት አላቸው ። ዋኖቹ ኢንዱስትሪዎች ደግሞ በዙርያቸው ብዙ ተናናሾች ኢንዱስትሪዎች ያበቅላሉ ። አስረጅ) በአገራችን ኢትዮጵያ ፤ አንድ ሁለት ማተምያ ቤት ቈመዋል ። ግን አንድ መጽሐፍ ብቻ ለማሳተም ብንፈልግ ፤ ብዙ ተናናሾች ክፍል ኢንዱስትሪና ሠራተኞች ያስፈልጉናል።(ምሳሌ) ፎንዳቶሬ የሚባል ፊደል የሚቀርጥ ፤ ሚካኒቺ የሚባሉ የምታትም መኪና የሚሠሩ ፤ ክርቴሬ የሚባሉ ወረቀት የሚሠሩ ፤ ቀለም የምታነጥር ፋብሪካ፡ ውል የሚጨርስ አታሚው ወይም ዲሬክተሩ ፤ አውቶሬ የሚባል እስበ መጽሐፉን የሚጽፍ ፤ ኮምፓዚቶሪ የሚባሉ ፊደሉን የሚለቅሙ ፤ ክሬቶሬ የሚባል በመጀመር ታትሞ የሚወጣውን የተሳሳተው የሚያርም ፤ ቶርኬሊዬሬ የሚባል ወረቀትን የሚያትም ፤ ሌሎች ሰራተኞች ወረቀት የሚያጣፉ ፤ ሌሎች ሠራተኞች የሚጠርዙ ፤ ሊብራዮ የሚባል መጽሐፉን የሚሸጥ እየሆኑ ይለያሉ ። እዩት አንዲት መጽሐፍ ለማሳተም ብቻ የተክኒካው ሥራው በስንትና ስንት ክፍል እንደተከፋፈለ ። የኢንዱስትሪ የተክኒካው ሥራው ኁልቍና ስፍር የለውም የሚባል ስለዚህ ነው ። ሚካኤል ተሰማ ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ዲሚትሪ ናዚራአውሎ በ፫፻፺፪ ቁጥር የተነሣው የቦታዬ ካርታ ጠፍቶብኛል ብለው ለማዘጋጃ ቤት አስታውቀው በቀድሞው ሥዕል ልክ ሌላ ካርታ የሚቀበሉ ስለሆነ ምናልባት ይህኑ በ፫፻፺፪ ቁጥር የተነሣውን የቦታ ካርታ በብድር ወይም በማያዣ የያዘ ሰው እንዳለ ከ፲፱፻፳፪ ዓ ም ከመስከረም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፪ ዓ ም ኅዳር ፴ ቀን ድረስ ወደ ማዘጋጃ ቤት እንዲአመጣ እናስታውቃለን። ነገር ግን ከዚህ ከተወሰነው ቀን አሳልፎ ቢያመጣ ይህ ካርታ ከምንም ሊቈጠርለት የማይችል መሆኑን እናስታውቃለን ። መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፳፪ዓም።

የማዘጋጃ ቤት ዋና ዲሬክተር

ማተሚያ ቤትን ስለመጐብኘት ።

መስከረም ፳፱ ቀን የክቡር ደጃዝማች አያሌው መላከተኛ ክቡር ፊታውራሪ ነጋሽ በግርማዊ ንጉሥ ማተሚያ ቤት ገብተው ማተሚያ ቤቱን አይተው ክቡር ደጃዝማች አያሌው እንዲገዙዋቸው የታዘዙትን መጻሕፍት ከየዓይነቱ ሁለት ሁለት ገዝተው ሔዱ ። ክቡር ደጃዝማች አያሌው በግዛታቸው አስተዳደርም የተመሰገኑ መሆናቸውን ማንም ሰው ያውቃል። በየጊዜው መንፈሳዊና ሥጋዊ እውቀትን የሚሰጡ መጻሕፍት መግዛታቸውም የሥልጣኔና የዕውቀት ወዳጅ መሆናቸውን ይመሰክራል ።

ማስታወቂያ

አንድ ትንሽ ሕፃን ወንድ ልጅ በመስከረም ወር በምድር ባቡር ተሳፍሮ ሲሔድ ሞጆ ከሚባለው ጣቢያ ሲደርስ እናትና አባቱን የሚአውቀውንም ሰው አጥቶ ሲለቀስ ዘበኞች አገኙት ስሙንም ብንጠይቀው ሙሉ ጌታ ነኝ አለ ። ዕድሜው በግምት ፬ዓመት ተኩል ይሆናል ።

ያባትና የናቱን ስም ብንጠይቀው ክራሱ ስም በቀር አስተሐክሎ ለመናገር የማይችል ስለሆነ ፤ ይህን የመሰለ ልጅ የጠፋበት ሰው ከልጅ ፍቅሬ ያየህ ይራድ ቤት አዲስ አበባ መጥቶ ይጠይቅ ። ፲፱፻፳፪ ዓ መ

ማስታወቂያ ።

የትምሕርትና የጥበብ ሚኒስቴር የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የክረምቱ እረፍት ጊዜ ስለ ተፈጸመ የ፲፱፻፳፪ ዓ ም ትምሕርት በጥቅምት ፩ ቀን መጀመሩን ለሕዝብ ያስታውቃል።



ስለ ክቡር ግራዝማች ዘገየ ዕረፍት

ክቡር ግራዝማች ዘገየ ቈለጭ በጨርጨር አውራጃ በዓሰበ ተፈሪ የግምጃ ቤት ሹም በመስከረም ፳፬ቀን አረፉ ።
ብርሃንና ሰላም ለባለቤታቸውና ለልጆቻቸው፥ለወንድሞቻቸው፥ ለዘመዶቻቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ስለ ክቡር ሚኒስትር እስትሬስማን ዕረፍት የጀርመንን መንግሥት ኀዘን ለመካፈል የሚከተለውን ቴሌግራም አሳልፈዋል ።

ቴሌግራም ።

ለሙሴ ሒንዴምቡርግ ።
የጀርመን መንግሥት ፕሬዚዳን ።
በርሊን ።

የመንግሥት አገልጋይ ክቡር ሙሴ እስትሬስማን ማረፋቸውን ስለሰማን እጅግ እያዘንን የጀርመን መንግሥት ኀዘን ተካፋይ መሆናችንን ለክቡርነትዎ እንገልጻለን። መስከረም ፳፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ም አዲስ አበባ

ንጉሥ ተፈሪ

የውጭ አገር ወሬ ።

ከኢጣሊያን ሌጋሲዮን የመጣ የመስከረም ፳፬ ቀን ራድዮ እንደሚያወራው ።

እስትሬስማን የጀርመን መንግሥት የውጭ ጕዳይ ሚኒስትር በድንገት ስለሞቱ በጣም ድንጋጤ ሁኑዋል ። ፕሬዚዳት ሒንዴምቡርግም የዕረፍት ጊዜያቸውን አቋርጠው ወደ በርሊን ከተማ ተመለሱ። በመንግሥት ኪሳራ እሑድ (መስከረም ፳፯ቀን) ትልቅ የክብር ውሎ ተደርጎላቸዋል ። ከያገሩ ሹማምንቶችና ከውጭ አገር መንግሥታት የኀዘን ተካፋይነት መልእክት ይደርሳል። የኢጣሊያ መላክተኛም በሙሶሊኒ ስም የእስትሬስማንን ባለቤት እግዚአብሔር ያጥናዎ ለማለት ሔደ ።

የፈረንሳዊ ጋዜጦች ስለ እስትሬስማን ሞት ኀዘናቸውን እየገለጡ ስለ ኤውሮጳ ሰላምና ስለ ፈረንሳዊና ጀርመን መስማማት የሠራውን ሥራ ያሳስባሉ ።

የመስከረም ፳፰ ቀን የዕለት ወሬ ።

ዋሽንግቶን ማክዶናልድ የእንግሊዝ ሚኒስትር በሆቤር ቢርጂና የተባለች መንደር ሰንብቶ ተመለሰ ወደ ራፕሬሰንታንትና ወደ ሴናት ቤት ደረሰና በረጅም ዕልልታ ተቀበሉት ። በዚያን ጊዜም ረጅም ንግግር አደረገ። በንግግሩ ውሥጥም በስታቲኡኒቲና በእንግሊዝ መካከል ያለውን መቀያየም ማስወገድ የሚያስገድድ መሆኑና እንደ ኬሎግ ውል የዓለምን ሰላም አጥብቆ ማጠንከር፥ ጦርነትንም ጨርሶ መተው እንደ ሚያስፈልግ ተናገረ ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጂዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ነህ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የማልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪ (ካሌንደር)	፲ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የበገና ግጥም	፪ መሐ

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S.E.& A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኰኛክ በፈረንሳይ አገር ኰኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር ተ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብርተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፺ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፬ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፸፰ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፫ ብር
ባለ ድመ ።		፻፵፰
ባለአህያ ።		፻፵
ባለሳቢ ግመል ።		፻፳
ባለ አንበሳ	አሜሪካ	፻፷
" "	ጃፖን	፻፸፰ብር
ሱካር	ጁኒያ	፷፰ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፷ሳንቲም
በአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፶፬ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የቀስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።

አ በ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ብአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

ድ ራ ሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቂ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

ፄሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ።

ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሽክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፓር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒክላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ፥ የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት በርሳሊን በርኔጣ። መዋታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።

ANTICA CASA FONDATA NEL 1857
Borsalino

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

የላስቲክ ማኅተም መሥሪያ ቤት ።

ሕራንት ባግዳሣሪያን ።

ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ራስ መኰንን ።
መንገድ ላይ ።

በላስቲክ (ላፒስ) ማናቸውም ዓይነትና በማናቸውም ቋንቋ ማኅተም እሠራለሁ ሥራውም የሚያምር ሆኖ ዋጋውግን ርካሽ ይሆናል ።

ሥራውን የምቀበለው ሁሉቀን ነው የማስረክበው ግን ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ።

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
5me ANNEE № 42

ሐሙስ ጥቅምት ፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 17 OCTOBRE 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ማስታወቂያ ።

ወደ ለጋር መሔጃ ላይ ያለውን ን ኤዱረያንን መደብር የንግድ እቃ ያለበትን በ፯ ኅዳር፣ ፲፱፻፳፪ ዓ ም የግብፅ ቆንስል በሐራጅ መሸጡን ለመግዛት ለሚፈቅድ ሕዝብ ያስታውቃል።

በቆንሲላ በኩል የተያዘውን የእቃውን ዝርዝር ለማወቅ የሚፈቅድ ሰው ከጧቱ በሦስት ሰዓት ዠምሮ እስከ ፯ ሰዓት ድረስ እግብፅ ቆንሲላ ሒዶ ለማየት የበዓል ቀን ካልሆነ ይችላል።

የክቡር ራስ ከበደ በኢጣልያን አገር አሰነባበት ።

በቍርጥማት እመም የተነሣ ብዙኅ ጊዜ ታመው ሲኖሩ በሽታው ኢያደር በርትቶ፣ ፍጹም ሽባ አድርጎ እንዲያ የኢትዮጵያ ጀግና እቤት ሊያስቀራቸው ነበር ። ለውድ አገራቸው ሕዝቡንና ከብታም ለድኃው ሌት ተቀን የሚያስቡት የኢትዮጵያውያን ዓይን የሆኑ ንጉሣችን የክቡር ራስ ከበደን በሽታ ጥናት አይተው ወደኤውሮፓ ሒደው እንዲታከሙ በገንዘባቸው ረድተው ወደኢጣልያ አገር በሚያዝያ ውሥጥ ሰደዷቸው ። ክቡር ራስም በቃሬዛ ከባቡር ወደ መርከብ ኢያለፉ ናፓሊ ከሚባለው የኢጣልያን ከተማ ከመርከብ ሲወርዱ ክቡር ሙሶሊኒ የኢትዮጵያ ትልቅ መኳንንት ከአገራቸው ሊታከሙ መምጣታቸውን ሰምተው ኖሮ የሚያስታምሟቸውን ሐኪም በፊት አዘው ነበርና እጅግ ማለፊያ ደግ ሰው የሆኑ ካስተሊኒ የሚባሉትን በናፓሊ ከተማ ባለው ታላቅ ሆስፒታል ለሚሠሩ ሐኪሞች መምህርና አለቃ ሊያስታምሙአቸው መታዘዛቸውን ገና ከመርከብ ሳወይርዱ እድንዎታለሁ ግድ የለም ሲሉ ተገናኝዋቸው።

ሕመማቸውንም ለማወቅ ደማቸውን መርምረው ከሁለት ወር ብኋላ ፈጽመው እንዲድኑ አስታወቋቸው ። ራስም ሐኪሙ የሚሉአቸውን ምክርና መድኃኒት ሁሉ በደስታ ሲቀበሉ ቈዩ። ሰው እየተሸከማቸው ይሔዱ የነበሩት በጃቀናቸው ጥቂት ጥቂት በምርኩዝ መሔድ ጀመሩ ። ልክ በሁለት ወራቸው ተቈልፎ የነበረው ጕልበታቸው ተዘርግቶ፣ በሽታው ጨርሶ እንደጠፋና ደማቸው እንደ ጠራ የሚያስታውቅ የምስክር ወረቀቱን ሰጥቶ፣ እንግዲህ ገመምተኛ ነዎት እንጂ በሽታ የለብዎትም፣ወዳገረዎም ለመመለስ ይችላሉ ሲል አስታወቃቸው ። ክቡር ራስም ወደሚወዷት አገራቸው ለመመለስ በጣም ይጣደፉ የነበሩት የማይድኑ ከመሰላቸው በሽታ እየዳኑና ሰውነታቸው እየበረታ መሔዱን አይተው ክረምቱ እስቲያልቅ ድረስ የበሽታቸውን ልክ እርግጡን ለመረዳት ሲታከሙ ለመሰንበት ቈረጡ።በዚህም ጊዜአቸው የሮምን ከተማ ለማየት ወደ ታልቋ ከተማ መጥተው ሰነበቱ ። የኢትዮጵያንና የኢጣልያን ወዳጅነት ለማበርታትና ለማስፋት የሚሠሩትን ክቡር ሙሶሊኒን ተገናኝተው ላደረጉላቸው ውለታ የሚገባ ምስጋናቸውን አቀረቡ። ከሮም ትልልቅ ሰዎች ሁሉ ተዋወቁ ። የጥንት የሮማውያንን ሥራ ሁሉ አደነቁ።ጥንት የኢትዮጵያ ካህናት የሠሩትን የቅዱስ እስጢፋኖስንም ገዳም ጐበኙ፣ በዚያ ያሉት የኢትዮጵያ ካህናቶች ቡን ጋበዙአቸው ። ያቡን ማስያስን ደብርና መቃብር አዩ።ካዲሱ እውቀትና ብልሐት እንዳውሮፕላን ልባቸውን የነካና ደስ ያሰኛቸው፣ያፈቀሩት ነገር የለም ። ከበሽታቸው ሳይድኑ እንኳ በአውሮፕላን ለመብረር ብዙ ያስቡ ነበር ።

ክብርት እኅታቸው ወይዘሮ ዘውዲቱ ከፈረንሳይ አገር ወንድማቸውን ለማየት ወደሮም መጡና ውድ ወንድማቸውን ድነው ቢያገኝዋቸው እጅግ ደስ እያላቸው አብረው ሰነበቱ ። የተወደዱ ወንድማቸውም ካዳናቸው ሐኪም ለማስተዋወቅ ከሮም ወደ ናፓሊ ከእኅታቸውና ያሥመራ አገረገዢ ከላከላቸው አነጋጋሪ ጋራ በአውሮፕላን ሁነው ወደናፓሊ ከብዙ መንገ-

ደኞች ጋር ሔዱ ። እጅግ ደስ በሚአሰኛቸው በትምህርትና በጥበብ በተሰናዳው አሞራ ላይ ወጥተው የሁለቱንቀን መንገድ ባንድ ሰዓት ሔዱት፤ወደሌላም ከተማ በአውሮፕላን ለመሔድ ያስቡ ነበር ። እንዲህ አየብቀው አውሮፕላንን እንደሚወዱ መስተማርና ጥበብ የሚፈልጉትን ያገራቸውን ልጆች መርዳት ቢወዱ ኖሮ የብረቱን አሞራ ባገራቸው በመሉት ነበር ። እንግዲህ አውሮፕላን ደስ ስላሰኛቸው ስንት ልጆች ለአውሮፕላን ትምህርት ይልኩ ይሆን ። እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሥልጣኔና ለሕዝቧ ክብረት ሲል መርጦ የሰጠን ሰው ይኑር እንጂ ኢትዮጵያን በጥበብ መንገድ ላይ ማስኬድ ጀምሮአል።አገራችንም እንደኤውሮፓ ሁና ወደምትታይበት ጊዜ ልትደርስ ትቃትታለች።

የኢትዮጵያ ወይዛዝሮችም በሥልጣንና መንገድና በብልሐት ጐዳና ለመሔድ ታጥቀው መገስገስ ጀምረዋል። መኳንንቱና ሴት ወይዘሮው ኤውሮፓን ቢያዩ በውነት እኛ ያለንበትን ሸለቆ አዘቅዝቀው እያዩ ውሸቱንና እውነቱን እየተረዱ አገራቸውን ለማስተማርና ለማሠልጠን፤ ለማስጠበብ ታጥቀው የቆሙትን ንግሥተ ነገሥታትንና ንጉሣችንን በሁሉ መንገድ ለመርዳት እንዲነሡ ብዙ ብልሐትና ጥበብ ያየው ልቡናቸው የግድ ወደ ደጉና ወደ መልካሙ ፤ ወደሚጠቅመው እውቀትና ብልሐት እየሳባቸው ይነቁ ነበር። ወደኤውሮፓ ለመምጣት የሚችሉት ሁሉ እየመጡ ቢጐበኙት መልካም ፍሬ ለሕዝባችንና ላገራችን ይገኝበት ነበር ።

ይኸውና ዛሬ ክብርት ወይዘሮ ዘውዲቱ ያለንበትን ሸለቆ አይተው ንዴትና ኀዘን ሳያሸንፋቸው እጅግ የበረቱ ጥበብን ፈላጊ ሴትወይዘሮ ሆኑልን ። ይኸውና የፈረንሳዩን ቋንቋ ይዘው ያቀላጥፉት ጀምረዋል ። ይኸው እንደ ኤውሮፓ ሴትወይዘሮች እንዲት ትንሽ አሽከራቸው ብቻ ጋር ከፓሪስ እስከ ሮም ድረስ መጡ ። ይኸውና ቋንቋውንና ሕዝቡን በማያውቁበት አገር ለብቻቸው ይዞራሉ። ከወንድማቸው ጋር በሚሰነብቱበት ሰሙን እንኳን ሥራ አይፈቱም። ይኸው እንደኤውሮፓ ወይዛዝሮች ሊጠበቡ አውቶመቢል መንዳት ይማራሉ ። ይኸው ድንቁ ምንም ሰውነታቸው ሳይፈራና ልባቸው ሳይበባ የደስታ ሳቅ ፊታቸውን ሲያበራው በአውሮፕላን እየወጡ ይበራሉ ። በሎንዶን በሚሰነብቱበት ጊዜአቸው ሁሉ የእንግሊዝን ቋንቋና ለወይዛዝር የሚያስፈልገውን ጥበብ ሁሉ እንዲመረምሩ እርግጥ ነው ። ከውድ ባሎቻቸው ጋር ወደ ኤውሮፓ የሚመጡት የኢትዮጵያ ሚንስቴር ወይዛዝሮች ሁሉ እንደ ወይዘሮ ዘውዲቱ ጥበብና ብልሐት የሚፈልጉ እንደ ሆነ ላገራቸው መልካም ፍሬ፤ ለራሳቸው ክብሬታ ፤ ለዘመድ ወዳጃቸው እርዳታ ፤ ለባሎቻቸው በብልሐትና በእውቀት በምክር ደገፌታ ፤ ይሆኑልናል ስንል ተስፋ ልናደርግ እንችላለን ። ጥበብን ለሚፈልጉ ጠቢብ አምላክ ይርዳቸው። ጥበብን ለማይፈልጉ ልቡና ይስጣቸው ።

ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑር ። መኩሯ ወልደ ሥላሴ ።

የደስታ ብዛት ።

ብርሃንና ሰላም የሚባል መልክተኛ ደጃፌን ከፍቶ ሲገባ እየሁትና በችኰላ ተነሥቼ እንኳን ደኅና ደረስክልኝ እህ ። አገሬ እንዴት አለች እያልኩ ብርሃን ልቡን ለመመልከት ስገላልጥ አንተስ ራስ ከበደና አጎታቸው ደፍረ » ባውሮፕላን በመብረራቸው ደስ እያለህ ባገርህ ለመድኀኒት እንኳ ኤውሮፕላን ባለመታየቱ ስታዝን የነበርከው ይኸው ደስ ይበልህ፡ ብሩህ የሆነው ሰሎሞን ንጉሥህ መቼ አገሩ አንዳች ነገር ጐድሎአት እያየ እንቀልፍ ይወስደዋል ። ይኸውልህ ከጂቡቲ ተነሥቶ ንሥረ ተፈሪ የሚባለው በራሪ አገርህ አየር ላይ አይበበልህ » ይኸው የሦስቱን ቀን መንገድ በሦስት ሰአት ቈረጠልህ እያለ የምስራቹን ቢነግረኝ የደስታዬን ልክ እንዴት አድርጌ ልገልጽለት ቸግሮኝ እየሳምኹ አራስኩት ። እሱ ባይኖር ኖሮ ይኸን ዘለዓለም ልቤን የሚበላውንና ያመነመነኝን አሳብ መፈጸሙን ሳላውቅ ስንት ጊዜ ባለፈ ኖሮአል ። ትልቅ ሥራ የማይሠራ ሰው ያስባል ፤ ያሰበው በሚቻለው እጅ ተፈጽሞ ሲያየው ራሱ እንዳደረገው ያህል ይቈጥረዋል።ስንቱ ለእውቀት የተበታተኑት ወንድሞቼ የዚህን ነገር በመስማት በደስታ ጦፈው ይሆን ። ስንቱ የአውሮፕላን ወሬ ሲነሣ ራሳቸውን ይደፉ ፤ ዠሮአቸውን ይዘጉ የነበሩት አንገታቸውን ያቀኑ፤ዓይናቸውን ያበሩ ፤ ጀሮአቸውን ይከፈቱ፤ መላሳቸውን ያጣሙ ይሆን፤ ስንቱ ያለዕፍረት የተገባ መልሱን ለመስጠት ይችሉ ይሆን ። ተፈሪ ይኑር ፤ ማፈር ሊጠፋ ነው በሁሉ ወገን እያልኩ ጁርናሌን እንደገና መሳም ጀመርሁ ።

ማናቸውም ሆነ ዓለሙን እንዲረዳ ወደፈጣሪ እየጸለዩን ለንግድ ሆነ ለመንግሥት ጕዳይ፤ለበሽታ ሆነ ለመንገደኞች፤ከሠለጠኑት አገሮች በፍጥነት የሚያገናኙን አውሮፕላኖች ለኢትዮጵያ በግድ ያስፈልጓት ነበር ። አውሮፕላን መሥራቱ ነው እንጂ መንዳቱስ ልክ አውቶመቢል እንደመንዳት ያህል ነውና ብዙ ጥበብና ብልሐት አያስፈልገውም። ከአሁንም በፊት አውሮፕላን መንዳት የቻሉና በዚህ ሥራ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ወገኖች አሉ።መሥራቱ በይቻላቸው እንኳ መንዳቱን ለመማር የሚፈልጉ ያገሬ ልጆች ነበሩ ። ምንይሆናል ኑሮውና ጊዜው ሳይፈቅድላቸው እንደተመኙት ይቀራሉ። የባቡርና የካሚዮን መንገድ በሌለው አገር አውሮፕላን ቢገባ ስንት በጠቀመ ነበር። ኢትዮጵያ የባቡር መንገድ ለማሠራት ብዙ ገንዘብና አያሌ ጊዜ የሚያስፈልጋት ምን ብትጠበብ በተሻላት ነበር ።

በየጊዜው እየመጣ አገራችንን ከሚያጠፋ አውሬ መከላከያ ማግኘታችን እጅግ ትልቅ ነገር ነው ። ከእንግዲህ ወዲያ ረኃብና ችግር አገራችንን በንበጣ ሰበብ እንዳያገኛት እርግጥ ነው ። ያሜሪክ አገር ጥንት አንበጣ እጅግ የሞላበትና የከፋበት ነበር።አውሮፕላን ከሠለጠነ በኋላ ግን በምድር ተዋግተው ማሸነፍ አቅቶአቸው የነበረውን በራሪ ጠላት አውሮፕላን ከንበጣው ጉም በላይ እየበረሩ መርዙን እያዘነቡበት ሥሩን ሊነቅሉት ችለዋል።እንደዱሮው በዚያ አገር እጅግ አይታይበትም ይባላል ። አሁን ባለፉት ወራቶች የኢጣልያና የእንግሊዝ፤የዓረብ መንግሥቶች፤የቅኙ አገራቸውን በየጊዜው የሚያጠፋውን አውሬ ተጋግዘው ሥሩን ለመንቀል በከርቱም ምክር ይዘው ነበር።ተጋግዘው የሚዋጉት ባላጋራ ምንም ብዙ ቢሆን መሸነፉ አይቀርምና ኢትዮጵያም በእንደዚህ ያለው ምክር እየገባች

የጋሬ ጠላቷን ልትዋጋ ያስፈልጋታል ። የኢጣልያ መንግሥት ከሁን በፊት ብዙ ዓይነት ያንበጣ መከላከያ መሣሪያ አስሠርቷል ። በሱማሌ አገር እሳት በሚወረውር በረሽ ዓይነት መሣሪያ ይዘው ይከላከላሉ ። እንደዚህ ያሉትን መሣሪያዎች የኛም መንግሥት ማስመጣት ያስፈልገዋል ። ከየአዋሳኞቹ እየተዋዋለ ቢከላከል አንበጣ እንደጨፈረብን አይኖርም ነበር ።

መ ስ ወ ።

የ፫፻፲፬ ገጽ ተከታይ የኢኮኖሚያ ፖለቲክ ።

፫ኛ ክፍል ምዕራፍ ፮ ።

፴፰)የሀብት ክፍፍል ።

ሀብት እንደ ምንድር ነው የሚከፋፈለው?፡ ሀብት ምን እንደሆነችና እንደምን እንደ ምታፈራ ከተናገርንና ከየን ወዲያ ሀብትን ለማግኘት ለጣሩ ሰዎች እንደምን እንደምትከፈል ወደ ጥኑ የሆነች ፕሮብሌም (ሒሳብ ማውጣት) እናልፋለን ። በአሁን ጊዜያችን የማፍራትን ፋቶሪ በልዩ ልዩ ክፍል ወገን ሰዎች ይከፋፈላሉ ። ማፍራት በአንድ ሰው ፈቃድ አትገዛም። ግን መሬት ሥራ፥ ካፒታል አገጣጥሞ የሚያቆም ኢምፕሬንዲቶሬ የሚባል ዋነኛ አሠሪ ሰውም ያስፈልጋል ። ልዩ ልዩ ክፍል ሰዎች ናቸው ለዚች ሥራ የሚያቆሙ ያልናቸው ስለዚህ ነው ። ማለት ሮንዲያሪ የሚባሉ መሬት የሚሰጡ ፥ ኦፔሬይ የየሚባሉ ሠራተኞች ፥ ካፒታሊስቲ የሚባሉ ገንዘብ የሚያበድሩ፥ ኢምፕሬንደቶሬ የሚባሉ የኢንደስትሪ ሥራውን የሚያዘጋጁና የሚያከናውኑ እየሆኑ ይከፋፈላሉ ።

አሁን ሀብትን በሶስት ፋቶሪ ነገሮች ናቱራ (መሬት ወይም ጸጋ) ሥራ ካፒታል (ገንዘብ) እንዴት እንደምታፈራ አይተናል ። ካለቀች ሀብት ይልቅ ያች አዲሲቱ የተፈጠረች ሀብት በማፍራትዋ እየበለጠችና እየበረከተች፥እየበዛችና እየሰፋች የምትሄድ ያለች ስለ ምንድር ነው?። እነዚያ አፍሪዎች ኔቶ የሚባል ጥሩ ትርፍ ለሶቼታ የሚሰጡት ስለአላቸው ነው። ይህ የሀብት አዘራዘር ፕሮብሌም ወይም ሒሳብ ይባላል ።

ከዚህ የተገኘችውን ሀብት በሁለት ልንከፍላት እንችላለን። ፩ኛ) ያች የምትጐድለው የካፒታል፥ የሥራ፥ የፍጥረት፥ መሬት በማፍራት ያለቁ መተካት። አስረጅ) ኢምፕሬዲቶሬ የሚባል አሠሪ፥ ለመሬት ለሠራተኞች፥ ለካፒታል (መሣሪያ) መግዢያ፥ ፹ ብር ቢያጠፋ ኋላ ከፈራ ወደያ ፺ ብር ቢሸጠው ፥ ፲ ብር ያተርፋል። ለሠራተኛም ለኑሮው ለሚያስፈልገው ብቻ አይሰጥም፤ ከሚያስፈልገው በላይ ትርፍም ይወስዳል እንጂ። ሶቼታ ኡማና የሚባል የዓለም ሰው ሁሉም ምንም አይከስርም። ስለ ምን ከዚህ ፍሬ መንግሥት ቀረጥ ወይም ግብር በሚባል ስም ብዙ ያተርፋል። ሕዝብም ሀብት እያደገ ስለሔደ ይጠቀማል ። ስለዚህ የሶቼታ ኡማና ከሳራ ያለቀው ብቻ ነው ይባላል። ምሳሌ የተቃጠለ የደንጊያ ከሰል ወይም የሚለበስ ልብስ፤ማለት ጠጉሩ ወይም ጥጡ አንድ ጊዜ ካለቀ አይመለስም። ግን ከ፲፩ዓመት በፊት የነበረ የዓለም ጦርነት አንድ ሚሊዮን ሚሊያርድ ገንዘብ ጨርሶዋል ይባላል። ይህ ንግግር ግን እውነተና ትክክል ስላይደለ ፤ መንግሥታት አውጥተው ጕዳይ ሠሩበት ይባላል እንጂ፥ ሁሉ አልቀዋል ማለት እንደ ኤኮኖሚያ መንገድ ትልቅ ስህተት ነው። አስረጅ) ስንት ኢንዱስትሪያሊና ስንት ነጋዴዎች ናቸው ከሚገባቸው በላይ በጦርነት ጊዜ ብዙ ትርፍ ያገኙና ታላላቆች ሀብታሞች የሆኑ?።የሶቼታ ኡማና ከሳራ የተጨረሰው ብቻ ነው የሚባል ያልነው ስለዚህ ነው ።

፪ኛ) ያች ያፈራች ኔቶ የምትባል ጥሩ ትርፍ ነች።ኢምፕሬንዲቶሬም (አሠሪ)ሀብትን የሚዘረዝር ነው። በማፍራት የሚጨምሩ በአራት ክፍል ሊከፍሉ ይችላሉ ።

ፍሬ == (ፕሮዶቶ) ። ደመወዝ (ሳላሪዮ)። የመሬት ኪራይ (ሬንዲታ) ። ወለድ (ኢንቲሬሴ) ። ትርፍ (ፕሮፊቶ)።

ፕሮዶቶ ማለት ፍሬ፤ ሳላሪዮ ማለት የሠራተኛ ደመወዝ፤ ሬንዲታ ማለት ለመሬት ዋኖች የሚሰጥ ፤ ኢንቲሬሴ ማለት ለብር አበዳሪዎች የሚሰጥ ወለድ፤ ፕሮፊቶ ማለት ለዋናው ኢምፕሬንደቶሬ የሚቀርለት ትርፍ ነው። ባጭሩ ሠራተኞች፤ የሀብት ፍጥረት ዋኖች፤ ካፒታሊስቲ ኢምፕሬንዲቶሮች ከነዚህ እያንዳንዱ እየፈንታው ዋጋው ይወስዳል። ስሙም የሠራተኛ ደመወዝ ሳላሪዮ፤ የዋኖቹ ባለመሬቶች ትርፍ ሬንዲታ፤ የካፒታሊስት ወለድ የኢምፕሬንዲቶሬ ትርፍ ፕሮፊቶ ይባላል ብለን በፊት አመልክተናል ።

በነዚሁ ዝርዝር በያንዳንዳቸው አንድ ክፍል በፊት ለጠፋ ሀብት መተኪያ ነው። ሁለተኛ ክፍል የሁሉ ሰው ሶቻሌ (ማኅበር) ኔቶ ትርፍ ነው ። (ኔቶ የጠራ ትርፍ ማለት ገቢና ወጪ የሆነ ሁሉ በሁለት ልይ ልይ መዝገብ ተደምሮ ከጠቅላላው ገቢ ሲጐድል የሚተርፍ በቂ ገንዘብ ነው። አስረጅ ገብረ ማርያም የሚባል ነጋዴ ከባንክ የተበደረውን ፻ ብር ገቢ እንለዋለን ፤ በ፺ብር የገዛትን በቅሎ ወጪ እንላታለን ። እንደገና ለ፻ብር ቢሸጣት ያተረፈውን ፲ብር ኔቶ የጠራ ትርፍ ብለን እንጠረዋለን ።

ግን ይህነን የአዲሱ ፍሬ እንደ ኢምንፕሬንዲቶሬ ፍቃድ እንደሆን የሚዘረዘር አለ።ማመን ነው። ስለምን ከተፈጥሮ ልምድ ይልቅ ደግሞ ከነፃነት አሸቅድድም ጋራ ተሠርታለችና።ስለዚህ ሶቻሊስቲ የሚባሉ ወገን የአሁን ሥራትና ወግ፥የሀብትንአዘራዘር መለወጥ የሚፈልጉ፤በዚች በነፃነት ጋራ መንግሥት ሊገባ እንደሚገባው ማለት መንግሥት ሀብትን በትክክል ለሕዝቡ ሁሉ ሊዘረዝረው በህላቸውን በዓለም ሁሉ ሊያሰፉ ይጥራሉ።እውነት ነው፥መድኃኒታችንም ሁለት ቀሚስ አታድርጉ ብሏል። በህሉስ እጅግ መልካም ነበር።ግን ቴዎርያና ሬያልታ (ባህልና የሚሆን ነገር) ልዩና ሩቅ ነው እንደሚሉት ፥ ከብልሆቹ ፈረንጆች ፥ መጀመሪያ ሊሆን አይችልም ።

ቢሆን ደግሞ ለኤኮኖምያ ፖለቲክ እጅግ ጉዳት ነው። ማለት ሀብትን ማፍራትና ማከፋፈል መንግሥት የነፃነት ጋራን አስለቅቆ ቢይዛቸው አገርና መንግሥታት ሁሉ ጥንት ወነደበረች ድኅነትና ችግር የምትብስ ጊዜ በተመለሰ ። ከሁሉ በፊት ሀብትን መንግሥት ቢከፍላት ከአሁን ጊዜያችን የምትበልጥ አድርጎ እንዳይዘረዝራት የታወቀ ነው ።(የዛሬ መስከቦች ምሳሌ ሁነው ያሳያሉ)ስለምን መንግሥት የራሱ ሥራ እንኳ እንደሚገባው አያውቅምና ። ብናገባውም በሁሉ የሚገባና የሚያ-

ደርግ መንግሥት እንደሚሉት የላቲን ተረቶች ፡ የትኛው ይሆን የሱ የኤኮኖሚያ ፍሬ እውነት ነው ፤ መንግሥት የያንዳንዱ ሰው ጥቅም ነፃነት ቢከለክል ማፍራት በጣም በነሰችና ለሚሠሩ ጠባቂዎች ብዙ ስጌዣ(ወጭገንዘብ)በጠፋ ።

ሁለተኛ ደግሞ መልካሚቱ የሀብት አከፋፈል ለመልካሚቱ የሀብት ማፍራት በገደለቻት ። ማንዜኒ የሚባል» ኮሌቲቢዝም (ሥራ ሆነ ከሥራ የተገኘ ጥቅም ለሁሉ እኩል እንዲከፈል የሚል ባህል) የሰልባጅ (የአውሬነት) ኃይል ነው፡ ፍሬን ለመልቀም ዛፉን ቈራርጦ እንደሚጥለው መሆኑን ጥርጥር የለበትም።እንደ ሶቻሊስቲ ባህልከሆነ ማንም እንደሚገባው የሚያፈራ ባልተገኘም ። ስለዚህ የኤኮኖሚያ ታላቅ ጉዳት ብሆን። ሰው በተፈጥሮው ገንዘብ ወዳጅ ነውና ትርፉ ለራሱ መሆኑን ቢያውቅ በጣም በብዙ ትጋት ሠርቶ ኤኮኖሚያ ፖለቲክን ይበለጥጋል።ትርፉንስ መንግሥት ወስዶ ለብዙዎች ሰዎች እንዲከፋፍለው ካወቀ በኋላ በጥንክሬ የሚያሠራና እየቈጠበ ገንዘብ የሚያስቀምጥ ማን ሰው ነው ።

እውነት ነው፤ የውርስን ገንዘብ የሚሰበስብ ሰው አይሠራምና ለኤኮኖሚያ ጉዳት ነው ። ግን እንደ ሶቻሊስቲ ባህል ውርስ ሁሉ መንግሥት የሚወስደው ቢሆንም ጉዳቱ በጣም የባሰ በሆነ ነበር። ማለት የወዴትም አገር ሰው ቢሆን ለልጁ ወይም ለሚስቱ ፡ ለወዳጁ ወይም ለመስተዋሻው አንድ ነገር ሊያሠራበት ፡ ለነፍሱ ማጽደቂያ ለድኆች ምጽዋት ወይም ለፍታቱና ለተዝካሩ ፡ ባጭሩ ለወደደውና ለፈቀደው ነገር ሊተወው አለመቻሉን ከተረዳ ወዲያ ፡ ገንዘቡን ሁሉ አባክኖት ብሞቱና በፊት እንዳመለከትነው ኤኮኖሚያ አለ ሦስተኛው አካላትዋ ካፒታል ልትቆም አትችልምና አብሬው በተቀበረች ። ገበሬ ቢሆንም መሬቱ ለሚመጡ ዓመቶች የራሱ አለመሆኑን ቢያውቅ መሬቱን እንደሚገባው አይከባከበውም። እለ ሀብትም አገር ምን እንደ ሆነች ለማንም ሰው አይሠወርበትም ይመስለኛል ።

የሆነ ሁኖ ሌላ የተሻለ የሀብት አከፋፈል እንዳለ ከማሰብ ሊያስጥለን አይደለም ። በጣም እንደፈቃድዋ የሆነች አሁን ያለች የሀብት አዘራዘር በትልቁ ይሁን በትንሹ የተለየች ነች ። የአሁን ዘመናችን የሀብት አከፋፈል ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው የተዘረዘረችው፡ ፩ኛ የነፃነት የኤኮኖሚያ የያንዳንዱ ሰው በነፍስ አላፊነትና ዋነኝነት ፤ ፪ኛ እያንዳንዱ ውርስ ነው ። ዋነኝነት ማለት በነፍስ አንዳንድ ሰው ይሁን ሶቼታ በብዙ ድካም ያጠራቀመው ገንዘብ ወድቆ ያገኘው ዋና የሌለው ዕቃ፡ባለ ቤት አልባ ያገኘው መሬት ይሁን የገለጠው ሚኔራል፡አድኖ ያገኘው ሥጋና አጥምዶ የያዘው ዓሣ የመሰለውም ሁሉ ነው ። ውርስ ማለት ወላጆቹ ይሁኑ የሥጋ ዘመዶቹ ወዳጆቹ ይሁኑ ጌቶቹ ያወረሱት ወይም የተናዘዙለት ሀብት ነው ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ሚካኤል ተሰማ ።

ስለ ክቡር ግራዝማች ዘገየ ቈለጭ ሞት የልቅሶ ግጥም።

ግርማዊ ንጉሥን እግዚአብሔር ያጥናዎ ። ይኸው ዛሬ ሞተ አንድ ሰው ቢኖረዎ ።

ይኸው ዛሬ ሙቶ ዛሬ ተቀበረ። የንጉሥ ተፈሪ አሽከር አንድ ሰው ነበረ ።

ዝምተኛ ሁሉ ጭምት ነው ይባላል ። ባያውቅ ነው እንጂ ቢያውቅስ ይናገራል ።

ተናገር ካላሉት ከለሥራው በቀር ። ዘገየ ነበረ አውቆ ማይናገር ። በልብ የሚያውቁትን የሰሙትን ነገር ። እጅግ ያስደንቃል ሲያውቁ አለመናገር ።

የዛሬ ሰልፋችን እጅግ አርጎ አማረ ። ግራዝማች ዘገየ ወዴት ሒዶ ቀረ ። በጣም መልካም ነበር እሱማ በኖረ ።

ዘመቻ አዘውትሮ ግርማዊ ንጉሥ።ሰውም ትናንት ሒዷል ቀድሞ በፈረስ ። ዘገየ አሁን ሒዶ በሰውም አይደርስ ።

ፌታውራሪ ቆለጭ ልንገርዎ ወሬ፡ መልክዎን ሲያጠፉት እኔ አየሁኝ ዛሬ ።

ይኸን ሁሉ እያየ ልቡም አልተከፋ። ልጅዎ ዘገየ መልክዎ ሲጠፋ ። ሞት መጣ ይሉኛል ያው እዝያ ላይ ታየ። ወደዚያው በቀረ ምነው በዘገየ። ጌታችን አይደለ ንጉሥ አልሾሙት ። አሁን ማን ነው ያለው ዘገየ ይሙት ። አርገውት ይሆናል ንጉሥ በስተውጭ።የሰው መረጠሚያ ዘገየ ቆለጭ። ንጉሥ የሰጡህን የሾሙህን አገር። እኔም ዳኛ አይደለሁ ብለህ ስትናገር። ደግነት ትዕግሥት እውቀት ትሕትና መታመን ሰው መውደድ ያለም ጠባቆች ለሕዝቡ የቆሙ። ይኸውና ሁሉም ባንተ ተፈጠሙ። ግራዝማች ዘገየ ያንተን ነገር ማውጋት ። ሰማይን መሳብ ነው በሰናፍጭ ቅንጣት ። ዐባይን በጭልፋ ጨልፎ መጠጣት።

ይኸንን የሚችል አንድ አዋቂ ቢገኝ ። ልቡ ይታዘበኝ እኔን ሰው አያርገኝ ። ልባልባ ግዛልን ብለውት ነበረ። ሐር ቀሚስ ግዛልን ብለውት ነበረ። ተስማምቶም ለመግዛት ጀምሮ ነበረ ። ግራዝማች ዘገየ የት ገብያ ቀረ ። ጠፍቶ ይኖር ነበር ትናንትና ታየ ። እስከ ዛሬ ድረስ የት ነበር ዘገየ ። ትናንት ባደባባይ ዘመዶቹ ሁሉ ። ይላቀሱ ነበር የት ነበርህ እያሉ ። እንዳንዲት ፍሬ ልጅ ትልቂቱ ሴት ። ከመንገድ ላይ ቁማ የዘገየ ሚስት ። ታለቅስ ነበረ ቤቷ ጠፍቶባት ።

አላዋቂ አይደለህ ሁሉንም ታውቃለህ ። ትቢተኛ አይደለህ ወንድም ታከብራለህ ። ቅልብልብ አይደለህ አውቀህ ዝም ትላለህ ። ሰው እንዳታስቀይም ብዙ ትዕግሥት አለህ ። ዘማዊም አይደለህ በሕግ ትኖራለህ ። መጠጥም አትወድ ሰካርም አይደለህ ። ሐሰትም አትወድ እውነት ትወዳለህ ። በሁሉም ውብ ሰውነህ አንድም ሳካ የለህ ። ነገር ግን ስትሞት ሔድህ ሰው በድለህ ።

ይኸን ሁሉ ሞያ ይዘህ ስትቀበር ። ለየችግረኛው ብትሰጠው ምን ነበር ። ከጠባይህ ሁሉ እኔ ካየሁት ። ይኸን ብቻ አገኘሁ ባንተ ላይ ጥፋት ።

የተሻ ወርቅ ።

ስለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓል አከባበር ።

ጥቅምት ፭ቀን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓል ነበርና ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በክቡራ መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው ሒደው በዓሉን አክብረው ተመለሱ ።

መወድስ።

እግዚአ አእምሮ ንጉሥ ኀይለ ሥላሴ
ለዓበይተ ሸዋ ሕዝብከ አርአይከሙ ዕፁበተ።
ወለዘይፈርሁ ትሁብ አውሮፕላንላሃ ትእምርተ።
እንዘ ምስለ ኖህ ኅሩይከ ትሠይም በገጸ ደመና ዘምሕረት ቀስተ።
ኢትዮጵያ ቤተ አቡከ ኢትኩን እንከ ዘሙስና ኀጕለ ዳግሚተ።
ስቡሕኒ ኀይለ ሥላሴ ወልዑለ ፍጥረት አንተ።
ላዕለ አውሮፕላን ነቢረከ ዘትሬኢ ቀላያተ ።
ወስብሐተ ንግሥከ ታንክ ለእመ መልዓ መሬተ።
ሥንከ አውሮፕላን ከደነ ሰማያተ ።
ከሳ ተክሉ ማኅደረ ማርያም ።

ስለ ዘንድሮ አዝመራ ።

ከክረምት በፊት በገራችን በኢትዮጵያ ብዙ አንበጣ መጥቶ የበልጉን አገር የህል ቡቃያና የእንሰሳትንም ምግብ ማር ቅጠል አጠፋ ። ነገር ግን ሰው ለጊዜው ሆዱ ቢባ እንጂ ተከታዩ ክረምት ስለ ሆነ ሰውም እንስሳም እጅግ አልተጐዳም። የዘንድሮም ክረምት ዝናቡ በልክ የሆነና እጅግ ያልተጫጫነ፥ ለሰውም ፥ ለምድር አዝርእትና አትክልትም ሁሉ የተስማማ ማለፊያ ክረምት ነበር ። ከቈላ ከደጋ የመጣውንም ሰው ብንጠይቅ ማናቸውም እህል ሁሉ በያይነቱ እንደ ዘንድሮ ሁኖ አያውቅም እግዚአብሔር ሕዝቡን ከመንግሥቱ ጋራ አስማምቶልን ፥ አገራችን ሰላምና ጤና ሁኖልን ፥ የዘንድሮውን መልካሙን ሰብል እንድንበላው ያድርገን እያለ መልካም ወሬ ያሰማናል ።

ዘንድሮ ዋናው የሰዉ ፍርሃት ምናልባት አንበጣው ወደ ቈላ ወርዶ ከርሞ እንቍላል የጣለና የፈለፈለ እንደ ሆነ መስከረም ሲጠባ ተነሥቶ በአገር ላይ ጥፋት እንዳያመጣ ነበር። ስለዚህም አሳቢውና ርኅሩኁ መንግሥታችን ሕዝቡ ሲጐዳ የራሱ ጕዳት እንደ ሆነ ተሰምቶት በያለንበት እግዚአ እንድንልና ወደ ፈጣሪያችን እንድናመለከት ባዋጅ አስታወቀን ። አሁንም ወንድሞች ሆይ ፤ እንኳን ይህ ገና እሸት ፥ ነምር ያለው ፥ ታጭዶ ያልተወቃው እህል ና በምጣድ የገባው ሊጥ ምናልባት እንዲይታነኰር ወይም በሌላ ምክንያት ከምጣዱ ውሥጥ እንዳይበላሽ ፥ እንጀራ ሁኖ ወጥቶ እስኪበላ ድረስ ያስጋልና መንግሥታችን ስለ ሕዝቡ አስቦ የነበረውን አዋጅ (ምህላውን) ችላ ሳንል ፥ ይህን ዓይናችን ያየውን ፥ ልባችን የተመኘውን ኃይላችን የደከመበትን መልካሙን ፍሬ ለመብላት እንዲያበቃን ሁሉ ጊዜ እግዚአብሔርን እንለምን ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ ባማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞ ንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጆኦግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኀሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋሰው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጽሐፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪ (ካሌንደር)	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፰ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፰ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፰ መሐ
የበገና ግጥም	፰ መሐ


COGNAC SaE&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ዶግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር ተ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፩ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፸፭ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፫ ብር
ባለ ድመ ።		፻፴፭
ባለአህያ ።		፻፵
ባለሳቢ ግመል ።		፻፳
ባለ አንበሳ	አሜሪካ	፻፰
" "	ጃፓን	፻፸፲ ብር
ሱኳር	ጁኒያ	፳፰ብር
ቻይ	፳ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፹ሳቲንም
ባአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፶፬ሳንተም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፹፭ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵

የውጭ አገር ወሬ ።

ከኢጣልያ ሌጋሲዮን የሚመጣ ራድዮ የዕለት ወሬ ።

በምባይ ፤ ከአፍጋኒስታን የሚገኙ ወሬዎች የናድሪክ ቀሐን ድሮ የአማኑላህ የጦር ሚኒስትር የነበረውን ሠራዊት ክቡልን እንደያዙ ያስረግጣሉ ። ደግሞ ሕዝቡን አዲስ ንጉሥ እንዲመርጥ ማሰቡን ይወራል ።

ፓሪስ ፤ የሬፑብሊክ ፕሬሲዳን በሚኒስትር በብርያን ተሸኝቶ ወደ ብሩክሰሌስ ዛሬ ይነሣል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

ድ ራ ሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ሳይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፣ የፋብሪካ፣የደን፣ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየዐይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

ያሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቀባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም በለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሬም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ረ ብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፈኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ያገኛል ኒኳላ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው





አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዴስና ልጆቹ ። የወንዶችና የሴቶች ልብ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE

BORSALINO

ALESSANDRIA

(ITALIA)

MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
5me ANNÉE № 43

ሐሙስ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 24 OCTOBRE 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የመንግሥት ማስታወቂያ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴር።

ከ፲፱፻፳፪ ዓመት ጥቅምት ፲ቀን ጀምሮ ወደፊት ማናቸውንም ዓይነት አውሬና ወፍ ለማደንና ለመግደል ወይም ከነነፍሱ እየያዘ ከኢትዮጵያ ግዛት ውሥጥ ወደ ውጭ አገር ለመውሰድ የሚፈልግ ሰው ። አስቀድሞ ከርሻና ከመሥሪያ ሚኒስቴር የፈቃድ ወረቀት መቀበል አለበት። ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃል አስቀድሞ የፈቃድ ወቀረት ሳይቀበል ማደንና መግደል፤መያዝና መውሰድም፤ ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑን እናስታውቃለን ።

የ፫፻፵፯ ገጽ ተከታይ ።

(፴፯)የካፒታሊስታ ገቢና ወለድ ።

የካፒታሊስታ ኢንቴሬሴ የሚባል ገቢና ወለድ ፤ የአበዳሪ ሙሉ በብር ይሁን በመሬት የሚሰጥ ገንዘብ ነው ። ለስዚህ ወለድን በካፒታል ልክ ዋጋና በቄየው ጊዜ ፕሮፖርጺዮን ግምት ሊሆን ይገባል ። በመቶ አምስት በዓመት የሚሰጠው ታሶ ይባላል ። ኢንተሬሴ የሚባለውን ወለድ ብንመረምረው፤ ከአንድ ክፍል ለመጀመርያው የቆመው ካፒታል አሞርታሜንቶ የሚባል መተክያው እንደተሰጠች ልናውቅ እንችላለን። ማለት ከአንድ መኪና አንዱ ክፍል ቢባላሽ፥ ወይም ቢሰበር፤ ዋስ ቢተካለት፥ ወይም ቢበጅ ፥ አሞርታሜንቶ ይባላል። የኢንተሬሴ የምትባል ወለድ ሁለተኛዋ ክፍል ደግሞ ፥ ለአሲኩራጺዮኔ የሚባል የድንገት ከሳራ መጠበቅያ ለዋና አላፊዎች (ዋሶች) ትሰጣለች ። በመጨረሻ ሰስተኛዋ ክፍል ፍሩቶ ኔቶ የምትባል የጠራች ፍሬ ካፒታል እውነተኛ የጠራች አንቴሬሴ የምትባል ወለድ ነች ። እኛ በጣም የምናጠናትም (የምንማራትም)ይህች ፍሩቶ ኔቶ የምትባል ወለድ ነች ። የኢንቴሬሴ ታሶ የሚባል ወለድ ፥ ከአገርና አገር ፥ከጊዜና ጊዜ የተለያየ ነው ። ግን፡ እሱ ፥ በሁሉ ፥ ካፒታል ፥ በአንድ አገርና በአንድ ጊዜ ልክ ሊሆን ይደዛል ። ስለዚህ አንድ ካፒታል ከሌሎቹ የሚበልጥ የሚያፈራ ቢኖር ሁሉ ይህን ካፒታል ለማፍራት በገቡና ብዛቱ ሲያድግ ዋጋውን በረከሱት ። እስረፎ) ካፒታል በዓመት ስድስት ብር ወለድ ቢያተርፍ ፤ የመኪና ሰሬ ሻን ሰባት ብር የሚሰጥ (የሚያተርፍ)በሆን ፤ ሁሉ ሰሬዎች በሆኑ ። ግን ትንሽ እንደቄዩ ብዙ በችሬራና ዋጋው ርካሽ በሆን ። በመጨረሻ እንዲህ ልንል እንችላለን፤ ሳጂዮ ፥ ዴሊ ፥ ኢንተሬሴ የሚባል ወለድ ፥ በአመርታሜንቶ የሚባል መተክያና አሲኩራጺዮኒ የሚባል መጠበቅያ አንሶ ከካፒታል ጥያቄና ማቅረብ(ዶማንዳ ና ኦፌርታ)ነው የሚገዛ። በጣም የታመኑ ባንኮችና ለብዙ ረዥም ጊዜ የሚያበድሩ ሰዎች ወለዳቸው ጥቂት ነው ።

የዚህን አኳኋን አሳብ ሰፋ ባለ አካሔድ ብንመረምረው፡ የኢንቴሬሴ ሳጅዮ (ወለድ) እንደ ካፒታል መብዛቱ ከመንግሥታትና ከመንግሥታት የተለያየ መሆኑን በጣም ልንረዳው እንችላለን። ሁለተኛም ከሠራተኞች ማስረገጥና ከኢምፕሬንዲቶሬ ጥያቄነትም ስምምነትና ችሎትም ይገዛል ፥ ሶስተኛ ፤ ከኋለኛው ጥቅም የያዘው ካፒታል ማደግም ቁምዋል ። እስረጅ አንድ ካፒታሊስታ ፫ሺ ብር ያለው ብድር ለሚጠይቀው

ሰው ሬተኛው ሺብር ለፍለጋው በጣም በብዙ የሚያስፈልጉት ናቸውና መቶውን በመቶ ብር ወለድ በፈለገ ። በሁለተኛው ሺብር ለፍለጋው ጥቅማቸው ዝቅ የሚል ናቸውና በመቶ ኻያ ብር ወለድ በፈለገ ። በኋለኛይቱ ስስተኛ ሺብር ለፍለጋው ጥቅምዋ ከሁሉ በጣም ያነሰ ፥ ከልከኛው ትርፍዋ ብላይ ለማግኘትም ባይችል በመቶ አምስት ብር ወለድ መውሰድ ደስ ባለው ።

እውነት ነው ፤ የተሰጠ ካፒታልሁሉ አንድ ዓይነትና ብዛቱም ትክክል ነበር ፤ ግን የሚያቆሙት ክፍሎች ከነሱ አለ ልዩነት ሊለዋወውጡና ፥ ካፒታሊስታ የኢንቴሬሴ ሳጅዮ ለጥቅሙና ፍለጋው በጣም ላነሰ ሊይዝ ይችላል ። ተአምራቱንም ቀጥሎ ያለው ፫ኛ ሥዕል ሊገልጥልን ይችላል ።

በ(ሀ)(ለ)የተያዘች መስመር የካፒታልን ብዛት፤ ያች በ(ነ)(ሠ) የተያዘች ጉባጣ መስመር የጥቅማቸው እያነሰመሄድ በ(ሀ)(ተ)የተያዘች መስመር የሚያፈራ ከፒታል፤በ(ሀ)(ነ)(ሠ)ተ)የተያዘች ስፋት ያሳያል ።በ(ሠ)(ተ)የተያዘች መስመር የኢንቴሬሴ ሳጅዮን ይሰፍራል ።



ሥዕል ፫ ።

እንዲሁም ለካፒታሊስታ ሬታንጎሎ በሚባል መዓዝን በ(ሀ)(መ)(ሠ)(ተ)የተያዘ ፍሬ ይሆናልና ይወስዳል።(ካፒታል(ሀ)(ለ በወለድ(ሠ)(ረ)ሞልቲፕሊካሲዮን(የበዛ)የፕሮፌቶ ባቂ(ነ)(መ)(ሠ)ላበለ ዕዳ ይቀራል ። ግን ካፒታል ከሚያስፈልግ ያነሰ ቢሆን በ(ሀ)(በ)የተያዘ መስመር የኢንቴሬሴ ሳጅዮ በ(ቀ)(በ)የተያዘ መስመር የተለካ በሆነና ለካፒታሊስታ በ(ሀ)(ረ)(ቀ)(በ) የተያዘ ስፋት ፍሬ ፈንታው በሆነ የባለ ዕዳው ፈንታ በታናሽነቱ ክፍል በ(ነ) (ረ)(ቀ)የተያዘች ስፋት ፍሬ በሆነች ።

በቀላል አሳብና ባጭሩ አስረጅ ፥ በድኆች መንግሥታትና አገሮች የኢንተሬሴ ሳጅዮ በጣም ከፍ ያለ ነው ። በኢኮኖሚያ በበለጸጉ ሀብታሞች ጌቶች እንደነ እንግሊዝና እንደአሚሪካ ስታቲ ኡኒቲ የመሰሉ አገሮች የኢንተሬሴ ወለድ በጣም ዝቅ ያለ ቀላል ነው ። ሚካኤል ተሰማ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ስለ ኢትዮጵያ ምድረባቡር ።

በጎታና በየረር መካከል ያለው የብረት መንገድ አንድ ድልድይ ጐርፍ ስላበላሸው ፥ የተበላሸው ድልድይ እንደገና እስኪሠራ ድረስ ከድሬ ዳዋ የሚመጣውንና ካዲስ አበባ ወደ ድሬዳዋ የሚወርደውን እቃ በካሚዮን ያቀብቡላሉ።በዚህ ምክንያት እቃው በቶሎ የማይደርስ ስለሆነ በሌላም ምክንያት ከውጭ አገር እየመጣ በአዲስ አበባ የሚሸጥ እቃ ሁሉ በጣም ተወደ ል ። የንግድ ሱቅ ሁሉም ገበያው እንደ ድሮ አይዶለም በረድ ብሏል ።

ከውጭ አገር እቃ እያስመጡ የሚነግዱ ነጋዴዎችም የንግዱን እቃ እንደዚህ ውድ መሆንኑና የንግድሥራ አለመቅናቱን ቢጠየቁ ፩ኛ፤ የባቡሩ ኪራይ ከልክ ያለፈ ስለሆነና እንደሚገባ እቃው በቶሎና በደህናው የማይደርስ ባለመሆኑ ነው ። ፪ኛ ፤ ደግሞ ገንዘብ ሽረፋ አንዳንድ ጊዜ መሐለቅ እየተወደደ አንዳንድ ጊዜም ቤሳና መሐለቅ ዋጋው እኩል እስኪሆን ድረስ መሐለቅ እልረከሰ ፥ ገበያተኛውም በመሐለቅ ይገዛና መሐለቅ ምላሽ ቢሰጡት የማይቀበል ስለሆነ ነው ። ብዙ ሰውም መሐለቅ እየሸጠ ብር ይቀበላል እንጂ ፥ መሐለቅ ሰጥተው ብርን ሊገዙ ለሚፈልጉ መሐለቅ የማይሰጥ ስለሆነ የገንዘቡ ነገር በልክና በሥርዓት አይሔድም እያሉ ሳያመኻኙ አይቀሩም ።

ስለ ንግድ ነገር ።

በመስከረም ወር የንግድ ሚኒስቴር ንግድን የሚያሻሽልና የሚያሰፋ ፥ ለነጋዴ ሥራና ለነጋዴውም ለራሱ ጥቅም የሚሆን ማስታወቂያ አውጥቶ ጽሕፈት ቤቱንም በከተማ ውሥጥ እንደሚገባ አሰናድቶ ሥራውን ጀመረ ። የሥርዓቱ ጥቅምና የሚያስፈልግ መሆኑን የተረዱ ብልህ የሆኑ ብዙ ነጋዴዎችም ማስታወቂያውን አይተው እንደታዘዘው ቃል ስማቸውን በመዝገብ እያስጻፉ፥ የሚገባቸውን እየከፈሉ፥የፈቃድ ወረቀት እየተቀበሉ ሲሔዱ ሰነበቱ ። ዲረክተሩ ክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔርም በብርቱ ትጋት ሥራው እንዲከናወንና የኢትዮጵያ ነጋዴ እንዲጠቀም ያለመሰልቸት ይሠራሉ።ለንግድ ሥራ አማካሪ የሆኑ አቦካት ክቡር ሙሴ ባሌአሎንስም ስለንግድ ሥራ በማማከራቸው የንግድ ሚኒስቴርን በጣም ይረዳሉ ። በጉምሩክ ሥራ በየክፍሉ ጽሕፈት ቤት የሚሠሩ አለቆችና ጸሐፊዎችም በሥራቸው አፈጣጠንና ጥዳት፤ በሥርዓታቸው መተከከልና መጠንቀቅ በጣም የተመሰገኑ ሁነዋል ።

የንግድ ሚኒስቴር ማስታወቅያውን ከወጣ በኋላ ብዙ ሰዎች ለዕለቱ ለምስክር ወረቀት የሚወጣውን ገንዘባቸው ብቻ

እንጂ ለኋላ ንግድ ትዳራቸውን ባለማሰባቸው አጕረምርመው ነበር ። ግን የከተማውና ያገርቤቱ ንግድ ተስማምቶ በሥርዓት ከሆነ እውነተኛውም ነጋዴ ተለይቶ ከታወቀ ነጋዴው አይከስርም ። ገበያተኛውም አይጕላላም ። ሥርዓት የሌለው ንግድ ግን የዘረፋ ያህል ነው ።

ኢትዮጵያ በንግድ ረገድ ብዙ ትርፍ የሚገኝበት አገር ነው ። ግን እስካሁን ድረስ በንግድ የከበረ ኢትዮጵያዊ እጅግ የለም ። የኢትዮጵያ ልጅ በንግድ ነገር ትልቅ ሀብታም ነጋዴ አለመሆኑና የተከናወነ የንግድ ማኅበር አቋሞ እስካሁን ድረስ ላገር ጥቅም የሚሆን ሥራ እየተረዳዳ አልመፈጸሙም፤ ለወደፊቱ ግን ላገሩ ጥቅም ማኅበር አቋሞ እንዲረዳዳ ተስፋ እናደርጋለን።

ግንአሁን የንግድን ሥራ የሚያግድ ብዙ መሰናከል ጠፍቶ ሥርዓቱ ሁሉ ተተክክሎ ነጋዴው ያለችግርና ያለስጋት የንግድ ሥራውን እንዲፈጸምና የዚህ ወደዚያ ፥ የዚያ ወደዚህ እያመላለሰ ለሕዝቡ ምቾት እንዲሰጠውና የያገሩ ገበያ ከየዓይነቱ ሁሉ እንደፍላጎቱ እንዲያጠግበው ተስፋ እናደርጋለን። ግርማዊት ንግሥታችንና ግርማዊ ንጉሣችንም ለነጋዴና ለገበሬ አስተዳደር እንዲመች ማሰባቸውና መርዳታቸው ከልክ ያለፈ ነው።ስለዚህ አሁን የተጀመረው የንግድ ሥራ ማሻሻል የንግድ ሚኒስቴሩ ዲሬክተር ክቡር አቶ ገብረ እግዚአሁሔር እንደ አሁኑ አጀማመራቸው ትጋታቸው እየሰፋና እየሠለጠነ እንዲሔድ ጥርጥር የለበትም ። መንግሥታችንም ርዳታቸውን አያጓድልባቸውም ።

የውሀልትና ሥራ በመሥራት በችሎት ስለ ተፈረደባቸው ሰዎች።

በየጊዜው አንዳንድ ክፉ ሰዎች እየተነሡ እግዚአብሔርም የከፋት ሥራቸውን እየገለጸባቸውና እየተያዙ ቅጣት እንደ ተፈረደባቸው በአዲስአበባ ከሚኖር ሰው የማያውቅ አይገኝም።

አሁንም በቅርቡ ባለፈው ክረምት ውሥጥ ቀኛዝማች ዋቅጅራና ቀኛዝማች ዓለሙ፣ ግራዝማች ወልደ ማርያም የሚባሉ ሰዎች ተነሥተው በግርማዊ ንጉሥ ላይ ክፉ ምክር የመከሩ ሰዎች አሉ ብለው ከልባቸው ያነቁትን የሐሰት ወሬ በአጋፋሪነት ሥራ ውሥጥ ለሚሠራው ለግራዝማች ይገዙ ነገሩት።ከዚህም በኋላ የሐሰት ወሬያቸውን እውነት አስመስለው የሚያስረዱበት ምክንያት ቢቸግራቸው በዳር አገር በገሙ ተሹሞ የሚኖረውን የፊተውራሪ ተሰማ ጋረደውን ማኅተም አስመስለው አሰርተው ከልባቸው ያነቁትን የሐሰት ቃል ላራት መኳንንቶች ከፊታውራሪ ተሰማ ጋረደው የተላከ አስመስለው ጽፈው ለግራዝማች ይገዙ ሰጡት ።

ግራዝማች ይገዙም እነዚህን ደብዳቤዎች እንደምን አገኛችኋቸው ብሎ ቢጠይቃቸው የፊታውራሪ ተሰማ አሽከር ተልኮ መጥቶ ነበርና ገና ደብዳቤዎቹን ለተላከላቸው መኳንንቶች ሳይሰጥ ከከተማ ውጭ ወጥቶ ነበርና በቦርሳው ውሥጥ ሳይኖር አይቀርም ብለን ጠርጥረን ቦርሳውን ብንቀደው አራቱን ደብዳቤዎች አገኘን ብለው ነገሩት ። ይህስ ከሆነ ነገራችሁ ሁሉ እውነት ይመስላል ብሎ ሰዎቹንም ደብዳቤዎቹንም ይዞ ወደ ግርማዊ ንጉሥ አቀረባቸው ።

ግርማዊ ንጉሥም ደብዳቤዎቹን አይተው እንደምን ተገኘ ብለው ቢጠይቋቸው ለግራዝማች ይገዙ እንደተናገሩት ቃል አድርገው ተናገሩ ።

ነገር ግን ግርማዊ ንጉሥ ገና ደብዳቤዎቹን ከማየታቸው እነዚህ ደብዳቤ የተላከላቸው ፥ የተባሉት መኳንንቶች ሁሉም ለኛ ዋና ታማኞችና የሚያስቡ ዋና ዋና ሰዎች ናቸውና ምንም ቢሆን ይህን የመሰለ መንግሥትንና ሕዝብን የሚያጠፋ ሥራ አይሠሩም ። ዳሩ ግን እነዚህ ሶስቱ ሰዎች ሰውን በከንቱ ለማጥፋት ከልባቸው አንቅተው የሠሩት ሥራ ይመስላልና ተይዘው ይመርመሩ ብለው ስለ አዘዙ ያቀረባቸው ግራዝማች ይገዙም ጭምር ተያዘ።ወዲያውም ፊታውራሪ ተሰማ ጋረደው ከዚህ ቀድሞ ወደ እኔ የጻፈው ደብዳቤ አይቃጣምና ሁለቱንም እያስተያያችሁ ማኅተሙ ልክ መሆኑን መርምሩ ብለው አዘዙ።

ለመመርመርም የታዘዙት ሰዎች ለየብቻቸው አድርገው በመረመርዋቸው ጊዜ በዚህ ምክያት ሹመት የምናገኝ፣ እንጀራ የምንበላ ስለ መሰለን የፊታውራሪ ተሰማን ማኅተም ፈልገን ባይነቱ የሚሠራ ሰው አግኝተን አሠርተን ቃሉን ቀኛዝማች ዋቅጅራ ጽፎ ለግራዝማች ይገዙ አሳይተን እርሱ ወደ ግርማዊ ንጉሥ አቅርቦ አሳየልን እንጂ ፊታውራሪ ተሰማ ይህን የመሰለ ቃል ጽፎና አትሞ አልላከም ብለው ሶስቱም ባንድ ቃል ኃጢአታቸውን አምነው ተናገሩ ።

ከዚህ በኋላ በጥቅምት ፲፩ ቀን ወደ ግርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርበው በምርመራ የተናገሩት ቃል ከተነበበ በኋላ የሐሰት ቃል የተጻፈባቸው መኳንንቶች ተነሥተው እኛ በልባችን እንኳ ያላሰብነውን ደህን የመሰለ ለእኛ መጥፊያ የሚሆን የሐሰት ቃል ከተናገራችሁና ጽፋችሁ ካተማችሁ፥አንተም ግራዝማች ይገዙ እንደዚህ ያለ ክፉ ነገር የያዙ ሰዎች አቅርበህ ካነጋገርህ ያስቀጣችኋል እያሉ ተናገሩ።

በዚያም የተቀመጡት ወንበሮችና ሌሎችም ትልልቆች ሰዎች ፍረዱ ስለ ተባሉ ቀኛዝማች ዋቅጅራና ቀኛዝማች ዓለሙ፥ግራዝማች ወልደ ማርያም እነዚህን ትልልቆች መኳንንቶች በሐሰት ለማስጠፋት የሐሰት ማኅተም አስቀርጸው የሐሰት ቃል ጽፈው ካቀረቡ ይቀጣሉ፡፡ግራዝማች ይገዙ ግን ያየውንና የሰማውን ለንጉሡ ነገረ እንጂ የሐሰት ቃል መሆኑን አላውቅም ካለ ፥ እነርሱም ማኅተሙ ቡሐት መቀረጹን ፥ ቃሉም በሐሰት መጻፉን አልነገርነውም እርሱም አያውቀውም ብለው ባንድ ቃል ከመሰከሩለት አይቀጣም ብለው ፈረዱ።

ከዚህ በኋላ ቀኛዝማች ዋቅጅራና ቀኛዝማች ዓለሙ ግራዝማች ወልደ ማሪያም አርባ አርባ ተገርፈው ዓሥር ዓሥር ዓመት እንዲታሠሩ ተፈረደባቸውና ተገርፈው በወህኒ ታሠሩ ።

ለሌላ ሰው የከፋት ጕድጓድ የሚቈፍር ራሱ ይገባበታል የሚባለው ቃል በእነዚህ ሰዎች ደረሰባቸው ።

በችሎትም የነበረው መኳንንቱና ሕዝቡ ሁሉ በሐሰት ሰው እንዳይጠፋ መርምሮ የሚፈርድ እውነተኛ ንጉሥና ዳኛ የሰጠኸን ተመስገን እያለ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ከችሎት ተመለሰ ።

ከጕዳት ስለ መጠንቀቅ ።

ብዙ ሰዎች ወደ ጕዳትና ወደጥፋት የሚያደርሳቸው በገዛ ራሳቸው ያሰቡትና የሠሩት ክፋት መሆኑ ከታሪክ እናገኘዋለን ። ግን አያሌ ሰዎች በታሪክ ያነበቡትንና በዜና የሰሙት ነገር፥በዓይናቸውም ያዩትና በዘመናቸው የተደረገውን ብዙ ሰዎች ወደ ጕዳትና ወደ ጥፋት የደረሱበትን መንገድ እየተመለከቱ በዚያው ጕዳና ለጥቀው ይሔዱበትና እንሮጥበታለን ያሉትን ሜዳ ማጥ ሁኖ ያሰጥማቸዋል ። ለመጭው ትውልድ ማስጠንቀቂያ ሁነው ይቀራሉ ።

ብዙ ሰዎች ባለመጠንቀቃቸውና በገዛ ክፋታቸው ባነሱትና ባሰቡት የተንኰል ወንጀል በተቀጡ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ያመክኛሉ ። ግን እግዚአብሔር ለበጎ ሥራ ይረዳል እንጂ ሰዎች ወደ ክፉ ሥራ እንዲገሠግሡ አይፈቅድም ።

እንዲህም ማሰባቸው ባይማሩና ሊገሠፁበትና ሊመከሩበት የተጻፈውን መጽሐፍ ባይመለከቱ ነው ። ተመልክተውትና አስተውለውት ኑሮ ቢሆን ግን እንሆ ዓመፀኛ ክፋትን አረገዘ ፥ ድካምንም ፀንሶ ሐሰትን ወለደ ። ጕድጓድንም ማሰና ቈፈረ ። ባደረገውም ዓዘቅት ላይ ይወድቃል። ድካሙም በራሱ ይመለሳል። ዓመፃውም በናቱ ላይ ትወርዳለች ያለው ቃል በቂያቸው ነበር ። መዝ ፯ ፲፬ ፲፮ ።

አገርን የሚያጠፉ ሰዎች አገርን የሚጠቅሙ አስመስለው መስበክና ማውራት ይችላሉ።ግን እእምሮ ያለው ሰው በፍሬአቸው ያውቃቸዋል። አገር መውደድ በሥራ መርዳትና ለሕዝብና ለመንግሥት የሚጠቅም በጎ ነገር በማሰብ ይገለጣል ። ለገዛ ራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ሰዎች ግን ወንድሞቻቸው በሕዝባቸውና በመንግሥታቸውም ሳይቀር ጕዳት ቢያመጡ ቅርታም አይገባቸውም ። ግን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስብ ንጉሥና ለሚወዳቸው ለገራሞች ሕዝቡ ይረዳቸዋል፥ይጠብቃቸዋል፥ክፉዎች ጠላቶቻቸውንም በእጃቸው አሳልፎ ይሰጣቸዋል ።

በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በግርማዊ ንጉሥም ሳይቀር የተንኰል ሥራ ሠርተው የተገኙትን ወንጀለኞች ብዙ ጊዜ ያሰቡትን ክፋታቸውን ሳይፈጽሙ በእጃቸው ጣለላቸው። እሁንም ቢሆን በቅንነት ላገራቸው የሚያስቡና ሌት ተቀን በትጋት ላገራቸው ጥቅም የሚሠሩ ናቸውና የመንግሥታችነን ጕዳት የሚያስበውን ጠላት እግዚአብሔር በእጃቸው ይጥልላቸዋል ። ክፋተኛ ሆይ ፥ ተንኰለኛ ሆይ ፥ የኢትዮጵያን ነፃነት ማጥፋት የምታስብ የራስህን ጥቅም ብቻ የምታስብ፥ ወንድሞችህንና ሕዝብህን የማትመለከት ሰነፍ ሆይ ፥ እይ ተመልከት፥ ተጠንቀቅ ፥ ከክፋትህ ተመለስ።ከክፋት ብትመለስ፥ በጎ ነገር ብታስብና ብትሠራ እግዚአብሔር ይወድሃል ላገርህና ለመንግሥትህ እንድትረዳም ኃይል ይሰጥሃል ።

አገራችን ቤታችን ናት መንግሥታችንም በአምላክ ኃይል ጋሻችንና ረዳታችን ነው ። አገራችንን እንውደድ መንግሥታችንንም እናክብርና እንታዘዝ ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ኩብኩባን ስለ ማሸነፍ ።

ልክ የሌለው ኩብኩባ ተነሥቶ መቶ ዓሥራምስት ሺ ኤክታር (አንድ ኤክታር ዓሥር ሺ ሜትር ካሬነው) የሚያህል መሬት አለበሰ ። ክዚሁ ስድሳውሺ በአልጀሪና በኰንስታተን መካከል ነው ። በዚያን ጊዜ በዚያ ያሉ የሁሉ ወገን አድሚኒስትራሲዮን ለማጥፋቱ አንድነት ሁነው እንዲሠሩ ተሰማሙ ።

ሀያ ሺ የሚያህሉ ያገር ልጆች ቤታቸውን እየተዉ በዳስ ሰፈሩ ፥ ቍጥራቸውም እየበዛ ሔደ የጦር ሠራዊት አለቆችም ለመርዳት አራት ሺ አምስት መቶ ወታደር ሰጡ ።

ኩብኩባውን ለማጥፋት የተደረገው መሰናዳት የሚያስደንቅ ነው ። ሁለት መቶ ሺ ዚንጎ ዛኒጋባ የሚሆን ፥ ሰስት ሺ ማልሐፋ (አንበጣው የሚገፈፍበት የጨርቅ ሥራ) የእሳት ነበልባልና የሚገድል መርዝ የሚወረወርበት መሣሪያም ከሁለት ሺ የሚበልጥ ነበራቸው ። ለዚሁ እርዳታ የሚሆን የቀረበ ዕቃ እጅግ ብዙ ነበር።

ኩብኩባው ባሰፈረበት ቦታ ላይ ሦስት መቶ ሀያ ሺ ኪሎ ዘይትና እንዲሁ የመሰለውን አፈሰሱበት ። የበረሀው ጥፋት ዓሥራ ሁለት ሚልዮን ያህል ይሆናል ። ግን ብዙ መቶ ሚልዮን ይድንበታል ።

በሜዳውና በተራራው በወንዙም የነበረ አንበጣ ሁሉ አለቀ ። አሁን በሆጋርና በአቅራቢያው ባለ አገር የኩብኩባ መጀመሯ ድል ማድረግ ተገኘ ይባላል። እንግዲህ በዚያ የሚበር ኩብኩባ የለም ።

እንደዚሁ ደግሞ በአሥራ አምስት ቀን ያህል የአኒስአውራጃ አገረ ገዢ በማሮክ ያለውን ኩብኩባ እንዲያጠፉ ተስፋ ይደረጋል ።

የአነሣሡ አኳኋን እጅግ ትልቅ ነገር ነው ፤ ጄኔራሎች ኰሎኔሎች፥ ወታደሮች፥የልዩልዩ ሥራ ዋና ሠራተኞች፥ቃዲዮችና ያገርልጆችም በሙሉ ቅናትና ትጋት በብርቱ ሠርተዋል። ትልልቅ ሹሞች ቤታቸውን እየተው በዳስ ወይም በድንኳን ኩብኩባውን በሚገደልበት ቦታ ዙርያ ሰፍረው ነበር ። ለአልጀሪ መሬት የመጣበት የጥፋት አደጋ ክልብ ያለፈ ሊነገር የማይቻል ነበር። ይኸው ለዘንድሮ ዓመት ተመልሷል ። በሚመጣው ዓመትም ጨርሶ ይቀራል የሚል ወሬ ከጋዜጣ አገኘን ።

በገራችን በኢትዮጵያዙሯም በቈላ በቈላው ኩብኩባ ስላለ በየቦታው መቀጥቀጥ ይዘዋል። በየቤተ ክርስቲያኑም ጸሎት ተይዟል ደግሞ ከጸሎት ጋራ ሰው ሁሉ በክተት እየተሰበሰበ ኩብኩባ ወዳለበት እየሰፈረ በመቀጥቀጥና ዘይትና ጋዝ እየገዛ ኩብኩባውን እያቃጠለ ቢያጠፉ መልካም ነው። እግዚአብሔርም እየሠሩ ቢለምኑት ይረዳል፤ የተሠራውም ሥራ የተባረከ ይሆናል ።

ጉባዔ ቃና

ነገሥተ ዛቲ ዓለም ዘበምድር ሠረገላ ሐፂን መነኑ ።
አኮኑ እንሥርት ዘበሰማያት ዴገኑ ።

ዘአምላኪየ

ለተረፈ ዘመን ይኩን ኃይለ ሥላሴ በልማደ ኖኅ በዠር ።
መተረት ጠማሪ ዜናሃ ቈጽለ ዘይት ንሥር ።
እንዘ ትብል ኀፀ ማየ ጽማዌ መሪር ።

ሚበዝኁ ።

ለሕዝበ እስራኤል አበው ከመ ይነግር ዓውዱ፣ ምልክና
ነገሥት ኄራን።
በከተማ በትሩ ሰገደ ያዕቆብ አኤሮፕላን ።
ሥርዓተ ሰማይ ክንፍ አኮኑ ተሠርዐ በዘምኒልክ መከን ።

ዋዜማ ።

ንሥር ዘተፈሪ ሚጠተ ሰላም ይነግር እዝነ ልቡና ለዘቦ።
ኤርምያስ ጽንፈ ሀገርነ ጠማሪ ወሀቦ ።
ወአመ ተበሃሉ ረቀ ለዘረከቦ ይርከቦ ።
እንሥርተ ተፈሪ ጠበብት እምኀበ አልቦ ።
ለከተማ በይፋት ተውህበ።

ሥላሴ ።

ለስምዕ አመ ተከሥታ ብርሃንና ሰላም መጻሕፍት ኃይለ
ሥላሴ ይብሎሙ ለእለ በጸጋም ሐሩ ።
ወሐሰት ነፍስ ኃጥአን ትርዕድ እምክብሩ ።
እስመ በሰላማ ለጽዮን ዘውዲቱ ጸላእቲሁ ተኃፍሩ ።
ይረውፁኂ ወይትባደሩ ።
እንሥርተ ተፈሪ ጻድቃን እንዘ ይፀውሩ ።
ምግባሮሙ በሮሜ ዘገብሩ ።

በትረ ያርክ ገብረ ኪሮስ

ማስታወቂያ ።

በነጋድራስ በሀብቴና ባቶ ምትኬ፣ ባቶ ይታጠቁ በነዚህ ሹመት ጊዜ ከርሻና ከንግድ ማስፈያ ከኢትዮጵያ ማኅበር ቤት ገንዘብ የተበደረና ዋስ የሆነ ሰው ሁሉ የተበደረውንና ዋስ የሆነበትን ገንዘብ እንዲአገባ እጣቢ እገንዘብ ሚኒስቴር ክፍል ቤት ተደርጓልና ገንዘቡን እያመጣችሁ እንድትከፍሉ ይሁን።ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚሁ እንዳስታወቅነው ቃል በቶሎ ገንዘቡን ያልከፈለ ሰው ርስቱና ከብቱ ተይዞ በሐራጅ መሸጡን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፮ ብር
ጎህ ጽባሕ	፮ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪ (ካሌንደር)	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የበገና ግጥም	፪ መሐ

የውጭ አገር ወሬ ።

ከኢጣልያ ሌጋሲዮን የሚመጣ ራዲዮ የዕለት ወሬ ።

በምባይ ፤ ከአፍጋኒስታን የሚገኙ ወሬዎች የናድሪክ ቀሐን ድሮ የአማኑላህ የጦር ሚኒስትር የነበረውን ሠራዊት ክቡልን እንደያዙ ያስረግጣሉ ። ደግሞ ሕዝቡን አዲስ ገዥ እንዲመርጥ ማሰቡን ይወራል ።

ፓሪስ ፤ የሬፑብሊክ ፕሬሲዳን በሚኒስትር በብርያንድ ተሸኝቶ ወደ ብሩክሰሌስ ዛሬ ይነግሏ ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ይገኛል ቤቴም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞ ቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ሙዲያም ባለማግኜቶና ባለባትሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ሙዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርከፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርከፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och **Karlstad**

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር ተ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ብርተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፫ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፩ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፭ ብር
ባለሰይጣን		፻፴፫ ብር
ባለ ድመ	።	፻፵፭
ባለአሀያ	።	፻፵
ባለሳቢ ግመል	።	፻፲
ባለ አንበሳ	አሜሪካ	፻፳
" "	ጃፖን	፻፴፲ብር
ሱኳር	ጁኒያ	፳፲ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፳ሳቲንም
በአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፺፬ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፹፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፈኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒካላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።ብጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።

ANTICA CASA
FONDATA NEL
1857
Borsalino

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያየሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔዶ ።

አቦካት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
5me ANNEE № 44

ሐሙስ ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 31 OCTOBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢኮኖሚያ ፖለቲክ የ፫፻፱ ገጽ ተከታይ።

ግን ወለድ ሲያድግ ጕዳቱ ለኢንዱስትሪና ለአገር ብቻ አይደለም ለባለ ገንዘቦቹ ከፒታሊስቲ ጭምርም ነው እንጂ። አስረጅ ካፒታሊስቲ አምስት በመቶ እስከ ዓሥር በመቶ ወለድ ቢፈልጉ የሚበደሩላቸው ሰዎች ጥቂቶች ይሆኑና ገንዘባቸው ሳያፈራ ተቀብሮ ስለ ተቀመጠ ብዙ ትርፍ ስለ ቀረባቸው ይጐዳሉ።ግን በዓመት ከሁለት በመቶ እስከ ሦስት ዓመት ወለድ ቢፈልጉ ሁሉ ሰው በሽቅድድም ካፒታላቸውን በሞላ ይበደሩላቸዋልና ጥቅማቸው ብዙ ይሆናል ። ኢንዱስቲትሪ ሲሰፉ ድኃ ሁሉ ሥራ አግኝቶ ይይዛል ፤ ሕዝብ ይበለጥጋልና በኤኮኖሚያ ነፃነት ይወጣል ፤ መንግሥት ይከበራል ፥ ይታፈራል ፥ ይፈራልም ። ምስኪኒቱ ኢትዮጵያ ሆይ በአንዲት ከተማ በሎንዶን ብቻ ፫፻፫ ኢንዱስትሪ ሲኖር አንዲት ስንኳ የሌለሽ እስከ መቼ ትተኛያለሽ ። ወይስ እንደምን ቢያደርጉሽ ይሆን ከእንቅልፍሽ የምትነቂ ሥልጣን ያላቸው ልጆችስ መቼ ይሆን ርኅራኄና ያገር ቅናት የምታሳድሪባቸው።?አሁን ምሳሌ ያቀረብናት እንግሊዝ ከሰማንያ ሚሊያርድ ፍራንክ የሚበልጥ በዓመት ለመንግሥታቸው የሚገባላቸው ኢንዱስትሪያቸው በማስፋት ነው።ይህን እንተውና የሒሳባችን አካሔድ ወደ መመርመር እንመለስ ።

፴፺) የኢምጥሬንዲቶሬ ትርፍ ።

በጦርነት ጊዜ የጦር አበጋዝ ሰልፍን እንደሚያደራጅ ኢምፕሬንዲቶሬም የማፍራትን ውጊያ ያደራጃል ይመራልም። የፍጥረት (ናቱራ ወይም መሬት) የካፒታል ዋናና እሱ ራሱም ሠራተኛ ሊሆን ይችላል። አሁን እኛ እኒህ ሶስቱ ሥራዎች የሚይዛቸው ከእውነተኛይቱ የኢምፕሬንዲቶሬ ሥራው ልንለያቸው ይገባናል።ስለዚህ ከሚነካው የጠቅላላ ትርፉ በላይ እሱ የመሬትን (ናቱራ) ዋነኛ እንደሆነ ሬንዲታ የምትባል ትርፍ፤ እሱ ካፒታሊስታ (ባለ ገንዘብ) እንደሆነ ኢንተሬሴ የሚባል ወለድ እሱ ራሱ ሠራተኛ እንደሆነ ሳለርዮ የሚባል ደመወዝ ልናወጣ እንችላለን ። የጠራ ዋጋ የቀረለት ፕሮፌቶ የሚባል ትርፉን ይሠራል ፤ የትኛው በችግሮኞች ዓመቶች ክሳራ ይሆናልና ስለዚህ ፕሮፌቶ የሚባል ትርፍ ከኢምፕራንዲቶሬ የሚባል ዋና (አሠሪ) ብልህነት ብቻ አይደለም፤ ግን ከገበያ አኳሆንና ከዕድልም ነው ። እንግዲያስ ፕሮፌቶ ከዕጣና ዕድል የተገዛ ነው ልንል እሳምረን እንችላለን ። አሁን በፍጥነት (ዋጋው) ያድጋል ወዲያውም በፍጥነት (ዋጋው) ዝቅ ይላል ።

አሁን ይህነን ነገር ትርጓሜ በገበያ ምን እንደሚመጣና ምን እንዲሆን በአሳባችን ማውጣት ማውረድ ነው።አንድ ዓይነት ሀብት የሚያፈሩ ብዙ ኢምፕሬዛዎች (ሥራዎች) እናገኛለን።ግን እያንዳንዱ ኢምፕሬዛ በጅምላ ብናስበው ፤ ለሀብት ማፍራት የምታጠፋው ወጭ ልዩ ልዩ ነው እንጂ ልክ አይደለም ። (እዚህ የምንናገረው አንድ አንድ ሰው የሚያጠፋው ነው እንጂ ፤ የአንድነት ማኅበር ሕዝብ ሁሉ የሚጣፋ እንዳልሆነ እናስጠነቅቃለን) ። ኢምፕሬዛ ማርጂናሌ (ወሰን ወይም መጨረሻ የምትባል ያች በጣም ከፍባለ ዋጋ (ወጭ) የምታፈራ ነች ። አሁን ይህች ኢምፕሬዛ ያች የመሸጫ ዋጋ የሚታደርግ ፥ ማለት የገበያ መሸጫ ዋጋ ታላቅ ቢሆን ፥ ማንም ባልከለከለውም ። ሌላይቱ የምታፈራ ኢምፕሬዛ ዋጋው ትልቅ በሆነባትና በመሸጫ ባልመጣችም ። ግን ኢምፕሬዛዋም የማርጂናሬ (መጨረሻ) ዋጋው ትንሽ ቢሆን ከገበያ ልትወጣ በተገደደች ። ስለዚህ ሁሉ የማርጂናሌ (ወሰን) ኢምፕሬዛዎች ፤ የሁሉ ዋጋና የመሸጫ ልዩ ልዩ የሆነ ለማፍራት ያጠፉት ገንዘብም ልክ ፕሮ-

ፊቶ (ትርፍ) ሊያደርጉ ይይዛሉ ። የዚች ኢምፕሬዛ ማርጂሬናሌ ተአምራትም ፥ ቀጥሎ ባለው ፩ኛ ሥዕል ጨምረን እናሳያለን ።



ሥዕል ፩ ።

በ(ሀ)(ለ)የተያዘች ጐባጣ መስመር የማፍራትን ጥያቄ ፤ ክሷዋ አንድ አንድ ነጥብ እያንዳንዱ ጨራሽ (ሰው) ታመለክታለች ። በ(ሠ)(ረ) የተያዘች መስመር የተገኘችን ብዛት ፤ በ(መ)(ለ)የተያዘች መስመር የሽያጭ ብዛት ያሳያሉ ። (ሠ)(ረ) እና (መ)(ለ)ልክ ናቸው ። በ (ለ)(ረ)የተያዘች መሰመር ለሁሉ ልክ የሆነ የሽያጭ ዋጋ ነው ።

በ(ሠ)(ነ)የተያዘች መስመር ፩ኛዪቱ ኢምፕሬዛ(ሥራ)ለማፍራት ያጠፋቸው (ያዋለችው) ስፔዛ (ገንዘብ) ፤ በ (አ)(ተ) የተያዘች መስመር ፪ኛተይቱ ኢምፕሬዛ ለማፍራት ያጠፋችው ፤ በ(ዘ)(በ)የተያዘች መስመር ፫ኛይቱ ኢምፕሬዛ ለማፍራት ያጠፋችው ፤ በ(ቀ)(የ)የተያዘች መሰመር ፬ኛይቱ ኢምፕሬዛ ለማፍራት ያጠፋችው ያመለክታሉ (ያሳያሉ) ።

፬ኛይቱ ኢምፕሬዛ ለማፍራት ከሁሉ የበለጠ ብዙ ገንዘብ (ስፔዜ)የምታጠፋ ነች ። እስዋ ኢምፕሬዛ ማርጂናሌ (ወሰን) ወይም መጨረሻትባላለች ። ሶስቱ ሬታንጎሎ የሚባሉ መአዝኖች በቀለም የጫርናቸውን የኤምፕሬዛ ትርፍ ያሳያሉ ። በ (ሀ)ለ)(መ)የተያዘ ስፋት የጨራሺዎች (ሰዎች)ገቢ ወይም ትርፍ ያሳያል ።

እውነት ነው፤ የአርነት (ጋራ) ባላንጣ ለኢምፕሬንዲቶሬ እስከሚቻል ድረስ ለማፍራት የሚያጠፋውን ዋጋ (ስፔዜ)ለማሳነስ ትገፋዋለች ። ወዲያውም የገበያ ዋጋ በፍጥነት ለመሸጥ ዋጋውን ዝቅ ለማድረግ ለነጋዴዎችም ትገፋቸዋለች።ስለዚህ ሁሉ ጊዜ አዲሶቹን ኢምፕሬዜ(ሥራ)ባጣም እየተከናወኑ እየሄዱ የማርጂኔ (የመጨረሻ) ፕሮፊቶን (ትርፍ) ተዘዋዋሪዎች የሆኑትን እያሰነሱ ይሄዳሉ።ኢምፕሬንዲቶሬወይም ሥራ አቀኚ የሚሰጥ ዋናጌታ ብለን የምንሠይመው አንድ ሰው ወይም ሶቼታ (ማኅበር) በፊት እንዳመለከትነው መሬት ይገዛል ወይም ይከራያል ፥ ፋብሪካ ማቆምያ ቤት ይሠራል ፤ መኪና ይገዛል ፤ ገንዘብ ከባለ ካፒታሎች ይበደራል፤ የእጅ ሠራተኞችን ሰብስቦ ያመጣል፤ማፍራትን ይመራል፤የሚበልጥ ጊዜም እንደ ሠራተኞቹ ያህል ወይም ይበልጥ ይሠራል ።ፍሬው ካገኘ ሸጦ ገንዘቡን (ብሩን)ሁሉ እሱ ራሱ ይይዘዋል ። ግን ይህ ገንዘብ የሚበልጥ በፊት ስፔዛ አውሎት አጥፍቶታል ። ማለት ለእጅ ሠራተኞች ሳላርዮ (ደመወዝ) ለቤት ኪራይ ሬንዲታ ፥ ለካፒታሊስታ (ባለ ገንዘብ)ወለድ ሰጥተዋል እነዚህን ለማፍራት ያጠፋቸው ስፔዝ(ገንዘብ) አውጥቶ እሱ ብልህና ባለ ዕድል ሆኖ ካጠፋው ገንዘብ የሸጠው የበለጠ እንዴሆነ በልጠው ፕሮፊቶ የሚባል ትርፍ ያተርፋል ።

ፕሬንዲቶሬ በራሱ አሳብና በብርዑ ጽፈት ብዙ ይሠራል። ከሸቀጥ የሚያተርፈውን ሒሳብ፥ መልካም ዓይነት የሆነ ማቴሪዮ ፕሪሜ (ያልተሠራ ነገር ሁሉ እንደነ ብረት ጠጉር ጥጥ ቆዳ የመሰለ ሁሉ) በተሻለ ዋጋ ለመግዛት፤ መልካሞች ሠራተኞች መምረጥ፤ የወጪና የገቢ መዝገብ በጥንቃቄ መያዝ ፤ እሱን የመሰለ ሁሉ በብዙ ትጋትና ችሎት ይሠራል። እውነት ነው ከእጅ ሥራ ይልቅ የማሰብ ሥራ የሚያደክምና የሚጐዳ ብርቱ ሥራ ነውና፤ በጊዜው የሠራውና በትጋቱ ልክ፥ ከተረኞች ሠራተኞች ይልቅ የበለጠ ብዙ ገንዘብ ያተርፋል ። ስለ ሆነ ግን ኢንዱስትሪ በጣም የታመነ አይደለም።በጣም ብልህና ጥንቁቅ የሆነ ኢምፕሬንዲቶሬ፤ ባልተመቸ የችግር ጊዜ ሊኪስር ይችላል ። አንድ አንድ ጊዜም ፋብሪካው ክቆመ ወዲያ፤ ያፈራው ሸቀጡን የሚፈልገው ይጠፋልና ፥ ፋብሪካው ቁሞ ቤቱን ለመዝጋት ይገደዳል። አንድ አንድ ጊዜ ደግሞ የሚገዛ ማቴሪዮ ፕሪሜ ያጣል፤ አንድ አንድ ጊዜ የእጅ ሠራተኞች ደመወዛችን አብዛልን የምንሠራበት ሰዓት አሳንስልን ሲሉ አድማ መትተው መሥራቱን ይተውታል።በነዚሁና እነዚህንም በሚመስሉ ነገሮች ሁሉ፤ ለኢምፕሬንዲቶሬ ብዙ ችግር ይደርሰዋል። ስለምን ለማፍራት ለማቆም በፊት ብዙ ገንዘብ አጥፍተዋልና ስንት ብልሆችና ትጉሆች፥ እውነተኞችና ጠንካሮች ሰዎች ናቸው ። በብዙ የማይንቀሳቀስ (የቆመ) ፍለጋ በሞላ ሕይወታቸው ሠርተው ፥ ቀስ ቀስ እያሉ ሀብታሞች ለመሆን የደረሱና ከሁሉ ገንዘባቸው በአንድ ጊዜ በድንገት ይሁን በሌላ ብዙ ልዩ ልዩ ምክንያት ከስረው ባዶ እጃቸውን የቀሩ።ስንት ሰዎች ናቸው ጥፋት ወይም በደል ሳይኖራቸው በተቀሳቀሰ ፍርድ ወይም ዕድላቸው በመከፋት የቷነኙ የተጐዱ። ስለዚህ ለኢምፕሬንዲቶሬ ከነዚህ ድንገት ለማዳንና ከነዚህ ሁሉ ስጋት ለማበረታት አይዞህ ብሎ የሚያጠናክረውና የሚያግዘው ጥግ መንግሥትና የአሲኩራጺዮኒ (የመጠበቂያ ዋስ ማኅበር) ሊኖር ያስፈልጋል፥ ይገባልም ። ሚካኤል ተሰማ።

በሚመጣው ይቀጥላል

የቅዱስ እስጢፋኖስ በዓል አከባበር ።

ጥቅምት ፲፯ ቀን የቅዱስ እስጢፋኖስበዓል ነበረና ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ባማረ ዓጀብ ወደ ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ሔዱ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም በደረሱ ጊዜ ቅዳሴ ተጀመረ።ከቅ-

ጻሴም በኋላ ታቦቱ ወጥቶ ዑደት ተደረገ።ከዑደቱም በኋላ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሕዝቡን ባርከው አሳርገው አሰናበቱት ። ከዚያ በኋላ መድፍ ተተኰሰና ታቦቱም ገባ በዓሉን ለማክበር የተሰበሰበው ሠራዊትና መኳንንት እጅግ ብዙ ነበረ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥተው በፍል ውኃ ሜዳ በኦቶሞቢል ሲጓዙ በቀኝና በግራ በፊትና በኋላ የነበረው ሠራዊት እጅግ ብዙ ነበረ። በሜዳው ግራና ቀኝም ዘበኞች ተሰልፈው እየቈዩ ሰላምታ እየሰጡ ሰልፋቸውን ያሳዩ ነበር ። እንደዚሁም ዓጀቡ እንዳማረ በዋናው መንገድ በከተማው ማከከል አድርገው በአራት ሰዓት ተሩብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ገቡ ።

ዕጣነ ሞገር ዘአለቃ ቀጸላ።

ቀዳሜ ሰማዕት ያርጐ እንቀጸ ሰማይ ዕፁተ።
ተመጠወኑ ዘጴጥሮስ መራኁተ።
ላእከነ ምሥጢር አዕይንቲሁ ድኅረ ወጠኑ ፍኖተ።
እስከ በጽሑ አየራተ።
እስመ ለፅምአሙ ሰትዩ እምነቅዓ ሕይወት ንስቲተ።
ወረከቡ ዓዲ አፍላገ ዓበይተ።
ኀይለ ሥላሴ አርአየ ለሕዝቡ ኀይላተ መንግሥት ሰብዓተ ።
፪ተ በምድር ወበሰማያት ፭ተ።
እስመ አንጎድጎደ ደመናተ።
እስከለ ማርያም ትኩን እዴሁ ፅንዕተ።
ለፈጽሞ ዘተርፈ ሥርዓተ ።

ፍልሰታ ለእቴጌ ጣይቱ ።

እቴጌ ጣይቱ ብርሃንና ዘኢትዮጵያ ከሞቱ ፲፪ኛ ዓመት መሆኑ ነው ። ወይ ሰው ምንም ኃይለኛ ምንም አዋቂ ቢሆን ምንም ጌታ ቢሆን ከሞት ወጥመድ ለማለፍ ባለመቻሉ እጅግ ያሳዝናል። ካቶ ተሰማ እሸቴ ግራማፎን (ሙዚቃ)እንደ ሰማነው ከላይ ያለውን ቆጣጥሮ የሰው መጨረሻው መደምደሚያው ሞት ይላል ። ምንም ዘመን የሰጠው ሰው ቀላል ባይሆን ካለፉት እቴጌዎች ሁሉ እንደ እቴጌ ጣይቱ ያለ ብልህና ጀግና በታሪክ ይገኝ አይመስለኝም።በጦርነት ጊዜ ከጃንሆይ ተለይተው በከተማ የቆዩበት ቀን እጅግ ጥቂት ነው ይባላል ። ይልቁንም በአድዋ ዘመቻ ጊዜ እጦርነቱ ውሥጥ ገብተው ወይዛዝሩንና ገረዶቻቸውን ሁሉ ሰብስበው ውኃ እያስቀዱ ለቁስለኛው ሁሉ ያጠጡ ነበር አሉ ። ግሩም ነው ። ሴቶች ወፍ ኮሽ ሲአረግ ነፍሳቸውን እሚአጠፉ የመጣ መስሎአቸው ወየው እናቴ ይላሉ እንጂ ከጦር መሀል ገብተው ሥራ ይሠራሉ ሲባል ከሀገራችን ሴቶች አልሰማንም ። ደግሞ በቤት ውሥጥ ሥራ በማዘጋጀት እሚመስላቸው አልነበረም። የወይን ጠጁን ሳይቀር አጅግ ያሳምሩት ነበር ። ይልቁንም እቴጌ መባልን ያዘል ማድረግ ተሸክመው ወጥቤቱና ጠጅ ቤቱ ይቅርና ወደ ማድቤቱ [illegible] ወርደው የምጣዱንና የወፍጮውን መስማማት ያዩ ነበር። [illegible] መጊዱንና ብርታትንም ለሴት ወይዘሮዎች ያስተማሩ እቴጌ ነበሩ ። አገራቸውንና ሕዝባቸውን እጅግ ይወዱ ነበር፣ የአገር ቅናትማ ነገር በሳቸው ተፈጽሟል ። መቸም ሰው እርስበርሱ በምቀኝነት ለመጣላት አያርፍምና ቤተ ሰቡ ነገር እየሠራ ከሚአጣላው በቀር ጉዳት ያገኘው ሰው የለም ። ምንም ካሽከሮቻቸው ደኅቹ አንሰው ከፋዎቹ ቢበዙ ብዙ ምሕረት እንደነበራቸው ባየሁት እመሰክራለሁ ።

ጃንሆይ ታመው እቤት ከዋሉ ወዲህ እጅጓ ከፍቷቸው አዝነው ጥቂት ጊዜ ቆይተው ነበር ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ከነገሡ ግርማዊ ንጉሥ አልጋወራሽ ከተባሉ በኋላግን እጅግ ደስ ብሏቸው ነበረ ። መቸም የሰው ነገር ይህ ነውና ። በብርቱ ታመው ግርማዊትና ግርማዊም እዚያው ሰፍረው ያስታምሟቸው ነበር ። ምንም አስታማሚ ቢበረታ ከሞት አያድንምና ሙተው በብዙ ክብር ቀበሯቸው። ተስካሩም እስከዛሬ አልታጐለም ።

ልጅ ማለት ዕድል ነው እንጂ ልጅ ያለውስ ከዚህ ወዲያ ምን ይደረግለታል እያለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትንና ግርማዊ ንጉሥን እማያመሰግን ሰው የለም ። መቸም ለምስጋና ታድለዋልና በጥቅምት ፲፯ ቀን ሌሊት ዓፅማቸውን ከተቀበሩበት ከእንጦጦ ማርያም አውጥተው ወደ ጃንሆይ መታሰቢያ ቤት በታላቅ በዓል አገቧቸው ። አምሮ በተሰናዳውም ከሮፓ በተሠራው የእብነ በረድ ሣጥን አገቧቸው ። ቅዳሴውም እጅጓ አምሮ ነበር ። ገባሬ ሠናይ ሁነውም የቀደሱት ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ነበሩ ።

እግዚአብሔር ይባርከው በሕያዋንና በሙታን መካከል ምሕረት አድርጓልና ብላ ናዕሚን (ኑኃአሚን) ቦዓዝን እንደመረቀችው እኔም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክንና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እመርቃለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።

ሥላሴ ።

ንጉሠ ሰላም ፤ ክሂል ንድቁ ለዕበይከ ።
ዓረፍተ ኂሩትከ ቅጽር አኮኑ በአምጣነ ፃሕቀየ ዓምድ ።
ወነዋህ ጥቅማ እምነዌ ማኅፈድ
ታሕተ ጽላሎትከ አዕርፍ ባሕቱ ከመ ኢይክልአኒ ባዕድ ።
ወፍሬ ኢይኅጣዕ ጊዜ ገሚድ ።
እንቲአከ ይእቲ ምድር ውሂበ መፍቅድ ።
ወዚአከ ይእቲ ልማድ ።

ሥላሴ

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡ-
ሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም ።
በንሥርከ ተፈናዊ አሐዱ ይብለከ ኤርምያስሃ ።
ወቦ ዘይብል ዮሐንስሃ ዘንሥር ።
እስመ ከነ ልደተ ዚአከ በብዙኅ ነገር ።
አንሰኬ እብለከ መሢሐ ለእግዚአብሔር ኄር ።
ኃይለ ሥላሴ መዋዒ ፀር ።
አምጣነ ኬድከ ለሞት በዘንሥር እግር ።
ወአንሣእከ ለምውት ፍቅር ። አለቃ ዳኜ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች እምሩ ታሞ መዳን ።

የሐረርና ያውራጃዋ ገዥ ክቡር ደጃዝማች እምሩ በመስከረም ፩ ር ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ጥቂት ቀን ታመው በቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ተኝተው ሰንብተው ነበር ። ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪም ወደ ሆስፒታሉ እየመጡ ብዙ ጊዜ ጠየቋቸዋል ። የእውቀት ወዳጅና ብልህ ሰውም ስለ ሆኑ ብዙ ሰው አዝኖላቸው ነበር። ይልቁንም በሐረር ከተማና በአውራጃዋ ያለ ሕዝብ ሁሉ ብርቱው ደካማውን እንዳይጠቃው ግፈኛን ዓማፀኛን ካገር አጥፍተው በፍርድም ጊዜ ድኃና ሀብታም ሳይለዩ ሁሉን አስተካክለው አስማምተው የሚገዙ ስለ ሆነ እጅግ ይወዷቸዋልና መታመማቸውን ሰምቶ እጥብቆ አዘነላቸው ። እግዚአብሔርም የሕዝቡን ጉዳት አይወድምና ልመናቸውን ሰምቶ ምሕረት አደረገላቸው ። ለጊዜውም የውጭውን አየር ለመቀበል የማይችሉ ስለ ሆነ ኃይላቸው እስቲበረታና ደማቸው እስቲበዛ ድረስ በሆስፒታሉ ትንሽ ቈይተው ነበር። አሁን ግን በሰው ኀዘንና በእግዚአብሔር ቸርነት ፍጹም ጤና አግኝተው ጥቅምት ፳ ቀን ከሆስፒታል ወጡ።

ክቡር ደጃዝማች እምሩ ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ቀናተኛና የመንግሥትም የታመኑ ዋና ረዳት በመሆናቸው በኢትዮጵያውያን ዘንድ የታወቀ ነውና ስለዚህ ብዙ ዕድሜና ፍጹም ጤናእንዲያገኙ ወደ እግዚአብሔር ልንለምንላቸው ይገባል ።

ብርሃንና ሰላም ስለ ወዳጁ ስለ ክቡር ደጃዝማች እምሩ ጤንነት ደስታውን ይገልጻል ።

ሕዝብን ስለ መርዳት ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ በየአርሻው ያለ እህል ገብቶ አገሩ ይጠግባል የገባያውም ሸመታ ተሻሽሎታል ብለን ከዚህ ቀደም ጽፈናል ። በከተማም የሚቀመጥ ሕዝብ እጅግ ብዙ ነውና የሚያስፈልገው ምግብ ካገር ቤት ተጭኖ እየመጣና እየሸመተ ነው ። እህሉም ተጭኖ የሚመጣው በአህያና በበቅሎ ስለሆነ ከቅርቡ እንጂ ከሩቅ ለማምጣት በጣም ችግር ነው ። ሸማቹ እጅግ ብዙ ስለሆነም በበቅሎና በአህያ ተጭኖ የመጣ እህል እጅግ አይጠቅመውም ። ስለዚህ በሚመጣው በጋ አገሩ ሜዳ ነውና የተጀመረው የአቶሞቢል መንገድ ጠንካራ ሆኖ እስኪሠራ ድረስ ብዙ ያቈያልና ላሁኑ መንገዱ አቶሞቢል እንደሚያስኬድ እያደረገ ጕድጓዳውን በአፈር ብቻ እያደላደለ አደጋ ያለ ቦታ ቢያገኝም እየቈፈረ እንዲያስተካክል መንግሥታችን ለየሻለቃው ቢያከፍለው እስከ ሶስት ወር ድረስ መንገዱ ተስተካክሎ እስከ ሩቅ ይደርሳልና እህል በካምዮን እየተመላለሰ ከተማው በጠገበ፡በሩቅ ያለ እህሉን ይዞ ብርና ልብስ የሚቸግረው ገበሬም ትርፍ እህሉን እየሸጠ ባለጸጋ በሆነና አስፍቶ ባረሰ ። በከተማ የሚንጋጋ መንገድ የሚጠበው ካሚዮንና አቶሞቢልም ብዙ ሥራ ባገኘ ባቡር በሚሔድበት አገር ያለ እህል በባቡር ቢመጣ ካሚዮን በሚያስኬድም አገር መንገድ ተደላድሎለት እህልና የንግድ እቃ ቢያመላልስ አገሩ ይሠለጥናል ሰውም ብዙ ሥራ ይለምዳል ሠራተኛ ይሆናል ወስላታ ሌባ መሳይም ጨርሶ እንኳ ባይጠፋ እያነሰ እንደሚሔድ ጥርጥር የለበትም። በየትም አገር ቢሆን መንገድ ሲከፈት ብዙ ደህና ሰው ይሰፍርበትና ንግድ ይለማበታል ሠራተኛም ይበዛበታል በዚያ መካከል ሌባና ቀጣፊ ቢገኝም ለመያዝ አይቸግርም አገር የሚጠበቅ ደህና ሰው ሲበዛ ነው ። ሥራ ሲያከብር ወስላታነትና ወሮ በላነት ሲያስነሳ በቆዩ ጊዜ ወስላታና ሌባ ወደ ሥራ (ክብር)ይመለስና ኑሮው ይለወጣል ።

ይህን መጻፋችን ለማስታወስ ነው እንጂ የአስተዳዳሪነት ሥራ የተሰጣቸው ሰዎች ይህ ሥራም ሥራቸው የሆነ አሉና ሳያስቡበት አይቀሩም ።

ትምህርትን ስለ ማስፋት ።

በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የተሠራው ትምህርት ቤት በመስከረም ወር ተከፍቶ ሥራው ተጀመረ በዚሁም ትምህርት ቤት መጀመሪያ አማርኛና ግዕዝ ሆኖ የኢትዮጵያ መምህራን ያስተምራሉ ። ፈረንሳዊና እንግሊዝንም የሚያስተምሩ መምህራን ማስተማር ጀምረዋል። ትምህርት ቤቱም እንዲከናወንና ሌላ ትምህርት ቤትም እንዲከፈት ክቡር አቶ ሣህሌ ፀዳሉ የጥበብና የትምህርት ዲሬክተር በሙሉ ትጋትና በልብ ቅንነት ይሠራሉ። ትምህርትና ጥበብ ባገራችን ለማስፋት እግዚአብሔር እንዲረዳቸውም እንመኝላቸዋለን ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት

ማስታወቂያ ።

ስለ አቶሞቢልና ሞቶሲክሌት ካሚዎን ቢስክሌት ጋሪ ሠረገላ ይኸንንም የመሰሉ የመንገድ ተመላላሽ መኪናዎች ሁሉ ለማዘጋጃ ቤት ግብር ስለሚከፍሉ መኪናው በመሰናከል ወይም በሌላም ምክንያት ሳይሠራ የቈዬ እንደሆነ ያልሠራበት ቀንና ምክንያቱን ከሚቆምበት ቀን ጀምሮ ከአቶመቢል ደምብ መጠባበቂያ ጽሕፈት ቤት በጽሕፈት ማስታወቅ አለበት ከዚህ በላይም እንደተጻፈው ሁሉ ስለ ግብሩ መክፈል ሊቀርለት አለመቻሉን የማዘጋጃ ቤት ያስታውቃል ። ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ።

ስለ ደጊቱ ሃገራችን ። አሳብና ምኞት ።

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ይህች ለምለም ሀገራችን ስመ ጥሩ ኢትዮጵያ እውቀቷ እየሰፋና ሥልጣኔዋ እየበረከተ እንዲሔድ እኛም ልጆቿ እውቀትን እየፈለግን ለሀገራችን ጥቅም የሚሆነውን እያሰብን መንግሥታችንን የማይጐረብጥ ሥራ እየሠራን ይኸንን የእውቀታችንን መሪ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ለዘለዓለም ያኑርልን እያልን በፍጹም ልባችን ብናስብ ቸሩ ጌታ እንዲለምነን አይጠረጠርም ግን እኛ የኢትዮጵያ

ልጆች የተቀበልነውን የማዕርግ ሥራችንን እየተውን ያንኑ ሥራችንን እያሰፋንና የጐደለውን እየሞላን እንደ መሔድ ሁሉ አለ ሥራችን ባንዱ ክፍል እየገባን እማንደርስበት ከበላያችን ያለውን ማዕርግ እየተመኘን ምቀኛነት እየደረብን የምንሠራው የተንኰል ሥራ ሁሉ ፈጽሞ ለመተው የሚአሳስበን ነው። ከቡራኖች ሆይ ከዚህ ቀደም የነበርንበትንም የሕጋጓት አንዋዋር መመልከት ነው ሁሉን እንዳልጽፈው አንባቢ ይሰለቻል ።

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ስንኳን አውቀተኛ ሀገሩን ጠቃሚ የሆነ ጉዳዩን አስታውቆ ሰራተኛም ቢሆን እንደውቀቱ መጠን አይተውየሚበቃውን ያህል ቀለብ እየበላ ይቀመጣል። እንደዚህ መንግሥታችን በትህክል ሳልጸ በየነበት ጊዜ እኛም ፍቅር እያበረከትን የልብን ክፋት ከሰውነታችን አስወጥተን በጸዋታ መኖር ሳድ እንዲሆንብን አይጠረጠርም። በ፲፱፻፳፩ ዓመት መስከረም ፳፯ ቀን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ታላቁን ማዕርግ ከተቀበሉ እስከ አሁን ድረስ ለሕዝቡና ለሀገራችን የሚስማማ እያሰቡ ማሻሻል አዲሱን ዓይነት ሥራ ለመከተል ጀምረው ያሠራሉ።ቀዳማዊ የሆነው ንጉሣችን አዲሱን የሕይወት ደምብ ገብቶት ሥራውንም ማነቃቃት ጀምሯል።ይኸውም የሥራ ድካም ከጥቂት ጊዜ በኋላ መልካም ፍሬ እንዲአፈራልን በሙሉልባችን እንመኛለን መልካም ሀገራችን ለምለም ኢትዮጵያ በውቀት መጕናጸፊያ የተጐናጸፈች አንድ ጊዜ የሥልጣኔዋን ደረጃ ስለተቀበችልን ደስ ለሚለን ሰዎች ሁሉ እኛም ልጆቿ ከመልካም ፍሬዋን እየተመገብን እሷም እየሰፋችና ሥልጣኔዋ እየበረከተ እንዲሔድልን አጥብቀን እንመኛለን ።

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ድካምና ሀሳባቸው ሁሉ በሀራቸው ጥቃትእንዳይገባ ድህነት እንዳይጫነን እኛምየኢትዮጵያ ልጆች አለአንድ ሥራ እየተቀመጥን ስንፍና እንዳይጫነን ድንቁርና ጉረቤታችን ሆኖ እንዳይቀር ነው። አሁንም መንግሥት በትህክል ለሕዝቡ ረዳትነት በተነሣ ጊዜ ሕዝቡም በተሰጠው እውቀቱ በጸጥታ እንደሚችለው ያህል መንግሥቱን እንደማገዝ በመንግሥቱ ላይ ክፉ ሥራ እየሠራ እየተገኘ ። ከተቀበለው ማዕርግ እየተዋረደ የማይገኘውን ነገር እየተመኘ በመቀመጡ ብዙን የሚአሳዝን ነው ። እንደግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ የሚረዳ በትህክል ታማኝ የሆኑ ወየውበርክት ባለው በነበሩ ። በደግየሚጠሩ ሀገር ለመበደል ያልተጠረጠሩ ።

በለጠ ።

የውጭ አገር ወሬ

ከኢጣልያን ሌጋሲዮን የመጣ ራድዮ እንደሚያወራው። የኢጣልያ የንጉሥ ልጅ ፕሪንስ ኡምቤርቶ የቤልጅግ ንጉሥ ፕሪንሴስ ማርያን ስላጩ በኢጣልያና በቤልጂግ አገር ትልቅ ደስታ ሁኖ ብዙ ፈንጠዝያ ተደረገ ። የኢጣልያ ጋዜጦችም ይህ ያሁኑ ደስ የሚያሰኝ ወሬ ለሁለቱ መንግሥታት የፍቅርን ማሠሪያ የሚያጠነክር መሆኑን እያስረገጡ የቤልጂግንና የኢጣልያንን የሁለቱን ጀግኖችወገን ያገናኙ ለፕሪንስና ለፕሪንሰስ ልክ የሌለው ምስጋናና ምርቃት ያቀርቡላቸዋል ።

በብሩክሴልም ግርማዊ ንጉሥ አልቤርቶ ስለ እጮኞቹ ክብር ትልቅ ግብር አድርገው ብዙ መኳንንቶችን ጋበዙ።

ብርሃንና ሰላምም የሁለቱ እጮኞች መጋባትና ሠርግ በደህና እንዲፈጸምላቸው መልካም ምኞቱን ያቀርባል።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጆግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኅሀ ጸባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፷ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋሰው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፷ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፷ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፷ መሐ
የሚልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፷ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፷ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፷ መሐ
አሳብና ምኞት	፵ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፵ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፳ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፳ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፳ መሐ
የበገና ግጥም	፳ መሐ

የውጭ አገር ወሬ ።

ከኢጣልያ ሌጋሲዮን የሚመጣ ራድዮ የዕለት ወሬ ።

ቦምባይ ፤ ከአፍጋኒስታን የሚገኙ ወሬዎች የናድሪክ ቀሐን ድሮ የአማኑላህ የጦር ሚኒስትር የነበረውን ሠራዊት ክቡልን እንደያዙ ያስረግጣሉ ። ደግሞ ሕዝቡን አዲስ ገዥ እንዲመርጥ ማሰቡን ይወራል ።

ፓሪስ ፤ የሬፑብሊክ ፕሬሲዳን በሚኒስትር በብርያንድ ተሸኝቶ ወደ ብሩክሰሌስ ዛሬ ይነግሉ ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ደገኛል ቤቱም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪከን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተልኩ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር ተ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ብርተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፩ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጅር	፩ ኮረጃ	፻፴፫ ብር
ባለሰይጣን		፻፴፭ ብር
ባለ ድመ ።		፻፵፫
ባለአህያ ።		፻[illegible]
ባለሳቢ ግመል ።		፻፳
ባለ አንበሳ	አሜሪካ	፻፳፱
" "	ጃፖን	፻፴፫ብር
ሱካር	ጁኒያ	፳፯ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፳፭ሳንቲም
በአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፶፬ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፷ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኲላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጆርጅ ፎቶስሉቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው





አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ ።

የወንዶችና የሴቶች ልብ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE

BORSALINO

ALESSANDRIA

(ITALIA)

MARCA DEPOSITATA

S F. FERNANDES&SONS,

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግ ማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።

አ በ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በዓርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን, እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
5me ANNEE № 45

ሐሙስ ጥቅምት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 7 OCTOBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction.
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ክቡር አባ ወልደ ኢየሱስ ዕረፍት

አባ ወልደ ኢየሱስ የቀኛዝማች አባይነህ ልጅ የክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥሌሴ ወንድም ናቸው።መነኰሴ ሁነው በደብረ ሊባኖስ ሲኖሩ ነበርና ከዚያ በኋላ ኢየሩሳሌም ሀገር ቅድስትን አይተውና ስመው ተመልሰው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቀምጠው ነበር።

ከዚህ በኋላ ከወንድማቸው ከአባ ሐና ጋራ ሁነው በግርማዊ ንጉሥ እርዳታ ቦታ ገዝተው ድሆች የሚጠሩበት ገዳም አቁመው ቤተ ሰሊሆም ብለው ሰየሙት ።

እሊህ ሁለቱ መነኰሳት ልብሳቸውንና ቆባቸውን አንድ ዓይነት አድርገው በስምምነት ሥራቸውን ይሠሩ፥ ድሆችና ደካሞችን ይረዱ ነበር ። የመስማማታቸውና የፍቅራቸው፥ የደግነታቸውናየትጋታቸው፥ለሕዝብና ለመንግሥት የማሰባቸው ነገር መጠንና ቊጥር የለውም። በዚያ በገዳማቸውም እንደ ማንም ሠራተኛ በእጃቸው እየሠሩ የሚደክሙት ድካም እጅግ የሚያስገርም ነው። በነሱ ኃይልና ብርታት የቀናው ገዳም የጥዳቱና የማማሩ፥ያታክልቱና የውኃው አገባብ አይተውት ለመጡ ፈረንጆች ሳይቀር አስደንቋቸዋል። እንድያው ጠፍ ሁኖ የነበረውንም ቦታ ገነት አድርገውታል።

እነዚህ ከሥጋ ወንድማማች ፍቅር በሚበልጥ በመንፈሳዊ ወንድምነት ፍቅር የታሠሩ ሰዎች በጥቅምት ወር ክቡር ደጃዝማች እምሩን ለማስታመም በቤተ ሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ሆስፒታል ሰንብተው ነበርና ደጃዝማች እምሩ በጎ ሲሆኑ አባ ወልደ ኢየሱስ በጠና ታመሙና በጥቅምት፳፱ ቀን በድንገት ዓረፉ። ሞታቸው በተሰማ ጊዜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን፥ ለልዕልት መነን ለታላቅ ወንድማቸው ለክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ለዘመዶቻቸውና ለወዳጆቻቸ ሁሉትልቅ ኃዘን ሆነ።

ሬሳቸውም ወደ ደብረ ሊባኖስ በአውቶመቢል እንዲሔድ ታዘዘና ግርማዊ ንጉሥ ከሠራዊታቸው ጋራ እስከእንጦጦ ጥግ ድረስ ሸኝተው ተመለሱ። ክቡር ፊታውራሪ ዓምዴ ክቡር አባ ሐና ከብዙ መኳንንትና ሠራዊት ጋራ እስከ ደብረ ሊባኖስ ድረስ አብረው ሔዱ።

ብርሃንናሰላም ስለ አባ ወልደ ኢየሱስ ጥልቅ ኃዘኑን እየገለጠ ለግርማዊ ንጉሥና ለልዕልት መነን ለወንድማቸው ለክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ለክቡር ደጃዝማች እምሩ ለወንድማቸውም ለክቡር አባ ሐና ለወንድሞቻቸውና ለዘመዶቻቸው ሁሉ ለወዳጆቻቸውም እግዚአሔር ያጥናችሁይላል።

ስለ ሕዝብ ጤንነት ።

በአዲስ አበባ ብዙ ሐኪሞች አሉ ። እኰሌቶቹ የመንግሥት እኰሌቶቹም በራሳቸው ገንዘብ ዋጋ እየተቀበሉ ያክማሉ፥ አንድ ሁለትም የሚሲዮኖች ሐኪሞች አሉ ። ሐኪሞቹ ሁሉም የሚታከም በሽተኛ ብዙ ይመጣላቸዋል ። ብዙ ሰው በተሰበሰበበት በትልቅ ከተማ ምንም ቢሆን ብዙ ዓይነት በሽታ ሳይነሣበት አይቀርም ። በኤውሮጳ እንኳ በብዙ ብልኀትና በብዙ መድኀኒት ከልክ ባለፈ መጠንቀቅና ንጽሕና የሚከላከሉ ሠራተኞችና ሐኪሞች ባሉበት ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት በሽታ እንደሚነሣ እንሰማለን ። በዚህ ከተማችን በአዲስ አበባም በየ-

ጊዜው በሽታ እየተነሣ ብዙ ሰው ይሞታል ። ሐኪሞችም የመጣላቸውን ያክማሉ፤ ወደ ጠራቸውም ይሔዳሉ ። ግን ለሕዝቡ ማስጠንቀቅያ የሚሆን ምክርና በሽታ እንዳይጋባበት በየቤቱ የሚደረግ በሽታን የሚቃወም ነገር እየጻፉ አያስታውቁም። በዚህ ምክንያትም በሽታው እየሰፋና እየሠለጠነ ይሔዳል ። ብዙ ሰዎችም ባለመጠንቀቅ ይሞታሉ ። ሐኪሞቹ ብንጽፍ የሚሰማን የለም፤ ብንናገርም እንዳስጠንቀቅነው የሚያደርግ የለም የሚል ምክንያት ይናገሩ ይሆናል ። ግን ሐኪሞች በእውቀታቸው የሕዝብን ጤንነት ጠባቂዎች ናቸውና የሕዝብን ጤንነት የሚጐዳ ነገር ባወቁ ጊዜ በቶሎ እየጻፉ ሊያስታውቁ ይገባቸዋል እንጂ ዝም ማለት አይገባቸውም። በምክርና በማስጠንቀቅ ሕዝብ የሚጐዳውን በሽታ ታልተቃወሙትና ሕዝቡም በገዛጁ በሽታን እንዲቃወም ታላደረጉ፤በሽታ ቢሰለጥን በሽተኛ ቢበዛ ሕዝቡም ቢጐዳ ሐኪሞቹ አይመሰገኑም ።

ክቡር ዶክቶር ኮንቲ ሮሲኒ ስለ ጻፉት የኢትዮጵያ ታሪክ ።

ያገራችን ሊቃውንት ስለ ቋንቋችንና ስለ ታሪካችን የተቻላቸውን ያህል ደክመውበታል። ነገር ግን ከዚህ በፊት አንድ ያገራችን ልጅ እንዳለው፤ ሊቃውንቶቻችን ብርዕ በጣታቸው መጨበጡን ባለመውደዳቸው ጽሕፈትን ያህል ትልቅ የሥልጣኔ ሥራ ጉባኤ በሚነግሩት በዋኖች መምህራን መደረጉ ቀርቶ ብዙ ጊዜ ትምህርቱ መጠን በሆነው በደብተራ እጅ በመሆኑ ያገራችን መጽሐፍ የጽሕፈት ግድፈት መልቶበት ይገኛል ። የውነት ነው ግድፈቱን ሊቃውንቱ ያርሙታል ነገር ግን ያረሞው ሥራ ደግሞ በጣት፤በብርዕ መሆኑ ቀርቶ በቃል፤ባንደበት ብቻ ስለሆነ፤ ሊቃውንቱም ሲያርሙት የሚሰሙዋቸው ደቀ መዛሙርት ቍጥራቸው መጠን በመሆኑ መጽሐፉ ከነግድፈቱ ይኖራል። ወደ ታሪክ ነገሥቱ ብናልፍ የባሰ ጥፋት እናገኝበታለን ። በኢትዮጵያ ያለን መጽሐፍ ሁሉ ወሬው ለሰሚው በሚያስገርም በቃላቸው ይዘው ካባ ላንቃ መስሎ የሚታየንን ተራ ጨርቅ ለብሰው እውቀት ካለበት ዘንድ የወደቁበት ዝኒጋባ ግርማ የተጫነው ቤተ መንግሥት መስሎ ሲታየን ለሆዳቸው ክሰው ሳይሰንፉ ለሰው እንተርፋለን ሲሉ የሚመገቡትን የመከራ እንጀራ ማየታችን እብነት ሁኖን ከብዙ ጥንክርና ሲያደርሰን ርቀት ከሞላበት ዘንድ ራሳቸው ባለ ዘውድ መስሎ የሚታይ ነው፤ አራት ጉባኤ የሚነግሩት ሊቃውንቶቻችን በቃላቸው እያቃኑ እያረሙ ከመተረክ በቀር ሥራችን ብለው የኢትዮጵያን ታሪክ የጻፉልን አይመስለነም ።

ስለዚህ ትክክለኛውን ታሪክ ነገሥት ሳናገኘው እንኖራለን ። ይህን ሁሉ ሳናይ ታሪካችንን የሰው አገር ሰዎች ቢጽፉት በተሻለ ይሆን ያሰኘናል ግን ደግሞ ይህን እንዳንል፤ ሰው ከሆነ የሥጋ ለባሽ ጉዶሎነት የሌለበት አይገኝምና በሰው አገር ሰዎችም ብዙ ግድፈት እናገኝባቸዋለን። ከሰው አገር ሰዎች ቋንቋችንን፤ጠባያችንን፤ ልማዳችንን፤ያጠፋነውን፤ያለማነውን፤አስተካክለው የሚያውቁት በጣም ጥቂቶች ናቸው ። ለራሳቸው ትርፍ ሲሉ ለመደለል ያህል ኢትዮጵያን እስከ አርያም እስከ ኢዮር የሚያደርስዋት አሉ።በንዴት፤በብስጭት ደግሞ ያላሰበችውን ያልሠራቻውን ሠርቃለች የሚልዋት ያለስምዋ ስም ያለመልክዋ መልክ ሰጥተው እንጦርጦስ የሚያወርድዋት አሉባቸው። በትክክል ያገራችንን ታሪክ የሚጽፍ የሰው አገር ሰው ሲገኝም ከመጽሐፉ ውሥጥ የሚያነቃቃ አሳብ የሕዝቡን አካሔድ የሚያድስና የሚያበረታ መንፈስ ጐድሎበት ደረቅ ሁኖ ይገኛል። ለዚህ ሁሉ ኢትዮጵያ በማናቸውም ትምህርት በማናቸውም ሥራ ራስዋን ችላ ለሰው ካልተረፈች ምንም መዳኛ አይገኝላትም። ባገራችን እስካለን ድረስ የሁኔታችንን ልኩን ሳናገኘው እንኖራለን። ከሰው አገር ስንሔድ ግን ያለበትን ደረጃ እናየዋለን የሔድንባቸው ሕዝቦችም ምቀኝነት ከሌለበት አነጋገር ታሪካችንን ለማወቅ ያህል፤ ሊቃውንቶቻችሁ ጸሐፎቻችሁ ለዓለም ምን ሠሩለት ሕግ አጋጎቻችሁ ለሰው የተረፉት ከምን ላይ ነው ጥበበኞቻችሁስ ለሰው ጥቅም የሠሩት እቃ መሣሪያ ግንብ እንዴት ያለ ነው እያሉ ያስቸግሩናል። ኢትዮጵያዊ ከሰው አገር ሲሔድ አፉን ሞልቶ በማዓረግ፤ ያገሩ ወታደር በትክክል ሥራውን መሥራቱን ሲወድቅ ሲነሣ አገሩን ለባዕድ አሳልፎ ሰጥቶ አለማወቁን አንድ አንድ ጊዜም ለወዳጁ ለወገኑ ነፃነት ሲል ደምበሩን አልፎ ከሰው አገር ሒዶ ደሙን ማፍሰሱን ነው።ይህ ትልቅ የጀግንነት ሥራ ነው ስለሆነ ይህ ብቻ እንዳይበቃ ያልተረዳው ሰው የለም ።

ነገር ግን አሁን ምስጋናና ዘለፋ ለማደል አይደለምና አሳባችንና ወደ ታሪኩ እንመለስ።ከታሪኩ በፊት ደግሞ ስለ ጸሐፊው በጥቂቱ ብናመለክት የተገባ ነው።ኮንቲ ሮሲኒ አላፊነት ከመላበት ከብዙው የቤተ መንግሥት ሥራቸው በላይ በየጊዜው የሚያሳትሙትን ለተመለከተ ሰው፤የኢትዮጵያ ልሳናት መጻሕፍትና ታሪክ መመርመር እንጂ ሌላ ሥራ የላቸውም ባሰኘው። ከሀያ ዓመት በፊት ጀምረው እስከ ዛሬ ድረስ ስለ ኢትዮጵያ የሚናገር መጽሐፍ በያገሩ ፥ በየቋንቋው እንዳሳተሙ ነው የሚኖሩ ። ኢትዮጵያን የሚያነሣ ነገር ከተገኘ ከማናቸውም ሕዝብ ቢመጣ ኮንቲ ሮሲኒ በቸልታ የሚተውት ፍጹም ጥቂት ነው። ስለ ኢትዮጵያ በቃልም በጽሕፈትም የሚተረከውን ሁሉ ካንድ ላይ ሰብስበው ዕረፍት በመያውቀው ናላቸው እንዳሰተያዩት እንደ መረመሩት፤እንደ ፈተጉት እንዳበጠሩት እንዳፈረሱት እንደ ገነቡት ነው የሚኖሩ ። ስለዚህ ከጻፉት ሁሉ ፤ ይህን ቢቀርም ግድ አልነበረም የሚያሰኝ አንድ መስመር አይገኝበትም ። ይህስ ያህል የደከሙበትን በጥቃቅን መጻሕፍትና በሊቃውንት ጋዜጣ በየዘመኑ ሲያትሙት ኑረው ዛሬ Storia d'Etiopia የኢትዮጵያ ታሪክ ብለው ሰይመውት አንዱን ክፍል ብድግ ባለ መጽሐፍ አሳትመውታል ።

ሁለተኛው ክፍል እስኪወጣ ድረስም L'Abissinia ሐበሻ ብለው ሌላ ትንሽ መጽሐፍ ለሕዝብ የምትሆን አሳትመዋል ። ከዚህ ቀጥሎ ያለው ከትንሹ መጽሐፋቸው ያመጣነው ነው። ነገር ግን ደግሞ ከዋናውና በየዘመኑ ካሳተሙዋቸው ከሌሎች መጻሕፍቶቻቸው የተቀዳ አለበት። ትንሹ የታሪክ መጽሐፋቸው እስከ መስከረም ፲፱፻፳፩ ይደርሳል። ስለሆነ ከጤ ቴዎድሮስ

በኋላ የተደረገው ለጋዜጣ አንባቦች ስንትም እያስፈልግ ብለን ትተነዋል። ሊጻፍ የተገባው ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጠባይ የተናገሩት እውነት የሆነ አሳብ ነበረበት፤ነገር ግን ላንባቢው እንዳይጐፈንነው ስንል ትተነዋል። ከሦስት ሺሕ-ዓመት የበለጠውን ታሪክ በጥቂትመስመር እስታወቅነ ስንል ከጻፍነው ሰነፍ አሳብ መስሎ ላንባቢ የሚታየው እንዳለ ስንፍናውን ወደ ተርጓሞቹ እንጅ በጠራ ንግግር ወደ ጻፉት ወደ ኮንቲ ሮሲኒ አያስጠጋብን። በዚሁ በጭሩ ቃላት ውሥጥ የማያስረዳው ወይም የማያስተውለውን ክፍል የሚያገኝ አንባቢ በጣልያን ቋንቋ የተጻፈውን ዋናውን ታሪካቸውን ይመልከት ።

ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ትውልድ ።

ቢሆንም የተሳሳተ ትርጒም ነው። እንጂ፥ ዓረቦች ሐበሺያ ሲል በቋንቋችን ደበላለቀ ቀላቀለ ማለት ነውና ሐበሻ ማለት፤ ዘሩ ትውልዱ እየብቻ ሲሆን ክንድ ላይ ተቀላቅሎ ድብልቅ ሁኖ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው የሚሉት የኢትዮጵያን ዘር ሁነታ ይነግራል ። ኢትዮጵያ የምንለው አገር ሐበሻ መባሉ ቅልቅል ስለሆነ እንዳይደለ ግን ወደ ፊት እናስረዳለን። ከአዋሽ ጀምሮ እስከ ሐማሴን ዳርቻ በዋናው ኢትዮጵያ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋንቋው ብቻ ከሴም ጋራ የተቀላቀለ ወይም ፈጽሞ የሴም ሁኖ አልፎ አልፎ ስንኳ የሴም መልክ የጐላበት ቢገኝበት የሚበዛው ዋናው ዘራቸው የኩሽ፥ የካም ዘር ነው ። ኋላ መጥቶ የሴም ዘር ቢሠለጥንበት እስከ ዛሬ ድረስ የኩሽን፥ የካምን ቋንቋ የሚናገር አለበት። መልካቸው የሴም ዘር አለመሆናቸውን በግልጽ የሚመሰክርባቸውን በኢትዮጵያ ወሰን ለወሰን ያሉትን ነገድ ስንኳ ብንተዋቸው በኢትዮጵያ ውሥጥ ሁለት ዓይነት ሕዝብ አሉ፤ ፩ኛው መልኩ የከካዝ መልክ የሚባለውን የመሰለ ፥ የቀይ ዳማ ፥ ጠጒረ ላዛ የኩሽ ዘር ነው ። ፪ኛው ጥቍረቱ ሻንቅላን የመሰለ ጠጒረ ኩርዳዳ የዓባይ (የኒል)ሕዝብ ነው። ይህን ስላልነ በብዙ ሺሕ ዘመናት ውሥጥ ሕዝብና ሕዝብ በሰላምና በጦር፥ በመጋባትም የሚገናኝ በመሆኑ ከዚህ በላይ የጠራናቸው ሁለቱ ዓይነት ነገዶች ዛሬ ጥንት የጥንት መልካቸውን እንደያዙ አይገኙም ።

ቋንቋውን እያዩ ሕዝብን በወገን በወገኑ ይከፍሉታል ። ይህ ሥራ ለታሪክ መርዳቱ እርግጥ ነው፥ ነገር ግን ብዙ ጥንቃቄ ይላል ፤ ዘሩ ትውልዱ አንድ ሲሆን ቋንቋው የተለያየ ሕዝብ አለ ። ቋንቋው አንድ ሲሆንም ትውልዱ እየብቻ የሆነ ሕዝብ አለ ። ስለዚህ ሁልጊዜ የቋንቋ መገናኘት የሕዝብን ትውልድ አንድነት፥የቋንቋ ደግሞ መለያየት የሕዝብን ትውልድ መለያየት ያመለክታል ማለት ከስሕተት ይጥላል ።

ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ቋንቋ ።

የኢትዮጵያን ቋንቋ ከ፮ ታላላቅ ክፍል ክፍሎ ፮ቱን ደግሞ ክ፵፩ ቢከፋፍሉት ይሆናል ። ፊተኛ ክፍል የሴም ቋንቋ ፤ ፩ኛ ግዕዝ ከዓረብ አገር የመጡት የአግዓዝያን ቋንቋ ኑሮ ይሆናል ይባላል ። የሴም ነገድ የሆኑት አገሩን ይገዙት የነበሩት የሐበሻት ነገድ ቋንቋም ግዕዝን ይመሳሰለው ኑሮዋል። ግዕዝን ከዓጋሜ ወደ ሰሜን ባለው ወረዳ የነበሩት ነገዶች ይነጋገሩበት የነበሩ ይመስላል።ግዕዝ ከጽሕፈት ደረጃ የደረሰ በጥራቱና በማማሩ እጅግ ከሠለጠኑት ሕዝብ ንግግር ጋራ ተፈካካሪ ሁኖ የሚኖር ቋንቋ ነው ።

፪ኛ ፤ ትግሬኛ። ይህ ቋንቋ በደህላቅ ደሴቶችና በምጥዋ፥ በሰምሐር፥ በመንሳዕ በነዚሁም አቅራቢያ ያሉት ሕዝብ የሚነጋገሩበት ቋንቋ ነው ።

፫ኛ፥ ትግርኛ በትግሬ አውራጃና በሐማሴን ፥ በጸለምትና በወልቃይት የሚነጋገሩበት ቋንቋ ነው ። ትግሬ ጥንት የነገድ ስም የነበረው ይመስላል። ትግሬኛንና ትግርኛን ባላባቶቹ የታረመ የተከረከመ ለመጽሐፍ የተገባው ቋንቋ ለማድረግ ሳይተጉባቸው ይኖራሉ ።

፬ኛ፥አማርኛ የአማራ፥የበጌ ምድር፥ የሸዋ የጎጃም፥ የዳሞት የደምብያ፥ የሰሜን ቋንቋ ነው ። ብዙ የሴም ያይደለ ንግግር ተቀላቅሎበታል ። ከሺሕ ፫፻ ዓመት ከልደት በኋላ የኢትዮጵያ ነጋሥታት መኖሪያ አማርኛ በሚነጋገሩት ሕዝብ ማኸል ከሆነ ዘንድ የመንግሥት ቋንቋ ነው ። ካምስት መቶ ዓመት ወዲህ ከጽሕፈት ደረጃ ደርሰዋል ነገር ግን አሁን በቅርቡ ይልቁንም ባዲስ አበባ የተነሣው ያገርና የወገን ፍቅር ያለበት አዲሱ መንፈስ ነው አማርኛን እያጠራ ፍጹም የጽሕፈት ቋንቋ አድርጎት ያለ ። ባላባቶቹ አማረ ካለው የመጣ የሚያምር ቋንቋ ነው የሚሉት ቃል ያጋጠመው ሕዝባዊ ትርጉም ነው።እንደ እውነቱ ባማራ(ሳይንት)ወረዳ ሲነገር ከነበረ ዘንድ ነው በወረዳው ስም አማርኛ ተብሎ ያለ።በሀረር አጠገብ የሚነጋገሩበት እየጠፋ የሚሔድ አርጎባ የሚሉት ቋንቋ ደግሞ አለ።

፭ኛ ጋፋትኛ ። የጋፋት ቋንቋ አሁን በቅርቡ ዘመናት ፈጽሞ እስኪጠፋ ድረስ ካማራ በስተ ምዕራብ፥ ከሸዋም በስተ ምዕራብ፥በጎጃምም በስተ ሰሜን ምሥራቅ ያሉት ነገዶች ይነጋገሩበት የነበረ ቋንቋ ነው።

፮ኛ ጕራጌኛ፥ የጕራጌ ሕዝብ ጥንት በወታደርነት የመጣ ቋንቋውም ካማርኛ ለትግርኛበዝምድና የቀረበ ይመስላል ።

፯ኛ ሀረርኛ የሀረር ሕዝብ ደግሞ እንደ ጕራጌው ለወታደርነት ብሎ ከዋኖቹ ኢትዮጵያውያን የመጣ ይመስላል።በሀረር ቋንቋ በዓረብ ፊደል የተጻፈ አንዳንድ መጽሐፍ አለ።ተፈጸመ የሴም ቋንቋ ።

ስለባንክ ኖት አሸራረፍ በድሬ ደዋ ።

በጥቅምት ወር ውሥጥ አንድ ጓደኛዬ ወደ ድሬ ደዋ ሲወርድ ለጕዳዩ ብሎ የ፮ መቶ ብር ባንክ ኖት ሸርፎ ይዞ ሔዶ ድሬ ደዋ ያገኘውን ችግር በሸረፋ ምክንያት ስላጫወተኝ እኔም ይኸነን ነገር ቀጥዬ በብርሃንና ሰላም ልገልጸው እወዳለሁ።

ይህ ጓደኛዬ የ፮ መቶውን ብር ባንክ ኖት ይዞ ሒዶ ነበርና ድሬ ደዋም በገባ ጊዜ ለሚያስፈልገው ጕዳዩቹና ችግሩ ይኸነን የያዘውን የባንክ ኖት በብር ለመሸረፍ አስቦ ወደባንክኖት ቤት ሔደና ባንኮችን ምንዛሪ ጠየቃቸው ባንኮችም ይህ የባንክ ኖት የገዛ ገንዘባቸው መሆኑን እያወቁ የ፮ መቶውን ብር ባንክኖት፥ በብር ለመለወጥ ፲፩ ብር ኮሚሲዮን ጠየቁት ይኸውም የሚሸርፈው ሰውዬ ይህ ባንክ ኖት የገዛ ገንዘባችሁ ነው በገዛ ገንዘባችሁ ላይ ይህነን ፲፩ ብር ኮሚሲዮን ከጠየቃችሁኝ አል

ሸርፍም ብሎ ትቶ ሔደና ደግሞ በከተማ ውሥጥ ወዳሉት የኢትዮጵያ ነጋዴዎችና ባለገንዘቦች ዘንድ ሔዶ ሸረፋ ቢጠይቅ በ፩ መቶው ብር ፲ ብር ከሚሲዮን ከባንኮች ግማሽ የሚሆን ጠየቁትና ሸርፎ ጕዳዩንና ገበያውን ገብይቶ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰና ይኸነን ያገኘውን ችግርና ኪሳራ አጫወተኝ ።

ደግሞ ከሁን ቀድሞ ብዙ ሰዎች ወደ ድሬ ደዋ ሲወርዱ ለስንቃቸው የሚሆን የባንክ ኖት እየያዙ እየወረዱ እዚያ ያለ ኮምሲዮን አንሸርፍላችሁም እያሉን በነጻ የምንሸርፍበት ስላጣን ባንክ ኖቱን ይዘን ተመለስን እያሉ ሲያወሩና ሲያጫውቱኝ ሳሉ ለጊዜው ነገሩን ለማስረገጥ ሳለሁኝ አሁን ይሀ ጓደኛዬ ወርዶ ባገኘው ነገር እርግጥነቱን ለመረዳት ቻልኩኝና ይኸንም ለመጻፍ አሰብኩኝ። እንግዲህ ባንድ መንግሥት ውሥጥ ባንኩ በራሱ አላፊነት ያወጣውን ማርክና ገንዘብ መልሶ ያለኮምሲዮን አልቀበልም ሲል ይህ ጥፋት የሕዝቡ ነውን ወይንስ የባንኩ ነው፥ ይኸነን ነገር መርምሬ ለማወቅና ለመረዳት ለብቻዬ የማይቻለኝ ስለሆነ ለብርሃንና ሰላም ለሰፊው ጉባኤ አቀርብ ዘንድ ወደድኩ ።

በቀለ ዘለቀ ።

የኢኮኖሚያ ፖለቲክ የ፫፻፶፰ ገጽ ተከታይ ።

ምዕራፍ ፯ ፥

፴፰ የዋነኛ (ባለ ገንዘብ ጸጋ ሰው) አዘራዘርና ትርፍ።

የፍጥረት ጥቅም ሀብት (መሬት ሚኔራል የመኪና ኃይል) ዋኖች ሰዎች ከእውነተኞቹ ካፒታሊስቲ ልንደባልቃቸው አይገባንም ። እነዚህ ቤኒ የሚባሉ ሀብቶች እንደነ የመሬት ስፋት ወይም ሚኔራል (መዓድን) በብዙ መሥዋዕትና ድካም ሊያድጉ የማይችሉ ናቸው።እኒህ ቤኒ የሚባሉ የፍጥረት ሀብቶች ያሉዋቸው ሰዎች ሀብቲቱ ሁሉዋ እስክትያዝ ድረስ በአርነት (ባላንጣ) የተያዙ ናቸው ። ማለት መጀመሪያ የነበረች የፍጥረት ሀብት (መሬት) ሁሉዋ እስክትያዝ ድረስ ግን ሕዝቡ እየበዛ ሲሔድ ወይም የፍጥረት ከብት ፈላጊ ሲበዛ ዋጋን ከመስጠት የተሠራች አይደለችም። ስለምን ቤኒ የሚባሉ መሬትና ለጥቅም የሚሆን ያልተሠራ ነገር ማቴርዬ ፕሪሚ የሚባሉ ሁሉ የተወሰኑ ናቸው ። ግን ከኦፌርታና ደማንዳ (ማቅረብና ጥያቄ) ስለ ሆነ የሚገዛ ዋጋን እንደጥያቄው ብዛት መጨረሻ የሌለው እያደገ ይሔዳል ። ስለዚህ የፍጥረት ሀብቱ (መሬት) ጌቶች የነሱ ቤኒ (ጸጋቸው) የተወሰነ ባይሆን ከሚገባቸው በላይ ሬንዲታ የሚባል ትርፍን በብዙ ባተረፉ ነበር፤ ማለት የመሬትን ተፎካካሪ ኮንኩሬንሳየለበትምና።ሕዝቡ እያደገ ሲሔድ ማቅረብና ስጦታ (ኦፌርታና ደማንደ) ያው ነው ። መሬት ልታድግ አትችልምና ያነን ለዋጋ የሚያመዛዝን ወይም የሚሠራና የሚያቆም ስጦታና ጥያቄ ከሌላ ሬንዲታ (ትርፍ) በጣም ብዙ ይሆናል ። አስረጂ ከ፴፫ ዓመት በፊት በአዲስ አበባ ጥቂት ሰው ሳለ የአራዳ መሬት ዋጋው ዝቅ ያለ ርካሽ እንደነበረ ዛሬ ሕዝቡ ሲበዛ ግን እንዴት ውድ እንደሆነ የሚሠወርበት ሰው የለም ይሆናል። እንዲሁም ከአሁኑ ይልቅ ከተማው እያደገ ሲሔድ ከመቶ ዓመት በኋላ ስንት ጊዜ የሚበልጥ ዕጥፍ ዋጋ እንደሚያወጣ ግልጥ ነው ።

ቤኒ ናቱራሊ የሚባሉ የጥቅምን ፍጥረት ዋነኛ ሰው ካፒታሊስትም ሊሆን ይችላል ስለምን የማፍራትን ጸጋ (ቤኒ) አጥፍቶዋልና ። እንዲሁ የአንድ መሬት (ቀላድ) ጌታ ለማፍራት መሬቱን የሚያሰናዱ ሠራተኞች ማለት፤ ማስተካከል፥ መሬቱን ጕርፍ እንዳይነቃቅለው ለማገጃው ቦይ ለማግባቱ ለመንገድ መጥረጉና ፍግ መነስነሱ ባጭሩ ለማልማቱ ብዙ ገንዘብ አጥፍተዋልና ። ይህነን ሁሉ ካፒታል የዋለበትን ያመለክታል ። ስለዚህ ለዋነኛው መሬቱን ለማልማት ያዋለውን የካፒታል ወለድ ይገባዋል።ያነን ሬንዲታ የሚባል ትርፍ ከፕሮፊቶ የሚባል ትርፍ በላይ ለእሱ የሚገባለት ከቀላሉ ወለድ ፈንታ ነው ። ስለምን መሬቱ ተይዝዋል፣ ሕዝቡ ግን እያደገ ይሔዳል ።

ዋነኛው ሰው ከሚገባው በላይ የሚወስደው ትርፍ ሦስት ዓይነት ነው ። ፩ኛ የሞኖፖል ሬንዲታ የሚባሉ ትርፍ ፤ በብዛታቸው የተወሰኑ ጥቅሞች። ፪ኛ የስፍራ ወይም ቦታ ምቹት ሬንዲታ ፤ ማለት ፤ ዋኖቹን ከሚገባቸው በላይ የሚወስዱትን ጥቅም ፤ መሬታቸውን በከተማ አቅራቢያ ፤ ወይም (በፖርቶ) መርከብ መቆምያ አጠገብ፡ወይም በመላለክያ መንገድ የተመቸ የቀናና ተደልድሎ የተጠረገ መቃረብያ መንገድ ያለበት ጥጓ። ፫ኛ፡ሬንዲታ (ትርፍ) ደግሞ የመሬቲቱን ብልጫ፡ከሌላው ይልቅ ፍርያምነትና ብዙ ሚኔራል (የብረትዘር ሁሉ) ስላለበት ነው ።

በሚመጣው ይቀጥላል ። ሚከኤል ተሰማ።

የውጪ አገር ወሬ።

ባለፈው ሳምንት በሮማ የፋሺስት የሰባተኛ ዓመታቸው በዓል ተደርጎ ክቡር ሙሶሊኒ የፋሺስት መሪ ፋሺስት ከተጀመረ እስከሁን ድረስ የተሠራውን ለሕዝብ ጥቅም የሚሆን ሥራ እያስታወሱ ፤ ሕዝቡን የሚያነቃቃና የሚያበረታታ ንግግር ተናገሩ።ሕዝቡም ንግግራቸውን በደስታ ተቀበለ፥ከንግግሩም በኋላ የሰንደቅ ዓላማው መወዛወዝና የሕዝቡ የደስታ ውካታ እጅግ የሚያስደንቅ እንደነበረ ከኢጣሊያን ራድዮ አገኘን ።

እውነት በኢጣልያን አገር የፋሺስት ወገን ከተነሣ ከቀድሞ የበለጠ የወንድምነት ፍቅር ፤ አንድ ወገን ሕዝብ ባንድነት እንደ አንድ አካል ሁኖ ሩቁም ቅርቡም፤ ላገሩ መንግሥትና ሕዝብ ባንድ ልብ ማሰብና መርዳት እንዲገባ በጣም ተሰማው። በኤውሮጳ አገር አንዳንዱ መንግሥታት የሕዝብ ታላላቆች ባለመስማማታቸውና እንደ ክቡር ሙሶሊኒ ያለ ያገሩንና የመንግሥቱን ሕይወት ከፍ ለማድረግ ፤ የራሱን ሕይወት እንደ መሥዋዕት አድርጎ የሚያቀርብ ብርቱ ወንድ በማጣት ኃይላቸው የደከመና የሰነፉ ይገኛሉ ። በዚሁ ፈንታ የኢጣልያን አገር ባገር ውሥጥ ያለውና በውጭ አገር ያለው የሙሶሊኒን ስብከት እያዳመጠ ሁሉም ያገሩን ሕይወት መርዳት እየተሰማው በያለበት ራሱን ያነሣ ጀመር ። ሕዝቡ በመላው አገሩን ለመርዳት የተሰናዳ ሁኖዋል ። በገንዘብም ደርጅቷል፥ እግረኛና ፈረሰኛ፤ የባሕርና የአየር ወታደር ስንዱ ሁኖ የአገሩን ነጻነት እንዲጠብቅ ተዘጋጅቷል።የፋሺስት ወገን እንዲህ ሁኖ አገሩንና መንግሥቱን በማበርታቱ ለብዙ መንግሥታት የያሚስቀናቸው ሁኖዋል።

የምሥጋና ቃል ።

አብርሃም ያስተማረው ሳይኖር ተመራምሮ ፡ ፈጣሪውን አውቆ እንደ ወደደ ። እኔም ባገር ቤት ሁኜ በከተማ ያለውን የሥልጣኔ አካሔድ ሳላይ መንገደኛ የያዘውን ጋዜጣ አይቼ በልቤ ተመራምሬ ለብርሃንና ሰላም ወዶ ገባ አሽከሩና የታመነ ወዳጁ እኔ ነኝ፤ ነገር ግን እኔም ከተማ ገብቼ የወንጌል ሥራ ስለ ያዝሁና ለጽሕፈት ባያደርሰኝ ብርሃንና ሰላምም ዜኖች አብዝቶ ችሎት እየዋለ ሳንጻጻፍ ጥቂት ብንዘገይ ለሰው የተለያየን እንዳይመስለው ጥቂት ማስታወሻ እጽፋለሁ። ይልቁንም የቴየዎች አለቃ። የሃይማኖት ጠበቃ ለብርሃን ኢትዮጵያ እቴጌ ጣይቱ በዓለ ፍልሰት ከበረላቸው ማለትን ብሰማ የበላሁት ያንቀኛል፤የጠጣሁት ያነዘኛል ብዬ ለመጽሐፍ አሰብሁ። እቴጌ ጣይቱ ባመት ለካህን ፲ ቀን ምሉ ግብር ከበሉ በኋላ ትርፍያ አንድ እሑድ ደብረ ኃይል ራጉኤል፤ አንድ እሑድ መንበረ ፀሐይ ማርያም። ጽጌን ብመላው ለካህን ግብር ያበሉ ነበር ።

ከሁሉ ይበልጣል የተፈሪ አውቀቱ ። ሥራቸው ብርቱ ነው ግርማዊት ዘውዲቱ ። ይኸ መታሰቢያ ምንድር ነው ብልሃቱ ። ሳይገጠም ቀርቶ ባንድ ወገን መስኮቱ።በጃንሆይ አጠገብ ወድቃለች ጣይቱ ። በሰማይ በምድር አልተገኘም አንዳች ። ምነዋ ብቻዋን ጣይቱ ያለፈች ። ምንኛ ተጐዱ. ወይዘሮ አሰለፈች ።

ሥላሴ

ለሳዖል ኢያአምሮ ማዕከለ ነዋይ ዘተኀብአ ።
ሶበ ቀተሎ ጥበብ በኩናተ ብርሃን ጽሩይ ።
ወፈትሕዎ ጳጳሳተ ግዕዝ እምኵሉ ጌጋይ ።
አኅጻረ አትናቴዎስ ሊቀ በክሂሎቱ ዓቢይ ።
ሥያሜ ክህናት ይሰመይ ።
ኃይለ ሥላሴ ጸለየ መንገደ ሰማይ ።
ወአዋመቀ ልበ ሰብእ በማይ ።
አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኃዘን

የከተማ ወሬ ።

ከአዲስ አበባ ወደ ደሉባበር የአይሮፕላን መነሣት ።

ክቡር ራስ ናደው በድንገት ታመው ጠንቶባቸዋል ብሎ አሽከራቸው ፊታውራሪ መኰንን የሚባለው በስልክ ወደ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አስታውቆ ነበርና ግርማዊ ንጉሥም ይኸንን በሰሙ ጊዜ አዝነው ወደ ክቡር ራስ ናደውም እግዚአብሔር ይማርዎ የሚል ቃል አሳለፉ ።

ሕመማቸውም እያደር እየጠናባቸው ሔደ ስለተባለ ፤ ጐሬ ያሉትም ሐኪሞች እረዳት የሚሆን ሐኪም ቢመጣልን መልካም ነው ስላሉ ፤ ግርማዊ ንጉሥ የቤተ ሳይዳ ዋና ሐኪማቸውን ዶክቶር ማይምበርግን በአይሮፕላን ሔደው ጐሬ ካሉት ሐኪሞች ጋራ ሁነው እንዲያክሙ አዘዙዋቸው ።

ዶክቶር ማይምበርግም የግርማዊ ንጉሥን ትእዛዝ በደስታ ተቀብለው ፤ የሚያስፈልገውን መድኃኒት ሁሉ አዘጋጅተው ትላንትና በጥቅምት ፳፪ ቀን ከጧቱ በ፬ ሰዓት ተኩል ወደ ይሉባበር ርግበ ተፈሪ በሚባለው አይሮፕላን ተጓዙ ። የግርማዊ ንጉሥም አሳብ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን ክቡር ራስ ናደው እዚያው ታክመው እንዲድኑ፤ ይህም ባይሆን ሐኪሞቹ መርምረው ወደ አዲስ አበባ ይዘዋቸው እንዲመጡና እዚህ እንዲታከሙ ለማድረግ ስለሳቸው ለዚሁ ለአይሮፕላኑ የሚገባው አልጋና ፍራሽ ተሰናድቶ ሔዷል ።

ባይሮፕላኑም ላይ የተሳፈሩ ዋናው ነጂ ሙሴ ባሮን ኤንግልና መካኒሲያው ሙሴ አስሚት፤ ዶክቶር ማይምበርግ ፤ ደግሞ አቶ ካብትህ ሃመር የሚባለው ስልከኛ አገሩን የሚያውቅ ስለሆነ የመንገዱን አኳኋን በማሳየት እንዲረዳ አብሮ ተሳፍሯል። ይኸውም አይሮፕላን ወደ ክቡር ራስ ናደውና ወደ ሹማምንቶቻቸው። ወደ ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠውና ወደ ክብርት ወይዘሮ ተናኘወርቅ የተጻፈ ፖስታና ሌላም ኮሊ ይዞ ነበር ።

ነገር ግን አይሮፕላኑ ወደዚያ ሲሔድ ጉምና ጭጋግ ስላስቸገረው ጅማና ጉማ ደግሞ ጉማይና ሳዬ ከሚባለው አገር ደርሶ ያለችግር ወደዚሁ ተመልሶ ጊዜው ስለ መሸበት እነሞር ከሚባለው ቦታ ላይ አድሮ ጥቅምት ፳፫ ቀን ሐሙስ ከጧቱ በ፪ ሰዓት አዲስ አበባ ገባ።

አሁንም የክቡር ራስ ናደው ሕመም ተጠይቆ የሥልኩ ምላሽ ሲመጣ የሚያስፈልግ ነው ብለው በስታወቁ ጊዜ ነገ በጥቅምት ፳፬ ቀን ሊሄድ ተዘጋጅቷል ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዞርባስ በኢትዮጵያና በጂቡቲ የሲንጄር የስፌት መኪና ኩባንያ ዋና አለቃ፤ ማኅበሩ ሲንጄር ማኒፋክቱር (የሲንጄር የእጅ ሥራ) ከምፓኒ መባሉ ቀርቶ አሁን የሲንጄር ሸዊንግ ማሺን ከምፓኒ (የሲንጄር የስፌት መኪና ማኅበር)ተብሎ መጠራቱን ያስታውቃል።ይህ የአሜሪካ ማኅበር በኢትዮጵያ አዲስ አበባ የሥራ ዋና ጽሕፈት ቤቱ በልጅ እማኙ ቤት በኢምፔሪያል ሆቴል አጠገብ ሁኖዋል።ደግሞ የሚሸጥ እቃ የሚቀመጥበት በድሮ ሲንጄር ቤት በተባለ ያገር ልጆች የብርና የወርቅ ሥራ በሚሸጥበት ገበያ ነው ።

AVIS.

Monsieur Zorbas Manager de Singer Sewing Machine Company pour l'abyssinie et Djibouti a l'honneur de porter à la connaissance du public que la société connue sous le nom de The Singer Manufacturing Company a changé de dénomination et s'appelle actuellement Singer Sewing Machine Company, société américaine ayant le siège de ses affaires en Ethiopie à Addis-Abeba en l'immeuble Lidje Ymegnou près de l'hôtel Impérial et son magasin de vente à l'ancien emplacement du magasin de The Singer Manufacturing Company, Magasin situé sur le Marché des bijoux indigènes.

የውጭ አገር ወሬ ።

ከኢጣልያ ሌጋሲዮን የሚመጣ ራድዮ የዕለት ወሬ ።

ቦምባይ ፤ ከአፍጋኒስታን የሚገኙ ወሬዎች የናድሪክ ቀሐን ድሮ የአማኑላህ የጦር ሚኒስትር የነበረውን ሠራዊት ከቡልን እንደያዙ ያስረግጣሉ ። ደግሞ ሕዝቡን አዲስ ገጋር እንዲመርጥ ማሰቡን ይወራል ።

ፓሪስ ፤ የሬፑብሊክ ፕሬሲዳን በሚኒስትር በብርያንድ ተሸኝቶ ወደ ብሩክሰሌስ ዛሬ ይነሣሉ ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪክ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ የቅባኑግ(ዘይት)መዓዛው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለምግብ የተስማማ በሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን ቤት ደገኛል ቤቴም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሙሴ ዜርቦስ ቤት ፊት ለፊት ነው ። ዮሐንስ አሳዱርያን።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC SbE&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተልኩ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፫ ብር ተ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ብርተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፫ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፩ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፳፫ ብር
ባለሰይጣን		፻፳፭ ብር
ባለ ድመ ።		፻፶፫
ባለአህያ ።		፻፵፫
ባለሳቢ ግመል ።		፻፳
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፳፱
“ “ ጃፓን		፻፳፫ብር
ሱካር	ጁኒያ	፳፯ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፳፭ሳንቲም
በአንድ ብር	፰ ሊሬ ከ ፶፬ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፩ ከ፺ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵

ዓለም

ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።ብጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ

ANTICA CASA
FONDATA NEL
1857
Borsalino

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዮሐንስ አሳዱርያን የሚያወጡትን የሚበላ ዘይት ስለፈተንሁት እጅግማለፊያ የሆነ ጣዕሙም በጣም የተስማማ ነው ፤ ለሰውነትም ጤና የሚሰጥ መሆኑ የተፈተነ ነው ።

ፊርማ በጅሮንድ ዘለቀ ።

ፔር ዳኔይ ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጄዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በማርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
5me ANNÉE № 46

ሐሙስ ኅዳር ፬ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 14 OCTOBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ክቡር ኮንቲ ሮሲኒ ስለ ጻፉት
የኢትዮጵያ ታሪክ ።
ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ቋንቋ የ፫፻፹፪ ገጽ ተከታይ ።

ሁለተኛ ክፍል ፤ የአገው ቋንቋ ። አገውኛን የኩሽ ቋንቋ ደግሞ ይሉታል ። አገው ማለት ከሤም በፊት በኢትዮጵያ ይኖር የነበረ ሕዝብ ቅሬታ ነው ።

፰ኛ ፤ የመካከለኛው ኢትዮጵያ ቋንቋ ። ከነዚህ ዋናው የካሚር ቋንቋ ነው ። ይህም ካሚር የላስቶች ብቻ ነው ። ብዋግና በሰቈጣ ጥቂት ከካሚር የተለየ ንግግር አለ ። ከትግሬ በቦራ ሰለዋ፥ ባበርገሌ ደግሞ ካምታ የሚባል አገውኛ አለ ።

፱ኛ ፤ ብሌን ወይም ቦጎስ ። ይህ የከረን ቋንቋ ነው ። ሕዝቡ ባ፲፭ኛው መቶ ዓመት ግድም ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከላስታ ወደ ከረን ያለፉ ይመስላል ።

፲ኛ ፤ ጥንት በደምቢያ አገውኛን የሚመስል ንግግር ነበረ ። በቋራ እስከ ዛሬም አለ ። በወገራ ካይልኛ የሚሉት ንግግር ነበረ ፥ በስሜንም ካይልኛን የሚመስል ቋንቋ ነበረ ። የዚህን ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ በጐንደር፥ በጭልጋ አፋፍ ዛሬውንም ቅማንቶች አሉ ። ዳግመኛም ፈላሾች በጸሎት መጻሕፍታቸው ቋረኛውንና እርሱን የሚመስል ቋንቋ ከግዕዝ ጋራ ጽፈው ያቈዩት አለ ። በዚህ ባ፲ኛው ቍጥር የተጠሩት ቋንቋዎች ከላስትኛው ለብሌንኛው ይቀርቡታል።

፲፩ኛ ፤ አውያ የተባለ ንግግር በአገው ምድርና በዳሞት አለ ።

ሦስተኛ ክፍል ። ከኢትዮጵያ በስተ ሰሜን ያሉት የኩሽ ቋንቋዎች ።

፲፪ኛ፤ ቤጂያ (ሐባብ፤ በሽያር ፥ ሀዶንዶዋ) ብን ዓምር። ሐለንጋ የተባለው የከሰላ ንግግር ከብን ዓምር ጥቂት ይለያል።

አራተኛ ክፍል ። በኋላ ዘመን የመጣ ኩሻዊ ቋንቋ ።

፲፫ኛ ፤ ሻሁኛ ። ሻሁ በአክለ ጉዛይ ደምበርና በሽመዛናይ፥ በዓጋሜ ያሉ ነገዶች ናቸው ። ከነዚህ እገላ እንደማሉት ያሉና ሌላ ብዙ ነገዶች ዛሬ ትግርኛ ሁነዋል ቋንቋቸው ። ሌሎቹ ደግሞ እንደ መንሳዕና መሬያ ያሉ ነገዶች ትግሬኛ ሁነዋል ንግግራቸው ። ከሻሁ ጋራ የሚዛመዱ ንግግሮች፤ ዓሳውርታ፥ ሚና፥ ኢሮብ ናቸው ።

፲፬ኛ ፤ አፋርኛ ፥ ወይም የደንከሊ የአዳል ቋንቋ ከብዙ ይከፋፈላል ።

፲፭ኛ ፤ ሶማልኛ ፥ ካራት ይከፈላል ።

፲፮ኛ፤ ጋልኛ ፥ የጋልኛ ቋንቋ ሥሩ አንድ ሲሆን ከብዙ ይከፋፈላል ። ዋኖች ክፍሎች ፤ ወሎኛ ፥ ኢቱኛ ፥ ጐጄብኛ፥ የሸዋ ጋልኛ ናቸው ።

አምስተኛ ክፍል ሲዳማኛ ። ሲዳማ አገሩም ቋንቋውም ፬ክፍል ነው ።

ፊተኛ ፤ የምዕራብ ሲዳማ ፥ በዚህ ስም የሚጠሩ እኒህ ናቸው ።

፲፯ኛ፤ የከፋ ቋንቋ ከነዘመዶቹ።

ሁለተኛ የኦሞ ሲዳማ ፥ በዚህ ስም የሚጠሩ እኒህ ናቸው።

፲፰ኛ፤ ወላሞኛ ።

፲፱ኛ፤ ዳውሮ ከወላሞኛ ጋራ ይመሳሰላል ። ይህን ቋንቋ የሚነጋገሩ ነገዶች መኖሪያቸው፥ ጎፋ ፥ ዛላ ፥ ዶኮ ፥ ዶሎ፥ ኡባ ፥ አራ ኰሎ ፥ ነው ።

ሦስተኛ የምሥራቅ ሲዳማ ፥ በዚህ ስም የተጠሩ እኒህ ናቸው ።

፳ኛ፤ ከምባታ ከነዘመዶቹ ።

፳፩ኛ፤ ሃዲያ ወይም ጉዴላ ከነዘመዶቹ ።

፳፪ኛ ፤ ሲዳሞ ።

፳፫ኛ ፤ ጋጻሞቦ (ሀሩሮ ።)

፳፬ኛ ፤ ከይራ (ባዲቱ ።)

አራተኛ የሰሜን ሲዳማ በዚህ ስም የተጠሩ እኒህ ናቸው።

፳፭ኛ ፤ ጄንጀሮ ፥ ያንጋሮ ፥ ዬማ ። ሲዳማ ጋላ ።

፳፮ኛ ፤ ባምባላ ።

ስድስተኛ ክፍል ። ኒላዊ (ያበይ ዳር ቋንቆች ።)

፳፯ኛ ፡ ሱዳንኛ (የበዣ ቋንቋ)

፳፰ኛ ፤ ባርያኛ ። ባርያ የሚባለው ነገድ ከሐማሴን ወደ ምዕራብ ከኩናማ ወደ ሰሜን ያለው ነው ። ይህ ነገድ ይሸጥ ይለወጥ ከነበረ ዘንድ ስሙ በማርኛና በትግርኛ ቋንቋ የነገድ ስም መሆን ቀርቶበት እንድያውን በወርቅ የተገዛ አገልጋይ ማለት ሁኖ ቀርትዋል ።

፳፱ኛ ፤ ማዖኛ ።

፴ኛ ፤ መካንኛ ።

፴፩ኛ ፤ ኬሬኛ ።

፴፪ኛ ፤ ሙርሴኛ ።

፴፫ኛ ፤ ቡሜኛ ። ከዚህ ቀጥለው የሚመጡት ልክቸውና ያልታወቀ ቋንቆች ናቸው ።

፴፬ኛ ፤ ጉንዛኛ ። ጉንዛ በአገው ምድር ምዕራብ አጠገብ ያለው ሻንቅላ ነው ።

፴፭ኛ ፤ ገሚላኛ በሰናርና በኢትዮጵያ ማኸል ያለው የሻንቃላ ንግግር ነው ።

፴፮ኛ ፤ ማሰንጎኛ በከፋና በሱዳን ደምበር ።

፴፯ኛ ፤ ናኦኛ ።

፴፰ኛ ፤ የሺ ወይም የሺ ጊሚራ ቋንቋ ።

፴፱ኛ ፤ የዲማ ቋንቋ ።

፵ኛ ፤ ዲሜኛ ። የዱሜ ሕዝብ ትውልዱ ለብቻው ቢሆን ከቋንቋው ጋልኛ ተቀላቅሎበታል ።

፵፩ ከንሰኛ ከንሶ ትውልዱ ወደ ሻንቅሎች ቢሆን ቋንቋው ጋልኛ አለበት።በጣም አሳጥረን ያመጣነው የክቡር ኮንቲ ሮሲኒ ቋንቋ አከፋፈል ከዚህ ላይ ያልቃል ይህና ይህን የመሰለው ምርምር ሁሉ ላገሩ እኛ እንቀርብ ነበርና ሥራው በኛው ላይ መሆን ይገባው ነበር ።

ግን ወደፊቱ ግርማዊ ንጉሣችንን ያሰንብትልን እንጂ በእግዚአብሔር ረድኤት ከብዙም እንደርሳለን እያልን በተሥፋ እንኖራለን ።

የሕዝብ ዘርና ቋንቋ መለያየት ላንባቢ የሕዝብን አንድነት የሚለያይ አይምሰለው፡ ሕዝብ ማለት ወገን ማለት የፈረንሳዊው ሊቅ እንዳለው መልኩና ቋንቋው፡ሃይማኖቱም አንድ ስለሆነ አይደለም።አንድ ወገን የሚባል፡ ሕዝብ ወገን ማለት ያንዱ ጉዳት ላንዱ፡ ያንዱ ጥቅም ላንዱ የሚተርፈው ሁኖ ከባልንጀራው ጋራ አንድ ወገንነቱ በልቡ የተሰማው ሁኖ ከዚህ ቀደም ባንድነቱ መከራንና ደስታን አብሮ ተካፍሎ ለወደፊቱ የሚመኘው ደግሞ አንድ ሲሆን ነው አንድ ሕዝብ አንድ ወገን የሚባል ። በተቀረው የፈረንሳዊ ሊቅ እንደሚለው ሕዝብና ሕዝብ አንድ ወገንነቱ በልቡ ተሰምቶት ባንድነት ገመድ ታሥሮ ከሚኖርበት ሒደው መልክህና ቋንቋህ እየብቻ ነውና ልለያይህ ቢሉት ወይም ሕዝብና ሕዝብ ወገን ለይቶ መገናኛ አጥቶ ሲዋጋ ሒደው ፊት አወራረድህና ጭንቅላትህ፡ አፍንጫህም ቋንቋህም የዚያኑ የምትዋጋውን ሕዝብ ነውና የሚመስል ወንድማማች ናችሁ አትዋጉ ብለው የሰዋስውን መጽሐፍና ያፍንጫ መለኪያ ሜትር ይዘው ቢሔዱ ነገሩ የሚያስቅ በሆነ። አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ወገን የመሆኑ አሳብ ከልቡ ይደር እንጂ ትውልዱ፡ ቋንቋውና መልኩ ቢለያይ አንድነቱ አይፈርስም ይህን አሳብ ሳትረሳ አንባቢ ሆይ ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣውን አንብብልኝ ።

ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ።

ጥንት በኢትዮጵያ ሲኖር የነበረ ሕዝብ ነገደ ኩሽና ሥልጣኔው በጣም ዝቅተኛ የሆነ የኒል ሕዝብ ነው ። አንዳንዱን አውራጃ አገር ግብፃውያን ለዘመቻ መጥቶው ሲበዘብዙት ነበር። ይልቁንም ሽሕ ፭፻ ዓመት ከክርስቶስ በፊት ሀትሼፕ ሱት በግብፅ ከነገሠችበት ዘመን ጀምሮ ከዚያ በኋላ እስከ አምስት መቶ ዓመት ድረስ ኢትዮጵያን ዱና ሲመቱት ይኖሩ ኑርዋል ። ግብፃውያን ግን ዛሬ ኢትዮጵያ (ሐበሻ) የምንለውን አገር ሲገዙት እንደነበሩ ምስክር አልተገኘም ።

ከኤርትራ ባሕር ማዶ የነበረው የሤም ነገድ ጥቂት በጥቂት ለንግድ ሲል ባሕር እየተሻገረ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የጀመረ ከዘመን ክርስቲያን በፊት ነው ። የመጣበት አገርም በዚያን ዘመን እጅግ ሠልጥኖ ከነበረው ከየመን አውራጃ ነው፡ እንግዲህ ከመጣበት አገር ሁኖም በየመን አውራጃ ላለው ለሳባ መንግሥት ዜጋ ሁኖ ሲኖር እየበዛና እየበረታ ሒዶ ከዘመን ክርስቲያን በፊት ራሱን የቻለ መንግሥት ሆነ።ይህን አዲስ መንግሥት የየመን ሕዝብ የሐበሻት መንግሥት ይለው ነበር፤ወደ ኢትዮጵያ ለመጣው ነገድ ዘመድ የሚሆን ሐበሻት የተባለ ነገድም ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ፫ኛው መቶ ዓመት ድረስ በየመን አውራጃ ይገኝ ነበር ። ወደ ኢትዮጵያ ከመጣው የሤም ሕዝብ አንዱ ሐበሻት ወይም ሐበሳት ይባል ነበር። ፊትም ኋላም ኢትዮጵያ ሐበሻ መባልዋ ምክንያቱ አገሩን ከያዙት ነገደ ሤም አንዱ ሐበሻት በመባሉ እንደሆነ ገና እንግዲህ ጥርጥር የሚነሣበት ነገር የለም ። ይህን አዲስ የሤም መንግሥት ያቆመው ሕዝብ ፊት አስቀድሞ ሰፍሮበት የነበረ ወረዳ በዓጋሜ በሽመዛናይ በአከለጉዛይ ግድም ነው ። ኋላ ግን እስከ ሐማሴን ዳርቻ እስከ በለስ ፤ እስከ መረብ ያለውን አገር ሁሉ ይዞት ነበር። ዋና ከተማውንም አኵስም ላይ ቈርቍሮ በከተማው ስም የአኵስም መንግሥት ይባል ነበር ። ሌላው ስሙ ደግሞ ግዕዝ አዓጋዚ ነበር። አኵስም በስተ ሰሜን የነበረው የመሮዌ መንግሥት ሲደክም ተከዜን፡ ዓባይን ፤ እየተከተለ ሒዶ ብዙ አገር አቅንቶ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን እስከ ፪፻ ዓመት ክክርስቶስ ልደት በኋላ የአኵስም ሕዝብ የጥንት አገሩን የመንን ፤ ሳባን ሳይረሳ ባሕር እየተሻገረ ከጥንት ዘመዶቹ ጋራ ሲጠያየቅ፡ከጭቅጭቃቸው ሲገባ አንዳንድ ጊዜም በጦርነት ሲረዳ፡ሲገዛቸው ፥ ሲያስገብራቸው ይኖር ነበር ። ኋላ ግን ወገኑ ድል ሁኖ ጦሩን ማስወጣት ግድ የሆነበት ይመስላል ።

አኵስም ከሮም መንግሥት ጋራ ብዙ ግንኙት አልነበረውም ፡ ተራርቀው ከሚኖሩበት ጋን ብዙ ፍቅር የነበራቸው አይመስልም ። አኵስም ሮምን ቢያጣው በበሕርም በምድርም ዜጎቹንና ፍቅረኞቹን ሲያውክበት የነበረ ይመስላል ። በሶርያ አገር በፓልሚር አውራጃ ባላባቱ ሸፍቶ ለሮም አንገዛም ሲል ፤ የአኵስም መንግሥት ከመፀኛው ጋራ ቃል ኪዳን ተጋብና ከግብፅ አጠገብ የነበሩትን ብሌሚይ የተባሉትን ሕዝብ በሮም መንግሥት ላይ እንዲነሡ አደረገበት።ይህም ሥራ ዓመፀኛው የፓልሚር ባላባት ግብፅን እንዲይዝ ጥቂት ረድኤት ሆነው ። ኋላም አውሬልዮስ ቄሣር የፓልሚርን ባላባት ድል አድርጎ ባጀብ ወደ ሮም ከተማ ሲገባ ከማረካቸው ሠራዊት ውሥጥ አኵስማውያንና የመናውያን ከ፫ኛው ረድፍ ተሰልፈው ከምርኮኞቹ ጋራ እንደ ገቡ በዘመኑ የነበሩት ባለታሪኮች ጽፈዋል ። በዚሁ ዘመን አኵስም እንደ ገና ወደ የመን ዘምቶ ድል አድርጎ ገዝቶት ንጉሡ የአኵስም፤የሳባ፡የሒምያር፡የረይዳን ንጉሥ አሰኝትዋል ። ጥቂት ቈይቶ አኵስም መሮዌን ድል ነሥቶ ከመንግሥቱ ውሥጥ ደርቦታል ። ደግሞ ከጥቂት ዘመን በኋላ ተከዜ ዓባይ ባወረደ ብዙ አገር አቅንትዋል። በ፬ኛው መቶ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ኤዛና በተባለ ንጉሥ ዘመን የክርስቲያን ሃይማኖት አኵስም ገባ፡ አዲሱ ሃይማኖት የአኵስምን መንግሥት እንደ ገና ወደ ዓረብ አገር ከመዝመት አደረሰው ። በየመን አገር ይልቁንም በናግራን ባላባቱ የአይሁድን ሃይማኖት ተቀብሎ በክርስቲያኖች ላይ መከራ ሲያመጣባቸው ጊዜ ፤ አፄ ካሌብ ከአኵስም ተነሥቶ ፡ ባሕር ተሻግሮ አይሁዳዊውን ንጉሥ ድል አድርጎ በተዋጋበት አገር አብርሃ የተባለ አሽከሩን ሹሞ አኵስም ተመለሰ ። ከዚህ ጦርነት በኋላ የአኵስም ንጉሥ ለጥቂት ጊዜ ያህል ለምሥራቅ ክርስቲያን ጋሻ ሁኖት ኖረ ። አብርሃ በየመን አገር እጅግ ሠልጥኖ ኖረ።ጥቂት ቈያይቶም በየመን አገር ራሱን የቻለ የኢትዮጵያ መንግሥት አቆመ ። ከቍስጥንጥንያ መንግሥት ጋራ ፍቅረኛ ነበርና የቍስጥንጥንያን ንጉሥ ለመርዳት እስከ መካ አጠገብ ጦር አስከትቶ ሔዶ ነበር ። ቍርአኑ ከመቶ አምስተኛው ሱራ ላይ ስለ ዝሆን የሚለው የአብርሃን ዘመቻ ሳይሆን አይቀርም ይባላል ። የፋርስ መንግሥት ከየመን ባላባቶች ጋራ ተባብሮ አብርሃን ድል የመታው ጊዜ የአኵስም መንግሥት ትልቅ ጕዳት አገኘው ። ጥቂት ቈይቶ እስላሞች የደህላቅን ደሴት ወሰዱበት። ጥቂት ቈይቶ ምጥዋን ጭምርት የያዙበት ይመስላል። ጥቂት ቈይቶ ጥንት አንሥቶ ወዳጁ የነበረው የብሌሜ መንግሥት በቍስጥንጥንያውያን እጅ ለሁለጊዜው ጠፋበት ። ቀጥሎ በሱዳን ምሥራቅ (አኵስምን)የማይወደው ሕዝብ መጥቶ ሰፈረበት ። ቀጥሎ እስላሞች ግብፅን ይዘው ከሕዝበ ክርስቲያን ለዩት ። ቀጥሎ ቤጃያ የተባለ ሕዝብ በስተ ሰሜን መጥቶ አገሩን ሳይቀር ደፈረበት ፤ አያሌውንም አጋምሶ ያዘበት ። በዚህ ሁሉ ጥንታዊው የአኵስም መንግሥት አልወደቀም እንጂ ሥራው እጅግ ይሰናከልበት ጀመር ። የመን የጥንት አገሩ ባዕድ እየሆነበት በመሔዱ እንደወትሮው በየጊዜው የሜም ዘር አኵስም ከያዘው አገር ሕዝብ ጋራ እየተቀላቀለ የአፍሪቃውን ዘር ማደስና ማበርታት ፈጽሞ ቀረበት ። የኵሽ ዘር የሆነው እየበዛ የሜምን ዘር እያጣፋው ይሔድ ጀመር።ቈይቶም የአኵስም መንግሥት ጋሻውን ሲነሣ ሥልጣኔው ከርሱ ወዳነሰው ወደ ደቡብ ፊቱን ሲመልስ እናየዋለን እንጂ ወደ ሰሜን ወደ ምሥራቅ ሥልጣኔ ወደ ደመቀበት አገር መዝመቱን ፈጽሞ ይተወዋል ። ወደ ደቡብ ግን በ፲ኛው መቶ ዓመት ከክርስቶስ በኋላ እስከ ዜይላ ድረስ አገር አቅንትዋል ።

ከዚህ ዘመን ቀጥሎ የሚመጣው የኢትዮጵያ ታሪክ ፈጽሞ ጨለማ ነው ። በወላሞ ግድም የተነሣች ያረመኔ ንግሥት አገሩን አጥፍታዋለች ። በሽሕ ፻፹፩ ዓመት ክክርስቶስ በኋላ ፥ ከዶንጊያ ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናትን ያሠራው የላሊበላ ወገኖች ላስቶች አልጋ ይዘዋል ። በ፲፪፻፸ ዓመት ግድም በማራ ሳይንት ሲገዛ ከነበረው ሹም የተወለደው ይኵኖ አምላክ አልጋ አዛውርዋል። ይኵኖ አምላክ ከሰሎሞን እወለዳለሁ አለ ይኵኖ አምላክ ከአኵስሞችም እዋለዳለሁ አለ ። አኵስሞችም ትውልዳቸው የየመን ባላባቶች መሆን ቀርቶባቸው የሰሎሞን የልጅ ልጆች ተባሉ ። ይህነን ለማስረዳት ይስሐቅ የአኵስም ንቡረ እድ የሳባ ንግሥት ወደ ሰሎሞን የሔደች ጊዜ ፀንሳ መመለስዋን ካገርዋም ስትደርስ ምኒልክ የተባለ ልጅ መውለድዋንና ሌላ ሌላ ይህን የመሰለ ልብ ወለድ ታሪክ በ፲፫፻፲፱ ዓመት ግድም ጻፈ ። ቤተ መንግሥቱም ሰሎሞናዊ ተባለ ። እንግዲህ ወዲህም እኛም በታሪክ የኢትዮጵያን ቤተ መንግሥት ሰሎሞናዊ እንለዋለን ።

ሰሎሞናውያን አልጋ ሲይዙ አገራቸው በሰላምና ባረመኔ ተከቦ ነበርና ዋና ሥራቸው አረመኔውንና እስላሙን በትክክል ከመንግሥታቸው በታች እንዲገዛ ለማድረግ ሆነ ። ዓምደ ጽዮንና ዘርአ ያዕቆብ አዳልን አቅንተው አስገብረውታል።ዓምደ ጽዮን ከብዙ ሥራው ዳሞትንና ሌላ ሌላ አውራጆች ከኢትዮጵያ መንግሥት በመደረቡ በውነት የሰሎሞናውያንን አልጋ ያጠና እርሱ ነው ። ዘርአ ያዕቆብ እስላሞችን ከመውጋት ሌላ በኢትዮጵያ ያለ የመንግሥት ሥራ ሁሉ ባንድ በርሱ ፈቃድና ትእዛዝ እንዲሔድ አድርጓል ። የሃይማኖት ሥርዓታት አሻሽልዋል ። በርሱ ትጋት አያሌ መጻሕፍት ተተርጕመዋል። እንደዚህ እንደ ገና ከፍ ከፍ እያለ ሲሔድ የነበረው መንግሥት፡በልብነ ድንግል ዘመን እስላሞች ይሠሩታል ተብሎ ያልታሰበ አደጋ መጣበት።በሀረር አውራጃ አውራ ሁኖ የነበረው ኢማም አሕመድ በን ኢብራሂም (ግራኝ)አዳልንና ሶማሊን ይዞ ኢትዮጵያን ገለባበጣት። አገሩ በእሳት፤ ሕዝቡ በሰለት አለቀ ። ከአኵስም ሕዝብ የተረፈው የሥልጣኔ ጥሪት ሁሉ ሠጠመ። መንግሥቱ እንድያውን ሊጠፋ ነው ሲባል ገላውዴዎስ ባባቱ በልብነ ድንግል እግር ተተክቶ ይከላከል ጀመር ። ወዲያው ከፖርቱጋል አገር ፬፻ ነፍጥ ያዘው ኤውሮጳውያን መጡለት። ግራኝ በነፍጥ ቈሰለ ወደቀ ። እርሱ ሲወድቅ ጦሩ ተበታተነ አብሮትም የስላሞች ሥልጣን መዳረሻው ጠፋ ። በዚህ ጦርነት ክርስቲያኖች ድል መምታታቸው የተደላደለ ነው።እስላሞች ድል መሆናቸው ጥርጥር የሌለበት ነው ።ነገር ግን ኢትዮጵያ መትነፍዋ ደግሞ እርግጥ ነው ። በርዋ ለባዕድ ሕዝብ ተከፈተ ። ከወቢ ጠንዝ

ማዶ አርበኞችዋ መዳረሻ ነሥተው አግደውት ሲኖር የነበረው ጋላ እንደ ጐርፍ ፈሰሰባት። በጥቂት ዘመን ጋላ ኢትዮጵያን አጥለቀለቃት። የጋላ ሕዝብ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ የሥልጣኔ ወሬው የደረሰለት ስንኳ አይመስልም ነበር ። አገራቸው ከንዲህ ያለ ጥፋት እንዳይደርስ ለመጠበቅ ችሎት የነበራቸው ነገሥታት ስንኳ ገና ነበሩ። እንሆ ሠርፀ ድንግል እስላምን ዳግመኛ ራሱን ሊያነሣ ሲል ለሁለጊዜው እንዳያስበው አድርጎት ነበር። ቱርኮችን ድንቅኛ አድርጎ ወቅቶዋቸው ነበር። ፈላሾችን ድል መቶ አስገብርዋቸው ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ጋሎች እነርሱን ጭምር ወደ ሥልጣኔ ዝቅተኛ ደረጃ ይዘዋቸው እንዲወርዱ አላስተዋሉትም ነበር ። ዳግመኛ ሰልፈኞች ይሁኑ እንጂ የሠራዊት አስተዳደራቸው አስቸጋሪ ነው ። ከዚህ በላይ በዚያው ዘመን የሃይማኖት ክርክር ተነሥቶ ሕዝቡን እርስ በርሱ አለያይቶት ነበር ። በዚህ በዚህ ምክንያት ባገራቸው መመከት ለጊዜው አቃታቸው ። እንሆ በሱስንዮስ ዘመን ጋሎች እየገፉ ሲሔዱ ሕዝቡ ድምበሩን በመጠበቅ ፈንታ በሃይማኖት እርስ በርሱ ሲዋጋ ነበር። ጐንደር እስከ ፻፹ ዓመት ያህል የነገሥታት መኖሪያ በሆነችበት ዘመን ሁሉም የኢትዮጵያ አረማመድ እንደ ጥንቱ የጠነከረ አልነበረም ። የውነት ነው አድያም ሰገድ ኢያሱ የሥልጣኔን አካሔድ እንደ ገና ከሥር ጀምሮት ነበር ። ነገር ግን እጅግ ብልህ የነበረችው እቴጌ ምንትዋብ ከምድረ ቋቢው የነበሩትን ጋሎችና ወገኖችዋን ቋረኞችን ይዛ በጐንደር ቤተ መንግሥት ሥራ ከገባችበት በኋላ መሳፍንቱ እንደልባቸው በዘውዱ ያዙበት ጀመር ። ሥልጣን ያለው ባለ ዘውድ ፈጽሞ ጠፋ ። በየውራጃው ራስ ራሱን የቻለ መስፍን ተነሣበት። አነ ስሞች የጣሉት የሥልጣኔ መሠረት ደንጊያም በመሳፍንት ዘመን እንደሆነው ሁኖ ከዝቅተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ደርሶ አያውቅም። ነገር ግን ከበሽታው ማኽል መድኃኒት ተገኘለት ። ኢትዮጵያን አንድ አድርጌ ከጥንተኛው መዓርጓዋ ልመልሳት የሚል ካሳ የተባለ ሰው ከቋራ ተነሣ። ካሣ በጥቂት ጊዜ በያገሩ የነበረውን መስፍን ድምጥማጡን አጠፋው። ቴዎድሮስ በሉኝ ብሎም ዘውድ ጫነ ። ቴዎድሮስ ማለትም ከዓለም ፍጻሜ በፊት ኢትዮጵያን አስማምቶ ገዝቶ በዓለም ሁሉ ላይ እንድትሠለጥን ያደርጋታል ተብሎ በኢትዮጵያ ንግርት ያለውን የንጉሥ ስም ነው የነበረ። አፄ ቴዎድሮስ በከንቱ አይደለም በዚህ ስም ጥሩኝ ያለ ኢትዮጵያን አንድ የማይለያይ መንግሥት አድርጎ ለማስኬድ እግዚአብሔር እንደ ላከው በፍጹም ልቡ እንደሃይማኖት አድርጎ ይዞት ነበር ። አልጋ እንደያዘው ሁለት ትልልቅ አሳብ ከፍጻሜ ሊያደርስ ጀመረ። ፩ኛ የኢትዮጵያን አንድነት፤ ፪ኛ የሕዝብ ክርስቲያንን አንድነት። ይህን አሳብ ለማስተዋል በዘመኑ የነበሩት ያገሩ ልጆች አቅም አልነበራቸውም። በሽታ ከባሰዎችና እጅግ ከሚያስለቅስ የጭከና ሥራ እስኪያደርሰው ድረስ ለአፄ ቴዎድሮስ ወንድነት የጦር ስልት፣ የአእምሮ ስፋት ባንድነት ተሰጥቶት ነበር። ኢትዮጵያን አንድ መንግሥት በማድረጉ ጥርጥር ሊገባበት የማይቻል ብርታት ያለበት ትልቅ ሥራ የፈጸመ ንጉሥ ነው ። የዛሬይቱን ኢትዮጵያ የመሠረተ ማነው ቢባል ቴዎድሮስ ማለትም የተገባ ነው ።

ክቡር ኮንቲ ሮሲኒ ካወጡት የኢትዮጵያ ታሪክ ከብዙው ጥቂቱ ይህ ነው ። ከዋናው መጽሐፋቸው ባገራችን ከሚተርከው ጋራ የሚጣላም፣ የሚስማማም ብዙ አለበት ። እነ ምናልባት፣ እነ ድንገት፣ እነ እንዲህ ሳይሆን አይቀርም ፣ እነ እንዲህ ይመስላል ከመጽሐፉ ብዙውን ስፍራ አሰፋፍተው ይዘውታል ። ይህም የሊቅ ፣ የመርማሪ ፣ የጥንቁቅ ሰው አነጋገር መሆኑን አእምሮ ያለው ሁሉ ያስተውለዋል ። የኢትዮጵያ ታሪክ እመረምራለሁ ፣ እጽፋለሁ ለሚል ሁሉ ይህ መጽሐፍ ዋና መሆኑን እናስገነዝባለን ። ይህን ስንል ላንባቢ ባገራችን ታሪክ ነገሥት መኖሩን ያጣነው መስለን እንዳንታየው ። የሰው አገር ሊቃውንት የጻፉትን ተመልክቱ የሚያሰኘን ፣ ባገራችን ያለው ታሪክ ነገሥት ታርሞ ፣ ታድሶ ፣ ታትሞ በሰፊው ካልወጣ ዘንድ አልጥመን እያለ ነው እንጂ ፣ ከብዙዎች ነገሥታት የያንዳንዱን ታሪክ የሚነግር መጽሐፍ በኢትዮጵያ መኖሩን አልሳትነውም ። በዘመኑ የነበሩት የኤውሮጳ ሊቃውንት እንደሚመሰክሩለትም የበጌምድሩ ባላባት ደጃዝማች አሼቴ ኃይሉ ያን ሁሉ ታሪክ ነገሥት ካንድ ላይ ሰብስቦ ባጭሩ እንዳወጣው አግኝተነዋል ። ከርሱው መጽሐፍ እያስቀጣጠሉም የእስከ ዛሬውን ታሪክ የሚነግሩ በማርኛም፣ በግዕዝም የተጻፉ መጻሕፍት መኖራቸውን አደላድለን ይዘናል ። የዛሬውን ትውልድ አእምሮ የሚያጠግብ ታሪክ ለመጻፍ ያሰቡ፣ ሥራውንም የጀመሩ ሊቃውንት እንዳልጠፉብን ተረድተነዋል ። ይህ ሁሉ ቢሆን ጠንካራ ምርምር የበዛበት ፣ አዲስ መንፈስ የተዘራበት የኢትዮጵያ ታሪክ ገና አልወጣልንም ። ክቡር አለቃ ታየ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ብለው ያወጡት እንደ ማስታወሻ ያለ መጽሐፍ አለ ። በዚሁ መጽሐፍ ደጋፊ ምስክር አልባ ያመለከቱትን አሳባቸውን የሚያስረዳ ሰፊ የኢትዮጵያ ታሪክ ጽፈው ነበር ፣ ነገር ግን ለሕዝብ ሳያስታውቁት ሳያሳትሙት ሞት ከቀደማቸው ዘንድ መጽሐፋቸው መክፋት መበጀቱን ለማወቅ ይቸግረናል ። ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ፣ ከመጽሐፋቸው መቅድም እንደሚሉት ፣ ዋናውን ብዙ ዘመን የደከሙበትን ታሪክ እስኪያወጡ ድረስ ዋዜማ ብለው ሰይመው አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ አሳትመዋልና፣ የዚህ ዋዜማ ክብረ በዓሉ የደመቀ እንዲሆን ተስፋ በማድረግ እንጠባበቃለን። ተአምራት አማኑኤል።

የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ክቡር ዶክቶር ፕሩፈር የሹመት ወረቀታቸውን እንዳስረከቡ ።

ጥቅምት ፳፰ ቀን ክቡር ዶክቶር ፕሩፈር የጀርመን መንግሥት ሚኒስትር ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ የሹመት ወረቀታቸውን ሲያስረክቡ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ ።
ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

ከእኔ በፊት የነበሩት ሚኒስትር ሙሴ ዋይስ መመለሳቸውንና ደግሞ እኔ ልዩ መላከተኛ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆኜ መሾሜን የሚያመለክቱ ደብዳቤዎች ዛሬ ለግርማዊነታችሁ በማክበር አቀርባለሁ ።

ሙሴ ዋይስ ከተመለሱበት ቀን ጀምሮ የጀርመን ሌጋሲዮንን ሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ታምኜ ስሠራ፤ ያለፉትን ጊዜያቶች ሳስብ ፤ ለኢትዮጵያ ገዦዎች ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ሙሉ የወዳጅነት አሳቤን ከመግለጽ በቀር ሌላ አሳብ በልቤ አይገኝም ።

በዚሁ በሁለቱ ዓመት ውሥጥ ብዙ ጊዜ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በደግነታችሁ ለእኔ ያላችሁትን መልካም አሳብ ተመልክቻለሁ። በሁለቱም መንግሥቶች መከከል የቈየውን ወዳጅነት ለማፅናትና ለማስፋት ሥራዬ ስለ ሆነ ለዚሁ አሳቤ የኢትዮጵያ መንግሥት በመልካም ምኞች ተከፋይ መሆኑን ዘወትር ተረድቻለሁ ።

አሁንም የጀርመንና የኢትዮጵያ ፍቅር ያለችግር እስከሁን ስለ ቈየ ወደ ፊትም ይህነኑ ፍቅር ለማፅናትና ለማጥበቅ ተመርጬ ስለ ተሾምሁ እጅግ ደስ ብሎኛልና እንዳለፈው ጊዜያት ከፍ ያለ እምነታችሁ በእኔ ላይ እንዲኖር ሙሉ ተስፋ አለኝ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ፤ ግርማዊ ንጉሥ ሆይ፤ እጅግ ላማረች ለኢትዮጵያ ለምለምነትና ሰላም፤ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ረጅም ዕድሜና መልካም ጤና ከፍጹም ልቤ የምመኘውን ጥልቅ የሆነ ምኞቴን እገልጻለሁ ።ጥቅምት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ፕሩፈር።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ ።

የጀርመን ሬፑብሊክ መንግሥት ከእርሰዎ አስቀድመው የነበሩት ሚኒስትር ወደ ሌላ ስፍራ መዛወራቸውን ያስታወቀበትንና ክቡርነትዎን በእኛ ዘንድ ልዩ መልክተኛ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርጎ የሾመበትን ደብዳቤ ስንቀበል ለዚህ ሹመት በመመረጥዎ ደስ ብሎናል ።

የጀርመን ሬፑብሊክ መንግሥት ጕዳይ ፈጻሚ ሁነው ባገራችን በተቀመጡባቸው ባለፉት ሁለት ዘመናት ውሥጥ የኢትዮጵያንና ፤ የጀርመንን መንግሥት መልካም መገናኘት እያጠበቁ ለመሔድ ዘወትር አሳብዎ መሆኑን እኛም ተረድተነዋል። ደግሞ ወደ ፊት በዚሁ አሳብ እየተመሩ፤ ከዚህ ይበልጥ እየሰፋና እየጠበቀ እንዲሔድ የምንመኘውን፤ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በሁለቱ መንግሥቶች መከከል ያለውን የወዳጅነትና የጥቅም ማስተሣሠሪያ እያፀኑ ይሔዳሉ ብለን እናምናለን።

የእኛም ፍጹም አሳባችንና ምኞታችን ይኸው ስለ ሆነ በወዳጅነት አሳብ የሚመራ ይህ ሥራዎ እንዲከናወን የሚገባ እርዳታችንን አናጐድልብዎትም ።

ክቡር ሆይ ለእኛ ለራሳችንና ለአገራችን ስላቀረቡልን መልካም ምኞት እያመሰገንን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በራሳችን ስም ሁነን እንኳን ደስ አለዎ እያልን ለጀርመን አገር ልማት የምንመኘውን መልካም ምኞት እንገልጽልዎታለን።

ስለ ሹም ሽር ።

ንጉሡንና መንግሥቱን የሚያገለግል ሰው መቸም ቢሆን ዋጋውን አያጣም ።

ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ በጃንሆይ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የአዲስ አበባና የጐንደር ከንቲባ ተብለው ተሹመው ነበር ። ቀጥሎም በኢትዮጵያ የሚኒስትርነት ሹመት ሲጀመር በከንቲባነት ላይ የርሻና የመሥሪያ ቤት ሚኒስትር ተብለው ተሹመው ነበር ።

በኋላ ደግሞ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዘመን ደጃዝማች ተብለው ያገር ግዛት ሚኒስትርነት ተሹመው ሲኖሩ አሁን ደግሞ በኅዳር ፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም በደጃዝማችነታቸውና በገር ግዛት ሚኒስትርነታቸው ላይ የደብረ ጽዮንን ንቡረ እድነት ጨምረው ፤ ራስ ወርቅ አሥረው፤ ካባ ላንቃ አልብሰው የወርቅ ጥልፍ ጫማ አጫምተው አረንጓዴ ጥላ አሲዘው ስለ ሾሟቸው የማዕርግ ስማቸውም ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ዘውእቱ ንቡረ እድ ዘደብረ ጽዮን ተባለ ።

ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ በቀድሞ ግዛታቸው ላይ ያሩሴን አበጋዝነት ተሾሙ።

ክቡር አፈ ንጉሥ አረጋይ በያዙት አገር ላይ ዋዩን ተሾሙ።

ክቡር ደጃዝማች መኰንን ተወንድ በላይ ጅሩንና ፈሪሶ ጥፍርን ተሾሙ ።

ክቡር ፊታውራሪ በየነ መርድ በረዳን ተሾሙ ።

ክብር ልጅ ዘውዴ አባኰራ ቀኛዝማች ተብለው ቆጫን፤ የፊታውራሪ ሳዘው ጅማን የነበረውን ተሾሙ ።

ክቡር ቀኛዝማች ፍቅረ ሥላሴ በሶን ተሾሙ።

ክቡር ግራዝማች ደምሴ ጎፉ የፊታውራሪ በየነ የነበረውን ግዛት ተቀብለው የሸምበልነት ተሾሙ ።

ክቡር ባሻ ጌታሁን የዕቃ ቤት አጋፋሪነት ተሾሙ ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለህገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጆዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር

ኅሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፰ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጀ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጸሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፰ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፯ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፯ መሐ
የማልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፯ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፰ መሐ
የቀን መቁጠሪ (ካሌንድር)	፯ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፈደልና ፈደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የበገና ግጥም	፪ መሐ

የርሻና የንግድ ማስፈፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

KONIAK
COGNAC SaE&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden).
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ፣ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተልኩ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር ተ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ብርተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፱ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፯ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፳ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጸር	፩ ክረጃ	፻፸፰ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፬ ብር
ባለ ድመ ።		፻፵፰
ባለአህያ ።		፻፵፫
ባለሳቢ ግመል ።		፻፳
ባለ አንበሳ	አሜሪካ	፻፸፯
“ “	ጃፖን	፻፸፰ብር
ሱኳር	ጁኒያ	፴ብር
ቻይ	፩ ነጥር	ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፹፭ሳቲንም
በአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፭ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፱ ፹ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵፬

ዓለም

ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኔክላ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው





Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊ ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብ ሰፊ ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S F FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።
ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።
የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።
የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
5me ANNEE № 47

ሐሙስ ኅዳር ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 21 NOVEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በዓመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር በዓመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣቱ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ግርማዊ ንጉሥ ስለ ነገሡበት ። መታሰቢያ የብር ዕቃ እንዳቀረቡ።

ኅዳር ፱ ቀን በ፲ ሰዓት ግርማዊ ንጉሥ ባማረ አቶሞቢል ሁነው፥ ልዑል ልጅ አስፋወሰንም በሁለተኛ አቶሞቢል ተቀምጠው፥ብዙ ሚኒስትሮችና መኳንንቶችም በአቶሞቢል እየተቀመጡ ተከትለው ወደ ንግድ ሚኒስቴር ሔዱ ። ክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔር የጉምሩክ ዋና ዲሬክተርም ከንግድ ሚኒስቴር ሹማምንት ጋራ ቤቱን እንደሚገባ አዘጋጅተው ይጠባበቁ ነበርና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሲገቡ ባማረ አቀባበል ተቀበልዋቸው ።

ግርማዊ ንጉሥም አምሮ በተሰናዳላቸው ቦታ በተቀመጡ ጊዜ የውጭ አገርና የኢትዮጵያ ሚኒስትሮች፥ መኳንንቶችም በየመዓርጋቸው ተቀመጡ ። በዚያን ጊዜ ነጋዴዎች ለግርማዊ ንጉሥ የሚሰጡትን መታሰቢያ ዘመከበል በአንድ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው ተሰብስበው ቆሙና ሙሴ ጃን ፕዊግ በነጋዴዎቹ ስም ሁነው ከዚህ በታች ያለውን ንግግር ተናገሩ ።

ጌታዬ

ግርማዊ ዛሬ ከዚህ ቦታ በመምጣትዎ ይህችን ቀን ስለ አከበሯት እኛም በዚች ታላቂቱ ቀን ከእርስዎ ዘንድ በመገኘታችን ይልቁንም ግርማዊነትዎ የመንግሥትዎ ጥቅም በትክክል እንዲከናወን በታላቅ ሐሳብ መጣጣርዎን እያየን እጅግ ደስታችን ሁኑዋል ።

በግርማዊ ከተማ ዋና ዋናውን ነገር ሰብስባ የቆመችው ሕፃኒቱ የንግድ ማኅበር ቤታችን በዚችም ማኅበር ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች በአንድ ሐሳብ ተባብረው እንዲሠሩ በማለት ቆማለች። ደግሞም በመላው ከተማ ዋና ዋኖችን የንግድ ጉዳዮች የአገሯ ልማትና ብልጥግና የሚገኝበትን መንገድ በትክክል ተዘጋጅቶ ይከናወናል በማለት ትጠብቃለች ።

በዓለም ካሉት ዋና ዋና አገሮች መካከል እንደዚሁም የቆመውን ማኅበር ምሳሌ አደረግን ኢትዮጵያ በንግድ ሥራ ከምትገናኛቸው ከባሕር ማዶ ካሉት ልዩ ልዩ አገሮች ጋር ስለ ሚሠራው የንግድ ሥራ ሁሉ እተቻለን ደረጃ ድረስ እርዳታችንን እናደርጋለን ስል ተስፋ አለኝ ።

ይኸም ሐሳባችን የተፈጸመ እንደሆነ ለግርማዊ መንግሥትዎ ለሠሩልን ሥራ ብድር ለመመለስ ታላቅ ደስታችን ይሆን ነበር ።

በኢትዮጵያ ላሉት በየአንዳንዱ ክፍል አገሮች የኢትዮጵያ ንግድ በየጊዜው እየሰፋ መሔዱን ተመልክቶ ስለ አገሩ ብልጽግና ሥራ መከናወን መንግሥት በትክክል እንዲዘጋጅለት ሲመኝ የነበረውን ነገር ሁሉ በማፅናትና ለሥራውም አካሔድ ዕንቅፋት የነበሩትን ብዙ ነገሮች ለማስቀረት የታሰበውን ነገር ሁሉ የዚህ ሥራ ክፍል ቤት ትክክል አካሔድ በትንሽ ቀን እነዚህንም ችግሮች ሁሉ ሊአስቀራቸው ቻለ።የንግድ ሚኒስቴርና በርሱም ውስጥ ያሉት ልዩ ልዩ የሆኑ ክፍል ሥራዎች በመቆማቸው የዚህን የተፈጸመው ሥራ ሐሳብ ሁሉ መመሥረቻ ሆኑ ።

ስለዚህ ከግርማዊነትዎ አጠገብ ላሉት ይህነንም ሥራ ለማስኬድ የሚበቃ ዕውቀት ለተሰጣቸው በታላቅ ትጋትና በጥልቅ ማስተዋል የዚህን ሥራ ክፍል ቤት ለሚመሩት ረዳቶችዎ ታላቅ ምስጋና እናቀርባለን ።

ደግሞም አያሌ መንገዶች በየአለበት ተሠርተው ለማየት ብዙ ተስፋ አለን።የነዚሁም መንገዶች መብዛት የሚያልፉበትን ሀገሮች ሀብትና ልማት ለማረጋገጥ ስለሆነ በየእውራጃው ያ

ሉት ገበያዎች ሁሉ ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር በአቶሞቢል መንገድ ሊገናኙ የምናይበት ቀን ቀርባለች ። የዚሁም ሥራ መቋቋም የእርሻን የኢንዱስትሪና የንግድ ሥራ በጣም ስለሚከናወን ለኛም ለየአንዳንዳችን ስናስብበት የነበረውን የራቀውን አሳብ ሁሉ አስፈጽሞ አዲሱ አሳብ ይተካልናል።

ግርማዊነትዎ በሥልጣኔ ጕዳና የሚመራው ሰፊው የኢትዮጵያ መንግሥት የእርሻና የማዕድን ሀብት ታላቁ ምንጭ እየፈለቀ ለሚመጣው ዘመን በብዙ ብልጽግና የተጠራ ሁንዋል። በዚህ መልክም አካሔድ የተነሣ ወደ በጎ ሥራ ለመድረስና ወደፊት በሚመጣው ጊዜ በሥራ የሚያበረታታ ነገር እናገኛለን በማለት ስለደከምነው ድካምና ስለ ተቀበልነው መከራ ለውጡን ሽልማት በግርማዊ ረዳትነትዎ ያለጥርጥር እናገኘዋለን

ለግርማዊ ንጉሥ ከዙፋን ለደረሱበት ቀን በዓል ክብር የምናቀርበውን ትንሽ መታሰቢያ እንዲቀበሉን እየለመንዎ የተጀመረው አሳብ እንዲፈጸምና ከግርማዊ ሰውነትዎ ጋራ ያለ መሰልቸት የሚያስተሳስረንን ነገር በዚች መታሰቢያ ውሥጥ መገኘቱን እንዲያውቁት ስንል እናመለክታለን ።

ንጉሥ ሆይ ።

በዛሬ ቀን ማኅበራችንን በመቀበልዎ ታላቅ ፍቅር ምልክት ስለሆነ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊነትዎ ታላቅ ምስጋና እናቀርባለን ።

ለግርማዊነታችሁም ቤተ ሰብ ታላቅ ጤናና ምስጋና ይሁን ስንል ለትልቂቱና ለከበረችው ኢትዮጵያም ሀብትና ልማት ጥልቅ ምኞታችንን እናቀርባለን።

ሙሴ ጃን ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ክቡር አቶ ተስፋዬ ተገኝ በፈረንሳዊ እየተረጐሙት ተናገሩና ጭብጨባው ቀለጠ ።

ክቡር የንግድ ማኅበር እንደራሴ ።

በአዲስ አበባ የንግድ ማኅበር ቤት ስም ሁነው የጓደኞ-ምችዎን የቃመነ አሳብ ስለ አስረዱን ታላቅ ደስታ ተሰምቶናል።

የሀገራችንም ንግድ ከሌሎች መንግሥታት ንግድ ጋራ ተያይዞ እየተስፋፋ እንዲሔድ በመትጋትዎ ታላቅ ዋጋ ያለው ነገር ስለሆነ እናመሰግንዎታለን ።

ይህም አሳብዎና ሥራዎ ወደ መልካም ፍጻሜ እንዲደርስ የልባችን ምኞት መሆኑን እንገልጽልዎታለን ።

እርስዎም ባመንግሥቱ መልካም እርዳታ ላይ ሙሉ ተስፋዎን እንዲያደርጉ እናስታውቅዎታለን ።

ባሁኑ የንግድ ሥራ አካሔድ የኢትዮጵያን ንግድ ጕዳትና ችግር እንዳገኘው ተሰምቶናል ። ስለዚህም መንግሥታችን ይህን ችግር ለማስቀረት ሲል በሚቻለው ነገር ሁሉ እርዳታውን ለማድረግ ቍርጥ አሳብ አድርጓል ።

በዚህም አሁን በተናገሩት ነገር ሁሉ እጅጓ ደስ ብሎናል በንግድ ማኅበሩም ውሥጥ የሚገኙት ማኅበረተኞች በዚህ በንግድ ሥራ አካሔድ ላይ በመጣው ችግር ሁሉም ባንድ አሳብ ሁነው ተረዳድተው በመላው ያገሩንና የሕዝቡን ጥቅም ለማዳን ሲሉ በትጋት ያስቡበታል በማለት ብዙ ተስፋ አለን።

ደግሞም የአዲስ አበባ ንግድ ማኅበር ቤት ስለነገሥንበት በዓል ክብር ብሎ ይህን መልካም መታሰቢያ ስለ አቀረበልን ምስጋናችንን እናቀርባለን ።

ይህም የንግድ ማኅበር ለኢትዮጵያ ንግድ ዋና ረዳቱ መሆኑን ተረድተነዋልና ማኅበሩ እየበዛና እየተስፋፋ እንዲሔድ የልባችን ምኞት መሆኑን እናስረዳዎታለን ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትን ይጠብቅ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ኑር ብለው ሲጨርሱ ረጅም ጭብጨባ ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ የቃይና የሻምፓኝ ግብዣ ተደረገና ግብዣው ከተፈጸመ በኋላ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ትልልቅ ነጋዴዎችም ግርማዊ ንጉሥን እየተሰናበቱ ወጡ። ፲፩ ሰዓት ከሆነ በኋላም ግርማዊ ንጉሥ ወጥተው ወደቤታቸው ተመለሱ ።

ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የዘውድ በዓል ለዓመቱ መታሰቢያ በኢሉባቦር በገነት ከተማ የተደረገው ደስታ።

ነጻነቱን የሚወድ ሕዝብ ሀገሩን ይወዳል መንግሥቱንም ያከብራል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የዘውድ በዓል ክብር በመስከረም ፳፯ ፲፱፻፳፩ዓም ስለሆነ እኒሁ የሥልጣን መሪ የሰላም አባት የሆኑት ንጉሥ ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ በብርታት አገልጋይነታቸው በመላ ኢትዮጵያ ልብ ዘልቆ ተሰምቶታል ። የኒህን የንጉሁን ዘውድ በዓል የዓመቱን መታሰቢያ ለማድረግ ግድ ነው ብለው ከዚህ በታች ስማቸው የተጻፈ ብልህ ማኅበረተኞች አቶ ወልደ ሚካኤል የጐሬ ማዘጋጃ ቤት ሹም ። በሻ ወርቂ ተገኝ የኢሉባቦር አውራጃ ጉምሩክ የጸሐፊዎች ሹም አቶ ጌታሁን አስረስ የኢሉባቦር አውራጃ የትምህርት ሬጂ ሹም፤ አቶ በየነ ሻረው የፕራስ ማዕድ ንክንስሲዮን ኩባንያ ጉዳይፈጻሚ፤ አቶ ኃይሉ ለውጤ የእንግሊዝ መንግሥት የምዕራብ ኢትዮጵያ ቈንሲል አነጋጋሪና ጸሐፊ፤ ልጅ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ አማኑኤል የኢሉባቦር አውራጃ ጉምሩክ ዲሬክተር አቶ ደምሴ ወልደ አማኑኤል የምዕራብ አውራጃ ያልኮል ሞኖፖል ሹም፤ እነዚህ ባንድነት ተሰብስበው የዘውዱ በዓል ባለፈው ዓመት ቀን ልክ እንዲከበር ሐሳባቸውን ቈረጡ። የደስታውም ክብር የሚደረግበት ቦታ በክቡር ራስ ናደው ሆቴል መስከረም ፳፯ ቀን ከቀኑ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ የቴያትሮ ጨዋታና የበዓሉ ምረቃ መደረጉን የከተማው ሰው ሁሉ እንዲያውቀው ማስታወቂያ በየስፍራው ተለጥፎ ነበር። ሕዝቡም ይህቺን ቀን በመናፈቅ ያለትዕግሥት ሲጠብቅ ቈየ። ሆቴሉም ከሁለት ቀን አስቀድሞ ውሥጡ ሁሉ በኢትዮጵያ በትልቁ በባለአንበሳው፥በእንግሊዝ ባንዲራና በግሪክም፥ በሌላም በልዩ ልዩ አበባና ጌጥና በለመለመ ዘምባባ አጊጦ።በውጭው በልዩ ልዩ ጌጥ የኢትዮጵያ ባንዲራ በረጅም ሰንጨት ላይ ሁኖ ነፋስ ሲያውለበልበው ላየው ሰው እጅግ ያስደንቅ ነበር። እሑድ ለትም ገና በሁለት ሰዓት ጀምረው እነዚሁ ማኅበረተኞች ለመለዮ የሚከሩበት ። ባንዲራቸውን እንደክርዶን ኒሻን በቀኝ ትከሻቸው አጓግተው ስፍራውን ለማሰናዳት በፎቅ ላይ

ሽር ሽር ሲሉ የከተማው ሰው በውጭ ሁኖ ሲት ወንዱ እንድብርቅ ለማየት ሲተናነቅ ለተመለከተው እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ። ስምንት ሰዓትም ሲሆን ክቡር ራስ ናደው በመኳንንቶቻቸው ታጅበው መጡ ። ከበቅሎም እንደወረዱ የከተማው ዘበኞች ተሰልፈው ይጠብቁ ነበርና በጥሩባ ሰላምታ ሰጡአቸው ወዲያው ማኅበረተኞቹ አጥር ውጭ ድረስ ወጥተው የሚገባ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ፊትና ኋላ ግራና ቀኝ ከበው ይዘዋቸው ፎቁን ሲወጡ እጅግ የተዋቡና ምሳሌ የሌላቸው መስለው ታዩ ። አግብተውም ለጨዋታ በተሰናዳው ቦታ በልዩ ስፍራ አስቀመጧቸው ። ከ፳ ደቂቃም በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት የምዕራብ አውራጃ ቆንሲል በፈረሰኛ ታጅበው በመጡ ጊዜ እንደፊተኛው ብማረ ከበሬታ ተቀብለው በክቡር ራስ ናደው ቀኝ አስቀመጧቸው ።ከዚያ ወዲያ መኳንንቶችና የውጭ ሀገር ነጋዴዎች የከተማውም ታላላቅ ሕዝብም ብዛቱ እንደጉርፍ ውኃ መስሎ ነጫጭ ልብሱን ለብሶ ሲገባ ለሚያየው ላይን ያስናፍቁ ነበር ። ወዲያውም የተያትሮው ጨዋታ እንዲጀመር ፕሮግራሙ ለጨዋታ አስኪያጆች ተሰጠ ።

ፕሮግራሙም እንዲህ ነበር ።

፩ኛ ጨዋታ፤ጌታችን በምድረ በዳ እንደተፈተነና ድል እንዳደረገ ።

፪ኛ ጨዋታ፤ ጌታችን የድል ዘውዱን አድርጎ በሕፃናት ተከቦ ከሚያምር መዝሙራቸው ጋራ ።

፫ኛ ጨዋታ፤ለዘውዱ በዓል ምስማክ ቅኔም ።

፬ኛ፤እዝራ በመሰንቆ ስለንጉሥ ድልን ስለሰጠው እግዚአብሔር ያመሰግናል።

፭ኛ፤የሴት ዘፋኞች በመሰንቆ እየተመሩ ።

፮ኛ፤ድል ስለነሳው ንጉሥ ፋከራ ።

፯ኛ፤ክራር ።

፰ኛ፤ዋሽንት ።

፩ኛ ጨዋታ፤አንድ ሰው በጌታችን ምሳሌ ነጭ ልብስ ለብሶ ብቻውን በበረኃ ሲጸልይ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰይጣን መጥቶ በማቴዎስ ወንጌል።ም ፬ ከቁጥር ፩ እስከ ፲፩ ያለውን በግጥም ይመላለሳሉ፤ በመጨረሻው ሰይጣን ወደረጅም ስፍራ ወሰደውና የሱስም ከኔ ራቅ አንት ሰይጣን ሲለው በፈተናው ተሸንፎ ሰይጣኑ ሲጠፋ ወዲያው ሕፃናት ነጫጭ ልብስ ለብሰው መጥተው ከመልካም ስፍራ ያስቀምጡትና ሁለቱ ከግሩ በታች ይቀመጣሉ፤ ሌሎቹም ዙሯውን ቁመው እንደተጻፈው ቃል ሰይጣንም ተረታ ያዳም ልጆች ሁሉ ዕልል በሉ እንበርታ እያሉ በደስታ ሲዘምሩ መጋረጃ ወደቀ ።

፪ኛ ጨዋታ፤መጋረጃ ሲገለጥ የፊተኞቹ ነጭ ልብስ የለበሱ ሕፃናት አንድ መልከ መልካም ዳዊት የሚባል ልጅ ባማረ ወንበር ተቀምጦ የድል ዘውዱን በደስታ ሲያደርጉለት ብዙ ልጆች ነጫጭ ልብሳቸውን ለብሰው የኢትዮጵያን ባንዲራ በወገባቸው የታጠቁና ለምለም ዘምባባ የያዙ ከመጋረጃው ወጥተው በንጉሡ ዙሯ ቁመው ከዚህ በታች ያለውን ባማረ ዜማ አዘመሩ ።

ማርሽ ኢትዮጵያ ።

፩ ተነሺ ኢትዮጵ በጣሙን ኩሪ ።
አውቀተኛው ልጅ ነጋሲል ተፈሪ ።
አምላክ ይመስገን ክብሩን አሳየን ።
ወጣት ልጆችሽ በሱ ተማርን ።
አዝማች ተነሺ ተነሺ ኢትዮጵያ ኩሪ ።
እውቀተኛው ልጅ ነጋሲል ተፈሪ ።
እንጓዴህ ልጆች በጣም ተማሩ ።
የውቀቱ ብርሃን ተከፍቷል በሩ ።
፪፤ ጥበብ ሠሪ ነው ተፈሪ ልጅሺ።
ዘውዲቱ እንግዴህ ሁኚ እንደ ልብሺ ።
ያገርሽ ኩታ ጉዳ ነበረ ። ተፈሪ በውቀት ጥበብ አስተማረ ።
የጥንቱን በለሴ ዳሰሶ አስቀረ ። በሱ መሪነት ሕዝብሽ ተማረ።
አዝማች ተነሺ ተነሺ ኢትዮጵያ ኩሪ ። እውቀተኛው ልጅ ነጋሢል ተፈሪ።
እንግዲህ ልጆች በጣም ተማሩ። የውቀቱ ብርሃን ተከፍቷል በሩ።
፫፤ወጣቶች ተነሱ ጊዜአችን ደርሶአል። ጨለማው ሁሉ ብርሃኑን ለብሷል። እናንተ ልጆች ወደኋላ አትቅሩ።እሬት ቀደሙ ጥበብን ተማሩ ።
አዝማች ተነሺ ተነሺ ኢትዮጵያ ኩሪ።እውቀተኛው ልጅ ነጋሢል ተፈሪ ። እንጓዲህ ልጆች በጣም ተማሩ ። የውቀቱ ብርሃን ተከፍቷል በሩ ።

መዝሙር ።

አዝማች ልጆች ተነሡ እውቀትን እንሻ።ሳለ ተፈሪ የጀግኖችን ጋሻ። ክብር ለኛ ነው ለመላ አበሻ።ክብር ለኛ ነው ለመላው አበሻ።
፩፤ ክብራችን ዛሬ ነው የዘውዱ በዓል ። እንዳለን ሁላችን ዕልል እንበል ።

፪፤ዛውዲቱን ባርከልን ፈቃዱ ነውና።በርትተን እንማር ለጥበብ እንቅና ።
፫፤ ምቀኝነት ቀርቶ ተስማምተን በደኅና ። ዘውዲቱን እንውደድ ክብሯችን ናትና ።
አዝማች ልጆች ተነሡ እውቀት እንሻ ።
ሳለ ተፈሪ የጅግኖች ጋሻ ። ክብር ለኛ ነው ለመላ አበሻ ።
ክብር ለኛ ነው ለመላ አበሻ ።

ኢትዮጵያ ሰማችሁ ልጆቼ ተፈሪ አለ ድረስ እውቀት ያልተሻማ ። ገባ ተመልሶ ወደቀ ጨለማ ።
እኒህ ንግሥት ንጉሥ እንዲህ የሚጥሩት።ተኹላ እንዳይለቅማችሁ (ነው)ከያላችሁበት ።
ልጆች እንጸልይ እንጸልይ እውነት ነው እናትሆይ ። ጸሎት ይገባናል ይንገሡ ልጅ ልጅ ።

ትምህርት የጀመረ ፍጻሜውን እንዲያይ ።
ግርማቸው ተፈሪ እንደሳት ይፋጅ ።

ከዚህ ባኋላ መጋረጃ ወደቀ ።

፫ኛ ጨዋታ። መጋረጃ ሲገለጥ አንድ ድምፃዊ ዲያቆን ከሁለተኛው መጋረጃ ብቅ ብሎ ከንጉሡ በስተቀኝ ሁኖ ። እስመ በጻሕኮ በበረከት ሠናይ ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘእም ዕንቍ ክቡር።ሐይወ ሰአለከ ወሀብከ (መዝሙር ም ፳፩ ቁጥር ፫ ፬) እያለ ሶስት ጊዜ ደጋገመ በያንዳንዱም መጨረሻ ከመጋረጃ ውሥጥ ሁነው ተሰጥዎ የሚቀበሉት ድምፃቸው እጅግ

ያምር ነበር፡፡ይህም ዲያቆን ወደመጋረጃው ሲገባ አሁንም አንድ ባለድምፅ ደብተራ ወጥቶ ከዚህ በታች ያለውን መወድስ ቅኔ ሲመራ ጠፈሩ የሚሰነጠቅ ይመስል ነበር።

ኃይለ ሥላሴ ክርስቶስ ስቡሐ አክሊል— —
ለእንተ እምርተ ከነት ዕለተ መንግሥቱ ቀደሰ።
ከመ በበዓመት ትንበር ለዓለመ ዓለም ነጊሣ ።
ወበቲ ተፈሥሐት ሥነ ሥርጋዌ ፀሐይ ለቢሳ ።
አስካለ ማርያም ንግሥተ ኃይል እስመ ኢገደፈት ምንተ ኃይለ ሥላሴ ሞገሳ ።
አመ ቆመሂ ንሥረ ተፈሪ ለአየረ ሰማይ በርእሳ።
ህቡረ ተጋብዑ ሰብእ ወእንስሳ ።
ውስተ ቢዓሉ ዓቢይ ከመ ይኅሥሡ ኃሠሣ ።
ጽድቆ ወመንግሥቶ ለኃይለ ሥላሴ ወልደ አንበሳ ።
የገነት ማርያም አለቃ ቢረሳው ።

፬ኛ ጨዋታ፡ መጋረጃ ወደቀና ሲገለጥ ዘውዱ ከፍ ባለ ስፍራ ባማረ ጠረጴዛ ላይ ታየ ወዲያው እዝራ ባማረ ወንበር ተቀምጦ ስለ ንጉሥ ድል መንሳት ባማረ ዜማ በመሰንቆ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን ፭ ደቂቃ ያህል እንደቈየ መጋረጃ ወደቀ።

፭ኛ ጨዋታ፡ከመጋረጃው ውሥጥ ሁለት የተዋቡ የሴት ዘፋኞች ወጡና በመሰንቆ እየተመሩ ወዲህና ወዲያ እየተዘዋወሩ ብዙ የንጉሥን ምስጋና ዘፈኑና መኳንንቱን ደስ አሰኝተው ወዲያው መጋረጃ ወደቀ።

፮ኛ ጨዋታ፡ መሰንቆ መቺ ብቻውን ከመጋረጃ ብቅ ብሎ ንጉሥን ስለብርታታቸውና ድል ስለመንሳታቸው እያነሳ መሰንቆውን በሰንጎ መገን ጥቂት እንደመታ ወደመጋረጃው ጥልቅ ሲል አንድ ጀግና የራሱ ጠጕር ያንበሳ ጋማ የመሰለ ጋሻውን እንግቡ፡ጣምራ ጦሩን ይዞ፡ ጕራዴውን ታጥቆ፡ ምን የመሰለ ጕፈሩን ደርቦ፡ ከዱር ተቈጥቶ እንደተነሳ አንበሳ ከመጋረጃው እየፎከረ ብቅ ሲል ተቀማጩ ሁሉ በግርማው ደነቀጠ ወዲያው እየተዘዋወረ የድል መንሳቱን ነገር ፉከራውን ደቅድቆት ብቶሎ ተመለሰ ።

፯ኛ ጨዋታ፡ ከሁለት ደቂቃ በኋላ መጋረጃው ሲገለጥ ክራር ተጫዋች በሚዳ እግሩን ዘርግቶ ተቀምጦ ጥልቅ በሆነ ግጥም የንጉሥ ምስጋና ሰጥቶ ወደ መጋረጃው ገባ ።

፰ኛ ጨዋታ፤ ወዲያው መጋረጃው ሲገለጥ ሁለት አቡቀዳዴ በራሳቸው ያደረጉ ዋሽንት የሚመቱ ከመጋረጃው ወጥተው ብዋሽንት ድምፅ ከሰዩ በኋላ መጋረጃ ወደቀ። ይህ ሁሉ ጨዋታ ሲታይ ማኅበረተኞቹ የኢትዮጵያን ባንዲራ ከበረድ ይልቅ በነፃ ልብሳቸው ላይ ጣል አድርገው ለተቀማጩ መኳንንት ቢራውን እንደ ውኃ ሲቀዱትና ሲያፋስሱት ከመናፈቃቸው ጋራ የሥራቸው አቀለጣጠፍ ከደን ቅጽበት ሲቀድም ደስታው ልብ ይሠውር ነበር። የቤቱ ጌጥና የማኅበረተኞቹ ነጭ ልብሳቸውና መለዮ ባንዲራቸው ከማደው መብራት ጋር ገጥሞ ሲያንጸባርቅ ባይን ሙሉ ተደፍሮ አይታይም።የተሰበሰበውም መኳንንት ሁሉ ከቤቱ ጌጥ የመጠጡ ብዛት፤ ከመጠጡ የጨዋታው፤ ከጨዋታው ከልዩ ልዩ አበባ የተሸለሙ የሚመስሉ የማኅበረተኞች ማማርና አቀለጣጠፍ ደንቆት አንዱን አንድ ከንዱ አስተባብረለሁ በማለት ልቡ ወሰን በሌለው ደስታ ሰክሮ ነበር፡፡የሆቴሉም ባለቤት ሙሴ አናስታሲ ዲ ባዮናኪስ የኢትዮጵያን ባንዲራ በትክሻው የማሪክን ፤በወገቡ ከነቦዮቹ ታጥቆ ልዩ ልዩ የንጉሡ ስዕ' የተጻፈበትን ብስኩትና ሌላውንም ቅምሻ በያይነቱ ሲያመላልሱ ጌጠኞች ነበሩ። ጨዋታው ከተጨረሰ በኋላ የማኅበሩ ዲስኩር ለኢሉባቦር አውራጃ ጕምሩክ ዲሬክተር ለልጅ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደማኤል ሲሰጥ ሽምጋኙን በእጁ ሲከፍተው ከብዛቱ የተነሣ ለድንገት ደራሽ መትረየስ የተጠመደ ይመስል ነበር፤በዚህም መሐከል ከዚህ በታች ያለው ዲስኩር ተነበበ ።

ርእሰ መኳንንት ክቡር ራስ ናደው፥ ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት ቈንሲል፥ ክቡራንም መኳንንቶች ሆይ።ለኢትዮጵያ ከልብ አገልጋይ የሆኑትን የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን የዘውዳቸውን ክብር የዓመቱን መታሰቢያ በዓል ስናከብር የዛሬው ደስታችን እንደዚህ ያለ ነው ብለን ወሰን ባለው ነገር ልንገልጸው አንችልም። ምንም እንኳን ይህ ለዘላለም መረሳት የማይገባውን የውቀቱን መሪ የዘውድ በዓል ለማክበር በየሐሳባችሁ መኖሩን ብናውቀው እኛ የሐሳባችሁ ፈጻሚ ሁነን የበዓሉን ደስታ ባዘጋጀነው ሥፍራ ስለተሰበሰባችሁልን አስቀድመን በኢትዮጵያ ወጣቶች ሁሉ ስም ሆነን ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እናቀርብላችኋለን ። ጌቶች ሆይ ግርማዊ ንጉሣችን ፈትም አስቀድመው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው እንደምን እንዳገለገሉና እንደለፉለት የማያውቅ ሰው አይገኝም። አሁንም ደግሞ ለውድ ሀገራችን ልማትና ለዝሕቦችዋ ሥልጣኔን ለማግባት ስለነጻነቷም በመታገል ላመኑዋቸው ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፤ ለኢትዮጵያና ለኛም ደፋር ጀግና የማይረታ ጠበቃ፥ የማይደፈር ምሽግ ሁነው የማናቸውም ዓይነት የውቀት መማለጫ ስላደረግናቸው። በሐሳብ ላይ ሐሳብ በድካም ላይ ድካም ተጨመረላቸው እንጂ ዘውድ መጫናቸው ለሀገርና ለሕዝብ የሚያስቡበት ከባድ ሸክም እንዳልቀለለላቸው የማይረዳው የለም። ስለዚህ አገልግሎታቸው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን እንደምናየው ወደፊት በማራመዳቸው ምንም እንኳን ብድራቸውን ለመመለስ ባንችል ይህን ዘላለም የማይረሳውን የዘውድ በዓል በየሙቱ ለማክበር ማሰብ ብዙ ነውን? ጌቶች ሆይ፥ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ጊዜ በበታቸው፤በዳግማዊ ምኒልክ በሀገራችን የተጀመረውን የሥልጣኔ አገባብ ብልሁ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የበለጠውን አከናወኑት።ከዚሁም ውሥጥ ከልባችን ዘልቆ በደስታ የሚሰማንን ምረቃቸውን እናነሣለን ። ይኸውም በራሪ መኪና መጀመሪያ ጊዜ በትጋታቸው አየራችንን አቋርጦ እንዲመጣላቸው ማድረጋቸው ኢትዮጵያ ወደ ጓደኞቿ እንድትደርስ ከልቢ ማሰባቸውን ያስረዳናል ። ስለዚህ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ሕዝቧ ኢትዮጵያም እንደምን ያለ መልካም የበለጠ ዕድል አገኙ።ጌቶች ሆይ፤ ቤዚች በምዕራብ ሃገር በውነተኛው ለኢትዮጵያ አንደኛ ረዳት ክቡር ራስ ናደው ንጉሣችንና ምሽጋችን የሆኑትን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ተከታይነታቸውን የሚያስረዳ ባሳመሩት ሥዛታቸው ክፍል ይህን አዲስ የሆ ብንል ስናከበር ለመንግሥታችን ከልብ በሆነ ታማኝነት

ለኢትዮጵያ ረዳቶች እንድንሆን እንገልጽለታለንና በዚህ በደስታችን በዓል ተከፋይ የማይሆን የለም ። ጌቶች ሆይ ፤ እኛ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ወረታ ይህን ለማድረግ ብዙ አችን አይደለም ። የቀደሙት አባቶቻችን በኃይላቸው ብርታትና ደማቸውን በማፍሰስ ያቈዩንን ውድና ለምለም አገራችንን እኒህ ብርቱ ንጉሥ በዓለም ጥበብ በነቃበት ጊዜ ተነሥተው ከስንቱ ዕንቅፋት እየታገሉ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ሕይወታቸውን እንደመሥዋዕት ለማድረግ ከልብ አገልጋይነታቸውን ሲያቀርቡ እግዚአብሔር ከብዙ ፈተና አውጥቶ በዚህ ባንድ ዓመት ውሥጥ እንኳን የሠሩአቸውን ሥራዎች በዝርዝር ማን ሊመናገር ይችላል ። ክቡር ራስ ሆይ ይህን የማይነገር ደስታዎን ተከፋይ በመሆናችን ለደስታችን ወሰን የለውም። ይኸው የርስዎም የኢትዮጵያ ዋና ረዳት መሆንዎ ከልባችን የማይጠፋ መሆኑን በግዛትዎ ውሥጥ የሠሩአቸው ከተማና መንገድ፡ድልድይም፡ሌሎችም ሥራዎች ይመሰክሩ ብናል። ስለዚህ እኒህን የመሰሉ ሥራዎች ከኢትዮጵያ ረዳቶች በግዛቱ ላይ የሠራ የለምና መጀመሪያቸው ነዎት ለማለት ደፍረን እንናገራለን።

እርስዎም የታላቂቱ ብሪታንያ መንግሥት የምዕራብ ኢትዮጵያ ቆንሲል ይህን ከመንግሥታችሁ በወዳጅነት መንግሥታችን የተሣሠረውን የመንግሥታችንን አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ የኢትዮጵያን ጠባቂ የግርማዊን ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ዘውድ በዓል ስናከብር በጥሪያችን ደስ ብለዎት መጥተው የደስታችን ተከፋይ በመሆንዎ የተለየ ምስጋናችንን እናቀርብልዎታለን ፤ እናንተም የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ለዚሁ በዓል በመምጣታችሁ በጣም ደስ ብሎናል ።

ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፤ ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ኢትዮጵያን ከነሕዝቧ ለዘላለም በነጻነት ይጠብቅ ብሎ ሲጨርስ ከግቢ አንሥቶ እመንገድ ድረስ ጭብጨባው ቀለጠ ። ቀጥሎም ባሻ ወርቁ ተገኝ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ ።

እኔም ስለበዓሉ አንድ ትንሽ ነገር እናገር ዘንድ በስመሰልቸት ክቡራኑ እንድትሰሙኝ ልመናዬን አቀርባለሁ ። ታላቁ ንጉሥ ዳግማዊ ምኒልክ ምንም ኢትዮጵያን ከአባቶቻቸው እጅ ቢያገኟዋት ሕዝቡን ደስ ለማሰኘትና ጉድለቱን ለመሙላት ሐሳባቸው መሆኑን ሁሉ በማወቁ ባንድ ልብ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ፍቅራቸውን እንደልብስ ለብሶት ይኖር ነበር። ይኸውም ፍቅራቸው በኢትዮጵያዊ ሁሉ መኖሩ ይታወቅ ዘንድ ከኅልፈታቸው በኋላ በ፲፱፻፱ ዓ ም መስከረም ፲፯ ቀን እግዚአብሔር ፈቃዱ ሲሆን ደገኛይቱን ልጃቸውን ንግሥት ዘውዲቱን ለኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት አድርጎ ወዲያው መንፈስ እግዚአብሔር ሕዝቡንና መኳንንቱን አነሣሥቶ የኢትዮጵያን መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንንን አድርገናል ብሎ ደስታውን አሰምቶ ይሁንልን፤ ይደረግልን እያለ ከዳር እስከዳር አጨበጨበ ። ከዚህም በኋላ ኢትዮጵያም ከዕለት ዕለት በየዘመናቱ መታደስ ስላገኘች ከመንግሥታቶች ማኅበር ሥልጣኔን መክፈል ጀመረች ። የኢትዮጵያም አልጋ ወራሽ ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንደተባለ ጥበባቸው እግዚአብሔርን መፍራት ፤ ሰውን ደስ ማሰኘት ስለሆነ በ፲፱፻፳፩ ዓ ም መስከረም ፳፯ ቀን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ንጉሥ ተፈሪ ተብለው የከበረ የመንግሥቱን ዘውድ እንዲለብሱ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆነ ሰውም ሁሉ ደሳለው።ደግሞ ለዚሁ በዓል የዛሬ ዓመት የኢሉባቦር አውራጃ ገዥ ክቡር ራስ ናደው የደስታው መዓዛ ተሰምቷቸው ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፌሣሕ ወንትኀሠይ ባቲ እንዳለ ነቢዩ የዛሬዋ ቀን የከበረች የደስታችን ቀን ናትና ብለው ያደረጉትን ደስታ ንግግር ይበዛብኛል እንጂ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እናገረው ዘንድ እወድ ነበር ።አሁንም ሁላችንበዓመቱ በዓሉን ለማክበር ሐሳባችን ሁኖ በጥሪው የመጡትን ክቡራን መኳንንቶችና ደስታችንን ተከፋይ ለሆኑት የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲልና የውጭ ሀገር ክቡራን ነጋዴዎች ሁልጊዜ ደስታ ዕድላቸው ይሁን ስል ጽዋዬን አነሣለሁ ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበ ። ቀጥሎም ክቡር ራስ ናደው ከዚህ በታች ያለውን ለሕዝብ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር ተናገሩ ።

ልጆቼ ሆይ ፤

የማስተዋልና የሥልጣኔ መሪ የሆኑትን የንጉሣችንን ዘውድ ዓመት በዓል ለማክበር ስላሰባችሁና እንደዚህ ድንቅ በሆነ ጨዋታ ልቤን ደስ ስላሰኛችሁት አስቀድሜ አመሰግናችኋለሁ ።

ምንም እንኳ ይህን ሐሳብ እኔ አስቀድሜ ባስበው እናንተ በሐሳባችሁ ተበብራችሁ እንዲህ ያለ ደስ የሚያሰኝ ጨዋታና አዲስ የሆነ በዓል በማድረጋችሁ ለደስታዬ ወሰን የለውም ። ይኸውም ደስታዬ እናንተ የኢትዮጵያ ወጣቶች ወደ ሥልጣኔ መንገድ አቃንቶ በፍጥነት የሚያራምደውን ንጉሣችንን በመውደዳችሁ ነው ። ይልቁንም ደግሞ ታላቁ ንጉሥ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ በእውቀታቸው የጀመሩልንን ሐሳብና የኢትዮጵያ አገልጋዮች ልጆቻቸው በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ጊዜ እንደዚህ በእውቀት የተሸለሙትን በእውነት ከልባቸው ለኢትዮጵያና ለሕዝባቸው የሚያገለግሉትን እግዚአብሔር የሰጠን የኢትዮጵያን ብርሃን ማየታችን ባለ ዕድሎች ነን ለማለት እደፍራለሁ ። እናንተም ወጣቶች በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መሪነት የታየውን የብርሃን ብልጭታ ዋና ተከታዮች እንድትሆኑ በውነት ከልቤ የምመኘው ይህ ነው ።እኒህ ንጉሥ ያለፈው ቀርቶ በዚህ ባንድ ዓመት ውሥጥ እንኳ ምንኛ ሀገራችንን እንዳራመዱት ትጋታቸውና አገልግሎታቸው ከማንም የተሠወረ አይደለምና ልተወው ። ብቻ እግዚአብሔር ብዙ ዕድሜ ሰጥቶልን ኢትዮጵያን ከጓደኞቿ የምትተካከልበትን ዘመን ለማየት ያብቃን ፤ እናንተም በዚሁ ብርሃን ጊዜ በፍጥነት እየተሸቀዳደማችሁ እንድትረዱና ለኢትዮጵያ ረዳቶች እንድትሆኑ እግዚአብሔር ይርዳችሁ ።

እርስዎም ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት የምዕራብ አውራጃ ቆንሲል ይህችን በዓል ለማክበር ፈቃድዎ ሁኖ የማክበር ጥሪአቸውን ተቀብለዋቸው አብረን በማምሸታችን ለኔ እጅግ

ደስ ይለኛል ። አሁንም ስለ ሀገራችን ነጻነት፡ስለመንግሥታችን ሰላምነት ስለ ሕዝባችን ጤንነት ጽዋዬን አነሣለሁ ብለው ሲጨርሱ ሶስት ጊዜ ጭብጨባው ቀለጠ ። ቀጥሎም ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት የምዕራብ ኢትዮጵያ ቆንስል ከዚህ በታች ያለውን ተናገሩ ።

Coronation day .

I most heartily thank the organisers of this ceremony for invinting me to attend today.

The coronation day of His Majesty the Nigus Tafari Makonnen who is welknown for his progressive rule of this beatiful country of Ethiopia.

Not only is H. M. the Nigus the chosen ruler by his nobles, officials and subjects but he has also the full support of all the great powers of the world who wish to see him secure on his throne so as to see fruits of his wise policy ripen and the future of his country grow richer and expand to the trade of the world.

It is a pleasure to be here with Ras Nadow today who has done so much for the peace of Yiloobabor.

We celebrate this occasion today which is outcome of the love of H. M. the Nigus for his country and the love of his people for him.

I congratulate the officials of Gore in organising a public entertainment in honour of His Majesty I ask you to drink to his honour– Viva viva viva.

All rose to feet and drunk his health.

ትርጉም ።

መጀመሪያ ለዚሁ በዓል እንድመጣ ጥብዣቸውን ስላቀረቡልኝ ይህን በዓል ላከናወኑ ሰዎች ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ይህውም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ዘውድ የጫኑበት ቀን ነውና በተዋበች አገራቸው በኢትዮጵያ ላይ በመልካም ነገር ወደፊት እየገፉ በሚሔደው አገዛዛቸው በዓለሙ ሁሉ በጣም የታወቁ ናቸው ።

ግርማዊ ንጉሥ በኢትዮጵያ ባላባቶችና መኳንንቶች ሕዝቦችም ብቻ የተመረጡ አይደሉም ። የእውቀታቸው ፍሬ ደርሶ ለማየት በሚመኙ በውጭ ሀገር ባለ ሥልጣኖች ሁሉ እዙፋናቸው ላይ ፀንተው እንዲኖሩና ሀገራቸውም በብልጽግና እያደገች ንግዷም ለቀሩት ዓለሞች እንዲሆን ይጠብቋቸዋል።

ደግሞ ለኢሉባቦር ሰላም ካደረጉላት ከክቡር ራስ ናደው ጋራ እዚህ በመገናኘታችን ታላቅ ደስታ ነው ። ዛሬም ይህን በዓል የምናከብርበት ምክንያቱም ስለ ንጉሡ ፍቅር ፍሬና ሀገራቸውንም ስለሚወዱ ሕዝቦቻቸውም እሳቸውን ስለሚወዱ ነው ። የጐሬ መኳንንቶች ስለ ንጉሥ ክብር ሲሉ በግልጽ በዓል ስላደረጉ እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ ። ስለ ግርማዊ ንጉሥ ክብር ይህችን ጽዋ እንጠጣ ዘንድ እለምናችኋለሁ።ሁላችንም ተነሥተን ስለ ጤንነታቸው እንጠጣ ። ለዘላለም ይኑሩ። ብለው ሲጨርሱ ሶስት ጊዜ እያስተጋባ ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ ከየ መኳንንቱ የሚወጣው ልብ የሚነካካው ደስ የሚያሰኘው ቃል ስንቱ ቃል ተቈጥሮ በእንደዚህ ያለ ደስታ ከቈየ በኋላ ፲ሰዓት ሲሆን ክቡር ራስ ናደውና ክቡር የእንግሊዝ ቆንሲል በውጭ ያለውን የሕዝቡን ብዛት ስለሰሙ ጨዋታውን ሳይጠግቡ ወጡና ባማረ አጀብ ወደየቤታቸው ሔዱ። ቤቱም ጠባብ ስለሆነ ብዙ ሕዝብ በውጭ ነበርና መጀመሪያ የገቡት መኳንንቶች ባ፲፩ ሰዓት የጨዋታውን ናፍቆት ሳይጠግቡ ሲወጡ ላያቸው የናቱን ጡት የተቀማ ሕፃን ይመስላሉ። ባ፲፪ ሰዓትም ጊዜ የቀሩት መኳንንትና የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ገቡ። አንዳንዳቸውም በፊት የነበሩት ተመልሰው ገቡና ጨዋታውም ከፊተኛው ይልቅ የደመቀ ሆኖ ልክ እንደ መጀመሪያው ሲታይ በቅኔ ጊዜ እንዲሁ አንድ ድምፃዊ ደብተራ ከዚህ በታች ያለውን ተመራ ።

መወድስ ።

የዮም ውእቱ በዓለ ፋሲካ ዘናከብሮ በጽድቅ ።
ዘውደ ተፈሪ ከከበ ጽባሕ ።
አምጣነ መድኀኒተ ከነ ለኢትዮጵያ በፍትሕ ።
ወናስተቄጽሎ አክሊለ ዘንጽሕ ።
ወበመንግሥቱ ለንጉሥነ መስፍነ ሮምያ ኀያል በኀይሉ
ኢይትሜከህ ።
መልአክሂ ንሥረ ተፈሪ በአምሳለ ፀሐይ ወወርኀ ።
አመ ቆመ ማእከሌኪ ኢትዮጵያ ሐመረ ኖህ ።
እምተሀውከቱ አርመመ ማዕበለ ተሡጥሞ በሊሕ ።
እስመ ውስተ ብርሃን ይመርሖ ንጉሠ ጣርማ ገጸመፍርህ።
ቀለመ ወርቅ መምህረ ሕፃናት ጐሬ።

እንዲህ ሆኖ ጨዋታው እስኪያልቅ ድረስ ሻምፓኝ ለፈለገው ሻምፓኝ፥ ቢራ ለፈለገው ቢራ እንደ ወሃ እንደተቀዳ በፊት ጊዜ ሳያገኙ የቀሩ ባለ ዲስኩሮች ባጭር ቃል ደስ የሚያሰኝ ነገር ብዙ መኳንንቶች ተናገሩ ። አቶ አብርሃም አብዲም ጐሬ የመንግሥት ተማሪ ቤት የእንግሊዝ ቋንቋ አስተማሪ ቀጥሎ ያለውን ተናገረና ደስ አሰኘ ። ክቡራን መኳንንቶች ሆይ እላንተም ወንድሞቼ ስለዚሁ ቡሩክ ቀን ትንሽ እንድናገር ክቡር ፈቃዳችሁን በትሕትና እለምናለሁ።ክቡራን ጌቶቼ ሆይ ይህን የተባረከ ቀን በማክበራችን የከተማው ሰው ሁሉ በደስታ ተጨንቋል።ግርማዊ ንጉሥ ለኢትዮጵያ የሠሩትን ሁሉ እያንዳንዷ ብንቈጥረው ምናልባት ሁላችን ደስታና ኀዘን ባደባለቀን ነበር ። ስለድካማቸውና ስለፈተናቸው አዝነን ስለ ድካማቸው ፍሬ ደስ ብሎን ማለቴ ነው ። በዚህ በደስታ ቀን የሚያሳዝን ነገር ማንሣቴ ይልቁን እንዲያተጋጋን ነው ። ግርማዊ ንጉሥም ያደረጉት ለኢትዮጵያ ከሆነ ድካማቸው ለማን ው ። እንግዲህ ግርማዊ ላደረጉልን ሁሉ ደስ ከሚለን በቀር ሌላ ምን ለማድረግ እንችላለን ። ? ለዚሁ ድካማቸው በማን

ሩንታ ለራሳቸው ጥቅም ስንል እንከፍላቸዋለን ። እንዴት አድርገን ።? እኛ እስከ ዛሬ ለመገበችን እናት በውነተኛ ልብ ብናገለግል በተቃጠለ ሐሳብ ብንማር ከፍ ባለ ማስተዋልም ብን ሠለጥን በውነት ግርማዊ መምህራችን ደስታቸውን በኛ ላይ በዩ ። ሰው የዘራውን አትክልት ፍሬ ሲያይ እንዴት ደስ ይለዋል ።? ይልቁንም የፍሬው ጣም ሲሆን ደስታው እንዴት ይበዛል ። የብዙ ድካሙን በደስታ ይለውጠዋል ። የግርማዊ ንጉሥ ደስታ ግን ከዚህ እጅግ መብለጡን ልንረዳው እንችላለን ሰው ከትክልት ይበልጣልና ።

ክቡራን ሆይ ። ይህ የተባረከ ማኅበር ይህን ግሩም የሆነ በዓል በማከናወናቸው የኢትዮጵያና የንጉሣቸው አፍቃሪ መሆናቸውን ግብራቸው ገለጸልን ። ሁላችንም ለዚህ ትጉህ ማኅበር ምኞታችን መልካም እንደሆነ ጥርጥር የለውም ብሎ ሲጨርስ ተጨበጨበለት ።

ከዚህም ቀጥሎ የክቡር ራስ ናደው ፍርድ ጸሐፊ ፀሐይ መለሰ እጅግ ድንቅ የሆነ ዲስኩር ተናገረና ደስ አሰኘ ።

ይኸውም ጨዋታ ከሌሊቱ እስከ ፩ ሰዓት ቈየና ማኅበሩም በየወምበራቸው ዕርፈት አድርገው ከዚህ ወዲያ የሴት ዘፋኞች በመሰንቆ እየተመሩ ከሌሊቱ እስከ ፰ ሰዓት ድረስ በጨዋታቸው ሕዝቡን ደስ አሰኙ ። የውጭ ሃገር ሰዎች አለመጣን በደስታ ሰክረው እያነዳንዱ ምስጋና በተነማ ጊዜ እንደ ተጨበጨበ አደረ። ተቀማጩም ሁሉ ከደስታው ብዛት የተነማ ገንዘብ ለዘፋኞች ያልበተነ አይገኝም ይህም የዘውድ በዓል ቀን ጽፎ ለመናገር በማይወጠን ደስታ ያ ሁሉ ሲሆን አንድ ደቂቃ እንኳን እንጻልታየ ሁሉ እንጻንድ ልብን እጅግ ደስ የሚያሰኝና ላዩን እንደሚያስገመጅ ነገር በቶሎ ታይቶ ሊጠፋ ልብን በሰቀቀን እንደሚመስጥ ሆነበት ። በዚህ ቀን የተደረገው ደስታ ከዚህ ቀደም በምዕራብ አውራጃ ባለ መጀመሩ እንደ እንግዳ ነገር አድርጎት የከተማው ሰው ሁሉ የገባውም ያልገባውም በየቤቱ ታላቅ በዓል አድርጎ በከተማ የደስታ ዘፈንና ጨዋታ ሌሊቱን ሁሉ ይሰማ ነበር ። ሕዝቡና መኳንንቱም ይህን በዓል እንደምን አሰቡት እያለ የማይደነቅና ለማኅበሩ ምርቃት የማይሠጥ አልነበረም ። እንደዚህ ሁኖ ለማይነገ በማይቻል ደስታ የበዓሉ ቀን ተፈጸመ።እኒህም ማኅበርተኞች የሆኑት የህን የዘውድ በዓል መታሰቢያ በየዓመቱ ለማድረግ ቁርጥ አድርገዋል ይላል ። የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ስለ ክቡር ራስ ናደው ዕረፍት።

ክቡር ራስ ናደው ላፄ ምኒልክ ዋና ባለሟል ነበሩ ። ወደ ኤውሮጳና ወደ አሜሪካም ከመንግሥት እየተላኩ ሒደው ነበር በይሉብ ባቡሬ ተሹመው ግዛታቸውን ደኅና አድርገው በማስተዳደራቸውም የተመሰገኑ አገረ ገዥ ነበሩ። በሚገዙበት አገርም ለማሠልጠንና የበለጠ አድርጎ ለማሻሻል በጣም ይተጉ ነበር። ግን ሰው ሆኖ ከሞት የሚቀር የለምና አሁን በኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመ ዓረፉና በቤተ መንግሥት ትልቅ ኀዘን ሆኖ ሰነበተ። ጥልቅ ኃዘኑን እየገለጠ ብርሃንና ሰላም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ለዘመዶቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል።

ይድረስ ከክቡር የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ዲሬክተር ።

ክቡር ሆይ

በጥቅምት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት በአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫ በታተመው በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በቀል ዘለቀ የሚባል በድሬ ደዋ ወኪላችን ዘንድ ስለ ባንክ ኖት አሸራረፍ የጻፈው ቃል ሐሰት መሆኑን በብርሃንና ሰላም እንዲገለጽ ን እንለምንዎታለን ።

በባንክ ኖቶቻችን ሁሉ ገጽ ላይ በማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ እንዲህ የሚል ታትሞበታል ።

አዲስ አበባ ላይ ላምጪው የሚከፈል ይላል ። ስለዚህ በባንክ ኖቶቻችን ከድሬ ደዋ ላይ ገንዘብ የሚቀበሉባቸው አይደሉም።ነገር ግን አንድ አንድ ጊዜ የሚያስፈልግ ቢሆን ኰሚሲዮን እየተከፈለባቸው እንቀበላለን ።

ክቡር ዲሬክተር ሆይ በልዩየሆነ የማክበር ሰላምታችንን እንዲቀበሉ እንለምንዎታለን ።

ስለኢትዮጵያ ባንክ አለቃ ሙሴ ራይት ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጂዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፰ ብር

ጎሀ ጽባሕ	፳ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፰ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡኣትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፰ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፲ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፲ መሐ
የማልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፰ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፰ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፲ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የበገና ግጥም	፪ መሐ

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ

ድራሌ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቁርቁር መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
5me ANNÉE № 48

ሐሙስ ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 28 NOVEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መፃሀት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት መላክተኞች ።

የሐዋርያት አለቃ ቅዱስ ጴጥሮስ በሮማ ከተማ እንደ ጌታው እንደ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ስለ ሞተ፣ መንበሩ በሮማ ላይ እንዲሆን በሲኖዶስ ስለ ተወሰነ በሹመት የቅዱስ ጴጥሮስ ተከታይ የሆነው መንበሩ ለዘወትር በሮማ ላይ ፀንቶ ይኖራል ።

ይኸውም የቅዱስ ጴጥሮስ ተከታይ ሁኖ በመንበሩ የሚቀመጠው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በላይ ስለሆነ በንጉሥነት ስም ይጠራል ። እንደ ሌሎቹም ነገሥታት አምባሳዶሮችና ሚኒስትሮች በየመንግሥቱ ይልካል። ከየመንግሥቱም እየተሾሙ ወደ ሮማ ባቲካን የሚመጡትን አምባሳዶሮችና ሚኒስትሮች ሁሉ እንደ ንጉሥ ሁኖ ይቀበላል።

ከዚህም ቀድሞ በአፄ ምኒልክ ዘመን የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የነበሩት ሟቹ ፒዮስ ፲ኛ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ወዳጅነት ለማድረግ ስለ አሰቡ ዋና መልእክተኛና ደብዳቤ ልከው ነበር ። መልእክተኛውም አዲስ አበባ የደረሰው በመጋቢት ፲፪ቀን ፲፰፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ነበርና ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ በታላቅ ማዕርግ ተቀብለው ለደብዳቤውም ምላሹን ጨምረው መልእክተኛውን ደስ አሰኝተው ሰደዱት ።

ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱም ዳግመኛ በመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምሕረት የኢየሩሳሌም የታላቁ መስቀል የሚባለውን ታላቁን ኒሻን ጨምረው እንደገና ወደ አፄ ምኒልክ መልእክተኛ ልከው ነበርና ፤ ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያን ጊዜ የአዲስ አበባ ከንቲባ ሁነው ሳሉ በጃንሆይ ትእዛዝ በብዙ ሰልፍ ተቀበለዋቸው ነበር ።

መልእክተኛውም ከጃንሆይ ጋራ በሚገናኝበት ቀን፤እጅግ ባማረ ዕቃ የተጫነች በቅሎ እስከ ሰፈሩ ድረስ ልከውለት ባማረ ሰልፍና በብዙ ሠራዊት ታጅቦ ወደ ቤተ መንግሥት በመጣ ጊዜ ጃንሆይ መኳንንቱን ሁሉ በዙሪያቸው አድርገው በታላቅ ክብር ተቀበሉት ። ወዲያውም የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፒዮስ ፲ኛ የላከላቸውን ታላቁን ኒሻን ቀርቦ አስረከባቸው ። ኒሻኑንም ሲያስረክብ ብዙ መድፍ ተተኰሰለት ።

መልእክተኛውም እስከ መስቀል በዓል በአዲስ አበባ ቈይቶ ነበርና ፤ ጃንሆይ አፄ ምኒልክ ስለ መስቀል በዓል ለውጭ አገር ሚኒስትሮችና ቆንሲሎች ግብር ባደረጉ ጊዜ በከፍተኛው ማዕርግ በመካከለኛው መንበር የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን መልእክተኛ አስቀምጠውት ነበር ።

በዚሁም ዓመት በመስከረም ፴ቀን እቴጌ ጣይቱ የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን መልእክተኛ ተቀብለውት ነበርና ፤ ያመጣላቸውን የሥዕል ገጸ በረከት አይተው እጅግ በማድነቅ ሥዕሉን ተሣልመው ፤ መልእክተኛው ወደ ሮማ ሲመለስ ወደ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ደብዳቤ ይዞላቸው እንዲሔድ አስታወቁት ።

መልእክተኛውም ሦስት ወር ያህል በአዲስ አበባ ከቈየ በኋላ ከጃንሆይ ተሰናብቶ በሚሔድበት ጊዜ ለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ መታሰቢያ የሚሆኑ ሁለት አንበሶች ከደብዳቤ ጋራ ሰጥተውት በታኅሣሥ ፲ቀን ፲፱፻ ዓመተ ምሕረት ተመልሶ ሔደ ።

አሁን ዛሬ በቅዱስ ጴጥሮስ መንበር የተቀመጡት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፒዮስ ፲፩ኛ ናቸው ።

በ፲፱፻፲፮ ዓመ ምሕ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ወደ አውሮፓ ሔደው ሳሉ የኢጣልያ ንጉሥ ግርማዊ ቢክቶር አማኑኤል ከጐበኙ በኋላ ወዲያው ወደ ባቲካን ሔደው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን ፒዮስ ፲፩ኛ ሲጐበኙ ታላቅ የክብር አቀባበል ተደርጎላቸው ነበር ።

ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱም ለግርማዊ ንጉሥ ታላቁን ባለ ከርዶን

ኒሻን ሸልመው ተከትለውም ለሐዲት መሳፍንትና መኳንንት በየማዕርጋቸው ኒሻን ሸልመዋቸው ነበር ።

አሁን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ከዚህ ቀድሞ በ፲ኛው ፒዮስና በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የተጀመረውን ወዳጅነት እያሰፉና እያፀኑ ለመሐድ፤ ሁለተኛም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን ጐብኝተው ነበርና ቢዚት ለመመለስ፤ ሶስተኛም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዘውድ ስለጫኑ እንኳን ደስ አለዎ ለማለት በኤስሬ የሥላሴ ሊቀ ጳጳስ የሆኑትን ክቡር ሞንሲኜር ፍራንሷ ማርኪቲ ሴልቤጂያንን አምባሰደር አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ላኳቸው ። እርሳቸውንም ተከትለው የመጡ መልእክተኞች ፩ኛው በባቲካን መጻሕፍት ቤት የምሥራቃዊ ቋንቋ ጸሐፊ ሞንሲኜር አገርንቲ ቲሰራ ናቸው። ፪ኛው የማርኪኖል ማኅበር ዋና ፕሮኩሬር ዮሐንስ ክንሲዲን ነው ። በፊን ፕሮፖጋንድ በኡርቢ ትምህርት ቤት የሺን ቋንቋ የሚያስተምሩ ፖልዩ ናቸው ።

መልእክተኞቹም በኅዳር ፰ ቀን ጅቡቲ መድረሳቸውን የሚያስታውቅ ደብዳቤ ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት መንግሥት ዋና ጸሐፊ ከክቡር ካርዲናል ጴጥሮስ ጋስፓሪ አስቀድሞ ወደ ግርማዊ ንጉሥ ተልኮ ነበርና ፤ ጅቡቲ ላይ መልእክተኞቹን ለመቀበል ያገር ግዛት ሚኒስቴር ዲሬክተር ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም ታዘው ወርደው ነበር ።

መልእክተኞቹም በኅዳር ፱ ቀን ከጅቡቲ ተነሥተው ድሬ ደዋ በገቡ ጊዜ በሐረር ከተማ የሚኖሩት የካቶሊካውያን ጳጳስ ክቡር ሞንሰኜር እንድርያስ ዠሮሰ ተቀብለው እስከ አዲስ አበባ ድረስ በአንድነት መጥተው በኅዳር ፲፩ ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

በአዲስ አበባ በባቡር መቆሚያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይና የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር አቶ አየለ ገብሬ የከተማ ዘበኞች አሰልፈው በክብር ከተቀበሏቸው በኋላ ባማረ አቶሞቢል ሁነው በፈረሰኞች ታጅበው ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው ስፍራ ወሰዱዋቸው ።

በኅዳር ፲፬ ቀን በቤተ መንግሥት ታላቅ ሰልፍ ተደርጎ በክብር አቀባበል መልክተኞቹ ገብተው የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን ደብዳቤዎች ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ አስረከቡ ። ደብዳቤውንም ሲያስረክቡ ዋናው መልእክተኛ ክቡር ሞንሰኜር ፍራንሷ ማርኬቲ ሴልባጂያን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ
ግርማዊ ንጉሥ ሆይ

ከፍ ያሉ ገዢዬ ቅዱስነታቸው ፒ ፲፩ኛ ወደ ግርማዊነታችሁ ልዩ መልእክተኛ አድርገው የላኩበትን ደብዳቤና ፤ ደግሞ ከልብ የሆነ እውነተኛ ወዳጅነታቸውን ለመግለጽ ቅዱስነታቸው ለግርማዊነታችሁ በደስታ የሚያቀርበውን መታሰቢያ በማክበር አስረክባለሁ ።

ከጥንት ዘመናት ጀምራ እውነተኛውን ሃይማኖት ለማወቅ የቻለችው ኢትዮጵያ ፤ የክርስቲያንን ሃይማኖት እንዴት እንደተከተለችና ፤ ደግሞ በየዘመኑ ምንም ልዩ ልዩ ሁከት ቢነሣ፤ እስካሁን በክርስቲያን ሃይማኖት እንዴት ፀንታ እንደኖረች የሚያውቁ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፤ በቅድስት ሐዋርያዊት መንበርና በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት መካከል ስለ አሉት መልካም መገናኛዎች በተለየ ከልባቸው ያስባሉ ።

ከዚህ ቀድሞ በታላቁ ንጉሠ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን እጅግ መልካም የነበሩትን እነዚህን መገናኛዎች ፤ ቤኑዋ ፲፭ኛ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በሆኑበት ዘመን እርስዎ ታላቂቱ ንግሥተ ነገሥታት አነቃቋቸው። የኢትዮጵያም መንግሥት አልጋ ወራሽ ከጥቂት ዘመን በፊት ወደ ባቲካ ቤተ መንግሥት መጥተው ቅዱስነታቸውን ፒ ፲፩ኛ በጐበኙ ጊዜ እነዚህ መገናኛዎች እንደ ገና በአዲስ ፍቅር ታደሱ ። ከዚያም ወዲህ የተቀደሱት አባት ይህን በተለየ አስተያየት የሚገምቱትንና ከሁሉ የበለጠ ውድ የሆነ መልካም መታሰቢያ የሚያኖሩለትን መጐብኘት ለመመለስ አሰቡ። የተቀደሱት አባት ያለማቋረጥ ያሰቡት የነበረ ይህ አሳብ አሁን መፈጸሙን ሲመለከቱ ፤ ስለ ተደረገላቸው መጐብኘት ምስጋናቸውን እያቀረቡ ፤ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት የከበረውን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ፈቃዳቸው ሁኖ በአልጋ ወራሽ ራስ ላይ ስላደረጉልዎ ፤ እንኳን ደስ አለዎ እያሉ የጋለ ምኞታቸውን የሚገልጹበትን ቃል በቀጥታ ያቀርባሉ ።

ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱም ግርማዊነታችሁ ካቶሊካውያን ዜጎቹን ፍጹም በሆነ በጎ አድራጊነትና ከፍ ባለደግነት ስለማስተዳደራችሁ በተለየ ምስጋና አቀርብ ዘንድ አዘውኛል ። ደግሞ ለተማሩት ትምህርት ከልባቸው የታመኑ እንደ ሆኑ ሁሉ ፤ የኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ንጉሣቸውን የሚያከብሩ፥ አገራቸውን የሚወዱና የታመኑ ዜጎች እንዲሆኑ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ለግርማዊነታችሁ ያስረግጣሉ ።

የተቀደሱት አባት ፤ ሰማያዊ ቡራኬ በሙሉ እንዲወርድላት የሚመኙላት ግርማዊነታችሁ ፤ በጥበብ በሚገዛበት ዘመን፤ ኢትዮጵያ እጅግ የበዛ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሀብት በፍጹም ሰላም እንድታገኝ እግዚአብሔርን ይለምናሉ ። የግርማዊነታችሁ መንግሥት ፤ ለመንግሥታት ኃይልን የሚሰጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ያስተማረውን ብርሃናዊ ትምህርት ይዞ ፤ በፍቅርና በጽድቅ የተመሠረተ ስለ ሆነ ይህ ይፈጽምለት ዘንድ አያስቸግረውም ።

ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ አምነው የሰጡኝን ከፍ ያለና እጅግ የከበረ መልእክት ከፈጸምሁ በኋላ ፤ ለግርማዊነታችሁና ለንጉሣዊ ቤተ ዘመድ ታላቅ ደስታ፥ ለኢትዮጵያም ሕዝብ ተድላ እንዲሆን ፤ በተመሰገነችው በአምላክ እናት በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ፤ ሁሉንየሚችል እግዚአብሔርን እየለመንሁ ፤ ጥልቅ የሆነ የአክብሮቴን አሳብ ግርማዊነታችሁ ፈቃዱ ሁኖ ይቀበል ዘንድ እለምናለሁ

Majestsé .

J'a' l'honneur de déposer entre les mains de Vos Majestés les lettres, par lesquelles Sa Sainteté

Pie XI, mon Auguste Souverrain, m'accrédite comme Son Envoyé Extraordinaire spécial auprès de Vos Majestés, et les dons que Sa Sainteté a le plaisir d'offrir a Vos Majestés en témoignage de Sa sincère et très cordinale amitié .

Le Souverrain Pontife qui sait comment l'Ethiopie, parvenue dès les ages les plus reculés à la connaissance de la vraie religion, embrassa en son temps le christianisme et s'y maintint jusqu'à ce jour nonobstant les vicissitudes des siècles, a particulièrement a cœur les bonnes relations entre le Saint-Siège Apostolique et la Cour d'Ethiopie. Ces relations, qui étaient déjà excellentes sous le glorieux Empereur Menelik II furent cultivées par vous, Puissante Impératrice, dès le temps du Souverrain Pontife Benoît XV et devinrent empreintes d'une nouvelle cordialité, lorsque l'Héritier du Trône d'Ethiopie visita Sa Sainteté Pie XI, il y a peu d'années, en son palais du Vatican. Le Saint Père, se proposa dès lors de rendre cette visite, qu'il avait appreciée d'une façon toute particulière et dont il garde toujours le plus cher et le plus précieux souvenir. En ce moment, qui voit la réalisation de ce dessein constant, le Saint Père est heureux d'ajouter aux remerciements pour la visite recue l'expression directe de Ses vives félicitations pour ce qu il a plu a Sa Majesté l'Impératrice de placer sur le front de l'Héritier du Trône la glorieuse couronne de Roi des Rois .

Le Souverrain Pontife m'a chargé tout spécialement de remercier Vos Majestés pour la parfaite équité et la haute bienveillance, dont Elles entourent leurs sujets catholiques, et il assure Vos Majestés qu'Elles trouveront toujours les catholiques d'Ethiopie, pour autant qu'ils seront fidèles aux enseignements reçus, parmi leurs sujets les meilleurs et les plus déférents envers l'autorité civille. parmi les fils de la Patrie les plus aiments et les plus dévoués.

Le Saint Père élève Sa prière à Dieu pour que sous le sage gouvernement de Vos Majestés, à qui il souhaite la plénitude des bénédictions célestes, l'Ethiopie connaisse, avec le grand bienfait de la Paix, la plus abondante richesse des biens spirituels et matériels. Il est aisé qu' il en soit ainsi, puisque le gouvernement de Vos Majestés est fondé sur la charité et la justice, tout imprégné de la doctrine lumineuse apportée aux hommes par Celui qui donne la force aux Empires. Notre-Seigneur Jesus Christ .

En m'acquittant de la haute et très honorable mission,que le Souverain pontife m'a confiée' je demande a Vos Majestés de daigner agréer les sentiments de mon profond respect, tandis que je prie ardemment le Tout-Puissant, par l'intercession de la glorieuse Mère de Dieu, la Très-Sainte Vierge Marie, de combler de Ses faveurs Vos Majestés et l'Auguste Famille Royale, pour Leur plus grand bonhenr et celui du Peuple Ethiopien.

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዋናው መልእክተኛ ለተናገሩት ዲስኩር ምላሽ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡር ሆይ

ክርስቲያንነቱን ከጥንት ጀምሮ ጠብቆ በሚኖረው ጥንታዊ አገራችን ዋና ከተማ ርእሰ ጳጳስ ንጉሥ ወደ ንጉሡ ነገሥቱ መንግሥታችን መልካም ፈቃዳቸው ሁኖ የላኩትን የከበረ መላክተኛ ዛሬ ስንቀበል ለግርማዊት ንግሥተና ለእኛም ለራሳችን በተለየ ደስ ብሎናል ።

ርእሰ ጳጳስ ንጉሥ ይህን ከፍ ያለ አሳባቸውን ሲያደርጉልን የገለጹልን ይህ ከፍተኛ የወዳጅነት ማስረጃ ስውነታችንን ደስ አሰኘው ።

በ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረትም በርእሰ ጳጳሱ ቤተ መንግሥት የተደረገልንን አቀባበል በአሰብን ቍጥር ደስ ይለናልና ክቡርነትዎም አሁን መንግሥታችንን ለመጐብኘት መጥተውሳሉ ይህ መጐብኘትዎ ደስ የሚያሰኝና ለዘወትር የሚኖር መታሰቢያ እንዲሆንልዎ እንመኛለን ።

የማይዘነጉት ታላቁ ንጉሣችን ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘወትር የክርስቲያንን መሠረት አሳቦች ተከትለው አገራቸውን በፍቅርና በትክክል ሥርዓት ሲገዙ ኖሩ ።

እግዚአብሔር በፈቃዱ በእኛ ላይ ያደረገውን ከባድ የሆነ ሥራ ተመልክተን ሁሉን የሚችል እግዚአብሔርም ኃይሉን ሰጥቶን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት እየተከተልን የተወደደች አገራችንን ወደ መልካም እንድንመራት ያብቃን።

ክቡር ሆይ እንኳን ደኅና ገቡ የማለት ሰላምታችንን ስናቀርብልዎ ወደ ዘለዓለማዊት ከተማ ወደ ሮማ በደረሱ ጊዜ ለርእሰ ጳጳሳት ንጉሥ የማክበር ሰላምታችንንና ምስጋናችንን እንዲያደርሱልን እንለምንዎታለን ።

Excellence.

Il Nous est particulièrement agréable à sa Majesté l'impératrice et à nous même, d'accueillir aujourd'hui en la capitale du vieil Empire Chrétien d'Ethiopie, l'Illustre envoyé du très Saint Père, le souverrain Pontife, auprès de notre Gouvernement Impérial.

Nous sommes particulièrement sensibles à ce haut témoignage de la grande sollicitude du souverrain Pontife à notre égard.

C'est toujours avec la plus grande émotion que nous nous souvenons de l'accueil paternel qui nous a été réservé au palai du vatican à Rome lors de notre voyage en 1924 et notre désir le plus cher serait que votre Excellence rempote de sa visite à notre Cour Impériale un souvenir agréable et durable.

Notre grand Empereur Ménélick II, d'impérissable mémoire, a toujours en en vue de gouverner son Empire selon les principales Chrétiens de Haute Justice et de Charité.

Nous nous efforcerons toujours de suivre les enseignements du christ,conscients des lourdes responsabilités qu'il a plu au Très Haut de placer sur Nos têtes et Nous prions Dieu de nous accorder la force de conduire les destinées de notre chère patrie.

Veuillez, Excellence, accepter nos souhaits de cordiale bienvenue et affirmer lorsque vous regagnerez Rome, la ville eternelle, les sentiments de respectueuse gratitude envers le souverrain pontife, dont nous sommes animés.

ከዚህ በኋላ የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ስለ መታሰቢያ የላኩትን ሁለት የሥዕል ገጸ በረከቶች አንደኛውን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት፥ ሁለተኛውን ለግርማዊ ንጉሥ አቀረቡ ። ገጸ በረከቶቹም በወርቅና በሌላም በልዩ ልዩ ቀለም ሞዛይክ በሚባል ሥራ የተሠሩ እጅግ የሚያምሩና የሚያስደንቁ የምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕሎች ናቸው ።

ደግሞ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ፒዮስ ፲፩ኛ ዕድሜያቸው ፶ ዓመት በሆነ ጊዜ ስለ መታሰቢያ ከተሠራላቸው በአንዱ ወገን መልካቸው፥ በሁለተኛው ወገን የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ከታተመበት ሁለት የወርቅ ሜዳይ ነው ።

ከዚህ በኋላ መልእክተኞቹ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ከግርማዊ ንጉሥ ተሰናብተው እንደ ፊተኛው ታጅበው በሰልፉ መካከል ወደ ማረፊያ ሰፍራቸው ተመለሱ ።

ያገር ውሥጥ ወሬ ።

አዳም በኃጢአት ከወደቀበት ቀን ጀምሮ የሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአታቸው ስለ በዛ ብዙ የሚያስጨንቅ መቅሠፍት ይወርድባቸው ነበር ። ይልቁንም ፈርዖን የምስር ንጉሥ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማም ብሎ ልቡን ስላፀና አገሩን የሚያጠፉ ልዩ ልዩ መቅሠፍት ታዘዘበት ። ከነዚህ ለማጥፋት ከታዘዙትም ስምንተኛው መቅሠፍት አንበጣ ነበር ። ይህም አንበጣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በየጊዜው አልፎ አልፎ በአንዳንድ አገር እህል ማጥፋት አልተወም ። አሁን ባለፈው ክረምት በየሀገሩ አንበጣ ብቻ ሁኖ በጣም አስፈርቶ ነበርና በጐጃም አንበጣ መጀመርያ እንደተነሣ ክቡር ራስ ኃይሉ አንድ ዓመትና ሁለት ዓመት ድኃየን የምረዳበት ገንዘብ አላጣም።ነገር ግን አለኝ ብሎ ሰንፎ መቀመጥ እንደ ትልቅ ነውር ይቈጠራልና ። በየሀገርህና በየመልክህ እየወረድህ አንበጣን ደብድበህ አጥፋ ብለው አዋጅ ስለ ነገሩ ።

ይህነን አዋጅ ባላገሩ በደስታ ተቀብሎ ሁሉም በየአውራጃውና በየመልክው እየፈለገ አንበጣው ገና ጕልበት ሳያደርግ እየደበደበ አጠፋው ስለዚህ በጐጃም የበቀለ እህል እጅግ ደስ ያሰኛል ይባላል ።

ደግሞ በኅዳር ዓሥር ቀን ማር ጭኖ የመጣ አንድ ነጋዴ አግኝቼ ስለ ጐጃም አገር ደኅንነት እየተጠያየቅን ስንጨዋወት ቈየንና ስለ ማር ግብር ብጠይቀው ክቡር ራስ ኃይሉ አገሩን የማር ግብር ከተውት ሰባት ዓመት አልፎ ዘንድሮ ስምተኛው ዓመት ነው ብሎ አጫወተኝ።እኔም ይህ የማር ግብር ከቀረላችሁ በመት ግብራችሁ ምን ያህል ነው ብየ ጠየቅሁት።እሱም ስለ ዓሥራት እህል በመቶ ሁለት ብርና ለፍሪዳ ፩ብር ነው እንጂ ሌላ የለብንም አለኝ።

እንዲህ ከሆነስ ራስ ኃይሉ ለሚገዙት አገራቸው መልካም ገገርና ለመንግሥታቸውና ለሕዝባቸው የተመሰገነ ረዳት ሁነዋል። ይህነን በጎ ሥራቸውን በማየቱም ሕዝቡ እንደሚወዳቸውና እንደሚያመሰግናቸው እርግጥ ነው ። ሌሎች አገረገዦችም ለመንግሥታቸውና ለሕዝባቸው እንደዚሁ እያሰቡ ቢረዱ ሕዝባቸው ይወዳቸውና ያመሰግናቸዋል ። በመንግሥት ፊትም ሞገስ ያገኛሉ እያልኩ መልካም ለመሥራት እንዲሽቀዳደሙ ክቡራን መኳንንቶችን አሳስባለሁ ። ቂ ባ ያ ።

የከተማ ወሬ ።

ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ የአየር ባቡር መብረር ።

ንሥረ ተፈሪና ርግበ ተፈሪ የሚባሉ ሁለት የአየር ባቡሮች የጥንቱን ታላላቆች ከተሞች ለማየትና ፊት የነበረውንም የመንገድና ያገር፥የከተማም ካርታ ለማስተካከል፥ ፎቶግራፍም ለማንሣት ካዲስ አበባ እስከ ደሴና ኰረም ድረስ ደርሰው እንዲመለሱ ካዲስ አበባ ኅዳር ፲፰ ቀን ከጧቱ ባንድ ሰዓት ተነሥተው ሦስት ሰዓት ከምስት ደቂቃ ሲሆን ደሴ ደረሱ ።

እነዚሁም የአየር ባቡሮች ከዚህ ሲሔዱ አንዱ በጅሁርና በህያ ፈጅ አልፎ በወረይሉ መንገድ አድርጎ ከዚህ በላይ እንደ ተጻፈው ሰዓት ደሴ ገባ።ሁለተኛውም በደብረብርሃን፥ ባንኮበር፥በመንዝ፥ በግሼና በአልቡኮ አድርጎ ደሴ ገባ።ሁለቱም የአየር ባቡሮች ሲገቡ የገባያውና የከተማው ሰው ሁሉ ይህን ድንቅ ነገር ለማየትና የአየር ባቡሮችንም ለመቀበል ሆጤ በተባለ ሜዳ ተሰብስቦ ይጠባበቅ ነበር። በዚያ ያሉ የግርማዊ ንጉሥ ሹማምንቶች፥ ደጃዝማች ስለሺና ቀኛዝማችፍቅረማርያም ሌሎችም ብዙ መኳንንቶች ድንኳን አስተክለው፥ ሠራዊቱን አሰልፈው ይጠባበቁ ነበርና የአየር ባቡሮቹ በገቡ ጊዜ በብዙ ደስታና ዕልልታ ፥ በትልቅ ክብርም ተቀብለው፥የአየር ባቡር ነጂዎችን አክብረው በሚገባ አስተናገድዋቸው ። በዚያ የተሰበሰበ ሰው ሁሉም በጣም ደስ አለውና አደነቀ።ይህነን ያሳየውን አምላክ እያመሰገነ ግርማዊ ንጉሣችንንም ዘለዓለም ያኑርልን እያለ ወደየቤቱ ተመለሰ። የአየር ባቡሮችም ወደ ማታ ወደ ታዘዙበት ስፍራ ደርሰው ተመልሰው ደሴ አደሩ ።

ዛሬም በኅዳር ፲፱ ቀን ከደሴ በ፩ ሰዓት ተኩል ተነስተው ልክ በስድስት ሰዓት አዲስ አበባ ተመልሰው ገቡ ።

የኢኮኖምያ ፖለቲክ

የ፫፻፷፰ገጽ ተከታይ።

ብዙ ጸሐፊዎችና የመንግሥት ወገኖች ሰዎች ሬቱታን ለማስተው(ለመውረስ)ብዙ ጊዜ በጣም ጥረዋል ግን ተከራካሪዎች ወደረኞች ደግሞ መጀመሪያ መንግሥት በሬንዲቱ ፓሲቲቤ የሚባል የገቢ ትርፍ እንደሚገባ ፡ እንዲሁም ብዙ ጊዜ የሚገለጠው በሬንዲቴ ነጋቲቤ የሚባል የገቢ ክሳራ (ጥፋት)ሊከስ በተገባው። ምሳሌ በሺ፰፻፵፮ ዓ ም (በፈረ ቀኑ)የእንግሊዝ መንግሥት ከገበሬዎቹ አድልቶ የትራስፖርትን የመመላለስ ንድግን ማግባትና ማጣት፣ ለቀረጥ አርነት ሲሰጥ፣ የእንግሊዝ ርስተኞችና ገበሬዎች ፥ በጣም ተጐዱ ። ፪ኛ እውነተኛይቱን ወለድ ከዚያች ወለድ እንደምን ይለያል ?ማለት ወይም የሸጠለት ወይም አባቱ ወይም አያቱ ያጠፋው ምን ያውቃል ፫ኛ)የተኛው ዋነኛ እንደሆነ ሬንዲታን (ትርፍ)በጣም ያተረፈበትን እንዴት ይለያል፣ ያሁን የመሬቱ ዋነኛ ብዙ ሬንዲታ አያገኝም፣ስለምን ከሚገባው ይልቅ በውድ ገዝቶታልና ። ፬ኛ)ፍሬና ክፒታል ሁሉ ባጠፋው ። የሬንዲታን እውነተኞች ምክንያቶች ለማግኘት እንመርምር ። ኤኮኖሚያ የምትሆነውን እንዴት እንደሆነች በፊት እንዳ መለከትነው ፍጥረት ሥራ ፥ ክፒታል እርስ በእርሳቸው ልክ ጥሮፓርጺዮን (ሁነው ተመዛዝነው ሲገጣጠሙ ማለት ከነሱ ትንሽ ብትሆንም ሳትበላሽና ሳትጠፋ እንደሆነች ማፍራትን የምትበለጥገው ተረድተና ። ሚካኤል ተሰማ።

ከዚህ የቀረው በሚመጣው ሳምንት ይታተማል ።

የፍቅር አቀባበል።

ክቡር አባ እንድርያስ በኢትዮጵያ ሀያ አምስት ዓመት አገልግለዋል አገልግሎታቸውም ማስተማርና ልጆች በትምህርት ማሳደግ ነው ። በኖሩበት ዘመንም ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች በትምህርት አሳድገው ልጆቻቸውም ደርሰው በኢትዮጵያ መንግሥት ውሥጥ በሥራቸው የተመሰገኑ ዋና ዋና የሥራ አለቆች ሠራተኞች እንዳሉዋቸው ማንም ያውቃል ።

ክቡር አባ እንድርያስም እስኪሸመግሉ ድረስ ቄይተው አሁን በሽምግልናቸው ጊዜ ወደ አዲስ አበባ ስለመጡ ልጆቻቸውና ወዳጆቻቸው ሁሉ በትልቅ ደስታ ተቀብለዋቸው ይልቁንም እሑድ ኅዳር ፲፫ ቀን ልጆቻቸው አባታቸውን ደስ ለማሰኘት በፊታቸው ተሰብስበው የልጅነታቸውን ፍቅር የሚገልጽ ላባታቸው ሲናገሩዋቸው የአባ እንድርያስ ልብ በደስታና በፍቅር እንደሞላ ልጆቻቸውን ሲመርቁ በተናገሩት ንግግር ይገለጥ ነበር። ስለ ደስታቸውም የሸፓኝ ግብዣ ተደርጎ በሰላም ተሰነባበቱ። እውነትም አስተምሮ አሳድጎ በሽምግልናው ጊዜ ፍሬ ማየት ትልቅ መታደል ነውና አባ እንድርያስ ይህን ቀን እንደትልቅ ዕድል ሳይቈጥሩት አይቀሩም።

ስለ ሹም ሽር ።

ኅዳር ፲፫ ቀን ክቡር ደጃዝማች እምሩ የወሎ አውራጃ እንደራሴ ተብለው ትሁለ አደሬ ማደሯ ተቀብለው ተሾሙ ።

ግራዝማች ኃይሌ አባመርሳ ፈረስ ባልደራስነትን ተሾሙ።

ልጅ መንገሻ ወልደ ጊዮርጊስ ባላምባራስ ተብለው የቀኛዝማች ለጥይበሉ የነበረውን የእልፍኝ አስከልካይነትን ተሾሙ።

ፊታውራሪ አረጋ ግራዝማች ተብለው የግራዝማች ኃይሌ የነበረውን አጋፋሪነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ለተቀበሉ ሹማምት እንኳን ደስ ያላችሁ እያለ የሥራቸውን መከናወን ይመኝላቸዋል

ሽልማት

አለቃ ማፈኛ ወርቅ ዘዓሰበ ተፈሪ ዘውእቱ ደብረ ሰላም ኅዳር ፲ ቀን ጥሩ ካባና ድርብ ተሸልመው በይባቤ እስከ አቡነ ጴጥሮስ ቤት ደረሱ ። አቡነ ጴጥሮስም ትሕትና ልማዳቸው ነውና ግራና ቀኝ ኤሌክተሪክ አስበርተው፣ወምበር አዘርግተው፣ አበባ ምንጣፍ አስለብሰው ሲያስጠብቁ ነበረና በደስታ ተቀበሏቸው ይኸን ያየ ወዳጃቸውም ሁሉ ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥና ለብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ እያለ ምስጋናውን ሲያቀብር አመሸ።ብርሃንና ሰላምም ለወዳጁ ለክቡር አለቃ ማፈኛ ወርቅ የደስታና የጤና ሽልማት ይሁንላቸው እያለ ምኞቱን ያቀርባል ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር

ኑሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋሰው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መዛኛ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የማልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፲ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ ሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ ሐ
የበገና ግጥም	፪ መሐ

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል አሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጩት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው ።



ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስ ፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተልኩ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፯ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፪ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፫ ብር
ባለሰይጣን		፻፹ ብር
ባለ ድመ ።		፻፹
ባለአህያ ።		፻፵፫
ባለሳቢ ግመል ።		፻፳፩
ባለ አንበሳ	አሜሪካ	፻፴፮
" "	ጃፖን	፻፴፫ብር
ሱካር	ጁኒያ	፴፯ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብርተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፱ ፍራንክ ከ፶ሳቲንም
በአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፩ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፫ ብር ፳፭ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፺፬

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት በርሳሊን በርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።ብጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።

ANTICA CASA FONDATA NEL 1857
Borsalino

በኢትዮጵያና በፈረንሰዊ ሱማሌ ወኪል ፣ ፊ. ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም ባአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
5me ANNÉE №. 49

ሐሙስ ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 5 DÉCEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ መንግሥት የአገር ግዛት ሚኒስትር ።

አዋጅ

የአገሩን የማዕድን ብልጥግና ለመጠበቅና ወደ ውጪ አገር የሚወጣን ማዕድን አጠንክሮ ለመቈጣጠር በማለት በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ስም ያገር ግዛት ሚኒስቴር ይህነን አዋጅ ያውጃል ።

፩ኛ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የማዕድን ሥራቤት የሚሰጠውን ደንበኛ ፈቃድ ያልተቀበለ ማናቸውም ሰው በመሬት ውሥጥ ወይም በላዩም ቢሆን የሚገኘው እንደ ሜታልና ሚኔራል የሆነውን ፕላቲንና ወርቅ ያለበትን ነገር ማናቸውንም ዓይነት ክቡር ድንጋይና በክቡር ድንጋይም ዘር የሆነ ነገር መመርመርና መፈለግ፥ ከመሬት ላይ መቈፈርና ማውጣት በኢትዮጵያ ግዛት ሁሉ ተከልክሏል ።

፪ኛ፤ ከዚህ በላይ ባንደኛው ክፍል ከተባሉት ቃሎች የሚተላለፍ ሰው ሁሉ የመንግሥት የሥራ ቤት የቈረጠውን ከ፫፻ እስከ ፪ሺ ብር ድረስ መቀጮ ይከፍላል ። የያዘውንም ማዕድን ይወረሰል ።

የአገር ግዛት ሚኒስቴር ይህነን ደንብ የሚተላለፈውን ሰው እንዲይዝና እየመረመረ ነገሩን እንዲፈርድ ታዟል ።

፫ኛ፤ እንደ ሜታልና ሚኔራል የሆነ ፕላቲንና ወርቅ ያለበትን ነገርና ማናቸውም ዓይነት ክቡር ድንጋይና የክቡር ድንጋይም ዘር የሆነ ነገር ሁሉ የማዕድን የሥራ ቤት የሚሰጠውን ወደ ውጪ አገር የማውጫ ፈቃድና የወጪ ቀረጥ መክፈሉን የሚያስታውቅ የምስክር ወረቀት ሳይዝ ወደ ውጪ አገር እንዳያወጣ ተከልክሏል ።

የጉምሩክም ሠራተኞች የማዕድን ሥራ ቤት የሚሰጠውን ወደ ውጪ አገር ማውጫ የፈቃድ ወረቀት እንዲያቀርብላቸው ያስገድዳሉ። ወደ ውጪ አገር የሚላከውንም ማዕድን ለጉምሩክ ከተሰጠው ማስታወቂያና ወደ ውጪ አገር ከማውጫው ፈቃድ ጋራ መተካከሉን ይመረምራሉ ።

የማዕድንም ሥራ ቤት በሰጠው ወደ ውጪ አገር ማውጫ ፈቃድ ላይ ወደ ውጪ አገር የሚወጣውን ማዕድን መላኩንና የፈቃዱም ወረቀት የፈረሰ መሆኑን የሚያመለክት ማኅተም ያትሙበታል ።

፬ኛ፤ ከዚህ በላይ ባለው በሦስተኛው ክፍል የተባለውን ቃል ተላልፎ ወደ ውጪ አገር ማዕድን የሚያወጣና ለማውጣትም የማፈትን ሰው እስከ ሺ፭፻ ብር ድረስ የሚሆን የመንግሥት የሥራ ቤት የሚቈርጠውን መቀጮ ይከፍላል። ማዕድኑንም ይወረሳል ።

ባንድ ዓመት ውሥጥ ደጋግሞ ይህነን ሕግ ሲተላለፍ የተገኘ እንደሆነ የተገኘው ሰው የዚህን መቀጮ ዓጠፌታ ይከፍላል ።

፭ኛ፤ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ይህነን ደንብ የሚተላለፈውን ሰው እንዲይዝና ነገሩንም እንዲፈርድ ታዟል ።

፯ኛ፤ ይህነን ደንብ የተላለፈውን የሚያስይዝና እንዲፈረድበት የሚያደርግ ሰው ሁሉ የተቈረጠው መቀጮ ከተከፈለ በኋላ ከመቀጮው ገንዘብ ከሦስት አንዱን እጅ ይቀበላል ።

አዲስ አበባ

ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት

የአገር ግዛት ሚኒስቴር

የንግድ ሚኒስቴር

Au nom de Sa Majesté le Negus Tafari, Régent Suprême de l'empire et Héritier du Trône d'Ethiopie; Dans le but de conserver les richesses minières de l'Empire, et d'assurer le contrôle de leur exportation. Le Ministère de l'intérieur .

Décrète :

1.- La prospection, le recherche, la fouille l'extraction, la récolte, tant en profondeur qu'en surface des matières platinifères et aurifères, sous forme de métaux ou de minerais des gemmes des pierres précieuses, sont interdites dans tout le territoire de l'Empire, à toute personne non munie d'une autorisation régulière délivrée par le Département des Mines du Gouvernement Impérial .

2.- Toute contravention aux dispositions de l'article 1 sera passible d'une amende administrative pouvant s'élever jusqu'à la somme de 500 à 2000 thalers et de la confiscation des produits.

Le Ministère de l'intérieur est chargé de la poursuite et de l'Instruction des contraventions.

3.- L'exportation des matières platinifères et aurifères, sous forme de métaux ou de minerais, des gemmes et des pierres précieusess sont interdites sans un certificat d'autorisation délivré par le Département des Mines portant acquit des droits d'exportation .

L'exportation devra obligatoirement faire l'objet d'une déclaration douanière .

Les autorités douanières exigeront la production de l'autorisation d'exportation du Département des Mines. Elles contrôleront la concordance de l'expédition avec la déclaration en douane et l'autorisation d'exportation .

Elles apposeront sur l'autorisation d'exportation du Département des Mines un timbre qui indiquera que la dite autorisation a été annulé par le fait de l'expédition des produits

4.- Toute exportation ou tentative d'exportation en contravention aux dispositions de l'article 3 ci-dessus sera passible d'une amende administrative pouvant s'élever jusqu'à 1500 thalers, et de la confiscation des produits .

En cas de récidive dans le délai d'un e année le maximun de l'amende sera doublé .

5.- Le Ministère de l'Intérieur est chargé de la poursuite et de l'Instruction des contraventions.

La décision infligent l'amende administrative sera notifié au contrevenant par pli recommandé.

6.- Toute personne qui par ses indications permettra la poursuite des contraventions à ce décrèt et la condamnation des contraventions, aura droit à titre de récompense, au tiers de l'amende infligée après recouvrement de celle-ci.

Addis-Abeba le

Au nom du Gonvernement Impérial;

le Ministère de l'Intérieur

Le Ministère du Commerce

ስለ ባቡር ማረፊያ ቤት ምርቃት ።

የባቡር ማረፊያ ቤት ተፈጽሞ የሚመረቅበት ጊዜ ስለደረሰ ከፈረንሳዊ አገር የፍራንኮ ኢትዮጵያ ኩባንያ ፕሬዚዳን ወደ አዲስ አበባ መጡ ። የጂቡቲ አገረ ገዥና የባሕር ወታደር አለቆች ፤ እያሉ የባሕር ወታደርም የባቡር ማረፊያ ቤት ሲመርቅ በዓሉን ለማክበር ወደ አዲስ አባባ መጡ ። ኩባንያውም ለምረቃው ብዙ ሰው ጠርቶ ነበር ።

ኅዳር ፳፬ ቀን የባቡር ማረፊያ ቤት ለመመረቅ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ እንደሚመጡ ስለ ታወቀ ብዙ ሕዝብ ወደ ባቡር ማረፊያ ይጓዝ ጀመር። ከባቡር ማረፊያ የተሠራው አዲሱ ቤትም የኢትዮጵያና የፈረንሳዊ ሰንደቅ ዓላማ እየተሰባጠረ ተሰቅሎበት ሰንደቅ ዓላማው ሲውለበለብ ላይታው ደስ የሚያሰኝ ሁኖ ነበር ። በውሥጡም እሰፌው አዳራሽ ማለፊያ ምንጣፍ ተነጥፎበት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ የሚቀመጡበት የወርቅ ወንበር ተዘርግቶበት ጣራው በትንንሽ የኢትዮጵያና የፈረንሳዊ ሰንደቅ ዓለማ አጊጦ ነበር። አዲስ ከተሠራው የባቡር ማረፊያ ቤት ፊት ለፊትም ዙርያው የተሰናዳ ለአቶሞቢል ማዞሪያ የሚሆን ክብ መንገድ በዞረበት ሜዳ ላይ መሠረቱ ከጥሩ ድንጋይ የተሠራ በላዩ ትልቅ የነሐስ አንበሳ የቆመበት ባንዱ ወገን የግርማዊ ንጉሥ ዳግማዊ ምኒልክ ከነሐስ የተሠራ ሥዕል ፤ ባንዱ ወገን የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ከነሐስ የተሠራ ሥዕል፤ ባንድ ወገንም የልዑል ራስ መኰንን ከነሐስ የተሠራ ሥዕል ፤ ባንድ ወገንም የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ከነሐስ የተሠራ ሥዕል ፤ የተደረገበት ሐውልት ቁሞ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለብሶ ነበር። ልክ አራት ሰዓት ሲሆን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በክቡራን መኳንንቶቻቸው ታጅበው መጡና ተሰልፎ ይጠባበቅ የነበረ የከተማ ዘመኛ የሚገባ ሰላምታውን

ሰጠ ። ቀጥሎም የፈረንሳዊ የባሕር ወታደሮች በሙዚቃ ሰላምታ ሰጥተው ማርሽ ኢትዮጵያን ነፉ ። ከዚያ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ገብተው እየዞሩ የቤቱን ክፍል አዩና በሐውልቱ ፊት ለፊት በሜዳው በተሰናዳላቸው ቦታ ላይ ተቀመጡ። ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳቱ ሚኒስትሮችና መኳንንቶችም በግራና በቀኝ በተዘረጋላቸው ወንበር ላይ ተቀመጡ። በዚያን ጊዜ ሰንደቅ ዓላማ የለበሰው ሐውልት ተገለጠና ሰው ሁሉ ከደስታው ብዛት የተነሣ አጨበጨበ ።

በሐውልቱም ላይ« ለዳግማዊ ምኒልክ አገራቸውን አንድ አድርገው ለገዙ የዘወትር መታሰቢያ እንዲሆን፣ ፍራንኮ ኢትዮጵያ፣የምድር ባቡር ኩባንያ ይህን ሐውልት አቆመ» የሚል ቃል በወርቅ ቀለም ተጽፎበታል ። ሐውልቱ በተገለጠ ጊዜ የአድሚኒስትራስዮኑ አማካሪ ቤት ፕሬዚዳን ሙሴ ገርተን ቀጥሎ ያለውን ንግግር ተናገሩ ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

አሁን በቅርቡ ወራት ግርማዊነትዎ የማገናኛ መንገድ እየሰፋ የመሔዱ ሥራ ላገር ሕይወትና ችሎት ዋና አድራጊው መሆኑን ከስገነዘቡ በኋላ አዲስ አበባን ከባሕር ጠረፍ ጋራ በምድር ባቡር ስላገናኙ ኢትዮጵያ እስከ ዘለዓለም የምኒልክን ወረታ አለማጥፋትዋን አስታውሰው ነበር ።

ይህ ወረታ ከልብ የሚሰማ በመሆኑና ምድር ባቡርን ላቆመው ንጉሠ ነገሥት ከፍ ያለ ክብር ስንል ነው በኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ የምስል ሥራ መምህር የሆነውን የሙሴ ክርዴን ዝክረ ነገሩ ለዘለዓለም ለማይረሳው ለትልቁ ንጉሠ ነገሥት መታሰቢያ አቁመን ተከታዮቻቸው ሊሆኑ ለተገባቸው ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የምናበረክተው ።

ኢትዮጵያ ከባሕር ጠረፍ የሚለያት በረሃ የሆነ ሰፊ አውራጃ ነው ። ባለፈው መቶ ዘመን ውስጥ በዚሁ ወረዳ የነበሩት መንገዶች ጥቂቶችና የሚያስጉ ነበሩ ፤ ጓዝ ማመላለሱም ብዙ ጭንቅ ያለበትና ዋጋውም ውድ ነበረ ፤ የኢትዮጵያ ደጋ ደጋው ባለ ጠጋ አውራጃ ሁሉ ከከብት ፤ ከእርሻና ከማዕድን የሚያገኘውን ዋና ጥሬቱን ወደ ባሕር ለማቃናት አንድ የብረት መንገድ ብቻ መቆሙ አገሩን ወደ እውነተኛ ከፍታ ለመድረስ አበቃው ። ለወደፊቱ የሚሆነውን ነገር ሁሉ አጥርቶ በማየት የሥራ ማቆም ንቃት ባለበት ልባዊነታቸው ውስጥ ይህን ነገር ከፍጻሜ ለማድረስ በአእምሯቸው ላይ ያሳደሩ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ አፄ ምኒልክ ናቸው ።

በመጋቢት ፱ ቀን ፲፰፻፹፮ ዓመት ውስጥ በተደረገው ውል ለሙሴ ኢልግና ለሙሴ ሽፍኔ ጂቡቲን ከሐረር ጋራ ሐረርን የዚያን ጊዜ ዋና ከተማ ከነበረው ከንጦጦ ጋራ ፤ እንጦጦንም በከፋ በኩል አድርጎ ከነጭ አባይ ጋራ የሚያገናኝ የምድር ባቡር እንዲሠራ ኮንሴስዮን ተፈቅዶ ነበር ።

በዚሁ ምክንያትም የፈረንሳዊ መንግሥት ደግሞ በበኩሉ በሶማሊ ጠረፍ ውስጥ በርሱ ጥገኝነት ባለው አውራጃ ላይ የባቡር መንገድ እንዲሠራና ለጥቅም እንዲሆን ማከናወንን ፈቅዶ ተፈራርሞ (ኮምፓኚ) ኢንፔሪያል ዴ ሽመን ዴ ፈር (ኤቲዮፒን) የተባለ ማኅበር ቁሞ ይዘት ነበር ።

የብረቱ መንገድ ባሸዋው በረኻ ላይ ተነጥሮ አልፎ የሰርመንጋብን ዓቀበት ለመውጣትና በኢትዮጵያ ቅጥር ተራራ ላይ ተንጠላጥሎ ዘልቆ ከሐረርጌ በስተቀኝ በኩል ካለው ከጨርጨር እግር ለመድረስም አምስት ዓመት አስፈለገው ። በጥር መጀመሪያ ቀን ፲፱፻፫ ዓመት ውስጥ ምድር ባቡሩ ጂቡቲን ከድሬ ደዋ ጋራ አገናኝቶ ፍሬውን ከጥቅም ለማዋል መንገዱ የተከፈተ ሁኖ ነበር። ነገር ግን በዚሁ ሥራ ውስጥ የነበረበት ችግር ትልቅ በመሆኑ ምክንያት ኮምፓኚ ኢምፔሪያልን ሥራውን ከድሬ ዳዋ ወደ ላይ እንዳይገፋ አደረገው ።

ከልባቸው ውስጥ ያሳደሩትን አሳብ በፍጥነት ከፍጻሜ አድርሶ ለማረጋገጥና አዲሱን ዋና ከተማ በቀጥታ ከባሕር ጋራ ለማገናኘት በዚህም ለመንግሥታቸው ትልቅ ሕይወታዊ ጥቅም ሁሉ እንዳለበት በልባቸው ስለ ተሰማቸውና ወዲያውም ደግሞ የኢትዮጵያንና የፈረንሳዊን አንድነት ፈጽሞ ለማቀራረብ ሲሉ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ አፄ ምኒልክ የፊተኛውን ኮንሴስዮን (የፍራንኮ) ኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኩምፓኒያ ለተባለ አዲስ ማኅበር አሳልፈው ሰጡት ። የፈረንሳዊ መንግሥት ደግሞ በበኩሉ ከዚሁ ማኅበር ጋራ ተስማምቶ በመጋቢት ፰ ቀን ፲፱፻፱ ዓመት ውስጥ ተፈራርመው በተከታዩ በሚያዝያ ወር በሕግ የተቀበለ ሆነ ።

የዚያን ጊዜ ማኅበራችን ሳይዘገይ በውዝፍ ቀርቶ የነበረውን የመንገድ ሥራ እጅ አድርጎ ወዲያው እስከ ተመደበው ዳርቻ ድረስ ለመቀጸል ችሎት ከማግኘት አቅም ደረሰ።

ኩምፓኒያው ዓለምን ሁሉ በገለባበጠው በትልቁ ጦርነት ጊዜ ይህን ሰፊ የሆነ ሥራ ለመፈጸም ሲል ካገኘው ብዙ ዓይነት ችግሩ ሌላ ደግሞ ከጓይቱ ላይ ጥልቅ የሆነ አለታም ጉድጓድ ያለበትን ተራራና ጤና የሌለበትን ቈላ ሜዳና ለእጅ ሥራ የሚሆን ገንዘብ የማይገኝበትንና ማናቸውንም ነገር ሁሉ ለማመላለስ የሚያስቸግረውን ወረዳ ዘልቆ ጥልቅ የሆነውን ያዋሽን ጉድጓዳና ቆላ ወንዝ ተሻግሮ ከፍ ያለው የደጋው አገር ከሚጀመርበት መሬት ዘንድ ቈርጦ እስኪደርስ ድረስ በቴክኒክ ሥራ አስተያየት ያገኘውን ይህነው ሊባል የማይቻል ጭንቅና ችግር ሁሉም ለመዝለቅ መንገድ አገኘለት ።

በግንቦት መጀመሪያ ቀን ፲፱፻፲፪ ዓመት ውስጥም እስከ ስድስት ኪሎሜትር ደርሶ ከአንድ ዓመት በኋላም እስከ መቶ ታምሳ ኪሎሜትር መዔሶ ላይ ደርሶ አዲሱ የባቡር መንገድ ዱሮ ፍሬን መስጠት ጀምሮ ነበር ፤ ርዝመቱ መቶ አምሳ አንድ ሜትር የሆነውና ከድልድዩ መሠረት በላይ ቁመቱ ስድስት ሜትር የሆነው ያዋሹ ድልድይ ደግሞ በታኅሣሥ ፳፮ ቀን ፲፱፻፲፫ ዓመት ውስጥ ተቀጥሎ አልፎ ነበርና ሎኮሞቲቡ በ፲፱፻፲፬ ዓመት በጥር ወር ማለቂያ ላይ ወንዙን ተሻግሮት ነበር ፤ ምንምኳ በዚሁ ትክክለኛ ዓመት መጨረሻ ለጦርነት ከተት ስለ

ተባለ ይሁ ጦርነት ያመጣበት ችግር የተወሰነውን ሥርዓትና የሥራውን አካሔድ በማፍረሱ የጒዳቱ መሰማት ኩምፓንያውን በቀጥታ ቢነካበት ፤ የተዘረጋው ሐዲድ ዱሮ ከሞጆ ጣቢያ ደርሶ ነበር፤ ይህም ከጅቡቲ አንሥቶ እስከ ፯፻፲፭ ኪሎሜትር ድረስ ደርሶ ነበር ማለት ነው ። በመጨረሻውም አዲስ አበባ ሊገባ ጥቂት ያህል ኪሎሜትር ቀርቶት ሲኖር ግርማዊነትዎ ያልጋ ወራሽነትንና የእንደራሴነትን ሥልጣን ከያዙ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው የሚያስፈልገውን ቦታ ሰጥተውን ዛሬ ያለን ቤት ባቡር መቋሚያ የቆመው ።

ይኸው ከዚያ ወዲህም ለንግድ የሚሆነው ሥራ እንዲሻሻልና የኢትዮጵያ ሀብት በንግድ እንዲሰፋና እንዲበለጽግ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ከመጋደል አልበዘነም፤ ለወደ ፊቱም አንበዝንም ።

በሌላ በኰልደግሞ ብዙ ገንዘብ ያወጣንለት የምድር ባቡሩ መሣሪ ልክ ሊወሳ በተገባው መጠን ዱሮ እየበዛና እየተሻሻለ ሔዷል ፤ አሁን ባዲስ አበባና ለም በሆነው ደጋ ደጋው አገር መካከል እየለቱ የሚመላለስ ባቡር ቁሟል ፤ አዲስ አበባንና ባሕርን የሚያገናኘው ባቡርም ተሻሽሎ ቁሟል ፤እቃ ለማሳፈር የሚመቹ ሰፋ ሰፋ ያሉ ለንግድ ጒዳይ የተሠሩ ቤቶች ያሉባቸው የባቡር ማረፊያዎችም አልፈው አልፈው ተከፍተዋል። በዚሁ አካሔዳችን ዘወትር አስበን እየጨመርን መሥራታችንንና ሳናቋርጥ ፍሬ የሚያወጣውን ተግባራችንን ፍቅረኛና በጣም የተቀራረበ በሆነ የሥራ ባልንጀርነት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ የምንሠራ መሆናችንን ጌታዬ ቢተማመኑት ይቻልዎታል ።

ለአዲሱ ዘመን የተገባ ባቡር መቋሚያ አዲስ አበባ ላይ መሥራቱ ባንድ ወገን የሥራችንን መፈጸም ሲያስረዳ፥ ባንድ ወገን ደግሞ ለኋላ ልጅ ለዚሁ ሥራ የዛሬው ትውልድ ምንያህል ትጋት ያለበት ኃይሉን እንደሰጠለት ይመሰክራል፤ የባቡር መቋሚያ መሥራትም በዓለም ላይ ባለው ባለ ጠግነት እየገፋ የሚሔደውን ስፍራውን የሚያያዝ ከተማ መሆኑን ጭምርት እንጂ ስሙ በገነነው በንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ልጅና ጥልቅ በሆነ አሳብ የሕዝቡን መታደል በሚመኘው ሥልጣኔ ሳለበት ሥራ ሁሉ በሚተጋ ንጉሥ ክንፍ ጥላ በታች ሁኖ እዲስ አዲስ በሆነ ለማየቱ ደስ በሚያሰኝ እየለቱ እያጌጠ የሚሔደው የዋና ከተማው መግቢያ ብቻ ሁኖ አይታይም ።

ይህን በልባዊ ዓይን አሻግሮ በማየትና ለወደፊቱ የሚሆነውን ተማምኖ በተስፋ በመመልከት ነው በፍራንኮ ኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኩምፓንያ ስም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የማክበር ፍቅራችንንና ለግርማዊነታቸው ከበሬታ ለኢትዮጵያ መንግሥትም ልማትና ስፋት የምናቀርበውን ምኞት እንዲቀበሉን የምንለምን ።

ፕሬዚዳንቱ እንዲህ ብለው ከጨረሱ በኋላም የፈረንሳዊ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሙሴ ዶረፌይ የሚከተለውን ንግግር ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ ፤

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

ሙሴ ለፕሬዚዳን ።

ክቡራን መኳንንቶችና ወይዛዝሮች የኢትዮጵያና የፈረንሳዊ የምድር ባቡር ኩባንያ ሥራ ጠቅላይ አማካሪ ኩባንያ በልዩ ልዩ የሚያስቸግር ጊዜ የሆነውን ነገር አሳልፎ የምድር ባቡር መንገድ ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ ዋና ከተማ ወደ አዲስ አበባ መድረሱን በአማረ ቃል አሁን አመልክቷችሁ፡በጥበብና በችሎት ሥራውን የሚሠራው ይህ ኩባንያ በር ለሚሆነው ለዋናው ከተማና ለማገልገል ለተሰናዳው ለታላላቅ የንግድ ሥራ የሚገባውን የሥራውም መከናወን ምልክት የሆነውን በመሐንድሶች ጥበብ በአሁኑ ዘመን የሚሠራውን የባቡር መቆሚያ ባቡር በደረሰበት በመጨረሻው ስፍራ ላይ ለመሥራት ፈቃዱ ሆነ ።

ይህ የምድር ባቡር መንገድ ስንት ችግር አሸናፊ ሁኖ እንደ ተፈጸመ አመልክተዋችኋል። ደግሞ ታላቁ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ በኩባንያው ላይ ያደረጉበትን እምነት ለመጠበቅ ኩባንያው የደከመውን ድካም ሁሉ የፈጸመውን ሥራና ግርማዊነታችሁም ለሚያኖርበት እምነት የተገባ ይሆን ዘንድ ወደፊት እየበረታ እንዲሔድ አስታውቀዋችኋል ።

ኩባንያው ይህ አገር በገንዘብ ረገድ ጥቅሙ እየሰፋ እንዲሔድ ዋና መሣሪ ይሆን ዘንድ ከልቡ ያስባል ። ይህንንም ሥራ የአገሩን ገዦዎች በመልካም ፈቃድ ካልረዱት ለመፈጸም አይችልም ። የአገሩም ገዦዎች እርዳታ እንዳያጒድሉበት ርግጥ ነው። ይህም የምድር ባቡር ለኢትዮጵያ ዘወትር በትጋትና በአዲስ ጥበብ የሚሠራ ለመንገደኞችም የተመቸ፡ዘወትርም እየበዛ የሚሔደውን የንግድ ዕቃ ብዙ ገንዘብ ሳይፈጅ ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላው የሚያመላልስ እንዲሆን ያስፈልጋል ። የገንዘብ ጥቅም ስፋት ወደ ሥልጣኔ መቅደም የአገሩም ሕይወት ከምድር ባቡር ሥራ ስፋት ከሥራው መከናወንና ከመቋቋሙ ጋራ የተሣሠሩ ናቸው። ፍሬው ያማረ፡ለሚመጣውም ጊዜ ብዙ ጥቅም ያለበት ደስ የሚያሰኝ ነገር የሚያመጣ ይህን የመሰለ መረዳዳት ነው እንጂ ከቶ ባለፈው ዘመን ሁሉ ከዚህ የበለጠ የሚጠቅም ሌላ ነገር አልተገኘም ።

ግርማዊት ንግሥት ሆይ ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

ይህ ዛሬ የተዋበ የባቡር መቆሚያ ተሠርቶለት የተፈጸመው የምድር ባቡር ከፍ ባለው እርዳታችሁ ተማምኖ ቁሙዋል። በበጎ አድራጊነታችሁ እየተመለከታችሁት የኢትዮጵያ መንግሥት ልማት ለማረጋገጥና በቀን በቀኑ የሚበረታ መሣሪ ሁኖ እንዲያግዛቸው ፈቃዱ ነው ።

ይህ የምድር ባቡር መንገድ ሳይሠራ አስቀድሞ ኢትዮጵያ ከፍ ባለ ወደርሱ ለመቅረብ በሚያስቸግር ታላቅ ተራራ ላይ ተለይቶ እንደ ተሠራ ታላቅ ቤት ነበረች ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ፥ ግርማዊነታችሁም አገራችሁ በመላው ዓለም የሚደረገውን የሥልጣኔ ሥራ ተከፋይ ይሆን ዘንድ ፈቃዳችሁ ሆነ ። በጥበብም አስባችሁ ኢትዮጵያ ተለይታ መኖሯ እንዲቀር ፈቀዳችሁ ። ስለዚሁ ተለይታ ትኖር የነበረችው ኢትዮጵያ በምድር ላይ ካሉ ከሌሎች አገሮች ጋራ አሁን የምትገናኝበትን ፤ ኢትዮጵያን ለመጐብኘት የሚፈልጉ ሰዎች ያለ ድካም በቶሎ የሚመጡበትን፥ ለኢትዮጵያም የሚያስፈልጋት ብዙ የንግድ ዕቃ የሚመላለስበትንና ደግሞ ብልጽግና የሆኑዋትን ከርሷ የሚወጡትን ነገሮች በመላው ዓለም ሁሉ የሚላክበትን ይህን እንደ ሽበ ስልክ መሬ የሆነውን የብረት መንገድ አሠራችሁ ።

በዚህም በብረት መንገድ ጫፍ ሕዝብን ሳያለያይ የሚያገናኘው ታላቁን መንገድ ጠረፍ እናገኛለን እርሱም ባሕር ነው ።

በባሕርም ላይ በመርከብ ተጕዘን ፖርት ሣይድ፤ ማርሴይ፥ ናፖል ፥ ሎንዶን ፤ ሐምቡርግ ፤ አንቬርስ ፥ ኔው ዮርክ ፤ ሕንድ፥ ዣፖን የሚባሉትን ያለ ችግር ወደ ኢትዮጵያ መንገዶቻቸውንና በዚያም የሚገኘውን ነገር የሚያመጡ ከኢትዮጵያም የሚሔዱትን የሚቀበሉ አገሮች እናገኛለን ።

ስለዚህ ይህ የምድር ባቡር የሥልጣኔ መንገድ ነው፥ የግርማዊነታችሁን መንግሥት ከሌሎቹ ከዓለም ክፍሎች ጋራ የሚያገናኝ መስመር ነው። የኢትዮጵያ ገዦዎች ይህን የምድር ባቡር መንገድና፥ ማመላለሱን ሥራ ለፈረንሳዊ መሐንዲሶችና ልዩ ሠራተኞች መርጠው በእምነት በመስጠታቸው የተነሣ ልቤ ሊኰራ የተገባው ነው።

የምድር ባቡርን ሥራ ለጀመሩት ለዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የተሠራውን የአክብሮት ምልክት የሆነውን ይህን ሐውልትና ለኢትዮጵያ ጥቅም ታስበ የታላቅ ሥራ አክሊል የሆነውን ይህን የባቡር መቆሚያ ለግርማዊነታችሁ ለማስረከብ ረጅም መንገድ ተጕዘው የመጡትን የሥልጣኔ መሪ የሆኑትን መልካም ሠራተኞች የኩባንያውን ሥራ ጠቅላይ አማካሪ ሙሴ ዠተንን ፤ የሥራው አማካሪ የሆኑትን ሙሴ ሚሼል ኮትንና ዋናውን ዲሬክተር ሙሴ ከሙን እዚህ አመሰግናቸው ዘንድ ግርማዊነታችሁ ይፍቀዱልኝ።ደግሞ በሥራ የሚረዳቸውን የባቡርን ኩባንያ ዲረክተር ሙሴ ዱዋዜሊንና የኩባንያው እንደራሴ የሆኑትን ሙሴ ዤርባልን በዙርያቸው ሁነው የባቡሩ መንገድ በመልካም እንዲኖርና ሥራውም እንዲሠራ፥የባቡሩን ሥራ እየሰፋ እንዲሔድ በየጊዜው በመታመን በጥበባቸው፤በሥራቸው፥ በድካማቸው የሚሠሩትን ሠራተኞች ሁሉ አመሰግናለሁ ።

ሥራውን ለማጠንከርና ለኢትዮጵያ ከሁሉ ይበልጥ ዋና የሆነውን ለሕዝብ የሚያገለግል ሥራ ለማሻሻል በትጋት ሠርተው አገራችንን ስላመሰገኑ አመሰግናቸዋለሁ ።

ደግሞ ይህን የባቡር መቆሚያ የሠራውን ስሲዬቴ ቴክኒክ እንዱስትሪዬል የሚባለውን ኩባንያና እንደራሴውን ሙሴ ሽቢያርን መሐንዲሶቻችንና በጥበብ ለሚሠሩት ሠራተኞቻችን ማስከበሪያ የሚሆነውን የተዋበ ታላቅ ሥራ በዚህ አገር ስለ ሠሩ ማመስገን የተገባኝ ነው።የፈረንሳዊ ታላቅ ወዳጅ ለሆኑት ለዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ እንዲሆን የተሠራውንና ለአዲስ አበባ ከተማ ጌጥ የሚሆነውን ይህን ሐውልት ለማስረከብና የባቡሩን መቋሚያ ለመመረቅ የፈረንሳዊን የአንደኛው ፥ የተዋበውን የጦር መርከብ አዛዥና ቱርንቢል በሚባለው መርከብ ላይ የሚሠሩትን የወታደር ሹማምንቶች የመርቡንም ሠራተኞች የበዓሉን አፈጻጸም ለማድመቅ ወደዚህ በመላኩ የፈረንሳዊ መንግሥት ለግርማዊነታችሁና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍ ያለ አሳቡን ገለጸ ።

ዳግም በዚህ በዋና ከተማ ታሪክ ታላቅ ቀን ሁኖ የሚጸፈውን ይህን በዓል ለማክበር የመጡትን የሥራ ጓደኞቼንና መኳንንቶችን አመሰግናለሁ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ ።

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

ለዋና ከተማችሁ የሚገባ የባቡር መቆሚያ ለመሥራትና ደግሞ አገሩ በየቀኑ ከፍ ያለ ጥቅም እንዲያገኝበት የባቡሩን መንገድ ለመሥራት የደከሙትን ሠራተኞች ወረታቸውን ለመመለስ የዛሬውን በዓል ለማክበር ስለመጣችሁ አመሰግናለሁ።

በኢትዮጵያና በሌላውም የዓለም ክፍል መካከል አቀራራቢ የሆነው የምድር ባቡር መንገድ በመንግሥታችሁና በሌሎቹም መንግሥታት መካከል ያለውን ወዳጅነት የሚያጠብቅ እንዲሆን ዛሬ የገለጻችሁላቸውን የበጎ አድራጊነት አሳብ ወደ ፊትም እንደዚሁ እንድታደርጉላቸው እለምናለሁ ።

በብዙ ችግር ቈይተው አሁን በችግራቸው ፋንታ ክብራቸው የሚሆነውን ይህን ሽልማት ያገኙ ውድ የሆኑ የአገራችን ሰዎች ይህንኑ ምኞት ይመኛሉ ።

ሚኒስትሩ ተናገረው ከጨረሱ በኋላም ግርማዊ ንጉሥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ንግግር ተናገሩ

ሙሴ ፕሬዚዳንት ሆይ ።

ሙሴ ሚኒስትር ሆይ ።

በኢትዮጵያ መጀመሪያውን የምድር ባቡር ለመሠረቱ ከእኛ በፊት ለነበሩት ለዳግማዊ አፄ ምኒልክ መታሰቢያ ከፍ ያለ አክብሮታችሁን ለመግለጽ አሁን የተናገራችሁት የምስጋና ቃል መስማታችን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው ።

ዛሬ ዋና ነገር መሆኑን ልንገምተው የምንችለው የከፍተኛ አሳብ ፍሬ የሆነው የምድር ባቡር ሥራ በተፈጸመበት ቀን ፤ ይህን የምስጋናችሁ ምስክር የሆነውን ፤ በሜትር ጋርዲ ጥበብ የተቀረጸውን የተዋበ ሐውልት በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስምና በእኛም በራሳችን ስም ሁነን በመቀበላችን ደስ ብሎናል ።

እርስዎም ራስዎ እስታውሰው እንደ ተናገሩት ይህ በኢትዮጵያ የተሠራው መጀመሪያ የምድር ባቡር በአንድ አንዱ ስፍራ በመሬቱ አስቸጋሪነት አኳኋን የተነሣ ብዙ ድካም ነበረበትና ፤ ስለዚህ በማናቸውም በኩል ለዚህ ሥራ በብርታት ተባብረው ሥራውን ለፈጸሙ ሠራተኞች ምስጋናችንን እንሰጣቸዋለን ።

በእነርሱም ድካም፥ ይህ የምድር ባቡር ተዘጋጅቶ አዲስ አበባን ከጅቡቲ ጋራ በቀጥታ የሚያገናኝ መንገድ ላገራችን ተሠርቶ ላአገሩም ጥቅም ስፋት የሚያስፈልገውን በር ከፍቶለት ፤ በፍጹም ከሌሎቹ አገሮች ጋራ የጥቅምን መተባበር አዘጋጀለት ።

ብዙ ዘመን ከተደከመበት በኋላ አሁን ስለ ተፈጸመ የብልሆችና የጠንካሮች መመስገኛ ጊዜ ተጀመረ ። እስከሁንም የተገኘው የሥራው ፍሬ የሚያፅናና ነው ።

ስለዚህ ከፍ ያሉት የምድር ባቡር ኩባንያ የሥራው አስናጂዎች አሳባቸው ፤ እንደ ተቻለ መጠን ለንግዱና ለኢትዮጵያ ጥቅም ልማት እንደሚስማማ የሥራቸውን አካሔድ ለመምራት ዘወትር እንዲደክሙ የሚገልጹበትን ማስታወቂያ አሁን ዘርዝረው ሲነግሩን በተለይ ደስ እያለን ሰማን ።

እኛም በበኩላችን የኢትዮጵያን መንግሥትና የምድር ባቡርን ኩባንያ የሚያስተሣሥረውን ሥራ እየጠበቅን ፤ የበጎ ፈቃድ እርዳታችንንና በወዳጅነት ተባብረን ለመሥራት ምኞታችን መሆኑን እናረጋግጥልዎታለን ።

መሪ የሚሆነንን ለሁሉ ጥቅም ያለውን ፍጹም የሆነን ስምምነት አጠንክሮ ለመኖር መልካም መንገድ በሁለቱም ወገን ያለውን ወዳጅነት በትክክል ተከትሎ መጠበቅ ነው ።

አሁንም የምድር ባቡሩ መንገድ እንዲደርስ እስከ ታሰበበት እስከ መጨረሻው ቦታ ስለ ደረሰ ፤ እንደ ጊዜው እንደ አዲሱ ጥበብ ሁኖ የተሠራው የባቡር ማረፊያ የሥራውን መፈጸም እየገለጸ ለዋና ከተማችን ጌጥ የሚሆናትን ያማረ ቤት አቆመለት ።

ሥራው የተዋበ ሁኖ ለሚሠራበትም ሥራ የተስማማ የሆነው ይህ የባቡር ማረፊያ ቤት በቶሎ ፣ሠራውን«ሶሲኤቴ ቴክኒክ ኤአንዱስትሪኤል ዳንትርፕሪዝ»የሚባለውን ኩባንያ ያስመሰግነዋል።

በመዘጋጀትና በልማት መንገድ እየተፋጠነ በሚሔደው በኢትዮጵያ ፤ በአገሩ ያሉት የሥራ ክፍሎች ሁሉ ባለማቋረጥ ለሥራ መትጋታቸውን በሁሉ ፊት የዚህ ቤት ሥራ ምስክር ይሆናል የተባለው ቃል እርግጠኛና ትክክለኛ ነው ።

ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት፤ ለእኛም ለራሳችንና ለኢትዮጵያም ልማት ስለ አቀረቡት ምኞት አጥብቀን እናመሰግንዎታለን ።

ከእኛም አስቀድመው የነበሩት ፤ በብልህነታቸውና በመልካም አስተያየታቸው ያማረውን የዛሬውን ደስታ የሰጡንና ለወደፊትም እጅግ የተሻለውን የአሳብ መንገድ የገለጹልንን የስመ ጥሩውንና የታላቁን የዳግማዊ አፄ ምኒልክን የማይረሳ ስማቸውን ከልባችን ሳናጠፋ ስናስባቸው እንኖራለን ።

ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፤ ኢትዮጵያ በሥልጣኔ እየገፋች ለዘለዓለም ትኑር ።

Monsieur le président
Monsieur le Ministre

C'est avec émotion et fierté que nous venons d'entendre les paroles de gratitude par lesquelles vous avez rendu un éclatant hommage à la mémoire de notre Auguste prédécesseur S. M. L'Empereur MENELIK II, créateur du premier Chemin de Fer en Ethiopie.

Nous sommes heureux de recevoir aujourd'hui au nom de S.M. L'Impératrice ZAOUDITOU et en notre nom personnel ce beau monument du au talent de maître Cardet; expression de votre gratitude à l'occasion de ce couronnement de l'œuvre de haute clairvoyance qu'a été la construction de ce Chemin de fer dont nous pouvons aujourd'hui apprécier toute l'importance

Ainsi que vous l'avez rappelé, l'établissement de ce premier Chemin de fer en Ethiopie, a coûté des sacrifices de tous genre, de longs efforts et de la ténacité à cause de la natures du terrain par endroits Aussi, notre reconnaissance va-t-elle vers tous les travailleurs, à quelque degré de l'echelle que ce soit, qui ont participé courageusement à cet construction.

L'effort de tous a ainsi doté notre pays d'une voie directe relient Addi-Abeba à Djibouti, et lui ouvert un débouché sur la mer, indispensable au développement économique de l'Empire, ainsi qu'à 'union économique plus complète avec les autres pays.

Après la période de lutte et venue la période de succès. Maintenant, celle de la récompence des efforts, intelligents et tenaces s'est ouverte, et les fruits déja recueillis sont encourageants.

Aussi, c'est avec un plaisir particulièrement vif que nous vous avons entendu définir le programme de la haute Administration du Chemin de fer comme étant d'apporter sans cesse tout ses efforts à l'organisation méthodique de l'exploitation dans toute la limite du possible, pour satisfaire aux nécessités du trafic et au développement économique de L'Ethiopie.

De notre côté, vous pouvez être assuré de notre bienveillant appui et de notre désir desamicale collaboration unissant le Gouvernement Ethiopien et la Compagnie du Chemin de fer. Nous sommes persuadés que le juste observation des obligations réciproques, constitue le moyen le plus propre à maintenir l'amicale et parfaite entente profitable à l'intérêt général qui nous sert de guide.

A présent la Voie ferrée a atteint le point terminus qui lui avait été assigné; et l'édification

d'une gare moderne à Addis-Abeba, consacre cet achèvement et le pare d'une belle construction dont s'en orgueillit Notre Capitale.

Cette gare moderne dont nous admirons l'élégance de à la ligne et les dispositions pratiques, fait pleinement honneur à la Société Technique et Industrielle d'Entreprise qui l'a édifiée rapidement.

Nous nous associons à ces paroles justes: que cettte édification atteste aux yeux de tous, l'effort constant développé dans toutes les branches de l'activité dans L'Empire d'Ethiopie en marche rapide dans la voie de l'ordre et du progrés

Nous vous remercions bien sincèrement des Voeux que Vous venez d'adresser à S.M.L'Impératrice ZAOUDITOU et à Nous-même et pour la prospérité de L'Empire d'Ethiopie·

Nous nous inclinons devant L'immortelle Mémoire de Notre Auguste prédécesseur L'Empereur MENELIK II dont L'intelligence, la clairvoyance nous ont procuré la joie de ce beau jour, et ouvert les plus belles perspectives pour l'avenir.

Vive S. M. L'Impératrice ZAOUDITOU

Vive L'Empire d'Ethiopie dans la voie du progrès.

ግርማዊ ንጉሥ ተናግረው ከጨረሱ በኋላም ከዳር እስከዳር ጭብጨባው ቀለጠ።

ይህ ሁሉ ሲሆንም ሁለት የአየር ባቡሮች በአየሩ ላይ ይንዣበቡ ነበር። ይልቁን ንሥረ ተፈሪ በአየሩ ላይ እየተገለባበጠ ብዙ ጊዜ ሲመላለስ ስለቈየ ለሰው ሁሉ አስደነቀው ። ከዚህ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ሐውልቱን እየዞሩ አይተው ወደ ቤቱ ተመለሱና የሽፓኝ ግብዣ ተደረገ። ከሽፓኙ ግብዣ በኋላ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ወይዛዝሮችም ከግርማዊት ንግግሥተ ነገሥታትና ከግርማዊ ንጉሥ ተሰነባበቱ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም በማረአጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

KONIAK
COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት



ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገናል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው



Borsalino



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊ ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛ ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶
5me ANNÉE № 50

ሐሙስ ታኅሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 12 DÉCEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir reguer dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አስተማሪና ሃኪም ሲዳሞ ስለመግባት ።

ሲዳሞ ከሁን ቀደም የሥልጣኔ መንገድ ጨልሞበት በሕሊናዋ ስላልተጻፈበት አሁን ዛሬ ቢወድቁ ይነሷል በ፳፥ቢዘገዩ ይከብሯል በገጋ እንደተባለ ተደርጎ የማይታወቅ በክቡር ደጃዝማች ብሩ ጊዜ መልካም ሐሣብዋ ተፈጽሞላት ደስታዋ ከልክ ያለፈ መሆኑ የታወቀ ነው። ኅዳር ፳ቀን ሐኪሙና አስተማሪው ሲዳሞ ገቡና ክቡር ደጃዝማች ብሩ ግሩም በሆነ አቀባበል እንደተቀበሏቸው ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን። ገርብቾ ከሚባለው ከተማ ሲደርሱ የክቡር ደጃዝማች ብሩ አሽከሮችና የክቡር ደጃዝማች ባልቻ አሽከሮች የነበሩትም ባማረ ጐፈርና በተለየ መሣሪያ ተሰልፈው ነበርና እሑድ ጧት ተከተማው በሁለት ሰዓት ሒደው ተቀብለው ተቀኑ በ፫ሰዓት ባማረ ሰልፍና ዓጀብ ሁነው ከዋናው ከተማ ሀገረ ሰላም ደረሱ። በከተማው ውሥጥና በየመንገዱም ላይ መለዮ የሆነ የደስታ መግለጫ ባንዲራ ተተክሎ ነበር ።

በሰልፍ ትምህርት የሠለጠኑትም ኮት ለባሽ ዘበኞች በመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፈው ቁመው የሚገባቸውን ሰላምታ ሰጡ።

ከሠራዊቱም ብዛት የተነሣ መሬቷ ተጨናንቃ ነበረች። ክቡር ደጃዝማች ብሩም ልዩ የሆነ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ከትልቁ አደራሻቸው ወርደው መኳንንቶቻቸውን ግራና ቀኝ አድርገው ጌጠኛ በሆነ ወንበራቸው ተቀምጠው ነበር ። አዳራሹም ጥሩ ጥሩ ምንጣፍ ተነጥፎበት ያማረ ያማረ ወንበርም ተደርድሮበት ግሩም በሆነ ጌጥና ሰንደቅ ዓላማ በሌላም በሚያስደንቅ አበባ አጊጦ አምሮ ነበር።ሐኪሙና አስተማሪውም በገቡ ጊዜ ለክቡር ደጃዝማች ብሩ የሚገባቸውን ሰላምታ ሰጥተው አምሮ በተሰናዳላቸው ወንበር ተቀመጡ ። የደኅና መድረሳቸውንም ነገር ከጠየቋቸው በኋላ ሐኪሙና አስተማሪው እየተነሡ ደስታቸውን ይገልጻሉ ።

ክቡር ዶክተር ሽሪኮፍ ተነሡና ቀጥሎ ያለውን ንግግር ተናገሩ።

ክቡር ደጃዝማች ሆይ ለሀገርዎ ጥቅም እንደሆን እኔና ባለቤቴ በመምጣታችን እጅግ አድርገን ደስ ብሎናል። መጀመሪያ ስመጣ ለሀገሩ እንግዳ ነበርሁ።በሀገሬ ሳለሁ የኢትዮጵያ ልምላሜና እሷ እራሷ ሕልም መስላ ትታየኝ ነበር ። ከጥቂት ቀን በኋላ ግን ሀገሩንና ሕዝቧን በለመድሁ ጊዜ አገሬ ካለሁ ከስማሁት አፈቀርኋቸው። እኔም ከሀገሬ መምጣቴ በማውቀው ሕክምናና መድኃኒት ከእግዚአብሔር ጋራ ሕሙማንን ለማከም ክልቤ በጣም ተስፋ አድርጌ ነው።ክቡር ደጃዝማች ብሩም እኔን ያመጡኝ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው አረዳትና ጠቃሚ እንድሆን ነው ደግሞም ለሲዳሞ አውራጃ ሕዝብ ረዳትና እውቀት መሪ እንድንሆን እኔንአስተማሪዎቹን በራስዎ ገንዘብ አስበው ማስመጣትዎ ውዴታዎን ለኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ይገልጻሉ።ሕዝቡም ስለ ደጉ ሐሳብዎ እግዚአብሔር ይርዳዎ እያለ ያመሰግንዎታል ። እንደዚሁ በጥቂቱ መሻሻል ኢትዮጵያ በሥልጣኔ መንገድ እውቀት እየጨመረች ጥበብን እየተማረች ብርሃን እየታያት ወደ ታላቁ ደረጃ ትደርሳለች በመንገዳችን አከሔድ ድካም ተሰምቶን ነበር። ነገር ግን የሀገሩን፥የወንዛ ወንዙን ልምላሜና ያገሩን ጸጥታ በያደርንበት ባየነው ጊዜ ደስ እያለን ብርታትም ይሰጠን ጀመር ። ይልቁንም በርስዎ ግዛት በሲዳሞ አውራጃ በደረስን ጊዜ ሠራዊትዎ ሁሉ በየመንገዱና በያደርንበት እየተሰለፈ በደስታ ስለ ተቀበለን እጅግ አድርጎ ደስ አለን። ክቡር ሆይ ኢትዮጵያ በዙሪያዋ ባሉት ብዙ ሚሊዮን ሕዝብ ላይ ታላቁ ንጉሥ ዳግማዊ ምኒልክ ነግሠው እየተጋፉና እየተዋጉ ሀገራቸውን እንደዚህ ሰፊና ለም ለመሆን አበ

ቋት። እንደዚሁ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪም የደጉን ንጉሥ የዳግማዊ ምኒልክን ሐሳብ እየተከተሉ ለኢትዮጵያ የሚሆናቸውን ጥቅም ጥበብና እውቀትን እያሰፉ ይሔዳሉ ለሕፃናቶቹም የተማሪ ቤት አቆሙ ። ሆስፒታልም ከፈቱ፤ በደጓ በኢትዮጵያ ላይም ብዙ ልዩ ልዩ የሆኑ ነገሮች በሳሉበትና በጣም ባለ ጸጋ ስለሆነች ፋብሪካዎችና መንገዶች በጥቂት ቀን እንደሚሠሩ ይታወቀኛል ። አምላክም በኢትዮጵያ ላይ እጁን እንደ ዘረጋበት ትልቁን ሕይወትና ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ደግሞ ለሠራዊቱ ይስጥልኝ ስል ታላቁን ልመናዬን ለኢትዮጵያ አቀርባለሁ። ክቡር ሆይ እኔና ባለቤቴ ከዚህ በታች የሚከተለውን ምስጋና እናቀርባለን። እኛም በርዳታዎ በሕዝቡ ላይ ሥራችንን በደስታ እንድናዘጋጅ እንመኛለን በማናቸውም ነገር ሁሉ ልንረዳ ባለ ሙሉ ተስፋ ነን ። አሁንም ረጅም ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪና ለክቡር ደጃዝማች ብሩ ይስጥልን ብለን ደግ አሳቢውን አምላክ እንለምናለን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ብለው ጨረሱና ተጨበጨበላቸው ።

ከዚህ በኋላ የተማሪ ቤቱ ዲሬክተር ሙሴ አይበዲያን ዚህክ ቀጥሎ የተጻፈውን ንግግር ተናገሩ ።

ክቡር ሆይ፤ዛሬ እኛን በመቀበል ለሚያደረጉት ታላቅ ክብር መጨረሻ የሌለውን ምስጋናዬን አቀርብልዎታለሁ። እንደሁም ይህ ታላቁ የዛሬ ክብርዎ ለሕዝቡ ሥልጣኔ መሆኑ የታወቀ ነው። እኔ ሰውነቴ ምንም ዋጋ የማወጣ አይደለሁም እኛ ሁላችንም በዚህ ዓለም ኑዋሪዎች አይደለንም ለሌሎች እኛን ለመሰሉ እንለቃለን። ነገር ግን ሥልጣኔ ከትውልድ እስከ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ ይኖራል። እሱም ሕዝብን ከፍ ወዳለው ዕድል ተራራ ድረስ ያሳድጋል፤ በዚህ ዛሬ ባደረጉልን ታላቅ ክብር እርስዎን ታምነው ለመጡት ልጆች ማስተማር ለሕዝቡ ሥልጣኔ በውነት ሐሳብዎን ቍርጥ አድርገው እንደ ተነሡ ይገልጻሉ ።

ይኸም ታላቁ የሚያስደንቀው ቍርጥ ሐሳብዎ ታላቅ የማይደረስ ምስጋናና ክብር የሚገባው ነው እርስዎ በኢትዮጵያ ውሥጥ ዋና አገረ ገዢ ነዎት ። እንደዚሁም ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ቀጥለው በሀገርዎ የተማሪ ቤትና ሆቢታል አቆሙ በኢትዮጵያም በሥልጣኔ መጽሐፍ ውሥጥ ስምዎ ተጽፎ ለዘለዓለም ሲነበብና ሲከበር ይኖራል። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሁለቱ የዳግማዊ ምኒልክን መልካም ወራሾች ስለሆኑ ታላቁ ንጉሠ ነገሥት የጀመሩትን የሥልጣኔ ጕዳና እያሰፉ ያባታቸው የደጉ ምኒልክ ስም እያስጠሩ ኢትዮጵያን ወደ ብርሃን ይመሯታል ። እንዲሁም የጌታዬ የክቡር ደጃዝማች ብሩም ስም ከነሱ ስም ቀጥሎ ይጠራል። እኔ ይኸን መናገሬ የለበጣ አይደለም ሥራዬ አይደለምና ዓለም ሁሉ የሚያውቀውን እውነተኛውን ሐሳብዎን መሠረት አድርጌ እናገራለሁ ዓይን ያለው ያያል፤ጆሮም ያለው ይሰማል ። እኔ በኢትዮጵያ ፲፪ ዓመት በጤና ኖርሁ ኢትዮጵያን ገና በልጅነቴ በተማሪ ቤት ሳለሁ እወዳት ነበርሁ ። ደግሞ በየጊዜው የኢትዮጵያን መልካም ሥራዋን ለውጭ አገር ሕዝብ በጋዜጣ እየጻፍኩ ሳስታውቅ እውነተኛውን እርዳታዬን አስቀርቼበት አላውቅም። ዛሬ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደውቀት ጕዳና እንዳቀናች ተረድቼ መልካሙን የሚመቸውን ከተማ ትቼ ከልጆቼና ከባለቤቴ ጋራ ፲፰ ቀን ሙሉ በብዙ ድካም ተጕዤ አዲስ የተወለደችውን አገርዎን ልጆቿን ለማስተማር መምጣቴ በውነት ኢትዮጵያን እንድወዳት ይመሰክርልኛል ።

አሁንም በርስዎና በታላላቅ ሹማምንትዎ በሕፃናቱም በአልፍ አእላፍ ሕዝብ መኻከል ቆሜ ሁላችሁ ከልብ በጥንቃቄ ስለምትሰሙኝ ባለኝ ዐቅሜ ሕፃናቱን ለማስተማርና ለአገርዎ ሥልጣኔ በመርዳቴ ታላቅ ጥቅም እንድሰጥ እገልጻለሁ ። ለኢትዮጵያ ነገሥታትና ለሹማምንቷ ለሕዝቧ በውቀት ለሚያገለግሉት ልጆች ረጅም የደስታ ዘመን ይስጣቸው ስል እመኛለሁ ብለው ጨረሱና ሕዝቡ በደስታ አጨበጨበላቸው ።

ከዚህ በኋላ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ተነሡና ቀጥሎ ያለውን ንግግር ተናገሩ ። ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ደጉ የኢትዮጵያ ብርሃኑዋ አባቷ መሥራቷ ዳግማዊ ምኒልክ መንግሥታቸው ኢትዮጵያ ተከፋፍላ የነበረችውን በጕልበታቸው ኃያሉ ንጉሥ ድል እያደረጉ በደግነታቸውም ለሕዝቡ ለሠራዊቱ እየተመቹ በፍቅርና በውቀት ልቡንም ስአደረጉት ተነጣጥላ የነበረች ኢትዮጵያን በግድም በውድም በፍቅርም በጠብም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ባ፩ሰገነት ዳኙት ባ፩አዳራሽ ግብር አበሉት ። ሠራዊቱም በትክክል እንደባት እንደናት ነበር የሚያያቸው እንጂ እንደንጉሥ ብቻ አልበረም ስማቸውንም እምዬ ምኒልክ ደጉ ምኒልክ ብሎ ነው የሚጠራቸው። እናንተ ሕፃናቶች እኔ የምወዳችሁ ልጆቼ ወደፊትም እግዚአብሔር በገለጸላችሁ እውቀትና ክፍል የሚያሳድራችሁ እንደቸርነቱም የሚሰጣችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እምነታችሁንና ተስፋችሁን በሱ ብቻ አድርጉ።

እኔም አባታችሁ ወዳጃችሁ ታላቁ ደጉ ግርማዊ አጤ ምኒልክ ታላቂቱ እቴጌ ጣይቱ ከተወለድኩ ጀምሮ እናት አባት ሳላውቅ ሲያሳድጉኝ ከሌላ ሟያ ሁሉ በትምህርት ብፀናላቸው ነበር የሚወዱኝ ። እንዲሁም ለሃገራቸው ትምህርት እንዲጠቅማት ስላወቁ በሃይማኖታችን ፩የሆኑ አስተማሪዎች እንዲያመጡ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ማቴዎስን አዘዋቸው እነሙሴ ሐና ስሊብን ከእስክንድርያ አስመጡ እነሱም እደመጡ እኩሉ ለሐረር እኩሉ ለወሎ እኩሉ ለበጌምድር ተደራጁ ። አዲስ አበባ ለሚቀመጡትም አስተማሪዎች ለኔ ባልደረባ አድርገው ከዚህ በኋላ የልዑላኑ የራሶቹ የደጃዝማቾቹ የመሳፍንቶቹ ልጆች የመኳንንቱም የባላባቱ የካህናቱም ልጆች ብዙ ገቡ ትምህርቱም እንደተጀመረ ታላቁ የኢትዮጵያ ብርሃን ዳግማዊ ምኒልክ አቤት ስለዋሉ ግማሹም እየተደናገጠ ግማሹም ታላላቁ የጌቶች ልጆች ሕዝባቸው እየበዛ ግዛታቸውም እየራቀ ከቤታቸው ሥራ ጋራ የማይቻል ስለሆነ ያነቃቃቸውም ብርሃን ስለታወከ እስከኔው የተውነው በዛን። አሁን ግን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ከነገሡና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አልጋወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሁነው ያዬ ምኒልክን መሠረት ይዘው እየሰፋና እየበዛ እንዲሄድ አደረጉት

ይልቁንም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ኤውሮፓ ብዙ ልጆች ሰደው በገዛ ገንዘባቸው አስተምረው እነሱም ትምርታቸውን እየጨረሱ መምጣት ጀምረዋል ።

ሕሙማን ይፈቅድዎ ለዓቃቤ ሥራዩ ወአከ ጥዑያን እንዳኅው ሐምሌ ፳ቀን ፲፱፻፳ዓመት ፱፻፳ገጽ የኢትዮጵያ ብርሃን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን አገረ ገዥ የሆኑ ሁሉ በሚገዛው አገር የትምህርትና የሕክምና ቤት ሠርቶ ሕዝቡን እንዲያስተምርና እንዲያሠለጥን፡ይልቁንም ምንም ቢሆን ሥጋ ለብሶ በዚህ ዓለም ፩ቀን ሳይታመም መላ ዘመኑን በጤና የሚፈጽም አይገኝምና ከሐኪም እየሔደ ደዌውን ታክሞ ጤና እንዲአገኝ ሲሉ ሥጋዊ እውቀትንና መንፈሳዊ ትምህርትን የሚሰጥ በብርሃን ልበናቸው አስበው የተናገሩትን ቃል ሰምቼ ያገሬ ፍቅር ስላነሣሣኝ እኔም በገንዘቤ አስተማሪና ሐኪም ቀጥሬ የትምህርት ቤትና ሆስፒታል ሠርቼ በተሾምኩበት አገር የሚኖሩትን ሕዝብ ለመርዳት አስቤአለሁና ፈቃድ ያድርጉልኝ ብዬ ለግርማዊነታችሁ አመልክቼ ነበርና አሁንም ለምለሚቱ አገራችን ኢትዮጵያ ሐሳቢና ረዳት አግኝታ በዕውቀትና በሥልጣኔ፥ በሥራም እንዳውሮፓ ሰዎች እንድትሆንና ደግሞም እግዚአብሔር (ም ፵ ቁ ፫ – ፭) በነቢዩ በኢሳኢያስ አድሮ የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ፥ በምድረ በዳ ላምላኳችን መንገድ አስተካክሉ ዝቅ ያለው ሁሉ ከፍ ይበል ተራራውና ኰረብታውም ሁሉ ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና ዓቀበቱም ሜዳ ይሁን (ም፵፥፫–፭) ብሎ የተናገረው ትንቢት በቁሙ ስለመንገድ እንዳይደለ ስለ ልብ ጠማማነትና ስለ ድንቊርና እንደሆነ ተመራምሬ እውቀ መንፈሳዊ ትምህርትን ገንዘብ አድርጋ ራሷን እንድትችል ፈቃዳቸው ስለሆነ ሑሩ ወመሀሩ ወስብኩ ወንጌለ መንግሥት ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም(ማር፲፮፥፲፭)ድውያን ፈውሱ ወእለ ለምጽ አንጽሑ (ማቴ፲፥፯)ብለዋችሁ እናንተ ወደዚህ ስለመጣችሁልኝ በጣም ደስ አለኝ።ግርማዊ ንጉሥተፈሪ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ተብለው ከያዙ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አስተማሪ ላጣ አስተማሪ ገንዘብ ላጣ ገንዘብ እየሰጡ ለኢትዮጵያ ዓይንና ብርሃን ናቸውና ሁሉን ለማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ብርሃንነታቸውን ለዘለዓለም አኑሮ የወጣቶችን መልካም ፍጻሜ ለማየት ያብቃልን።በመንፈሳዊም ነገር ፈጻሚ ፈቃድ ለሆኑት ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዕድሜና ጤና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፍቅርና ሰላም ይስጥልን።

እናንተም ክቡር ዶክቶር ሸሪኮፍ ከነባለቤትዎ፥ ክቡር ሙሴ አይባዲያን ከነባለቤትዎ በአውቶሞቢልና በሠረገላ በሌላም እውቀት የሠለጠነው አገራችሁን ትታችሁ የኛን ሕዝብ በትምህርት አሠልጥናችሁና የታመመውን በእግዚአብሔር ፈቃድ አክማችሁ ሐዋርያነታችሁን ለመግለጽ እኔን አምናችሁ ወደዚህ ስለመጣችሁ ለቈራጥነታችሁ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ የመጣችሁበትንም መልካም ሥራ ለመፈጸም ያብቃችሁ ብዬ እግዚአብሔርን ለመለመን የተጋሁ ነኝ ።

ደግሞ እናንተም ክቡር ዶክቶር ሸሪኮፍ ከነባለቤትዎ ክቡር ሙሴ አይባዲያን ከነባለቤትዎ ይህንን የመጣችሁበትን ሥራ በሙሉ ልባችሁ እየተጋችሁ ሕዝቡን ለመጠበቅና ሕፃናቱን ለማስተማርና ለማሠልጠን ብርቱ ምኞት እንዳላችሁ ስለተረዳሁት እኔም በበኩሌ ይህ በእግዚአብሔር ኃይል የሚሠራው ሥራችሁ እንዲከናወንላችሁ የሚገባ እርዳታችሁን አላጐድልባችሁም ።

ግርማዊ ንጉሣችንም መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ለኛ ለራሳችንና ለሕዝባችን ደህንነት ላገራችን ሥልጣኔና ልማት የሚመኙትን የልብ ምኞት ስለ ተረዳኹት እኛም ግርማዊ ንጉሣችንን እያመሰገን ሕዝቡን ከደዌው እየመረመራችሁ እንድትጠብቁትና ሕፃናቱን አስተምራችሁ ከፍ ካለው ደረጃ እንድታደርሱልን ብዙ ተስፋ አለን ።

እናንተም ከዚህ የተሰበሰባችሁ መኳንንቶች ሆይ አሁን ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃል እንደኤውሮፓ ሰዎችእውቀትንና ሥልጣኔን ተምረው ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው ረዳት እንዲሆኑ ልጆቻችሁ ከትምህርት ደረጃ የደረሱና ተምረው የሠለጠኑ እንደሆነ አገልግሎታቸውንና ደስታቸውን የምትካፈሉ እናንተ ናችሁ ለኔስ በማናቸውም ወገን ቢሆን ፩ ሥራ እንኳ አያሠራልኝም።በገንዘቤ ቀጥሬ ሐኪምና አስተማሪ ማምጣቴ ከሰው የበለጠ ገንዘብ ኑሮኝ አይደለም ፥ነገር ግን አውሮፓ ተሻግሬ የመርከቡን ጸጥታና የባቡሩን ፍጥነት አይቼ ደስ እያሰኘኝ ታላቁንም የፈረንሣይ መንግሥት ከተማ ፓሪስንና ቬርሳይን የነገሥታቱን ከተማ ሁሉ ፋብሪካውን ሙዝየሙን፥ ባላገሩንም ሁሉ አይቼ ያላደረሰኝን ባይሮፕላን ሆኜ አየሁ የታላቁን የእንግሊዝ መንግሥት ከተማ ሎንደንን አይቼ በኢየሩሳሌም አድርጌ ምስርን፥ካይሮን፥እስክንድርያን እነዚህ ሁሉ ስለ መንግሥታቸውና ስለ ሕዝባቸው እርዳታ እንደነፋስ ሲፋጠኑ አይቼ ለምለሚቱ አገራችን ኢትዮጵያ ከገራቸው ሳታንስ ከውቀትና ከትምህርት ወደኋላ ስለቀረች ያገሬ ፍቅር እንደእሳት አቃጥሎኝ ለከ ቅዱስ ጳውሎስ ቅንዑ ለእንተ ተዓቢ ጸጋ ያለው ስለ ሃገር ፍቅርና ስለ መንፈሳዊ ሥራ ነፄልን ብዬ ሆስፒታልና የትምህርት ቤቱን ለማቆም ያሳሰበኝ ስለዚህ ነው ። የሕይወት ጕደና መሪያችን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የዳግማዊ ምኒልክን መልካም ሐሳብ ተከትለው እኛን ካለማወቅ ወደማወቅ ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማውጣት ሌትና ቀን ሲደክሙ እያየንበተቻለን ሁሉ አለመርዳታችን ስለምን ይሆን?ገንዘብ አጣን እንል በያውራጃው ከፍለው የሰጡንን አገራችን ያፈራትውን የምንበለው እኛ ነን፥እረ ስለምን ምክንያት ወደ ኋላ እናፈገፍጋለን ወይንስ ምዕ፲፩ ፲፯ በማቴዎስ ወንጌል በመኑ አስተማስሎሙ ለሰብእ ዘቲ ትውልድ ይመስሉ ደቂቀ እለ ይነብሩ ውስተ ምስያጥ ወይጼውዑ ቢጸሙ ወይቤልዎሙ አንዘርነ ለክሙ ወኢዘፈንክሙ አስቆቀውነ ለክሙ ወኢበከይክሙ የተባለውን ባናስተውለው ይሆን? በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ሳይስቁብን ይቀራሉ ብዬ አልጠረጥርም፥ እንዴት ማለት ከመንግሥት በታች ያለን በሹመትና በሽልማት የታወቅን ሰዎች ለመንግሥታችን የሚሆን ፩ ሥራ ሳንሠራ የናታችን የኢትዮጵያን ገንዘቧን ወርሰን ልጆቿን አናሳድግም ብንል ግፍ እንዲደርስብን የታወቀ ነው። አሁንም የሀገራችሁና የመንግሥታችሁ ፍቅር ያደረባችሁ ሰዎች ሁሉ ልጆቻችሁን እንድታስተምሩ ሙሉ ተስፋ አድርጌ

እለምናችኋለሁ ያስተማረውን ዋጋ እኔ ችዬ ነው ያመጣሁላችሁ። ነገር ግን ስለልጆቻችሁ የተቻለንን ያህል እንረዳለን ብትሉ እንደፍቃዳችሁ ስለመድኃኒቱም ነገር አውሮፓ በተገዛበት ሒሳብ በርካሽ ዋጋ ጥቂት ጥቂት እየሰጣችሁ ታከሙ ።

ደግሞ ሰው ፩ም ፪ም ፫ም ልጅ ወልዶ ርስቱንና ገንዘቤን መሣሪዮን ይወርሳል ስሜን ያስጠራል ብሎ ይኰራል ያም ከባቱ የወረሰው ገንዘብ ሁሉ ይጠፋል እኔ ግን ሌባ የማይወስደውን፤ሽፍታ ወንበዴ የማይቀማውን የእግዚአብሔርን እምነትንና እውቀትንም የምታገኙበትን የተማሪ ቤት አቋሚላችኋለሁ ይልቁንም እኔ እናንተን ሁሉ ልጆች በማግኘቴ በጣም አድርጌ እመከባችኋለሁ ልቤንም በተስፋ አኰራራታለሁ ብለው ተናግረው በጨረሱ ጊዜ ከግቢም ከውጭም ጭብጨባው ቀለጠ ። ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ትምህርት የሠለጠኑት ልጆች ለፈረንጅ ትምህርት ሲመረጡ ሰንብተው ነበርና በየመምህራቸው ክፍል ልዩ የሆነ አበባና ባንዲራ ይዘው ተሰልፈው ነበርና ወመሠረቱ ለዓለም አንቲ እስክለ ማርያም እኅቶ አንበሳ ወልደ ዮሐንስ በክርስቲ ያርኪ ቡርክት አንቲ እምአንስት ቡርክት አንቲ እያሉ ወረቡን በክበሮ ባሉት ጊዜ ከድምፃቸው ማማር የተነሣ ምድሪቱ አብራ የምታጨበጭብ ትመስል ነበረች ።

ይኸ ሲፈጸም አቡነ ዘበሰማያት ተደረገና ሠራዊቱ እንደዚያው እንዳማረ ሁኖ እንግዶቹን ዓጅበ አምሮ ወደተሰናዳላቸው ቤት አድርሶ ሲመለስ የፈንጠዝያ ግብር ተደርጎለት ያሽከር አሽከር ሳይቀር እንደ የማዕርጉ በልቶና ጠጥቶ ልክ በ፱ሰዓት ወደቤቱ ገባ ።

በ፪ ተና ክፍል ያሉትም ተማሪዎች ቀርበው ።

እስመ ተሐውር ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ትጺሕ ፍኖቶ ለኃይለ ሥላሴ ወትሰብክ በስሙ ይመልእ ላዕሌከ መንፈሰ እግዚአብሔር ።

ወይቤሎሙ ወልደ ዮሐንስ ለሕዝብ እንሰ ኢኮንኩ ኪያሁ ዳዕሙ ተፈኖኩ ቅድሜሁ ለኃይለ ሥላሴ እያሉ በተናገሩ ጊዜ ከምሥጢሩ ርቀት የተነሣ በጣም ተደነቀላቸው ።

ወድያውም የተማሪ ቤት ስም ብሩ ኮከበ ጽባሕ ተብሎ ተሰየመ ።

የብሃንና ሰላም ተላላኪ።

ከጅቡቲ ተላላኪያችን የመጣ ወሬ ።

ፍራንኮ ኢትዮጵያ የሚባለው የምድር ባቡር ኩምፓኒያ የምድር ባቡሩን ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ በባቡር የሚሳፈሩት መንገደኞች የሚያርፉበትን ቤት አልሠራም ነበርና ባለፈው ዓመት ሠርቶ ስለ ጨረሰ ወዲያውም ለጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክና ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፥ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪና ለአባታቸው ለልዑል ራስ መኰንን ከጥሩ ነሐስ የተሠራ ሐውልት በባቡሩ መቋሚያ በስተ ሰሜን ስለ አቆሙ ቤቱንና ሐውልቱን ለመመረቅ፥ በዓሉን ለማክበር የምድር ባቡሩ ኩምፓኒያ ፕሬዜዳን ሙሴ ገርቴንና ዲሬክተሩ ሙሴ ካሚ ፤ ከአማካሪዎቹም አንዱ ዋናው ሙሴ ሸርል ሚሸል ኮታ ሌሎችም ትልልቆች ሰዎች ከፈረንሳዊ አገር መጥተው በጅቡቲ ባኩል ወደ አዲስ አበባ ወጥተው ነበር።

ደግሞ ቁርቢል የሚባለው የፈረንሳዊ የጦር መርከብ አለቃና አዛጋር ሙሴ አዳንዳል ከጦር መርከቡ ውሥጥ ፳፪ መኳንንቶች ፴ ወታደሮች ይዘው ይህኑ የምድር ባቡር ምረቃ በዓል ለማክበር ወደ አዲስ አበባ ወጥተው ነበር ።

ከጅቡቲም አገረ ገዣው ሙሴ ሻፖ ቤሻኩና ሌሎችም ትልልቆች ሰዎች ወጥተው ነበር ። የምረቃውም በዓል መልክም ሁኖ ተከብሮ ካለፈ በኋላ የፈረንሳዊ ሚኒስትር ክቡር ሙሴ ደረፌ ልዑል አስፋ ወሰን ስለ ግርማዊ ንጉሥ ሁነው በጅቡቲ ባሕር የቆመውን ቁርቤል የሚባለውን የጦር መርከብ እንዲያዩ ፈቃድ ጠይቀው ነበርና ። ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ፈቃዳቸው ሁኖ ልዑል አስፋ ወሰን ወደ ጅቡቲ ወርደው የጦር መርከቡን እንዲያዩ ትእዛዝ አደረጉ ።

ስለዚህ በኅዳር ፳፫ ቀን ከማታው በሦስት ሰዓት ከአዲስ አበባ ተነሡ ።

የፈረንሳዊ ሚኒስትር ክቡር ሙሴ ደረፌና የጅቡቲ አገረ ገዢ ሙሴ ሻፖቢሻክ ሌሎችም ትልልቆች ሰዎች ባንድነት ነበሩ ።

ልዑል አስፋ ወሰንን ተከትለው ወደ ጅቡቲ ለመውረድ የታዘዙ መኳንንቶች የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይና የግርማዊ ንጉሥ ዋና የጸሐፊዎች አለቃ ክቡር ፊታውራሪ ኃይሌ ነበሩ ።

በኅዳር ፳፯ ቀን ዓርብ ከጧቱ በ፬ ሰዓት ባቡሩ ጅቡቲ ደረሰ። በባቡር መቋሚያም ብዙ ወታደሮች ተሰልፈው ጥሩምባ እየነፉ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ የጅቡቲ አገረ ገዥ ልዑል አስፋ ወሰንን በአውቶሞቢል አድርገው ወደ ቤተ መንግሥት ወሰዱዋቸው ።

በዚሁም ቀን በ፮ ሰዓት የጦር መርከቡን ለማየት በጢስ ጀልባ ሁነው ወደ ባሕሩ ሔዱ። የጦር መርከብም አለቃ መኳንንቱንና ወታደሩን አሰልፎ ይጠባበቅ ነበረና እንደ ደረሱ ማርሽ ተፈሪ የሚባለውን ሙዚቃ አሳነፍቶ በክቡር ሰላምታ ተቀበላቸው ። ወዲያውም በሰልፉ መካከል እያዞረ ከመኳንንቱ ጋራ አስተዋወቃቸው ።

ከዚህም በኋላ በመርከቡ ውሥጥ በየክፍሉ እያዞረ ትልልቆቹን መድፎችና መትረየሶችን ፤ የወታደሮችንም መኝታና ምሳ መጋቢያ አሳያቸው ። ከዚህም ቀጥሎ በመድፉ ውሥጥ ጥይት ሲገባና ሲተኰስ ቀለሁም ሲወጣ ፍጥነቱን ፤ ምትረየስም ሲተኰስ ፍጥነቱን አሳዩዋቸው ።

ቁርቤል ማለት ከ፵፬ ዓመት በፊት የነበረ የጦር መርከብ አለቃ አሚራል ነበር ። እርሱም በየጊዜው ድል አድራጊ ነበረና ይህን አዲስ የጦር መርብ ሠርተው ሲጨርሱ በስሙ ቁርቤል ብለው ሰየሙት ።

በዚሁም ቀን የመርከቡ አለቃ ልዑል አስፋ ወሰንንና ተከታዮቻቸውንም የፈረንሳዊን ሚኒስቴር ሙሴ ደረፌንና የጅቡቲን አገረ ገዢ፣ ሌሎችንም ትልልቅ ሰዎች ለምሳ ጋብዞ ነበርና ከምሳ አስቀድሞ በአሚራል ቁርቤል መልክ የተሠራ አንዳንድ ሜዳይ ምሳ ለተጋበዙት ሰዎች ሁሉ አደላቸው ።

ደግሞ ልዑል አስፋ ወሰን ወደ አይሮፕላን ላይ እንዲወጡ የመርከቡ አለቃ ፈቃድ ጠይቆ ነበርና ፈቃዳቸው መሆኑን ከስታወቁት ቦኋላ አይሮፕላኑን ከመርከቡ ላይ አውርዶ በባሕሩ ላይ አደረገው ። ልዑል አስፋ ወሰንም ከመርከቡ ወርደው በጢስ ጀልባ ሁነው ወደ አይሮፕላኑ በቀረቡ ጊዜ አይሮፕላኑንና ጀልባውን በገመድ ጠልፈው አቀረቡላቸውና ከፊታውራሪ ኃይሌ ጋራ ባንድነት ወጥተው ስምንት ደቂቃ ያህል ባሕሩን ዞረው ወረዱ ።

ከአይሮፕላኑም ላይ ከወረዱ በኋላ እንደገና ተመልሰው ወደ መርከቡ በገቡ ጊዜ መኳንንቱና ወታደሩ እንደፊተኛው ተሰልፎ ቈየቻቸው። ወዲያው ለሰላምታ ማርሽ ተፈሪ የሚባለው ሙዚቃ ተነፋና የመሰናበቻ ሰላምታ ፲፱ ጊዜ መድፎች ተተኰሱ።

ተኩሱም ሲጨረስ በመርከቡ ላይ ተሰቅሎ የነበረው የኢትዮጵያ ባንዲራ ወረደ ። ልዑል አስፋ ወሰንም ከተከታዮቻቸው ጋራ ሁነው ክቡር ሙሴ ዶረፌና አገረ ገዢው ሙሴ ሽፖ ቤሳክም ሳይለዩ ባንድ ጀልባ ሁነው ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

ለወይዛዝሮች ማስታወሻ ።

ግርማዊ ንጉሥ የኢትዮጵያ ብርሃንና የውቀት መሪያችንን ሐሳብ አሁን እንደምናየውና እንደሚመስለን ስናስብና ስንመለከት ሳለን በጣም ደስ የሚያሰኝና ወይዛዝርንም የሚያነቃቃ ሁኖ ይገለጻል ።

ካሁን ቀደም ባለፉት ዘመናቶች ከወንዶች ወገን ብዙ የደኃ ልጆችና የባለጸጋ ልጆችም ይህ በሀገራችን በተፈሪ መኰንን ጊዜ በያለበት ሐሳቡን አሰፋፍቶና አቃንቶ በትጋት የቆመው የትምህርት ቤት መጥቀሙን ህፃናቶቹ አይተውና ቀርጸተው በትጋት ሲማሩ ሳሉ ብዙዎችም ልጆች እንደተቻላቸው ትምህርታቸውን አፍቅረውና ወደው በትጋት ወደ ትምህርት ቤት ሲመላለሱ ጌታችንም እያዩና እየተረዱ ደስ እያላቸው ደኖሩ ነበርና አሁን በቅርብ ጊዜ ከወይዛዝሮች ወገን ለትምህርት የሚያስብና በትጋት ሐሳቡን የሚያዘጋጅ ስላልታየ ለወይዛዝሮች ማነቃቂያና ማስታወሻ ሲሉ ልጃቸውን ወይዘሮ የሺመቤትን ወደኤውሮፓ ለትምህርት በ፲፱፻፲፱ ዓም ከወይዘሮ አምሳለ ኅሩይ ጋራ ልከዋቸው ሳሉ እነዚህም ሁለት ሕፃናት ወይዛዝሮች ትምህርታቸውን አፍቅረው ሲማሩ የትምህርት ቤታቸው ስለ ዕረፍት ስለተዘጋ በ፲፱፻፳፩ ዓመት በሐምሌ ፮፥ ቀን ወደሀገራቸው ተመልሰው መጡ። አሁን በ፲፱፻፳፪፡ዓም በኅዳር ፳፰ ፡ቀን ተመልሰው ትምህርታቸውን ሲሉ ወዳውሮፓ ጕዞ አደረጉ። እነሱም ሲሔዱ እኅታቸውን ወይዘሮ የምስራች እምሩን ጨምረው ተጓዙ። ከናትና ካባታቸው ፡ከዘመዶቻቸውና ከሀገራቸው ተለይተው የትምህርትን ጣሚንስላገኙአት በደስታ ወደናትና አባታቸው ዘንድ እንዲሔዱ ብላቴናዎች ደስታቸውንና ሐሳባቸውን እያሰፉ ቅርታና ትካዜ ሳይነካቸው ሲጓዙ ሳሉ ያዩአቸው የሥልጣኔን መንገድ ለሚከተሉ ኢትዮጵያውያንና ለውጭ አገር ሕዝቦችም እያስደነቁና ደስታን እያሰፉ ሲሔዱ ስላየሁ ፣ እኔም የንጉሣችን ሐሳብ እንደመሰለኝና የልጆቹንም ትጋት ስለተመለከትኩ ቀጥዬ ማስወታሻዬን ለወይዛዝሮች ላቀርብ እወዳለሁ።

ወይዛዝር ሆይ።

አሁን ለጊዜው የሚያስፈልጋችሁ ወንዶች ልጆቻችሁን በትጋት ወደትምህርት ቤት እየላካችሁ እንደምታስተምሯቸው ሁሉ ሴቶቹንም ልጆቻችሁን ወደትምህርት ቤት መላክና ማስተማር ያስፈልጋችኋል።ምናልባት ይኸውም ነገር እንግዳ ነገር መስሎ ቢያስፈራችሁ እፍረትን ከወይዛዝሮች ላይ የሚያስወግዱትን ምክሮች ከብርሃንና ሰላም ጉባኤ ውሥጥ እያነበባችሁ ዳግም የንጉሣችሁን ሐሳብና ሥራ እየተመለከታችሁ ልጆቻችሁን ብታስተምሩቸው ይሻላል እንጅ በትምህርት አረገድ ለመታገስ አይገባችሁም።

ይህ ያሁኑ ጊዜ የትምህርትና በድፍረት የሥራ መሥሪ ጊዜ ነው እንጂ የዕረፍት ጊዜና ወቅት ያለመሆኑን በደከማዋ እውቀቴ ይቅርታችሁን እየለመንኩ አሳስባችኋለሁ ።

በቀለ ዘለቀ።

ስላቶ ምንዳ ሀብተ ኢየሱስ ዕረፍት ።

አቶ ምንዳ ሀብተ ኢየሱስ ከሀገራቸው ከመርሐ ቤቴ ሐረርጌ ምድር መጥተው እንደቈዩ ጅጅጋ የንግድ ሥራ ይዘው ሲሠሩ ገንዘባቸው እየበዛ ንግዳቸው እየሰፋ ብዙ ጊዜ ወደ አደን እየተመላለሱ በንግዳቸው ከብረው ከላከመቻን ጋራ ሽሪክ ሁነው በጅጅጋም ሐዋላ ገንዘብ ለሚፈልገው ሰው ያለኮሚሲዮን ሐረርጌም ድሬ ዳዋም አዲስ አበባም ድረስ በብዙ ደግነታቸው የሐዋላ ወረቀት እየቈረጡ ይሰጡ ነበር ማንም ችግረኛም ችግሩን በነገራቸው ጊዜ ያለቅያሜ ደስ እያላቸው እንደችግሩ መጠን በብድርም በስጦታም ወገን ይፈጽሙለት ነበር። መቼም ይኸ ሁሉ ከሞት ጥላ የማያድን ነውና በ፱ ቀን በሽታ በተወለዱ በ፵፪ ዓመታቸው በጥቅምት ፴ ቀን ማታ ዓረፉ ሌሊቱንም እሑድ የጽጌ መፈጸሚያ ስለሆነ የከተማው ሕዝብ ዕረፍታቸውን በሰማ ጊዜ ህንዶችና አረቦችም ሳይቀሩ ተሰብስበ በእንባ ከተራጩ በኋላ አስከሬናቸው በሳንዱቅ ተሞቶ ማታውኑ ሬሣው ወደ ደብረ መዊዕ ሚካኤል ሲሔድ ኅዳር ሚካኤልን ከዋልኩ በኋላ ልጄን ተፈራ ምንዳን ይዤ በበርበራ በኩል ወደ አደን እሻገራለሁ ብለው ብዙ ለመጫን የታሠረ የንግድ እቃ በአጥረ ግቢው ምሉእ ነበርና ያ በታየ ጊዜ ለሕዝቡ ሁሉ የመረረ ኃዘን ሆነበት። አስከሬናቸውም እቤተ ክርስቲያን በደረሰ ጊዜ የደብሩ አለቃ፤ አለቃ ገብረ ጊዮርጊስ አስደውለው አስከሬኑ በሳንዱቅ እንደተመታ ከቅኔ ማኅሌት

ገብቶ ከሀናቱ ተሰብስበው ስቡሕ ተብሎ ሲፈቱ አደሩና ጧት በህዳር ፩ ቀን ተቀበሩ ያቶ ምንዳ መሞት ግን ጉዳቱ ለቤቶቻቸው ብቻም አይደል ለጅጅጋ ሕዝብ ሁሉ ነውና ስለ ቸኰለባቸው በጣም የደግነታቸው ነገር አሳዝኖኛል ።

የአሽከሮቹ ትዳር የምንዳ ነበረ ።
በጥፋት ተቆርጦ ውሩ ሲያልቅ ቀረ ።
ኣስከሬኑ ግብቶ እቅኔ ማኅሌት
ናሁ ተፈጸመ ሲባል አደረለት

ግሪካዊ ጅጅጋ ነጋዴ መሴ በርበያኒ ።

አቶ ምንዳ ሀብተ ኢየሱስ አገራቸውን ወዳጅ ተሥልጣኔም ተከታይ ከመሆናቸው የተነሣ ከብርሃንና ሰላም ማኅበረተኝነት ገብተው በእርሳቸውም ምክንያት እጅግ ሰዎች ወደዚሁ ጋዜጣ ገብተው ማኅበረኝነት ይዘዋል ።

ብርሃንና ሰላም ስለሞታቸው ኀዘኑን እየገለጠ ለባለቤታቸውና ለልጆቻቸው ለቤተ ሰዎቻቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ስለ ባሻ ወልደ ሰማዕት ዕረፍት ።

ባሻ ወልደ ሰማዕት ከጥንት ጀምሮ በከተማ የዘበኝነት ጥበቃ ሥራ የአምሳ አለቃ ሳለ በጣም አገልጋይና ትጉህ ስለሆነ በአለቆቹ ዘንድ የተመረጠ ሆኖ የመቶ አለቅነት ከተሾመ ብዙ ጊዜ ይሆናል ።

በዚሁም በመቶ አለቅነቱ ላይ በመጀመሪያ መጠባበቂያ ክፍል የሻምበሉ እንደራሴ ሆኖ የዳኝነት ሥራ ይሠራ ነበርና በዘበኞች እጅ የሚያዘው ጥፋተኛ ሁሉ ወደሱ ዘንድ በቀረበ ጊዜ በስውር የሠራውን የጥፋት ሥራ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ በአመራመሩ አኳኋን ያናግረው ነበረ ።

በሌላውና በሱም በኩል የዘበኝነት ጥበቃ ክፍል ያለው የከተማ ሕዝብ ሁሉ ዕቃ በታሰረቀ ጊዜ መጥቶ ያመለከተው እንደሆነ ለሥራው እጅግ አጥብቆ ትጉህ በመሆኑ ያንን የተሰረቀ እቃ ከሌባው ጋራ አንድነት አስተባብሮ እስቲይዘው ድረስ እንቅልፍ አይወስደውም ነበረ ። ይልቁንም ከባሻ ወልደ ሰማዕት እጅ አንድም ጥፋተኛ አምልጦ እንደማያውቅ የቀረውቀርቶ በዳኝነቱ የተመረመሩና በእጁ የተያዙ ጥፋተኞች ሁሉ ያለጥርጥር ይመሰክሩለታል ።

ይኸውም ትጉህነቱ ይታወቅለት ዘንድ ጠመንጃ የሰረቁ ሌቦች አሉ ማለትን አስቀድሞ ስለሰማ በየበሩ ሰላይ አድርጎ ነበረና በኅዳር ፲፯ቀን ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት አንዱ ሰላይ መጥቶ የጓድግዳ መሠርሰሪያ የሚሆን ድጅኖ የያዙ ሰዎች ተከናንበው ካንድ ሥፍራ ላይ ተቀምጠዋል ። ጠመንጃ የሰረቁ ሌቦች መስለውኛል ብሎ ስላመለከተው ካጠገቡ የነበሩትን ዘበኞች አስከትሎ በፍጥነት ሄደና ሌቦችን በድንገት ሳያስፀውት ያዛቸው ። ከዚህ በኋላ የያዛቸውን ሌቦች ለዘበኞች አሣልፎ ሰጥቶ ሌላውን ጥፋተኛ እይዛለሁ ብሎ ተሯሩጦ ሄዶ ሊይዘው በደረሰበት ጊዜ ያ የሚያዘው ጥፋተኛ የመንገድ መሳበሪያ ስለተመቸው ባሻ ወልደ ሰማዕትን በሽጉጥ መታውና አመለጠ

ባሻ ወልደ ሰማዕትም ከቆሰለ በኋላ እንደገና ሄዶ ከሌቦቹ ጋራ ስምምነት እያደረገ ከቤቱ የሚያሳድራቸውን ሰው ይዞ ወደ አራዳ ድረስ በእግሩ መጣና የያዛቸውን ሌቦች ወደ መመርመሪያ ክፍል አሣልፎ ሰጥቶ የቤተ ሳይደርስ እየታከመ ፪ቀን እንደዋለ በኅዳር ፳ቀን ዓርብ ሞቶ በአዲስ አበባ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ።

ለቀብሩም የተሰበሰበው ሕዝብ እጅግ አድርጎ ብዙ ነበረና ስለሃገሩና ስለ መንግሥቱ ሲል ይህነን መሪር የሆነ ሞት መቀበሉን እያሰበ እንባ በንባ ይራጭ ነበር።ነገር ግን ምንም ሐዘን ቢበዛ ከሞት ለማዳን የማይቻል ነውና ባሻ ወልደ ሰማዕት መንግሥት በዘዘው ሥራ ላይ ደሙን አፍስሶ መሞቱ አገልግሎቱን ይመሰክርለታል ። ለሞቱም ዋጋና ክብር ያለው ነው እያለ ይህነን ተሥፋ እያደረገ ወደ ቤቱ ተመለሰ ።

ደጉ ይመር።

ስለ ንሥረ ተፈሪ አለቃ ዳንኤል የተቀኙት ቅኔ ።

መወድስ

ፈንዎተ ንሥር ወርዓብ እለ ይፈቅዱ፤
ኃይለ ሥላሴ ወኖኅ፤ እመ በዘመን ኃበሩ።
ሕሊና ልበ ኖኅ እምቀንዐ፤ ለኃይለ ሥላሴ በንሥሩ።
ንሥረ ተፈሪ ዘተፈነወ
ለምድር አምጣነ ረሰያ ምክያደ ለእግሩ።
ሰማየ ሰማያት እንዘ መንበሩ። (ኢሳ ፷፮ ፩)
ወፍጡነ ገብአ ኀበ ዘተከተ መንበረ ክብሩ።
ኢተሰምዐኒ በእገዚነ ኖኅ ለሐሜተ ማይ ነገሩ።(መክ ፲፰)
ንሥረ ኖኅ ዖፈ ሰማይ እምከመ ኢያግህዳ ለምሥጢሩ።
ንሥረ ቤተ ኖኅ ይበእ፤ ኃበ ሐመረ ኖኅ ሀገሩ።
ለሰሎሞን ንሥረ ተፈሪ እስመ ኢያንሶሰወ በሕዋሩ።

ሥላሴ

ዳዊት በክንፈ ርግብ ሰማያተ ይስርግ ዘተመነየ፤ እመቦ
በምድር ይእዜ፤ ምስለ ተፈሪ መክብብ።
እምኢተርፈ ከመ ተመነየ አክናፈ ዘርግብ ፣
በጊዜ ተፈሪ ንጉሥ እኩይነገሥታተ ምድር ወሕዝብ።
ለዓሪግ ሰማየ አንተ ኪሩብ።
ነሢአሙ ክንፈ፤ ዘርግበ ጥበብ ።
መላእክተ ከንዎ ለአብ።

አለቃ እ ዳንኤል ።

በዳኅር ጽዮን በዓል ቀኝ ጌታ ቸርነት የተቀኙት ቅኔ ።

ክብር ይእቲ ።

መስዋዕተ አባግዕ ጥበበ ወልደ ዳዊት እመ አብዝሐ ፈድፋደ።
ኢያድኅኖ ምንተ እምአዝማዲሁ አሐደ ።
ወልድሰ ነጋዴ ምሥያጠ ምሕረት ዘሖደ ።
ኵሎ አትረፈ በወርቀ ደሙ እስመ ብዙኃ ወለደ ።

ዕጣነ ሞገር ፤

በዓለ ፋሲክ ይግበሩ ልደተ ሕፃናት ኵሎሙ ።
በሕጽበተ እግር ወእድ ወሀበሙ ።
ለሕዋሳተ ዳኅን እርዳኢሁ ዘጸውዖሙ ቀዲሙ ።
ኃይለ ጽዮን አምላክሙ ።
ወተካፈሉ ሀገረ በዕፃ ከመ ይስብኩ በስሙ ።
ዝርወት ባሕርየ ደመና እስመ ወጽአ በሙ ።

አሠረ ንጉሥ

ገጸ አንበሳ ወላህም ሐመይዎ ለኃይለ ሥላሴ ሊቆሙ ።
እስመ ለገጸ ሰብእ ወንሥር ክልኤቱ እለተፋቅሮ አልበሙ።
ሰላመ ገብረ ማዕከሎሙ ።
ለአስከለ ድንግል ወንጌል በበብሔሮሙ ።
ይስብክዋ በመፍርሀ ድምፆሙ ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፬ ብር ተ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
ያበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፩ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፸ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፩ ብር
ባለ ድመ ።		፻፹
ባለአህያ ።		፻፵፫
ባለሳቢ ግመል ።		፻፷፭
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፷
" " ጃፖን		፻፸፰ብር
ሱክር	ጁኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፭ ብርተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፱ ፍራንክ ከ፶ሳንቲም
ባአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፳ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፪ ብር ፳፭ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ ፴፱	

የርሻና የንግድ ማስፌያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጆማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐ ፎዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከጳሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ ።



በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ፡፡ ፊ. ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኜይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቍጥር ፶፩
5me ANNÉE № 51

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 19 DÉCEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ልዑል ሲክስቲ ደቡርቦ አቀባበል ።

ልዑል ሲክስቲ ደቡርቦ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ታኅሣሥ አምስት ቀን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታና ግርማዊ ንጉሥ በቤተ መንግሥቱ በክብር ተቀበልዋቸው፥ በዚያን ጊዜም ልዑል ፕሪንስ ሲክስቲ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ ፤

ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

ክፍ ያሉት የወንድሜ ባለቤት የሉግዘምቡርግ ታላቂቱ ዱሼስ ልዕልት ሻርሎትና ፤ እጅግ የተወደዱ ወንድሜ የሉግዘምቡርግ መስፍን ልዑል ፌሊክስ ደቡርቦ ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ የማይረሳ መጐብኘት ከደረጉላቸው ጀምሮ፥የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥታዊ ቤተ መንግሥትና የልዑላንነታቸውን ቤተ መንግሥት የሚያገናኙትን የወዳጅነት ማስተሣሰሮዎች እያሰቡ ፤ ወደ ንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥት ዋና ከተማ መጥተው ይህን መጐብኘት ራሣቸው ሊመልሱ ታላቅ ምኞታቸው እንደ ነበረ እየገለጹሁ ይህን በእጅ የተጻፈ ደብዳቤ ለግርማዊነታችሁ አቀርብ ዘንድ አዘዙኝ ።

ስለ ሆነ ይህን እጅግ የተወደደ ምኞታቸውን ለመፈጸም እስከሁን ጊዜው ሳይፈቅድላቸው ስለ ቀረ ፤ ግርማዊ ንጉሥ ለልዑላንነታቸው ስላደረጉላቸት መጐብኘት ምስጋናቸውን ለግርማዊነታችሁ ሳያቀርቡ ከዚህ የበለጠ ጊዜ መቈየት የማይቻል ሁኖ ታያቸው ። ስለዚህ የልዑላንነታቸው ልዩ እንደራሴ ሁኜ ታላቂቱ ዱሼስና መስፍኑ የሚያስቡትን እጅግ የጋለ ከልብ የሆነ አሳብ ለግርማዊነታችሁ አደርሳለሁ ፥ በሉግዘምቡርግ ስለ ተደረገላቸው መጐብኘት እንደ ገና ምስጋና እያቀረብሁ፤ ይህም መጐብኘት በልዑላንነታቸው ዘንድ የማይረሳ ሁኖ መኖሩን አረጋግጣለሁ ። ደግሞ ለግርማዊነታችሁ ፤ ለግርማዊት ንግሥት ለንጉሣዊው መስፍንና ለስመ ጥሩዋ ለከበረችው ለኢትዮጵያ ነገሥታት ቤተ ዘመድ ሁሉ ደስታና ጤና፤ ለግርማዊነታችሁም ዘውድ ክብር እንዲሆን ከልብ የሆነውን ምኞት እገልጻለሁ።

ከጥንታዊ የአውሮፓ ነገሥታት ወገን የሆንሁ አንድ መስፍን ፤ የጥንታዊ የአፍሪቃ ነገሥታት ስመ ጥሩ እንደራሴዎች ለሆናችሁ ከምገልጸው አሳብ ጋራ ከፍ ባለ ክብር የሚተሳሠሩትን ፤ በመንግሥታችሁ ዋና ከተማ በግርማዊነታችሁ መንበረ መንግሥት ፊት ሁኜ የማቀርባቸውን ከልብ የሆኑ መልካም ምኞቶች ግርማዊነታችሁ ይቀበሉ ዘንድ ፈቃዱ ይሁን።

Madame ,

Sire,

Leurs Altesses Royales la Grande Duchesse Charlotte de Luxembourg mon Auguste belle sœur, ainsi que Son Altesse Royale le Prince Félix de Bourbon, Prince de Luxembourg, mon très aimé Frère, m'ont chargé de présenter à vos Majestés Impériales et Royales une lettre autograhe par laquelle, se souvenant des liens d'amitié qui unissent depuis la mémorale visite de son glorieux Régent et Roi la Maison Impériale d'Ethiopie avec la leur, Ils me demandent d'exprimer à Vos Majestés combien ils auraient désiré pouvoir rendre personnellement cette visite dans la capitale Impériale. Les circonstances cependant ayant empêché jusqu'ici de réaliser ce vœu très cher, Leurs Altesses Royales n'ont pas cru pouvoir différer plus longtemps de témoigner

à vos Majestés Leurs remerciements pour la visite que Sa Majesté le Negous Leur a faite. C'est comme représentant spécial de Leurs Altesses Royales que je viens donc transmettre à Vos Majestés les sentiments d'amitié très vive et sincère qui animent La Grande Duchesse et le Prince à Leur égard, Les remercier nouvellement pour la visite faite à Luxembourg, Les assurer que la mémoire Leur en est restée chère et former enfin pour Vos Majestés Impériales et Royales pour Sa Majesté la Reine, pour le Prince Royale ainsi que pour tous les membres de l'illustre et glorieuse Dynastie Ethiopienne les vœux les plus sincères pour Leur bonheur Leur santé et la gloire de leur Couronne . .

Que Vos Majestés veuillent bien accepter également ceux que de toute mon âme je forme pour Elles, et qui énoncés dans le cœur même de Leur Empire devant la Majesté de Leur Trône en acquièrent toute la haute signification qui s'attachent aux sentiments qu'un Prince de la plus ancienne dynastie d'Europe peut adresser aux illustres représentants de la plus ancienne dynastie d'Afrique.

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ቀጥሎ ያለውን ንግግር ተናገሩ።

ልዑል ሆይ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና እኛም ራሳችን ፤ ጥንታዊ በሆነ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዋና ከተማ ዛሬ ልዑልነትዎን በመቀበላችን እጅግ ደስ ብሎናል።

በታላቂቱ በሉግዘምቡርግ ዱቼስ በልዕልት ሻርሎትና ፤ በልዑልነትዎ ወንድም በመስፍኑ በልዑል ፌሌክስ ደቡርቦ ስም ሁነው ፤ እውነተኛ የሆነውን የወዳጅነት አሳብ ፈቃድዎ ሁኖ ስለ ገለጹልን ልባችን በደስታ ተነክቶዋል ።

ባ፲፱፻፲፬ ዓመተ ምሕረት ወደ ታላቁ ዱካል ቤተ መንግሥት ሒደን ያደረግነው መጎብኘት ለእኛም ለራሳችን እጅግ መልካም የሆነ መታሰቢያ ሁኖ ይኖራል ።

ልዑልነትዎ ፈቃዱ ሁኖ ስላደረሰልን መልእክት እያመሰገን ፤ ለታላቂቱ ለልዕልት ዱቼስና ለልዑል ፌሌክስ ደቡርቦ ለቤተ ዘመዳቸውም ደስታ ፤ ለሕዝባቸውም በረከት እንዲሆን የምንመኘውን ምኞት እንዲያደርሱልን እንለምንዎታለን ።

ይህነንም ምክንያት አድርገን ልዕልናዎ ለእኛና ለቤተ ዘመዳችን ስለ ገለጸው ምኞት እያመሰገን ፤ እንኳን ደኅና ገቡ ብለን ለልዕልናዎ ደስታና ጤና እንዲሆን እንመኛለን ።

Altesse Royale,

Sa Majesté l'Impératrice et Nous même sommes extrêmement heureux d'accueillir aujourd'hui Votre Altesse Royale dans la capitale du viel Empire Ethiopien.

Nous sommes très sensibles aux sentiments cordiaux que Votre Altesse Royale a bien voulu exprimer à Notre égard au nom de Son Altesse Royale la Grande Duchesse Charlotte de Luxembourg et au Nom de Son auguste frère le Prince Félix de Bourbon .

Nous avons personnelement conservé un souvenir excellent de Notre visite de 1924 à la Cour Grand Ducale.

En vous remerciant profondement des messages chaleureux que Votre Altesse Royale a bien voulu Nous transmettre Nous vous prions de bien vouloir en retour Vous charger de dire à Son Altesse Royale la Grande Duchesse ainsi qu'à Son Altesse Royale le Prince Félix de Bourbon, les vœux que Nous formons pour le bonheur de Leurs Altesses ainsi que de leur famille et la prospérité de Leur Peuple.

En Vous souhaitant une cordiale bienvenue, nous saisissons l'occassion de remercier encore Votre Altesse Royale des souhaits qu'Elle a personnelement exprimés pour Nos Personnes et Nos Familles et Nous formons Nos vœux sincères pour sa santé et sa prospérité.

ስለ ክቡር ራስ ናደው በይሉ ባቦር የተደረገው ልቅሶ ።

ከዚህ አስቀድሞ በብርሃንና ሰላም በምስተኛ ዓመ ቍጥር ፵፮ ስለ ክቡር ራስ ናደው ዕረፍት አመልክተን ነበር ። የኢሉባቦር አውራጃ ገገር ክቡር ራስ ናደው ከስድስት ወር አስቀድሞ አንድ ጊዜ በጠና ታመው ነበር ።እርሳቸውም ከሥራቸው ብዛት የተነሣ ለበሽታቸው አልተጠነቀቁለትም ስለዚህ ምንም ለጊዜው ቢድኑ አልፎ አልፎ ማመሙንና እያደር እየበረታ መሔዱን አልተወም ነበር ። ግን እኒህ ትጉህ የሆኑ ሰው ከበሽታቸው ጋራ እየታገሉ ያሰቡትንና የጀመሩትን ሥራ ለመፈጸም ይጥሩ ነበር ። ከሥራቸውም አንዱ የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን በኖራ ግምብ ለማሠራት በሰኔ ወር መሠረቱን አስጥለው ነበር። ይህነኑም ለመፈጸም ከእንቅልፋቸው ተለይተው ማለዳ ተነሥተው እስከ ማታ ድረስ ድንጋይና ማእዘን፣ ሳንቃ፣ ሌላውንም የሚያስፈልገውን ሁሉ በማጋዝ ስንብተው ባ፩ኛው፤ ወር የቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳው አልቆ የጣራውን ቆርቆሮ ከስጨረሱ በኋላ በሽታቸው ጠናባቸው ሐሳባቸውም በቶሎ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ጨርሸ ታቦቷን ካገባሁ ለሕይወት ግድ የለኝም ይሉ ነበር።ለዚቹም ቤተ ክርስቲያን ከውሮፓ ሥዕል ያለበትን መስተዋትና ሌላም ለክህናቱና ለወታደር ታቦቷ የገባች ጊዜ የሚሸልሙት መሣሪያና ሌላም ከህንድ አገር ለዘር የሚሆን ቻይ ለማስመጣት አዘው ነበር ። ሌላውማ ስንቱ ምንም ይህን ሁሉ ትጋት ቢያደርጉ የእግዚአብሔር ሐሳብ ሌላ ነውና በሽታቸው እየበረታ ቢሔድ እቤት ዋሉ ። የቤተ ክርስቲያኑም ሥራ ቆመ ክቡር ራስን የሚያክሙ ሁለት ሐኪሞች ሌት ከቀን ሲለፉላቸው ሰንብተው በኋ

ዳር ፳ቀን ከሌሊቱ በ፫ ሰዓት (ሂፖቲክ ከፍ ዚሊቦር) በሚባል የጉበት በሽታ ታመው ዐረፉና ተሸሽጎ ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው እስኪገቡ ድረስ ቈዩ። በማግሥቱም ከቀኑ በ፮ ሰዓት ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ከባለቤታቸው ከልዕልት ተናኘ ወርቅ ተፈሪ ጋራ በደሴና ገቡና ልቅሶው ከሌሊቱ በ፯ሰዓት ተጀመረ። እስኪነጋም ነጋሪቱና መለከት እምቢልታው ከልቀሰኞቹ ጋራ ሲንጫጫ አድሮ፥ ጧትም ሁለት ሰዓት ሲሆን የክቡሩ አስከሬን በሣጥን ውሥጥ ሁኖ፥ሣጥኑም በኢትዮጵያ ባንዲራ ተሸፍኖ፥ በራስጌም በወርቅ ላንቃ አንገት ራስ ወርቁ ተደርጎ ልዩ ልዩ ጌጥና ከየመንግሥቱም የተሸለሙት ኒሻን ዙሪያውን ተንጠልጥሎ ከቤት ሲወጣ የተሰበሰበው ፍጥረት ዕንባ ለንባ ተራጨ። ከቤት ወጥቶ በሜዳ ላይ ድንኳን በተተከለበት ስፍራ ዐረፉና ፈረሶችና በቅሎዎች ላይን በሚያንጸበርቅ የወርቅ ዕቃ ተጭነው መኳንንቶቻቸውም ልዩ ልዩ የጌታቸውን ጌጥ መሣሪያ ይዘው አስከሬኑን እየዞሩ ሲያስለቅሱ እንኳን አሽከራቸውና ዘመዳቸው፥ የሚያውቃቸው ይቅርና የማያውቃቸው ሴቱ፥እረኛው፥የከተማውም ደኃ ሁሉ እጅግ ዕንባ አፈሰሰ።የልቅሶውም መድመቅ ዕፁብ ድንቅ ነው። በጎሬ ያሉ ፈረንጆች ሁሉ ሴቱም ሳይቀር ተሰብስበው በያይነቱ አበባ እያበጁ በስከሬኑ ላይ ያስቀምጡ ነበር ።

አንደኛውም ክብ ሁኖ በተሠራው አበባ በዙሪ «ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር የሚል ጽሕፈት ነበረበት» ሀገሩም እንደዚህ ሁኖ ለመውደዱ የሰላም ገጋ፥ የድኃ አጥር እያለ ሴት ወንዱ ፥ እረኞች ፥ሕፃናት ሳይቀሩ ሲፋጅ ያሳዝናል ።) ከዚህ አንደኛ ድንቅ ነገር (አንድ በጥፋት ተገርፎ የታሠረ ነበር የሞቱ ለት በውህኒ ቤት እንዳለ ሲያለቅስ አባ መብረቅ ድኖ ሁለተኛ አርባ በገረፈኝ አለ(እንዲህ ያለ መውደድ ያገኙ በሥራቸው ነው ። ነገር ግን ምንም ሰው ቢወዳቸውና ቢያዝንላቸው ከዚህ የሚቀር የለም በሕይወታቸው ሳሉ እንደ ሌሎች መኳንንቶች ያለ ባሕሪ አልነበራቸውም ለደኃና ለተጠቃ አዛኝና ጠበቃ፥ ወስላታንና ቀጣፊንም ለማጥፋት የታጠቁ ጀግና ነበሩ ። በቤታቸውም እንደመኳንንቶች የኩራትና የመሬቅ ባሕሪ አልነበራቸውም ተራ ሰው ሁሉ ወዳጃቸው ነበር። ገብቶም ጉዳዩን በቶሎ ፈጽሞ ይወጣል።አሳባቂና ሐሜተኛ በቤታቸው አይደርስም ነበር፤ለሀገራቸውም በማገልገል በኢትዮጵያ ካሉ መሳፍንትና መኳንንት ይልቅ መጀመሪ የሥልጣኔ ተከታይ ነበሩ እንጂ እንደ ጥንት ሽማግሌዎቻችን አዲሱን ሥራ አይቃወሙም።በሥራቸውም ከመኳንንቶች የሚተከከላቸው የለም ብሎን በግልጽ ለኢትዮጵያ ልጆች እናወራለን ጉድለት የማይገኝበት የማይስት ሰው ነበሩ ። ነገር ግን እውነተኛ ትሕትናን ለብሰው ለሀገራቸው መንገድና ድልድይ ሌላዎቹንም በመሥራት ሲያገለግሉ ቈይተው ከመንግሥታቸውም ታማኝነት ፈቀቅ ሳይሉና ከሀገራቸው ቅናት ሳይበርዱ እፍጻሜያቸው ድረስ ጠንካራ ጀግና ሁነው ሲያገለግሉ ነበር። ደግሞ የቅንነታቸው ምልክት የሚወዷቸው ልጃቸው ክቡር ደጃዝማች ደስታ ድንገት ከሞቻቸው ላይ ደርሰው ለሃገር ጥበቃ መድኃኒት መሆናቸው ለክቡር ራስ ናደውም እንደዚህ ድንቅ በሆነ አለቃቀስ ውሎ አስውለውላቸው በ፯ ሰዓት ባስጀመሩት በማርያም ቤተ ክርስቲያን በቤተ ልሔም አጠገብ በተሰናዳው የመቃብር ቤት አገቡአቸው።በማግሥቱም ኅዳር ፳ ቀን ማልስታቸው ነበርና በጧት ምስል ተመስሎ በንድ ወምበር በመሐከል ፎቶግራፋቸውን በራስጌ የወርቅ ላንቃ፥በንገቱም ላይ ራስ ወርቁ ሁኖ፥ በመደገፊያቸው ዙሪያም አርባ የሚያህሉ የልዩ ልዩ መንግሥት ኒሻኖች በክፈፉ ላይ ተንጠልጥለው በሰልፍ ሁኖ መጀመሪያ ፊት ወታደሮች፥ ቀጥሎ መደፍና መትረየስ የተጫኑ ከዘበኞቻቸው ጋራ፥ቀጥሎም በወርቅ መረሻት የተጫኑ በቅሎዎች ከፈረሶች በኋላ፥ ቀጥሎ ፎቶግራፋቸውን የተሸከሙ በወርቅ እቃ የተጫኑች በቅሎ ከልፍኝ አሽከሮች ጋራ ልዩ ጌጣቸውን የያዙ፥ ቀጥሎም የራስ ወርቅ ያደረገ የሚመስለው ጌጠኛው ፎቶግራፍና ቀኝ ባለሟሎች፥ቀጥሎም ጋሻ ዣግሬዎቻቸው፥ ቀጥሎም ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠውና ሌሎች መኳንንቶቻቸው በብዙ ረድፍ ተሰልፎ፥በኋላም ዘበኞች ከመኳንንቱ ለይተው እየተላቀሰ ሲጓዝ በነጋሪትና በእቢልታ፥ በመለከትና ከጥሩባው ጋራ የሕዝብ ለቅሶ እንደብዙ ወሆች ድምፅ ከሩቅ ሲሰማ አለፋቃድ ያስለቅሳል ።

እንዲህ እንደተሰለፈ መቃብር ደርሶ ተመልሰ ድንኳትን ሦስት ጊዜ ዙሮ እግቢ ገባ እንዲህ ያለ ያስከሬን ጉዞ የሰልፍ ማማር፥የልቅሶ መድመቅ፥የሰው ብዛት ከቶ ታይቶ አይታወቅም። በሕይወታቸው ሳሉ እንደአማረባቸው እንደከበሩ በሞታቸውም የሚወዱትን ልጃቸውን ክቡር ደጃዝማች ደስታን አምጥቶላቸው እንዲህ ያለ የደመቀ የክብር ልቅሶ ስለአዋሉላቸው ሕዝቡ ሁሉ ደስ አለው። እግዚአብሔርም እኒህን እውነተኛ የሀገር አጋልጋይ የነበሩትን ሽማግሌ ለጻድቃን ያዘጋጀላቸውን ክብር ተካፋይ ያድርጋቸው። እንዲህ ያሉትን ባለ ትሕትና የመኳንንት ባሕሪ ኩራት የሌለባቸው ስለሀገራቸው ልጆች የሚቀኑ ሽማግሌ ሰው ዛሬ በሞት ስለተነጠሉ ለመንግሥታችንና ለኢትዮጵያም ታላቅ ኅዘንና ጉዳት ነውና ለኢትዮጵያ መንግሥትና ሀገራቸውንም ለሚወዱ ልጆች ለዘመዶቻቸውና ለአሽከሮቻቸውም እግዚአብሔር ያጥናችሁ እንላለን ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ደብሪቱ በሻህ ዕረፍት ።

ለክቡር ራስ ናደው እኅት የሚሆኑ ክብርት ወይዘሮ ደብሪቱ በሻህ የተባሉ እጅግ የሚወዱአቸው ነበሩ ከመዋደዳቸው የተነሣ ሴቲቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን በወጡ ቍጥር ከናደው በፊት አድርገኝ፥ ሞቱን አታሳየኝ እያሉ ይጸልዩ ነበር ይላሉ። ክቡር ራስ ናደውም በወገናቸው ከኅቴ አስቀድመኝ ይሉ ነበር ይባላል። ክብርት ወይዘሮ ደብሪቱም ክቡር ራስናደው ታመውባቸው ጥቂት ቀን እንዳስታመሙ እራሳቸው በጋላ ቈርሳ በሚባል እባጭ በሽታ ታመው ከክቡር ራስ ናደው ዕረፍት አምስት ቀን በፊት ሞቱና በማርያም ቤተክርስቲያን ተቀበሩ።ክቡር ራስ ናደውም ሕመማቸው ጠንቶባቸው ነበርና የኅታቸውን ሞት ሳይሰሙ ዐረፉ። የእግዚአብሔር ሥራ ሁሉ ድንቅ ነው ሁለቱ ባለ ፍቅሮች አንደኛው ያንዱን ጥፋት ሳያዩ ተከታተሉ።ለባላቸው ለክቡር ፊታውራሪ መኰንን ኃይሌና ለልጆቻቸው ለወንድሞቻቸውም፥ ለቤተ ዘመዶቻቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እንላለን ። አ ወ ዳ

ማስታወቂያ ።

በሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ከዣፓን የሚመጣው ድር ባለ፯ ሰባት ትት እንዲሆን ግዴታ መኖሩን በብርሃንና ሰላም ለነጋዴዎች ከስታወቅን በኋላ ዣፓን ባለ ትት ድር አይሠራም እያሉ ትት የሌለው ድር ነጋዴዎች ስላመጡ አሁን ነጋዴዎቹ ለአመጡት ዕቃና ለተዋዋሉት ዕቃ ችግር እንዳያገኛቸው ስንል እንዲአወጡ ፈቅደናል ። ነገር ግን ለወደፊቱ ከዣፓንም የሚመጣው ድር ያለትት ከሆነ ከዚህ ቀደም እንዳስታወቅን ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ አጥብቆ መከልከሉን ነጋዴዎች እንዲአውቁት የዚህ ዓይነቲ ዕቃ በመንገድም ያላቸው ወይም የተዋዋሉ ነጋዴዎች እንዳሉ ዕቀው በመንገድ መኖሩንና ከዛሬ በፊትም መዋዋላቸውን እስከ ፲፭ ቀን ድረስ ወረቀቱን እያቀረቡ ለጉምሩክ እያስረዱ መፈረም ከሚገባው ወረቀትና ከውሉ ወረቀት ላይ ያስፈርሙ ። ከዚህ በኋላ ወደኢትዮጵያ እንዳይገባ ጉምሩክ ያልፈቀደው ትት የሌለው ድር ከመጣ የመጣው ነጋዴ ወይም ሌላው ሰው ሁሉ በ፲፫ኛው ክፍል በጉምሩክ ደንብ ይቀጣል ። የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ።

የኢኮኖምያ ፖለቲክ ። የ፫፻፺፫ገጽ ተከታይ ።

ግን አንዱ ከነዚህ ሦስት ፋቶሪ (ዋኖች ነገሮች ይልቅ መሬት እንደ ፍለጋችን ልታድግ አትችልም ። ለተወሰነ ፋቶሪ ለመጨመር ብንቀጥል የሁለቱን ፋቶሪ የምናገኛቸው ትርፍ ሁለ ጊዜ እያነሱ ይሔዳሉ ። ምሳሌ በአንድ መሬት (ቀላድ)በዋልኩዋቸው ካፒታልና በሠራሁት ልክ ዋጋ ፍሬን አገኛለሁን? በአንድ ቀላድ ዓሥራ ዓምስት ኩንታል (ሺ፭፻ ኪሎግራም)እህል እንደሚገኝ እንገምተው። እኔ ሌላ ካፒታልና ሥራ ብጨምርለት አለ ጥርጥር (ዓሥራ ሰባት ኩንታል፤እህል በአንድ ቀላድ አገኛለሁ።ግን ይህነን(ሁለት) ኩንታል እህል አሳድጎ ለማግኘት እኔ አንድ ከምሳ ሳንቲም ካፒታልና ሥራ ብጨምር፥የኔ እውነተኛው ትርፍ አምሳ ሳንቲም ይሆናል።ደግሞ እኔ ሌላ ካፒታል ገንዘብና ሥራ እንደገና ልጨምር ብፈልግና፥ዓሥራስምንት ተአምሳ ሳንቲም ኩንታል እህል በአንድ ቀላድ ለማግኘት ብችል ፤ አንድ ከአምሳ ሳንቲም ሎርድ የሚባል ገቢ ባደገልኝ ፥ ግን ይህንን እድገት አንድ በሰማኒያ ሳንቲም ካፒታልና(ገንዘብ)ሥራ ጨርሶብኛል። ስለዚህ እንደገና ሌላ ካፒታልና ሥራ ለመጨመር እደክማለሁኝ? አይደለም ስለምን የኋለኛይቱ ክፍልአንድ ከሰማንያ ሳንቲም የጨመርኩዋትወጭ አንድ ከምሳ ሳንቲም ብቻ ካፒታል አገኘሁ እና ፥ ሠላሳ ሳንቲም ከሣራ ጥፋት ደረሰኝ።ስለዚህ የትርፍን እያጐደለ መሔድ የሚባል ሕግ ሳልደርስ የመጨ ረሻይቱን ክፍል ወጭ ሳላደርግ በፊት እቆማለሁ።በብዙ ኢንዱስትሪዎች ግን በመሬቱ አኳኋን ግልብጥ ነገር የሆነ ተአምራት ይታያል ። ማለት ካፒታልና ሥራ ባደጉ ቍጥር ትርፋቸው እየበዛ ይሔዳል ። አስረጅ)አንዲት የሸማ ፋብሪካ መቶሺ ሸማ ብ፻ (አምሳ ሺ (ገንዘብ ማለት በአንዲት ሸማ አምሳ ሳንቲም ታፈራ ፥ ኋላ ደግሞ ካፒታልና (ገንዘብ ሥራ በመጨመር (ሁለት መቶ ሺ)ሸማ ለማፍራት ቢቻል ማለት የተፈራውን ብዛት ዕጥፍ ቢሆን፥የሚወጣው ገንዘብና ሥራ ዕጥፍ አይሆንም። ስለዚህ የወጣውን ሰማንያ ሺ እንገምተዋለን። ማለት አንድ ሸማ ለማፍራት የወጣ ዋጋ ለማወቅ ሰማንያሺ ለሁለት መቶሺ ቢከፈል አርባ ሳንቲም ይገኛል ስለምድርን ነው እንዲህ የሆነ ምላሹ ቀላል ነው ። እውነት ነው። በፋብሪካ በተገኘ ብዛት ልክ የማይገዙ (ነፃ)ብዙዎች የቆሙ ወጭ ያልሆኑ አሉ ።

የካፒታልን ቀዋሚ ወጭ፥ ማለት መሬት፥ የተሠራ ቤት፥ መኪና፥ የእጅ ሥራዎች፥ እነሱን የሚመስሉ ሁሉ ተመዛዝነው ልክ ሁነው አያድጉም። ሌላ ሁለተኛ አስረጅ ምሳሌ ደግሞ ፥ ከአዲስ አበባ ወደ ድሬዳዋ የሚሔድ ባቡር ሦስት ሩብ የሚገዝ ሰው ቢይዘው፥ ግን ሰው በጣብያ ቈይቶ የቀረውን እንዱን ሩብ ስፍራ ሁሉ ጭርሱን ቢሞላው ይህ አንድ ሩብ ለተጨመሩ ሰዎች ወጪው ያው ነው ምንም አያድግም ፤ ትርፍ ገቢው ግን አንድ ሩብ ያድጋል። ይህ እያደገ የሚሔድ ሕግ ይባላል። ስለሆነም እነዚህ ትርፎች መጨረሻ እስከሌላቸው ድረስ እያደጉ ይሔዳሉ፥ ማለት ትልቅ ስሕተት ይሆናል ስለምን እዚህም ማጕደል የሚባል ሕግ (ከዚያ ልኩ አልፎ ስፍራ የለም እንደማለት) ደርሶ ይቆማል ። ስለምን በጣም ከልክ ያለፈ እንደ ሆነ እንደእርሻ ትርፍ እየጐደለ የሚሔድ ከሚባል ሕግ ይደርሳል። ምሳሌ፥ ሥኳርና ወይም ጨው ከውኃ ሲገባ ይሟሟል ግን ከሚገባው ልክ በላይ አልፎ እንደ ገና ሥኳርን ብትጨምርበት ይዘግጣል እንጂ አይሟሟም እንዲሟሟ ብትፈልግ ግን እንደገና ውኃ መጨመር ያስፈልጋል ። እንዲሁም በፋብሪካ ከሚገባው ከልኩ በላይ ልትጨምር ብትፈልግ ሌላ መሬትና ሠራተኞች ካፒታል መጨመር ያስፈልጋልና ሌላ ወጭ መጨመር ይመጣል። ለምሳሌ ያቀረብነው ፋብሪካ አንድ ሚሊያርድ ሸማ ለማፍራት ብትፈልግ እንደ ማለት ነው። የሆነ ሁኖ ኢንዱስትሪን በትርፍ (ውለታ) ማደግን ሕግ ስትቆም፥እርሻ ግን እየጐደለ የሚሔድ ትርፍን (ውለታ) ለማስቀረት ትገደዳለች ማለት መሬቲቱየተወሰነች ሳለች ሕዝቡ እያደገ ይሔዳል ስለዚህ ሬንዲታን የምትባል ለዋነኛ ሰው ከሚገባው በላይ ትርፍ የተወለደችው ምክንያቱ ይህነን ነው። ባህልዋ፤ በሦስት ዓይነትዋ ማለት በሞኖፖልዋ፥በብልጫዋ በቦታው ምቾት፥ሬንዲታ አላት ተብሎ ይወሰናል ።

ይህነን በቍጥር ፴፰ ባጭሩ የሰጠነው ርእስ አሳብ ለአንባቢው በጣም ቀላልና ግልጥ ሊሆንለት ሰፋ አድርገን በሰባት አሳብ በተወሰነ ለያይተን ትርጓሜውን አብርተን እናቀርብለታለን። ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ። ሚካኤል ተሰማ ።

በአዲስ አበባ ዘበኞች ትጋት ተይዞ በምርመራ የተገለጠ ።
የሚያስመሰግን ሥራ ።

፩ኛ)ሽፈራው የሚባል ሰው ብዙ ልብስ ተሸክሞ ሲሔድ በስምንተኛው የዘበኛ መጠባበቂያ ሲደርስ ዘበኞች በጥራጣሬ ይህ ሰው የያዘው ልብስ የሰረቀው ሳይሆን አይቀርም በማለት እስከነ ልብሱ ይዘው ወደ አለቃቸው አደረሱት።

አለቃቸውም እስከተቻለው ድረስ መርምሮ በአመራመሩ የመስረቁን ምልክት ስላገኘበት ወደ ቅጣት ፍርድ መለያ ቤት (ቢሮ ክሮክሲኦን) አሳለፈውና የቢሮ ክሮክሲኦን ሹም ሽፈራው እንደቀረበላቸው ይህነን ልብስ ከወዴት አመጣኸው በዚሁስ ልብስ ላይ ምን ዓይነት ምልክት አለበት ብለው ልብሱን ሠውረው ቢጠይቁት መቸም ይህ ልብስ ገንዘቡ ስላልሆነ እስከ ፲፫ ቀን ድረስ ይዘው የሰነበተውን ልብስ ምልክቱን ፈጽሞ የማያውቀው ሁኖ በልብሱ ላይ የሌለውን ምልክት ተነገረና ወዲያው ትኬ ከሚባል አገር ነው ያመጣሁት ስላለ ልብሱ ቀረበና ቢታይ እሱ የተናገረው ምልክት በተሰረቀው ልብስ ላይ አልተገኘለትም ።

ከዚህ በኋላ መስረቅህን ባነጋገርህ ተረድተነዋልና ይልቁንም ይህነን ልብስ ከወዴት ሰርቀህ እንደ አመጣኸውና ከዚህም ቀደም በሌብነት ተይዘህ እንደሆነ ንገረን ብለው ቢጠይቁት እጁን ተቀብሎ ባለገንዘቡ ወስዶኝ ነበር እንጂ በሌብነት ተይጋ ነበረ ይህነኑም ልብስ ከዚሁ ሰውዬ ቤት ነው ሰርቄ ያመጣሁት ያን ጊዜም ስሜን ደበላ ነው ብዬ በመዝገብ አስጽፈአለሁ።ነገር ግን ሽፈራው ያልኳችሁ የክርስትና ስሜ ነው እንጂ የምጠራውም በደበላ ነው ሲል ተናገረ ።

እንደዚህም በማለቱ ተደነቁና ጥንቱንም ክርስትና አልተነሣህ እንደሆነ ነው እንጂ ክርስትናስ ተነሥተህ ቢሆን ሽፈራው ተብሎ የክርስትስና ስም እንደማይሰየም ታውቅ ነበር ብለው ለቅጣቱ በዘብጥያ ታሥሮ እንዲቈይና የሰረቀውንም ልብስ ባለ ቤቱ እስቲመጣ ድረስ በግምጃ ቤት እንዲቈይ አድርገዋል።

፪ኛ ፤ ብርሃኑ የሚባል ሰው በኅዳር ፯ ቀን አንድ ጸናጽል ይዞ በገበያ ሲዞር ዘበኞች ከወደኋላው እየተከተሉ ሲመለከቱ ቈይተው ሳሉ የአካሔዱና የንግግሩ አኳኋን የሰረቀ መሆኑን ስላስረዳቸው ይዘው በመጀመሪያ መጠባበቂያ ቢሮ ላለው ዳኛ አቀረቡለትና ብርሃኑ ቢጠየቅ ይህነኑ ጸናጽል ከቍስቋም ቤተ ክርስቲያን ሰርቆ ማምጣቱን ካመነ በኋላ ይልቁንም በሙሎ አውራጃ አቦ ከሚባል ቤተ ክርስቲያንን መጻሕፍትና ሌላም ንዋየ ቅድሳት ፤ ሁለተኛም የአዲስ አበባ መድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን መጋረጃ እንደሰረቀ ስለተናገረ ለቅጣቱ ታሥሮ ቈይቷል ።

፫ኛ ፡ ሉል ሰገድ የሚባል የፊታውራሪ ወልዳማኑኤል ብልደረባ በጥቅምት ፳፱ ቀን ሌሊት እኔ ወደ ሥራዬ ሒጄ ሳለ ሌባ ቤቱን ሰብሮ እቃዬን ሁሉ ወስዶብኛልና በዘበኛ ይመርመርልኝ ብሎ የጠፋውን እቃ ሁሉ ለይቶ ዓይነቱን በዝርዝር ጽፎ ስላቀረበ ዘበኞቹ እንዲመረምሩ ከምልክቱ ጋራ ትእዛዝ አለፈላቸው ።ዘበኞቹም በትጋት ይህነኑ የጠፋውን እቃ ሲመረምሩ አንዳንድ ኩታ በምልክቱ ተረድተው ደበሎ ከሚባል ሰው እጅ ስላገኙት ደበሎን ይዘው ወደ አለቃቸው ዘንድ አቀረቡትና ቢመረመር የሉል ሰገድን እቃ ግድግዳ ሰብሮ መስረቁን ስላመነ ለቅጣቱ በዘብጥያ ታሥሯል ።

ነገር ግን ይህነን እቃ እንድሰርቅ ያደረገኝ ገብረየስ የሚባል ሰው ነው ስላለ ገብረየስ ተይዞ መጥቶ ቢጠየቅ ደበሎ ሌባ መሆኑን እያወቀ በደባል ስም ከቤቱ እንዲኖር መፍቀዱንና ይህነኑም የሰረቀ ለት ከቤቱ ማደሩን ስላመነ ለሉልሰገድ የተሰረቀ እቃውን ሁሉ ሌባው እንደተናገረ ክፈል ተብሎ ተፈረደበት ።

ሉል ሰገድም የተሰረቀ እቃውን ከገብረየስ ላይ እንዲቀበል ካስረገጠ በኋላ የዘበኞችን የትጋት ሥራና የዳኛውን የውቀት ምርምር እያደነቀ መንግሥቱንም እያመሰገነ ወደ ቤቱ በደስታ ተመለሰ ። እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተጻፉት ቃሎች የአዲስ አበባ ከተማ ዘበኞች በትጋታቸው የሚሠሩት ሥራና በጥርጣሬም የሚይዙት ነገር ሁሉ የሌባን ፍለጋ በጭራሽ ፈጽሞ ሳያጠፋው አይቀርም ለማለት እንደፍራለን ። ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ ም ።

ደጉ ይመር።

የሚያሳዝን ወሬ።

በታኅሣሥ ፩ ቀን ጕዳይ ነበረኝና የመዘጋጃ ቤት ወምበሮች ግራዝማች ዝቄና አቶ ገዝሙ በሚአስችሉበት ችሎት ተቀምጬ ነበር።ወዲያው ፩ የሚያሳዝን ገና ወጣት መልኩ እጅግ እምያምር ጕበዝ በአቶመቢል አስገፍተህ ሰው ገድለሃል ተብሎ ታሥሮ መጣ እሱም መግደሉን አምኖ ጥሩምባ ብነፋ እምቢ ብሎ ከባልንጀራው ጋራ እጅለጅ ተያይዘው አቋርጠን እንሔዳለን ሲሉ ነው አስገፍቸ የገደልኩት አለ ።

አቋርጦ መሔዱን ትረታለህን ቢሉት አዎን አለ ወዲያውም ምስክር ቈጥሮ ፫ ምስክሮች መሰከሩበትና ገዳዩ ተረታ። ከዚህ በኋላ የምስክሮቹን አነጋገር ዳኞቹ ጠረጠሩና ስለዚህ ሰው አሟሟት የጠየቃችሁ ሰው የለምን ብለው ቢጠይቋቸው ደምሴ እሚባለው የአቶመቢል ፈታሽ የተሟጋቹ የአቶ አራጋው ልጅ የገዳዩን ወንድም ይዞ ፪ት ሦስት ቀን እየተመላለሰ ቃላችሁ አንድ ይሁን እያለ ማባበሉን ፫ ምስክሮች በደምሴ አራጋው መሰከሩበት ዳኞችም ቢጠይቁት አዎን የገዳዩ ዘመዶች ወዳጆቼ ናቸው መሽታም እምጠጣው ከነሱ ቤት ነው መጠየቁንም ጠይቄአቸዋለሁ ብሎ አመነ ።

ከዚህ በኋላ ዳኞች አምሳ ብር መቀጮ ጣሉበትና ሁለት ዋሶች ጠርቶ ሔደ የዚያ ሰው ልጅ ባይሆን ዋስም አያገኝ ታሥሮ በወህኒ ይሞት ነበር እንጂ ማን ይለቀው ነበር የጨዋ ልብሱን ለብሶ መለዮውን እንዳደረገ እየተጕላመመ ሔደ። ወይ መታደል በድሎ እንዳልበደለ መሆን? አረ ደምሴ አራጋው ይህን ሼፍጥና በሰው ነገር መግባትን ከወዴት አገኘው? በወህኒም ያሉ እሥረኞች ከዚህ የበለጠ ኃጢአት ያላቸው ጥቂቶች ሳይሆኑ አይቀሩም ይህንም መጻፌ ለብቻ ያደረጉት በደባበይ ሳይገለጥ አይቀርምና ጆሮ ላላቸው ሠራተኞች ተሰ

ምቷቸው በሥራቸው ጥንቃቄ እንዲአበዙ ነው እንጂ ተገዳዩም ተሟቹም ወገን አይደለሁም ። ተመልካቹ ።

ስለ አቤቱታ።

ጩኸ ለንጉሥ አቤት አቤት ይላል
እሱ ሲጣራ ።
ማን ጠራውና አቤት አቤት ይላል
አቤት ቋንቋ ነው የንጉሥ ስም አይደለም
ወደ ንጉሥ የሚጮህ ሰው
ንጉሥን መጥራቱ ነውና ጃንሆይ ጃንሆይ ማለት ይገባዋል ።
ከጥንት የተለመደ የንጉሥ ስም ነው
የደጅ አጋፋሪዎች እንደዚህ ያለውን ነገር
ማስተከከል ይገባቸዋልና ጃንሆይ ጃንሆይ ማለትን አስታውሳለሁ
ታኅሣሥ ፩ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ተ አ አበባ ።

ዓለሙ ሀብተ ሚከኤል ።

ሹመት ።

ታኅሣሥ ፳ ቀን ክቡር ደጃዝማች ዋቄ ጩቦንና ወሊሶን ተሹመው ካባ ላንቃ ለበሱ ።

ክቡር ነጋድራስ ታሬሰ ሀብተ ሚከኤል ከዚህ ቀደም የይሉባቦርንና የዓረብ አገርን ነጋድራስነቱን ተሹመው ሥራውን ሁሉ በተከከለ ደንብ በማስኬዳቸውና ሠራተኞቹን ነጋዴዎቹንም እንደሚገባ በማስተዳደራቸው ሕዝቡ በጣም ያመሰግናቸው ነበር ። አሁንም በጥቂት የታመነ በብዙ የታመነ ይሆናል እንደተባለ ፊታውራሪ ተብለው የጅጅጋ አውራጃ ገዥ ሁነው ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ለተቀበሉ ወዳጆቹ ለክቡር ደጃዝማች ዋቄና ለክቡር ፊታውራሪ ታሬሰ ሀብተ ሚከኤል እንኳን ደስ ያላችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ያቀርብላቸዋል ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ከኢጣልያ ሌጋሲዮን የታኅሣሥ ፲ ቀን ።

የዕለት ወሬ ።

አቴኔ ፤ ዛይሚስ የሬፑብሊክ ፕሬሲዳን እንዲሆን መመረጡን ለውጭ አገር ሌጋሲዮኖች በኡፊሲል ተነገረ ።

ብሩክሴል ፤ ፕሬንሴስ ማሪያ የቤልጂክ ንጉሥ ልጅ ቤልጅክ በምትተውበት ቀን ሕዝቧን እንደምታፈቅር ምስክር የሚሆን አምሳሺ ፍራንክ ለድኆች እንዲሰጥላት አዘዘች ።

ፓሪስ ፤ ሂድራ የግሪክ መርከብ፥ ከአንቶንዮ ጋርጃ የስፓኛ መርከብ ተጋጩና የስፓኛ መርከብ ከአምሳ የባሕር ወታደር ጋራ ሰጠመና ከነዚሁ ሀያ ሰዎች ከሞት እንደ ዳኑ ይወራል።

አቴኔ፤በየኤጌዎ ባሕር ብርቱ ሞገድ ተነሣና ዓሥር የሚያህሉ መርከቦች በወደቡ እንዲጠጉ ግድ ሆነባቸው ። እስካሁን ድረስ የጉዳት ነገር ምንም አልተወራም ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ድጓዋ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፮ ብር
ገብረ ጽባሕ	፮ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፭ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፭ ብር
የቁጥር ትምህርት	፭ ብር
የአማርኛ ሰዋሰው	፭ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፭ ብር
የብድር ደንብ	፭ ብር
የነፃነት ደንብ	፭ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፭ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፭ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፲ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ

የልጓ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፌደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የበገና ግጥም	፪ መሐ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ቀ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
ጎበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፺ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፮ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጽር	፩ ኮረጃ	፻፸ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፩ ብር
ባለ ድመ ።		፻፹
ባለአህያ ።		፻፵፫
ባለሳቢ ግመል ።		፻፷፩
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፷
" " ጃፖን		፻፸፰ብር
ሱካር	ጁኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብርተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፱ ፍራንክ ከ፺ሳቲንም
ባአንድ ብር	፺ ሊሬ ከ ፭ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፪ ብር ፳፭ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፱

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግጋርና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ΕΛΛΗΝΙΚΗΣ ΚΥΒΕΡΝΗΣΕΩΣ
KONIAK

COGNAC S.& E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት

12
1
2
3
4
5
7
8
9
10
11

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐ ፎዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊ ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወይዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማስታወቂያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛ ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ስይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አበከት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በማርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
5me ANNÉE № 52

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።
JEUDI 26 DÉCEMBRE 1929

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ዕረፍት።

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ የደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ልጅ ፤ የልዑል ራስ መኰንን ወንድም ናቸው ።

ከጕልማስነታቸው ጀምረው ለወንድማቸው ለልዑል ራስ መኰንን የታመኑ አገልጋይ ሁነው ይኖሩ ነበር ። ልዑል ራስ መኰንንም ካረፉ በኋላ ለልጃቸው ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የታመኑ አገልጋይና ጠባቂ ሁነው በመከራም፥ በደስታም ሳይለዩ ይኖሩ ነበር ። ነገር ግን ያገልግሎታቸውንና የመታመናቸውን ነገር በሙሉ ለመጻፍ አሁን ጊዜ የለንምና ለታሪክ ጸሐፊዎች ትተን የዕረፍታቸውን ምክንያት ብቻ እንጽፋለን ።

አሁን ባለፈው ዓመት የራያና፥ የዋጅራት፥ የዘብልና፥ የአውሳም አውራጃ ባላገሮች እርስ በርሳቸው እየተዋጉ መዘረፋቸውን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ስለ ሰሙ ከወሎም ፥ ከየጁም፥ ከትግሬም ፥ ወታደሮች እየታዘዙ አገር እንዲጠብቁ አድርገው ነበርና አሁን የባላገሩን አኳኋን ፥ ያገሩንም አጠባበቅ በቶሎ ለማወቅ ስለፈለጉ ደጃዝማች ወልደ ሥላሴንና ፊታውራሪ ዓምዴን፥ ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅን በአይሮፕላን ለመላክና የነገሩን ፍጻሜ ለማየት ማሰባቸውን ቢነግሯቸው ትእዛዝዎን ለመፈጸም የተዘጋጀሁ ነኝ ብለው ያለ አንዳች ቅርታ የግርማዊ ንጉሥን ትእዛዝ በደስታ ተቀበሉ ።

ከዚህም በኋላ በታኅሣሥ ፩ ቀን ከአዲስ አበባ ተነሥተው በ፱ ሰዓት ደሴ ከተማ ደረሱ ። ነገር ግን በወሎና ከወሎም ወዲያ ባለው አገር ዝናም ይዘንም ነበርና አገሩን ጉም እየሸፈነው በአይሮፕላን ለመሔድ የማይመች ስለ ሆነ ደሴ ላይ እንዲቈዩ ከግርማዊ ንጉሥ ትእዛዝ ተቀበሉ ።

፮ቀንም ያህል ከቈዩ በኋላ ዝናሙ የማያባራ፥ ጉሙ የማይለቅ ስለሆነ እንደ ገና ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ትእዛዝ ተቀብለው በታኅሣሥ ፲ ቀን ከጧቱ በ፩ ሰዓት ተኩል ከደሴ ተነሥተው በአይሮፕላን ሁነው ጕዞ ሲጀምሩ አይሮፕላን ነጂው በትክክል ለመንዳት የማይመቸው መሆኑን አውቆ ተመልሶ ለማረፍ ሲወርድ በኀይል ወረደና ከመሬት ላይ ተጋጨ ። አይሮፕላኑም ከመሬት ላይ ሲጋጭ ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ልባቸው ስለ ተነካ ደከሙና መናገር አቃታቸው ።

ከዚህም በኋላ ደሴ ላይ ወደ ተሠራው ወደ ተፈሪ መኰንን ሆፒታል ወስደው ለሐኪሙ ቢያሳዩት ልባቸው በጣም ተነክቷል ብሎ ተናገረ። በሆፒታልም ፲፩ሰዓት ያህል ቈይተው በታኅሣሥ ፲፩ ቀን ከሌሊቱ ፮ ሰዓት ተኩል ዓረፉ ።

አይሮፕላኑንም አደጋ እንዳገኘው ስለ ተሰማ ስልከኞች ሁሉ ሌሊት ሲጠባበቁ ነበርና ከሌቱ በ፯ሰዓት ማረፋቸውን ለአዲስ አበባ ስልከኞች አስታወቁ ።

ወዲያውም በየመኳንንቱ ሁሉ ተልኮ ከተሰበሰቡ በኋላ ጧት በ፲፪ ሰዓት መድፍ እየተተኰሰ ግርማዊ ንጉሥና ቤተ ዘመዶቻቸው ሁሉ የደጃዝማች ወልደ ሥላሴን ሞት ተረዱ።

ግርማዊ ንጉሥና ቤተ ዘመዶቻቸው ፤ መኳንንቱና ሕዝቡም ሁሉ በታላቅ ኀዘን አለቀሱላቸው ። እንኳን የሚያውቋቸው ሰውና የማያውቃቸውም የከተማው ሰው ሁሉ ፅኑ ኀዘን አዘነላቸው ።

ይህንም የመሰለ ኀዘንና ልቅሶ ለወንድማቸው ለልዑል ራስ መኰንን ተደርጎ እንደሆነ ነው እንጂ ለሌላ ሰው አልተደረገም ።

ወደ ደሴም ከሔዱት ከሦስቱ አይሮፕላኖች አደጋ ያገኘው አንዱን ብቻ ስለሆነ የክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴን ሬሳ ባንድ አይሮፕላን አድርገው ወደ አዲስ አበባ አመጡት። ስለዚሁም ጃንሜዳ ላይ ድንኳን ተተክሎ ይጠበቅ ነበረና በ፫ ሰዓት ደረሰ ።

በአዲስ አበባ የሚኖሩ መኳንንቶች በሙሉ ጳጳሳቱና የዲፕሎማቲክ ሰዎች ሁሉ መጥተው ጓርማዊ ንጉሥንና ቤተ ዘመዶቻቸውን ሁሉ ያፅናኑ ነበር ። ከዚህ በኋላ በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በ፱ ሰዓት ተቀበሩ ።

ምናልባት ወደ ፊት አይሮፕላን ላይ መውጣት የሚያስፈራ ነው እያሉ የሰውን ልብ ለማስነፍ በከተማ እየዞሩ የሚያወሩ አንዳንድ ሰዎች አይታጡም።ይህንም የመሰለ ወሬ የሚያወሩ ሰዎች የመንግሥታችን ጠላቶች የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ፈላጊዎች እንደሆኑ የታወቀ ነው ።

በዓለም ላይ ስለ ንጉሣቸውና ስለ መንግሥታቸው ልዩ ልዩ መከራና ሞት የሚያገኛቸው ብዙ ሰዎች ናቸው ።

አንዳንድ ሰዎች ስለ ንጉሣቸውና ስለ መንግሥታቸው በጦርነት ገብተው ከጠላት ጋራ ሲዋጉ ይሞታሉ ። እንግዲህ ሌላው ሰው እነእገሌ በጦርነት ሙተዋልና።ዘምቼ አልዋጋም ቢል ይመሰገናልን ።

አንዳንድ ሰዎች ከንጉሣቸው ተልከው ወይም ጉግሥ ሲጫወቱ ከፈረስ ወድቀው ይሞታሉ። እንግዲህ ሌላው ሰው እነእገሌ ከፈረስ ወድቀው ሙተዋልና በፈረስ አልጋልብም ቢል ይመሰገናልን ።

ደግሞ አንዳንድ ሰዎች በመንግሥታቸው ጉዳይ ወይም ለራሳቸው ጉዳይ በመርከብ ሲሔዱ መርከቡ ተሰብሮ በባሕር ይሠጥማሉ። እንግዲህ ሌላው ሰው እነእገሌ በመርከብ ሲሔዱ ሠጥመዋልና በመርከብ አልሔድም ቢል ይመሰገናልን ።

አንዳንድ ሰዎች ከንጉሣቸው ተልከው ወይም ለራሳቸው ጉዳይ ወንዝ ተሻግረን እንሔዳለን ሲሉ ውሀ ይወስዳቸዋል ። እንግዲህ ሌላው ሰው እነእገሌን ውሀ ወስዶዋቸዋልና ወንዝ አልሻገርም ቢል ይመሰገናልን ።

ደግሞ አንዳንድ ሰዎች ለቤት ወይም ለአጥር የሚሆን ዕንጨት ለመቍረጥ ከዛፍ ላይ ወጥተው ወድቀው ይሞታሉ። እንግዲህ ሌላው ሰው እነገሌ ከዛፍ ወድቀው ሙተዋልና ከዛፍ ላይ ወጥቼ ዕንጨት አልቈርጥም ቢል ይመሰገናልን ።

ይህንም የመሰለ የስንፍና ወሬ የሚያወሩ ሰዎች የእግዚአብሔርንም ፍርድ ተቃዋሚዎች መሆናቸው የማይጠረጠር ነው ። እንደምን ማለት ፤ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና ፍርድ ሰው ሊሞት አይችልም።ስለ ሆነም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሰው ሁሉ በንድ ዓይነት ሞት ሙቶ አያውቅም። ወደ ፊትም ሰው ሁሉ ባንድ ዓይነት የሚሞትበት ጊዜ ይመጣል ተብሎ አይታሰብም ።

አባት እንኳ ልጁን ሲቀጣ አንድ ቀን በጨንገር አንድ ቀን በለንጋ ፤ አንድ ቀን በቍንጢጥ፤ አንድ ቀን በጥፊ ይቀጣል እንጂ ዘወትር ባንድ ቅጣት ብቻ አይቀጣም ።

እግዚአብሔርም የሞት ፍርድ ሲፈርድ ምንም ፍርዱ አንድ ሞት ቢሆን ያሟሟቱ ምክንያት ልዩ ልዩ መሆኑን ሰው ሁሉ ያውቀዋል ። ስለዚህ ደጃዝማች ወልደ ሥላሴም ባንደኛው ልዩ ምክንያት ቢሞቱ አዲስ ነገር አይደለም ።

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ለጨዋታና ለመናፈስ ሳይሆን የጌታቸውንና የንጉሣቸውን ትእዛዝ ለመፈጸምና መንግሥታቸውን ለማገልገል ሲሉ ከዚህ ቀድሞ በማያውቁትና ባለመዱት በአይሮፕላን ላይ ወጥተው ይህ አደጋ ስለ አገኛቸውና ስለ ሞቱ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ወሮታቸውን ለልጆቻቸውና ለቤተ ዘመዶቻቸው እንዲመልሱ ማንም የሚጠራጠር የለም።

ደግሞ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ለኢትዮጵያ ታላቅነትና ጥቅም ሲሉ መጀመሪያ አይሮፕላን በማስመጣታቸው በሚመሰገኑበት ጊዜ ሁሉ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴም የንጉሣቸውን ትእዛዝ ለመፈጸምና መንግሥታቸውን ለማገልገል ሲሉ በመጀመሪያ ይህ አደጋ ስለ አገኛቸውና ስለ ሞቱ አገሩን ኢትዮጵያን የሚወድ ሰው ሁሉ እያመሰገናቸው እንዲኖር የተገባ ነው ።

ሞት ላትቀር መንገድ ትለዋውጣለች ።

የክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ሞት ለድፍን ኢትዮጵያ ትልቅ ጉዳት ትልቅ ኀዘን ነው ። ኢትዮጵያን የሚወድ ሰው በሳቸው ሞት ማዘን ግዱ ነው ። ስለምን የጓርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አጐት በመሆናቸው አይደለም ። ብቻ ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ለኢትዮጵያ በውነት ባንድ ልብ አለውልውል ባንድ ሃይማኖት ሁነው አሳቢ ተቈርቋሪ ነበሩ ። የንጉሥ አጐት በመሆናቸው ሳይኰሩ ዘወትር በትሕትና በትዕግሥት ለኢትዮጵያ ሕይወት እንጂ ለራሳቸው ጥቅም አያስቡ፤ በሰው ነገር አይገቡ፤እንደዘመኑ ሰው ፖለቲካ የሚሉትን አይወዱ፤ አይተበትቡ፤ ብቻ ለሀገራችን ጥቅም ለመንግሥታችን ሕይወት ነበረ አሳባቸውና ምኞታቸው ሁሉ ። ስለምን ያገር ሕይወት ለሁሉ ጥቅም ያገር ሁከት ለሁሉ ጉዳትና መከራ መሆኑን ያውቁ ነበረ ። የገዛ አገር ከታወከ አንድም ሰው እንዳይጠቀም የታወቀ ነው። ሁላችን እናውቃለን ። እንዲህ ያለው ለራሱ ትቶ ላገሩ ጤና ለመንግሥቱ ግርማ የሚመኝና የሚጥር ሰው ሲሞት ላገር ጉዳት ነው ብዙ ያሳዝናል ። ለራሱ ግን ትልቅ ኵራት ትልቅ ማዕርግ ነው ። ስለምን መዓርግና ኵራት ማለት ከሞት በኋላ የሚገኝ ነገር ነው እንጂ በቁሙ ሳለ የሚአገኘው ኵራት በከንቱ ውዳሴና በመፈራት የተቀመመ የማይጠቅም ነገር ነው። ለሁሉም ነገር ሰው የመወለዱን እንጂ ያሟሟቱን ነገር አያውቅም ። ሞትም ላትቀር መንገድ ትለዋወጣለች መንገዱን አታስታውቅም ። ወይ በጕንፋን በሳል ፤ ወይ በጦር ፤ ወይ በብራቅ ፤ ወይ ከፈረስ በመውደቅ፤ ከልጋ ከወንበር በመውደቅ፤ወይ በንቅፋት በትንታ በማንላቸውም ተመስላ ትመጣለች ። በዚያም በዚህም ሆነ ሞት መቸም ሞት ነው ። ነገር ግን ሰው ላገሩ ለወንዙ ለመንግሥቱ ሲል ቢሞት ደስ ያለ የሚአኰራ ሞት ነው ። እሱ በማይቀርለት ሞት ቢሞትና አፈር ቢሆን ስሙ እንደ ወርቅ ተጣርቶ ሳይዝግ ለዘላለሙ ይኖራል አይሞትም። ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ላገራቸው ለመንግሥታቸው ሲዋጉ ሲቆስሉ ሲገሉ ሲማርኩ ይኖሩ ነበረ ። አሁን ዳግም በስተር

ጅና አዲስ ነገር ነው ብለው ሳይፈሩ በአይሮፕላን ለመንግሥታቸው ለታመነ ጉዳይ ከታመኑ መኳንንቶች ጋራ ተልከው ሔዱና አጋጣሚ ሁኖ በሔዱበት ሞቱ።መሞትም አይበል፡ስማቸው እንዳይረሳ ሁኖ ተተክሎ ቀረ።አጋጣሚ ማለቴ በድፍኗ አውሮፓ እንኳን ወንዶች ሴቶች ሳይቀሩ ፤ ሴቶቹ ራሳቸው እየነዱ በዚሁ በአይሮፕላን አገር ላገር ሲሮጡ ሲራወጡ ይኖራሉ ምንም አያገኛቸው።አሁን እንኳ በቅርቡ ያገራችን ወይዘሮ የነጋድራስ መኰንን ባለቤት ወይዘሮ ዘውዲቱ በዚሁ በአይሮፕላን መሔዳቸውን ብርሃንና ሰላም አስታውቆናል። በአመሪካ አገር ገረዶች ሳይቀሩ ማለዳ ማለዳ ለጌቶቻቸው የሚገዙትን የለት ምግብ ገዝተው በገልግላቸው ቆልፈው ይዘው ታንዱ ገቢአ ወዳንዱ እየሳቁ እየተጫለቁ በዚሁ በሰማይ መርከብ ሲሔዱ እንሞታለን ብለው ምንም አይፈሩ ምንም አያገኛቸው የክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ሞት ግን አጋጣሚ ሁኖ ቀናቸው ደርሶ ኑሮ በዚሁ ምክንያት እግዚአብሔር ጠራቸው አጋጣሚ ሁኖ ዓሥር ዓመት፣ ዓሥራምስት ዓመት ሀያ ዓመት፣ ሙሉ ሲበሩ የሚኖሩ ሰዎች ሳይሞቱ እሳቸው ያ፩ሰዓት መንገድ በሔዱ ሞቱ ። ነፍሳቸውን ይማር ። በኤውሮጳ አገር በየከተማውና በየተራራው ሺህ የሺህ ሺ አሬዎፕላን እንዳንበጣ አየሩን እያላበሰ፣ ነፋስና ደመናውን እየቀደደ ሲራወጥ ይውላል ። እንደ ብዛቱ መጠን ግን ሞት የለበትም አያስፈራም ። ከሺ አንድ ቀን እንኳ አንዱ ቢወድቅና ሰው ቢሞት አያስደንቅም ። ስለምን ሞት ጉግሥ ሲጫወቱ ፈረስ እየተንደላቀፈ፣ ፈረሰኛ እየወደቀ ይሞታል። ያም ይሔን አከል ነው ። ይሔንም ማለቴ የኢትዮጵያ ጅግና ሺህ መድፍ እሳት ሲተፋ ዓረሩ እንደበረዶ ሲፈስ ጐራዴውን መዞ እየፈከረ ጻፉን ሲሔድ ላገሩ፣ ለንጉሡ፣ ለመንግሥቱ ሲል ነፍሱን እንደተበደራት እንጂ የራሱ መሆኑዋን እስቲረሳ ድረስ ወደ መድፍ የሚወረወረው ሽምሽግ የሚንጠላጠለው የኢትዮጵያ ጐበዝ ደጅዝማች ወልደ ሥላሴ ባጋጣሚ ሞቱ ብሎ ከሰማይ በቡር መውጣት ያሰጋዋል ስለማለት ብየ አይደለም ። እንዲህ ያለ የከንቱ አሳብ የለብኝም ። እውነት የሚአስፈራ ነገር ሁኖ ቢሆን በድፍን ኤውሮፓ በዚሁ አሬዎ ፕላን ያን ያህል የንግድ ነገር ያን ያህል የሥልጣኔ ሥራ ባልተያዘበትም ነበር ። ከሱ ይልቅ ቁጡ ፈረስ በጣም ያስፈራል ጉድጓድና ገደል ያገባል ። ለሁሉም ነገር እንደ ኢትዮጵያ ላለ የምድር ባቡርና የቀና መንገድ በሌለበት አገር አሬዎ ፕላን መጠን የሌለው ትልቅ ጥቅም አለውና መንግሥታችን በጣም ቢተጋበት ይሻል ይመስለኛል ። ብቻ አንድ ነገር ያስፈልጋል አሬዎ ፕላን የሚነዱት ሰዎች ደመ ባራድ የሆኑና የረጉ፣ መጠጥ የማያታልላቸው ፤ በጣም መንዳት የለመዱ እንዲሆኑና የተመረጡም እንዲሆኑ የተገባ ነው ። ከዚህ ላይ ብቻ ነው መጠንቀቅ ።

አፈ ወርቅ ዘብሔር ዘጌ ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ዕረፍት ደብተራ ወልደ ኪዳን የተቀኘው ቅኔ።

ልዕልና ልዑላን ረከበ እምዕፀወ ገዳም በለስ ።
እምጣነ ሰሐበ ለቃል ከመ ፈረስ ።
እምርጉቅ ጠፈረ ላዕል ዘኢይገፍዖ ነፋስ ።
ከመ ዓለማተ ይፈውስ ።
ወጊዜ ሥጋዌ ይኅድጉ ተዝህሮ ፀዋርያነ ቃል አልባስ ።
ውእቱ እስመ ተወሰነ በጸባብ ከርሥ ።
አሠረ ንጉሥ ፤ ኃይለ ሥላሴ ኢትኅዝን በሞቱ።
ለወልደ ሥሉስ ቅዱስ ።
አከኑ ወፈረ ለተድላ መንገለ መኰንን ርእስ ።
በሠረገላሁ ለኤልያስ ።
ወተወክፈ ካዕበ ሥጋ ኢየሱስ ።
ወወረሰ ለገነት ሐዳስ ።

፡፡ የ በ ገ ና ሰ ላ ም ታ ፡፡



ከጥንት ጀምሮ ሲነገር ከመጣው የበለጠ አድርጎ ከብሉይና ከሐዲስ እያሰማማ ደብተራ አድማሱ ዘዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንደጻፈው ።
በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን
ማተሚያ ቤት ታተመ ።
ዋጋውም አላድ ነው ።

የኢትዮጵያ መላክተኛ

ክቡር ነጋድራስ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር በሎንዶን ከገራቸው ከኢትዮጵያ ወደ እንግሊዝ አገር ከሔዱ ብዙ ቀን ሆናቸው፣የእንግሊዝ ንጉሥ ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ፭ኛ ስለ ታመሙ የሹመታቸውን ደብዳቤ ለማስረከብ አልተቻላቸውም ነበር።ንጉሥም በሕመማቸው ምክንያት ለመናፈስ ከዋናው ከተማቸው ከሎንዶን ወጥተው ሣንድሬን ጋም ከሚባል ከተማ ነበሩ በጥቅምት ወር መጨረሻ ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ የጤናቸው መሻሻልና ወደ ሎንዶን የመመለሳቸው በጋዜጣ መወራት ሲሰማ ክቡር ነጋድራስ መኰንን ስለ መገናኘታቸው ነገር ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መነጋገርና መጻጻፍ ጀመሩ

ንጉሥም እንደተባለው በኅዳር ወር መጀመሪያ ከሎንዶን ተመልሰው መጡ፡ንጉሡ ከገቡ በኋላ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለነጋድራስ መኰንን የሚገናኙበትን ቀንና የሚቀበሏቸውም ስለ ንጉሡ ልዑል ፕርንስ አብዌልዝ መሆናቸውን በጽሕፈት አስታወቋቸው የሚገናኙበትም ቀን ኅዳር ፲ቀን በአውሮጳ ቍጥር ፲፱ ኖባምብር ፲፱፻፴፮ ነበር። የንጉሡ የዲፕሎማቲክ ሰዎች አገናኝ የሆኑ ስርጆን ዊልየምስ ለመገናኘታቸው ያቀባበሉን አኳኋንና የመጣጣቸው የሚቀበሏቸውም ከዋናው ቤተ መንግሥት ከባኪንጋም ፓሊስ መሆኑን አስታወቁዋቸው በዚያው ዕለት የፖሎኝ፡ አምባሳደር፡ የሺን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር እንደዚሁ የሚገናኙበት ቀን ነበርና ያቀባበሉን ተርታ ለይተውላቸው ነበር ።



ይኸውም በመጀመሪ የፖሎኝ ሁለተኛ የኢትዮጵያ ሦስተኛ የሺን መላክተኛ ነበር ። በዚሁ ለመገናኘት በተቀጠረው ቀን ማክሰኞ ኅዳር ፲ቀን የኢትዮጵያ ታማኝ መልክተኛ ክቡር ነጋድራስ መኰንን ካሉበት ስፍራ የሹመት ልብሳቸውን ለብሰው የሌጋሲዮኑ ዋና ጸሐፊ አቶ በቀለ ሀብተ ሚካኤልና ዋናው አነጋጋሪ አቶ ተድላ አበባየሁ ሁነው ተሰልፈው ካሉበት ማሻይ ከሚባል ታላቅ ሆቴል ብቅ ባሉ ጊዜ ከውጭ የነበሩ ፎቶግራፍ አንሺዎችና ጋዜጠኞች አዲሱን የኢትዮጵያዊ ታማኝ መላክተኛ ውበት እያደነቁ በያለበት ጕድ ጕድ እያሉ ይሸቀዳደሙ ነበር። የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዛ አምራ በተሰናዳችው አውቶሞቢል ተቀምጠው ወደ ቤተመንግሥቱ ይጓዙ ጀመሩ ልክ በተባለው ሰዓት ለስድስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ከባኪንጋም ፓላስ ከትልቁ አዳራሽ በር ደረሱ ከዚሁ ከዳራሹ በር በግራና በቀኝ በቀይ ልብስ አምረው የተሸለሙ ተሰልፈው ሰላምታ ሰጡ ክቡር ስር ጆን ዊልያም በስተቀኝ ክቡር ሎርድ አንዌቲንግ በስተግራ ሁነው ተቀበሏቸውና ከሁለተኛው እልፍኝ አዳራሽ እያንከባከቡ ልዑል ፕሬንስ አብ ዋልስ ስለንጉሡ በተቀመጡበት ስፍራ ይዘዋቸው ገቡ ክቡር ነጋድራስ መኰንንም ልዑል ፕሬንስ አብ ዋልስ ካሉበት እልፍኝ ከዳራሽ ሲገቡ ስርጆን ዊልያምዝ ድምጣቸውን ከፍ አድርገው የኢትዮጵያ ሚኒስትር ብለው አስታወቁ። ልዑል ፕሬንስ አብ ዋልስ ቁመው ይጠብቋቸው ነበርና እበሩ ላይ ሲገቡ የክብር ሰላምታ ሦስት ጊዜ ሲሰጡ ልዑል ፕሬንስ አብ ዋልስ ካሉበት ስፍራ ወደ ነጋድራስ መኰንን ተራምደው እጅለጅ ሰላምታ ተሰጣጥው የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ተብለው የተሾሙበትን የሹመት ወረቀት አስረከቡ። ልዑል ፕሬንስ አብ ዋልስም ወረቀቱን ተቀብለው ስለንጉሡ ሁኜ በደስታ እቀበልዎታለሁ ብለው ተናገሩ።ክቡር ነጋድራስ መኰንንም በታላቁ ብሪታንያና በወዳጁ በኢትዮጵያ መካከል ከጥንት የቈየው እውነተኛ ፍቅር እየጠበቀና እየታደሰ እዲኖር ፈቅዶ የኢትዮጵያ መንግሥት ታማኝ መልክተኛው አድርጎ ሹሞ ስለላከኝ የደስታዬን ብዛት ገልጬ ለልዑልነትዎ እናገር ዘንድ ደስ እያለኝ ለግርማዊ ንጉሥ ለደጓንነታቸው ምኞት የመላበት ጥልቅ የሆነ ሰላምታዬን እንዲነግሩልኝ እለምናለሁ ብለው ተናገሩ በመጨረሻም ልዑል ፕሬንስ የኢትዮጵያን መልካምነት ተናግረው በደስታ ተሰነባበቱ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ።

በሲዳሞ የትምህርት ቤት መከፈት ።

፲፱፻፳፱ ዓ ኅዳር ፳፪ ቀን የተማሪቤቱ የሚከፈትበት ቀን ስለሆነ የተማሪ ቤቱ ሹም ቀኛዝማች ከበደ መኳንንቱን ብዚህ ቀን ተቀኑ በ፭ ሰዓት መጥታችሁ የተማሪ ቤቱን እንድትመርቁ ሲል አስታውቆ ነበርና ልክ ፭ሰዓት ሲሆን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ባማረ ዓጀብ ሁነው ወደ ተማሪ ቤቱሔዱ ። የተማሪ ቤቱም ያማረ ያማረ ወንበርና ጠረጴዛ ተደርድሮበት ባማረ ዓይነት ጌጥ አጊጦ ነበር ። በውጭውም ትልቅ ድንኳን ተተክሎ ልዩ ልዩ የሆነ ምንጣፍ ተነጥፎበት ብዙም ወንበር ተደርድሮበት ነበር።ክቡር ደጃዝማች ብሩም ገብተው ከተቀመጡ በኋላ የውጭ

አገር የፈረንጅ ታጁሮችና መኳንንቶቹ በየማዕርጋቸው እየተጠሩ በወንበር ተቀመጡ።ከዚህ በኋላ የተማሪ ቤቱ ዲሬክተር ክቡር ሙሴ አይባዲየን ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ክቡር ሆይ የተከበራችሁ ሕዝብና የተወደዳችሁ ተማሪዎች ።

እንድትሰሙኝ እለምናችኋለሁ ። የዛሬው ቀን ለዚህ አገርና ለዚህ አውራጃ፥ለእናንተም የተከበረና የተወደደ ነው። የዛሬን ቀን ከቶ አትርሱት ዛሬውኑ በወርቅ ቀለም ጽፋችሁ በልባችሁ አስቀምጡት። በክቡር ጌታችን ደጃዝማች ብሩ እጅግ ገንዘብ ታላቁ የትምህርት ቤት በር ተከፍቶበታልና።ትምህርት፥መልካም አስተዳደግ፥ሥልጣኔ ለሰው የሚገባ ዋና የበረቱ መሣሪያዎች ናቸው።በዓይናችሁ ፀሐይ ሲያበራ በርግጥ ፀሐይ መሆኑን እንደምታውቁ እንዲሁ ያለ ትምህርትና ያለ ሥልጣኔ አንድም ነገር እንዳይደረግ እርግጥ መሆኑን ተረዱት። ፀሐይ ብርሃንና ሕይወትን እንደምትሰጠን እንዲሁ የትምህርት ቤት ለመንፈሳችን ብርሃንና ሕይወት ይሰጣል።ያለተማሪቤት ያለ ዕውቀት ሰው ጐደሎ ነው ከቶውንም ያለተማሪ ቤት ሃይማኖት አትገኝም ።

የዛሬን ቀን አትርሱት እርሱም የሚአስደንቀውን መሰወጥና ለሰው ፍጥረት የተገባውን ኑሮ የሚያመለክታችሁንና የሚያስረዳችሁን ሁናቴ አምጥቶላችኋልና እናንት ቤተ ዘመዶች እጅግ የታደላችሁ ናችሁ፤ልጆቻችሁ ተምረው ከጠለቀው የድንቍርና ጨለማ ወጥተው ወደ ብርሃን ወጥተው አእምሮ ያላቸውና አዋቂዎች ይሆናሉ ። እኔም አውቃለሁ ሁላችሁ ወፍራሙን የድንቍርና ጨለማ እንደረገማችሁ ያንድ አገር ድምብርና የሕዝቡ ነፃነት የሚጠበቀው በትምህርት ዕውቀት ነው እንጂ በጦር መሣሪያ አይደለም ። ዋናው ሰው የሚመክትበት መሣሪያ የተማሪ ቤት ነው፤በርሱም ተሰልፋችሁ ወደተከበረው ከፍታ ከደረሳችሁ በኋላ በስዋ ማኅበር ትገባላችሁ።እናንተና አገራችሁ ከመላው ዓለም ቀደምት እንደሆናችሁ እርግጥ ነው። ደግሞ አሁን የቀድሞውን የድንቍርና ጨለማን ለማራቅ ሐሳባችሁን ቍርጥ እንዳደረጋችሁ እርግጥ ነው ። ደግሞ አገራችሁ ትምህርትን በለተጸማ አውቃችሁ አእምሮዋችሁ የተዋበ የፍጥረት ስጦታ ማግኘቱ እርግጥ ነው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከፍ ብለው የዕውቀት ተራራ ጫፍ ላይ ከሚኖሩት ሕዝብና ታላቅ ክብር ወዳለው ኑሮ ትደርሳላችሁ ።

በቀድሞ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሊያመልኩበት የምትገባ ናት ተብሎ ይታመን ነበር፤ነገር ግን እንደቤተ ክርስቲያን ሊያመልኩበት የሚገባ ተማሪቤት እንደሆነ አስረዳችኋለሁ ።

እስከ ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን አጥብቃችሁ ትይዙ ነበር ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ወደ ሥልጣኔ እንድትአደርስ አላገዛቻችሁም ከናንተ በኋላ የተወለዱት ሕዝቦች ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተማሪ ቤትን ጨምረው ስለያዙ ወደታላቁ እውቀት ተራራ ጫፍ ደርሰው ታላቁን ክብርና ድልን አገኙ እነሆ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችሁ አጠገብ አንድ ተማሪ ቤት አቆማችሁ ። እርሱም ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ሊያመልኩበት የሚገባ ነው ተማሪቤት የቤተ ክርስቲያንን አኳኋንና ሃይማኖትን ያስተምራችኋልና ።

ቤተ ክርስቲያንና ሃይማኖት ነፍስን በማስተማር ሰውን ወደ አንደኛው ዓለም ለማግባት ያሰናዳሉ የተማሪቤት ግን ነፍስን፥መንፈስን፥ ልብን በማስተማር ሰውን በዚህ ዓለም በሕይወት ለመኖር ወደ ኋለኛው ዓለምም ከአእምሮ ጋር ለመድረስ ይጥራል።ተማሪ ቤት ከሌለ የሰውን ሃይማኖት የሚመሠርቱ የመጻሕፍት ቃላት ሳይታወቁ ይኖራሉ ።ከንደኞቻችሁ ጋር መልካም አስተዳደግ እንድታገኙ ያለኝን ዓቅሜን አልነፍጋችሁም።የተወደዳችሁ ልጆቼ ሆይ እናንተ መልካሚ ሀገራችሁ በክንፈሮቿ የደስታ ፈገግታ የምትጠብቃቸውን አዲስ ትውልድ ትሰበስባላችሁ ። በቶሎ ተማሩ፥በትምርታችሁም ተቀዳደሙ ። ይኸው ዛሬ ከ፴፱ ዓመት በኋላ የዚች ያአገራችሁ ነግህ ብቅ አለ። በሚያስደንቀው ነግህ ብሩ ከከበ ጽባሕ ተማሪ ቤት ይታያል እርሱም ያማረ ሽቱ ያለው አበባ ይዞ ብርሃንና ደስታ ተመርኩዞ ይቀርባችኋል።እናንተምን በያዛቸው አበባ ብርሃን ደስታ ከብዙ ዘመን እንቅልፋችሁ ያነቃችኋል ።

ይህ አገር በታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ የታወቀ ስለሆነ ደግሞ ዛሬ የታላቁ ንጉሥ ወራሾች ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ቀድሞ በታላቁ ንጉሥ ጊዜ የተጀመረውን የሥልጣኔ ጐዳና ስለሚያሰፉ ፈጽሞ የታወቀና የተከበረ ነው።ከነዚህም ከታወቁት ታላላቅ ሰዎች በኋላ ቀጥለው ብርሃን የሚሰጧችሁ ክቡር። ደጃዝማች ብሩ ናቸው እርሳቸውም ያለተማሪቤት ባገር ሰላምና ጤና እንዳይፀና ስለተረዱ ተማሪቤት አቆሙላችሁ። ወንድሞቼ ሆይ ትልቆችም ትንሾችም ከቶ የነዚህን የታላላቅ ሰዎች ስም እንዳትረሱ ሰማቸውን በወርቅ ቀለም ጽፋችሁ እንድታኖሩት እመክራችኋለሁ።የታላቁ የደጉ ንጉሥ ዳግማዊ ምኒልክን ነፍስ ይማርልን

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትንና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን ለዘላለም ያኑርልን፥ ክቡር ደጃዝማች ብሩንና ብሩ ከከበ ጽባሕ ተማሪቤትን ያኑርልን ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑርልን ።

ዲሬክተሩ ይኸን ሲጨርሱ ዶክተር ሸሪኮፍ ቀጥሎ ያለውን ተናገሩ።

ክቡር ሆይ ።

ዛሬ ለሀገርዎና በውሥጡ ላሉት ወጣቶችና ለሠራዊቱ እጅግ ደስታ ስላደረጉ እኔም ይህነን የደስታን ቃል እናገር ዘንድ ፈቀድሁኝ፤ ክቡር ጌታዬ ግን ሐሳብዎ ለሲዳሞ ብቻ አይደለም ለድፍን ኢትዮጵያ ነው እንጂ ይህ ሁሉ ጌታዬ ያሰቡት ሀሐብ ለድፍን ኢትዮጵያ እንደ ፀሐይ ብርሃን ሁኖ ይታያል በዚህ መንገድ ጌታዬ ባሰቡት የኢትዮጵያ የሁሉ መኳንንቶች ልብ እየነቃቃ እውቀትም እየገባቸው ለትልቅ ማዕርግ ይደርሳሉ ክቡር ሆይ፤ የሀሳብዎን ፍጻሜ እንዲጨርስልዎ አምላክ ይርዳዎ ረጅም ዕድሜ ለክቡር ጌታዬ ለደጃዝማች ብሩ ይስጥልኝ ።

፪ኛ፤ደግሞ እናንት ሕፃናት እኔም በእንደዚሁ በጭር ቃል ልነግራችሁ እወዳለሁ፥በዚህ አገር እናንት ወጣቶች በመሆናችሁ ለናንት አምላክ ዕድሜ ሰጥቶዋችሁና ደግሞ ዓይናችሁን ከፍቶላችሁ ለአገራችሁ ረዳት እንድትሆኑና ደግሞ ለአዲስ ጥበብና ብልሃት ከዋና ማዕርግ ደርሳችሁ እንዲህ ያለ ትምህርት ማስተማርና ሕክምናን በብዙም ልዩ ልዩ ዓይነት ዕውቀት በዚህ መንገድ ኢትዮጵያን አገራችሁን ለመርዳት ትችላላችሁ

አንተም ክቡር ሙሴ አይበድያን እኔም ተስፋ አደርጋለሁ አንተ የምታደርገውን ሥራ ሁሉ ለኒህ ልጆች፤ እነርሱ የራስህ ናቸውና እንደዚሁም አባታቸው ሁነህ በጎ ነገር እንድታስብላቸው እንዚያም በኋለኛው ቀን ያከቡሩ አባታችን እንዲህ በጎ ዋለልን ብለው ያስቡሀል ደግሞ እግዚአብሔር ይርዳህ በዚሁ በሥራህ አምላክ ካንተ ጋራ ይሁን ።

እናንት በአገረ ሰላም የምትኖሩ ሰዎች ደግሞም በዙሪዋ በሲዳሞ ሁሉ የምትኖሩ ሰዎች እኔ የምለምናችሁን ልመናዬን ስሙኝ። ክቡር ፊቃዳችሁ ሁኖ ልጆቻችሁን ወደ ተማሪ ቤት ሰዳችሁ እንደሚቻላችሁ ለተማሪ ቤት እየረዳችሁ ከብዙ ዕውቀት እንድታደርስዋቸው በዚህም እኛ ሲዳሞ ያለነው ሰዎች ማስታወቂያ እንጽፋለን፡ዳግም እኔና ባለቤቴ አምሳ ብር ለተማሪ ቤት እርዳታ ሰጥተናል ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር አሜን።

ከዚህም በኋላ አስፋው አብዲ ቀጥሎ ያለውን ቃልተናገረ።

ክቡር ሆይ ።

ዛሬ ለአገርዎ እርዳታ ሴት ተቀን በልብዎ ውሥጥ ሲወጣና ሲወርድ የሚኖረውን እውነተኛ አሳብዎን ለሕዝቡ የሚገልፁበት ቀን ስለሆነ በዚህ ለተሰበሰቡት መኳንንትና ወታደር ቀጥዬ የጻፍሁትን ላመለክት እወዳለሁ ።

ክቡራን ጌቶቼ ሆይ መጀመሪያ ሰው አምላኩን አውቆ ከፈጣሪው በተቀበለው ዕውቀት ክፉንና ደግን ለይቶ ማወቅ ይገባል ። ሰው ክፉንና ደግን ካላወቀ ከእንስሳ ምንም ያህል አይበልጥም ዕውቀት የሌለው ያልተማረ ሕዝብ ዕውቀት ላለው ሕዝብ ታዛጋር ሁኖ ይኖራል። ከቶ ነጻነት የለውም ስለዚህ የልጆች አባቶች የሆናችሁ ሁሉ ለልጆቻችሁ ብዙ ገንዘብ ከምታጠራቅሙላቸው ይልቅ ወደ ዕውቀት ብትመሯቸው ከባርነት ነጻነት እንደምታወጧቸው የታወቀ ነው ። ገንዘብ ይጠፋል ሌባም ይሰርቀዋል ዕውቀት ግን ልትነጠቅ፣ ልትሰረቀም አትችልም እስከ መቃብር ድረስ አብራ ትገባለች ለወዲያኛውም ዓለም መሪ ትሆናለች እንግዲህ የሰው ርስቱ ዕውቀት ናት ።

አባቶቻችን በዘመናቸው የተገኘውን ዕውቀት ይዘው ወደ አገራቸው ጥቃት ሳያስገቡ ነጻነትንና አገርን አቄዩን።እኛ ደግሞ በዘመናችን የተገኘውን ዕውቀት ብንይዝ ወደጐዳናዋም ብንመራ ከፍ ወዳለው የውቀት ደረጃ ደርሰን ከሠለጠነው ሕዝብ ጋር እንድንተካከል ጥርጥር የለውም ።

ደንቆሮ ሰው በዱሮ ልማድ ለመኖር ይመኛል። ልጁንም ወደተማሪ ቤት አይሰድም ነገር ግን ልጁ ባደገ ጊዜ አባቱ ያጠራቀመውን ገንዘብ በትኖ አንባጓሮኛ፣ መሸተኛ፤ወስላታ ሁኖ ገንዘቡ ባለቀ ጊዜ ስርቆት ወይም ቅሚያ ይጀምራል፤አባቱም ይረግመዋል፣ እሱም ክፉ ጠባዩ እየባሰበት ይሔዳል ፤ነፍስም እስከ መግደል ይደርሳል፣ በዚያን ጊዜ ልጁን አላስተምርም ያለው አባት ሆዬ አዬጕድን ይዞ ይቀራል ።

እንሆ ይህን ደንቆሮ ሰው የመሰሉ የልጆች አባቶች ከንደዚህ ያለው መከራ እንዳያመልጡ የታመነ የተረገጠ ነው ። ልጆቻቸውንም በድለው፣ እራሳቸውንም ጐድተው፤ከእግዚአብሔርም ዘንድ ሳይጠቀሙ ሁሉን ያጡ ሁነው ይቀራሉ።

ክቡር ጌታችን ደጃዝማች ብሩ ከእንደዚህ ያለው ጥፋት አባቶችንና ልጆችን ለማዳን፤አገርን ለማሠልጠን በገዛ ገንዘባቸው የተማሪ ቤት በማቆማቸው በዚህ ዓለም ስማቸው በኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ ከትውልድ እስከ ትውልድ ዘለዓለም ሲጠራ ይኖራል ። በአምላክም ዘንድ ብዳራቸውን አያጡትም።

እንዲሁ ለተማሪ ቤት እርዳታ ገንዘብ ለሰጡት ሰዎች የጠለቀ ምስጋናየን አቀርባለሁ ።

እግዚአብሔር ለውቀት መሪዎቻችን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን፤ለክቡር ጌታችን ለደጃዝማች ብሩ ረጅም ዕድሜና የደስታ ዘመን ይስጣቸው ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ስለ ከተማ ዘበኞች ትጋት

፩ኛ፤ጌታሁን የሚባል ሰው ዘለለው የሚባለውን የአጐቱን ልጅ ተያጋር አድርጎ የወታደርነት ሥራ ሲሠራ ቈይቶ ሳለ በደምብ የተቀበለውን ጠመንጃ ሳያስረክብ ስለከዳ ዘለለው የሚባለው በተያዢነቱ ተይዞ ኑሮ ጌታሁን ያለበትን ስፍራ ሲጠየየቅ ሰንብቶ አገኘውና በኅዳር ፲ ቀን በጥዋት ሒዶ ወንድሜ ጠመንጃውን ሳታስረክበኝ ለምን ከዳህ አሁንም ተይዣለሁና ጠመንጃውን ስጠኝ ብሎ በትሕትና ቢጠይቀው ለጥያቄው ምንም መልስ ሳይሰጥ ጌታሁን የሚባለው ጨካኝ ሰው ዘለለው የሚባለውን ተያጋር ሁኖ እንጀራ ያበላውን ወንድሙን በጠመንጃ ገደለው ።

ከዚህ በኋላ ባራተኛው የመጠባበቂያ ክፍል ያሉ የከተማ ዘበኞች የባሻ ገሰሰ ባልደረቦች ተኵሱን ስለሰሙ ወዲያው በፍጥነት የጌታሁንን ፍለጋ ተከታትለው ሒደው ያዙት ።

ጌታሁንም ቢጠየቅ ከዚህ በላይ እንደተነገረው ሌላ በደል ሳይኖር ጠመንጃውን አስረክበኝ በማለቱ ብቻ መግደሉን አምኖ ቈይቶ ነበረና በባሻ ገሰሰ በኩል ወደ ግርማዊ ንጉሥ ችሎት ቀርቦ ከዘለለው ወገኖች ጋራ ተፋርዶ የሚገባውን የሞት ፍርድ ተቀብሎ ተደበደበ ።

፪ኛ፤ ዑመር ሰይድ የሚባል ነጋዴ ጃርሶ ከሚባለው አገር ብዙ ሰዎች ሁነን ቆዳ ጭነን ወደ አዲስ አበባ መጥተን ነበረ ቆዳውን ለቱጃር ከሸጥን በኋላ ዳግም ወደ ውጭ አገር ክራይ እንጭናለን ብለን ከብቶቻችንን ዳለቲ ከሚባለው አገር አሳርፈን ስንጠባበቅ ኅዳር ፳፫ ቀን ማታ ሌቦች ብዙ ሁነው መጥተው ጠባቂዎች አንሰው ነበሩና በብዛታቸው አስፈራርተው ሠላሳ ስድስት አጋሰሶች ወሰዱብን። አሁንም ወደ ዋሻ ውሥጥ የገቡ ይመስለኛል ብሎ ለዘበኛ አለቃው ለግራዝማች አማረ አመለከተ።

ግራዝማች አማረም ዑመር ያአቤቱታውን ነገር ሳይጨርስ በችኮላ ተነሥተው ከዓሥር ፈረሰኛ ጋራ ሁነው ግስጋሴ አደረጉ። ብዙዎችም ዘበኞች በእግር እየተሯሯጡ ተከታትለዋቸው ነበረ። ከዚህ በኋላ እነዚህኑ የተሰረቁትን በቅሎዎች በትልልቅ ጋራዎች መካከል ሁለት ሌቦች እንደጠባቂ መስለው ሣር ሲያበሉ ደርሰው ያዟቸው።

ነጋዴዎቹም ከብቶቻቸውና ሌቦች አንድነት በዘበኞች እጅ ተይዘው መምጣታቸውን ባዩ ጊዜ የግራዝማች አማረን ትጋትና የዘበኞችን ብርታት እያደነቁ መንግሥትንም በልዩ ልዩ ምስጋና አመስግነው በቅሎቻቸውን ተረክበው በደስታ ወደንግዳቸው ተመለሱ።ሌቦቹግን አብረዋቸው የሰረቁትን ሌቦች እያመለከቱ አስይዘዋል።

፫ኛ፤ አሁን በኅዳር ወር አንድ የግሪክ አገር ሰው የንግዱን እቃና ሸቀጡንም ሁሉ ካኖረበት ቤት ውሥጥ የእሳት አደጋ ስለተነሣ የዘበኛ አለቃው ይህነኑ የሳት አደጋ አይተው ዘበኞችን አስከትለው በፍጥነት ደረሱና በተቃጠለው ቤት የነበሩትን ሰዎች እቃውንም ሲያወጡ እሳቱንም ሲያጠፉ ላያቸው ሰው ከፍጥነታቸው የተነሣ ሰው ሁሉ አደነቀ። ይልቁንም በዚህ በተቃጠለው ቤት አጠገብ የሚበዛው እቃ ቤንዚን ነበረ።ይህነኑ ቤንዚን ዘበኞቹ ደርሰው ባያወጡት ኑሮ ስንት ቤቶች ይቃጠሉ ነበር።

እንደዚሁም ደግሞ የልጅ ንጋቱ ይመር ሦስት ክፍል በሆነው በሣር ክዳን ቤቱ ውሥጥ ካንዱ ክፍል የእሳት አደጋ ተነሥቶ ነበረና የሳቱን ውጋገን በሩቁ አይተው በፍጥነት ተሯሩጠው ስለደረሱ ዕቃውንና ሁለቱን ክፍል ቤት ከእሳቱ አደጋ ተከላክለው የከተማ ዘበኞች አድነውለታል ።

እንደዚህ በመሰለ የሚያስጨንቅ አደጋ ላይ ፈጥነው የሚደርሱ ዘበኞች ሁሉ በታዘዙት ሥራ ፀንተው የከተማውን ሕዝብ ከጥፋትና ከመከራ በማዳናቸው ምሳሌአቸው በመላእክት ሊሆን የተገባ ነው።ስለዚህ ይህነን ደስ የሚያሰኘውን የከተማ ዘበኞችን የትጋት ሥራ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሳናስረዳ ቀርተን እንደ ወሬ በቃል ንግግር ቢሰሙት ለደስታቸው ጥርጥር ይገባቸዋል በማለት እርግጠኛውን ነገር ጽፈናል።

ደጉ ይመር።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



COGNAC SaE&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፺ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገናል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የድማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።



በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በዓርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

BRITISH MUSEUM 21 JUL 36